የእስራኤል ሎቢ

እና

በአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ

ጆን ጄ ሚርሸይመር እና ስቴፈን ኤም ዋልት

ማስታወሻነቱ

ለሚቹ አጉቴ ለመሐመድ ጢሂር

የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው

All rights are reserved

አንደኛ እትም ሰኔ 2004

Addis Ababa Ethiopia

First Edition May 2012

ማውጫ

ርዕስ **ገጽ**

መቅድም.....7
መግቢያ.....12
ሎቢውና የዩናይትድ ስቴትስ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲ.....17
ሎቢው የሚሠራበት የተለየ መንገድ.....23
የእስራኤልንና ሎቢ አስመልክቶ መወያየት ከባድ የሆነው 26

ምዕራፍ አንድ.....32
አሜሪካ የእስራኤል ታላቋ አጋር.....32
ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ 33
ወታደራዊ ድጋፍ.....47
ዲፕሎማሲያዊ መከታና በጦርነት ጊዜ የሚደረግ ድጋፍ.....63
ማጠቃለያ.....77

ምዕራፍ ሁለት.....79
እስራኤል - የአሜሪካ ስትራቴጂያዊ አጋር ወይስ እዳ?.....79
የሶቪየትን መስፋፋት ለመግታት እስራኤልን መርዳት 82
ከቀዝቃዛው ጦርነት ወደ 9/11.....95
‹‹የፀረ-አሸባሪነት ሽርክና›› አዲሱ የግንኙነት ሰበብ.....99
ተጋፊ መንግሥታትን መጋፈጥ 116
የማትታመን አጋር 125

ምዕራፍ ሶስት.....128
እየመነመነ የሄደ የሞራል ምክንያት 128
ደካማውን ማገዝ.....132
የዲሞክራሲ አጋሮችን መርዳት 141
አይሁዳውያን ባለፉት ዘመናት የደረሰባቸውን መከራ ማካካስ.....150
ደግ አድራጊ እስራኤላውያንና መጥፎ አረቦች!.....161
የካምፕ ዴቪድ ተረቶች.....170
እስራኤልን መደገፍ የአምላክ ፈቃድ ነው.....177
ለመሆኑ የአሜሪካ ሕዝብ የሚፈልገው ምንድን ነው? 178

ምዕራፍ አራት 182
‹‹የእስራኤል ሎቢ›› ምንድን ነው? 182
የእስራኤል ሎቢ ምንነት ሲገለጽ 184
የአሜሪካ አይሁዶች የሚጫወቱት ሚና 188
በልዩነት ውስጥ አንድነት፣ ባለመስማማት 197
ውስጥ ስምምነት 197
ሎቢው እርምጃውን ቀጠለ 208
የወግ አጥባቂዎቹ ሚና 212
ክርስቲያን ጽዮናውያን 218
የሎቢው የኃይል ምንጮች 232
ነዳጅ ዘይት የሚያስከትለው መጠነኛ ተጽዕኖ 236
የሁለትዮሽ ታማኝነት (Dual loyality) ጥያቄ 243

ምዕራፍ-አምስት 250
የፖሊሲውን ሂደት አቅጣጫ መተለም 250
ካፒቶል ሂልን በተጽዕኖ መወዝወዝ 251
አፍቃሪ እስራኤል ፕሬዝዳንቶችን ወደ ሥልጣን ማምጣት 270
የአሜሪካን አስተዳደራዊ መዋቅር መቆጣጠር 274

ምዕራፍ ስድስት 279
የህዝብ አስተያየቶችን መጫን 279
መገናኛ ብዙሃንን በሚገባ መጠቀም 280
በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚያስቡ ሐሳብ አፍላቂዎች 291
የአካዳሚውን ዓለም መቆጣጠር 297
የተቃውሞ ስልቶች 310
አዲሱ ‹‹ጸረ-ሴማዊነት›› 315
ታላቁ ዝም ማሰኛ መሳሪያ 321

የክፍል ሁለት መግቢያ 332
የሎቢው አጀንዳ 333
ዩናይትድ ስቴትስና እስራኤል ከመሰከረም 11 በኋላ 335

ምዕራፍ ሰባት 339
ሎቢውና የፍልስጤማውያን ሁኔታ 339
ሎቢው ቡሽን ሲያዋርድ 346

“የነገሮች ይበልጥ እየተቀየሩ መሄድ…” 351
ለሮድ ማፕ የአንድ ወገን ድጋፍ 359
አረፋት ቢሞቱም የተለወጠ ነገር አልነበረም 364
ራይስ “የፓወል እጣ” ደረሳቸው[101] 367
ማጠቃለያ 376

ምዕራፍ ስምንት 381
ኢራቅንና መካከለኛው ምሥራቅን ወደ ዲሞክራሲ የማሸጋገር ህልም 381
እስራኤልና የኢራቅ ጦርነት 388
ሎቢውና የኢራቅ ጦርነት 397
ለምታመነታዋ አሜሪካ ጦርነቱን መሸጥ 405
በኢራቅ ላይ የስለላ መረጃዎችን ማሰባሰብ 417
እውን የኢራቅ ጦርነት የነዳጅ ዘይት ጦርነት ነውን? 422
ክልሉን ወደ ዲሞክራሲ የማሸጋገር ህልም 424
መካከለኛው ምስራቅን እንደገና ከማደራጀት አንጻር 429
ማጠቃለያ 432

ምዕራፍ ዘጠኝ 439
በሶሪያ ላይ የተነጣጠረ ዒላማ 439
ሶሪያ የምታሳድረው ስጋት 441
እስራኤልና የጎላን ከፍታዎች 445
ቱልአቪቭና ደማስቆ ከመስከረም 11 በኋላ 453
ሎቢውና ደማስቆ ከመስከረም 11 በኋላ 455
ቡሽ ያቅማሙት ለምንድን ነው? 460
ማጠቃለያ 464

ምዕራፍ አስር 467
ኢራን ዒላማ ውስጥ ገብታለች 467
መጋጨት ወይስ መስማማት 472
የክሊንተን አስተዳደርና ዱዋል ኮንቴይንመንት 478
የቡሽ አስተዳደርና የኢራንን አጣዝ የመለወጥ ሃሳብ 487
እስራኤልን ከጥቃት ለመታደግ ከጎኗ መቆም 492
አማራጮች 498
የመጨረሻው መጥፎ አማራጭ 506

ምዕራፍ አስራ አንድ.....511
ሎቢውና ሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት.....511
ከጦርነቱ በፊት የተነደፈው እቅድ.....514
ታላቁ ድጋፍ እያለ ምን ጎድሎ![13].....518
ስትራቴጂያዊ ስህተት.....523
በዩ.ኤስ. አሜሪካ ጥቅም ላይ የደረሰ ጉዳት.....528
የጦር ሕግጋትን መጣስ.....534
የሎቢው መራር እርምጃ.....545
የአሜሪካ ሕዝብና ሊባኖስ.....553
እውን እስራኤል የአሜሪካን ትዕዛዝ ትፈጽማለች?.....556
ማጠቃለያ.....559
ምን ይደረግ?.....559
የ.ዩ.ኤስ. አሜሪካ ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?.....562
የተለየ ስትራቴጂ- ‹‹ከጠረፍ ማዶ ያለ አረጋጊ ኃይል››.....565
-እስራኤልን እንደማንኛውም መንግሥት መመልከት.....570
የእስራኤል- ፍልስጤማውያንን ግጭት ማብቃት.....572
የሎቢውን ተጽዕኖ ማለዘብ.....584
ሎቢውን ማዳከም?.....585
ሎቢውን መቃወም?.....586
ይበልጥ ግልጽነት የሚንጸባረቅበትን.....587
አዲስ የእስራኤል ሎቢ ማቋቋም?.....591
የመጨረሻው አስተያየቶች.....595

መቅድም

‹‹ሁሉንም ጉዳዮችህን በተመለከተ መልስ ሳታገኝላችው ረዥም ጊዜ ካስቆጠሩ ነገሮች መጨረሻ ላይ አሁንም ሆነ ወደፊት የጥያቄ ምልክት ማስቀመጥህ ተገቢ ነው::›› ቦርትራንድ ሩሴል

እ.አ.አ. በ2002 ማብቂያ ላይ ‹‹ዘ -አትላንቲክ መንዝሊ›› የተባለው እውቅ መጽሔት የእስራኢልን ሎቢ[1] እና በዩ.ኤስ. አሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ አስመልክቶ አንድ መጣጥፍ ቢጤ እንድናዘጋጅ ጋበዘን፡፡ ሆኖም ግን እኛ ይህንን ግብዣ ከተወሰነ ቁጥብነት ጋር ነበር የተቀበልነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ጉዳይ አወዛጋቢ እንደመሆኑ በዚህ ርዕስ ዙሪያ የሚደረጉና የእስራኤልን ሎቢ የሚፈትሹ እንዲሁም ዩ. ኤስ አሜሪካ ለእስራኤል የምታደርገውን ጭፍን ድጋፍ ወይም ደግሞ የራሷን የእስራኤልን ፖሊሲ የሚመረምሩ መጣጥፎች ከባድ ቁጣና ኃይለኛ አጸፋ እንደሚያስነሱ ጠንቅቀን ስለምናውቅ ነበር፡፡ የሆነ ሆኖ ይህ ጉዳይ በተለይም ደግሞ ከመስከረም አስራ አንዱ ጥቃትና ከኢራቅ ጋር እየተደረገ ካለው ጦርነት በኋላ ለረዥም ጊዜ ችላ ተብሎ የሚቆይ እንዳልሆነ ይሰማን ነበር፡፡ ዩ.ኤስ. አሜሪካ ለእስራኤል የምታደርገው ግልጽ ድጋፍ በመካከለኛው ምሥራቅ ጸረ-አሜረካ ለሆኑ አቋሞች መነሻ፣ እንዲሁም ከዋና ዋና ስትራቴጂያዊ አጋሮቻችን ጋር ባለን ግንኙነት የውጥረት ምንጭ ሆኖ እስከተገኘ ድረስና የእስራኤል አጋር የሆኑ ቡድኖችና ግለሰቦች በዩ.ኤስ. አሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ላይ ተፅእኖ ማድረጋቸውን እስከገፉበት ድረስ ይህን ጉዳይ በግልጽና በአደባባይ ልንወያይበትና መፍትሄም ልናበጅለት ይገባል።

---

[1] *"የእስራኤል ሎቢ› ተብሎ ከዚህ በኋላ እስከመጨረሻው የመጽሐፉ ገጽ የሚጠቀሰው ስያሜ ከእስራኤላውያንና የአይሁድ ማህበረሰብ የተወሰኑ ክፍሎች በአሜሪካ ውስጥ የሚገኙ ታላላቅ የፖለቲካ ሰዎችን፣ ሴናተሮችን፣ ሀገረ ገዢዎችን፣ ሚኒስትሮችን እና በአሜሪካ ፖለቲካ ላይ ተጽዕኖ ሊያመጡ ይችላሉ የሚባሉ ሰዎችን በማባበልና በማግባባት ይህም ካልተቻለ በማስፈራራትና ስማቸውን በማጥፋት የእስራኤልን ጥቅም እንዲያስጠብቁ የማድረግ ሂደት ወይም አግባብ ነው፡፡ (ተርጓሚው)*

ከዚያ በኋላ በቀጠሉት ሁለት ዓመታት ይህን መጣጥፍ ለማዘጋጀት ሙከራችንን ያገዘ ለቀቅ እያደረግን ከአትላንቲክ መንገዘሊ ዋና አዘጋጆች ጋር በመሆን የገፋንበት ሲሆን፣ ቅድመ ስምምነታችንን ታሳቢ ያደረጉና የእነርሱንም አስተያየቶች ያካተቱ ረቂቅ ጽሑፎቻችንን ላክንላቸው። ዳሩ ግን ይህ ከሆነ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ የአትላንቲክ መጽሔት ዋና አዘጋጅ ይድነቃችሁ ብሎ ይህን ረቂቅና ቀጣዮቹንም ሥራዎቻችንን በመጽሔቱ ላይ ላለማውጣት የወሰነ መሆኑን ገለጸልን።

እኛም በዚህ ሁኔታ ተስፋ ባለመቁረጥ መጣጥፎቻችንን ለተለያዩ ጋዜጦች መላካችን አልቀረም። ሆኖም ግን ሁሉም በሚያስደንቅ ሁኔታ ተመሳሳይ አቋም በመያዝ አንድም ጽሑፋችን በያዘው ጭብጥ፣ አለያም ደግሞ ረዥም መሆኑን ሰበብ እያደረጉ እንደማያትሙት ገለጹልን። በዚህ መሀል እልህ ምላጭ ያስቆረጥማል እንዲሉ እነዚህን መጣጥፎች ወደ መጽሐፍ የመቀየር ሀሳብ ብልጭ ብሎልን የተወሰነ ርቀት መጓዛችን አልቀረም። ዳሩ ግን በመጀመሪያው ሙከራችን ያጋጠሙን መሰናክሎች ይህን ጽሑፍ ተጨማሪ ጊዜና ጉልበት ዋጅተን በመጽሐፍ መልክ እንድናዘጋጀው ግፊት አልፈጠሩብንም ነበር። ስለሆነም ይህን ጉዳይ ለጊዜው ወደጎን ብለን ትኩረትታችንን ወደ ሌሎች ስራዎቻችን አዞርን።

እንደዚያም ሆኖ የተወሰነና አጠር ተደርጎ የተዘጋጀ የረቂቅ ጽሑፋችን ቅጂ “ቴሚንግ አሜሪካን ፓወር ” በተባለና በስቴፈን ኤም ዋልትስ በሚዘጋጅ መጽሔት 2005 እትም ላይ ወጥቷል። (ስቴፈን ከዚህ መጽሐፍአዘጋጆች አንዱ ነው።)

ይህ በእንዲህ እያለም በጥቅምት 2005 ከአንድ አሜሪካዊ ምሁር ጋር ተገናኝተን መጣጥፋችንን ‹ለንደን ሪቪው ኦቭ ቡክስ› በተባለው መጽሔት እንድናሳትመው ሀሳብ አቀረበልን። በአትላንቲክ መንገዘሊ ላይ የሚሠራ አንድ የሚያውቀው ሰው ውድቅ የተደረገብንን መጣጥፍ ቅጂ እንደላከለትና መጣጥፉ የለንደን ሪቪው አዘጋጅ የሆነችውን ሜሪ ኬይ ዊልመርሰንን እንደሚያስደስታት ገለጸልን። እኛም ወዲያውኑ የመጣጥፋችንን ቅጂ ለሜሪ የላክንላት ሲሆን፣ እርሷም ልታትመው እንደምትፈልግ ወዲያውኑ ነበር የገለጸችልን። ከሌላ ዙር የማሻሻልና የማስተካከል ሥራ በኋላ ይህ አሁን

"የእስራኤል ሎቢና በዩ.ኤስ አሜሪካ የውጭ ፖ.ሊሲ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ" የሚሰኝ ጽሑፍ በለንደን ሪቪው የመጋቢት 23/2006 እትም ላይ ለመውጣት ቻለ። ይህንን ጽሑፍ ባነበበና አስተያየቱን ባካፈለን አንድ ምሁር አነሳሽነትም ሁሉንም የጽሑፉን ክፍል በሀርቫርድ የጆን ኤፍ ኬኔዲ ስኩል ኦፍ ገቨርንሜንት ድረ ገጽ ላይ እንዳለ ለቀቅነው። ይህን ያደረግነው የለንደን ሪቪው መጽሔት የግርጌ ማስታወሻዎችን በስፋት ሊያስተናግድልን ስላልቻለና እኛም ያቀረብናቸው አሳማኝ የሆኑ ማስረጃዎችና የመከራከሪያ ሀሳቦች ከታማኝ ምንጮች ያገኘናቸው መሆናችንን ለአንባቢዎቻችን ለማሳወቅ ፈልገን ስለነበር ነው። እርግጥ ነው በመጣጥፋችን ያነሳናቸው ጭብጦች መደባበስና መሸፋፈን ያልታየባቸውና ፊት ለፊት የተቀመጡ ናቸው። ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል በገፍ የምታቀርበውን ቁሳዊና ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ካብራራን በኋላ፣ ይህ ድጋፍ ራሱ በስትራቴጂያዊም ሆነ ሞራላዊ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ያልተገለጸ መሆኑን ለማሳየት ሞክረናል። ከዚያ ይልቅ ድጋፉ የተደረገው በስፋት በሚካሄደው የእስራኤል ፖለቲካዊ ሎቢ ጫና እንዲሁም የአሜሪካን የውጭ ፖ.ሊሲ ላይ ተጽእኖ በማሳረፍ ለእስራኤል በሚበጅ መልኩ እንዲራመድ ግፊት በሚያደርጉ ግለሰቦችና ቡድኖች ምክንያት ነው።

እነዚህ አካላት በየጊዜው በሚያደርጉት ጫና አሜሪካ ሁልጊዜም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በሁሉም መልኩ እስራኤልን እንድትደግፍ ማድረግ የቻሉ ሲሆን፣ በአሜሪካ የውጭ ፖ.ሊሲ ላይ ስውር እጃቸውን በማሳረፍ በእስራኤልና ፍልስጥኤም ውዝግብ፣ ታላቅ የሕዝብ እልቂትና ፖለቲካዊ ድቅቀት ባስከተለው የኢራቅ ወረራ፣ እንዲሁም እስካሁንም ድረስ ተደባብሶ በቀጠለው አሜሪካ ከኢራንና ሶሪያ ጋር ባላት ፍጥጫ ላይ ወሳኝ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ። እኛ እዚህ ላይ የምንሰጠው አስተያየት እነዚህ በቅጡ ያልተጠኑ የአሜሪካ የውጭ ፖ.ሊሲዎች የራሷን ጥቅም የማያስከብሩ፣ በረዥም ጊዜ ሁኔታው ሲሰላ ደግሞ ለእስራኤልም ቢሆን የማይበጁ ናቸው እያልን ነው።

በኢንተርኔት የለቀቅነው መጣጥፋችን ያስገኘልን አዎንታዊ አጸፋ ትንፋሽ ቀጥ አድርጎ የሚያቆም ነበር። በሐምሌ 2006 ብቻ የኬኔዲ ስኩል ድረ

ገጽን ተጠቅመው የእኛን ጽሑፍ ያነበቡ ሰዎች ቁጥር 275,000 ደርሶ ነበር። ከዚያም በለንደን ሪቪው ላይ የወጣውን ጽሑፍ አስመልክቶም እጅግ ብዙ የሆኑ የእንተርጉመውና የእናባዛው ጥያቄዎችም ጎረፉልን። አስቀድመን እንደገመትነውም ይህ መጣጥፍ እንደተለቀቀ በሎቢው ዋና ዋና አንቀሳቃሽ አካላት አካባቢ ታላቅ ፖለቲካዊ አቧራ በማስነሳቱ ከዚህም ከዚያም የሰላ ሂስ ይሰነዘርብን ጀመር። እንዲያውም ጉዳዩ ከዚያም ፈቀቅ ብሎ ኢየሩሳሌም ፖስት፣ ኒውዮርክ ሰን፣ ዎል ስትሪት ጆርናልና ዋሽንግተን ፖስትን በመሳሰሉ ታዋቂ ጋዜጦች ፀረ-ሴማዊ አቋም ያለን መሆኑ እየተጠቀሰ ክፉኛ ተብጠለጠልን። ‹‹ዘ ኒው ሪፖብሊክ›› የተባለው ጋዜጣ ደግሞ አራት የተለያዩ መጣጥፎችን በአምዶቹ በአንድ ጊዜ በማውጣት መዓቱን አወረደብን። ከዚህም ጋር ተያይዞ የታሪክ መፋለሶችን እንዳስከተልን ተደርገን ኢ-ርቱእ በሆነ አኳኋን ትችት ይሻርጎደጎድብን ጀመር።

ጥቂት የማይባሉ ሀያሲያን ደግሞ ‹‹ይህ መጣጥፍም ሆነ አዘጋጆቹ በቅርቡ የሚያስታውሳቸው አጥተው ጨለማ ውስጥ ይጣላሉ" እስከማለት ርቀው ነበር የሄዱት።

ሆኖም ግን ይህን ሲሉ ተሳስተው ነበር። ምክንያቱም እጅግ ብዛት ያላቸው አይሁዳውያንና አይሁድም ያልሆኑ አንባቢያን የእኛን ጽሑፍ ደግፈው ቆመው ነበርና። እርግጥ ነው በጽሑፋችን ውስጥ ባቀረብነው በእያንዳንዱ ነጥብ ላይስማሙ ይችላሉ። ሆኖም ግን ከሞላ ጎደል የሁሉም ስምምነት በአንድ ነገር ላይ አርፎ ነበር። ይኸውም የማይካውን መንካታችንና የማይተቸውን ደፍረን መተቸታችን ጉዳዩን ርቆ እንዲሄድ የሚያደርግና ለውይይትም በር የሚከፍት በመሆኑ ነው። ይህን ጉዳይ አስመልክተን መገመት እንደቻልነው ከዩናይትድ ስቴትስ ውጪ የነበረው አጸፋ እንደአጠቃላይ ጥሩ የሚባል ሲሆን በእስራኤል በራሷ ውስጥም እንኳ የተወሰኑ አዎንታዊ አስተያየቶችን አግኝተናል ማለት ይቻላል።

ለአብነት ያክል እኛን የሚደግፉና ጥሩ ግምት የሚሰጣቸው መጣጥፎች በኒው ዮርክ ታይምስ፣ በፋይናንሺያል ታይምስ፣ በኒውዮርክ ሪቪው ኦቭ ቡክስ፣ በቺካጎ ትሪቡዩንና ኒውዮርክ ኦብዘርቨርን በመሳሰሉት ጋዜጦችና መጽሔቶች ወጥተዋል። ይህ አወዛጋቢ ጉዳይ በመጨረሻ እስራኤል ውስጥ

በሚታተመው ‹‹ሃ-ኤሬትዝ›› ጋዜጣና በአሜሪካን አገርም በብሔራዊው የሕዝብ ሬዲዮ ማለፊያ የሚባል ሽፋን ተሰጥቶት ነበር፡፡ ስመጥር የሆነው “ፎሬን ፖሊሲ” የተባለው ጋዜጣ በሐምሌ 2006 ሲምፖዚየም ያዘጋጀ ሲሆን፣ ዋሽንግተን ፖስት ሰንደሪ መጽሔት ደግሞ በሐምሌ ወር እኛ ባነሳነው ጉዳይ ላይ ሁነኛ ሽፋን ሰጥቶ ተችቶበታል፡፡

በ2006 ዓመት ስለ እስራኤልና ዩ. ኤስ አሜሪካ በመካከለኛው ምሥራቅ ስለምታራምደው ፖሊሲ በግልጽ መነጋገሩና ሀሳብን ማንሸራሸሩ እየጨመረ ሲሄድ ይታይ ነበር፡፡ ከዚህም በላይ አይሁዳውያኑ በአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ላይ ሎቢ በማድረግ ስለሚያሳድሩት ተጽዕኖም መናገሩ ቀላል እየሆነ ሄዶ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው እንደአጠቃላይ እኛ ባሠራጨነው ጽሑፍ ምክንያት ነበር ለማለት ባንደፍርም፣ የእኛ ተጽእኖ እንዳለ ግን መታወቅ አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግን እስራኤል በ2006 በጋዛ ላይ የከፈተችውና ሊባኖስን እጅጉን ያፈራረሳት ጦርነት፣ በኢራቅ የቀጠለው ድቀት፣ “ለፓልስታይን አፓርታይድ ሳይሆን ሰላም” የሚል ርዕስ ሰጥተው ጂሚ ካርተር ያሳተሙት መጽሐፍ፣ እንዲሁም በአሜሪካና በኢራን መካከል የቀጠለው የቃላት እንካስላንቲያና ሎቢውን አስመልክቶ ትችት ያቀረቡ ሰዎችን ዝም የማሰኘት ወይም ስማቸውን የማጥፋት ከንቱ ሙከራዎች ለዚህ የውይይት በር መከፈት የየራሳቸውን ሚና ተጫውተዋል፡፡

መግቢያ

አሜሪካ ወደ ምርጫ የምትገባበት ዓመት ተቃርቧል። በእርግጥ ሁኔታዎች በዚህ ደረጃ ላይ እያሉ ስለውጤቱ መናገር ቢያስቸግርም የምርጫውን አንዳንድ ገጽታዎች ከወዲሁ ለመገመት ግን የሚከብድ አልነበረም። ተወዳዳሪዎቹ የጤና ፖሊሲን፣ ውርጃን፣ የግብረሶዶማውያን ጋብቻን፣ ግብርን፣ ትምህርትን፣ የስደተኞችን ጉዳይ በመሳሰሉት የተለያዩ የሀገር ውስጥ ጉዳዮች ልዩነቶችን ማንጸባረቃቸው የሚጠበቅ ነገር ነው። እንዲሁም የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን በተመለከተ ሞቅ ያሉ ክርክሮች መነሳታቸው አይቀርም። ከእነዚህም መካከል አሜሪካ በኢራቅ አንባር ከእንግዲህ ልታራምደው የምትችለው አቋም ምንድን ነው? በዳርፉር ለተፈጠረው ሰብአዊ ቀውስ ምን መፍትሔ ይኖራል? የኢራን ኒኩሊየር ሕልም፣ ሩሲያ ከኔቶ ጋር የገባችው ፍጥጫና የቻይና አስፈሪ እድገት ያስነሳው ተግዳሮት፣ ዩናይትድ ስቴትስ የዓለምን ሙቀት መጨመር ከመቋቋም አኳያ የምታበረክተው አስተዋጽኦ፣ ሽብርተኛነትን መዋጋትና በዚህ አንባር ባለፉት ዓመታት የተሸረሸረውን ገጽታዋን እንዴት ማደስ ይቻላታል? የሚሉትና ሌሎችም አጀንዳዎች የፖለቲካውን ምህዳር ያግሉታል ተብሎ ይገመታል።

ሆኖም ግን አንድን ጉዳይ በተመለከተ ተወዳዳሪዎች ሁሉ ተመሳሳይ አቋም እንደሚኖራቸው አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል። አዎን! በ2008ቱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ውድድር ልክ እንደ ቀድሞዎቹ የውድድር ዘመናት ሁሉ እያንዳንዱ ተወዳዳሪ ለእስራኤል በሕልውና መቆየትና ጠላቶቿን የመከላከል መብቷን ለማስከበር የማይቋረጥ ድጋፉን ሊሰጣት ዝግጁ እንደሆነ በሙሉ ስሜት ይገልጻል ። ሀገሩ ዩናይትድ ስቴትስም ለዚያች ትንሽ የአይሁዳውያን ሀገር በህልውና መቀጠል ሙሉ በሙሉ መቆሟን በአንክሮ ያሳውቃል። እያንዳንዱ ወንድም ሆነ ሴት ተወዳዳሪ እስራኤልን ፊት ለፊቷ ተደቅኖ ለህልውናዋ የሚያስፈራትን አደጋ ሁሉ አንድ በአንድ በመጋፈጥ በማንኛውም ሁኔታና አጋጣሚ ጥቅሞቿን አሳልፎ እንደማይሰጥ ምሎ እየተገዘተ ያስረዳል። ከተወዳዳሪዎቹ ሁሉ አንዱም ቢሆን እስራኤልንና

የምታራምዳቸውን ፖሊሲዎቿን ለመተቸት አይሞክርም። እንዲሁም ዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ በክልሉ አወቃቀር ፍትሀዊ አቋም እንድትይዝ እንደሚሞከር በመግለጽ አስተያየት ለመስጠት አይዳዳም። ይህን የሚያደርግ ደፋር ሰው ብቅ ቢል በፊት ለፊቱ እንደሚወድቅና "የአንድ ወቅት የአሜሪካ ፖሬዚዳንታዊ ምርጫ ተወዳዳሪ" የሚል ማዕረግ ብቻ ይዞ እስከወዲያኛው እንደሚቀር ያውቀዋል።

ይህ አስተያየት ምናልባት ድፍረት የተሞላበት ትንበያ ይመስል ይሆናል። ሆኖም ግን ለፕሬዚዳንታዊ ተወዳዳሪነት የታጩ ሥዩማን 2007 ላይ ለእስራኤል የሚኖራቸውን ድጋፍ በግልጽ አሳውቀዋል። ሂደቱ የተጀመረው ገና ጥር ላይ ነበር። እነዚህ ተወዳዳሪዎች ለዓመታዊው የሄርዝሊያ ኮንፈረንስ በሳተላይት አማካይነት ባቀረቡት ንግግር የጀዊሽ ዊክ ጋዜጣ ሪፖርተር የሆነው ጆሽዋ ሚትኒክ እንደታዘበው "የአይሁዳውያኑን ሀገር ማን ይበልጥ ከጠላቶቿ ሊታደጋት እንደሚችል ለማሳመን የተደረገ ፍልሚያ ይመስላል" ብሏል። በዚያው የሳተላይት መስኮት ብቅ ብለው አቋማቸውን ካሳወቁት ፖለቲከኞች አንዱ የ2004ቱ የዲሞክራቲክ ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት እጩ ጆን ኤድዋርድስ ሲሆኑ፣ ለእስራኤላውያኑ አድማጮቻቸው "የእናንተ የወደፊት ዕጣ ፈንታ የእኛም ዕጣ ፈንታ ነው" አሉ። ከዚያም ቀጠል አድርገው፡- "በዩናይትድ ስቴትስና በእስራኤል መካከል ያለው ግንኙነት ፈጽሞ አይበጠስም" በማለት አከሉ። የቀድሞው የማሳቹሴስ አገረ ገዢ ሚት ሮምኒ ደግሞ ,,በምወዳት ሀገር ውስጥ ያላችሁ የምወዳችሁ ሕዝቦች!" በማለት ንግግራቸውን ጀምረው የኢራን ኒኩሌር መታጠቅ የእስራኤል አቢይ ስጋት መሆኑን በማጤን እንደሚከተለው አሉ፡- "ለዓለም ሶስት እውነታዎችን የምንናገርበት ጊዜው አሁን ነው። አንደኛ ኢራን መቆም አለባት። ሁለተኛ ኢራንን ማቆም ይቻላል። ሶስተኛ ኢራን እንድትቆም ይደረጋል!" የፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ዋነኛ ተቀናቃኝ በመሆን እስከመጨረሻው የገፉት የአሪዞናው ሴናተርና የሪፖብሊካን ፓርቲ ተወካይ ጆን ማኬይን በተራቸው "የእስራኤልን ሕልውና መከላከልን በተመለከተ ለድርድር የምናቀርበው ነገር አይኖርም" ሲሉ አቋማቸውን ገለጹ። የቀድሞው የምክር ቤት አፈ ጉባዔና የጆርጂያው ሪፐብሊካን ተወካይ ኒዊት

ጊንግሪች ደግሞ እንዲህ ሲሉ ደሰኮሩ፡- ‘‘እስራኤል ምናልባትም ከ1967ቱ ድል በኋላ ታላቅ ከሆነ አደጋ ፊት ለፊት ቆማለች ’’[2]…

ይህ ከሆነ ከአጭር ጊዜ በኋላ በየካቲት ወር መጀመሪያ ላይ የኒውዮርክ ዲሞክራቲክ ፓርቲ ተወካይና ሴናተር ሂላሪ ክሊንተን ከፍተኛ ተደማጭነት ባለው የአሜሪካን እስራኤል ፐብሊክ ኦፌርስ ኮሚቴ አይፓክ ፊት ቀርበው እንዲህ አሉ፡- ‹‹በዚህ ለእስራኤል አስቸጋሪና እጅግ አደገኛ በሆነ ጊዜ … አስፈላጊው ነገር ከአጋሮቻችንና ከጓደኞቻችን ከናንተ ጋር መቆምን ከፍ ያለ ዋጋ ለምንሰጠው ነገር እንደመቆም የምንቆጠረው መሆኑ ነው፡፡ እስራኤል የሃይማኖት መሠረተኝነት፣ ጽንፈኝነት፣ ጨቋኝነትና ሽብርተኝነት በተንሰራፋበት በዚያ ምድር፣ ልክ እንደ ወደብ ላይ የማማ መብራት በብርሃን ጸዳል የፈካች የዲሞክራሲ አምባ ናት፡፡"[2]

የክሊንተን ዋነኛ ተቃዋሚ እና የኤሊኖይ ግዛት የዲሞክራቲክ ፓርቲ እጩ ሆነው የቀረቡት ሴናተር ባራክ ኦባማ ከአንድ ወር በፊት የአይፓክ አባላት በተገኙበት ቺካጎ ውስጥ ንግግር አድርገው ነበር፡፡ ኦባማ ፍልስጤማውያን ባለፉት በርካታ ዓመታት ያሳለፉትን ስቃይና መከራ እንደሚገነዘቡላቸው በመግለጽ፤ ሆኖም ግን እስራኤልንና ህልውናዋን በተመለከተ ከሌሎች ተፎካካሪዎቻቸው ባልተለዩ መልኩ ጽኑ አቋም እንዳላቸው አብራርተው የዩናይትድ ስቴትስንና የእስራኤልን ግንኙነት በተመለከተ አንዳች ለውጥ እንደማያደርጉ በአጽንኦት አሳወቁ፡፡[3] ሌሎቹ የፕሬዚዳንታዊው ምርጫ ተስፈኞች የካንሳሱ ሪፖብሊካን ሴናተር ካራውንባክና የኒው ሜክሲኮው አገረ ገዥ ቢል ሪቻርድሰን ከሌሎቹ ተፎካሪዎቻቸው እኩል ወይም በበለጠ ሁኔታ የእስራኤል ደጋፊነታቸውን የሚያሳይ ግለት ያለው ንግግር አቀረቡ፡፡ [4]

ይህ ሁኔታ ምንድን ነው የሚያሳየን? እነዚህ ፕሬዚዳንታዊ እጩዎች የተለያዩ ጉዳዮችን አስመልክተው በያዟቸው አቋሞች አይንና ናጫ ሆነው

---

[2] ከዚህ በኋላ እስከ መጽሐፉ የመጨረሻ ገጽ ድረስ የዚህን ኮሚቴ ስም አይፓክ (ኤ.አይ.ፒ.ኤ.ሲ) በማለት በአህጽሮት የምናወሳው መሆኑን ያጤኗል (ተርጓሚው)

እርስ በእርሳቸው ሲሻኮቱ እስራኤልን በተመለከተ ግን ከሞላ ጎደል አንድ ዓይነት አቋም ሊይዙ የቻሉት እንዴት ነው? ሁኔታቸውን ግራ የሚያደርገው ደግሞ ወቅቱ ዩናይትድ ስቴትስ በመካከለኛው ምሥራቅ የምትከተለው ፖሊሲ የተንሻፈፈና ዝብርቅርቁ የወጣ መሆኑ ግልጽ የሆነበትና የራሷ የእስራኤል ዜጎች ሳይቀሩ የመንግሥታቸውን ፖሊሲዎች በጥልቀት እየተቹ የሚገኙበት ጊዜ መሆኑ ነው። ታዲያ እነዚህ የአሜሪካን ፕሬዘዳንታዊ መንበር ለመቆናጠጥ የቋመጡ ሰዎች ሌሎች ሃገራት በግልጽ እያደረጉት እንዳለው ለምን ሃቁን ለማስቀመጥ ያመነታሉ? ከዓለም ሀገራት ሁሉ መሐል እስራኤል ብቻ የአሜሪካን አመራር በሚዘውሩ ፖለቲከኞች ይህን ያክል ድጋፍ ለምን ልታገኝ ቻለች?

ጥቂት ሰዎች ይህ ሊሆን የቻለው እስራኤል ለዩናይትድ ስቴትስ ስትራቴጂያዊ አጋር በመሆኗ ነው ይላሉ። እርግጥ ነው እስራኤል በአሸባሪነት አንፃር ጠቃሚና ዋኛ አጋር መሆኗ አይካድም። ሌሎች ደግሞ፡- ‹‹እስራኤልን ለመደገፍ የሚያበቃን ታላቅ የሆነ ሞራላዊ ምክንያት አለን። እርሱም የእኛን እሴቶች የምትጋራ በክልሉ የምትገኝ ብቸኛ ሀገር ስለሆነች ነው›› ይላሉ። ሆኖም ከዚህ በላይ ከቀረቡት መከራከሪያዎች መሐል አንዳቸውም በጥልቀት የተፈተሹና ውሃ የሚያነሱ አይደሉም። አሸባሪነትን በተመለከተ ዋሽንግተን ከእየሩሳሌም ጋር ያደረገችው ቅርርብ ጉዳዩን ይበልጥ አባብሶት እንደሆነ እንጂ፣ ፈጽሞ ቀላልና ያልተወሳሰበ ብልሀትን በማስገኘት ሽብርተኝነትን ድል ለማድረግ አላስቻለም። ይህም በአንፃሩ ዩናይትድ ስቴትስ የበለጠ ዒላማ ውስጥ እንድትገባ በማድረግ ብቻ ሳይወሰን በመላው ዓለም ከሚገኙ ጠቃሚ አጋሮቿ ጋር ያላትን ግንኙነት እጅጉን በመጉዳት ለጥላቻ ዳርጓታል። የሆነ ሆኖ ቀዝቃዛው ጦርነት አብቅቷል። እስራኤልም ለአሜሪካ ጠቃሚ አጋር ሳትሆን ስትራቶጂያዊ እዳ ሆና ብቅ ብላለች። እንደዚያም ሆኖ ይህንን ፀሐይ የሞቀው ሀቅ በአደባባይ በግልጽ ለመናገር ወኔ ያለው ፖሊቲከኛ እስካሁን አልታየም።

አሜሪካ እስራኤልን እንዳትተች የሚደረግበትና በሁለቱ መካከል ያለው ጉዳይ ለድርድር የማይቀርብ ሆኖ የሚቀጥልበት ሞራላዊና መሠረታዊ ምክንያት አሁንም ግልጽ አይደለም። እርግጥ ነው የእስራኤል ህልውና

አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ በሕልውና እንድትቀጥል መርዳት የአሜሪካ ሞራላዊ ግዴታ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ግን እስራኤል በኃይል በያዘቻቸው የፍልስጥኤማውያን መሬቶች ውስጥ በፍልስጤማውያኑ ላይ ከልክ ያለፈ ግፍ እየፈጸመች ባለችበት ጊዜ ዩናይትድ ስቴትስ ለሁለቱም ወገኖች ፍትሀዊ እጇን መዘርጋት፣ ይበልጡንም ደግሞ ግፉአኑን ፍልስጤማውያን ማገዝ በተገባት ነበር። ሆኖም ግን እንዳለመታደል ሆኖ በዩናይትድ ስቴትስ ነጩ ቤተመንግሥት ፕሬዚዳንት ሆኖ ለመሾም ወይም የኮንግረስ አባል ሆኖ ለመመረጥ ከሚሻ ማንም ፖለቲከኛ ሰው ይህን የመሰለ አቋም እስካሁን አላየንም። እንዲህ ዓይነቱ ስሜት ሲንጸባረቅም አላስተዋልንም።

የአሜሪካ ፖለቲከኞች ይህን ጉዳይ በፍርሃት እንዲይዙት ያደረጋቸው እውነተኛው ምክንያት የእስራኤል ሎቢስቶች የሚያሳድሩት ፖለቲካዊ ተጽእኖ ነው። ይህ ሎቢ በመከከላቸው ላላ ያለ የሚመስል ትስስር ባላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች የተደራጀ አካል ሆኖ የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ፖሊሲ እስራኤልን በሚጠቅም መንገድ እንዲዘወር በትጋት የሚሠራ ነው። ቀጥሎ ባሉት ተከታታይ ምዕራፎች በስፋት የምናወሳው እንደመሆኑ፣ ይህ ሎቢ የሚያደርግ አካል በአንድ ማዕከላዊ አሠራር ሥር ያለ አንድ ነጠላ ድርጅት እንዳለመሆኑ የዩናይትድ ስቴትስን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ሁሉ በአድማና በሴራ ይቆጣጠራል ማለትም ያሳስታል። ከዚያ ይልቅ ይህ ሎቢ አድራጊ አካል ተጽእኖ መፍጠር የሚችሉ ሰዎች በፍላጎት የተሰባሰቡበትና አይሁዳውያንና አይሁዳውያን ያልሆኑ ሰዎችንም በማሳመን የእስራኤልን ጉዳይ አስመልክቶ የአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ እርሷን በሚጠቅም አቅጣጫ እንዲራመድ የሚሠራ መሆኑ ነው ሃቁ። የሎቢው የተለያዩ ቡድኖች ምንም እንኳን ዩናይትድ ስቴትስና እስራኤል የተለየ ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚጥሩ ቢሆንም፣ በሁሉም ጉዳዮች ላይ ተመሳሳይ አቋም የሚያራምዱ ግን አይደሉም። ልክ ሌሎች በጎሣ የተደራጁ ሎቢ አድራጊ ቡድኖችና በጋራ ፍላጎት ዙሪያ የተሰባሰቡ ሰዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ የእስራኤል ሎቢ የተለያዩ ከፍሎች በሕጋዊው የዲሞክራሲ ባህል የሚንቀሳቀሱና በአሜካውያን የቆዩ ፖለቲካዊ ጨዋታ የተካኑ ናቸው።

በዚህም ምክንያት የእስራኤል ሎቢ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ቀስ በቀስ እየተደራጀና ጡንቻውን እያፈረጠመ የሄደና በፖለቲካው ጨዋታ ውስጥ

ሚና ለማግኘት የሚሹ ሁሉ ፍላጎቱን የሚያዳምጡለት መሆኑ ተሳክቶለታል፡፡ እናም ይህን ሎቢ የሚያሸክሩት ግለሰቦችና ቡድኖች፣ ስለ እስራኤል በጥልቀት የሚጨነቁና የሚያስቡ ሆነው የአሜሪካ ፖለቲከኞችም ይህንን ጉዳይ እንዳይተዉ ለማድረግ ሁሉንም ዓይነት ጥረት የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ትችት እንዲኖር ቢፈቅዱ እንኳን ብዙ ርቀት የማይጓዝና የእስራኤልን ጥቅም የማይፃረር እንዲሆን ይሻሉ፡፡ ነገሩ ምፀት ቢመስልም፣ እነዚህ አካላት የዩናይት ስቴትስ መሪዎች እስራኤልን ልክ እንደ አምሳ አንደኛ ግዛታቸው እንዲቆጥሯት ነው የሚፈልጉት፡፡ ዲሞክራቶችም ሆኑ ሪፖብሊካኖች አንዳንድ ጊዜ ከተለመደው አሠራር ፈቀቅ ብለው ከተገኙ የሎቢውን ኩርኩም እንዳይቀምሱ ይፈራሉ። ይህን የሎቢውን አሠራር ባህል ተጻርሮ የቆመና የተገዳደረ ማንም ቢሆን ፕሬዚዳንት የመሆንን ዕድል ፈጽሞ አያገኝም፡፡ ሴናተር ወይም የምክር ቤት አባል መሆንም አይሳካለትም፡፡

ሎቢውና የዩናይትድ ስቴትስ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲ

የሎቢው የፖለቲካ አቅም ጠቃሚ የሚሆነው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ለመሆን የሚወዳደሩ ሰዎች በሚናገሩት ነገር ላይ ተጽእኖ ለመሳደር ብቻ ሳይሆን፣ በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ በተለይም የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲን በተመለከተ ሚና ለመጫወት ጭምር ነው። አሜሪካ ሁኔታዎች ቶሎ ቶሎ በሚለዋወጡበት በዚያ ክልል የምትወስደው እርምጃ በመላው ዓለም ይበልጡንም በአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች ዘንድ ትልቅ መዘዝ ያስከትላል፡፡ ቡሽ ሳይታሰብ ኢራቅን በመውረር ያስከተሉት ሁልቆ መሳፍርት የሌለው ጥፋት፣ የሕዝቦችን ሰቆቃ፣ የአሥር ሺዎችን ሞት፤ የመቶ ሺዎችን ደግሞ ሀገር ጥሎ መሰደድና መንከራተት ያጤኗል፡፡ ያ ጦርነት ለዩናይትድ ስቴትስ ለራሷ እስራቴጂያዊ ውድመት ያስከተለባት ሲሆን፣ በክልሉ ውስጥም ሆነ ከክለሉ ውጭ ለሚገኙ አጋሮቿ አደጋ እንደደነቀባቸው መገንዘብ አይከብድም፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ መቋጫው መቼና በምን ሁኔታ እንደሆነ መገመት ይከብዳል፡፡

ዩናይትድ ስቴትስ በመካከለኛው ምሥራቅ ካሉ ሀገራት ጋር ግንኙነት የጀመረችው ነፃ ሆና ከተመሠረተች በኋላ ብዙም ሳትቆይ ነው። በተለይም ደግሞ ሚስዮናውያን ትምህርት እናስተምራለን በማለት በክልሉ ውስጥ የሃይማኖት ተልዕኳቸውን ለማስፈጸም ላይና ታች ሲሉ መቆየታቸውም እውነት ነው። እነዚያ አካላት በይበልጥም በቅዱሳን መጻሕፍት ተነግሯል በሚባለው ማርና ወተት የምታፈስ ቅድስት አገር ተረት የናወዙ አይሁዳዊያን ወደ ፍልስጤኤም ምድር ከተለያዩ የዓለም ማዕዘኖች እየመጡ እንዲሰፍሩ እገዛ አድርገውላቸዋል። ይሁን እንጂ ይህ ግንኙነት አሁን በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሚታየውን ዓይነት ዓይን ያወጣ ወገንተኝነት እንደሚያስከትል ቢታወቅ ኖሮ፤ ያኔ ጉዳዩ እንደዘበት ባልታየ ነበር። ይህ ክስተት በእርግጥም አሁን አሜሪካና እስራኤል ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የተለዩ ግንኙነት እንዲመሠረቱ መሠረት ጥሏል።[5] እንደዚያም ቢሆን በአረብ ባህር አካባቢ ይዘዋወሩ የነበሩና አረመኔዎች (Barbarian) የሚል ቅጽል የተሰጣቸው የባሕር ላይ ነጣቂዎች ከ200 ዓመታት በፊት ሲንቀሳቀሱ በነበሩበት ጊዜና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መካከል የዩናይትድ ስቴትስ መሪዎች አንዳች ዓይነት ፍላጎት በክልሉ ላይ አላሳዩም። [6]

ውድሮው ዊልሰን በ1917 የወጣውን የባልፎር ዲክላሬሽን (ታላቋ ብሪታኒያ የፍልስጥኤምን ምድር ለሁለት መከፈል አስመልክቶ ያቀረበችው ሰነድ) የደገፉ ቢሆንም፤ ያንን ለማስፈጸም ያደረጉት አንዳች ነገር አልነበረም። በወቅቱ ዩናይትድ ስቴትስ በክልሉ ትርጉም ያለው ሥራ ሠርታለች ከተባለ በ1919 በተካሄደው የፓሪስ የሰላም ኮንፈረንስ መሠረት በሄኔሪ ቸርችል ኪንግ እና ቻርለስ ክሬን የሚመራ ቡድን ወደ ክልሉ መላኳና ያ ቡድንም የሀገሬው ሰዎች (ፍልስጤማውያን) የጽዮናውያንን እንደ አዲስ መደራጀትና ራሱን የቻለ የአይሁድ ሀገር መቋቋሙን በጽኑ እንደሚቃወሙ የሚገልጽ ዘገባ ይዞ እንዲመለስ ማድረጓ ነው። የታሪክ ምሁሯ ማርጋሬት ማክሚላን እንደገለጹት፡- ‹‹በዚያ አካባቢ የሚሆነውን ጉዳይ አስመልክቶ ማንም ትኩረት አልሰጠውም›› ብለዋል። እርግጥ ነው በጊዜው ዩናይትድ ስቴትስ የክልሉን የተወሰነ ክፍል በሞግዚትነት እንድታስተዳድር አደራ የተጣለባት

መሆኑ ቢታወቅም፣ ያንን ኃላፊነት ያስፈጸመ አካል ስላልነበረ ታላቋ ብሪታኒያና ፈረንሳይ አቶማን ቱርኮችን ካስወጡ በኋላ አካባቢውን ተቀራመቱት።። [7]

ዩናይትድ ስቴትስ ወሳኝና በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን ሚናዋን በክልሉ መጫወት የጀመረችው ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ሲሆን፣ ይህ የሆነውም በመጀመሪያ በነዳጅ ዘይት መውጣት፣ ከዚያም በመቀጠል በጸረ-ኮሚኒዝም አነሳሽነት፣ ከዚያ በኋላ ደግሞ ከእስራኤል ጋር በፈጠረችው ቁርኝት ምክንያት ነው። አሜሪካ የፀጥታ ፖለቲካ ላይ የመጀመሪያውን ወሳኝ ጣልቃ ገብነት በክልሉ ያደረገችው በ1940ዎቹ አጋማሽ ላይ ከሳዑዲ አረቢያ ጋር ባደረገችው እያደገ የሄደ ግንኙነት ነበር። (ሁለቱም ወገኖች እንግሊዞች በክልሉ ውስጥ ለመቆየት ያላቸውን ፍላጎት ለማወቅና ለማረጋገጥ መፈለጋቸው በግልጽ ይታይ ነበር)። ሌሎቹ መልካም አጋጣሚዎች ደግሞ ቱርክ በ1952 የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን (NATO) አባል መሆኗ እንዲሁም በ1954 የተደረገው የባግዳድ ጸረ-ሶቬት ስምምነት (Baghdad pact) ናቸው። [8]

የአሜሪካ መሪዎች በ1948 እስራኤል እንደ ሀገር እንድትፈጠር ከደገፉ በኋላ በአረብና እስራኤል መካከል ሚዛናቸውን ጠብቀው መጓዙን የፈለጉ ሲሆን፣ እስራኤልን በግልጽ ከመደገፍ በመቆጠብ በክልሉ ያላቸውን ስትራቴጂያዊ ጥቅም ማስቀደሙን መርጠዋል። ሆኖም ግን ይህ ፖሊሲያቸው በተለይም ከስድስቱ ቀን ጦርነት በኋላ እየተቀየረ መጥቷል። ለዚህም ዋነኞቹ ምክንያቶች ሶቪዮቶች በክልሉ ለሚገኙ የአረብ ሀገራት በየጊዜው የሚሸጡት የጦር መሣሪያ ያመጣው ተጽእኖና አይሁዳውያን በአሜሪካ ፖለቲካ የሚያሳድሩት ጫና (ሎቢ) እያደገ መምጣቱ ነው።

ከ1967 የስድስቱ ቀን ጦርነት በኋላ ጎላ ብሎ የሚታይና አከራካሪ የሆነው የአሜሪካ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲ ከእስራኤል ጋር ያላት ግንኙነት ነው። ላለፉት አራት አሥርት ዓመታት አሜሪካ ለእስራኤል የሰጠችውን ቁሳዊና ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ካየን ለሌሎች አገሮች ያደረገችውን ሁሉ ድንክዬ የሚያደርግ ነው። ይህ ድጋፍ በምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ

ያልተገደበና እስራኤል የፈለገችውን ነገር ብታደርግ ብዙ ለውጥ የማያሳይ ነው። በተለይ ደግሞ የአሜሪካ እርዳታ እስራኤል በፍልስጤማውያን ላይ ጫና እንድትፈጥርና መከራቸውን እንድታበዛ የሚያደርግ መሆኑ ሲታሰብ ሁኔታው እጅግ ሀዘን ላይ ይጥላል። ይህም ሲሆንና ሲባል አሜሪካ አልፎ አልፎም ቢሆን እጅግ የተጋነነና የዓለምን ትኩረት የሚስብ ነገር በእስራኤል በኩል ሲፈጸም፣ ለምሳሌ በምዕራባዊው ወንዝ ዳርቻ ተጨማሪ ግንባታዎችንና መንደሮችን ስትሠራ እንድታቆም ጫና ማሳረፏ አልቀረም። ምንም እንኳን ከአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች ሁሉ ቢል ክሊንተንና ጆርጅ ደብሊው ቡሽ ፍልስጤማውያን የራሳቸውን መንግሥት እንዲመሠርቱ በግልጽ መደገፋቸው ቢታወቅም፣ ማንኛቸውም ቢሆኑ ይህን ሐሳብ ወደ ተግባር ለመቀየር የአሜሪካንን ጉልበትና የዲፕሎማሲ አቅም ሲጠቀሙ አልታዩም።

ዩናይትድ ስቴትስ በተጨማሪም በመካከለኛው ምሥራቅ በየጊዜው ለእስራኤል የሚመቹና የእርሷን ጥቅም የሚያስከብሩ ፖሊሲዎችን በመንደፍ በስፋት ስትንቀሳቀስ ቆይታለች። ለምሳሌ ከ1990ዎቹ ጀምሮ አሜሪካ በኢራን ላይ የምታራምደው ፖሊሲ በተከታታይ በእስራኤል አመራር ላይ በተቀመጡ መንግሥታት ፍላጎት ከባድ ተጽዕኖ ሲያርፍበት ቆይቷል። ቴህራን ከአሜሪካ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማሻሻል የተለያዩ ሙከራዎችን አድርጋለች። ሆኖም ግን እስራኤልና ዋሽንግተን ውስጥ ያሉ ደጋፊዎቿ እነዚህ በሁለቱ ሀገራት መካከል በየጊዜው የሚጀመሩ ድርድሮችና የመለሳለስ አዝማሚያዎች እንዲከሽፉ በማሴር ሀገራቱ ተራርቀው እንዲቆዩ ማድረግ ተሳክቶላቸዋል። ከዚያም በተጨማሪ በ2006 በጋ ላይ እስራኤል ሊባኖስን ባጠቃች ጊዜ የቡሽ አስተዳደር ያሳየው ባህሪ ሌላው ምሳሌ ነው። በዓለም ላይ የሚገኙ ሀገራት ሁሉ ይህን የእስራኤልን ድርጊት በመኮነን ከ1000 በላይ ሰላማዊ ሰዎች የተገደሉበትን የጭካኔ ተግባር አውግዘው ከሊባኖስ ጎን ሲቆሙ አሜሪካ ግን ያን ለማድረግ አልደፈረችም። ከዚያ ይልቅ እስራኤል በጦርነቱ እንድትገፋበት ዋና ዋና የሚባሉት የፓርቲ መሪዎች በግልጽ ድጋፍ ሰጥተዋል። ይህ ማስተዋል የጎደለው የአሜሪካ ድርጊት የአሜሪካ ደጋፊ በመሆኑ የሚወቀሰውን የቤይሩት መንግሥት አዳክሞ ሂዝቡላህን በማጠናከር ኢራን እጇን በሰፊው

እንድታስገባ መንገዱን ጠርጎላታል። እንዲሁም ኢራን፣ ሶሪያና ሂዝቡላህ እንዲተባበሩና ለዋንሸንግተንም ሆነ ለእስራኤል መልካም ያልሆነ ጉድኝት እንዲያበጁ አስችሏል።

በአሁኑ ጊዜ አሜሪካ እስራኤልን ለማስደሰት ስትል የምትከተላቸው ፖሊሲዎቿ ብሔራዊ ደህንነቷን ስጋት ላይ የሚጥል ዋጋ እያስከፈሏት ይገኛሉ። ገደብ ያልተበጀለትና አሜሪካ ለእስራኤል የምታደርገው ድጋፍ እንዲሁም እስራኤል የፍልስጤማውያንን መሬት ይዛ ለረዥም ጊዜ የቆየችበት ሁኔታ በዓረቡና በሙስሊሙ ዓለም ፀረ አሜሪካ አቋም እንዲጠናከር አድርጓል። የዚህ አዝማሚያ ተጽእኖ አሜሪካ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሽብርተኝነት ጥቃት ሰለባ እንድትሆን በማድረግ እዚህም እዚያም ስጋት ደቅኖባታል። ይህ ሁኔታ ደግሞ አሜሪካ የኢራንን የኑክሌር ግንባታ ለማስቆም ጥረት እንዳታደርግና ፊቷን ወደ ሌሎች ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች እንዳታዞር ወጥሯታል። ምክንያቱም አሜሪካ ሰፊ በሆነው የዓረቡ ዓለምና የመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ተቀባይነቷ እጅግ የወረደ ሲሆን፣ ከእርሷ ጋር በተወሰኑ የጋራ ጥቅሞች ስምምነት ያላቸው የአረብ ዓለም መሪዎች ሳይቀሩ በግልጽ ከእርሷ ጋር መተባበሩን በመፍራት ሲያመነቱ ይታያልና። እንግዲህ ይህ ሁሉ ነገር ሲደማመር ዩናይትድ ስቴትስ በክልሉ በየጊዜው የሚከሰቱ ፖለቲካዊ ተግዳሮቶችን (Political Challenges) በቅጡ እንዳትይዛቸውና እንዳትጋፈጣቸውም አጣብቂኝ ውስጥ መግባቷ እውነት ሆኗል።

ይህ ሁሉ በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ክስተት የተፈጠረው እስራኤል በምታደርገው ሎቢ ምክንያት ነው። ለምሳሌ ሌሎች የራሳቸውን ፍላጎት ለማሳካት የሚጥሩ እንደ ኩባ አሜሪካውያን፣ አየርላንድ አሜሪካዊያን፣ አርሜኒያ አሜሪካውያንና ሕንድ አሜሪካውያን ያሉ ማህበረሰቦች የአሜሪካን የውጭ ፖሊሲ ለእነርሱ በሚጠቅም መልኩ ለማዞር (ሎቢ ለማድረግ) ቢሞክሩም ጥረታቸው የሚሳካላቸው የራሷን የአሜሪካን ብሔራዊ ጥቅም የማይጋፋ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ብቻ ነው። የእስራኤላውያን ሎቢ ግን የአሜሪካና የእስራኤል ጥቅም አንድና ተመሳሳይ

መሆኑን ብዙ አሜሪካውያን እንዲያምኑ ለማድረግ አስችሏል። እውነታው ግን የሁለቱ ጥቅም አንድና ተመሳሳይ ያለመሆኑ ነው።

ምንም እንኳን ይህ መጽሐፍ ትኩረት ሰጥቶ የሚዳስሰው የእስራኤል ሎቢ በዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ፖሊሲ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳትና በአሜሪካ ጥቅሞች ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተጽእኖ ቢሆንም፣ የሎቢው ተጽእኖ ለራሷ ለእስራኤልም ቢሆን ጎጂ መሆኑን ለማሳየት ይሞክራል። ለምሳሌ እስራኤል በፍልስጤማውያን መሬት ላይ አዳዲስ የሠፈራ መንደሮችን መገንባቷን አስመልክቶ ሊዮን ዋይሰልቲየር የተባሉ የእስራኤል ደጋፊ የሆኑ ፀሐፊ ሳይቀሩ ‹‹ ሞራላዊና እስትራቲጂያዊ ስህተት ያለበት እርምጃ››[9] ብለውታል። አሜሪካ ቀደም ባሉት ዘመናት በፋይናንስና በፖለቲካ አንፃር በእስራኤል ላይ ተጽእኖ በማሳረፍ እስራኤል አዳዲስ መንደሮችን በፍልስጤማዊያኑ መሬት ላይ እንዳትገነባ ማሳመን ችላ ቢሆን ኖሮ፤ ዛሬ የእስራኤል ሁኔታ የተሻለ ሊሆን በቻለ ነበር። ፍልስጥኤማዊያንም የራሳቸውን አገር መሥርተው በሰላም እንዲኖሩ ባስቻላቸው ነበር። ሆኖም ግን ዋሽንግተን ይህን ሳታደርግ ቀርታለች። ምክንያቱም በነጩ ቤተ-ምንግሥት የሚቀመጥ የትኛውም ፕሬዚዳንት ይህን ተግዳሮት መጋፈጥና ማስፈጸም ብዙ ዋጋ ስለሚያስከፍለው ነው። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በ2006 እስራኤል በሊባኖስ ላይ የከፈተችው ውጊያ በወታደራዊ ስትራቴጂ ስህተት ያለበትና ለስኬት የማያበቃት መሆኑን ዩናይትድ ስቴትስ እያወቀች እንዳትገፋበት ጫና በማሳደር ፋንታ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ድጋፏን መቸሯ እስራኤል ለደረሰባት የሞራልና ወታደራዊ ኪሣራ ተጠያቂ ያደርጋታል። እንግዲህ በተጨባጭ እንደሚታየው በክልሉ ያለው የፖለቲካ አካሄድ ጤናማ እንዳይሆንና ምስቅልቅል እንዲፈጠር ከኋላ ሆኖ በስውር እጁ የሚገፋው የአይሁዳዊያኑ ሎቢ የእስራኤልን የረዥም ጊዜ ዕድልና ተስፋ አደጋ ላይ የሚጥል ሆኖ ቀጥሏል።

ሎቢው የሚሠራበት የተለየ መንገድ

የአይሁዳዊያን ሎቢ በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ያስከተለውን ተፅእኖ በዩናይትድ ስቴትስ የመገናኛ ብዙሃን መናገርም ሆነ መጻፍ እጅግ ከባድ ከመሆኑ የተነሣ ‹‹ ፀረ ሴማዊ ›› ወይም ‹‹ ለአይሁዳዊያን የግል ጥላቻ ያለው ›› የሚል ስያሜ ሳይሰጠው ማንም ይህንን ማድረግ አይችልም፡፡ ይህም ልክ የእስራኤልን ፖሊሲዎች ወይም አሜሪካ ለእስራኤል የምታደርገውን ግልጽ ድጋፍ ጥያቄ ውስጥ ማስገባት እንደማይቻለው ማለት ነው፡፡ በዚህም የተነሣ አሜሪካ ለእስራኤል የምታደርገው ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ ያልወደቀበት ድጋፍ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ጥያቄ ውስጥ አይገባም፡፡ ምክንያቱም በሎቢው ውስጥ ያሉ ቡደኖች ይህን ጉዳይ አስመልክቶ በይፋ ውይይት መክፈት ስትራቴጂያዊና ሞራላዊ ጥያቄ አስነስቶ የሁለቱን አገሮች ግንኙነት የሚያሻክር አሳራ እንዳይቀሰቅስ ስለሚሰጉና ያ እንዳይሆን በትጋት ስለሚሠሩ ነው፡፡

የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር የጻፉትና ‹‹ለፓለስታይን አፓርታይድ ሳይሆን ሰላም›› (Palestine peace Not apartied) የተባለው መጽሐፋቸው ለዚህ አባባል ጥሩ ማሳያ ነው። ካርተር በዚህ መጽሐፍ በግላቸው የሚሠማቸውንና በፖለቲካው ምህዳር ውስጥ የቆዩ እንደመሆናቸው አገራቸው በሰላሙ ጥረት መጫወት ስለሚገባት ሁኔኛ ሚና ባለፉት ሶስት አሥርት ዓመታት የነበራቸውን ተሞክሮ ጨምቀው በማቅረብ የበኩላቸውን ለመወጣት ሞክረዋል፡፡ ምክንያታዊ የሆኑ ሰዎች እርሳቸው ያቀረቧቸውን ማስረጃዎች ሊያጠያይቁ እንዲሁም ባቀረቧቸው የመደምደሚያ ሀሳቦች ላይስማሙ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ የእርሳቸው ዋነኛ ግብ እንደ አንድ ቅንና የማንም ተጽእኖ እንዲያርፍበት የማይፈቅድ ነፃ አሳቢ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ ነበር፡፡ ካርተር ከዚህም በላይ ፈቀቅ ብለው እስራኤል በክልሉ እንደ ሀገር ታውቃና ሰላሟ ተጠብቆ የመኖር መብት እንዳላት አብራርተዋል፡፡ እንደዚያም ሆኖ ‹‹እስራኤል በኃይል በያዘቻቸው የፍልስጥኤም መሬቶች ላይ የምታራምደው ፖሊሲ በደቡብ አፍሪካ ለዘመናት ሰፍኖ የቆየውን የአፓርታይድ ሥርዓት ያስታውሳል ›› በማለት ደፍረው ለመጻፍ ችለዋል፡፡ ካርተር በተጨማሪም

እስራኤል የሰላሙን መንገድ ታራምድ ዘንድ አሜሪካ ጫና እንዳታሳድርባት ‹‹የእስራኤልን ፖሊሲ የሚደግፉ የተለያዩ አካላት በአሜሪካ መንግሥት አመራሮች ላይ ተጽእኖአቸውን በማሳረፍ ጉዳዩን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያወሳሰቡት ነው›› በማለት ወቅሰዋል፡፡ በዚህም ድርጊታቸው ካርተር ታላቅ የሆነ የስም ማጥፋት ዘመቻ ተከፈተባቸው፡፡ ‹‹ፀረ-ሴማዊ›› ተብለው በአደባባይ መጠቀሳቸው ሳያንስ ‹‹የአይሁዳዊያን ጠላት›› የሚል መጠሪያም ተሰጥቷቸዋል፡፡ አንዳንድ ተቺዎች እንዲያውም ካርተርን ‹‹የናዚ ደጋፊ›› እስከማለት ርቀው ሄደዋል፡፡[10]

የሎቢው ጥረት እንዳለ ሆኖ ቁጥራቸው ቀላል የማይባልና ወደ 40 ከመቶ የሚሆኑ አሜሪካዊያን በመላው ዓለም የተፈጠረው ፀረ-አሜሪካ አቋም ዋነኛ ምክንያት አሜሪካ ለእስራኤል የምታደርገው ድጋፍ መሆኑን ያምናሉ፡፡[11] ከዚህም በላይ በርካታ ቁጥር ያላቸው አሜሪካዊያን ሎቢው በዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ ሁልጊዜም አዎንታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል ብለው እንደማያምኑ ይናገራሉ፡፡ በብሔራዊ ደረጃ በአክቶበር/ 2006 በተደረገ ጥናት፣ ጥናቱ ካቀፋቸው ሰዎች መካከል 39 ከመቶ የሚሆኑት፣ አይሁዳዊያን በኮንግረስ እና በቡሽ አስተዳደር ላይ በሚያደርጉት ሎቢ ምክንያት የአሜሪካ መንግሥት ኢራቅን ለመውረር መብቃቱንና አሁንም ከኢራን ጋር መፋጠጡን እንደሚያምኑ ገልጸዋል፡፡[12] በ2006 በአሜሪካዊያን ዓለም አቀፋዊ ግንኙነት ምሁራን በተደረገ ጥናት መሠረት መጠይቅ ከቀረበላቸው ሰዎች 66 ከመቶ የሚሆኑት የእስራኤል ሎቢ በዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ እጅግ ታላቅ ተጽእኖ እንዳለው ገልጸዋል፡፡[13] ምንም እንኳን አሜሪካዊያን እንደ አጠቃላይ ለእስራኤል የሀዘኔታ ስሜት ያላቸው ቢሆንም፤ ከእነርሱ ውስጥ ብዙዎቹ የእስራኤልን የተወሰኑ ፖሊሲዎች እንደሚተቹና እስራኤል የምትፈጽማቸው ድርጊቶች ከአሜሪካ ጥቅም ጋር የሚጋጩ ከሆነ የሚደረግላት እርዳታ ሁሉ እንዲቋረጥ የሚፈልጉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

የእስራኤልንና አሜሪካን ልዩ ወዳጅነት በተመለከተ በሕዝቡ ዘንድ ይፋዊ ውይይት ቢደረግና ሀሳቦች ያለምንም ገደብ የሚንሸራሸሩበት ሁኔታ ቢፈጠር ሕዝቡ የበለጠ መረጃ ሊያገኝ በቻለና የሁለቱን ሀገራት ቅጥ ያጣና የተዛባ

ግንኙነት በስፋት ባወቀ ነበር። ማንም ሰው ቢሆን ሕዝቡ ለእስራኤል ሎቢና ለራሷ ለእስራኤል ያለውን አቋም ሲገነዘብና በሌላ በኩል ፖለቲከኞችና የፖሊሲ አርቃቂዎች እስራኤልን ለመተቸት ያለመፈለጋቸውን ሲያውቅ፣ እንዲሁም አሜሪካ ለእስራኤል በምትሰጣት እርዳታ ውስጥ የራሷን የአሜሪካን ጥቅም የሚያስከብር ቅድመ ሁኔታ የማታስቀምጥ መሆኑን ሲረዳ ይገረማል። አሜሪካዊያን ፖለቲከኞች እስራኤልን ከመስመር ወጥተው እንዲደግፏት የአሜሪካ ሕዝብ የማይፈልግ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ሆኗል። ሁኔታውን በዚህ መንፈስ ካየነው ሕዝቡ ስለእስራኤል በሚያስበውና በዋሽንግተን የሚገኙ ባለሥልጣናት በሚያራምዱት ፖሊሲ መካከል ታላቅ ገደል አልለ።

ለዚህ ታላቅ ሽለቆ መፈጠር ዓይነተኛውን አስተዋጽኦ ያበረከተው በፖለቲካው ጥልፍልፍ ውስጥ ስውር እጁን በመክተት አደገኛውን ድብብቆሽ መጫወቱን የቀጠለው ሎቢ አድራጊው አካል ነው። ይህ አካል በዲሞክራቶችና ሪፖብሊካኖቹ የፖሊሲ አውጪ ፖለቲከኞች ላይ ብቻ ሳይሆን በአሜሪካን ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት (Capitol Hill) ላይ ጭምር ተጽእኖ መፍጠር ችሏል።[14] ለእስራኤል ሀዘኔታ አለኝ የሚሉ አንድ የኮንግረስ አባል ማይክል ማሲንግ ለተባለ ጋዜጠኛ እንደነገሩት ከሆነ፡- ‹‹ከ250--300 የሚሆኑ የኮንግረስ አባላት አይፓክ (የአሜሪካን እስራኤል፣ ፐብሊክ አፌርስ ኮምቴ) የሚፈልገውን ነገር ለማስፈጸም ዝግጁ ናቸው›› ። በተመሳሳይ ሁኔታ ስቲቨን ሮሰን የተባሉ የቀድሞ አይፓክ አባልና የአሜሪካን መንግሥት ሰነዶች በቀጥታ ለእስራኤል መንግሥት አሳልፈው በመስጠት የተከሰሱ ሰው ጀፍሪ ጎልድበርግ ለተባለ የኒውዮርከር ጋዜጣ አዘጋጅ የአይፓክን ጉልበት ሲገልጹለት ከፊት ለፊቱ ላይ ናፕኪን አስቀምጠው እንዲህ አሉ፡- ‘‘በዚህ ናፕኪን ላይ ሰባ የሚሆኑ ሴናተሮችን ፊርማ በ24 ሰዓታት ውስጥ በቀላሉ ልናሰባስብ እንችላለን።’’[15] ይህ ተራ የሆነ ጉራ አልነበረም። በተደጋጋሚ ሲሆንና ሲደረግ እንደታየው የአሜሪካ ኮንግረስ የሎቢውን አቋም በመደገፍ አብዛኛውን ጊዜ አስደንጋጭ በሆነ የአብላጫ ድምፅ ውሳኔዎችን ሲያሳልፍ ቆይቷል።

የእስራኤልንና ሎቢ አስመልክቶ መወያየት ከባድ የሆነው ለምንድን ነው?

ዩናይትድ ስቴትስ የብዙሃን ዲሞክራሲ ተግባራዊ የተደረገባት ሀገር እንደመሆኗ የመናገርና የመደራጀት መብት የተከበረ ነው። በዚህም ሳቢያ በፍላጎታቸው የተደራጁ የተለያዩ ቡድናት ባለፉት ዘመናት የፖለቲካውን ሂደት መቆጣጠራቸው የማይቀር ነበር። ከተለያዩ ሀገራት ወደ አሜሪካ የተሰደዱ ሕዝቦች በጎሣና ከፍ ሲልም የዘር መስመርን ተከትለው መሟደንና መደራጀታቸውም እንዲሁ የሚጠበቅ ነበር። ይህም የአሜሪካን የውጭ ፖሊሲ በተለያዩ መንገዶች መፈታተኑና ተጽእኖ ለማሳደር መሞከሩ እያደር የሚታይ ሂደት መሆኑ አልቀረም።[16] ለምሳሌ ኩባ አሜሪካውያን በካስትሮ አስተዳደር ላይ አሜሪካ ማዕቀብ እንድትጥል ግፊት አድርገዋል። አርሜንያ አሜሪካዊያንም በበኩላቸው በ1915 ኦቶማን ቱርኮች ያደረሱባቸውን ጭፍጨፋ እንደ ዘር ፍጅት ቆጥራ እውቅና እንድትሰጣቸው በአሜሪካ ላይ ጫና አሳርፈዋል። ከዚያም አልፈው አሜሪካ ከአዘርባጃን ጋር ያላትን ግንኙነት እንድታቋርጥ ጎትጉተዋል። ሕንድ አሜሪካዊያን ደግሞ አሜሪካ ከሕንድ ጋር በቅርቡ ያደረገቻቸውን የኒኩሊየር ስምምነቶች ደግፈው ሰልፍ ወጥተዋል። ይህንና ይህን የመሰሉ የፖለቲካ ገጽታዎች አሜሪካ እንደመንግሥት ከተመሠረተች ጀምሮ ያሉና የነበሩ ሲሆኑ፣ እነዚህን ሁኔታዎች ለማስወገድ መሞከሩ ውዝግብ ከማስከተል የዘለለ ፋይዳ አያመጣም።[17]

ሆኖም ግን ስለእስራኤል ሎቢ በይፋ ለማውራት ለአሜሪካዊያን ከባድ መሆኑ ግልጽ ነው። ለዚህ ሁኔታ ከፊሉ ምክንያት ሎቢ አድራጊው አካል በማንኛውም መንገድ በዚህ አጀንዳ ዙሪያ የሚንቀሳቀስንና ተጽእኖ ለማሳረፍ የሚሞክርን ግለሰብም ሆነ አካል ኩርኩም ከማቅመስና ፈጣን አጸፋ ከመስጠት ስለማያመነታ ነው። የእስራኤልን ሎቢ አስመልክቶ ግልጽ ውይይት እንዳይካሄድ የሚያደርጉ ሌሎች ምክንያቶችም አሉ።

የእስራኤልን ሎቢ ማጠያየቅ የራሷን የእስራኤልን በሕልውና መቆየትና ሕጋዊነት ጥያቄ ውስጥ እንደማስገባት ያስቆጥራል የሚል ስሜት ያላቸው ወገኖች አይጠፉም። ምክንያቱም ከአሜሪካ ስቴቶች የተወሰኑት አሁንም ድረስ ለእስራኤል እውቅና ለመስጠት የማይፈልጉ ሲሆን፣ እስራኤልንና ሎቢውን የሚተቹ የተወሰኑ አካላት ደግሞ እስራኤል የሚሏት ሀገር ጭራሽ መኖር እንሌለባት ይሟገታሉ። ያም ቢሆን በሌላው ጽንፍ ያሉ ብዙ ሰዎች ደግሞ ለእስራኤል መኖርና ለአይሁዳዊያን አስተማማኝ መጠለያ ገነት (Safe Haven) በመሆን ሆሎኮስትን ከመሰለ መቅሰፍት እንደምትታደጋቸው በማመን ከዚህ በተፃራሪ የቆመንና ህልውናዋን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባን ማንኛውም አካል አይታገሱም።

ይሁን እንጂ የእስራኤልን ፖሊሲዎች የሚቃወሙ አሜሪካዊያንና ደጋፊዎቻቸው የሚያስነሱት ተግዳሮት ፀረ-እስራኤል ንቅናቄ ነው ብሎ ለመደምደም ያስቸግራል። በአሜሪካዊያን የጡረተኞች ማህበር አንፃር የሚነሱ ተግዳሮቶች ፀረ- አረጋዊያን ወይም ፀረ-ጡረተኞች ሊሰኙ እንደማይችሉ ሁሉ ማለት ነው። እኛም ይህን መጽሐፍ ስናዘጋጅ የአይሁዳዊቷን አገር በህልውና የመቆየት ሕጋዊነት እየተገዳደርን አይደለም። እርግጥ ነው እስራኤል መፈጠር የለባትም የሚሉ ወይም ከአይሁዳዊ ሀገርነት ወደ ጎሣ ወይም ሕዝብ ስብስብነት እንድትቀየር የሚሹ ይኖራሉ። እኛ ግን እንደዚያ አናስብም። እንዲያውም ከዚህ ሀሳብ በተቃራኒ በመቆም የአይሁድን ሕዝብ ታሪክ የምንቀበልና በአይሁዳዊያን መንግሥት ሕልውና የምናምን ነን። የእስራኤል ሕልውና አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜም ዩናይትድ ስቴትስ ከጎኗ እንድትቆምላትም እንሻለን። የእኛ ዋነኛ ትኩረት የእስራኤል ሎቢ በዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ፖሊሲ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩና ይህም ራሷን እስራኤልንም ጭምር እንደሚጎዳት ማጉላት ነው። በእኛ እምነት ሁለቱም ጉዳዮች የሚያሳዝኑና መጨረሻቸው አስከፊ ነው።

ከዚህም በላይ የተወሰኑ ቡድኖች በይበልጥም አይሁዳዊያን በየጊዜው ጡንቻቸው እየፈረጠመና ኢኮኖሚውንም ሆነ ፖለቲካውን እየተቆጣጠሩት መሄዳቸው ብዙ አሜሪካዊያንን አልተመቻቸውም። እንዲያውም እውነቱን

ለመናገር የተወሰኑት ፍርሃትና ንዴትም እያደረባቸው ሄዷል። ለዚህ ሁኔታ መፈጠር ዋነኛው ምክንያት በቆዩት አባባሎች ‹‹የጽዮናውያን አለቆች ዓለምን በምስጢር የመቆጣጠር ፍላጎታቸውን እየተገበሩ ነው›› የሚለው ፀረ-ሴማዊ አስተሳሰብ በሕዝቦች አእምሮ መስረጹ ይመስላል።

የአይሁዳውያንን የፖለቲካ አቅም የሚመለከት የትኛውም ውይይት ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት በአውሮፓ የተደረጉ ፀረ- ሴማውያን እንቅስቃሴዎች ታሪክ ያጠላበታል። ክርስትያን የመስቀል ጦረኞች በሺዎች የሚቆጠሩ አይሁዳውያንን ከእንግሊዝና ፈረንሳይ፣ ስፔን፣ ፓርቱጋልና ሌሎች አካባቢዎች በጅምላ አስወጥተዋቸዋል። ይህም የሆነው ከ1290-1497 ባሉት ዓመታት ሲሆን፣ አይሁዳውያኑ በተወሰኑ የአውሮፓ ቁጭራ ሠፈሮች (Ghettos) ውስጥ ተፋፍገው እንዲቀመጡ ተደርጓል። ከሀሉም በላይ ግን አይሁዳውያን ብዙ ግፍ የጨለጡት ስፓኒሽ ኢንኩዊዚሽን በመባል በሚታወቀው የታሪክ ክስተት ነው። ይህውም የስፔን ካቶሊኮች፣ አይሁዳውያንና ሙስሊሞችን በያኔዋ እንደሉስያ (የዛሬዋ ስፔን) ለመኖር ከፈለጉ ሃይማኖታቸውን እንዲቀይሩ ካልሆነም አገሩን እንዲለቁ ባስገደዱበት ጊዜ ነበር። በምሥራቅ አውሮፓና በሩሲያም ቀላል የማይባል መከራ ነበር አይሁዳዊያኑ የተቀበሉት። በእነዚያ ሀገራት እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ፀረ-ሴማዊ የሆኑ አክራሪ ቡድኖች ይገኙ ነበር። ከዚያ በኋላ ደግሞ በምድር ላይ አቻ ያልተገኘለትን ፍዳ በናዚ ማጎሪያ ካምፖች ውስጥ ሆነው ተቀበሉ። አይሁዳዊያኑ በአረቦች የተወሰነ ችግር ቢገጥማቸውም ከሌሎቹ ጋር ሲነጻጸር እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። [18]

ይህን የመሰለ ረዥም የስቃይ ታሪክ ባለቤት የሆኑት የአሜሪካ አይሁዶች፣ ለዚህ ሁሉ የፖሊሲ መዘበራረቅ ተጠያቂዎች እነርሱ እንደሆኑ በመጥቀስ የሚከራከራቸውን ማንኛውም ሰው ከመጋፈጥ ወደኋላ አይሉም። ይህ መራራ የሆነ አጸፋ የማሳየት ባህሪ የተጠናወታቸው የአይሁድ ኘሮቶኮል ያቋተው ሴራ በሚጭንባቸው ትውፊት ምክንያት ነው። አይሁዶችን ዓለምን ለመቆጣጠር የቋመጡና የሚያሴሩ አድርጎ የሚስላቸው ይህ ስሜት አሁንም ድረስ በኒዎ ናዚዎችና በሌሎች ዘረኛ ስብስቦች ዘንድ በዘመናችን ተንጸባርቋል፣ እየተንጸባረቀም ነው።

በአይሁዳዊያን ላይ ከሚሰነዘሩት የፀረ-ሴማዊ ኃይላት ክሶች መካከል ባንኮችን፣ የመገናኛ ብዙሃንና በየሀገራቱ የሚገኙ ሌሎች ቁልፍ የኢኮኖሚ

አውታሮችን የመቆጣጠራቸው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም የተነሣ አንድ ሰው ‹‹በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያሉ የሕትመት ውጤቶች ከጠላቶቿ ይልቅ ለእስራኤል ያደላሉ›› ቢል፤ ‹‹ምን ይደረግ፣ ሚዲያውን ሁሉ አይሁዳዊያን ተቆጣጥረውታል›› የሚል የተለመደ አባባል (አሉባልታ) ይሰነዘርለታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሌላው ‹‹የአሜሪካ አይሁዳዊያን ለበጎ አድራጊ ሰዎችና ቡድኖች እንዲሁም ለፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ገንዘብ የማዋጣት የቆዬ የዳበረ ባሕል አላቸው፡፡" ቢል ‹‹የአይሁዳዊያን ገንዘብ በፖለቲካው ላይ ተጽእኖ ለማሳረፍ ወይም ለተንኮል መሸረቢያ እንጂ ለሌላ ተግባር አይውልም›› የሚል መልስ ቢያገኝ አይገርምም፡፡ በእርግጥ ለፖለቲካ ውድድር ገንዘብ የሚያዋጣ ማንም አካል የተወሰኑ የፖለቲካ ግቦች እንዲሳኩለት ለማድረግ የሚያልም መሆኑ ያለና የነበረ ነው፡፡ እንዲሁም በበጎ ፈቃድ የተሰባሰበ የትኛውም ቡድን ወይም ማህበረሰብ የሕዝቡን አመለካከት ለመቅረጽ ይረዳው ዘንድ የመገናኛ ብዙሀንን ሽፋን መሻቱ ተገቢ ነው፡፡ በአንድ የፖለቲካ ምርጫ ወቅት የሚጫወተው ሚና፣ ሎቢ የማድረግ ጥረትና ሌሎች ተጓዳኝ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችም ያን ያክል የሚያወዛግቡ አይደሉም፡፡ ይህ ፀረ- ሴማዊ ስሜት እንዳለ ሆኖ በፋርማሲ ባለሙያዎች፣ በህብረት ሥራ ማህበራት፣ ወዘተ... ስለሚፈጸሙ ሎቢዎች መናገር ቀላል፣ ስለ አይሁዳውያን ሎቢ ማውጋት ግን እጅግ ከባድ መሆኑን መረዳት የሚከብድ አይደለም፡፡

በዩናይት ስትቴስ ውስጥ ባሉ የእስራኤል ደጋፊ ቡድኖችና ግለሰቦች ላይ የሚነሳው ሌላው ዕድሜ ጠገብ ክስ አይሁዳዊያን ለሚኖሩበት ሀገር ታማኝ ያለመሆናቸው ክስ ነው፡፡ በዚህ የጎፈዬ ወቀሳ መሠረት ብዙ አይሁዳዊያን የሚታሙት ለአሜሪካም ሆነ ለሌላ ያስጠጋቸው ሀገር የአርበኝነት ስሜት የላቸውም፤ ከዚያ ይልቅ ለአይሁዳዊነታቸው ያደላሉ÷ እየተባሉ ነው፡፡ ዛሬ በአሜሪካ እንደ ትልቅ ስጋት የሚነሳው ‹‹እስራኤልን የሚደግፉ አይሁዳዊያን ለአሜሪካ ታማኞች አይደሉም›› የሚለው አባባል ሆኗል፡፡ ሃይመን ቡክባይንደር የሚባሉ የቀድሞው የአሜሪካ አይሁዳዊያን ኮሚቴ የዋሽንግን ተጠሪ ይህን ክስ ሲያስተባብሉ እንዲህ ብለዋል፡- ... ‹‹


አይሁዳዊያን አሜሪካዊ የአርበኝነት ስሜት ይጎድላቸዋል የሚለውን ክስ ችላ ብለን ከማለፍ በስተቀር ምርጫ የለንም፡፡ [19]

እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ይኖርብናል፡፡ እኛ የእነዚህ ሁሉ ፀረ-ሴማዊ ክሶችና ወቀሳዎች ተጋሪዎች አይደለንም፡፡

በእኛ እምነት ከሌላ ሀገር ወደ አሜሪካ የገባ ማንኛውም አሜሪካዊ ከትውልድ ሀገሩ ጋር በጽኑ መተሳሰሩ ሕጋዊ መብቱ ነው፡፡ በእርግጥም አሜሪካዊያን ጥምር ዜግነት የመያዝና ወደሌላ ሀገር ሄደው ሌላው ቀርቶ በዚያ አገር ጦር ውስጥ የመሳተፍ መብት አላቸው፡፡ ይህ የሚሆነው ግን አሜሪካ ከዚያ አገር ጋር ይፋዊ ጦርነት ላይ እስካልሆነች ድረስ ብቻ ነው፡፡ ከላይ በተገጸው መሠረት አሜሪካ ውስጥ ይህን በመሰለ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ብዛት ያላቸውና በአሜሪካ መንግሥት ላይ ተጽእና ለማድረግ ጠንክረው የሚሠሩ ቡድኖች አልሉ፡፡ እነዚህ አካላት የአሜሪካ መንግሥትና ዜጎቹ ሀገራቸውን ወይም እነርሱ የፈለቁበትን የተለየ ወገን ይደግፉላቸው ዘንድ መትጋታቸው አዲስ ነገር አይደለም፡፡ መንግሥታትም ቢሆኑ ይህን የመሰለውን ለእናት ሀገርና ለወገን የሚኖርን የፍቅር ስሜት በሚገባ ይገነዘባሉ፡፡ በዚሁ መሠረት ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚኖሩ የተለያዩ አካላት የአሜሪካ መንግሥት የእነርሱን ሀገር እንዲረዳላቸው ተጽእኖ ለማድረግ መሞከራቸው አይቀርም፡፡ ይህ ጥረታቸው ይሳካል ወይስ አይሳካም የሚለው ጉዳይ በእርግጥ አከራካሪ ነው፡፡ ተጨባጭ የሆነው ሀቅ ይህን የሚመስል ከሆነ ዘንዳ አይሁድ አሜሪዊያን ከሌሎች ሕዝቦች የሚለያቸው ጉዳይ እስከሌለ ድረስ ለሐገራቸው ለእስራኤል በማድላታቸው ተወቃሽ መሆን አለባቸው ብለን አናምንም፡፡ [20]

የእስራኤል ሎቢ አድማ ወይም ሴራ አይደለም፡፡ ከዚያ ይልቅ በእኛ እምነት የአሜሪካዊያንን የፖለቲካ ባህል ያገናዘበ ፍፁም አሜሪካዊና ህጋዊ ነው፡፡ ይህን ስንል ግን ወጣ ያሉና አነጋጋሪ የሆኑ ክስተቶችን በውስጡ አልያዘም ማለታችን አይደለም፡፡ እነዚህን ክስተቶች ነው እንግዲህ በዚህ መጽሐፍ ተከታታይ ምዕራፎች ልናነሳቸው ያሰብነው፡፡

በእኛ እምነት ይህ ሎቢ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያሉ ጠቃሚ ተቋማትን ሁሉ ለመቆጣጠር የሚያበቃው ፍፁም ጉልበት የለውም፡፡ በቀጣዮቹ ምዕራፎች ልናነሳ እንደምንሞክረው ሎቢው ሊያልፍባቸው የማይችሉ ብዙ መሰመሮች አልሉ፡፡ እንደዚያም ቢሆን ሎቢው አስደናቂ ተጽእኖ ማሳደር የሚችል መሆኑን የምንገነዘብባቸው ማስረጃዎች ብዙ መሆናቸውን ማጤን ተገቢ ነው፡፡


ՈՒՆ ՆԴԻ
Ի.ՆՈ.Ն
ՆՈՒՆՆԻ ՆԿ
ՀՈՌԱ

ምዕራፍ አንድ

አሜሪካ የእስራኤል ታላቋ አጋር

"እኛ እናንተን የምናመሰግንባቸው በቂ ቃላት የሉንም።" ይህን ንግግር በሞቀ ስሜት ያደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሳቅ ራቢን ሲሆኑ፣ ጊዜው ወርሃ ሐምሌ 1994 በሁለቱ ምክር ቤቶች የጋራ ስብሰባ ወቅት ነበር። ራቢን ንግግራቸውን በመቀጠል፦ "እናንተ ግሩም የአሜሪካ ሕዝቦች!" በማለት አድናቆታቸውን ከገለጡ በኋላ "የእናንተ ችሮታ የተሞላበት ድጋፍ፣ ችግሮቻችንን መገንዘባችሁ፣ ያደረጋችሁልን ትብብር በዘመናዊ የሰው ዘር ታሪክ አቻ የማይገኝለት ነው ማለቱን እመርጣለሁ።" አሉ። ከራቢን ያልተጠበቀ ግድያ በኋላ በቀጣዩ ዓመት እርሳቸውን የተኳቸው ቤንጃሚን ናታንያሁም እንዲሁ በተመሳሳይ የጋራ የምክር ቤቶች ስብሰባ ፊት ቆመው እንዲህ አሉ። ‘‘ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል ያደረገቻቸውን ነገሮች ሁሉ ለዚህ ጉባዔ አባላት መዘርዘር ይከብዳል። የቱን አንስቼ የቱን ልተወው? ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል ያደረገችውን ፖለቲካዊና ወታደራዊ ድጋፍ ለጊዜው ልተወውና እጅግ ታላቅና አንጸባራቂ የሆነውን የኢኮኖሚ ድጋፏን ብቻ ልናዘዝ። ለዚህ የአሜሪካ እርዳታ ምስጋና ይግባውና እስራኤል ዛሬ ጉልበቷ የፈረጠመና ዘመናዊ ሀገር ሆና ብቅ ብላለች።" ናታንያሁ ንግግራቸውን በመቀጠል እንዲህ አሉ... ‹‹ እኔ ዛሬ በዚህ ቦታ ላይ ሆኜ ስናገር የምናገረው በመላው ዓለም ያሉትን አይሁዳውያን ወክዬ ሲሆን፣ "እናንተ የአሜሪካ ሕዝቦች! በጣም እናመሰግናችኋለን" እንድል ይፈቀድልኝ ››። [1]

የእስራኤል መሪዎች የሚናገሯቸው እነዚህና መሰል ንግግሮች ከውጭ የመጣ እንግዳ ባለሥልጣን በተለምዶ የሚወረውራቸው የሽንገላ ቃላት አይደሉም። የራቢንና የናታንያሁ ቃላት ዩናይትድ ስቴትስ ለዘመናት የአይሁዳዊቷን አገር ፖለቲከኞች አንጀት ስታርስ መቆየቷን የሚገልጹ ፍፁም ከግንኙት የፀዱ አባባሎች ናቸው። አሜሪካውያን ግብር ከፋዮች ገንዘብ

የእስራኤልን ኢኮኖሚ በመደጎም በኢኮኖሚ የቀውስ ጊዜያት ሳይቀር ሲታደጋት መኖሩ ሀቅ ነው። የአሜሪካ ያልተቋረጠ ወታደራዊ ድጋፍ በጦርነት ሰዓት እስራኤል አሸናፊ ሆና እንድትወጣ የሚያግዛት ሲሆን፣ በሰላም ጊዜያት ደግሞ ሰፊና ያልተቋረጠ ፖለቲካዊ ድጋፏ መከታ ሆኗታል። በዚህም ድጋፏ እስራኤል ራሷ በየጊዜው በምትፈጥራቸው ተንኳሽና ተጋፊ አካሄዶቿ የሚደርስባትን ውግዘትና ተቃውሞ ስታዳፍንላት ኖራለች። የዩናይትድ ስቴትስ እርዳታ በተጨማሪም በአረብ እስራኤል የተራዘመ የሰላም ስምምነት ሂደት ላይ (ለምሳሌ በካምፕ ዴቪድ የተደረገውን ያጤኑዋል) እስራኤል ከግብጽና ዮርዳኖስ ጋር በፈረመቻቸው ውሎች ወሳኝ ግብአት ሆኗታል። ይህ ስምምነት ሊፀና የቻለው ሁለቱ ሀገራት ከእስራኤል ጋር በሰላማቸው ጸንተው እስከቆዩ ድረስ በየዓመቱ አሜሪካ የተወሰነ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ እርዳት እንደምትለግሳቸው ቃል በመግባቷ እንደሆነ ስናጤን እውነትም ዩናይትድ ስቴትስ የእስራኤል ታላቅ አጋር መሆኗን እንገነዘባለን።

ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ

እስራኤል ከአሜሪካ ግብር ከፋዮች ከሚሰበሰበው ገንዘብ በየጊዜው ጠቀም ያለ እርዳታ እንደምታገኝ ለማረጋገጥ በየዓመቱ የሚሰጣትን የገንዘብና የቁስ መጠን ማየቱ ብቻ በቂ ነው። ለምሳሌ በ2005 የተሰጣት ቀጥተኛ የሆነ የአሜሪካ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ድጋፍ 154 ቢሊዮን ዶላር ነበር። ይህ የኢኮኖሚ ድጋፍ እጅግ በጣም ግዙፍ መሆኑ የሚታወቀው ደግሞ ገንዘቡ የተሰጠው በቀጥታ እንጂ በብድር መልክ ያለመሆኑ ሲታሰብ ነው።[2] በቀጠዮቹ ምዕራፎች በዝርዝር እንደሚቀርበው የአሜሪካ ድጋፍ ከተጠቀሰው አሀዝ እጅግ የላቀ ነው። ምክንያቱም ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል ቀጥተኛ በሆነ የውጭ እርዳታ የበጀት ዕቅድ ያልተካተቱ ብዙ ቁሳዊ ድጋፎችን ትቸራታለችና።

እርግጥ ነው ዛሬ ላይ ሆነን ሁኔታዎችን ስንቃኝ ይህ ሁሉ ድጋፍ ‹‹ልዩ ግንኙነት›› በሚለው ማዕቀፍ ውስጥ ሳይካተት በፊት እስራኤል

ከተመሠረተች በኋላ ለብዙ አስርት ዓመታት ያህል ፈጽሞ የማይታሰብ ነበር። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት የአሜሪካ መሪዎች ለአይሁዳዊያን ሀገር ምሥረታ የሚያሳዩት ድጋፍ እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። ፕሬዚዳንት ሀሪ ትሩማን የአይሁዳዊቷ ሀገር እንድትመሠረት ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል። ይህውም በ1947 የተባበሩት መንግሥታት የፍልስጥኤም ምድር ለሁለት እንዲከፈል የሚያደርግ ዕቅድ በነደፈ ጊዜ እቅዱን በመደገፍና እስራኤልም በ1948 ስትመሠረት ከየትኛውም አገር ቀድመው እውቅና በመስጠት የእስራኤል አጋርነታቸውን በተግባር አሳይተዋል። ይህም ሆኖ የሃሪ ትሩማንና የአይዘንሃወር አስተዳደሮች ከእስራኤል ጋር በጣም መቀራረቡ ከሌሎች የአረብ ሀገራት ጋር ቅራኔ ውስጥ እንዳያስገባቸውና ይህም ሶቪየቶችን ጎትቶ በማምጣት በመካከለኛው ምሥራቅ ተጽእኖ ፈጣሪ እንዳያደርጋቸው በመስጋት በጣም ይጠነቀቁ ነበር። በዚህም የተነሣ በ1950ዎቹ ዩናይትድ ስቴትስ በእስራኤልና በአረቦች መካከል ሚዛን ጠብቃ መጓዙን መርጣ ቆይታለች። ለእስራኤል የምትሰጠውም የኢኮኖሚ እርዳታ መካከለኛ የነበረ ሲሆን፣ ወታደራዊ ድጋፍ ለመስጠት ግን እጅግ ትችገር ነበር።[3] እስራኤል የአሜሪካን የጦር መሣሪያ ለመግዛት የምታቀርባቸው ጥያቄዎችም ትህትና በተሞላበት አኳኋን ውድቅ ይደረጉ ነበር። [4]

በእነዚያ ጊዜያት ውስጥ በእስራኤልና በዋሽንግተን መካከል ኃይለኛ የሆኑ ዲፕሎማሲያዊ እሰጥ አገባዎች ይፈጠሩ ነበር። ለአብነት ያክል እስራኤል የተባበሩት መንግሥታትን ጥያቄ ወደጎን ብላ ከዮርዳኖስ ወንዝ ውሃ በቦይ ቆፍራ ወደ ግዛቷ ለመጥለፍ በሞከረች ጊዜ በወርሃ መስከረም/1953 የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ጆን ፎስተር ዱለስ ሀገራቸው ለእስራኤል የምታደርገውን ማናቸውንም ድጋፍ እንደምታቆም በግልጽ አሳወቁ። ማስፈራሪያው ውጤታማ ነበር። እስራኤል ፕሮጀክቱን ለማቆም ጥቅምት 27 ቀን መወሰኗን ግልጽ አደረገች። የሚሰጣት እርዳታም ወዲያውኑ እንዲቀጥል ተደረገ። ተመሳሳይ የሆነ የአሜሪካ እርዳታ የማቆም ማስፈራሪያም እስራኤል በ1956 በተደረገው የስዊዝ ጦርነት ከያዘቻቸው የግብጽ መሬቶች እንድትወጣ አስገድዷታል። በጊዜው የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስቴር የነበሩት ዲቪድ ቢንጎሪዬን ያንን ጦርነት ግዛት ለማስፋፋት እንደ

መልካም አጋጣሚ ቆጥረውት ነበር። ከዚያ በኋላ ግብፅን አብረዋቸው ለወረሩት የእንግሊዝና ፈረንሣይ መንግሥታት ድህረ-ጦርነት ዕቅድ እንዳላቸው ገለጹ። በዚሁ ዕቅድ መሠረት ቤንጎሪዮን ዮርዳኖስ ለእስራኤልና ለኢራቅ እንድትከፋፈል፣ እስራኤል የሊባኖስን የተወሰኑ ክፍሎች እንድታገኝ እንዲሁም የቱራንን የባህር ወሽመጥ ሙሉ በሙሉ እንድትቆጣጠር ሀሳብ አቀረቡ።[6] ይሁን እንጂ ብሪታኒያና ፈረንሣይ በግብጽ ጉዳይ ተወጥረው ስለነበር ለዚህ አዲስ ዕቅድ የሚሰጡት ጆሮ አልነበራቸውም። በሁኔታው ተስፋ ያልቆረጡት ዴቪድ ቤንጎሪዬን የእስራኤል መከላከያ ኃይል ሲናይን ከወረረ በኋላ የሀገራቸውን ምክር ቤት (ክኔሴት) ጨምሮ በተለያዩ አጋጣሚዎችና ቦታዎች እየተገኙ ይህንን ዕቅዳቸውን ይፋ ማድረጉን ተያያዙት። በዚያ ንግግራቸው የ1949ኙ የተባበሩት መንግሥታት የጦር መሣሪያን አስመልክቶ ያወጣው ስምምነት መፍረሱንና እስራኤል አሁን የያዘቻቸውን ቦታዎች መልቀቅ እንደማትሻ ገለጹ። በዚህ ጊዜ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት አይዘንሃወር ማንኛውንም ግልጽና ምስጢራዊ እርዳታ ለእስራኤል መስጠቱን እንደሚያቆሙ ባሳወቁ ጊዜ፤ ቤንጎሪዮን ደንገጥ ብለው ‹‹በመርህ ደረጃ ›› ለእስራኤል ደህንነት ዋስትና እስከተሰጠ ድረስ ከያዙት ቦታ እንደሚለቅቁ ገለጹ። ከዚያ በኋላ ግን እስራኤል በአሜሪካ ውስጥ እርሷን የሚደግፉ ሰላማዊ ሰልፎች እንዲደራጁ በማድረግ አይዘንሃወር የወሰዱትን እርምጃ በብሔራዊ ደረጃ በቴሌቪዥን ቀርበው እንዲያስረዱ አስገደደቻቸው። ከዚያም በ1957 እስራኤል ጋዛን ጨምሮ ከያዘቻቸው ቦታዎች ሁሉ በመልቀቅ በጋዛ ፀጥታዋ እንዲረጋገጥላትና በቱራን የባህር ወሽመጥም የባህር ኃይሏ እንደልቡ መቅዘፍ እንዲችል ዋስትና እንዲሰጠው አደረገች። [7]

የዩናይትድ ስቴትስና የእስራኤል ግንኙነት በ1950ዎቹ ማለቂያ ላይ መሞቅ ጀምሮ ነበር። ይህም ሊሆን የበቃው የፕሬዚዳንት ኬኔዲ አስተዳደር የእስራኤልን ፀጥታ የሚመለከት ተጨባጭ አቋም [8] በመውሰዱ ነው። በነዳር ወር 1962 ኬነዲ የእስራኤል ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበሩትን ጎልዳ ሚዮርን እንዲህ ብለዋቸው ነበር፡- "ዩናይትድ ስቴትስ በዓለም አቀፍ የፖለቲካ ምህዳር ምናልባትም ከታላቋ ብሪታንያ ጋር በሚነፃፀር ሁኔታ

ከእስራኤል ጋር ልዩ ግንኙነት ትመሠርታለች፡፡" ከዚያም አክለው ሲናገሩ "የምነግርዎት ግልጽ ሆኖለዎታል ብዬ አስባለሁ፡፡ እስራኤል ከተወረረች ዩናይትድ ስቴትስ በቀጥታ ትረዳታለች፡፡ ይህን ለማድረግ ችሎታ ያለን ሲሆን አቅማችን ወደፊትም እያደገ የሚሄድ ነው፡፡"[9] ኬኔዲ ይህን ካሉ በኋላ ሃውክ የተባለው ፀረ- አውሮፕላን ሚሳዬል ለእስራኤል እንዲሸጥላት ሲያገዘዙ ብዙም አልቆዩ፡፡ ይህ የአቋም ለውጥ የተለያዩ ስትራቴጂያዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ነበር፡፡ ሶቪዬቶች ለግብፆች የሸጡላቸውን የጦር መሣሪያ ለማመጣጠን፣ እንዲሁም የእስራኤል ኑክሊዬር የመታጠቅ ፍላጎት ለማዳፈንና የእስራኤል መሪዎች አሜሪካ የምታንቀሳቅሳቸውን የሰላም ጥረቶች እንዲቀበሉም ጭምር ለማድረግ ነው፡፡ ኬኔዲ ይህን ያደረጉበት ሌላ ግላዊ ጉዳያቸው ደግሞ በአሜሪካ ውስጥ የሚገኙ አይሁዳዊያን ለመጪው ምርጫ ድምፅ እንዲሰጧቸውና ለፖለቲካ ውድድር ገንዘብ የሚያዋጡላቸውን ከበርቴ አይሁዳዊያን በማስደሰት እጃቸውን በበለጠ ሁኔት እንዲዘረጉላቸው ለማድረግ ነበር፡፡[10] የሃውክ ሚሳየሉ ሽያጭ ሌሎች ተጨማሪ መሣሪያዎችን ለእስራኤል ለመሸጥ የድርድር በር ከፈተ፡፡ ይህም ኤም 48 ኤ የሚባሉና 200 የሚሆኑ ዘመናዊ ታንኮችን በ1964 አሜሪካ ለእስራኤል እንድትሸጥላት አስችሏታል፡፡ ይህ የአሜሪካ ድርጊት በዓረቡ ዓለም መጫጫህ እንዳያስከትልም ታንኮቹ በቀጥታ ወደ ምዕራብ ጀርመን እንዲጫኑ ተደርገው ከዚያም ወደ እስራኤል ተወስደዋል፡፡ ምዕራብ ጀርመን ለዚህ አድራጎቷ ከዩናይትድ እስቴትስ ተገቢውን ማካካሻ አግኝታለች፡፡[11]

የ1967ቱን ጦርነት ተከትሎ አሜሪካ ለእስራኤል የምታደርገው እርዳታ እያደገ ሲሄድ ይታይ ነበር፡፡ ከ1949 እስከ 1965 ድረስ በአማካይ 63 ሚሊዮን ዶላር የነበረው (ከዚህ ውስጥ ከ95 ከመቶ በላይ የሚሆነው ኢኮኖሚያዊና የምግብ እርዳታ ነበር) ከ1966 እስከ 1970 ድረስ ባሉት ዓመታት ግን በአማካይ 102 ሚሊዮን ዶላር ደረሰ። በ1971 ደግሞ ይህ አሃዝ በአስደንጋጭ ሁኔታ አድጎ 634.5 ሚሊዮን ዶላር (በግምት ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው ወታደራዊ እርዳታ ነበር) ደርሷል፡፡ በ1973 የተካሄደውና ‹‹ የዮም ኪፑር ጦርነት ›› በመባል የሚታወቀው ግብፅና እስራኤል ያደረጉት ውጊያ እስራኤል ከዩናይትድ ስቴትስ እርዳታ ከሚያገኙ

ሀገራት መካከል የመጀመሪያውን ደረጃ እንድትይዝ አደረጋት፡፡ በዚህ ጊዜ ለእስራኤል የሚደረገው ድጋፍ ከብድር ወደ ቀጥታ እርዳታ የተሸጋገረ ሲሆን፣ ከእርዳታው አብዛኛውን የሚሸፍነውም ከኢኮኖሚያዊና ቴክኒካዊ እገዛ ይልቅ ለወታደራዊው ግልጋሎት የሚውለው ነበር፡፡ እንደ አሜሪካ ኮንግረስ የምርምር አገልግሎት ባለደረባው ክላይድ ማርክ ገለጻ ከሆነ ‹‹እስራኤል ይህ የሚሰጣት የአሜሪካ እርዳታ በእርዳታ መልክ ከሚሆን በብድር ስም ቢሆን ትመርጣለች፡፡ ምክንያቱም አሜሪካውያኑ ወታደራዊ ቁሳቁሶችንና መሣሪያዎችን በእርዳታ ከሰጡ በኋላ መሣሪያዎቹ የሚገኙበትን ሁኔታ ለመመርመር በድንገት ወደ እስራኤል ስለሚመጡ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ወታደራዊ አቋሟን የመሰለል ያክል ስለሆነ እስራኤልን አያስደስታትም፡፡ እርዳታውን እንዲሁ ስናየው በቴክኒካዊ አጠራር ብድር የሚል ስያሜ ቢሰጠውም በተግባራዊ ሂደቱ ሲገመገም ግን ወታደራዊ ስጦታ ነበር ማለት ይቻላል›› ብሏል፡፡[12]

በአሁኑ ጊዜ እስራኤል በየዓመቱ በአማካይ 3 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት እርዳታ ከአሜሪካ ታገኛለች፡፡ ይህም ከአሜሪካ የውጭ እርዳታ አንድ ስድስተኛው ይሆናል፡፡ ከእስራኤል የሀገር ውስጥ አጠቃላይ ምርት (GDP) ደግሞ 2 ከመቶውን ይሸፍናል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ 75 ከመቶ የሚሆነው ወታደራዊ እርዳታ[13] ሲሆን፣ በነፍስ ወከፍ ገቢ ሲመነዘር ለእያንዳንዱ ኢስራኤላዊ በዓመት ከ500 ዶላር በላይ ይደርሰዋል፡፡ የአሜሪካን እርዳታ ከሚያገኙ ሀገራት አንፃር ይህንን አሃዝ ማነፃፀር ከተፈለገ ግብፅ በነፍስ ወከፍ ለእያንዳንዱ ግብፃዊ በዓመት 20 ዶላር፤ ፓኪስታን 5 ዶላር፤ ሄይቲ ደግሞ 27 ዶላር ያገኛሉ፡፡[14] ዋሽንግተንና እስራኤል የአሜሪካን እርዳታ ቀስ በቀስ ለመቀነስ በ1997 በደረሱበት ስምምነት መሠረት ከ1999 ጀምሮ በየዓመቱ 120 ሚሊዮን ዶላር የሚሆን እርዳታ እየተቀነሰ ቆይቷል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ቅነሳ በሌላ በኩል የወታደራዊ እርዳታውን በዓመት ከ60 ሚሊዮን ዶላር በላይ ከፍ በማድረግ እየተካካሰ ይመስላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኮንግረስ በደረሰበት ስምምነት እስራኤል ከምዕራባዊ ወንዝ ዳርቻ ከ1998 ጀምሮ ቀስ በቀስ እንድትወጣ የሚያደርግ ማዕቀፍን ለማገዝ 1.2 ቢሊዮን ዶላር ወጪ ተደርጎ እንዲሰጣት ተፈቅዷል፡፡

ይህ ሁሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በ2003 በተደረገው የኢራቅ ጦርነት እስራኤል የራሷን ዝግጅት እንድታደርግ ለማገዝ አንድ ቢሊዮን ዶላር በውጭ ወታደራዊ ፋይናንስ (Foreign Military Finance) በጀት በኩል ወጪ ተደርጎ ተከፍሏታል።[15]

በዓመት ሶስት ቢሊዮን ዶላር ለአንድ ሀገር መስጠት እጅግ ሲበዛ ቸር መሆን ነው። ሆኖም ግን አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠው እርዳታ በዚህ ብቻ ይወሰናል ብሎ ማሰብ ያሳስታል። ምክንያቱም ይህ ሶስት ቢሊዮን ዶላር የማያካትታቸው ሌሎች ጠቀም ያሉ ድጎማዎችን በተለያዩ ርዕሶችና አጋጣሚዎች እስራኤል ታገኛለችና። ስለሆነም አሃዙን በዚህ ብቻ መገደብ የአሜሪካ ግብር ከፋይ ሕዝብ ባዋጣው ገንዘብ በየዓመቱ እንደዘበት የሌላን ሀገር ኢኮኖሚ የመደጎሙን ሂደት ዝቅተኛ ግምት ያሰጠዋል። ለዚህም ነው በ1991 የኢንዲያናው የዲሞክራቲክ ፓርቲ ተወካይ ሲ- ሃሚልተን ለሪፖርተሮች ሲገልጹ የሚከተለውን ያሉት፡- "እስራኤል የአሜሪካን እርዳታ በገፍ ከሚያገኙት ሶስት ሀገራት መካከል የመጀመሪያዋ ስትሆን ይፋዊ ያልሆነውና በዓመት ውስጥ በግልጽ የምታገኘው እርዳታ አንድ ላይ ሲደመሩ በአማካይ 4.3 ቢሊዮን ዶላር ይደርሳሉ።"[16]

የአሃዙ ልዩነት ከዚህም ከፍ ሊል እንደሚችል ነው የሚገመተው። ምክንያቱም እስራኤል ከሌሎች እርዳታ ተቀባይ ሀገራት በተሻለ ቅድመ ሁኔታ እርዳታ የምታገኝ በመሆኑ ነው።[17] ብዙዎቹ የአሜሪካን እርዳታ ተቀባይ ሀገራት የተወሰነላቸው ገንዘብ በየሩብ ዓመቱ ተከፋፍሎ በአራት ጊዜያት ነው የሚለቀቅላቸው። እስራኤል ግን የተወሰነላትን ገንዘብ አዲሱ ዓመት በተጀመረ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንድታገኝ ይደረጋል።[18] ይህ በእውነቱ አንድ ሰው የዓመቱን ደመወዙን በጥር አንድ ቀን ተቀብሎ ያንን ገንዘቡንም ሁኖ ባንክ ውስጥ በማስቀመጥ ጠቀም ያለ ወለድ ከሚያገኝበት ሁኔታ ጋር ይመሳሰላል።

ምክንያቱም የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ሥራውን የሚመራው በበጀት ጉድለት እንደመሆኑ ለአንድ ሀገር የተመደበውን የእርዳታ ገንዘብ ሁሉ በመጀመሪያው የዓመቱ ወቅት አንድ ጊዜ ለማስተላለፍ ያንን ሁሉ ገንዘብ

ዝግጁ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ በኮንግረስ የምርምር አገልግሎት (Congress Research Service) እምነት ከታክስ ከፋዩ ሕዝብ ገንዘብ ላይ ለፋይናንስ አሠራሩ ማቀላጠፊያ ከ50 እስከ 60 ሚሊዮን ዶላር ያስወጣል፡፡ ምክንያቱም ገንዘቡን አንድ ላይ አሰባስቦ ዝግጁ ማድረግ ባንኮች ለብድርና ለተለያዩ ግልጋሎቶች በማዋል የሚያገኙትን ጥቅም ያሳጣቸዋልና፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እስራኤል ገንዘቡ ከተለቀቀላት በኋላ ሙሉ በሙሉ ስለማትጠቀምበትና የተረፋትንም መልሳ በአሜሪካ ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት ላይ በመዋዕለ ንዋይ (Investment) መልክ ስለምታፈሰው ከዚያ ገንዘብ ማግኘት የሚገባትን ወለድ አሜሪካ ለመክፈል ትገደዳለች፡፡ ይህም በመንግሥት ግምጃ ቤት ሰነድ ሽያጭ ሥርዓት አማካኝነት እስራኤልን ተጠቃሚ ያደርጋታል፡፡ በእስራኤል የዩናይትድ ስቴትስ ኤምባሲ ዘገባ መሠረት እስራኤል በ2004 ብቻ በዚህ ዓይነት ቀደም ብሎ ከውጪ ወታደራዊ ፋይናንስ (F.M.F) ከተለቀቀላት ገንዘብ የግምጥ ቤት ሰነድ ሽያጭ ያገኘችው የወለድ መጠን 660 ሚሊዮን ዶላር ነበር፡፡[20] ሌላው እስራኤል ጥቅም ያገኘችበት መስክ ፡- ትርፍ የጦር መሣሪያ ክምችት ሕግን (Excess Defense Article) በመጠቀም ነበር፡፡ (ይህ ሕግ ከዩናይትድ ስቴትስ ፍጆታ በላይ የሆኑ የጦር መሣሪያዎችን ለወዳጅ ሀገራት በነፃ መስጠትን ወይም በታላቅ ቅናሽ መሸጥን የሚፈቅድ ነው)፡፡ በዚሁ መሠረት በ1976 ወደ ውጪ የሚወጡ የጦር መሣሪያዎችን አስመልክቶ በወጣው ደንብ መሠረት ከተወሰነው ኮታ በታች ማለትም እስከ 250 ሚሊዮን ዶላር (የማንጓጉጥ ወጪውን አይጨምርም) ማስወጣት ይፈቀዳል፡፡ ሆኖም ግን በጎዳር 5/1990 'ለአንድ ጊዜ ብቻ' በሚል እስራኤል በትርፍነት የተያዘና 700 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ መሣሪያ ለማስወጣት ችላለች፡፡[21]

በተመሳሳይ ሁኔታ የአሜሪካ የውጭ ወታደራዊ ፋይናንስ (FMF) መርሀ-ግብር በተለምዶ አሠራር ከዩናይትድ ስቴትስ ወታደራዊ እርዳታ የሚያገኙ ሀገራት ያላቸውን (ለጦር መሣሪያ ግዢ የሚመድቡትን) ገንዘብ ሁሉ እዚሁ ዩናትድስቴትስ ውስጥ እንዲያወጡት ይጠይቃል፡፡ ይህም እርምጃ በአሜሪካ መከላከያ ተቋማት ውስጥ ያሉ ሠራተኞች ሥራ እንዲያገኙ ለማድረግ

ያግዛል፡፡ ይሁን እንጂ የአሜሪካ ኮንግረስ ይህ ደንብ እስራኤልን እንደማይመለከታት ወስኗል፡፡ በዚህም የተነሣ አሜሪካ ለውጭ ወታደራዊ ድጋፍ ከመደበችው ከእያንዳንዱ አራት ዶላር አንዱን እስራኤል የራሷን መከላከያ እንድታደራጅበት ሁኔታዎች ተመቻችተውላታል፡፡ “የዩናይትድ ስቴትስን ወታደራዊ ድጋፍ ከሚያገኙት ሀገራት መካከል ይህን የመሰለ የተጠቃሚነት ዕድል ያገኘ አንድም ሐገር የለም” በማለት የሲ.አር.ኤስ. ዘገባ ያስረዳል፡፡ ዘገባው አያይዞ ሲያብራራ፡- ‹‹የዩናይትድ ስቴትስን የጦር መሣሪያ በመግዛት ከሚገኘው ትርፍ ተጠቃሚ የሆነችው እስራኤል የመከላከያ ኃይሏን እጅግ ዘመናዊና የተወሳሰበ ለማድረግ ችላለች›› ብሏል፡፡ በእርግጥም በ2004 ከሌሎች ሀገራት ጋር ስትነፃፀር በጣም ትንሽ የሆነችው እስራኤል በዓለም ላይ የጦር መሣሪያ አቅራቢ ከሆኑ ሀገራት በ8ኛ ደረጃ ላይ ለመገኘት በቅታለች፡፡[22]

እንደ ግብፅና ቱርክ ሁሉ እስራኤልም አጠቃላይ የሆነውን የውጭ ወታደራዊ ፋይናንስ (FMF) ዓመታዊ በጀቷን ትሸፍናለች፡፡[23] እስራኤል በተጨማሪም አሜሪካ የሰጠቻትን ብድር የመክፈያ ጊዜው ዘግየት ብሎ እንዲቆጠርላት በማድረግ የምትከፍለውን የወለድ መጠን ትቀንሳለች፡፡ [24]

በሚያስደንቅ ሁኔታ ከዩ.ኤስ. አሜሪካ የኢኮኖሚ ድጋፍ ከሚደረግላቸው ሀገራት መካከል የወሰደችውን ገንዘብ በምን ላይ እንዳዋለችው የማትጠየቀው ብቸኛ ሀገር እስራኤል ናት፡፡ ለሌሎች ሀገራት ግን ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን ለመከላከል፣ ፀረ- አደንዛዥ እጽ ዘመቻን ለማካሄድ፣ ለሕፃናት ጤና እንክብካቤ፣ ለዲሞክራሲ ማሳለጫ፣ ትምህርትን ለዜጎች ለማዳረስ ወዘተ... ተብሎ ነው የዩ.ኤስ አሜሪካ እርዳታ የሚመደብላቸው፡፡ ያም ቢሆን በሩብ ዓመትና በግማሽ ዓመት ወይም በምዕራፍ (phase) እየተሸነሸነ ነው የሚሰጣቸው፡፡ ለእስራኤል ግን የተመደበው ገንዘብ ሁሉ የሚለቀቅላት [25] ሲሆን፤ በሌሎቹ ሀገራት እንደሚደረገው ገንዘቡን እንዴትና በምን አኳኋን እንዳዋለችው ክትትል አይደረግባትም፡፡ ሆኖም ግን እስራኤል ይህን አሠራር ተጠቅማ ገንዘቡን ራሷ ዩ.ኤስ አሜሪካ ለማትፈልጋቸው ጉዳዮች ለምሳሌ በምዕራባዊ ወንዝ ዳርቻ አዳዲስ ቤት ለመገንባት የምታውለው መሆኑና ማንም ሊቆጣጠራት ያለመቻሉ ነው

አስተዛዛቢው ጉዳይ፡፡ እንደ ኮንግረስ የምርምር አገልግሎት (ሲ.አር.ኤስ) ባለሙያው ክላይድ ማርክ አባባል ከሆነ፡- “አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠው እርዳታ በሙሉ የተለየ የፕሮጀክት ዕቅድ ተነድፎ ወይም ይህ ለዚህ ጉዳይ፣ ይህ ደግሞ ለዚያኛው ተብሎ ሳይሆን መንግሥት ለመንግሥት ተነጋግሮና ተዋውሎ በጥቅሉ የሚሰጥ በመሆኑ ገንዘቡን እምን ላይ እንዳዋላቸው ለመጠየቅ ምንም ዓይነት መንገድ የለም፡፡›››[26]

ዩ.ኤስ. አሜሪካ እስራኤልን የምትደግፍበት ሌላው መንገድ እስራኤል ከአሜሪካ የንግድ ባንኮች በአነስተኛ የወለድ መጠን ብድር እንድታገኝ ማድረግ ነው፡፡ የዚህ ዕድል ተጠቃሚዋ እስራኤል በሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር ከአነስተኛ ወለድ ክፍያው ታድናለች፡፡ ለምሳሌ በ1990ዎቹ እስራኤል ከአሜሪካ ባንኮች 10 ቢሊዮን ዶላር በብድር መልክ አግኝታለች፡፡ ይህንንም ገንዘብ ከሶቪየት የፈለሱ አይይሁዳዊያንን ለማስፈር ለሚያስፈልጋት ወጪ አውላዋለች። የዩ.ኤስ. አሜሪካ መንግሥት ይህን የመሰለውን ብድር በቀጥታ አይሰጥም፡፡ እንደዚያ ቢያደርግ በተለያዩ የንግድ ባንኮች ገንዘባቸውን ለትርፍ የሚያስቀምጡ ዜጎች ትርጉም ያለው ጥቅም ስለማያገኙ ዞሮ ዞሮ ኢኮኖሚውን ይጎዳዋል ብሎ ስለሚሰጋ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ አሠራር እውነተኛ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰትን ስለሚጻረርና ለግብር ከፋዩ ሕዝብም ትክክለኛ ጥቅም ስለማያመጣም ጭምር ነው፡፡ የሆነ ሆኖ ኮንግረሱ በእንዲህ ዓይነት ድንበር ተሻጋሪ የብድር አሰጣጥ ሂደቶች ገንዘቡ ለእውነተኛ (ትክክለኛ) ልማታዊ ተበዳሪ ቢሰጥ ኖሮ ሊገኝ ይችል የነበረውን ጥቅም ለባንኮች ለመክፈል ይገደዳል፡፡ ለምሳሌ በ1992 እስራኤል በወሰደችውና ለእውነተኛ ተበዳሪዎች ገንዘቡ ቢሰጥ ኖሮ ይገኝ የነበረውን ከ100 እስከ 800 ሚሊዮን ዶላር የሚደርስ ጥቅም ኮንግረሱ ለአበዳሪዎቹ የፋይናስ ተቋማት እንዲተካ አድርጓል።[27]

ዋሽንግተን በ2003 ለእስራኤል ሁለተኛ ዙር ብድር የፈቀደች ሲሆን 9 ቢሊየን ዶላር የሚሆነው ይህ ገንዘብ እስራኤል ከኢራቅ ጋር ለሚደረገው ውጊያ ራሷን እንድታዛጅ፣ የተራዘመውን የኢኮኖሚ ውድቀት እንድትቋቋምበትና ሁለተኛውን የፍልስጤማውያን አንቲፋዳ ለመከላከል ያወጣችውን ወጪ እንድትሸፍንበት አግዟታል፡፡ ምክንያቱም እስራኤል

የሚሰጣትን ብድርና እርዳታ በኃይል በተያዙት ግዛቶች ለግንባታ እንዳታውለው የአሜካሪካ ሕግ ስለሚያግዳት ነው። በመሆኑም በመጨረሻ ላይ የተወሰደው እርምጃ እስራኤል በኃይል በያዘቻቸው የፍልስጤማውያን መሬቶች ላይ ልታውለው ያቀደችውን የግንባታ መዋዕለ ነዋይ በመቀነስ የቀረው እንዲለቀቅላት ማድረግ ነበር። ሆኖም ግን ይህ የእርዳታ ቅነሳ እንደተባለለት ያን ያህል እስራኤልን አልጎሸማትም። ከዚያ ይልቅ ከአሜሪካ ከወሰደችው ገንዘብ ውስጥ ለጥቂቱ ብቻ የተወሰነ የወለድ ጭማሬ እንድትከፍል ብቻ ነው የተገደደችው።

እስራኤል፣ አሜሪካ ከምትሰጣት ድጎማና የብድር ዋስትና በተጨማሪ ከአሜሪካ ዜጎች በየዓመቱ ወደ 2 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ በችሮታ መልክ የምታገኝ ሲሆን ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ግማሽ የሚሆነውን በቀጥታ፤ ቀሪውን ግማሽ ደግሞ ከራሷ (ከአሜሪካ) የመንግሥት ግምጃ ቤት ሰነድ ሽያጭ ታገኛለች።[28] ይህን የግምጃ ቤት ሰነድ ሽያጭ አሜሪካ ውስጥ እንድታካሂድ ሁኔኛ የሆኑ የሕግ ረቂቆች ተዘጋጅተው በኮንግረሱ የጸደቁ በመሆናቸውና ከዚያ የሚገኘውም ወለድ ከግብር ነፃ እንዲሆን በመደረጉ ሁኔታው ለእስራኤል ተመችቷታል። ይህም በ1984 በሌሎች የግምጃ ቤት ሰነድ ሽያጮች ከሚገኝ ገቢ መንግሥት ካስቀመጠው ጣራ በታች ታክስ እንዳይከፈል በሚያዘው ሕግ ማዕቀፍ ስር የሚጠቃለል ነው።[29] በሌላ በኩል ደግሞ አሜሪካ ውስጥ ከሚኖሩ ግለሰቦች ወደ ሌሎች ሀገራት የሚላኩ ችሮታዎች ግብር የሚከፈልባቸው ሲሆኑ፣ ዩ. ኤስ፣ አሜሪካና እስራኤል ባደረጉት ልዩ ስምምነት መሠረት ወደ እስራኤል የሚላኩ ችሮታዎች ግን ግብር አይከፈልባቸውም።[30]

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ የገንዘብ ፍሰቶች በዘመናችን የእስራኤል ኢኮኖሚ እንዲያንሰራራ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ከዩናይትድ ስቴትስ ዜጎች በመዋጮና በችሮታ መልክ ወደ እስራኤል የሚላከው ዳጎስ ያለ ገንዘብ እስራኤል እንደሀገር ከመመሥረቷ በፊት ጀምሮ የነበረና ቀደም ያለ ታሪክ ያለው ነው።[31] የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ከነበሩትና በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት በመሆን እያገለገሉ ካሉት ሽሞን ፔሬስ ትውስታዎች ለመገንዘብ እንደሚቻለው ባለፀጋ የሆኑ አይሁዳዊያን (ብዙ አሜሪካዊያን

አይሁዶችን ጨምሮ) ያደረጉት የገንዘብ ድጋፍ በ1950ዎቹና 60ዎቹ ለነበረው የእስራኤል የኑክሌር ሚሳኤል ፕሮግራም ወሳኝ የሆነ የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ነበር። እንደ እስራኤላዊው ጋዜጠኛ ሚካኤል ካርፒን አባባል ይህን ታላቅ ፕሮጀክት ለማስፈጸም የገንዘብ ማሰባሰቡን ሂደት ያስተባበረው ዋነኛ ሰው አብርሃም ፊንበርግ የተባለው አይሁድ አሜሪካዊ የንግድ ሰው፣ በጎ አድራጊና የፖለቲካ አማካሪ ነበር። ለዚህ ፕሮጀክት በዋነኛነት ጠቀም ያለ ገንዘብ ካዋጡት ውስጥ ካናዳዊው የመጠጥ ኢንዱስትሪ ባለቤት ቱጃሩ ሣሙኤል ብሮንፍማንና የሮዝ ቻይልድ ቤተሰቦች ይገኙበታል። ይሁን እንጂ ፊንበርግ ለፕሮጀክቱ ገንዘብ ያዋጡ ሰዎችን ዝርዝር ያላሳወቀ ሲሆን፣ የእርሱም ሚና ቢሆን በግልጽ ያልተነገረ መሆኑ ይታወቃል።[32] ዛሬም ቢሆን የተለያዩ አይሁዳዊያን ማህበረሰቦችን ያቀፉ ቡድኖች እስራኤል ውስጥ በማህበራዊ፣ በትምህርት፣ በባህልና በመዝናኛዎች ዘርፍ ድጋፍ ለማድረግ እንዲሁም አይሁዳዊቷን ሀገር ከጠላቶቿ በመከላከል ሂደት ላይ ዘብ የቆሙ ወጣቶችን ሕይወት ምቾት ያልተለየው እንዲሆን ለማድረግ፣ ገንዘብ እያሰባሰቡ መላካቸውን አላቆሙም። አሁን በቅርቡ በተደረገ አንድ የገቢ ማሰባሰቢያ የእራት ግብዣ ላይ ብቻ 18 ሚሊዮን ዶላር ተሰብስቧል።[33]

ከተለያዩ የአሜሪካ ዜጎች (አይሁዳውያን ከሆኑ ማለት ነው) የሚደረግላት እርዳታ እስራኤልን በኃይል በያዘቻቸው ግዛቶች ለተራዘመ ጊዜ የበላይነቷን ይዛ እንድትቆይ አግዟታል። በምዕራባዊው ወንዝ ዳርቻ ለአዳዲስ ሠፈራ ግንባታና ለሠፋሪዎች ማቋቋሚያ የሚሆኑ መዋጮዎች ግን ከግብር ነፃ አይደሉም። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ በየጊዜው እያጣሩና እየተከታተሉ ሕጉን ማስፈጸም ስለሚከብድ ግብር ሳይከፈልበት የሚሾልክ የገንዘብ መዋጮ ሊኖር ይችላል።[34] ይህን ለመቆጣጠር የተለያዩ የአሠራር ሥርዓቶች ቢዘረጉም የዓለም አቀፉ የጽዮናውያን ድርጅት (WZO) በሚፈጥራቸው ውስብስብ ሻጥሮች ምክንያት ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ከባድ ሆኗል።[35] በተለያዩ የአሜሪካ ክፍሎች የሚገኙ የአይሁዳዊያን በጎ አድራጊዎች ሥራቸውን የሚያከናውኑት ከሀገሪቱ የግብር አስከፋይ ባለሥልጣን አሠራር በተሰወረ መልኩ ስለሆነ ከአይሁዳዊያንና ከክርስትያን ወንጌላዊያን ማህበራት የሚገኘውን ገንዘብ ለመቆጣጠር ፈጽሞ ሳይቻል

የሚቀርበት ጊዜ ብዙ ነው።[36] በዚህም የተነሣ ብዛት ያለው ገንዘብ ከአሜሪካ እንዴት እንደወጣ ሳይታወቅ ወደ እስራኤል ይተላለፋል።[37]

ማንም ቢሆን ይህ ሁሉ ልገሳ፣ እርዳታና ብድር ወደ እስራኤል መኸርጎድጎዱን ሲገነዘብ ሊደነቅ ይችላል። ምክንያቱም እስራኤል እንደ አፍጋኒስታን በጦርነት የደቀቀች ወይም እንደ ኒጀር፣ በርማ፣ ሴራሊዮን ድህነት ያማቀቃት ሀገር አይደለችምና። እንደውም ዛሬ የሚታየው ሀቅ እስራኤል በኢንዱስትሪ የበለጸገች ዘመናዊ ሀገር መሆኗ ነው። በ2006 የነበራት የነፍስ ወከፍ ገቢ በዓለም ላይ ካሉ ሀገራት ሀያ ዘጠነኛ ደረጃ እንደያዘች ያሳያል። በዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ዘገባ መሠረት የእስራኤል የነፍስ ወከፍ ገቢ ከሀንጋሪ እና ቼክ ሪፐብሊክ በእጥፍ የሚበልጥ ሲሆን ከፖርቹጋል፣ ከደቡብ ኮሪያና ከታይዋን ደግሞ ከፍ ይላል፡ ፡ በላቲን አሜሪካና አፍሪካ ከሚገኙ በርካታ ሀገራት ጋር ግን በፍፁም አይገናኝም።[38]

በተባበሩት መንግሥታት የሕዝብ ዕድገት ቢሮ የ2006 ሪፖርት መሠረት እስራኤል ከዓለም ሀገራት 23ኛ ደረጃ ያላት ሲሆን፣ ኢኮኖሚክ ኢንተለጀንስ ዩኒት በተባለ ድርጅት የ2005 ዘገባ መሠረት ደግሞ 28ኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ የሰው ልጆች ሕይወት የተሻሻለባት ሀገር ሆናለች።[39] እንግዲህ ይህን በመሰለ ሁኔታ የበለጸገችና አንጻራዊ ዕድገት የሚታይባት ሀገር ናት ከአሜሪካ የውጭ እርዳታ የአንበሳውን ድርሻ በየጊዜው የምትወስደው። እርሷ ከአሜሪካ የምታገኘው እርዳታ በድህነት የሚታወቁት ባንግላዴሽ፣ ቦሊቪያና ላይቤሪያ በድምሩ ከሚያገኙት እርዳታ በእጅጉ የሚልቅ ነው። ይህ ቅጥ ያጣና የተዘበራረቀ የዩኤስ አሜሪካ አሠራር እዚያው አሜሪካ ውስጥ በሚገኙ የእስራኤል ደጋፊዎች ሳይቀር የሚታወቅ ነው። ለምሳሌ በ1997 የአይፓክ ልሳን የሆነው ኒር ኢስት ሪፖርት ጋዜጣ የቀድሞ ዋና አዘጋጅ የነበረው ሚቸል ባርድና የተባለው በመካከለኛው ምሥራቅ የእስራኤል ደጋፊዎች ፎረም መሥራች የሆነው ዳንኤል ፓይፕ እንዲህ በማለት ጽፈዋል፡- ‘‘እስራኤል ባለፀጋ ሀገር እየሆነች ከመሄዷ የተነሣ የሕዝቧ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከታላቋ ብሪታኒያ ጋር ይፎካከራል። ከዚህ በኋላ አሜሪካ

ለእስራኤል እርዳታ ለመስጠት የሚኖራት ፈቃደኝነት በእስራኤል እውነተኛ የተረጅነት ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሆኖ አይዘልቅም፡፡››[40]

ዩናይትድ ስቴትስ እስራኤልን ለመደገፍ ሌላም የተሸከመችላት የኢኮኖሚ ቀንበር አልለ። አሜሪካ ይህን እርዳታዋን እስራኤል ከጎረቤቶቿና በአካባቢው ካሉ የአረብ መንግሥታት ጋር የሰላም ስምምነት እንድትፈራረም የምታደርገው ጥረት አካል አድርጋ ነው የምትቆጥረው፡፡ ለምሳሌ በ1975 በእስራኤልና በግብፅ መካከል በተደረገው ስምምነት የወቅቱ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበሩትና (አይሁዳዊ ዝርያ እንዳላቸው የሚነገረው) ሄነሪ ኪሲንጀር አንድ የመግባቢያ ሰነድ ለእስራኤል ፈርመው ነበር፡፡ በዚያ ሰነድ የተጠቀሰው ሀሳብ እስራኤል በቀውስ ውስጥ በምትሆንበት ጊዜ ዩናይትድ ስቴትስ የእስራኤልን የነዳጅ ፍላጎት የሚያሟላ መጠባበቂያ (reserve) ለማቅረብ የሚያስችል በመቶ ሚሊዮን ዶላሮች የሚቆጠር ገንዘብ ዝግጁ እንደምታደርግ ነው።[41] ይህ የመጠባበቂያ ነዳጅ አቅርቦት ሀሳብ በ1979 በተፈረመው የግብጽ እና የእስራኤል ስምምነት ወቅት ይፋ የተደረገ ከመሆኑም በላይ፣ በየጊዜው የሚታደስ ነው፡፡[42]

በመጨረሻም ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል ጎረቤቶች የምትሰጠው እርዳታና የኢኮኖሚ ድጋፍ በተወሰነ መልኩ እስራኤልንም ለመጥቀም የታለመ መሆኑ መታወቅ አለበት። ግብጽና ዮርዳኖስ ለምሳሌ የዩናይትድ ስቴትስን እርዳታ በመቀበል ከእስራኤል ቀጥሎ በሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ የሚቀመጡ ሀገራት ናቸው። ሁለቱ ሀገራት ያን ያክል መጠን ያለው እርዳታ ሊያገኙ የቻሉት ከእስራኤል ጋር የሰላም ስምምነት ለመፈራረም ፈቃደኛ ሆነው በመገኘታቸው ነው፡፡ ለአብነት ያክል በ1974 ግብጽ 71.7 ሚሊዮን ዶላር አግኝታ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ይህ አሃዝ በ1975 ወደ 1.12 ቢሊዮን ዶላር በ1976 ደግሞ 1.32 ቢሊዮን ዶላር ከፍ ሊል በቅቷል፡፡ ይህ የሆነው እስራኤል ሲናይን ለግብጽ የምታስረክብበት ሂደት ሁለተኛ ምዕራፍ ከተገባደደ በኋላ ነበር፡፡ አሜሪካ ለግብጽ የምትሰጠው የእርዳታ ገንዘብ በሚያስደንቅ አኳኋን በ1978 2.3 ቢሊዮን ዶላር የደረሰ ሲሆን፣ በ1979 ደግሞ (ይህ ዓመት እስራኤልና ግብጽ በካምፕ ዴቪድ የሰላም ስምምነት የተፈራረሙበት ዓመት መሆኑ ይታወቃል፡፡) አሃዙ ወደ 5.9 ቢሊዮን ዶላር

ተመነደገ፡፡ ዛሬ ግብጽ ከአሜሪካ በየዓመቱ ወደ 2 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ ታገኛለች፡፡[43] ዮርዳኖስም በተመሳሳይ ሁኔታ በ1994 ብቻ 76 ሚሊዮን ደላር ቀጥተኛ እርዳታ ከአሜሪካ ያገኘች ሲሆን፣ በ1995 መጠኑ ወደ 57 ሚሊዮን ዶላር ዝቅ ብሏል፡፡ በተጨማሪም ንጉሥ ሁሴን ከእስራኤል ጋር የሰላም ስምምነት ለመፈራረም ፈቃደኛ ሆነው በመገኘታቸው አሜሪካ ካበደረቻቸው ገንዘብ ውስጥ 700 ሚሊዮን ዶላር እንዲሰረዝላቸው የአሜሪካ ኮንግረስ በዚያው ዓመት ወስኗል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች ማዕቀቦች ተወግደው እርዳታ እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡ ከ1997 ጀምሮ ደግሞ አሜሪካ ለዮርዳኖስ በአማካይ በየዓመቱ 566 ሚሊዮን ዶላር[44] የእርዳታ ገንዘብ ትለግሳታለች፡፡ ዩ.ኤስ አሜሪካ ለግብጽና ለዮርዳኖስ የምታጎርፈው ይህ ሁሉ እርዳታ ለአይሁዳዊቷ ሀገር ያላትን ለጋስነት የምታሳይበት መገለጫ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል፡፡

ወታደራዊ ድጋፍ

እስካሁን የተገለጹት እጅግ ጠቃሚ ኢኮኖሚያዊ እርዳታዎች ለእስራኤል ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ ለወደፊቱም እንደሚቀጥሉ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል በገፍ የምታቀርበው ወታደራዊ እርዳታ እስራኤልን በመካከለኛው ምሥራቅ በወታደራዊ ኃይል የበላይ ለማድረግ መቁረጧን ያሳያል፡፡[45]

እስራኤል ከአሜሪካ እጅግ የዘመኑ የጦር መሣሪያዎች (F-15 እና F--16 ተዋጊ አውሮፕላኖችን፣ ብላክ ሀውክ ሄሊኮፕተሮችን፣ የተራቀቁ የነፍስ ወከፍ የውጊያ መሣሪያዎችን፣ ስማርት ቦምቦችን ወዘተ...) የምታገኝ ብቻ ሳይሆን ከአሜሪካ የመከላከያ ስለላ ተቋማት ጋር ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ግንኙነት ያላት ሀገርም ለመሆን በቅታለች፡፡ በኮንግረስ ምርምር አገልግሎት (CRS) ዘገባ መሠረት "የአሜሪካ ወታደራዊ ድጋፍ የእስራኤልን ጦር በዓለም ላይ እጅግ ዘመናዊና በተወሳሰበ ቴክኖሎጂ የሚታገዝ እንዲሆን አስችሎታል፡፡››[46]

በዎል ስትሪት ጆርናል ዘገባ መሠረት ደግሞ “እስራኤል የዩኤስ. አሜሪካን ወታደራዊ እርዳታና ድጋፍ በስፋት የማግኘት እድሏ ሰፊ ሆኗል፡፡› [47] የመከላከያ ደህንነት ትብብር ወኪል የሆነውና DSCA በመባል የሚታወቀው ድርጅት ለውጭ ወታደራዊ እርዳታ ተቀባይ ሀገራት የሚገዙ ማናቸውንም ዓይነት ወታደራዊ ቁሳቁሶችን ይቆጣጠራል፣ ግዢውንም ይፈጽማል፡፡ እስራኤል ለዚህ የተለመደ አሰራር ተገዥ አይደለችም፡፡ ማለትም ከወታደራዊ ተቋራጮች ጋር ቀጥተኛ ንግግር በማድረግ ግዢ ትፈጽማለች፡፡ የገዛቻቸውን ወታደራዊ ቁሳቁሶችና መሣሪያዎች ሂሳብ ግን ከሚሰጣት የእርዳታ ገንዘብ እንዲከፈል ሁኔታዎችን ታመቻቻለች፡፡[48] እስራኤል ከዚህም በተጨማሪ በአሜሪካ የመሣሪያ ሽያጭ ገበያ ከ500,000 ዶላር በታች ለሆኑ የመሣሪያ ግዢዎች ቀረጥ እንዳትከፍል ዕድል የተሰጣት ብቸኛ ሀገር ናት፡፡[49]

ይህን በመሰለውና አንጻራዊ ልልነት በሚስተዋልበት የግዢና የሽያጭ ሂደት ላይ በ1990ዎቹ አንድ ችግር ተከስቶ ነበር፡፡ ይህ የሆነው የእስራኤል አየር

ኃይል የዕቃ ግዢ ዋና ኃላፊ የነበረው ጄኔራል ራሚ ዶታን በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ከዩናይትድ ስቴትስ የእርዳታ በጀት ላይ በማጭበርበሩ ነበር፡፡ ዎል ስተሪት ጆርናል ጉዳዩን አስመልክቶ ባወጣው ዘገባ፡- "ዶታን (በመጨረሻ ላይ የሠራው ወንጀል ስለተረጋገጠበት ለረዥም የእሥራት ፍርድ ተዳርጓል) በተደጋጋሚ የግዥ ሰነዶች እንዲዘጋጁ በማድረግና ከ500.000 በታች እንዲሆኑ በማመቻቸት ባገኘው ከቀረጥ ነፃ ግዢ ቀዳዳ እጁን ለማስገባት ችሏል" ብሏል፡፡ የሆነ ሆኖ በዚህ ጉዳይ ላይ ኃላፊነት የተጣለበት የፔንታጎን መምሪያ ኃላፊ ሌተናል ጀኔራል ቴዲ አለን፣ ኮንግረሱ ጉዳዩን እንዲያጣራ ባቋቋመው ንዑስ ኮሚቴ ፊት ቀርበው እንደተናገሩት ለእስራኤል የመከላከያ ኃይል የሚሰጠውን ልዩ የእርዳታ መሣሪያ ግዢ ሂደት "ላይ ላዩን የተቀባባ" በማለት ከተቹት በኋላ በወደፊቱ የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት ላይ ከሚያስከትለው አደጋ አንፃር ውድቅ እንዲደረግና ሌላ ደንብ እንዲዘጋጅ ሀሳብ አቀረቡ፡፡[50]

አሜሪካ ለእስራኤል ከምትሰጣቸውና እስካሁን ከተጠቀሰው አጠቃላይ የሆነ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ድጋፍ በተጨማሪ "ሌቪ" ለተባለው ተዋጊ አውሮፕላን፣ ለሜርኬቫ ታንክ እንዲሁም ‹አሮው› ለሚባለው ሚሳዬል ማሻሻያ ፕሮጀክት ሶስት ቢሊዮን ዶላር አቅርባለች፡፡[51] ይህ ድጋፍ በቀጥታ የቀረበው በአሜሪካ የመከላከያ ሚኒስቴር በኩል ሲሆን፣ ፕሮጀክቱ የሁለቱ ሀገራት ጦር ኃይል የጋራ ምርምርና ማሻሻያ መርሀ-ግብር አካል እንደሆነ ተደርጎ ነው ሲገለጽ የቆየው፡፡ ሆኖም ግን አሜሪካ በዚህ አካል ከተሠሩና ማሻሻያ ከተደረገላቸው የጦር መሣሪያዎች መካከል አንዱንም የማትፈልግና ለመከላከያ ኃይሏም ጥቅም ይውል ዘንድ ያልገዛች መሆኗ ታውቋል፡፡ የሌቪ ፕሮጀክት የተሰኘው የአውሮፕላን ማሻሻያ ሥራ ከወጪ አንፃር ተገምግሞ አዋጪ ሆኖ ባለመገኘቱ (ብዙውን ኪሣራ አሜሪካ ለመሸፈን ተስማምታ) እንዲዘጋ ተደርጓል፡፡ ሁለቱ (ሚርኬቫ ታንክና አሮው ሚሳዮል) ግን በአሜሪካ ወጪ ወደ ቴልአቪቭ እንዲጓዙ ተደርጓል፡፡[52] 166 ሚሊዮን ዶላር የሚሆን ገንዘብ ለዚያ አሮው ለተባለ ሚሳዮል የተመደበ መሆኑን የ2004 የአሜሪካ መከላከያ በጀት ያሳያል፡፡ ከዚያ ገንዘብ ውስጥ 66 ሚሊዮን ዶላር ለተጨማሪ የማሻሻያ ሥራ እንዲሁም 70 ሚሊዮን ዶላር

የሚሆነው ደግሞ ለተጨማሪ የሚሳዮል ክፍል ምርት እንዲሆን ነበር የተመደበው። ዋሽንግተን በዚህ በዚያ እያለች ለእስራኤል የመከላከያ ኢንዱስትሪ የምትሰጠው ይህ ገንዘብ በግልጽ እንደሚስተዋለው ሌላው የድጎማ አካል ነው።[53] እርግጥ ነው አሜሪካ አልፎ አልፎ የእስራኤል የመከላከያ ምርምር ተቋማት ከሚሠሯቸው አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ተጠቃሚ ትሆን ይሆናል። ሆኖም ግን አሜሪካ የበለጠ ተጠቃሚ የምትሆነው ይህን የሚያክል ገንዘብ በሀገሯ ለሚደረጉ የከፍተኛ ቴክኖሎጂ የኢንዱስትሪ ግንባታዎች ብታውለው ነበር።

በዩናይትድ ስቴትስና እስራኤል መካከል የነበረው ወታደራዊ ግንኙነት በ1980ዎቹ ከፍ ወዳለ ደረጃ አድጓል። ይህም የሆነበቱ ምክንያት የሬገን አስተዳደር በመካከለኛው ምሥራቅ ፀረ- ሶቪየት ስትራቴጂያዊ መግባባት እንዲኖር በነበረው ፍላጎት መሠረት ነው። የወቅቱ የመከላከያ ሚኒስትር ካስፐር ዋይንበርገርና የእስራኤሉ አቻቸው አሪዮል ሻሮን በ1981 አንድ የጋራ መግባቢያ ሰነድ ፈርመዋል። በዚያ ሰነድ ላይም ሁለቱ ሀገራት ብሔራዊ ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ የመመካከርና የመደጋገፍ ሚና ሊኖራቸው እንደሚገባ በጉልህ ተገልጧል።[54] ይህ ስምምነትም ሁለቱ ሀገራት የጋራ ፀጥታ ትብብር እቅድ (ጄ.ኤስ.ኤ.ፒ) እና የጋራ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ቡድን እንዲመሠርቱ አስችሏቸዋል። በዚሁ መሠረት ቡድኑ በየጊዜው እየተገናኘ የእስራኤልን ጥያቄ የሚያጠና ሲሆን፣ የጋራ ወታደራዊ እቅድ ይነድፋል፤ የጦር ልምምድ እንዲደረግ ያቅዳል፣ የወታደራዊ ትጥቅና ስንቅ አቅርቦትን ያመቻቻል። ምንም እንኳን የእስራኤል መሪዎች ይህን የመሰለውንና ውስን የሆነ የትብብር አካሄድ የሚታይበትን ጉድኝት ባይደሰቱበትና መደበኛ የሆነ የሁለቱን ሀገራት የትብብር ስምምነት (Formal Treaty of Alliance) ቢሹም የሁለቱ ግንኙነት አሁን ያለበት ደረጃ ሲታይ ፕሬዚዳንት ኬኔዲ ለጎልዳሚዬር በ1962 በግል ቃል ከገቡላቸው የበለጠና የተሻለ መሆኑ ገሀድ ነው።

በክልሉ የተፈጠሩ የተለያዩ አለመረጋጋቶች እንዳሉ ሆነው አሜሪካ ለሳዑዲ አረቢያ በ1981 የጦር መሣሪያ መሸጧ፣ እስራኤል የኢራቅን የኑክሌር ማብለያ በቦምብ ማፈራረሷ፣ እንዲሁም ከጎላን ከፍተኛ ቦታዎች ለመልቀቅ

አለመፈለን፣ በ1982 ሊባኖስን ከመውረሯ ጋር ተደማምሮ ውጥረቱን የበለጠ እንዲጋጋል አድርጎታል። ይህ ሁሉ ትኩሳት እያለ ሬገን በመስከረም 1982 ያቀረቡትን የሰላም ሀሳብ እስራኤል በድንገት ውድቅ ማድረጓ በአሜሪካና በእስራኤል መካከል ያለውን ግንኙነት በማሻከር ፋንታ ይባስ ብሎ የፀጥታ ትብብር እንዲያደርጉ በር ከፍቷል። የተፈጠረውን ውጥረት ተከትሎ በ1984 እና 1986 የአሜሪካና የእስራኤል ጦር የጋራ ልምምድ የጀመረ ሲሆን፣ እስራኤል በአሜሪካ ስትራቴጂያዊ የመከላከያ ኢኒሼዮቲቭ ወይም የኮከብ ጦርነት (Star- War) በተባለውና በአዲሱ የጦር መሣሪያ እሽቅድድም ውስጥ እንዲሳተፉ ከተጋበዙት ሶስት ሀገራት መካከል አንዷ ለመሆን በቅታለች። በመጨረሻም በ1988 አዲስ የተፈረመው የስምምነት ሰነድ እንዳመለከተው በአሜሪካና በእስራኤል መካከል የነበረው ግንኙነት የታደሰ መሆኑን ካብራራ በኋላ እስራኤልን ‹‹የኔቶ አባል ያልሆች ዋነኛ አጋራችን›› በማለት ከአውስትራሊያ፣ ግብፅ፣ ጃፓንና ደቡብ ኮሪያ ጋር አብራ የምትደመር መሆኗን ጠቅሶ አሞካሽቷታል። ይህን የልዩ ወዳጅነት ማዕረግ ያገኙ መንግሥታት የአሜሪካን የጦር መሣሪያ በርካሽ ዋጋ ለመግዛት ዕድል ይከፈትላቸዋል። እንዲሁም የወታደራዊ መለዋወጫ አቅርቦትን በተመለከተ ቅድሚያ የሚያገኙ ከመሆኑም በተጨማሪ አሜሪካ በነደፈችው ፀረ- ሽብር እንቅስቃሴ ላይ በሚደረግ የምርምርና ማሻሻያ ፕሮጀክት ውስጥ ተሳታፊዎች ይሆናሉ። በእነዚህ ሀገራት ውስጥ የሚገኙ አምራቾችና የንግድ ተቋማትም ከአሜሪካ መከላከያ ጋር በሚኖራቸው የሥራ ግንኙነት መልካም የሆነ አስተያየትና ተመራጭነት እንዲኖራቸው ዕድሉ ይመቻችላቸዋል። [55]

በሁለቱ ሀገራት መካከል ፀጥታን የሚመለከተው ግንኙነት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተጠናክሮ እንደቀጠለ ነው። አሜሪካ ያለምንም በቂ ምክንያት በ1989 ለእስራኤል ተጨማሪ ወታደራዊ ድጋፍ መስጠት የጀመረች ሲሆን፣ ይህንኑ አቋሟን ኮንግረሱ በ2006 ደግፎ ድምፅ ከሰጠበት በኋላ ተጨማሪው አቅርቦት በ2008 ከ100 ሚሊዮን ወደ 400 ሚሊዮን ዶላር ከፍ ብሏል።[56] ለዚህ ፖሊሲ የተሰጠው ምክንያት ፔንታጎን በክልሉ የሚፈጠሩ አስጊነት ያላቸውን ሁኔታዎች ለመቋቋም የሚያስችለውን ብቃት ማዳበር

የሚያስፈልገው በመሆኑ ነው የሚል ነበር። ይሁን እንጂ ችግሮችን የማስወገጃው መንገድ ለእስራኤል በገፍ የጦር መሣሪያ ማቅረብ መሆኑ ትክክለኛ አማራጭ እንዳልሆነ ፔንታጎንም ስለተገነዘበው ያን እርምጃ ሲወስድ እጅግም አይበረታታም ነበር። በቴሌአቪቭ ዩኒቨርስቲ በሻፊ የስትራቴጂ ጥናት ባለሙያ የነበሩት ሻይ ፊልድማን እንዲህ ብለዋል፡- "አሁን ፔንታጎን የሚከተለው አሠራር እስራኤል ውስጥ የሚገኘውን የመሣሪያ ክምችት ችግር በተፈጠረ ጊዜ እስራኤል ራሷ እንድትጠቀምበት የሚፈቅድ ነው። በዚህ አሠራር መሠረት የፔንታጎን ዕቅድ አውጪዎች የጦር ትጥቅና ስንቅ እስራኤል ውስጥ ለአስቢ ሁኔታ እንዲቀመጥ ማድረጋቸውን ራሳቸው የፔንታጎን ባለሥልጣናት የሚያምኑበት አይመስሉም ወይም እርግጠኞች አይደሉም። ከዚህም በላይ ይህ ለጋራ ጥቅም እንዲውል ታስቦ የሚደራጅ የጦር መሣሪያ በዩናይትድ ስቴትስ የተለያዩ የጦር ክፍሎች ውስጥ በቅድሚያ እንዲከፋፈል በመደረግ ፋንታ አስቢ ሁኔታ በደረሰ ጊዜ፣ ትጥቅና ስንቅ ከዋናው መጋዘን እንዲወጣ ለማድረግ የተዘረከረከ አሰራር ያጋልጣል።››[57] ስለሆነም የዚህ ሁሉ የመሣሪያ ክምችት ዋነኛ ምክንያት ሌላ ሳይሆን የእስራኤል የውጊያ ብቃት በትጥቅና ስንቅ እንዲጨምርና በመጠባበቂያነት የሚቀመጥላት መሣሪያም አስተማማኝ መጠን እንዲኖረው ለማድረግ ነው። ይህን ጉዳይ አስመልክቶ እስራኤል ውስጥ የሚታተመው ‹የዲኦት አህሮኖት› የተባለው ጋዜጣ በ2006 የታኅሣሥ እትሙ ላይ፡- "እስራኤል ከዚህ የአሜሪካ የመሣሪያ ክምችት ውስጥ ብዙ እጅ የሚሆነውን በ2006 ሊባኖስን በወረረች ጊዜ ጥቅም ላይ አውላዋለች" በማለት አጋልጧል።[58]

በሌላ በኩል ደግሞ በ1980ዎቹ ዩናይትድ ስቴትስ እና እስራኤል ሽብርተኝነትን ለመቋቋም የጋራ ጥምረት ያቋቋሙ ሲሆን፣ በ1966 የፔንታጎንና የእስራኤል መከላከያ ሚኒስትሮች የሚገናኙበት ቀጥተኛ የስልክ መስመር (Hot-Line) ተዘርግቷል። የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ከዚህም በላይ እንዲረቅ ያደረገው ደግሞ ከ1997 ጀምሮ እስራኤል የአሜሪካን በሳተላይት የሚመራ የፀረ-ሚሳዮል የማስጠንቀቂያ ሥርዓት እንድትጠቀምበት ዕድል በተሰጣት ጊዜ ነበር። ከዚያ በመቀጠል 2001 ላይ

በሁለቱ ሀገራት ከፍተኛ ወታደራዊ ወኪሎች መካከል ዓመታዊ ጉባዔ እንዲደረግ ተወሰነ፡፡ ይህ ጉባዔ የረዥም ጊዜ ጉዳዮችን (long term issues) እያነሳ የሚወያይ ነበር፡፡ ሆኖም ግን እስራኤል የአሜሪካን ወታደራዊ ቴክኖሎጂ ለቻይና በመሸጧ ምክንያት ንግግሩ ለተወሰነ ጊዜ ከተቋረጠ በኋላ በነዳር 2005 ላይ እንደገና ቀጠለ፡፡[59]

ማንም በቀላሉ ሊገምተው እንደሚችለው የአሜሪካና እስራኤል የስለላ ተቋማት በስለላው ዓለም ታላቅ የሆነ የግንኙነት አድማሳቸውን በማስፋፋት ይተባበራሉ፡፡ ይህ የሁለቱ ሀገራት የስለላ ግንኙነት ከ1950ዎቹ ጀምሮ የቆዬ ከመሆኑም በላይ፤ በ1985 ከሁለት ደርዘን በላይ የሚሆኑ የመረጃ ልውውጥ ሰነዶችን እንዲፈራረሙ አስችሏቸዋል፡፡ እስራኤል የሶቪዬትን የጦር መሣሪያ ዕድገትና ደረጃ እየተከታተለች ለአሜሪካ ስታቀብል የኖረችው በዋነኛነት በሶቪየት በኩል ወደ ሀገሯ ከሚገቡ አይሁድ ፈላሻዎች የምትቃርማቸውን ወሬዎች እንደመረጃ ምንጭ በመጠቀም ነበር፡፡ አሜሪካ በበኩሏ በ1973 ጥቅምት 18 በተደረገው የእስራኤልና ግብጽ ውጊያ ሙሉ የሳተላይት መረጃዎችን ለእስራኤል ሰጥታለች፡፡ እንዲሁም በ1976 በተከሰተው የኢንተቤው (ኡጋንዳ) አውሮፕላን ጠለፋ የእስራኤላውያኑን ሕይወት ለማትረፍ የበቃች ሲሆን፤ በአፍሪካ ውሰጥ የተደረጉ በርካታ የእስራኤል የስለላ እንቅሰቃሴዎችንም በፋይናንስ አግዛለች፡፡[60] በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ አሜሪካ ሌላው ቀርቶ ለኔቶ አጋሮቿ እንኳን ያላካፈለቻቸውን የስለላ ምስጢራት ለእስራኤል ሰጥታለች፡፡ እስራኤል በተለይም ደግሞ ውስብስብ በሆነው KH-11 የተሰኘ የሳተላይት መረጃ የመጠቀም ያልተገደበ ዕድል አግኝታለች፡ (ይህም እንደ እስራኤል ወታደራዊ ስለላ መግለጫ የጽሑፍ መረጃዎችን ብቻ ሳይሆን በፎቶግራፍ የተደገፉትንም ጭምር ያጠቃልላል፡) ይሁን እንጂ ይህን የመሰለውን መረጃ ብሪታኒያ ከአሜሪካ የምታገኘው በተወሰነ መልኩ ብቻ ነው፡፡[61] “የእስራኤል የስለላ ተቋም ከዚህ መሰሉ የተንበሸበሸ መረጃ የማግኘት ዕድል እቀባ የተደረገበት ጊዜ ቢኖር እስራኤል በ1981 የኢራቅን የኑክሌር ማብለያ (reactor) በቦምብ ካጋየች በኋላ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የመጀመሪያው (ትልቁ) ቡሽ በ1991 የባሕረ ሰላጤው ጦርነት ጊዜ የኢራቅ ሰኮድ ሚሳይሎች የተተከሉባቸውን ቦታዎች የሚያሳዩ

የሳተላይት መረጃዎችን ለወዳጅ ሀገራት የማስተላለፉን ሂደት እንደገና አነቃቁት”። [62]

አሜሪካ ዘወትር አቋሜ ነው እያለች ከምታራምደውና የጅምላ ጨራሽ የጦር መሣሪያዎችን መስፋፋት ከሚያግደው አሠራሯ በተቃራኒ እስራኤል በመካከለኛ ምሥራቅ ያላትን የበላይነት እንድታስጠብቅ ስታገዛት ቆይታለች። ይህንኑም የምታደረገው እስራኤል የዘራጋቻቸውን በርካታ የጅምላ ጨራሽ የጦር መሣሪያ እነፃዎችን አይታ እንዳላየች በመሆን ነው። ለምሳሌ እስራኤል በዲሞና የኑክሌር ምርምር ጣቢያዋ ወደ 200 የሚጠጉ የኑክሌር አረሮችን ሠርታ ማስቀመጧን አሜሪካ በሚገባ ታውቃለች። በሌላ በኩል ግን በርካታ ሀገራት በ1968 የተነደፈውንና የጅምላ ጨራሽ የጦር መሣሪያዎች እንዳይስፋፉ የሚያግደውን ቃል እንዲፈርሙ አሜሪካ ጫና ታደርግባቸዋለች። የአሜሪካ መሪዎች እስራኤል በድብቅ የምታራምደውን የኑክሌር መርሐግብር እንድታቆም ለመጫን የሞከሩት በትንሹ ነው። እንደሚታወቀው የኬኔዲ አስተዳደር በ1960ቹ እስራኤል የኑክሌር መሣሪያ ለመታጠቅ የነበራትን ምኞትና እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ሞክሮ ነበር። በዚህም ጥረቱ በመግፋት በመጨረሻ ላይ የአሜሪካ የኑክሌር ሳይንቲስቶች በዲሞና የኑክሊየር ምርምር ጣቢያ ተገኝተው እስራኤል ኑክሌር ቦምብ እየሠራች መሆኗንና አለመሆኗን እንዲያረጋግጡ እንድትፈቅድ ለማድረግ ችሏል። የእስራኤል መንግሥት በበኩሉ እንዲህ ዓይነት ፕሮጀክት የሌለው መሆኑን በመጥቀስ በተደጋጋሚ ለማስተባበል ሞክሯል። ከዚያ በኋላም የጠበቡቱን ወደ ሀገር ቤት መግባት በተለያዩ ምክንያቶች በማሳበብ ሲያጓትት ቆይቷል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ መዝለቁ የማያዋጣ ሲሆን፣ ግንቦት 18/1961 ሁለት አሜሪዊያን የኑክሌር ጠቢባን ወደ እስራኤል ገብተው ለአራት ቀናት ያክል መቆየት ችለዋል። ነገር ግን ከሁለቱ አንዱ ብቻ ነበር ወደ ዲሞና የምርምር ጣቢያ እንዲገባ የተፈቀደለት። ዋረን ባስ የተባሉ የፖለቲካ ተንታኝ ሁኔታውን ሲገልጹት እንዲህ ብለዋል። ‹‹የእሰራኤል ስትራቴጂ እንዳያማህ ጥራው ዓይነት ሲሆን፣ ጠበብቱ ጉብኝቱን እንዲያደርጉ ፈቅዳለች። ... ሆኖም ግን አንዳች ዓይነት መረጃ እንዲያገኙ አልፈለገችም።” ይህ ከሆነ ከዓመት በኋላ እስራኤል የአሜሪካን

የአቶሚክ ኃይል ጠበብት ባልተጠበቀ ሁኔታና ሳይዘጋጁ ወደ ዲሞና እንዲመጡ ፈቀደች። ዋረን ባስ ሁኔታውን ሲገልጹት ‹‹ቁጥጥር› የሚል ማዕረግ በተሰጠው በዚህ ጉብኝት፣ የኬነዲ አስተዳደር ከዚህ በላይ ገፍቶ እሰጥ አገባ ውስጥ መግባት እንደማይችል የተገነዘበ የመሆኑ እውነታ በግልጽ ታይቷል” ብለዋል። [64]

ኬኔዲ በቀጣዩም ዓመት ግፊታቸውን በመጨመር ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ዴቪድ ቤንጎሪኖንና እሳቸውን ለተኳቸው ሌቪ ኤሽቆል የተለያዩ ደብዳቤዎችን በመላክ ቢያንስ በዓመት ለሁለት ጊዜያት ያክል የኑክሊየር ምርምር ጣቢያው ክትትል እንዲደረግበት ጠይቀዋል። ኬኔዲ ይህን ጥያቄ ሲያቀርቡም የዓለም አቀፉን የአቶሚክ ኃይል ተቆጣጣሪ ተቋም መስፈርት የሚያሟላ ቁጥጥር እንዲደረግ በማሳሰብ ጭምር ሲሆን፣ የእስራኤል መንግሥት ይህ እንዲሆን የማይፈቅድ ከሆነ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ግንኙነት አደጋ ላይ እንደሚጥለው አስጠንቅቀዋል። በተጨማሪም ኬኔዲ፣ እስራኤል የኑክሌር ቦምብ ለመታጠቅ ያላትን ፍላጎት አሜሪካ በትክክል ለማወቅና ለመከታተል አለመቻሏ ያበሳጫቸው መሆኑን ጠቅሰው የእስራኤል መሪዎች ተጨማሪ የአሜሪካ ተቆጣጣሪዎችን ጉብኝት እንዲፈቅዱ በማስፈራራት ጭምር ጠይቀዋል።[65] የኬኔዲ ማስፈራሪያ ያስደነገጣቸው መሪዎች ተጨማሪ ጠበብት ገብተው እንዲፈትሹ የፈቀዱ ቢሆንም፣ ስምምነቱን ለማክበር ግን ፍላጎት ሲያንሳቸው ታይተዋል። ጠቅላይ ሚኒስቴር ሌቪ ኤሽቆል፣ ኬኔዲ የላኩላቸውን ደብዳቤ በሐምሌ 1963 እንደተቀበሉ ለባልደረቦቻቸው እንዲህ እንዳሉ ተጠቅሷል፡- ‘‘እኔን ምን ያስፈራኛል? የኬኔዲ መልዕእክተኛ ይመጣል። ከዚያም የዲሞናን የኒኩሊየር ጣቢያ መጎብኘት እንዲችል ወደፈለገው ቦታ ሁሉ ይወሰዳል። የተወሰኑ በሮች እንዲከፈቱለት ሲጠይቅም አማኑኤል (የዲሞናው ምርምር ጣቢያ ኃላፊ)፡- "ይህን ማየት አይቻልም ይለዋል።”[66] በሌሎች ጉብኝቶች ወቅትም ተቆጣጣሪዎች ከውጭ የመቆጣጠሪያ መሣሪያን ማስገባትም ሆነ ምንም ዓይነት የናሙና ማስረጃ መውሰድ እንዳይችሉ የእስራኤል መንግሥት እገዳ ጣለ።

አሁን በቅርቡ የታዩትን የኢራቅና የሰሜን ኮሪያን ሁኔታዎች ካስታወስን፣ እነዚያ ሀገራት የሚከተሏቸው አደናጋሪ የሆኑ ታክቲኮች በምስጢር የሚያራምዱት የኑክሊየር መርሀ-ግብር አካል መሆናቸውን እንገነዘባለን፡፡ ዩ.ኤስ፣ አሜሪካ የእስራኤልን የኑክሊየር ዕቅድ በተመለከተ እስካሁንም ድረስ በጥርጣሬ ላይ ያለች ሲሆን፤ በዚያ ዘመን የነበሩት ፕሬዚዳንት ኬኔዲና እርሳቸውን የተኳቸው ሊንደን ጆንሰን እስራኤል እየዋሸቻቸው መሆኑን ቢያውቁ የአሜሪካን እርዳታዎች እንደሚያቆሙት የእስራኤል ባለሥልጣናት ጠንቅቀው ይገነዘቡ ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ‹የእስራኤል የኑክሌር መርሐ-ግብር› በሚል ርዕስ ጥልቅ የታሪክ ትንተና ያቀረቡት አቭነር ኮሽን የሚከተለውን ጽፈዋል፡- “እስራኤላውያኑ የአሜሪካን ጠበብት ጉብኝት በተመለከተ ሕግ-ጋትን ማውጣት ነበረባቸው፡፡ የጆንሰን አስተዳደርም በዚህ ጉዳይ ዙሪያ እስጥ አገባ ውስጥ መነከር አልፈለገም፡፡ ምክንያቱም ኬኔዲ ለዴቪድ ቤንጎሪያንና ለሌቪ ኢሽቆል በሰጧቸው ማስጠንቀቂያዎች መሠረት የተጀመረው የእስራኤልን የኑክሌር አውታሮችን የመፈተሽ ሂደት እንዳይቋረጥና የአሜሪካና እስራኤል ግንኙነትም እንዳይታወክ ጆንሰን በመፍራታቸው ነው፡፡ ጆንሰን ከዚህም በላይ የአሜሪካና እስራኤል ግንኙነት አደጋ ላይ መውደቁ የሚያስከትለውን ኃላፊነት መሸከም አልፈለጉም፡፡[67] ‹‹ቀደም ሲል በኬኔዲ ጊዜ በተደረሰው ስምምነት መሠረት በየ6 ወሩ ፍተሻ ማካሄዱ እንዲቋረጥ በዚያ ምትክ በዓመት አንድ ጊዜ አጠር ያለ ጉብኝት ብቻ እንዲካሄድ ጆንሰን ሁኔታዎችን አመቻቹ፡፡››[68] እናም የሲ.አይ.ኤ ዳይሬክተር የሆኑት ሪቻርድ ኧልምስ በ1968 ወደ ሁዋይት ሐውስ መጥተው እስራኤል የኑክሌር ቦምብ ሠርታ መታጠቋን የአሜሪካ የስለላ ተቋም እንደደረሰበት ሲገልጹላቸው፣ ጆንሰን ሪቻርድን ይህን ጉዳይ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዲን ሩስክና ለመከላከያ ሚኒስትሩ ሮበርት ማክናማራም ሆነ ለሌላ ሰው ትንፍሽ እንዳይሉ ነበር ያስጠነቀቋቸው፡፡ እንደ ጋዜጠኛው ሳይሙና ኧርሽ ትዝብት ከሆነ፡-

‹‹ፕሬዚዳንት ጆንሰን፣ የስለላው ኃላፊ ኧልምስና ቡድናቸው ወደዚያ ራቅ እንዲሉላቸው የፈለጉበት ዋነኛው ምክንያት ግልጽ ነበር፡፡ ይኸውም ሲ.አይ.ኤ ሊነግራቸው የሚፈልገውን መረጃ ለማወቅ የማይሹ መሆናቸውን

ለማሳየት ነው። ምክንያቱም ይህን ሀቅ አንድ ጊዜ ከተቀበሉት በኋላ በአንጻሩ ማድረግ የሚጠበቅባቸውን ጉዳይ ስለሚያውቁትም ጭምር ነው። በዚያም አለ በዚህ በ1968 ፕሬዚዳንት ጆንሰን የእስራኤልን ቦምብ በተመለከተ ምንም ነገር ለማድረግ ዝግጁ አልነበሩም።››[69]

እስራኤል ከኑክሊየር መሣሪያዎቿ በተጨማሪ የኬሚካልና ባዮሎጂካል የጦር መሣሪያዎችን የታጠቀች ሲሆን መሣሪያዎቹ እንዳይስፋፉ የሚያግዱትን ውሎችም አልፈረመችም።[70] እዚህ ላይ ትልቁ ምጸት ሌሎች ብዙ ሀገራት የእነዚህን መሣሪያዎች መስፋፋት የሚያግደውን ውል እንዲፈርሙ አሜሪካ ስታግባባ፤ እምቢ ያሉትንም በማዕቀብ ስትቀጣ፤ እስራኤልን ግን አይታ እንዳላየች መሆኗ ነው። ለምሳሌ የኢራቅን የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ትጥቅ ለማስፈታት በሚል ሰበብ በ2003 በኢራቅ ላይ ወረራ አድርጋለች። ኢራንንና ሰሜን ኮሪያንም እንዲሁ ልትቀጣቸው እንደምትችል እየዛተች ታስፈራራለች። የኑክሌር መሣሪያዎች እንዳሏት በግልጽ ለምትታወቀው አጋሯ ለእስራኤል ግን ያልተቋረጠ ድጋፍ በመስጠት በጎረቤቶቿና በቀጠናው የበላይ እንድትሆን ማገዙንና አይታ እንዳላየች መሆኑን መምረጧ አድሏዊነቷን ያሳያል።

ሶቭየት ሕብረት ኩባን በከፊል ከረዳችበት ሁኔታ በስተቀር አንድ ሀገር ሌላውን ይህን ለሚያክል የተራዘመ ጊዜና በዚህ ያክል መጠን የረዳ መሆኑ በታሪክ አልተመዘገበም።[71] እርግጥ ነው አሜሪካ እስራኤልን በተወሰነ መልኩ ለመርዳት ፈቃደኛ መሆኗ አያስደንቅም። ምክንያቱም የአሜሪካ መሪዎች ሁሉ ማለት ይቻላል የእስራኤልን በሕልውና መቆየት ሲደግፉ ቆይተዋልና። ይህንንም ያደርጉ የነበረው እስራኤል ከአካባቢዋ ሕዝቦችና ሀገራት ጋር በነበረባት ሥር የሰደደ ውዝግብ የተነሳ ነው። በምዕራፍ 2 በስፋት እንደሚገለጸው የአሜሪካ መሪዎች በሚነድፉት ሰፋ ያለ የውጭ ፖሊሲ እስራኤልን መርዳቱን እንደ አንድ የግባቸው አካል አድርገው ይቆጥሩታል። ይህም ሆኖ ግን አሜሪካ ለእስራኤል ያጎረፈችው መጠን አልባ እርዳታ የሚያስደንቅ ነው። በምዕራፍ 3 እንደምንቃኘው ይህ ለጉድ የዘነበላት እርዳታ ከአሜሪካ በኩል ሳይደርሳት በፊትም ቢሆን እስራኤል ከጎረቤቶቿ የበለጠች ጠንካራ ሀገር ነበረች። አሁን ደግሞ ጠንካራ ብቻ

ሳትሆን የበለጸገችም ሆናለች። ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ግን የአሜሪካ እርዳታ እስራኤልን ይጠቅማት እንደሆነ እንጂ ለሕልውናዋ ላያስፈልጋት እንደሚችል መታወቅ አለበት።

አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠው ድጋፍ ልዩ ባህሪ ተደጋግሞ እንደተገለጸው ቅድመ ሁኔታ የማያርፍበት መሆኑ ነው። እስራኤል በስዊዝ ጦርነት የግዛት ማስፋፋት ህልም እንዳላት ፕሬዚዳንት አይዘንሐወር ሲገነዘቡ እርዳታ እንዳይሰጣት እገዳ እንደሚያደርጉ በመግለጽ አስፈራሩ። (ለዚያውም ቢሆን ከኮንገረስ አባላት በኩል በርከት ያለ ተቃውሞ ተነስቶባቸው የነበረ መሆኑ ይታወቃል።) ሆኖም ግን እነዚያ ቀናት ካለፉ ብዙ ዘመናት ተቆጥረዋል። ከ1960ዎቹ ጀምሮ እስራኤል ተንኳሽ ባህሪ እያንጸባረቀች መሆኑን የአሜሪካ መሪዎች እያወቁ የሀገራቸውን ጥቅም በሚጻረር መልኩ እርዳታ ማጉረፋቸውን አላቋረጡም። እስራኤል የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎችን ማስፋፋትን የሚያግደውን ውል ለመፈረም አሻፈረኝ በምትልባቸው ጊዜያት ሁሉ እርዳታው እንዳይቋረጥባት መደረጉ ሌላው አነጋጋሪ ጉዳይ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፣ በኃይል በተያዙት የፍልስጤም መሬቶች የሰፈራ መንደሮችን እየገነባችም ጭምር ይኼው እርዳታ በገፍ የሚጎርፍላት መሆኑ ግራ ያጋባል። ይህን የመስፋፋት ፖሊሲዋን የአሜሪካ መንግሥት እንደሚቃወም ግልጽ ነው። የጎላን ከፍተኛ ቦታዎችንና ምሥራቃዊ እየሩሳሌምን በኃይል እንደያዘች መቆየቷ እየታወቀ፣ የአሜሪካን የተራቀቁ ወታደራዊ ቴክኖሎጂዎች ቻይናን ለመሰሉ የዩ.ኤስ. ስትራቴጂያዊ ጠላቶች እየሸጠችና በራሷ በዩ.ኤስ. አሜሪካ ላይ የስለላ ተግባር እየፈጸመች፤ እንዲሁም የራሷን የአሜሪካን የጦር መሣሪያ በመጠቀም የአሜሪካን ሕግ እየጣሰች (ለምሳሌ የክላስተር ቦምብን በሊባኖስ ሲቪሎች ላይ እየጣለች) እርዳታው አይታገድባትም። እስራኤል ከአጎራባቾቿ ጋር የሰላም ስምምነት ለመፈራረም ፈቃደኛ በሆነች ጊዜ ተጨማሪ እርዳታ የሚሰጣት ሲሆን፣ የሰላም ስምምነቱን የማይጨበጥ ሕልም ባደረገችው ጊዜ ግን አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር እርዳታው አይታገድባትም። የእስራኤል መሪዎች ለዩኤስ. አሜሪካ ፕሬዚዳንቶች የገቡትን ቃል ባፈረሱ ጊዜ ሁሉ የአሜሪካ የእርዳታ እጅ አይታጠፍም። ለምሳሌ አሜሪካ AWACS የተባሉትን ተዋጊ

አውሮፕላኖች ለሳዑዲ አረቢያ መሸጧን እንደማይቃወሙ ሜናሂም ቤጊን በ1981 ለሮናልድ ሬገን ገልጸውላቸው ነበር። ሆኖም ግን ቤጊን በካፒቶል ሂል የሴኔቱ ጉባዔ ላይ ለመገኘት በሄዱ ጊዜ ይህን ስምምነት እንደሚቃወሙ ለጉባዔተኞቹ አሳወቁ።[72]

ማንም ቢሆን ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል ከምታደርገው እጅግ የበዛ ችሮታ የተነሳ በእስራኤል ላይ ተጽእኖ የማሳረፍ ችሎታ ይኖራታል ብሎ ሊያስብ ይችላል። ሆኖም ግን እውነታው ያለው ወዲህ ነው። የአሜሪካ መሪዎች ሁልጊዜም ቢሆን የእስራኤልን መሪዎች ትብብር ማግኘት የሚሹት ተጨማሪ ካሮት በመስጠት (እርዳታ በመጨመር) እንጂ ልምጭ በመጠቀም (እርዳታቸውን እንደሚያቋርጡ በማስፈራራት) አይደለም። ለምሳሌ የእስራኤል ካቢኔ በ1967 የተላለፈውን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ውሳኔ ቁጥር 242 በመደገፍ እስራኤል በስድስቱ ቀን ጦርነት ከያዘቻቸው ቦታዎች እንደምትወጣ ገልጾ ነበር። ይህም የሆነው ሪቻርድ ኒክሰን ለእስራኤል ተጨማሪ የጦር ጀቶችን ለመስጠት ዋስትና ከገቡ በኋላ ነበር። [73] በተጨማሪም ‹የማድከም ጦርነት› በመባል የሚታወቀውንና ከግብጽ ጋር የተደረገውን (ከመጋቢት 1969 እስከ ሐምሌ 1970 ድረስ የተራዘመውንና የአየር፣ የመድፈኛና እግረኛ ኃይሎችን ያሳተፈውን ውጊያ) ለማስቆም አሜሪካ የተሳካለት ለእስራኤል ምርጥ የሆኑ ተዋጊ ጀቶችን፤ ሶቭዮቶች ለግብጾች የሰጧቸውን ፀረ-አውሮፕላን ሚሳይሎች የሚመክቱ በኤሌክትሮኒክስ የተራቀቁ መሣሪያዎችን ለማቅረብና በአጠቃላይ የኃይል ማመጣጠን ሥራ እንደምታሠራ ምላ ከተገዘቱት በኋላ ነው።[74] ሽሞን-ፔሬስ (ያኔ ሚኒስትር ነበሩ) የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት አስመልክተው ሲናገሩ ‹‹ዩናይትድ ስቴትስ በእኛ ላይ የምታሳድረውን ተጽእኖ በተመለከተ ለማለት የሚቻለው የእነርሱን መርሐ-ግብር እንድንቀበል ለማድረግ የተጠቀሙት ዘዴ እኛን በልምጭ ሸንቆጥ በማድረግ ፋንታ ካሮት መስጠቱን ነው። በማንኛውም ክስተት በእኛ ላይ ማዕቀብ እንደሚጥሉ በመግለጽ አስፈራርተውን አያውቁም›› ብለዋል።[75]

ይህን የመሰለው አገም ጠቀም የሆነ አካሄድ በ1970 ዎቹ በፕሬዚዳንት ኒክሰን፣ ፎርድና ካርተር ጊዜ ቀጥሎ እስራኤል ብዛት ያለው እርዳታ

እንደሚሰጣት እየተማለላት ከግብጽ ጋር የተደረገውን የካምፕ ዴቪድ ስምምነት በጂሚ-ካርተር አደራዳሪነት በ1979 ለመደምደም ተቻለ። በዚያ ወቅት እስራኤል ቃል በተገባላት መሠረት በ1975 ካገኘችው 1.9 ቢሊዮን ዶላር የአሜሪካ እርዳታ እጅግ በጣም ጨምሮ በ1976 ወደ 6.2 ቢሊዮን ዶላር ተመንድጓል። (ይህም ሲናይን የመልቀቅ ሁለተኛው ምዕራፍ መጠናቀቁን ተከትሎ የተደረገ ነው)። እንዲሁም በ1978 ከነበረው 4.4 ቢሊዮን ዶላር በ1979 (እስራኤል የመጨረሻውን የካምፕ ዴቪድ ስምምነት መፈራረሚን ተከትሎ) ወደ 10.9 ቢለዮን ዶላር አድጓል። [76] ከዚህ ቀጥሎ እንደሚገለጸው ዩናይትድ ስቴትስ እስራኤልን ወደ ስምምነት ፊርማው ለማምጣት የተለያዩ ማባበያ ቃሎች መግባት ነበረባት። ከግብጽ ጋር ከተደረገው ስምምነት ጋር በብዙ ሁኔታ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ እስራኤል ከዮርዳኖስ ጋር በ1994 ያደረገችውን ስምምነት ተከትሎ የክሊንተን አስተዳደር እርዳታውን አዝንቦላታል። እስራኤል የኦስሎን ውል እንድታከብር ለማግባባት ተጨማሪ 1.2 ቢሊዮን ዶላር የሚያወጣ ወታደታዊ እርዳታ እንደሚቀርብላት ክሊንተን ቃል መግባት ነበረባቸው። ይሁን እንጂ በሁለት እስራኤላውያንና በፍልስጠማውያን ሰልፈኞች መካከል የተፈጠረውን የጠብ ክስተት ተከትሎ የኦስሎው ስምምነት በተፈረመ በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንጃሚን ናታኒያሁ እገዳ ጥለውበታል። [77] በዩ.ኤስ፣ አሜሪካ በኩል አደራዳሪ የነበሩት ዴኒስ ሮዝ ክስተቱን አስመልክተው ሲናገሩ፡- ‹‹ናታንያሁ ክስተቱን ተንተርሰው የወሰዱትን የእገዳ አቋም ተሻግሮ ለማለፍና ስምምነቱን ተፈጻሚ ለማድረግ ፈተናው ከባድ ነው። ... እውነቱን ለመናገር የተፈጠረው ነገር አሳዛኝ ነው። ምክንያቱም ፍልስጤማውያን ሰላሙን ለማምጣት በኦስሎ ስምምነት እንዲፈጽሙት የተሰጣቸውን ግዴታ በአብዛኛው እየተወጡት ነበርና። በተለይም ደግሞ የአሸባሪዎችን ድርጊት መግታትና በዚህ ድርጊት የሚጠረጠሩና የተሳተፉ ሰዎችን ማሰርን የተመለከተውን የስምምነቱን ነጥብ በሚገባ እየፈጸሙት ነበር።›› ብለዋል። [78] እንደዚያም ቢሆን እንደ እስራኤላዊው ምሁር አብረሃም ቤን ዜቪ ምልከታ፣ “ ... የክሊንተን

አስተዳደር የናታኒያሁን አያያዝ አስመልክቶ ያደረበት ተስፋ መቁረጥ የአሜሪካንና እስራኤልን ልዩ ግንኙነት ሲጎዳው አልተስተዋለም፡፡››[79]

አሜሪካ በእስራኤል ላይ ልታሳድረው የምትችለውን ተጽእኖ የአሜሪካ መሪዎች በእስራኤል ድርጊት በበገኑባቸው ጊዜያትም እንኳን ሳይቀር ሲጠቀሙበት አልታዩም። ፕሬዚዳንት ጀራርድ ፎርድና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሄነሪ ኪስንጀር በ1975፣ ማለትም እስራኤልን ከግብጽ ጋር ለማስታረቅ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ በነበሩባቸው ጊዜያት በእስራኤላውያኑ ሀሳብ ግትርነት ትዕግሥታቸው እየተሟጠጠ በመሄዱ እርዳታ አድንደሚያግዱና አሜሪካ በእስራኤል አንጻር የምትከተለውን ፖሊሲ እንደሚገመግሙ በመግለጽ አስፈራሩ፡፡ በሚያስደንቅ ሁኔታ አይፓክ የተባለውና የአሜሪካና የእስራኤል የሕዝብ ጉዳዮች ኮሚቴ በመባል የሚታወቀው ሎቢ አድራጊ አካል የሰባ ስድስት ሴናተሮችን ፊርማ የያዘና ፕሬዚዳንት ፎርድ ለእስራኤል የኢኮኖሚና ወታደራዊ ድጋፍ ማድረጋቸውን እንዲቀጥሉ የሚጠይቅ የድጋፍ ደብዳቤ አቀረበ፡፡ ለእስራኤል የሚሰጠውን እርዳታ ለማቆም ችሎታ የነበራቸው ፎርድና ኪሲንጀር በዚህ ጊዜ ያንን አቋማቸውን ይዘው ለመጓዝ ያላቸው እድል አነስተኛ ነበር፡፡ በመሆኑም የዲፕሎማሲውን ጥረታቸውን በመቀጠል እስራኤልን የሚያነቃቁበትን ተጨማሪ እርዳታ ለመልቀቅ ተገደዱ፡፡[80]

በ1978 የተዘጋጀውንና በቀጣዩ ዓመት ለካምካፕ ዴቪድ ሙሉ ስምምነት የሚያደርሰውን ዕቅድ የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ሜናሂም ቤጊን ባለመተግበራቸው ፕሬዝዳንት ጂሚካርተር ተናደውባቸው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጣትን እርዳታ ከዚህኛው ጉዳይ ጋር ለማስተሳሰር አልሞከሩም፡፡[81] የክሊንተን አስተዳደርም ቢሆን ጠቅላይ ሚኒስትር ናታንያሁና እርሳቸውን የተካቸው ኢሁድ ባራክ በኦስሎ ስምምነት መሠረት እስራኤል የገባቻቸውን ግዴታዎች እንደማያሟሉ ሲያውቅ ስጋት አድሮበት ነበር፡፡ ኢሁድ ባራክ ሶስት የእየሩሳሌም መንደሮችን ለፍልስጤማውያን ለመመለስ የገቡትን ቃል በማፍረሳቸው ክሊንተን በጣም ተበሳጭተው እንደነበር ተዘግቧል፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ ክሊንተን በያሲር አረፋት ዓይን ሚዛን የሌላቸውና በተናገሩት የማይረጉ

ቀላል ሆነው እንዲታዩ ስላደረጋቸው ነው። ክሊንተን በንዴት የጦፉበት ሌላ አጋጣሚም ተከስቶ ነበር። ይኸውም በ2000 ዓ.ል በተደረገው የካምፕ ዴቪድ ግንኙነት ላይ ኢሁድ ባራክ እንዲህ ባሏቸው ጊዜ ነበር፦ "እኔ አራፋትን መሬታቸውን እንደወሰደ ሰው ሆኜ ላያቸው አልሻም! እርስዎ ሊያደርጉት ይችላሉ። እኔ ግን እንዲያ ለማድረግ ፈጽሞ አልችልም። ይህ እውነት አይደለም። ይህ ክብደት የሚሰጠው ድርድር መሆን የለበትም።"[82] እንደዚያም ሆኖ አሁንም ክሊንተን የእርዳታ እጃቸውን ላይዘረጉ እንደሚችሉ በመናገር እስራኤልን ለማስፈራራት አልሞከሩም።

እርግጠኞች ሆነን መናገር የምንችለው አሜሪካ በእስራኤል ድርጊት አለመደሰቷን ለመግለጽ አልፎ አልፎም ቢሆን የተወሰነ የእርዳታ እቀባ የምታደርግ መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ እርምጃ ጊዜያዊና በእስራኤል ባህሪ ላይ ብዙም ተጽእኖ የማያስከትል ሆኖ ነው የሚያልፈው። ለምሳሌ እስራኤል፣ በ1977 በደቡብ ሊባኖስ በነበረው ውዝግብ ጣልቃ ለመግባት በማሰብ አሜሪካ ሠራሽ የሆኑ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎችን በክልሉ አዘመተች። (ይህ ድርጊት፣ ከአሜሪካ ጋር በደረሰችበት ስምምነት መሠረት ራሷን ለመከላከል ጉዳይ ብቻ የአሜሪካን መሣሪያዎች መጠቀም እንዳለባት የሚያዘውን ውል ማፍረሷን ያሳያል። ከዚህም በተጨማሪ በሊባኖስ ጉዳይ እስራኤል አሜሪካን ሳታማክር ምንም ነገር እንደማትፈጽም ሜናሂም ቤጊን የገቡትን ቃል ማፍረሳቸውን ያመለክታል።) ድርጊቱ መፈጸሙን መጀመሪያ ላይ ቤጊን የካዱ ቢሆንም፤ የተወሳሰቡ የስለሳ መረጃዎች እስራኤል ድርጊቱን መፈጸሟን በማረጋገጣቸው የካርተር አስተዳደር ለእስራኤል የሚሠጡ እርዳታዎችን እንደሚገታ በመጥቀስ አስፈራራ። ቤጊንም እነዚያ አሜሪካን ሠራሽ የሆኑ ብረት ለበስ ካሚዎኖች ከሊባኖስ እንዲወጡ ወዲያው ትእዛዝ ሰጡ።[83]

በተመሣሣይ ሁኔታ የሬገን አስተዳደር በ1981 በአሜሪካና እስራኤል መካከል የተደረሰውን ስትራቴጂያዊ ስምምነት ለማገድ ወሰነ። ያንንም ያደረገው እስራኤል የጎላን ከፍታዎችን በተጨባጭ ይዛ መቆየቷን በመቃወም ነበር። ምንም እንኳን እስራኤል ከጎላን ከፍታዎች ለመልቀቅ ፈጽሞ ባታቅድም፤ ቤጊን ቆየት ብለው የስምምነቱን ዋና ዋና ደንቦች ተግባራዊ ማድረጋቸውን

ቀጥለዋል፡፡ እስራኤል በ1982 ሊባኖስን በወረረችበት ጊዜ የክላስተር ቦምብ ጥቅም ላይ ማዋሏ ከተረጋገጠ በኋላ አሜሪካ ይህን መሣሪያ ለእስራኤል ላለመስጠት ወስናለች፡፡ ሆኖም ግን በ1988 አሜሪካ ይህን መሣሪያ እንደገና ለእስራኤል መስጠቷን ቀጠለች፡፡[84] አሜሪካ በእስራኤል ላይ የምታሳድረው ጫና እስራኤል ቤይሩትን በ1982 ከወረረች በኋላ በፒ.ኤል.ኦ. ሠራዊት ላይ ሙሉ ጥቃት እንዳትፈጽም አድርጓታል። ያም ሆኖ የእስራኤል መሪዎች ይህን እቀባ ለማክበር ሲያመነቱ ታይተዋል፡፡ ከዚያ በኋላም እነርሱን ለማሳመን ሳይቻል በመቅረቱ ፒ.ኤል.ኦ. ተመትቷል፡፡[85]

በ1991 ላይ ደግሞ ትልቁ ቡሽ የኢሳቅ ሻሚርን መንግሥት በማሳመን አዳዲስ የሰፈራ መንደሮችን እንዳይገነቡ ማድረግ ችለው ነበር። ይህንንም ለማሳካት የተጠቀሙት ስልት ሻሚር የሰላም ስምምነት ለመፈረም ዝግጁ እንዲሆኑና ለዚሁም ማካካሻ ይሆን ዘንድ የ10 ቢሊዮን ዶላር የብድር ዋስትና ማቅረብ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የዋስትና እገዳው የቆየው ለጥቂት ወራት ብቻ ሲሆን፣ኢሳቅ ራቢን፣ ኢሳቅ ሻሚርን በተካቸው ጊዜ እገዳው ሊነሳ በቅቷል፡፡[86] እስራኤል አዳዲስ የሰፈራ መንደሮችን መገንባትን ለማቆም ብትስማማም ቀደም ብለው የተገነቡትን የማስፋፋቱን ሥራ በመቀጠሏ በኃይል በተያዙት መሬቶች ላይ የሠፈሩት ዜጎች ቁጥር በ1991 8000 (በ14.7 በመቶ)፣ በ1993 ላይ 6900(በ10.3 በመቶ)፣ በ1994 ደግሞ 6300 (በ9.7 በመቶ) እንዲሁም በ1994 ላይ 7300 (በ9.1 በመቶ) ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ይህ አሃዝ በእነዚያ ዓመታት አጠቃላዩ የእስራኤል ሕዝብ ዕድገት ከሚያሳየው አሃዝ የበለጠ ሆኖ ተገኝቷል፡፡[87]

እስራኤል በምዕራባዊ ወንዝ ዳርቻ የምትገነባውን የግንብ አጥር በሁለተኛው ቡሽ ዘመነ ሥልጣን ወቅት በ2003 አሜሪካ ተቃውማ ልትሰጣት የምትችለውን የብድር ዋስትና በመቀነስ ልትቀጣት ሞክራለች፡፡ አጠቃላይ የሆነውን የብድር ዋስትና ማገድ ወይም የፀጥታ እርዳታን መጠን መቀነስ ውጤት ያለው ተጽእኖ ሊያመጣ ይችል ነበር፡፡ ሆኖም ግን ለእስራኤል ከሚሰጣት ብድር ውስጥ በፍልስጤማውያን መሬት ላይ ግንብ የምታንጽበትን ገንዘብ የሚመጥን ብቻ እንዲቆረጥባት ማድረግን ነበር ቡሽ የመረጡት፡፡ በዚህ ሁኔታ እስራኤል ባትደሰትም ከአነስተኛ የብድር ገንዘብ

ከፍተኛ የወለድ መጠን በመክፈል ጥቂት ሚሊዮን ዶላሮችን በቅጣት መልክ ወጪ አድርጋ የምትፈልገውን የግንብ አጥር ማጠሯን ቀጠለች። ዩ.ኤስ.አሜሪካ ለእስራኤል ከሰጠቻትና ወደፊትም ከምትሰጣት በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር እርዳታ አንጻር ይህ በቡሽ የተጣለባት አነስተኛ ቅጣት በአንደኛው የእጅ መዳፍ ሌላኛውን በጥፊ የመምታት ያህል ሕመም የማያስከትል ነበር። በመሆኑም ይህ እርምጃ በእስራኤል አጠቃላይ ባህሪ ላይ ይህ ነው የሚባል ተጽእኖ ሊያስከትል አልቻለም።

ዲፕሎማሲያዊ መከታና በጦርነት ጊዜ የሚደረግ ድጋፍ

እነዚህን ከመሳሰሉት ተጨባጭ የሆኑ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ እርዳታዎች በተጨማሪ ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል በየትኛውም የዓለም ፖለቲካ መድረክ ቋሚና ሙሉ ድጋፏን ስትሰጣት ኖራለች፤ እየሰጠቻትም ነው። ከ1972 እስከ 2006 ባሉት ዓመታት እንኳን ዋሽንግተን ለእስራኤል እጅግ አደገኛ የሆኑ የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔዎችን ውድቅ ለማድረግ ድምፅን በድምፅ የመሻር መብቷን ለ42 ጊዜያት ያክል ተጠቅማለች። ይህ ቁጥር ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት (Veto power) ያላቸው ሌሎች አገራት ሀገራት በተመሳሳይ ዓመታት ካደረጓቸው አጠቃላይ ድምጽን በድምጽ የመሻር ውሳኔዎች የሚበልጥ ሲሆን፤ አሜሪካ ካደረገቻቸው አጠቃላይ ድምጽን በድምጽ የመሻር ውሳኔዎች ደግሞ ከግማሽ በላይ የሚሆነውን መጠን ይሏል።[88] ከዚህ ጋር መታየት የሚገባው ነገር በእነዚያ ዘመናት እስራኤልን የሚመለከቱ በርካታ የውሳኔ ሀሳቦች (resolutions) ለፀጥታው ምክር ቤት ያልቀረቡ መሆኑን ነው። እንደዚያ ሊሆን የቻለው አሜሪካ የውሳኔ ሀሳቦቹ ቢቀርቡ ድምፅን በድምፅ የመሻር መብቷን ተጠቅማ ውድቅ እንደምታደርጋቸው በየጊዜው ስለምታስፈራራ ነው። በ2002 በተባበሩት መንግሥታት የአሜሪካ አምባሳደር የነበሩት ጆን ኔግሮፖንቴ ለፀጥታው ምክር ቤት እንዳስታወቁት «ከእንግዲህ እስራኤልን የሚያወግዝ ማንኛውም የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ አሸባሪነትን በአጠቃላይ፣ ኢስላሚክ ጀሃድን፣ ሃማስንና የአል - አቅሷ ብርጌድን ደግሞ

በተለይ በስም ጠቅሶ እስካላወገዘ ድረስ ድምፅን በድምፅ በመሻር መብታችን ተጠቅመን ውድቅ እናደርገዋለን›› ብለዋል፡፡[89] ዩናይትድ ስቴትስ እስራኤልን ገስፃለች ከተባለ በጥቂት አጋጣሚዎች ብቻ ሲሆን፣ ይህም እስራኤል መጥፎ የሚባል ተግባር መፈጸሟ ሲረጋገጥና የፀጥታው ምክር ቤትም በእርሷ ላይ የሚያሰማው ክስ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ሲሆን ወይም ደግሞ በእስራኤል ሀሳብ ግትርነት ያልተደሰተች እንደሆነ ብቻ ነው፡፡[90]

ከፀጥታው ምክር ቤት ውጪ አሜሪካ ምንጊዜም እስራኤልን ደግፋ የምትቆም ሲሆን፣ ጉዳዩ በተመድ ጠቅላላ ጉባዔ ከታዬ ደግሞ ውሳኔው አሳሪ ባይሆንም እንኳ፣ የእስራኤልን ድርጊት ለስሙ ብቻ በማውገዝና ከፍልስጤማዊያን ጎን ለይስሙላ ብቻ በመቆም የሚወሰን ቢሆንም እንኳ አሜሪካ እስራኤልን መደገፏን አትተውም፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከብዙ አጋሮቿ የተለዩ አቋም በመያዝ በጣት ከሚቆጠሩ ጥቃቅን ሀገራት ጋር ብቻዋን ትቀራለች፡፡ ለዚህ አባባል እንደጥሩ ማሳያ ተደርጎ ሊቀርብ የሚችለው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔ 59/124 ሲሆን፤ ‹‹እስራኤል የፍልስጤማውያንን ሰብዓዊ መብት ረግጣለች ›› የሚል ነበር፡፡ ይህ የውሣኔ ሀሳብ 149 ለ 7 በሆነ ድምፅ አልፏል፡፡ (22 ሀገራት ድምፀ ተአቅቦ ያደረጉ ሲሆን 13 የሚሆኑት ደግሞ ድምፅ አልሰጡም)፡፡ ታኅሣሥ 10 ቀን 2004 የተካሄደውን ይህን የውሣኔ ሀሳብ ከደገፉት ሐገራት ውስጥ ጃፓን፣ ጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ ቻይና እና ታላቋ ብሪታንያ ይገኙበታል፡፡ ከአሜሪካ ውጭ ይህን ሀሳብ የተቃወሙት ሀገራት ከአውስትራሊያ በስተቀር የቀሩት ራሷ እስራኤል፣ የማርሻል ደሴቶች፣ ሚክሮኔሺያ፣ ናኡሩና፣ ፓላኢ የሚባሉ ደቃቃ ሀገራት ናቸው፡፡[91]

በተመሳሳይ ሁኔታ እስራኤል የምታካሂደው ግልጽ ያልወጣ የኑክሊዬር መሣሪያ ጉዳይ በአቶሚክ ኃይል ተቆጣጣሪ ድርጅት በኩል እንዲነሳ የአረብ ሀገራት ጥረት ሲያደርጉ ድርጅቱ ይህን ጉዳይ በአጀንዳነት እንዳይዘው ዋሽንግተን ትከላከላለች፡፡ የእስራኤል ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ የሆኑት ጆናታን ፔልድ ፎርዋርድ ለተባለው የአይሁዳዊያን ጋዜጣ የ2003 እትም በሰጡት ቃለ ምልልስ በጉዳዩ ዙሪያ የሚከተለውን ብለዋል፡- “ይህ ጉዳይ በየዓመቱ በአጀንዳነት እንዲያዝ ለማድረግ አረቦች የሚጥሩ ቢሆንም፣

በእስራኤል ላይ የውሣኔ ሀሳብ እንዲሰጥ የአቶሚክ ኃይል ተቆጣጣሪ ድርጅቱ የገዢዎች ቦርድ (IAEA Board of governers) ይሁንታ ያስፈልጋል፡፡ ይሁንታው እንዳይገኝ ደግሞ ዋሽንግተን በቦርዱ ላይ ተጽእኖዋን ታሳርፋለች፡፡››[92]

አሜሪካ በዲፕሎማሲና በጦርነት ጊዜያት ለእስራኤል የምታደርገው እገዛ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ሄዷል፡፡ ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተገለጸው በ1950 የአይዘንሃወር አስተዳደር እስራኤልን በስዊስ ጦርነት ጊዜ ከያዘችው የግብጽ መሬት እንድትወጣና የወንዞቹን አቅጣጫ በመለወጥ ለራሷ ጥቅም ለማዋል የምታደርጋቸውን ሙከራዎች እንድታቆም ማድረግ ተሳክቶለታል፡፡ ከ1960ዎቹ በኋላ ግን አሜሪካ የእስራኤልን ፍላጎት ለማስከበር የበለጠ እየተነሳሳች የሄደችበት ሁኔታ ተከስቷል፡፡ ፍላጎቷንም በተለያዩ ዋና ዋና የግጭት ጊዜያቶችና ስምምነት በተደረገባቸው አጋጣሚዎች አንጸባርቃለች፡፡ እርግጥ ነው ዋሽንግተን፣ ቴሌአቪቭ የጠየቀቻትን ሁሉ ሰጥታታለች ማለት አይደለም፡፡ሆኖም ግን የምታደርግላት ድጋፍ የማይቋረጥና አንጀት የሚያርስ ሆኖ መቀጠሉ ገሀድ ነው፡፡

በእስራኤልና በሶሪያ መካከል የነበረው ቁርቁስ እየተባባሰ በሄደበት ከ1966--67 በነበረው ጊዜ የግብጹ ፕሬዚዳንት ጀማል አብዱልናስር ወታደሮቻቸው በግንቦት ወር ወደ ሲናይ ምድረ-በዳ እንዲመለሱ ትዕዛዝ ሰጡ። ይህ የናስር ድርጊትም የእስራኤልን መሪዎች በማንቃት ሰፊ ለሆነ ውጊያ እንዲዘጋጁ አነሳሳቸው፡፡ የጆንሰን መንግሥት ግን የእስራኤል ጦር ከአረብ ጠላቶቹ በተሻለ የበላይነት ላይ እንደሚገኝ ያምን ነበር። እንደዚያም ቢታሰብ የአረብን ጦር ጥቃት አደገኛነት ሁሉም በሚገባ ተገንዝበውታል፡፡[93] የእስራኤል ጦር የበላይ አዛዥ ጂኤራል ኧርል ሀዊለር ለፕሬዚዳንት ጆንሰን እንዲህ ብለዋቸው ነበር፡- ‹‹በእስራኤልና በአረቦች መካከል ጦርነት ቢጀመር ጦርነቱን ከአምስት እስከ ሰባት በሆኑ ቀናት ውስጥ እናሸንፋለን ብለን እንገምታለን፡፡›› ፕሬዚዳንት ሊንደን ጆንሰን ለያኬው የእስራኤል ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አባ ኢባን እንዲህ ብለዋቸዋል፡- ‹‹ግብፅ ጥቃት ከጀመረች በላይዋ ላይ የገሃነምን እሳት አንድዱባት፡፡››[94] ዋና ዋና የሚባሉት የእስራኤል መሪዎች ከዚህ አስተያየት ጋር ቢስማሙም ስሜታቸውን ትጋራና ድጋፏን

ትሰጣቸው ዘንድ በመሻት የማስጠንቀቂያ ሪፖርቶችን ወደ ዋሽንግተን መላካቸውን ቀጥለው ነበር።[95]

ይህ በእንዲህ እያለ አሜሪካ የራሷን ግምገማ ካደረገች በኋላ የእስራኤል መንግሥት ኃይልን ከመጠቀም ይልቅ የዲፕሎማሲን መንገድ እንዲመርጥ በመገፋፋት ጦርነቱ እንዳይፈነዳ ለማድረግ ጥረት ታደርግ ነበር።[96] ፕሬዚዳንት ጆንሰን ግብፅ የቴራንን የባህር ወሽመጥ ለመዝጋት መወሰኗን ‹‹ሕገወጥ›› ብለው የጠሩት ሲሆን፣ ምንም እንኳን ለእስራኤል የሀዘኔታ ስሜት ቢያድርባቸውም እንደ ቬትናሙ ጦርነት በመሰለ ሁኔታ ሀገራቸውን ለመዝፈቅ ስላልፈቀዱ እስራኤላውያንን ለመርዳት ቃል መግባት አልፈለጉም። ይሁን እንጂ እስራኤል ወደ ጦርነቱ እንዳትገባ የሚያደርጉትን ግፊት ቀስ በቀስ እያለዘቡ ቆይተው በሰኔ ወር ላይ እርሳቸውና በርካታ አማካሪዎቻቸው እስራኤል በጦርነቱ ብትገፋበት እንደማይቃወሙ፣ ሆኖም ግን ነገሮች መጥፎ አዝማሚያ እየያዙ ከሄዱ የአሜሪካን እገዛ መጠበቅ እንደማይኖርባቸው ለእስራኤል ሹማምነት ገለጹላቸው። የአሜሪካ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ዲን ሩስክ ደግሞ ለአንድ ጋዜጠኛ “እኛ ማንንም ቢሆን የማቀብ ኃላፊነት አለብን ብዬ አላስብም’’ በማለት አቋማቸውን ግልጽ አደረጉ። “ሰኔ 3 ቀን ላይ የነበረው አዝማሚያ’’ ይላሉ ሚካኤል ብራቸር የተባሉ ሰው ሁኔታውን ከገመገሙ በኋላ ሲናገሩ፡- “እስራኤል ጦርነቱን የመጀመሩን ቅድሚያ ብትወስድ አሜሪካ የማትቃወማት መሆኑን መገንዘብ ችላ ነበር።›› በኋላ በግልጽ እንደታየውም ፕሬዚዳንት ጆንሰን ለእስራኤል ያደረጉትን አንድ ተንታኝ ሲገልጹት፡- “ለጥቃት ቢጫ መብራት እንደማሳየት ነበር›› ብለውታል።[97] ጆንሰን ሀሳባቸውን ባልተጠበቀ ሁኔታ መቀየራቸው እስካሁን ድረስ እንቆቅልሽ እንደሆነ ቀርቷል። እርግጥ ነው የእስራኤል ደጋፊ የሆኑ ክፍሎችና አማካሪዎቻቸው እንዲሁም በእስራኤል ኤምባሲ አደራጅነት በደብዳቤ የድጋፍ ድምፅ ያሰባሰቡ ሰዎችና ‹‹እስራኤል ልትጠቃ ትችላለች›› የሚለው ስጋት ተጽእኖ አድርጎባቸው ሊሆን ይቻላል።[98]

አሜሪካ ጦርነቱን ለማስቆም በእስራኤል ላይ በቂ ጫና ማሳረፉን አልመረጠችም። ምክንያቱም እስራኤል በጦርነቱ አሸንፋ እንድትወጣ

በመፈለጓ ነበር። ጦርነቱ እንዳለቀም አስራኤል የፈጸመቻቸውን ጉዳዮች በማንሳት አልወቀሰቻትም። የእስራኤልን የጎላን ከፍታዎች ወረራ ተከትሎ ሶቪየት ሕብረት ጣልቃ እንደምትገባ በመግለጽ ማስፈራሪያ ባሰማች ጊዜ ፕሬዚዳንት ጆንሰን የሶቪየቶችን ጣልቃ ገብነት መከላከል ይቻል ዘንድ የአሜሪካ ሶስተኛው የባሕር ኃይል ብርጌድ መርከቦች ወደ እስራኤል ድንበር እንዲጠጉ አዘዙ። በ1956 ከተካሄደው የስዊዝ ጦርነት ጋር በሚመሳሰል ሁኔታ የጆንሰን አስተዳደር ሰፋ ያለ የሰላም ንግግር ካልተደረገ በስተቀር እስራኤል ከያዘቻቸው ግዛቶች እንድትወጣ ጫና እንደማያደርግባት ግልጽ አደረገ።[99] እንዲሁም የእስራኤል ባህር ኃይልና የአየር ኃይል ሰኔ 8 ቀን 1956 ዮ.ኤስ. "ሊበሪቲ" በተባለችው የአሜሪካ ቃኚ መርከብ ላይ ያደረሰችውን አሳዛኝ ጥቃት አስመልክቶ እስራኤልን ተጠያቂ እንደማታደርግ አሳወቀች።[100] ዩናይትድ ስቴትስ በጦርነቱ መጀመሪያ ላይ ለእስራኤል ዲፕሎማሲያዊና ወታደራዊ ጥበቃ አላደረገችላት ይሆናል። ይሁን እንጂ ይህ ማለት አሜሪካ ለእስራኤል የሀዘኔታ ስሜት የላትም ማለት አይደለም።

ዩናይትድ ስቴትስ ከዚህም በላይ ከ1969 - 70 በእስራኤልና በግብፅ መካከል በተደረገው የማድከም ጦርነት (War of Attrition) ወደ እስራኤል በግልጽ አዘንብላለች። በዚህ ጦርነት ጊዜ የአሜሪካ እርዳታ ቀጣይነት እንዲኖረው መደረጉ -እንደ ፕሬዚዳንት ኒክሰንና ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኪሲንጀር እምነት - ሶቪየት ሕብረት ለግብጽ የምተሰጣት ወታደራዊ እርዳታ ውስን መሆኑ እንዲታወቅና በመጨረሻ የሞስኮ አረብ ወዳጆች ጉድኝታቸውን ከአሜሪካ ጋር እንዲያደርጉ ተጽእኖ ያሳድርባቸዋል። ምንም እንኳን የኒክሰን አስተዳደር እስራኤል የምትልጋቸውንና እንዲሰጧት የጠየቀቻቸውን መሣሪያዎች ሁሉ ባያቀርብላትም፣ (ይህ ሁኔታ አልፎ አልፎ በሁለቱ ሀገራት መካከል መካረርን ሲያስከትል መቆየቱ እንዳለ ሆኖ) እስራኤል ለሰላሙ ጥረት ትኩረት ሰጥታ እንድትንቀሳቀስ ከመገፋፋት ይልቅ በጦር መሣሪያ መደገፉን ነበር መርጦ የቆየው። ሆኖም ግን በሁለቱ ተቃራኒ ኃይላት በኩል ግጭቶች እየተባባሱ በመሄዳቸው የኃይል ቁርቁስን የሚጋብዝ ሁኔታ ሲፈጠር ዋሽንግተን ፈጠን ብላ እስራኤልን የተኩስ ማቆም እንድታደርግ በማግባባት እርዳታ እንደምትሰጣትም ቃል ገባች። [101]

ለምሳሌ፡- በ1972 በአሜሪካና በእስራኤል መካከል የተደረገው የመግባቢያ ስምምነት አሜሪካ ለእስራኤል የጦር አወሮፕላኖችንና ታንኮችን እንድትሰጣት፣ ይህንንም በረዥም ጊዜ እቅድ ውስጥ አስገብታ እንድትሠራበት የሚያዝ ነበር። ከዚህም በላይ ኒክሰንና ኪሲንጀር ለወደፊቱ አዲስ የሰላም ሀሳብ ከማቅረባቸው በፊት እስራኤልን እንደሚያማክሯት ቃል የገቡበት ስምምነት ነው። ይህን በማድረግ በዘመኑ ከነበሩት ሁለት ልዕለ ኃያላን መካከል እንዱ የሆነው የአሜሪካ መንግሥት ለዚያች ትንሽ ሀገር ከሚገባት በለይ ትኩረትና የዲፕሎማሲ ከለላ ሰጥቷታል። ዊሊያም ኩሃንድት የተባሉ ሰው ይህን ሁሉ ካስተዋሉ በኋላ የሚከተለውን መጻፋቸው አያስደንቅም። "በ1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ ዩናይትድ ስቴትስ በመካከለኛው ምሥራቅ ታራምደው የነበረው ፖሊሲ እስራኤልን በግልጽ ከመደገፍም በላይ ብዙ ርቀት የተጓዘ ነበር።" በተመሳሳይ ሁኔታ የእስራኤል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት አባ ኢባን ይህን ዘመን "ዩናይትድ ስቴትስ እስራኤልን በሚገባ ያስታጠቀችበት ወርቃማው ዘመን" በማለት ጠርተውታል።[102]

ጥቀምት ወር በ1973 በተደረገው የእስራኤል - ግብጽ ጦርነት አሜሪካ ለእስራኤል ያቀረበችው እርዳታ እጅግ የሚያስደንቅ ነበር። ፕሬዚዳንት ኒክሰንና ውጭ ገዳይ ሚኒስትራቸው ኪሲንጀር መጀመሪያ ላይ እስራኤል ጦርነቱን በፍጥነት እንደምታሸንፍ ተማምነው የነበረ ቢሆንም፣ ዘግይተው እንደተገነዘቡት ግብፅ የእስራኤልን ጦር በሲናይ በረሃ አደባይታ አከርካሪውን መስበር በመቻሏ አሜሪካን የሚጠብቃት የድህረ-ጦርነት እርዳታ ጫና ግልጽ ሆኖ ታዬ። ይህም እስራኤል ጦርነቱን በወሳኝነት ማሸነፏ ቀርቶ ታላቅ የሆነ አጣብቂኝ ውስጥ በመግባቷ የተከሰተ ምስቅልቅል ነበር። ኪሲንጀር ያንን ክስተት በማስታወሻቸው ላይ እንዲህ በማለት አስፍረውታል፡- ‹‹መጀመሪያ እንደገመትነው ጦርነቱን እስራኤል በአሳማኝ ሁኔታ ካሸነፈች የሁሉም አረቦች ቅሬታ የሚያርፍብን የትኩረት ማዕከል እንዳንሆን መጠንቀቅ አለብን። ሶቪየት ሕብረትም የአረቦች አዳኝ (Savior of Arabs) ሆና ብቅ እንዳትል የቻልነውን ያክል መጣር አለብን። ሆኖም ግን ያላሰብነው ሁኔታ ከተከሰተና እስራኤል አደጋ ላይ ከወደቀች እርሷን ለማዳን

ማንኛውንም አስፈላጊ ነገር ሁሉ መፈጸም ይኖርብናል፡፡››[103] እንግዲህ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ታሳቢ በማድረግና እስትራቴጂያዊ ዒላማዎችን በማውጠንጠን አሜሪካ የእስራኤልን የድረሱልኝ ጥያቄ ለዘብ አድርጋ ያዘች፡፡ ይሁን እንጂ እስራኤል ከግብጽ ጦር በደረሰባት ከባድ ጡጫ የተነሳ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መውደቋ ሲረጋገጥ ኒክሰንና ኪሲንጀር ሙሉ የሆነ ወታደራዊ አቅርቦት በአየር እንዲጓጓዝ በመፍቀድና ይህንኑም በማስፈጸም 2.2 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታቸውን ለእስራኤል አሸርጎደጎዱ፡፡[104] ምንም እንኳን መጀመሪያውኑም የድሉ አዝማሚያ በተቃራኒ አቅጣጫ እየዞረና እስራኤል እያጠቃች ቢሆንም፣ አሜሪካ የላከችው ይህ ግዙፍ እርዳታ የእስራኤልን ሞራል ከፍ በማድረግ ድል አድራጊነቷን እንድታረጋግጥ አስችሏታል፡፡[105] እንዳለመታደል ሆኖ ግን ይህ ጊዜ ለአሜሪካ መልካም ነገር አላመጣላትም፡፡ በዚህ ድርጊቷ የአረቦች የነዳጅ ዘይት እቀባ ሰለባ በመሆን ፍዳዋን አይታለች፡፡ በዚያ ሳቢያ የነዳጅ ዋጋ በመላው ዓለም የጨመረ ሲሆን፣ አሜሪካና አጋሮቿ በዚህ ዕቀባና የአቅርቦት ቅነሳ ብዙ ዋጋ ከፍለዋል፡፡

የዩናይትድ ስቴትስ የዲፕሎማሲ ጥረት በተወሰነ መልኩም ቢሆን እስራኤልን አግዟታል፡፡ አሜሪካ ንጉሥ ሁሴንን በማግባባት ዮርዳኖስ በዚህ ጦርነት ውስጥ እንዳትገባ ለማድረግ የቻለች ሲሆን፣ ግብጽና እስራኤልም ከተኩስ አቁም ስምምነት ላይ እንዲደርሱ ኪሲንጀር ላይ ታች ማለቱን ተያያዙት፡፡ (በተለይም ደግሞ ጥቅምት 21 ቀን ከሞስኮ መሪዎች ጋር ያደረጉት ንግግር ወሳኝ ነበር)፡፡ ይህን ሁሉ ሲያደርጉም ጦርነቱ እስኪገባደድ ድረስ እስራኤል በወሳኝነት ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት መሸጋገሯን በዓይነ ቁራኛ እየተመለከቱ ነበር፡፡ አሜሪካ ይህን ጦርነት በመካከለኛው ምሥራቅ አጠቃላይና የሚያግባባ ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ ጫና ማሳደሪያ መሳሪያ አድርጋ እንደምትጠቀምበት ለሶቪየቱ ዋና ፀሐፊ ሊኦኔድ ብሪዥኔቭ እንዲገልጹላቸው ኒክሰን ኪሲንጀርን አዘዟቸው፡፡ ይሁን እንጂ ኪሲንጀር ሞስኮ ከገቡ በኋላ እስራኤል የበላይ የምትሆንበት ቀላል የተኩስ አቁም ስምምነት እንዲደረስ ዲፕሎማሲውን ያቀላጥፉት ያዙ፡፡ ሶቪየት ሕብረትን ከሰላሙ ስምምነት የማግለል ይፋ ያልሆነ ጥረታቸውንም በጎን ተያይዘውት

ነበር። የታሪክ ባለሙያው ኬኔት ስቴይን እንደሚገልጹት፡- ‹‹ኪሲንጀር ከብሬዝኔቭ ጋር ባደረጓቸው ሶስት ተከታታይ የግንኙነት ጊዜያት ሁሉ በተደጋጋሚ ከኒክሰን አቋም ተባራሪ በሆነ ሁኔታ የእስራኤልን ፍላጎት ወክለው ነበር ሲደራደሩ የቆዩት። ኪሲንጀር ያለምንም መሸፋፈን በክሬምሊን ቤተ-መንግሥት ውስጥ አሜሪካን ሳይሆን እስራኤልን ወክለው ነበር የቀረቡት ማለቱ ይቀላል።››[106]

የፀጥታው ምክር ቤት ጥቅምት 22 የተኩስ አቁም ስምምነት ውሳኔ ሲያሳልፍና ሁለቱም ወገኖች በ12 ሰዓታት ውስጥ ተኩስ እንዲያቆሙ ሲያዝ ኪሲንጀር በጎን እስራኤል ይህን አቋም እንዳትቀበልና ድሉ ፍፁም የእርሷ መሆኑ እስኪረጋገጥ ድረስ ውጊያውን እንዳታቆም ይጎተጉቱ ነበር። ኪሲንጀር ቀደም ብለው ለእስራኤል አምባሳደር ሲምቻ ዲኒትዝ እርሳቸው የዲፕሎማሲውን ጣጣ ለመጨረስ ላይና ታች ሲሉ እስራኤል የግብጽን ጦር አከርካሪ ለመስበርና ወታደራዊ የበላይነቷን ለማረጋገጥ ጊዜ መግዣ ይሆናታል ብለዋቸዋል። የተኩስ አቁም ስምምነቱ በፀጥታው ምክር ቤት ከተወሰነ በኋላ ኪሲንጀር በምስጢር እስራኤል ተኩስ አቁሙን እንድትጥስና የመጨረሻው የተኩስ አቁም ማስፈጸሚያ ቀን ከመድረሱ በፊት ሁነኛ ድል እንድትጨብጥ ፈቃድ ሰጥተዋትም ነበር።[107] ተኩስ አቁሙ ሙሉ በሙሉ ተጥሶ የእስራኤል ኃይል የግብፅን ሶስተኛውን ሠራዊት በከበበት ጊዜ ሶቪየት የራሷን ሠራዊት በማዘመት ጣልቃ እንደምትገባ በመግለጽ አስፈራራች። በዚህ ጊዜ ሊክሰንና ኪሲንጀር፣ ሞስኮ ከዚህ ጦርነት ራሷን እንድታርቅ የሚያስጠነቅቅ መግለጫ አወጡ። እስራኤልን ደግሞ ‹‹ውጊያ ማቆሚያው ትክክለኛ ጊዜ አሁን ነው!›› በማለት አስገነዘቡ።

ምንም እንኳን የ1975ቱ የእስራኤል ጦር ከሲናይ ምድረ-በዳ ቀስ በቀስ የሚወጣበት ስምምነት ጠንካራ የሰላም ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ መሆኑ ባይካድም፤ አሜሪካ በማንኛውም መልኩ የእስራኤል ፍላጎት እንዲከበር ትጥር ነበር። ተጨማሪ እርዳታ ከመስጠት አንስቶ ለወደፊቱ የሰላም ስምምነት እስራኤል ከፒ. ኤል.ኦ. ጋር በምታደርጋቸው ድርድሮች አሜሪካ በተጨባጭ የሚታይ ድጋፍ እንደምትሰጣት ቃል ገባችላት። ፒ.ኤል.ኦ. የእስራኤልን ሕልውና እስካልተቀበለና የተባበሩት መንግሥታትን ውሳኔ

ቁጥር 242 እና 338[3] እስካላከበረ ድረስ ከአሜሪካ ጋር ስምምነት እንደማይኖረው ኪሲንጀር ገለጹ። ይህን የተ.መ.ድ. ውሣኔ የአሜሪካ ኮንግረስ በ1984 ወደ ሕግነት ቀይሮታል።[108] እስራኤላዊው የታሪክ ምሁር አቪ ሽሌይም ‹‹የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ራቢን ግልጽ እንዳደረጉት ሲናይን የመልቀቁ ሁለተኛ ምዕራፍ ስምምነት ተፈጻሚ የሚሆነው አሜሪካና እስራኤል ሲስማሙ ብቻ ነው።›› ማለታቸውን ጽፈዋል። ይህን ስምምነት ሽሌይም ሲገልጹት ‹‹ከስም በስተቀር በሁሉም ነገር አሜሪካና እስራኤል አንድ የሆኑበት ውል" ብለውታል።[109]

የ1982ቱን የእስራኤል ያልታቀደ የሊባኖስ ወረራ ተከትሎ አሜሪካ እንደተለመደው እስራኤልን ለመርዳት ተነሳች። በእስራኤልና በፒ.ኤል.ኦ. መካከል በደቡብ ሊባኖስ በተነሳው ብጥብጥ የእስራኤል መከላከያ ሚኒስቴር አርዮል ሻሮን አንድ ሀሳብ ይዘው ብቅ አሉ። ይህ የሻሮን እቅድ የሚያተኩረው የፒ.ኤል.ኦን ኃይል ከሊባኖስ ጠርጎ በማስወጣት የሶሪያን ተጽእኖ ማጥፋትና የሊባኖስ ክርስቲያን መሪ የሆኑትን በሸር ጀማየልን ወደ ሥልጣን ማምጣት የሚል ነው።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አሌክሳንደር ሄይግ እቅዱን በተመለከተ ከእስራኤል ባለሥልጣናት ጋር በተነጋገሩ ጊዜ ቅድመ ሁኔታ የታከለበት ይሁንታቸውን ገለጹላቸው። እንደ ቅድመ ሁኔታ ያስቀመጡትም እስራኤል ሊባኖስ ውስጥ ብዙ መቆዬት እንደሌለባት ሲሆን፡- “ልክ እንደ አንጎል ቀዶ ጥገና ፈጣን መሆን አለበት” በማለት ሁኔታውን ለመግለጽ ሞክረዋል። ምናልባትም ሄይግ የእስራኤልን ሙሉ ፍላጎት አልተገነዘቡት ይሆናል። ‹‹በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የማጽዳት ሥራ መሆን አለበት›› ሲሉም አክለው ተናገሩ።[110] እስራኤል በ1982 ሰኔ ወር ላይ (የሄይግ

[3] የ1967ቱን ጦርነት ያበቃው የተኩስ አቁም ስምምነት እና የ1973ቱን የረመዳን ወይም የዮኪፑር ጦርነት ያበቃው ተኩስ አቁም ስምምነትን በየተራ የሚወክሉ ቁጥሮች ሲሆኑ፣ እስራኤልንም ከያዘቻቸው የፍልስጥኤም ግዛቶች እንድትወጣ የሚያዝዙ ናቸው። ይህም ሉዓላዊነቷና ነፃ ሀገር መሆኗ እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው።

ቅድመ ሁኔታ ባይከበርም) ሊባኖስን ወረረች። ይሁን እንጂ የሊባኖስን ውስጣዊ ፖለቲካ የማስተካከል ሕልሟ ወዲያውኑ ነበር ዝብርቅርቁ የወጣው። ምንም እንኳ የእስራኤል ጦር የፒ.ኤል.ኦን ተዋጊ ሠራዊትና የሶሪያን ኃይል ከሊባኖስ ማባረሩ ቢሳካለትም ከፒ ኤል.ኦ ሠራዊት የተረፉት እዚያው ቤይሩት ውስጥ እየተሸሎከሎኩ ገትረው ስለያዙት እነርሱን ጨርሶ ለማስወገድ ታላቅ መስዋእትነትን የሚጠይቅና የሊባኖስን ሲቪል ሕዝብም እጅጉን የሚጎዳ ሆኖ በመገኘቱ ሳይሳካለት ቀረ። የአሜሪካው ልዩ መልእክተኛ (አረብ አሜሪካዊው ፊልፕ ሀቢብ) በሁለቱ ኃይሎች መካከል የሽምግልና ጥረት በማድረግ የእስራኤል ከበባ እንዲያበቃና የፒ.ኤል.ኦ. ኃይልም እንዲወጣ ማድረግ ተሳካላቸው። ከዚያ በኋላ በሺዎች የሚቆጠሩ የአሜሪካ ባህር ኃይል (ማሪን) ወታደሮች በዓለም አቀፉ የሰላም አስከባሪ ሠራዊት ሥር ታቅፈው ወደ ቤይሩት አቀኑ።

የጀማየል በመስከረም ወር በቦንብ መገደል የእስራኤል ደጋፊ የሆነ የክርስቲያን መሪ በሊባኖስ ለማስቀመጥ የተለፋበትንና ተስፋ የተደረገበትን ጥረት ሁሉ መና አስቀረው። በዚህ የተበሳጨው የእስራኤል ጦር ሳብራና ሻቲላ ወደተባሉት የፍልስጥኤም ስደተኞች መኖሪያ ሠፈሮች ክርስቲያን ሚሊሺያ ፈዳይኖች እንዲገቡ በማድረግ ፍልስጥኤማውያንና ሙስሊም ሊባኖሳውያን እየተመረጡ እንዲታረዱ አደረገ። በዚያ የሰቆቃ ዘመቻ በግምት ከ700 እስከ 2000 የሚደርሱ ንፁሐን እንደተፈጁ ይገመታል።[111] ይህን በመሰለው ሁኔታም የሊባኖስን ውስጣዊ አለመረጋጋት ለማብቃት የተደረገው የእስራኤል ዘመቻ በውድቀት አሳረገ። በዚህም የተነሣ የአሜሪካ ሠራዊት ሳያስበው ቀስ እያለ በሊባኖስ ድቅቀት ውስጥ ተጎትቶ ገባ። በ1983 ሚያዝያ ወር በአሜሪካ ኤምባሲ ላይ ጥቃት ደርሶ 63 ሰዎች የተገደሉ ሲሆን፣ የአሜሪካ ባሕር ኃይል ጦር ከሰፈረበት አንድ ባለ ስድስት ፎቅ ሕንፃ ጋር በተጋጨ ቦንብ የተጫነ መኪና ምክንያትም 241 አሜሪካውያን ማሪኖች አለቁ። በቀጣዩ ዓመትም የአሜሪካ ጦር ሊባኖስን ለቅቆ ለመውጣት ተገደደ።

ምንም እንኳን ፕሬዚዳንት ሬገንን ጨምሮ የአሜሪካ ሹማምንት እስራኤል በጦርነቱ ወቅት ባሳየችው ድርጊት ቢበግኑም፤ እርሷን ለመቅጣት

አልሞከሩም፡፡ ሬገን ለእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ሜናሂም ቤጊን ሰኔ 9 ቀን በተጻፈ ደብዳቤ ከሶሪያ ጋር የተኩስ አቁም ስምምነት እንዲፈራረሙ አሳስበዋቸዋል፡፡ ሆኖም ግን ሶሪያን የሚመለከተው የእስራኤል የቤት ሥራ የተጠናቀቀ በመሆኑ በጊዜው ስምምነት ለማድረግ የሚያስገድድ ሁኔታ እስራኤልን አልታያትም ነበር፡፡››[112]

‹‹ዩናይትድ ስቴትስ በየጊዜውና በየቦታው ያጋጠማትን የሕዝብ ተቃውሞና ቁጣ ችላ ብላ›› ይላሉ የታሪክ ተመራማሪውና ዲፕሎማቱ ኢትማሪ ራቢኖቪች ‹‹ለእስራኤል ያልተለመደ በሆነ ሁኔታ የተራዘመ ጦርነት እንድታደርግ የሚያስችላትን የዲፕሎማሲ ድጋፍ መስጠቷን ቀጠለች፡፡››[113]

እስራኤል ጎረቤቷን በመውረሯ ምክንያት ማዕቀብ እንዲጣልባት በማድረግ ፋንታ የአሜሪካ ኮንግረስ ተጨማሪ 250 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ወታደራዊ እርዳታ በ1982 ታኅሣሥ ወር ላይ እንዲሰጣት ወሰነ፡፡ ይህ የሆነው ፕሬዚዳንት ሬገንና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ጆርጅ ሹልዝ በፅኑ እየተቃወሙ ነበር፡፡ ሹልዝ ቆዬት ብለው ሁኔታውን እንዲህ ያስታውሱታል፡-

‹‹በ1982 የታኅሣሥ ወር መጀመሪያ ላይ ... ደካማ በሆነው የኮንግረስ የውሳኔ አካል በኩል ለእስራኤል 250 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ወታደራው እርዳታ እንደሚሰጥ ሰማሁ፡፡ ይህ የሆነው እስራኤል በሊባኖስ ላይ ወረራ ፈጽማ በንፁሃን ዜጎች ላይ ክላስተር ቦምብ ተጠቅማ እያለችና በሳብራና ሻቲላ የፍልስጤማውያን ስደተኞች መንደር ያን የመሰለ የንፁሃን ደም በከንቱ እንዲፈስ የአመጹ ተባባሪ ሆና በተገኘችበት ሁኔታ ነበር፡፡ ስለሆነም ይህንን ጉዳይ በጽናት ልንወጣው የሚገባ እንደመሆኑ እኔና ፕሬዚዳንት ሬገን ለተለያዩ ሴናተሮችና የኮንግረስ አባላት ስልክ እየደወልን ሁኔታውን ልናስረዳቸው ሞከርን፡፡ ታኅሣሥ 9 ላይ ደግሞ ይህንኑ አቋማችንን የሚገልጽ ደብዳቤ ጽፈን ‹‹ይህንን ወታደራዊ እርዳታ ከፈቀድን እስራኤል የምትከተለውን ፖሊሲ መደገፍ ይሆንብናል›› በማለት አስረዳን፡፡ በዚህ ጊዜ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኢሳሃቅ ሻሚር ለፕሬዚዳንት ሬገን ደውለው ‹‹ይህ አቋምዎ ወዳጅነትን አያንጸባርቅም›› አሏቸው፡፡ አክለውም፡- ‹‹የሰላሙን

ጥረትም ሊጎዳው ይችላል›› በማለት ቅሬታቸውን አሰሙ። ‹‹ያን ሁሉ ጥረታችንን እያደረግን ኮንግረሱ እኔና ፕሬዚዳንት ሬገን ባልተገኘንበት ያንን ወታደራዊ እርዳታ አጽድቆ አሳለፈው። ይህ ከሆነ በኋላ በተፈጠረው ነገር በጣም ተደነቅሁ። ልቤም ተሳካ። ከሁኔታው እንደተገነዘብኩት እስራኤል በኅንግረሱ ላይ ያላት ተጽእኖ በግልጽ እየታየና ከቁጥጥራችንም እየወጣ ነበር። ስለሆነም ከዚህ በኋላ ከኮንግረሱ ጋር በሚኖረን ግንኙነት ነገሮችን በጥንቃቄ መያዝና እስራኤልንም በማይጎዳ መልኩ መንቀሳቀስ እንደሚኖርብኝ አመንኩ። እንደዚያ በማድረግም በመካከለኛው ምሥራቅ የሰላም ሂደት ውስጥ አዎንታዊ ሚና መጫወት እችላለሁ ብዬ አሰብኩ።››[114]

ይህ ከሆነ በኋላ፣ ኮንግረሱ በ1981 ያንቀሳቀሰውንና ከእስራኤል ጋር ስትራቴጂያዊ ትብብር ማድረግን በተመለከተ የተጀመረውን (ሆኖም ግን እስራኤል የጎላን ከፍታዎችን ለመልቀቅ ባለመፍቀዷ የተቋረጠውን) ውል ሬገንና ሹልዝ እንደገና በ1983 ህዳር ወር ላይ አንቀሳቀሱት። ምክንያቱም የእስራኤልን ባህሪ ለመግራት ዋነኛው ዘዴ ከእርሷ ጋር ትብብር ማድረግ እንደሆነ የአሜሪካ ሹማምንት ያምኑ ስለነበር ነው።[115]

አሜሪካ እስራኤልን በመደገፍ ያደረገችው እንቅስቃሴ እንደተገመተው የሰላሙን ሂደት ወደፊት ያራመደው መሰለ። ዩናይትድ ስቴትስ የስድስቱን ቀን ጦርነት ተከትሎ በተካሄደውና በተጨናገፈው የሰላም ስምምነት እንዲሁም ‹የማድከም ጦርነት› (War of attrition) የሚባለውንና ከግብፅ ጋር የተደረገውን ውጊያ ያበቃውን የ1970ውን ውል በማስፈጸም ወሳኝ ሚና ተጫውታለች። አሜሪካ ተጨማሪ የሰላም ሀሳቦችን ከማራመዷ በፊት አስቀድማ እስራኤልን ለማማከር በ1972 ተስማማች። በዚሁ መሠረት መራመድ ያልቻሉት ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኪሲንጀር ግን፣ “ደረጃ በደረጃ ሰላምን ማምጣት” በሚሉት ፈሊጣቸው በመመራት የጥቅምቱን ጦርነት ተከትሎ ባደረጉት የዲፕሎማሲ ጥረታቸው በእስራኤል ላይ ይህ ነው የሚባል ተጽእኖ ማምጣት አልቻሉም። እንዲህ ብለው ሲያማርሩ ተደምጠዋል፡- ‘‘ራቢንን የሰላሙን ጥረት ለማራመድ እንዲፈቅዱ ጠየቅኳቸው። እርሳቸው ግን እስራኤል ደካማ በመሆኗ አይቻልም አሉኝ። ከዚያም ብዙ መሣሪያ ሰጠኋቸው። በዚህም ጊዜ ቢሆን ስምምነት ሊያደርጉ አልፈለጉም። ምክንያቱም አሁን እስራኤል ጠንካራ ሀገር ሆናለችና”።[116]

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በግብጽና በእስራኤል መካከል የተፈረመውን ስምምነት ተከትሎ ሲናይን የመልቀቁ ሂደት ሊሳካ የቻለው አሜሪካ ለእስራኤል ተጨማሪ እርዳታ እንደምታቀርብላት ቃል በመግባቷና ይህንኑ ሂደት የሚቆጣጠሩ ሲቪል ሰዎችን በሲናይ በረሃ ውስጥ ለማስቀመጥ በመፍቀዷ ነው።

በክሊንተን አስተዳደር ጊዜም በ1993 የተፈረመውን የኦስሎ ስምምነት ለማስፈጸም ተመሳሳይ ችግር አጋጥሞ ነበር። ከዚያ በኋላም ከ1999-2000 ድረስ ባለው ጊዜ ከመጨረሻ የስምምነት ምዕራፍ ላይ ለመድረስ የተደረገው ጥረት አልሰመረም። በክሊንተን ባለሥልጣናትና በእስራኤላውያኑ አቻዎቻቸው መካከልም አልፎ አልፎ ውዝግቦች መነሳታቸው የተለመደ ነበር። ይሁን እንጂ አሜሪካ የራሷን አቋም ከእስራኤል አቋም ጋር በማቀናጀትና በአጠቃላይም የእስራኤልን የሰላም አቋም በመደገፍ መንዝን መርጣ ቆይታለች። ይህንንም ስታደርግ የራሷ ተወካዮች ከእስራኤል ስትራቴጂ አንባር ግልጽና ጠንካራ የሆነ ቁጥብነትን ያንፀባርቁ ነበር።[117] የኦስሎውን የእስራኤል ተደራዳሪ ቡድን የመሩትና ቀደም ሲልም በ2000 በካምፕ ዴቪድ የተደረሰውን የመጨረሻ የሰላም ስምምነት ንግግር የቀየሱት ሮን ፕንዳክ እንዲህ ይላሉ፦ ‹‹ተለምዶአዊ የሆነው የአሜሪካ መንግሥት አሠራር ... የእስራኤልን ጠቅላይ ሚኒስትር አቋም መቀበልና በሥራ ላይ ማዋል ነው። ይህ አሠራር በተለይም በናታንያሁ መንግሥት ጊዜ በስፋት ተግባር ላይ ውሏል። ያኔ እንደተስተዋለውም የአሜሪካ መንግሥት ለእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስቴር የሚሠራ እስኪመስል ድረስ የፍልስጤማውያን ተደራዳሪዎች የእስራኤልን ሀሳብ እንዲቀበሉ ጫና ሲያደርግ ይታይ ነበር። ይህ የአሜሪካ መንግሥት አሠራር በተወሰነ መልኩም ቢሆን በኢሁድ ባራክ መንግሥት ተንጸባርቋል።››[118]

የአሜሪካን መንግሥት በመወከል በሰላም ስምምነቱ ላይ የተሳተፉት ልዑካን ተመሳሳይ የሆነ አቋም ነበር ይዘው የቀረቡት። ሮበርት ማሊ የተባሉት በፕሬዚዳንት ክሊንተን መንግሥት የአረብ እስራኤል ጉዳይ ልዩ አማካሪና የካምፕ ዴቪድ ቁልፍ አደራዳሪ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹በካምፕ ዴቪድ የተንጸባረቀው የእስራኤል አቋም በጽሑፍ የቀረበ አልነበረም። .....ከዚያ ይልቅ እንደ አጠቃላይ የእስራኤል ሀሳብ ሳይሆን የአሜሪካ ሀሳብ ተደርጎ ነበር የቀረበው።›› ይህ አካሄድ አሜሪካ ገለልተኛ አደራዳሪ እንደሆነች

በሚታሰብበት ጊዜ እንኳ እስራኤልን በዲፕሎማሲ ለማገዝ ምን ያክል ቆርጣ እንደተነሳች ያሳያል፡፡ የአሜሪካ ተደራዳሪዎች የኋላ ኋላ አሜሪካ (ብዙውን ጊዜ ሳይታወቃት) የእስራኤልን የተደራዳሪነት ሚና በመውሰድ እስራኤል ልትሻገረው እስከማትችለው ጥግ ድረስ ተጉዛ ትረዳታለች፡፡[119] በአሜሪካ ስድስት የሚሆኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮችን በመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ በማማከር ያገለገሉና በክሊንተን አስተዳደር ዋና የሰላም ተደራዳሪ የነበሩት አሮን ዴቪድ ሚለር ሁኔታውን አጠር ባሉ ቃላት ሲገልጹት ‹‹ሁልጊዜም ባይሆን እኛ ያገለገልነው …. ልክ እንደ እስራኤል የሕግ ሰዎች ሆነን ነው›› ብለዋል፡፡[120]

ማጠቃለያ

እስራኤል እንደሀገር ከተመሠረተችበት ከ1948 አንስቶ ብዛት ያላቸው የአሜሪካ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲዎች ያችን ሀገር እንደ አይሁድ መንግሥት በሕልውና እንድትቀጥል ለማድረግ በሥራ ላይ ውለዋል። በዚህ መጽሐፍ ክፍል ሁለት ውስጥ በስፋት እንደምንዳስሰው ይህ አዝማማያ ጊዜ ባለፈ ቁጥር የበለጠ ተጨባጭ እየሆነ ሲሄድ ይታያል። አሜሪካ ካሏት ወዳጆች ሁሉ እስራኤል የበለጠ ተጠቃሚ መሆኗን ከሚያሳዩት ምልክቶች መካከል አንዱ ከ1976 አንስቶ ስድስት የሚሆኑ የእስራኤል መሪዎች በአሜሪካ ምክር ቤቶች የጋራ ጉባዔ (Joint Session of Congres) ፊት እየቀረቡ ንግግር ለማድረግ ዕድል የተሰጣቸው መሆኑ ነው። ይህም ለሌላ ለማንም ሀገር ያልተሰጠ ታላቅ ዕድል ነው።[121] ሁኔታውን ቀለል አድርጎ ማየት ይቻል ይሆናል። ሆኖም ግን ሁላችንም አንድ ነገር ማስተዋል ይኖርብናል። ይህን ዕድል ያገኘችውና ስድስት መሪዎቿ የወከሏት ሀገር በ2007 የነበራት አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት ሲታይ ከኒውዮርክ ከተማ ያነሰ ነበር።

ኢሳቅ ራቢን በአንድ ወቅት ‹‹አሜሪካ ለእስራኤል ያደረገችላት ችሮታ በዘመናዊ ታሪክ አቻ አይገኝላትም›› ማለታቸው ትክክል ነበር። የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት መካከለኛ ከነበረበት ደረጃ ተነስቶ ‹‹ ልዩ ግንኙነት›› ወደ ተባለ ማዕረግ ከፍ ማለቱም እውነት ነው። ሚቸል ፓት እና ዳንኤል ፓይፕ የተባሉ ፖለቲከኞች ይህን ሁኔታ እንዲህ በማለት ይገልጹታል፦ “አንጻራዊ በሆነ እይታ ስንቃኘው ዩናይትድ ስቴትስና እስራኤል በዓለም አቀፋዊው የፖለቲካ መድረክ ልዩ የሆነ ግንኙነት መመስረታቸውን እንገነዘባለን።››[122]

ይህ ግንኙነት አንድ መልካም ውጤት አስገኝቷል። አዎ! እስራኤልን የበለጸገች ሀገር እንድትሆን አግዟታል። ለብዙ ሰዎች ይህ እውነታ ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል ለዓመታት ያደረገችውን ድጋፍ ምክንያታዊ ለማድረግ በቂ ሆኖ ይታያቸዋል። ይህ እንዳለ ሆኖ በ2003 21 ሃገራት

ውስጥ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየው የነዚህ ሐገራት ብዙሐን ሕዝብ የአሜሪካ ፖሊሲ ለእስራኤል ያደላ እንደሆነ ያምናል፡፡ በጥናቱ ከተካተቱት ሐገራት ውስጥ 20ዎቹ እንደ ብሪታንያ፣ ፈረንሳይ፣ ካናዳና አውስትራሊያ ያሉ የአሜሪካ ወዳጅ ሐገራት መሆናቸው ውጤቱን አስገራሚ ያደርገዋል፡፡ ይበልጥ አስደናቂ የሚሆነው ደግሞ ብዙ እስራኤላውያን (47%ቱ) በዚህ ሃሳብ የሚስማሙ መሆናቸው ነው፡፡[123]

ምንም እንኳን አሜሪካ እስራኤልን በመደገፏ በርካታ ጥቅሞችን ያገኘች ቢሆንም፣ ካገኘችው ይልቅ የሰጠችው ነገር የበለጠ መሆኑ ሃቅ ነው፡፡ እስራኤል ወሳኝ የሆነች ስትራቴጂያዊ አጋር ብትሆን ኖሮ ይህ ሁሉ ችሮታ ተገቢነቱ አጠያያቂ ባልሆነ ነበር፡፡ ማለትም የእስራኤል በህልውና መቆየትና ቀጣይነት ያለው እድገቷ ዩናይትድ ስቴትስን የበለጠ የተረጋጋች እንድትሆን የሚያስችላት ቢሆን ኖሮ እሰከዛሬ የተደረጉትም ሆነ ወደፊት የሚደረጉት እጅግ ግዙፍ የሆኑ እርዳታዎችና የዲፕሎማሲ ድጋፎች የበለጠ ምክንያታዊ እንዲሆኑ ያደርጋቸው ነበር፡፡ እውነታው እንደዚያ ሳይሆን የተለዩ መልክ ያለው መሆኑ ነው አነገጋሪው ጉዳይ:: ዩናይትድ ስቴትስ ይህን ያክል ችሮታና ያልተቋረጠ ድጋፍ የምትሰጣት ሀገር በስትራቴጂያዊም ሆነ ሞራላዊ ምልከታ ይህን ለማግኘት የሚያበቃት ጠቀሜታ ለአሜሪካ የማታስገኝ መሆኗን በቀጣዮቹ ሁለት ምእራፎች በስፋት እንዳስሳለን፡፡

ምዕራፍ ሁለት

እስራኤል - የአሜሪካ ስትራቴጂያዊ አጋር ወይስ እዳ?

አሜሪካ ለእስራኤል በየጊዜው የምታጎርፍላት ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ እርዳታ እንዲሁም ዲፕሎሲያዊ ድጋፍ ለአጠቃላዩ ስትራቴጂያዊ ፍላጎቷ ጠቃሚ ቢሆን ኖሮ መልካም በሆነ ነበር፡፡ ዋሽንግተን በጠላትነት የፈረጀችው ሀገር ቢኖርና ያንን ሀገር ወደ ሰላማዊ ድርድር ለማምጣት የምትከፍለው ቤዛ ቢሆን ኖሮም ጉዳዩ ባላነጋገረ ነበር፡፡ ወይም ደግሞ ዘላቂ ጥቅም የሚያመጠላት ቢሆንና ያም ጥቅም በኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ ፋይዳው ሲመዘን ካወጣችው ወጪ የሚበልጥ ሆኖ ቢገኝ ኖሮ ልግስናዋ ማለፊያ በተባለ ነበር፡፡ አሊያም ደግሞ እስራኤል አንዳች ዓይነት ተፈጥሯዊ ሀብት (ለምሳሌ ነዳጅ ዘይት ወይም የተፈጥሮ ጋዝ) ቢኖራት ወይም ወሳኝ የሆነ መልከዓ-ምድራዊ አቀማመጥ የታደለች ብትሆን ኖሮ በእርግጥም ዩናይትድ ስቴትስ ለዚህች ሀገር እርዳታ ብታቀርብላትና መልካም የሆነ ወዳጅነቷን በሰጥቶ መቀበል ፖሲሲ ብታራምድ ወግ ያለው ጉዳይ በሆነ ነበር፡፡ በአጭር አነጋገር ለእስራኤል የሚሰጠው ሁልቆ መሳፍርት የሌለው እርዳታና ድጋፍ አሜሪካን የበለጠ የተረጋጋችና የበለጸገች እንድትሆን የሚያግዝ ቢሆን ኖሮ በተጨበጨበለት ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አሜሪካ በሁሉም መልኩ እስራኤልን መደገፏ በመላው ዓለም ተጨማሪ ወዳጆችን እንድታፈራ የሚያግዛት ቢሆንና ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ካላቸው ሌሎች ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት የማያበላሽ ቢሆን ኖሮ እሰየው በተሰኘ ነበር፡፡

አሜሪካ ከላይ ከተጠቀሱት መልካም ነገሮች መካከል አንዱን እንኳ የምታገኝ ቢሆን ኖሮ ለእስራኤል ያን ያክል የችሮታ እጃቸውን በየጊዜው በሰፊው የሚዘረጉት አካላት ሁሉ ለድርጊታቸው የሚያቀርቡት በቂ ምክንያት ባላጡ ነበር፡፡ ለምሳሌ በ1980ዎቹ ስቲቨን ስፒግል እና ኤ.ኤፍ.ኬ ኦርጋንስኪን የመሳሰሉት ምሁራን “እስራኤል በቀዝቃዛው ጦርነት ዋነኛዋ ስትራቴጂያዊ

አጋር በመሆኗ የአሜሪካ እርዳታ በሰፊው ሊሰጣት ይገባል›› በማለት ተከራክረዋል፡፡[1]

ሀይመን ቡክባይንደር የተባሉት የአሜሪካ አይሁዳዊያን ኮሚቴ ተወካይ በ1984 እንዲህ ብለው ነበር፡-- ‹‹እስራኤልን መርዳት የአሜሪካን ጥቅም ማስከበር መሆኑን ሰዎቸ ይገነዘቡ ዘንድ ወደኋላ ዞረን የታሪክ ማስረጃዎችን እያጣቀስን ማስገንዘብ ይኖርብናል፡፡››[2] ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በዋነኛነት እስራኤልን በመደገፍ ሎቢ የሚያደርገው የአሜሪካን እስራኤል ሕዝብ ጉዳይ ኮሚቴ አይፓክ እንዳስታወቀው፡- ‹‹አሜሪካና እስራኤል ትልቅ የሆነ ስትራቴጂያዊ ጉድኝት ያላቸው ሲሆን፣ ይህም የጋራ ስጋታቸውን ለመጋፈጥ ያግዛቸዋል›› በማለት ከገለጸ በኋላ፣ አሜሪካና እስራኤል በመከላከያና በሀገር ውስጥ ጸጥታ የሚያደርጉትን ትብብር፡- ‹‹በጣም አስፈላጊና ጠቀሜታው ዘላቂነት ያለው ነው›› ሲል አክሎ ሀሳቡን ይፋ አድርጓል፡፡[3] ‹‹ዘ ኒዎ ኮንሰረቫቲብ ፕሮጀክት ፎር ዘ-ኒው አሜሪካን ሴንቸሪ (PNAC) የተባለው ድርጅት ደግሞ እስራኤልን ‹‹የአሜሪካን ታማኝና ቆራጥ የሆነች የፀረ ሽብርተኝነት ተጓደኛ›› ሲል አሞካሽቷታል፡፡ ጀዊሽ ፎር ናሽናል ሴኩሪቲ አፌርስ (JINSA) የተባለ የአይሁዳውያን ድርጅትም፡- ‹‹የአሜሪካና የእስራኤል ስትራቴጂያዊ ትብብር ለዩናይትድ ስቴትስ ወሳኝ የሆነ ዓለም አቀፋዊ የፀጥታ ዋስትና ነው፡፡›› በማለት ግለት ያለው መግለጫ ሰጥቷል፡፡[4] ማርቲን ክራመር የተባለው የእስራኤል ሻሎም ሴንተር ተመራማሪና በዋሽንግተን ኢኒስቲትዩት የመካካለኛው ምሥራቅ ጠቢብ እንደገለጸው ከሆነ፡- ‹‹ዩናይትድ ስቴትስ እስራኤልን የምትረዳት በሆለኮስት ለደረሰባት እልቂት ወይም ባሏት ዲሞክራሲያዊ እሴቶቿ ምክንያት አይደለም፡፡ ከዚያ ይልቅ አሜሪካ በምሥራቃዊ ሜዲትራንያን ለሚኖራት አዲስ የሰላም መሠረትና በመካከለኛው ምሥራቅ አነስተኛ ወጪን የሚያስወጣ ሥርዓት ለማስፈን ስለሚያግዛት ነው፡፡›› በማለት ሀሳቡን አስቀምጧል፡፡[5] እስራኤላዊው ስትራቴጂስት ኤፍሬም ኢንባር በዚህ ሀሳብ የሚስማማ ሲሆን፣ እንዲህ ይላል፡- ‹‹አሜሪካ እስራኤልን እንደ ጠቃሚ ስትራቴጂያዊ ተጓዳኝ በመቁጠር እርዳታ መስጠቷን እንድትቀጥል ያደረጋት እስራኤል ያላት ስትራቴጂያዊ

አቀማመጥና የፖለቲካ መረጋጋታ፣ እንዲሁም ቴክኖሎጂያዊና ወታደራዊ እሴቶች ያስገኙላት ጥንካሬ ናቸው፡፡››[6]

አሜሪካ ለእስራኤል የምታዘንበው እጅግ ግዙፍ የሆነ እርዳታ እንደነዚህ ስትራቴጂስቶች አገላለጽ ከሆነ እንደ ልግስና ወይም የሞራል ግዴታ የሚቆጠር አየደደለም። እንዲሁም ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ አይሁዳዊያኑ በሚያደርጉት ሎቢ ስበብም አይደለም፡፡ [7] ከዚያ ይልቅ ዘላቂነት ያለው ይህ እርዳታ አሜሪካ ስትራቴጂያዊ ጥቅሞቿን ለማስከበር የምታደርገው ሲሆን፣ ይህን በማድረጓም የሁሉም አሜሪካዊያን ሕይወት ከአደጋ የተጠበቀ እንዲሆን ያስችላል ባይ ናቸው፡፡

ይህ ዓይነቱ አመለካከት እጅግ ኋላ ቀርና በቀላል አገላለጽ ውሃ የማይቋጥር መሆኑን በዚህ ምዕራፍ በስፋት ለማሳየት እንሞክራለን፡፡ እርግጥ ነው አሜሪካ እስራኤልን ባለፉት ዘመናት መደገፏ የተወሰኑ ስትራቴጂያዊ ጥቅሞችን አስገኝቶላት ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ይህን ጥቅም ለማስጠበቅ የምትከፍለው ኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ ዋጋ ጥቅሙ ይዘላት የሚመጣውን ነገር በየጊዜው እየቀነሰውና እያሳነሰው ሄዷል፡፡ ስለሆነም እስራኤል ዛሬ የአሜሪካ ጠቃሚና ስትራቴጂያዊ ወዳጅ ከመሆን ይልቅ ስትራቴጂያዊ እዳ ሆና ብቅ ብላለች፡፡ እስራኤልን እንደ ቀድሞው በኃይል መርዳትና ማገዝ አሜሪካዊያንን የሚጎዳና ዩናይትድ ስቴትስም ለራሷ ወሳኝና ጠቃሚ የሆኑ ዓለምአቀፋዊ ግቦቿን እንዳታሳካ የሚያደርጋት ጋሬጣ ነው፡፡ ምንም እንኳን ዛሬም ቢሆን አሜሪካ የእስራኤልን በሕልውና መቀጠል የምታግዝበት በቂ ምክንያት ቢኖራትም አሁን የምታራምደውና ቅድመ ሁኔታን ባላገናዘበ መልኩ እስራኤልን መርዳቷን መቀጠሏ ስትራቴጂያዊ መሠረት የሌለውና አሳማኝ ምክንያት ሊቀርብለት የማይችል ስህተት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ስለሆነም ዳሰሳችንን የምንጀምረው እስራኤል በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት የነበራትን ሚና በመገምገም ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ‹‹እስራኤል ስትራቴጂያዊ አጋር ነች ›› የሚለው መከራከሪያ ሀሳብ በዚያ ወቅት አሳማኝ የነበረ በመሆኑ ነው። ሶቪየት ሕብረት ከፈራረሰችና ቀዝቃዛው ጦርነት ካበቃ በኋላ ደግሞ እስራኤልን ለመደገፍ የሚቀርበው መከራከሪያ ‹‹ ከዓለም

አቀፍ አሸባሪነት የሚደቀንን የጋራ ስጋትና አንዳንድ ሀገራት የሚያስነሱትን ጠብ ጫሪነት ለመከላከል›› የሚል ነው። ይህም አባባል ቢሆን ትክክል ያለመሆኑንና እስራኤልን ለዘለቄታው ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለመደገፍ የሚቀርብ አሳማኝ ምክንያት እንደሌለ በቀጣዮቹ ምዕራፎች በምናቀርባቸው ትንታኔዎች ለማሳየት እንጥራለን።

የሶቪየትን መስፋፋት ለመግታት እስራኤልን መርዳት

በ1948 እስራኤል እንደ ሀገር ስትመሠረት የአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎች ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላት አጋር አድርገው አልቆጠሯትም ነበር። እንዲያውም ይህች አዲስ ሀገር ደካማና መዘዝ ልታማዝዝ የምትችል ተደርጋ ነበር ትታሰብ የነበረው። በዚህም የተነሣ እስራኤልን በጣም ማቅረብ አሜሪካ በመካከለኛው ምሥራቅ ያላትን ተቀባይነት የሚጎዳ እንደሆነ አድርገው ቢያምኑ አያስደንቅም። ፕሬዚዳንት ትሩማን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያራመደውን የፍልስጤኤምን ምድር ለሁለት የመክፈል ዕቅድ የደገፉት ስትራቴጂያዊ አስፈላጊነት ስላለው ሳይሆን፣ ለአይሁዳዊያን መሰቃየት በነበራቸው ልባዊ ሀዘኔታ ነበር። እንዲሁም የተወሰኑ ሃይማኖታዊ ቡድኖች የእስራኤልን ሕዝብ በቅዱሳን መጽሐፍት ወደተሰጠው ታሪካዊ ቦታው የመመለሱን አስፈላጊነት ማሳመን በመቻላቸውና ትሩማንና ፓርቲያቸው ለእስራኤል እውቅና በመስጠት አሜሪካ ውስጥ የሚገኙ አይሁዳዊያንን ድምፅ ለማግኘት በመሻታቸው ጭምር ነበር ማለት ይቻላል።[8] እንደዚያም ቢሆን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጆርጅ ማርሻልንና የፖሊሲ እቅድ አውጪ ዋና ኃላፊ የሆኑትን ጆርጅ ኬናን የመሳሰሉ የትሩማን አማካሪዎች ይህን እቅድ ተቃውመውታል። ምክንያቱም ይህ ድርጊት አሜሪካ ከአረቡ ዓለም ጋር ያላትን ግንኙነት አደጋ ላይ ይጥለዋል፤ ሶቪየቶችን ጎትቶ በማምጣትም የክልሉን የበላይነት እንዲይዙ ያደርጋቸዋል ብለው በመስጋታቸው ነበር። ኬናን በ1948 የግል ማስታወሻቸው ላይ “የፂዮኒዝምን ፖለቲካዊ ጽንፈኝነት ዓላማዎች መደገፍ የአሜሪካን አጠቃላይ የመካከለኛው ምሥራቅ ፀጥታ ይጎዳል ›› በማለት

አስፍረዋል፡፡ ኬናን በተጨማሪም ‹‹ጽዮናዊያንን ማገዝና ከእነርሱ ጎን መሰለፍ ሶቪዬት ሕብረት በክልሉ ያላትን ተሰሚነት ከፍ በማድረግ የነዳጅ ዘይት ሀብትን ስጋት ላይ ከመጣሉም ባሻገር አሜሪካ በክልሉ ያላትን መብትም አደጋ ይደቅንበታል ›› በማለት ተከራክረዋል።[9]

ይሁን እንጂ ይህን መሳዩ የአሜሪካ አቋም በ1960ዎቹ እየተሸረሸረ ሄዶ የኬኔዲ አስተዳደር እያደገ ከሄደውና ሶቪዬት ሕብረት ለግብፅ፣ ለሶሪያና ለኢራቅ ከምትሰጣቸው በበለጠ እስራኤል የአሜሪካን እርዳታ ማግኘት ይገባታል የሚል አቋም ያዘ።[10] የእስራኤል መሪዎች እስራኤል ለአሜሪካ ጠቃሚ አጋር ልትሆን እንደምትችል በ1967 የስድስቱ ቀን ጦርነት ያገኙትን አንጸባራቂ ድል እየጠቀሱ በብቃት ማስረዳት መቻላቸውም ተጽእኖ አላደረገም አይባልም፡፡ ቀደም ባለው ምዕራፍ ለማየት እንደሞከርነው ፕሬዝዳንት ኒክሰንና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ኪሲንጀር፣ አሜሪካ ለእስራኤል የምተሰጣትን እርዳታ በብዙ እጅ መጨመሯ በክልሉ የሶቪዬቶችን ተጽእኖ ለመቋቋም ብቸኛው መፍትሄ ነው የሚል አቋም አራምደዋል፡፡ [11] እንግዲህ የእስራኤል ስትራቴጂያዊ አጋርነት ሐሳብ የበቀለው በ1970ዎቹ ሲሆን፣ ስር የሰደደውና ጽኑ መሠረት የያዘው ደግሞ በ1980ዎቹ መካከል ላይ ነበር፡፡

እስራኤል ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላት ሀገር የነበረችው ከ1967 እስከ 1989 ባለው ጊዜ መሆኑ የማይታበል ጉዳይ ነው፡፡ በክልሉ የአሜሪካ ወኪል ሆና የሶቪዬት ተስፋፊነት ፖሊሲ እንዲገታ የበኩሏን አድርጋለች፡፡ እስራኤል ይህን በማድረጓ አሜሪካ በሌሎች ክልሎች በሚፈጠሩ ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረቷን እንድታሳርፍ እድል አስገኝቶላታል፡፡[12] የሶቭዬት ወዳጆች የነበሩትን ግብጽና ሶሪያ በተከታታይ በ1967 የስድስቱ ቀን ጦርነትና በ1973 ጦርነት በማሸነፍና በማዋረድ እስራኤል የሶቭዬትን ዝና የናደች ሲሆን፣ በአኳያው የአሜሪካን ክብር ከፍ ለማድረግ ችላለች። እንግዲህ ይህ የኒክሰንና የኪሲንጀር የቀዝቃዛው ጦርነት ስትራቴጂ አንዱ ገጽታ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ አሜሪካ እስራኤልን ከኋላ ሆና በመደገፏ ምክንያት ግብጽና ሶሪያ በ1967ቱ ጦርነት የተነጠቁትን ግዛት መልሰው እንዳያገኙ አድርጓቸዋል። ይህም የሶቪዬቶችን እርዳታ ደካማነት ይፋ በማውጣት

ይበልጥ እንዲጎላ አድርጎታል። ይህ ስትራቴጂ ፍሬ አፍርቶ በ1970ዎቹ ላይ የግብጹ ፕሬዝዳንት አንዋር ሳዳት ከሶቪዬቶች ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አቋርጠው ፊታቸውን ወደ አሜሪካ እንዲያዞሩ በማድረግ ለ1979ኙ የግብጽና እስራኤል የካምፕ ዴቪድ ስምምነት አብቅቷቸዋል። እስራኤል በአረቦች ላይ በተደጋጋሚ የተቀዳጀቻቸው ድሎች ሶቭዬቶችን ከእያንዳንዱ ሽንፈት በኋላ ለደንበኞቻቸው አረቦች ልዩና ውድ የሆነ ትጥቅ ለማስታጠቅ እንዲገደዱ በማድረጉ የዚህ ተጽእኖ አዙሪት ኢኮኖሚያቸውን በማዳከም ሌላ ፈተና አስከተለባቸው። እንዲህ ያለውን ክስተት ደግሞ አሜሪካና እስራኤል መጀመሪያውኑ የሚፈልጉት መሆኑ የታወቀ ነው።

እስራኤል መካከለኛውን ምሥራቅ፣ ይበልጡኑም የሶቪዬት ወዳጆች የሆኑትን አጎራባች የአረብ ሀገራት በመሰለልና ለአሜሪካ ስለመካከለኛው ምሥራቅ ተጨባጭ ስዕል በማቀበል የሶቪዬትን ችሎታና ያላትን አጠቃላይ አቅም እንድትመዝን አግዛታለች ማለት ይቻላል።

እንግዲህ ከፍ ሲል እንደተገለጸው እስራኤል ስለሶቪዬት አጠቃላይ አቅም፣ ስለ አረብ ወዳጆቿ ሁኔታና ስለ መካከለኛው ምሥራቅ ነባራዊ ሁኔታ ለአሜሪካ መረጃዎችን ማቅረብ መቻሏ አሜሪካ በሶቪዬት አንባር ታካሂደው ለነበረው ሁለንተናዊ ዘመቻ እገዛ አድርጎላታል። ለምሳሌ በ1956 የሶቭዬቱ መሪ ኒኪታ ክሩስቸቭ ስታሊንን ሲያወግዙ የሚሰሙበትን ምስጢራዊ ድምፅ አንድ የእስራኤል ሰላይ ለአሜሪካ አሳልፎ ሰጥቷል። በ1960ዎቹ ደግሞ እስራኤል የሶቪዬት ስሪት የሆነ ሚግ-21 አውሮፕላን ከአንድ ከዳተኛ ኢራቃዊ ፓይለት ማግኘት በመቻሏ በቀጥታ ለአሜሪካ አሳልፋ ሰጥታለች፡ ይህን በመሰለ ሁኔታም ከ1967 እስከ 1973 በተደረጉ የአረብ እስራኤል ጦርነቶች የተማረኩ የተለያዩ ሶቪዬት ሰራሽ አውሮፕላኖችና ሌሎች የውጊያ መሣሪያዎችን ለአሜሪካ ሰጥታለች።[13] በመጨረሻም ዩ.ኤስ. አሜሪካ ከእስራኤል ወታደራዊ ማሰልጠኛ ተቋማት ብዙ ጠቃሚ ነገሮችን አግኝታለች። እንዲሁም እስራኤል በወታደራዊ የምርምር ጣቢያዎቿ ያጎለበተቻቸውን የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች አሜሪካ በግብጓትነት የመጠቀም እድል ተመቻችቶላታል። የፀረ-ሽብርተኝነት ዘመቻዎችን ለማጧጧፍ

በሚያግዙና የፀጥታ ጉዳዮችን በሚመለከቱ ሌሎች እቅዶች ዙሪያ አሜሪካ ከእስራኤል አማካሪዎች ብዙ ምክሮችን አግኝታለች።

እነዚህን ሁሉ መልካም ነገሮች ለሰጠቻት እስራኤል ሙሉ የእርዳታ እጇን ብትዘረጋላት የሚደገፍና ትክክለኛ እርምጃ ሊመስል ይችላል። ምክንያቱም በእነዚያ ጊዜያት እስራኤል ምትክ ያልነበራት እስትራቴጂያዊ አጋር ተደርጋ ትቆጠር ነበርና። እንደዚያም ሆኖ የእስራኤል ደጋፊዎች እንደሚያስወሩት ይህ ጉዳይ ሙሉ ተቀባይነትን ያገኘ አልነበረም። ያኔም ቢሆን በአንዳንድ የአሜሪካ ኤክስፐርቶች ተቃውሞ ገጥሞታል።[14] ለምን? ምክንያቱም አሜሪካ እስራኤልን ልትጋራት ከሚገባት ቀጥተኛ የሆኑ የኢኮኖሚ ሸክሞች በተጨማሪ ከእስራኤል ጋር እያደገ የሄደው ሽርክና አሜሪካን ለከባድ ወጪ እየዳረጋት ስለሄደ። በእስራኤልም በኩል ይህችን ግዙፍና ታላቅ ኃያል አጋር ለመርዳት ያላት ተፈጥሮአዊ አቅም ውስን መሆኑ ግልጽ ነበር። ይህንን ሁሉ ለማለት በቂ ምክንያቶችን ማስቀመጥ ይቻላል።

በመጀመሪያ ደረጃ ምንም እንኳን የእስራኤል ወታደራዊና የስለላ አቅም የሶቪዬት አጋር የነበሩትን ግብጽ፣ ሶሪያ፣ ኢራቅና መሰል ሀገራትን አቅም ለመፈተሽ ቢያግዝም አሜሪካ እስራኤልን ለመደገፍ ያደረገችው ተነሳሽነት እነዚያን ሀገራት ወደ ሶቪዬት እቅፍ ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል። ግብጽና ሶሪያ ከ1940ዎቹ ጀምረው የእስራኤል የምር ጠላቶች በመሆናቸው ምክንያት ከአሜሪካን አንዳች ድጋፍ ለማግኘት በተደጋጋሚ ቢሹም ያንን ማሳካት አልቻሉም። እርግጥ ነው በዚያን ጊዜ አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጣት እርዳታ አሁን እያደረገችላት ካለው ጋር በምንም መልኩ አይገናኝም። ሆኖም ግን የእስራኤልን ሕልውና በተመለከተ አሜሪካ ያኔም ቢሆን ለድርድር የምታቀርበው ነገር አልነበራትም። ለዚህም ነው አሜሪካ ለግብጽና ለሶሪያ የጦር መሣሪያ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልነበረችው። ለምን ቢባል እርሷ የሰጠቻቸውን መሣሪያዎች ተጠቅመው አይሁዳዊቷን ሀገር እንዳያጠቁ በመስጋት ነው። በዚህም የተነሣ እስራኤል በጋዛ የሚገኘውን የግብጽ ጦር ሠፈር በ1955 በማጥቃት ሰላሳ ሰባት ግብጻዊያን ወታደሮችን ስትገድልና ሰላሳ አንድ የሚሆኑትን ስታቆስል የግብጽ መሪ ጀማል አብዱልናስር ፊታቸውን ወደ ሶቪዬቶች ለማዞር ተገደዱ። ናስር የጋዛውን

ወረራ በተደጋጋሚ እያነሱ ሶቪዬት በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ትልቅ ወታደራዊ ኃይል ካላት ከግብጽ ጋር ሽሪክ እንድትሆን ተጠቅመውበታል። ወረራው ናስር ከእስራኤል ጋር ጀምረውት የነበረውን ምስጢራዊ ስምምነት እንዲያቋርጡና መካከለኛ የነበረውን አቋማቸውን ትተው የአረብ ብሔረተኝነትን በመቀስቀስ አረቦች እርሳቸውን እንዲደግፉ የማድረጉን ጥረት እንዲያያዙት አደረጋቸው።[15] ከእስራኤል ጋር የነበራቸው ውዝግብ እየገፋ ሲሄድና አሜሪካም ዓረቦችን ለማገዝ ማቅማማቷን ሲመለከቱ ከሶቪዬት ጉያ ውስጥ ከመወሸቅ የተሻለ ምርጫ ሊያገኙ አልቻሉም።[16]

በሁለተኛ ደረጃ ምንም እንኳን አሜሪካ ለእስራኤል የምታደርገው ድጋፍ በሶቪዬት ላይ የበለጠ ጫና እያሳደረ ቢመጣም፣ በአረብ እስራኤል ግጭት ላይ ነዳጅ በማርከፍከፍ መረጋጋት እንዳይፈጠር ያደረገ ሲሆን፣ እስራኤልና ዩናይትድ ስቴትስም የበለጠ ስጋት ውስጥ እንዲወድቁ አድርጓቸዋል። የኒክሰን ኪሲንጀር ስትራቴጂ ውሎ አድሮም ቢሆን ግብፅን ከሶቪዬት ምሁዋር በማስወጣት የአሜሪካ አጋር እንድትሆን ማድረግ አስችሏል። ይሁን እንጂ መካከለኛው ምሥራቅ በቀዝቃዛው ጦርነት መነጽር እንዲታይና ሁሉም ቅኝቱን በዚያው የፖለቲካ ፍትጊያ ዙሪያ እንዲያደርግ (ብሎም በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ እስራኤልን የመደገፍ አቋም የበለጠ እንዲጸና) ሁኔታው መጋበዙ አልቀረም። አሜሪካም በርካታ የሰላም ጥረቶችን ችላ እንድትል አድርጓታል። ለአብነት ያክል የግብጹ መሪ አንዋር ሳዳት ከ1971–72 ባለው ጊዜ ውስጥ ያሳዩትን ተደጋጋሚ የሰላም ምልክት አሜሪካ እያየች በቸልታ አልፋዋለች።[17] ኪሲንጀር በ1975 ለተወሰኑ ግለሰቦች ባደረጉት ንግግር የቀድሞው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዊሊያም ሮጀርስ በ1971 የመሸጋገሪያ ስምምነት ለማድረግ የጀመሩት ጥረት መፍረሱን ሲያስታውሱ፡- ‹‹1000 የሚሆኑ የግብፅ ወታደሮች ከፊሉን የሲዊዝ ቦይ ተሻግረው እንዲሰፍሩ መፍቀድ ከባድ ነበር። ያን ብናደርግ ኖሮ ምናልባትም የ1973ቱን ጦርነት ማስቀረት እንችል ይሆናል። ይቅርታ ይደረግልኝና ያኔ ማድረግ ከምችለው ነገር በላይ የኖጀርን ጥረት መደገፍ የማልችል መሆኔን መግለጽ ሳይኖርብኝ አይቀርም።››[18]

ሶስተኛ ከ1960ዎቹ እስከ 1970ዎቹ የተጠናከረውና ጥልቀት ያገኘው የአሜሪካ እስራል ጉድኝት በዓረቡና በሙስሊሙ ዓለም ውስጥ ፀረ-አሜሪካ አቋም ከፍ እንዲል አስተዋጽዖ አድርጓል። "በአንደኛው የዓለም ጦርነት" ይላሉ የራይስ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ምሁር የሆኑት አሳማ መቅዲሲ "በኡቶማን ቱርክ አስተዳደር ስር በነበሩ የአረብ ግዛቶች ውስጥ ሕዝቡ ለአሜሪካ የነበረው አመለካከት በአጠቀላይ አዎንታዊ ነበር። በዚያ የነበሩ አረቦች አሜሪካን የሚያውቋት ታላቅ ኃይል ያላትና እንደ ብሪታንያ፣ ፈረንሳይና ሩሲያ የኢምፔሪያሊስት ባህሪ የማታንጸባርቅ መሆኗን ነበር።[19] እስራኤል ከተመሰረተች በኋላ እንኳ አሜሪካ የማታዳላና በመካከለኛው ምሥራቅ ፍትህን የምታሰፍን ተደርጋ ትታይ ነበር። ምክንያቱም እስከ 1967 ድረስ ለእስራኤል ዋና የጦር መሣሪያ አቀባይ አሜሪካ ሳትሆን ፈረንሳይ ነበረችና። በጊዜው የተራማጅ አረብ መንግሥታት ለምሳሌ የናስሯ ግብጽ በአሜሪካ ላይ የነበራቸው ቅሬታ በዋነኛነት አሜሪካ እስራኤልን በጽኑ መደገፏ ብቻ ሳይሆን ወግ አጥባቂ የሚባሉትን የመካከለኛው ምሥራቅ ነገሥታት (የኢራኑን ሻህ፣ የዮርዳኖሱን ንጉስ ሁሴንና የሳዑዲን ቤተሰብ) ወዳጅ አድርጋ መያዟም ጭምር ነበር። ምክንያቱም እነዚህ መንግሥታት ለናስር ከፍተኛ ጥላቻ ነበራቸው። እንዳለመታደል ሆኖ አሜሪካ እነዚህን መንግሥታት መደገፏ (ዋሽንግተን ወግ አጥባቂ ያልሆኑና መካከለኛ አቋም ያላቸው ናቸው ብላ ታስብ ነበር) እና እስራኤልን መርዳቷ አሜሪካን በአረቡ ዓለም የታላቋን ብሪታንያ የኢምፔሪያሊስት አገዛዝ ለመተካት ወደ ክልሉ እንደመጣች አስቆጠራት።[20] አረቦች ለአሜሪካ ያላቸው ጥላቻ ይበልጥ እየጠነከረ የሄደው ግን እስራኤልን በማገዝ እስራኤል ምዕራባዊውን ወንዝ ዳርቻ፣ ሲናይን፣ ጋዛንና የጎላን ከፍታዎች በ1967 በወረረች ጊዜና በተያዙት ግዛቶች የሚኖሩ ፍልስጤማውያንም ጭቆናው እየበረታባቸው በመምጣቱ ነው። በዚህም ምክንያት በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት በርካታ የመካከለኛው ምሥራቅ መንግስታት ጉድኝታቸውን ከሶቪዬት ጋር በማድረግ የአሜሪካ ተጽእኖ ይበልጥ እንዳይስፋፋ ሲጥሩ ይታዩ ነበር። የዚህ ሁሉ ተለዋዋጭ ክስተት አንደምታ -የወደፊቱን ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ የሚዳስስ ትንተና የሚያቀርቡ አንዳንድ ምሁራን ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት

እንደተነበዩት የአረባዊነት ስሜትና እስላማዊ አክራሪነት ከፍ እንዲል አድርጓል። ለምሳሌ ሃሪ ሾው የተባሉት የቀድሞ የአሜሪካ ወታደራዊ አስተዳደር በጆት ኃላፊ ከ1985--86 በጻፉት መጽሐፍ እንዳስጠነቀቁት፡- "እስራኤል በምዕራባዊው ወንዝ የምታደርጋቸው የሰፈራ ፖሊሲዎች ከዩናይትድ ስትቴስ ፍላጎት ጋር የማይሄዱና ከፖሊሲዋም ጋር በቀጥታ የሚጋጩ ናቸው። እስራኤልና አረብ አጎራባቾቿ ኃላፊነታቸውን ተጋርተው በሰላም እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ሁኔታ አለመሻሻሉ የኢስላም አክራሪነትን መስመር የሚከተሉና በክልሉ መረጋጋት እንዲኖር የማይሹ ወገኖችን እንዲበረታቱ ያደርጋቸዋል። እንዲህ የመሰለው አጠቃላይ ስሜት መስፈኑ ደግሞ የአሜሪካን ፍላጎት የሚጻረርና ለእስራኤልም ፀጥታ የማይጠቅም መሆኑ ግልጽ ነው ›› ብለዋል።[21] አሜሪካ ከአረቡም ሆነ ከሙስሊሙ ዓለም ጋር የሚኖራት ግንኙነት የተሳካ ሊሆን ይችል የነበረው ከእስራኤል ጋር ወዳጅነት ባትመሥረት ነበር። ይህን እንተወውና አሜሪካ ሁለቱንም በመልካምና ሚዛኑን በጠበቀ ሁኔታ ማስተናገድ ብትችል እንኳ ግንኙነቱ እጅግ መሻሻል ሊያሳይ እንደሚችል መገመት አይከብድም። ይህ አንኳር ሀቅ የእስራኤል ወታደራዊ አዛዥና ፖለቲከኛ በነበሩት ሞሼ ዳያን እንኳን ሊስተባበል አልቻለም። ዳያን በ1973ቱ የረመዳን ጦርነት ከአሜሪካው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኪሲንጀር ጋር የተለዋወጧቸውን ቃላት በማስታወሻቸው ላይ አስፍረዋቸዋል። እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹ ከእኛ ጎን ለመቆም ዝግጁ የሆነችው ሀገር ዩናይትድ ስቴትስ ብቻ ብትሆን ኖሮ እንኳ አረቦችን መደገፍ እንደነበረባት ሕሊናዬ ይነግረኛል።››[22]

አሜሪካ እስራኤልን መደገፏ ብዙ ዋጋ እንድትከፍል አድርጓታል። ለአብነት ያክል በረመዳን ጦርነት የአረቦች የነዳጅ ዘይት ማዕቀብና ምርቱን መቀነሳቸው ዋነኛው ተጠቃሽ ክስተት ነው። "ዘይትን በመሣሪያነት መጠቀም" የሚለው ውሳኔ በዚያ ጦርነት ኒክሰን ለእስራኤል 2.2 ቢሊዮን ዶላር የሚያወጣ አስቸኳይ ወታደራዊ እርዳታ ለመስጠት የመወሰናቸው ቀጥተኛ መልስ ነበር። ያ ማዕቀብና እርሱን ተከትሎ የመጣው የአቅርቦት መቀነስ አሜሪካን በ1974 ብቻ 48.5 ቢሊዮን ዶላር ተጨማሪ ወጪ እንድታወጣ ያደረጋት ሲሆን አጠቃላዩን የሀገር ውስጥ ምርቷን (GDP)

በ2 ከመቶ እንዲያሽቆለቁል አስገድዶታል፡፡ የነዳጅ ቀውስ በተጨማሪም አሜሪካ ከአውሮፓውያንና ከኢሲያ ቁልፍ ተጓዳኞቿ ጋር ያላትን ግንኙነት አዳክሞታል፡፡[23] እስራኤልን መደገፏ ሁለቱን የሶቪዬት ወዳጆች (ግብጽና ሶሪያ) ለማሸነፍ በማስቻሉ አሜሪካ በቀዝቃዛው ጦርነት የነበራትን ገጽታ ከማሻሻል አንፃር እገዛ አድርጎ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ዩናይትድ ስቴትስ ይህን ድል (ድል ከተባለ) ያገኘችው አጅግ ብዙ ዋጋ ከፍላ ነው፡፡

እስራኤል በቀዝቃዛው ጦርነት ያበረከተቻቸው አስተዋጽዎች ጠቃሚዎች ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ያላቸው ስትራቴጂያዊ ዋጋ ተጋንኖ መታየት የለበትም፡፡ በእርግጥ እስራአል ለአሜሪካ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን አቀብላታለች፡፡ ይሁን እንጂ ቴሌአቪቭ ለዋሽንግተን የሰጠቻት መረጃዎች አሜሪካ በነበረባት የቀዝቃዛው ጦርነት የልዕለ ኃያልነት (Supper Power) ትንቅንቅ በጠላቶቿ ላይ ወሳኝ የሆኑ ጡጫዎችን እንድታሳርፍ ያገዟት ለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ አይቻልም፡፡ በእነዚያ ጊዜያት ከእስራኤል በኩል ተጨባጭ ነገር ተገኝቷል ከተባለ ሶቪዬት ሠራሽ የሆኑና ከጠላት የተማረኩ መሣሪያዎች እንዲሁም እነዚያ መሣሪያዎች በጦር ሜዳ ላይ ያላቸውን ተግበራዊ እንቅስቃሴ የሚያሳዩ መረጃዎችና ከሶቪዬት ወደ እስራኤል ከገቡ አይሁዳውያን የተገኙ ቅርምራሚ ወሬዎች ናቸው፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ እነዚህን መረጃዎች ተጠቅማ የውጊያ ብቃት እንዲኖራት የሚያስችሏትን መሣሪዎች በመሥራቷና የጦር ስልቷን ለማስተካከል በመብቃቷ ኢራቅን የመሰለ የሶቭዬት ወዳጅ በ1991 በገጠመች ጊዜ ለድል አብቅቷታል፡፡ ይሁን እንጂ የኢራቅ ወታደዊ ኃይል ሶስተኛ ደረጃ የሚሰጠው ስለነበር አሜሪካ በ1991 ሳዳምን ለማዳከም እንዲሁም በ2003 ከስልጣናቸው ለማባረር ብዙ የዲፕሎማሲ ጥረት ቢጠይቃትም፣ ያን ያክል ተግዳሮት ያስከተለ ወታደራዊ ዘመቻ ማድረግ አላስፈለጋትም፡፡ በዚያ ወቅት እስራኤል ያቀረበችው ወታደራዊ ሥልጠናና የማማከር አገልግሎት ጠቃሚ ቢሆንም ዩናይትድ ስቴትስ ሶቪዬትን እንድትፈረካከስ ለማድረግና ዘላቂ የበላይነቷን ለማረጋገጥ ያን ያክል አስፈላጊዋ ነበር ለማለት ሲበዛ ያስቸግራል፡፡

እንዲያውም እስራኤል ለአሜሪካ የምትሰጣት መረጃ አንዳንድ ጊዜ እምነት የማይጣልበት ነበር፡፡ አንድ የቀድሞ ሲ.አይ. ኤ ኃላፊ ባቀረቡት ሪፖርት፡-

‹‹እስራኤል የአረቡን ዓለም አስመልክቶ ያላት ፖለቲካዊ የሥለላ መረጃ ጥራት የሌለውና ደካማ የሚባል ነው፡፡ .... እስራኤሎች ከሚያቀርቡት ፖለቲካዊ የስለላ ሪፖርት ይልቅ ወታደራዊ መረጃዎቻቸው አንደኛ ደረጃ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡፡ እንደዚያም ቢሆን ጠላቶቻቸውን በሚገባ ያውቋቸዋል ማለት ያሳስታል፡፡ የፖለቲካዊ ስለላ መረጃዎቻቸውን ተመልክቻቸዋለሁ፡፡ ብዙዎቹ በማይረቡና አስቂኝ በሆኑ ነገሮች፣ በፍሬቢስ ስም ማጥፋቶችና በፍሬፈርስኪ ነገሮች የተሞሉ ናቸው፡፡›› ብለዋል፡፡[24] ከዚህም አልፎ እስራኤል በተለያዩ ጊዜያት ለአሜሪካ የተጭበረበሩና ምናልባትም ወደ ስህተት ጎዳና የመሯትን መረጃዎች ሆነ ብላ ስትሰጣት መኖሯን የሚያሳዩ ሰነዶች ተገኝተዋል፡፡ ይህን ያደረገችው ምናልባትም እርሷ የምትሻቸውን እርምጃዎች አሜሪካ እንድትወስድላት ለማደፋፈር ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ከስደስቱ ቀን ጦርነት በፊት የእስራኤል የስለላ ወኪሎች የግብጽን ጦር ኃይል አጋንነው ለአሜሪካ አቅርበዋል፡፡ ኋላ ላይ እነዚያን መረጃዎች በጽሞና የመረመሩት የአሜሪካ የደህንነት አባላት መረጃዎቹ በውሸት የተሞሉና ለፖለቲካ ፍጆታ የዋሉ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። የአሜሪካ ብሔራዊ የፀጥታ አማካሪ የነበሩት ደብሊው ደብሊው ሮስቶው ፕሬዚዳንት ጆንሰንን እንዲህ ብለዋቸው ነበር፡- “የእስራኤላዊያኑ የመረጃ ሰዎች ለእኛ የሰጡንን የተጋነኑ መረጃዎች ለበላይ አለቆቻቸው ያቀርባሉ የሚል እምነት የለንም፡፡ ይህን ያደረጉት ምናልባትም፡- ሀ/ወታደራዊ እርዳታ ለማግኘት፣ ለ/ እስራኤል የአሜካውያንን ትኩረት በበለጠ ሁኔታ እንድታገኝ ለማስቻል፣ ሐ/ የእስራኤልን ወታደራዊ ግለት ለማነቃቃት፣ መ/ በናስር ላይ የበለጠ ጫና ለመፍጠር ይሆናል፡፡[25] በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ ስምንት ላይ በስፋት እንደምናዩው እስራኤል በተጨማሪም ከ2003 የኢራቅ ወረራ በፊት ኢራቅ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ የታጠቀች መሆኗን እንድታምን የሚያደርግ የተሳሳተ መረጃ ለአሜሪካ አቅርባላታለች። በዚህም የተነሣ ሳዳም ሁሴን የነበራቸው ኃይልና የደቀኑት አደጋ በተጨባጭ ከተደረሰበት እውነታ ጋር ፈጽሞ የተራራቀ ሆኖ ሳለ፣ አሜሪካ በተሳሳተ ስሌት ኢራቅን ወርራ በታሪኳ አቻ ለማይገኝለት ታላቅ ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ሰብአዊ ውድቀት ተዳርጋለች።[26]

ይህም ብቻ ሳይሆን እስራኤል በክልሉ የአሜሪካን ሌሎች ጥቅሞች ለማስጠበቅ የምትችል አስተማማኝ አጋር አይደለችም፡፡ ማርቲን ክራመር ‹‹አሜሪካ እስራኤልን መርዳቷ በምሥራቃዊው ሜዲትራንያን ባሕር የአሜሪካን ጥቅም የሚያስጠብቅ ሰላማዊ ቀጣና እንዲፈጠር ያስችላል፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛው ምሥራቅ አነስተኛ ዋጋ የሚያስከፍልና ጥቅሙ ታላቅ የሆነ ጉድኝትን ይፈጥራል››::[27] በማለት መናገራቸው የተጋነነ ነበር፡፡ በሜዲትራንያን ዳርቻ መረጋጋት መኖሩ ተፈላጊ ቢሆንም ያ አካባቢ በነዳጅ ዘይት ከበለጸገው የባህረ ሰላጤው አካባቢ ጋር ሲነጻጸር ለአሜሪካ ያለው ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የእስራኤል ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ‹‹ፓክስ አሜሪካ›› ከተሰኘው ለአሜሪካ የሚስማማ የሰላም ቀጣና የመመስረት ራዕይ የመነጨ ከሆነ በዚህ ረገድም እስራኤል የሚጠበቅባትን ሥራ እየሰራች አይደለም፡፡ እስራኤል በ1982 ሊባኖስን መውረሯ አካባቢውን ሰላም የራቀው በማድረጉና ሒዝቡላህን የመሰለ ኃያል የአሜሪካ ጠላት በመፍጠሩ አሜሪካ በጊዜው 250 የሚሆኑ ዜጎቿን እንድታጣ አድርጓታል፡፡ የአሜሪካ የባህር ኃይል ማሪኖች የነበሩበትን ቦታ በማጥቃት ተጠያቂው አጥፍቶ ጠፊው ቢሆንም፣ ሰዎቹ ያለቁበት ዋነኛ ምክንያት እስራኤል የፈጠረችውን ችግር ሁሉ እንድትፈጥር አሜሪካ የደገፈቻት በመሆኑ ቅጣት ይሆናት ዘንድ ሂሳቧን ማወራረድ ስለነበረባት ነው፡፡ እስራኤል ምዕራባዊውን ወንዝ ዳርቻና ጋዛን በመያዝ ያንን ሁሉ መከራ በነዋሪዎቹ ላይ ለተራዘመ ጊዜ የምትፈጽመው አሜሪካ በምትሰጣት እርዳታና እርሷ ባስታጠቀቻት መሣሪያ መሆኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ፍልስጤማውያንና እስራኤላውያን ያለቁበትን ኢንቲፋዳ ቀስቅሷል፡፡ ስለሆነም ክራመር “ክልሉን ለማረጋጋት አነስተኛ ዋጋ የሚያስከፍል ወዳጅነት ያስገኛል›› በማለት የእስራኤልን አስፈላጊነት ከፍ ማድረጋቸው የተጋነነ አባባል ነው፡፡

የእስራኤል ውስን ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ፣ ለአሜሪካ በፋርስ ባህረ ሰላጤ ያላትን የነዳጅ ዘይት ጥቅም ለማስጠበቅ ምንም ዓይነት አስተዋጽኦ የሌላት ከመሆኗ አኳያም ሊታይ ይችላል፡፡ እስራኤል ምንም እንኳ ወታደራዊ ብቃት አላት ቢባልም፤ ዩናይትድ ስቴትስ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት

ከሶቪዬት ኃይል ይደርስባት በነበረው የነዳጅ ዘይት አቅርቦቷን የሚገዳደር አደጋ ስታግዛት አልታየችም፡፡ ስለሆነም እስራኤል ለአሜሪካ የወርቅ እንቁላል የምትጥል ዳክዬ አይደለችም፡፡ በ1980ዎቹ ላይ ሃሪ ሾው ሁኔታውን ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡ "የተወሰኑ የእስራኤል ባለሥልጣናት የእስራኤል ጦር የሀገሩን ዳር ድንበር ከማስከበር አልፎ የሶቪዬትን የእግረኛ ጦር መግጠሙን በግልጽ ተቃውመዋል፡፡ የእስራኤል ኃይል ከክልሉ ወጥቶ በፋርስ ባሕረ ሰላጤ ሶቪዬትን የመግጠሙን ሀሳብ የማይሆን ነገር አድርገው ነበር የወሰዱት"[28] እናም አንድ የቀድሞ የፔንታጎን ባለሥልጣን እንዲህ ሲሉ እውነትን ተናግረዋል፡- ‹‹እስራኤል ለዩናይትድ ስቴትስ ስትራቴጂያዊ ጥቅም አላት መባሉ በሚያስደንቅ ሁኔታ የተጋነነ ነው፡፡ በ1980ዎቹ ላይ ለመካከለኛው ምሥራቅ የሚበጅ እቅድ ስናረቅ እስራኤል 95 በመቶ ለሚሆኑት የአሜሪካ አጀንዳዎች እምብዛም ጠቀሜታ እንደሌላት አረጋግጠናል፡፡››[29]

ከዚህ የተነሳ በ1979 የኢራቅ ሻህ ሲወድቅ አሜሪካ በዚያ አካባቢ ሶቪዬቶች ወረራ ሊያደርጉ ይችላሉ በሚል ስጋት ወረራውን የሚመክት ፈጣን የሆነ አጥቂ ጦር ማደራጀት ነበረባት፡፡ ስለሆነም በአረብ ሀገራት የጦር ሠፈር በማዘጋጀት የውጊያ አቅርቦቷን አደራጀች፡፡ በዚያ ወቅት እስራኤል በግዛቷ ውስጥ ሆና ሶቪዬትን እንድትገጥም ወይም እንደ ጦር አምባ (base) እንድታገለግላት አሜሪካ አልፈለገችም፡፡ ምክንያቱም ያን ማድረግ በአረቡ ዓለም የፖለቲካ ችግሮችን በመቀስቀስ ሶቪዬትን ከክልሉ ለማስወጣት የሚደረገውን ጥረት ስለሚያወሳስበው ነው፡፡ ሃሪ ሾው በ1986 እንደተናገሩት ‹‹እስራኤልን የጦር አምባ አድርጎ የአሜሪካን ኃይል ወደ አረብ መሬት ማስገባት .... ከእስራኤል ውጭ በስፋት ተቀባይነት የሌለው ሃሳብ ነው፡፡ የአረብ የፖለቲካ ተንታኞች እንደሚሉት ማንኛውም የአረብ መንግሥት በእስራኤል በኩል የሚመጣለትን የአሜሪካ እርዳታ የሚቀበል ከሆነ የገዛ ሕዝቡ ዋጋ ያሳጣዋል፡፡ የመውደቅ እድሉም ከፍ ያለ ነው፡፡..... የአሜሪካ ባለሥልጣናትም ቢሆኑ እስራኤልን እንደ ጦር አምባ መጠቀም ስኬታማ አያደርገንም የሚል ጥርጣሬ አላቸው፡፡ እስራኤል ይህን ዓይነት ግብጥ የምታቀርበው ምናልባትም ከአሜሪካ ጋር ያላትን ግንኙነት ይበልጥ

ለማሳደግ፤ እንዲሁም የአሜሪካን እርዳታ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለማግኘት ሊሆን ይችላል፡፡››[30] እስራኤል ይበልጡንም በባሕረ ሰላጤው አካባቢ በሚፈጠሩ ችግሮች ሚና ለመጫወት ያላት ችሎታ ውስን መሆኑ በ1980ዎቹ የኢራን-ኢራቅ ጦርነት ወቅት በፋርስ ባሕረ ሰላጤ የሚዘዋወሩ ነዳጅ ጫኝ መርከቦች አደጋ በገጠማቸው ጊዜ ተረጋግጧል። ዩናይትድ ስቴትስና በርካታ የአውሮፓ ወዳጆቿ የባሕር ኃይላቸውን ወደ ክልሉ በመላክና ነዳጅ ጫኝ መርከቦችን በማጀብ የኢራን ቃኝ ጀልባዎችን ማጥቃት ችለው ነበር፡፡ እስራኤል በዚህ ዘመቻ ምንም ዓይነት ሚና አልነበራትም፡፡[31]

ምንም እንኳን በቀዝቃዛው ጦርነት ዘመናት እስራኤል በተወሰነ መልኩ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ የነበራት መሆኑ ቢታወቅም፣ ይህ ብቻውን ለዚያ ሁሉ ዘመን፣ ያን በሚያክል መጠን የአሜሪካን ኢኮኖሚያዊ፣ ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ማግኘት እንድትችል በቂ ምክንያት አይሆንም፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ በአውሮፓ የሚገኙ የኔቶ አጋሮቿን ከጥቃት ለመጠበቅ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ብትከሰክስ አይደንቅም፡፡ ምክንያቱም አውሮፓ ቁልፍ የሆነ የኢንዱስትሪ ኃይል እንደመሆኑ ከሶቪዬት ጥቃት ጥበቃ ሊደረግለት ግድ ይላል፡፡ በሌላ በኩል ሳኡዲ አረቢያን ለመሰሉ በነዳጅ የበለጸጉ ሀገራት አሜሪካ ጥበቃ ማድረጓም እንዲሁ ለመገንዘብ ቀላልና የማያስቸግር ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህ ሁሉ ለእስራኤል ሲሆን ስትራቴጂያዊ አስፈላጊነቱ ፈጽሞ ግልጽ አይደለም፡፡ ሄነሪ ኪሲንጀር በጊዜያቸው ያን ያክል የዩአስ አሜረካ አርዳታ ለእስራኤል ያጎረፉት በሞስኮና በካይሮ መሐል በመግባት ሁለቱን ለማራራቅ አልመው ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ኪሲንጀር እንዳመኑት ‹‹የእስራኤል ጥንካሬ በአረቡ ዓለም ኮሚኒዝም እንዳይስፋፋ ለማድረግ የሚያስችል አልነበረም፡፡ ስለሆነም ጠንካራ የሆነችው እስራኤል በአረቡ ዓለም ኮሚኒዝም እንዳይስፋፋ በመግታት የአሜሪካን ጥቅም አስጠብቃለች የሚለው አባባል ውሃ አያነሳም፡፡ ይልቁንም አሜሪካ ናት ለእስራኤል ህልውና የጠቀመቻት” ብለዋል፡፡[32] ሮናልድ ሬገን በ1980 ለፕሬዝዳንትነት በውድድር ላይ በነበሩበት ጊዜ እስራኤልን ‹‹ስትራቴጂያዊ አጋር›› በማለት አሞካሽተዋታል፡፡ ሆኖም ግን በጻፏቸው ማስታወሻዎቻቸው ላይ እስራኤል ስትራቴጂያዊ ዋጋ ያላት ሀገር መሆኗን በመጥቀስ ፋንታ

የአይሁዳዊቷን ሀገር ለመርዳት ያነሳሷቸው ብዙ ሞራላዊ ጉዳዮች እንደነበሩ መግለጹን መርጠዋል።[33]

አስተዋይ የሆኑ እስራኤላዊያን የፖለቲካ ተንታኞች ይህን መሠረታዊ ሃቅ በሚገባ ይቀበላሉ። ስተራቴጂያዊ ኤክስፐርትና የቀድሞው የቴሌአቪቭ ዩኒቨርስቲ ስትራቴጂያዊ መካነ ጥናት ዋና ኃላፊ የነበሩት ሻይ ፊልድማን ባቀረቡት ጥናት የአሜሪካንና የእስራኤልን የፀጥታ ትብብር አስመልክቶ እንዲህ ብለዋል፦ ‘‘አሜሪካ እስራኤልን ለመርዳት የምታሳየው ተነሳሽነት፣ እስራኤል ስትራቴጂያዊ ጠቄሜታ ያላት በመሆኗ ላይ የተመሠረተ አይደለም። ከዚያ ይልቅ ይህ ግንኙነት ወርድና ስፋት እያገኘ የሄደው በ1980ዎቹ የእስራአልና አሜሪካ ደጋፊዎች በሪፖብሊካኖች አስተዳደር ውስጥ የዚህን ግንኙነት መሠረት በመጣላቸው ነው። እንደዚያም ቢሆን የአሜሪካና የእስራኤል ስትራቴጂያዊ ትብብርና እስራኤል ለዩናይትድ ስቴትስ ስትራቴጂያዊ አጋር የመሆኗ ጉዳይ፣ በአሜሪካና በእስራኤል መካከል ግንኙነት እንዲፈጠር ምክንያት ከሆኑ ሌሎች መሠረታዊ ነገሮች ጋር ሲነፃፀር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።›› ‘‘ሌሎች መሠረታዊ ነገሮች’’ በማለት ፊልድማን የጠቀሷቸው አይሁዳዊያን በናዚ ጀርመን የሆሎኮስት እልቂት ሰለባ መሆናቸው፣ የጋራ ፖለቲካዊ እሴቶች፣ የእስራኤላውያን አሳዛኝ መስሎ መታየት፣ የጋራ ከሆኑ ባሕላዊ ግንኙነቶችና የአይሁድ ማህበረሰብ በአሜሪካ ፖለቲካ ውስጥ የሚጫወተው ሚና ናቸው።[34]

ከቀዝቃዛው ጦርነት ወደ 9/11

ምንም እንኳን እስራኤል በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት ሁነኛ የአሜሪካ ተጓዳኝ ናት ቢባልም፣ ሶቭዬት ሕብረት ከተበታተነች በኋላ ግን የእርሷ ነገር አብቅቶለታል። እንደ ታሪክ ምሁሩ በርናርድ ሊዊስ አባባል ከሆነ (እርሳቸው ራሳቸው ዋነኛ የእስራኤል ደጋፊ ናቸው።)፡- ‹‹እስራኤል በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት ምንም ያክል ስትራቴጂያዊ ዋጋ ያላት ሀገር ብትሆንም፣ ቀዝቃዛው ጦርነት እንዳበቃ ግን ያን ሚናዋን ሙሉ በሙሉ አጥታለች ማለት ይቻላል።›› በአሜሪካና እስራኤል ግንኙነት ዙሪያ በርካታ መጻህፍትን የጻፉትና በጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ የፖስቲካል ሣይንስ ምሁር የሆኑት በርናርድሪች በ1995 እንደሚከተለው በማለት ከተመሣሣይ መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡- “ እስራኤል ለዩናይትድ ስቴትስ ልትሰጣት የምትችለው ውስን የሆነ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ጥቅም ነው። ስለሆነም ስትራቴጂያዊ ጥቅም ያላት ሀገር አይደለችም።” በብራንዲስ ዩኒቨርስቲ የመከላከያ ኤክስፐርት የሆኑት ሮበርት አርት ደግሞ በ2003 ላይ በሰጡት አስተያየት የሚከተለውን ብለዋል፡- ‘‘ እስራኤል ለዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ ያላት ስትራቴጂያዊ ጥቅም እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። እንዲያውም በብዙ መልኩ ካየነው እስራኤል ስትራቴጂያዊ እዳነቷ ያመዝናል።››[35]

በእርግጥም በ1991 የተደረገው የባህረ ሰላጤው ጦርነት እስራኤል ስትራጂያዊ ሸክም መሆኗ የታየበት ጊዜ ነበር ማለት ይቻላል። አሜሪካና አጋሮቿ በዚያ ጦርነት ከ400 ሺህ የሚበልጡ ወታደሮችን አዘጋጅተው ኩዌትን ከሳዳም እጅ ለማስለቀቅ ተነሱ። ሆኖም ግን በዚያ ዘመቻ የእስራኤልን ጦር አምባ (base) መጠቀም ወይም የጦር ሠራዊቷን ማሰለፍ አልቻሉም። ይህን ቢያደርጉ ብዙ የሕብረ ብሄሩ ጦር አባል ሀገራት ትብብር አደጋ ላይ መውደቁ የማይቀር ነበር። በዚህ መሃል ሳዳም ወደ እስራኤል እስከድ ሚሳይሎችን በመተኮስ እርሷን ለማስቆጣትና ወደ ጦርነቱ ውስጥ እንድትገባ በማድረግ የሕብረ ብሄሩን ኃይላት ትብብር ለመናድ ሙከራ አደረጉ። በዚያ ጊዜ ዋሽንግተን የመከላከያ መሣሪያዎችን (ፓትሪዮት

ሚሳዮልና ባትሪዎች) ወደ እስራኤል ማጓጓዝና እርሷን ለመከላከል መሯሯጥ ነበረባት። እርግጥ ነው በዚህ ጉዳይ ላይ እስራኤል ለአሜሪካ ጠቃሚ ስትራቴጂያዊ አጋር ሳትሆን ከባድ ስትራቴጂያዊ እዳ መሆኗ በግልጽ ታወቀ። ያንን ክስተት በሚገባ የታዘቡት ዊሊያም ዋልድግራቭ የተባሉና በእንግሊዝ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚኒስትር ማዕረግ ያገለገሉ ሰው እንዲህ ብለዋል፡- "ዩናይትድ ስቴትስ ከዚህ ክስተት የምትማረው ነገር ይኖራታል ብዬ አስባለሁ። ከእስራኤል ጋር ስትራቴጂያዊ ጉድኝት መፍጠር ይህን ለመሰለው ክፉ ቀን ካላገዛት ምንም ጠቀሜታ የለውም።›› ይህን ነጥብ በርናርድ ሉዊስም ቢሆን በሚገባ ተገንዝበውት የነበረ መሆኑን ከሚከተለው ጽሑፋቸው መገንዘብ አይከብድም፡- ‹‹የእስራኤል ስትራቴጂያዊ ወዳጅነት መለወጫ ጊዜው መድረሱ በባህረ ሰላጤው ጦርነት ወቅት በግልጽ ተንጸባርቋል።.....ዩናይትድ ስቴትስ ከሁሉም በላይ ለጊዜው ትፈልግ የነበረው እስራኤል ከውዝግቡ እንድትርቅ፣ ዝም እንድትል፣ ነገሮቸን ችላ ብላ እንድታይና ከተቻለም እንቅስቃሴ አልባ ሆና እንድትደበቅ ነበር። ..... እስራኤል መልካም ተጓዳኝ አልነበረችም፡ እንዲያውም ጠንቋ የማይለቅና ጣጣዋ የማያበቃ እዳ ነች።››[36]

ከዓለም አቀፍ አሸባሪነት በሚሰነዘር የጋራ ስጋት የተነሣ አሜሪካና አስራአል የቀዝቃዛው ጦርነት ካበቃ በኋላ ትብብር ማድረጋቸው ምክንያታዊ ነው ብሎ ማንም ሰው ሊያስብ ይችላል። እውነታው ግን ይህ አይደለም። በ1990ዎቹ የኦስሎ የሰላም ስምምነት እየተካሄደ የነበረ ሲሆን፣ የፍልስጥኤም አሸባሪዎች በእስራኤል ላይ ያደረሱት ጥቃት በ1994 ከነበረው 67 የሞትና 167 የመቁሰል አደጋ በ2000 ላይ ወደ 1 የሞትና 12 የመቁሰል አደጋ ዝቅ ብሏል። (ይሁን እንጂ የኦስሎ የሰላም ስምምነት መፍረሱ ከታወቀ በኋላ በ2001 ላይ ይህ አደጋ ከፍ ብሎ 111 እስራኤላውያን ሲገደሉ 918 የሚሆኑት ቆስለዋል። በ2002 ደግሞ 320 ሲሞቱ 1498 ቁስለኞች ተመዝግበዋል።)[37] የአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎች አልቃዒዳን ጨምሮ ስለ ኢስላማዊ አሸባሪነት ትኩረት መስጠት የጀመሩት የዓለም የንግድ ማዕከልን ለማፈንዳት ከተደረገው የ1993ቱ ሙከራ፣ በ1996 ከተደረገው የሳዑዲ አረቢያው ኾባር ህንፃ ጥቃት፣ በ1998 በኬንያና

በታንዛኒያ የአሜሪካን ኤምባሲዎች ጥቃትና በ1999 በየመን ከደረሰው የአሜሪካ ኮሌጅ ጥቃት በኋላ ነበር። ከእነዚህ ሁሉ ጥቃቶች በኋላ ችግሩን በተመለከተ የመከላከል ጥረቶች የተጀመሩ ቢሆንም፣ የመስከረም 11,2001 ጥቃት እስከተፈጸመበት ጊዜ ድረስ አሜሪካ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዘመቻ አልጀመረችም ነበር።[38]

በተመሣሣይ ሁኔታ ምንም እንኳ ኢራቅ፣ ኢራን፣ ሊቢያና ሶሪያን የመሰሉ መንግሥታት ሽብር ፈጠራን የሚደግፉ መሆናቸው እስራኤልንና አሜሪካን ቢያስጨነቃቸውም እነዚህ ሀገራት በዚያ ሁሉ ዘመን በአሜሪካ ላይ ይህ ነው የሚባል ጥቃት የመሰንዘርና ከባድ ሥጋት የመፍጠር አቅም አልነበራቸውም። ለአብነት ያክል እነዚህ ሀገራት በጋራ በ2000 የነበራቸው የሕዝብ ቁጥር አሜሪካ ካላት ሕዝብ ከ40 ከመቶ በታች ሲሆን፣ የሁሉም አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ዓመታዊ የምርት መጠናቸው (GDP) ከአሜሪካ ጋር ሲነፃፀር ከ5 በመቶ በጥቂቱ ብቻ ነበር የሚበልጠው። እንዲሁም አጠቃላይ የሆነው ወታደራዊ በጀታቸው አሜሪካ ካላት ወታደራዊ በጀት ከ3 ከመቶ ያነሰ ነው።[39] በዚያ ላይ ኢራቅ የተባበሩት መንግሥታት ማዕቀብ ያደቀቃት ስትሆን፣ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ለመሥራት ጥረት ብታደርግም፣ ብዙ እንዳልገፋችበት ይታወቃል። ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ እነዚህ ሀገራት እርስበርሳቸው የማይስማሙ በመሆኑ አሜሪካ እነርሱን ለማጥፋት ፍላጎት አልነበራትም።

በዚያ ፋንታ አሜሪካ፣ ኢራንና ኢራቅን በተመለከተ የምትከተለው የሁለትዮሽ የፖለቲካ ተቃርኖን የማስታመም ፖሊሲ ነበር። ሶሪያን በተመለከተ ግን ምንም እንኳ ያልተሳካ ቢሆንም፣ ከእስራኤል ጋር የመጨረሻ የሰላም ስምምነት እንዲያደርጉ ጥረት አድርጋለች።[40] ከሊቢያ ጋር የነበረው ሁኔታ ደግሞ ለየት ያለ ሲሆን፣ በስኬት የተደመደመ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ መርሃ-ግበሯን እንድታቆም የማሳመን የተራዘመና በመጨረሻም ጥረት ተደርጓል። ሊቢያ በተጨማሪም የፓን አሜሪካን የሕዝብ ማመላለሻ አውሮፕላን ሰለባዎችን ኃላፊነት እንድትሸከም ለዓመታት የዘለቀ የማዕቀብና ትዕግሥት የጠየቀ ዓለም አቀፋዊ የዲፕሎማሲ ጥረት ተደርጎ ለተጎጂዎቹ ተገቢውን ካሣ እንድትከፍል ተደርጓል።[41] እንግዲህ

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል እነዚህን ጉዳዮች ለማሳካት የእስራኤል እገዛና ጥረት ተፈላጊ አልነበረም። ምክንቱም ዩናይትድ ስቴትስ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ብቻዋን የመፈጸም ብቃት ነበራትና።

በሌላ በኩል የአሜሪካ ፖሊሲ እውጪዎች ከእነዚህ በጥባጭ ሀገራት ጋር ለመነጋገር የእስራኤል ሚና ወሳኝ ነው ማለታቸው እስራኤልን ከፍ ያለ ዋጋ የሚሰጣት አገር አያደርጋትም። ምክንያቱም አሜሪካ ከእነዚህን ሀገራት ጋር እሰጥ አገባ ውስጥ የተዘፈቀችው የእስራኤልን ሕልውና ለመጠበቅ ሐላፊነቱን በመሸከሟ የተነሳ ነው። ለምሳሌ በቴህራንና ዋሽንግተን መካከል ያለው ዋነኛ የተቃርኖ ምክንያት ኢራን የካምፕ ዴቪድን የሰላም ስምምነት በመቃወሟ፣ ሂዝቡላህን በመርዳቷና የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ የማነጽ መርሐ-ግብር ያላት በመሆኑ ነው። በኢራን በኩል የእነዚህ ጉዳዮች ጠቃሚነት ይበልጥ የሚጎላው አሜሪካ ከእስራኤል ጋር ባላት ልዩ የሆነ ግንኙነት ምክንያት ነው።[42] በእርግጥ ዋሽንግተን በክልሉ ማንም ሀገር የበላይ እንዲሆንና የባህረ ሰላጤውን የነዳጅ አቅርቦት አደጋ ላይ እንዲጥለው አትፈቅድም። በተለይም ደግሞ የኢራንን የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ መታጠቅ -እስራኤል የምትባል ሀገር በሕልውና ባትኖር እንኳ- አሜሪካ አጥብቃ ትቃወመዋለች። ሆኖም ግን አሜሪካ ለእስራኤል በሕልውና መቀጠል ያላት ኃላፊነት ይህን ጉዳይ ይበልጥ አውሰብስቦታል።

እስከ መስከረም 2001 ድረስ የሽብርተኝነት አደጋና ሽብርን ከሚደግፉ ሀገራት የሚመነጩ ችግሮች አሜሪካ እስራኤልን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንድትደግፍ የሚያደርጋት ስትራቴጂያዊ ምክንያት አልነበረም። አሜሪካ ለእስራኤል የምታደርግላትን ይህን የመሰለውን ቸርነት ትክክለኛ ምክንያቱን ለመገንዘብ አስቸጋሪ፣ እንዲሁም እስራኤልም የአሜካን እርዳታ ለምን እንደምትሻና ዳሩ ግን ያንን እርዳታ እንደ ችሮታ ሳይሆን እንደ መብቷ መቁጠሯን ማብራሪያ የሚሻ ጉዳይ ያደርጉታል።

‹‹የፀረ-አሸባሪነት ሽርክና›› አዲሱ የግንኙነት ሰበብ

ከመስከረም 11 የአሸባሪዎች ጥቃት በኋላ አሜሪካ እስራኤልን ለመርዳት የምታቀርበው ስትራቴጂያዊ ምክንያት “ሁለቱ ሀገራት የፀረ- አሸባሪነት ሽሪክ ናቸው" የሚል ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ ምክንያት የሚያሳየው ዩናይትድ ስቴትስና እስራኤል ተመሣሣይ በሆኑ የሽብር ቡድኖች ማስፈራሪያ እንደሚደርስባቸውና እነዚህን ቡድኖች የሚደግፉ ጠብ ጫሪ ሀገራት ደግሞ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ለመታጠቅ የሚሞክሩ መሆናቸው ነው፡፡ እነዚህ ቡድኖች ለእስራኤልና አሜሪካ የሚያሳዩት ጠላትነት መነሻው መሠረታዊ ለሆነው የምእራባውያን የአይሁድ ክርስቲያን (Judio–Chstian) እሴቶች፣ ባህልና ዲሞክራሲያዊ ተቋማት ያላቸው ጥላቻ እንደሆነ ይነገራል፡፡ በሌላ አባባል እነርሱ እኛን አሜሪካውያንን የሚጠሉን አሜሪካዊያን በመሆናችን እንጂ በምንፈጽመው ተግባር አይደለም፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ እስራአልን የሚጠሏት የምዕራባውያንን ዘመናዊ ባህል የምትከተል በመሆኗ እንጂ ቅዱሳን ቦታዎችን ጨምሮ የአረብ መሬቶችን በመያዟና በዚያ የሚገኙ አረቦችን በመጨቆኗ አይደለም፡፡

ይህ አዲስ መሠረታዊ ምክንያት (The new rational) አሜሪካ ከአረቡና ከሙስሊሙ ዓለም ጋር ላላት የሻከረ ግንኙነት እስራኤልን ተጠያቂ በማድረግ ፋንታ በዓለም አቀፋዊው ፀረ-ሽብር ትግል ቁልፍ ተዋናይና አጋር አድርጎ ያቀርባታል፡፡ ለምን? ምክንያቱም የእርሷ ጠላቶች ሁሉ የአሜሪካም ጠላቶች ናቸው የሚል እሳቦት በሕዝቡ ዘንድ አንዴ ሰርጿልና፡፡ ለዚህ አባባል ማሳያ ይሆን ዘንድ አሪዮል ሻሮን ከመስከረም 2001 አደጋ በኋላ አሜሪካን በጎበኙ ጊዜ የተናገሩትን መጥቀስ ይጠቅማል፡፡ እንዲህ ነበር ያሉት፡- ‘‘እናንተ እዚህ በአሜሪካ ያላችሁ ከአሸባሪነት ጋር ጦርነት ላይ ናችሁ፡፡ እኛም በእስራኤል የምንገኝ እንዲሁ ከአሸባሪነት ጋር ጦርነት ላይ ነን፡፡” በትልቁ ቡሽ ዘመን በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ የነበሩ አንድ ፖለቲከኛ ይህን የሻሮን አባባል አስመልክተው ሲናገሩ፡- “ሻሮን፡- እኔ የምዋጋው የእርሰዎን ጦርነት ነው፤ ሽብር ፈጠራ ሌላ ሳይሆን ያው ሽብር ፈጠራ ነው

ወዘተ.....እያሉ በኘሬዝዳንቱ ላይ ቀልደዋል" ብለዋል።[43] የቀድሞው የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንጃሚን ናታንያሁ በ2002 ከአሜሪካ ሴኔት ፊት ቀርበው እንዲህ አሉ፡- ‹‹አረፋት የሚያመርቱትን የአሸባሪነት ሰብዓዊ ቦምብ የሚፈለፍለውን ፋብሪካ በአስቸኳይ ካልዘጋችሁ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ነገ አጥፍቶ ጠፊዎች የእናንተን ከተሞች ያተራምሷቸዋል። ይህ እብደት በጊዜ ካልተገታ በአውቶቡሶቻችሁ፣ በገበያ አዳራሾቻችሁ፣ በፒዛ መሸጫዎቻችሁና በካፌቴሪያዎቻችሁ ነገ የሚሆነውን ታያላችሁ።›› ናታንያሁ በተጨማሪም፡- ‹ቺካጎ ሰን ታይምስ› በተባለው ጋዜጣ የሕዝብ አስተያየት መስጫ አምድ ላይ እንዲህ በማለት ጽፈዋል፡- ‹‹በአሸባሪነት ሊገለጽ የሚችል በእውን ወይም በሀሳብ የሚንፀባረቅ ቅሬታ ፈጽሞ አይገኝም።.....የአሜሪካ ጡጫ በአፍጋኒስታን ያለውን የታሊባን መንግሥት ገንድሶታል። በዚያ የሚገኘው የአል-ቀኢዳ መረብም በራሱ ጊዜ ተበጣጥሷል። አሜሪካ ከዚህ በኋላ ደግሞ በኢራን፣ በኢራቅ፣ በሶሪያ፣ በያሲር አረፋትና መሰል አሸባሪ ኃይላት ላይ ተመሣሣይ የሆነ ክርኗን ማሳረፍ ይኖርባታል።"[44] እርሳቸውን የተኳቸው ኢሁድ ባራክም በሰንደይ ታይምስ ላይ እንዲህ በማለት ጽፈዋል፡- ‹‹አሸባሪው ማን እንደሆነና ሽብርን የሚደግፉት ተንኳሽ መንግሥታት እነማን እንደሆኑ ዓለም በትክክል ያውቃል። ኢራንን፣ ኢራቅን፣ ሊቢያን፣ ሱዳንንና ሰሜን ኮሪያን የመሳሰሉት መንግሥታት ሽብር ፈጠራን በመደገፍ ረገድ ሪከርድ የሰበሩ ናቸው። ሀማስ፣ ሂዝቡላህ፣ ኢስላሚክ ጅሃድ፣ ሌላው ቀርቶ የያሲር አረፋቱ ፒ.ኤል.ኦ የሚፈጽሙትን ድርጊት የማያውቅ አይገኝም››[45] ። ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሁድ ኦልመርት በ2006 በአሜሪካ ኮንግረስ ፊት ቀርበው ሲናገሩ፡- ‹‹ሀገሮቻችን አሸባሪነት የሚያስከትለውን ሕመምና አደጋ በእኩል ደረጃ አልተጋፈጡም። እኛ ከመካከላችን ንፁሃን ሰዎቻችንን በግፍ የሚነጥቁንን ጨካኝ አሸባሪዎች ለማስወገድ ዝግጁነቱና ውሳኔው አለን››።[46]

የእስራኤል ደጋፊዎች የሆኑ አሜሪካዊያንም እንዲሁ ተመሣሣይ የሆነ የማሳመኛ ምክንያት ያቀርባሉ። ለምሳሌ በጥቅምት ወር 2001 ሮበርት ሳትሎፍ የተባሉ ሰው አሜሪካ ከመስከረም 11 በኋላ እስራኤልን መደገፏን መቀጠል የሚኖርባት ለምን እንደሆነ ሲያብራሩ፡- ‹‹መልሱ ግልጽ ነው።

በምንጋራቸው የጋራ ዲሞክራሲያዊ እሴቶቻችንና በምንጋፈጣቸው የጋራ ጠላቶቻችን ምክንያት ሲሆን ..... የዓለም ንግድ ማዕከልንና ፔንታጎንን ካወደሙት አሸባሪዎች ጥቃት የሚቃጣበት ከእስራኤል በስተቀር ሌላ ሀገር የለም›› ብለዋል፡፡[47] የኒውዮርኩ የዲሞክራቲክ ፓርቲ ተወካይ ሴናተር ቻርለስ ስኩመር በ2001 እንደገለጹት፡- ‹‹ፒ.ኤል.ኦ ልክ እንደታሊባን፣ አሸባሪዎችን የሚረዳ፣ የሚያደፋፍርና አስተማማኝ የሆነ መጠለያቸው {Safe Havn) ነው፡፡ እስራኤል ደግሞ ልክ እንደ አሜሪካ ደጇን ከጥቃት የምትከላከል ናት፡፡ .....ሙላህ መሐመድ ለአሜሪካ ጠንቅ እንደሆኑት ሁሉ፣ አረፋትም ለእስራኤል እንደዚያው ናቸው፡፡›› በማለት ተናግረዋል፡፡[48] ይህ በእንዲህ እያለ በሚያዝያና ግንቦት ወር 2002 ኮንግረሱ (በሕግ አውጪው አካል 352 ለ21 እንዲሁም በሴኔቱ 94 ለ2) በሆነ ሰፊ የድምፅ ልዩነት ሁለት ተመሣሣይ ውሳኔዎችን አሳለፈ፡፡ በእነዚህ ውሳኔዎች የተላለፈው መልእክት ‹‹ዩናይትድ ስቴትስና እስራኤል በሽብርተኝነት ላይ የጋራ ግምባር በመፍጠር ዘመቻ ጀምረዋል፡፡›› የሚል ነው፡፡[49] የ2002ቱ የአሜሪካና እስራኤል የሕዝብ ጉዳይ ኮሚቴ (ኤ.አይ.ፒ. ኤ.ሲ ወይም አይፓክ) መልእክት፡- “አሜሪካና እስራኤል ሽብርተኝነትን ለመዋጋት አንድ ላይ ተነስተዋል” የሚል ነበር፡፡ በዚያ ኮንፈረንስ ላይ የቀረቡት ጽሑፎች ትኩረት ያደረጉት የጋራ ስጋት ምንጭ ናቸው በተባሉትና በያሲር አረፋት፣ ኦሳማ ቢንላደን፣ ሳዳም ሁሴን፣ ታሊባን፣ ሐማስ፣ ሂዝቡላህ፣ ኢራንና ሶሪያ ላይ ነበር፡፡[50] ፒ.ኤን.ኤ.ሲ.የተባለው ሌላ የአይሁዶች ድርጅት በሚያዝያ 2002 ለፕሬዚዳንት ቡሽ በላከው ደብዳቤ ላይ ዊሊያም ክሪስቶል፣ ሪቻርድ ፐርል፣ ዊሊያም ቤኔት፣ ዳንኤል ፓይፕ፣ ጀምስ ውልሲ፣ ኢሊዮት ኮሽን፣ ኖርማን ፓድሆርትዝና ሌሎች ሃያ ስምንት የሚሆኑ ዋነኛ ወግ አጥባቂ ፖለቲከኞች ፊርማቸውን አስፍረዋል፡፡ በዚያ ደብዳቤ ውስጥ የሰፈረው መልዕክት እንዲህ የሚል ነበር፡- “ዮናይትድ ስቴትስና እስራኤል የጋራ የሆነ ጠላት የተጋፈጡ መሆኑን ማንም ሊጠራጠር አይችልም፡፡ እኛ ሁላችንም ብንሆን እራስዎ (ፕሬዚዳንት ቡሽን ማለታቸው ነው) በትክክል እንደገለጿቸው የሰይጣን ዛቢያዎች ከሚባሉትና መከላከያ ሚኒስቴር ዶናልድ ራምስፌልድ ከዘረዘሯቸው ከኢራን፣ ኢራቅና ሶሪያ ጋር ተፋጥጠናል፡፡

እነዚህ ሀገራት በአሜሪካ ላይ የሽብር ዘመቻ እንደከፈቱት ሁሉ በእስራኤልም ላይ የፖለቲካዊ ግድያና አጥፍቶ መጥፋት እንዲፈጸም ለአሸባሪዎች የገንዘብ ድጋፍና ቅስቀሳ ያደርጋሉ፡፡ ...እርስዎ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአሸባሪነት ላይ ዘመቻ እንደከፈቱት ሁሉ፣ እስራኤልም ተመሣሣይ ጦርነት በመዋጋት ላይ ናት፡፡››[51]

በአዲሱ መሠረታዊ ምክንያት አስተጋብኦት የተነሣ ብዙ አሜሪካዊያን የመስከረም 11ዱን ክስተት በእስራኤል ላይ ከሚደርሰው ጥቃት ጋር ቢያመሳስሉት አያስደንቅም፡፡ የአሜሪካና የእስራኤል በሽብርተኝነት ላይ የተደረገ ይህ ቁርኝት እስራኤል ከአሜሪካ ያለምንም ቅድመ ሁኔታና ገደብ እርዳታ እንድታገኝ በር የከፈተላት መሆኑ እውነት ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ ጥልፍልፎሽና እሰጥ አገባ መጨረሻ ላይ ማንም አመዛዛኝ የሆነ ሰው ሊደርስበት የሚችለው ሃቅ እስራኤል ከአሸባሪነት ጋር በሚደረገው ጦርነትም ሆነ ጎረቤቶቿ ከሆኑት ተንኳሽ መንግሥታት ከሚቃጣባት ጥቃት አንፃር ለአሜሪካ እዳ መሆኗን ነው፡፡

አዲሱ ስትራቴጂያዊ ምክንያት፣ ፍልስጤማውያን ሽብርተኞች ለእስራኤል አደገኛና አስፈሪዎች እንደሆኑ ሁሉ ለአሜሪካም እንደዚያው ናቸው በማለት ሽብር ፈጠራ የተባበረና የተደራጀ አንድ ኃይል እንደሆነ አድርጎ ሊያሳየን ይሞክራል፡፡ በዚህ እሳቦት መሠረት መስከረም 11 አሜሪካን ያጠቁት ሽብርተኞች በሚገባ የተደራጀው ዓለምአቀፋዊ የሽብር ፈጠራ እንቅስቃሴ አካል ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አስተያየት ስለ ሽብር ፈጠራ የተሳሳተ ግንዛቤን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ሽብርተኝነት አንድ የተደራጀ አካል ወይም እንቅስቃሴ፣ ሌላው ቀርቶ ጦርነት ሊታወጅበት የሚችል ግልጽ ጠላት አይደለም፡፡ ከዚያ ይልቅ ሽብር ፈጠራ የጠላትን ይዞታዎች በተለይም ሲቪሎችን አጥቅቶ በጠላት ላይ ፍርሃትና የሞራል መላሸቅን በማስከተል ውጤታማ የማይሆኑ አጸፋዎችን እንዲወስድና ለተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ሞራላዊ ኪሳራዎች እንዲዳረግ የሚያስችል ስልት ነው፡፡ ይህን ስልት ብዙ የተለያዩ ቡድኖች የሚጠቀሙበት ሲሆን፣ በተለይም ደግሞ አቅማቸው ከጠላታቸው በጣም ያነሰ ሆኖ ከተገኘ ከዚህ ስልት የተሻለ መልካም ዘዴ አያገኙም፡፡ ዒዮናዊያን እንግሊዞችን ከፍልስጥኤም ምድር

ለማስወጣትና የራሳቸውን መንግሥት ለመመሥረት ይህን ዘዴ አሳምረው ተጠቅመዋል፡፡ ለምሳሌ በ1946 እየሩሳሌም የሚገኘውን የንጉሥ ዳዊት ሆቴል በቦምብ በማጋዬት የተባበሩት መንግሥታት አደራዳሪ የነበሩትን ፎልክ በርናዶቴን ገድለዋል። ዩናይትድ ስቴትስ ራሷ ብዙ አሸባሪ የሆኑ ድርጅቶችን የረዳች ሲሆን፣ ከእነዚህም ውስጥ የኒካራጓው ኮንትራስና የአንጎላው ዩኒታ ይገኙበታል። የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶችም ብዙ የቀድሞ አሸባሪዎችን (ለምሳሌ የፒ.ኤል. ኦን መሪ ያሲር አራፋትን፣ የሃጋና ዒዮናዊያን አሸባሪ ቡድን መሪ የነበሩትንና በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር የሆኑት ሜሪሃም ቤጊንና ይስሃቅ ሻሚርን) ወደ ኋይት ሃውስ ጋብዘዋል። ይህ ድርጊታቸው የሚያሳየው ሽብርተኝነት የዓላማ ማሳኪያ ስልት እንጂ የተደራጀ እንቅስቃሴ አለመሆኑን ነው። በዚያም አለ በዚህ በሲቪሎችና በንፁሃን ላይ ጥቃት ማድረስ ምንም አይነት ማስተባበያ ሊቀርብበት የማይችል አስከፊ ድርጊት ነው። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነት የሽብር ፈጠራ ቡድናት ሁልጊዜም ቢሆን በአሜሪካ ጥቅሞች ላይ አደጋ ለማድረስ ያልማሉ ማለት ያሳስታል፡፡ በሌላ በኩል አሜሪካ አሁንም ድረስ የምትደግፋቸው ሽብርተኛ ቡድኖች የሉም ማለትም ስህተት ላይ ይጥላል፡፡

ከአል-ቃዒዳ ውጭ ያሉ ጸረ ኢስራኤል አሸባሪ ቡድኖች (ለምሳሌ ሐማስ፣ ኢስላሚክ ጀሃድና ሂዝቡላህ) ጥቃታቸው በእስራኤል እንጅ በአሜሪካ ላይ አይደለም፡፡ ሂዝቡላህን ብንወስድ፣ የሄብሩ ዩኒቨርስቲው ምሁር ሞሼ ማአዝ ‹‹ብዙውን ጊዜ አደጋ የሚደቅነው በእስራኤል ላይ ነው፡፡ የአሜሪካን ማሪን ወታደሮች በሊባኖስ፤ ቤይሩት በቦምብ መፍጀቱ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ግን ያን ያደረገው የውጭ ኃይሎችን ከሊባኖስ ለማስወጣት ነበር፡፡ ሂዝቡላህ ከክልሉ ወጥቶ አሜሪካን ለማጥቃት ይሞክራል የሚል ጥርጣሬ የለኝም›› በማለት ግምገማቸውን አስፍረዋል። የመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳዮች ጠቢብ የሆኑት ፓትሪክ ሲል በዚህ ግምገማ የሚስማሙ ሲሆን፣ እንዲህ ይላሉ፡- “ሂዝቡላህ ሙሉ በሙሉ የሀገር ውስጥ እንቅስቃሴ ሲሆን ያነጣጠረውም በቀጥታ በእስራኤል ላይ ብቻ ነው፡፡" የሽብር ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች የሆኑት ዳንኤል ቤንጃሚንና ስቴቭን ሲሞን ሃማስን አስመልክተው ከላይ የቀረበውን ሀሳብ የሚያስተጋቡ ሲሆን፣ “እስካሁን ድረስ በአሜሪካና

አሜሪካውያን ላይ ጥቃት አድርሶ አያውቅም›› ብለዋል፡፡[52] ምናልባትም የሁሉም አሸባሪ ቡድኖች ድርጊቶች ከሞራል አንፃር ከታዩ የተሳሳቱ ናቸው ብለን ልናምን እንችላለን፡፡ ከአሜሪካ ስትራቴጂያዊ ጥቅም አንፃር ግን ሁሉም አሸባሪዎች በእኩል አይን አይታዩም፣ ወይም አንድ አይነት አይደሉም፡፡

ኦሳማ ቢን ላደንና የእርሱ መስመር ተከታዮች ከተለያዩት የፍልስጤም አሸባሪ ቡድኖች ጋር ያላቸውን ትስስር የሚያሳይ አሳማኝ ማስረጃ አልተገኘም፡፡ እንዲሁም ብዙ የፍልስጤም አሸባሪ ቡድናት የአል-ቃዒዳ ፍላጎት የሆነውን በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢስላማዊ ተሃድሶን የማምጣትና በሽሊፋዎች የሚመራ መስተዳደር የመመስረትን ዓላማ አይጋሩም፡፡ ከዚህም አልፎ ፒ.ኤል.ኦ ኢስላማዊ ሳይሆን በአመዛኙ የሴኩላሪስቶችና የብሔርተኞች (Nationalists) ስብስብ ነው፡፡ ብዙ ፍልስጤማውያን በኢስላማዊው አስተሳሰብ እየተማረኩና ወደዚያው እየተሳቡ ያሉት ከቅርብ አሰርት ዓመታት ወዲህ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የእነዚህ ቡድኖች እንቅስቃሴ የሚያተኩረው በአብዛኛው በእስራኤል ላይ ሲሆን፣ በምዕራቡ ዓለም ላይ ግን የሚያሰቅቅና በአስከፊ ጥቃት የታጀበ ደመ-ነፍሳዊ እርምጃ እንዲፈጸም አይሹም፡፡ ከዚያ ይልቅ የፍልስጥኤም አሸባሪዎች ኢላማቸው ያነጣጠረው በእስራኤል ላይ ባላቸው የቆዬና የተራዘመ ታሪካዊ ቅሬታ ላይ ነው፡፡ ይህም ቀደም ሲል ወደ ፍልስጤም ምድር የተደረጉትን የሚዮናዊያን ፍልሰቶች ተከትሎ ከ1948 ጦርነት በኋላ ፍልስጤማውያንን ከምድራቸው በስፋት ከማባረሩ ሂደት ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ዛሬ ይህ እንቅስቃሴ እስራኤል የምዕራባዊውን ወንዝ ዳርቻና ጋዛ ስርጥን በቅኝ ግዛትነት ለመያዝ በምታደርገው የተራዘመና አሰልቺ ዘመቻዋ ምክንያት ተባብሶ ቀጥሏል፡፡ ለዚህም አንዱና ተጠቃሽ የሚሆነው ምክንያት የፍልስጤማውያን ቀድሞ ያለመደራጀትና ደካማ ሆኖ መገኘት ነው፡፡ እስራኤል እነዚያን መሬቶች በ1967ቱ ጦርነት ስትይዝ በጣም ጥቂት አይሁዳውያን ብቻ በዚያ ይገኙ የነበረ ሲሆን፣ እስራኤል ቀጣዮቹን አርባ ዓመታት ያሳለፈችው አካባቢውን በቅኝ ገዥነት በመያዝ፣ መንደሮችን በማስፋፋት፣ መንገዶችን በመሥራትና ወታደራዊ ሰፈሮችን በመመስረት፣ እንዲሁም እነዚህን እንቅስቃሴዎች

በመቃወም በየጊዜው የሚነሱ ፍልስጤማውያንን በኃይል በመጨፍለቅ ነው።[53] ከዚህ ሁሉ በኋላ የፍልስጤማውያን እንቅስቃሴ በሽብርኝነት የታጀበ ቢሆን ምንም አያስደንቅም። ይህን በመሰለ ሁኔታ ላይ የወደቁ ሌሎች ሕዝቦችም ቢሆኑ ከዚህ የተሻለ ምርጫ አይኖራቸውም ነበር።[54] ምንም እንኳን ዛሬም ድረስ ሐማስን የመሰሉ ቡድኖች የእስራኤልን ሕልውና ባይቀበሉም ያሲር አራፋትና ሌሎችም የፍልስጥኤም ነፃ አውጭ ድርጅት (ፒ.ኤል.ኦ) አንጃዎች የእስራኤልን ህልውና መቀበላቸውን መዘንጋት የለብንም። አሁን የፍልስጥኤም ፕሬዚዳንት ሆነው እያገለገሉ ያሉት ማህሙድ አባስም የእስራኤልን ህልውና የሚቀበሉ መሆኑን ደጋግመው እየገለጹ ይገኛሉ።

እስራኤልና አሜሪካ ከአሸባሪዎች ሊሰነዘርባቸው የሚችለው አደጋ ስጋት እንዳለ ሆኖ አሜሪካ ይህንን ጥቃት ለመመከት ከእስራኤል ጋር የፀረ-አሸባሪነት ቁርኝት ፈጥና አልፈጠረችም። ሆኖም ግን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሽብርተኝነት ጥቃት ሊሰነዝርባት እንደሚችል በተገነዘበች ጊዜ ዘመቻዋን በድል ለመወጣት የእስራልን አጋርነት ጠይቃለች። እርግጥ ነው አሜሪካ በአሸባሪዎች እዚህም እዚያም የመጠቃት አደጋ ቢደርስባት አያስገርምም። በመካከለኛው ምሥራቅ የትም ሥፍራ ላይ አሜሪካ እስራኤልን እንደምትደግፍ የሚያሳዩ የዜና ዘገበዎች በብዛት ይነበባሉ። ይደመጣሉም። ይህም ለብዙ አስርተ ዓመታት የተለመደ ክስተት ሆኖ ቆይቷል። ዳሩ ግን ብዙዎች ያልተገነዘቡት ሃቅ አሜሪካ በእነዚያ ሁሉ ዓመታት ለአንድ ወገን ያዘነበለ ድጋፍ ስታደርግ መቆየቷ ያስከፈላት ዋጋ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ነው። እነዚህ የአሜሪካ ፖሊሲዎች አል--ቃዒዳ እንዲፈጠርና አስተሳሰቡም በብዙ ሰዎች ልብ ውስጥ ቦታ እንዲያገኝ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ተከታዮቹን ለመመልመል እንዲችል፣ እንዲሁም በክልሉ ውስጥ የፀረ አሜሪካዊነት ስሜት በእጅጉ እንዲያይል አድርገዋል።

እስራኤል አሁንም ቢሆን የአሜሪካ ጠቃሚ ስትራቴጂያዊ ተጓዳኝ ናት ብለው የሚያምኑ ወገኖች፣ አሜሪካ እስራኤልን በመርዳቷና በሽብር ስጋቶቿ፣ በተለይም ደግሞ በመስከረም 11ዱ ጥቃት መካከል ግንኙነት መኖሩን ይክዳሉ። ‹‹ኡሳማ ቢን ላደን የፍልስጤማውያንን መከራ ለዓላማው

መጠቀሚያ ያደረገው ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ነው፡፡ ምክንያቱም ተከታዮቹን ለመመልመል ያስችለዋልና›› በማለትም ይከራከራሉ፡፡ ይህን ሀሳብ ከሚያራምዱ ሰዎች መካከል አንዱ ሮበርት ሳትሎፍ ሲሆኑ፣ ‹‹ቢን ላደን ራሱን ከፍልስጤማውያን ትግል ጋር ማዛመድ የጀመረው በቅርቡ ሲሆን፣ ይህም በእርግጠኝነት የአድርባይነትና የማስመሰል ስልት እንጂ ሌላ አይደለም›› ይላሉ፡፡ አለን ደርሾዊዝ የተባለ ሌላ ምሁር ደግሞ፡- ‹‹ከመስከረም 11ዱ ጥቃት በፊት እስራኤል በግልጽ ከቢን ላደን ኢላማ ውስጥ እምብዛም አልነበረችም›› ባይ ናቸው፡፡ አሜሪካዊው የፖለቲካ ሰው ዴኒስ ሮስ ‹‹ቢን ላደን በአሜሪካ ላይ ያወረደው መዓት ሰበቡ ለፍልስጥኤማዊያን ያለው ሀዘኔታና ተቆርቋሪነት እንደሆነ በመናገር ድርጊቱን ሕጋዊ ለማድረግ ይሞክራል" ብለዋል፡፡ ማርቲን ክራመር የተባሉ ሌላ ፖለቲከኛ በበኩላቸው፡- ‹‹አሜሪካ ለእስራኤል የምታደርገው ድጋፍ ለብዙ ሕዝቦች የቅሬታ መነሻ እንደሆነና ለአል--ቃዒዳም ተከታዮቹን በቀላሉ ለመመልመል አመቺ ሁኔታ እንደፈጠረለት ከሚያምኑ ምሁራን መካከል አንዳቸውም ከአድሏዊነት የጸዱ አይደሉም›› ሲሉ ተናግረዋል። ኖርማን ፓድሆርትዝም ተመሣሣይ አቋም አላቸው፡፡ “እስራኤል የምትባል ሀገር በሕልውና ባትኖር ወይም ደግሞ በአንዳች ምትሃታዊ ኃይል ብትጠፋ እንኳን አሜሪካ ከእነዚህ አረቦች በአብዛኛዎቹ ዓይን ሰይጣናዊ መናፍስት የሚፈነጩባት የእርጉማን ምድር ተደርጋ መታየቷ አይቀርም”ብለዋል።[55]

እነዚህ አቋሞች የእስራኤል ደጋፊ በሆኑ ወገኖች መነገራቸው የሚያስገርም አይደለም፡፡ ምክንያቱም አሜሪካ እስራኤልን ደግፋ መቆሟ በፀረ--አሜሪካ እንቅስቃሴዎች ላይ ነዳጅ በማርከፍከፍ እዚህም እዚያም እንደምናየው ብዙ ዋጋ እንድትከፍል አድርጓታል የሚለውን ሃቅ አምኖ መቀበልና እስራኤል ስትራቴጂያዊ ጥቅም የምታስገኝ አጋር መሆኗን ጥያቄ ውስጥ ማስገባት ማለት፣ ዋሽንግተን ለእርሷ የምትሰጠውን እርዳታ ለቅድመ ሁኔታዎች ማስገዛትና ከፍልስጤማውያን ጋር ያላትን ግንኙነት በተመለከተም ከእስካሁኑ የተለዩ ስልት ልትከተል እንደሚገባት መቀበል ማለት ነውና፡፡

ይሁንና አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠው እርዳታ በአረቡና ሙስሊሙ ዓለም ፀረ-አሜሪካ አቋም እና የአሸባሪነት እንቅስቃሴ እንዲባባስ ማድረጉን

የሚያሳዩ ብዙ ማስረጃዎች ይገኛሉ።[56] አንዳንድ ሙስሊም አክራሪዎች፣ አሜሪካን ጨምሮ የምዕራቡ ዓለም የሚያራምደው ቁሳዊነት የሚያመዝንበት አካሄድ፣ በአረቡ ዓለም የሚገኙና የነቀዙ መንግሥታትን በመደገፍ ነዳጅ ዘይትን ለመመዝበር የሚያደርገው ሸኩቻ፣ እንዲሁም ተደጋጋሚ የሆነው ወታደራዊ ጣልቃ ገብነቱ ..... የሚያበግናቸውን ያህል፣ አሜሪካ እስራኤልን በመደገፏና እስራኤልም በፍልስጤማውያን ላይ ለምትወስደው ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ ይበግናሉ። ከእነዚህ ምሁራን መካከል ሰይድ ቁጥብ አንዱ ናቸው። ሰይድ ቁጥብ ግብፃዊ የሙስሊም ወንድማማቾች ቡድን መሪና በጻፏቸው መጽሐፍት በዘመናቸው የነበረውን ሙስሊም መሠረተኛ ማህበረሰብ የቀሰቀሱ ሲሆን፣ የአሜሪካ ማህበረሰብ በአብዛኛው የነቀዘና ምግባረ ብልሹ በመሆኑና መንግሥቱም እስራኤልን ስለሚደግፍ ይጠሉት ነበር።[57] ሰይድ መሐመድ ፈድለላህ የተባሉ የሂዝቡላህ መንፈሳዊ መሪ በ2002 እንዲህ ብለው ነበር፡- ‹‹በእኔ እምነት እስራኤል ለፈጸመቻቸው ድርጊቶች ሁሉ አሜሪካ ኃላፊነቱን መሸከም ይኖርባታል። ይኸውም እስራኤል በ1948 የፍልስጤማውያንን ሀገር በመውረር መንግሥት ሆና ስትመሰረትና በ1967 የተስፋፊነት ፖሊሲዋን በማራመድ ተጨማሪ መሬቶችን ስትቀማ አሜሪካ የአስመሳይነት መንፈስ የሚታይባቸውን እርምጃዎች አልፎ አልፎ ከመውሰዷና የእስራኤልን ተስፋፊነት በቃላት ደረጃ ለመቃወም ከመሞከሯ ውጭ እዚህ ግባ የሚባል ጥረት ባለማድረጓ መናፍቅነቷን አስመስክራለች። ለእስራኤል ገዳይ ጠመንጃዎችን ስታቀብል ፍልስጤማውያንን ግን በባዶ ቃላት ስትሸነግላቸው ኖራለች።››[58] ማንም ቢሆን ይህን ንግግር ለማስተባበል ወይም በአረቦች ጭንቅላት ላይ መጥፎ ስሜት አያሳድርም ብሎ ለመከራከር መሞከሩ ከንቱ ነው። ይህ ንግግር የሚያሳየው አሜሪካ በፍጹም ፈቃደኝነት ያንን ለሚያክሉ ዘመናት እስራኤልን ስታግዝ መኖሯ በአረብ ሕዝቦች ጭንቅላት ውስጥ ምን ያህል ጥላቻና ቅሬታ እንዳተረፈላት ነው።

አሜሪካ እስራኤልን በጭፍን መርዳቷ ፀረ-አሜሪካ ሽብር ፈጠራን እንደወለደ ለማረጋገጥ የራምዚ ዩሱፍን ታሪክ መዳሰሱ ይጠቅማል። ራምዚ የመጀመሪያውንና የዓለም ንግድ ማዕከልን (World Trade Center) በ1993

ለመምታት የታለመውን ኦፕሬሽን ያቀናበረ ሰው ሲሆን፣ በዚህ ድርጊቱ ተይዞ የዕድሜ ልክ እስራት ከተፈረደበት በኋላ አሜሪካ ውስጥ እስር ላይ ይገኛል። ራምዚ ድርጊቱን በማመን ያንን እርምጃ መውሰድ የፈለገው አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠውን እርዳታ እንድታቆም ጫና ለመፍጠር መሆኑን ጠቅሶ ይህንኑ አቋሙን የሚገልጹ ጽሑፎችን ለተለያዩ የኒውዮርክ ጋዜጦች ቀደም ሲል ከመያዙ በፊት መላኩን ተናግሯል። ከዚያ በኋላ በ1995 ራምዚ ፓኪስታን ላይ ተይዞ ወደ አሜሪካ እንዲበር በተደረገበት ጊዜ ለጠፋው የሰው ሕይወት ሁሉ ተጠያቂ መሆኑን ተናዟል። ስቲቭ ኮል የተባሉ ፀሐፊ 'ከጣዕረ ሞት ጋር ትንቅንቅ' (Ghost Wars) ብለው በሰየሙትና በብዛት በተሸጠላቸው መጽሐፋቸው ውስጥ ይህን ጉዳይ አንስተው ሲጽፉ፡- ‹‹ራምዚ ዩሱፍ ላጠፋቸው ነፍሶች ያደረበትን ጸጸት የእስራኤል ወታደሮች ፍልስጤማውያን ንጹሐንን እንዳይገድሉ የማስቆም ፍላጎቱ ጠንክሮ ሲጫነው አስተውያለሁ›› ብለዋል። ኮል በጻፉት መጽሐፍ "የአሜሪካውያን የሆኑ ዒላማዎችን ለይቶ መምታት ይህን ግፍ ለማስቆም ብቸኛው ምርጫ ሲሆን፣ ድርጊቱ ትክክልና ሥነ አመክኖአዊ ነው። ምክንያቱም አሜሪካ በእስራኤል ላይ ያላትን የተዛባ ፖሊሲ እንድታስተካክል የሚያደርጋት ብቸኛው መንገድ ይህን ማድረግ ነውና።" በማለት ራምዚ ዩሱፍ ከፖኪስታን ወደ አሜሪካ በሚበርበት ወቅት ተናዝዟል። ከዚህ የበለጠ የሚያሳስበው ነገር እንደሌለም ገልጿል " ብለዋል። በዚያ የራምዚ ኦፕሬሽን ላይ ተባባሪ ሆኖ የተገኘው ሌላው ሰው አብዱረህማን ያሲን ሲሆን፣ የጋዜጣ ዘጋቢ ለሆነው ሌስሊ ስታህል ሁኔታውን ሲገልጽ፣ "ዩሱፍ የመለመለኝ በፍልስጤማውያንና በሳኡዲ አረቢያ ወንድሞቻችን ላይ የሚፈጸመውን ግፍ የምንበቀለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው በማለት ካስረዳኝ በኋላ ሲሆን፤ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ብዙ ዝርዝር ነገሮችን እየተነተነ ነግሮኛል›› ብሏል።[59]

ሳትሎፍ፣ ዶርሽዊዝ፣ ክራመርና ሌሎችም ከተናገሩት በተጻራሪ ቢን ላደን ገና ከልጅነቱ ጀምሮ የፍልስጤማውያን ጉዳይ ሲያሳዝነው እንደኖረና አሜሪካ እስራኤልን በመርዳቷ የዚያ ሁሉ ግፍ ተባባሪ መሆኗ እያስቆጣው ማደጉን የሚጠቁሙ መረጃዎች ተገኝተዋል። ሚካኤል ስኪወር የተባሉ

በሲ፣አይ፣ኤ. ውስጥ አል-ቃዒዳን የሚከታተለውን ክፍል ሲመሩ የነበሩ ታዋቂ የደህንነት ሰው ‹‹ ኡሳማ ቢን ላደን በብዙ ባሕሪው ጨዋና ቁጥብ ሆኖ ያደገ ልጅ ነው፡፡ ከአንድ ነገር በስተቀርም ይህ ነው የሚባል ውጫዊ እንከን የማይታይበትና የተረጋጋ ሰው ነበር፡፡ ስለ ፍልስጥማውያን ያለው ስሜት ግን በሀዘንና በቁጣ የተሞላ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ እስራኤልንና አሜሪካን ደግሞ በጣም እንዲጠላ አብቅቶታል፡፡››[60] በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከመስከረም 11 ጥቃት በኋላ የኡሳማ እናት ቃለ መጠይቅ ላደረገላቸው ሰው እንዲህ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡- ‹‹ገና ታዳጊ ወጣት እያለ እንደማንኛውም ልጅ ነበር፡፡ የተለዬ ፀባይ አልነበረውም፡፡ ጥሩ ልጅ ነበር፡፡ …. ሆኖም ግን በተለይ በፍልስጤም አካባቢ ባለውና በአጠቃላይ ደግሞ በአረቡና በሙስሊሙ ዓለም ሁኔታ ከሌሎች ልጆች ሁሉ በተለዬ የሚረበሽ፣ የሚያዝንና የሚቆረቆር መሆኑን አውቃለሁ››፡[61]

በተጨማሪም ታኅሣሥ 29/1994 የተለቀቀው የቢን ላደን የመጀመሪያው ለሕዝብ የቀረበ ንግግር ብዙ አድማጮችን በማግኘቱ የሚታወቅና በቀጥታ ስለ ፍልስጤምና ፍልስጤማውያን ብቻ የሚያጠነጥን ነበር፡፡ ብሩስ ላውረንስ የተባሉና ቢን ላደን ለሕዝብ ያደረጋቸውን ንግግሮች መዘግበው የሚያስቀምጡ ሰው “የቢን ላደንን ንግግሮች አንድ በአንድ ለመመርመር እድል ያገኘ ሰው መቼም ቢሆን የፍልስጤምን ጉዳይ ተለዋጭ አጀንዳ አድርጎት እንደማያውቅ መገንዘብ ይችላል” በማለት ሐቁን አስቀምጠውታል፡፡[62]

ቢን ላደን ከመስከረም 11 በፊት በተለያዩ አጋጣሚዎች አሜሪካ ለእስራኤል የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገች በፍልስጤማውያን ላይ ለሚፈጸመው ግፍ ተባባሪ መሆኗን እየጠቀስ ሲያወግዛት መስማት የተለመደ ነበር፡፡ ቤንጃሚንና ስምዖን የተባሉ የፖለቲካ ተንታኞች ቢን ላደን በ1996 ባስተላለፈው ሐይማኖታዊ ብይን (ፈትዋ) (አሜሪካ ሁለቱን የሙስሊም ቅዱሳን ቦታዎች በመያዟ በእሷ ላይ ጦርነት ማወጅን የገለጸበት ፈትዋ) ያሰማው ዋነኛ ቅሬታ የቢን ላደን መለያ ሆኖ የሚታወቀው የጽዮናዊያንና የመስቀለኞች ጸረ-ኢስላም ጥምረት ጉዳይ ነው›› ይላሉ፡፡ እንዲህ ሲሉም

ያክላሉ፡- ‹‹ቢን ላደን በተለይም ደግሞ በፍልስጤምና በኢራቅ የሙስሊሞች ደም በከንቱ መፍሰሱን በመጥቀስ ይህ የአሜሪካና እስራኤል ደባ ውጤት ነው በማለት ተናግሯል፡፡››[63] የሲ.ኤን.ኤን. ቴሌቪዥን ጣቢያ ሪፖርተር ፒተር አርኔት በ1997 አሳማን ለምን በአሜሪካ ላይ ጂሀድ እንዳወጀ ጠይቆት እንዲህ በማለት መልሶለታል፡- ‹‹እኛ በአሜሪካ መንግሥት ላይ ጂሀድ ያወጅነው ፍትሀዊነት የጎደለው፣ ወንጀለኛና አምባገነን በመሆኑ ነው፡፡ አሜሪካ እጅግ ፍትህ የጎደላቸው ድርጊቶችን በተለያዩ ጊዜያት ስትፈጽም ቆይታለች፡፡ ይህን ፍትህ አልባነቷን ደግሞ በቀጥታ ወይም አጋሯ የሆነችውንና የነቢዩን የተዓምራዊው የሌሊት ጉዞ ሀገር (ፍልስጤምን) በኃይል የያዘችውን እስራኤልን በመደገፍ በተደጋጋሚ አሳይታለች፡፡ ዩ.ኤስ. አሜሪካ በፍልስጤም፣ በሊባኖስና በኢራቅ ለፈሰሰው የንፁሐን ደም ሁሉ ተጠያቂ መሆኗን እናምናለን፡፡››[64] እነዚህን ክሶች ለማስተባበል በምንም መልኩ ጥረት ቢደረግ እምብዛም የሚሳካ አይመስልም፡፡ በመካከለኛው ምሥራቅ የኢኮኖሚስት መጽሔት ሪፖርተር ማክስ ሮድንቤክ ስለ ቢን ላደን የተጻፉ ሁለት መጽሐፍትን ሲሐይስ እንዲህ ብሏል፡- ‘‘ ከመጽሐፍቱ ጭብጦች ውስጥ ፍልስጥኤማውያን የተነፈጉትን ፍትህ ስለማስመለስ የሚያወሳው የቢን ላደን ንግግር ክፍል ይበልጥ ጠንካራ መልእክት ያዘለ ነው ማለት ይቻላል፡፡››[65]

የመስከረም 11ዱን ጥቃት የሚያጣራው ኮሚሽን እንዳረጋገጠው ቢን ላደንና ሌሎች የአል-ቃዒዳ ቡድን አባላት ለዚያ ድርጊት ያነሳሳቸው እስራኤል በፍልስጤማውያን ላይ የምትፈጽማቸው ግፎችና አሜሪካም ይህን ግፍ በተለያዩ መንገዶች መደገፏ ነው፡፡ በአጣሪ ኮሚሽኑ መነሻ ጥናት መሠረት ቢን ላደን ጥቃቱን በ2000 መግቢያ ላይ ለማድረግ በማሰብ ጥረቱን ተያይዞት ነበር፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የእስራኤሉ ተቃዋሚ ፓርቲ መሪ አሪዮል ሻሮን የሙስሊሞች ሶስተኛ ቅዱስ ሥፍራ በሆነው በአል አቅሷ መስጊድ ያደረጉት ጸብ ጫሪ ጉብኝት ነበር፡፡ የአጣሪ ኮሚሽኑ ሪፖርት እንደሚያሳዬው ምንም እንኳን የመስከረም 11ዱን ጥቃት የመራው መሐመድ አታና ጓደኞቹ የበረራ ትምህርታቸውን ለመቅሰም ገና ወደ አሜሪካ መግባታቸው መሆኑን ቢን ላደን ቢያውቅም፣ አሜሪካ እስራኤልን

በመደገፏ ምክንያት ለመቅጣት ከፍ ያለ ፍላጎት አደረበት።[66] በቀጣዩ ዓመት ሰኔ ወይም ሐምሌ 2001 ላይ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ሥፍራ የያዙት ሻሮን ለገብኝት ወደ ‹ሁዋይት ሐውስ› እንደሚመጡ ከተለያዩ መገናኛ ብዙሀን የተገነዘበው ቢን ላደን ዘመቻውን አፋጥኖ ለመፈጸም ፍላጎቱ እየጠነከረ ሄደ።[67] ትክክለኛው የአደጋ መጣያ ቀን መስከረም 11/2001 መሆኑ ከታወቀ በኋላ ቢን ላደን፣ አሜሪካ ለእስራኤል በምትሰጠው ያልተቋረጠ ድጋፍ መብገኑን አመላካች ሆኖ የሚወሰደው ለጥቃት የመረጣቸው ቦታዎች ሲታሰቡ ነው። ከአደጋ ጣዩ ቡድን መሪ ጋር የመጀመሪያውን ስብሰባ በ1999 ያደረገው ቢን ላደን የመጀመሪያ ዒላማ እንዲሆን የመረጠው “ካፒቶል ሂል” በመባል የሚታወቀው የኮንግረሱ ሕንፃ ነበር።[68] ምክንያቱም እስራኤልን በመደገፍ የፍልስጤማውያን መከራ እንዲበዛ የሚያደርጉ ፖሊሲዎች የሚወጡት በዚያ ቦታ ውስጥ ነው የሚል ታሳቢን ከግምት ውስጥ በማስገባቱ ነው። በአጭሩ የቢን ላደን እና የተከታዮቹ የአጀንዳቸው ማዕከላዊ ትኩረት የፍልስጥኤም ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል።

የመስከረም 11ዱን ጉዳይ የሚያጣራው ኮሚሽን በተጨማሪ እንደገለጸው የጥቃቱን ዋነኛው መሐንዲስ ካሊድ ሸይኽ ሙሐመድንም ለዚህ ድርጊት ያነሳሳው የፍልስጤማውያን ጉዳይ ነው። ራሱ ካሊድ እንደተናገረውም፣ “ይህን ድርጊት ለመፈጸም የተነሳሳውና በአሜሪካ ላይ የጠላትነት ስሜት ያሳደረበት ነገር እዚያ ተማሪ እያለ ያጋጠመው ጉዳይ ሳይሆን የአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ፣ በተለይም ለእስራኤል የምትሰጠው አድሏዊ ድጋፍ መሆኑን አስምሮበታል።[69] እንግዲህ በአሜሪካ ምድር በመስከረም 11/2001 የደረሰውን ኃያል ዱላ ያነሳሳው አሜሪካ ራሷ የምታራምደው የተዛባ የውጭ ፖሊሲ መሆኑን ለማሳዬት ከእነዚህ ማስረጃዎች የተሻለ ነገር ማቅረብ ይከብዳል።

ምንም እንኳ ቢን ላደን ራሱ በፍልስጤማውያን ጉዳይ በቀጥታ ለመግባት ባይችልም ተዋጊዎቹን (አባላቱን) ለመመልመል የፍልስጤምን ጉዳይ እንደትልቅ ማነቃቂያ መሳሪያ የተገለገለበት መሆኑን ለማወቅ አይከብድም። የአረቡና የሙስሊሙ ዓለም ቁጣ መንደድ የጀመረው ገና የቀዝቃዛው

ጦርነት እንዳበቃ ነበር። በተለይም ደግሞ ሁለተኛው የፍልስጤማውያን ኢንቲፋዳ በ2000 ከፈነዳ በኋላ በፍልስጤማውያን ላይ የሚወሰደው የኃይል እርምጃ እየበዛና እያየለ መሄድ ለዚህ ሁኔታ ትልቁን አስተዋፅኦ አድርጓል።[70] የመጀመሪያው ኢንቲፋዳ (ከ1987-1992) ከሁለተኛው ጋር ሲነፃፀር ደከም ያለና ብዙ አመፅ ያልታየበት ነበር ማለት ይቻላል። በይበልጥም ደግሞ የኦስሎ ስምምነት በሂደት ላይ በነበረባቸው ዓመታት (ከ1993-2000) በኃይል በተያዙት ግዛቶች ውስጥ አንፃራዊ ሰላም ሰፍኖ የነበረ መሆኑ እውነት ነው። ከዚያ በኋላ በቀጠሉት ዓመታት ግን የኢንተርኔት አገልግሎት መስፋፋት፤ እንዲሁም አማራጭ የሆኑ የዜና ማሰራጫ ጣቢያዎች (አልጀዚራን የመሳሰሉት) አገልግሎት መስጠታቸው፤ በዚያ አካባቢ የሚፈፀመውን እልቂት 24 ሰዓት የዓለም ሕዝብ እንዲመለከተው አስችሏል። ያ ሁሉ ግፍና መከራ በፍልስጤም ሕዝብ ላይ የሚወርደው አሜሪካ በሠራችው የጦር መሳሪያና በእርሷ ፈቃድ ጭምር መሆኑና ወረራውን ለማስቆም የምታደርገው ጥረት እዚህ ግባ የሚባል አለመሆኑ፣ እንዲያውም ዝምታን መምረጧ የሕዝቡን ቁጣ ይበልጥ አንሮታል። ይህ ሁሉ ተደማምሮ አሜሪካን ተጠያቂ ለማድረግ ለተሰናዱ ሐይሎች ሁሉ ትልቅ መነሳሻ ሆነላቸው። ከዚህ የተነሳ የሂዝቡላህ ምክትል መሪ ሸይኽ ነኢም ቃሲም በ2006 ታኅሣሥ ወር በሊባኖስ ለተሰበሰበ ሕዝብ የሚከተለውን ንግግር ማድረጋቸው አያስደንቅም፡- ‹‹ከዚህ በኋላ አሜሪካ ሊባኖስ ውስጥ ምንም ዓይነት የፖለቲካ ሥፍራ አይኖራትም። ሀገራችን ሊባኖስ ያን ያክል ዱላ ከእስራኤል ሲወርድባት የቆየው አሜሪካ ሠራሽ በሆነ መሣሪያ መሆኑን አታስታውሱምን?››[71]

እነዚህ ፖሊሲዎች ብዙ አረቦችና ሙስሊሞች በአሜሪካ ለምን እንደሚናደዱና ለምንስ ለአልቃኢዳ የሀዘኔታ ስሜት እንደሚያሳዩ፣ አንዳንዶቹም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለምን ሊደግፉት ፈቃደኛ እንደሚሆኑ በግልጽ ያመለክታሉ። በ2004 በሞሮኮአዊያን ላይ የተደረገ ጥናት እንዳመለከተው ለፕሬዚዳንት ቡሽ ‹‹ጥሩ›› ወይም ‹‹በጣም ጥሩ›› አመለካከት ያላቸው ዜጎች 8 ከመቶ የሚሆኑት ብቻ ሲሆኑ፣ ለቢን ላደን ግን 45 ከመቶ የሚሆኑት አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ተናግረዋል። ቁልፍ

የአሜሪካ ወዳጅ በሆነችው በዮርዳኖስ ደግሞ ይህ የዳሰሳ ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው ለቡሽ አዎንታዊ አስተያየት ያላቸው 3 ከመቶ ሲሆኑ፣ ለቢን ላደን ግን 55 ከመቶ ናቸው። በሌላዋና የአሜሪካ የቅርብ አጋር በሆነችው በፓኪስታን ቢንላደን ቡሽን በ58 ከመቶ የሚሆን ልዩነት ይመራል።[72] ኢራቅ ከመወረሯ በፊት በ2002 የተደረገ ዓለም አቀፋዊ የዳሰሳ ጥናት (Global Survey) እንዳመለከተው በመካከለኛው ምሥራቅ ሕዝቡ ለአሜሪካ ያለው አመለካከት በሚያስደነግጥ ሁኔታ አሉታዊ ሆኖ ተገኝቷል። ለዚህ አመለካከት መውረድ ዋነኛው ምክንያት ደግሞ የፍልስጤም ጉዳይ ነው።[73] እንደመካከለኛው ምሥራቅ ኤክስፐርት ሼብሊ ጠልሃሚ አስተያዬት ‹‹ከፍልስጤም ጉዳይ የበለጠ የአረቡና የሙስሊሙ ዓለም ሕዝብ ድምፁን የሚያስተጋባበት ምንም አይነት ነገር የለም››[74] ኡሳማ መቅዲሲም በዚህ ሀሳብ የሚስማሙ ሲሆን፤ እንዲህ ይላሉ፡- ‘‘አረብ ለሆነ ማንኛውም ሰው ከፍልስጤም ጉዳይ የበለጠ የሚያበግነው ነገር አለ ለማለት ያስቸግራል። በዚህ ጉዳይ ላይ ሴኩላሪስትም ይሁን ሐይማኖተኛው ሁሉም አንጀቱ ቆስሏል። በአሜሪካ የተንሸዋረረ ፖሊሲና በፍልስጥኤም ላይ በምትጫወተው አሉታዊ ሚናዋ አንጀቱ የማይጨስ ማንም የለም።››[75] ዩ.ኤስ. አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠው እርዳታ ብቻ አይደለም በክልሉ ፀረ-አሜሪካዊነት ስሜት እንዲስፋፋ የሚያደርገው። ግና ይህ ዋነኛው ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነው።

ሌሎች መንግስታዊ ጥናቶችና የሕዝብ አስተያየት ውጤቶችም ተመሳሳይ ከሆነ መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል። የአረብ ሕዝቦች በአሜሪካዊያን ሁኔታና በመንግሥታቸው ፖሊሲዎች ሁልጊዜም ግራ ይጋባሉ፣ ይታወካሉ።አሜሪካ እስራኤልን ብቻ ልዩ ወዳጅ አድርጋ በመያዝ ስትረዳት ለመኖር መምረጧ ዓረቦችን በጣም አበሳጭቷል። ለአረብ ሕዝቦች ጥቅሞ ደንታ ቢስ መሆኗንና ለእሴቶቿ የማትገዛ አፈንጋጭ መሆኗንም ያረጋግጥላቸዋል። ምንም እንኳን ብዙ አረቦች ለአሜሪካ ሳይንስና የቴክኖሎጂ ምጥቀት አድናቆት ቢኖራቸውም፣ ለኢንዱስትሪ ውጤቶቿ፣ ለፊልሞቿና ለዲሞክራሲያዊ ባህሏ ለየት ያለ ስሜት ቢያድርባቸውም፣ የውጭ ፖሊሲዋን በተለይም ደግሞ ለእስራኤል የምትሰጠውን ያልተቋረጠ ድጋፍ በጽኑ ይቃወማሉ።[76] አንድ የመናዊ ሐኪም

በ2001 አሜሪካን ጎብኝቶ ሲመለስ እንዲህ ብሏል፡- ‹‹ወደዚያ በሄድክ ጊዜ አሜሪካን በጣም ትወዳታለህ። ... ወደ ሀገርህ ስትመለስ ግን አሜሪካ የፍትህንና የእኩልነትን ማዕድ የዘረጋችው ለራሷ ሕዝቦች ብቻ መሆኑን ትገነዘባለህ›››[77] በፔንታጎን ዲፌንስ ሳይንስ ቦርድ የቀረበ ሪፖርት እንዲህ የሚል መደምደሚያ ይዞ ወጥቶ ነበር፡- ‹‹ሙስሊሞች የሚጠሉት ነፃነታችንን ሳይሆን ፖሊሲዎቻችንን ነው።›› የመስከረም 11ዱን ጥቃት ሲያጣራ የነበረው ኮሚሽን እንዳረጋገጠው፣ ‘‘አሜሪካ የእስራኤል--ፍልስጤምን ግጭት አስመልክታ የምትከተለው ፖሊሲና ኢራቅን የተመለከተው ፖሊሲዋ በአረቡና በሙስሊሙ ዓለም የዕለት ተዕለት የመነጋገሪያ አጀንዳ መሆኑ የማይስተባበል እውነታ ነው’’ ብሏል።[78]

በተመሳሳይ ሁኔታ ዞግቢ ኢንተርናሽናል የተባለ ስመጥርና የተከበረ ድርጅት በስድስት የአረብ ሀገራት እየተዘዋወረ የዳሰሳ ጥናት አድርጎ ነበር። የጥናቱ ዓላማ ሕዝቡ ስለ አሜሪካ ያለው አስተሳሰብ የተቀረጸው ለአሜሪካ እሴቶች ባለው ስሜት ነው ወይስ በፖሊሲዎቿ ባለው እይታ? የሚለውን ማጋገጥ ነበር። እጅግ ብዛት ያለው ሕዝብ ፖሊሲዎቿ ወሳኝ ጉዳዮች መሆናቸውን አረጋግጧል። ለሕዝቡ በቀረበው መጠይቅ ላይ በብዛት የተሰጠው አስተያየት ‹‹መልካም ያልሆነ የውጭ ፖሊሲ’’ የሚል ሲሆን፣ ‹‹ዩናይትድ ስቴትስ ገጽታዋን ለማሳመር ምን ማድረግ ይኖርበታል?›› ለሚለው መጠይቅ በተደጋጋሚ የተሰጠው መልስ፡- “የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲዋን ትቀይር” የሚልና “እስራኤልን መደገፍ ታቁም’’ የሚል ሆኖ ተገኝቷል።[79] የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በአረቡና በመስሊሙ ዓለም የሚኖሩ ሕዝቦችን አመለካከት ለማስተካከል የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ ቡድን እንዲያዋቅርና ወደዚያው እንዲልክ የአሜሪካ ኮንግረስ ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር። የአማካሪዎች ቡድን በተለያዩ የአረብና ሙስሊም ሀገራት የሚኖሩ ሕዝቦችን አስተያየት ከሰበሰበ በኋላ በ2003 የሚከተለውን የማጠቃለያ ሀሳብ በሪፖርቱ መጨረሻ ላይ አሰፈረ፡-- ‹‹በእነዘያ ሀገራት የሚኖሩ ሕዝቦች ባጠቃላይ በፍልስጤማውያን መከራና አሜሪካም በዚያ ምድር ላይ በምትጫወተው ሚና ከልባቸው ያዘኑ መሆኑን ተገንዝበናል።››[80]

እውቅ የአረብ መሪዎችና የሕዝብ ጉዳይ ጥናት ባለሙያዎች እንዳረጋገጡት አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠው ገደብ የለሽ እርዳታ በመካከለኛው ምሥራቅ የምትጠላ ሀገር እንድትሆን አድርጓታል። የተባበሩት መንግሥታትም ልዩ መልዕክተኛና የቡሽ አስተዳደር በ2004 የኢራቅን ሽግግር መንግሥታት እንዲረዱ የሰየማቸው ላክዳር ኢብራሂሚ እንዲህ ብለዋል፡- ‘‘በክልሉ ያለው ታላቅ መርዝ እስራኤል የምትከተለው የተስፋፊነት ፖሊሲና በፍልስጤማውያን ላይ የተጫነባቸው መከራ ነው።’’ በ2004 የግብፁ ፕሬዚዳንት ሆስኒ ሙባረክ ፡- ‹‹አሁን እየታየ ያለው የአሜሪካ ጥላቻ በክልላችን ታይቶ የሚታወቅ አይደለም›› በማለት አስጠንቅቀዋል። ሙባረክ ቀጥለው ሲናገሩ፡- ‘‘ይህ ሊከሰት የቻለው ለእኔ እንደገባኝ በከፊል ኢርዮል ሻሮን ያለማንም ሀይ ባይ የፈለጉትን እንዲሠሩ የተፈቀደላቸው በመሆኑና እንዳሻቸው ሲሆኑ አሜሪካ ምንም ትንፍሽ ባለማለቷ ነው’’ ብለዋል።[81] የዮርዳኖሱ ንጉሥ አብደላህ በ2007 ለአሜሪካ ምክር ቤቶች የጋራ ስብሰባ (Joint Session of Congress) ንግግር ሲያደርጉ እንዲህ ብለዋል፡፡ ‹‹በፍልስጤኤም ምድር ፍትህና ሰላም መጥፋታቸው ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው። ይህ ጉዳይ ደግሞ ለክልላችን ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም የሚተርፍ መዘዝ ማስከተሉ አይቀርም፡፡››[82] ዮርዳኖስና መሰል የአሜሪካ ወዳጅና ደጋፊ መንግሥታት ሳይቀሩ ጦሱ ለነዚህ መንግስታትም የሚተርፈውን የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲያቸውን እንዲቀይሩ አሜሪካውያንን እየወተወቱ መሆናቸው አያስደንቅም።

ተጋፊ መንግሥታትን መጋፈጥ

በተጨማሪም ተጋፊና አምባገነን ከሆኑ፣ ሽብርተኝትን ከሚደግፉና የጅምላ ጨራሽ የጦር መሣሪያ ለመታጠቅ ከሚሞክሩ መንግሥታት ጋር በሚደረገው ትግል እስራኤል ዋነኛ አጋር እንደሆነች አዲሱ ስትራቴጂያዊ ምክንያት ያሳያል። ይህም እንግዲህ "እስራኤል የፀረ- ሽብርተኝነት ዋነኛ አጋር ናት" ከሚለው ምክንያት ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ነገሩን መጀመሪያ ለሚሰማው ሰው የሚያሳምን ይመስላል። እውነትም ሶሪያን፣ ኢራንን ወይም የሳዳም ሁሴንን ኢራቅ የመሳሰሉ ሀገራት ለእስራኤልና ለአሜሪካ ዋነኛ ጠላቶች አይደሉምን? እነዚህ መንግሥታት የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ በመታጠቅ አሜሪካን ከማስፈራራትና መሣሪያውን ለአሸባሪዎች አሳልፈው ከመስጠት ይመለሳሉን? እናም ለእስራኤል በብዛት እርዳታ በማጉረፍ አንድም ራሷን ከእነዚህ አደገኛ የሆኑ መንግሥታት እንድትከላከል አለያም እነዚህ ጨካኝ መንግሥታት እስኪወድቁ ወይም አካሄዳቸውን እስኪያስተካክሉ ደረስ በእነርሱ ላይ ጫና ማድረግ አያስፈልግምን?

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች በጥልቀት የተፈተሹ አለመሆናቸው ግልጽ ነው። ምንም እንኳን አሜሪካ ከእነዚህ ሀገራት ጋር፣ በይበልጥም አሸባሪ ቡድኖችን በመደገፋቸውና የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ለመታጠቅ በሚያደርጉት ግልጽ ጥረት ምክንያት፣ ቅራኔ ውስጥ የገባች መሆኑ ቢታወቅም ሐገራቱ የአሜሪካን ጥቅሞች በቀጥታ ይነካሉ ማለት አይደለም። አሜሪካ እስራኤልን ለመከላከልና እርሷን ለማገዝ ካላት የሁልጊዜ ዝግጁነት ባሻገር ሀገራቱ በራሷ ጥቅሞች ላይ ቀጥተኛ ስጋት ፈጥረውባት አያውቁም። አሜሪካ በመካከለኛው ምሥራቅ ያላት ስትራቴጂያዊ ጥቅም የነዳጅ ዘይት ነው። አካባቢው በአንድ ጠንካራ መንግስት ቁጥጥር ስር እንዳይወድቅ በመከላከል የነዳጅ አቅርቦቱን አስተማማኝ ማድረግ ትችላለች። ስለሆነም ይህ ምክንያት ሊሰራ የሚችለው ከነዚህ ሐገራት መካከል አንዱ አድጎና ጡንቻው ፈርጥሞ ኢራቅ ኩዌትን እንደወረረችው

ዓይነት ወረራ ሲፈጽም ብቻ ነው። ይሁንና እነዚህ ሐገራት በተናጠል ይቅርና በአንድ ቢደመሩ እንኳ ይህን ስጋት ተጨባጭ አያደርጉትም።

አሜሪካ እስራኤልን ለመርዳት ያነሳሳት ሌላው ምክንያት እነዚህ ሐገራት በአምባገነን መንግስታት ስለሚመሩ ነው ሊባል ይችላል። በራሳቸው ሕዝብ ላይ አምባገነን መሆናቸው አሜሪካን ለምን አሳሰባት? ይህ ምክንያት ያስኬዳልን? በፍጹም። ምክንያቱም አሜሪካ ጥቅሞቿ እስከተጠበቁ ድረስ ከሌሎች አምባገነን መንግሥታት ጋር በትብብር መሥራቱን ታውቅበታለችና። ሀገራቱ አሸባሪ ቡድኖችን መደገፋቸውስ ከእርሷ ጋር ጠብ ለማብቀል በቂ ምክንያት ነውን? በእውነቱ አይደለም። ምክንያቱም እነዚህ ሀገራትም ሆኑ እነርሱ ይረዷቸዋል የሚባሉት አሸባሪ ቡድኖች ዩናይትድ ስቴትስንና ጥቅሞቿን ከመጉዳት ተቆጥበው የቆዩ ናቸው። በተጨማሪም እነዚህም ሆኑ ሌሎች ሀገራት ባለፉት ዘመናት አሸባሪነትን ሲያስፋፉ አሜሪካ አይታ እንዳላየች ስትሆን ቆይታለችና። አሜሪካ ልክ እንደማንኛውም ሐገር ጥቅሞቿን ከሚያስጠብቁላት መንግስታት ጋር፣ ስርዓታቸውን ባትወደው እንኳ ተባብራ መስራቷ የተለመደ ነው። ለምሳሌ አሜሪካ በ1980ዎቹ በተደረገው የኢራን - ኢራቅ ጦርነት የሳዳም ሁሴንን ኢራቅ ስትረዳ ቆይታለች። አሁንም ቢሆን የፓኪስታን ወታደራዊ ጁንታ[4] በካሽሚርና የተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ኢስላማዊ አሸባሪ ቡድኖችን እንደሚረዳ የሚያመለክቱ መረጃዎች መኖራቸውን እያወቀች በትብብር መንፈስ አብራው ትሠራለች። ዩናይትድ ስቴትስ ሌላው ቀርቶ ታሊባንን አስመልክቶ ከኢራን ጋር ለመነጋገር ዝግጁነቷን ያሳየች ሲሆን፣ አል-ቃኢዳን የሚመለከቱ መረጃዎችን ደግሞ ከሶሪያ በደስታ ተቀብላለች። እርግጥ ነው ይህ አይነቱ አሠራር የሚከሰተው አልፎ አልፎ ነው ሊባል ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን ከእነዚህ ሁሉ ሀገራት አንዱም በአሜሪካ ጥቅሞች ላይ ስጋት ደቅኖ አያውቅም።

---

[4] ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ፔርቬዝ ሙሻረፍ በነዋዝ ሸሪፍ የሚመራውን በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት አባርረው ሥልጣኑን በመቀማት የወታደራዊ ጁንታ መንግሥት በሚመሩበት ጊዜ መሆኑን ልብ ይሏል። (ተርጓሚው)

ሶሪያ በሊባኖስ ፖለቲካ ጣልቃ ስለመግባቷና ኢራን በፋርስ ባህረ-ሰላጤ በሚገኙ የአሜሪካ ወዳጆች ላይ ስላነሳችው ተግዳሮትስ ምን ለማለት ይቻላል? ይህ ጉዳይ ቀላል ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ሆኖም ግን አሁን አሜሪካ እያደረገችው እንዳለችው ለእስራኤል ጠንካራ ድጋፍ ለመስጠት ምክንያት ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡ እሰራኤል ራሷ በተደጋጋሚ በሊባኖስ ውስጥ ጣልቃ መግባቷ አሜሪካን ያችን ሀገር ለማረጋጋት ያደረገቻቸውን ጥረቶች መና አስቀርቶባታል፡፡ እንዲሁም እስራአል ያከማቸቻቸው ጅምላ ጨራሽ የጦር መሣሪያዎችና በተደጋገሚ ኃይልን ለመጠቀም የምታደርጋቸው ሙከራዎች በአካባቢው የሚገኙ ሌሎች ሀገራትም የራሳቸውን ጅምላ ጨራሽ መሣሪያ እንዲሠሩ ገፋፍቷቸዋል፡፡ እንግዲህ ቀደም ብለን በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደሞከርነው ሁሉ እስራኤል በሊባኖስ መረጋጋት እንዲሰፍንና በባህረ ሰላጤው ሀገራት መካከልም የኃይል መመጣጠን እንዲኖር ለማስቻል ምንም አይነት ስትራቴጂያዊ ጥቅም አትሰጥም፡፡ በዚህ መጽሐፍ ክፍል ሁለት ላይ በሰፊው እንደምንመለከተው ዩ.ኤስ. አሜሪካ በክልሉ ከሚገኙና ችግር ፈጣሪዎች ከሚባሉ ሀገራት ጋር እንዳትነጋገርና መፍትሄዎችን እንዳታመጣ የእስራኤል ሎቢ በተደጋጋሚ እንቅፋት ሲፈጥር ቆይቷል፡፡

ይህ ሁሉ እስራኤልን ለመርዳት የሚቀርብ ምክንያት፣ በተለይም ደግሞ ስትራቴጂያዊ አጋርነቷን ለማጉላት የሚደረገው ጥረት ከንቱ ድካም ከመሆን አይዘልም፡፡ አሜሪካ እነዚህን ተጋፊና አደገኛ ሀገራት አደብ ለማስያዝ ለምታደርገው ጥረት እስራኤል ጠቃሚ አገር ተደርጋ መቅረቧም ተገቢ ምክንያት አይደለም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሐገራት ለአሜሪካ እንደ ስጋት ምንጭ ተደርገው የተወሰዱበት ሁኔታ በዋነኛነት በእስራኤል ላይ ሊያደርሱት ከሚችሉት ጉዳት አኳያ እንጅ የአሜሪካን ጥቅሞች ታሳቢ ያደረገ አይደለም፡፡ የአሜሪካ ፖሊሲዎች ለእስራኤል ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት አባዜ ባይተበተቡ ኖሮ ከነዚህ ሐገሮች ጋር የሚኖራትን ችግር በቀላሉ መፍታት በቻለች ነበር፡፡ ይህም ሆኖ እነዚህ ሐገራት አሁን ባሉበት ሁኔታ አሜሪካን ትርጉም ባለው መልኩ ለመጉዳት የሚችሉበት አቅም

የላቸውም፡፡ በተጨማሪም አሜሪካ በእነዚያ ሀገራት ላይ እርምጃዎችን ለመውሰድ ብትገደድ እንኳ ለነዚህ እርምጃዎች እስራኤል አታስፈልጋትም፡፡

አሜሪካ በአካባቢው የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ከእነዚያ ሀገራት በአንዷ እጅ ይገባል የሚል ስጋት ቢኖራት እንኳን፣ አሁን እንደምታደርገው እስራኤልን በሁለንተናዊ መልኩ ነጥላ እንድታግዝ ምክንያት ሊሆናት አይገባም፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ በመካከለኛው ምሥራቅ እና በሌሎችም አካባቢዎች የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ እንዳይስፋፋ የምትፈልግበት የራሷ ምክንያት ሊኖራት ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ይህ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ከእነዚያ ሀገራት መካከል በአንዳቸው እጅ ቢገባ እንኳ ለአሜሪካ ስትራቴጂያዊ ኪሳራ ሊሆንባት አይችልም፡፡ እውነቱን ለመናገር የሳዳም ኢራቅና አሁን ደግሞ ኢራን ‹‹ለሰላማዊ አገልግሎት›› በሚል ሽፋን የሚያንጹትን የአቶሚክ ኃይል ለማስቆም አሜሪካ የምታደርጋቸው ግፊቶች ሁሉ ያለሙት እስራኤልን ከአደጋ ከመታደግ አንጻር እንጅ ከአሜሪካ ስትራቴጂያዊ ጥቅሞች አኳያ አይደለም፡፡ ፕሬዚዳንት ቡሽ ይህን እውነታ መጋቢት 2006 ላይ ያለምንም ማድበስበስ እንዲህ በማለት ገልጸውታል፡- ‹‹ከኢራናውያን በኩል የተደቀነብን ስጋት ጠንካራዋን ወዳጃችንን እስራኤልን ለማውደም ያለሙ መሆናቸው ነው፡፡››[83]

በተጨማሪም እስራኤልም ሆነች አሜሪካ የራሳቸው የኑክሌር ኃይል ያላቸው መሆኑ ይህን ስጋት የተጋነነ ያደርገዋል፡፡ አሜሪካንም ሆነ እስራኤልን በጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ለማጥቃት መሞከር የማይታሰብ ነው፡፡ ምክንያቱም አሜሪካ በሺዎች፤ እስራኤልም ምናልባት በመቶዎች የሚቆጠሩ ጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎችን ታጥቀዋልና፡፡ ከሁለቱ ሀገራት እንዳቸው በዚህ መሣሪያ ከተጠቁ፣ ወንጀለኛው ወዲያውኑ አስደንጋጭና እጅግ አውዳሚ ብቀላ የሚፈጸምበት መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ስለሆነም ሁለቱም ሀገራት የኑክሌር ቃታ በጨበጡ ጠብ ጫሪ መንግሥታት ማስፈራሪያ ሊደረግባቸው አይችልም፡፡ ሶቪዬት ሕብረት በቀዝቃዛው ጦርነት ጊዜ በሺዎች የሚቆጠሩ የኑክሌር አረሮችን አምርታ በማከማቸት በአብዮታዊው ፍልስፍና በሚመሩና ለሰው ሕይወት ደንታ በሌላቸው ሰዎች እጅ አስገብታ ነበር፡፡ ያም ሆኖ ሞስኮ በዚያ የኑክሌር መሣሪያ አሜሪካን ለማስፈራራት አልደፈረችም፡፡

ስታሊን፣ ክሩስቾቭም ሆኑ ብረዠኔቭ ይህን ለማድረግ ፈጽሞ አልሞከሩም። ምክንያቱ ግልጽ ነው። ዩናይትድ ስቴትስም ያንኑ የሚያክል የራሷ የሆነ መሣሪያ በመታጠቋና ከተኳች መበቀሏ እንደማይቀር ስለሚታወቅ።

ከእነዚያ ጠብ ጫሪ ከሚባሉ መንግሥታት አንዳቸው ከኑክሌር መሣሪያዎቻቸው አንዱን ወይም የተወሰኑትን ለአሸባሪ ቡድናት ይሰጣሉ የሚለው ስጋትም እንዲሁ እምብዛም የሚያሳስብ አይደለም። ምክንያቱም ይህን የሚያደርጉ የሀገር መሪዎች ድርጊታቸው የማይደረስበት ወይም በፈጸሙት ወንጀል የማይጠየቁ ስለመሆናቸው ከቶም እርግጠኛ ሊሆኑ አይችሉምና። በእርግጥም የኑክሌር መሣሪያን ኃላፊነት ለማይሰማቸው ቡድኖች አሳልፎ መስጠት እነዚህ ሀገራት ሊሠሩት ከሚችሉት እጅግ የከፋው ወንጀል ነው። አንድ ጊዜ መሣሪያውን አሳልፈው ከሰጡ በኋላ ደግሞ በምን አኳኋንና በማን ላይ ጥቃት ሊፈጸምበት እንደሚችል የሚቆጣጠሩበት ምንም አይነት መንገድ የላቸውም። እንዲሁም ዩናይትድ ስቴትስ እና እስራኤል እነዚያ ሀገራት ለፈጸሙት ወንጀል ተመጣጣኝ ቅጣት ሊቀጧቸው እንደሚችሉም ሳይታለም የተፈታ ነው። እዚህ ላይ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ አለ። ይኸውም አሜሪካ ኑክሌር ከታጠቀችው ሶቪዬት ሕብረት ወይም ከቻይና ጋር መኖር (የእነዚህ ሀገራት መሪዎች የታወቁ የጅምላ ፍጅቶችን ያካሄዱ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ)፣ እንዲሁም ከባለ ኒኩሌሮቹ ፓኪስታንና ሕንድ ጋር ተስማምታ መዝለቅ ከቻለች፣ ኒኩሌር ከታጠቀችው ኢራን ጋር (ጉዳዩን የማትፈልገውም ቢሆን) መኖር የሚሳናት አይሆንም።

እነዚህን ሀገራት ማስፈራራቱ ውጤት ሊያመጣ አይችልም ሲባል አልፎ አልፎ ይደመጣል። ምክንያቱም መሪዎቻቸው (ለምሳሌ አጥባቂ ሐይማኖተኛ የኢራኑን ፕሬዚዳንት ማህሙድ አህመዲን ኤጃድ) አንዳች ጉዳት ለማድረስ የማይመለሱና በሂደቱም ሰማዕት ለመሆን ጭምር ፍላጎት ያላቸው ስለሆኑ ነው። እንደ ዋሽንግተን ፖስቱ ቻርለስ ክራውታመር አገላለጽ ከሆነ ‹‹ሃይማኖት አጥባቂዎች ሞትንም ቢሆን በደስታ ለመቀበል የተዘጋጁ በመሆናቸው በነርሱ ላይ የሚደረግ ማንኛውም አይነት ጫና የሚፈለገውን ውጤት አያመጣም።››[84] በእርግጥ እንዲህ ዓይነት እብደት የሚፈጽም መሪ

የለም ብሎ መቶ በመቶ መደምደም አይቻል ይሆናል። እንደዚያም ቢሆን ግን እብደት ከተጠናወታቸው መሪዎች አንዱም ቢሆን የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ በሌላ ሀገር ላይ ይተኩሳል ተብሎ አይታሰብም። ምክንያቱም አጸፋውን የሚቀበሉና የሰማዕታትን ክብር ለመጎናጸፍ በሙሉ ልብ ድጋፍ የሚሰጡ ሌሎች ሰዎች በዙሪያው ያስፈልጉታልና። (ለዚያውም ቢሆን ለምሳሌ በኢራን ያለውን ሁኔታ ካየን ወታደራዊው ሥልጣን የሚገኘው በፕሬዚዳንቱ በአህመዲን ኤጃድ እጅ እንዳልሆነ ይታወቃል።) ሁኔታውን በሌላ አቅጣጫ ካየነው ደግሞ እንዲህ አይነት መሪዎች ይዜን የመሰለ ሰማዕት የመሆን ፍላጎት በትክክል እንዳላቸው ማረጋገጫ ማግኘት አይቻልም። (ሳዳም ሁሴንን ብንወስድ የሰማእትነት ፍቅር እንዳልነበራቸው ታይቷል። ምክንያቱም ገመዱ አንገታቸው ላይ እስኪጠለቅባቸው ድረስ ያደረጉት ነገር አልነበረም።)

በመጨረሻም ተመሳሳይ ስጋቶች በየጊዜው እንደሚነሱና የኋላ ኋላ ግን የተሳሳቱ ሆነው እንደሚገኙ ማወቁ ተገቢ ነው። በዩ.ኤስ. አሜሪካ የሚገኙና ጠጣሩን መስመር የሚከተሉ ፖለቲከኞች የሶቪዬት መሪዎች በሚከተሉት ርዕዮተ ዓለም ምክንያት ለሰብአዊው ፍጡር ያላቸው ንቀት ከፍ ያለ በመሆኑ በዚህ አንፃር አደጋ ሊደቅኑ ይችላሉ የሚል ስጋት ነበራቸው። ሌሎቹ የአሜሪካ መሪዎች ደግሞ ይፈሩ የነበሩት የቻይናን የኒኩሊየር ባለቤትነት ነው። ምክንያቱም ማኦ ዚዱንግ አፈንጋጭ ባህሪ የነበራቸው ሰው ስለነበሩ ምናልባት አንድ ወቅት ደስ ያላቸውን ነገር በዚያ መሣሪያ ፈጽመው በአስር ሚሊዮኖች የሚሆኑ ሰዎችን ለታላቅ አደጋ ይዳርጉ ይሆናል ብለው በማሰባቸው ነው። ይህ አይነት ስጋት ካደረባቸው የአሜሪካ ፖለቲከኞች አንዱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዲን ሩስክ ሲሆኑ፣ ቻይናን አስመልክተው እንደሚከተለው በማለት ተናግረዋል። " ቻይናን የመሰለ ተጋፊ፣ ጠብ ጫሪ፣ አይበገሬና ጉልበተኛ መንግሥት ተምኔታዊ በሆነና ሊጨበጥ በማይችል ርዕዮተ ዓለም በሚመራ ሰው እጅ መውደቁ በሁሉም መልኩ ሲታይ የስጋት ምንጭ መሆኑ አይቀሬ ነው።" ይሁን እንጂ የቻይና የኒኩሌር ባለቤትነት ገጽታ ከዚህ አስተሳሰብ በተቃራኒው ሆኖ ነው የተገኘው። ቻይና የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎቿን በተመለከተ ባልተጠበቀ

ሁኔታ አርቆ አሳቢነትና ጨዋነት የሚታይበት ምግባርን ነበር መከተል የመረጠችው።[85] በጥቅሉ የዩ.ኤስ. አሜሪካ መሪዎች በመካከለኛው ምሥራቅ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች እንዲስፋፉ አለመፈለጋቸው ተገቢ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ አሁን አሜሪካ እያደረገችው እንዳለው እስራኤልን በሰፊው ለመርዳት የሚያበቃ በቂ ምክንያት ሆኖ ሊቀርብ አይችልም ። አይገባውምም።

ሶሪያና ኢራን በሊባኖስ፣ ዮርዳኖስና መሰል ቦታዎች ዩናይትድ ስቴትስን የሚፈታተን አደጋ ቢደግኑም እንኳ፣ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ቢኖራቸውና ወይም ለመታጠቅ ቢፈልጉም እንኳ አሜሪካ ከእስራኤል ጋር ያላት ጥብቅ ትስስር ከእነርሱ ጋር የተያያዙ አጀንዳዎችን በወጉ እንዳትፈታ እንቅፋት ይሆንባት እንደሁ እንጅ አይፈይዳትም። በተደጋጋሚ እንደተጠቀሰው የእስራኤል የኒኩሌር መሣሪያ ባለቤት መሆን ጎረቤቶቿም መሣሪያውን እንዲታጠቁ የገፋፋቸው ሲሆን፣ አሜሪካ እነዚያን መንግሥታት ለመቀየር የምታደርገው ዛቻም መሣሪያውን ለመታጠቅ የጀመሩትን ጥረት የበለጠ አጠናክረው እንዲቀጥሉበት እያደረጋቸው ይገኛል። እስራኤል የኒኩሌር ቃታ መጨበጧንና ይህንኑም በአቶሚክ ኃይል መርማሪ ቡድን ለማስፈተሽ ፈቃደኛ አለመሆኗን እያወቀች አሜሪካ ልትደግፋት መፍቀዷ ፖለቲካዊ መናፍቅነት የሚያጠቃት ሀገር የመሆኗ ነገር ጎልቶ እንዲወጣ አድርጎታል። ምክንያቱም ወዳጇን እስራኤልን አይታ አንዳላዬች ስታልፍ ሌሎቹን ግን ፋታ በሚነሳ መልኩ ጓዳ ጎድጓዳቸውን ታስበረብራለች። ይህ እንዳለ ሆኖ ዋሽንግተን ከእነዚህ አገራት ጋር ጦርነት በገጠመች ጊዜም (በኢራቅ ይህ ሁኔታ ለሁለት ጊዜያት ያክል ተከስቷል) እስራኤል የአሜሪካ ጠቃሚ ስትራቴጂያዊ አጋር አለመሆኗ በሚገባ ተስተውሏል።

በምዕራፍ አንድ ላይ እንደተጠቀሰው የዓለም ሕዝብ፣ ዩናይትድ ስቴትስ እጅግ አድሏዊና ጭፍን የእስራኤል ደጋፊ መሆኗን በተደጋጋሚ ታዝቧል። እንዲሁም ብዙ የውጭ ምሁራን እስራኤል በኃይል በያዘቻቸው የአረብ መሬቶች ያሻትን ግፍ ስትፈጽም አሜሪካ ዝም ብላ መመልከቷ ሞራል የጎደለው አሠራር መሆኑን እየጠቀሱ እንዲነቅፉአት መንገድ ከፍቶላቸዋል። በመጋቢት 2004 ለምሳሌ 52 የሚሆኑ የብሪታኒያ የቀድሞ ዲፕሎማቶች

ለቶኒ ብሊዬር በጻፉት ደብዳቤ፡- ‹‹በእስራኤልና በፍልስጤማውያን መካከል ያለው ግጭት በምዕራቡና በሙስሊሙ (አረቡ) ዓለም መካከል ያለውን ግንኙነት መርዞታል ›› በማለት የገለጹ ሲሆን፣ በቡሽና በሻሮን መካከል የሚስተዋለው ግንኙነት ወደ አንድ ወገን ያደላና ሕገ-ወጥ በመሆኑ ለወደፊቱም ገና ብዙ የእስራኤላውያንና ፍልስጤማውያንን ደም እንደሚጠይቅ ጨምረው በመግለጽ አስጠንቅቀዋል። ይህን የተረዱት ቶኒ ብሌየር የቡሽ አስተዳደር ጉዳዩን በጥልቅ እንዲያስብበት ከመጎትጎት (ምንም ያክል ባይሳካላቸው) ወደኋላ ብለው አያውቁም። የእንግሊዛውያን ዲፕሎማቶችን ጥረት የተመለከቱ ሰማኒያ ስምንት የሚሆኑ የቀድሞ የዩናይትድ ስቴትስ ዲፕሎማቶችም በተራቸው የቡሽ አስተዳደር ጉዳዩን በበለጠ ፖለቲካዊ ቅንነት እንዲመለከተው የሚያሳስብ ደብዳቤ ጽፈው ለፕሬዚዳንት ቡሽ ሰጥተዋል።[86] ሌላው ቀርቶ የቀድሞ ወታደራዊ ዘመቻና ዜና አጠናቃሪ ዜቭ ስኬቭን የመሰሉ እውቅ እስራኤላውያን ጭምር ‹‹የዚህ ግጭት መባባስና እስራኤል ወረራዋን አፋፍማ መቀጠሏ አሜሪካ በጣም ወደምትፈራውና አዲስ ወደሆነ የሁከት ማዕበል፣ እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ሽብር ፈጠራ ሊያመራ ይችላል›› በማለት አሰጠንቅቀዋቸዋል።[87]

የዚህ ሁሉ ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ ውጤት በ2006 ዩናይትድ ስቴትስ በኢራቅ እየተባባሰ የሄደውን ሁኔታ ለማስተካከልና እያንሰራራች ያለችውን ኢራንን ለመግታት የሱኒ ኃይሎችን ትብብር በጠየቀችበት ጊዜ ግልጽ ሆኗል። አሜሪካ የፈለገችውን እንዳያደርጉላት የሱኒ ኃይላትን ያገዳቸው አሜሪካ ሁልጊዜም ከእስራኤል ጎን የምትቆም ከመሆኗ አኳያ ከእርሷ ጋር መወገን የሚያስከትለውን አደገኛ ፖለቲካዊ መገለል መፍራታቸው ነው። በዎል ስትሪት ጆርናል ዘገባ መሠረት የአረብ ዲፕሎማቶች፣ ሳውዲ አረቢያ፣ ግብጽ ኳታር፣ ኩዌትና የተባበሩት አረብ ኢሚሬት አሜሪካ በኢራንና በክልሉ ባሉ ፖለቲካዊ ትኩሳቶች ውስጥ የምታደርገውን ጣልቃ ገብነት በይፋ ለመደገፍ ይቸገራሉ። አሜሪካ ያን እንዲያደርጉ ከፈለገች እስራኤል ወደሰላም ጠረጴዛ እንድትመጣ ግፊት ማድረግ አለባት። ወይም ደግሞ አንድ የአረብ ዲፕሎማት ቀለል ባለ መንገድ እንደሚከተለው ያስቀመጡትን ሃቅ መቀበሉ ለምርጫ የሚቀል ይመስላል፡- ‹‹ወደ ባግዳድ

የሚወስደው መንገድ የሚያልፈው በቀጥታ በቴሌአቪቭ በኩል ነው፡፡››[88] ለዚህም ነው የኢራቅ የጋር ጥናት ቡድኖች በ2006 ታህሣሥ ላይ ከሚከተለው መደምደሚያ ላይ የደረሱት፡- “ዩናይትድ ስቴትስ የአረብ እስራኤልን ውዝግብ እስካልፈታች ድረስ በመካከለኛው ምሥራቅ የነደፈቻቸውን እቅዶች ማሳካት አትችልም፡፡››[89]

በአጭር አነጋገር በሽብርተኝነትና በመካከለኛው ምሥረቅ አምባገነን መንግስታት ላይ በሚወሰደው እርምጃ እስራኤልን የአሜሪካ ጠቃሚ አጋር አድርጎ መውሰዱ የእስራኤልን ችሎታ ያላገነዘበና የተጋነነ ነው፡፡ በተጨማሪም የሁለቱ ሀገራት ጥብቅ ትስስር ከላይ የተጠቀሱ ችግሮችን ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶችን በማወሳሰብ የሚጫወተውን አሉታዊ ሚና ያላገናዘበ ምልከታ ነው፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለጸው የእስራኤል ስትራቴጂያዊ አጋርነት ከቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም በኋላ እጅግ በሚያስደንቅ አኳኋን እያሽቆለቆለ ሄዷል፡፡ ስለሆነም አሜሪካ እስራኤልን በመርዳት መጽናቷ የተጋረጡባትን አደጋዎች ለማስወገድ ያግዛታል የሚለውን የቀድሞ አባባል መጣል የሚገባበት ሰዓት አሁን ነው፡፡ እንዲያውም በአገልባጩ እስራኤልን መርዳት ዩናይትድ ስቴትስን እዚህም እዚያም እንደሚታዩው ለሃይማኖት መሠረተኞች ርህራሄ የሌለው የበቀል ዱላ እየዳረጋት ይገኛል። እንዲሁም አሜሪካ በአውሮፓና በአረብ አጋሮቿ፣ እንዲሁም በሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ዓይን ጨካኝና መናፍቅ ተደርጋ እንድትታይ ያደርጋታል፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ ከተለያዩ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች አንፃር ከእስራኤል ጋር ወደፊትም መደጋገፏ አይቀር ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን እስራኤል ለአሜሪካ ከአጋርነቷ ይልቅ እዳነቷ የሚያመዝን የመሆኑን መሪር ሃቅ መቀበል አለባት፡፡

የማትታመን አጋር

የእስራኤልን ስትራቴጂያዊ አጋርነት ጥያቄ ውስጥ የሚጥለው ሌላው ምክንያት እንደታማኝ አጋር ሆና የማትገኝባቸው አጋጣሚዎች ስለሚከሰቱ ነው። ልክ እንደሌሎቹ ሀገራት ሁሉ እስራኤልም የራሷን ጥቅም ታስቀድማለች። በመሆኑም ብሄራዊ ጥቅሜን ያስከብርልኛል ብላ ያመነችባቸውን ማናቸውም ዓይነት እርምጃዎች ከአሜሪካ ጥቅሞች ጋር የሚጋጩ ቢሆንም እንኳ ከመውሰድ ወደኋላ አትልም። ለምሳሌ በ1954 አንድ የእስራኤል ሰላይ ግብጽንና አሜሪካን ለማጋጨት በማሰብ በግብጽ አገር የሚገኙ በርካታ የአሜሪካ መንግሥት ቢሮዎችን በቦምብ ለማጋዬት ሞክሯል። በኢራን አብዮት ጊዜ የዩናይትድ ስቴትስ ዲፕሎማቶች ከ1979 - 80 በቴህራን ታግተው እያለ እስራኤል ለኢራን የጦር መሣሪያ ትሸጥ ነበር። እንዲሁም በኢራንና ኢራቅ መካከል በተደረገው ጦርነት ዩናይትድ ስቴትስ የኢራንን ሁኔታ እየፈራች በነበረችበትና ኢራቅን ድምጿን አጥፍታ በምትረዳበት ሰዓት እስራኤል ዋነኛዋ የኢራን መሣሪያ አቀባይ ነበረች። በ1989 ደግሞ እስራኤል በሊባኖስ የታገቱባትን ዜጉቿን ለማስለቀቅ የ36 ሚሊዮን ዶላር ነዳጅ ከኢራን ገዝታለች። እነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴዎች ለእስራኤል ስሜት የሚሰጧት ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ግን የዋነኛዋ አጋሯን የአሜሪካን ፖሊሲዎች የሚፃረሩና ጥቅሞቿንም የሚጎዱ ነበሩ።[90]

እስራኤል ለአሜሪካ ጠላቶች መሣሪያ ከመሸጧም በተጨማሪ የአሜሪካን ቴክኖሎጂ፣ የወደፊቷን የአሜሪካ እምቅ ተፎካካሪና ባለጋራ (Potential Enemy) ቻይናን ጨምሮ ለሌሎች ሶስተኛ ሀገሮች አሳልፋ ሰጥታለች። በ1992 የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ተቆጣጣሪ ባቀረበው ዘገባ መሠረት ‹‹ከ1983 ጀምሮ ያለ አሜሪካ መንግሥት ፈቃድና እውቅና እስራኤል ስልታዊና እያደገ የሄደ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለተለያዩ ሀገራት አስተላልፋለች።››[91] በተመሳሳይ ሁኔታ "የዶታን አፊር" በመባል የሚታወቀውንና (ከዩ.ኤስ.አሜሪካ ለእስራኤል የተሰጠውን በሚሊዮኖች የሚቆጠር ወታደራዊ እርዳታ በተለያዩ ዘዴዎች ለራሱ ጥቅም ያዋለውን የእስራኤል አየር ኃይል ባለሥልጣን ድርጊት) የአሜሪካ ጠቅላይ ምርመራ ቢሮ እየተከታተለው ነበር።[92] (ድርጊቱ ምናልባትም ከሌሎች ሀገራት ጋርም ንክኪ ሊኖረው ይችላል።)

እስራኤል ይህን ባህሪዋን እስከቅርብ ዓመታት ድረስ አልቀየረችም ማለት ይቻላል። ለአብነት ያክል ቀደም ሲል በ1994 ለቻይና ሽጣላት የነበረውን ድምፅ አልባ አውሮፕላን ደረጃውን ለማሻሻል በ2004 መስማማቷ ጽኑ ደጋፊዋ የነበሩትን የቀድሞው የፔንጋጎን ባለሥልጣን ዶግላስ ፊይዝን ሳይቀር አበሳጭቷል።[93] እንዲሁም "በዩ.ኤስ. አሜሪካ-እስራኤል ወታደራዊ ግንኙነት ውስጥ አንድ መጥፎ ነገር እየተካሄደ ነው›› በማለት አንድ የቡሽ አስተዳደር ፖለቲከኛ ክስተቱን ተችተዋል።[94]

በሁለቱ ሀገራት መካከል የተነሳውን ይህን ውጥረት የበለጠ ያባባሰው ነገር ደግሞ እስራኤል በዩናይትድ ስቴትስ ላይ በስፋት የምትፈጽማቸው የስለላ ተግባራት ናቸው። ዲ.ኤ.ኦ. የተባለው ድርጅት እንደዘገበው ከሆነ ‹‹አይሁዳዊቷ ሀገር ከማንኛውም የአሜሪካ አጋር የሆነ አገር በማይጠበቅ ሁኔታ በመላዋ ዩናይትድ ስቴትስ እጅግ ስፋትና ጥልቅ ያለው የስለላ ተግባር ታከናውናለች"[95] ኢኮኖሚያዊ ምስጢሮችን መሥረቅ የእስራኤል ድርጅቶች በዓለም አቀፉ ገበያ የአሜሪካ አቻዎቻቸውን በልጠውና ተሸለው እንዲገኙ ስለሚያደርግ በአሜሪካ ግብር ከፋይ ሕዝብ ላይ ተጨማሪ ወጪዎችን እያስከተለ ይገኛል።

ከሁሉም በላይ የሚያስጨንቀው ግን እስራኤል የአሜሪካን ወታደራዊ ምስጢሮች ለመስረቅ የምታደርገው ያላሰለሰ ጥረት ነው። ይህ ችግር ይበልጥ የጎላው ጆናታን ፖላርድ የተባለው የአሜሪካ ስለላ አገልግሎት የመረጃ ባለሙያ ከ1981–85 በነበሩት ዓመታት ታላቅ የሚባሉ የአሜሪካ ወታደራዊ ምስጢራትን ለእስራኤል ሲያቀብል መኖሩ ከታወቀ በኋላ ነበር። ፖላርድ ከተያዘ በኋላ እስራኤል እርሱ ሲያቀብላት የኖረውን ምስጢራት ለአሜሪካ ለመግለጽ ፈቃደኛ ሆና አልተገኘችም።[96] የፓላርድ ሁኔታ በበረዶ ከተሸፈነው ተራራ በዓይን በሚታዬው ኢምንት ክፍል ሊመሰል ይችላል። የእስራኤል የስለላ ወኪሎች በ1986 ከአንድ የአሜሪካ የስለላ ካሜራ አምራች ኩባንያ የካሜራውን ቴክኒዮሎጂ በምስጢር ለመመንተፍ ሲሞክሩ ተይዘዋል። በኋላ ላይ እስራኤልን ከኩባንያው ለማስታረቅ የተሰየመው ቡድን እስራኤልን ‹‹አታላይ››፣ ‹‹ሸፍጠኛ›› እና ‹‹ምስጢር መንታፊ›› በማለት ያሳየችውን ባህሪ ኮነኑ ጥቃቱ ለደረሰበት ድርጅት የ3 ሚሊዮን ዶላር ካሣ እንድትከፍል ወስኗል። የእስራኤል ሰላዮች የፔንታጎንን

ኤሌክትሮኒክ መርሐ-ግብር መረጃዎች ለመስረቅ በነበራቸው ጉጉት ‹‹ኒኦል ኮች›› የተባለውን በመከላከያ ሚኒስቴር ሲኒዩር የፀረ ሽብር ባለሙያ ለመመልመል ያልተሳካ ሙከራ አድርገዋል፡፡ ይህን መዘዘኛ ጉዳይ አስመልክቶ ጆን ዳቪት የተባሉት የቀድሞው የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር የውስጥ ደህንነት ክፍል አዛዥር የሚከተለውን ማለታቸውን ዎል ስትሪት አስነብቧል፡- ‘‘ዩናይትድ ስቴትስን በመሰለል እስራኤል ሁለተኛዋ አገር እንደሆነች እኛ የደህንነት ሰዎች እናምናለን።’’[97]

ሌላው አወዛጋቢ ጉዳይ የፈነዳው ደግሞ በ2004 ላይ ሲሆን፣ ይህም የተከሰተው ቁልፍ የፔንታጎን ኃላፊ የነበረው ላሪ ፍራንክሊን ዩናይትድ ስቴትስ ከኢራን አኳያ የምታራምደውን ፖሊሲ በተመለከተ ለአንድ የእስራኤል ዲፕሎማት የተለያዩ መረጃዎችን ማቀበሉ በተረጋገጠ ጊዜ ነበር፡፡ ላሪ ይህን ድርጊት እንዲፈጽም የአሜሪካ እስራኤል ሕዝብ ጉዳይ ኮሚቴ (አይፓክ) ከፍተኛ ኃላፊዎች የሆኑት ስቲቭን ሮስን እና ኬዝ ዋይስማን የተባበሩት መሆናቸው በመታወቁ ተጠያቂዎች ሆነዋል፡፡ በመጨረሻም ፍራንክሊን ያቀረባቸው አንዳንድ ተማጽኖዎች እግምት ውስጥ ገብተው በ12 ዓመታት እስራት እንዲቀጣ ተወስኖበታል፡፡ ሮስንና ዋይዝማን ደግሞ በ2007 ማብቂያ ላይ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ቀጠሮ ተይዞላቸዋል፡፡[98]

ዩናይትድ ስቴትስን ለመሰለል እስራኤል ብቸኛ አገር አይደለችም፡፡ ራሷ ዋሽንግተንም ብትሆን ወዳጆቿንም ሆነ ጠላቶቿን ለመሰለል ሰፊ መዋቅር ዘርግታለች፡፡ በእርግጥ እንዲህ ዓይነቱ ባህሪ የሚያስደንቅ ወይም የሚያስከፋ ሆኖ አይታይም፡፡ ምክንያቱም ዓለም አቀፉ ፖለቲካ ጋጠ-ወጥነት የሚታይበት፣ ይሉኝታ የሌለውና በጭካኔ የተሞላ እየሆነ ሄዷል፡፡ ማሳየት የተፈለገው በዋሽንግተንና ቴሌአቪቭ መካከል ያለው ልቅ ግንኙነት እስራኤል የአሜሪካን ምስጢሮች በቀላሉ እንድትዘርፍ ሁኔታዎችን አመቺ ያደረገላት መሆኑን ነው፡፡ እርሷም አጋጣሚውን ከመጠቀም የምታመነታ አይደለችም፡፡ ይህን ሁሉ ስንመለከትና እስራኤል ዋነኛ ባለውለታዋ የሆነችውን አሜሪካን ለመሰለል አይኗን የማታሽ መሆኑ ሲታይ የአሜሪካ ስትራቴጂያዊ አጋርነቷ ጥያቄ ውስጥ ይወድቃል። በተለይም ቀዝቃዛው ጦርነት ባበቃበት በአሁኑ ጊዜ፡፡

ምዕራፍ ሶስት

እየመነመነ የሄደ የሞራል ምክንያት

ጆርጅ ደብሊው ቡሽ በ2004 በተደረገው የአሜሪካ- እስራኤል ሕዝብ ጉዳይ ኮሚቴ (አይፓክ) ዓመታዊ ስብሰባ ላይ እስራኤልን ለመርዳት የሚያበቁ የሞራል ግዴታዎችን እየዘረዘሩ ለማብራራት ሞክረው ነበር፡፡ ኘሬዝዳንቱ ንግግራቸውን የጀመሩት አይፓክ የሁለቱን ሐገሮች ሕዝቦች ትስስር፣ የጋራ እሴቶችና ለነጻነት ያላቸውን ጽኑ ፍላጎት ለማጠናከር የሚያደርገውን ጥረት በማድነቅ ነበር፡፡ በመቀጠልም እንዲህ አሉ፡- ‹‹የምንጋራቸው ነገሮች ብዙ ሆነዋል፡፡ ….. ሁላችንም የተወለድነው ከትግልና ከመስዋዕትነት ማሕጸን ነው፡፡ አሜሪካና እስራኤል የተፈጠሩት በየምድራቸው ኃይማኖታዊ ጭቆናን እየሸሹ በተሰደዱ ሕዝቦች ነው። ሁላችንም በሕግ የሚመራና ነፃ ገበያን ያቀፈ አንፀባራቂ ዲሞክራሲ ባለቤቶች ነን፡፡ የሁለታችንም ሀገራት በተመሳሳይ መሠረታዊ እምነቶች ላይ የተገነቡ ሲሆኑ፣ እነርሱም፡- "አምላክ የሰውን ልጅ ጉዳዮችና የእያንዳንዷን ሕይወት እሴት ይመለከታል›› የሚሉት ናቸው፡፡ እኛን የሚያስተሳስሩንና ተፈጥሮአዊ ተጓዳኞች የሚያደርጉን እነዚህ ነገሮች እስከመቸውም ድረስ አይበጠሱም፡፡"

ቡሽ ንግግራቸውን ያሳረጉት ዩናይትድ ስቴትስ ከጠላቶቿ ዱላ የራቀችው ባላት መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ሳቢያ መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን፣ ‹‹እስራኤል ግን›› አሉ። ‹‹እስራኤል ግን በጠንካራ ጎረቤቶች የተከበበችና ብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የተጋፈጠች ትንሽ ሀገር ናት፡፡ የእስራኤል ሕዝቦች ምንጊዜም ቢሆን በሀገራቸው ድንበሮች ላይ አሰፍስፈው የሚጠብቋቸው ጠላቶች አሏቸው። ይሁን እንጂ እስራኤል ይህን በየዘመናቱ የተቃጣባትን አደጋ ሁሉ በታላቅ ጥበብና አርበኝነት ተወጥታዋለች፡፡ በዚህ የሕዝቧ የጀግንነት ተግባር የተነሳ እስራኤል የአሜሪካውያንን አክብሮት ልታተርፍ ችላለች፡፡"

ቡሽ በንግግራቸው ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል የምትሰጠው እርዳታ በዋነኛነት ስትራቴጂያዊ ወዳጅነትን ያገናዘበ ሳይሆን፣ አስፈላጊ በሆኑ ሞራላዊ መሠረቶች ላይ ያረፈ መሆኑን ነው ሊያሰምሩበት የፈለጉት። አሜሪካ እስራኤልን ለመርዳት በዋነኛነት የምታቀርባቸው የመከራከሪያ መነሻዎች ሞራላዊ ምክንያት የሚባሉትን ታሳቢዎች ነው። የእስራኤል ደጋፊዎችም ቢሆኑ እነዚህን ሞራላዊ ምክንያቶች እየጠቀሱ "ልዩ ግንኙነት" ለሚሉት አስተሳሰብ በመከራከሪያነት ይጠቀሙበታል። ከነዚህ ሞራላዊ ምክንያቶች መሐከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ። እስራኤል ደካማና ዙሪያዋን ሊያጠፏት በሚያደቡ ጠላቶች የተከበበች በመሆኗ፤ የዲሞክራሲ አምባ በመሆኗ፣ በሞራል ተመራጭ የሆነ መንግሥት ስላላት፣ ከጠላቶቿ ይልቅ የእስራኤል ጠባይ የተሻለ በመሆኑ፣ በተለይም ከፍልስጤማውያን (ለምሳሌ ፍልስጤማውያን ሐምሌ/2000 ላይ እስራኤል በካምፕ ዴቪድ የዘረጋችውን የሰላም ግብዣ ከመቀበል ይልቅ ብጥብጥ ማድረጉን መርጠዋል።)፤ እስራኤል የተመሠረተችው በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደተጠቀሰው በአምላክ ፈቃድ በመሆኑ ነው። እነዚህ ሁሉ የመከራከሪያ ሀሳቦች አንድ ላይ ሆነው እስራኤል በመካከለኛው ምሥራቅ የአሜሪካን እሴቶች የምትጋራና የአሜሪካን ሕዝብ ሰፊ ድጋፍ ለማግኘትም ተገቢ የሆነች ብቸኛ ሀገር እንድትሆን ያስቸሏታል። ብዙ የአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎችም እነዚህን ሞራላዊ ምክንያቶች ይቀበላሉ። ባይቀበሏቸውም እንኳ እስራኤልን እንዲደግፉና በርሷ ላይ ምንም ዓይነት ጫና እንዳያደርጉ የአሜሪካ ሕዝብ በእንድምታ ይሻል።

ሁኔታውን ጠጋ ብሎ ለሚመረምር ማንም አካል ለእስራኤል የሚሰጣት ገደብና ቅድመ ሁኔታ አልባ የዩ. ኤስ. አሜሪካ እርዳታ ከሞራላዊው ምክንያት አንፃር ከታዬ ግዴታ አለመሆኑን ይገነዘባል። በእርግጥ የእስራኤልን ሕልውና ለማስቀጠል እርሷን መደገፍ ጠንካራ ሞራላዊ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ይሁንና አሁን ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ካየን የእስራኤልን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ያለ አይመስልም። በተጨማሪም እስራኤል ባለፉት ጊዜያትና አሁንም በተጨባጭ የምታሳየውን

ባህሪ ስንመለከት እርሷን ከፍልስጤማውያን አብልጦ ተጠቃሚ እንድትሆን ማድረግ ከሞራላዊነቱ ይልቅ ኢ-ሞራላዊነቱ ይጎላል፡፡

ይህ ሞራላዊ ምክንያት (Morale Rationale) ይበልጡኑ የታነጸው የእስራኤልን ታሪክ አስመልክቶ በብዙ አሜሪካዊያን (አይሁድ የሆኑና ያልሆኑም ጭምር) አእምሮ ውስጥ ከሰረጸ ተረት ላይ ነው። ሆነ ተብሎ በተዘጋጀ በዚህ ተረት አይሁዳውያን ልክ በአውሮፓ እንደሆነው ሁሉ በመካከለኛው ምሥራቅም የጥቃት ሰለባ ሆነው እንደቆዩ ተደርጎ ይወራል፡፡ ኤሊ.ዊስል እንዲህ ይላል፡- “አይሁድ ሁልጊዜም ቢሆን በስቃይ ኖረ እንጂ አንድም ጊዜ የስቃይ ምንጭ ሆኖ አያውቅም።››[2] በዚህ አስተሳሰብ መሠረት በአውሮፓ የሚኖሩ ፀረ- ሴማውያን አይሁዳዊያንን እንደጨፈጨፉት ሁሉ አረቦች በተለይም ፍልስጤማዊያን ጨፍጭፈዋቸዋል። ይህ አስተያየት በግልጽ ሊዮን.አሪስ በ1958 በጻፈው ዝነኛ ልብ ወለድ መጽሐፍ በምጽአተ እስራኤል (Exodus) በግልጽ ተንፀበርቋል፡፡ በዚያ መጽሐፍ አይሁዳዊያን የግፍ ሰለባዎችና ጀግኖች፣ ፍልስጤማውያን ደግሞ ተንኮለኞችና ፈሪዎች ተደርገው ተስለዋል፡፡ ይህ መጸሕፍ በመላው ዓለም ከ1958 እስከ 1980 ድረስ በ8 ሚሊዮን ኮፒዎች ተባዝቶ የተቸበቸበ ሲሆን፣ በ1960 ደግሞ ወደ ፊልም ተቀይሯል፡፡ የታሪክ ምሁራን እንደሚናገሩት ይህ ምጽአተ እስራኤል የተባለ መጽሐፍ በውስጡ የያዘው ትረካ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ባሉ አሜሪካውያን አእምሮ ላይ ዘላቂና ለረዥም ጊዜ የማይጠፋ የአረብ - እስራኤል ግጭት ስዕል ትቷል፡፡[3]

ትክክለኛው የእስራኤል አመሠራረትና በፍልስጤማውያንም ሆነ በአጎራባች መንግሥታት ላይ ስትፈጽመው የቆዬችው በደል ሁሉ በእነዚያ የእስራኤል ታሪክ ምሁራን ዘንድ ፈጽሞ እንደሌለ ተደርጎ ነበር የተሳለው። ያለፉ ክስተቶችን በአፈ ታሪኮች ላይ በተመሠረቱና ስልታዊ በሆኑ የታሪክ ቅንብሮች የመተካቱን ሂደት ባለፉት ሃያ ዓመታት ምሁራኑ ሲፈጽሙ ቆይተዋል፡፡[4] አይሁዳዊያኑ ምንም እንኳን በአውሮፓ ውስጥ ባለፈው ምዕተ ዓመት የጥቃት ሰለባ ሆነው መቆየታቸው ጥያቄ ውስጥ ባይወድቅም፣ አሁን ደግሞ በመካከለኛው ምሥራቅ አጥቂዎቹ እነርሱ ሆነዋል፡፡ ግፍ የሚፈጽሙትም በፍልስጥኤማውያን ላይ ነው፡፡ ይህ ድርጊት በብዙ

ማስረጃዎች የተደገፈ ብቻ ሳይሆን በደመነፍስም ጭምር ሊረዱት የሚገባ ነው። ማለትም ከአውሮፓ የመጡ አይሁዳዊያን የራሳቸውን መንግሥት ለመመሥረት በፈለጉ ጊዜ እዚያ ምድር ያገኙትን ነባር የአረብ ሕዝብ ሳይጨፈጨፉ ይህን ጉዳይ በምን መንገድ ሊያስፈጽሙ ይችላሉ ተብሎ ይታሰባል? ዩናይትድ ስቴትስንና ካናዳን የመሠረቱት አውሮፓውያን እዚያ ያገኙዋቸውን የአገሬው ቀይ ሕንዶች ሳይጨፈጭፉ ያን የመሰለ የሕዝብ ማስፈር ሥራ እንዲሁ እንዳላደረጉ ሁሉ ጽዮናውያኑም በፍልስጤም የነበሩና ድርጊታቸውን የተቃወሚቸውን ሕዝቦች ሳይጨፈጭፉ ሕልማቸውን እውን ማድረግ እንደማይችሉ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው። እንዳለመታደል ሆኖ፣ ይህ በአፈታሪክ የተሞላው የእስራኤል "አዲስ ታሪክ" በብዙ አሜሪካውያን ዘንድ እንደ እውነተኛው ታሪክ ይቆጠራል። ለዚህም ነው ከላይ የቀረቡ ሞራላዊ ምክንያቶች አሁንም ድረስ በብዙ አሜሪካውያን ዘንድ ሚዛን መድፋታቸውን የቀጠሉት።[5]

ይሁን እንጂ የእስራኤል ክፉ ባህሪ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለእይታ እየተጋለጠ መጥቷል። በኢንተርኔትና 24 ሰዓት በሚተላለፍ የኬብል ኒውስ ኔትወርክ ቴሌቪዥን ጣቢያ አማካኝነት ብዙ አሜሪካውያን እስራኤል በኃይል በያዘቻቸው የፍልስጤም ግዛቶች በሕዝቡ ላይ የምታራምዳቸውን የጭካኔ ተግባራት በስፋት እያዩ ነው። አንዲሁም በ2006 ላይ በተደረገው ሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት ወቅት እስራኤል የሊባኖስን ሲቪል ሕዝብ እንዴት ትደበድብ እንደነበርና በደቡብ ሊባኖስ ከተሞችና መንደሮች ላይ የክላስተር ቦምብ መጠቀሟን ታዝበዋል።[6]

ምንም እንኳን እነዚህ ሁሉ ድርጊቶች የእስራኤልን ገጽታ በብዙ አሜሪካውያን ዘንድ ያወየበው ቢሆንም፣ ደጋፊዎቿ አሁንም ቢሆን ይህን የሞራል ጉዳይ እያነሱ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ትስስር እንደቀድሞው እንዲቀጥል እየወተወቱ ይገኛሉ። የሞራል ጉዳይ በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ ሁነኛ ሚና የሚጫወት ቢሆን ኖሮ፤ ምናልባትም ዩናይትድ ስቴትስ እስራኤልን ሳይሆን ፍልስጤማውያንን ለመርዳት በበቃች ነበር። ለምን ቢባል እስራኤል የበለጸገችና በመካከለኛው ምሥራቅ ኃያል የሆነ ጦር ያላት ሐገር ሆናለች። ዛሬ ከእስራኤል ጋር ሆነ ብሎ ጦርነት

የሚገጥም ሐገር የለም። እስራኤል የአሸባሪነት ችግሮች ያለባት መሆኑ እውነት ነው። ሆኖም ግን ይህ በኃይል በያዘቻቸው የፍልስጤማውያን ግዛቶች ምክንያት የተከሰተ ችግር ነው። ፍልስጤማውያን ከእርሷ ጋር ሲነፃፀሩ መንግሥት አልባ፣ ችግረኞች፣ እንዲሁም የወደፊት ተስፋቸው ጥርጣሬ ላይ የወደቀ ሕዝቦች ናቸው። ፍልስጤማውያን ያሉባቸውን ብዙ ድክመቶች ለጊዜው ወደ ጎን ትተን አሁን ካለው መሪር ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ከሁለቱ ወገኖች የትኛው ነው የዩናይትድ ስቴትስን የሞራል ድጋፍና ሃዘኔታ ማግኘት ያለበት ? ብለን ራሳችንን እንጠይቅ።

ደካማውን ማገዝ

እስራኤል ብዙ ጊዜ ደካማ፣ በጠላት የተከበበች ተደርጋ ነው የምትሳለው። በብሉይ ኪዳን የተተረከው ደካማው ዳዊት በጦረኛው ከነዓናዊ በጎሊያድ እንደተከበበው። ይህ አይነቱ ገጽታ በእስራኤል መሪዎችና የእርሷ ደጋፊ በሆኑ ጸሐፍት በጥንቃቄ እንዲጎለብት ተደርጓል። እውነቱ ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። እስራኤል ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ከአረብ ጠላቶቿ የተሻለ ወታደራዊ ጥንካሬ ይዛ ቆይታለች። በ1948 እስራኤል ስትመሠረት የነበረውን ሁኔታ እንመልከት። በጊዜው ሁሉም ያስብ የነበረው የአምስት ሀገራትን ጥምር ጦርና ፍልስጤማውያንን የገጠሙት ጽዮናውያን በቁጥርም በመሣሪያም ብዛት በጠላቶቻቸው እንደሚበለጡ ነበር። ቤኒ ሞሪስ የተባሉት ዋና የእስራኤል የታሪክ ምሁር ይህን ሁኔታ፡- "የ1948ቱን ጦርነት አስመልክቶ ይነገሩ ከነበሩት መሠረተ ቢስ ወሬዎች አንዱ ነው" በማለት ይገልጹታል።[7]

ማንም ቢሆን በ1948 የነበረውን የሁለቱን ኃይሎች አሰላለፍ በመገመት እስራኤል ገና እየተቋቋመች ያለች ሀገርና በኃያላን ጎረቤቶቿ ግዙፍ ጦር የተከበበች አድርጎ በማየት ጠላቶቿ ብዙ ሠራዊትና የተሻለ የመሣሪያ አቅርቦት እንዳላቸው ቢናገር ተሳስቷል አይባልም። ዳሩ ግን የሕዝብ ብዛትና የቆዳ ስፋት ስለ አንድ ሀገር የጦር ኃይል አቅም የሚናገረው በጥቂቱ ብቻ ነው። ሞሪስ እንዲህ ይላሉ፡- "የአካባቢውን ካርታ ስንቃኘው እስራኤል

በአረብና ሜዲትራኒያን ባሕር ዙሪያ ገባ በተንጣለለው የአረብ መሬት የተሰነቀረች ሚጢጢ ሀገር ሆና ነው የምትታየን። ይሁን እንጂ ይህ የቆዳ ስፋት ማነስ በክልሉ ያለውን የኃይል አሰላለፍ በትክክል የሚወክል አይደለም። የሕዝብ ብዛትም እንደዚሁ ወታደራዊ አቅምን አያሳይም። ለምሳሌ በ1948 (እስራኤል ከመመሥረቷ በፊት) በፍልስጤም ምድር የነበረው የአይሁዳዊያን ነዋሪዎች ብዛት 650000 ሲሆን፣ በተመሳሳይ ጊዜ 1.2 ሚሊዬን ፍልስጤማውያንና 30 ሚሊዬን የሚሆኑ አረቦች (ኢራቅን ጨምሮ) በአካባቢው ይኖሩ ነበር።››[8] ይሁንና ይህ የሕዝብ ቁጥር ልዩነት ከወታደራዊ ጉልበት ጋር ግንኙነት የለውም። አረቦቹ የመሸነፋቸውን ምስጢር ለማወቅ ቀላል ነው። የአረብ መንግሥታት በጊዜው ለዚያ ወሳኝ ጦርነት የሚያሰልፉትን የሰው ኃይል በአግባቡና በብቃት ማደራጀትና መምራት አልቻሉም ነበር። በአኳያው አይሁዳዊያኑ ያንን ማድረግ ተሳክቶላቸዋል።

አይሁዳዊያኑ የራሳቸውን መንግሥት ለማቋቋም በሚሞክሩባቸው በእነዚያ ጊዜያት ሁለት ዓይነት የግጭት ግንባሮች ተከፍተውባቸው ነበር። የመጀመሪያው ህዳር 29/1947 በፍልስጤማውያንና አይሁዳዊያን መካከል የተጀመረው ውጊያ ሲሆን፣ (ይህ ቀን የተባበሩት መንግሥታት የፍልስጤም ምድር ለሁለት እንዲከፈል የወሰነበት ጊዜ ነው) እስከ ግንቦት 14/1948 ድረስ (እስራኤል ራሷን የቻለች ሀገር መሆኗን ያወጀችበት ቀን) ቀጥሏል። ሁለተኛው ግንባር ደግሞ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለውና እስራኤል ከአምስቱ የአረብ ሀገራት ሠራዊት ጋር ከሚያዝያ 15/1948 እስከ ጥር 7/1949 ድረስ ያደረገችው ጦርነት ነው።

ጽዮናዊያኑ ከፍልስጤማውያን ጋር ባደረጉት የእርስ በርስ ጦርነት ወሳኝ የሆነ ድል ተቀዳጅተዋል። ምክንያቱም የእነርሱ ሠራዊት በቁጥርም ሆነ በመሣሪያ ጥራት የተሻለ ስለነበር ነው።[9] አይሁዳዊያን ተዋጊዎች ከፍልስጤማውያን ጠላቶቻቸው በበለጠ ሁኔታ የተደራጁና በቂ ሥልጠና የወሰዱ ሲሆን፣ ከ1936–39 በእንግዞች ላይ በተደረገው አመጽ ክፉኛ የደቀቁት ፍልስጤማውያን ግን በ1948 ጠንካራ የሆኑትን ባላጋራዎቻቸውን ለመቋቋም በሚያስችል ሁኔታ አላገገሙም ነበር። እስራኤላዊው የታሪክ

ምሁር ኢላን ፓፔ፡- ‹‹ በጥቂት ሺዎች የሚቆጠሩ በሚገባ ያልተደራጁ ፍልስጤማውያንና አረቦች በሚገባ የተደራጀውንና በቂ ስልጠና ያገኘውን በሺዎች የሚቆጠር የአይሁድ ጦር ነበር የተጋፈጡት" ብለዋል፡፡[10] የእስራኤል መሪዎች ይህን ያልተመጣጠነ የኃይል አሰላለፍ በሚገባ የተገነዘቡ በመሆኑ ያንን ዕድል ለመጠቀም መፈለጋቸው አያስደንቅም፡፡ በ1948 የእስራኤል ጦር ሁለተኛ ኤታመገር ሹም የነበሩት ይጋል የዲን እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹እንግሊዛዊያን በዚያ ምድር እስከ ግንቦት 1948 ባይቆዩ ኖሮ የአረቦችን አመጽ በአንድ ወር ውስጥ ብቻ በደመሰስነው ነበር፡፡››[11]

ከላይ እንደተጠቀሰው እስራኤላውያኑ ከአረብ ሀገራት ጣምራ ሠራዊት አንፃር ሲታዩ በቁጥር ላቅ ያለ ተዋጊ ማሰለፋቸው ግልጽ ነበር። ሞሪስ እንደገለጹት፡- “ውጊያው በግንቦት ወር እኩለ ቀን ላይ እንደተጀመረ 35000 የሚሆኑት የእስራኤል ተዋጊዎች ከ25000-30000 ይሆናል ተብሎ ከሚገመተው የተባበረው ወራሪ የአረብ ጦር ጋር ነበር የተጋጠሙት፡፡ ‹የዳኒ ዘመቻ› ተብሎ በሚጠራው ሐምሌ ወር ላይ በተደረገው ውጊያ 65000 በሚገባ የታጠቀ የእስራኤል ሠራዊት የተዋጋ ሲሆን፣ ታህሣሥ ላይ ደግሞ ወደ 90.000 የሚጠጋ የታጠቀ ጦር ነበር በቁጥር እጅግ ዝቅተኛ ከነበረው የተባበረው የአረብ ጦር ጋር የተፋለመው››[12] እስራኤል በተጨማሪም የመሣሪያ የበላይነት ነበራት፡፡ ግጭቱ እንደተጀመረ (ከግንቦት 15 እስከ ሰኔ 10/1948) ድረስ ለ25 ቀናት የሚበቃትን የጦር መሣሪያ ክምችት ይዛ ነበር። ከትራንስ ጆርዳን አነስተኛ የአረብ ክ/ጦር በስተቀር የእስራኤል ተዋጊዎች ከጠላቶቻቸው ይልቅ በሁሉም መልኩ የተሻለ ብቃትና አደረጃጀት ነበራቸው፡፡ በአጭር አነጋገር ጽዮናዊያኑ በአካባቢያዊ ጦርነት ፍልስጤማውያንን ያሸነፉ ሲሆን፣ በዓለም አቀፋዊው ጦርነት ደግሞ ወራሪውን የአረብ ጦር ድል ማድረግ ችለዋል፡፡ ምንም እንኳን የአረብ ሀገራት የነበራቸው የሕዝብ ቁጥር እጅግ የላቀ ቢሆንም፣ በተዋጊ ሠራዊት መልክ አሠልጥነው፣ አስታጥቀውና አደራጅተው ያሰለፉት ትንሽ በመሆኑና ጠላቶቻቸው ደግሞ የበለጠ የታጠቀና የተደራጀ የሠራዊት ቁጥር ስለነበራቸው የድል ጽዋ አንስተዋል፡፡ እንደ አጠቃላይ ሁኔታው ሲገመገም አረቦች እስራኤላውያኑን ዝቅ አድርገው የገመቷቸው ይመስላል፡፡ ሞሪስ

እንዳሉት፡- ‹‹በጊዜው የአይሁድ ጦር ለአንድ ሠራዊት ድል ወሳኝ በሆኑት መመዘኛዎች ማለትም በመሣሪያ፣ በተዋጊ ብዛት፣ በአደረጃጀትና በእዝ ተዋረድ የበላይነቱን ይዞ ነበር፡፡››[13]

የእስራኤል መከላከያ ሠራዊት የአሜሪካን እርዳታ ማግኘት ከመጀመሩ በፊት በ1956 ከግብፅ ጋር፣ በ1967 ደግሞ ከግብፅ፣ ከዮርዳኖስና ከሶሪያ ኃይሎች ጋር ተጋጥሞ ወሳኝ ድል ተጎናጽፏል፡፡ በጥቅምት 1973 እስራኤል ከግብጽና ከሶሪያ ጥምር ኃይል ጥቃት ተሰነዘረባት፡፡ ምንም እንኳን በቁጥር ብልጫ ያለው የእስራኤል ጦር በመጀመሪያዎቹ የውጊያ ቀናት ክፉኛ ቢመታም፣ በፍጥነት አገግሞ የግብፅንና የሶሪያን ሠራዊት ለማውደም በተቃረበበት ወቅት ነበር አሜሪካና ሶቪዬት ጦርነቱ እንዲቆም ያደረጉት፡፡ በዚህም ጦርነት ቢሆን በሞሪስ አስተያየት መሠረት ‹‹አስደናቂ የሆነው የእስራኤል ጦር ድል የተገኘው በሌላ ሳይሆን በአየርና በምድር የተጠቀመቻቸው የውጊያ መሣሪያዎች የላቁ ስለነበሩ ብቻ ነው፡፡ እንዲሁም የሠለጠነ ተዋጊ ኃይሏ፣ ፓይለቶች፣ የጥገና ባለሙያዎችና የምድር ላይ ተቆጣጣሪዎች አባላት፣ ታንከሮችና ተራ ተዋጊዎች ሁሉ ከአረብ ጠላቶቻቸው የተሻለ ብቃት ስለነበራቸው ጭምር ነው፡፡[14] ይህ ድል የእስራኤልን ጦር የአርበኝነት ስሜት፣ የማደራጀት ችሎታና ወታደራዊ ብቃት ያረጋገጠ ሆኖ አልፏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ክስተቱ እስራኤል ከተመሠረተች በኋላ ለብዙ ጊዜያት ያለ አንዳች ረዳት ሕልውናዋን ማስጠበቅ መቻሏን ለመገንዘብ ያግዛል፡፡[15]

ዛሬ እስራኤል በመካከለኛው ምሥራቅ በጣም ጠንካራ ሠራዊት ያላት ሀገር ሆናለች፡፡ መደበኛ ጦሯ ከአጎራባቾቿ የላቀ ሲሆን በክልሉ ውስጥ ብቸኛዋ የኑክሌር መሣሪያ ባለቤትም ነች፡፡ ግብጽና ዮርዳኖስ ከእስራኤል ጋር ስምምነት የተፈራረሙ የአረብ ሀገራት ሲሆኑ፣ ሳዑዲ አረቢያም ወደዚያው እያመራች ይመስላል፡፡ ሶሪያ የሶቪዬትን ድጋፍ አጥታለች፡፡ ኢራቅ ደግሞ ሶስት አውዳሚ ጦርነቶችን በማሳለፏ ተዳክማለች፡፡ ኢራን ብዙ መቶ ማይሎች ርቃ የምትገኝ በመሆኑ እስራኤልን በቀጥታ ታጠቃለች ተብሎ አይታሰብም፡፡ ፍልስጤማውያን በበኩላቸው እስራኤልን የሚገዳደር ሠራዊት ሊኖራቸው ይቅርና ብቃት ያለው የፖሊስ ኃይል እንኳ በቅጡ አላደራጁም፡፡ በዚህ ሁኔታቸው ውስጥ እያሉ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ

እርስበርሳቸው የተከፋፈሉ ናቸው። ፍልስጤማውያን አጥፍቶ ጠፊዎች የሚያደርሱት አደጋ በብዙ እስራኤላውያን ልብ ውስጥ ፍርሃትን የሚለቅ መሆኑ ባይካድም በእስራኤል ኢኮኖሚ እንዲሁም በሉዓላዊነቷ ላይ የሚያደርሰው ተጽእኖ በጣም ኢምንት ነው።[16] ሂዝቡላህን የመሳሰሉ ቡድኖች ዝቅተኛ ውጤት የሚያስከትሉ ሚሳዮሎችንና ሮኬቶችን ወደ እስራኤል ግዛት በማስወንጨፍ በወራትና በዓመታት ዕድሜዎች በመቶዎች የሚቆጠሩ እስራኤላውያንን ሊገድሉ ይችላሉ። ይሁን እንጂ የእስራኤልን ሕልውና ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ የጥቃት ምንጮች ግን አይደሉም። በቴሌአቪቭ ዩኒቨርስቲ የጃፌ ስትራቴጂ ጥናት ማዕከል የ2005 ግምት መሠረት "ስትራቴጂያዊ የሆነው ኃይልን የማመጣጠን የአሜሪካ ስልት እስራኤል የራሷን ወታደራዊ አቅም እንድትገነባና ጎረቤቶቿን የማስፈራራት ኃይሏን እንድታዳብር ረድታቷል››[17] ይላል። ስለሆነም ደካማውን መርዳት ለአሜሪካ አስገዳጅ ሞራላዊ ምክንያት ቢሆን ኖሮ፤ በዚህ የጥንካሬ ደረጃ ላይ የምትገኘውን እስራኤልን ሳይሆን ደካሞቹን ተቀናቃኞቿን በረዳች ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ ሁኔታዎችን ከተለዩ አቅጣጫ የሚመለከቱ ተንታኞች "እስራኤል በብዙ የአረብ እስራኤል ግጭቶች ውስጥ የጥቃት ሰለባ ሆናለች። ምንም እንኳን በጦር ኃይል ጥንካሬ የበላይነቱን ብትጨበጥም፣ የአረብ አጎራባቾቿ ሊያጠፏት ወስነዋል። ከ1948–1967 እና በ1973 የተደረጉት ጦርነቶች አይሁዳውያንን በሙሉ ጠራርጎ ወደ ባሕር ውስጥ የመጨመር ዓላማን ያነገቡ ነበሩ›› ይላሉ።[18] ስለዚህም እስራኤል ጠንካራ ብትሆንም እንኳ ምንጊዜም እገዛ ያስፈልጋታል ነው የዚህ አስተሳሰብ ማሳረጊያ።

የአረቦች ጥምር ጦር ምንም እንኳን ቀደም ባሉት ዓመታት ለእስራኤል ታላቅ ስጋት የነበረ ቢሆንም፣ ዓረቦች በሶስቱም ዘመቻዎች ሊያጠፏት አልሞከሩም። የዚህም ምክንያቱ አረቦች የአይሁዶቹ ሀገር በመካከላቸው መኖሯ አስደስቷቸው ሳይሆን፣ ጦርነቶቹን በሙሉ ማሸነፍ ስላልቻሉ ነበር። የተወሰኑ የአረብ መሪዎች በ1948 አይሁዳዊያንን ጠራርጎ ባሕር ውስጥ ስለመጨመር ተናግረው የነበረ ስለመሆኑ ጥያቄ አይነሳም። ሆኖም ግን ይህን ያደረጉት ሕዝባቸው ጦርነቱን እንዲደግፍላቸው ለማነሳሳት ነበር። እዚህ ላይ ሁሉም ሊያውቀው የሚገባው ሐቅ የአረብ መሪዎች በእነዚያ

ጦርነቶች ያራምዱት የነበረው ዓላማ ፍልስጤማውያንን ነፃ ማውጣት ሳይሆን በዋነኛነት በፍልስጤማውያን ኪሳራ የራሳቸውን ተጨማሪ ግዛት ለማግኘት ነበር። ሞሪስ እንዲህ በማለት ስለጉዳዩ ያትታሉ፡-

‹‹እስራኤል ግንቦት 14/1948 ሉዓላዊ ሀገር ሆና ስትመሠረት አረቦች ወረራ አድርገውባታል። ዳሩ ግን ራሷን እስራኤልን ጨምሮ፣ ዮርዳኖስ፣ ሶሪያ፣ ግብጽና ሊባኖስም ጭምር ይሻኩቱ የነበረው የፍልስጤማውያን አረብ መንግሥት እንዲቋቋም ሳይሆን ለራሳቸው ቁራጭ መሬት በመውሰድ ወደ ግዛታቸው ለመቀላቀል ነበር። ለምሳሌ የዩርዳኖሱ ንጉሥ አብዱላህ አይሁዳዊቷን ሀገር ለመደምሰስ ሳይሆን ግዛቱን ለማስፋፋት የሚያግዘውን ተጨማሪ መሬት በፍልስጤማውያን ኪሳራ ለማግኘት ነበር ሲንቀሳቀስ የነበረው። አብዱላህን ከአይሁዳዊቱ ሀገር መመሥረት የበለጠ ያሳስበው የነበረው የፍልስጤኤም አረብ መንግሥት መመሥረቱና የታላቋ ሶሪያና የግብጽ መንግሥታት ከግዛቱ ድንበሮች ባሻገር ተጠናክረው መውጣታቸው ነበር።››[19]

ሻሎም ቤን አሚ የተባሉት የታወቁ የታሪክ ባለሙያና የቀድሞ የእስራኤል ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በ1948 የነበረውን የአረቦች ጦር ሲተቹ “ በሚገባ ያልተዘጋጀና ቅንጅት የጎደለው ሲሆን፣ ወደ ውጊያ የገባው በየሀገራቱ በነበረው የሕዝቡ ግፊትና መሪዎቻቸው በነበራቸው ግዛት የማስፋፋት ዓላማ ነበር። የፍልስጤማውያን መንግሥት መመስረቱን ማረጋገጥ ለአረብ መሪዎች ተቀዳሚ ዓላማቸው አልነበረም ማለት ይቻላል። በመሆኑም ሠራዊታቸውን ወደ ፍልስጥኤም ሲልኩ ተጨማሪ ግዛት ለማግኘት በመሆኑ በሕብረቱ ውስጥ የታቀፉትን ወዳጆቻቸውን ሳይቀር የማጨናገፍ ሙከራ ያደርጉ ነበር።››[20]

እስራኤል ተጠቂ ነች የሚለው ተረት በ1967ቱ ጦርነት ሳይቀር ተንፀባርቆ የነበረ ሲሆን፣ ግብጽንና ሶሪያን ያንን ጦርነት በዋነኛነት በመቀስቀስ ተጠያቂ ያደርጋል። ዓረቦች የእስራኤል ጦር ኃይለኛ ጡጫ ሳያሳርፍባቸው በፊት እስራኤልን ለማጥቃት እየተዘጋጁ ነበር የሚል ክስ ነው የቀረበው።[21] ይሁን እንጂ ስለዚያ ጦርነት የሚያወሱ አዳዲስ መረጃዎች እንዳረጋገጡት በ1967

አረቦች እስራኤልን ከናካቴው ሊያወድሟት ይቅርና[22] ጦርነት ለመጀመር እንኳን አልሞከሩም። አቪ ሻሊዮም የተባሉት የታሪክ ተመራማሪ እንደጻፉት፡- ‹‹የግብፁ ፕሬዚዳንት ናስር ወደ ጦርነት ለመግባት ፍላጎቱም ሆነ እቅዱ የሌላቸው ስለመሆኑ አጠቃላይ የሆነ የታሪክ ምሁራን ስምምነት አለ።››[23] በእርግጥ የ1967ቱን ጦርነት በመቀስቀስ ኃላፊነቱን መውሰድ ያለባት እስራኤል ናት። ሻሊዮም በዚህም ጉዳይ ላይ የሚሉት አላቸው፡- ‹‹እስራኤል በሶሪያ ድንበር በኩል ጠብ መጫሯ ምናልባትም መካከለኛውን ምሥራቅ ወደ 1967ቱ ጦርነት በማስገባቱ ሂደት ዋነኛው ምክንያት ነው።››[24] ቤን አሚ በበኩላቸው ጨምረው ሲጽፉ፡- ‹‹በጊዜው የእስራኤል ጦር ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም የነበሩት ኢሳቅ ራቢን እስራልን ሆነ ብለው ከሶሪያ ጋር ጦርነት እንድትገጥም አድርገዋታል። ራቢን ይህን ያደረጉት ሶሪያ እስራኤልን የሚያጠቃውን ፋታህን መርዳቷን እንድታቆም ለማስገደድ ብቸኛው መንገድ ጦርነት ነው ብለው በማመናቸው ነበር›› ብለዋል።[25]

በ1967 ግብጽ የቲራንን የባህር ወሽመጥ ለመዝጋት በመወሰኑዋ እስራኤል ከእርሷ ጋር ጦርነት እንድትገጥም የገፋፋት ስለመሆኑ የሚያስተባብል አይኖርም። ምክንያቱም እስራኤል በዚያ የባሕር ወሽመጥ የመጠቀም ሕጋዊ መብት አለኝ ብላ ታምናለችና። ይሁን እንጂ የግብፃዊያን ጥቃት አይደለም ጦርነቱ እንዲጀመር ያደረገው። ይህ እንዳልሆነ የአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎችና የእስራኤልም መሪዎች በሚገባ ይቀበላሉ። በጊዜው ያንን ግጭት በሰላም ለመፍታት የተለያዩ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች መደረጋቸው አልቀረም። እንደዚያም ቢሆን ግን የእስራኤል መሪዎች በሁሉም አቅጣጫ ጥቃት መክፈቱን ነበር የመረጡት። ምክንያቱም የአረብን መሪዎች በማስገደድ ለሰላም እንዲንበረከኩ የሚያደርጋቸው ይህ የጦርነት ዘዴ መሆኑን ጠንቅቀው ያውቁ ስለነበር ነው። የእስራኤል ወታደራዊ አዛዦች በሁለቱ የእስራኤል ዋነኛ ጠላቶች፣ በግብጽና በሶሪያ ላይ የማያዳግም ድል ለመቀዳጀት ፈልገው ነበር። ያንን ማድረግ ከቻሉ ለረዥሙ የወደፊት የድርድር ሂደት ማስፈራሪያ ያገኛሉ ማለት ነው።[26] እንዲያውም የተወሰኑት የእስራኤል ባለስልጣናት ግዛቶችን ቆርሰው ለመውሰድ ነበር እቅዳቸው። ጀኔራል ኢዘር ዋይዝማን የተባሉት የዘመቻ መምሪያ ኃላፊ ይህን አይነት

ዓላማ ከሚያራምዱት ሰዎች መካከል የነበሩ ሲሆን በጦርነቱ ዋዜማ ላይ እንዲህ በማለት ተናግረው ነበር፡- ‹‹እኛ አሁን የምንገኘው በሁሉም አፈጻጸም ሲመዘን በሁለተኛው የነጻነታችን ጦርነት ላይ ነው።››[27] በአጭሩ እስራኤል በግንቦት 5ቱ የ1967 ጦርነት እንዲጀመር ትንኮሳ ታድርግ እንጂ የመጀመሪያውን ጥቃት ለመሰንዘር ቀዳሚ አልነበረችም። ከዚያ ይልቅ በመከላከል ላይ ያተኮረ ሆኖ በሂደት የጠላትን ኃይል በመስበር ሚዛኑን እንዲስት የማድረግ ስልትን ተከተለች። ሜናሂም ቤጊን ስለሁኔታው ሲገልጹ ‹‹እውነቱን መናገር አለብን። እኛ እርሱን (የግብጹን ፕሬዚዳንት ናስርን ማለታቸው ነው) ልናጠቃው ወስነን ነበር›› ብለዋል።[28]

በ1973 የዮም ኪፑር (ረመዳን) ጦርነት ሶሪያና ግብፅ እስራኤልን ለማጥቃት በተለያዩ ግንባሮች ውጊያ ከፈቱ። በዚያ ጦርነት የግብፆች ዓላማ ከሲናይ ግዛት የተወሰነ መሬት ቆርሰው በመያዝ የቀረውን ደግሞ ከእስራኤል ጋር በመደራደር ማስለቀቅ ሲሆን የሶሪያ ዓላማ ደግሞ የጎላን ከፍታዎች ማስመለስ ነበር። ግብፅም ሆነች ሶሪያ እስራኤልን ለመውረርና ሕልውናዋን አደጋ ላይ ለመጣል አላሰቡም። እንደዚያ አይነት ሙከራ ቢያደርጉ ኖሮ እስራኤል በጊዜው ኃያል ጦር ያዘጋጀች ብቻ ሳይሆን፣ የኑክሌር መሣሪያም የታጠቀች በመሆኗ ራሳቸውን በራሳቸው እንደማጥፋት ነበር የሚቆጠርባቸው። ቤኒ ሞሪስ እንዲህ ሲል ጽፏል፡- ‹‹....ፕሬዚዳንት ሳዳትና የሶሪያው መሪ ሀፊዝ አል-አሳድ በ1967 የተወሰደባቸውን መሬት ከማስመለስ ባሻገር እስራኤልን ለመውረር አላቀዱም።››[29] በካይሮና በደማስቆ ያሉ የጦር ስልት አውጪዎች ኃያል የሆነውን የእስራኤል መከላከያ ጦር መግጠም ያለውን አደገኛነት ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። የግብፁን የጦር እቅድ ከነደፉት ባለሙያዎች አንዱ የሆኑት ጄኔራል ሀሰን ኤል በድር እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡- ‹‹ድል ይገኛል ብሎ ማሰብ የሚቻል አልነበረም።››[30] የእነዚህ የጦር አዛገቦች ጥርጣሬ ትክክል ነበር። ምክንያቱም የእስራኤል ጦር በውጊያው መጀመሪያ ላይ ካጋጠመው ከባድ ምት በኋላ፣ አገግሞና እንደገና ተደራጅቶ በወሰደው መልሶ ማጥቃት የአረብን ጦር ሊፈረካክሰው በቅቷል።

ምናልባትም ከኢራን በስተቀር እስራኤልን ለማጥፋት የሚሞክርና ይህን ለማድረግ አቅም ያለው ጦር ያላቸው የአረብ ሀገራት የሉም። ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተገለፀው እስራኤል ከግብፅና ዮርዳኖስ ጋር የሰላም ስምምነት የፈረመች ሲሆን፣ በምዕራፍ 9 ላይ እንደሚብራራው ከሶሪያ ጋር በ2000 ሲደረግ ከነበረውም የስምምነት ሂደት ራሷን አግልላለች። በ2002 ላይ በተደረገው የአረብ ሀገራት ጉባዔ ላይ የሳዑዲ አረቢያ አልጋ ወራሽ የእስራኤል ፍልስጤኤምን ውዝግብ ለመፍታት ሁሉም የአረብ ሀገራት ለእስራኤል እውቅና እንዲሰጡና ግንኙነታቸውንም በተለመደው ሁኔታ እንዲያካሂዱ ሀሳብ አቀረቡ። በአጸፋውም እስራኤል በኃይል ከያዘቻቸው የፍልስጤም መሬቶች እንድትወጣና የፍልስጤማውያን ስደተኞችንም ወደ ሀገር ቤት የመመለስ ሂደቱን እንድታፋጥን ጠየቁ። ይህ የሰላም ሀሳብ ያለምንም ተቃውሞ በሁሉም የአረብ ሃገራት ተቀባይነት አገኘ። ሌላው ቀርቶ ሳዳም ሁሴን እንኳ ደገፉት።[31] ሆኖም ግን ያ የሰላም ሀሳብ ከዚያ በኋላ የትም አልደረሰም። ሳውዲዎች እንደገና በ2007 ሀሳቡን መልሰው አንቀሳቀሱት። ከሳዳም በኋላ የተፈጠረችው ኢራቅ እስራኤል እንድትጠፋ የምትፈልግ ስለመሆኗ በይፋ የታወቀ ነገር የለም። ይሁን እንጂ ሃማስና ሂዝቡላህ የእስራኤልን በህልውና መቆዬት ይቃወማሉ። በየጊዜው ጥቃቶችን እያደረጉባት ቢሆንም እርሷን ለማጥፋት ግን ችሎታ የላቸውም። ኢራን በርግጥም የኑክሌር መሣሪያ መታጠቅ ከተሳካለት ለእስራኤል ህልውና አደገኛ ልትሆን ትችላለች። ይሁን እንጂ እስራኤል ራሷ ኒኩሊዮር የታጠቀች በመሆኗ ኢራን ያንን እርምጃ ከወሰደች አጸፋው አይቀርላትም።

የዲሞክራሲ አጋሮችን መርዳት

አሜሪካ እስራኤልን የምታግዝበት ሌላው ምክንያት እስራኤል የዲሞክራሲ አጋር በመሆኗ እንደሆነ ይጠቀሳል፡፡ ለእርሷ ጥብቅና የቆሙ ፖለቲከኞች ለአሜሪካውያን በተደጋጋሚ የሚገልጹት ‹‹እስራኤል በመካከለኛው ምሥራቅ ጠብ ጫሪ በሆኑ አምባገነን መንግሥታት ዙሪያዋን የታጠረች የዲሞክደራሲ አምባ ናት›› እያሉ ነው፡፡ ይህ ምክንያት ላይ ላዩን ሲያዩት አሳማኝ ሊመስል ይችላል፡፡ ሆኖም ግን አሜሪካ አሁን እስራኤልን በስፋት ለማገዟ ተቀባይነት ያለው ሰበብ ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም በመላው ዓለም ብዙ ዲሞክራሲያዊ ሀገራት ያሉ ሲሆን እስራኤል የምታገኘውን የመሰለ ገደብና ቅድመ ሁኔታ አልባ የአሜሪካ ድጋፍ ሲያገኙ አይታዩምና፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ አንድ አገር ከአሜሪካ ጋር ያለው ግንኙነት የሠመረ የመሆኑ ጉዳይ ከዲሞክራሲ ጋር የተሳሰረ አይደለም፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ ጥቂት የዲሞክራሲ መንግሥታትን ባለፉት ዓመታት የገለበጠች ሲሆን፣ የራሷን ጥቅም የሚያስጠብቁላት ሆነው እስካገኘቻቸው ድረስ ደግሞ የለየላቸውን አምባገነን መንግሥታት ስትደግፍ ቆይታለች፡፡ ለምሳሌ የአይዘንሃወር አስተዳደር በ1953 በኢራን የነበረውን በዲሞክራሲ የተመረጠ መንግሥት አስገልብጧል፡፡ የሬገን አስተዳደርም በ1980 ዎቹ ሳዳም ሁሴንን ሲደግፍ ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ የቡሽ አስተዳደር የግብፁን ሆስኒ ሙባረክና የፓኪስታኑን ፔርቬዝ ሙሻረፍ ከመሳሰሉ አምባገነኖች ጋር መልካም ግንኙነት አለው፡፡ በሌላ በኩል ግን በኃይል በተያዙት የፍልስጤም ግዛቶች በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ያሸነፈውን ሃማስን በጠላትነት ፈርጆታል፡፡ በተጨማሪም በቪኑዝኤላ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጡትን መሪ ሁጎ ሻቬዝን ምርር አድርጎ ይጠላል፡፡ ስለሆነም ‹‹አሜሪካ እስራኤልን የምትረዳው ዲሞክራሲያዊ በመሆኗ ነው›› የሚለው አባባል ሚዛን የሚደፋ አይደለም፡፡

‹‹የጋራ ዲሞክራሲያዊ እሴቶች አሉን›› የሚለው ምክንያትም ወንዝ አያሻግርም፡፡ ምክንያቱም የእስራኤል ዲሞክራሲ የአሜሪካን ቁልፍ እሴቶች

የሚጻረር በመሆኑ። ዩናይትድ ስቴትስ የምትመራው የማንኛውም ዘር፣ ሃይማኖትና ጎሣ አባል የሆነን ሰው እኩል መብት የሚያጎናጽፍ በሆነ ነፃ ዲሞክራሲ ነው። በአንጻሩ እስራኤል አይሁድ፣ አረብ፣ ሙስሊም፣ ክርስቲያንና ሌሎችም ሕዝቦች የሚገኙባት ሀገር ብትሆንም፣ ሕልውናዋ ተማግሮ የተለሰነው በአይሁዳዊነት ላይ ነው። አይሁዳዊነት የሚጣራበትና የሚመዘንበትም የተለየ መስፈርት ይገኛል።[32] እስራኤል ዘረኛ አይሁዳዊት ሀገር መሆኗ ግንቦት 14 ቀን 1948 በይፋ በፀደቀው የእስራኤል መንግሥት አዋጅ በግልጽ ተንጸባርቋል። ያ አዋጅ፣ የተባበሩት መንግሥታት የአይሁድ ሕዝቦች የራሳቸውን መንግሥት የመመሥረት መብት እንዳላቸው ያስተላለፈውን ውሳኔ መነሻ ያደረገ ነበር። ስለሆነም አዋጁ ‹‹በእስራኤል ምድር የአይሁድ መንግሥት›› መመስረቱን አብስሯል።[33]

ይህ የእስራኤል አይሁዳዊነት ባህሪ እንዳለ ሆኖ በእስራኤል ድንበር ውስጥ የአይሁድ የበላይነት ምንጊዜም ተጠብቆ መኖር እንዳለበት የእስራኤል መሪዎች አጠንክረው ያምናሉ። ለዚህም በርትተው ይሰራሉ። የአይሁዳውያንና የፍልስጤማውያን ከሀገር የመውጣትና ወደ ሀገር ውስጥ የመግባት ፍስሰት፣ የፍልስጤማውያን የወሊድ ቁጥር ከአይሁዳዊያን መብለጥና ከ1967 በፊት የነበረውን ድንበሯን የማስፋት ዕቅዷን እውን ስታደርግ ብዙ አረቦች በግዛቷ ውስጥ የሚካተቱ የመሆናቸው ጉዳይ እስራኤልን በጣም ያሳስባታል። ለምሳሌ ዴቪድ ቤንጎሪዮን ‹‹በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ያለች እያንዳንዷ አይሁዳዊት እንስት ቢያንስ አራት ጤናማ ሕፃናትን የማትወልድ ከሆነ፣ የውትድርና አገልግሎትን እንደሸሸ ሰው ብሔራዊ ክህደት እንደፈጸመች ይቆጠራል።›› የሚል አዋጅ አውጥተው ነበር።[34] ዛሬ በእስራኤል ምድር 5.3 ሚሊዮን አይሁዳውያንና 1.36 ሚሊዮን አረቦች በአወዛጋቢዋ እየሩሳሌምና አካባቢዋ ጭምር ይኖራሉ። እንዲሁም በጋዛና ምዕራባዊው ወንዝ ዳርቻ 3.8 ሚሊዮን ፍልስጤማስያን ይኖራሉ። ይህም ማለት አጠቃላይ ፍልስጤም ተብላ ትጠራ በነበረችው ምድር አይሁዳዊያን ከፍልስጤማውያን የሚበልጡት በ140,000 ብቻ ነው ማለት ነው። አንደሚታወቀው ፍልስጤማውያን ከአይሁዳዊያን የበለጠ የወሊድ

እድገት አላቸው።[35] እናም አይሁዳዊያን በአሁኑ ጊዜ ስለፍልስጤማውያን (አረቦች) የሕዝብ ቁጥር የመጨመር አደጋ ቢጨነቁ አያስደንቅም።[36]

ማንም ቢሆን ላይ ላዩን በማየት ብቻ እስራኤል ምንም እንኳን የአይሁዳዊያን ሀገር ብትሆንም መሠረታዊ የሚባሉ ሕጎችን በመደንገጓ ለሕዝቦቿ ሁሉ (ለአረቡም ለአይሁዱም) እኩል የሆነ የዜግነት መብት ታጎናጽፋለች ብሎ ሊያስብ ይችላል። ዳሩ ግን ሃቁ ያለው ወዲህ ነው። የሰው ልጆችን ክብርና ነፃነት የሚያከብረውና ከአሜሪካን ቢል ኦፍ ራይትስ ጋር ተመሳሳይነት ያለው የእስራኤል የሕግ ረቂቅ ሁሉም እስራኤላውያን በሕግ ፊት እኩል እንደሆኑ ሲገልጽ፦ ‹‹ሁሉም ዜጎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው። የፆታ፣ የሃይማኖት፣ የብሔር፣ የዘር፣ የጎሣ የትውልድ ቦታና ሌሎች ሕጋዊ መሠረት የሌላቸው ጉዳዮች ሰዎችን ለማበላለጥ ምክንያት ሊሆኑ አይችሉም›› ይላል።[37] ውሎ አድሮ ግን ይህ ረቂቅ ሕግ ሆኖ በ1992 ከመውጣቱ በፊት በእስራኤል ምክር ቤት ጉዳዩን የተመለከተው ኮሚቴ ቆርጦ አውጥቶታል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም አረብ የምክር ቤቱ አባላት መሠረታዊ የሰው ልጆች መብት በሕጉ ውስጥ እንዲካተት ተደጋጋሚ ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም ቅሉ፣ አይሁዳዊያን የምክር ቤት አባላት ጥያቄያቸውን ውድቅ አድርገውታል።[38]

እስራኤል የአይሁዳዊነት መለያዋን ይዛ ለመቀጠል ካላት ብርቱ ፍላጎት በተጓዳኝ አይሁድ ያልሆኑ 1.36 ሚሊዮን አረብ ዜጎቿን እንደ ሁለተኛ ዜጋ ነው የምትመለከታቸው። በእስራኤል መንግሥት በ2003 የተቋቋመ አንድ ኮሚሽን ይህን ጉዳይ እስመልክቶ ሲተች፦ ‹‹እስራኤል እነዚህን አይሁዳዊ ያልሆኑ ዜጎቿን የማግለልና በእነርሱ ላይ አድልዎ የመፈጸም መንገድ መከተልን መርጣለች።›› ሲል ወርፏታል።[39] አረቦችን መጨቆንና አድሎአዊ በሆነ መንገድ መያዝ በምድረ እስራኤል ሰፊ ተቀባይነት ያለው ተግባር ሆኖአል። አንድ የሕዝብ አስተያዬት መጠይቅ በ2007 እንዳረጋገጠው 55 በመቶ የሚሆኑ አይሁዳውያን ከአረቦች የተለዩ የመዝናኛ አይነቶች ቢኖራቸው እንደሚመርጡ የተናገሩ ሲሆን ከ75 በመቶ በላይ የሚሆኑት ደግሞ ከአረብ እስራኤላዊ ጋር በአንድ ሕንፃ ውስጥ መኖር እንደማይፈልጉ ገልጸዋል። ጥያቄ ከቀረበላቸው ሰዎች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አንዲት

እስራኤላዊ ሴት የአረብን ወንድ ማግባቷ እንደብሔራዊ ክህደት ይቆጠራል ብለዋል፡፡ 50 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ የበላይ አለቃቸው አረብ ከሆነ ሥራ መቀጠር እንደማይፈልጉ ገልጸዋል፡፡[40] የእስራኤል ዲሞክራሲያዊ ኢንስቲትዩት የተባለው ድርጅት በወርሃ ግንቦት 2003 ባወጣው ዘገባ 53 ከመቶ የሚሆኑት የእስራኤል አይሁዳዊያን ከአረቦች ጋር በእኩልነት መታየቱን እንደሚቃወሙ ገልጿል፡፡ 31 ከመቶ የሚሆኑ ብቻ ናቸው በመንግሥቱ ውስጥ የአረብ ፖለቲካ ፓርቲዎች ቢኖሩ እንደሚደግፉ የገለጹት፡፡[41] ይህ ስሜት በትክክል በተግባር ታይቷል፡፡ እስራኤል እስከ ቅርብ ጊዜ ምንም አይነት ሙስሊም አረብ ዜጋዋን ለከፍተኛ ሹመት ሳታበቃ ቆይታ በጥር/2007 ነበር የመጀመሪያውን ሙስሊም አረብ ሚኒስትር የሾመችው፡፡ ይህም ከሞላ ጎደል እስራኤል ከተመሠረተች ከ60 ዓመታት በኋላ የተደረገ መሆኑ ነው፡፡ ሰውዬው የተሾሙት ብዙም ግምት የማይሰጠው ለሆነው የሳይንስ፣ ስፖርትና ባሕል ሚኒስትርነት ቢሆንም፣ ጉዳዩ ብዙ ውዝግብ አስነስቷል፡፡[42]

እስራኤል የአረብ ዜጎቿን የምትይዝበት መንገድ ከአድሎአዊነትም ይብሳል፡፡ ለምሳሌ በግዛቷ ውስጥ የሚኖሩትን አረቦች ቁጥር ለመገደብ ባወጣችው ሕግ መሠረት አንድ እስራኤላዊ አንድን ፍልስጤማዊ ቢያገባ የዜግነት መብቱ ይገፈፋል፡፡ እስራኤል ውስጥ እንዲኖርም አይፈቀድለትም፡፡ የእስራኤል ሰብዓዊ መብት አስጠባቂ ድርጅት (ቤተ ሰላም) ሕጉን ‹‹እዚህ እስራኤል ውስጥ ማን መኖር እንዳለበት የሚወስን በዘረኝነት መስፈርት የተዘጋጀ ዘረኛ ሕግ ነው›› ሲል አብጠልጥሎታል፡፡[43] የኢሀድ ኦልመርት መንግሥት ወደ እስራኤል ምክር ቤት የመራውና የምክር ቤቱ (ክኔሴት) የሕግ ጉዳዮች ኮሚቴ ጥር 10 ቀን 2007 ያጸደቀው ሌላው ሕግ ደግሞ ለአይሁዳዊት እስራኤል የአርበኝነት ስሜት የሌላቸውን ዜጎች ዜግነት የመግፈፍን ስልጣን ለፍርድ ቤት ይሰጣል፡፡ ይህ ሕግ በቀጥታ ያነጣጠረው በአረብ እስራኤላውያን ላይ ሲሆን፣ ዋናው ጠበቃ ይህን ሕግ፡- ‹‹ጥብቅ የሆነና ሰብአዊ መብትን ክፉኛ የሚጋፋ›› ብለውታል፡፡[44] እንግዲህ ይህን የመሳሰሉ ሕጎች በየጊዜው መውጣታቸው እስራኤል በመጀመሪያ ከተመሠረተችበት ዋነኛ መርህ (የአይሁዳዊያንን መንግሥት ከማቋቋም) ጋር

አብሮ የሚሄድ በመሆኑ አያስደንቅም። ይሁንና የእስራኤል ዲሞክራሲ የሁሉንም ዜጎች እኩልነት ከሚያጸናው የአሜሪካ ዲሞክራሲ ጋር ተመሳሳይ ነው መባሉ ያስተዛዝባል።

በ2007 ዓመት መጀመሪያ ላይ ቤንጃሚን ናታንያሁ የገንዘብ ሚኒስትር በነበሩበት ጊዜ ለአክራሪ ኦርቶዶክስ አይሁዳዊያን ኮሚኒቲ ይሰጥ የነበረውን የገንዘብ ድጎማ በማቋረጣቸው ይቅርታ ጠየቁ። ይሁን አንጂ ናታንያሁ በዚያ የይቅርታ መጠየቂያ ንግግራቸው ላይ እንዲህ በማለት አስገንዝበው ነበር፡- " ምንም እንኳን የገንዘቡ ድጎማ ቢቋረጥም፣ አንድ ያልተገመተና ጠቃሚ የሆነ ጥቅም አስገኝቷል። አይሁዳዊያን ባልሆኑ እስራኤላዊያን ማህበረሰቦች ውስጥ የወሊድ እድገቱ ዝቅ እንዲል አስችሏል።"[45] ናታንያሁ ልክ እንደሌሎቹ እስራኤላውያን ሁሉ በአረብ እስራኤላውያን አካባቢ ያለው የሕዝብ እድገት ማሻቀብ ክፉኛ የሚያሳስባቸው በመሆኑ ነበር እንደዚህ ዓይነት ንግግር ለማድረግ የደፈሩት።

ይህ የናታንያሁ አስተያየት በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ቀርቦ ቢሆን ኖሮ በእርግጠኝነት የውግዘት ውርጅብኝን ባስተናገደ ነበር። ከአንድ የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ሚኒስትር ‹‹የአፍሪካ አሜሪካዊያንና የሂስፓኒኮች የወሊድ መጠን መቀነስ የነጮችን የበላይነት ለመጠበቅ አግዟል።›› የሚል ንግግር ቢሰማ ሊያስከትለው የሚችለውን ኡኡታና ትርምስ አስቡት! እስራኤል ውስጥ ግን እንደዚህ አይነት አስተያየቶችን መስማት ያልተለመደ አይደለም። በተለያዩ ጊዜያት በርካታ የፖለቲካና የመንግሥት መሪዎች የፍልስጤማውያንንና የአረቦችን ክብር የሚነካ ንግግር ሲያደርጉ ተደምጠዋል። ሜናሂም ቤጊን አንድ ጊዜ፣ ‹‹ፍስጤማዊያን በሁለት እግራቸው የሚሄዱ አውሬዎች ናቸው።›› በማለት ተናግረዋል። የቀድሞው የእስራኤል ጦር ኤታማዦር ሹም ራፋኤል ኤታን ደግሞ እነዚያኑ መከረኛ ፍልስጤኤማውያን፡- ‹‹በጠርሙስ ውስጥ የታጨቁ በረሮዎች›› ብለዋቸዋል። እንዲሁም ‹‹የአረብ ጥሩ የሞተ ብቻ ነው" በማለት እኚህ ሰው ተናግረዋል። ሌላው የቀድሞ ኤታማዦር ሹም ሞሼ ያሎን በበኩላቸው ‹‹ፍልስጤማውያን ልክ እንደ ካንሰር በመሆናቸው ኬሞ ቴራፒ እየሰጠናቸው ነው›› ብለዋል።[46]

እንዲህ የመሰለው ጋጠወጥነት የሚንጸባረቅበት አስተያየት በእስራኤል መሪዎች ብቻ የተገደበ አይደለም። በቅርቡ በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ የተደረገ ጥናት እንዳመለከተው 75 ከመቶ የሚሆኑት ‹‹አረቦች ያልተማሩ ናቸው›› የሚል መልስ ሰጥተዋል። ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው ደግሞ ‹‹አረቦች ያልሠለጠኑ ናቸው›› ብለዋል። 74 ከመቶ የሚሆኑት በጥናቱ የተካተቱ ተማሪዎች ‹‹አረቦች ንፁህ ያልሆኑ ሕዝቦች ናቸው›› የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። የመጨረሻውን አስተያየት በተመለከተ ላሪ ደርፍነር የተባለ ሰው በእየሩሳሌም ፖስት ላይ ሲተች፡- ‹‹አረቦች ንፁህ አይደሉም ብሎ መናገር የጠጣር ፖለቲከኛነት ንግግር አይደለም። የአረቦችን ባህሪ ለማሳየት ከመጠን ያለፈ አገላለጽ መጠቀምንም አያሳይም። አረቦች ንፁህ አይደሉም የሚለው አባባል መሠረተ ቢስ፣ የሚያናድድ፣ ለምክንያት ቦታ የማይተው፣ በአንድ ሕዝብ ላይ ፍፁማዊ ጥላቻን የሚያንጸባርቅ ሲሆን፣ አረቦች ንፁህ አይደሉም ከተባለ በእርግጥ እድፋቸው ከአይሁዳዊያን እድፍ አይበልጥም። አረቦች ያልፀዱ ሕዝቦች ናቸው የሚለው አገላለጽ መሪር ከሆነ የዘረኝነት ስሜት የሚመነጭ አባባል እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም›› ብሏል። ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ጥናት የተመለከተ ሌላ ሰው ደግሞ እንደሚከተለው ብሏል፡- ‹‹ከጥናቱ በተገኘው ውጤት አልተደነቅንም። በዚህ መስክ እውቀት ያለው ማንም ሰው በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ እንዲህ ዓይነት አመለካከት መኖሩን በጥቅሉ ያውቃል። ሆኖም ግን እነዚህ ከጥናቱ ተገኙ የተባሉ ውጤቶች በጣም ከባድና የሚረብሹ ናቸው።›› ለአረብ እስራኤላውያን ወጣቶችም ተመሳሳይ መጠይቅ ቀርቦላቸው እንደነበር ማወቅ ስሜት የሚሰጥ ጉዳይ ነው። ላሪ ደርፍነር እንደታዘበው ‘‘እነርሱም ቢሆኑ ለአይሁዳዊያኑ ያላቸው አመለካከት መጥፎ ነው ማለት ቢቻልም አይሁዳውያን ተማሪዎች ለእነርሱ ካላቸው ጥላቻ ግን ያነሰ ነው” ብሏል።[47]

በአረብ እስራኤላውያን ላይ እየተባባሰ የመጣ ይህ ጥላቻ ከዐረቦች መብዛት (ዲሞግራፊ) ስጋትና የአይሁዳውያንን አሐዝ አብላጫ ከማድረግ ፍላጎት ጋር ተዳምሮ የእስራኤልን አረቦች ከሀገረ አይሁድ ጠራርጎ የማስወጣቱ ዓላማ ብዙ ደጋፊዎችን እንዲያፈራ አስችሏል። ለምሳሌ በ2006 ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆኑት አቬግዶር ሊበርማን

እስራኤልን በተቻለ መጠን የአንድ ዘር ሐገር (homoginious) ለማድረግ ሲባል አረብ እስራኤላውያንን ጠራርጎ የማስወጣቱን ዕቅድ በይፋ ደግፈዋል። ሊበርማን በተለይም በአሁኗ እስራኤል ውስጥ አረቦች በብዛት የሚኖሩበትን መሬት፣ በምዕራባዊው ወንዝ ዳርቻ በሚገኙ የእስራኤል የሠፈራ መንደሮች የመለወጥን ሀሳብ ይደግፋሉ። ለነገሩ አረብ እስራኤላውያንን ከአይሁዷ ሀገር የማስወጣትን ሐሳብ በመደገፍ ሊበርማን የመጀመሪያው የእስራኤል ካቢኔ አባል እና ሚኒስትር አይደሉም።[48]

ሊበርማን ምንም እንኳን አወዛጋቢ ፖለቲከኛ ቢሆኑም በዚህ ጉዳይ ላይ ያን ያክል ድንበር አላለፉም። የእስራኤል ዲሞክራሲያዊ ኢንስትትዩት በ2003 ባቀረበው ዘገባ መሠረት 57 ከመቶ የሚሆኑ የእስራኤል አይሁዶች፣ አረብ እስራኤላውያን ከእስራኤል እንዲወጡ ቢበረታቱ መልካም እንደሆነ ያስባሉ። በ2004 በሃይፋ ዩኒቨርስቲ የብሔራዊ ፀጥታ ጥናት ተቋም ባወጣው ዘገባ ይህ ከላይ የቀረበው አሃዝ ወደ 64.7 ከመቶ አድጓል። ከአንድ ዓመት በኋላ በ2005 በእስራኤል የፓልስታይን የጥናት ማዕከል ባወጣው ዘገባ 42 ከመቶ የሚሆኑት የእስራኤል አይሁዶች መንግሥታቸው አረቦችን በኃይል እንዲያስወጣ ይፈልጋሉ ብሏል። ሌሎች 17 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ በዚሁ ሀሳብ የመስማማት አዝማሚያ አሳይተዋል። አሁንም በቀጣዩ ዓመት የፀረ ዘረኝነት ማዕከል ባደረገው የዳሰሳ ጥናት 40 ከመቶ የሚሆኑት የእስራኤል አይሁዶች መሪዎቻቸው አረቦችን እንዲያስወጡላቸው የሚፈልጉ መሆናቸውን ያሳያል። የእስራኤል ዲሞክራሲያዊ ኢንስቲትዩት ባወጣው ሌላ ዘገባ ደግሞ ይህ ቁጥር 62 ከመቶ እንደሆነ ገልጿል።[49] ዛሬ በአሜሪካ ሀገር 40 ከመቶ የሚሆኑት ነጮች፣ ጥቁሮች፣ ሂስፓኒኮችና ኢሲያውያን ከመላዋ ዩናይትድ ስቴትስ ተጠራርገው እንዲወጡ የሚፈልጉ መሆናቸውን ቢናገሩ ታላቅ ነውጥ ይፈጠር እንደነበር የታወቀ ነው።

ይህ ዓይነቱ አመለካከት ምናልባትም በአይሁዳውያንና ፍልስጤማውያን መካከል ለረዥም ጊዜ በቆየው ውዝግብእና ውዝግቡ ለሁለቱም ወገኖች ባስከተለው ስቃይ ምክንያት የተከሰተ ነው ሊባል ይችላል። አሜሪካውያን በአንዳንድ ወገኖች (በተለይም በአፍሪካ አሜሪካውያን) ላይ የሚያሳዩት ዓይነት የጥላቻ አዝማሚያ ተደርጎም ሊወሰድ ይችላል። ይህ ዓይነቱ ስሜት

በአሜሪካ ውስጥ በስፋት ቢታወቅ አንገት የሚያስደፋና ክፉኛ የሚያሳዝን ነው፡፡ ስለሆነም እስራኤልን መርዳት ያስፈለገው ‹‹የጋራ የዲሞክራሲ እሴቶች ስላለንና ለነጻነት ባለን ቁርጠኝነት ነው›› የሚለው ምክንያት እርሾ አያነሳም፡፡

በመጨረሻም የእስራኤል ዲሞክራሲያዊነት ገጽታ ይበልጥ የጠለሸው ፍልስጤማውያን የራሳቸው የሆነ መንግሥት እንዲመሠርቱ ባለመፍቀዷ፣ እንዲሁም በኃይል በያዘቻቸው የፍልስጤማውያን መሬቶች ላይ የራሷን ፖለቲካዊ፣ አስተዳደራዊና ወታደራዊ ጫና በማድረግ መሠረታዊ የሆኑ ሰብዓዊ መብቶችን በመንፈጓ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ እስራኤል በጋዛና በምዕራባዊ ዳርቻ የሚኖሩ 3.8 ሚሊዮን ፍልስጤማውያንን ትቆጣጠራለች፡፡ እስራኤል ምንም እንኳን በ2005 በተናጠል በወሰደችው እርምጃ ጋዛን ለቅቃ የወጣች ቢሆንም፣ በሕዝቡ ላይ የምታደርገውን ጠንካራ ቁጥጥር አሁንም እንደቀጠለች ነው፡፡[50] በተለይም ደግሞ እስራኤል የአየር፣ የባሕርና የየብስ መገናኛዎችን ሁሉ በቁጥጥር ስር በማድረግ በጋዛ የሚኖሩ ፍልስጤማውያንን ልክ እንደ እስር ቤት ከጋዛ ለመውጣትም ሆነ ወደዚያ ለመግባት የእርሷን ሙሉ ፈቃደኛነት የሚጠብቁ እንዲሆኑ አድርጋቸዋለች፡፡ ጃን ኢንግላንድ የተባሉ ከፍተኛ የተባበሩት መንግሥታት ባለሥልጣንና የቀድሞው የስዊድን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኤሊሰን በመስከረም 2006 ላይ በጋራ እንደጻፉት፡- ‹‹ፍልስጤማውያን የሚገኙበት ሁኔታ በሸቦ በታጠረ ጎጆ በሚኖር እንስሳ ይመስላል፡፡ ይህ ሁኔታ በኢኮኖሚያቸው፣ በአስተሳሰባቸውና በአጠቃላይ ስብዕናቸው ላይ ልኩ ያልታወቀ ጉዳት ያስከትልባቸዋል“ ብለዋል፡፡

በምዕራባዊው ዳርቻም ቢሆን እስራኤል በየጊዜው አዳዲስ ሕጎች እያወጣች የፍልስጤማውያኑን መሬት በመቀማት የሰፈራ መንደር መመስረቷን ቀጥላለች፡፡ በዚያ የሰፈነውን ተጨባጭ ሁኔታ በታህሣሥ ወር 2006 ላይ የወጣው ሃ ኤሬትዝ ጋዜጣ በርዕሰ አንቀጹ አጠር አድርጎ ያቀረበው ሲሆን እንዲህ ይላል፡- ‹‹በዚህ የግንባታ ሂደት በእያንዳንዱ ሳምንት ማለት ይቻላል፣ ካለፈው የበለጠ ተቃውሞና ብጥብጥ ሳይከሰት በምዕራቡ ወንዝ ዳርቻ የተገነባ ሰፈር የለም። ሕጉን በመጣርና የእስራኤልን መንግሥት

ፖሊሲ በመቃወም ዘወትር አመጽ ይከሰታል፡፡››[52] አንድ የእስራኤል መንግሥታዊ ድርጅት በቅርቡ ባወጣው የጥናት ዘገባው መሠረት፡- ‹‹እስራኤል ለሰፈራ ከምትጠቀምበት መሬት ከ32 በመቶ በላይ የሚሆነው በፍልስጤማውያን የግል ይዞታ ሥር የነበረ ነው፡፡ እስራኤል ይህን ዓይነት መሬት አንድ ጊዜ ከወረሰች እስከመቼውም ለባለቤቶቹ አይመለስላቸውም፡፡ ይህ የፍልስጤማውያንን ንብረት የመውረስ ሂደት የእስራኤልን ሕግ ብቻ ሳይሆን የዲሞክራሲን መሠረታዊ ደንቦችና የግል ንብረት የማፍራትና የመያዝ መብትን ሙሉ በሙሉ የሚጻረር አሠራር ነው››[53] ብሏል፡፡

ለማጠቃለል ያክል እስራኤል በእርግጥም አይሁዳዊያን ለሆኑ ዜጎቿ ሞልቶ የሚፈስ ዲሞክራሲያዊ አሠራር ዘርግታለች። እያንዳንዱ አይሁዳዊ መንግሥትን ሳይቀር መተቸት እንዲሁም መሪውን በግልጽና በነፃ የምርጫ ሂደት መሰየም ይችላል፡፡ የመጻፍ ነፃነቱም እንደዚያው በሸበሸ መሆኑ ምፀት ቢመስልም፣ የእስራኤልን ፖሊሲ አሜሪካ ውስጥ ለመተቸት ከመሞከር ይልቅ በራሷ ምድር ያን ማድረጉ ቀላል መሆኑ ይነገራል፡፡ ለዚህም ነው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት አብዛኛዎቹ መረጃዎች ከራሷ ከእስራኤል የህትመት ውጤቶች የተገኙ ለመሆን የቻሉት፡፡ እንዲህ አይነቱ መልካም ገጽታ እንዳለ ሆኖ ግን አረብ እስራኤላውያን ስልታዊ በሆነ አሠራር ወደዳር እየተገፉ ይገኛሉ። በኃይል በተያዙት ግዛቶች የሚኖሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ፍልስጤማውያን ሙሉ ፖለቲካዊ መብታቸውን ተነፍገዋል፡፡ ስለሆነም ‹‹የጋራ ዲሞክራሲያዊ እሴቶች አሉን›› የሚለው አባባል ደካማ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

አይሁዳውያን ባለፉት ዘመናት የደረሰባቸውን መከራ ማካካስ

አይሁዳዊያንን ለማገዝ የሚቀርበው ሶስተኛው ሞራላዊ ምክንያት በክርስቲያኑ የምዕራቡ ዓለም በተለይም ደግሞ በናዚ ጀርመን የደረሰባቸው የሆሎኮስት እልቂት ነው፡፡ አይሁዳዊያን ለብዙ ምዕተ-ዓመታት ብዙ ግፍ ስለደረሰባቸው የራሳቸውን ሀገር ቢመሠርቱ ለሀገራቸው ልዩ እንክብካቤና ድጋፍ በማድረግ ከእንዲህ ዓይነቱ መቅሰፍት እነርሱን መታደግ እንደሚቻል ብዙዎቹ አመኑ፡፡ ይህ ምልከታ የመጀመሪያውን የጽዮናውያን እንቅስቃሴ ወልዶ ዩናይትድ ስቴትስና ሌሎች ሀገራት የእስራኤልን መመሥረት እንዲደግፉ እና ዛሬም ድረስ ይህንኑ እንዲያስተጋቡ መሠረት ጥሏል፡፡

አይሁዳዊያን በጸረ-ሴማዊነት ውርስ ብዙ ስቃይና ውርደት የደረሰባቸው ለመሆኑ ጥያቄ አይነሳም፡፡ ስለሆነም የእስራኤል እንደ ሀገር መመሥረት ረዥም ጊዜ ለቆዬው ለዚህ ግፍ እንደ ትክክለኛ ምላሽ ይቆጠራል፡፡ ይህ የታሪክ ሁኔታ እስራኤል እንድትመሠረትና ከተመሠረተችም በኋላ በሕልውና እንድትቆይ ጠንካራ የሞራል ምክንያት ሆኗል፡፡ ሆኖም ግን ማንም ቢሆን ሊረሳው የማይገባው ዓቢይ ክስተት፣ የእስራኤል መመስረት ባለፉት የአይሁዳውያን የታሪክ ጠባሳዎች አንድም አይነት ተሳትፎ በሌለው በንጹሁ የፍልስጤም ሕዝብ ላይ ወንጀል እንዲፈጸም አድርጓል፡፡ በአይሁዳውያኑ ላይ የተፈጸመው ወንጀል እስራኤል እንድትመሠረት ድጋፍ ያስገኘ ሲሆን፣ በፍልስጤማውያን ላይ የተፈጸመው ወንጀል ግን ምንም ዓይነት ልዩ ትኩረት አላገኘም፡፡

በዚህ የታሪክ ሂደት የተከሰቱ ነገሮች በሚገባ ተመዝግበው ተቀምጠዋል፡፡ የጽዮናዊነት ፖለቲካ በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ አካባቢ ሲወጠን ፍልስጤም ውስጥ የነበሩት አይሁዳውያን ከ15–17 ሺህ የሚሆኑ ብቻ ነበሩ፡፡[54] ለምሳሌ በ1893 95 ከመቶ የሚሆነው የፍልስጤም ሕዝብ አረብ ነበር፡፡ ምንም እንኳን ሀገሩን የሚያስተዳድሩት የአቶማን ቱርኮች ቢሆኑም፣ ፍልስጤማውያን ከዚያ በፊት ለ13 ምዕተ ዓመታት በዚያ ቦታ ላይ ነበሩ፡፡[55]

‹‹ሕዝብ ያልሰፈረባትን ምድር፣ አገር ለሌለው ሕዝብ›› በማለት ፍልስጥኤምን ከእስራኤል መመስረት በፊት ሕዝብ አልባ ሃገር አድርጎ የሚያቀርበው የጽዮናውያን ብሂል ፍጹም ስህተት ነው፡፡ ጽዮናውያን ከአውሮፓ ፈልሰው ሲመጡ በፍልስጥኤም ምድር ላይ ብዙ ሕዝብ ይኖር ነበር፡፡[56]

የመጀመሪያዎቹ ጽዮናውያን ተስፋ አድርገው የነበረው አይሁዳውያን በ20ኛው መቶ ክ/ዘመን የመጨረሻዎቹ አስር ዓመታት ከአውሮፓ እየፈለሱ ወደ ፍልስጤም በብዛት በመሰደድ አካባቢውን ያጥለቀልቁታል፤ በዚህም የተነሣ ፍልሰቱ የአይሁዳውያኑ ቁጥር በሥፍራው ከሚኖሩት ፍልስጤማውያን የበለጠ እንዲሆን ያስችላል ብለው ነበር ፡፡ ግና እነርሱ ያሰቡት አልሆነም፡፡ ምክንያቱም ብዙ አይሁዳውያን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ መጓዝን ነበር የመረጡት፡፡ ከ1880–1920 ባለው ጊዜ ውስጥ ከአውሮፓ ከፈለሱት አራት ሚሊዮን አይሁዳውያን መካከል ወደ ፍልስጤም ለመሄድ የመረጡት አንድ መቶ ሺህ የሚሆኑት ብቻ ነበሩ፡፡[57] በእርግጥም ሂትለር እስኪነሳ ድረስ ፍልስጤምን ከቱርኮች ቀምተው ያስተዳድሩ የነበሩት እንግሊዞች የሰጧቸውን የፍልሰት ኮታ አይሁዳዊያኑ መሙላት አልቻሉም ነበር፡፡[58] በ1948 እስራኤል ስትመሠረት በፍልስጤም የነበሩት አይሁዳውያን 650,000 ሲሆኑ፣ ይህም ከፍልስጤም አጠቃላይ ሕዝብ 35 ከመቶ የሚሆነውንና ከምድሯ ደግሞ 7 ከመቶ የሚሆነውን ብቻ የሚሸፍን ነበር፡፡[59]

ጽዮናውያኑ ወደ ፍልስጤም ሲገቡ ያሰቡት ሁሉንም የፍልስጤም ምድርና ከሊባኖስና ከሶሪያ የተወሰነውን ክፍል የሚሸፍን የአይሁዳውያን መንግሥት (ታላቋን እስራኤል) ለመመስረት ነበር፡፡[60] ምንም እንኳን በጽዮናዊያኑ መካከል አዲስ የሚመሠረተው መንግሥት ድንበሮቹ የት ድረስ እንደሚሆኑ ስምምነት ያልነበረ ቢሆንም፣ ግዛት የማስፋት ሕልማቸው ያሰቡትን ያህል ላይሳካ እንደሚችል ሁሉም ገምተዋል፡፡ ዋነኞቹ የጽዮናውያን አመራሮች በምንም መልኩ በፍልስጤም ግዛት ውስጥ አረቦችና አይሁዶች ጎን ለጎን የሚኖሩበትና የሃይማኖት ማንነት ያልተለየበት እንዲሁም ከአይሁዳውያን የሚበልጥ ቁጥር ያላቸው አረቦች የሚገኙበት መንግሥት መመሥረት እንደማይፈልጉ ተስማምተዋል፡፡ አይሁዳውያኑ ያስቀመጡት ግብ

ከመጀመሪያው ቢያንስ ከሕዝቡ 85 ከመቶ የሚሆነው አይሁዳዊ የሆነባት የአይሁድ ሀገር መመሥረት ነበር።[61]

የጽዮናውያኑ ምኞትና ፍላጎት የፍልስጤምን ምድር ከፍልስጤማውያን ጋር በቋሚነት መካፈል ከሚለው በላይ ርቆ የሄደ ነበር ማለት ይቻላል። በዩናይትድ ስቴትስ በተለይም ደግሞ በእስራኤል ደጋፊዎች ዘንድ ሲታመንበት የነበረው ጽዮናዊያን የፍልስጤምን ምድር በቋሚነት ለሁለት መከፈል እንደሚደግፉ፣ ማለትም የእንግሊዝ የግዛት መከፋፈል ጉዳይ ኮሚሽን በ1937 ያቀረበውን እቅድና እንዲሁም በ1947 በተባበሩት መንግሥታት የቀረበውን ሌላ እቅድ እንደሚቀበሉ ነበር። ሆኖም ግን ይህን እቅድ ጽዮናውያን ለጊዜው መቀበላቸው በዚያ ምድር ላይ ሌላ የፍልስጤማውያን መንግሥት ለዘለቄታው እንዲቋቋም መፍቀዳቸው አልነበረም። በቅርብ ጊዜ የተነሱ ምሁራን ያንን ራቅ ያለ ዘመን የፖለቲካ አስተውሎት እየዳሰሱ ሲተቹ እንዲህ ይላሉ፦ ‹‹የጽዮናውያን መሪዎች የፍልስጤምን ምድር ለሁለት መከፈል እንደ መጀመሪያ ደረጃ ስልት ይቀበላሉ። ሆኖም ግን ይህ የፖለቲካ ጨዋታ እንጂ እውነተኛው ዓላማቸው ያ አልነበረም። በረዥም ጊዜ እይታ ከእነርሱ ሀገር ጎን የሚቆይ የፍልስጤማውያን መንግሥት እንዲኖር አይሹም ነበር። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነት ክስተት ለረዥም ጊዜ መላዋን ፍልስጤም የሚጠቀልል የሆነ የአይሁድ መንግሥት ከማቋቋም ሕልማቸው ጋር የሚጋጭ ነውና።››

የፍልስጥኤም ምድር ለሁለት እንዲከፈል የሚያዘው የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ ገና እንደተሰማ ጽዮናውያኑ በጽኑ ነበር የተቃወሙት። መሪያቸው ዴቪድ ቤን ጎሪዮን ጽዮናውያን ያንን ሀሳብ እንዲቀበሉ ለማግባባት ብዙ ደክመዋል። በመጨረሻ ላይ ግን ውሳኔውን ለመቀበል ተስማሙ። ምክንያቱም ዴቪድ ቤንጎሪዮን የኋላ ኋላ ሁሉንም የፍልስጤም መሬት ቀስ በቀስ ለመንጠቅ እንደሚቻል አሳምነዋቸው ስለነበር ነው። የጽዮናዊያኑ መሪ ቤን ጎሪዮን በ1937 ለጽዮናዊያኑ ጉባዔ እንዲህ የሚል ንግግር አድርገው ነበር፦ ‹‹ጠንካራ ወታደራዊ ሐይል ያለው የአይሁድ መንግሥት እንደተመሠረተ ይህን ክፍፍል የሚባል ነገር አስወግደን ሁሉንም የፍልስጤም ምድር ጠቅልለን እንይዘዋለን።›› በተመሳሳይ ሁኔታ

ለልጃቸው ለአሞስ በዚያው ዓመት ቤንጎሪዮን እንዲህ ብለውት ነበር፡- ‹‹ሁሉንም የፍልስጤም ምድር ባያካትት እንኳን አንድ ጊዜ የአይሁዶችን መንግሥት እንደምንም አቋቁም። ከዚያ በኋላ የቀረው በጊዜ ሂደት ቀስ በቀስ ይመጣል፡፡ የግድ መምጣትም አለበት፡፡››[62]

በ1937 የቀረበው የእንግሊዞች ግዛት የማካፈል እቅድ የትም ሊራመድ አልቻለም፡፡ ምክንያቱም ጽዮናውያኑ እስከመጨረሻው የፍልስጤምን ምድር ሁሉንም ጠቅልለው በመያዝ በወደፊቱ የአይሁድ መንግሥት ሥር እንዲሆን ነበርና የሚፈልጉት። ቤን- ጎሪዮን በ1947 የመጀመሪያው አጋማሽ አካባቢ ብዙ ዓይነት አስተያየቶችን ይሰጡ የነበሩ መሆኑን ስናጤን መላዋን ፍልስጤም ለመጠቅለል ይከጅሉ እንደነበር መገንዘብ አይከብደንም፡፡ ለምሳሌ እስራኤላዊው ምሁር አሪ ቤን ኤሊዘር እንዲህ በማለት ጽፈዋል፡-

‹‹በዩናይትድ ስቴትስ ግንቦት 13 ቀን 1947 በተደረገው የአይሁዳውያን ተወካዮች ስብሰባ ላይ ቤን ጎሪዮን እንዲህ አሉ፡- ‹እኛ የምንፈልገው ለእስራኤል የሚገባትን መሬት በሙሉ ነው፡፡ ይህ ነው የመጀመሪያው ሀሳባችን፡፡› ከሳምንት በኋላ ደግሞ እየሩሳሌም ውስጥ ለተሰበሰቡ አይሁዳውያን የሚከተለውን ጥያቄ አቀረቡ፡- ‹ከእኛ መካከል የመጀመሪያውን የባልፎር አዋጅ (ዲክላሬሽን)፣ እንዲሁም የአይሁድ ሕዝብ ሊመሠርተው ያሰበው መንግሥት መላዋን ፍልስጤም ሊያጠቃልል እንደሚገባ ያለንን ፍላጎት የሚቃወም ይኖራልን?› ቤን ጎሬዮን በሰኔ ወር ላይም ለአንድ የአይሁዳውያን ጉባዔ ከዚያች ምድር አንድም ስንዝር መሬት ለማጣት እንደማይፈልጉ ሲገልጹ፣ ‹ ይህን ብናደርግ ትልቅ ስህተት እንደሠራን ይቆጠራል፡፡ ከመሬታችን ምንም ያክል አነስተኛ ብትሆን እንኳን ቆርሰን ለመስጠት መብት የለንም › በማለት አስረግጠው ተናግረዋል፡፡[63]

በዚያው ዓመት ህዳር ወር ላይ የተባበሩት መንግሥታት የፍልስጤምን ምድር ለጽዮናውያንና ለፍልስጤማውያን አረቦች ለማካፈል እቅድ አቀረበ፡፡ ጽዮናውያን ይህን እቅድ በይፋ ተቀበሉት፡፡ ይሁን እንጂ ቤን ጎሪዮን ከትራንስ ጆርዳን ንጉሥ አብዱላህ ጋር በሚስጢር የፍልስጤምን ምድር ለመከፋፈልና የፍልስጤም መንግሥት የሚባል ነገር እንዳይኖር ለማድረግ

ተስማምተው ነበር።[64] እንግሊዝም ጭምር ይሁንታዋን ያሳየችበት ይህ ምስጢራዊ ድርድር ትራንስ ጆርዳን (የአሁኗ ዮርዳኖስ) ምዕራባዊውን የወንዝ ዳርቻ እንድትወስድና እስራኤል ደግሞ የቀረውን የፍልስጤም መሬት እንድትይዝ የሚያደርግ ነበር። ስምምነቱ የኋላ ኋላ በ1948ቱ ጦርነት ወቅት በተበታተነ መልኩም ቢሆን ተግባራዊ ሆኗል። የእስራኤል መሪዎች ጦርነቱ በሚካሄድበት ጊዜ ምዕራባዊውን ወንዝ ዳርቻ ለመውረርና አጠቃላይዋን የፍልስጤም መሬት ለመያዝ ማሰባቸው አያስደንቅም። ይሁን እንጂ ከሚያስገኘው ጥቅም የበለጠ የሚያስከፍለውን ዋጋ መዘነው ነበር ለጊዜው የተውት። በውላቸው መሠረተ ትራንስ ጆርዳን እስከ 1967ቱ የስድስቱ ቀን ጦርነት ምዕራባዊውን ዳርቻ ተቆጣጥራ ቆይታለች። ከዚያ በኋላ ግን እየሩሳሌምን ጨምሮ ምዕራባዊው ዳርቻ (West bank) በአይሁዶች እጅ ገባ። በአጭሩ የእስራኤል መሥራች አባቶች በመባል የሚታወቁት እነ ቤንጎሪዮን ከመጀመሪያው ጀምረው ‹‹ታላቋን እስራኤል›› በመመሥረት ሕልም ናውዘው የነበረ ሲሆን፣ ይህ እቅዳቸው ደግሞ የፍልስጤማውያን መንግሥት ለሚባል ነገር ምንም ዓይነት ክፍተት የሌለውና ከአይሁዳውያን መንግሥት ሥር ለሚኖሩ ፍልስጤማውያን ደግሞ ትንሽ ቦታ ብቻ የሚተው ነበር።

በጊዜው አረቦች ከአይሁዳውያን በቁጥር የሚበልጡ መሆናቸውና ጽዮናውያኑ ደግሞ የቻሉትን ያክል መሬት በቁጥጥራቸው ሥር ማድረጋቸው እስራኤል የሚባል አገር የሚመሠረት ከሆነ ፍልስጤማውያኑን ከማባረር የተሻለ ምርጫ እንዳይኖራቸው አድርጓቸዋል። በዚያ ወቅት የአይሁድ ሀገር ምሥረታን ሕልም እውን ለማድረግ ለሚፈልጉት አይሁዳውያን የፍልስጤም አረቦች መሬታቸውን በፈቃደኝነት በመልቀቅ ትብብር የሚያሳዩበት ምንም ዓይነት ተጨባጭ ምክንያት አልነበረም። ለዚህም ነው የተባበሩት መንግሥታት ያወጣውና 55 ከመቶ አይሁዳውያንና 45 ከመቶ አረቦች የሚኖሩበት የእስራኤል መንግሥት እንዲመሠረት የሚያዘው እቅድ ተግባራዊ ሊሆን ያልቻለው።[65] ምክንያቱም ብዙ ቁጥር ያላቸውን አረቦች ከዚያ ቦታ እንዲለቅቁ ማሳመን ካልተቻለ በስተቀር የአይሁድን መንግሥት መመስረት የማይታሰብ ነበርና።

ከፍልስጥኤማውያን ጋር በተያያዘ ይለውን የዲሞግራፊ ችግር ለማስወገድ ብቸኛው መፍትሄ ፍልስጥኤማውያንን ማፈናቀል መሆኑን ጽዮናውያን ገና ከእንቅስቃሴያቸው መነሻ ጊዜ ጀምሮ እንዳመኑበት እነዚህ እውነታዎች በጉልህ ያሳያሉ።[66] ዴቪድ ቤን ጎሪዮን ቀደም ብለው በ1941 እንደጻፉት ‹‹አረቦችን ሳናፈናቅልና የጭካኔ ተግባር በመፈጸም ሳናባርር[60] አጠቃላይ የሆነ የአረብን ሕዝብ ፍልሰት እውን ልናደርግ አንችልም››[67] ብለዋል። ‹‹እንዲሁም ለልጃቸው ጥቅምት 1937 በጻፉት ደብዳቤ፦ ‹‹ዘመናዊ የሆነ የመከላከያ ሠራዊት እንገነባለን። ...ከዚያ በኋላ ከአረብ ጎረቤቶቻችን ጋር በሚደረግ ስምምነትም ይሁን በሌላ በማንኛውም መንገድ በቀረው የፍልስጤም ግዛት እንዳንሰፍር የሚያግደን ኃይል አይኖርም።››[68] ብለዋል። ቤንጎሪዮን ይህን ሀሳባቸውን በሰላማዊ ስምምነት ቢያደርጉት ይመርጡ እንደነበር መገንዘብ አይከብድም። ሆኖም ግን እርሳቸው ትኩረት የሰጡት በመጀመሪያ ጽዮናውያን ጠንካራ የመከላከያ ሠራዊት እንዲኖራቸው በማድረጉ ላይ ነበር። ‹‹ቤን-ጎሪዮን በእርግጥም አርቆ አሳቢ ነበሩ›› ይላሉ ሞሪስ። ‹‹ምክንያቱም ብዛት ያላቸውና በቁጣ የነደዱ ፍልስጤማውያንን በአናሳነት ሊይዝ የሚችልና በዚህ መልኩ በሰላም የሚዘልቅ የአይሁድ አገር ሊኖር እንደማይችል ግልጽ ሆኖላቸው ነበርና። ስለሆነም ቤን ጎሪዮን ትክክል ነበሩ። ያደረጉትን ባያደርጉ ኖሮ የተመኟት እና ብዙ የደከሙላት የአይሁድ ሀገር አትገኝም ነበር። እዚህ ላይ ሁላችንም ግልጽ መሆን አለብን። ምንም አደባብሰን ልናልፈው የሚገባ ጉዳይ አይኖርም። ፍልስጤማውያንን እነ ቤን-ጎሪዮን ባደረጉት መልኩ ከሥራቸው መንግሎ በመጣል እስከወዲያኛው ከሀገራቸው ተፈጥመው እንዲባረሩ በማድረግ ካልሆነ አሁን እስራኤል የሚሏት የአይሁድ ሀገር እውን አትሆንም ነበር።››[69] በማለት ሀሳባቸውን ይደመድማሉ።

ሕዝብን ማፈናቀል አስፈሪና አወዛጋቢ ስትራቴጂ መሆኑ አይካድም። ዳሩ ግን የጉዳዩ ተጠቃሚ ለሆነው አካል ሁኔታው በዓለም ፊት ቢገለጽና መጫጫህ ቢከሰት ዋናው ዓላማ እስከተሳካ ድረስ ብዙም ስሜትን አይጎዳም። ቤን ጎሪዮን የአረብን ሕዝብ በምን ብልሃት እንደሚያስወግዱ ግራ የገባቸው መሆኑን ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ፍልስጤማውያን

በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ከኖሩባቸው ቀያቸው በጭካኔ ከማፈናቀል ውጭ ሌላ ዘዴ ሊከሰትልኝ አልቻለም፡፡ እኛ ጽዮናውያን ሀገራችንን ለመመሥረት የረዱንን እንግኢዞችን ወይም አሜሪካውያንን አላስከፋንም፡፡ ባይሆን ይህን እቅዳችንን በዋናው መርሃ-ግብራችን አካትተን ይፋ ማውጣት የለብንም››[70] ቤንጎሪዮን ይህን ሲሉ የማፈናቀሉን ሂደት ውድቅ እያደረጉ አልነበረም፡፡ ሆኖም ግን ጽዮናውያን የማፈናቀል ድርጊታቸውን ይፋ አውጥተው መሥራት የለባቸውም ማለታቸው እንጂ። ቤኒ ሞሪስ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹ይህ አንጡራዎቹን ሕዝቦች ከፍልስጤም ምድር የማፈናቀል ዕቅድ በጣም አደገኛ እርምጃ እንደመሆኑ ለውይይት በሚቀርብባቸው መድረኮች ሁሉ የቃለ-ጉባዔ ፀሐፊዎች እረፍት እንዲያደርጉ ይጠየቁና በዝግ ውይይት ይደረግበታል፡፡ በወረቀት ላይ ምንም የሚያሰፍር ነገር አይኖርም፡፡ ይህ ዓይነቱ አሠራር ለጽዮናውያን አባቶች የተለመደ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በተጨማሪም ቤን ጎሪዮንም ሆኑ ባልደረቦቻቸው የጽዮናውያን መሪዎች ሌሎች ጉዳዮችን አስመልክተው በሚሰጧቸው መግለጫዎች ስማቸው መነሳቱ የተለመደ ቢሆንም፣ ታላቁን የማፈናቀል ተልዕኮ በተመለከተ ግን የአንዳቸውም ስም ተነስቶ አያውቅም፡፡››[71]

ፍልስጤማውያንን ከቀያቸው የማፈናቀሉ ተግባር የተጀመረው በ1948 ሲሆን፣ የአይሁድ ኃይሎች ሰባት መቶ ሺህ የሚሆኑትን አፈናቅለው ለስደት ዳርገዋቸዋል፡፡[72] እስራኤልና በዩናይትድ ስቴትስ የሚገኙ ደጋፊዎቿ ‹‹አረቦች የፈለሱት መሪዎቻቸው በአይሁዳውያን ላይ ለሚወስዱት መጠነ ሰፊ እርምጃ መንገዱን ንጹህ ለማድረግ ነው›› የሚል ክስ ያቀርባሉ፡፡ ሆኖም ግን ይህን አባባል ብዙ ምሁራን የፈጠራ ወሬ ነው በማለት ያጣጥሉታል፡፡ አይሁዳውያን እንደሚሉት ሳይሆን እንዲያውም ከዚያ በተቃራኒው የአረብ መሪዎች ፍልስጤማውያን ከቀያቸው እንዳይነቃነቁ ነበር በጥብቅ ያሳስቧቸው የነበረው፡፡ ሆኖም ግን በጽዮናውያን እጅ ስቃይና ሞትን ከመቅመስ ነፍሳቸውን ማትረፍ እንደሚሻል በማመናቸው ነበር ብዙዎቹ ሀገራቸውን ጥለው የወጡት፡፡[73] ጦርነቱ እንደተጠናቀቀም እስራኤል የፍልስጤም ስደተኞች ወደ ቀያቸው እንዳይመለሱ አገደች፡፡

በ1948 ቤን ጎሪዮን ‹‹የእነርሱን ወደ ሀገር ቤት መመለስ በማንኛውም መስዋዕትነት ማገድ አለብን ›› በማለት ተናገሩ።[74] በ1962 እስራኤል ከሞላ ጎደል በድንበሯ ውስጥ የሚኘውንና 93 ከመቶ የሚሆነውን መሬት ተቆጣጠረች።[75] ይህን ለማሳካትና እዚህ ግብ ላይ ለመድረስ 531 የሚሆኑ መንደሮችን ከነዋሪዎቻቸው የማጽዳቱ ሥራ ተጠናቀቀ።[76] የእስራኤልን መንግሥት ለማቋቋም አይሁዶች በፍልስጤማውያን ላይ ያወረዱባቸውን መቅሰፍት የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት ሞሼ ዳያን ሲገልጹ፡- ‘‘በአረብ መንደሮች ምትክ የአይሁዳውያን መንደሮች ተገነቡ። የእነዚያን የአረብ መንደሮች ስሞች ልታውቁ እንደማትችሉ እገነዘባለሁ። ለዚህ ደግሞ ተጠያቂዎች አይደላችሁም። ምክንያቱም የአረብ መንደሮችን የሚያሳዩ የመልክዓ ምድር ካርታዎች ከነስሞቻቸው ተወግደዋልና። .....በዚህች አገር እያንዳንዱ አዲስ የአይሁድ መንደር የተገነባው በነባሮቹ የአረብ መንደሮች ፍርስራሽ ላይ ሲሆን መንደሮቹም በነዋሪዎች የተሞሉ ነበሩ’’[77] ብለዋል።

እስራኤል የምትሰኝ ሀገር የተገነባችው በፍልስጤማውያን ላይ በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በተፈጸመ ግፍ መሆኑን የእስራኤል መሪዎች ሳይቀር አያስተባብሉም። ቤን ጎሪዮን የዓለም አይሁድ ኮንግረስ ፕሬዚዳንት ለነበሩት ኑሃም ጎልድማን በ1956 እንዲህ እንዳሏቸው ተዘግቧል፡- ‹‹እኔ የአረብ መሪ ብሆን ኖሮ ከእስራኤል ጋር ምንም ዓይነት ስምምነት አላደርግም ነበር። ይህ ተፈጥሮአዊ ነው። እኛ ሀገራቸውን ወሰድንባቸው። እርግጥ ነው እግዚአብሔር ለእኛ ቃል የገባልን ምድር ነው። ሆኖም ግን ይህ ለእነርሱ ምናቸው ነው? የእኛ አምላክ የእነርሱ አይደለም። እኛ የወጣነው ከእስራኤል ነው። ሆኖም ግን ያ የሆነው ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት ሲሆን ይህ ለእነርሱ ምን ትርጉም ይኖረዋል? ፀረ-ሴማዊነት በአውሮፓ ነበር። ናዚ፣ ሂትለር፣ ኦሽዊትዝ፣ ይህ ሁሉ የእነርሱ ጥፋት ነው እንዴ? እነርሱ የሚያውቁት አንድ ነገር ብቻ ነው። እኛ መጥተን ሀገራቸውን ስንወስድባቸው በዓይናቸው አይተዋል፣ በቃ። ታዲያ ይህን እንዴት ሊቀበሉት ይችላሉ?››[78]

የእስራኤል የቀኝ ክንፍ ፓርቲ መስራች አባት የሚባሉት ዜቭ ጃቦትንስኪ በ1923 በጻፉት ማስታወሻ ተመሳሳይ ሀሳብ አንጸባርቀዋል፡- “ቅኝ አገዛዝ

በራሱ ገላጭ (Self-explanatory) ሲሆን፣ የሚያመለክተውን ነገር እያንዳንዱ አይሁዳዊና አረብ የሆነ ሁሉ ሙሉ በሙሉ ይገነዘበዋል። ለቅኝ ግዛት የሚያበቃው ምክንያት አንድ ብቻ ነው። ለዚህች ሀገር አረቦች ደግሞ ያ ምክንያት ተቀባይነት የለውም። ይህ ተፈጠሮአዊ አጸፋ እንደመሆኑ ምንም ነገር ሊቀይረው አይችልም።››[79] በርል ካትዝኔልሰን የተባሉ የቤንጎሪዮን ጓደኛና ከቀደምት ጽዮናውያን ምሁራን አንዱ የሆኑት ሰው ሃቁን በግልጽ እንዲህ በማለት ነበር ያስቀመጡት፡- ‹‹የጽዮናውያን ሥራ መሬት የመቀማት ሥራ ነው።››[80]

እስራኤል እንደ ሀገር ከተመሠረተች ካለፉት ስድስት አሥርተ ዓመታት ጀምሮ መሪዎቿ የፍልስጤምን ሕዝብ ብሔራዊ ፍላጎት ሲክዱ ቆይተዋል።[81] ጠቅላይ ሚኒስትር ጎልዳሚዮር ለምሳሌ ታዋቂነትን ባተረፈው ንግግራቸው ‹‹ፍልስጤማውያን የሚባሉ ሕዝቦች የሉም›› ሲሉ ተደምጠዋል።[82] በርካታ የእስራኤል መሪዎች ምዕራባዊውን ዳርቻና ጋዛ ሰርጥን ወደ እስራኤል የመቀላቀል ጽኑ ፍላጎት አንጸባርቀዋል። ለምሳሌ በ1949 ሞሼ ዳያን የእስራኤልን ድንበሮች አስመልክተው አስተያዬታቸውን ሲሰጡ፡- ‹‹ምሥራቃዊው ድንበሯ የዮርዳኖስ ወንዝ ነው›› ብለዋል። ዳያን ይህን ማለታቸው የተለዬ አያደርጋቸውም። ምክንያቱም ሌሎች ጀኔራል ባልደረቦቻቸውም ሌላው ቀርቶ ቤንጎሪዮንም ራሳቸው ምዕራባዊያን ዳርቻ የእስራኤል አካል ለማድረግ ሁልጊዜም እንደቋመጡ ነው የኖሩት።[83] ቤን ሞሪስ፡- ‹‹የታላቋ እስራኤል ራዕይ ከጽዮናውያን የመጨረሻ ግብ አንጻር ከ1948ቱ ጦርነት ጋር አላበቃም››[84] ማለታቸው ፍፁም ትክክለኛ አገላለጽ ነበር።

የመጀመሪያው ኢንቲፋዳ በ1987 እንደፈነዳ የተወሰኑ የእስራኤል መሪዎች በምዕራቡ ዳርቻና በጋዛ ሰርጥ ውስን የሆነ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ለፍልስጤማውያን ለመስጠት ተስማሙ። ጠቅላይ ሚኒስትር ይስሀቅ ራቢን የ1993 ቱን የኦስሎ ስምምነት ሲፈርሙ በኃይል በተያዙት ግዛቶች ከሞላ ጎደል የሚሠራ የሆነ መንግሥት እንደሚፈቅዱ በተደጋጋሚ ይናገሩ ነበር። ይሁን እንጂ ይህ አመለካከት ትክክል አልነበረም። ራቢን የተሟላ ሥልጣንና ሉዓላዊነት ያለው የፍልስጤም መንግሥት እንዲመሠረት

አይፈልጉም ነበር። በ1995 በተገደሉበት ዓመት እንዲህ በማለት ተናግረዋል፦ ‹‹እስራኤል የአይሁዳውያን መንግሥት ሆና በምትቆጣጠረው መሬት በሁሉም ወይም በአብዛኛው ዋና ከተማዋን ያልተከፋፈለችው እየሩሳሌም አድርጋ በሰላም እንድትኖር እሻለሁ። ከእርሷ ቀጥሎ ደግሞ ከመንግሥት አነስ ያለ የፍልስጤማውያን ይዞታ እንዲኖርና የፍልስጤማውያንን ሕይወት እንዲደግፍ፣ ሁለቱ አካላትም በሰላም እንዲኖሩ እሻለሁ።... የእኔ ግብ ይህ እንጅ ወደ ቅድመ ስድስቱ ቀን ጦርነት ይዞታ መመለስ አይደለም...››[85]

እስራኤል የፍልስጤም መንግሥት ራሱን ችሎ እንዲቋቋም የማትፈልግ መሆኗን ከሚገልጹ ጥልቅ ተቃውሞዎች አንዱ ኢጋጣሚ የተፈጠረው በ1998 የጸደይ ወራት ቀዳማዊት እመቤት ሂላሪ ክሊንተን ንግግር ባሰሙ ጊዜ ነበር። ክሊንተን፦ ‹‹በመካከለኛው ምሥራቅ ዘላቂ ሰላምና ፀጥታን ማረጋገጥ ከተፈለገ ሉዓላዊነቱ የተረጋገጠ ዘመናዊ የፍልሰጤማውያን መንግሥት መመሥረት ይኖርበታል›› የሚለውን ንግግራቸውን ባደረጉ ጊዜ እስራኤውያንና አሜሪካውያን ደጋፊዎቻቸው የሰላ ትችት ነበር የሰነዘሩባቸው። በኒው ዮርክ ታይምስ ዘገባ መሠረት የዋይት ሃውስ ባለሥልጣናት ‹‹የሴትዮዋ ንግግር የራሳቸው አቋም እንጂ የአሜሪካን መንግሥት አቋም የሚወክል አይደለም›› በማለት ማስተባበያ ሰጡ። የዋይት ሃውስ ፕሬስ ፀሐፊ እንዲህ አሉ፦ ‹‹ይህ አስተያየት የፕሬዚዳንቱ አስተያየት አይደለም።››[86]

ይሁን እንጂ በ2000 የአሜሪካ ፖለቲከኞች ስለ ፍልስጤም መንግሥት መመሥረት በይፋ መናገራቸው ተቀባይነት እያገኘ የመጣበት ጊዜ ነበር። እንደዚያም ቢሆን እስካሁንም ድረስ የትኛውም የእስራኤል መንግሥት ፍልስጤማውያን በተጨባጭ የራሳቸውን መንግሥት እንዲያቋቁሙ ሲፈቅድ አልታየም። ኢሁድ ባራክ በሐምሌ 2000 ላይ በካምፕ ዴቪድ ይፋ ያደረጉት ቀናነት ታየበት የተባለው የሰላም ሀሳብ አንድ የፍልስጤም መንግሥት እንዲቋቋም ይፈቀድና፣ ሆኖም ግን የራሱ የመከላከያ ኃይል የሌለውና በእስራኤል ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ይጠይቃል። የቀድሞው ጠቃላይ ሚኒስትር ይስሃቅ ሻሚር በ2002፣ ፍልስጤማውያን ምንም

ዓይነት መንግሥት እንዲመሠርቱ የማይፈልጉ መሆኑን ደጋግመው በመናገር ተቃውሟቸውን ያሰሙ ነበር፡፡ በቀጣዩ ዓመት ቤንጃሚን ኔታንያሁ ከፊል ሎዓላዊ የሆነ የፍልስጤማውያን መንግሥት እንዲመሠረት ብቻ የሚፈልጉ መሆኑን ይፋ አድርገዋል፡፡[87]

አውሮፓውያን በአይሁዶች ላይ የፈጸሙት ወንጀል ለእስራኤል በሕልውና መቀጠል ጠንካራ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል። በተጨማሪም አዲስ መንግስት ወደ ሕይወት ለመምጣት የተወሰነ ግጭት መከሰቱ አይቀርም፡፡ እስራኤል ግን በፍልስጥኤማውያን ላይ ለብዙ አስርት ዓመታት ግፏንና አግላይ ፖሊሲዋን ቀጥላለች። እነዚህን ፖሊሲዎች ለመቀጠል ‹‹የእስራኤል በሕልውና መቀጠል›› ጉዳይ ምክንያት ሆኖ ሊቀርብ ፈጽሞ አይችልም፡፡ ምክንያቱም ጽዮናዊያን ለዚህ የዓረቦች ተቃውሞ የሚሰነዝሩት አጸፋ በጭካኔ የተሞላ ነበር፡፡ ስለዚህ ከሁለቱ ባላንጣ ወገኖች መካከል አንዳቸውም በዚህ የታሪክ ወቅት ሞራላዊ መሠረት አልነበራቸውም፡፡ እስካሁን ባየናቸው የተለያዩ ምልከታዎች የእስራኤል በሕልውና መኖር ጥርጣሬ ላይ አልወደቀም፡፡ ምንም እንኳን የኢራኑ ፕሬዚዳንት ማህሙድ አህመዲን ኤጃድ ‹‹እስራኤል ከምድረ ገጽ መወገድ አለባት››[88] በማለት ቢናገሩም ይህ የሚታሰብ አይደለም፡፡ በዋነኛነት የአይሁድ ሕዝቦች ባለፉት ዘመናት መከራ ማየታቸው እስራኤል ዛሬ የፈለገችውን ብትፈጽምም እንኳን ዩናይትድ ስቴትስን ሁልጊዜም ድጋፏን እንድትሰጣት ከሚያደርግ ግዴታ ውስጥ አያስገባትም፡፡

ደግ አድራጊ እስራኤላውያንና መጥፎ አረቦች!

ሌላው ሞራላዊ ምክንያት እስራኤል ከአረቦች ጋር በሚፈጠር በማንኛውም ግጭት፣ በተቆጣች ጊዜ ሳይቀር የተከበረና ሲቪሎችን የማይጎዳ ባህሪ ታሳያለች፡፡ በተቃራኒው ደግሞ አረቦች ጥፋት ሲያደርሱ ሲቪሉን ከወታደሩ ሳይለዩ በመሆኑ መጥፎ ናቸው የሚል ሲሆን፣ ይህ አባባል በእስራኤል መሪዎችና በአሜሪካውያን ደጋፊዎቻቸው ዘወትር ይነገራል፡፡ ፔርትዝ የተባሉ ምሁር ይህን የእስራኤል አሠራር፡- ‹‹ጉዳት ከማድረስ መታቀብ፣ በሚል መመሪያ ወይም ፍልስፍና የሚታገዝና ማንኛውም እርምጃ አቅም በፈቀደ መጠን ሲቪሎችን የማይጎዳ እንዲሆን የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም በእስራኤል ወታደሮች ላይ ተጨማሪ አደጋ የሚደቅን ቢሆን እንኳን ተፈጻሚነት ይኖረዋል›› በማለት ያሞካሸዋል፡፡ ፔርትዝ በተጨማሪም እንዲህ ይላል፡- ‹‹እስራኤል ለዓመታት ያክል ለአሸባሪዎች ጥቃት ተገቢ መልስ በመስጠትና እነርሱ የጠየቁትን ነገር በከፊል እንዲያገኙ አድርጎ ጥቃታቸውን በማቀዝቀዝ መሐል ስታወላውል ኖራለች፡፡ አረብ ጠላቶቿ ግን በእኛ በአሜሪካውያን ላይ መስከረም 11 የደረሰው ሽብርተኝነት አካል ናቸው››[89] የእስራኤል ጦር በአሪዮል ሻሮንና ኢሁድ ኦልመርት አባባል መሠረት፡- ‹‹በዓለም ላይ ካሉ ሠራዊቶች ሁሉ ሞራላዊ ይዞታው ከፍ ያለ ነው››[90] የሚደንቀው ነገር እንዲህ ዓይነቱ የእስራኤል ባህሪ ራሱ ተረት ወይም አፈታሪክ መሆኑ ነው፡፡ የቀድሞው የእየሩሳሌም ምክትል ከንቲባ ሜሮን ቤንቬንስቲ ሁኔታውን ሲገልጹት ‹‹የእስራኤል የተቀደሰ ትውፊት››[91] ብለውታል፡፡

የእስራኤል ምሁራን እንደሚገልጹት ቀደምት ጽዮናውያን ለፍልስጤማውያን አረቦች ሀዘኔታና ርህርሄ ይሉት ነገር የማያውቁ ነበሩ፡፡[92] የአረብ ነዋሪዎች አንዳንድ ጊዜ የጽዮናውያኑ ግፍ ሲበዛባቸው ይገድሏቸውና ቤታቸውንም ያቃጥሉባቸው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ጽዮናውያኑ የራሳቸውን መንግሥት በአረቦች መሬት ላይ እየመሠረቱ የነበረ መሆኑ ሲታሰብ ይህን መሳዩ ተቃውሞ የሚደንቅ አልነበረም፡፡ ‹‹እኔ አረብ ብሆን ኖሮ›› ይላሉ ቤን ጎሪዮን

በ1937 በቅንነት ሲናገሩ፡- ‹‹ፍልስጤምንና መላውን የአረብ መንደሮች ወደ አይሁድ አገዛዝ ሊቀይር የሚችለውን ያንን የአይሁዳውያን ፍልሰት በጽናትና በኃይል አምርሬ ነበር የምቃወመው፡፡››[93]

እነዚህ የአይሁድ ምሁራን እንደሚገልጹት እስራኤል በ1948 ስትመሠረት አይሁዳውያን በአረቦች ላይ ግልጽ የሆነ የዘር ማጽዳት፣ ግድያ፣ ፍጅት እንዲሁም ሴቶችን የመድፈር ወንጀል ይፈጽሙ ነበር፡፡[94] ምንም እንኳን የጽዮናውያን መሪዎች ወታደሮቻቸው ግድያ እንዲፈጽሙና ሴቶችን እንዲደፍሩ በግልጽ ባይነግሯቸውም ለወደፊቱ የአይሁድ መንግሥት በሚቋቋምበት መሬት ላይ በሚኖሩ እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸው ፍልስጤማውያን ላይ ጭካኔ የተሞላበት ተግባር የመፈጸምን አስፈላጊነት ያስገነዝቧቸው ነበር፡፡ ለምሳሌ ደቪድ ቤንጎሪዮ ከሌሎች የጽዮናውያን መሪዎች ጋር እጅግ ወሳኝ የሆነ ስብሰባ በማድረግ ፍልስጤማውያንን ከቀያቸው እንዴት እንደሚያስወግዷቸው የተወያዩበትን የጥር 1 ቀን 1948 ክስተት በግል ማስታወሻቸው ላይ እንዲህ ብለው አስፍረውታል፡- ‹‹ከዚህ በኋላ ጠንካራና ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ የመውሰጃችን ጊዜ ነው፡፡ ጊዜን፣ ቦታንና የምንመታቸውን አካባቢዎች በተመለከተ ምንጊዜም ትክክለኛ መሆን አለብን፡፡ አንድን ቤተሰብ ስናጠቃ ያለምንም ሀዘኔታ ሴቶችንና ሕፃናትን ሳንለይ ማስወገድ አለብን፡፡ ይህን ማድረግ የማንችል ከሆነ እርምጃችን ውጤት አያሳይም፡፡ ...ከእንግዲህ ጥፋተኛውን ጥፋተኛ ካልሆነው መለየት አስፈላጊ አይደለም፡፡››[95] የእስራኤል ወታደሮች አጥብቀው የሚከተሉትን የግፈኝነት መመሪያ ዋነኞቹ የጽዮናውያን አመራሮች ይህን በመሰለ አኳኋን የነደፉላቸው መሆኑን ስናስብ መደነቅ አይኖርብንም፡፡ ምክንያቱም እስራኤል ከተመሠረተች ጀምሮ ከተለያዩ ሕዝቦችና ሀገራት ጋር ባደረገቻቸው ጦርነቶች ከተዋጊዎቻቸው ይህን መሰል ባህሪ ማየት የተለመደ ሆኖ ቆይቷልና፡፡ ታዲያ እንዲህ ዓይነት ግፍ የሚፈጽም ጦር እያላትም ነው እንግዲህ እስራኤል በዓለም ላይ ካሉ ሠራዊቶች ሁሉ የተሻለ የሆነ የሞራል ይዞታ ያለው ሠራዊት እንዳላት የምትናገረው፡፡

እስራኤል በአረባውያን ጠላቶቿና በፍልስጤማውያን ላይ በተደጋጋሚ ያንጸባረቀቻቸው ባህሪያት ላቅ ያለ የሞራል ይዞታ አላት የሚለውን

አስተያየት ፈጽሞ የሚቃረን ነበር። ለምሳሌ ከ1949-1956 ባለው ጊዜ ሞሪስ እንደገመቱት ከሆነ የእስራኤል ፀጥታ ኃይሎችና ሲቪል ኑጭ ለባሾች እንዲሁም ተቀባሪ ፈንጅዎቻቸው ከ2700-5000 የሚሆኑ ፍልስጤማውያንን ገድለዋል። እርግጥ ነው ከእነዚያ ሰዎች ውስጥ እስራኤላውያንን የገደሉ ቢኖሩም አብዛኛዎቹ ግን ታጣቂ ያልሆኑና ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች እስራኤል ወደያዘቻቸው ቦታዎች ገብተው የተገኙ ናቸው። ሞሪስ እንደሚሉት፡- ‹‹ይህ በነፃነት የመተኮስ ፖሊሲ በኃይል ወደተያዙ ግዛቶች ለተለያዩ ጉዳዮች በሚገቡት ሰዎች ላይ ታላቅ ግፍ እንዲፈጸም በር ከፍቷል››[96]

እንዲህ ዓይነቱ ተግባር በአይሁዶች ዘንድ ያልተለመደ አልነበረም። የእስራኤል ጦር ከ1956-67 ድረስ በእጁ ገብተው የነበሩ በመቶዎች የሚቆጠሩ ምርኮኞችን ገድሏል።[97] በ1967 ከ100-260 ሺህ ፍልስጤማውያንን ከምዕራባዊው ወንዝ ዳርቻ እንዲሁም 800 ሺህ የሚሆኑትን ከጎላን ከፍታዎች አባርሯል።[98] ከእነዚህ የዘር ማጽዳት ሰለባዎች መካከል የተወሰኑት ተመልሰው ወደ ቀያቸው ሲመጡ ከታዩ ወዲያውኑ በተኩስ እሩምታ ይረሸኑ ነበር።[99] አምንስቲ ኢንተርናሽናል እንደሚገምተው ከ1967-2003 ድረስ ባሉት ዓመታት እስራኤል በምዕራባዊው ዳርቻና በጋዛ ሰርጥ ከ10000 በላይ ቤቶችን አፍርሳለች።[100] ራሷ ከምትፈጽመው እንዲህ ዓይነቱ የጭካኔ ተግባር በተጨማሪም የክርስቲያን ሚሊሻያ ፋላንጂስቶች በ1982 የሊባኖስ ወረራ ጊዜ ሳብራና ሻቲላ ወደሚባሉት የፍልስጤማውያን ስደተኞች ካምፖች ገብተው ንፁሐንን እንዲፈጁ ተባብራለች። ከዚያ በኋላ ያቋቋመችው የአጣሪ ኮሚሽን ባሰፈረው ሪፖርት መሠረት በጊዜው የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት አሪዮል ሻሮን የክርስትያን ሚሊሻዎች ወደ ካምፖቹ እንዲገቡ በመፍቀዳቸው በግል ኃላፊነቱን እንዲወስዱ ተደርጓል።[101] ኮሚሽኑ አሪዮል ሻሮንን በመሰሉ ከፍተኛ ባለሥልጣን ላይ የተጠያቂነት ውሣኔ ማስተላለፉ የሚደንቅ ቢሆንም የእስራኤል ሕዝብ ግን በዚህ የሻሮን ገድል ተደንቋል። እናም ወዲያው ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ መርጧቸዋል።

እስራኤል ምዕራባዊውን ዳርቻና ጋዛን ከተቆጣጠረች እነሆ አርባ ዓመታት እንደዋሣ አለፉ። የታሪክ ፀሐፊው ፔሪ አንደርሰን ይህን ክስተት፡- ‹‹በዘመናዊ ታሪክ ረዥም ዘመን የቆየው ወታደራዊ ወረራ››[102] ብለው የጠሩት ሲሆን፣ ገለጻቸውን በመቀጠል፡- ‹‹እስራኤሎች ወረራውን ሲጀምሩ ለዓለም ሕዝብ አንድ ነገር ሊነግሩት ቃል ገብተው ነበር። ይህውም ይህ ወረራ ዓለም ከዚያ በፊት አይታው የማታውቀው፣ ደግነት የሚንጸባረቅነትና በማንኛውም ሁኔታ ከሌሎች ወረራዎች የተሻለ እንደሚሆን። እውነታው ግን ከዚህ አባባል ፈጽሞ የተለዬ ነው። ልክ እንደ ሌሎች ወረራዎች ሁሉ እስራኤል የተመሠረተችው ጭካኔ በተሞላበት አገዛዝ፣ በጭቆና፣ በማስፈራራት፣ በክህደት፣ በድብደባ፣ በግርፋትና ቁምስቅል በማሳየት፣ እንዲሁም በየዕለቱ በሚፈጸም ዛቻ፣ ማዋረድና ውክቢያ ነው›› ብለዋል።[103] ለምሳሌ ከ1987-91 በተደረገው የመጀመሪያው ኢንቲፋዳ የእስራኤል ኃይል ለወታደሮቹ ቆመጥ ከሰጠ በኋላ ፍልስጤማውያን አመጻቸውን በዚያ እየመቱ አጥንታቸውን እንዲሰባብሩት መመሪያ ሰጥቷቸዋል። የስዊድን ሕፃናት አድን ድርጅት በ1990 ግንቦት ወር ላይ ባቀረበው አንድ ሺህ ገጽ የሚሆን ዘገባ የሆነውን ሁሉ አንድ በአንድ ዘርዝሮታል። በዘገባው መሠረት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ በግምት ከ23600 እስከ 29900 የሚሆኑ ሕጻናት በደረሰባቸው ድብደባ ምክንያት ሕክምና ተደርጎላቸዋል። ከእነዚህ ሕጻናት መካከል በግምት አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት አስር ዓመትና ከዚያ በታች ዕድሜ ያላቸው ነበሩ። አንድ አምስተኛ የሚሆኑት ደግሞ አምስት ዓመትና ከዚያ በታች ዕድሜ ያላቸው ነበሩ። ከአራት አምስተኛ በላይ የሚሆኑት ጭንቅላታቸውንና ከወገብ በላይ ያለውን የሰውነታቸውን ክፍል ጨምሮ በብዙ የሰውነታቸው ክፍል ላይ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል። እንዲሁም አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት የአጥንት ስብራትና ቅጥቀጣ አጋጥሟቸዋል።[104]

በጊዜው የእስራኤል ጦር ምክትል ኤታማዦር ሹም የነበሩት ኢሁድ ባራክ በመጀመሪያው ኢንቲፋዳ እንዲህ ብለው ነበር፡-- ‹‹በማንኛውም ሁኔታ በሕጻናት ላይ ተኩስ እንዲከፈት አንፈልግም። ለሠራዊታችንም ይህንኑ ትእዛዝ አስተላልፈናል።›› ይሁን እንጂ የሕፃናት አድን ድርጅቱ ባቀረበው

ግምታዊ መረጃ መሠረት "ከ6500-8500 የሚሆኑ ሕጻናት በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት በጥይት ቆስለዋል። ከእነርሱ ውስጥ 106 የሚሆኑት የሞቱ ሲሆን ከሞላ ጎደል ሁሉም ሆነ ተብሎ በእነርሱ ላይ በታለመ ተኩስ እንጂ በተባራሪ ጥይት እንዳልተመቱም ተረጋግጧል። ከሚቾቹ ሃያ በመቶ የሚሆኑት በተደጋጋሚ ጥይቶች የተመቱ መሆኑና፤ አስራ ሁለት ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ ከኋላቸው ተተኩሶባቸው እንደተመቱ ሊረጋገጥ በቅቷል። አስራ አምስት በመቶዎቹ አሥር ዓመትና ከዚያ በታች ዕድሜ ያላቸው ሲሆን፣ ብዙዎቹ ልጆች በተተኮሰባቸው ጊዜ ድንጋይ እየወረወሩ ያልነበሩ መሆናቸውና አንድ አምስተኛ የሚሆኑት ደግሞ በቤታቸው ወይም ከቤታቸው በአሥር ሜትሮች ርቀት ላይ ተተኩሶባቸው የሞቱ ናቸው›› ብሏል።

እስራኤል ከ2000-2005 በተደረገው ሁለተኛው ኢንቲፋዳ የበለጠ ነፍስ ያጠፋች መሆኗን የታዘበው ሃ ኤሬቲዝ የተባለው የራሷ ጋዜጣ እንዲህ በማለት ትዝብቱን አስቀምጧል፡- ‹‹የእስራኤል ጦር ወደ ገዳይ ማሽንነት ተቀይሯል። የመግደል ብቃቱም የሚያስደምም ሳይሆን፣ በጣም የሚያስደነግጥ ሆኗል።››[105] የእስራኤል ጦር በመጀመሪያዎቹ የኢንቲፋዳው ቀናት አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ ጥይቶችን ያዘነበ[106] ሲሆን፣ አመጹ በቆየባቸው ጊዜያት በድምሩ 3386 ፍልስጤማውያንና 992 እስራኤላውያን ተገድለዋል። ይህ ማለት እስራኤል ለእያንዳንዱ ለተገደሉባት ዜጎቿ አራት የሚሆኑ ፍልስጤማውያንን ገድላለች ማለት ነው። ከተገደሉት ውስጥ 676 ፍልስጤማውያንና 118 እስራኤላውያን ሕጻናት ይገኙበታል። 5.7 ለ1 የሆነ ምጥጥን። ከ3386 ፍልስጤማውያን ሟቾች ውስጥ 1815 የሚሆኑት ቆመው ሁኔታውን ሲታዘቡ የነበሩና 1008 የሚሆኑት ደግሞ በቀጥታ እስራኤላውያኑን ሲዋጉ የሞቱ መሆናቸው ይታመናል። 563 የሚሆኑት ሟቾች ሁኔታ ግን በግልጽ አልታወቀም። በሌላ አባባል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ፍልስጤማውያን ሟቾች በአመጹ ላይ እየተሳተፉ አልነበረም የተገደሉት ማለት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በእስራኤል በኩል ከሞቱት 992 ሰዎች ውስጥ 683 የሚሆኑት ሲቪሎች ሲሆኑ፣ የቀሩት 309 የሚሆኑት ግን ወታደሮች ነበሩ።[107] የእስራኤል ጦር የሃያ ሶስት ዓመት

እድሜ ያላትን አሜሪካዊት (የፍልስጤማውያን ቤት እንዳይፈርስ በቤቱ ውስጥ ሆና ስትማጸን በመጋቢት 2003 በቡል ዶዘር ተገድላለች) ጨምሮ ብዙ የውጭ ዜጎችንም ገድሏል።[108] እንዲህ ዓይነት ግድያዎችን የእስራኤል መንግሥት ለማጣራት የሚሞክረው አልፎ አልፎ ብቻ ሲሆን በወንጀለኞቹ ላይም በጣም አነስተኛ የሆነ ቅጣት ነበር የሚጥልባቸው።[109]

ይህን የመሰሉ የእስራኤልን ባህሪ የሚያሳዩ ሰነዶች የእስራኤልን ዋና ዋና ሰብአዊ መብት ድርጅቶችን ጨምሮ በርካታ በሆኑ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች እጅ ይገኛሉ።[110] ለዚህም ነው አራት የሚሆኑ የሺን ቤት (የእስራኤል ሀገር ውስጥ ደህንነት ድርጅት) አባላት በ2003 ህዳር ላይ እስራኤል በሁለተኛው ኢንቲፋዳ የፈጸመችውን ግፍ በመቃወም ለማውገዝ የበቁት። ከእነርሱ አንዱ ‹‹የሚያሳፍር ድርጊት ነው የፈጸምነው›› ሲል፣ ሌላኛው ሰው ደግሞ ‹‹የእስራኤል ድርጊት ግልጽ የሆነ ኢ-ሞራላዊ ነው›› በማለት አውግዟል።[111]

በጋዛና በሊባኖስ በተነሳው የ2006ቱ ብጥብጥ እስራኤል ተመሳሳይ ባህሪ ነበር ያሳየችው። ሁለት እስራኤላውያን በሃማስ መገደላቸውንና አንዱ መማረኩን ተከትሎ እስራኤል ጋዛን መልሳ ለመቆጣጠር ከአየር በቦምብ፣ ከምድር ደግሞ በመድፍ በመደብደብ፣ የጋዛን ሕዝብ የኤሌክትሪክ አቅርቦት በግማሽ የሚሸፍነውን የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ጨምሮ በርካታ መሠረተ ልማቶችን አወደመች። የእስራኤል ጦር ከዚህም በተጨማሪ በመቶዎች የሚቆጠሩ ፍልስጤማውያንን (ከእነርሱ ውስጥ ብዙዎቹ ሕፃናት ናቸው) ገደለ።[112] እንዲህ ዓይነቱን ጭካኔ የተሞላበት ጭፍጨፋ የተመለከቱት የአካባቢው የተባበሩት መንግሥታት ሰብዓዊ ኮምሽን ተወካይ ሉዊስ አርቦር ህዳር 2006 ላይ ባወጡት መግለጫ፣ ‹‹በዚህ አካባቢ እየተደረገ ያለው የሰብዓዊ መብት ጥሰት እጅግ በጣም ሰፊ ነው›› በማለት ሁኔታውን አጋለጡ።[113] በተመሳሳይ ሁኔታ በ2006 ሐምሌ ወር ላይ የሂዝቡላህ ተዋጊዎች የእስራኤል-ሊባኖስን ድንበር ተሻግረው ሁለት የእስራኤል ወታደሮችን በመማረክ በርካታዎቹን በገደሉ ጊዜ እስራኤል በሊባኖስን ሲቪል ሕዝብ ላይ ያካሄደረ ከፍተኛ ጥቃት ከፈተች። መንገዶችን፣ ድልድዮችን የጋዝ ማከፋፈያ ጣቢያዎችንና፣ ታላላቅ

ሕንፃዎችን፣ እንዲሁም ሌሎች መሠረተ ልማቶችን ክፉኛ አወደመች፡፡ በዚያ ውርጅብኝ ከአንድ ሺህ በላይ ሲባኖሳውያን የተገደሉ ሲሆን ከእነርሱ ውስጥ ብዙዎች ሲቪሎች ነበሩ፡፡ በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 11 ላይ በስፋት እንደምናነሳው ይህ አጸፋ ስትራቴጂያዊ ዒላማውን ያልመታና እርባናቢስ ሲሆን የጦር ሕግጋትንም በስፋት የጣሰ የጅብደኝነት ተግባር ነበር፡፡ በአጭሩ ለማስቀመጥ በተደጋጋሚ የሚነገረው፡- ‹‹እስራኤል የሚያጋጥሟትን ችግሮች የምትፈታው በከፍተኛ ቁጥብነት ነው›› የሚለው አባባል መሠረት የሌላው ተራ ወሬ ነው፡፡

ከላይ የቀረበውን መደምደሚያ በማስመልከት የሚነሳው ተግዳሮት ‹‹እስራኤል በታሪኳ ሕልውናዋን ከሚቃወሙ አረብ መንግሥታትና ከፍልስጤማውያን አሸባሪዎች ጭምር ብዙ አደገኛ ጥቃቶችን ተጋፍጣለች፡፡ የዜጎቿን ደህንነት ለመጠበቅ ስትል እርምጃ ተገዳ መውሰዷ አግባብ አይደለምን? የአሸባሪዎች ድርጊት እስራኤልን ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ እንድትወስድ የሚያስገድድ አይደለምን?›› የሚል ነው፡፡

እውነቱን ለመናገር ይህ የክርክር ሐሳብ የተፈጸሙትን ድርጊቶች ትክክለኛነት በምክንያት ለመግለጽ በቂ አቅም አይኖረውም፡፡ እስራኤላውያኑም ሆኑ ፍልስጤማውያኑ በየጊዜው በሚወስዷቸው እርምጃዎች ሲቪሎችን ዒላማ ማድረጋቸው በምንም መልኩ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል ድርጊት አይደለም፡፡ ነገሩን ከሌላ ጥግ ካየነው ደግሞ ፍልስጤማውያን ያደረጉትን ነገር ሁሉ ማድረጋቸው ሊያስገርመን አይገባም፡፡ ምክንያቱም በእስራኤል በኃይል ከተያዙበት ጊዜ ጀምሮ ዓላማዎቻቸውን በሰላማዊ መንገድ ለማራመድ ፖለቲካዊ መንገዶች ሁሉ ዝግ ሆነውባቸው ቆይተዋል፡፡ ስለሆነም ኃይልን ከመጠቀምና አልፎ አልፎ እንደምናየው ወጣ ያሉ የሽብር ድርጊቶችን ከመፈጸም ውጭ የረዥም ዘመን ተገፊነታቸውን ለዓለም ሕዝብ የሚያሳውቁበት ሌላ ዘዴ የቀራቸው አይመስልም፡፡ የቀድሞው የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሁድ ባራክ፡- ‹‹እኔ ፍልስጤማዊ ሆኜ ብወለድ ኖሮ አሸባሪ ድርጅቶችን መቀላቀሌ አይቀርም ነበር››[114] ማለታቸው ተጨባጭ የሆነውን እውነታ ፍንትው አድርጎ ያሳያል፡፡ ይህ ክስተት የተገላቢጦሽ ቢሆንና አይሁዳውያን በአረቦች

ተጽእኖ ስር ወድቀው ቢሆን ኖሮ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ የሆነ ስልት በመጠቀም በዓለም የተቃውሞ እንቅስቃሴ የሚያራምዱ ሌሎች ቡድኖች እንደሚያደርጉት ማድረጋቸው አይቀሬ ነበር።[115]

በእርግጥም አይሁዳውያንም ገና በደካማ እንቅስቃሴ ላይ በነበሩባቸው ጊዜያት አሸባሪነትን እንደ ዋነኛ ስልት በስፋት ተጠቅመውበታል። ኢርጉን የተባለ የጽዮናውያን አሸባሪ ቡድን በ1937 የመጨረሻዎቹ ወራት አካባቢ አዲስ የቀመረውን የሽብር ስልት በመጠቀም በአውቶቡሶች ውስጥና ሰው በተሰበሰበባቸው ሥፍራዎች ፈንጂዎችን ያኖር ነበር። ቤን ሞሪስ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹አረቦች ምናልባትም ቦምብን ለሽብር ፈጠራ የመጠቀምን ዘዴ ከአይሁዳውያን ሳይማሩት አልቀሩም።››[116] ከ1944-1947 በነበሩት ዓመታት በርካታ የጽዮናውያን አሸባሪ ቡድኖች እንግሊዞችን ከፍልስጤም ምድር ለማባረር ብዙ ሲቪሎች ያለቁባቸውን የሽብር ጥቃቶች ፈጽመዋል።[117] በ1948 የአይሁድ አሸባሪዎች የተባበሩት መንግሥታት አደራዳሪ የነበሩትን ስዊድናዊውን ካውንት ፎልኬ በርናዶቴን በንጉሥ ዳዊት ሆቴል ውስጥ እንዳሉ ሆቴሉን በቦምብ በማጋዬት ገድለዋቸዋል። ጽዮናውያን ይህን ያደረጉት በርናዶቴ እየሩሳሌምን ዓለም አቀፋዊ ከተማ ለማድረግ አዲስ ጥረት ማነቃቃታቸውን በመቃወም ነበር።[118] ይህን ወንጀል የፈጸሙት የተለዩና እምብዛም ሕቡዕ የሆኑ ቡድኖች አልነበሩም። የቡድኑ መሪዎች የኋላ ኋላ በእስራኤል መንግሥት ምህረት የተደረገላቸው ሲሆን፣ ከእነርሱ መካከል አንደኛው እንዲያውም የእስራኤል ፓርላማ (ክኔሴት) አባል እስከመሆን ደርሷል። ሌላው የሽብርተኞች ቡድን መሪ ደግሞ በቤርናዶቴን መገደል እጃቸው ባይኖርበትም ለግድያው ጽድቅ ችረዋል። ይህ ሰው ኋላ ላይ የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር የሆኑት ኢሳቅ ሻሚር ነበሩ። ስለ ድርጊቱ ሻሚር አስተያየታቸውን ሲሰጡ፡- ‹‹የአይሁዳውያን ሥነ-ምግባርም ሆነ ባህላቸው ጠላትን ለመዋጋት የአሸባሪነትን ስልት መጠቀምን ውድቅ አያደርግም›› በማለት በግልጽ ተከራክረዋል። ሻሚር አያይዘውም ‹‹ይህን ስልት ወራሪዎቹን እንግሊዛውያን ለማባረር በሰፊው እንጠቀምበታለን›› ያሉ ሲሆን፣ በ1998 በአንድ ቃለ መጠየቅ ላይ በአሸባሪነት ያሳለፉትን ሕይወት እንደማይጸጸቱበት ሲገልጹ፡- ‹‹ያደረግኩትን ሁሉ ባላደርግ ኖሮ የራሳችን

የሆነችውንና ነፃዋን የአይሁድ ሀገር አንመሰርትም ነበር›› በማለት ተናግረዋል፡፡[119]

ሚናሂም ቤኒንም ቢሆኑ የታወቁ የኢርጉን ሕቡዕ ሽማቂዎች ቡድን መሪ ነበሩ፡፡ በኋለኞቹና ከነፃነት በኋላ በነበሩት ዘመናት ደግሞ ጠጣሩን የጽዮናውያን የፖለቲካ መስመር የሚከተሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን በቅተዋል፡፡ ሚናሂም ቤጊንን ጠቅላይ ሚኒስትር ሌቪ ኤሽቆል በአጭሩ ሲገልጿቸው ‹‹አሸባሪው›› እያሉ ነበር፡፡[120] ፍልስጤማውያን ዛሬ ሽብር ፈጠራን የፖለቲካ ትግል ስልታቸው አድርገው መጠቀማቸው አስከፊ መሆኑ አይካድም፡፡ ሆኖም ግን ጽዮናውያኑም ቢሆኑ ዓላማቸውን ለማስፈጸም በስፋት የተጠቀመብት ዘዴ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡ ስለሆነም ማንም ቢሆን አሜሪካ እስራኤልን በስፋት ማገዝ ያለባት እስራኤል ባለፉት ዘመናትም ሆነ አሁን በምታሳያቸው ባህሪዎች የሞራል ልዕልናዋ ከፍ ያለ በመሆኑ ምክንያት ነው ብሎ መናገር አይችልም፡፡ ለምን ቢባል ገሀዱ እውነታ ፍፁም ተቃራኒውን ነውና የሚያሳየው፡፡

ከአይሁዳውያኑና ከደጋፊዎቻቸው በኩል የሚነሳው ሌላው የመከራከሪያ ሀሳብ እንዲህ የሚል ነው፡- ‹‹እስራኤል ንጹሐን ዜጎችን ሆነ ብላ አታጠቃም፡፡ ዳሩ ግን ሂዝቡላህና ፍልስጤማውያን እስራኤላውያን ሲቪሎችን ሆነ ብለው ያጠቃሉ፡፡ በተጨማሪም እስራኤልን የሚያጠቁት አሸባሪዎች ሰላማዊ ሰዎችን ሰብዓዊ ጋሻ አድርገው ስለሚይዙ የእስራኤል ጦር ቀንደኛ ጠላቶቹን ለመምታት በሚፈልግበት ጊዜ በሚያሳዝን ሁኔታ ሰላማዊ ሰዎችን ከመግደል ውጪ ምርጫ ያጣል፡፡›› ይህም ምክንያት አሳማኝ አይደለም፡፡ ምዕራፍ 11 ላይ እንደተብራራው የእስራኤል ሠራዊት ሊባኖስን በ2006 በመታበት ጊዜ የሲቪል መኖሪያ ሰፈሮችን ሆነ ብሎ ዒላማው አድርጎ ነበር፡፡ በዚያ ጦርነት ሂዝቦላህ ሲቪሎችን በሰብዓዊ ጋሻነት የተጠቀመባቸው ስለመሆኑ የሚያሳይ አንድም መረጃ የለም፡፡ እንዲሁም የእስራኤል መንግሥት ይፋዊ ፖሊሲ ፍልስጤማውያን ሲቪሎች እንዳይገደሉ ያዘዛል የሚለውም ክስ መረጃ የለውም፡፡ የእስራኤል ጦር ሀማስንና ኢስላሚክ ጀሀድን ከመሰሉ ቡድኖች ጋር ውጊያ ሲያካሂድ ሲቪሎች እንዳይጎዱ ለማድረግ ሳይችል መቅረቱ በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡

እውነታው ሂዝቡላህና የፍልስጤም ተዋጊዎች ሲቪሎችን ዒላማ ማድረጋቸው እስራኤል በሲቪሎች ላይ ተመጣጣኝ ያልሆነ ኃይል በመጠቀም ሕይወታቸውን አደጋ ላይ እንድትጥለው የሚያደርግ መብት አይሰጣትም፡፡

ሃማስንና ሂዝቡላህን የመሰሉ ኃይሎች ለሚያደርሱባት ጥቃት አጸፋ የመመለስ መብቷ የተረጋገጠ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ሆኖም ግን ይህ ማለት ታላቅ የሆነውን ወታደራዊ ኃይሏን የንፁሐን ሲቪሎችን ሕይወት በስፋት አደጋ ላይ ለመጣል ተግባር ካዋለችው በተደጋጋሚ የሚነገርላት የጦሯ ሞራላዊ ልቅና ጥርጣሬ ላይ ይወድቃል፡፡

የካምፕ ዴቪድ ተረቶች

እስራኤል ሰላም ወዳድ፣ ፍልስጤማውያን ደግሞ ጠብ ጫሪ እንደሆኑ ተደርገው ይበልጥ የተሳሉበት ዋነኛ ምክንያት የክሊንተን አስተዳደር የኦስሎውን የሰላም ሃሳብ ለማነቃቃት ባለመቻሉ ነበር፡፡ በዚህ ተረት መሠረት "ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሁድ ባራክ በሐምሌ 2000 ፍልስጤማውያን የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ ከሞላ ጎደል ሰጥተዋቸው ነበር፡፡[121] ሆኖም ግን አራፋት ያንን ቸርነት የተሞላበት የሰላም ስምምነት ሂደት አቅጣጫ ለውጠው መስከረም/2000 መጨረሻ ላይ እስራኤልን ለማውደም ሁለተኛውን ኢንቲፋዳ ቀስቅሰዋል፡፡ በተጨማሪም ፕሬዚዳንት ክሊንተን በታህሣሥ 23/2000 ያቀረቡትንና እስራኤል የተቀበለችውን Clinton parameters በሚል ስያሜ የሚታወቀውን -ቸርነት የተሞላበት ሀሳብ አራፋት ወደጎን ብለው ሰላማዊውን ሂደት አጣጥለዋል፡፡›››

ከዚህ ትረካ የምንገነዘበው አጠቃላዩ የሰላም ስምምነት ሳንካ የገጠመው ሙሉ በሙሉ በአረፋት ስህተት እንደሆነ ነው፡፡ እስራኤል ሰላም እንዲወርድ ብትሻም ታማኝ የሆነ የሰላም አጋር ከፍልስጤማውያኑ በኩል አላገኘችም፡፡ ይህም የቀድሞውን የእስራኤል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የአባ ኢባንን፡- ‹‹አረቦች እድላቸውን ለማበላሸት ያላቸውን አጋጣሚ ፈጽሞ አያበላሹም›› የሚለውን ታዋቂ ቀልድ ያስታውሳል፡፡ በመሆኑም ሁኔታው እስራኤልም

ሆነች ዩናይትድ ስቴትስ፣ አራፋት በሥልጣን ላይ እስከቆዩ ድረስ ከፍልስጤማውያን ጋር ስምምነት ማድረግ አይቻልም የሚለውን አባባል በጽኑ መቀበላቸውን ያሳያል።

በስፋት በተነገረውና ተቀባይነት ባገኘው በዚህ ተረት ውስጥ አንድ ችግር በጉልህ እናስተውላለን። እርሱም ተረቱ ውሸት መሆኑ ነው።[122] ምንም እንኳን ባራክ፣ ፍልስጤማውያን የራሳቸውን መንግሥት እንዲመሠርቱ ዕድል የሰጡ የእስራኤል መሪ መሆናቸው የታወቀ ቢሆንም፣ የካምፕ ዴቪዱ የሰላም ሀሳብ ከቸርነት ፈጽሞ የራቀ ነበር። ነገሩን ከሥሩ ጀምረን ለማየት ከቻልን ባራክ በካምፕ ዴቪድ ለፍልስጤማውያን ያቀረቡት ችሮታ ፍልስጤማውያን ጋዛ ሰርጥን አሁኑኑ እንዲረከቡና የምዕራቡን ዳርቻ ደግሞ 91 በመቶ የሚሆነውን መጨረሻ ላይ እንደሚያገኙ ቃል ይገባል።[123] ያም ቢሆን ችሮታው በፍልስጤማውያን እይታ ታላላቅ ችግሮች ነበሩበት። ምክንያቱም በስምምነቱ ላይ እስራኤል በግምት ከምዕራቡ ወንዝ ዳርቻ 10 ከመቶ የሚሆነውንና የወንዙን ተፋሰስ ሙሉ በሙሉ ከስድስት እስከ ሃያ ዓመት ለሚሆን ጊዜ (በዚህ ቆይታ ላይ ልዩነቶች ታይተዋል) ይዛ እንደምትቆይ ይገልጻል። በዚህ ስሌት ከተሄደ ፍልስጥኤማውያን የምዕራቡን ወንዝ ዳርቻ 91 ከመቶ ሳይሆን 81 ከመቶውን ብቻ ያገኛሉ። እንደዚያም ሆኖ እስራኤል አንድ ጊዜ ያንን ወንዝ ከተቆጣጠረች በኋላ ለመልቀቅ ትስማማለች ብለው ፍልስጤማውያኑ እርግጠኛ ሊሆኑ አይችሉም።

ከዚህም በተጨማሪ ፍልስጤማውያን የምዕራቡ ዳርቻ አካል ነው ብለው የሚያስቡት እስራኤል ከምታስበው የበለጠ ሰፋ ያለ ይዞታን የሚጠቀልል ነው። ሁለቱ ክፍሎች በምዕራቡ ዳርቻ ላይ ያላቸው ልዩነት በግምት 5 ከመቶ የሚሆነውን መሬት ጥያቄ ላይ የሚጥለው በመሆኑ ፍልስጤማውያን ያለምንም አጨቃጫቂ ሁኔታ ለጊዜው ሊረከቡ የሚችሉት 76 ከመቶ የሚሆነውን መሬት ብቻ ይሆናል። ከተወሰነ ቆይታ በኋላ እስራኤል የወንዙን ተፋሰስ ይዞታ በስምምነቱ መሠረት የምትለቅ ከሆነ ይዞታቸው ወደ 86 ከመቶ ከፍ ይላል። ይህን ስምምነት ለመቀበል ለፍለስጤማውያን አስቸጋሪ የሚያደርገው በ1993 የኦስሎ ውል መሠረት ከቀድሞዋ ቅኝ ገዢ ከእንግሊዝ የሞግዚት አስተዳደር (British Mandate)

78 ከመቶ የሚሆነው የፍልስጤም መሬት ሉዓላዊ ለሆነው የእስራኤል መንግሥት እንደሚሰጥ ተስማምተው ነበር።[124] አሁን ደግሞ ከቀራቸው 22 ከመቶ ድርሻ ላይ ባራክ 86 ከመቶ የሚሆነውን ብቻ ለመውሰድ እንዲስማሙ ጠየቋቸው።

ሁኔታዎች የበለጠ የከፉ እንዲሆኑ ያደረገው በ2000 በጋ ላይ በካምፕ ዴቪድ የቀረበው ስምምነት ፍልስጤማውያንን በዚያች በምትደርሳቸው የበሬ ግንባር የምታክል የምዕራባዊው ዳርቻ መሬታቸው ውስጥ ሉዓላዊ መንግስት እንዲያቋቁሙ ስምምነቱ አይፈቅድላቸውም። ይልቁንም ፍልስጤማውያን እንዲቀበሉት በቀረበላቸው በዚህ ግብዣ መሠረት ምዕራባዊው ዳርቻ ከሦስት ግዛቶች ይከፈልና በየግዛቶቹ መሐከል የእስራኤል ይዞታዎች ጣልቃ እንዲገቡ ይደረጋል። እስራኤላሰውያን ራሳቸው ይህን ሀሳብ ቢቃወሙትም ኢሁድ ባራክ ግን እስራኤል ከእየሩሳሌም እስከ ዮርዳኖስ ወንዝ የሚደርስ ቀጭን መተላለፊያ (corridor) እንደሚኖራት በመግለጽ ለማላመን ሞክረዋል።[125] የምዕራቡን ዳርቻ የሚያካፍለው ይህ መተላለፊያ እስራኤል የወንዙን ተፋሰስ ሽለቆዎች በሚገባ እንድትቆጣጠር ያግዛታል። እንግዲህ ፍልስጤማውያን በካምፕ ዴቪድ የቀረበላቸው ችሮታ ይህን የሚመስል ሲሆን፣ በሁለት ወይም ሶስት ግዛቶች (Cantons) የሚሸነሸኑት የጋዛና የምዕራቡ ዳርቻ መሬቶች እንደገና በየመካከሉ በእስራኤል መሬቶች የሚከፋፈሉ ይሆናሉ ማለት ነው። ባራክ በኋላ ላይ እንደገልጹት የፍልስጤማውያን ግዛቶች (Cantons) እርስበርሳቸው የሚገናኙበት የምድር ውስጥ መሿለኪያ (tunnel) ወይም ድልድይ የሚኖራቸው ሲሆን፤ ጋዛና ምዕራባዊው ዳርቻ ደግሞ በቀጭን መተላለፊያ (corridor) ይገናኛሉ።[126]

አስቸጋሪውንና በአሜኬላ የተሞላውን የእየሩሳሌም ጉዳይ አስመልክቶ ባራክ ከተማዋ ለሁለት አንድትከፈል በመፍቀድ መልካም እርምጃ አሳይተዋል። እንደዚያም ቢሆን ፍልስጤማውያን በተለያዩ የምሥራቃዊ እየሩሳሌም የአረብ መኖሪያ ሠፈሮች ውስጥ ሙሉ ሉዓላዊነት ስላልተፈቀደላቸው ስምምነቱ አልማረካቸውም። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ እስራኤል የፍልስጤማውያንን ድንበሮች፣ የአየርና የባሕር ክልል እንድትቆጣጠር

ስምምነቱ ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም ፍልስጤማውያን እስከመጨረሻው ራሳቸውን የሚከላከሉበት ሠራዊት ማደራጀት እንዳይችሉም ያግዳል፡፡[127] እንግዲህ ይህን የመሰለውን የተቆላለፈ ስምምነት አንድ መሪ እንዴት ሊቀበለው ይችላል ተብሎ ይታሰባል? በዓለም ሎዓላዊነቱ እንደዚህ የተገደበ፣ ትክክለኛ ኢኮኖሚና ሕዝብን ለመገንባት መሰናክል የተደቀነበት መንግሥት እንደሌለ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ሁኔታዎች እንዲህ በመሰሉበት ጊዜ የባራክ የቀድሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና በካምፕ ዴቪድ ስምምነት ወሳኝ ተደራዳሪ የነበሩት ሽሎሞ ቤን አሚ ቃለ መጠየቅ ላደረገላቸው አንድ ጋዜጠኛ የሚከተለውን ማለታቸው አያስደንቅም፡- ‹‹እኔ ፍልስጤማዊ ብሆን ኖሮ የካምፕ ዴቪድን ስምምነት ወድቅ አደርገው ነበር፡፡››[128]

መስከረም 2000 ላይ አራፋት ኢንቲፋዳውን የቀሰቀሱት በስምምነቱ ላይ ተጽዕኖአቸው ከፍ እንዲል ለማድረግ ወይም ራሱን የሰላም ስምምነቱን ለማፍረስ ነው የሚለው አባባልም መሠረት የሌለው ነው፡፡[129] አራፋት ከእስራኤልና ከአሜሪካ ጋር ከካምፕ ዴቪድ በኋላም ስምምነቱን መቀጠላቸው፣ እንዲያውም የኢሁድ ባራክን ቤት ኢንቲፋዳው ከመጀመሩ የተወሰኑ ምሽቶች በፊት መጎብኘታቸው ተረጋግጧል፡፡ የስምምነቱን መፍረስ አስመልክቶ ዘገባ ያዘጋጀው ፈረንሳዊው ጋዜጠኛ ቻርለስ አንደርሰን በዚያ ምሽት ሁለቱ መሪዎች ባልተለመደ ሁኔታ ጓደኛሞች ሆነው ይታዩ የነበረ ከመሆናቸውም በላይ ስምምነቱን በተመለከተም አዎንታዊ ስሜት የነበራቸው መሆኑን ገልጿል፡፡[130] በተጨማሪም የቀድሞው የእስራኤል ሀገር ውስጥ ስለላ ድርጅት (ሸን ቤት) ኃላፊ አሚ-አያሎን፣ ‹‹አራፋት ኢንቲፋዳውን አላቀዱትም፣ እንዲጀመርም አላደረጉትም›› ብለዋል፡፡[131] በቀድሞው አሜሪካዊ ሲናተር ጆርጅ ሚቸል የሚመራውና የሰላሙን ሀሳብ ያንቀሳቀሰው ኮሚሽንም ተመሳሳይ መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡[132]

ሁለተኛው ኢንቲፋዳ የፈነዳው አሪዮል ሻሮን በመስከረም 28 ቀን 2000 ቴምፕል ማውንት የሚባለውንና በአይሁዳውያን ዘንድ ቅዱስ ቦታ ተደርጎ የሚወሰደውን ሥፍራ በጎበኙ ጊዜ ነበር፡፡ በዚያ ጉብኝታቸው ወቅት ከአንድ ሺህ በላይ ፖሊሶች አጅበዋቸው ነበር፡፡ ምክንያቱም ሙስሊሞች አል-አቅሷ ብለው የሚጠሩት ሶስተኛው ቅዱስ ሥፍራቸው የሚገኘው ከዚያ ብዙም

ባልራቀ ሥፍራ ላይ ነበርና ተቃውሟቸውን በመፍራት፡፡ የሻሮን ጠብ ጫሪ ድርጊት የብጥብጡ ሰበብ ይሆን እንደሆነ እንጂ ለኢንቲፋዳው ዋናው ምክንያት አይደለም፡፡ ከሻሮን ጉብኝት በፊት በፍልስጤማውያን ዘንድ አለመረጋጋት ሰፍኖ የነበረ ሲሆን፣ ከሁለቱም ወገኖች በኩል ቁልፍ የሆኑ ባለሥልጣናት አደጋውን ቀደም ብለው ተገንዝበውት ነበር፡፡ እንዲያውም የፍለስጤም መሪዎች የሻሮን ጉብኝት የሚቀርበት ሁኔታ እንዲፈጠር የእስራኤልንና የአሜሪካ ባለሥልጣናትን በጥብቅ አስገንዝበው ነበር፡፡[133]

የዚህ ትልቅ ችግር አካል ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለው የፍልስጤማውያን ውስጣዊ ብሶት የወለደው እርካታ ማጣት፣ በሙስና የተዘፈቀውና ሕይወታቸው እንዲሻሻልም ሆነ የራሳቸው የሆነ መንግሥት እንዲኖራቸው ጥቂት ጥረት በማድረግ ብቻ የተወሰነው የአረፋት አስተዳደር ነው፡፡ ሆኖም ግን ዋነኛው ምክንያት በኃይል በተያዙት ግዛቶች እስራኤል የምታራምዳቸው የሚያበሳጩ ፖሊሲዎችና ይህን ተቃውመው ለሚነሱ ሰዎች የምትሰጣቸው ጭካኔ የተሞላባቸው አጸፋዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ከሻሮን ጉብኝት ጋር ተደማምረው ያናሩት የሕዝብ ቁጣ ኢንቲፋዳውን ወለደ፡፡[134] ቤን አሚ ‹‹ሁለተኛው ኢንቲፋዳ እንደ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የተጀመረ ሳይሆን የክብር ሕይወትና የኑሮ ዋስትና አምጥቶላቸው ከነበረው የኦስሎ ስምምነት መፍረስ በኋላ ሲጠራቀም የቆዩ የፍልስጤማውያን ብሶትና ቁጣ በመፈንዳቱ ምክንያት የተከሰተ አመጽ ነው፡ ፡›› ማለታቸው ትክክል ነበር፡፡[135]

የፍልስጤማውያንን ተስፋ መቁረጥ ለመገንዘብ ከባድ አልነበረም፡፡ የኦስሎ ስምምነት ከተጀመረበት ከመስከረም 1993 አንስቶ ከሰባት ዓመታት በኋላ ሁለተኛው ኢንቲፋዳ እስከፈነዳበት ጊዜ ድረስ እስራኤል አርባ ሺህ ኤክር (16 ሺህ ሄክታር) የሚሆን የፍልስጤማውያንን መሬት በመውረስ 250 ማይል እርዝመት ያላቸው መተላለፊያና የፀጥታ ማጠናከሪያ መንገዶችን፣ ሰላሳ አዳዲስ የሠፈራ መንደሮችን ገንብታለች፡፡ እንዲሁም በምዕራባዊው ዳርቻና በጋዛ የሰፋሪዎቿን ቁጥር ከሞላ ጎደል በመቶ ሺህ አሳድጋለች፡፡ ይህም ቀድሞ ከነበሩት እጥፍ የሚያክል መሆኑ ነው፡፡[136] እስራኤላውያኑ ለፍልስጤሞች ሊመልሱላቸው ቃል የገቧቸውን መሬቶች በመካድ ቃላቸውን

ያፈረሱ ሲሆን፣ በየሥፍራው የፍተሻ ጣቢያዎችን በማዘጋጀት የፍልስጤማውያኑን እንደፈለጉ የመዘዋወር ነፃነት በመገደባቸው ኢኮኖሚያቸውን ክፉኛ ጎድተውታል። በዚህ ሁሉ ውጥረት ውስጥ የነበሩት ፍልስጤማውያን በ2000 ኢንቲፋዳውን ሲጀምሩት እስራኤል ተቃውሞውን ባልተመጣጠነ ኃይል ለመስበር ተንቀሳቅሳለች።[137] የእስራኤል ጦር በጥቂት ቀናት ውስጥ ወደ ፍልስጤማውያኑ የተኮሰው ጥይት አንድ ሚሊዮን ያክል እንደሆነ ተዘግቧል።

ምንም እንኳን አራፋት ኢንቲፋዳውን ራሳቸው እንዲጀመር ባያደርጉትም የመደራደር አቅማቸውን ለማጠናከር ሊጠቀሙበት በማሰብ የሞኝ ስሌት ማውጠንጠናቸው ሊካድ አይችልም። በሌላ በኩል ደግሞ ሁኔታው የባራክን ድርድሩን የመቀጠል ፍላጎት ብቻ ሳይሆን በእስራኤል መራጮች ዘንድ የነበራቸውን ገጽታ በመጉዳት በየካቲት 2001 ላይ በተደረገው ምርጫ በሻሮን እንዲሸነፉ ተጽእኖ አድርጎባቸዋል። አራፋት አመፁን ለተጽእኖ ማሳደሪያነት ለመጠቀም ያደረጉት ሙከራም ድርድሩን በማጓተቱ ደካማው የክሊንተን አስተዳደር ስምምነቱን ዳር ለማድረስ አነስተኛ ጊዜ እንኳን እንዲኖረው አላስቻለውም ነበር።

አንዳንዶች እንዲያውም የአረፋት የመጨረሻ ግብ ያንን ብጥብጥ ተጠቅመው እስራኤልን ከካርታ ላይ ለመፋቅ ነበር በማለት ይከራከራሉ። እርግጥ ነው አራፋት በ1960 ወደ ፖለቲካው መድረክ ብቅ እንዳሉ ዓላማቸው እንዲያ ነበር። ሆኖም ግን በ1980ዎቹ መጨረሻ ላይ ፍልስጤማውያን እስራኤላውያኑን ከዚያ ምድር ሊያስወጧቸው የሚችሉበት ምንም ዓይነት መንገድ እንደሌለ የተገነዘቡበት ጊዜ ነበር። እንዲያውም አራፋት በ1990ዎቹ የኦስሎ ስምምነት ጊዜያት የተወሰኑ ርቀቶችን በሰላም ጎዳናው ላይ በመጓዝ የእስራኤልን ሕልውና እስከማወቅ የደረሱ ከመሆኑም በላይ፤ በኃይል ከተያዙት መሬቶቹ በስተቀር የታሪካዊቷ ፍልስጤምን የይገባኛል ጥያቄም እርግፍ አድርገው ትተው ነበር።[138] ስለሆነም የካምፕ ዴቪዱ ድርድር እንደከሸፈና ሁለተኛው ኢንቲፋዳ እንደተጀመረ ሁሉም የእስራኤል ቁልፍ የጸጥታና የፖለቲካ ሰዎች አራፋት የእስራኤልን ሕልውና የተቀበሉና በምዕራባዊው ዳርቻና በጋዛ የፍልስጤሞች መንግሥት እንዲቋቋም ብቻ

የሚፈልጉ መሆኑን ያምኑ ነበር፡፡[139] የመካከለኛው ምሥራቅ የፖለቲካ ጠቢብ ጆርሚ ፕሬስማን እንደታዘቡት ከሆነ ‹‹ አራፋትና ፍልስጤማውያን እስራኤልን ለማጥፋት ወስነው ቢሆን ኖሮ፣ የባራክን ግብዣ ተቀብለው አዲሱን መንግሥታቸውን እስራኤልን ለማጥፋት የኃይል ማደራጃ ሊያደርጉት ይችሉ ነበር፡፡ ሆኖም እነርሱ ያን ከማድረግ ይልቅ መደራደሩን በመምረጥ በዚያ ማዕቀፍ ውስጥ ሆነው የሁለት የተለያዩ መንግሥታት ምሥረታን መንገድ ነበር እንደመፍትሄ የተከተሉት፡፡››[140]

በተደጋጋሚ ሲስተጋባ የነበረውና አራፋት በ2000 ካምፕ ዴቪድ ላይ ኢሁድ ባራክ ያቀረቡላቸውን የእርቅ ስምምነት የሚያሻሽለውን የክሊንተንን ሀሳብ ውድቅ አድርገዋል የተባለውም እንዲሁ ስህተት ነው፡፡ ኦፊሴላዊ የሆነው የፍልስጤማውያን መልስ ክሊንተን ላደረጉት ያላሰለሰ ጥረት ካመሰገናቸው በኋላ፣ የሰላም ሂደቱ እርምጃ ማሳየቱን ጠቅሶ፣ ሆኖም ግን እርሳቸው ያቀረቧቸው የተወሰኑ የማሻሻያ ነጥቦች እንዲብራሩለት በመጠየቅ በተወሰኑት ላይ ደግሞ ቅሬታውን ይገልጻል፡፡[141] የእስራኤል መንግሥትም፣ ባራክ በሃያ ገጽ አጠናቅረው ባቀረቡት የስምምነት ሰነድ ላይ ቅሬታውን አንጸባርቋል፡፡ ስለሆነም ፍልስጤማውያኑም ሆኑ እስራኤላውያኑ የክሊንተንን የማስማሚያ ሀሳቦች ለእርቅ ሂደቱ እንደ መሠረት የሚጠቅሙ መሆናቸውን ከመግለጻቸው ውጪ ሙሉ ለሙሉ አልተቀበሏቸውም፡፡ የሁዋይት ሃውስ ቃል አቀባይ ጥቅምት 3/2001 ላይ ‹‹ሁለቱም ክፍሎች የፕሬዚዳንቱን የማስማሚያ ሀሳቦች ከተወሰነ ቁጥብነት ጋር ተቀብለዋቸዋል›› በማለት መግለጫ ሰጡ፡፡ ይህ ከሆነ ከአራት ቀናት በኋላ የእስራኤል ፖሊሲ ፎረም ለተባለው አካል ባደረጉት ንግግር ይህንኑ አረጋገጡ፡፡[142] ከዚያ በኋላም በሁለቱ መካከል የነበረው ድርድር ታግ በተባለችው የግብፅ ከተማ ቀጥሎ ነበር፡፡ በጥር 2001 ድርድሩን ያቆሙት አረፋት ሳይሆኑ ይሁድ ባራክ ናቸው፡፡ ባራክ ይህን ያደረጉት ለእስራኤል ምርጫ የተሰበሰበ የሕዝቡ አስተያየት ከዚህ ድርድር ተቃራኒ መሆኑንና ሕዝቡ የእርሳቸውን አካሄድ በጽናት መቃወሙን ስለተገነዘቡ ነበር፡፡[143] እርሳቸውን የተኳቸውና የኦስሎንም ሆነ የክሊንተንን የማሻሻያ ሀሳቦች ያልተቀበሉት ኦርዮል ሻሮን ምንም እንኳን ፍልስጤማውያኑ ተደጋጋሚ

ጥያቄ ቢያቀርቡም፣ ድርድሩ እንዳይቀጥል አገዱ። በ2001 መጀመሪያ ላይ ሰላም በቅርብ ርቀት ይታይ ኖሮ እንደሁ የማውቀው ነገር የለም። ሆኖም ግን አራፋትና ፍልስጤማውያን ለሰላም የቀረበላቸውን የመጨረሻ ዕድል ውድቅ አድርገው የብጥብጥን መንገድ መርጠዋል የሚለው ክስ ከሀቅ ፍጹም የራቀ ነው።

እስራኤልን መደገፍ የአምላክ ፈቃድ ነው

እስራኤልን ያለ ገደብና ቅድመ ሁኔታ ለመርዳት እደሰበብ የሚቀርበው የመጨረሻው ሞራላዊ ምክንያት ከሃይማኖት ሰዎች በኩል ሲሆን በምዕራፍ አራት ይበልጥ እንደሚብራራው የተወሰኑ የክርስቲያን ወንጌላውያን ክፍሎች በተለይም ክርስቲያን ጽዮናዊያን የሚባሉት "የአይሁድ መንግሥት የተመሠረተው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በተጠቀሱት የነቢያት ትንቢቶች አማካኝነት ነው" የሚል አቋም ይዘው ብቅ ባሉበት ጊዜ ነበር። «በኦሪት ዘፍጥረት እንደተገለጸው ለአብርሃም እና ለዘሮቹ ይህችን የእስራኤል ምድር የሰጣቸው አምላክ ነው። ስለሆነም የምዕራባዊውን ዳርቻ አይሁዶች መውረራቸው ሌላ ሳይሆን፣ አምላክ ጥንቱኑ የሰጣቸውን ምድር መያዛቸው ነው።» የሚል ነው የእነዚህ ወንጌላውያን የክርክር መነሻ። የተወሰኑ ክርስቲያኖች ከዚህ አባባልም ጥቂት ፈቀቅ በማለት «የታላቁ እስራኤል መመሥረት የመጨረሻውን የምዕአት ቀን መድረስ ለሚያበስረው ታላቁ ጦርነት (አርማጌዶን) መቃረብ በአዲስ ኪዳን መጽሐፍት የተጠቀሰ መልክት ነው» ብለው እስከመናገር ደርሰዋል። ሁለቱም አስተያየቶች እስራኤል የዩ.ኤስ. አሜሪካን ድጋፍ ማግኘት ያለባት የዲሞክራሲ ሀገር በመሆኗ ወይም ተጠቂ ስለሆነች አሊያም ደግሞ ሞራሉ ከፍ ያለ ሠራዊት ስላላት ሳይሆን፣ እስራኤልን መደገፍ የአምላክን ውሳኔ መደገፍ በመሆኑ ነው የሚለውን ሃይማኖታዊ ቀኖና ያስተጋባሉ።

እርግጥ ነው ይህን የመሰለው የመከራከሪያ ሀሳብ ለተወሰኑ ሃይማኖተኞች አሳማኝ ሊመስል ይችላል። ሆኖም ግን የአርማጌዶን ትንቢት የአሜሪካን የውጭ ፖሊሲ ለመቅረጽ መሠረት ሊሆን አይችልም። ሀይማኖትና

መንግሥት በዩናይትድ ስቴትስ የተለያዩ ሲሆኑ የማንኛውም ቡድን ሀይማኖታዊ አስተያየት የአሜሪካን የውጭ ፖሊሲ በመቅረጽ በኩል የሚጫወተው ሚና ሊኖር አይገባም፡፡ ከዚህም በላይ ኃያሏ እስራኤል ግፉአን የሆኑትን ፍልስጤማውያን እንድትጨቁንና መብታቸውን እንድትገፍ ማገዝ ክክርስትና የስነ ምግባር አስተምህሮ ጋር ፍጹም ይቃረናል፡፡

ለመሆኑ የአሜሪካ ሕዝብ የሚፈልገው ምንድን ነው?

እስካሁን የዳሰስናቸው ስድስቱ የሞራል የመከራከሪያ ነጥቦች ዩ.ኤስ. አሜሪካ እስራኤልን የምትደግፍበት እውነተኛ ምክንያት ያረፈው የአሜሪካ ሕዝቦች ከአይሁዳዊቷ ሀገር ጋር ባላቸው የፀና ትስስር መሆኑን ያሳያሉ፡፡ የቦስተን ግሎብ ጋዜጣ አምደኛ የሆነው ጆፍ ጃኮቢ እንደሚከተለው በማለት ጽፏል፡- ‹‹ከእስራኤል ጋር አንድነት መመሥረት የአሜሪካ ሕዝብ ፍላጎት ነጸብራቅ ነው፡፡ ምክንያቱም የአሜሪካ ሕዝብ የእስራኤል ደጋፊ ሲሆን መንግሥቱም እንደዚያው ለእስራኤል የቆመ በመሆኑ፡፡ እስራኤል ከአረቦች ጋር በምታደርገው ግጭት አሜሪካ ጠንካራ ድጋፏን የምትሰጣት በመሆኑ መካከለኛውን ምሥራቅ በተመለከተ የምትከተለው ፖሊሲ እስራኤልን ከጥቃት የመጠበቅ ፖሊሲ ነው፡፡›› የአሜሪካና እስራኤል ሕዝብ ጉዳዮች ኮሚቴ (አይፓክ) ቃል አቀባይ ጆሽ ብሎክ በ2007ቱ ኮንፈረንስ ዋዜማ ላይ እንዲህ ብለዋል፡-- ‘‘የሚያሳስበን አንድ ጉዳይ ብቻ ነው፤ የዩ.ኤስ. አሜሪካንና የእስራኤልን ግንኙነት መደገፍ፡፡ ያ ነው ሁሉንም ሰው አንድ ላይ የሚያሰባስበው፡፡ በእርግጥ ሁሉም ተሞክሮዎቻችን የሚያሳዩንና በግልጽ የተገነዘብነው ነገር በመካከለኛው ምሥራቅ ክብር የምንሰጣቸው መሠረታዊ እሴቶች የሚንጸባረቁባት ሀገር እስራኤል ብቻ መሆኗን ነው፡፡››[144]

ይሁን እንጂ ይህ በሰፊው የሚታመንበት አባባል በጥልቀት መፈተሽ ይኖርበታል፡፡ እርግጥ ነው በዩናይትድ ስቴትስና እስራኤል መካከል በአይሁድ-ክርስቲያን (Judeo-Christian) ወግ ላይ የተመሠረተ የባህል ግንኙነት አለ፡፡ እንዲሁም ብዙ አሜሪካውያን እስራኤል በምታራምደው ወግ

ያለው ዲሞክራሲ፣ በአይሁዳዊያን ላይ በደረሰው ፀረ-ሴማዊነት ግፍ እንዲሁም ከፍልስጤማውያን አሸባሪዎች ጋር በምታካሂደው ትግል ምክንያት ለእስራኤል ያዘናሉ፡፡ ዳሩ ግን የአይሁድ-ክርስቲያን ግንኙነት ያረፈባቸው መሠረቶች ባለፉት ዘመናት በአይሁዶችና ክርስቲያኖች መካከል ከወዳጅነት ይልቅ የጠላትነትን ስሜት ሲቀሰቅሱ መኖራቸው ልብ ሊባል ይገባል፡፡[145] ባለፉት ምዕተ ዓመታት ክርስቲያኖች እርስበርሳቸው በጦርነት የተጨፋጨፉ ቢሆንም፣ ፀረ-ሴማዊነትን በማራገብና በዚያው ዙሪያ በአይሁዳዊያን ላይ ታላቅ እልቂትንና ጭፍጨፋን በማካሄድ አንደኛ ደረጃ የሚሰጣቸው የአይሁዳዊያን ጠላቶች ክርስትያኖች መሆናቸውንም አሳይተዋል፡፡ እንዲሁም ክርስቲያን ጽዮናውያንን ጨምሮ አንዳንድ የክርስቲያን መሠረተኞች አሁንም ቢሆን የአይሁዳውያንን ወደ ክርስትና መጠመቅ እንደ አንድ ትልቅ የወንጌል ተልዕኳቸው አድርገው ይመለከቱታል፡፡ ስለሆነም በአይሁድና በክርስትያኖች መካከል እንዳለ የሚነገረው ይህ ‹‹የባህል ትስስሮሽ›› አሜሪካውያን ለአይሁድ ሕዝብና መንግሥት ዘላቂ ድጋፍ እንዲሰጥ ይፈልጋሉ ከሚል መደምደሚያ ላይ ላያደርስ እንደሚችል ሊሰመርበት ይገባል፡፡

በተከታታይ በሚመጡት ምዕራፎች በግልጽ እንደምናብራራው የአሜሪካ ሕዝብ እስራኤልን የመደገፍ ዝንባሌ እንዲኖረው በከፊል አስተዋጽኦ የሚያደርገው የእስራኤል ደጋፊዎች በእስራኤል ላይ የሚነሱ ትችቶች እንዲታፈኑና በአንጻሩ ግን የእርሷን ገጽታ አጉልተው የሚያሳዩ ጥረቶችን በማድረግ በሕዝቡ ሕሊና ውስጥ የሀዘኔታ ስሜት እንዲያብብ ሁኔታዎችን ስለሚያመቻቹ ነው፡፡ እውነቱን ለመናገር የእስራኤልን አጉራ ዘለል ድርጊቶች በአሜሪካ ሀገር ከመተቸት ይልቅ በራሷ በእስራኤል ውስጥ በስፋት መተቸቱ ይቀላል፡፡ አሜሪካ ውስጥ እስራኤልን የሚመለከቱ ግልጽነትና ቅንነት የሚታይባቸው ትችቶች በስፋት ቢለመዱ በተለይም ደግሞ በኃይል በያዘቻቸው ግዛቶች የምታራምደው መራር የሆነ የአፈና ፖሊሲ ለግልጽ ውይይት ቢቀርብ ኖሮ እስራኤል በአሜሪካ ሕዝብ ዘንድ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላት አጋር የመሆኗ ነገር አነስተኛ ድጋፍን ብቻ ባገኘ ነበር፡፡

የሆነ ሆኖ አሁንም ቢሆን የአሜሪካ ሕዝብ ለእስራኤል ያለው ሀዘኔታ በተለይም ደግሞ የተወሰኑ ፖሊሲዎቿን በተመለከተ የሚሰጠው ድጋፍ ያን ያክል ተጋንኖ መታየት የለበትም። ይህን ለማለት በቂ ምክንያቶችን ማቅረብ ይቻላል። ምንም እንኳን የአሜሪካ ሕዝብ ለእስራኤል ማለፊያ የሚባል ስሜት ቢኖረውና የአይሁዳዊቷ ሀገር በሕልውና እንድትኖር የሚፈልግ ቢሆንም፣ እስራኤልን ለመደገፍ ያለው ፍላጎት ያን ያክል ጥልቅ አይደለም። በአሁኑ ሰዓት ብዙ አሜሪካውያን ሀገራቸው እስራኤልን በጽናት በመደገፏ ምክንያት ምን ያክል ዋጋ እየከፈለች እንደሆነ ተገንዝበዋል። ለምሳሌ የፔው ጥናት ማዕከል ከእስራኤላውያንና ፍልስጤማውያን ለማን እንደሚያዝኑ አሜሪካውያንን ለብዙ ዓመታት ሲጠይቅ ቆይቷል።[146]

ዩናይትድ ስቴትስ እስራኤልን መደገፏ ያስከተለውን ውጤት በተመለከተ ይኸው የፔው ጥናት ማዕከል በጎዳር 2005 ባደረገው የአሰሳ ጥናት 39 ከመቶ የሚሆነው የአሜሪካ ሕዝብ ይህ ድጋፍ "ዋነኛው ዓለም አቀፋዊ የቅሬታ ምንጭ" መሆኑን ገልጿል። እንዲያውም ሃቁን ለማስቀመጥ ከተፈለገ 78 ከመቶ የሚሆኑት የውጭ ጉዳይ ልዩ ባለሙያዎች እስራኤልን መደገፍ አሜሪካ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን ገጽታ ክፉኛ እየጎዳው እንደሆነ የሚያምኑ መሆናቸውን ተናግረዋል።[147] የመስከረም 11ዱ ጥቃት ከደረሰ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ኒውስዊክ መጽሔት ባቀረበው የሕዝቦች አስተያየት መሠረት 58 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠው ያልተቋረጠ ድጋፍ ኡሳማ ቢን ላደን አሜሪካን ለማጥቃት እንዲወስን ምክንያት እንደሆነው የሚያምኑ መሆናቸውን ተናግረዋል።[148]

ከአሜሪካ ፖለቲከኞች ይልቅ ሕዝቡ የተወሰኑ የእስራኤል ድርጊቶችን የበለጠ የሚተች ሲሆን፣ ነገሮች እየተካረሩ ሄደው የአሜሪካን ብሔራዊ ጥቅም ጉዳት ላይ የሚጥሉ ከሆነ ከእስራኤል ጋር ያለው ግንኙነት ቢቋረጥ እንደሚመርጡ ብዙዎች እየገለጹ ይገኛሉ። በምዕራፍ 7 ላይ እንደምናብራራው በ2003 የተደረገ ሌላ የአሰሳ ጥናት እንዳሳየው 60 ከመቶ የሚሆኑት አስተያየት ሰጭዎች እስራኤል ከፍልስጤማውያን ጋር ያላትን ውዝግብ በአግባቡ ለመፍታት ፈቃደኛ የማትሆን ከሆነ እርዳታ እንዳይሰጣት እንደሚፈልጉ ገልጸዋል። 73 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ በዚያ ግጭት ውስጥ አሜሪካ የትኛውንም ወገን እንዳትረዳ የሚፈልጉ ሆነው ተገኝተዋል።[149] ከሁለት ዓመታት በኋላ በፀረ- ስም ማጥፋት ሊግ (ኤ.ዲ.ኤል) የተደረገ ሌላ ጥናት እንዳሳየው 78 ከመቶ የሚሆኑ አሜሪካውያን ዋሽንግተን እስራኤልንም ሆነ

ፍለስጤማውያንን መደገፍ እንደሌለባት ተናግረዋል።[150] የፔው ጥናት ማዕከል ዳይሬክተር የሆኑት አንድሪው ኮውት፡- “አማካኝ ቁጥር ያላቸው አሜሪካውያን ይህን የመሳከለኛውን ምሥራቅ ውዝግብ የሚመለከቱት በገለልተኛነት ስሜት ሲሆን ሀገራቸው አሜሪካም ብትሆን የገለልተኝነት ሚና እንድትጫወት ነው የሚሹት›› በማለት አስገንዝበዋል።[151]

በ2006 በተደረገው የሊባኖስ ጦርነት አሜሪካውያን ከመሪዎቻቸው በተቃራኒ እስራኤልን በተመለከተ ጠንካራ አቋም ያንጸባረቁ መሆኑ ይታወቃል። ጥናቶች እንዳመለከቱት ከግማሽ በላይ አሜሪካውያን እስራኤል በዚያ ጦርነት ለደረሰው ውድመት ግማሹን ወይም የበለጠውን ኃላፊነት መውሰድ አለባት የሚል አቋም ነበራቸው። በሁለት ሌሎች ጥናቶች ደግሞ መጠይቅ ከተደረገላቸው ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ዩናይትድ ስቴትስ ለየትኛውም ወገን አድሎ ማድረግ የለባትም ብለዋል።[152] አሜሪካ ይህ ሁሉ ተቃውሞ እያለባትም ከዚያ በፊት ታደርገው እንደነበረው ሁሉ በሊባኖስም ጦርነት ጊዜ እስራኤልን በግልጽ መደገፉን መርጣለች። ስለዚህ አሜሪካ ለእስራኤል የምታደርገው ለከት አልባ ድጋፍ በአሜሪካ ሕዝብ ፍላጎት ሊሳበብ የሚችል ፈጽሞ አይደለም።

ምዕራፍ አራት

‹‹የእስራኤል ሎቢ›› ምንድን ነው?

በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ብሔራዊው ፍላጎት እነርሱን በሚጠቅማቸው አቅጣጫ እንዲራመድ ያለመታከት የሚጥሩ፣ ሕግ አውጪዎችንና ፕሬዚዳንቶችን እንዲሁም ሌሎች የፖለቲካ አካላትን በማግባባትና በማሳመን እነርሱ የሚሹት ፖሊሲ በሥራ ላይ እንዲያውል ለማድረግ የሚታትሩ በፍላጎት የተደራጁ አካላት አሉ። እነዚህ እርስበርስ የሚደጋገፉ አካላት ተጽዕኖአቸው ጦርነትን የሚመለከት ውሳኔን ጨምሮ በብዙ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዎች ላይ ይንጸባረቃል።

አንድ ቡድን ኃያል ከሆነ ወይም በፖለቲካው አካባቢ ተደማጭነቱ ከፍ ካለ ለሀገሪቱ የማይበጁ ፖሊሲዎች እንዲወጡና ተግባር ላይ እንዲውሉ ተጽዕኖ ሊያደርግ ይችላል። አንድ የተለዩ ኢንዱስትሪ ከውጭ ተፎካካሪዎቹ የሚደርስበትን ውድድር እንዲቋቋም የሚደረግለት የታሪፍ ማስተካከያ (ድጎማ) የተወሰኑ ኩባንያዎችን ይጠቅም ይሆናል። ሆኖም ግን የዚያን ኢንዱስትሪ ምርቶች የሚሸምቱ ተጠቃሚዎች ምርቶቹን ለመግዛት ተጨማሪ ገንዘብ እንዲከፍሉ ያደርጋቸዋል። ብሔራዊው የጠብመንጃ አምራቾች ማህበር የመሣሪያ ቁጥጥር እንዲኖር የሚያስችል ሕግ እንዳይፀድቅ ማድረግ መቻሉ ያለጥርጥር መሣሪያ አምራቾችንና ነጋዴዎችን ጠቅሟቸዋል። ሆኖም ግን የቀረውን የህብረተሰብ ክፍል ከጦር መሣሪያ ጋር ለተያያዙ ዘርፈ ብዙ ጉዳቶችና ግጭቶች ዳርጎታል። የቀድሞው የአሜሪካ ፔትሮሊዮም ኢኒስቲትዩት መብት ተቆርቋሪ የነበሩ ሰው በሁዋይት ሃውስ የአካባቢ ጥበቃ ካውንስል ዋና ሰብሳቢ ሆነው በተሾሙ ጊዜ ይህን ሥልጣናቸውን በግሪን ሃውስ የጋዝ ፍልቀትና በአካባቢ መቀት መጨመር (Global Warming) መካከል የሚነሳውን እሰጥ አገባ ለማቀዝቀዝ ተጠቅመውበታል። (ሰውዬው በኋላ ላይ ኤክሶን ሞቢል ኩባንያ ውስጥ ለመቀጠር ሥራቸውን በፈቃዳቸው ከመልቀቃቸው በፊት ነበር ያን

ያደረጉት)፡፡ ታዲያ ይህን የታዘበ ማንም ቢሆን የነዳጁ ኢንዱስትሪ ሁላችንንም በሚጎዳ መልኩ ጥቅሙን እያስከበረ መሆኑን ሲመለከት የመረበሽ ስሜት ቢያድርበት አያስደንቅም፡፡[1]

የነዳጅና የኃይል ፍላጎት በአካባቢ ጥበቃ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያመጣው ሁሉ በተመሣሣይ ሁኔታ የእስራኤል ሎቢም በአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ላይ ተጽዕኖ ያሳድርበታል፡፡ ሎቢ በሚያደርገው አካል ውስጥ የሚገኙ ቡድኖችና ግለሰቦች ዩናይትድ ስቴትስ በመካከለኛው ምሥራቅ ስትራቴጂያዊና ሞራላዊ መሠረቶችን ያላገናዘበ ፖሊሲ እንድትከተል ዋነኛ ምክንያት መሆናቸውን እናምናለን፡፡ ይህ የሎቢ ጥረት ባይኖር ኖሮ አሜሪካ ስትራቴጂያዊና ሞራላዊ ታሳቢዎችን እግምት ውስጥ ሳታስገባ ገደብ የለሽ እርዳታዋን ለእስራኤል ለመስጠት ባልበቃችና ዛሬ በመካከለኛው ምሥራቅ የምትከተለው ፖሊሲ የተለዬ ሊሆን በቻለ ነበር፡፡ እስራኤልን የሚደግፉ ኃይሎች ያደረጓቸውን ግፊቶችና ጥረቶች ሁሉ በማድረጋቸው ዛሬ የአሜሪካንም ሆነ የእስራኤልን ብሔራዊ ጥቅም ያራመዱ መስሎ እንደሚሰማቸው አያጠያይቅም፡፡ እኛ ግን በዚህ አንስማማም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ አካላት የደገፏቸውና ያራመዷቸው ፖሊሲዎች የአሜሪካንም ሆነ የእስራኤልን ጥቅሞች አስከብረዋል ብለን አናምንምና፡፡ በእኛ እምነት ሁለቱም ሀገራት የተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኙ የነበረው ዩናይትድ ስቴትስ የተለዬ የፖለቲካ አካሄድ ተከትላ ቢሆን ኖሮ ነበር፡፡

በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደሞከርነው አሜሪካ የእስራኤልን በሕልውና መኖር መደገፏን ጥያቄ ውስጥ እየከተትን አይደለም፡፡ ይህማ በግልጽ ተገቢነቱ ታምኖበት በመላው ዓለም የሚገኙ ቢያንስ 160 የሚሆኑ ሀገራት እውቅና የሰጡት ጉዳይ ነው፡፡ እኛ ጥያቄ የምናነሳውና በትክክልም ማብራሪያ የሚያሻው ነገር ዩ.ኤስ. አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠው የድጋፍ መጠንና ይህም ድጋፍ ገደብና ቅድመ ሁኔታ አልባ የመሆኑን ጉዳይ ነው፡፡ (በምዕራፍ አንድ ላይ በይበልጥ እንደተብራራው ማለት ነው)፡፡ እንዲሁም ዩናይትድ ስቴትስ በመካከለኛው ምሥራቅ የምታራምደው የእስራኤልን ደህንነትና ብልጽግና ብቻ ታሳቢ ያደረገ ፖሊሲም ተገቢ ማብራሪያ ያሻዋል፡፡ (ይህም በይበልጥ በምዕራፍ ሁለት ተብራርቷል)፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ

የእስራኤልን ሎቢ የሚያንቀሳቅሱትን ማዕከላዊ ቡድኖች ማንነት፣ በጊዜ ሂደት እንዴት እንዳደጉና አሁን ያሉበትን ደረጃ እንመለከታለን። ከዚህም በተጨማሪ የእነርሱ ተፎካካሪ ከሆኑት ‹‹የአረብ ሎቢ›› እና ‹‹የነዳጅ ሎቢን›› ከመሣሰሉት ጋር ሲነፃፀሩ ተጽእኖአቸው እንዴት ከፍተኛ ሊሆን እንደቻለ ማብራሪያዎችን እናቀርባለን። በቀጣዮቹ ምዕራፎች እነዚህ አካላት የመካከለኛውን ምሥራቅ የዩ.ኤስ. አሜሪካ ፖሊሲ ለእነርሱ በሚበጅ መንገድ ለመጠምዘዝ የተጠቀሙባቸውን ዘዴዎችና ስትራቴጂዎች እንዳስሳለን።

የእስራኤል ሎቢ ምንነት ሲገለጽ

ይህን ‹‹የእስራኤል ሎቢ›› የሚባለውን ቃል የተጠቀምነው የዩ.ኤስ. አሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እስራኤልን በሚጠቅም አቅጣጫ እንዲጓዝ የሚፈልጉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ለፈጠሩት ላላ ያለ ሕብረት (loose Coalition) መጠሪያነት ነው። ሎቢው ብቸኛ የሆነና በማዕከላዊ አመራር ስር የተዋቀረ ድርጅት አይደለም። ከዚያ ይልቅ በዚህ ዓይነተኛ ዓላማ ዙሪያ በስፋት የተሰባሰቡ ግለሰቦችና ቡድኖች ሲሆኑ፣ እነዚህ ቡድኖች አንዳንድ ጊዜ በተወሰነ ፖሊሲ ላይ የማይስማሙበት አካሄድ ይስተዋላል። ይህም ማለት አንዱ በሌላው ላይ አድማ ወይም ሴራ ይጎነጉናል ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል። ከዚያ በተቃራኒ እንዲያውም ሎቢ የሚያደርገውን አካል የሚያስገኙት ቡድኖችና ግለሰቦች፣ በፍላጎት የተሰባሰቡ ሌሎች ቡድኖችና ግለሰቦች በሚሠሩበት መንገድና አኳኋን ነው ተግባራቸውን የሚያከናውኑት።

‹‹ሎቢ›› የሚለውን ቃል ስንጠቀም በተወሰነ መልኩ የተሳሳተ ትርጉም እንዳይሰጠው እንሰጋለን። ምክንያቱም ብዙ ግለሰቦች እና አንዳንድ የተደራጁ ቡድኖች ይህን ላላ ያለ የግንኙነት ትስስራቸውን በመጠቀም ተጽእኖ በማድረጉ እንቅስቃሴ ውስጥ በቀጥታ ይሳተፋሉ ማለት አይደለም። (ማለትም በቀጥታ፣ በመደበኛነትና በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጡትን ባለሥልጣናት የማሳመን ሥራ ይሠራሉ ማለት አይደለም።) ከዚያ ይልቅ የሎቢው የተለያዩ ክፍሎች በተለያየ ሁኔታና መንገድ፣ ሆኖም ግን

አቅጣጫውና ግቡ ተመሣሣይ በሆነ አካኋን የአሜሪካን የውጭ ፖሊሲዎች ለሀገራቸው በሚጠቅም መልኩ ለመቃኘት ይረባረባሉ። አንድ ሰው የበለጠ እርግጠኛ ለመሆን ሎቢ በማለት ፋንታ ‹‹አፍቃሪ እስራኤል ማህበረሰቦች›› (Pro-Israel Communities) ወይም ‹‹የእስራኤል እንቅስቃሴ ደጋፊዎች›› የሚሉ ስያሜዎችን ሊጠቀም ይችላል። ምክንያቱም የተለያዩ ቡድኖች ተራ ከሆነ ሎቢ ራቅ ያለ እንቅስቃሴ ስለሚያደርጉ ነው። የሆነ ሆኖ ልክ እንደ "እርሻ ሎቢ" "የኢንሹራንስ ሎቢ"፣ "የጦር መሣሪያ ሎቢ" ወይም ሌሎች በጎሣ ዙሪያ የተሰባሰቡ ሎቢዎች በሚጠሩበት መንገድ እኛም ‹‹የእስራኤል ሎቢ›› የሚለውን ስያሜ መጠቀምን መርጠናል።[2]

ልክ እንደ ሌሎቹ የሚመሠረቱ ቡድኖች ሁሉ የእስራኤል ሎቢ የሚያካልለው ድንበር እንዲህ በቀላሉ ሊገኝ አይችልም። ምክንያቱም ሁልጊዜም ቢሆን ጠርዙ አካባቢ የያዙትን ደረጃና የሚጫወቱትን ሚና በትክክል ለመግለጽ አስቸጋሪ የሆኑ ግለሰቦችና ቡድኖች አይጠፉምና።[3] ያም ቢሆን የአሜሪካ ጽዮናዊያን ድርጅትን (ዜድ.ኦ.ኤ) የመሰሉ የሎቢውን አካላትና ኤ.ፒ.ኤም.ኤ.ጄ.ኦ (ኮንፈረንስ ኦፍ ሜጀር አሜሪካን ጅዊሽ ኦርጋናይዜሽን) የሚሰኘውን ድርጅት ም/ሊቀመንበር ማልኮልም ሆኒሊን የመሰሉ ወሳኝ ሰዎችን መለዬት አያስቸግርም። በተጨማሪም የሎቢው አካላት ያልሆኑት የአረብ አሜሪካውያን ብሔራዊ ሕብረት (ኤን.ኤ.ኤ.ኤ) እና የኮሎምቢያ የኒቨርስቲ ምሁር የሆኑትን ራሺድ ኻሊዲን የመሳሰሉትን ሰዎች በግልጽ ከዚህ የጽዮናውያን ሎቢ ለይቶ ማውጣት ያስፈልጋል። ይህ በእንዲህ እያለ ግን ሁልጊዜም ቢሆን የተወሰኑ ቡድኖችና ግለሰቦች ሚናቸው በሚገባ ግልጽ ባለመሆኑ ከአሻሚ ሁኔታ ላይ የሚወድቁ አይጠፉም። ልክ እንደሌሎቹ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የእስራኤል ሎቢ ድንበሮችም በግልጽ ያልተለዩና የተድበሰበሱ ናቸው ያልነው በዚህ ምክንያት ነው።

እንዲህ ያለውን ሁኔታ ግልጽ የሚያደርግልን ሎቢው ያልተማከለ፣ በሥልጣን ተዋረድ ያልተደራጀና የአባላቱ ቁጥርም የማይታወቅ መሆኑን ሲሆን፣ የአባልነት ካርድም ሆነ የመሥራችነት መብት የሚባል ነገርም የለም። የሎቢው አስኳል ድርጅቶች በግልጽ የተቀመጠ ግብ የዩ.ኤስ.

አሜሪካ መንግሥትና የአሜሪካ ሕዝብ ለእስራኤል ቁሳዊና ፖለቲካዊ ድጋፍ እንዲሰጡ ማነሳሳትና የእስራኤልን መንግስት ፖሊሲዎችና ይህን ግብ የሚያራምዱ ተጽእኖ ፈጣሪ ሰዎችን እንዲደግፉ ማድረግ ነው። ይሁን እንጂ ከሎቢው አስኳል ድርጅቶች ውጭ ያሉና ደብዛዛ ጥላ ያላቸው፣ ግና ለእስራኤል ራሳቸውን የሰጡ ቡድኖችና ግለሰቦችን እርዳታም የሎቢው አስኳል ድርጅቶች ይቀበላሉ። እንግዲህ ይህ የሎቢው አስኳል ብለን የምንጠራው አካል የተዋቀረው አሜሪካ-እስራኤል የሕዝብ ጉዳዮች ኮሚቴ (አይፓክ)፤ ዋሽንግተን ኢኒስቲትዩት ኒር ኢስት ፖሊሲ (ደብሊው አይ፣ ኤን፣ኢ፣ፒ)፣ ፀረ- ስም ማጥፋት ሊግ (ኤ.ዲ.ኤል) እና የተባበሩት የእስራኤል ክርስቲያኖች (ሲ.ዩ.ኤፍ.አይ) ከተባሉ ድርጅቶች አመራሮች ስብስብ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እስራኤልን በመደገፍ በየአካባቢያቸው ባሉ ጋዜጦች ላይ ጽሑፎችን የሚያወጡ፣ እንዲሁም የእስራኤልን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች በዋነኛነት ለሚያራምዱት የሎቢ አካላት ድጋፍ ይሆን ዘንድ ቼክ የሚልኩ ግለሰቦች ሰፊ በሆነው የሎቢው ማዕቀፍ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው።

ይህ ማለት ግን ለእስራኤል ጥሩ አመለካከት ያለው አሜሪካዊ ሁሉ የሎቢው አካል ነው ማለት አይደለም። የዚህን መጽሐፍ አዘጋጆች ሁኔታ እንደአብነት መጥቀስ የሚጠቅም ከሆነ እኛ አፍቃሪ እስራኤል (Pro-Israel) ነን። ይህን ስንል እስራኤል በሕልውና እንድትቆይ እንደግፋለን። ያከናወነቻቸውን ብዙ ስኬቶቿን እናደንቃለን፣ ሕዝቧም ሰላማዊና ብልጽግና የተሞላበት ሕይወት እንዲኖረው እንመኛለን። እንዲሁም የእስራኤል ሕልውና አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ዩናይትድ ስቴትስ ልትረዳት እንደሚገባ እናምናለን ማለታችን ነው። ሆኖም ግን የሎቢው አካሎች አይደለንም። እንዲሁም እስራኤልን የሚደግፍ የአሜሪካ ባለሥልጣን ሁሉም የሎቢው አካል ላይሆን ይችላል። እስራኤልን በመደገፍ በቋሚነት ድምፁን የሚሰጥ ሴናተር የግድ የሎቢው አካል ነው ሊባል አይችልም። ምክንያቱም ያን የሚያደርገው በቀላሉ እስራኤልን የሚደግፉ የተለያዩ ቡድኖችና ግለሰቦች ለሚያሳድሩበት ፖለቲካዊ ተጽዕኖ መልስ ለመስጠት ይሆናል።

በሌላ አገላለጽ የሎቢው አካል መሆን ማለት የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ለእስራኤል በሚበጅ መልኩ ይራመድ ዘንድ በትጋግ መንቀሳቀስ ማለት ነው። አንድ ድርጅት ይህን መስመር መከተል ዋነኛ የተመሠረተበት ግቡ እስከሆነ ድረስ ጠቀም ያለውን የበጀቱን ክፍልና አብዛኛውን ትኩረቱን ለዚሁ ዓላማው ማዋል አለበት። ጉዳዩን በግለሰብ ደረጃ የምናየው ከሆነ ደግሞ የተወሰነውን ሙያዊ ክህሎቱንና ግላዊ ሕይወቱን (በአንዳንድ አጋጣሚዎች እንዲያውም ከጥሪቱ አብዛኛውን ክፍል) የዩ.ኤስ.አሜሪካ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲ፣ ሀገሩን እስራኤልን በሚጠቅም መልኩ እንዲራመድ መዋጀት አለበት። የኒውዮርክ ታይምሱን ዴቪድ ሴንገር የመሰሉ ጋዜጠኞችና የዱክ ዩኒቨርስቲውን ፕሮፌሰር ጆንስተንን የመሰሉ የትምህርት ባለሙያዎች አልፎ አልፎ በሚያወጧቸው መካከለኛውን ምሥራቅ የሚመለከቱ ጽሑፎች ላይ የእስራኤልን ገጽታ መልካም አድርገው ቢያቀርቡ የሎቢው አካላት ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም። ሆኖም ግን የዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ አምድ አዘጋጅ (Columnist) ቻርለስ ክራውታመርና የቀድሞው የፕሪንስተን ዩኒቨርስቲ የታሪክ ባለሙያ በርናርድ ሊዊስ እንዲሁም እነርሱን የመሰሉ ለእስራኤል ሙሉ ወገንተኝነትን የሚያሳዩና አብዛኛውን ትኩረታቸውን ዋሽንግተን እስራኤልን የመርዳቷን ተገቢነት ለማሳመን የሚያውሉ ግለሰቦች በእርግጥ የሎቢው አካል ናቸው ቢባል ያስኬዳል።

እርግጥ ነው እያንዳንዱ ግለሰብና ቡድን ይህን ጉዳይ ለማራመድ የሚያደርገው ጥረትና የሚከፍለው መስዋዕት የሚለያይ የመሆኑን ያክል እያንዳንዱ ቡድን እስራኤልን በሚመለከት ጉዳይ የሚኖረው አቋምም እንደዚያው ይለያያል። ለምሳሌ የአሜሪካ ጽዮናውያን ድርጅት (ዜድ.ኦ.ኤ) የበላይ የሆኑት ሞሮቶን ክሌይን፣ የተባበሩት የእስራኤል ክርስቲያኖቹ (ሲ.ዩ.ኤፍ.ኤይ) ጆን ሄይግ እና አሜሪካን ፎር ሴፍ እስራኤል (ኤ.ኤፍ.ኤስ.አይ) የተባለው ድርጅት አባል ራኤል ጂን በመካከለኛው ምሥራቅ ሮድ ማፕ. የጸደቀውን የሁለት መንግሥታት እቅድ ይቃወማሉ። በእነርሱ እምነት እስራኤል ሁሉንም ወይም አብዛኛውን በኃይል የተያዘውን መሬት መውሰድ ይኖርባታል። በሌላ በኩል የዋሽንግተን ኢንስቲትዩት ፎር

ኒር ኤስት ፖ'ሊሲ (ደብሊው አይ. ኤን ኤ) አባል የሆኑት ዶኒስ ሮስ እና የብሩኪንግ ኢንስቲትዮሽን አባል የሆኑት ማርቲን ኢንዲክ የሰላሙን ሀሳብ በመደገፍ የእስራኤልን ድርጊቶች አልፎ አልፎ የሚያወግዙ ናቸው። ሆኖም ግን እነዚህ ሁሉ ግለሰቦች በመካከላቸው ያለው ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል ጠቀም ያለ ዲፕሎማዲያዊ፣ ኢሎኖሚያዊና ወታደራዊ ድጋፍ እንድትሰጣት ለማድረግ ያላቸውን ሙያዊና ፖ'ለቲካዊ ተጽዕኖ ይጠቀማሉ። እንደዚያም የሚያደርጉት እስራኤል፣ ዩናይትድ ስቴትስ የምትቃወመውን እርምጃ በምትወስድባቸው ጊዜያት ጭምር ነው። ስለሆነም ሎቢው በአንድ አቅጣጫ የሚራመድ ጠጣርና የማይለወጥ አድማ (ሴራ) እንደሆነ አድርጎ ማሰብ የተሳሳተ የመሆኑን ያክል የአሜሪካና የአይሁዳዊቷ ሀገር ልዩ ግንኙነት ተጠብቆ እንዲቆይ በትጋት የሚሠራን ሰው ከሎቢው ነጥሎ መመልከትም የዚያኑ ያክል ስህተት ይሆናል።

የአሜሪካ አይሁዶች የሚጫወቱት ሚና

የሎቢውን አብዛኛውን ክፍል የሚያሽከረክሩት የዩ.ኤስ.አሜሪካ የውጭ ፖ'ሊሲ በእነርሱ እምነት የእስራኤልን ጥቅም እንዲያስከብር እርግጠኛ ለመሆን በጥልቀት የሚሠሩና ዝግጁነት ያላቸው የአሜሪካ አይሁዶች ናቸው። እንደ ታሪክ ባለሙያው ሜልቪን አይ ኡርፍስኪ አገላለጽ፣ ‹‹በአሜሪካ ታሪክ የአይሁዶችን ያክል ለአንዲት የውጭ ሀገር እንደዚህ ዓይነት መጠነ ሰፊ የፖ'ለቲካ ጣልቃ ገብነት ያሳዩ ዘር አልታየም።›› ስቴቨን ቲ ሮዚንታል ይህን ሀሳብ በመጋራት የሚከተለውን ከትበዋል፡- ‹‹ከ1967 ወዲህ የአሜሪካ አይሁዳውያን ለእስራኤል ያደረጉትን ያክል የማንም ሀገር ዜጎች የሌላ ሀገርን ስኬት ለማፋጠን ዝግጁ ሆነው አልታዩም።››[4] የፖ'ለቲካ ሳይንስ ጠቢቡ ሮበርት ኤች ትሪስ በ1981 እንደገለጹት፡- ‹‹የእስራኤል ሎቢ 75 የሚሆኑ የተለያዩ ድርጅቶችን (በአብዛኛው አይሁዳዊ የሆኑ) ያቀፈ ሲሆን ሁሉም የእስራኤል መንግሥት የሚያራምደውን ፖ'ሊሲና የሚወስዳቸውን እርምጃዎች በትጋት የሚደግፉ ናቸው›› ብለዋል።[5] የእነዚህ ቡድኖችና ግለሰቦች እንቅስቃሴ አፍቃሪ እስራኤል የሆኑ የአሜሪካ

ፖለቲከኞችን ዝም ብሎ ከመደገፍ ራቅ ያለ ሆኖ ለፖለቲከኞችና ለዜና ወኪሎች ደብዳቤ መጻፍ፣ ለእስራኤል ለሚያደሉ የፖለቲካ ተወዳዳሪዎች የገንዘብ መዋጮ ማድረግና የእነርሱን አጀንዳ በቀጥታ ለሚያቀርብላቸው ወይም በቀጥታ ለሚያነጋግራቸው አፍቃሪ እስራኤል የፖለቲካ መሪ ሞቅ ያለ ድጋፍ መስጠትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ግን የእስራኤል ሎቢ ከአሜሪካ አይሁድ ማኅበረሰብ ጋር አንድ ነው ማለት አይደለም። "የአይሁድ ሎቢ" የሚለው አገላለጽ ዩ.ኤስ አሜሪካ እስራኤልን እንድትረዳ የሚያበረታቱ ግለሰቦችንና ቡድኖችን ሁሉ የሚወክል አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ በአሜሪካ አይሁዳውውያን መካከል ለእስራኤል ባላቸው ስሜትና በዝግጁነታቸው ጥልቀት (depth of Commitment) ልዩነት ያለ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በግምት ከእነርሱ ውስጥ ሲሶ የሚሆኑት እስራኤልን እንደ ትልቅና የተለዩ አጀንዳቸው አድርገው አይመለከቱም። ለምሳሌ በ2004 በሚገባ የተከናወነ ጥናት እንዳሳየው 36 ከመቶ የሚሆኑት የአሜሪካ አይሁዶች ከእስራኤል ጋር ያላቸው ስሜታዊ ቅርርብ ‹‹በጣም ጥሩ›› የሚባል ያልሆነ እንዲሁም፣ ‹‹ጨርሶ የሌለ›› የማይባል መጠነኛ ሆኖ ተገኝቷል።[6] በተጨማሪም ለእስራኤል የሚጨነቁ የሚባሉ ብዙ አይሁዳውያን ሎቢውን የተቆጣጠሩት ድርጅቶች የሚያራምዷቸውን ፖሊሲዎች እንደማይደግፉ ተረጋግጧል። ይህም ማለት ማንኛውም መሣሪያ የመታጠቅ ፈቃድ ያለው አሜሪካዊ አር.ኤን.ኤ. የሚባለው ማህበር የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች ወይም ማንኛውም ጡረተኛ የAARPን ፖሊሲዎች እንደማይደግፈው ሁሉ ማለት ነው። ለምሳሌ የአሜሪካ አይሁዶች ከጠቅላላው የአሜሪካ ሕዝብ ይልቅ አሜሪካ ወደ ኢራቅ ጦርነት መግባቷን በአነስተኛ ሁኔታ ነበር የደገፉት። ያም አቋማቸው ቁልፍ ከሚባሉት የእስራኤል ሎቢ አድራጊ ድርጅቶች አቋም ተቃራኒ ነበር። ምክንያቱም ድርጅቶቹ ጦርነቱ እንዲደረግ እጅግ የበዛ ፍላጎት አሳይተዋልና። በመጨረሻም እስራኤልን በጽናት ከሚደግፉ ግለሰቦችና ድርጅቶች መካከል የተወሰኑት ለምሳሌ ክርስቲያን ጽዮናውያን- አይሁዶች አይደሉም። ስለሆነም በሎቢው ውስጥ አብላጫውን ሥፍራ የያዙት

አይሁዶች ቢሆኑም የእስራኤል ሎቢ ብለን የምንጠራው በእስካሁኑ የተካተቱትንና ልል የሆነ ግንኙነት ያላቸውን አካላት በሙሉ ነው። እናም ሎቢ የሚሰኘውን አካል ይበልጥ የሚገልጸው ሃይማኖታዊ ወይም ጎሣዊ ማንነት ሳይሆን የሚያራምደው የተለዬ ፖለቲካዊ አጀንዳ እንደሆነ ሊሰመርበት ግድ ይላል።

ብዙ አሜሪካያን አይሁዶች ከእስራኤል ጋር ያላቸው ግንኙነት የበለጠ እየተጠናከረ መሄዱን ለመገንዘብ አስቸጋሪ አይለም። ይህ ጉዳይ ይበልጥ በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ እንደተብራራው ከሀገራቸው ውጭ የሚኖሩ ሌሎች የተለያዩ ዜጎች ለትውልድ ሀገራቸው ካላቸው ዳራ (Back ground) ጋር ተመሳሳይነት አለው።[7] ምንም እንኳን በዩናይትድ ስቴትስ የሚኖሩ አይሁዳውያን የጽዮናዊነት እንቅስቃሴ ገና በጮርቃነት ላይ በነበረባቸው ጊዜያት እንቅስቃሴውን ለመደገፍ ያመነቱ ቢሆንም፤ ሒትለር በ1933 ሥልጣን እንደያዘ ግን ሀሳባቸውን ቀይረው በሚያስገርም ሁኔታ የጽዮናዊነትን እንቅስቃሴ ደገፉ። ከዚያ በኋላ ደግሞ በተለይ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት እንደፈነዳ በአይሁዳውያን ላይ ሽብርና መከራ በስፋት ከመድረሱ ጋር ተያይዞ የነርሱም ድጋፍ ጨመረ።[8]

ይህ በእንዲህ እያለም በ1948 እስራኤል እንደተመሠረተች ጥቂት አይሁዶች ብቻ ነበሩ ወደ እስራኤል ሄደው ለመኖር ፈቃደኛ ሆነው የተገኙት። ሁኔታውን ያስተዋሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ቤን ጎርዮንና ሌሎች የእስራኤል መሪዎች መጀመሪያ ላይ ቅር ተሰኝተውበታል። የሆነ ሆኖ እስራኤልን ለመደገፍ ቃል መግባትና ዝግጁ ሆኖ መገኘት የብዙ አሜሪካውያን አይሁዶች መታወቂያ ባሕሪ ለመሆን ብዙ ጊዜ አልወሰደም።[9] ታሪካዊ በሆነችው የፍልስጤም ምድር የአይሁዳውያንን መንግሥት ማቋቋም ታላቅ ተሳምራዊ ክስተት ሆኖ መቆጠሩ አልቀረም። ክስተቱ ይበልጥ ጎላ ብሎ የታዬው ደግሞ ከአይሁዳውያኑ የናዚ ሆሎኮስት እልቂት በኋላ ነበር። እስራኤል በዚያ በረሃ ውስጥ ያሳየቻቸው ሁለንተናዊ እመርታዎች ልክ እንደ እምቡጥ አበባ ያማሩና ግልጽ የሆኑ የኩራቷ ምንጮች ለመሆን በቁ። ከአሜሪካ ማህበረሰብ ጋር በፍጥነት እየተዋሃዱና ከሃይማኖተኛነትም እየራቁ ሲሄዱ ይታዩ የነበሩት አይሁዶች ራሳቸውን ከእስራኤል ጋር

ይበልጥ አስተሳሰሩ፡፡ ሮዚንታል የተባሉ ፀሐፊ ሁኔታውን ከታዘቡ በኋላ የሚከተለውን አስፍረዋል፡-

“እስራኤልን ከአይሁድ ሃይማኖት ጋር የተያያዘች እንደሆነች አድርጎ ማሰብ ለብዙዎቹ አይሁድ አሜሪካውያን ራሳቸውን ከሃይማኖት ለማራቅ አመቺ ዘዴ ሆኖላቸው ነበር፡፡ ምክንያቱም አሜሪካን ሀገር ያለው የጠለቀ ዓለማዊነት 8000 ማይሎች ርቆ በአይሁዳዊቷ ሀገር ምኩራቦች የሚፈጸመውን ሃይማኖታዊ ትውፊት እንደጥንት ዘመን ተረት ስላራቀው የአሜሪካ አይሁዳዊያን ሕይወት በዓለማዊነት ላይ ብቻ የተንጠለጠለ እስራኤል ተኮር (Israel-centered) ሆኖ እንዲታይ አድርጎታል፡፡ ስለሆነም በየጊዜው እያደገ የሄደውን ለሃይማኖት ግድየለሽ መሆን ለመቋቋም ብቸኛው መድሃኒት እስራኤል ብቻ መሆኗን ብዙዎች አመኑበት፡፡ እናም በመጀመሪያ የእስራኤልን እጅግ ሰፊ የሆነ የፋይናንስና ፖለቲካ ድጋፍ ፍላጎት ለማርካት የተለያዩ ድርጅቶች አቆጠቆጡ...ገንዘብ ማሰባሰብና ሎቢ ማድረግ የአሜሪካ አይሁዶች ከእስራኤል ጋር ያላቸው ግንኙነት መገለጫዎች ሆነው ብቅ አሉ፡፡››[10]

የአሜሪካ አይሁዶች ዋነኛ አጀንዳቸው እስራኤልን መጥቀም የሆነ የሲቪል ድርጅቶች ሰልፍ የሚታይባቸው አስደናቂ ማህበረሰቦች ሆኑ፡፡ ይህንን ግባቸውንም ለመምታት የሚከተሉት ስትራቴጂ ይበልጥኑ ያተኮረው በአሜሪካን የውጭ ፖሊሲ ላይ ተጽዕኖ በማሳረፍ ነበር፡፡ ከእነዚህ ሎቢ አድራጊ ድርጅቶች መካከል ዋነኞቹ የአሜሪካ እስራኤል ሕዝብ ጉዳዮች ኮሚቴ (አይፓክ)፣ የአሜሪካ አይሁዶች ድርጅት (ዜድ.ኦ.ኤ)፣ የእስራኤል ፖሊሲ ፎረም (አይ.ፒ.ኤፍ)፣ የአሜሪካ አይሁዳውያን ኮሚቴ (ኤ.ጄ.ሲ)፣ አሜሪካን ፎር ሴፍ እስራኤል (ኤ.ኤፍ.ኤስ.አይ)፣ የተሻሻለው ጽዳይዝም ሃይማኖታዊ ማዕከል፣ የአሜሪካን ሊኩድ ፍሬንድስ፣ መርከዝ ዩ.ኤስ.ኤ፣ ሐዳስ እና ሌሎች ብዙ ድርጅቶች ይገኙበታል፡፡ የማህበራዊ ሳይንስ ጥናት ጠቢብ የሆኑት ቻይም አይ ዋክስማን ባቀረቡት ዘገባ መሠረት፡- ‹‹በ1992 የአሜሪካን ጂዊሽ ይር ቡክ የተባለው መጽሐፍ ከ90 በላይ ብሔራዊ የአይሁድ ድርጅቶች እንዳሉ የዘገበ ሲሆን፣ እነዚህ ድርጅቶች ይበልጡንም ለጽዮናዊነትና ለአፍቃሪ እስራኤል እንቅስቃሴዎች ራሳቸውን የሰጡ ናቸው፡፡

ሌሎቹ ደግሞ የእስራኤልን ደህንነት በማስከበር፣ መንግሥቷን በመደገፍና ገጽታዋን በማሳመር ሂደት ላይ የተሰማሩ ናቸው በማለት ይገልጻል›› ብለዋል፡፡ ዋክስማን አክለው ሲናገሩ "ከእነዚያ 90 የሚሆኑ ድርጅቶች ውስጥ 51 የሚሆኑት ትላልቅና በጣም ጠቃሚ ድርጅቶች አንድ ላይ በመሆን "ኮንፈረንስ ኦፍ ፕሬዚዳንትስ ኦፍ ሜጀር አሜሪካን ጀዊሽ ኦርጋናይዜሽን" በሚል ስያሜ በአንድ ጥላ ስር ተሰባሰቡ፡፡ የዚህ መሪ ድርጅት ዋነኛ ዓላማ እነዚያን የተበታተኑ ቡድኖች እስራኤልን በሚጠቅም መልኩ ወደ አንድነት ማምጣት እና የዩ.ኤስ.አሜሪካንና የእስራኤልን ልዩ ግንኙነት ማጠናከር ወይም ማሳደግ" ነበር፡፡[12]

ሎቢው በተጨማሪም ጀዊሽ ኢንስቲትዩት ፎር ናሽናል ሴኪውሪቲ አፌርስ (ጄ.አይ.ኤን.ኤስ.ኤ)፣ ሚድልኢስት ፎረም (ኤ.ም.ኢ.ኤፍ)ና ዋሽንግተን ኢኒስቲትዩት ፎር ኒር ኢስት ፖሊሲ (ደብሊው፣አይ.ኤን.ኢ.ፒ) የተባሉትን የምርምርና ሐሳብ አፍላቂ ማእከላት እንዲሁም በዩኒቨርስቲዎችና ሌሎች የምርምር ማዕከላት የሚሠሩ ግለሰቦችን ያካትታል፡፡ ከዚህ ሁሉ በተጓዳኝ ደግሞ በደርዘን የሚቆጠሩና አፍቃሪ እስራኤል የሆኑ የሕዝብ ጉዳይ ኮሚቴዎች (ፒ.ኤ.ሲ.ኤስ) የእስራኤል አጋር ለሆኑ ፖለቲካዊ ተወዳዳሪዎች ገንዘብ ለማንቆርቆር ዝግጁ ናቸው፡፡ ዘገባዎች እንደሚያሳዩት እነዚህ ኮሚቴዎች ብቻ በ2006 በተደረገው የአጋማሽ ዘመን (Mid-term) ምርጫ እስራኤልን ለሚደግፉ የኮንግረስ ተወዳዳሪዎች በግምት 3 ሚሊዮን ዶላር አዋጥተዋል፡፡[13]

ሎቢ ከሚያደርጉት አይሁዳዊያን ድርጅቶች መካከል የአሜሪካን የውጭ ፖሊሲ ማዕከላዊ አጀንዳው በማድረግ አይፓክን ወይም ኤ.አይ.ፒ.ኤ.ሲን የሚስተካከልና ታዋቂነት ያለው ማንም የለም። በ1997 ፎርቹን መጽሔት ዋሽንግተን ውስጥ ታላቁ ሎቢ አድራጊ ማን እንደሆነ ለኮንግረስ አባላት ባቀረበው መጠይቅ ኤ.ኤ.አር.ፒ. ተብሎ ከሚታወቀው የአሜሪካን ጡረተኞች ማህበር ቀጥሎ የአሜሪካ -እስራኤል ሕዝብ ጉዳዮች ኮሚቴ አይፓክ የሁለተኛነት ደረጃ ተሰጥቶታል፡፡ አይፓክ ጠንካራ ከሚባሉ ሌሎች ድርጅቶች፣ ማለትም ከኤን.አር.ኤ. እና ከመሳሰሉት ሎቢ አድራጊዎች ቅድሚያ ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡[14] ናሽናል ጆርናል ስተዲ በ2005 መጋቢት

ባቀረበው ተመሳሳይ መደምደሚያ ላይ አይፓክ ከኤ.ኤ.አር.ፒ. በመቀጠል ሁለተኛ ደረጃ ያለው ሎቢ አድራጊ ድርጅት እንደሆነ መስክሯል።[15] የቀድሞው የካንሳስ ስቴት የዲሞክራት ፓርቲ ተወካይ መርቪን ዲማሊ፣ ‹‹አይፓክ፣ ያለምንም ጥያቄ በኮንግረስ ውስጥ በሚገባ የተሳካለት ሎቢ አድራጊ ድርጅት ነው›› ብለዋል። የቀድሞው የኮንግረስ ውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበርና በኮንግረሱ ውስጥ ለ34 ዓመታት ያገለገሉት ሊ-ሃሚልተን በ1991፡- ‹‹አይፓክን በኮንግረስ ውስጥ የሚወዳደር ተጽዕኖ ፈጣሪ ድርጅት የለም። እነርሱ ራሳቸው በኮንግረሱ ውስጥ የኮሚቴ ያክል ሆነዋል።›› በማለት ሃቁን አስቀምጠዋል።[16]

አይፓክን የመሳሰሉት ቡድኖች እንዲህ ዓይነት ተጽዕኖ ለማድረግ የቻሉት በአንድ ሌሊት አልነበረም። በጽዮናዊነት ንቅናቄ የቀድሞ ዘመናትና እስራኤልም ከተመሠረተች በኋላ እንኳን ከመጋረጃ ጀርባ እስራኤልን በመወከል በአሜሪካ ፖለቲካ ላይ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ ሰዎችን ሎቢ ማድረግ የተለመደ ነበር። በተለይም ደግሞ ፕሬዚዳንቱንና ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ባለሥልጣኖቻቸውን፣ በአይሁዳውያን ጓደኞቻቸው፣ አፍቃሪ አይሁድ በሆኑ አማካሪዎቻቸውና በአይሁድ መሪዎች አማካኝነት ነበር ይህ ሎቢ የማድረግ ሥራ ይከናወን የነበረው። ለምሳሌ ፕሬዚዳንት ውድሮው ዊልሰን በ1917 የባልፎርን ሰነድ ሊቀበሉ የቻሉት የከፍተኛው ፍ/ቤት ዳኛ በነበሩትና ሊዊስ ዲ ብራንዲስና ራቢ ስቴፈን ዋይስ በተባሉ አይሁዳዊያን ጓደኞቻቸው ከፊል ተጽዕኖ ነበር። በተመሳሳይ ሁኔታ ፕሬዚዳንት ሃሪ ኤስ ትሩማን የእስራኤልን መንግሥት መመስረት ሊደግፉና ከሁሉም ሀገራት በፊት እውቅና ሊሰጧት የቻሉት (ምንም እንኳን ስማቸው በትክክል ባይገለጽም) በአይሁዳውያን ጓደኞቻቸውና አማካሪዎቻቸው ተጽዕኖ ፈጣሪነት ምክንያት ነበር።[17]

የኋላ ኋላ አሜሪካ ውስጥ ያሉ አይሁዳውያን ተጽዕኖአቸው እጅግ እያየለ በመሄዱ አሜሪካ እስራኤልን በሁሉም መስክ እንድትደግፍ ለማድረግ የከፈቱት ዘመቻ ፈሩን እየሳተ ሄደ። ይህም የፀረ- ሴማዊነት እንቅስቃሴ በአሜሪካ ውስጥ እንዲያቆጠቁጥ ምክንያት ከመሆኑም በላይ፣ የአሜሪካ አይሁዶች የሁለት መንግሥታት ታማኝነት (dual Loyalty) ጥያቄ እያስነሳ

መምጣቱ አልቀረም፡፡ በመሆኑም ነገሮችን ረገብ አድርጎ በዘዴ መያዝና ሎቢ የማድረጉን ሂደትም ለስለስ ብሎ እንዲንዝ መወሰን ግድ ነበር፡፡ አይፓክ ራሱ በግልጽ የጽዮናውያን ድርጅት መሆኑ ይታወቃል፡፡ መስራቹ አይ.ኤል.ሲ.ኬናን በ1951 የአሜሪካ ጽዮናውያን ካውንስል ሰብሳቢ የነበሩ ሲሆን፣ ይህ ካውንስል ሎቢ ከሚያደርጉ ቡድኖች አንዱ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ከ1953 -54 ባለው ጊዜ ኬናን ይህን ካውንስል የአሜሪካ ጽዮናውያን የሕዝብ ጉዳዮች ኮሚቴ በሚል መጠሪያ አደራጅተውት ነበር፡፡ ቆይት ብሎ ደግሞ በ1959 ኤ.አይ.ፒ.ኤ.ሲ. (አይፓክ) የሚለውን መጠሪያውን ያዘ፡፡ የኬናን ሎቢ የማድረግ ስልት ይበልጡን የተመሠረተው የሕዝብ ንቅናቄ በመፍጠርና ዘመቻ በማድረግ ሳይሆን ‹‹የኬናን ስልቶች›› የሚባሉ ስልቶችን ተጠቅመው የእስራኤልን ጥቅም ለማስከበር በመሞከር ነበር፡፡ ከእነዚህ ስልቶች መካከል ለምሳሌ አንዱ እንዲህ ይላል፡- ‹‹ከሕጉ ጎላ ተሰውረህ ተንቀሳቀስ፡፡ በምንም መልኩ ፊት ለፊት ቀድመህ አትገኝ፡፡››[18]

ፎርዋርድ የተባለው የአይሁዳውያን መጽሔት ዋና አዘጋጅ ጄ.ጄ. ጎልድ በርግ እንዲህ ይላል፡- ‹‹በአሜሪካ የፖለቲካ ምህዳር የጽዮናውያን ተጽዕኖ እያየለ የመጣው በፕሬዚዳንት ኬኔዲና ጆንሰን አስተዳደር ጊዜ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚያ ዘመን የአይሁዳውያን ብልጽግና እና ተሰሚነት ጨምሮ ስለነበር ነው፡፡ በዚህም የተነሣ በርካታ አይሁዳውያን የሁለቱ ፕሬዚዳንቶች አማካሪዎችና የግል ጓደኞቻቸው ለመሆን የቻሉ ሲሆን፣ በምርጫ ውድድር ጊዜ ጠቀም ያለ ገንዘብ በመለገስ የሚታወቁ ሀብታም አይሁዶች ጭምር በዙሪያቸው ተሰባስበው ይገኙ ነበር፡፡"[19] እንግዲህ ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል አይፓክ መካከለኛ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞችና በጀት በማንቀሳቀስ አነስተኛ ተግባር የሚያከናውን ድርጅት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ "እስከ 1960ዎቹ አጋማሽ ድረስ እስራኤልን የሚወክልና የተደራጀ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ግልጽ ሆኖ አልወጣም ነበር" በማለት ስቱዋርት ኤዚኒስታት የተባሉ ሰው ይገልጻሉ፡፡[20]

የሎቢው እንቅስቃሴ አድማስ፣ የገንዘብ አቅሙና ተጽዕኖ ፈጣሪነቱ እያደገና ትርጉም ያለው እየሆነ የሄደው ከ1967ቱ የስድስት ቀን ጦርነት በኋላ ነው፡፡ ኤዚኒስታት እንደሚገልጹት ‹‹ይህ የስድስቱ ቀን ጦርነት እስራኤል ነፃ ሀገር

ለመሆን ካደረገችው ጦርነት በኋላ የአሜሪካ አይሁድ ማህበረሰቦች ብቃት እንዳላቸው እንዲሰማቸው ያደረገ ክስተት ነበር፡፡›› በሆሎኮስት የተፈጠረውን ዘግናኝ ክስተት የፀረ-ሴማዊነት ንቅናቄው ለአይሁድ ሕዝብ በሚገባ ማድረስና ማሳመን በመቻሉ የአሜሪካ አይሁዳውያን በመካከላቸው ልዩነቶችን አስወግደው የሚፈልጉትን የፖለቲካ ግብ ለማራመድ ቀደም ባሉት ዓመታት ይታይባቸው የነበረውን ፍርሃት እንዲያሸንፉ አግዟቸዋል፡፡ እስራኤል የአይሁዳዊነት ማንነት መገለጫ የትኩረት ማዕከል እየሆነች በመምጣቷ ምክንያት አይሁዳውያን በመላው ዓለም ያለምንም ችግር ከየሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋራ ሳይሳቀቁ የመዋሃድ እድላቸው እንዲሰፋ አጋጣሚውን ፈጥሮላቸዋል፡፡ ስለሆነም ይህን ተጨባጭ ሁኔታ ከፖለቲካው ጋር ላለማዛመድ የሚያስችሉ ምክንያቶች በጣም ኢምንት ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡[21]

ከ1969-70 በግብጽና እስራኤል መካከል በተደረገው የማድከም ጦርነት (War of attrition) እና በ1973 በተደረገው የረመዳን ጦርነት ጊዜያት የአይሁድ ድርጅቶች ለእስራኤል ደህንነት የሚያደርጉትን ጥረት ይበልጥ አሳድገውታል፡፡ ከሁለቱ የጦርነት ውጤቶችም በተገኘው የእስራኤል ጦር የውጊያ ብቃት ኩራት የተሰማቸው ቢሆንም፣ በሌላ በኩል ደግሞ በማንኛውም ሰዓት ሊደፈርስ የሚችለው የእስራኤል ፀጥታ ስጋት ላይ የጣላቸው በመሆኑ የአይሁድ ማህበረሰብን የሚወክሉ ብዙ ድርጅቶች እስራኤልን ማዕከል ያደረገ የእርስ በርስ ግንኙነት ለመመስረት ተነሳሱ፡፡[22] ቀደም ሲል ናሽናል ጆዊሽ ኮሚኒቲ ሪሌሽንስ አድቫይዘሪ ካውንስል (ኤን.ጄ.ሲ.አር.ኤ.ሲ) ይባል የነበረውና በኋላ ጀዊሽ ካውንስል ፎር ፐብሊክ አፌርስ የሚል ስያሜ የተሰጠው ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ አልበርት ቸርኒን ይህን አስተያየት እደሚጋሩ በ1978 በሚከተለው አባባል ገልጸውታል፡- ‹‹እርግጥ ነው የአሜሪካ አይሁድ ድርጅቶች የእርስ በርስ ግንኙነት ዋና ትኩረት እስራኤል ናት፡፡››[23]

አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠው እርዳታ አፍቃሪ እስራኤል የሆኑ ድርጅቶች በመዋጮ ወደ ሀገራቸው የሚልኩትን ገንዘብ መብለጥ ሲጀምር ድርጅቶቹ ፊታቸውን ከኢኮኖሚያዊ እርዳታ ወደ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ

መልሰው አሜሪካ ለሀገራቸው የምትሰጠውን እርዳታ ታሳድግ ዘንድ ግፊት ማድረጋቸውን ተያያዙት፡፡ ወርዝማየር እንደሚገልጹት፡- ‹‹የአሜሪካ ፖለቲከኞችን ሎቢ የማድረጉ ኃላፊነት በጠቅላላ የወደቀው በአይሁድ ድርጅቶች ፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስና በአይፓክ ትከሻ ላይ ነበር፡፡ ሁለቱም የተመሠረቱት በ1950ዎቹ ሲሆን ከ1967ቱ የስድስቱ ቀናት ጦርነት በፊት ይጫወቱት የነበረው ሚና በመካከለኛ ደረጃ የተወሰነ ነበር፡፡ እስራኤልን በዓለም አቀፉ የፖለቲካ ምህዳር የመደገፍ ፍላጎት እነዚህን ሁለት ደርጅቶች በ1970ዎቹና በ1980ዎቹ ወደ ታዋቂነቱ መንበር አስፈነጠራቸው፡፡›››[24]

እንግዲህ በዚህ መልኩ ሲጓዝ የቆየው እስራኤልን በሁለንተናዊ መልኩ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የመደገፍ ፖሊሲ እጅግ ውድ ዋጋ የሚያስወጣ እየሆነ መሄዱን ሁሉም የተገነዘበውና ይህንንም በፖለቲካው መድረክ በሚገባ ማሳመንና ማብራራት እንደሚያስፈልግ የተረዳው ከዚህ ሁሉ በኋላ ነበር፡፡ የአይፓክን የሥራ አመራር ዳይሬክተርነት ኬናን ከተባሉ ሰው በ1975 የተረከቡት ሞሪስ አሚታይ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹እስራኤልን ለመርዳት ከፈለግክ ልትሳተፍበት የሚገባህ ውድድር ስሙ የፖለቲካ ጨዋታ ይባላል፡፡ ››[25] በሞሪስ አሚታይና እርሳቸውን በተኳቸው ቶም ዳይን የአመራር ዘመን አይፓክ በአነስተኛ በጀት ከሚመራ እንቅስቃሴ 150 ሠራተኞችን ያቀፈ ወደመሆንና ከግል መዋጮ ከሚሰበሰብ ዓመታዊ በጀት (ለምሳሌ በ1973 300,000 ዶላር ነበር) አሁን ከ40-60 ሚሊዮን ዶላር በሚደርስ በጀት የሚንቀሳቀስ ሰፊ መሠረት ያለው ድርጅት ለመሆን በቅቷል፡፡[26] በኬናን ጊዜ እንደሆነው የመድረክ ላይ መብራት አጥፍቶ በመንቀሳቀስ ፋንታ አይፓክ ይባስ ብሎ ያለውን ጠንካራ ጉልበት ማስተዋወቁን ነበር የመረጠው፡፡ የዚህ ሎቢ አድራጊ ድርጅት አንድ የቀድሞ ባለሥልጣን ያለፉትን ዘመናት የድርጅቱን አሠራር ሲገልጹ፡- ‹‹እንከተለው የነበረው ንድፈ ሀሳብ ‹ሌሎች ስላንተ እስካላወቁ ድረስ ማንም ሊያስፈራራህ አይችልም› የሚል ነበር ብለዋል፡፡›[27] በቀድሞ ዘመን ይደረግ የነበረውን ሎቢ ከአሁኑ ጋር ስናነጻጽረው ፈጽሞ የተለዩ ሊሆንብን ይችላል፡፡ ቀድሞ የአይሁዶችን ጥቅም ለማስከበር የአይሁድ አማካሪዎችን እንዲሁም አይሁድ ያልሆኑና ለእስራኤል ሀዘኔታ ያላቸውን ሰዎች በመጠቀም ሎቢ የማድረግ ሂደት

የነበረ ሲሆን፣ ዛሬ ግን አይፓክ እና ሌሎች ሎቢ አድራጊ ድርጅቶች የሚያነሱትን አጀንዳ ‹‹እስራኤል ውስጥ ለሚገኙ አይሁዶች ሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረግ›› በማለት መሸፋፈን አይፈልጉም፡፡ ከዚያ ይልቅ አሁን የሚያተኩሩት የአሜሪካና እስራኤልን ስትራቴጂያዊ ፍላጎቶች እጅግ በረቀቁና በተውሰበሰቡ ስልቶች በማገላትና ሁለቱ አገሮች የሚደጋገፉባቸው የሞራል እሴቶች በፖለቲካው ምህዳር ላይ እንዲሰርጹ በማድረግ ነው፡፡

በቀዝቃዛው ጦርነት ጊዜያት የፓንዘብ አቅሙን ሲያጠናክርና በፖለቲካው ምህዳር ተገቢውን ቦታ ሲያመቻች የነበረው አይፓክ ከጊዜ በኋላ ደግሞ አዳዲስ በወጡና የምርጫ ተወዳዳሪዎችን በፓንዘብ ማገዝን በሚፈቅዱ የፌዴራሉ መንግሥት ሕጎች በመደገፍ ጡንቻውን እያፍታታ ሄደ ራሳቸውን የቻሉ የሕዝብ ጉዳይ ኮሚቴዎችን ወደማቋቋም ተስፈንጥሯል፡፡ በእነዚያ የሕዝብ ጉዳይ ኮሚቴዎች (ፒ.ኤ.ሲ.) አማካይነትም በመላ አሜሪካ ለሚገኙ አፍቃሪ እስራኤል (pro-Israel) የፖለቲካ ተወዳዳሪዎች የሚያስፈልጋቸውን ያክል የምርጫ ማካሄጃ ገንዘብ ይልክላቸዋል፡፡ አይፓክ በ1960ዎቹ ከፍ ያለና የተመሰገነ እንቅስቃሴ አሳይቷል ሊባል አይችል ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን በ1980ዎቹ በዋረን ባስ አገላለጽ፡- ‹‹የዋሽንግተን የጉልበት ቋት›› ለመሆን በቅቷል፡፡[28]

በልዩነት ውስጥ አንድነት፣ ባለመስማማት ውስጥ ስምምነት

ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተጠቀሰው የእስራኤል ሎቢ ማዕከላዊ በሆነ እዝ ስር ያልተደራጀና የሥልጣን ተዋረድ የማይታይበት ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ በሎቢው አይሁድ አካላት መካከል በተወሰኑ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ወሳኝ የሆኑ ልዩነቶች ይስተዋላሉ፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አይፓክ እና የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ የሚባሉት ሎቢ አድራጊ ድርጅቶች ሊኩድን ጨምሮ ጠጣሩን መስመር ከሚከተሉት የእስራኤል ፓርቲዎች ጋር የወገኑ ሲሆን፣ የኦስሎውን ስምምነትም በጥርጣሬ ነው የሚመለከቱት፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አሚኑ፣ አሜሪካንስ ፎር ፒስ ናው፣ ብሪት ጸዳቅ ቪሻሎም

(የአይሁዳውያን ጉድኝት ለፍትህና ለሰላም) ፣ እስራኤል ፖሊሲ ፎረም፣ ጀዊሽ ቮይስ ፎር ፒስ፣ ሜሬትዝ ዩ.ኤስ.ኤ እና ቲኩን ኮሚኒቲ የተባሉት አነስተኛ የአይሁድ ድርጅቶች የሁለት መንግሥታትን ፖሊሲ በጽናት የሚደግፉና እስራኤልም ፖሊሲውን ለማስፈጸም በቂ ጥረት ማድረግ አለባት ብለው የሚያምኑ ናቸው።[29]

ይህ በሎቢ ድርጅቶች መካከል የሚፈጠር ልዩነት አልፎ አልፎ በራሳቸው በድርጅቶቹ ውስጥ ወይም ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ካላቸው ግንኙነት አኳያ ስንጥቅ ሲፈጥር ይታያል። በ2006 ለምሳሌ የእስራኤል ፖሊሲ ፎረም፣ አሜሪካን ፎር ፒስ ናው፣ ጀዊሽ ፎር ፒስ እና ብሪት ጸዲቅ ቪሻሎም፣ የአሜሪካ ኮንግረስ ውሳኔ ቁጥር ኤች.አር 4681ን እንዲያሳልፍ አይፓክ ግፊት ማድረጉን በግልጽ ተቃውመዋል። ይህ የኮንግረስ ውሳኔ የእስራኤል መንግሥት እንኳ አድርጎት በማያውቀው ሁኔታ ለፍልስጤማውያን እርዳታ እንዳይደርስ እቀባ የሚጥል ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ ነበር።[30] ያ ውሳኔ በመጨረሻ ለስላሳ በሆነ ሁኔታ ተከልሶ እንዲያልፍ የተደረገ ቢሆንም፣ ክስተቱ የሚያስገነዝበን አፍቃሪ-እስራኤል ቡድኖች የአንድ ፓርቲ አሠራር መስመርን ተከትለው ሊንዙ የማይችሉ መሆኑን ነው።

ይሁን እንጂ ክፍፍሉ በአብዛኛው ትላልቅና ሀብታም በሚባሉት ድርጅቶች አሠራር ላይ ብዙም ተጽዕኖ ስለማያስከትል ዩ.ኤስ.አሜሪካ ምንም እንኳን እስራኤል ያሻትን ነገር ብትፈጽም እርዳታዋን እንዳታቋርጥባት ግፊት ከማድረግ አይመለሱም። የአይፓክ ቃል አቀባይ ሰኔ 2000 ላይ የሆነውን ሲያስታውሱ እንዲህ ይላሉ፦ ‹‹እስራኤል ለቻይና የጦር መሣሪያ መሸጧ እንደታወቀ አሜሪካ እርዳታዋን እንድትቀንስ የሚል ግፊት ተንቀሳቀሰ። እኛም አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠውን እርዳት ከማንኛውም ሁኔታና ክስተት ጋር ማገናኘት እንደማይገባ በመግለጽ ተቃወምን። የተጀመረው እርዳታ ፈጽሞ መቋረጥ የለበትምና።››[31] ዘ-ደቪሽ አሜሪካን ፎር ፒስ የተባሉት የሰላም ድርጅቶች እንኳን ሳይቀሩ ዩ.ኤስ.አሜሪካ የምትሰጣትን እርዳታ እስራኤል በኃይል በተያዙት ግዛቶች አዳዲስ ሠፈራ መንደሮችን ለመመስረት እስካላዋለችው ድረስ መቋረጥ የለበትም ሲሉ ተከራከሩ።[32] ሞደሬት እስራኤል ፖሊሲ ፎረም የሚባለው ድርጅት አሜሪካ ለእስራኤል

የምትሰጣት እርዳታ ከቅድመ ሁኔታ ጋር እንዲያያዝ በማድረግ ፋንታ አሜሪካ የሁለት መንግሥት ምሥረታ ሃሳብን እንድትገፋበት ለማሳመን ከመጣሩ ላይ ነበር ትኩረቱን ያደረገው።[33] ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል በሰላሙ ሀሳብ ዙሪያ አፍቃሪ እስራኤል ድርጅቶች የተለያየ አቋም የያዙና ልዩነት ያላቸው ቢሆንም፤ ሁሉም በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ልዩ ግንኙነት ግን እንዲቋረጥ አይፈልጉም። "ጆዊሽ ቮይስ ፎር ፒስ (ጄ.ቮ.ፒ)›› የተባለ አንድ ድርጅት ብቻ የዩ.ኤስ.አሜሪካ መንግሥት ለእስራኤል የሚሰጠውን ወታደራዊ እርዳታ እስራኤል በምዕራባዊው ዳርቻ፣ በጋዛና በእየሩሳሌም የምታደርገውን የአፈና አገዛዝ እስክታበቃ ድረስ ሙሉ በሙሉ እንዲያቋርጥባት ጠይቋል።[34] እርግጥ ነው እንዲህ ዓይነት አቋም የሚያራምደውን የአይሁድ ድርጅት ሁኔታ የሰማ ሰው በአጠቃላይ ድርጅቱ የሎቢው አካል አይደለም ብሎ ሊከራከር ይችላል።

የእስራኤል መሪዎች ዩ.ኤስ.አሜሪካ የምትሰጣቸውን እርዳታ ከፍ እንድታደርግላቸው በሚፈልጉ ጊዜ በተደጋጋሚ የሚያደርጉት የአሜሪካ አይሁድ መሪዎች በተወሰነ የእስራኤል ፖሊሲ ዙሪያ ድጋፍ እንዲያሰባስቡና በአሜሪካ ፖለቲከኞች ላይ ጫና ማሳረፋቸውን እንዲቀጥሉ ማሳሰብ ነው። የቀድሞው የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ ሊቀመንበር ራቢ አሌክሳንደር ሺንድለር ለአንድ የእስራኤል መጽሔት በ1976 በሰጡት ቃለ መጠይቅ፣ ‹‹የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስና አባል ድርጅቶቹ የእስራኤል መንግሥት ባለሥልጣናት መሣሪያዎች ሆነው ቆይተዋል›› በማለት ሃቁን ሳይሸሸጉ አስቀምጠዋል። ሺንድለር ቀጥለው ሲናገሩ፦ ‹‹ከመንግሥት የሥልጣን መዋቅር አካባቢ መመሪያ መቀበልና መተግበር በአይሁድ ማህበረሰብ ዘንድ የፈለገውን ዓይነት ተጽዕኖ ቢያስከትል እንኳን እንደ አንድ ትልቅ ግባችን አድርገን ነበር የምንወስደው›› ብለዋል። ሺንድለር አሁን ያንን ሁኔታ ሲያስታውሱት ‹‹ተቀባይነት የሌለው ነበር። ምክንያቱም የአሜሪካ አይሁድ ማህበረሰብ ማንም እንደፈለገ ወዲያና ወዲህ የሚያተረማምሰው መንጋ መሆን የለበትም›› በማለት ተናግረዋል።[35] ኤን.ጄ.ሲ.አር.ኤ.ሲ. የተባለው ድርጅት አባል የነበሩት አልበርት ቸርኒን በ1970ዎቹ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹አሜሪካ ውስጥ ለሚፈጠሩ ሁኔታዎች የራሳችን ፖሊሲዎች ነበሩን።

ሆኖም ግን የእስራኤልን ጉዳይ በተመለከተ ፖሊሲዎች በቀጥታ ከእስራኤል መንግሥት ነበር የሚወርዱልን፡፡..እውነቱን ለመናገር የአይሁድ ድርጅቶች ፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ እስራኤል ከአሜሪካ አይሁዶች ጋር የምትገናኝበት መሣሪያ ነበር ማለት ይቻላል፡፡››[36] አሪ ኒር የተባለው አንድ ስማቸው ያልተጠቀሰ የከፍተኛ አይሁድ ድርጅት አባል በ2005 የተናገሩትን የፎርዋርድ መጽሔት አዘጋጅ እንዲህ በማለት አስፍሮት ነበር፡- ‹‹እኛ ሁልጊዜም በአንድ ጉዳይ ስንወያይ ይህ የእኛ ፖሊሲ ነው እንላለን፡፡ ሆኖም ግን የእስራኤል ባለሥልጣናት በጉዳዩ ላይ ያላቸው አቋም ምን እንደሆነ ማረጋገጥ ግዴታችን ነው፡፡ በማህበረሰብ ደረጃ ተሰባስበን ተግባራችንን ስንከውን የኖርነው በዚህ መልክ ነበር፡፡›› ሃይመን ቡክባይንደር የተባሉት የአሜሪካ አይሁድ ማህበረሰብ ከፍተኛ ባለሥልጣን፡- ‹‹የተለየ ጫናና ሁኔታ ካላጋጠመን በስተቀር የእስራኤልን የፖለቲካ መስመር በመከተል ፍላጎቷን መደገፍ ግዴታችን ነው፡፡ እኛ እንደ አሜሪካ አይሁድ ማህበረሰብ ‹እስራኤል ማንኛውንም ጉዳይ በተመለከተ የምትከተለው ፖሊሲ የተሳሳተ ነው› ብለን አናውቅም” በማለት ተጨባጩን ሁኔታ አምነዋል፡፡››[37]

እስራኤል በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ደጋፊዎቿን ለማነሳሳት ያላትን ችሎታ በተለያዩ አጋጣሚዎች አስመስክራለች፡፡ ጽዮናውያን (በኋላ እስራኤላውያን) ባለሥልጣኖች በ1947 የተደረገውን የተባበሩት መንግሥታት የፍልስጤምን ምድር ለሁለት የመክፈል እቅድ እንዲሳካ ለማድረግ የአሜሪካ አይሁድ መሪዎች ዘመቻ እንዲከፍቱ ነግረዋቸው ነበር፡፡ እንዲሁም አሜሪካ በ1948 እስራኤል ራሷን የቻለች ሀገር መሆኗን እውቅና እንድትሰጣት ለማድረግም የቻሉ ሲሆን፣ የተባበሩት መንግሥታት ልዑክ የሆኑት ፎልክ በርናዶቴ ያቀረቡትን የሰላም ሀሳብ ውድቅ ለማድረግም እንዲሁ ሌላ ዘመቻ ማድረግ አስፈልጎ ነበር፡፡ ተመሳሳይ የሆነ የተቀናጀ ጥረት ማድረግ ያስፈለገበት ሌላም አጋጣሚ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ይኸውም በ1952 የፕሬዚዳንት ትሩማን አስተዳደር ለእስራኤል የሚሰጠውን እርዳታ ከፍ እንዲያደርግ ለማግባባትና ፔንታጎንና ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለግብጽ የ10 ሚሊዮን ዶላር ወታደራዊ እርዳታ እንዲሰጣት ያቀረቡትን እቅድ ውድቅ ለማድረግ ነበር፡፡[38] ከ1967ቱ የስድስቱ ቀን ጦርነት በፊት የእስራኤል

መንግሥት በዋሽንግተን ተቀማጭ ለነበሩት ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደሩ የሚከተለውን መመሪያ ሰጥቷቸው ነበር፡- “በጆንሰን አስተዳደር ላይ ግፊት የሚያሳድር የሕዝብ ንቅናቄ ፍጠር:: ያንንም ስታደርግ እኛ (የእስራኤልን መንግሥት ማለታቸው ነው) ከዚህ የሕዝብ ንቅናቄ ጀርባ እንደምንገኝ በግልጽ መታወቅ የለበትም፡፡ ጥረታችሁ ለእስራኤል በጎ አመለካከት ያላቸውን አሜሪካውያን አድራሻ እያፈላለጋችሁ ደብዳቤ መጻፍ፣ በተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ርዕሰ አንቀጾች ላይ አቋማችንን ማንፀባረቅ፤ በሕዝብ አስተያየት መስጫ ሰሌዳዎች ላይ ጽሑፎችን መለጠፍ ወዘተ... ያካተተ ሊሆን ይገባል፡፡›› በእስራኤል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እምነት ይህን ሁሉ ማድረግ ያስፈለገው በየግዛቶቹ ያሉ ወዳጆቻቸውን የሚያጠናክር ሕዝባዊ የድጋፍ መንፈስ ለመፍጠር ነው፡፡ ጥረቱ ቀጥሎ በተፋፋመበት ጊዜ የሁዋይት ሀውስ ባለሥልጣናት የእስራኤል አቻዎቻቸውን ደብዳቤ የመጻፉን ዘመቻ እንዲያስቆሙላቸው ጠየቋቸው፡፡ ሆኖም ግን በአሜሪካ ተቀማጭ የሆኑት አምባሳደር ወደ ቴሌአቪቭ በላኩት መልዕክት ‹‹በእርግጥ እኛ መጻፋችንን ቀጥለንበታል›› የሚል ሐረግ ይገኝበታል። የታሪክ ባለሙያው ቶም ሰጌቭ ሁኔታውን ሲያብራሩ፡- ‘‘ሁዋይት ሃውስ ቤተ-መንግሥት ፕሬዚዳንቱ ከእስራኤል ጎን እንዲቆሙ በሚጠይቁ ቀን ያልተጻፈባቸው ደብዳቤዎች ተጥለቅልቋል’’ ብለዋል፡፡[39]

የእስራኤልን ድርጊት በይፋ ያን በመሰለ አኳኋን መደገፍ ዛሬ ዛሬ በብዛት የሚስተዋል ክስተት አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ዋና ዋና የሚባሉት ሎቢ አድራጊ ድርጅቶች አሁንም ቢሆን በብዙ አጋጣሚዎች የእስራኤል መሪዎች የሚያራምዱትን አማራጭ መመሪያቸው አድርገው ይገለገሉበታል፡፡ ለምሳሌ በ2003 መጋቢት ወር ላይ የቡሽ አስተዳደር "ሮድ ማፕ" የሚባለውን የመካከለኛው ምሥራቅ የሰላም ሰነድ ይፋ ማድረጉን ተከትሎ ማልኮሎም ሆነሊን የተባሉት የአይሁድ ሎቢ አድራጊ ድርጅቶች ፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ አባል ሃ›አራትዝ ለተባለው ጋዜጣ የሚከተለውን መግለጫ ሰጥተው ነበር፡- ‹‹የእስራኤል መንግሥት ሮድ ማፕ የተሰኘውን ዕቅድ (ሰነድ) በተመለከተ የገለልተኝነት ወይም ቁጥብነት አዝማሚያ ካንፀባረቀ

የአሜሪካ አይሁድ ማህበረሰብ ይደግፈዋል፡፡ እኛ ድምፃችን እንዲሰማ ከማድረግ አናመነታም፡፡››[40]

ምንም እንኳን በእስራኤል መንግሥትና በአሜሪካ አይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ በሚገኙ የተወሰኑ ቡድኖች መካከል ክፍተቶች የሚታዩ ቢሆንም፣ በአጠቃላይ ሁኔታው ሲገመገም መሠረታዊ የሆኑ የጸጥታ ጉዳዮችን በተመለከተ በእስራኤል መንግሥት ላይ የሕዝብ ትችት እምብዛም አይሰማም፡፡[41] ስቲቨን ሮዚንታል የተባሉ ሰው እንዳስቀመጡት፡- ‹‹በሚሊዮን ለሚቆጠሩ አሜሪካውያን አይሁዶች እስራኤልን መተቸት አይሁዳዊ ካልሆነ ሰው ጋር ከመጋባት ይልቅ የከፋ ሀጢአት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡" ወይም ቡክባይንደር እንዳረጋገጡት፡- ‹‹የእስራኤልን መንግሥት አሠራር መጠራጠርና መመርመር በብዙ አይሁዳውያን ዘንድ እንደ ስህተት የሚቆጠር ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም የመንግሥቱን አሠራር እንዳለ (ከነጉድፉ) መቀበልን ይመርጣሉ፡፡››[42] የአሜሪካ አይሁዳውያንን አስተያየት ያሳባሰበ አንድ ጥናት እንዳረጋገጠው፡- ‹‹የሰላም ስምምነቱን በተመለከተ በግል የሚሰማቸውን ወደ ጎን ትተን ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑ አሜሪካውያን አይሁዶች እስራኤል ውስጥ በምርጫ ሥልጣን የያዘውን መንግሥት ፖሊሲዎች ይደግፋሉ፡፡"[43] በዚህም የተነሣ ምንም እንኳን የአሜሪካ አይሁዳውያን መሪዎችና ከፍ ያለ ተሰሚነት ያላቸው ሰዎች እስራኤል የምትከተላቸውን ፖሊሲዎች አስመልክተው ከበድ ያለ ቅሬታ ቢኖራቸውም፣ አሜሪካ በእስራኤል መንግሥት ላይ ጫና እንድታሳርፍ ጥሪ የሚያደርጉት አልፎ አልፎ ብቻ ነው፡፡ በእስራኤል መንግሥት ላይ የሚነሱ ትችቶችን የመቃወም ልማድ ባለፉት በርካታ አስርት ዓመታት በግልጽ ሲንጸባረቅ ተስተውሏል፡፡ ለምሳሌ በ1973 ተራማጅ የሚባሉ የአሜሪካ-አይሁዶች ብሬይራ (አማራጭ) የሚባል ድርጅት አቋቁመው ነበር፡፡ ይህ ደርጅት በእስራኤልና በውጭ በሚገኘው ዲያስፖራ መከከል ግልጽ ውይይት እንዲካሄድና እስራኤልም በኃይል ከያዘቻቸው የፍልስጤም መሬቶች ወጥታ የሰላም ስምምነት እንዲደረግ ጥሪ አቀረበ፡፡ የብሬይራ አመራሮች የሚሰማቸውን ነገር ሁሉ በተለያዩ ጋዜጦች ላይ ከመውጣታቸውም በተጨማሪ አሜሪካን ፍሬንድስ ሰርቪስ ኮሚቴ በሚባለው

ድርጅት ድጋፍ ከፍልስጤማውያን ጋር የግል ግንኙነት ካደረገው የአሜሪካ አይሁዶች ልዑካን ቡድን ውስጥ ተሳትፎ ነበራቸው።

ምንም እንኳን ጥቂት የአሜሪካ አይሁድ መሪዎች ብሬይራን ደግፈው ቢቆሙም፣ ከሌሎች ዋና ዋና የአይሁድ ድርጅቶች ጠንካራ ተቃውሞ ተነሳበት። የአይፓክ የመካከለኛው ምሥራቅ ሪፖርት ብሬይራን ‹‹ለእስራኤል የሚደረግን ድጋፍ ያንኳስሳል›› በማለት ወቀሳ አቀረበ። የሪፎርምድ ራባዮች (የተሸሻለ የአይሁድ ቀሳውስት) ሲኖዶስ ፕሬዚዳንት አርተር ሌይቭልድ ብሬይራን አስመልክተው ሲናገሩ፡- ‹‹ብሬይራን የመሰሉ ቡድኖች ለእነዚያ እስራኤል እርዳታ እንዳይሰጣት ለሚሟገቱና በገዳዮችና አሸባሪዎች ፊት መከላከያ አልባ ሆና እንድትቀር ለሚሹ ጠላቶቿ ረዳቶች ናቸው›› አሉ። ሃዳሳህ የተባለው ጋዜጣ ደግሞ የብሬይራ አባላትን፡- ‹‹የተሸናፊነት ፊት-አውራሪዎች›› በማለት ከወረፋቸው በኋላ፤ አባላቱ ብሬይራን የመሰሉ ድርጅቶች እንዲያንሠራሩና ለእስራኤል ደህንነትና ሕልውና አደገኛ የሆነውን ቀኖናቸውን እንዲያሰራጩ መፍቀድ እንደሌለባቸው አሳስቧል። የወግ አጥባቂ ራባዮች ስብስብ የተሰኘው ድርጅትም በበኩሉ፡- ‹‹ብሬይራ የፒ.ኤል.ኦ. አጋር ነው›› ካለ በኋላ አርባ ሰባት ራባዮች የፈረሙበትንና ‹‹የብሬይራ አቋም በተግባር ከአረቦች አቋም ጋር ተመሳሳይ ነው›› የሚለውን መግለጫውን ይፋ አድርጓል። እስራኤል በፍልስጤም መሬቶች የምታካሂደውን የሠፈራ ግንባታዎች የሚደግፈው አሜሪካንስ ፎር ሴፍ እስራኤል የተባለው ቡድን የብሬይራን መሪዎች ስም የሚያብጠለጥልና በግራ ዘመም ፖለቲከኛነታቸው የሚኮንን ሰላሳ ገጽ ሙሉ በራሪ ወረቀት ከበተነ በኋላ ብሬይራን፣ ‹‹ለፋታህ የቆመ የአይሁዶች ድርጅት›› በማለት በጽኑ እንደሚቃወመው ገልጿል። የአሜሪካ ጽዮናውያን ድርጅት (ዜድ.ኦ.ኤ) የሚያሳትመው "አሜሪካን ዚዮኒስት" የተባለው መጽሔት ደግሞ፣ ‹‹ብሬይራ የመናገርን ነፃነት አለአግባብ ይጠቀማል›› በማለት ክስ ካቀረበበት በኋላ፣ ‹‹በአደባባይ ለጠላቶቻችን የአዞ እንባ የሚያነቡ ወገኖች የዚህ ተንኮላቸው ውጤት እነርሱን የማይነካ ቢሆንም፣ በሺህ ማይሎች ርቀው ለሚገኙ አይሁድ ወገኖቻቸው እንደሚተርፍ ይገንዘቡት›› በማለት አስጠንቅቋል።

እንግዲህ በዚህ ሁሉ የስድብና የነቀፋ ውርጅብኝ ፊት የቆመው ብሬይራ ለውይይትና መቻቻል የሚያግዙ ሰፊ አጋጣሚዎችን ለመፍጠር ሳይችል ቀርቷል። ከዚያ በኋላ አሜሪካ ውስጥ የሚገኙ የአይሁድ ማህበረሰብ ቡድኖች ብሬይራን ከማህበራቸው የሰረዙት ሲሆን ኒው ሄቨን የሚባለው የአይሁዳውያን ማህበረሰብ ካውንስል በበኩሉ ብሬይራን ሊቀበለው የሚችለው የሚያቀርባቸውን ትችቶቹን ሁሉ ከአይሁድ ማህበረሰብ ውጭ ይፋ ላለማድረግ ከወሰነ ብቻ መሆኑን ግልጽ አደረገ። በአሜሪካ አይሁድ ኮሚቴ የተዘጋጀ አንድ ማዘጋጥ ግልጽ አንዳደረገው፣ ‹‹ብሬይራ አባል እንዲሆን የምትተባበሩት አባላቱ ወሳኝ በሆኑ የእስራኤል ዲያስፖራ አጀንዳዎች ዙሪያ ያሏቸውን ልዩነቶች ከአይሁድ ማህበረሰብ ውጭ ለሕዝብ ይፋ ላለማድረግ እስከተስማሙ ድረስ ብቻ ነው›› ይላል። ከዚህ ሁሉ ጫና በኋላ ነበር ለድርጅቱ ሥራ ማስኬጃ በቂ ገንዘብ ማግኘት ባለመቻሉና በመሪዎቹ የአስተዳደር ብቃት ማነስ መጀመሪያ እየደከመ የሄደው ብሬይራ ከተመሠረተ ከአምስት ዓመት በኋላ ከናካቴው ለመፍረስ የተገደደው።[44]

ብሬይራ ያስከተለውን ውዝግብ ተከትሎ ለዚህ ዓይነቱ ችግር ምላሽ ይሆን ዘንድ የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ፤ የአሜሪካ ሲናጎግ ካውንስል፣ የአሜሪካ አይሁዳውያን ኮሚቴ እና ኤን.ጄ.ሲ.አር.ኤ.ሲ. የሚባለው ድርጅት አጠቃላይ የሆነ የውስጣዊ አደረጃጀትና አሠራር ጥናት ካደረጉ በኋላ ከአንድ መደምደሚያ ላይ ደረሱ። ጄ.ጄ.ጎልድበርግ ይህን የመደምደሚያ ሀሳብ እንደሚከተለው ያቀርቡታል፦ ‹‹እነዚህ ሁሉ ድርጅቶች የደረሱበት ማጠቃለያ እያንዳንዱ የአሜሪካ አይሁድ በሚፈልገው ጉዳይ ዙሪያ ነፃ ውይይት ማድረግ ይችላል። ሆኖም ግን ምስጢራዊ በሆኑ ፎረሞችና ከአይሁድ ማህበረሰብ ውጭ ያሉ ሕዝቦች በማይሰሙበት መንገድ ብቻ መሆን ይኖርበታል።›› በ1976 በዩናይትድ ስቴትስ የእስራኤል አምባሳደር የነበሩት ሲምቻ ዲኒትዝ ኤን.ጄ.ሲ.አር.ኤ.ሲ. ከሚባለውና የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ ከተሰኘው ድርጅት ጋር በመሆን በአይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ በመመሪያነት የሚያገለግሉ ደንቦችን አርቅቀው አዘጋጁ። ጎልድበርግ እንደገለጹት የመጀመሪያው ደንብ እንዲህ ይላል፦ ‹‹የእስራኤል ፖሊሲ ምን መሆን እንዳለበት የመወሰን መብት ያላቸው እስራኤላውያን ብቻ ናቸው።›› ሁለተኛው ደንብ ደግሞ ‹‹የአሜሪካ አይሁዶች በእስራኤላዊነታቸው

በአደባባይ አንድነታቸውን ጠብቀው መታየት ያለባቸው ሲሆን፣ ልዩነትና ጠብ የግል ጉዳዮች ብቻ ናቸው።››[45] ኤድዋርድ ቲብናን የተባሉ ፖለቲከኛ በ1970ዎቹ እንደጻፉት፡- ‹‹በመላው አሜሪካ ውስጥ በሚገኙ የአይሁድ ማህበረሰቦች ዘንድ የአመራሩን መዘውር ለመጨበጥ እስራኤልን በአጠቃላይ መልኩ መደገፍ እንደ አንድ ወሳኝ መስፈርት ይቆጠር ነበር።››[46]

ይህ ሁሉ የሚያሳየው የእስራልን ፖሊሲዎች መተቸት ተቃውሞ የሚያስነሳ ጉዳይ እንደሆነ መቀጠሉን ነው።[47] ለምሳሌ በጥቅምት 1996 የአሜሪካ ጽዮናውያን ድርጅት (ዜድ.ኦ.ኤ.) ፕሬዚዳንት የሆኑት ሞሪስ ክሌይን የፀረ-ስም ማጥፋት ሊግ (ኤ.ዲ.ኤል.) ለሚባለው ድርጅት መሪ አብርሃም ፎክስማን ደብዳቤ ጽፈውላቸው ነበር። ሞሪስ ክሌይን በዚያ ደብዳቤያቸው ላይ፣ የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ አምድ አዘጋጅ የሆነው ቶማስ ኤል ፍሪድማን ኤ.ዲ.ኤል. ባዘጋጀው የራት ግብዣ ላይ ንግግር እንዲያደርግ መጠራቱን እንደሚቃወሙ ጠቅሰው፣ ያን ለማለት ያበቃቸው ፍሬድማን እስራኤልንና መሪዋን ቤንጃሚን ናታንያሁን በተደጋጋሚ ስማቸውን የሚያጠፋ በመሆኑ እንደሆነ ገልጸዋል። ክሌይን ከዚያ በኋላ በፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ ላይ ያንን ደብዳቤ ለባለሥልጣኖች ማሳየት ሲጀምሩ ፎክስማን ድርጊታቸውን በማውገዝ፣ ‹‹የሀሳብ ነፃነት ፖሊስ›› በማለት ወርፈዋቸዋል። ይህ ጠብ ይበልጥ የተባባሰው ደግሞ ዴቪድ ባር ኢላን የተባሉት የናታንያሁ ኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር ፍሪድ ማን ከእንግዲህ በማንኛውም ጽዮናዊ ነኝ በሚል ድርጅት ውስጥ መድረክ እንዳይሰጠው በግልጽ በተናገሩ ጊዜ ነበር። ፍሬድማን ምንም እንኳን የተወሰኑ የእስራኤል ፖሊሲዎችን የሚተች ቢሆንም፣ ያን ያክል ፀረ-እስራኤል አቋም ያለው ሰው አልነበረም። እንዲሁም ፎክስማንም ቢሆኑ እጅግ በጣም ኃይለኛ የሆኑ የእስራኤል ጠበቃ መሆናቸው ይታወቃል። ሆኖም ግን የክሌይን ድርጊት የሚያሳየው በመካከላቸው ያለው መቃቃር ከፍ ያለ ከመሆኑ የተነሣ በግልጽ ለመወያየት ያላስቻላቸው መሆኑን ነው።[48]

ይህ ሁሉ ከሆነ ከጥቂት ዓመታት በኋላ የዓለም አይሁዳውያን ኮንግረስ (ደብሊው ጄ.ሲ) ፕሬዚዳንት የነበሩት ኤድጋር ብሮንፍማን ለፕሬዚዳንት ቡሽ ደብዳቤ በመጻፍ እስራኤል አወዛጋቢ የሆነውን የፀጥታ ማስጠበቂያ ግንብ መገንባቷን እንድትገታ ጫና ያደርጉ ዘንድ በመጠየቃቸው በሽፍጠኝነት ተከሰሱ። የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ ምክትል ሥራ አስፈጻሚ

የነበሩት ኤሲ ሊብለር ለብሮፍማን ድርጊት ያላቸውን ተቃውሞ ሲገልጹት እንዲህ ነበር ያሉት፡- ‹‹ የዓለም አይሁዳውያን ኮንግረስ ፕሬዚዳንት ለሆነ ሰው የዩናይትድ ስቴትስን ፕሬዚዳንት ሎቢ በማድረግ፣ በእስራኤል መንግሥት ተነድፎ በተግባር ላይ እየዋለ ያለውን ፖሊሲ ለማጨናገፍ መሞከር አሳፋሪና ጸያፍ ድርጊት ነው፡፡››[49]

ሊብለርና ሌሎች አጋሮቻቸው በተመሳሳይ ሁኔታ ከሁለት ዓመት በኋላ ሌላ የሚያበሳጭ ነገር አጋጠማቸው። ይህም የሆነው ሞደራት እስራኤል ፖሊሲ ፎረም (ኤም.አይ.ፒ.ኤፍ) የተባለው ድርጅት ፕሬዚዳንት ሰይሙር ሪች እስራኤል በ2005 በጋዛ ሰርጥ ያለውን ወሳኝ የሆነ መተላለፊያ ትከፍት ዘንድ ተጽእኖ እንዲያደርጉ የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮንዶሊዛ ራይስን ባማከሩበት ጊዜ ነበር። ሪች ለኮንዶሊዛ ያቀረቡላቸው ምክር በሚገባ የታሰበበትና ተገቢነት ያለው ጭምር ነበር። ሆኖም ግን ሊብለር ድርጊቱን፡- ‹‹ኃላፊነት የማይሰማው ሰው ባሕሪ›› በማለት አወገዙት፡፡ ኦርቶዶክስ ዩኒያን የተባለው ድርጅት ፕሬዚዳንት ስቴፈን ሳቪትስኪ ደግሞ፣ ‹‹ይህ ድርጊት የእስራኤልን መንግሥት ያለማክበር ብቻ ሳይሆን እንዲህ ያለውን ተግባር የሚቃወሙ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አይሁዳዊያንን የሚያስከፋ ነው›› በማለት ውግዘታቸውን አሰሙ፡፡ ሊብለር በበኩላቸው የሁኔታውን አፍራሽነት ሲያስጠነቅቁ እንዲህ አሉ፡- ‹‹በዓለም አቀፉ የአይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ አንድ የተበላሸ ነገር ያለ መሆኑን የሚያሳየን ዋና ዋና የሚባሉ አመራሮች በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠው የእስራኤል መንግሥት የሚከተላቸውን ፖሊሲዎች በመቃወም እንዳሻቸው ሎቢ ማድረግ የሚችሉ የሚመስላቸው መሆኑን ስንመለከት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ባሕሪ ችለን የምናልፍ ከሆነ በመላው ዓለም ተበትኖ ያለው የአይሁድ ዲያስፖራ የጣለብንን አደራ ልንሸከም አልቻልንምና ሁሉንም ነገር ትተን ዝም ብለን መቀመጥ ነው ያለብን››፡፡ ሪች ከዚህ የወቀሳ ዱላ በኋላ አስተያየታቸውን ሲሰጡ፡- ‹‹የእስራኤልን ጉዳይ በተመለከተ "ግፊት ያድርጉ" የሚል ቃል ከአንደበቱ አልወጣም›› በማለት ከፍልሚያው ለማፈግፈግ ሞክረዋል፡፡[50]

የእስራኤልን ፖሊሲዎች በግልጽ ለመተቸት ሁሉም የማይፈልግ እየሆነ መሄዱን ለመገንዘብ አይከብድም፡፡ የእስራኤልን ጠላቶች ሊያግዝ የሚችል አንዳች ዓይነት ትችት ከማሰማት የመቆጠብ አስፈላጊነት ግፊቱ እያየለ

መምጣቱ እንዳለ ሆኖ የእስራኤልን ፖሊሲዎች ወይም የእስራኤልንና አሜሪካን ግንኙነት የሚተቹ ቡድኖችና ግለሰቦች በአይሁድ ኮሚዩኒቲ ውስጥ ድጋፍ ለማግኘትም ሆነ ገንዘብ ለማሰባሰብ ይቸገራሉ። በተጨማሪም ዋና ዋና በሚባሉት ድርጅቶች የመገለልና ወደ ዳር ተገፍቶ የመቅረትን አደጋም ይጋፈጣሉ። ይህን በመሰለው ሂደት ነበር ብሬይራ የተባለው ቡድን ወድቆ የቀረው። እንዲሁም አሜሪካን ፒስ.ፎር. ናው፣ ዘ ቲኩን ኮሚዩኒቲ፣ ዘ ኢስራኤል ፖሊሲ ፎረምና ዘ ኒው እስራኤል ፈንድ የተባሉት ድርጅቶች ለመትረፍ የበቁትና እስካሁንም ድረስ በሕልውና የሚገኙት ጠባብ በሆነ እድል ነው። ሌሎች ተራማጅ የሆኑና እንደ ኒው ጀዊሽ አጀንዳ ያሉት ቡድኖችም ተመሳሳይ ተቃውሞ አጋጥሟቸው ከአስር ዓመታት የበለጠ በሕልውና ሊቆዩ አልቻሉም።[51] ምንም እንኳ አሜሪካን ፎር ፒስ ናው የተባለው ድርጅት ከተከታታይ ትግል በኋላ በ1993 በፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ ተቀባይነት ማግኘት ቢችልም÷ ፕሮግሬሲቭ ሜሬትዝ ዩ.ኤስ.ኤ. እና ሊበራል ራኮን ሪኮንስትራንሽኒስት ራቢኒካል አሶሴዮሽን የተባሉ ድርጀቶች በኮንፈረንሱ ውስጥ መካከለኛ አቋም ባላቸው አባላት ቢደገፉም ቅሉ፣ በ2002 ግን የአባልነት መብት ተነፍጓቸዋል።[52]

በዛሬው ጊዜ የእስራኤልን ፖሊሲዎች በቀጥታ የሚቃወሙ አይሁዳውያንን ማግለል በስፋት እየተሠራበት ይገኛል። ተራማጅ የጽዮናውያን ሕብረት (ዩ.ፒ.ዜድ) የተባለው ድርጅት 2006 ላይ ዝምታውን በመግፈፍ የቀድሞ የእስራኤል ወታደሮች ሕብረት፣ የእስራኤል ጦር በኃይል በያዛቸው ግዛቶች የሚፈጽመውን ግፍ እንዲያወግዝ ገፋፍቶት ነበር። በዚህ ጊዜ የአሜሪካ ጽዮናውያን ድርጅት (ዜድ.ኦ.ኤ.) ተራማጅ የጽዮናውያን ሕብረትን (ዩ.ፒ.ዜድ) በማውገዝ አይ.ሲ.ሲ በሚል አህጽሮት ከሚጠራው የእስራኤል ካምፓስ ኮአሊሼን ከሚባለው ሕብረት እንዲባረር ጠየቀ። ሆኖም ግን ዩ.ፒ.ዜድ የተባለው ድርጅት ዳይሬክተር ቡድናቸው ለእስራኤል ያለውን ፍቅር በመግለጻቸውና ሌሎች አጋር ድርጅቶችም ከጎናቸው በመቆማቸው የአይ.ሲ.ሲ. መርማሪ ኮሚቴ የአሜሪካ ጽዮናውያን ድርጅት (ዜድ.ኦ.ኤ) ያቀረበውን ጥያቄ በሙሉ ድምፅ ወድቅ አደረጉ። በዚህ ሁኔታ የተበሳጨው የእስራኤል ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲህ የሚል ሪፖርት አወጣ፦ ‹‹የአይሁድ ኮሚኒቲዎች እንደዚህ ዓይነት ድርጅቶችን ለማቀፍ መፍቀዳቸው የሚያሳዝን ነው። ...እነዚህ ድርጅቶች በእስራኤል ገጽታ ላይ የሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽዕኖ መቆም አለበት።››[53]

ሎቢው እርምጃውን ቀጠለ

ብዙ የአሜሪካ አይሁዶች ሊበራል (ነፃ) አስተሳሰቦችንና ዲሞክራቲክ ፓርቲን ሲደግፉ መኖራቸው የሚታወቅ ሲሆን ከእነርሱ ውስጥ ብዙዎቹ ለእስራኤልና ፍልስጤም ግጭት የሁለት መንግሥታትን መመሥረት እንደ ሁነኛ መፍትሄ ይቀበላሉ፡፡[54] እንደዚያም ቢሆን በሎቢው ውስጥ ዋነኛ የሚባሉት አይፓክ እና የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስን የመሳሰሉት ድርጅቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ወግ አጥባቂና አክራሪ በሆኑ የእስራኤል የፖለቲካ አጋሮች በሚደገፉ ሰዎች ነው የሚመሩት፡፡ ጄ.ጄ. ጎልድበርግ የተባሉት ሰው በጻፉት የአይሁዳውያን ጉልበት (Jewish Power) የተባለ መጽሐፋቸው ላይ እንደጠቀሱት ‹‹ከስድስቱ ቀን ጦርነትና ከዚያ በኋላ የተከሰቱ ሁኔታዎች አይበገሬነታቸው የጸናና ቁጣቸው የበረታ ‹‹አዲስ አይሁዳውያን›› ጠጣሩን መስመር ከሚከተሉት ጽዮናውያንና ከወግ አጥባቂዎች ማህጸን ውስጥ እንዲፈጠሩ አደረጉ፡፡ ሌላው የአይሁድ ማህበረሰብ ከኋላ ሆኖ እነርሱ አመራር እንዲሰጡት በአክብሮት ፈቀደላቸው፡፡ በዚህም የተነሳ አናሳዎቹ ብዙሃኑን እንዲወክሉና በአይሁድ ፖለቲካ ላይ ተጽዕኖአቸውን እንዲያሳርፉ እድል አገኙ፡፡››[55]

ይህ አካሄድ በ1974 ጆንሰን ቫኒክ አሜንድመንት የተሰኘውን ስምምነት ለመደገፍ በተደረገው ዘመቻም ተጠናክሮ ቀጠለ፡፡ (ሶቬት ሕብረት የአይሁዳውያንን ስደት በመደገፏ የንግድ ተጠቃሚነቷን ያሳደገ ስምምነት ነበር፡፡) የአዲሱ ወግ አጥባቂ ቡድን በድንገት ማቆጥቆጥና የሊኩዊድ ፓርቲው ወደ ስልጣን መምጣት መስመሩን ይበልጥ አጠናከረው፡፡ ሊኩድ ፓርቲው አፍቃሪ እስራኤል በሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ጠጣሩን መስመር የሚከተሉ ቡድኖችን ለመደገፍ የተሳካ ጥረት ያደረገው ከእስራኤሉ ሌበር ፓርቲ ጋር በመጣመር ስልጣን በያዘ ጊዜ ነበር፡፡ ጎልድ በርግ እንዳሉት፡- ‹‹የሻሚር ስትራቴጂ በሳልነት የታየው ...የአይሁዳውያን ተወካዮች ዋነኛውን ማዕከላዊ ክፍል በማንቀሳቀስ -ወገንተኝነት ያሳዩ ሳይመስሉ የመንግሥት ግማሽ ለሆነው ሊኩድ ፓርቲ እንዲቆሙ ማድረግ በመቻላቸው

ነው፡፡ የሊኩድ ፓርቲው ባለሥልጣናት (የጠቅላይ ሚኒስትሩን ኢታማዦር ሹም ዩሲ.ቤን አህሮንን ጨምሮ) የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ የሚባለው የሎቢ ድርጅት በወግ አጥባቂዎች እንዲመራና ማልኮለም ሆነሊን ደግሞ በ1986 ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው እንዲመረጡ በትጋት ተንቀሳሰዋል፡፡ በዚሁ አሠራር መሠረት ጠጣሩን መስመር የሚከተሉ ብዙ ቡድኖች በእስራኤል መሪዎች ዘንድ የበለጠ ዕድልና ተሰሚነት ያገኙ ሲሆን፣ ይህም የአይሁድ ማህበረሰብ ባለሙሉ ሥልጣን ተወካዮች እንዲሆኑ አስችሏቸዋል፡፡ የሌበር ፓርቲው አማካሪ በመሆን ያገለገሉት ሽሞን ፔሪስ ቆየት ብለው እንዳመኑት፡- ‹‹የአሜሪካን አይሁድ ማህበረሰብ ችላ ማለታችን ነበር ትልቁ ስህተታችን፡፡ ….ያን በማድረጋችንም የሻሚር ሰዎች የፈገለጉትን እንዲያደርጉ መንገዱን አመቻችንላቸው›› ብለዋል፡፡[56]

ይህ ወደ ቀኝ የማዘመም ሂደት የሚያሳየው በአንዳንድ ቁልፍ የሎቢው ድርጅቶች ውስጥ ያለውን የውሳኔ አሰጣጥና ሀብታም የሆኑ አነስተኛ የወግ አጥባቂ ድርጅቶች አይፓክን የመሳሰሉትን ድርጅቶች ለመጫን በየጊዜው እያሳዩ የመጡትን ጉልበት ነው። ለምሳሌ የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ በሚባለው ትልቅ ድርጅት ውስጥ ከ50 የሚበልጡ ቡድኖች የታቀፉ ሲሆን፣ እያንዳንዳቸውም አቅማቸውንና ሁኔታቸውን ባላገናዘበ መልኩ በነፍስ ወከፍ አንድ ድምፅ አላቸው። ይሁን እንጂ ሚካኤል ማሲንግ እንዳስገነዘቡት፡- ‹‹በፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ ውስጥ ያሉት አናሳ ወግ አጥባቂ ቡድኖች ትልልቆችን ሊበራል ድርጅቶች በወሳኝ መልኩ በቁጥር ስለሚበልጡ የትላልቆቹን ተጽዕኖ ዋጋ ያሳጣዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ምክትል ፕሬዚዳንት ለሆኑት ማልኮለም ሆኒሊን ያሻቸውን ነገር በነፃነት የመወሰን ኃይል አጎናጽፎአቸዋል›› ብለዋል፡፡ እንደሚታወቀው እርሳቸው የእስራኤልን አዳዲስ የሠፈራ ግንባታዎች የሚደግፉና የኦሰሎን የሰላም ሂደትም የሚያጣጥሉ ናቸው፡፡[57]

በተመሳሳይ ሁኔታ የአይፓክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚወሰነው እያንዳንዱ ዳይሬክተር በሚያደርገው የገንዘብ አስተዋጽኦ እንጂ በአይፓክ ውስጥ ባላቸው የአባላት ብዛት አይደለም፡፡[58] አይፓክን ለሚደግፉ ፖለቲከኞች በምርጫ ጊዜ ግዙፉን የገንዘብ መዋጮ የሚሰጡ ድርጅቶች

እጅግ በጣም ቀናዒ የእስራኤል ደጋፊዎች እንደሆኑ ስለሚቆጠር የኤ.አይ.ፒ.ኤ.ሲን ወይም አይፓክን አመራርም የመቆናጠጥ እድላቸው ሰፊ ይሆናል፡፡ (ቀደም ሲል የነበሩ ፕሬዚዳንቶች አመራሩን የጨበጡት በዚሁ መልክ እንደነበረ ያጤኗል፡፡) ስለሆነም እነዚህ ወግ አጥባቂዎች በመካከለኛው ምሥራቅ ፖለቲካ ውስጥ ከሌላው የአሜሪካ አይሁድ ማህበረሰብ የበለጠ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ምንም እንኳን አይፓክ በ1993 የኦስሎን የሰላም ሂደት የደገፈ ቢሆንም፣ ለተግባራዊነቱ የተጫወተው ሚና ኢምንት ከመሆኑም በላይ፣ ኢሁድ ባራክ በ1999 ሥልጣን እንደያዙ የፍልስጤማውያን መንግሥት እንዳይቋቋም የነበረውን ተቃውሞ ይፋ ባልሆነ ሁኔታ ስቧል፡፡[59]

እርግጥ ነው አይፓክና ሌሎች ጠጣሩን መስመር የሚከተሉ ድርጅቶች በእስራኤል ከሚደገፉት ቡድኖች ሁሉ የበለጠ የጠርዘኝነት አቋም አራምደዋል፡፡ ለምሳሌ በ1994 አክራሪው የአሜሪካ ጽዮናውያን ድርጅት (ዜድ.ኦ.ኤ) ለፍልስጤማውያን አስተዳደር እርዳታ እንዲሰጥ የቀረበውን የሕግ ረቂቅ ማሻሻያ የራቢን መንግሥትና የክሊንተን አስተዳደር ጭምር እየደገፉት የሎቢ ጉልበቱን ተጠቅሞ በኮንግረሱ ወድቅ አስደርጎታል፡፡[60] የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ የኦስሎውን የሰላም ሂደት ፈጽሞ ያላፀደቀ ሲሆን፣ አይፓክ ደግሞ በ1995 አሜሪካ ኤምባሲዋን ከቴልአቪቭ ወደ እየሩሳሌም ለማዛወር ያደረገችውን ሙከራ ደግፏል፡፡[61] እርግጥ ነው ለአይፓክ በዋነኛነት ገንዘብ የሚለግሱት አካላት ምክትል ዳይሬክተሩን ቶም ዲንን የአክራሪነት አቋማቸው በቂ ባለመሆኑ ከዚያ ቦታ እንዲነሱ አድርገዋል፡፡[62]

በሎቢው ውስጥ ጽንፈኛ አቋም ያላቸውን ቡድኖች የመደገፉ አዝማሚያ እንዳለ ሆኖ፣ አፍቃሪ እስራኤል አንጃዎች ወደ ቀኝ የሚያዘነብሉበት ሌላ ምክንያትም ነበራቸው። ዋክስማን የተባሉ ፖለቲከኛ እንዳስቀመጡት፣ ‹‹ብዙ የአይሁድ አሜሪካውያን ድርጅቶች የራሳቸውን ሕልውና ሕጋዊ ለማድረግ ሲሉ እስራኤልን የግድ ይፈልጋሉ፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ድርጅቶች የተመሠረቱት እስራኤልን ለማጠናከርና ተጽዕኖዋን ከፍ ለማድረግ ቢሆንም፤ ዛሬ ግን በሕልውና ለመቆየት እስራኤል የግድ ታስፈልጋቸዋለች፡፡››[63] እነዚህ ድርጅቶች እስራኤልን በጠላቶቿ ዙሪያዋን

የተከበበችና ለጥቃት የተጋለጠች ደካማ አድርገው በማቅረብ፣ እንዲሁም የፀረ-ሴማዊነት እንቅስቃሴዎች እየተስፋፉ መሆናቸውን በመስበክ ብዛት ያላቸው ደጋፊዎቻቸውን በዙሪያቸው ለማሰባሰብና የድርጅታቸውን ሕልውና ለማራዘም ይጥራሉ፡፡ በ1992 ጆናታን ሬቸር የተባሉ የሰሜን አሜሪካ አይሁዳውያን ትምህርት አገልግሎት ባልደረባ ሁኔታውን ከታዘቡ በኋላ እንዲህ በማለት አስቀምጠውታል፡- ‹‹በመላው አሜሪካ እያቆጠቆጠ ያለውን አዲስ ኢንዱስትሪ እያየን ነው፡፡ ይህ ኢንዱስትሪ የተመሠረተው በመላው ዓለም የሚፈጠርን ፀረ- ሴማሲዊነት ለመዋጋት ሲሆን፣.... የስምዖን ዊዘንስታልን ማዕከል ስኬት ማየት ብቻ ያስደምማል፡፡ ይህ ድርጅት የፀረ-ስም ማጥፋት ሊግ (ኤ.ዲ.ኤል) የሚባለውንና የአይሁዳውያንን ፀጥታ የሚከታተለውን ሌላ ዋነኛ ድርጅት ከኋላው የመውጋት ያህል (ሥራውን በመሻማት ማለት ነው) በፖስታ በሚላኩ የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች ተጥለቅልቋል፡፡ ዛሬ ይህን የፀረ-ሴማዊነት ንቅናቄ ምሽግ አድርገው በመንቀሳቀስ በአይሁድ የህትመት ውጤቶች እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ እያሉ እርስበርስ የሚሻኮቱትን ድርጅቶች ሁኔታ ስናይ ማዘናችን አይቀርም››[64] ወይም ቶማስ ኤል-ፍሪድማን በኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ላይ እንደሚከተለው በማለት የጻፈውን ሁኔታው ያስታውሰናል፡- “ሚስተር ራቢንና ሚስተር አራፋት እጅ ለእጅ ከተጨባበጡ በኋላ ከዋና ዋና የአሜሪካ አይሁድ ድርጅቶች ያገኙት ድጋፍ በጣም ልዝብነት የተሞላበት ነበር፡፡ ይህ ሁኔታቸው ሲታይ እነዚህ ድርጅቶች ሊዋጉት የሚፈልጉት ድርጅት ከሌለ በስተቀር በሕልውና ሊቆዩ የማይችሉ እስኪመስል ድረስ ነበር የሰላሙን ሀሳብ እንደበረዶ ያቀዘቀዙት፡፡››[65]

በሌላ በኩል ደግሞ በአሜሪካ አይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ የእስራኤልን ፖሊሲዎች የሚቃወሙና በተለይም ደግሞ በኃይል በያዘቻቸው ግዛቶች መቆየቷን የማይደገፉ የተወሰኑ ድርጅች እንዳሉ መናገር ተገቢ ነው፡፡ ከእነዚህ ድርጅቶች መካከል የእስራኤል ፖሊሲ ፎረምና ብሪት ጻዲቅ ቪ ሻሎም የተባሉት ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ድርጅቶች፣ ዩ.ስ.አሜሪካ በሰላሙ ሂደት እንድትሳተፍ ባደረጉት ሂደት በቅርብ ዓመታት መለስተኛ የሆኑ ድሎችን ተጎናጽፈዋል፡፡ ሆኖም ግን በቂ የሆነ የፋይናንስ አቅም የሌላቸው

ከመሆኑም በላይ፣ የአይፓክን፣ ኤ.ዲ.ኤልን (የፀረ- ስም ማጥፋት ሊግ)፣ የአሜሪካ ጽዮናውያን ድርጅትን (ዜድ.ኦ.ኤ.)፣ የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስንና መሰል ድርጅቶችን ሃሳብ ብቻ ነው ፖለቲከኞች፣ የፖሊሲ አርቃቂዎች እና የአሜሪካ አይሁድ ማህበረተሰብን ልብ የሚስቡ የዜና ማሰራጫዎች የሚያራምዱት።[66] በዚህ ሁሉ ምክንያት የተነሳ ለጊዜው በሎቢው ውስጥ ያሉት ዋና ዋናዎቹ ድርጅቶች እንወክለዋለን ከሚሉት የአይሁድ ማህበረተሰብ መካከል የአብዛኛዎቹን አባላት ሀሳብ በሚቃረን መንገድ መንዛቱን ተያይዘውታል።

የወግ አጥባቂዎቹ ሚና

የሎቢው ወደ ቀኝ ማዘንበል ኒዎኮንሰርቫቲቭስ በሚሰኙት ዳግም ወግ አጥባቂዎች የሚደገፍ ነው። የኒዎኮንሰርቫቲቭ (ዳግም ወግ አጥባቂነት) ንቅናቄ ከ1970ዎቹ ጀምሮ የአሜሪካ ምሁራንና ፖለቲከኞች ሕይወት አካል ቢሆንም፣ ይበልጥ ትኩረት እያገኘ የመጣው ግን ከመስከረም 11 የሽብር ጥቃት በኋላ ነበር። ይህ ቡድን የፕሬዚዳንት ቡሽን አስተዳደር የአንድ ወገን ብቻ የሆነ የውጭ ፖሊሲ እንዲከተልና አሳዛኝ እጣ የገጠመውን የ2003 ቱን የኢራቅ ወረራ እንዲያደርግ ግፊት አሳርፎበታል።

ኒዎኮንሰርቫቲቪዝም የሚባለው የፖለቲካ ዘይቤ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ለዪት ያለ አመለካከት የሚያራምድ ቢሆንም፣ በዚህ ርዕስ ለጊዜው ትኩረት የምናደርገው የውጭውን ፖሊሲ የተመለከተውን ብቻ ይሆናል።[67] ብዙዎቹ የኒዎኮንሰርቫቲቭ አመለካከት አራማጆች አሜሪካ የሌሎች ሀገራትን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የምትቆጣጠርበትን የፖለቲካ ዘይቤ በማሞገስ የሚያበረታቱ ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም የአሜሪካ ኢምፓየርን ሀሳብም ያቀነቅናሉ። እንዲሁም የዩ.ኤስ. አሜሪካ ኃይል ዲሞክራሲን ለማስፋፋትና ከዩናይት ስቴትስ ጋር የሚፎካከር እምቅ ኃይል ያለው አገር ብቅ እንዳይል ለማዳከም መዋል አለበት ብለው ያምናሉ።[68] በእነርሱ እምነት የዲሞክራሴ መስፋፋትና የዩ.ኤስ አሜሪካ ልዕለ ኃይል ሆኖ መቆየት ለዓለም ሰላም ዘላቂነት ከሁሉም የተሻለው መንገድ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ

ኒዎኮንሰርቫቲቮች ተ.መ.ድን የመሳሰሉ ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶችን በጥርጣሬ የሚመለከቱ ከመሆኑም በላይ፣ ፀረ- እስራኤል የሆነ አቋም ያላቸውና አሜሪካ በነፃነት የፈለገችውን እንዳትፈጽም የሚያግዱ ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡ አውሮፓውያን አጋሮችን ደግሞ ሀሳባዊያን የሞሉበት፣ ያረጀና ያፈጀ የአመራር ዘይቤ የሚከተሉ ገትጋታዎች ጥርቅም እንደሆኑ ነው የሚያስቡት፡፡[69]

ከሁሉም በላይ ትኩረት የሚስበው ጉዳይ አሜሪካ ዓለምን በምትፈልገውና በሚጠቅማት መንገድ ለመቅረጽ ወታደራዊ ኃይል እጅግ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ የሚያምኑ መሆኑ ነው፡፡ ‹‹ዩናይትድ ስቴትስ ወታደራዊ ብቃቷን በየጊዜው ካሳየችና አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ ኃይሏን ለመጠቀም ከቻለች አጋሮቻችን አመራራችንን የሚቀበሉ ሲሆን፣ ጠላቶቻችን ደግሞ አሜሪካን ለመቋቋም መሞከር ከንቱ መሆኑን ተገንዝበው በፍጥነት አሰላለፋቸውን ከእኛ ጋር ያደርጋሉ፡፡››[70] ብለው ያስባሉ፡፡ ኒዎኮንሰርቫቲዝም በአጭሩ አገላለጽ አክራሪነትንና ተጋፊነትን የሚወክል የፖለቲካ ዘይቤ ነው ማለቱ ያስኬዳል፡፡

ኒዎኮንሰርቫቲቮች አሜሪካ ውስጥ በሚገኙ ብዙ ድርጅቶችና ተቋማት ውስጥ ወሳኝ የሆኑ ቦታዎችን ተቆጣጥረዋል፡፡ ዋነኛ ከሆኑት የዚህ የፖለቲካ ዘይቤ አራማጆች መካከል የቀድሞና የአሁን ዘመን ፖሊሲ አውጭዎች የሆኑት ኢሊዮት አብረሃም፣ ኬኔት ኤድልማን፣ ዊሊያም ቤኔት፣ ጆን ቦልተን፣ ዶግላስ ፌይዝ ፣ ጄን ኪርክፓትሪክ፣ አይ. ሊዊስ፣ ስኩተር ሊቢ፣ ሪቻርድ ፐርል፣ ፓውል ወልፍወኢትዝ፣ ጀምስ ውስሊ፣ ዴቪድ ውርምሰር እና መሰሎቻቸው ይገኙበታል። ከምሁራኑ በኩል ደግሞ ፉአድ አጃሚ፣ ኢሊዮት ኮኸን፣ አሮን ፍሪድበርግ፣ በርናርድ ሊዊስ እና ሩት ዌድጉድ እንዲሁም የመንግሥት አማካሪዎች ከሆኑት ባለሙያዎች ውስጥም እንደ ማክስ ቡት፣ ዴቪድ፣ ፍሩም፣ ራውል ማርክ ግሬች፣ ፎበርት ኬጋን፣ ሚካኤል ሌደን፣ ጆሹዋ ሙራቪክ፣ ዳንኤል፣ ፓይፕ፣ ዳንኤል ፕሌትካ፣ ሚካኤል ሩብንና መይራቭ ውርምሰርን የመሳሰሉት ይካተታሉ፡፡ ዋና ዋና የሚባሉት የኒውኮንሰርቫቲቭ መጽሔቶችና ጋዜጦች ደግሞ ኮሜንታሪ፣ ዘ ኒውዮርክ ሰን፣ የዎል ስትሪት ጆርናል የአስተያየት መስጫ አምድና ዘ ዊክሊ

ስታንዳርድ ናቸው፡፡ የመንግሥት አማካሪና ደጋፊ የሆኑና ከኒዎኮንሰርቫቲቭ ኃይሎች ጋር ቅርርብ ያላቸው ቡድኖች አሜሪካን ኢንተርፕራይዝ ኢንስቲትዩት (ኤ.ኢ.አይ)፣ ዘ ሴንተር ፎር ሴኩሪቲ ፖሊሲ (ሴ.ኤስ.ፒ)፣ ዘ ሆድሰን ኢንስቲትዩት፣ ዘ ፋውንዴሽን ፎር ዲፌንስ አፍ ዲሞክራሲስ (ኤፍ ዲ.ዲ)፣ ዘ ጆዊሽ ኢንስቲትዩት ፎር ናሽናል ሴኩሪቲ አፌርስ (ጄ.አይ.ኤን.ኤስ.ኤ)፣ ዘ ሚድል ኢስት ፎርም (ኤም.ኢ.ኤፍ) ፣ ዘ ፕሮጀክት ፎር ኒው አሜሪካን ሴንቸሪ (ፒ.ኤን.ኤ.ሲ.) እና ዘ ዋሽንግተን ኢንስቲትዩት ፎር ኒር ኢስት ፖሊሲ (ደብሊው አይ.ኤን.ኤ.ፒ) ናቸው፡፡

ከሞላ ጎደል ሁሉም የኒዎኮንሰርቫቲቭ የፖለቲካ ዘይቤ ተከታዮች እስራኤልን የሚደግፉና ያለምንም ማመንታት በግልጽ እርሷን ለማገዝ የቆሙ ናቸው፡፡ ማክስ ቡት የተባሉት ግንባር ቀደም የኒዎኮንሰርቫቲቭ አመለካከት አራማጅና ባለሙያ ‹‹እስራኤልን መደገፍ የኒዎኪንሰርቫቲዝም ዋናው መሰብሰቢያ ድንኳን እንደመሆኑ የሊበራል (ነፃ አስተሳሰብ) አራማጆች ዲሞክራሲያዊ እሴት ነው" በማለት የፖለቲካ ዘይቤውን ባሕሪ ለመግለጽ ሞክረዋል፡፡[71] ቤንጃሚን ጊንስበርግ የተባሉ የፖለቲካ ተመራማሪና ስለአሜሪካ ፖለቲካና በፀረ-ሴማዊነት እንቅስቃሴ ዙሪያ በስፋት የጻፉ ሰው አሳማኝ በሚመስል ሁኔታ የኒዎኮንሰቫቲቮች ወደ ቀኝ ማዘመም ዋነኛ ምክንያቶችን ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹ከእስራኤል ጋር ያላቸው ቁርኝትና በ1960ዎቹ የዲሞክራቲክ ፓርቲ የአሜሪካን መንግሥት ወታደራዊ ዝግጁነት በተመለከተ የሚያደርገው ተቃውሞ እየተጠናከረ መሄዱ፣ በሶስተኛው ዓለም ሀገራት ጉዳዮች ክፉኛ የመሳቡ ጉዳይ ተደማምረው ያሳደሩት ተጽዕኖ ነው፡፡›› ‹‹በተለይም›› ይላሉ ጊንስበርግ "ኒዎኮንሰርቫቲስቶች፣ የሮናልድ ሬገንን ፀረ-ኮሚኒዝም ጠባር መስመር መደገፍን መርጠዋል። ምክንያቱም ያንን መስመር መከተል የእስራኤልን ፀጥታ ለማስከበር የሚያስችል የፖለቲካ እንቅስቃሴ ነው ብለው በማመናቸው ነው፡፡››[72]

ኒዎኮንሰርቫቲስቶች አክራሪ የፖለቲካ አቋም አራማጆች መሆናቸውን ስናጤን በእስራኤል በራሷ ውስጥ ከቀኝ ክንፍ መስመር ተከታዮች ጋር መሰለፋቸው ሊደንቀን አይገባም፡፡ ለምሳሌ በሪቻርድ ፐርል የሚመራና ዶግላስ ሬይዝንና ዴቪድ ውርምሰርን ያካተተ ስምንት አባላት የሚገኙበት

የኒዎኮንሰርቫቲቮች ቡድን በ1996 ያረቀቀው “ክሊን ብሪክ” የተባለው ጥናት ቤንጃሚን ናታንያሁ ወደ ሥልጣን መንበር እንዲመጡ መንገድ ጠርጎላቸዋል። ይህ ጥናት እስራኤል የኦስሎን ስምምነት ወድቅ እንድታደርግ እንዲሁም ጋጠወጥነት የሚታይበት እርምጃ በመውሰድና ትብብር የማያሳዩ የመካከለኛው ምሥራቅ መንግሥታትን በመገርሰስ የአረብ እስራኤልን ግጭት በበላይነት ለመደምደም እንድትችል ያበረታታል።[73]

ብዙ የኒዎኮንሰርቫቲቭ የፖለቲካ ዘይቤ አራማጆች መሠረታቸውን ዋሽንግተን ካደረጉ የመንግሥት አማካሪዎች፣ ኮሚቴዎች፣ እንዲሁም ቀዳሚ አጀንዳቸውን የአሜሪካንና እስራኤልን ልዩ ግንኙነት ማራመድ ካደረጉ የህትመት ውጤቶች ጋር ንክኪ አላቸው። ለምሳሌ ቀንደኛ የኒዎኮንሰርቫቲቭ አባል የሆነው ሪቻርድ ፐርል የአሜሪካን ኢንተርፕራይዝ ኢንስቲትዩት (ኤ.ኢ..አይ.) ባልደረባ፣ እንዲሁም ዘ ሴንተር ፎር ሴኩሪቲ ፖሊሲ (ሲ.ኤስ.ፒ) ከተባለው የቀኝ ክንፍ ድርጅት እና ጄ.አይ.ኤን.ኤስ.ኤ፣ ፒ.ኤን፣ኤ.ሲ፣ ኤም.ኢ.ኤፍ እና ኤፍ.ዲ.ዲ. ከተባሉት ድርጅቶች ጋር ንክኪ ያለው ሲሆን ደብሊው አይ፣ኤን.ኤ.ፒ. ለተባለው ድርጅት ደግሞ የአማካሪዎች ቦርድ አባል በመሆን ያገለግላል። የእርሱ ባልደረባ የሆነው ኒዎኮንሰርቫቲቭ ዊሊያም ክሪስቶል፣ ዊክሊ ስታንዳርድ የተባለው ጋዜጣ ዋና አርታኢ፣ ፒ.ኤን.ኤ.ሲ የተባለው ድርጅት መስራች ሲሆን፤ ቀደም ሲል ደግሞ ኤፍ.ዲ.ዲ፣ ኤም.ኤ.ኤፍ እና ኤ.ኢ.አይ ከተባሉት ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ነበረው። የዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ አምድ አዘጋጅ ቻርለስ ክራውታመር የአሜሪካን ኢንተርፕራይዝ ኢኒስቲትዩት (ኤ.ኢ.አይ) ኸርቪንግ ክረስቶል ሽልማት አሸናፊ (ኮንሰርቫቲቪዝም የሚባለውን የፖለቲካ ዘይቤ ከመሠረቱት ሰዎች አንዱ በሆኑት በዊሊያም አባት የተሰየመ ሽልማት ነው)፣ የፒ.ኤን.ኤ.ሲ በርካታ ደብዳቤዎች ላይ ፈራሚ፣ ዊክሊ ስታንዳርድ የተባለው ጋዜጣ አርታኢና እንዲሁም ኤፍ.ዲ.ዲ ከተባለው ድርጅት ጋርም ንክኪ ያለው ሰው ነው። ባለፉት ጊዜያትና አሁንም ድረስ አሜሪካ ውስጥ ከሚገኙ አይሁዳውያን ድርጅቶች ጋር ንክኪ ያላቸው የኒዎኮንሰርቫቲስቶች ዝርዝር በጥቂቱ ይህን ይመስላል። ኢሊዮት አብራምስ (ሲ..ኤስ.ፒ.፣ ሁድሰን፣ ፒ.ኤን.ኤ.ሲ.) ዊሊያም ቤኔት፣ (ኤ.ኢ.አይ፣ ሲ.ኤስ.ፒ.፣ ፒ.ኤን.ኤ.ሲ) ጆን ቦልተን (ኤ.ኢ.አይ.፣ ጄ፣አይ.ኤን.ኤስ.ኤ.) ፣ ራውል ማርክ ግሬችት (ኤ.ኢ..አይ፣ ፒ.ኤን.ኤ.ሲ፣ ዊክሊ ስታንዳርድ) ፣

ሚካኤል ሌደን (ኤ.ኢ.አይ፣ ጄ.አይ.ኤን ኤስ.ኤ)፣ ጆን ኪርክ ፓትሪክ (ኤ.ኢ.አይ፣ ኤፍ.ዲ.ዲ፣ ጄ.አይ፣ኤስ.ኤን.ኤ.፣ ፒ.ኤን ኤ.ሲ.፣ ደብሊው አይ.ኤን.ኢ.ፒ)፣ ጆሽዋ ሙራቪክ (ኤ.ኢ.አይ፣ ጄ.አይ.ኤን፣ ኤስ.ኤ.ፒ.ኤን.ኤሲ፣ ደብሊው አይ.ኤን.ኢ.ፒ.) ዳንኤል ፓይፕ (ፒ.ኤን.ኤ.ሲ፣ ኤም ኢ.ኤፍ፣ ደብሊው አይ.ኤን.ኢ.ፒ.)፤ ኖርማን ፓድ ሆርትዝ (ሁድሰን፣ ኮሚንታሪ፣ ፒ.ኤን.ኤ.ሲ.)፣ ሚካኤል ሩቢን (ኤ.ኢ.አይ.፣ሲ.ኤስ.ፒ፣ ኤም.ኢ.ኤፍ)፣ ፓወል ዎልፎዊትዝ (ኤ.ኢ.አይ፣ ፒ.ኤን.ኤ.ሲ፣ ደብሊው ኢ.ኤን.ኢ.ፒ)፣ ዴቪድ ውርምሰር፣ (ኤ.ኢ.አይ.፣ ኤም.ኢ.፣ኤፍ፣ዲ.ዲ) ፣ እና ጆምስ ውልሲ (ሲ.ኤስ.ፒ.፣ ጄ.አይ.ኤን .ኤስ.ኤ፣ ፒ.ኤን.ኤ.ሲ፣ ኤፍ.ዲ.ዲ) ::

ይህ ማጠቃለያ የሚመስል ዝርዝር በምንም መልኩ በኒዎኮንሰርቫቲቭ እንቅስቃሴ ላይ ያለውን የእርስበርስ ንክኪ በሙሉ ያካትታል ማለት አይደለም:: አንዳንዶች ውስጥ ውስጡን ተንኮልና ደባ የሚፈጽም (ወይም የቀኝ ክንፍ ሴራ) አድርገው የሚያስቡት ኒዩ ኮንሰርቫቲዝም ሌላ ሳይሆን ብዛት ያላቸው የመንግሥት አማካሪዎች፣ ኮሚቴዎች፣ ድርጅቶችና የሕትመት ውጤቶች በሌሎች የመንግሥት አማካሪዎች መረባዊ ግንኙነቶች (Networks) እንደሚሆነው ሁሉ እየተንከባከቡ ያጎለበቱት እንቅስቃሴ ነው፡ ፡ የዚህ እንቅስቃሴ አራማጅ ግለሰቦችና ድርጅቶች ከሕዝብ መደበቅና ስውር ሴራ መሸረብ ሳያስፈልጋቸው የሚያምኑበትን ነገር በግልጽና ፊት ለፊት በማራመድ እንዲሁም የሕዝቡንና የምሁራኑን አመለካከት በመቅረጽ የአሜሪካን የውጭ ፖሊሲ እነርሱን በሚጠቅማቸው አቅጣጫ ለማራመድ ተሳክቶላቸዋል:: የኒዎኮንሰርቫቲቮች መረባዊ ግንኙነት (Network) ማንም ሊክደው በማይችለው ሁኔታ የሚደነቅና የግብር ማሻሻልን፣ የአካባቢን ወይም የስደተኞችን ጉዳይ የሚመለከቱ የፖሊሲ አቅጣጫዎች በሚነደፉበት ጊዜ የተፈጠሩ የግንኙነት መረቦች የተከተሉትን ዓይነት ተመሳሳይ አሠራር የሚከተል ነው::

እርግጥ ነው ኒዎኮንሰርቫቲቮች ለአሜሪካ ደህንነት የሚጨነቁትን ያክል ለእስራኤልም ደህንነት ይጨነቃሉ:: እንዲሁም በፖሊሲዎቻቸው ላይ የሚያዟቸው የመፍትሄ እንክብሎች ሁለቱንም ሀገራት እንደሚፈውሱ ያምናሉ:: ይሁን እንጂ በ1980ዎች ‹‹ፖሊ ኮንሰርቫቲቭስ›› በመባል የሚታወቁት ወግ አጥባቂዎች፣ ኮንሰርቫቲቮቹ ከአሜሪካ ይልቅ ለእስራኤል ይበልጥ ይጨነቃሉ የሚል ክስ አቅርበው ነበር:: ለምሳሌ የታወቀው ወግ አጥባቂ የፖለቲካ ንድፈ ሃሳብ አፍላቂ ሩሴል ኪርክ እንደተናገረው

‹‹ኒዎኮንሰርቫቲቮችን በእውነቱ የሚያሳስባቸው ጉዳይ በእስራኤል ላይ ክፉ ነገር እንዳይደርስ ማድረግ መቻል አለመቻላቸው ብቻ ነው፡፡››[74] ብሏል፡፡ ሆኖም ግን የኒዎኮንሰርቫቲቭ አቀንቃኞች ይህን ክስ ስለማይቀበሉ ከከሳሾቻቸው ጋር መራር የሆኑ ምልልሶችን ያደርጋሉ፡፡ ይህ ንትርክ በመጨረሻ እየቀዘቀዘ መሄዱ ባይቀርም በሁለቱ የኮንሰርቫቲቭ እንቅስቃሴዎች መካከል የተፈጠሩ ውጥረቶች መቀጠላቸው አልቀረም፡፡[75]

ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ተንታኞች ትኩረት ሰጥተው እንደሚያናገሩት ምንም እንኳን ብዙዎቹ የአይሁድ ኒዮኮንሰርቫቲቭ ንቅናቄ አባላት ወደ ሊባራል (ነፃ) አመለካከት የዞሩ ቢሆንም፣ አሁንም ቢሆን የአሜሪካውያን አይሁዶችን ማህበረሰብ አመለካከት እንደተቆጣጠሩ ይገኛሉ፡፡ ሙራይ ፍሪድማን ስለ ኒዎኮንሰርቫቲዝም በጻፈው ሃተታ ‹‹የአሜሪካ አይሁዳውያን ኮንሰርቫቲቪዝም›› በማለት ይጠራዋል፡፡[76] እንደዚያም ቢሆን ሁሉም ኒዎ ኮንሰርቫቲስቶች አይሁዳውያን ናቸው ማለት አይደለም፡፡ ይህ አባባል የሚያስታውሰን ሎቢው በጎሣ ወይም ሃይማኖታዊ እይታ ሳይሆን በፖለቲካ አጀንዳ የሚገለጽ ወይም የሚመራ መሆኑን ነው። ቁጥራቸው ቀላል የማይባልና አይሁድ ያልሆኑ ሰዎች ሁሉንም ባይሆን መሠረታዊ የሆኑትን ብዙዎቹን የኒዎኮንሰርቫቲቭ አመለካከቶች ይቀበላሉ፡፡ ከእነዚህ ሰዎች መካከል የዎል ስትሪት ጆርናሉ አርታዒ ሮበርት በርትሌይ፣ የቀድሞው የአሜሪካ የትምህርት ሚኒስትር ዊሊያም ቤኔት፣ የቀድሞዎቹ በተባበሩት መንግሥታት የአሜሪካ አምባሳደሮች ጆን ቦልተንና ጂን ኪርካፓትሪክ፣ እንዲሁም የቀድሞው የሲ.አይ.ኤ ዳይሬክተር ጀምስ ውልሲ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ አይሁዳውያን ያልሆኑ ፖለቲከኞች የኒዎኮንሰርቫቲቭን አጀንዳ ወደፊት ቢያራምዱትም ቅሉ፣ የዚህ ንቅናቄ ዋነኛ ዘዋሪዎች አይሁዳውያን መሆናቸው ይታወቃል፡፡ አይሁድ አሜሪካውያን ሎቢ የማድረጉን ተግባር በስፋት እንደሚያራምዱት ሁሉ የኒዎኮንሰርቫቲቭ (የዳግም ወግ አጥባቂነት) ንቅናቄንም እንደዚያው ናችተውበታል ማለት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ አይሁድ ያልሆኑ ሰዎች በሁለቱም (ሎቢ በማድረጉም ሆነ በፖለቲካው ጨዋታ) በትጋት ይሳተፋሉ፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ኒዎኮንሰርቫቲቮች ባህላዊውን የፖለቲካ አመለካከት በሚከተሉ ብዙ አሜሪካውያን አይሁዶች ዘንድ እስካሁንም ድረስ የተለዩ ጉዶች ተደርገው መታየታቸው አልቀረም፡፡

ክርስቲያን ጽዮናውያን

የእስራኤል ሎቢ ከአይሁዳውያን በተጨማሪ ወሳኝና ጠቃሚ የሆኑ፣ ሆኖም ግን አይሁዳውያን ያልሆኑ ቡድኖችንም ያጠቃልላል። እነርሱም ሰፊና የክርስቲያኖችን ፖለቲካዊ መብት ለማስከበር የቆመ ከሆነው ማህበረሰብ የሚከፈሉ ንዑሳን ክርስቲያን ጽዮናውያን ናቸው። ከዚህ ቡድን ዋና ዋና አባላት መካከል ጄሪ ፋልዌል፣ ጋሪ ባውር፣ ፓት ሮበርትሰንና ጆን ሀጌ፣ ከፖለቲከኞች ደግሞ የብዙሃን ምክር ቤት መሪ የሆኑትና የቴክሳስ ሪፖብሊካን ተወካይ ቶም ዲላይ እና ሌላው የቴክሳስ ሪፖብሊካን ፓርቲ ተወካይ ሪቻርድ አርሚ፣ እንዲሁም ሴናተር ጄምስ ኤንሆፌ (የኦክላሆማ ሪፐብሊካን ተወካይ) ይገኙበታል። እስራኤልን የመደገፍ ጽኑ ዓላማ ያላቸው እነዚህ ብቻ አይደሉም። ብዛት ያላቸው ክርስቲያን ወንጌላውያንም የአይሁዳውያኑን መንግሥት በመደገፍና ጉልህ ሚና በመጫወት ላይ ናቸው። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ደግሞ በፖለቲካው ጨዋታ ውስጥ ሚና ያላቸው ድርጅቶችን በማሰማራት ይህን ሚናቸውን የበለጠ ለማሳደግ እየጣሩ ነው።[77] ይህ ማለት በአሜሪካ አይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ ከሚገኙ አፍቃሪ እስራኤል ቡድኖች መካከል ክርስትያን ጽዮናውያን አዲስ አጋሮች እየሆኑ መጥተዋል ማለት ነው።

የክርስትያን ጽዮናዊነት መሠረት በ18ኛው ክፍለ ዘመን የእንግሊዝ ቤተክርስትያን ተከታይ በነበሩት በሉዊስ ዊይ እና በኔልሰን ደርቢ የተመሠረተው ‹‹ዲስፔንሴሽናሊዝም›› የተሰኘ የባይብል ትንተና ስልት ነው፡ ፡ የዲስፔንሴሽናሊዝም ቀኖና ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ ዓለም ብዙ መከራና ችግር የሚፈራረቅባት መሆኗን ያትታል። ልክ እንደሌሎቹ ክርስቲያኖች ዲስፔንሴሽናሊስቶችም የክርስቶስ ዳግም መመለስ በብሉይና አዲስ ኪዳን መጽሐፍት በተለያዩ ነቢያት አፍ ተተንብዮአል ብለው ያምናሉ። ስለሆነም የአይሁዳውያን ወደ ፍልስጤም ምድር መመለስ ለክርስቶስ መመለስ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚቆጠር ሲሆን፣ የእርሱንም መምጣት ያበስራል ባይ ናቸው። ለዚህም ነው ክርስቲያን ጽዮናውያን

አፍቃሪ እስራኤል ሊሆኑና የአይሁዳውያንን በመላ የፍልስጤም ምድር መስፈር ሊደግፉ የቻሉት። ደርቢ፣ ዌይና የእነርሱ ተከታዮች በርካታ ስመጥር በሆኑ የእንግሊዝ ፖለቲከኞች ላይ ተጽዕኖ በማሳደራቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት እና የባልፎርን ስምምነት ሀሳብ ያፈለቁት አርተር ባልፎርም ምናልባት በፍልስጤም ምድር የአይሁድን ብሔራዊ ሀገር የመመስረቱ ሀሳብ የመጣላቸው በዚህ ሃይማኖታዊ ተጽዕኖ ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚል አስተሳሰብ ይንጸባረቃል።[78]

የዲስፔንሴሽናሊስት ትምህርተ ቀኖና ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የዘለቀው በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያና በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ነበር። ወደዚያ የወሰዱትም የተለያዩ የፕሮቴስታንት ሰባኪዎች ሲሆኑ ከእነርሱም ውስጥ ወንጌላዊው ዳዊት ሙዲ (የቺካጎውን የመጽሐፍ ቅዱስ ኢንስቲትዩት ያቋቋመው ሰው)፣ ሲ.አይ.ስኮፊልድና ዊሊያም ኢ.ብላክስቶን ይገኙበታል። የቅርብ ጊዜ የዚህ ንቅናቄ ተከታዮች ደግሞ አርማጌዶን የተባለውን የምጽዓት ቀን ጦርነት ሁኔታ የሚገልጹ ትረካዎች የያዙ መጽሐፍትን ደርሰዋል፣ (አዘጋጅተዋል)። ከእነዚህ መጽሐፍት መካከል ሃል.ሊንዲሴይ የጻፈው Late Great planate Earth የተባለው በብዛት የተሸጠ መጽሐፍና ለሃይስ የጻፈው Left Behind Series በሚል ስያሜ የሚጠራው መጽሐፍ ይገኙበታል። ሁለቱ መጽሐፍት አንድ ላይ ወደ አስራ አምስት ሚሊዮን ቅጂ ተሸጠዋል።[79]

የእስራኤል መንግሥት በ1948 መመስረቱ ለዲስፔንሴሺናሊስት እንቅስቃሴ ነፍስ የዘራበት ቢሆንም፣ ከዚያ በበለጠ ሁኔታ የንቅናቄውን መሪዎች የመሰጣቸው በ1967ቱ የስድስት ቀን ጦርነት እስራኤል ድል ማድረጓ ነበር። ያንን ክስተት "የአምላክ ተዓምር" በማለት ጠርተውታል። ከዚያ በኋላ ነበር ይህ ንቅናቄ የፖለቲካ ኃይል ሆኖ ብቅ ያለው።[80] ዲስፔንሴሺናሊስቶች እስራኤል ሁሉንም የእየሩሳሌም ክፍልና የምዕራቡን ዳርቻ መያዟን (እነዚህን ቦታዎች የእስራኤሉ ሊኩድ ፓርቲ ከጥንቶቹ የእስራኤል ግዛቶች ጁዲያና ሰማሪያ ጋር ያመሳስላቸዋል) ከብሉይና አዲስ ኪዳን ትንቢቶች ጋር በማዛመድ የትንቢቶቹ ፍጻሜ መቃረቡን እንዲያምኑ አድርጓቸዋል። እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ወንጌላውያን በዚህ ሁኔታ በመነሳሳት ዩናይትድ

ስቴትስ በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች የተረጋገጠውን የዓለም ፍጻሜ መቃረብ ተገንዝባ በትክክለኛ አቋም ላይ እንድትሆን ለማድረግ ወሰኑ።[81] ቲሞቲ ወበር የተባሉት የቀድሞ የሜምፊስ መንፈሳዊ ሴሚናሪ ፕሬዝዳንት እንደሚገልጹት፡- ‹‹ከስድስቱ ቀን ጦርነት በኋላ ዲስፔንሴሽናሊስቶች የመጨረሻውን (የምጽዓት ቀን) መምጣት እየሰበኩ ተቀምጠው ነበር፡፡ ..... ሆኖም ግን እስራኤል በምዕራቡ ዳርቻና በጋዛ ወረራዋን በማድረግ ስትስፋፋ ከመሰብሰቢያ ሰገነታቸው ወርደው በቀጥታ በታሪኩ ሂደት ውስጥ ራሳቸውን ለማሳተፍ በመሻታቸው በፖለቲካ፣ ፋይናንስና ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ከዚያ በፊት አድርገውት በማያወቁት ሁኔታ ተንቀሳቀሱ" ብለዋል፡፡[78] ይህ ጥረታቸው "የክርስቲያኖች መብት" ብለው የሚጠሩትና እያደገ የሄደው የወንጌላውያን ንቅናቄ አካል ሲሆን እያደገ ከመጣው የኢቫንጂሊስቶች ፖለቲካዊ እንቅስቃሴም ግልጽ ድጋፍ እያገኙ ሄዱ፡፡

ይህን ሁኔታ እግምት ውስጥ ስናስገባ ዳንደኤል ፖይፕ የሚከተለውን ማለቱ አያስደንቅም፡- ‹‹ከእስራኤል መከላከያ ኃይል ቀጥሎ ምናልባትም የአሜሪካ ክርስቲያን ጽዮናውያንን ያክል ለእስራኤል ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያለው አካል ማንም የለም፡፡›› የቤንጃሚን ናታንያሁ የቀድሞው የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር ሚካኤል ፍሪውድ በ2002 እንዲህ ብለው ነበር፡- ‹‹ክርስቲያን ጽዮናዊያንን ለሰጠን አምላክ ምስጋና ይገባዋል፡፡ ወደዳችሁም ጠላችሁ የወደፊቱ የእስራኤልና ዩ.ኤስ.አሜሪካ ግንኙነት የተመሰረተው በአሜሪካ አይሁዳውያን ጥረት ሳይሆን በክርስቲያን ጽዮናውያን በጎ ፈቃድ ላይ ነው››[83]

ክርስቲያን ጽዮናውያን ዋናው ዓላማቸው እስራኤልን መርዳት የሆነ አያሌ ድርጅቶችን (ቡድኖችን) መሠረቱ። ከእነዚህ ቡድኖች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡- ክርስቲያንስ ዩናይትድ ፎር እስራኤል (መስራቹ ጆን ሃጊ ቡድኑን የአሜሪካ እስራኤል ሕዝብ ጉዳዮች ኮሚቴ ወይም አይፓክ ክርስቲያን ክንፍ በማለት ይጠራዋል)፣ ዘ ናሽናል ክርስቲያን ሊደርሽፕ ኮንፈረንስ ፎር እስራኤል፣ ዘ ዩኒት ኮአሊሽን ፎር እስራኤል፣ ክርስቲያን ፍሬንድስ ኦፍ እስራኤል ኮሚዩኒቲስ (ሲ.ኤፍ.አይ.ሲ)፣ ዘ ክርስቲያን እስራኤል ፕብሊክ አክሽን ኮሚቴ፣ ዘ ኢንተርናሽል ክርስቲያን ኤምባሲ

ጀሩሳሌም (አይ.ሲ.ኤ.ጄ) እና የተለያዩ ጥቃቅን ቡድኖች።[84] ኢንተርናሽናል ፊሎውሺፕ ኦፍ ክርስቲያን ኤንድ ጀውስ (አይ.ኤፍ.ሲ.ጄ) በተባለው ድርጅትም ውስጥ ክርስቲያን ጽዮናውያን ዋና ተዋናዮች ናቸው። ሌላው በራቢ ይትሄል ኤክስታይን የሚመራውና መሠረቱን በቺካጎ ያደረገው ድርጅት ዋነኛ ዓላማው በአይሁዳውያንና በክርስቲያኖች መካከል ያለውን ትብብር ማጠናከርና ለእስራኤል ሰፊ ድጋፍ ማስገኘት ነው። በ2002 አይ.ኤፍ.ሲ.ጄ. ከቀድሞው የክርስቲያን ትብብር ዳይሬክተርና ከጄ.ኦ.ቢ. ስትራቴጂስት ራልፍ ሪድ ጋር በመሆን ሰዎችን በመንፈሳዊና ፖለቲካዊ ሕይወታቸው ለእስራኤል ለመቆም ቃል እንዲገቡ ለማድረግ ግንባር የፈጠሩ ከመሆኑም በላይ፤ በእስራኤል ስም በየዓመቱ የሚከበር የዓለም አቀፍ አንድነትና ጸሎት ቀን እንዲኖር ተስማምተዋል።[85]

ይህን በመሰለው ዘመናዊ እንቅስቀሴ እየታገዙ ክርስቲያን ጽዮናውያን በአሜሪካ አይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ ከሚገኙ ቡድኖች እና ከእስራኤል ጋር ትስስር በመፍጠር በኃይል በተያዙት ግዛቶች ውስጥ የሰፈራ መንደሮች እንዲስፋፉ ድጋፋቸውን የሚገልጹ ሲሆን የሁለት መንግሥታትን የመፍትሄ ሀሳብ ደግሞ ይቃወማሉ። በዚህ እሳቤ የሚመራው የሲ.ዩ.ኤፍ፣ .አይ.መስራች የሆነው ጆን ሃጊ እንዲህ ይላል፦ ‹‹እኛ እስራኤልን እንደግፋለን። ምክንያቱም ሁሉም መንግሥታት የተመሠረቱት በሰው ልጅ ሕግ ሲሆን፣ እስራኤል የተመሠረተችው ግን በአምላክ ሕግ ነውና!›› ሃጊ በተጨማሪም ለተከታዮቹ፦ ‹‹አምላክ መሬት ቆርሶ መስጠትን ይቃወማል።›› በማለት የሁለት መንግሥታት ምሥረታ በፍልስጤም ምድር እንዳይካሄድ ተሟግቷል። ሰውዬው ከዚህም በላይ ፈቀቅ ያለ እርምጃ በመውሰድ በኃይል በተያዙት የፍልስጤም መሬቶች ላይ ጭምር የአይሁድ ሰፋሪዎች ወደ እስራኤል መጥተው እንዲሰፍሩ ለመርዳት አስራ ሁለት ሚሊዮን ዶላር ሰብስቧል።[86]

የሃጊ አመለካከት ዋነኛው የክርስቲያን ጽዮናዊነት መገለጫ ነው። የወንጌላውያን የክብ ጠረጴዛ ውይይት መሥራችና የክርስቲያኖችን መብት በተመለከተ አደራጅ የሆኑት ኤዲ ማክ አተር፦ ‹‹በሙት ባሕርና በዮርዳኖስ ወንዝ እንዲሁም በሜዲትራንያን ባህር መካከል የምትገኝ እያንዳንዷ የአሸዋ

ቅንጣት የአይሁዳውያን ንብረት ናት፡፡" በማለት አመለካከታቸው የት ድረስ ርቆ እንደሚሄ አሳይተዋል። የአይ.ሲ.ኢ.ጀ. ዳይሬክተር ማልኮለም ሄይንግ አባባል ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡- ‹‹አምላክ ከአራት ሺህ ዓመታት በፊት ለአብረሃም ቃል ኪዳን በገባለት መሠረት በቅድስቲቱ ምድር ያለው መሬት በሙሉ የእስራኤላውያን ሲሆን ፍልስጤማውያን የሚባሉ ሕዝቦችን እኛ አናውቅም፡፡››[87] በተመሰሳይ ሁኔታ የሲ.ኤፍ.አይ.ሲ. መሥራች ቴድ ቦኬት የድርጅታቸውን ተልዕኮ አስመልክተው ሲናገሩ፡- ‹‹አንድነትን፣ ምኞትንና ድጋፍን በይሁዳ፣ ሰማሪያና ጋዛ ለሚሰፍሩ አይሁዳውያን ማመቻቸት ነው›› ብለዋል፡፡ ይህ ድርጊት በዩ.ኤስ. አሜሪካ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን ከሰፋሪ ግለሰቦች ጋር የሚያገናኝ ሲሆን፣ አብያተ ክርስቲያናቱ ሰፋሪ ግለሰቦቹን በሁሉም መልኩ ያግዛሉ፡፡ ለአብነት ያክል ፌዝ ባይብል ቻናል የተባለ አርቫዳ ኮሎራዶ ግዛት የሚገኝ ድርጅት በምዕራቡ ዳርቻ ለሚገኘው ‹አሪዮል› ለተባለው የሠፈራ መንደር ቤተ-መጻሕፍት፣ ክሊኒክና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን አሟልቷል፡፡[89]

ከፍ ሲል እንደተገለጸው ክርስቲያን ጽዮናውያን የሁለት መንግሥት ሀሳብንም ሆነ ከፍልስጤማውያን ጋር የሚደረግን ማንኛውንም ዓይነት የመሬት ስምምነትን ይቃወማሉ። የግብጹ ፕሬዚዳንት አንዋር ሳዳት በ1977 በድንገት እየሩሳሌምን ከመጎብኘታቸው በፊት በዋዜማው ዋና ዋና በሚባሉት የአሜሪካ ጋዜጦች ላይ የሚወጡ ማስታወቂያዎች፣ ‹‹ከአይሁዳውያን መሬት ላይ ቆርሶ በመስጠት ሌላ ሀገር ወይም ግዛት ለመመስረት የሚደረገውን ጥረት በከፍተኛ ስጋት እንደሚመለከቱት›› ገልጸዋል፡፡[90] በ1996 የተደረገው ሶስተኛው ዓለም አቀፍ የክርስቲያን ጽዮናውያን ጉባዔ ባሳለፈው ውሳኔ ‹‹አምላክ ለሕዝቦች ቃል የገባላቸው ምድር መከፋፈል አይኖርበትም፡፡ ኤሬትዝ-እስራኤል በሚባለው ምድር ላይ ለሚመሠረተው የፍልስጤም መንግሥት ሀገራት እውቅና መስጠታቸው ትልቅ ስህተት ነው›› ብሏል፡፡[91] ይህን የመሰለው ጽኑ የሆነ እምነት የክርስቲያን መብት ተቆርቋሪ ድርጅት መሪ የሆኑት ፓት ሮበርትሰን፡- ‹‹የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አሪዮል ሻሮን በ2006 የደረሰባቸው ራስን የመሳት ችግር ከጋዛ ሰርጥ ለመውጣት ባደረጉት የተናጠል ውሳኔ

ከአምላክ የተሰጣቸው ቅጣት ነው›› በማለት በድፍረት እንዲናገሩ አድርጓቸዋል። ሮበርትሰን ንግግራቸውን በመቀጠል የሚከተለውን ይላሉ፡- ‹‹የአምላክን ምድር በተመሳሳይ ሁኔታ የሚከፋፍልን ባለሥልጣን፡- ‹አምላክ ወዮውልህ ይልሐል፡፡ የአውሮፓን ሕብረት፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትንና ዩናይትድ ስቴትን ለመለማመጥ ብለህ መሬት የምትከፋፍል የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆይ፣ ይህ ምድር የእኔ ነው። ምንም ነገር ከማድረግ እንድትቆጠብ አዝገርሃለሁ! ይልሐል እለዋለሁ፡፡›› ሮበርትሰን ቆዬት ብለው ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ያልተገባ ንግግር በማድረጋቸው ይቅርታ የጠየቁ ቢሆንም፣ ክርስቲያን ወንጌላውያን መሪዎች የታላቋን እስራኤል መመሥረት ምን ያህል እንደሚናፍቁ ከዚህ አቋማቸው እንድንገነዘብ ያግዘናል፡፡[92]

እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብና እምነት አያሌ በሆኑ የዩ.ኤስ.አሜሪካ ታዋቂ ፖለቲከኞች ላይም ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ በ2002 የብዙሃኑ (Majority) ኮንግረስ አባላት መሪ የነበሩት ቶም ዴላይ በአይፓክ ዓመታዊ የፖሊሲ ኮንፈረንስ ላይ ለፍልስጤማውያን መሬት የመስጠቱን ሂደት እንደሚቃወሙ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹እኔ በይሁዳና ሰማሪያ ተጓዘኩ። ከጎላን ከፍታዎችም ላይ ወጣሁ፡፡ በዚያ ሁሉ እይታየ አንድም በኃይል የተያዘ መሬት ከቶ አላስተዋልኩም፡፡ ያየሁት ነገር ቢኖር አንድ ነገር ብቻ ሲሆን እርሱም እስራኤል ናት፡፡"[93] ዴላይን በመተካት የብዙሀኑ ኮንግረስ መሪ የሆኑት ሪቻርድ አርሚ ለሃርድ ቦል-አዘጋጅ ክርስ ማቲው ግንቦት 2002 ላይ በሰጡት አስተያየት እስራኤል አጠቃላዩን የምዕራቡን ዳርቻ (West Bank) እንድትቆጣጠርና እዚያ የሚገኙ ፍልስጤማውያንም መባረር እንዳለባቸው የሚያምኑ መሆናቸውን ገልጸውለታል፡፡[94] ሴናተር ጀምስ ኢንሆፌ በበኩላቸው በምክር ቤት አባላት የክርክር መድረክ ላይ ለባልደረቦቻቸው መላ ፍልስጤም ለእስራኤል የሚገባት መሆኑ ለምን እንደሆነ ሲገልጹ የሚከተለውን ብለዋል፡- ‹‹ምክንያቱም አምላክ እንደዚያ ብሎ ስላዘዘ ነው፡፡ ... በዚያች ምድር (ሄብሮንን ማለታቸው ነው) ነበር አምላክ ለአብረሃም የተገለጸለትና፡- ‹ይህን ከዮርዳኖስ ወንዝ በመለስ ያለውን ሀገር (የምዕራቡን ዳርቻ) ሰጥቼሃለሁ› ብሎ የነገረው።››[95]

ይህን ሁሉ የክርስቲያን ጽዮናውያን ግፊትና ተጽዕኖ የሚያስተውሉት በእስራኤል መንግሥት ፓርላማ ውስጥ የሚገኙ ጠጣሩን መስመር የሚከተሉ ፖለቲከኞች (Hard Line Politicians) የመሬት ለሰላምን ጥሪ ውድቅ ቢያደርጉና ከእነዚህ ኃይላት ጋር ለማበር ፍላጎት ቢያሳዩ አያስደንቅም፡፡ በተለይም ደግሞ ኮሊን ሸንድለር እንዳስቀመጡት፡- ‹‹ከ1977 ጀምሮ ተግባራዊ የሆነው የእስራኤል ቀኝ ክንፈኞችና የክርስቲያን ቀኝ ክንፈኞች ትብብር ለዚህ አባባል ጥሩ ማሳያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡››[96] የሚናሂም ቤኒን ሊኩድ መንግሥት ወንጌላውያንን በማክበርና ከፍ ከፍ በማድረግ ከነርሱ ጋር መቀራረብ የፈጠረው በዚህ ጊዜ ነበር ፡፡ ለአብነት ያክል በ1979 ሜናሂም ቤኒን የክርስቲያን ጽዮናውያን መሪ ለሆነው ጄሪ ፋልዌል የግል ጀት አውሮፕላን የሰጡት ሲሆን በ1990 ደግሞ ብቸኛው አይሁድ ያልሆነ የጃቦትንስኪ ሜዳይ ተሸላሚ እንዲሆን አብቅተውታል፡፡ (ሌሎቹ የዚህ ሜዳይ ተሸላሚዎች የምጽዓተ እስራኤል ደራሲ፣ ሊዮን አሪስና ኤሊ ዋይዝል ናቸው)፡፡ እስራኤል የኢራቅን ኦሲራክ የኒኩሌዩር ማብለያ በ1981 በቦምብ በደበደበች ጊዜ ቤኒን ለፕሬዚዳንት ሬገን ከመደወላቸው በፊት ለፋልዌል ደውለው የእስራኤልን እርምጃ ለአሜሪካ ሕዝብ እንዲያስረዳላቸው ጠይቀውታል፡፡[97] ጠቅላይ ሚኒስተር ናታንያሁም በበኩላቸው በ1996 በእስራኤል ክርስቲያን አድቮኬሲ ካውንስል ድጋፍ የወንጌላውያን መሪዎች ቡድን ወደ እስራኤል እንዲመጣ ጋብዘዋል፡፡ ፓት ሮበርትሰንና ኢሁድ ኦልመርትም (በዚያን ጊዜ ኦልመርት የኢየሩሳለም ከንቲባ ነበሩ) በ2002 በተደረገው ለእየሩሳሌም የመጸለይ ዘመቻ ዋና አስተባባሪዎች ሆነው አገልግለዋል፡፡[98]

የእስራኤል መንግሥት ብዙ ጊዜ ሲያደርግ እንደተስተዋለው የክርስቲያን ቱሪስት ቡድኖች እስራኤልን እንዲጎበኙ ያበረታታል፡፡ እንደዚያ የሚያደርገውም አንድም ከቱሪስቶች የሚገኘውን ዳጎስ ያለ ገቢ ለማግኘት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በዩናትድ ስቴትስ ውስጥ የሚኖሩ ወንጌላውያንን ድጋፍ ለማትረፍ በማለም ነው፡፡ ስለሆነም ጠቅላይ ሚኒስትር አርዮል ሻሮን በ2002 በአይ ሲ.ኢ.ጀ. ዓመታዊ የጽላተ ሙሴ በዓል አከባበር ላይ (በእስራኤል ታሪክ ትልቁ የውጭ ሰዎች የሃይማኖት ስብስብ እንደሆነ

ተጠቅሷል) የሚከተለውን ብለው ነበር፡- ‹‹እኛ እናንተን እንፈልጋለን፣ የእናንተን ድጋፍም እንሻለን፡፡ .... ወደቤታችሁ ስትሄዱ የምታደርሱልን መልዕክትም አለን፡፡ እዚያ እንደደረሳችሁ እንደእናንተው እስራኤልን ይጎበኙ ዘንድ ሰዎችን ወደዚህ ላኳቸው፡፡›› [90] ሻሮንን የተኳቸው ኢሁድ ኦልመርትም የእየሩሳሌም ከንቲባ በነበሩበት ጊዜ ተመሳሳይ መልዕክት ለጎብኝዎች ሲያስተላልፉ፡- “እናንተ የእኛ ሠራዊት አካሎች ናችሁ፣ የኃይላችንና የመከላከል ብቃታችንም ክንዶች ናችሁ›› ብለው ነበር፡፡[100]

የክርስቲያን ጽዮናውያን ድርጅቶች በሌሎች የመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳዮችም ላይ የተወሰነ ሚና ለመጫወት መሞከራቸውና ይህንኑም በየጊዜው እያሳደጉት መሄዳቸው አልቀረም፡፡ ክርስቲያን ዩኒየን ፎር ኢስራኤል (ሲ.ዩ.ኤፍ.አይ) የተባለውና በጆን ሃጊ የተመሠረተው ቡድን በ2006 በተደረገው የሊባኖስ ጦርነት እስራኤልን የሚደግፍ ስብሰባ ጠርቶ ነበር፡፡ ያንን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ጀሪ ፋልዌል እንዲህ አለ፡- ‹‹አሁን የምንገኘው ድንበር የማያግደው በሆነ የጦርነት ጫፍ ላይ ሲሆን፤ ይህም ወደፊት ለሚጠብቀን የአርማጌዶን ጦርነትና ለእየሱስ ክርስቶስም ዳግም መምጣት እንደ መቅድም ይቆጠራል፡፡››[101] ሚለናሪያን የተባለው በብዛት የተሸጠ መጽሐፍ ደራሲ ሃል ሊንድሴይ በ2007፡- ‹‹ኢራንን ቀድሞ በኒኩሌር መሣሪያ መደብደብ ብቸኛውና በስነ አምክኒዮ (logic) የተደገፈ የእስራኤል ምርጫ ነው፡፡›› በማለት ያለምንም መሳቀቅ ጽፏል፡፡ ጆን ሃጊም እንዲሁ Jerusalem Count dawn በሚል ርዕስ በ2002 ባሳተመው መጽሐፍ እንዲህ ብሏል፡- ‹‹ከኢራን ጋር የሚደረገው በኒኩሌር አረር የመፈታተሽ ግብግብ የማይቀር ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ መጽሐፍ ከመታተሙ በፊት የሕዝቅኤል 38-39 ጦርነት ይጀመራል፡፡››[102] ሃጊ በተጨማሪም በ2006 ታህሳስ ላይ የኢራቅ የጋራ ጥናት ቡድን ያቀረበውን ዘገባ በማውገዝ፣ ‹‹ጀምስ ቤከር አሁንም እንደገና የእስራኤልን ጀርባ በስለት እየወጋ ነው›› ካለ በኋላ፣ ‹‹የአባቴ ትውልድ በዚህ ጊዜ ኢራንን በቦምብ ለመደብደብ እየተዘጋጀ ይሆናል›› በማለት ሀሳቡን አጠቃሏል፡፡[103]

የተወሰኑ የአሜሪካ አይሁዳውያን ድርጅቶች ከክርስቲያን ጽዮናውያን ጋር መጎዳኘቱን አይጠሉትም፡፡ ዳሩ ግን ክርስቲያን ጽዮናውያኑ በዩናይትድ

ስቴትስ ውስጥ የሚገኙ አይሁዳውያንን ወደ ክርስትና የመመለስ እና የማጥመቅ ራቅ ያለ አጀንዳ ያላቸው መሆኑ ያስፈራቸዋል፡፡

እንደዚያም ቢሆን አይፓክ ከወንጌላውያን እንቅስቃሴዎችና አፍቃሪ ሊኩድ ከሆኑ ክርስቴያን ጽዮናውያን ጋር የሚያገናኘው የራሱ የሆነ ቢሮ ከፍቷል።[104] ናታን ፐርልሙተር የተባሉት የቀድሞ የፀረ- ስም ማጥፋት ሊግ (ኤ.ዲ.ኤል) ዳይሬክተር፣ ‹‹አይሁዳውያን የክርስቲያኖችን መብት የሚያስቀድም ሕግ ባለው ማንኛውም መንግሥት ስር መኖር ይችላሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ሊበራል የሆነ አይሁድ ከሌሎች ይለያል፡፡ ምክንያቱም ማንኛውም ነገር የእስራኤልን ያክል አስፈላጊ ሆኖ ስለማያገኘው ነው ›› ብለዋል፡፡ ናታንን የተኳቸው አብረሃም ፎክስማን ሁልጊዜም የክርስቲያኖችን የሀገር ውስጥ መብት በሚያቀነቅነው የፖለቲካ አጀንዳ ላይ ትችታቸውን ከመሰንዘር አይመለሱም። በመሆኑም በ2007 ያንኑ ሀሳባቸውን በማስተጋባት ሲናገሩ ‹‹ኤ.ዲ.ኤል የወንጌላውያንን እርዳታ ያስተናገደው አይሁዳዊቷ ሀገር ታላቅ የሆነ ስጋት ላይ በነበረችበት ጊዜ ነበር" ብለዋል፡፡ [105] የአሜሪካ አይሁዳዊያን ኮሚቴ ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ዴቪድ ሃሪስ “የክርስቲያኖችን መብት ከሚያስጠብቀው አሠራር ጋር መጓዝ እንደሁኔታው የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ እነርሱ እንደሚሉት የዓለም ፍጻሜ የሚመጣው ነገ ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ግን እስራኤል በዛሬ ሚዛን ላይ ተንጠልጥላ ትገኛለች››[106] በማለት ተናግረዋል፡፡

የእስራኤል ሎቢ ሁለት ዋና ዋና ቅርንጫፎች (የአሜሪካ አይሁዳዊያንና ክርስቲያን ጽዮናውያን) ጠንካራ ትስስር በ2007 በተደረገው የአይፓክ የፖሊሲ ኮንፈረንስ ላይ ተንጸባርቋል። የሲ.ዩ.ኤፍ.አይ. መሥራችና ከክርስቲያን ጽዮናውያን መሪዎች አንዱ የሆነው ጆን ሃጊ በመክፈቻው የእራት ሥነ ሥርዓት ላይ ንግግር ሲያደርግ የተደረገለት ሞቅ ያለ አቀባበል የግንኙነታቸውን ጥንካሬ ያጎላ ክስተት ነበር፡፡ አይሁዳውያኑ ለሃጊ ያሳዩት ያን የመሰለው አቀባበል የሚያስደንቅ ነበር፡፡ ምክንያቱም ከስብሰባው ጊዜ ጥቂት ቀናት በፊት ሃጊ ባቀረበው ጽሑፍ፣ ‹‹አይሁዳውያን ከመንፈሳዊ ሕይወት በስተቀር የሚጎድላቸው ነገር የለም›› በማለቱ ነበር፡፡ ሃጊ በዚያው ጽሑፍ ‹‹የፀረ- ሴማዊነት ንቅናቄ መጠናከር አይሁዳውያን በአምላክ

ባለማመናቸው ምክንያት የመጣባቸው መቅሰፍት ነው። ስለሆነም ፈጣሪ ፀረ- ሴማዊ የሆኑ ሕዝቦችን በማስነሳትና አይሁዶችን እንዲጨፈጭፉ በማድረግ እውነተኛው አምላካቸው እርሱ መሆኑን እንዲያውቁ ማድረጉን ፈቀደ››[107] በማለት ነበር ተጋፊ የሚመስል አባባሉን ያስቀመጠው። የሃጊ የሚያስጨንቁ ዓረፍተ ነገሮች እንዳሉ ሆነው የኤ.ዲ.ኤል መሪ ፎክስማን ሃጊን አስመልክተው እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል፡- ‹‹ ለእስራኤል ያለውን ድጋፍ ስናጤን አንድ ዓይነት ሚና መጫወት የሚችል ሰው መሆኑን እንድናምን ያደርገናል።››[108]

መካከለኛ አቋም ያላቸው እስራኤላውያንና የአሜሪካ አይሁዶች የክርስቲያን ጽዮናውያንን አጀንዳ ይበልጥ በተገነዘቡ ቁጥር እንቅስቃሴውን ለመቀበል እየተቸገሩ መሄዳቸው አልቀረም። "ሆኖም ግን ለእስራኤል ሲሉ ብዙዎቹ የአሜሪካ አይሁዶች ከአዲሱ የክርስቲያን መብት ንግግር ራሳቸውን አላገለሉም" በማለት የታሪክ ባለሙያዋ ናኦሚ ኮኸን ይናገራሉ።[109] አይሁዳውያኑን ወደ ክርስትና የመቀየሩ ሂደት የብዙ ወንጌላውያን ቡድኖች የረዥም ጊዜ ግብ ሲሆን ክርስርቲያን ጽዮናያውያን ፍልስጤምን በተመለከተ የሚከተሉት ለእርቅ ቦታ የማይሰጥ አቋም ከፍልስጤማውያን ጋር ከሰላም ስምምነት ላይ ለመድረስ ሁኔታዎችን እንዳያወሳስባቸው አይሁዳውያኑ መፍራታቸው ተገቢ ነበር። ጆ-አን ሞርት የተባሉት ‹አሜሪካንስ ፎር ፒስ ናው› የሚሰኘው ድርጅት አባል ሲናገሩ፣ ‹‹የአሜሪካ አይሁዶችና የክርስቲያን መብት ተሟጋቾች ጉድኝት ቅድስና የጎደለው ጉድኝነት ነው›› በማለት ተችተዋል። እስራኤላዊው ለዘብተኛ ፖለቲከኛ ዮሲ አልቸር ደግሞ፡- ‹‹ክርስቲያኖች የእስራኤልን የሠፈራ ግንባታ መቀጠል መደገፋቸው በጥፋት ላይ ጥፋት ወደምንፈጽመበት የውድመት አቅጣጫ ነው እየመራን ያለው›› በማለት አስጠንቅቀዋል። እኚህ ሰው ሲ.ቢ.ኤስ ለተባለው ዜና አገልግሎት በሰጡት ቃለ ምልልስ ‹‹አምላክ ከእነዚህ ሰዎች ይጠብቀን›› ሲሉ ተደምጠዋል። በተመሣሣይ ሁኔታ እስራኤላዊው አሜሪካዊ ምሁር ግሮሻም ጎርንበርግ እንዳስታወቁት "የዲስፔንሴሺናሊስቶች መንፈሳዊ ትምህርት የአይሁዳውያንን የወደፊት አጣ አስደሳች አያደርገውም። በመጨረሻም ላይ አይሁዳውያን ይሞታሉ ወይም ወደ ክርስትና ይቀየራሉ›› ካሉ በኋላ

በተለይም ደግሞ የክርስቲያን ጽዮናውያንን ድርጊት አስመልክተው ሲያስጠነቅቁ፡- ‹‹እነርሱ እውነተኛ አይሁዳውያንን አያፈቅሩም፡፡ እነርሱ የሚወዱን ለታሪካቸው ሂደትና ለሚጫወቱት ተውኔት አስፈላጊ ተዋናዮች ሆነን በመገኘታችን ነው፡፡ .. ይህ ተውኔታቸው ባለ አምስት ገቢር ሲሆን በአራተኛው ገቢር ላይ አይሁዳውያን ድራሻችን ይጠፋል›› ብለዋል፡፡[110]

ለመሆኑ የክርስቲያን ጽዮናያውያን ሎቢ ምን ያክል ጠቃሚ ነው? ለአዳዲስ የሠፈራ ግንባታ የገንዘብ እርዳታ በመስጠትና የመሬት ለሰላም ስምምነትን በይፋ በማውገዝ ክርስቲያን ጽዮናውያን በእስራኤልና ዩናይትድ እስቴትስ ፖለቲካ ላይ ጠጣሩን መስመር እያጠናከሩት በመሄዳቸው የአሜሪካ መሪዎች በእስራኤል ላይ ጫና ለማሳደር እንዲቸገሩ አድርጓቸዋል፡፡ የእነርሱ እርዳታ ባይኖር ኖሮ፤ የእስራኤል ሠፋሪዎች ቁጥር ይህን ያክል ባልበዛና የእስራኤልና አሜሪካ ፖለቲከኞችም በሰፋሪዎቹ አለመኖር ምክንያት በኃይል በተያዙት ግዛቶች አነስ ያለ ግፊትና የፖለቲካ እንቅስቃሴን መጋፈጥ ቀላል በሆነላቸው ነበር፡፡ ከዚህም በላይ የክርስቲያን ቱሪዝም እንቅስቃሴ (አብዛኛውና ጠቀም ያለ ገቢ የሚያስገኘው የቱሪስቶች ፍስት የሚከናወነው በወንጌላውያኑ ደጋፊነት ነው) ለእስራኤል ኢኮኖሚ በየዓመቱ ወደ አንድ ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ትርፍ ያስገኛል፡፡[111]

አይሁዳውያን ያልሆኑና እስራኤልን በድምፅ የሚደግፉ ሰዎች በዩ.ኤስ.አሜሪካ ውስጥ መኖራቸው የአሜሪካን አይሁዶች ልዩ ጥረትና ልመና ውጤት እንደመሆኑ አይሁዳውያን በማይበዙባቸው አካባቢዎች በሚገኙ ፖለቲከኞች የፖለቲካ ስሌት ላይ የተወሰነ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ኤርቪን አንደርሰን ሁኔታውን ሲገልጹ፡- ‹‹በዲስፔንሴሽናሊስቶች አስተሳሰብ መሠረት የአሜሪካውያን ባህላዊ ዳራ (Cultural Background) በብዛት በመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች ላይ ያጠነጠነ እንደመሆኑ የእስራኤልን መንግሥት መደገፋቸው አይቀርም፡፡ ….. ስለሆነም አይሁዳውያን በፍልስጤም ምድር መሰባሰባቸው በእነርሱ እምነት የእየሱስን ዳግም መምጣት የሚያበስር ስለሆነ የራሳቸውን መንግሥት በዚያ አጠናክረው መመሥረታቸውን አሜሪካውያን ከልብ ቢደግፉ አያስደንቅም›› ብለዋል፡፡[112]

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ግን የክርስቲያን ጽዮናውያንን ተጽዕኖ ያን ያክል አጋንኖ መመልከት አያስፈልግም፡፡ ለምን ቢባል የታላቋን እስራኤል መመስረት በጽናት የሚደግፉ ሆነውና የሁለት መንግሥታትን የሰላም ሀሳብ ክፉኛ እየተቃወሙ ባሉበት ሁኔታ የክሊንተን አስተዳደር በ2000 የካምፕ ዴቪድን የሰላም ጥረት እንዳያራምድ፣ እንዲሁም በ1998 የዌይ ስምምነት መሠረት እስራኤል ከምዕራቡ ዳርቻ የሠፈራ መንደር በከፊል እንዳትወጣ ሊያደርጓት አልቻሉምና፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በግልጽ እንደሚታወቀው ለክርስቲያን መብት እንቅስቃሴዎች ይበልጥ ቅርበት አላቸው የሚባሉት ጆርጅ ደብሊው ቡሽ በ2001 የፍልስጤማውያን መንግሥት መመስረቱን እንደሚደግፉ ይፋ ከማድረግ አላገዷቸውም፡፡

ክርስቲያን ጽዮናውያን በዩ.ኤስ.አሜሪካ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲ ከሌሎች የእስራኤል ሎቢ አድራጊ አካላት ይልቅ አነስተኛ ተጽዕኖ ያላቸው እንዲሆኑ የሚያደርጓቸው ብዙ ምክንያቶች አሉ፡፡ ምንም እንኳን ፕሬዚዳንት ቡሽ ራሳቸው የክርስቲያን መብት ተሟጋችነት የፖለቲካ ዳራ ያላቸው ቢሆንም፣ የክርስቲያን ጽዮናውያን የፖለቲካ አድማስ ከእስራኤል ጉዳይ ያለፈና ብዙ ነገሮችን የሚያካትት ነው፡፡ እሰራኤልን መደገፍ ሮበርትሰን፣ ባውርና ፋልዌልን የመሳሰሉ የክርስቲያን ጽዮናውያን መሪዎችና ተከታዮቻቸው ከሚያተኩሩባቸው አጀንዳዎች አንዱ ብቻ ቢሆንም፣ ያን ያክል በጣም አንገብጋቢ የሚባለው አጀንዳ ግን ላይሆን ይችላል፡፡

ሌላው የክርስቲያን ጽዮናውያን ችግር መሪዎቻቸው አርባ ሚሊዮንና ከዚያ በላይ የሆኑ ወንጌላውያን ተከታዮችን ወክለው እንደሚናገሩ በተደጋጋሚ ቢገልጹም ለእስራኤል በጥልቅ የሚያስቡ አባላቶቻቸው ያለጥርጥር በጣም ጥቂት ብቻ መሆናቸው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ አይፓክን ከመሳሰሉ የአይሁድ ሎቢስቶች ጋር ሲነጻጸሩ ክርስቲያን ጽዮናውያን ብሔራዊ ጸጥታን ወይም አንድ የተለየ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን የሚመለከት አጀንዳን አስመልክቶ በሚደረግ ክርክር ተጽኖአቸውን ለማሳረፍ ተጨባጭ የሆነና የተደራጀ ጉልበት ያንሳቸዋል፡፡ ሩዝ ሞውሊ በ1980ዎቹ እንዲሁም ኤርቪን አንደርሰን በ1999 ባደረጓቸው ጥናቶች ጀሪ ፋልዌል እና ሌሎች የክርስቲያን

ጽዮናውያን አመራሮች በኮንግረስ ውስጥ እስራኤልን አስመልክተው ያደረጉት ሎቢ በጣም አነስተኛ መሆኑን አስፍረዋል።[113] በተመሳሳይ ሁኔታ ራቢ የቺል ኤክስታይን የተባሉት የአይ. ኤፍ ሲ.ጄ ድርጅት መስራች ዜቭ ቻፌትስ ለተባለው ዘጋቢ እንደገለጹለት የብሔራዊ ጸጥታ አማካሪ የነበሩትን ኮንዳሊዛ ራይስን ለመጎብኘት በ2003 ወደዚያ የወሰዷቸው ወንጌላውያን ብቻ ናቸው እስራኤልን ወክለው በኋይት ሃውስ ሎቢ ያደረጉት።[114] እንደዚያም ሆኖ ኤክስታይን እንዳጋነኑት እንኳ ባይሆን እነዚያ ወንጌላውያን ለኮንደሊዛ ራይስ ካቀረቧቸው በርካታ ጉዳዮች መካከል የእስራኤል ጉዳይ አንዱ ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ነው። በተነፃፃሪ ሁኔታ አይፓክ፣ የፀረ ስም ማጥፋት ሊግ (ኤ.ም.ኤ.ዲ.ኤል)፣ የአሜሪካ ጽዮውያን ድርጅት (ዜድ.ኦ.ኤ) እና የፕሬዝዳንቶች ኮንፈረንስ አሜሪካ እስራኤልን እንድትረዳ ማድረግን የአጀንዳቸው የመጀመሪያ ነጥብ አድርገው የሚንቀሳቀሱ ከመሆኑም በላይ በአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ላይ ተጽዕኖ ለማሳረፍ ጄ.አይ.ኤን.ኤስ.ኤ እና ደብሊው አይ.ኤን.ኢ.ፒ.ን የመሳሰሉ የመንግስት አማካሪ ድርጅቶች (think tanks) እንዲያግዟቸው አነቃቅተዋል። የክርስቲያን ጽዮናውያን ተጽዕኖ አነስተኛ የሆነበት ሌላው ምክንያት የክርስትና ሃይማኖት የተወሳሰበ የሞራልና ሃይማኖት አስተምህሮቶችን ያቀፈ በመሆኑና ከእነዚህ ትምህርቶቹ የሚበዙት እስራኤልን ያለቅድመ ሁኔታና ያለ ድጋፍ መደገፍን ስለማያበረታቱ ነው። ክርስቲያን ጽዮናውያን፣ መጽሀፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች የፍልስጤምን ምድር አይሁዳውያን መቆጣጠራቸውን እንደሚደግፉ ያምኑ ይሆናል። ሆኖም ግን የክርስትና መርሆዎች፣ ለምሳሌ ‹‹ጎረቤትህን እንደራስህ ውደድ›› የሚለው የክርስቶስ ትምህርት እስራኤል ፍልስጤማውያንን ከምትይዝበት የስቃይ መንገድ ጋር ይጋጫል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከተጠቀሱት ታሪኮችና ከሌሎች የአይሁድ-ክርስቲያን ባህሎች አንጻር ሁኔታውን ሲያስተውሉት ብዙ ዋና ዋና የሚባሉ የአብያተ ክርስቲያናት ክፍልፋዮች የሁለት መንግስት መፍትሄን ከመቀበልና እስራኤል የምትከተላቸውን የተለያዩ ፖሊሲዎች ከመተቸት አይታቀቡም። እንደዚያ እንዲያደርጉ የሚገፋፋቸው ሌላ ሳይሆን በክርስትና ሃይማኖት ከፍተኛ ትኩረት ለተሰጠው ሰላምና ፍትህ ያላቸው ቀናዒነት ነው።[115]

የአሜሪካ አይሁዳውያን እስራኤል የምትፈጽማቸውን ብዙዎቹን ድርጊቶች እንደማይደግፉ ሁሉ የክርስቲያን ወንጌላውያንም አይደግፉም።

የክርስትያን ጽዮናውያንን ተጽዕኖ ዝቅ የሚያደርገው ሌላው ምክንያት ዋና ዋና የሚባሉት አፍቃሪ-እስራኤል የአይሁድ ቡድኖች ያላቸው ዓይነት የፋይናንስ (ገንዘብ) አቅም የሌላቸው በመሆኑ የመካከለኛው ምስራቅን ጉዳይ በተመለከተ የመገናኛ ብዙሃን የሚሰጧቸው ሽፋን ደካማ ነው።[116] ሮበርትስን ወይም ባውርን የመሳሰሉት የክርስቲያን ጽዮናውያን መሪዎች የሞራል ወይም ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን አንስተው ሲናገሩ የመገናኛ ብዙሃንን ሰፊ ሽፋን ያገኙ ይሆናል። የመካከለኛውን ምስራቅ ወቅታዊ ሁኔታ በሚመለከት ጉዳይ ግን የመገናኛ ብዙሐን ከነርሱ ይልቅ ፊታቸውን ወደ አይሁድ ድርጅት መሪዎች ማዞርን ይመርጣሉ። እንግዲህ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ክርስቲያን ጽዮናውያን ለአይሁዳዊያን ሎቢስቶች አጋዥ እንጂ ወሳኝና ጠቃሚ ኃይል ተደርገው አይታዩም።

የሎቢው የኃይል ምንጮች

ለመሆኑ የእስራኤል ሎቢ ውጤታማ የሚሆነው ለምንድን ነው? ለዚህ አንደኛው ምክንያት የአሜሪካ የፖለቲካ ስርዓት ባህሪ ሰፊና ክፍት በመሆኑ ነው። ዩናይትድ ስቴትስ እንደሚታወቀው የተከፋፈለ የመንግስት አስተዳደር ሥርዓት የምትከተል በመሆኗ፣ በሚገባ የተደራጀ የመናገርና ሃሳብን የመግለጽ መብት ባለቤት ስለሆነች፤ ምርጫ ለማካሄድ ብዙ ገንዘብ የሚያስፈልግ በመሆኑና የምረጡኝ ዘመቻዎችን ለመደገፍ በሚሰጡ መዋጮዎች ላይ የሚደረገው ቁጥጥር ደካማ በመሆኑ ጭምር ነው። ይህን በመሰለው የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቡድኖች ዩናይትድ ስቴትስን ያስገኙዋት የተለያዩ መንግስታት (states) በሚያወጧቸው ፖሊሲዎች ላይ የራሳቸውን ተጽዕኖ ለማሳረፍ ሰፊ ዕድል ተከፍቶላቸዋል። ስለሆነም በራስ አነሳሽነት የሚደራጁ ቡድኖች የሚፈልጓቸውን ተወዳዳሪዎች ለመደገፍ ለምርጫ ዘመቻ የሚሆን ገንዘብ ከማሰባሰብ ጀምሮ የፖለቲካ አቋማቸውን የተጠራጠሯቸውን ፖለቲከኞች እንዲሸነፉ ከማድረግ አይመለሱም። ተመራጮችንና የስራ አስፈጻሚውን ሎቢ ማድረግን ጨምሮ የሚደግፏቸውን ተመራጮች በፖሊሲ ቀረጻና ማርቀቅ ላይ እንዲመደቡ እስከማድረግ ድረስ ርቀው ይሄዳሉ። ከዚህ ሁሉ በላይ የሕዝቡን አመለካከት ለመቅረጽና እነርሱ ወደሚፈልጉት አቅጣጫ ለማዞር የሚጠቀሙባቸው ብዙ ዓይነት ዘዴዎች አሏቸው። ለምሳሌ የእነርሱ ደጋፊ የሆኑ ጋዜጠኞችን መልምለው በማዘጋጀት፤ መጽሐፍትን በመጻፍ፣ የተለያዩ አርቲክሎችንና አስተያየቶችን በጋዜጦችና በመጽሔቶች ላይ በማውጣት፤ ከእነርሱ ተቃራኒ የሆኑ ሃሳቦችን ዋጋ በማሳጣት ወዘተ አሸንፈው ለመውጣት ይታገላሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ በሚገባ የሚንቀሳቀሱና በቂ የሆነ ሃብት መድበው ከልብ የሚጥሩ ወገኖች የህዝቡን አስተያየት እነርሱ ወደሚፈልጉት የፖሊሲ አቅጣጫ ለማዞርና ደጋፊያቸው ለማድረግ ብዙ አይቸገሩም።[117]

የሎቢው ስኬት፣ የተለያዩ ሕዝቦች በሚኖሩበት ማሕበረሰብ ውስጥ ቡድኖች በየጊዜው የሚያራምዱትን ተለዋዋጭ ፍላጎት ለማስተናገድ የሚችል መሰረታዊ ዲሞክራሲ መኖሩን ያንጸባርቃል። በዲሞክራሲ አሰራር በአንጻራዊነት አነስተኛ የሚባሉ ቡድኖች እንኳ በጠንካራ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ዓላማ ይዘው እስከተገኙ ድረስ የሚፈልጉትን ለማሳካት በቀላሉ

የሚያስችል ተጽዕኖ መፍጠር አይሳናቸውም፡፡ ቀሪውና አብዛኛው ሕዝብ ግድየለሽ ነው፡፡ ምንም እንኳን የቡድኖቹ አባላት አነስተኛ ቢሆኑም የፖሊሲ አውጪዎች በተለይም ደግሞ የኮንግረስ አባላት ሊያስተናግዷቸው ዝግጁ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ይህን በማድረጋቸው የቀረው ሕዝብ እንዳማይቆጣቸው እርግጠኞች ስለሚሆኑ ነው፡፡ አንድ የዩ.ኤስ. አሜሪካ ሲናተር እርሳቸውና የእርሳቸው ባልደረቦች በሎቢው ግፊት አወዛጋቢ በሆነ የሕግ ረቂቅ ላይ ለምን እንደፈረሙ ተጠይቀው ሲመለሱ፡- ‹‹ባለመፈረም የሚገኝ ፖለቲካዊ ጥቅም የለም፡፡ ሆኖም ግን ብትፈርም ማንንም አታስቀይምም፡፡ ያንን ባታደርግ ግን አንተ ባለህበት ግዛት (state) የተወሰኑ አይሁዳዊያንን ማስቆጣትህ አይቀርም›› ብለዋል፡፡[118]

ይህን የመሰለው አናሳ በሆኑና ጠንካራ ፍላጎት ባላቸው ቡድኖች የሚፈጠር ያልተመጣጠነ ተጽዕኖ ይበልጥ እየጨመረ የሚሄደው ተቃዋሚ ቡድኖች ከሌሉ ወይም ደካማ ሆነው የሚገኙ ከሆነ ነው፡፡ ምክንያቱም ፖለቲከኞች የሚያስተናግዱት ከአንዱ አቅጣጫ የሚነሳውን ፍላጎት ብቻ ስለሚሆንና ሕዝቡም የሚዳምጠው የአንደኛውን ወገን ታሪክ ብቻ ስለሚሆን ነው፡፡ ጉዳዩ የእርሻ ድጎማ ወይም የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን የሚመለከት ቢሆንም ድምጻቸው እንዲሰማ ጠንካራ ፍላጎት ያነገቡ ቡድኖች በውስጣቸው ካቀፉት የአባላት ብዛት የላቀ የፖለቲካ ጉልበት ሲቀዳጁ በተደጋጋሚ ይስተዋላሉ፡፡

በቀጣዩ ምዕራፍ በይበልጥ እንደሚብራራው የእስራኤል ሎቢ ይህን በመሰለው አሠራር እየታገዘ ነው እንግዲህ በዩናይትድ ስቴትስ ፖለቲካ ላይ ሊነግስ የቻለው፡፡ የአሜሪካ አይሁዶች በአንጻራዊነት ሲታዩ የበለጸጉ፣ በሚገባ የተማሩና የሚደነቅ የበጎ አድራጊነቱ ባሕል ያላቸው ናቸው፡፡ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ታላቅ ችሮታ የሚያደርጉ ሲሆን የፖለቲካ ተሳታፎአቸውም በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ጠቀም ያለ ቁጥር ያላቸው ህዳጣን የአሜሪካ አይሁዶች ለእስራኤል ጠንካራ ስሜት ያላቸው ባይሆኑም ብዙሃኑ በሚያሳዩት የጋለ ስሜት መገፋታቸው አልቀረም፡፡ ለእስራኤል ጠንካራ ድጋፍ ከሚያሳዩ የክርስቲያን ጽዮናውያን ጋር ተዳምረው ለእስራኤል አስተማማኝ የድጋፍ ምንጭ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

ሌላው ከዚህ እኩል አስፈላጊ የሆነው ጉዳይ ሎቢ የሚያደርጉ ዋና ዋና ጽዮናዊ ድርጅቶች በአስደናቂ ደረጃ ላይ የሚገኝ የሃብትና የባለሙያ ብቃት ያላቸው መሆኑ ነው፡፡ የፖለቲካ ሳይንስ ሊቅ በሆኑት ሮበርት ትራይስ አገላለጽ፡- ‹‹ብዙዎቹ አቢይ የሚባሉት የአይሁድ ቡድኖች መለያ ባሕሪ የአባላቶቻቸው ብዙ መሆን፣ በሚገባ የሰለጠነ የሰው ኃይል ያላቸው መሆኑ፣ በበቂ የገንዘብ አቅም የሚታገዝ የማህበራዊ ደህንነትና የፖለቲካ

መርህግብር መንደፋቸው፣ የተለዩና ትኩረት የሚሹ ችግሮችን የመፍታት አቅምና ችሎታ ያላቸው ባለሙያዎችን ማደራጀታቸውና በውስጣዊ የግንኙነት መዋቅር የተሳሰሩ መሆናቸው ነው።" በተጨማሪም በክልሎችና በብሄራዊ ደረጃ የበርካታ ድርጅቶች ባለቤት መሆናቸው፡- ‹‹የውጭ ፖሊሲን የሚመለከት አስፈላጊና አጣዳፊ ጉዳይ ሲያጋጥም አፍቃሪ- እስራኤል የሆኑ ንቅናቄዎችን ከዚህም ከዚያም በፍጥነትና በተቀናጀ ሁኔታ ለማንቀሳቀስ ያላቸውን ችሎታ ያመለክታል።››[119]

ይህ ሁሉ ጥረት የሚሳለጠው ደግሞ እስራኤል በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ባላት አጠቃላይ የሆነ መልካም ገጽታ ነው። የቀድሞው የኒውሃምሻየር ሪፐብሊካን ፓርቲ ሲናተር ዋረን ሩድማን ይህን ጉዳይ ሲገልጹ፡- ‹‹እነርሱ (እስራኤላውያንን ማለታቸው ነው) ምርጥ የሆነና ለሽያጭ የቀረበ እቃ እንደያዘ ነጋዴ ናቸው›› ብለዋል።[120] በዝርዝር እንደምንዳስሰው ይህ መልካም ገጽታ የተገነባው እስራኤል ምንጊዜም ጥሩ ገጽታ እንዲኖራት ሎቢው በሚያደርገው ያላሰለሰ ጥረትና ሰፋ ባለ ግንዛቤ ከታየ ደግሞ ዩናይትድ ስቴትስና እስራኤል በሚጋሩት የአይሁድ- ክርስቲያን ባህል (judio - christian- culture)፣ እንዲሁም በሌሎች በርካታ ኢ-መደበኛ (informal) የሆኑ የግንኙነት ውጤቶች ምክንያት ነው።[121]

በመጨረሻም ሎቢው በሚገባ የተደራጀ ተቃዋሚ የሌለበት መሆኑ ተጠቃሚ እንዲሆን አስችሎታል። አንድ ሴናተር እንዳሉት ‹‹ታላቅ ከሆነው የአይፓክ ጫና በተቃራኒ ድምጽ ብትሰጥ "እሰይ አበጀህ" የሚልህን ማንም ሰው አታገኝም።››[122] ምንም እንኳን አረብ አሜሪካውያን በበቂ መልኩ በህዳጣንነት የሚገኙ ቢሆኑም ሃብት የላቸውም፤ አልተደራጁም፣ ብዛት የላቸውም አልያም ደግሞ እንደ አይሁድ አማሪካውያን በትምህርት፤ በንግድና በመገናኛ ብዙሃን (media) አመርቂ የሆኑ ቦታዎችን አልተቆናጠጡም። በፖለቲካውም ቢሆን ያን ያክል የጎላ ተሳትፎ አያሳዩም። ይህም እንዲሆን በከፊል ምክንያት የሆነው አረቦች ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በብዛት የጎረፉት ገና አሁን በቅርቡ በመሆኑ ነው። ቀድመው የደረሱት የመጀመሪያዎቹ ትውልዶችም በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ያላቸው ተሳትፎና ውክልና አነስተኛ የሆነ፣ ብዙ ሃብት ያላፈሩ፣ ከአሜሪካውያን ልማዶችና ተቋማት ጋር ብዙ ያልተለማመዱ፣ በፖለቲካውም ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ አናሳ ስለነበር ከኋለኞቹ መጤዎች ዝቅ ያለ ተጽዕኖ ያላቸው ሊሆኑ በቅተዋል።

አፍቃሪ አረብ (pro-arab) ድርጅቶችም ቢሆኑ የእስራኤልን ሎቢ ከመሠረቱት ታላላቅ ቡድኖች ጋር ሲነጻጸሩ እዚህ ግቡ የሚባሉ አይደሉም።

በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚገኙ አፋቃሪ አረብና ፍልስጤም ድርጅቶችም እንዲሁ እፍኝ የማይሞሉ ሲሆኑ ከአይፓክና ሌሎች የአይሁድ ድርጅቶች ያነሱ፤ ከሞላ ጎደል ሁሉም በቂ የሆነ የገንዘብ አቅም የሌላቸውና አፈጻጸማቸውም ደካማ ነው፡፡ የአይፓክ ልሳን በሆነው የኒር ኢስት ጋዜጣ የቀድሞ አዘጋጅ ሚቸል ባርድ ትዝብት መሠረት ‹‹ከመጀመሪያው ጀምሮ የአረብ ሎቢ ከምርጫ ፖለቲካ ጋር ብቻ ሳይሆን ከአደራጃጀት ጋር የተያያዙ ችግሮች ተጋርጠውበታል፡፡ በእርግጥ በፖለቲካ የተደራጁ ብዙ ቡድኖች ይገኛሉ፡፡ ሆኖም ግን በርካታዎቹ በአንድ ሰው የሚንቀሳቀሱ ወይም አነስተኛ የሆነ የገንዘብና የህዝብ ድጋፍ ያላቸው ናቸው፡፡›› የዩ.ኤስ አሜሪካ ፖለቲከኞች አልፎ አልፎ ከአረብ አሜሪካውያን የሎቢ ጫና እንደተደረገባቸው በመናገር ሲያማርሩ ይሰማሉ፡፡ ሆኖም ግን ያንን ሎቢ ለማስተናገድ ሲሉ ብቻ የፖለቲካ ባህሪያቸውን ለማስተካከል በቂ የሆነ ምክንያት አያገኙም፡፡ በአጭሩ የሃሪ ትሩማንን ታዋቂ ጥቅስ ለማስቀመጥ ‹‹እስከዛሬ ባሳለፍኩት የፖለቲካ ልምዴ አንድም የአረብ መራጭ ድምጽ ማግኘቴን አላስታውስም፡፡››[123]

ከዚህ ጋር አብሮ መታየት ያለበት ጉዳይ አረብ አሜሪካውያን ከተለያዩ አገራት መነሻ ወይም ዳራ (back ground) የመጡ፣ እንዲሁም የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖትን የሚከተሉ እንደመሆናቸው የመካከለኛውን ምሥራቅ ጉዳይ በተመለከተ ተመሳሳይ አቋም የማንጸባረቅ አጋጣሚያቸው የተመናመነ ነው፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ተቃራኒ የሆኑ ሃሳቦችን ሲያራምዱ ይስተዋላሉ፡፡ በሌላ በኩል ድግሞ ብዙ አሜሪካውያን በእስራኤልና አሜሪካ መካከል የባህል መመሳሰል እንዳለ ይሰማቸዋል፡፡ ስለሆነም አረቦችን ሁልጊዜም የውጭ ሰዎች (እንዲያውም ከእነርሱ የሚቃረን ስልጣኔ ያላቸው) አድርገው ይቆጥሯቸዋል፡፡ በዚህ የተነሳ የአሜሪካውያንን ልብና አዕምሮ ማሸነፍ ለአረብ አሜሪካውያን ብዙ ጥረትን የሚጠይቅ ሥራ ሆኖባቸዋል፡፡ ሮበርት ትራይስ በ1981 ስለ አረብ አሜሪካውያን የራሳቸውን ግምገማ ካደረጉ በኋላ የተናገሩት እስካሁንም ድረስ ብዙ የተለወጠ አይመስልም፡፡ እንዲህ ነበር ያሉት፡- ‹‹ዩ. ኤስ. አሜሪካ በመካከለኛው ምስራቅ የምትከተለውን ፖሊሲ አስመልክተው የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ከቁጥር የሚገባ አይደለም፡፡››[124]

ነዳጅ ዘይት የሚያስከትለው መጠነኛ ተጽዕኖ

የአረብ መንግስታትም ሆኑ የሚኩራሩበት የነዳጅ ዘይት ሎቢ በእስራኤል ሎቢ ላይ ይኸ ነው የሚባል የአጸፋ ድል አላስገኘም። የነዳጅ ዘይት አምራች ኩባንያዎችና ሃብታም ነዳጅ ላኪ የአረብ መንግስታት በዩናይትድ ስቴትስ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊስ ላይ ኃይለኛ የሆነ ተጽዕኖ ያሳርፋሉ የሚለው እምነት በስፋት ተንጸባርቋል። ይበልጡንም ደግሞ በኢራቅ የተደረገው የ2003ቱ ጦርነት "ለነዳጅ ዘይት የተደረገ ጦርነት" የሚል ስያሜ የተሰጠው እንደመሆኑ ሃሊባርቶንን የመሳሰሉ ከነዳጁ ጋር የተያያዙ ድርጅቶች በጥቅም ፈላጊነት ስማቸው ተነስቷል።[125] ይህ አስተሳሰብ የምንግዜም የእስራኤል ተቺዎች ከሆኑት መካከል ናአም ቾምስኪና ስቴፈን ዙነስን በመሳሰሉት እንዲሁም ማርቲን ፔሬትዝን በመሰሉ ደጋፊዎቻቸው በሚያስደንቅ ሁኔታ ሲራገብ ቆይቷል።[126] በቡሽ ቤተሰብና በሳዑድ ቤተሰብ መካከል ያለው ግላዊና ገንዘብ ነክ ግንኙነት የመካከለኛውን ምሥራቅ ፖሊሲ አሜሪካን በሚጎዳ መልኩ በመቅረጽ ተጽዕኖ አሳርፎበታል ተብሎ በዚህ አስተሳሰብ አራማጆች ይታመናል።[127]

የዩናይትድ ስቴትስ በመካከለኛው ምስራቅና በፋርስ ባህረ ሰላጤ ትልቅ ስትራቴጂያዊ ፍላጎት ያላት መሆኑ አያጠያይቅም። ምንም እንኳን ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የኃይል አቅርቦቷን ከመካከለኛው ምስራቅ ይበልጥ ከሜክሲኮና ቬኑዝኤላ፣ የተፈጥሮ ጋዝ ደግሞ ከዓለም አቀፋዊ ገበያ የምትሸምት ቢሆንም አጠቃላይ በዓለም ላይ ያለውን የነዳጅ አቅርቦት የሚቀንስ ማንኛውም ምክንያት ኢኮኖሚዋን እንደሚጎዳው ይታወቃል።[128] በምዕራፍ 2 ላይ እንደተገለጸው ለዚህም ነው የዩናይትድ ስቴትስ መሪዎች የፋርስ ባህረ ሰላጤን ወሳኝ እንደሆነ የጥቅም ምንጫቸው የሚመለከቱትና በክልሉ የኃይል ማመጣጠንን ለማምጣት የሚታገሉት። እንዲሁም ከዚያ አካባቢ የሚፈልቀውን ነዳጅ እንደልብ ወደ ዓለም ገበያ እንዳይፈስ የሚያግዱ መንግስታትንም አምርረው ይዋጋሉ። ምንም እንኳን ዩናይትድ ስቴትስ በዚያ አካባቢ ካሉ አገራት ጋር ከሚከተሏቸው የአገር ውስጥና የውጪ ፖሊሲዎች አኳያ -መሠረታዊ ልዩነት ያላት ቢሆንም ከነርሱ ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖራት ትሻለች። የመካከለኛው ምሥራቅ ነዳጅ ዘይት አስፋለጊ

መሆኑ ዩናይትድ ስቴትስ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የሳዑዲ ወዳጅ እንድትሆንና የኢራኑንም ሻህ ለብዙ ዓመታት እንድትደግፍ አድርጓታል፡፡ የኢራኑ ሻህ በ1979 ሲወድቅ ዩናይትስ ስቴትስ የክልሉን የሃይል ሚዛን አስተውላ የነዳጁም አቅርቦት እንዳይቋረጥ በማለም በሮናልድ ሬገን አስተዳደር (ከ1980-88) ወደ ሳዳም ሁሴኔ ኢራቅ አዘነበለች፡፡ ከዚያ በኋላ ኢራቅ ኩዌትን ስትወር ዩናይትስ ስቴትስ ቀድሞውንም በክልሉ ጡንቻው የፈረጠመ አንድም ኃይል እንዲኖር የማትፈልግ በመሆኗ በ1990 ጣልቃ ገብታ ኢራቅን ከኩዌት አስወጣች፡፡ አሜሪካ ይህን ፖሊሲዋን እንድትቀጥልበት ለማድረግ ጠንካራ ሎቢ አላስፈለገም፡፡ ምክንያቱም የባህረ ሰላጤውን ነዳጅ የወዳጅነት መንፈስ ከማያሳዩ ኃይሎች እጅ የማውጣቱ አስፈላጊነት ጥያቄ አይነሳበትምና፡፡

ከዚህ ግልጽ የሆነ የአሜሪካ ፍላጎትና የመካከለኛውን ምሥራቅ ሰላማዊ የነዳጅ ፍሰት ከማረጋገጥ ጥረት በመለስ ‹‹በነዳጅ ሃብት የከበሩ መንግስታት የዩናይትድ ስቴትስን የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲ ለማስቀየር ሎቢ አድርገዋል›› የሚለው አባባል በቂ ማስረጃ የለውም፡፡ የአረብ ጌትሮ ዶላር ወይም የኃይል አቅርቦት ኩባንያዎች የአሜሪካን ፖሊሲ ሎቢ በማድረግ ማስቀየር ቢችሉ ኖሮ ዩናይትስ ስቴትስ ገና ድሮ ራሷን ከእስራኤል በማራቅ ፍልስጤማውያን የራሳቸውን መንግስት እንዲመሰርቱ ባደረገች ነበር፡፡ ሳዑዲ አረቢያን የመሳሰሉት አገራት በተደጋጋሚ ዋሽንግተንን በመጫን በእስራኤል ፍልስጤም ጉዳይ ሚዛናዊ የሆነ ፖሊሲ እንዲኖራት ለማድረግ ሞክረዋል፡፡ ሆኖም ግን ጥረታቸው ለፍሬ ሊታደል አልቻለም፡፡ በ1973 የዩም ኪፑር ጦርነት ወቅትም አሜሪካ እስራኤልን በመርዳቷ ነዳጁን እንደመሳሪያ በመጠቀም አረቦች ሊቀጧት ሞክረዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የነዳጅ ኩባንያዎች የዩ.ኤስ.አሜሪካን ፖሊሲ የማስቀየር አቅም ቢኖራቸው ኖሮ ዋሽንግተን ታላላቅ የነዳጅ አምራቾች ለሆኑት ሐገራት፣ ማለትም ለሳዳም ሁሴኔ ኢራቅ፣ ለሙአመር ጋዳፊዋ ሊቢያ ወይም ለኢስላማዊ ሪፐብሊኳ ኢራን ውለታዎችን በመዋል ኩባንያዎቿ የእነዚያን ሃገራት ነዳጅ በሚገባ ለማውጣትና ወደ ገበያ ለማቅረብ እንዲረዷቸው ታበረታታ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ዩናይትድ ስቴትስ ያደረገችው በተቃራኒው ነው፡፡ የነዳጁን ኢንዱስትሪ ፍላጎት በተጻረረ መልኩ በእነዚህ ሶስት አገራት ላይ ማዕቀብ ጥላለች፡፡ በዚህ መጽሐፍ ክፍል ሁለት ላይ እንደምናየው በአንዳንድ

ሁኔታዎች እንዲያውም የአሜሪካ መንግስት የራሱ ኩባንያዎች ትርፍ የሚያገኙባቸውን ከእነዚህ አገራት ጋር የተደረጉ የንግድ ስምምነቶችን ሳይቀር ሆነ ብሎ ጣልቃ እየገባ ያደናቅፍ ነበር። አንዳንድ ተቺዎች እንደሚሉት የነዳጅ ሎቢ ጉልበት ያለው ቢሆን ኖሮ ይህን የመሰሉ ማዕቀቦች ባልተደረጉ ነበር።

በሌላ በኩል ሳዑዲ አረቢያን የመሳሰሉ ባለጸጋ መንግስታት የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎችን በመቅጠር ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያላቸው ገጽታ የተሻለ እንዲሆን ሎቢ ያደርጉላቸው ዘንድ፣ እንዲሁም የተወሰኑ የመሳሪያ ግዢ ስምምነቶችን ለማሳካት እንዲያግዟቸው ጥረት ያደርጋሉ። ይህ ጥረታቸውም አልፎ አልፎ ፍሬ ማሳየቱ አልቀረም። ከሁሉም በላይ ትልቅ የሚባለው ስኬት የተመዘገበው በ1982 ኮንግረስ ለሳዑዲ አረቢያ ‹‹አዋክስ›› የተባሉ የጦር ጀቶችን ለመሸጥ በተስማማ ጊዜ ነበር። ያ ስምምነት ከመደረጉ በፊት አይፓክ ስምምነቱ እንዳይሳካ ታላቅ የሆነ የሎቢ ዘመቻ ከፍቶ የነበረ ቢሆንም ሊሳካለት አልቻለም። ይህን ታሪካዊ ክስተት አንዳንድ ወገኖች የእስራኤልን ሎቢ ውስን የተጽዕኖ አቅምና የአረብ ሎቢን ጠንካራነት ለማሳየት እንደ ናሙና ይጠቀሙበታል። ይሁንና የአረብ ሎቢ እንዲህ አይነት ስኬቶችን የሚያገኘው አልፎ አልፎ ባልተለመዱና ሁልጊዜም በማይገኙ አጋጣሚዎች ምክንያት መሆኑን ግን ልብ ይሏል። ሁኔታውን በመጠኑ ለማብራራት ያክል የሳዑዲ አረቢያ ስትራቴጂዊ ጠቃሚነት ግልጽ ነው። በጊዜው ደግሞ ሶቪዬት ሕብረት ለባሕረ ሰላጤው ታላቅ ወታደራዊ ስጋት ደቅና ነበር። ሮናልድ ሬገን በሕዝብ ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት ያላቸው ተወዳጅ መሪ ስለነበሩ አስተዳደራቸው ማንኛውንም ገደብ በጣጥሶ የኮንግረሱን ስምምነት ለማግኘት አልተቸገረም። እንደዚያም ቢሆን የመሳሪያ ሽያጩ አጣብቂኝ ውስጥ ከገባ በኋላ በመጨረሻ 52 ለ48 በሆነ ጠባብ ውጤት ነበር ያለፈው። እናም ሬጋን በርካታ የሆኑ ተከታታይ የመሳሪያ ሽያጭ ማዕቀፎችን ለማድረግ ከሳዑዲና ዮርዳኖስ ጋር ውል ሲፈጽሙ ከአፍቃሪ-እስራኤል ድርጅቶችና ከኮንግረስ አባላት በአዲስ መልክ የተደራጀን ሎቢ ተጋፍጠው ነው።[129]

የአረብ ነዳጅ አምራቾች ውስን የሆነ ተጽዕኖ ብቻ እንዲኖራቸው ያስገደዳቸው ምክንያት ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ሕዝቡን መሠረት ያደረገ

ድጋፍ ስለሌላቸው ነው። ፕሮፌሽናል የሆኑ ሎቢስቶችንና የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያዎችን መጠቀም መምረጣቸው ተቺዎቻቸው ተወካዮቻቸውን የውጭ ኃይሎች ቅጥረኞች አድርገው እንዲያዩዋቸው በር ከፍቷል። የአይፓክ አባል የሆኑት ቶም ዳይን የሳዑዲን የሎቢ ጥረቶች እንደሚከተለው አጣጥለዋቸዋል፦ ‹‹ፍሬድ ዱቶንን የመሰሉ የውጭ ወኪሎችን በመቅጠር ትዕዛዞቻቸውን እንዲፈጽሙ ያደርጋሉ። በአሜሪካ መሬት ላይ ስሩን የሰደደ ምንም ዓይነት ድጋፍ የላቸውም።››[130] የእስራኤል ሎቢ በሌላ በኩል ከእነዚህ ጋር ሲነጻጸር የአሜሪካውያን ማህበረሰብ አካል የሆኑ ንዑሳን ዜጎች የፖለቲካ ተሳትፎ መገለጫ ነው ማለት ይችላል። ስለሆነም የፖለቲካ አካሄዱና እንቅስቃሴዎቹ በሙሉ በስፋት ተቀባይነት ያላቸው የህጋዊ ፖለቲካ እንቅስቃሴ አካሎች ተደርገው ነው የሚታዩት።

በተጨማሪም ብዙዎቹ የነዳጅ ላኪ መንግስታት በሥልጣን ላይ ለመቆየት ከነዳጅ ሽያጭ በሚያገኙት ትርፍ ላይ ጥገኛ በመሆናቸው አቅርቦቱን ለማቋረጥ የሚያደርጉት ማስፈራራት ተዓማኒነት የጎደለው ስለሚሆን ተጽዕኖአቸውን ዝቅ ያደርግባቸዋል። ከእነዚህ መንግስታት ብዙዎች በምዕራቡ ዓለም ምጣኔ ሃብት ላይ ጠቀም ያለ መዋዕለ ንዋይ ያፈሰሱ በመሆኑ ዘላቂ የሆነ የኢኮኖሚ ውድቀት ከተከሰተ በብዙው የሚጎዱት እነርሱ ጭምር ናቸው። የአቅርቦቱ መቀነስ ደግሞ ዋጋው እንዲያሻቅብ ምክንያት ስለሚሆን አማራጭ የኃይል ምንጭ ማፈላለግን እንደ አዲስ የትኩረት አቅጣጫ ሁሉም እንዲመለከተው በር ያከፍታል። እንዲሁም ዩናይትድ ስቴትስና ሌሎች ሃገራት ከነዳጅ ጥገኝነት ራሳቸውን ለማላቀቅ ሁኔታውን እንደመልካም አጋጣሚ እንዲጠቀሙበት ያነሳሳቸዋል። ስለሆነም ሳዑዲን የመሳሰሉት አበይት የነዳጅ አምራች ሃገራት የኢንዱስትሪው ማንቀሳቀሻ ዋነኛ ኃይል ነዳጅ ሆኖ እንዲቆይ ስለሚሹ የነዳጅ እቀባን ለፖለቲካዊ ግብ ማሳኪያነት እንደ መልካም የተጽዕኖ መሳሪያ አድርገው አይመለከቱም። በዚህም ምክንያት ምንም እንኳ ዩናይትድ ስቴትስ በምታስገባው የኃይል አቅርቦት ላይ ጥገኛ ብትሆንም እነዚህ ሃገራት እርሷ በምታወጣቸው ፖሊሲዎች ላይ ተጽዕኖአቸውን በሰፊው እንዲያሳርፉ እድል አትሰጣቸውም።

የኃይል አቅራቢ ኩባንያዎችን በተመለከተስ ምን ለማለት ይቻላል? እነዚህ ኩባንያዎች ብዛት ባላቸው የሎቢ እንቅስቃሴዎች ሲካፈሉ መቆየታቸው እውነት ነው፡፡ ሆኖም ግን ከቅርብ አሥርተ ዓመታት ወዲህ ትኩረታቸውን ሙሉ በሙሉ ከዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ ጉዳዩች ይልቅ ትርፋማ በሚያደርጓቸው የንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ አድርገዋል፡፡ በተለይም ደግሞ ይበልጡን ትኩረታቸውን ያሳረፉት ግብርን (tax) በሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ህጎች፤ የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከቱ ጉዳዮች፤ ተጨማሪ የነዳጅ ቁፋሮ ሊደረግባቸው የሚችሉ ቦታዎችን በማሰስና ከኃይል አቅርቦት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ሌሎች ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ ለእነርሱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በሁለተኛነት ደረጃ የሚታይ ነው፡፡ ሮበርት ትራይስ እንዳሉት ‹‹የእነርሱ ዋነኛ ግብ.....መካከለኛው ምስራቅ ትርፋቸውን ከፍ ለማድረግ የሚያስችላቸው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አመቺነት እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም የነዳጅ አምራች ኩባንያዎች አፍቃሪ-አረብ ከሆኑ ድርጅቶች በብዙ እጅ የሚያንስ ጠባብ የሆነ የፖለቲካ ተሳትፎ ፍላጎት ነው ያላቸው ብሎ መደምደም ያስኬዳል››[131]

ይህ ጠባብ የሆነ ተሳትፏቸው ይበልጥ በግልጽ የሚታየው አንድ ሰው የአሜሪካን ፔትሮሊየም ኢኒስቲትዩት ድረ ገጽ በሚመረምርበት ጊዜ ነው፡፡ "የፖሊሲ ጉዳዮች" (policy issues) በሚለው ዋና ርዕስ ስር የአየር ንብረት ለውጥ፣ ኤክስፕሎሬሽን፣ ምርት፣ ነዳጅ፣ ታክስና ንግድ እንዲሁም የአገር ውስጥ ጸጥታ የሚሉ ዝርዝሮች ይኖሉ፡፡ ‹‹እስራኤል›› ወይም ‹‹የአረብ እስራኤል ውዝግብ›› የሚል ነገር በዚያ ድረ ገጽ የሌለ ሲሆን የውጭ ጉዳይ ፖሊስን በተመለከተ ደግሞ አነስተኛ መረጃዎች ብቻ ናቸው የሚገኙት፡፡ የእስራኤል ሎቢስት ድርጅቶችን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዎች ስንመለከት ግን የመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ በአይፓክ ኤዲ ኤል እና የፕሬዝዳንቶች ኮንፈረንስ ድረ ገጽ ፊት ለፊትና መካከል ላይ እንደሚገኙ መገንዘብ እንችላለን፡፡[132] የአይፓኩ ሞሪስ አሚታይ እንደሚገልጹት ‹‹በ1980ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት የነዳጅ አምራችና አከፋፋይ ድርጅቶች 99 ከመቶ የሚሆነውን ሎቢያቸውን የሚጠቀሙት የራሳቸውን ፍላጎት ለማስከበር ሲሆን (ለምሳሌ የግብር አከፋፈልን በተመለከተ ወዘተ....) በውጭ ጉዳይ

ፖሊሲዎች ላይ ሎቢ ሲያደርጉ የታዩት አልፎ አልፎ ብቻ ነው። ስለሆነም የፖለቲካ ሜዳውን ብቻችንን ነበር የምንሮጥበት›› ብለዋል።[133]

ከዚህ ጋር በተያያዘ የአሜሪካ ኩባንያዎች የመካከለኛውን ምስራቅ ጉዳይ ሎቢ ቢያደርጉ በሚገባ የተደራጁትን አፋቃሪ -እስራኤል ድርጅቶች ብቀላ ይፈራሉ። ለምሳሌ በ1975 ሳይታሰብ "ገልፍ ኦይል" የሚባለው የነዳጅ ድርጅት ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ለሚገኙ አፍቃሪ አረብ ድርጅቶች ዋስትና የሰጠበት ሂደት የፕሬዝዳንቶች ኮንፈረንስና የፀረ-ስም ማጥፋት ድርጅት (ኤ ዲ.ኤልን) በመሣሠሉት አፍቃሪ-እስራኤል ድርጅቶች አማካይነት ይፋዊ ውግዘትን አስከተለ። ገልፍ ኦይል ለዚህ ውግዘት ምላሽ ይሆን ዘንድ በኒው ዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ላይ ግማሽ ገጽ የማስታወቂያ ቦታ (op-ed) ገዝቶ ለጥፋቱ ይቅርታ ይደረግለት ዘንድ አንባብያንን እንዲህ በማለት ተማጸነ፡- ‹‹ይህ ጉዳይ እንደማይደገም እርግጠኛ መሆን ተችላላችሁ።›› ትራይስ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹አፍቃሪ-እስራኤል የሆነው ሎቢ ሁልጊዜም ንቁ፣ ቁጡና አጸፋ የሚሰጥ መሆኑ የዩ.ኤስ. ኩባንያዎች መካከለኛው ምሥራቅን አስመልክቶ በአሜሪካ ውስጥ በሚደረግ ፖለቲካዊ ክርክር ቀጥተኛ ተሳታፊ የመሆን ፍላጎት እንዳይኖራቸው አድርጓቸዋል።››[134]

አንዳንድ ሃተታ አቅራቢዎች ‹‹የነዳጅ ዘይትና ጋዝ አምራች ኩባንያዎች አንድም ኢራቅን በመሰሉ ሃገራት ሞቅ ያለ ትርፍ የሚገኝበት ስምምነት ለመፈጸም፣ ያ ካልሆነላቸው ደግሞ እዚህም እዚያም መረጋጋት እንዳይኖር በማድረግ የነዳጅ ዋጋ ከፍ ሲል ብዙ ትርፍ ለማጋበስ የአሜሪካን ፖሊሲ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ›› በማለት ይከሳሉ።[135] ሆኖም ግን ይህ አባባል ኩባንያዎቹ ካላቸው ባህሪ ጋር ሲነጻጸር ያለው ተዓማኒነት አነስተኛ ብቻ ሳይሆን ከኩባንያዎቹ የረዥም ጊዜ ፍላጎት ጋር ፈጽሞ ተቃራኒ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ በኃይል አቅርቦት ላይ የተሠማሩት ኩባንያዎች በነዳጅ በበለጸጉ አካባቢዎች ጦርነት፣ ማዕቀብ፣ የመንግስት ለውጥም ሆነ አለመረጋጋትን የሚያስከትል ማንኛውም ሁኔታ እንዲፈጠር አይፈልጉም። ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ ነገሮች የነዳጅን አቅርቦት በማዳከምና ተቀማጭ የጋዝ ክምችት እንዳይኖር በማድረግ የእነርሱንም ትርፍ የማካበት ዕድል ስለሚያጠብቡ ነው። በተጨማሪም እንዲህ ላይነት ክስተቶች አሜሪካውያን የእነዚህን ኩባንያዎች ምርት (የነዳጅንና ጋዝን ፍላጎት) እንዴት መቀነስ እንዳለባቸው በአትኩሮት እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። ምክትል ፕሬዝዳንት ዲክ

ቸኒ በ1990ዎቹ ሃሊበርቶን ኢንኮርፖሬትድ የተባለውን ዋነኛ የነዳጅ አገልግሎት ሰጪ ተቋም በፕሬዝዳንትነት በሚመሩበት ወቅት በኢራን ላይ የተጫነውን ማዕቀብ እንዲህ በማለት ተቃውመው ነበር፡- ‹‹በአሜሪካ የማዕቀብ ፖሊሲ ምክንያት የዩናይትድ ስቴትስ ኩባንያዎች በዚያ ክልል ከሚደረገው የኢኮኖሚ ጨዋታ እንዲገለሉ ሆነዋል፡፡››[136] ከዲትቸኒ የቀድሞ አቋም የምንገነዘበው ጉዳይ የነዳጅ አምራች ኩባንያዎች የመካከለኛውን ምሥራቅ ፖሊሲ የሚቆጣጠሩ ቢሆን ኖሮ ዩናይትድ ስቴትስ ዛሬ በክልሉ የሚኖራት አጀንዳ የተለየ ይሆን እንደነበር ነው፡፡

ይህ ማለት ግን ጥሩ ካፒታሊስቶች የሆኑት የነዳጅ አምራች ኩባንያዎች ባላበረታቱት የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ሰበብ የሚፈጠሩ ክስተቶችን ትርፍ ለማግኘት አይጠቀምባቸውም ማለት አይደለም፡፡ ትርፋቸውን ለማሳደግ ከሳዳም ጋር እንደሰሩት ሁሉ ከሳዳም በኋላ ከተፈጠረው አዲስ የፖለቲካ ስርዓት ጋርም ይሰራሉ፡፡ ይህም ሆኖ ግን በነዳጅ ሃብት የበለጸጉ የአረብ መንግስታትም ሆኑ የሚያደርጉት የነዳጅ ዘይት ሎቢ በዩ.ኤስ አሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ የእስራኤልን ሎቢ ያህል የበረታ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የነዳጅ ፍላጎት የአሜሪካን የውጭ ፖሊሲ እነርሱ ወደሚፈልጉት አቅጣጫ የመጠምዘዝ ጉልበቱ አናሳ ነውና፡፡[137] የኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰርና የቀድሞው የአሜሪካ ረዳት ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበሩት ሮጀር ሂልስማን በ1970ዎቹ እንዲህ ብለው ነበር፡- ‹‹ሁኔታውን ለሚታዘብ ማንም ሰው ግልጽ እንደሆነው ዩናይትድ ስቴትስ በመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲዋ የነዳጅ ሃብት ትልቅ ቦታ ባገኘበት ጊዜ እንኳን ከአሜሪካውያን የነዳጅ ፍላጎት ይልቅ ለአሜሪካ አይሁድ ማህበረሰብና ተፈጥሮአዊ ለሆነው እስራኤልን የመደገፍ ፍላጎታቸው ግፊት ነበር ምላሽ የምትሰጠው፡፡›› ሚቸል ባርድ የእስራኤልንና አረብ ሎቢን ካነጻጸሩ በኋላ በሰጡት አስተያየት ‹‹አርማኮን የመሰሉ የነዳጅ ኩባንያዎች ባለፉት ዘመናት ሎቢ የማድረግ ዘመቻዎችን ቢያካሂዱም ጥረታቸው በዩ.ኤስ. አሜሪካ ላይ ይኽ ነው የሚባል ተጽዕኖ አላመጣም›› ብለዋል፡፡ የቀድሞው የአይፓክ የህግ ዳይሬክተር ዶግላስ ብሎመፊልድ በ2003 ለቢቢሲ በሰጡት ቃለ ምልልስ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ኤ.አይ.ፒ.ኤ.ሲ (አይፓክ) የአንድ ግዙፍ ዕድል ተጠቃሚ ነው፡፡ እንዲያ እንዲሆን ያገዘው ደግሞ ምንም ዓይነት ተቃዋሚ የሌለበት መሆኑ ነው፡፡››[138]

የሁለትዮሽ ታማኝነት (Dual loyality) ጥያቄ

በአብዛኛው የአሜሪካን አይሁዶች የሚያቅፈውና የዩኤስ.አሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን ለእስራኤል በሚበጅ አቅጣጫ እንዲጓዝ ሎቢ የሚያደርገው ድርጅት አካሄድ የተወሰኑ ሰዎችን አይመቻቸውም፡፡ ለዚህ ዋነኛው ምክንያት ‹‹የሁለት አገራት መንግስታትን እኩል በሆነ ታማኝነት ማገልገል አይቻልም›› የሚለው የተለመደና በአረጀው አውሮፓ ሲሰራበት የቆየ ጸረ-ሴማዊ አሉባልታ ነው፡፡ ይህ ክስ ከመጀመሪያው ጀምሮ በየአገራቱ የተበተኑት አይሁዳውያን ምን ጊዜም ቢሆን የውጭ አገር ዜግነት (ባዕድነት) የሚሰማቸው፣ ከሚኖሩበት አገር ዜጎች ጋር ለመዋሃድ የማይፈቀዱና ለሚኖሩበት አገር ጥሩ የአርበኝነት ስሜት የሚጎድላቸው እንደሆኑ አድርጎ ነው የሚገልፃቸው፡፡ እናም በዚህ ሚዛን የማይደፋ ክርክር መሠረት አይሁዳውያን ታማኝነታቸውን የሚያሳዩት ለራሳቸው ወገን ብቻ እንደሆነ ተደርገው ይታሰባሉ፡፡ Prototols of The Elders of Zion የተባለው አስከፊ የዛሮች (ሩሲያ) መጽሐፍ ‹‹አይሁዳውያን በሚኖሩበት አገር እንደ አምስተኛ ደረጃ ዜጋ ሆነው ነው የሚያገለግሉት፡፡ እነርሱ ከልባቸው የሚሠሩት ዓለምን ለመግዛት በምስጢር ለሚዶልቱ ጺዮናውያን አባቶች ነው›› ይላል፡፡

በዚህ ቆየት ያለ ጸረ-ሴማዊ የስም አጥፊነት አባባል መሠረት አይሁዳውያን ታማኝነታቸውን ለወገናቸው ብቻ የሚያሳዩ ሲሆን ለሚኖሩበት አገር ግን ልባዊ የሆነ ታማኝነት የላቸውም፡፡ ሆኖም ግን ዛሬ ምሁራንና የፖለቲካ ሃተታ ጸሐፊዎች እንደሚስማሙት ግለሰቦች ከአንድ በላይ ለሆኑ ሃገራት ከልብ ታማኝ መሆንና ከእነርሱም ጋር ጥብቅ ትስስር መፍጠራቸው የተለመደና ወቀሳም ሆነ ሂስ የማያስከትል አሰራር እየሆነ ሄዷል፡፡ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር የሆኑት ጋብሬላ ሻፊር ‹‹ቶታል፣ዱዋልና ዲቫይድድ የሚሰኙትን የእንግሊዙኛ ቃላት ሎያሊቲ (ታማኝነት) ከሚለው ቃል ጋር አንድ ላይ በየተራ በማጣመር የአንድ የተለየ ጎሳ፣ ብሔር ወይም ሃይማኖታዊ ቡድን አባል በሆኑና በተለያዩ መንግስታትና አገራት ተበትነው

በሚገኙ ሰዎች ላይ እነዚህ የታማኝነት ዓይነቶች አንድ ላይ ሊገኙ እንደሚችሉ አመልክተዋል።[139] እነርሱም ‹‹ቶታል ሎያሊት›› (አጠቃላይ ታማኝነት)፣ ‹‹ዱዋል ሎያሊቲ›› (ጥምር ታማኝነት) ‹‹ዲቫይድድ ሎያሊቲ›› (የተከፋፈለ ታማኝነት) የሚሉት ሲሆኑ ግለሰቡ እንደየ ሁኔታውና እንደሚገኝበት ተጨባጭ አቋም ይጠቀምባቸዋል ማለት ነው።

አይሁድ አሜሪካውያን ታማኝ ዜጎች አይደሉም የሚለው አስተሳሰብ የተሳሳተ ነው። እናም የፕሬዝዳንቶች ኮንፈረንስ ዳይሬክተር የነበሩት ማልኮለም ሆኔሊን ከሰጡት አስተያየት ጋር ሙሉ በሙሉ እንስማማለን። እንዲህ ነበር ያሉት፡- ‹‹አሜሪካውያን አይሁዶች እጅግ በጣም የአርበኝነት ስሜት ያላቸውና ታማኝ ከሆኑ የአሜሪካ ዜጎች መካከል ናቸው ብንል አጋነናችሁ አንባልም።››[140] ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደሞከርነው እስራኤልን ወክለው ሎቢ የሚያደርጉ ቡድኖችና ድርጅቶች ለረዥም ጊዜ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው የዲሞክራሲ ባህል በመጠለል ነው ይህን ፍላጎታቸውን እውን ለማድረግ የሚሰሩት።

እውነቱን ለመናገር በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ሁሉም የአገሪቱ ዜጎች ማለት ይቻላል በአንድ ወይም በሌላው መልኩ ከሌላ አገር፣ ሃይማኖት፣ ጎሳ፣ ቤተሰብ፣ አሰሪ ወዘተ ጋር ቅርርብ ወይም ንክኪ አላቸው። በመደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ እነዚህን ትስስሮቻቸውን በሚያንጸባርቅ አካኋን መደራጀታቸው የተለመደ ነው። ለምሳሌ በ2006 በግሎባል አቲቲዬድ ሰርቬይ አማካይነት የአስራ ሶስት አገራት ክርስቲያኖችን አመለካከት ለመፈተሽ በተደረገ ጥናት 42 ከመቶ የሚሆኑት አሜሪካውያን ራሳቸውን በመጀመሪያ አንደ ክርስቲያን እንደሚቆጥሩና ቀጥለው ደግሞ አሜሪካዊ መሆናቸውን እንደሚያምኑ ገልጸዋል።[141] እንዲህ ዓይነቱ ቅርርቦሽ አንዳንድ ጊዜ ከውጭ አገር፣ ከዘር፣ ከሃይማኖት ከግል ተሞክሮ ወዘተ ጋር ሊያያዝ ቢችል አያስደንቅም። የአሜሪካ ዜጎች በፖለቲካዊ ሕይወታቸው ይህን የመሰለውን ቁርኝት ወይም ቅርርብ የመመስረት ህጋዊ መብት አላቸው። ቀደም ብለን እንደገለጽነው የአሜሪካ ዜጎች ጥምር ዜግነት የመያዝና በሁለተኛ አገር ሠራዊት ውስጥ (የእስራኤልን የመከላከያ

ሠራዊት ጨምሮ) የማገልገል መብት ያላቸው ሲሆን ያን መብታቸውንም ብዙ እስራኤላውያን እየተጠቀሙበት ይገኛሉ።

የአሜሪካን የውጭ ፖሊሲ እስራኤልን በሚጠቅማት መልኩ ለማራማድ ሎቢ (ተጽዕኖ) የሚያደርጉ አይሁድ አሜሪካውያን ሁልጊዜም ቢሆን እነርሱ የሚደግፉት ፖሊሲ አሜሪካን ራሷንም እንደሚጠቅማት ነው የሚያምኑት። የቀድሞው የኤ.አይ.ፒ.ኤ.ሲ (አይፓክ) ዳይሬክተር ቶም ዳይን በአንድ ወቅት ቃለ መጠይቅ ላደረገላቸው ጋዜጠኛ ሲናገሩ እንዲህ ብለው ነበር፡- ‹‹የአሜሪካን ፖለቲካዊ አቋም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማጠናከር እሻለሁ። በተመሳሳይ ጊዜም ስለ እስራኤል ብዙ እጨነቃለሁ። ምክንያቱም እኔ አይሁዳዊ ነኝና።››[142] ወደ እውነታው ይበልጥ ለመጠጋት የቀድሞው የፕሬዝዳንቶች ኮንፈረንስ ዳይሬክተር ቲዎዶር ማንን አባባል መጥቀሱ ተገቢ ነው። በ2001 እንደሚከተለው ብለው ነበር፡- ‹‹ለአሜሪካ አይሁዶች የአሜሪካ ፍላጎትና የእስራኤል ፍላጎት አንድና ተመሳሳይ መሆናቸውን በጥልቀት እንዲሰማቸው ማድረግ ያስፈልጋል።››[143]

እንዲህም ሲባል ይህን መሳዩ አመለካከት በሰፊው ተቀባይነት ማግኘቱ ጥያቄ ባይነሳበትም ቅሉ በውስጡ ችግሮች አሉበት። ምክንያቱም ሁልጊዜም ቢሆን ሁለት የተለያዩ ሃገሮች አንድና ተመሳሳይ ፍላጎት ሊኖራቸው አይችልምና። ዓለም አቀፍ ፖለቲካም የሚራመደው በእንደዚህ ዓይነት መልኩ አይደለም። ባለፉት ጊዜያት የእስራኤልና የአሜሪካ ፍላጎቶች ተቃርኖ እንደታየባቸው ሁሉ ለወደፊቱም እንደዚያው ተቃርኖ ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ግልጽ ነው። ለምሳሌ በ1960ዎቹ እስራኤል የኑክሊዬር መሳሪያ መታጠቋን እንደ ዓይነተኛ ስትራቴጂ ግብ ትመለከተው የነበረ ሲሆን በአሜሪካ በኩል ደግሞ እስራኤል የኑክሊዮ ቃታ መጨበጧን ፈጽሞ አትደግፍም ነበር። እስራኤል ሰላማዊ ፍልስጤማውያንን መግደሏ ከዩ ኤስ. አሜሪካ ፍላጎት ተጻራሪ የሆነ ድርጊት ነው። በተለይም ደግሞ የሚገድሉበት መሳሪያ አሜሪካ ሰራሽና ለእስራኤል የጦር ኃይል በእርዳታ የተሰጠ መሆኑ ሲጨመርበት ሁኔታውን የበለጠ ያጣዝዋል። ሌላው ደግሞ እስራኤል በ1982 ሊባኖስን የወረረችበት ክስተት ሲሆን ድርጊቱን አሜሪካ ተቃውማው ነበር። በእስራኤል በኩልም ቢሆን አሜሪካ ለሳዑዲ አረቢያና

ለሌሎች የባህረ ሰላጤው አገራት የተራቀቁ የውጊያ መሳሪያዎችን መሸጧን ተቃውማለች።[144]

የሆነ ሆኖ ብዙዎቹ የእስራኤል ደጋፊዎች በቴሌአቪቭና በዋሽንግተን መካከል መሠረታዊ የሆነ የፍላጎቶች ተቃርኖ መኖሩን ማመን አይፈልጉም። በሌላ አገላለጽ በምዕራፍ ሁለትና ሶስት ላይ ማስተባባያ የሰጠንባቸውን ስትራቴጂያዊና ሞራላዊ ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ ይቀበላሉ ማለት ሲሆን የፖሊሲ አውጭዎችንም በዚያው መስመር እንዲጓዙ ለማሳመን ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋሉ። አይሁዳውያኑ ይህንን አመለካከታቸውን የሙጥኝ ብለው እንዲይዙ የሚያደርጋቸው ሌላው ምክንያት የሰው ልጆች ስንባል ብዙውን ጊዜ ዋና ዋና የሚባሉ እሴቶቻችንን በተመለከተ ተቃርኖ ሲገጥመን ምኞት ስለማይሰማን ነው። ሌላው ቀርቶ በዩናይትድ ስቴትስና በእስራኤል ፍላጎቶች መካከል ግልጽ የሆነ ግጭት ሲኖር ጥቂት የማይባሉ የእስራኤልና አሜሪካ ግንኙነት ደጋፊዎች የተወሰነ መሳከር እንደሚኖር እንኳ ማመን አይፈልጉም።

ይሁን እንጂ ፖሊሲ አውጪዎችን ጨምሮ አስተዋይ የሆኑ አይሁድ አሜሪካውያን በአይሁዳዊ ማንነታቸው፤ ለእስራኤል ደህንነት ባላቸው ፍላጎትና ለዩናይትድ ስቴትስ ባላቸው እውነተኛ ታማኝነት ላይ ውስጣዊ ተቃርኖዎች አጋጥመዋቸው እንደሚያውቁና ወደፊትም እንደሚያጋጥሟቸው በግልጽ ያምናሉ። ከእንዲህ ዓይነት ግልጽ ሰዎች መካከል የቀድሞው የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሄነሪ ኪሲንጀር አንዱ ሲሆኑ በማስታወሻቸው ላይ ያለምንም መሸፋፈን የሚከተለውን ከተበዋል፦ ‹‹ምንም እንኳን ሃይማኖቴን ባልተገብርም አስራ ሶስት የሚሆኑ የቤተሰቤ አባላት በናዚ ማጎሪያ ካምፖች ውስጥ ማለፋቸውን ፈጽሞ አልረሳውም። ..ብዙ የእስራኤል መሪዎችም የግል ጓደኞቼ ናቸው። እንደዚያም ሆኖ ልባዊ ምርጫዬንና ፍላጎቴን ለብሔራዊ (ለአሜሪካ ማለታቸው ነው) ጥቅም ማስገዛቱ ሁልጊዜም ቀላል ሆኖልኝ አያውቅም። አንዳንዴ እንዲያውም ስቃይ ያስከትልብኛል።››[145]

ኪሲንጀር ብዙዎች የሚያስተባብሉትን ጉዳይ ማመኑ ተሳክቶላቸዋል። ምንጊዜም ቢሆን አሜሪካውያን ከሌላ አገር ጋር ትስስር ያላቸው ከሆነ ውጥረት መንገሱ የማይቀር ሲሆን ይህ ትስስር ከወዴትም ይምጣ እንዲሁም የቱንም ያህል በአሜሪካዊነታቸው ላይ ጽናት ይኑራቸው በአንድ ወቅት ለትውልድ አገራቸው የተወሰነ አድልዎ ለማድረግ መወሰናቸው አይቀርም። በቢል ክሊንተን ጊዜ የመካከለኛው ምሥራቅ አማካሪ የነበሩና ስማቸው እንዲገለጽ ያልፈለጉ አንድ ዲፕሎማት ‹‹የአሜሪካን ፍላጎት ለማስከበር እንንቀሳቀሳለን። ሆኖም ግን አንዳንዴ በአጣብቂኝ ውስጥ ማለፍ ነበርብን›› ብለዋል። የቀድሞ ዘማች የነበሩ ሌላ አይሁድ አሜሪካዊ ዲፕሎማትም ተመሳሳይ የሆነ ስሜታቸውን ሲገልጹ ‹‹በመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ ወይም በተ.መ.ድ.ውስጥ ገብቼ ያልሰራሁ በመሆኔ ፈጣሪዮን አመሰግነዋለሁ። እዚያ ብሰራ ኖሮ ምናልባትም እስራኤልን ለማውገዝ ድምጼን መስጠት ይጠበቅብኝ ይሆናል።››[146] በማለት ሃቁን ሳያድበሰብሱ ተናግረዋል።

እነዚህ አባባሎች ታማኝ ያለመሆንን ሃጢአት የሚገልጹ ኑዛዜዎች አይደሉም። ከዚህ በተቃራኒ በሚደንቅ ሁኔታ ታማኝነታቸውን ከአንድ በላይ ለሆኑ አገራት ያደረጉ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ የሚሰማቸውን የሕሊና ፍጭት የገለጹበት መንገድ ነው። ጋዜጠኛው ኤሪክ አልተርማን በተመሳሳይ ሁኔታ በ2003 ቅንነት በተሞላበት ሁኔታ የጥምር ታማኝነት (dual loyality) ስሜት በስብዕናው ውስጥ እንዴት እንደገባ ሲገልጽ ‹‹ይህ ጉዳይ ወደ ውስጥ የገባው በወላጆቼ፣ በአያቶቼ፣ በእብራይስጥ ቋንቋ መምህራኖቼና በመንፈሳዊ የሃይማኖት አባቶች (ራቢዎች) አማካይነት ነው። የእስራኤልንና የአይፓክ መሪዎችን ስም መጥቀስ አልሻም›› ብሏል። ‹‹ሁላችንም ብንሆን ታማኝ መሆን አለብን። የሆነ ወቅት ላይ በአሜሪካና በእስራኤል ፍላጎቶች መካከል ግጭቶች መነሳታቸው አይቀርም። ከእንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎች በአንዱ ለእስራኤል የተሻለ ወደሆነው አማራጭ ማዘንበሌን አልክድም››[147] በማለትም ተናግሯል።

አልተርማን ሃቅ በመናገር ብቸኛው ሰው አይደለም። በአሜሪካ አይሁዳውያን ኮሚቴ ጉዳይ ዳይሬክተር የነበሩት ስቴፈን ስቴይንላይት እንደ አንድ

አይሁዳዊ በአሜሪካ የነበራቸውን አስተዳደግ ከዘረዘሩ በኋላ የሚከተለውን ብለዋል፡-

‹‹በብሄራዊ ደረጃ ከተሰጠኝ ስልጠና በዓለም ውስጥ ያለው መሠረታዊ ክፍፍል ‹በእኛና በእነርሱ መካከል ነው› የሚለውን ሃሳብ አስርጾብኛል፡፡ እርግጥ ነው ለአሜሪካም ሆነ ለካናዳ ባንዲራዎች ሰላምታ እናቀርብ ነበር፡፡ ከልባችንም ብሔራዊ መዝሙሮቻቸውን እንዘምር ነበር፡፡ ግና የመጀመሪያው ታማኝነታችን ለትውልድ አገራችን መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በየጊዜው ለሚነሱ ውጥረቶች የምንሰጣቸው የተለመዱ ምላሾች፡- "አሜሪካና እስራኤል ዲሞክራሲያዊ የሆኑ ሃገራት ሲሆኑ የተለያዩ እሴቶችንም ይጋራሉ፡፡ እንዲሁም የጋራ የሆኑ ስትራቴጂያዊ ፍላጎቶች አሏቸው፡፡ ስለሆነም ለአንደኛው ወገን ታማኝ መሆን ማለት ለሌላው ወገን ክህደት ማሳየት አይደለም" ...ወዘተ... የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ ግን ትልልቅ ጥይቄዎችን ማስነሳታቸው አልቀረም፡፡ በእርግጥ የተሟላ ነገር መጠበቅ ተገቢ አይደለም፡፡ የቡድንን ታማኝነት እና ሰፋ ባለ መንፈስ ለአሜሪካ የሚኖረንን ታማኝነት ሚዛን የመጠበቅ ችግር የለብንም፡፡ አሜሪካ ይህን ጥምር ታማኝነት በትልቁ ነው የምትታገሰው፡፡ ስለሆነም እንደልባችን ሆነን ኖረናል፡፡ እኔ በሆሎኮስት እልቂት ክርስቲያኖች ተጠያቂ በመደረጋቸው ላይ ጥራጣሬ ቢኖረኝም ነገሩ የመፈጸሙን እውነታ ግን አይቀይረውም፡፡››[148]

እንዲህ የመሰለውን የጥምር ታማኝነት ችግር በአይሁድ አማሪካውያን ብቻ የሚታይ ችግር አድርጎ መመልከት ተገቢ አለመሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ይህ ውጥረት በሁሉም የዓለም ክፍል አንድ ላይ ተቀላቅለው በሚኖሩ ሕዝቦች ዘንድ መከሰቱ አይቀሬ ነው፡፡[149] ከዚህ ጋር ሳይነሳ የማይታለፈውና ብዙ አሜሪካውያን አይሁዶች የማይቀበሉት ሌላው ሃሳብ ‹‹የአሜሪካ አይሁዶች በአሜሪካና እስራኤል ፍላጎቶች መካከል ግልጽ የሆነ ግጭት (ተቃርኖ) ቢነሳ ከአሜሪካ ፍላጎት ይልቅ የእስራኤልን ፍላጎት ያስቀድማሉ›› የሚለውን አባባል ነው፡፡

አይሁዳውያንም ሆኑ አይሁድ ያልሆኑ ሰዎች አሜሪካ ለእስራኤል ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ ያልተከለበት እርዳታ መስጠቷን እንድትቀጥል

የሚደግፉ መሆናቸው ለአሜሪካ ታማኝ በመሆናቸው ላይ ጥያቄ ሊያስነሳ አይገባም፡፡ ሆኖም ግን አይፓክን የመሰሉት ድርጅቶች ወይም ኤ.ዲ.ኤልን፣ ወይም የፕሬዝዳንቶች ኮንፈረንስንም ሆነ ሌላ ድርጅትን የሚመሩ ግለሰቦች የሚንቀሳቀሱት ከእስራኤል ጋር ባላቸው ቁርኝነት ነው፡፡ ስለሆነም ማንኛውንም የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የሚቃኙት ከዚሁ ዓላማቸው ጋር በማነጻጸር ነው የሚል ትችት የሚሰነዝሩ ሰዎች በሌላ በኩል ተቀባይነት አላቸው፡፡ እንደዚያማ ባይሆን ኖሮ ማልኮለም ሆኔሊን ስለ ስራቸው ሲናገሩ፡- ‹‹እኔ ራሴን አሳልፌ የሰጠሁት የአይሁዳዊቷን አገር ጸጥታ ለማስከበር ነው››[150] ለማለት ባልበቁ ነበር፡፡ የክርስቲያን ዩኒዮን ፎር ኢስራኤል (ሲ.ዩ.ኤፍ.አይ) ፕሬዝዳንት ጆን ሃጊም በኃይል በተያዙት ግዛቶች ሰፈራ እንዲስፋፋ በያዘው አቋምና የዩናይትድ ስቴትስ ባለስልጣናት ይህን አቋሙን በመቃወማቸው ምክንያት ‹‹የአምላክ ሕግ ከአሜሪካ መንግስት ወይም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሕግ ይበልጣል›› በማለት ባልተናገረ ነበር፡፡[151]

የቀድሞው የአይፓክ የመረጃና ምርምር ዳይሬክተር ከእስራኤል ጋር ጥብቅ የሆነ ትስስር ባይኖራቸው ኖሮ ከ1997-2000 ባሉት ዘመናት በዋሽንግተን የእስራኤል ምክትል አምባሳደር ሆነው ለማገልገል አይፈቅዱም ነበር[152]

በእነዚህ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የሚደገፉ ፖሊሲዎች የዩ.ኤስ.አሜሪካን ፍላጎት የሚወክሉ መሆንና አለመሆናቸውን መጠየቅ ሕጋዊ እንደሆነው ሁሉ በሌሎች የአገር ውስጥና የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዎች ላይ ሎቢ የሚያደርጉ ግለሰቦችና ቡድኖች የሚያሳድሩትን ተጽዕኖም እንዲሁ ማጠያየቅ ህጋዊ ነው፡፡ የአገር ፍቅር ስሜታቸው ሞልቶ ሊፈስ ይችል ይሆናል፡፡ ይሁንና የሚያቀርቧቸው ሐሳቦችና የሚሰጧቸው ምክሮች ለዩናይትድ ስቴትስና ለቀሪው ዓለም ስትራቴጂያዊ ጥቅም በሚያስገኙ ክልሎች ላይ ጥፋትና ውድመት የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ እነዚህ አካላት የሚሰጧቸውን ምክሮች ጥሩነት ማጠያየቁ ባረጀውና በአይሁዳውያን ላይ በሚነሳው የጥምር ታማኝነት (dual loyality) ችግር ምክንያት አይሁዳውያን የአርበኝነት መንፈስ ይጎድላቸዋል ከመባሉ ጋር የሚያያይዘው ነገር የለም፡፡

ምዕራፍ-አምስት

የፖሊሲውን ሂደት አቅጣጫ መተለም

ሎቢውን ተቀናጅተው የሚያራምዱት ቡድኖችና ግለሰቦች ዩናይትድ ስቴትስ በዘላቂነት እስራኤልን እንድትረዳ ለማድረግ ሁለት ዓይነት ስትራቴጂዎችን ይከተላሉ። የመጀመሪያው በዋሽንግተን ያለውን ፖሊሲ አውጭ አካል በመጫን የፖሊሲ አወጣጡ ሂደት ለእስራኤል በሚበጅ መልኩ እንዲሆን ማድረግ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ እስራኤልን የሚመለከቱ ውይይቶችም ሆኑ አስተያየቶች ሁሉ በምዕራፍ 2እና3 ላይ በስፋት ያየናቸውን የሞራል መሰረታዊ ምክንያቶች የሚያንጸባርቁ እንዲሆኑ በመጣር ነው። የመጀመሪያውን ስትራቴጂያቸውን በዚህ ምዕራፍ የምናየው ሲሆን ሁለተኛውን ደግሞ በምዕራፍ 6 እንመለከተዋለን።

የዩናይትድ ስቴትስ የፖለቲካ ጉልበት በህግ አውጭውና አስፈጻሚው የተከፋፈለ እንደመሆኑ የሎቢውም ታክቲክ እንደየሁኔታው ሚዛኑ ይበልጥ ወዳጋደለበት ክፍል የማዘንበል ባሕሪ ይታይበታል። በዚህም የተነሳ በሎቢው ውስጥ ያሉ ቡድኖች አፍቃሪ-እስራኤል ወይም ቢያንስ ደጋፊ የሆኑ ሰዎችን ለምክር ቤት (congress) እና ሴኔት አባልነት ከማስመረጥና ከተመረጡም በኋላ ቁልፍ ቦታ እንዲይዙ ከማድረግ ጀምሮ በራሳቸው አካሄድ ለመጓዝ ለሚፈልጉ የመንግሥት ኃላፊዎችም የፖለቲካ ስሌታቸው ምን መምሰል እንዳለበት ቀርጸው እስከመስጠት ርቀው ይሄዳሉ። የህግ አውጭው ወይም የፖሊሲ ቀራጩ ፖለቲከኛ ግላዊ አስተያየት ምንም ይምሰል ምን እስራኤልን የማይነቅፍና ሙሉ ድጋፉን የሚቸር እንዲሆን ነው ሎቢው የሚፈልገው። ልክ እንደ ሌሎች በራስ አነሳሽነት የተደራጁ ቡድኖች ሁሉ የእስራኤል ሎቢ ዓላማውን የሚያራምደው ዋና ዋና የሚባሉትን የፖሊሲ አውጭዎች በመጫንና የእርሱን የፖለቲካ ቀመር እንዲያስፈጽሙ በማስገደድ ሲሆን የዩናይትስ ስቴትስ መሪዎችም ሎቢው የሚቃወመውን አጀንዳ ለማስፈጸም ግፊት ማድረግ እንዳይችሉ፣ ካደረጉም በምክር ቤት አባላት እንዲታፈኑ የሚያስችል የፖለቲካ ስሌት በመንደፍ ነው።[1]

ካፒቶል ሂልን በተጽዕኖ መወዝወዝ

የሎቢው ስኬት ከሚገልጽባቸው ቁልፍ ጉዳዮች ዋነኛው በዩ.ኤስ. ኮንግረስ (ካፒቶል ሂል) ውስጥ ያለው ተጽዕኖ ነው። ከሌሎች አገሮች በተለየ ሁኔታ እስራኤል በካፒቶል ሂል ከማንኛውም ዓይነት ነቀፋና ትችት ነፃ የሆነች ብቸኛ አገር ነች። ይህ ክስተት በራሱ አስደናቂ ነው። ምክንያቱም ኮንግረሱ የተለያዩ ጉዳዮችን አስመልክቶ ተከታታይ በሆኑ ውይይቶችና ክርክሮች ተጠምዶ ጊዜውን የሚያጠፋ መሆኑ ይታወቃል። ለምሳሌ ውርጃን፣ የጦር መሳሪያ ቅነሳን፣ የግብረ ሰዶማውያንን መብት፣ የአካባቢ ጥበቃን፣ የንግድ ፖሊሲዎችን፣ የስደተኞችን ጉዳይ ወይም የደህንነት አጀንዳን በተመከለተ ሕይወት ያለውና የሞቀ ክርክር በካፒቶል ሂል ይደረጋል። ሆኖም ግን እስራኤልን በተመለከተ ከባድ የሆኑ ተከራካሪዎችና ተጽዕኖ ፈጣሪ ፖለቲከኞች ሳይቀሩ ጸጥ ማለቱን ነው የሚመርጡት። ስለሆነም ይኽ ነው የሚባል ክርክር ይቅርና ለውይይት የሚበቃ ነገር ሳይነሳ ነው የሚታለፈው።

እስራኤልን በተመለከተ በአሜሪካ ምክር ቤቶች ውስጥ ተገቢ የሆነ ውይይት እንደማይካሄድ በግልጽ የታየው በየካቲት 14/2007 የመካከለኛው ምሥራቅና ደቡብ ኢሲያ ንዑስ ኮሚቴ የእስራኤል-ፍልስጤማውያንን የሰላም ሂደት የተመለከተ በተወካዮች ምክር ቤት ለውይይት የሚሆን ሃሳብ ባቀረበ ጊዜ ነበር። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮንዶሊሳ ራይስ የተቋረጠውን የመካከለኛውን ምሥራቅ የሰላም ሂደት ለማስጀመር ሲሞክሩ ንዑስ ኮሚቴው የሶስት ሰዎችን የምሥክርነት ቃል እንዲያዳምጥ ተደርጎ ነበር። በተወሰኑ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ካላቸው ልዩነት በስተቀር ሶስቱም በሎቢው ውስጥ ዋነኛ ተዋናይ የሆኑ ሰዎች መሆናቸው ነበር ምስክርነታቸውን አስደናቂ ያደረገው። ማርቲን ኢንዲክን ብንወስድ ቀድሞ የአይፓክ ባለስልጣንና በእስራኤልም የዩ.ኤስ አሜካሪ አምባሳደር የነበረ ሲሆን አሁን ደግሞ ሳባን ሴንተር ፎር ሚድል ኢስት ፖሊሲ የተባለውንና በብሩኪንግ ኢኒስቲትዩሽን የሚገኘውን ድርጅት የሚመራ ሰው ነው። ሁለተኛው ምስክር አፍቃሪ-እስራኤል የሆነውን ዋሽንግተን ኢኒስቲትዩት ፎር ኒር ኢስት ፖሊሲ WINEP የተባለውን ድርጅት የሚያንቀሳቀሰው ዴቪድ ማኮቭስኪ

ነው። ሶስተኛው ምስክር ደግሞ የኒዎኮንሰርቫቲቭ ፖለቲካ ዘይቤ አቀንቃኙና ዘ ራይት ዊንግ ሚድል ኢስት ፎረም የተባለውን ድርጅት የሚመራው ዳንኤል ፓይፕ ነው። በዚያ የውይይት መድረክ በእስራኤል ላይ ሂስ የሰነዘረም ሆነ ወቀሳ ያሰማ አንድም ሰው ያልነበረ ሲሆን አንድም ፍልስጤማዊ ወይም አረብ አሜሪካዊ አማራጭ ሃሳብ እንዲያቀርብ አልተጋበዘም። ኤ.ም.ጂ ሮዝንበርግ የተባሉት በአንድ ወቅት በአይፓክ ውስጥ የሰሩና አሁን ደግሞ እስራኤል ፖሊሲ ፎረም በተባለውና መካከለኛ አቋም በማራመድ የሁለት መንግስታትን የመፍትሄ ሃሳብ በጽናት በሚደገፈው ድርጅት ውስጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ ሰው ሁኔታውን ከታዘቡ በኋላ እንዲህ በማለት አጠቃልለውታል፡- ‹‹ያ መድረክ የሁለቱን በግጭት ላይ ያሉ ኃይሎች ሁኔታ ሊያደምጥ የተቀመጠ ሆኖ እያለ አንደኛው ወገን ብቻ እንዲናገር የተፈቀደበት መድረክ ነበር። በኮንግረሱ ውስጥ የሁለቱን ተፋላሚ ቡድኖች ሁኔታ ለማድመጥ የተሰየመ መንግስታዊ አካል የአረቦችን አስተያት የማይቀበል ከሆነ አንድም በመጥፎ የፖለቲካ መነጽር የተጋረደ ነው አሊያም ደግሞ ወደ አንድ ጎን ያደላና ውስጡ በጥላቻ የተሞላ አካል ነው። ይህ ደግሞ የአሜሪካንም ሆነ እስራኤልን ፍላጎት አያስከብርም።››[2]

ሎቢው በኮንግረስ ውስጥ ስኬት እንዲያገኝ ያገዘው ሌላው ምክንያት ደግሞ ቁልፍ የሆኑት አባላቱ ክርስቲያን ጽዮናዊያን መሆናቸው ነው። ከእነዚህ ሰዎች አንዱ የቀድሞው የምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ሪቻርድ አርሚ ሲሆኑ መስከረም 2002 ላይ እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል፡- ‹‹በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ቁጥር አንድ ትኩረቱ እስራኤልን መከላከል ነው።›› እስቲ አስቡት ይህን አባባል! አንድ የአሜሪካ ምክር ቤት አባል ዋነኛውና ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ‹‹አሜሪካን ከጠላት መከላከል ነው›› ብሎ ቢናገር አያስደንቅ ይሆናል። ሆኖም ግን ሪቻርድ አርሚ እንዲያ ብለው አልተናገሩም። አርሚን የተካቸውን ቶም ዴላይን አስመልክተው የአሜሪካ ጽዮናውያን ድርጅት (ዜድ.ኦ.ኤ) ፕሬዝዳንት የሆኑት ሞሮቶን ክሌይን ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹በሕይወት እንቅስቀሴው ሁሉ ለእስራኤል ይጨነቃል።›› ዴላይ ራሳቸው ‹‹እኔ በውስጤ (በልቤ) እስራኤላዊ ነኝ›› ብለዋል።[3]

የዩ. ኤስ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የእስራኤልን ፍላጎት እንዲደግፍ የሚታገሉ አይሁዳውያን ሴናተሮችና የተወካዮች ምክር ቤት አባላትም ነበሩ፡፡ ከሁሉም ዓመታት በተለየ ሁኔታ በ2006 ብዙ አይሁድ አሜሪካውያን ለህግ አውጭው (house) እና ለሴኔቱ ተመርጠዋል፡፡ ይህም የአሜሪካ አይሁዶች በአሜሪካ ማህበረሰብ ውስጥ የተቀዳጁትን ትኩረት የሳበ ስኬት እንዲሁም በዲሞክራሲያዊ ባህል ውስጥ ያላቸውን ቦታና የፖለቲካ ተሳትፎ ያሳያል፡፡[4] ከእነዚህ ህግ አውጭዎች መካከል የኬንታኪዎቹ ዲሞክራት ሴናተሮች ጆሴፍ ሊበርማንና ቻርለስ ስኩመር እንዲሁም የኒውዮርኩ ዲሞክራት የተወካዮች ምክር ቤት አባል ጆሮልድ ናድለር፣ የካንሳሱ የዲሞክራቲክ ፓርቲ ተወካይ ሄነሪ ዋክስማንና የፊላደልፊያው ዲሞክራት ሮበርት ዊክስለር ዋነኞቹ አይሁድ የእስራኤል ደጋፊዎች ናቸው፡፡[5] በ2006 የምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ዋክስማን እንዲህ አሉ፡- ‹‹አንዳንድ የዲሞክራቲክ ፓርቲ መሪዎች እስራኤልን በተመለከተ የሚኖረኝን ሁሉንም ሃሳብ አይደግፉት ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ እስራኤልንና የመካከለኛውን ምስራቅ ጉዳይ የሚመለከቱ ኮሚቴዎች በእርግጠኝነት አይኖሩም ወይም ቢኖሩም ተግባራቸውን በሚገባ አያከናውኑም››[6] ዋክስማን ልክ ነበሩ፡፡ ምክንያቱም እርሳቸው የጠቀሱትን ጉዳይ የሚመለከተው ንኡስ ኮሚቴ ሊቀመንበር ሆነው የተመረጡት የኒውዮርኩ ዲሞክራትና ብርቱ የሆኑት የእስራኤል ደጋፊ ጋሪ አከርማን ነበሩ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የውጭ ጉዳይን የሚመለከተው ትልቁ ኮሚቴ ሊቀመንበር የካንሳሱ ዲመክራት ቶም ላንቶስ ሲሆኑ ለእስራኤል ባላቸው ታማኝነት በካፒቶል ሂል ተወዳዳሪ አልነበራቸውም፡፡ አንድ የቀድሞ አይፓክ መሪ ላንቶስን ሲገልጿቸው ‹‹እውነተኛው ታማኛችን›› ብለዋቸዋል፡፡[7]

በኮንግረስ ውስጥ የሚረቀቀው ሕግ እስራኤልን እንዲጠቅም ለማድረግ የሚሞክሩት የህዝብ ተወካዮቹ የኮንግረስ አባላትና ሴናተሮች ብቻ ሳይሆኑ የኮንግረሱ ሌሎች አባሎችም ጭምር ናቸው ውጪ ያሉትን አፍቃሪ እስራኤል ቡድኖች ፍላጎት ለማርካት ላይና ታች ሲሉ የሚታዩት፡፡ የቀድሞው የአይፓክ ፕሬዝዳንት ሞሪስ አሚቲ አንድ ጊዜ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹በዚህ በካፒቶል ህንፃ ውስጥ አይሁዳውያን የሆኑና ነገሮችን በአይሁዳዊነት

መነጽር የሚመለከቱ ሰዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች፣ እዚህ ውስጥ ያሉ ሴናተሮች ለሚያሳልፏቸው ውሳኔዎች አመቺ የሆኑ የመረጃ ግብዓቶችን ያቀርባሉ፡፡ ጉዳዮች በዚህ ዓይነት መንፈስ ይከናወናሉ››[8]

ሎቢ ከሚያደርጉ ቡድኖች ሁሉ ኮንግረስ ውስጥ ባሉ የሁለቱም ፓርቲ ፖለቲከኞች ዘንድ በሚገባ የተመሰከረለት ተጽእኖ ፈጣሪ አይፓክ ነው፡፡[9] ቢል ክሊንተን በአንድ ወቅት አይፓክን አስመልክተው ሲናገሩ ‹‹በሚያስደንቅና በሚመስጥ ሁኔታ ውጤታማ ነው›› ብለውታል፡፡ የቀድሞው የምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ኒወት ጊንግሪች ደግሞ ‹‹በመላው ፕላኔት ከሚገኙ በፍላጎት የተሰባሰቡ ቡድኖች ሁሉ እጅግ የተዋጣለት›› በማለት ያሞካሹት ሲሆን የኔቫዳው ዲሞክራቲክ ፓርቲ የብዙሃን መሪ ሃሪ ሬይድ በበኩላቸው ‹‹ብዚህች አገር እንደ አይፓክ በሚገባ የተደKጃና ክብር የሚሰጠው የፖሊሲ ቡድን አለ ብዬ አላስብም›› ብለዋል፡፡ የኒውዮርክር ጋዜጣ ባልደረባ የሆነው ጀፍሪ ጎልድበርግ አይፓክን ‹‹ሎቢ ከሚያደርጉ ቡድኖች ሁሉ እጅግ በጣም ትልቁና አስፈሪው›› በማለት የጠራው ሲሆን የአይፓክ ድረ-ገጽ ስለ ራሱ ስለ አይፓክ ኒውዮርክ ታይምስ የዘገበውን ጠቅሶ የሚከተለውን አውጥቷል፡- ‹‹አይፓክ በአሜሪካና በእስራኤል ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር እጅግ በጣም ጠቃሚው ድርጅት ነው፡፡ ››[10]

የአይፓክ ስኬት በአብዛኛው የተገነባው እርሱን የሚደግፉት የህግ አውጭዎችና ለኮንግረስ አባልነት የሚወዳደሩ ሰዎች ላደረጉት አስተዋጽኦ ዋጋ ለመክፈልና የተቃወሙትን ደግሞ ለመቅጣት ባለው ችሎታ ላይ ነው፡፡ ይህም ማበረታቻና ቅጣት ለምርጫ ማካሄጃ በሚከፈል መዋጮ በተግባር ይገለጻል፡፡ እንደሚታወቀው በዩናይትድ ስቴትስ የምርጫ ስርኣት አንድ ሰው አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት እጅግ ብዙ ገንዘብ ያስፈልገዋል፡፡ ስለሆነም አይፓክ ሁልጊዜም አጽንኦት ሰጥቶ የሚያረጋግጠው ፖለቲከኞች የእርሱ ወዳጆች የሆኑና ከእርሱ መመሪያ የማያፈነግጡ ሆነው እስከተገኙ ድረስ በቂ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ ሚያሰጣቸው መሆኑን ነው፡፡

ይህ የገንዘብ ድጎማ የሚከናወነው በብዙ መልኩ ነው። በመጀመሪያ አይፓክን በገንዘብ የሚረዱ ግለሰቦች በራሳቸው ፍላጎት መዋጮአቸውን ይፈጽማሉ። የፌደራሉን የምርጫ ኮሚሽን መረጃ ተንተርሶ ሚካኤል ማሲንግ ባጠናቀረው ዘገባ መሠረት ከ1997-2000 ባለው ጊዜ የአይፓክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሆኑ 46 ግለሰቦች ከ3 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚሆን የምርጫ ማስፈጸሚያ ገንዘብ አዋጥተዋል። ከእነዚህ ግለሰቦች አብዛኞዎቹ ዛሬም ድረስ አፍቃሪ እስራኤል ለሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ችሮታ የሚለግሱ ናቸው።" ዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ ባወጣው ዘገባ መሰረት ከ2004 ጀምሮ እያንዳንዱ የቦርድ አባል በአማካይ 72.000 ዶላር የሚሆን ገንዘብ ለምርጫና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ለሚያደርጉ ኮሚቴዎች እያወጣ ይገኛል።[12]

በሁለተኛ ደረጃ አይፓክ የፖለቲካ ተወዳዳሪዎችን ከሌሎች ረጂዎችና የገንዘብ ምንጮች ጋር ያገናኛቸዋል። አይፓክ የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደርግ ድርጅት ባለመሆኑ ተወዳዳሪዎችን በይፋ መደገፍም ሆነ በቀጥታ ለምርጫ ማካሄጂያ ገንዘብ መለገስ አይችልም። ከዚያ ይልቅ የፖለቲካ ተወዳዳሪዎችን ማንነት ካጣራ በኋላ በገንዘብ ሊረዷቸው ከሚችሉ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ጋር የማገናኘትና በየጊዜው ቁጥራቸው እያደገ ለሚሄዱ የፖለቲካ ተሳትፎ አድራጊ ድርጅቶች መረጃዎችን የመስጠት ሚና ነው የሚጫወተው። የታሪክ ምሁሩ ዴቪድ ቢያለ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹የአሜሪካ አይሁዳውያን ሎቢ ከስድስቱ ቀን ጦርነት ጀምሮ እያደገ የመጣ፣ በዩናይትድ ስቴትስ ኮንገረስ ውስጥ ከፍተኛ ተደማጭነት ያገኘና እጅግ የተወሳሰበ የእርስ በርስ ግንኙነት ያለው አካል ነው። ሥራውን የሚያከናውነው በብሔራዊ ደረጃ በዘረጋው መገናኛ መረብ ባስተሳሰራቸው የተለያዩ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ቡድኖች አማካይነት ሲሆን እስራኤልን ለመርዳት በወጣው መስፈርት መሠረት መንገዝ ለሚፈልጉ የኮንግረስ ተወዳዳሪዎች ገንዘብ ያሰባስባል።[13] የአይፓክ ፕሬዚዳንት የሆኑት ሃዋርድ ፍሪድማን በነሃሴ 2006 ለድርጅቱ አባላት የሚከተለውን ተናግረው ነበር፡- ‹‹አይፓክ ለኮንግረስ አባልነት ከሚወዳደር ማንኛውም ሰው ጋር ግንኙነት ያደርጋል። ይህ ተወዳዳሪ እስራኤል በመካከለኛው ምሥራቅ ያለችበትን ሁኔታና አርሱ

ምን ተግባራትን ቢፈጽም ሊያግዛቸው እንደሚችል ጥልቅ ማብራሪያ ይሰጠዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ እያንዳንዱ ተወዳዳሪ ያለውን አቋም ግልጽ የሚያደርግበት የአቋም መግለጫ ወረቀት (position paper) እንዲያወጣና በዚያ ላይ እርሱ በዩ. ኤስ አሜሪካና እስራኤል መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ሊከተለው የሚፈልገውን የፖለቲካ አካሄድ ያለምንም መሸፋፈን በግልጽ እንዲያቀርብ ይደርጋል፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ ተወዳዳሪ ማንን ደግፎ መቆም እንዳለበት በማያሻማ ሁኔታ ያሳውቃል ማለት ነው፡፡››[14]

ፍሪድማን የገለጹት የአይፓክ ልዩ አሰራር ድርጅቱ ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች የበለጠ ጽኑ ለመሆኑ ምስክር ነው፡፡ በ1980ዎቹ ለካሊፎርኒያ ምክር ቤት አባልነት የተወዳደሩት ቶም ሃይደን የረዥም ጊዜ የካሊፎርኒያ ኮንግረስ አባል የነበሩትን የሃዋርድ በርማንን ወንድም ሚካኤል በርማንን እንዴት አንዳሸነፏቸው ሲናገሩ፡- ‹‹ሁልጊዜም የእስራኤል ወዳጅ ሆነው በመገኘታቸው መሆኑን›› ገልጸዋል፡፡ ይህን ጨምረው ሲያብራሩ፡- ‹‹አንተ ሁልጊዜም ደግመህና ደጋግመህ ልክ በጆዲይዝም እንደተፈቀደ መንፈሳዊ ምግብ ራስህን ማቅረብ አለብህ፡፡ ብቃትህን የሚያረጋግጥልህ አይሁድ ምሁራን፣ ራቢዎች እና ዋና ዋና ድርጅቶች መሪዎች ሲሆኑ ነገሩ ጠጠር ካለ (ማንነትህ አነጋጋሪ ከሆነ) በእስራኤል መንግስት ውስጥ የሚሠሩና ስላንተ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሰዎች ሁሉ ይጋበዛሉ፡፡ ይህ ማለት አስፈላጊ ከሆነ በአሜሪካ የእስራኤል አምባሳደር፣ የኢምባሲው መማክርቶችና ሌሎች ባለስልጣናትም በጉዳዩ ጣልቃ እንዲገቡና የአንተን የእስራኤል ወዳጅ መሆን እንዲያረጋግጡ ይደረጋሉ›› ብለዋል፡፡[15]

በተመሳሳይ ሁኔታ የኦሪገኑን ሪፐብሊካን ሴናተር ማርክ ሃትፊልድን ለማሸነፍ በ1990 ያልተሳካ ሙከራ ያደረጉት ሃሪ ሎንስዴል በዚያ የምርጫ ዘመቻ ወደ አይፓክ ዋና መምሪያ ሄደው ያጋጠማቸውን እንዲህ በማለት አስፍረውታል፡- ‹‹አፍቃሪ እስራኤል የመሆኔ ነገር እንዲታወቅ ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው የአይፓክ ዋና መስሪያ ቤት ተጋብዤ በመሄድ ያጋጠመኝን ነገር ምንግዜም አልረሳውም፡፡ በጊዜው አፍቃሪ እስራኤል ነኝ ማለቱ በቂ ሆኖ አልተገኘም፡፡ እናም ከዚያ በኋላ በዝርዝር የተፃፉ ሃሳቦች ቀርበውልኝ በእያንዳንዳቸው ላይ ያለኝን አቋም እንዳሳውቅ ተጠየቅኩ (ወይም በጥያቄ

ተዋከብኩ ማለቱ ይቀለኛል፡፡) እርግጥ ነው በእያንዳንዱ ጉዳይ ሊኖረኝ የሚገባውን አቋምና አቋሜንም ለሕዝብ ስገልጽ የምጠቀማቸውን ቃላት ሳይቀር እንዳጠና ተደርጓል፡፡... ከዚያ በኋላ አይፓክ ለምርጫ ማካሄጃ የገንዘብ እርዳታ የሚለግሱኝን ግለሰቦች ዝርዝር ሰጠኝ፡፡ እኔም ደወልኩላቸው፡፡ ይገርማል! ከፍሎሪዳ እስከ አላስካ የሚገኙ ሰዎች የምፈልገውን ገንዘብ ላኩልኝ››[16]

የቀድሞው የአይዳሆ ስቴት ገዥ (governer) ጆን ቪ. ኢቫንስም በ1986 የአይዳሆ ስቴት ሴናተር የነበሩትን ስቲቭን ሲምሶን ለመጣል ባደረጉት የምርጫ ዘመቻ ተመሳሳይ ታሪክ አላቸው፡፡ ኢቫንስ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹የአይፓክን ዋና ቢሮ በጎበኙሁ ጊዜ ኃላፊዎቹ እነርሱ የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደርጉ ኮሚቴዎች እንዳልሆኑና ሆኖም ግን በመላ አገሪቱ የሚያውቋቸው የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ኮሚቴዎችና ግለሰቦች እንዳሉ፣ ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ካደረጉም እንደሚረዷቸው በተደጋጋሚና በአጽንኦት ይገልጹልኝ ነበር፡፡›› ዎልስትሪት ጆርናል እንደዘገበው በዚያ ዘመቻ ምንም እንኳን ኢቫንስ ሪፓብሊካኑን ሲናተር ስቲቭ ሲምሶን ማሸነፍ ባይችሉም አይፓክ ያገናኛቸው የተለያዩ ድርጅቶች በድምሩ 204950 ዶላር ለግሰዋቸዋል፡፡[17]

አይፓክ ምን ጊዜም ቢሆን የኮንግረሱን የድምጽ አሰጣጥ ፋይል (መዝገብ) ለአባላቱ በማቅረብ ለየትኛው ተወዳዳሪ ወይም የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያደርግ ኮሚቴ ገንዘባቸውን መለገስ እንዳለባቸው እንዲወስኑ የማድረግ ልማድ አለው፡፡[18] አዳዲስ ተወዳዳሪዎች ወይም በኮንግረስ ውስጥ ያሉና በዚያው ቦታ ለመቆየት የሚፎካከሩ ሆነው ለእስራኤል ጠላትነትን የሚያሳዩ ግለሰቦች፣ አይፓክ ተቀናቃኞቻቸውን በገንዘብ እንደሚያግዝ ይገምታሉ፡፡ ለምሳሌ በ1988 ዋሽንግተን ፖስት ይፋ ባደረገው የአይፓክ ሰነድ መሠረት ምክትል ዳይሬክተሩ በ1986 በተደረገው የሴኔት ውድድር ለብዙ ተወዳዳሪዎች የገንዘብ እርዳታ ለማሰባሰብ ሞክረዋል፡፡ ዎል ስትሪት ጆርናል በ1987 ባወጣው ዘገባ መሠረት አይፓክ ምንም እንኳን የፖለቲካ ተሳትፎም ሆነ የገንዘብ ልገሳ እንደማያደርግ ቢገልጽም ከ51 የማያንሱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ አድራጊ ድርጅቶች በአይፓክ ባለስልጣናት ወይም ፖሊሲ

አውጭ ግለሰቦች ነው የሚንቀሳቀሱት፡፡ ከእነርሱ ውስጥ ብዙዎቹ ገንዘብ የሚያገኙ ከአይሁዳውያን ለጋሾች ነው፡፡›› ብሏል፡፡[19] ከዚህም በተጨማሪ አይፓክ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ኮሚቴዎችን P.A.C መረባዊ ግንኙነት ይቆጣጠራል የሚለውን ጉዳይ የፌደራሉ የምርጫ ኮሚሽን ቆየት ብሎ በቂ መረጃ እንዳልቀረበበት ቢያስታውቅም የገንዘብ መዋጮ ሂደቱን እንደሚቆጣጠረው ግን ተደርሶበታል፡፡[20] ዴቪድ ኒውማን የተባሉት አሳውንት ዲፕሎማትና በኒክሰን የፕሬዝዳንትነት ዘመን ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበሩ እንዲሁም በጂሚ ካርተር አስተዳደር በሚኒስተር ማዕረግ ያገለገሉ ሰው፡- ‹‹በሕግ መወሰኛው ምክር ቤት ያን ያክል ጉልበት እንዴት ሊኖረው እንደቻለ አንድ እውቅ የሆነ የኮንግረስ አባል ተጠይቆ ሲመልስ ‹የጉልበቱ ምንጭ ገንዘብ እንጅ ሌላ ነገር አይደለም› ብሏል›› በማለት ተናግረዋል፡፡[21]

ዘ ሴንተር ፎር ሪስፖንሲቭ ፖለቲክስ P.A.C የተባለ የምርምር ቡድን ‹‹በቅርብ ጊዜ በተደረጉ ምርጫዎች በግምት ከሶስት ደርዘን በላይ የሚሆኑ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ የአይሁድ ኮሚቴዎች (ፒ. ኤ. ሲ) ተሳትፈዋል›› ብሏል፡፡ በ2006 የኢጋማሽ ዘመን (mid-term) ምርጫ እነዚህ ቡድኖች በሁለቱም ፓርቲዎች ውስጥ ለሚገኙ ተወዳዳሪዎች ከ3 ሚሊዮን ዶላር በላይ ለግሰዋል፡፡[22] ዘ- ኢኮኖሚስት መጽሔት እንደዘገበው አፍቃሪ እስራኤል የሆኑ ቡድኖች ከ1990-2004 ባለው ጊዜ ለተወዳዳሪዎችና ፓርቲዎች በድምሩ 57 ሚሊዮን ዶላር የሚሆን ገንዘብ አዋጥተዋል፡፡ በአንጻሩ አረብ አሜሪካውያንና ሙስሊም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ኮሚቴዎች (ፒ.ኢ.ሲ) ያዋጡት ገንዘብ ከ800,000 ዶላር ያነሰ ነበር፡፡[23] በዚህ ሁሉ ላይ ግለሰቦች ለግል ተወዳዳሪዎች የሚያወጡትንና በብሔራዊ ደረጃ ለተዋቀሩ ፓርቲዎች የሚሰጠውን ግዙፍ ድጋፍ እግምት ውስጥ ስናስገባ አፍቃሪ እስራኤል የሆኑ ኃይሎች ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የፖለቲካ ተጽዕኖ ማሳደራቸውን እንገነዘባለን፡፡ የሲ. አር.ፒ.ውን ስቲቨን ዋይስን አባባል ለመጥቀስ ‹‹የአይፓክን ድጋፍና ይሁንታ ያገኘህ አፍቃሪ እስራኤል ተወዳዳሪ ከሆንክ ከመላው የአገሪቱ ማዕዘናት ገንዘብ እንደጉድ ይጎርፍልሃል፡፡››[24]

የዚህን ታክቲክ ሃያልነት የሚጠራጠር ብዙ ሰው አይኖርም። ለምሳሌ በ2006 ከተለያዩ አፍቃሪ እስራኤል ቡድኖች የተሰባሰበ ገንዘብ ሴናተር ጆሴፍ ሊበርማን በግል ተወዳድረው በሽንፈት ያጡትን ቦታ፣ ዲሞክራቱን ኔድ ለሞንትን አሸንፈው መልሰው እንዲይዙ አግዟቸዋል። ሊበርማን በድምሩ ከ145.000 ዶላር በላይ ነበር ያገኙት። ይህን የለገሷቸው ከሁለት ደርዘን በላይ የሚሆኑ ፒ.ኤ.ሲ.ዎች ሲሆኑ በአንጻራቸው ለቆሙት ኔድ ለሞንት ግን ድንቡሎ አልሰጧቸውም። በዚያው ዓመት ሽልደን ዋይት ሃውስ የሪችሞድ ከቴቱን ሪፓብሊካን ሴናተር ሊንከለን ቻፌን ለማሸነፍ እንዲችሉ 76.000 ዶላር ከተለያዩ ፒ.ኤ.ሲዎች ተለግሷቸዋል። ሊንከለን ቻፌ እስራኤልን መርዘው የያዙ ፖለቲከኛ ተደርገው ነው በአይፓክ ይታሰቡ የነበረው።[25] አፍቃሪ እስራኤል ከሆኑ ፒ.ኤ.ሲዎች ድጋፍ ለማግኘት ከተሳካላቸው ፖለቲከኞች መካከል የኒው ጀርሲው ዲሞክራት ሮበርት ሚንዬዝና የኢንዲያናው ዲሞክራት ብራድ ኤልስዎርዝ ይገኙበታል።[26]

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ግን አይፓክና ያደራጃቸው መረባዊ ግንኙነቶች ሁልጊዜም በምርጫ ላይ ተጽዕኖ ያደርጋሉ ማለት አይደለም። እርግጥ ነው የአፍቃሪ እስራኤል ቡድኖች ድጋፍ ሎንስዬልና ኢቫንስ የተባሉት ተወዳዳሪዎች በምርጫ አሸንፈው እንዲያልፉ ወይም ደግሞ የደቡብ ዳኮታው የዲሞክራቲክ ሴኔት አናሳ (minority) መሪ ቶም ዳሽል እና የፔንሴልቪኒያው ሪፐብሊካን ሴናተር ሪክ ሳንቶርም በ2004 እና በ2006 ባደረጓቸው የድጋሚ ምርጫዎች እንዳይሸነፉ አላደረጋቸውም።[27] ይሁን እንጂ የእነዚህ ድርጅቶች ተጽዕኖ ባለፉት ሶስት አሥርተ ዓመታት ለምርጫ የቀረቡ ብዙ ተፎካካሪዎች እንዲያሸንፉ ከማድረጉም በላይ ለእስራኤል ወዳጅ አይደሉም የተባሉ ብዙ ሰዎችንም ከስልጣናቸው በማፈናቀል እንዲባረሩ ማድረግ ማስቻሉ ሊሰመርበት ይገባል። ለምሳሌ በ2002 የጆርጂያ ስቴት የኮንግረስ አባሏ ሲንቲያ ማክኬኒ እንዲሸነፉ ለተፎካካሪያቸው ብዙ ገንዘብ ተንቆርቁሮላቸዋል። ማክኬኒ በ2004 እንደምንም ተሳክቶላቸው ተመልሰው ኮንግረስ ቢገቡም እንደገና በ2006 በተደረገው ምርጫ ዳግመኛ እንዲሸነፉ ተደርጓል። ማክኬኒን ያሸነፉት ዲሞክራቱ ሃንክ ጆንሰን ለዚያ ፉክክር 34.000 ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ ሰባት ከሚሆኑ አፍቃሪ እስራኤል ፒ.ኤ

ሲዎች ተለግሷቸዋል።[28] በሌላ ታዋቂ ክስተት ደግሞ ባለጸጋው የቺካጎ ነጋዴና የቀድሞው የአይፓክ ፕሬዝዳንት ሮበርት አሸር፣ የኢሊኖዮ ጠበቃ ሪቻርድ ደርቢን በ1982ቱ የአሊኖይ ስቴት ሪፐብሊካን ሴናተር የነበሩትን ፓውል ፊንደሊን አሸንፈው ቦታቸውን እንዲይዙ የምርጫ ድጋፍ እንዲሰጣቸው አደረጉ። አሸር ቆየት ብለው ሁኔታውን በማስታወስ ሲናገሩ ‹‹የደርቢንን አመለካከት መረመርኩት። እኛ ድጋፍ የምንሰጠው ፓውል ፊንዲሊን ለሚቃወም ብቻ ሳይሆን የእስራኤልም ወዳጅ ለሚሆን ሰው መሆኑን እንዲገነዘብ ማድረግ ነበረብኝ። ከዚያ በኋላ ከተለያዩ አይሁዳውያን በተሰጠው ጠቀም ያለ ገንዘብ እየታገዘ ፊንደሊን አሸነፈ። በዚህ ዓይነት በመላ አገሪቱ እየተዘዋወርኩ እስራኤልን የማይወድን ፓለቲከኛ እንዴት ማሸነፍ እንደሚቻል ለማሳየት የተለያዩ ጥረቶችን ሳደርግ ቆየሁ። ከዚያ በኋላ በሩ ወለል ብሎ ተከፈተ።››[29] ደርቢን በዚያ ዘመቻ በድምሩ 104.325 ዶላር ከእጃቸው ውስጥ የገባ ሲሆን ይህንንም ሰላሳ አንድ ከሚሆኑ የተለያዩ አፍቃሪ እስራኤል ፒ.ኤ.ሲዎች ነበር ያገኙት። በ1982 የነበረውን ሁኔታ ካየን ሌሎች የኢሊኖይ ግዛት ተወዳዳሪዎች በአማካይ ያገኙት ገንዘብ 3700 ዶላር ነበር።[30] ደርቢን በዚያ ውድድር ለአሥራ አንድ ጊዜያት ያክል በማሸነፍ የኮንግረስ አባል ሆነው የቆዩትን ፊንደሊን ያሸነፏቸው በጠባብ የድምጽ ልዩነት ነበር። ፊንደሊ ቆየት ብለው ለሴኔት አባልነት ተወዳድረው በማለፋቸው እስካሁንም ድረስ የብዙሃኑ መሪ ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ።

በ2002 ደግሞ ሌላ ታሪክ የተከሰተው ጋንግ ኦፍ ፎር ከሚባሉት ከአራቱ የአይፓክ ፖሊሲ አውጪዎች አንዱ የሆኑት ከንቲባ ቡባ ሚችል የአሳስካውን ዲሞክራት ኮንግረስማን ኸርል ሂላርድን ለማፈናቀል ተመሳሳይ የሆነ ስልት በተጠቀሙበት ጊዜ ነበር። የሂላርድ ተቃዋሚ በመላው አገሪቱ ከሚገኙ አፍቃሪ እስራኤል ቡድኖች የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ ተደረገ። የኒውዬርኩ ጀፍሪ ጎልድበርግ ሁኔታውን ሲገልጽ ‹‹አሸር (ቀደም ሲል ደርቢንን እንዲሸነፉ ያደርጓቸው የአይፓክ ፕሬዝዳንት) ቆየት ብለው ቡባን በምን ምንገድ የሂላርድ ተቀናቃኝ እንዲያሸንፉ ማድረግ እንደቻሉ ሲጠይቋቸው "ልክ አንተ ደርቢን እንዲሸነፍ ባደረግክበት መንገድ" በማለት መልሰውላቸዋል›› ብሏል።[31] አይፓክ በተጨማሪም ከእርሱ አቋም ጋር

ስምምነት ያላሳዩ ሌሎች ፖለቲከኞችም እንዲሸነፉ አድርጓል። ከእነርሱም መካከል የካንሳሷ ሪፐብሊካን ተወካይ ፔት ማክ ክሎስኪ፤ የአሪዞናው ዲሞክራት ሲናተር ጄ ዊሊያም ፉልብራይትና የአይዋ ስቴቱ ሪፐብሊካን ሮጀር ጆንሰን ጥቂቶቹ ሲሆኑ የጆንሰን እጣ በተለይ አነጋጋሪ ነበር። ከአይፓክ ዒላማ ውስጥ የገቡት ሮናልድ ሬገን ከኮንግረስ ፍላጎት በተጻራሪ ለሳኡዲ አረቢያ አዋክ የሚባሉትን ተዋጊ ጀቶች ለመሸጥ በ1981 በፊለጉ ጊዜ የተወሰኑ የኮንግረስና ሴኔት አባላትን እያግባቡ አቋማቸውን እንዲደግፉላቸው ማድረግ ችለው ነበር። ከእነዚያ ሰዎች አንዱ ጆንሰን ነበሩ። ከዚያ በኋላ በ1984 በተደረገው የሴኔት ውድድር አይፓክ የተለያዩ ፒ.ኤ ሲዎችን በማስተባበር የጆንሰን ተቃዋሚ ለነበሩት ዲሞክራቱ ቶም ሃርኪን 100.000 የአሜሪካን ዶላር እንዲደርሳቸው አደረገ። ጆንሰንም ተሸነፉና መቀመጫቸውን አጡ። የካንሰሱ ዲሞክራት ሴናተር አለን ክራንስቶን ኋላ ላይ የጆንሰንን እጣ አስመልክተው አስተያየታቸውን ሲሰጡ፡ -‹‹መካከለኛው ምሥራቅን በተመለከተ የምንወስዳት እያንዳንዷ እርምጃ አደጋ ላይ ልትጥለን እንደምትችል በማሰብ በሴናተሮች ልብ ውስጥ ፍርሃትን የጨመረ ክስተት ነበር›› ብለዋል።[32]

ሎቢው ተጽዕኖውን ያሳየበት ሌላው አጋጣሚ የተከሰተው በ1982 የኢሊኖዩ ዲሞክራትና የቀድሞ ሴናተር አድላኢ ስቲቨንሰን ለኢሊኖይ ስቴት ገዥነት በተወዳደሩ ጊዜ ነበር። ስቲቨንሰን በመጀመሪያ በ1980 የማሻሻያ ህግ ለሴኔት ባቀረቡ ጊዜ ነበር አፍቃሪ እስራኤል ከሆኑ ቡድኖች ጋር የተጣመዱት። ስቲቨንስን ያቀረቡት የማሻሻያ ረቂቅ እስራኤል በሃይል በያዘቻቸው ግዛቶች የሰፈራ መንደር መመሥረቷን ካላቆመች በስተቀር አሜሪካ ምትሰጣትን እርዳታ እንድትቀንስባት የሚያሳስብ ነበር። እርግጥ ነው ስቲቨንስን የማሻሻያ ረቂቁ በሴኔቱ እንደማያልፍ ያወቁ ነበር። እርሳቸው የፈለጉት የሴኔት አባላት የሆኑት ባልደረቦቻቸው የዩናይትድ ስቴትስን ጥቅም የሚቃረን ቢሆንም እንኳ እስራኤልን የሚደግፉ ሕጎችን ከማሳለፍ የማይመለሱ መሆናቸውን ለማጋለጥ ነበር። የስቲቨንሰን እርምጃ የሚያስከትለው ውጤት ይታወቅ የነበረ ሲሆን ያገኙት ድጋፍ የሰባት የሴኔት አባላትን ድምጽ ብቻ ነበር። የማሻሻያ ረቂቁን ከተቃወሙት ሰዎች አንዱ የሆኑት የኔቫዳው

ዲሞክራት ሴናተር ኩዊንቲን ባርዲክ የኢሊኖዩን ሴናተር ስቲቨንስንን እንዲህ አሏቸው፡- ‹‹አዝናለሁ አድላኤ ስቲቨንሰን! እኔ ግን እንደገና ለመመረጥ እየተቃረብኩ ነው፡፡›› ስቲቨንሰን ሁለት ዓመት ዘግይተው የኢሊኖይ ገዢ ለመሆን ሲወዳደሩ የተገነዘቡት ነገር ለምርጫ ማስፈጸሚያ የገንዘብ ልገሳው እየነጠፈባቸው መሄዱን ነበር፡፡ በእርግጥም ገንዘቡ ወደ ተቃዋሚያቸው ነበር የጎረፈው፡፡ ስቲቨንሰን ዘግየት ብለው እርሳቸውም ሆኑ ባለቤታቸው ጸረ-ሴማዊ የሚል ቅጥያ የተሰጣቸው መሆኑንና በተለያዩ የፕሬስ ውጤቶችም ስማቸው መብጠልጠሉን፣ እንዲሁም የቀድሞ አይሁድ ጓደኞቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ሳይቀሩ ሙልጭ አድርገው እንደሰደቧቸውም ተናግረዋል፡፡ ስቲቨንሰን በመጨረሻ በጠባብ ውጤት የተሸነፉ ሲሆን ከውጤቱ በኋላ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹በምርጫው ላይ የሎቢው ተጽዕኖ ከሚገባው በላይ ከፍተኛ ነበር፡፡››[33]

ምናልባትም የአይፓክን ደንብ ለመጣስ በሞከረ ማንኛውም ፖለቲከኛ ላይ ደርሶ የማያውቅ ውድቀት የደረሰው በ1984 በአሊኖዩ የዲሞክራቲክ ፓርቲ ተወካይ በሴናተር ቻርለስ ፐርሲ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ፐርሲ ምንም እንኳን አፍቃሪ እስራኤል የሆነ የቀድሞ ታሪክ ያላቸው ቢሆንም ፕሬዝዳንት ፎርድ በ1975 የመካከለኛውን ምሥራቅ ፖሊሲ እንደገና ለማጤን መወሰናቸውን ተከትሎ አይፓክ ባዘጋጀውና letter of 76 በተባለው የተቃውሞ ማሳሰቢያ ደብዳቤ ላይ ፊርማቸውን ለማኖር ሳይፈቅዱ ቀሩ፡፡ በዚህም ምክንያት የአይፓክን ቁጣ አተረፉ። ከዚያ በኋላ ደግሞ ‹‹የፒ. ኤል. ኦ. ሊቀመንበር የሆኑት ያሲር አረፋት ከሌሎች ፍልስጤማውያን አሸባሪዎች ጋር ሲነጻጸሩ ለዘብተኛ የሚባሉ ናቸው›› የሚል አስተያየት በመስጠታቸው ነገሩ ተባብሶ የፐርሲ ተቃዋሚዎች በ1984 በተደረገው የመጀመሪያውና አጠቃላዩ ምርጫ ከተለያዩ አፍቃሪ-እስራኤል ፒ. ኤ. ሲዎች ዳጎስ ያለ ገንዘብ እንዲያገኙ ተደረገ፡፡ ለአብነት ያክል በካሊፎርኒያ ስቴት ነጋዴ የሆኑትና ለአይፓክ ገንዘብ በማዋጣት የታወቁት ሚካኤል ጎላንድ ለኢሊኖዩ ጸረ ፐርሲ የቅስቀሳ ወጪ 1.1 ሚሊዮን ዶላር ነበር የመደቡት፡፡ (ጎላንድ በ1986 ለካሊፎርኒያ የሴኔት ውድድር ህገ ወጥ መዋጮ በማድረግ ወንጀል መከሰሳቸው ይታወቃል)[34] ፐርሲ በጠባብ ድምጽ ከተሸነፉ በኋላ የአይፓኩ ፕሬዚዳንት

ቶም ዳይን ጉራ በተቀላቀለበት ሁኔታ እንዲህ አሉ፡- ‹‹በመላዋ አሜሪካ የሚገኙ አይሁዳውያን ከዳር እስከዳር ፕርሲን ለመጣል ተረባርበዋል፡፡ አሁን በስልጣን ላይ የሚገኙ አሜሪካውያን ፖለቲከኞችም ሆኑ ለወደፊቱ በምርጫ ለማሸነፍ የሚሹ ሁሉ ይህ መልዕክት ይደርሰቸዋል ብለን እናምናለን፡፡››[35] የቶም ዳይን የተጋነነ የሚመስል አባባል በጉራ ይታጀብ እንጂ በውስጡ ትልቅ ትምህርትን ነበር ለብዙ ፖለቲካኞች ትቶ ያለፈው፡፡ የፎርዋርድ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጂ.ጄ ጎልድበርግ በ2002 እንዲህ በማለት አስተያየቱን ሰጥቷል፡- ‹‹አንድ ወሳኝ መልዕክት በሁሉም የኮንግረስ አባላት ጭንቅላት ውስጥ ያለ ይመስለኛል፡፡ ያም እነዚህን ህዝቦች (አይሁዳውያንን ማለቱ ነው) ጥሳሃቸው ለማለፍ አትሞክር፡፡ አሻፈረኝ ብለህ ካደረግከው ግን ይዘውህ ይወርዳሉ" የሚል ነው፡፡[36]

አይፓክና አፍቃሪ - እስራኤል ፒ.ኤ.ሲዎች ምንጊዜም ቢሆን በምርጫ የሚወዳደር ማንኛውም ሰው እስራኤልን የሚደግፍ መሆኑን በዋነኝነት ማረጋገጥ ይፈልጋሉ፡፡ ከዚህም በላይ እነዚሁ አካላት የእስራኤልን ድርጊቶች የሚተቹ ፖለቲከኞችን በተጽዕኖአቸው ሥር በማስገባትና ጽኑ የሆኑ ደጋፊዎቻቸው እንዲሆኑ በማድረግ ተደጋጋሚ ስኬት አስመዝግበዋል፡፡ ለአብነት ያክል የቀድሞው የሰሜን ካሮላይና ሪፐብሊካን ሴናተር ጀሲ ኸልምስ የዩ.ኤስ አሜሪካን የውጭ ፖሊሲና ለእስራኤል የምትሰጠውን ግዙፍ እርዳታ በግልጽ በመተቸት የታወቁ ነበሩ፡፡ ይሁን እንጂ በ1984 እንደገና ለመመረጥ ተቀናቃኛቸው የሆኑትንና ታዋቂውን የሰሜን ካሮላይና ሃገረ ገዢ ጆምስ ሃንትን ማሸነፍ ነበረባቸው፡፡ አይፓክ እንደጠላት የተመለከታቸውን ጀሲ ኸልምስን እንዲሸነፉ ለማድረግ ለተፎካካሪያቸው ጀምስ ሃንት ዳጎስ ያለ ገንዘብ በማፍሰስ ውድድሩን እንዲያጧጡፉት አደረገ፡፡ ጀሲ ኸልምስ በዚህ ጊዜ መልዕክቱ በሚገባ ተገለጸላቸው፡፡ እናም ምንም ሳያቅማሙ በቀጥታ ወደ እስራኤል (እየሩሳሌም) ከበረሩ በኋላ "ዎሊንግ ዎል" የሚባለውን የአይሁዳውያን የጸሎት ስፍራ ግንቡን ሲስሙ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ "ያርሙልክ" በተባለ ጋዜጣ ላይ እንዲወጣ አደረጉ፡፡ በዚያም ብቻ ሳይወሰኑ ከአሪዮል ሻሮን ጋር በቢሯቸው ሆነው ሲነጋገሩ የሚያሳይ ሌላ ፎቶግራፍ እንዲወጣ አደረጉ፡፡ ከዚያ በኋላ በሚያስደንቅ

ሁኔታ ኧልምስ በ2002 በጡረታ እስከተገለሉበት ጊዜ ድረስ እስራኤልን በመደገፍ በየጊዜው በሴኔቱ ሃሳብ የሚሰጡ ሆነው ቀጠሉ።[37]

በሴናተር ሂላሪ ክሊንተን የፖለቲካ ሕይወት ላይም ተመሳሳይ የሆነ ሂደት እንመለከታለን። ክሊንተን በ1998 ገና ቀዳማዊ እመቤት ሆነው እያሉ የፍልስጤም አስተዳደር መንግስት ሆኖ ቢቋቋም እንደሚደግፉ ይፋ አደረጉ። እንዲሁም በቀጣዩ ዓመት 1999 ላይ የያሲር አረፋት ባለቤት የሆኑትን ሱሃ አራፋትን በይፋ አቅፈው በመቀበላቸው በሎቢው ውስጥ ያሉ አካላትን ክፉኛ በማናደድ ለትችት አነሳሱ። ከዚያ በኋላ ግን ክሊንተን አካሄዱን አወቁበትና ጽኑ የእስራኤል ደጋፊነታቸውን መግለጽ በመቻላቸው የገንዘብ መዋጮን ጨምሮ የተለያዩ ድጋፎችን አፍቃሪ እስራኤል ከሆኑ ቡድኖችና ግለሰቦች ማግኘት ቻሉ። ሂላሪ ክሊንተን የእስራኤል ጽኑ ደጋፊነታቸውን ይበልጥ ለማሳየት በሐምሌ 2006 ላይ እስራኤል ሊባኖስን መውረሯን በመደገፍ አሜሪካ ውስጥ ከተደረጉት ሰልፎች በአንዱ ላይ ብቅ ብለው አቋማቸውን በንግግራቸው ገለጡ። አሜሪካን ፎር ሴፍ እስራኤል የተባለው ጠጣሩን መስመር የሚከተል ድርጅት ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ሄለን ፍሪድማን የክሊንተንን አካሄድ አስመልክተው ሲተቹ ‹‹እንደማስበው እስካሁን እያደረገችው ያለው ነገር ሁሉ በተለይም ያለፈውን ታሪኳን ስናስታወስ መልካም ይመስለኛል። ሆኖም ግን ሱሃ አራፋትን በአደባባይ ተቀብላ ማቀፏን መርሳት የለብንም›› ብለዋል።[38] ያም ሆነ ይህ አፍቃሪ እስራኤል ፒ. ኤ. ሲዎች ወደ 30.000 ዶለር የሚጠጋ ገንዘብ በማዋጣት ስለሰጧቸው ክሊንተን ዳግም ለመመረጥ የሚያበቃቸውን ዘመቻ በጥሩ ሁኔታ ተወጥተውታል። ከዚያ በኋላ ጥር 2007 ላይ የታተመው ፎርዋርድ የተባለው የአይሁዶች ጋዜጣ ‹‹ክሊንተን በ2008ቱ ለዲሞክራቲክ ፓርቲ ፕሬዝዳንታዊ ተወካይነት በሚደረገው ቅስቀሳ ከአይሁድ ማህበረሰብ የአንበሳውን ድርሻ ያገኛሉ›› በማለት ገለጸ።[39]

ሌላው አስገራሚ ሁኔታ ደግሞ በምርጫ ጊዜ የሚወዳደሩ ሰዎችን ማሳመንና ግፊት ማድረግ የማይሰራ ከሆነ አይፓክ የእርሱን መንገድ ለመከተል አሻፈረኝ የሚሉትን ከማስፈራራት የማይመለስ መሆኑ ነው።[40] ለምሳሌ በ2006 የሚኖሶታዋ የዲሞክራቲክ ፓርቲ የኮንግረስ አካል ቤቲ

ማክኮለም ሊበራል የሆኑና እስራኤልንም በመደገፍ የሚታወቁ ፖለቲከኛ ቢሆኑም አይፓክ የደገፈውንና የፍልስጤማውያንን ጸረ-አሸባሪነት ህግ ተቃወሙ፡፡ በዚያ ረቂቅ የተካተተው ሕግ ፍልስጤማውያን ካካሄዱትና ሃማስን በአሸናፊነት እንዲወጣ ካስቻለው ምርጫ በኋላ በፍልስጤም መንግሰት ላይ ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ እንዲወሰድ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ነበር፡፡ ህጉን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የካቶሊክ ጳጳስ እንዲሁም አፍቃሪ እስራኤል የሆኑት አሜሪካን ፎር ፒስ ናው እና እስራኤል ፖሊሲ ፎረም የተባሉት ድርጅቶች ሳይቀሩ ተቃውመውታል፡፡ የሆነ ሆኖ የአይፓክ ሎቢስቶች የኮንግረስ አባል ማክኮለምን የምርጫ ኃላፊ ጠርተው አሸባሪዎችን የሚደግፍን ማንኛውም የምክር ቤት አባል እንደማይታገሱት ገለጡላቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ማክኮለም ይቅርታ ይደረግላቸው ዘንድ የአይፓክን ዋና ኃላፊ ሆዋርድ ኮርን መጠየቅ ግድ ሆኖባቸዋል፡፡[41]

መሠረታዊው መልዕክት ግልጽ ነበር፡፡ ማንኛውም ሴናተርም ሆነ የምክር ቤት ተወካይ አይፓክን ችላ ብሎ የፈለገውን ለመስራት ቢሞክር በእሳት እየተጫወተ እንደሆነ ማወቅ ይኖርበታል፡፡ አንድ የኮንግረስ ምንጭ በ1991 ሃቁን እንዲህ በማለት አስቀምጦታል፡- ‹‹እስራኤልን በመቃወም ድምጽ መስጠት ዋሽንግተን ስቴት ውስጥ የእንጨት ግንዲላ (lumber) ምርትን ተቃውሞ ድምጽ እንደመስጠት ይቆጠራል፡፡ ልዩነቱ አይፓክ መዋቅሩን የዘረጋው በመላው ዩናይትድ ስቴትስ መሆኑ ብቻ ነው፡፡››[42] ለዚህም ነው የቀድሞው የአይፓክ ዳይሬክተርና የአሁኑ የግምጉ ቤት ኃላፊ ሞሪስ አሚቲ በ2002፡- ‹‹በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ፖለቲከኛ በጣም ጥሩ እየሆነ ነው›› ያሉት፡፡ እንዲሁም ጂሚ ካርተር በየካቲት 2007 ‹‹ዛሬ ዛሬ በዩናይትድ ስቴትስ ኮንግረስ በሕግ መወሰኛውም ሆነ በሴኔቱ ውስጥ "እስራኤልንና ፍልስጤማውያንን በተመለከተ ሚዛናዊ መሆን ይኖርብናል፤ እንዲሁም ሁለቱንም ወደ ሰላምና ወደ ስምምነት ማምጣት አለብን" የሚል አንድም ሰው አላይም" ያሉት ለዚህ ነው፡፡ ካርተር ጨምረው ሲናገሩ፡- ‹‹በድጋሚ ለመመረጥ የሚፈልግ የኮንግረስ አባል ወግ አጥባቂ የሆነውን የእስራኤል

መንግስት አቋም የሚቃወም የሚመስል ትርጉም ያዘለ ንግግር መናገሩ ብቻ በፖለቲካው ምህዳር ራሱን እንደማጥፋት ይቆጠራል›› ብለዋል፡፡[43]

የአይፓክ ተጽዕኖ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠነከረ መሄዱን የምንገነዘበው ዓመታዊ የፖሊሲ ኮንፈረንስ በሚዘጋጅበት ጊዜ በሁለቱም ፓርቲዎች ውስጥ ያሉና ዋና ዋና የሚባሉ የፖለቲካ ሰዎች የመገኘት ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ስናስብ ነው፡፡ ለአብነት ያክል በ2007 የፖሊሲ ኮንፈረንስ ላይ ንግግር እንዲያደርጉ ከተጋበዙ ፖለቲከኞች መካከል ም/ፕሬዝዳንት ዲክ ቼኒ፣ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔና የካንሳሷ ዲሞክራት ናንሲ ፔሎሲ፣ የሴኔቱ ብዙሃን መሪ ሃሪ ሬይድና የአናሳዎቹ መሪ የኬንታኪው ሪፐብሊካን ሚች ማክኮኒል፣ እንዲሁም ጆን ቦህነር ይገኙበታል፡፡ ያለፈው ዓመት ማለትም የ2006 ተጋባዥ ንግግር አድርጊዎች ደግሞ ቼኒ፣ ቦህነር፣ በተባበሩት መንግስታት የአሜሪካ አምባሳደር ጆን ቦልተን፣ የሚዚዬሪ ስቴት ሪፓብሊካን ተወካይ ሲናተር ሱሳን ኮሊንስ፣ የኢንዲያናው ዲሞክራት ኢቫን ባይህ፣ የሞንታናው ሪፓብሊካን ሮይ ብለንት፣ የኔቫዳዋ ዲሞክራት ሼሊ በርክሌይ፣ የአላባማው ዲሞክራት አርተር ዴቪስ፣ የኒው ጀርሲው ዲሞክራት ቢል ፓስክሪል፣ ሮበርት ዋክስለር፣ እንዲሁም የቀድሞው ሴናተርና ለፕሬዚዳንትነት ለመወዳደር ተስፈኛ የሆኑት ጆን ኤድዋርድስ ነበሩ፡፡ በሌላ ዓመት በዚሁ መድረክ ተናጋሪ እንዲሆኑ ከተጋበዙት ውስጥ ጆርጅ ደብሊው ቡሽ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሮቹ ኮሊን ፓዎልና ኮንደሊዛ ራይስ፣ የኢሊኖዩ ሪፓብሊካንና የቀድሞው የምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ዴኒስ ዋስተርት፣ ሪቻርድ አርሚ፣ ኒዊት ጊንግሪችና ሌሎችም አፍቃሪ እስራኤል የሆኑ የመንግስት ባለስልጣናት ነበሩ፡፡ እንዲህ በመሰለ አካኋን የሁለቱንም ፓርቲ አባላት በማርበድበድ እጃቸውን የጎሊት ጠምዝዞ የፈለገውን እንዲያደርጉ የሚያስገድድ ከአይፓክ የሚበልጥ የሎቢ ድርጅት እንዳለ ማሰቡ ይከብዳል፡፡

አይፓክ በምርጫ ወቅት የሚፈጥረው ተፅዕኖ እስራኤል በየዓመቱ የአሜሪካን ችሮታ እንደልቧ እንድትዝቅና ሴናተሮችና የህዝብ ተወካዮችም የእስራኤልን ባሕሪ በተመለከተ የተለሳለሰ ትችት እንኳ እንዳይሰነዝሩ አድርጓል፡፡ በካፒቶል ሂል (ኮንግረስ ህንፃ) ያለው ተጽዕኖ ደግሞ ከዚህም

ላቅ ያለ ነው። ሁሉም ሎቢ የሚያደርጉ ቡድኖች ተጽዕኖአቸውን የሚያሳርፉት በቀጥታ የምክር ቤት አባላትን በማሳመንና ለምርጫ ቅስቀሳ ገንዘብ በማዋጣት ብቻ ሳይሆን ለሚደግፏቸው ሕግ አውጪዎች ጠቀም ያለ ድጎማ በመስጠት፣ ሥራ የሚበዛባቸውን የምክር ቤት ሠራተኞች አቅጣጫ ከመጠቆምና ነገሮችን ከመተንተን አንስቶ የምክር ቤት አባላት ለመራጮች የሚያደርጓቸውን ንግግሮች አዘጋጅተው እስማቅረብ ድረስ ርቆ የሚሄድ ነው።[44] ከዚህም በተጨማሪ እያንዳንዱ የኮንግረስ አባል አይፓክ በሳምንት ሁለት ጊዜ የሚያወጣውን ‹ኪር ኢስት ሪፖርት› የተባለ ጋዜጣ እንዲያገኝ የሚደረግ ሲሆን እስራኤልን የሚመለከት አዲስ ጉዳይ ሲኖር ደግሞ አባላቱ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አቅጣጫ የሚያሳይ ድጋፍ ሰጪ ሰው ይመድብላቸዋል። የቀድሞው የአይፓክ ስታፍ ባልደረባ ዶግላስ ብሎም ፊልድ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹የኮንግረስ አባላትና ባልደረቦቻቸው እስራኤልን የተመለከተ አንዳች መረጃ ማግኘት ሲያስፈልጋቸው ወደ ኮንግረስ ቤተ መጽሀፍት፣ ወይም ወደ ኮንግረስ የምርምር አገልግሎት ወይም ወደ ኮሚቴዎች ከመደወላቸው በፊት አይፓክን ማማከር የተለመደ አስራራቸው ነው። አይፓክ የኮንግረስ አባላት የሚያቀርቧቸውን ንግግሮች ከማርቀቅ ጀምሮ በሕግ ማውጣት ሂደት ላይ ይሠራል፣ አባላቱ መከተል ያለባቸውን ታክቲክ ያመላክታል፣ ምርምር ያካሄዳል፤ ምርምሩንና ሌሎች ጉዳዮችን በገንዘብ የሚያግዙ አካላትን ያፈላልጋል። እንዲሁም የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለማሳላጥ የሚረዱ ጉዳዮችን ያከናውናል።››[45] ከዚህ ሁሉ ገለጻ እንደምንገነዘበው አይፓክ በህግ ማውጣቱና በፖሊሲ መንደፉ ሂደት ላይ በቀጥታ ራሱን የሚያስገባ መሆኑን ሲሆን ይህም በዚህ መጽሀፍ ክፍል 2 ላይ በይበልጥ በስፋት የሚብራራ ይሆናል።

ሁኔታዎችን ይበልጥ ያማሩ ለማድረግ የአይፓክ እህት ድርጅት የሆነው የአሜሪካን እስራኤል ኢዱኬሽን ፋውንዴሽን A.I.E.F የኮንግረስ አባላትን በነጻ ወደ እስራኤል ወስዶ የማዝናናት ሥራ ይሠራል። እንዲህ ዓይነቱ አሠራር የኮንግረስ አባሉን አፍቃሪ እስራኤል አቋም ለማጽናትና ለምርጫ የሚያግዘውን የገንዘብ መዋጮ በአግባቡና በፍጥነት ለመሰብሰብ ከማገዙም በላይ ለእስራኤል መሪዎች የፖሊሲ አማራጭና መሠረታዊ ርዕዮት

ተጋላጭ እንዲሆን በማደረግ የበኩሉን ድርሻ ያበረክታል። ለዚህም ነው የኮንግረስ አባላት ወደ ውጭ ከሚያደርጓቸው ጉዞዎች አስር ከመቶ የሚሆነውን ወደ እስራኤል የሚያደርጉት። ይህ አሃዝ የኮንግረስ አባላት በዓለም ላይ ካሉ 200 የሚሆኑ ሃገራት ሁሉ ከእስራኤል ጋር ያላቸው ቅርርብ የቱን ያህል እንደሆነ በግልጽ ያሳያል። የኮንግረስ አባላቱ ቀሪውን 90 በመቶ የሚሆን ጉዞ ወደ ሌሎች 199 የሚሆኑ አገራት ያደርጋሉ ማለት ነው። አንድ ሪፖርት እንደሚያሳየው A.I.E.F ይህን ጉብኝት ለማስፈጸም ከጥር 2000 እስከ 2005 አጋማሽ ድረስ ወደ 1 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ አውጥቷል።[46]

አሁንም ደጋግመን ትኩረት ልንቸረው የሚገባን ጉዳይ አይፓክ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ በዩ ኤስ አሜሪካ የፖለቲካ ሥርዓት የተለመደ ከሆነውና በፍላጎት የተደራጁ ቡድኖች ከሚያደርጉት የሎቢ ተጽዕኖ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ነው። ስቴፈን አይዛክ ‹አይሁዳውያንና የአሜሪካ ፖለቲካ› በተባለው ጥናታቸው የአይፓኩ ሞሪስ አሚቲ የተናገሩትን እንደሚከተለው ጠቅሰዋል፡- ‹‹እዚህ ላይ ጠቃሚው ጉዳይ...ከምንጠቀምባቸው ስልቶች ሁሉ አንዱም ያለ አግባብ የማይፈጸም መሆኑና ተለምዶአዊ የሆኑት የዲሞክራሲ ስልቶች መሆናቸው ነው። እነርሱም ደብዳቤ፣ ስልክ ወዘተ. ናቸው።››[47]

እነዚህ ተለምዶአዊ (traditional) የሚሰኙ ተጽዕኖ ማሳረፊያ መንገዶች ሎቢው የኮንግረሱን የህግ አስፈጻሚ አካል በመጫን ከእስራኤል ፍላጎት ውጪ የሆነ ጉዳይ ሲገጥመው ተፈጻሚ እንዳያደርገው ያስገድደዋል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲከሰት ፕሬዝዳንቱ ወይም የካቢኔ ባለስልጣኑ ከኮንግረስ አካላት ማለትም ከህግ መወሰኛው ወይም ከሴኔቱ አሊያም ደግሞ ከሁለቱም የሆኑ በርካታ አባላቱ የፈረሙበት ጠንካራ ደብዳቤ ይደርሰዋል። እንዲህ የመሠለው ሁኔታ ከደረሰባቸው ፖለቲከኞች አንዱ ፕሬዝዳንት ጀራርድ ፎርድ ሲሆኑ በ1975 የአሜሪካንና የእስራኤልን ግንኙነት እንደገና ሊያጤኑት እንደሚፈልጉ ባሳወቁ ጊዜ ነበር አጋጣሚው የደረሰባቸው። ፕሬዝዳንት ቡሽም ቢሆኑ በ2002 ሚያዚያ ላይ እስራኤል በያዘቻቸው ግዛቶች ላይ የምታደርጋቸውን መጠነ ሰፊ የሆኑ ወታደራዊ ጥቃቶች

እንድታቆም ተጽዕኖ ሊያደርጉባት በሞከሩ ጊዜ ተመሳሳይ ሁኔታ አጋጥሟቸዋል። አይፓክ እነዚህን ደብዳቤዎች በማርቀቅ አብዛኛዎቹ የኮንግረስ አባላት እንዲፈርሙባቸው ማድረጉ፣ የፖለቲካኞችን እጅ ጠምዝዞ የፈለገውን ነገር እንዲያደርጉ የማስገደድ የላቀ ችሎታ ያለው መሆኑን የሚያሳይ በቂ ምስክር ነው። የሃዋዩ ዲሞክራት ሴናተር ዳንኤል ኢንኦይ በ1975 የፎርድን ሀሳብ ተቃውመው ከፈረሙ በኋላ አስተያየት ሲሰጡ፦ ‹‹ለአምስት ሺህ ሰዎች መልስ ከመስጠት ይልቅ ከአንድ ደብዳቤ ላይ መፈረም ይቀላል›› ብለዋል። የዲሞክራቲክ ፓርቲ የኢንዲያና ተወካዩ ሴናተር ጆን ኮልቨር ቆየት ብለው እንዳመኑት፦ ‹‹ተጽዕኖው እጅግ ኃያል ነበር። ስለሆነም ማምለጡን መርጫለሁ›› ብለዋል።[48] የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮንዶሊዛ ራይስም ቢሆኑ በ2007 የመካከለኛውን ምሥራቅ የሰላም ሥምምነት ለማስጀመር ወዲዚያው ሊያመሩ በተዘጋጁ ጊዜ ተመሳሳይ የሆነ ጫና ገጥሟቸዋል። ራይስ ልክ አሜሪካን ለቅቀው ለመብረር በተዘጋጁበት ቅጽበት በአይፓክ አነሳሽነት ተዘጋጅቶ 79 ሴናተሮች የፈረሙበት ደብዳቤ ደረሳቸው። ይህ ደብዳቤ አዲስ የተዋቀረው የፍልስጤማውያን መንግስት ለእስራኤል እውቅና እስካልሰጠ፤ ሽብርተኝነትን እስካላወገዘና የእስራኤልን ፍላጎት በሚያስከብር ስምምነት ለመፈጸም እስካልተስማማ ድረስ ራይስ ምንም አይነት ግንኙነት እንዳያደርጉ የሚያሳስብ ነበር። የቀድሞው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሎውረንስ ኤግልበርገር አንድ ጊዜ የአይፓክ ዳይሬክተር የሆኑትን ቶም ዳይን፦ ‹‹ካንተ ጋር የግድ መነጋገር ይኖርብኛል። ምክንያቱም ልትጎዳኝ ትችላለህና›› ማለታቸው አያስደንቅም።[50]

እንግዲህ ራሱን "የአሜሪካ አፍቃሪ እስራኤል ሎቢ" (the American pro-israel lobby) ብሎ የሚጠራው አይፓክ ከሞላ ጎደል በኮንግረስ ውስጥ ተግዳሮት የማይነሳበት ድርጅት መሆኑን ማመን ተገቢ ነው።[51] ከአሜሪካ መንግስት ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች አንዱ የሆነው ምክር ቤት (ኮንግረስ) ሙሉ የእስራኤል ደጋፊ መሆኑ ግልጽ ነው። ዩ. ኤስ. አሜሪካ በእስራኤል አንጻር የምትከተለውን ፖሊሲ በተመለከተ ምንም እንኳን የዚያ ፖሊሲ መዘዝ ለመላው ዓለም የሚተርፍ ቢሆንም እንኳ በፍጹም ለውይይት

አይቀርብም፡፡ የደቡብ ካሮላይናው ዲሞክራቲክ ፓርቲ ሴናተር ኧርነስት ሆሊንግስ ኃላፊነታቸውን በ2004 አገባደው ምክር ቤቱን ሲለቁ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹አይፓክ ከሰጠህ ውጪ እስራኤልን የሚመለከት የተለየ ፖሊሲ ሊኖርህ አይችልም፡፡››[52] አንድ ሌላ ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ ሴናተርም ለዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ በ1991 ሁኔታውን አስመልክተው ሲገልጹ፡- ‹‹አይፓክ እጅግ በጣም ኃያልና ምህረት የሌለው፣ እንዲሁም ንቁ ድርጅት እንደሆነ ባልደረቦቼ ያስባሉ፡፡ የተወሰኑ ጉዳዮች ለድምጽ አሰጣጥ እዚህ ሲቀርቡ ሰማኒያ በመቶ የሚሆኑት የሴኔቱ አባላት አይኖቻቸውን ወዲያና ወዲህ ያገላብጣሉ፡፡ እያደረጉ ያሉት ነገር ትክክል እንዳልሆነ ያምናሉ፡፡ ሆኖም ግን ነገ ኩርኩም ሊያስከትልባቸው የሚችል በሆነ ጉዳይ ላይ እንደምን በነጻነት የፈለጉትን ማድረግ ይችላሉ?›› ብለዋል፡፡[53]

መጠነኛ መገረምን የሚያጭረው ደግሞ የቀድሞው የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር አሪየል ሻሮን ለአሜሪካ አድማጮቻቸው የተናገሩት ነበር፡- ‹‹ሰዎች እስራኤልን እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ሲጠይቁኝ፡- ‹አይፓክን እርዱ" እላችዋለሁ፡፡›› እርሳቸውን የተኳቸው ኢሁድ ኦልመርትም ቢሆኑ በዚህ ሃሳብ እንደሚስማሙ እንዲህ በማለት ነበር የገለጹለት፡- ‹‹በመላው ዓለም ውስጥ ካለው ነገር ሁሉ በላጭ የሆነውን ደጋፊና ጓደኛ አይፓክን የሰጠንን አምላክ እናመሰግናለን፡፡››[54]

አፍቃሪ እስራኤል ፕሬዝዳንቶችን ወደ ሥልጣን ማምጣት

በኮንግረስ በኩል ተጽዕኖ በማድረግም ይሁን ቀጥተኛ በሆነ መንገድ በሎቢው ውስጥ ያሉ ቡድኖች በሕግ አስፈጻሚው አካል ላይ ትርጉም ያለው ተጽዕኖ ያሳድራሉ፡፡ ይሁን እንጂ የአሜሪካ ፕሬዝዳንቶች እንደኮንግረሱ ሙሉ በሙሉ ለተጽዕኖ ግፊት የሚንበረከኩ አይደሉም፡፡ ስለሆነም ከእነርሱ ብዙዎቹ በአንዱ ወይም በሌላው አጋጣሚና ጊዜ እስራኤልም ሆነች ሎቢው የሚቃወሙትን አቋም በመያዝ ሲያራምዱ ይስተዋላሉ፡፡ ይሁን እንጂ እንደዚህ ዓይነት አጋጣሚዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሱ ሲሄዱ ነው

የታየው። ይህም እየሆነ ያለው የእስራኤል ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ እየቀነሰና በኃይል በያዘቻቸው መሬቶች ላይ የምታሳያቸው ሞራል አልባ ድርጊቶች ከዩ ኤስ አሜሪካ ፖሊሲ ጋር ፍጹም የሚጋጩ ሆነው እየተገኙም ጭምር ነው።

በሕግ አስፈጻሚው አካል ላይ የሚደርሰው ተጽዕኖ በከፊል የሚመነጨው አይሁዳውያን መራጮች በፕሬዝዳንታዊ ውድድር ላይ ከሚያሳርፉት ጫና ነው። የአሜሪካ አይሁዶች ምንም እንኳን ቁጥራቸው ከአጠቃላዩ የአሜሪካ ሕዝብ አንጻር ትንሽ ቢሆንም (ከ3 ከመቶ በታች ነው) በሁለቱም ፓርቲዎች ውስጥ ለሚገኙ የምርጫ ተወዳዳሪዎች ከፍተኛ የሆነ የምርጫ ማስፈጸሚያ መዋጮ ያደርጋሉ። የቀድሞው የአሜሪካ ጦር ሃይሎች ኢታማጆር ሹምና የፕሬዝዳንቱ አማካሪ ሃሚልተን ጆርዳን በአንድ ወቅት ለፕሬዝዳንት ጂሚ ካርተር በጻፉት ደብዳቤ እንዲህ ብለው ነበር፦ ‹‹በዚህች አገር ውስጥ ዓይነተኛ የሚባል የፖለቲካ ገንዘብ መዋጮ በሚኖር ጊዜ የአሜሪካ አይሁዶች ትርጉም ያለው ሚና ሲጫወቱ ይታያሉ።››[55] እርግጥ ነው ዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ እንደገመተው ‹‹የዲሞክራቲክ ፓርቲ ፕሬዚዳንታዊ ተወዳዳሪዎች ወደ 60 ከመቶ የሚሆነውን ገንዘብ የሚያገኙት ከአይሁዳውያን ደጋፊዎቻቸው ነው›› ብሏል።[56] ሌሎች ደግሞ ይህን አሃዝ ዝቅ አድርገው የሚገምቱት ቢሆንም ዞሮ ዞሮ የአሜሪካ አይሁዶች ከ20 እስከ 50 በመቶ የሚሆነውን፤ ለዲሞክራቲክ ፓርቲና ለፕሬዝዳንትዊ ምርጫ ተወዳዳሪዎች የሚያስፈልገውን ገንዘብ ያዋጣሉ።[57] ይህን መዋጮ ከሚያነቃቁት ጉዳዮች እስራኤል አንዷ ምክንያት ትሁን እንጂ ብቸኛ ምክንያት ግን አይደለችም። ይሁን እንጂ ለእስራኤል ጠላት መሆናቸው በሚገባ የተረጋገጠባቸው ወይም ደግሞ ስለ እስራኤል ብዙም የማይጨነቁ ተወዳዳሪዎች፤ ከዚህ የመዋጮ ገንዘብ በርከት ያለው ወደ ተቀናቃኞቻቸው ኪስ ሲሄድ መመልከታቸው ግድ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ የአይሁድ መራጮች በምርጫ ጊዜ ግልብጥ ብለው የሚወጡ ከመሆናቸውም በላይ ካሊፎርኒያ፤ ፍሎሪዳ፤ ኢሊኖይስ፤ ኒውጀርሲ፤ ኒውዬርክና ፔንሲልቬኒያን በመሰሳሉት ግዛቶች በብዛት ተሰባስበው የሚገኙ በመሆኑ ድምጻቸው ፕሬዝዳንት በሚሆነው ሰው ላይ ወሳኝ የሆነ ክብደት ይኖረዋል። እንደዚያም ሆኖ ምንም እንኳ ለዲሞክራቲክ ፓርቲ ያደላ ድጋፍ እንዳላቸው ቢታወቅም ዲሞክራት ተመራጮችን

ሁልጊዜም የመደገፋቸው ነገር የተረጋገጠ አይደለም። ለምሳሌ በ1960 ጆን ኤፍ ኬኔዲ 82 ከመቶ የሚሆነውን የአይሁዳውያን ድጋፍ ያገኙ ሲሆን ጆርጅ ማክጎቨርን ግን በ1972 ያገኙት 64 ከመቶ የሚሆነውን ድምጽ ብቻ ነበር። በ1980 ለፕሬዝዳንትነት የተወዳደሩት ጂሚ ካርተር ደግሞ 45 ከመቶ ድምጽ ብቻ አግኝተዋል። ስለሆነም ተፎካካሪዎች አንባት ለአንባት በተያያዙባቸው ቁልፍ ግዛቶች (key states) የአይሁዳውያን ድምጽ ወሳኝ ሊሆን ይችላል። "እየሩሳሌም ሴንተር ፎር ፐብሊክ አፌርስ" የተባለው ተቋም ባልደረባ ጀፍሪ ሄልሜሪክ ሁኔታውን በመጠኑ አጋንነው ሲጽፉ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹አይሁድ መራጮች በብሔራዊ የምርጫ ውጤት ላይ ወሳኝ የሆነ ተጽዕኖ ያሳድራሉ... የአሜሪካ አይሁዶች ቁልፍ በሆኑ ግዛቶች ተከማችተው መገኘታቸው ከሌሎች ቡድኖች በተለየ ሁኔታ በአሜሪካ ፖለቲካ ላይ ልዩ ሚና እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል››።[58] መራጮች ተቀራራቢ ድምጽ ባላቸው ፕሬዚዳንታዊ ተፎካካሪዎች ዘንድ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ አለ እስከተባለ ድረስ ተፎካካሪዎቹ የእነርሱን ድምጽ ለማግኘት ወሳኝ ግምት የሚሰጠው ርቀት መጓዝ ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው። እየሩሳሌም ፖስት በ2007 ይዞት በወጣው ዘገባው የአይሁዳውያንን ድጋፍ ‹‹ዋሽንግተን ውስጥ እንደ ጸሎት የተለመደና እንደ ቸሪ አበባ ተወዳጅነቱ አስተማማኝ ነው›› በማለት አሞካሽቶታል።[59] ተወዳዳሪዎች በአይሁድ መራጮች ዘንድ እየዞሩ ቅስቀሳ ከማድረግ ይልቅ አይፓክን ጨምሮ በሌሎች የሎቢ ድርጅቶች ዘንድ እውቅና ለማግኘት ይጓጓሉ። ምክኒያቱም ዋና ዋና ከሚባሉት ድርጅቶች አንድ ጊዜ የእውቅና ማህተማቸውን ካስመቱ የገንዘብ መዋጮውም ሆነ እነርሱን የሚመርጠው የአይሁድ ሕዝብ በርካታ እንደሚሆን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ነው።

ይህን ሁሉ ድጋፍ ማግኘት ማለት የእስራኤልን አቋም ያለምንም ተግዳሮት መቀበልና ያንኑ ለማራመድ መስማማት ማለት ነው። ለዚያም ነው ፕሬዝዳንታዊ ተወዳዳሪዎቹ ጆን ኤድዋርድስ፣ ሚት ሮምኒና ጆን ማኬይን 2007 በተካሄደው የሄርዝልያ ኮንፈረንስ ላይ (በእስራኤል ብሔራዊ ጸጥታ ዙሪያ የሚያወያይና አክራሪ በሆነው ኢንስቲትዩት ፎር ፖሊሲ ኤንድ ስትራቴጂ በተባለው ድርጅት የሚዘጋጅ አመታዊ ጉባኤ ነው) የእስራኤል ደጋፊዎች መሆናቸውን በንግግራቸው በግልጽ ያንጸባረቁት። ምክንያቱም በ2004 ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ‹‹ዩናይትድ ስቴትስ የአረብ እስራኤልን

ግጭት ለማስወገድ ሁለቱንም በፍትሃዊነት መያዝ አለባት›› የሚል አቋም በማራመዳቸው መጥፎ እጣ እንዳጋጠማቸው ሃዋርድ ዲን መሆን አይፈልጉም፡፡ በዚያ ምርጫ ወቅት ከሃዋርድ ዲን ተፎካካሪዎች አንዱ የሆኑት ጆሴፍ ሊበርማን ‹‹ሃዋርድ ዲን እስራኤልን ቁልቁል ወደሚወርደው ወንዝ የዘፈቁ ኃላፊነት የማይሰማቸው›› በማለት ዘልፈዋቸዋል፡፡[60] ከዚያም በላይ ደግሞ በኮንግረስ ውስጥ ያሉ ከፍተኛ ዲሞክራቶች ሳይቀሩ የሃዋርድ ዲንን አቋም በመተቸት የፈረሙበትን ጠንካራ ደብዳቤ ለሃዋርድ ለራሳቸው ልከውላቸዋል፡፡ ‹ዘ ቺካጎ ጆዊሽ ስታር› የተባለው ጋዜጣ ባቀረበው ዘገባ መሠረት ‹‹ስማቸው ያልተገለጸ የተለያዩ ሰዎች የአይሁድ መሪዎችን የኢ-ሜይል መቀበያ በማጨናነቅ ሃዋርድ ዲን ለእስራኤል መጥፎ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ስጋታቸውን ያለ በቂ ማስረጃ አሻሃድጉደዋል›› ብሏል፡፡

ይህ ሁሉ ስጋት ዘበት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ሃዋርድ ዲን የማይናወጽ አቋም ያላቸው የእስራኤል ደጋፊ ነበሩና፡፡[62] የምርጫ አማካሪያቸው የቀድሞው የአይፓክ ፕሬዝዳንት ስቲቨን ግሮስማን የነበሩ ሲሆን አቋማቸው ይበልጥ ለዘብተኛ አቋም ከነበራቸው ከአሜሪካን ፎር ፒስ ናው እና መሰል ድርጅቶች ይልቅ ከአይፓክ አቋም ጋር እንደሚቀራረብ ዲን ራሳቸው ተናግረዋል፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ የዲን ባለቤት አይሁዳዊት ሲሆኑ ልጆቻቸውም እያደጉ ያሉት በአይሁድ ወግና ባህል ነበር፡፡ ሃዋርድ ዲን ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል የምታደርገውን እርዳታ ጥያቄ ውስጥ አላስገቡም፡፡ እርሳቸው ያንጸባረቁት አገራቸው ሁለቱንም ወገኖች በማቀራረብና ሚዛናዊ የሆነ ሚና በመያዝ መልካም ደላላ እንድትሆን የማድረግን ሃሳብ ነበር፡፡ ይህ በእርግጥ የለውጥ ፈላጊነት ወይም የተራማጅነት ሃሳብ አልነበረም፡፡ ሆኖም ግን በሎቢው ውስጥ ያሉ ቡድኖች ይህን የሚዛነዊነት ሃሳብ በአረብ እስራኤል ግጭት ላይ ሲሆን ሊቀበሉት አልፈለጉም፡፡ የሃዋርድ ዲን በዲሞክራቲክ ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ አሸናፊ አለመሆን ብዙ ምክንያቶች ያሉት ሲሆን ክስተቱ የሚያሳየን በፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ወቅት የሚፈለገውን ያህል ጽኑ የእስራኤል ደጋፊና አፍቃሪ ሆኖ አለመገኘት በአሜሪካውያን የፖለቲካ ሕይወት ላይ ሊያስከፍል የሚችለውን ዋጋ ነው፡፡

የአሜሪካን አስተዳደራዊ መዋቅር መቆጣጠር

በሎቢው ውስጥ ያሉ ቁልፍ ድርጅቶች በስልጣን ላይ ያለውን አስተዳደር በቀጥታ ዒላማ ውስጥ አስገብተው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ለምሳሌ የፕሬዝዳንቶች ኮንፈረንስ የሚባለው የሎቢ ድርጅት ዋነኛ ተልዕኮው የእርሱን አቋም የሚቃረኑ እርምጃዎች በሁዋይት ሃውስ ሲወሰዱ ተጽዕኖ በማድረግ ለማስቀየር መጣር ነው፡፡ ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተገለጸው ፕሬዝዳንት ጂራርድ ፎርድ የአሜሪካንና የእስራኤልን ግንኙነት እንደገና ለመመርመር እንደሚፈልጉ ባስፈራሩ ጊዜና በ1992 ትልቁ ጆርጅ ቡሽ ለእስራኤል የሚሰጠውን የብርድር ዋስትና በያዙ ጊዜ፤ እንዲሁም ወደፊት በሚመጣው ምዕራፍ 7 ላይ በይበልጥ እንደሚብራራው ከመስከረም አስራ አንዱ ጥቃት በኋላ ጆርጅ ደብሊው ቡሽ የፍልስጤም መንግስት እንደሚመሰረት በገለጡ ጊዜ ሎቢ አድራጊው አካል በኋይት ሐውስ ላይ ጠንካራ ተጽእኖ አሳርፏል፡፡

ሎቢው የአሜሪካ አስተዳደር የሚከተላቸውን ፖሊሲዎች ለመቅረጽ የሚጠቀምበት ከዚህም ይበልጥ ግልጽ የሆነ መንገድ አለ፡፡ ይህውም ያቀዳቸውን ግቦች በሚገባ ማሳካት የሚችለው የእርሱን አመለካከት የሚጋሩ ፖለቲከኞች በአሜሪካ መንግሥት የህግ አስፈጻሚ ክፍል (excutive branch) ሁነኛ ቦታዎች ላይ መቀመጥ ሲችሉ ነው፡፡ ለአብነት ያክል በ1992 የተከሰተን አንድ አጋጣሚ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ የኒውዮርኩ የንግድ ሰው ሃይም ካትዝ አፍቃሪ እስራኤል ለሆኑ የምርጫ ተወዳዳሪዎች ገንዘብ በመስጠት የሚታወቁ ባለሃብት ሲሆኑ ከአይፓክ ፕሬዝዳንት ዴቪድ ስቴይነር ጋር በስልክ ሲጨዋወቱ በምስጢር ተቀርጸው ነበር፡፡ በሁለቱ ሰዎች ጭውውት ወቅት አይፓክ የእስራኤል ደጋፊ ለሆኑ ፓለቲከኞች በምርጫ ውድድር ጊዜ እንዴት የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያደረግላቸው ስቴይነር ካብራሩላቸው በኋላ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጀምስ ቤከር ጋር ተገናኝተው አሜሪካ ለእስራኤል የ3 ቢሊዮን ዶላር እርዳታ የምትሰጥበትን ሁኔታና በብዙ ሰዎች ዘንድ የማይታወቁ ሌሎች ቢሊዮኖች ዶላሮችን እስራኤል የምታገኝበትን መንገድ ማመቻቸታቸውን ለካትዝ ገለጹላቸው፡፡ ከዚያም ቀጠል አድርገው በክሊንተን የምርጫ ዘመቻ ላይ የሚሳተፉ ከደርዘን በላይ ሰዎች እንዲላቸውና ምርጫው ሲያበቃ ሁሉም ታላላቅ በሆኑ ቦታዎች ላይ እንደሚሰየሙ ጨምረው

ነገሯቸው። ካትዝ ይህን የሁለቱን ሰዎች የስልክ ውይይት ይፋ ካደረጉ በኋላ ስቴይነር ስልጠናቸውን ለመልቀቅ የተገደዱ ሲሆን ለካትዝ የነገሯቸው ሁሉ እውነት እንዳልሆነ ቢናዘዙም ያሉትን ላለማመን የሚያስችል ምንም ምክንያት የለም። ሃሳቡን የሚጋራው ግለሰብ ከወሳኝ የፖለቲካ ስፍራ ላይ እንዳይሰየም የሚሻ ማን አለ? ሁሉም ይህን ይፈልጋል።[63] የሎቢ ድርጅቶች ያደረጉትና ሲያደርጉ የኖሩት ይህንን ነው። ለአብነት ያክል የቀድሞው የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ጋል ኖርቶንና ምክትላቸው ጄ. ስቴቨን ግሪልስ በቡሽ አስተዳደር የመንግስት ስልጣን ከመያዛቸው በፊት የነዳጅ ዘይትና የማዕድናት ሎቢስቶች ሆነው ሰርተዋል። እንዲሁም ዳንኤል ኤ. ትሮይ በተደጋጋሚ የትምባሆና የመድሃኒት አምራችና አሰራጭ ኩባንያዎችን በመወከል የህግ ጠበቃ የነበሩ ሲሆን በ2001 ላይ የምግብና የመድሃኒት አስተዳደር አማካሪ ሆነው ተሹመዋል።[64]

የእስራኤል ሎቢም ከዚህ የተለየ አይደለም። ቀደም ብለን እንደገለጽነው የክሊንተን አስተዳደር የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲ ይቀረጽ የነበረው ለእስራኤል ቀረቤታ በነበራቸው ባለስልጣናትና አፍቃሪ እስራኤል ድርጅቶች ነበር። በዚህ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ሚና ሲጫወቱ የነበሩት ሁለት ግለሰቦች ሲሆኑ አንደኛው የቀድሞው የአይፓክ የምርምር ዳይሬክተርና "ዋሽንግተን ኢንስቲትዩት ፎር ኒር ኢስት ፖሊሲ" የተባለውን ድርጅት ከመሠረቱት ሰዎች መካከል አንዱ የሆኑት ማርቲን ኢንዲክ ናቸው። እኚህ ሰው ከ1995-97 በክሊንተን አስተዳደር የብሔራዊ ጸጥታ አማካሪ የነበሩ ሲሆን ከ1997-2000 ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ከ2000-2001 ደግሞ በእስራኤል የአሜሪካ አምባሳደር ሆነው አገልገለዋል። ሁለተኛው ዴኒስ ሮስ ሲሆኑ በመካከለኛው ምሥራቅ የክሊንተን ልዑክ በመሆን ካገለገሉ በኋላ በ2001 የመንግስት ሥልጣናቸውን ትተው ዋሽንግተን ኢኒስቲዩት ፎር ኒር ኢስት ፓሊሲ (ደብሊው አይ. ኤን ኢ. ፒ) የተባለውን ድርጅት ተቀላቅለዋል። ሁለቱም በጁላይ 2000 የካምፕ ዴቪድ ኮንፈረንስ ወቅት የክሊንተን የቅርብ አማካሪዎች ነበሩ።[65]

ምንም እንኳን ኢንዲክም ሆኑ ሮስ የኦስሎውን የሰላም ስምምነትና የሁለት መንግስታትን የመፍትሄ አቅጣጫ በመደገፋቸው ጠጣር መስመር ተከታይ

የሆኑ ፓለቲከኞች እስራኤልን ክደዋል በማለት ያለ አግባብ ቢያወግዟቸውም አቋማቸውን ያራመዱት በእስራኤል መሪዎች ዘንድ ተቀባይነት ባለው ገደብ ልክ ነበር።[66] በምዕራፍ አንድ ለመግለጽ እንደሞከርነው በካምፕ ዴቪድ የተገኘው የአሜሪካ ልዑካን ቡድን አብዛኛውን የመደራደሪያ ሃሳቡን (መመሪያውን) የተቀበለው በቀጥታ ከጠቅላይ ሚኒስትር ኢሁድ ባራክ ነበር ማለት ይቻላል። ስለሆነም ግጭቱን ለማስወገድ የሚያግዙና የአደራዳሪነት ሚናውን የሚያጎሉ ነጻ ሃሳቦችን ማቅረብ አልቻለም። ሌላው ቀርቶ ታህሳስ 2000 ላይ የቀረቡት የክሊንተን የማስማሚያ እሴቶች (Clinton parameters) ከአሜሪካዊ የመደራደሪያ ሃሳብነታቸው ይልቅ የእስራኤል ተጽዕኖ ያረፈባቸው በመሆኑ ጨዋታውን በድል ለመደምደም የሚያስችሉ ሆነው አልተገኙም። እናም ክሊንተን አልተሳካላቸውም። የፍልስጤም ተደራዳሪዎች ደጋግመው እንዳማረሩት በመጀመሪያ ከእስራኤል በኩል እንደመደራደሪያነት የቀረቡላቸው የተወሰኑ ሃሳቦች ዘግየት ብለው በአሜሪካ በኩል የቀረቡላቸው ሲሆን ልዩነቱ አሜሪካ ነጥቦቹን ‹‹የማስማሚያ ሃሳብ (bridging propsal)›› የሚል ታርጋ የምትለጥፍላቸው መሆኑ ብቻ ነበር። አንድ የአሜሪካ አደራዳሪ ቡድን አባል ኋላ ላይ እንዳመኑት፡- ‹‹እስራኤል የምታቀርባቸው የማስማሚያ ሃሳቦች ልክ አሜሪካ እንዳቀረበቻቸው ተደርገው ነበር የሚቆርቡልን›› ብለዋል። በዚህም ምክንያት ነበር የፍልስጤም ተደራዳሪዎች ‹‹አንዱ የእስራኤልን ባንዲራ የያዘ ሌላው የአሜሪካን ባንዲራ የሚያውለበልብ ከሆኑ ሁለት የእስራኤል ተደራዳሪ ቡድኖች ጋር መደራደር አንፈልግም›› በማለት ተቃውሟቸውን ያሰሙት።[67]

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ ጥረት በኋላ የተገኘው ውጤት ማርቲን ኢንዲክም ሆኑ ዴኒስ ሮስ የለፉለትን ያህልና የአሜሪካን ጥቅም ያስጠብቃል ብለው እንዳሰቡት አልነበረም። ከዚያ ይልቅ የእስራኤል ደጋፊዎች ሁኔታዎችን በማወሳሰብና ድርድሩን አስቸጋሪ እንዲሆን በማድረግ የአሜሪካ አስተዳደር በእስራኤል መንግሥት ላይ የበኩሉን ተጽዕኖ እንዳያሳርፍና ሰላም እንዳይሰፍን ማድረጉን መርጠዋል። በእኛ እምነት ይህ ድርጊታቸው አጠቀላዩን የኦስሎ የስምምነት ሂደትና የካምፕ ዴቪድንም ስብሰባ መና ያስቀረ ነበር።

ችግሩ ይበልጥ የጎላውና መውጪያ መንገድ በሌለበት አዘቅት ውስጥ የተወሸቀው በሁለተኛው የቡሽ የአስተዳደር ዘመን አፍቃሪ እስራኤል የሆኑ የኒዎኮንሰርቫቲቭ አባላት በመንግስቱ አስተዳደር በተሰገሰጉ ጊዜ ነበር። ከእነዚህ ፖለቲከኞች መካከል ኢሊዮት አብራምስ፣ ጆን ቦልተን፣ ዶግላስ ፌይዝ፣ አሮን ፍሪድበርግ፣ ጆን ሃናህ፣ አይ ሊዊስ ሊቢ፣ ዊሊያም ሉቲ፣ ሪቻርድ፣ ፐርል፣ ፓውል፣ ዎልፎዊትዝና ዴቪድ ውርምሰር ይገኙበታል። በዚህ መጽሀፍ ክፍል ሁለት ላይ በዝርዝር እንደምንዳስሰው እነዚህ ባለስልጣናት እስራኤልን የሚጠቅሙ ፖሊሲዎችን በጽናት ከማራመዳቸውም በላይ በሎቢው ውስጥ ከሚገኙ ቁልፍ ድርጅቶች ድጋፍ ይደረግላቸው ነበር።

በተመሳሳይ ሁኔታ እስራኤልን የሚተቹ ሰዎች በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ ወሳኝ የተባሉ ቦታዎችን እንደማያገኙ በሎቢው ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶች እርግጠኛ መሆን ይፈልጉ ነበር። በ1987 የቀድሞው የአይፓክ ፕሬዝዳንት ቶም ዳይን አይፓክ ለምን የፕሬዝዳንቱን አማካሪዎች በጥንቃቄ እንደሚመርጥ ለጠየቃቸው ጋዜጠኛ ሲመልሱ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ወንድሜ! አንድ ምሳሌ ልስጥህ። በ1988 ለፕሬዝዳንታዊ ውድድር ከቀረቡት አንዱ እኛን ከጠራን በኋላ ‹እኔ አሁን የማስበውን በግልጽ ልነግራችሁ እሻለሁ። በምርጫው ካሸነፍኩ እገሌና እገሌን ከፍተኛ ስልጣን ልሰጣቸው አስቤያለሁ። እናንተስ ምን አስተያየት አላችሁ? አለን።›› ዳይን ምን መልስ እንደሰጡት ሲናገሩ ‹‹አውራ ጣቴን ወደላይ ቀስሬ ደስተኛ መሆናችንን ገለጽኩለት›› ብለዋል። ይሁን እንጂ ሌሎቹ ደግሞ እድለ ቢሶች ሆነዋል።[68] ለምሳሌ ጅሚ ካርተር ጆርጅ ቦልን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አድርገው ሊመርጧቸው ፈልገው ነበር። ሆኖም ግን ቦል እስራኤልን የሚነቅፉ በመሆናቸው ሎቢው እንደማይስማማ በማሰብ ነበር የተዋቸው።[69] በተመሳሳይ ሁኔታ ሪቻርድ ማሪዮስ የተባሉት የሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ገለጻ ሰጪ (lecturer) በ1995 የምክትል ፕሬዝዳንት አል ጎር ዋና የንግግር ጸሐፊ ሆነው የተቀጠሩ ቢሆንም ገና ስራ ሳይጀምሩ ነበር የተባረሩት። እንደዚያም ሊሆን የቻለው ዘ-ኒው ሪፐብሊክ የተባለው ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ማርቲን ፔርቴዝ (የአል ጎር ቅድመ ምረቃ መምህርና የምስጢር ጓደኛ) ማሪዩስ በ1992 በሃርቫርድ

መጽሔት ላይ የሰጡትን አስተያየት ተንተርሶ ጸረ- ሴማዊ መሆናቸውን በሃሰት በመናገሩ ነበር።[70]

ይህ ከሆነ ከጥቂት ዓመታት በኋላ 2001 ላይ ብሩስ ሪድል በብሔራዊ ጸጥታ ምክር ቤት የመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ ሃላፊነታቸውን ሲለቁ "ዘ ኒው ሪፓብሊክ" የተሰኘው ጋዜጣ ‹‹ፔንታጎን ሪድልን እንዲተኩ የሰየማቸው የመካከለኛው ምሥራቅ ባለሙያዋ አሊና ሮማኖውስኪ ለአይሁዳዊቱ አገር ያላቸው የድጋፍ ስሜት በቂ አይደለም በማለት የፔንታጎን ተቃውሞ በማቅረባቸው ሹመቱ አልጸደቀላቸውም›› የሚል ዘገባ ይዞ ወጣ።[71] በአሊና ምትክ ቦታውን የያዙት በኢራን ኮንትራ ቅሌት አስፈላጊ የሆነውን መረጃ ከኮንግረስ ደብቀዋል በሚል ክስ ጥፋተኛ ሆነው የተገኙት ኢሊዮት አብራምስ ነበሩ። አብራምስ ከሚገባው በላይ የእስራኤል አፍቃሪ ከመሆናቸውም በላይ ቀደም ሲል በ1997 በጻፉት መጽሀፍ ‹‹አምላክ ለአብራሐም በገባለት ቃል ኪዳን የጸኑና ሕጉን ጠብቀው የኖሩ አይሁዳውያን የተመረጡ ሕዝቦች በመሆናቸው ከእስራኤል ግዛት ውጭ በሚኖሩ ጊዜ ከሌሎች ሕዝቦች ተለይተው ሊታዩና ክብር ሊቸራቸው ይገባል›› በማለት ተናግረዋል።[72] እንግዲህ በዩ. ኤስ አሜሪካ መንግስት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ወሳኝ የሆነውን የመካከለኛውን ምሥራቅ ጉዳይ በኃላፊነት የያዙት ግለሰብ ማንነት ይህን ነበር የሚመስለው። ‹‹ለእስራኤል መንግሰት›› ይላል የሃ- ኤሬትዝ ጋዜጣ ሪፖርተር ናታን ጉትማን፡- ‹‹የኢሊዮት አብራምስ በዚያ ቦታ ላይ መመደብ ከሰማይ የወረደ ስጦታ ነው።››[73]

ምዕራፍ ስድስት

የህዝብ አስተያየቶችን መጫን

የሎቢው ማዕከላዊና ዋነኛ የትኩረት ነጥብ እስራኤልን አስመልክቶ የሚሰነዘሩ አስተያየቶችና ፖለቲካዊ አመለካከቶች ሁሉ በምዕራፍ 2 እና 3 እንደተገለጸው ስትራቴጂያዊና ሞራላዊ ታሳቢዎችን የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ያንንም ለማድረግ የሚጠቀመው ዘዴ የተለያዩት የሎቢው አካላት ደግመውና ደጋግመው የእስራኤልን ስትራቴጂያዊ ጠቃሚነት በማስጮህ የእስራኤልን ገጽታዎች የማሰማመር አካሄድ እንዲከተሉ ማድረግ ነው፡፡ የዚህ ሁሉ ጥረት ዋና ዓላማ ሕዝቡ የአሜሪካና የእስራኤል ፍላጎት አንድና ተመሳሳይ መሆኑን (ሃቁ በተቃራኒው ቢሆንም) እንዲቀበል ለማሳመን ነው፡፡

በተመሳሳይ ጊዜ በሎቢው ውስጥ ያሉ ቡድኖች የእስራኤልን ፖሊሲ የሚተቹ ወይም ‹‹ልዩ ግንኙነት›› የተባለውን የሚገዳደሩ ሰዎችን በፖለቲካው ምህዳር ብዙ አድማጭ እንዳያገኙ ለመከላከል ይጥራሉ፡፡ በዚሁ መሠረት ሎቢው አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን ዝም ለማሰኘት ጠንካራ የሚባል ስልት ይጠቀማል፡፡ ይህ ስልት ጸረ- ሴማዊነት ወይም ጸረ- እስራኤል በመባል ይታወቃል፡፡ በሕዝቡ መካከል የሚነሱ ውይይቶችን ማፈን ካልተቻለ አፍቃሪ እስራኤል በሆነ አካሄድ እንዲፈጸሙ ማድረጉ ለምርጫ የሚቀርብ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ግልጽና ሃቀኛ የሆነ ውይይት ቢካሄድና እስራኤል በሃይል በያዘቻቸው የፍልስጤማውያን ግዛቶች የምታራምዳቸው ፖሊሲዎች፣ የእስራኤል ታሪክ፣ ሎቢው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እስራኤልን እንዲጠቅም በማድረግ በሚጫወተው ሚና እና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ የአሜሪካ ሕዝብ ጥያቄ ማንሳቱ አይቀርም፡፡ በመጨረሻም ዩናይትድ ስቴትስ በመካከለኛው ምሥራቅ የምትከተለውን ፖሊሲ እንድትቀይርና ከእስራኤል ጋር የሚኖራትም ግንኙነት በይበልጥ የአሜሪካን ጥቅም የሚያስጠብቅ እንዲሆን ጫና ማድረጉ የሚጠበቅ ነገር ነው፡፡

በሎቢው ውስጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ ክፍሎች እስራኤልን የሚመለከቱና በመገናኛ ብዙሃን (media)ና በህትመት ውጤቶች (press)፣ በመንግስት አማካሪ አካላት (think tanks)፣ እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚደረጉ የሃሳብ ልውውጦች፣ ትምህርታዊ ስብሰባዎች ወዘተ.. ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ተቋማት የህዝብን አመለካከት በመቅረጽ የሚጫወቱት ሚና ታላቅ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ሎቢስቶች እስራኤልን አዎንታዊ ገጽታ ለማላበስ የእስራኤልን ያለፉትንም ሆነ የአሁን ባህሪዋን የሚያጠያየቅን ማንኛውም አካል ለማግለልና ለመነጠል ረዥም ርቀት ይጓዛሉ፡፡

መገናኛ ብዙሃንን በሚገባ መጠቀም

እስራኤልን በሚመለከት የሚሰነዘሩ የህዝብ አስተያቶች አዎንታዊ እንደሆኑ እንዲቆዩ ለማድረግ ቁልፍ የሆነው ስልት ዋና ዋና የሚባሉት የመገናኛ ዘዴዎች የሚሰጡት ሽፋን የእስራኤልን አዎንታዊ ገጽታ የሚያጎላ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ ምንም እንኳን አልፎ አልፎ እስራኤልን የሚተቹና የሚነቅፉ ሃተታዎችና ገለፃዎች በመላዋ ዩናይትድ ስቴትስ የሚዳረሱ ቢሆንም በአብዛኛው ግን የአሜሪካ መገናኛ ብዙሃን ለእስራኤል የሚያደላና ወገናዊነትን የሚያሳይ ሽፋን ነው ሲሰጡ የሚታዩት፡፡

ይህ ሁኔታ ደግሞ አንዳንድ የጸረ- ሴማዊነት እንቅስቃሴ ደጋፊዎች ‹‹መገናኛ ብዙሃኑን ሁሉ አይሁዶች ተቆጣጥረውታል›› እንዲሉ አድርጓቸዋል፡፡ ማርቲን ፔርትዝና ሞርትማየር ዙከርማንን የመሳሰሉት የአሜሪካ አይሁዶች እስራኤልንና መካከለኛው ምሥራቅን አስመልክተው የራሳቸውን አቋም ለማራመድ መገናኛ ብዙሃንን በስፋት መጠቀማቸው አያጠያይቅም፡፡ ይህ ባሕሪ ደግሞ ህጋዊ እንደመሆኑ መጠን ያን ያክል የሚያስደንቅ ሊሆን አይገባም፡፡ ምክንያቱም በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ምሁራን ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች ከተመቻቹላቸው ተመሳሳይ ድርጊት ከመፈጸም ስለማይቆጠቡ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የእስራኤልንና የአሜሪካን ግንኙነት መተቸት የሚወዱ መገናኛ ብዙሃን ባለቤቶች፣

አሳታሚዎች፣ ዋና አዘጋጆች፣ የአምድ አዘጋጆችና ሪፖርተሮች መኖራቸው እርግጥ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ለእስራኤል ምንም ዓይነት የተለየ ስሜት የሌላቸውና መጥፎ ድርጊቶችን መተቸት ይበልጥ ምቾት የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ ተጽዕኖ የማድረግ ችሎታ ያላቸው አንዳንድ አፍቃራ እስራኤል የሆኑ ሆኖም ግን ያችን አገር በተመለከተ ይበልጥ ግልጽ የሆነ ውይይት እንዲደረግ የሚፈልጉ እንዳሉም እንዲሁ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም ‹‹አይሁዳውያንና አፍቃራ- እስራኤል ሃይሎች መገናኛ ብዙሃንን እንዳለ ተቆጣጥረውታል›› የሚለው አባባል የተሳሳተ ነው፡፡ እርግጥ ነው ሎቢው የመገናኛ ቡዙሃን ስለ እስራኤል የሚናገሩትንና የሚጽፉትን በራሱ አቅጣጫ ለመቃኘትና ተጽዕኖውን ለማሳረፍ ታላቅ ርብርብ የሚያደርገው በቀጥታ ስለማይቆጣጠራቸው መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ የነገሩን ሌላ አቅጣጫ ማየት ከቻልን ደግሞ እነዚያን መገናኛ ብዙሃን ሎቢው በራሳቸው መንገድ እንዲሰሩና ያሻቸውን እንዲያደርጉ ቢተዋቸው ኖሮ አፍቃሪ እስራኤል ለሆኑ ጉዳዮች ሽፋን የማይሰጡ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም የአሜሪካንና የእስራኤልን ግንኙነት፤ የመካከለኛውን ምሥራቅ ሁኔታና አሜሪካ የምትከተላቸውን ፖሊሲዎች እንደልባቸው በመተቸት አፍራሽ የሆነ ተጽዕኖ ያስከትሉ ነበር፡፡ መገናኛ ብዙሃን ስለ እስራኤል ያሻቸውን የሚናገሩበትና የሚጽፉበት ቦታ አለ የሚባል ከሆነ አይሁዶች ሜዲያውን በተቆጣጠሩባት በራሷ በእስራኤል ውስጥ ብቻ ነው፡፡

ሎቢው እስራኤልን አስመልክቶ የሚከተለው አቋም ዋና ዋና በሚባሉት የአሜሪካ የመገናኛ ብዙሃን የሚንጸባረቅ ሲሆን ለዚህም ዋነኛው ምክንያት በርካታ ቁጥር ያላቸው እስራኤልን የሚመለከት ሃተታ የሚያቀርቡ ሰዎች (commentators) ራሳቸው አፍቃራ- እስራኤል በመሆናቸው ነው፡፡ በ1976 የተደረገ በአገር ውስጥ የበጎ ፈቃድ ቡድኖችንና የመካከለኛው ምስራቅ ፖሊሲን የሚያነጻጽርን ጥናት አስመልክተው ሮበርት ኤ ትሪስ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹ከ1966-1974 ባለው ጊዜ ውስጥ አፍቃሪ አረብ በሆኑ ቡድኖች ውስጥ በነበረው የፖለቲካ ሽባነት ምክንያት እጅግ ገናና በሆኑት ጋዜጦች ላይ እነርሱን ደግፈው የሚጽፉ አምደኞችን ማግኘት አልቻሉም ነበር፡፡›› ትሪስ ጨምረው ሲገልጹ ‹‹በአንጻሩ አፍቃሪ እስራኤል ቡድኖች የመገናኛ

ብዙሃን ድጋፍ ከአይሁድ ብሔር ብቻ ሳይሆን በመላ አገሪቱ በስፋት ተነባቢነት ካላቸው ጋዜጦች ዋና አዘጋጆች ጭምር ያገኙ ነበር›› ብለዋል፡፡ ከአፍቃሪ- አረብ ቡድኖች ይልቅ አፍቃሪ- እስራኤል ቡድኖች የመገናኛ ብዙሃን ሽፋኖችን ለእነርሱ በሚስማሙ መልኩ በመቅረጽ የተዋጣላቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ በ1970 የፕሬዝዳንቶች ኮንፈረንስ የተባለው የሎቢ ድርጅት አንድ ሺህ ሰባት መቶ ለሚሆኑ የህትመት ውጤቶች፤ የሬዲዮና ቴሌቭዥን ዝግጅት ክፍሎች (በፎቶግራፍ የተደገፉና የእስራኤልን መልካም ገጽታ የሚያሳዩ) የመረጃ ክምችቶችን (press kits) አሰራጭቷል። እንደትሪስ አነጋገር፡- ‹‹በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ የዜና ማሰራጫ ድርጅቶችን፣ የማህበረሰብ የሬዲዮ ጣቢያዎችን፣ የሙያ ማህበራት ልሳኖችን፣ ዋና ዋና የሚባሉና በብሔራዊ ደረጃ ሽፋን የሚሰጡ ጋዜጦችን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰፊ ሽፋን ያላቸው የዜና ማሰራጫዎችን እያንዳንዳቸውን በተሳካ ሁኔታ በመጠቀም አፍቃሪ እስራኤል ቡድኖች ከአረባውያኑ ቡድኖች እጅግ የተሻሉ ሆነው ቆይተዋል››[1]

ከዚያ በኋላ ባሉት ጊዜያትም ቢሆን ነገሮች ብዙም አልተለወጡም፡፡ መካከለኛው ምሥራቅን በሚመለከት በምሁራን መካከል የሚካሄደው ክርክር ኤሪክ አልተርማን በ2002 እንደጻፈው ‹‹እስራኤልን ለመተቸት አስበው በማያውቁ ሰዎች ተጽዕኖ ስር ወድቋል፡፡›› ኤሪክ አልተርማን ዋና ዋና በሚባሉ ጋዜጦችና መጽሔቶች በዓምድ አዘጋጅነት የሚጽፉና በታላላቅ የሬዲዮና ቴሌቭዥን ጣቢያዎች ሐተታ የሚያቀርቡ ሃምሳ ስድስት የሚሆኑ የማይናወጽ አቋም ያላቸው የእስራኤል ደጋፊ ጋዜጠኞችን ዘርዝሯል፡፡ በተቃራኒው አልተርማን የእስራኤልን አቋም በጽናት የሚተቹትና አፍቃሪ አረብ የሆኑት ጋዜጠኞች አምስት ብቻ መሆናቸውን ገልጿል፡፡[2] ምንም እንኳን ጥቂት አንባቢያን ይህን የአልተርማንን ጽሑፍ ካነበቡ በኋላ ‹‹አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ጭብጦች ዙሪያ ያጠነጠነ የዳሰሳ ውጤት ነው›› በማለት፣ እንዲሁም በዝርዝሩ ውስጥ ከተካተቱት ሰዎች መካከል የተወሰኑት በሞት የተለዩ መሆናቸውን እግምት ውስጥ አስገብተው ሊያጣጥሉት ቢሞክሩም እርሱ የተነሳበትን ዋነኛ የትኩረት ነጥብ ግን ሊያስተባብሉት አልቻሉም፡፡[3]

ለአብነት ያክል በኒው ዮርክ ታይምስና በዋሽንግተን ፖስት ጋዜጦች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ መካከለኛው ምስራቅን አስመልክተው የሚጽፉ የአምድ አዘጋጆችን እንመልከት፡፡ የኒውዮርክ ታይምሶቹ ዊሊያም ሳፊርና ኤ. ኤም. ሮዜንታል ጥልቅ ስሜት ያላቸው የእስራኤል ደጋፊዎች ናቸው፡፡ (ሳፊር የአሪዮል ሻሮን አድናቂ ነው። ዴቪድ ብሩክስም ቢሆን የእስራኤልን አቋም በጽናት የሚደግፍ ነው፡፡) ቶማስ ኤል ፍሪድማን ይበልጥ መካከለኛ አቋም ያለውና እስራኤል የምትወስዳቸውን አንዳንድ እርምጃዎች (አልፎ አልፎ ሎቢውን ጭምር) የሚተች ጋዜጠኛ ይሁን እንጂ በምንም መልኩ ለፍልስጤማውያን ወግኖም ሆነ የእነርሱን ዓላማ የሚያራምድ ጽሑፍ አቅርቦ የማያውቅ ከመሆኑም በላይ አሜሪካ ከእስራኤል ራሷን እንድታርቅ የሚጠይቅ ጽሑፍ አልጻፈም፡፡ ኒኮላስ ዲ. ክሪስቶፍ በተደጋጋሚ አሜሪካ የምትከተለውን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በመተቸት ይታወቃል፡፡ በ2007 በጻፈው አንድ አወዛጋቢ ጽሑፍ ዩናይትድ ስቴትስ ከእስራኤል ጋር ያላትን ግንኙነት አስመልክቶ ሕዝቡ በግልጽ እንዲወያይ ጠይቋል። ይሁን እንጂ እርሱም ቢሆን አብዛኛውን ጊዜ በጽሑፎቹ መካከለኛው ምሥራቅን በተደጋጋሚ የመዳሰስ አዝማማያ የማያሳይ ሲሆን አፍቃሪ ፍልስጤም እንዳልሆነ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡[4] ማውረን ዶድ አፍቃሪ እስራኤል የሆኑ ኒዎኮንሰርቫቲቮችን በሰላ ሂስ የምትጠርብ ብትሆንም እርሷም እንደ ክሪስቶፍ ስለ አይሁዳዊቷ አገር ወይም ዩ. ኤስ አሜሪካ ከእርሷ አኳያ ስለምታራምደው ፖሊሲ የምትጽፈው አልፎ አልፎ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም በኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ላይ በቋሚነት የሚጽፍና ፍልስጤማውያንን በጽናት የሚደግፍ ወይም ሌላው ቢቀር በ2001 ላይ በጡረታ የተገለለውን አምድ አዘጋጅ አንቶኒ ሊዊስን የመሰለ ሚዛናዊ አቋም የሚከተል የለም ብሎ መደምደም ያስኬዳል፡፡

ዋሽንግተን ፖስትን በተመለከተም እንዲሁ እስራኤልን በጽናት የሚደግፉ በርካታ የአምድ አዘጋጆች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የመጡ ሲሆን ከእነርሱ ውስጥ ጂም ሆግላንድ ሮበርት ኬጋን፣ ቻርለስ ካራውታመርና ጆርጅ ዊል ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ዘግየት ብለው ከመጡት ውስጥ ደግሞ ሚካኤል ኬሊ እና ዊሊያም ክሪስቶል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ክሪስቶል፣ ዊክሊ ስታንዳርድ

የተባለውን ጋዜጣ የሚመራ ሲሆን በኒው ዮርክ ታይምስም የራሱ የሆነ አምድ አለው። እነዚህ ግለሰቦች አፍቃሪ እስራኤል አቋም ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ መለስተኛ አቋም ካላቸው ፖለቲከኞች ይልቅ የአክራሪውን ሊኩድ ፓርቲን ሃሳቦችና ፖሊሲዎች ጭምር የሚያራዱ ናቸው። ሪቻርድ ኮኸን በዋሽንግተን ፖስት ላይ መካከልኛውን ምሥራቅ አስመልክቶ የሚጽፍ ቢሆንም ልክ እንደ ኒውዮርክ ታይምሱ ፍሬድማን ሁሉ እስራኤልን የሚመለከቱ ምሁራዊና የተዋጣላቸው ትችቶችን ነው የሚያቀርበው። እነዚህ በየዕለቱ የሚታተሙና በስፋት የሚነበቡ ጋዜጦች የአረቦችንና የፍልስጤማውያንን አቋም ደግፎ በጽናት የሚጽፍ አንድም ቋሚ የአምድ አዘጋጅ ቀጥረው ወይም ኖሮአቸው አያውቅም።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ እስራኤልን በተደጋጋሚ የሚተቸው ሮበርት ኖቫክ ሲሆን የእርሱ አምድ ቺካጎ ሰን ታይምስ በተባለው ጋዜጣ ላይም ከፖስት ጋር በተደረገ ስምምነት (syndicate) መሠረት ይወጣል። እንደዚያም ቢሆን ኖቫክ የፍልስጤማውያንን ጉዳይ የሚያራምድ ታጋይ (champion) ነው ለማለት አይቻልም። እውነታው ከአፍቃሪ እስራኤላውያኑ ሳፊርና ክራውታመር ቀርቶ መለስተኛ አቋም ካላቸው ፍሬድማንና ኮኸን ጋር እንኳን የሚነጻጸሩ ጸሐፍት በዚያኛው ወገን በኩል የሌሉ መሆኑ ነው። ለምሳሌ ሎስ አንጀለስ ታይምስ ጋዜጣ ማክስ ቡት፤ ጆናታን ቼይትና ጆን ጎልድበርግ የተባሉ የእስራኤል ታማኝ ደጋፊዎችን ጽሑፎች በቋሚነት ያወጣል። ሆኖም ግን እስራኤልን የሚተች ወይም ሌላው ቢቀር የፍልስጤማውያኑን አቋም የሚያንጸባርቅ አንድም ሰው አልቀጠረም።

ምንም እንኳን እነዚህ ጋዜጦች የእስራኤልን ፖሊሲ የሚተቹ የተጋባዥ ጸሐፊዎችን መጣጥፎች አልፎ አልፎ የሚያወጡ ቢሆንም በዚያኛው በኩል ካለው ጋር ሲነጻጸር እዚህ ግባ የሚባል ተጽዕኖ የሚፈጥሩ አይደሉም። በሌላ በኩል ደግሞ እስራኤልን በመተቸት በእንግሊዝ ጋዜጦች ላይ የሚጽፉትን ሮበርት ፊስክ እና ፓትሪክ ሲልን የሚስተካከል አንድም አሜሪካዊ ጸሐፊ የሌለ ሲሆን እስራኤላዊያን የሆኑት አሚራ ሃስ፣ አኪፋ ኤልዳር፣ ጌዲዮን፣ ሌቪና ብራድሊ በርስተንን ደግሞ የአገራቸውን የተወሰኑ

ፖሊሲዎች በግልጽ በመተቸት በርቀት እንኳን የሚጠጋቸው የለም። እዚህ ላይ ዋናው ነጥብ እነዚህ ጸሀፊዎች ሁልጊዜም ትክክል ናቸው፤ እንዲሁም አፍቃሪ እስራኤል የሆኑት ተንታኞች ደግሞ ስህተተኛ ናቸው ማለት አይደለም። ዋናውና ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ እነዚህን የመሰሉ አፍቃሪ አረብ (ፍልስጤም) ወይም እስራኤልን የሚተቹ ጸሐፍት ዋና ዋና በሚባሉት የአሜሪካ ጋዜጦች ላይ የሌሉ መሆኑ ነው።

አፍቃሪ እስራኤል የሆኑ አቋሞች በዋና ዋና ጋዜጦች ርዕሰ አንቀጾች ላይ መውጣታቸውም ሊያስደንቀን አይገባም። የዎል ስትሪት ጆርናል ዋና አዘጋጅ ሮበርት ባርትሌይ አንድ ጊዜ ሲናገር ‹‹ሻሚር፣ ሻሮንና፣ ቢቢ የሚፈልጉት ነገር ምንም ይሁን ምን ለእኔ በጣም ጥሩ ሆኖ ነው የሚታየኝ›› ብሏል።[5] ሌላው አስደናቂ ጉዳይ ቺካጎ ሰን ታይምስ፣ ዘ-ኒው ዮርክ ሰን እና ዋሽንግተን ታይምስ በቋሚነት የሚያወጧቸው ርዕሰ አንቀጾች ሙሉ በሙሉ እስራኤልን የሚደግፉ ከመሆናቸው የተነሳ የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስቴር የማስታወቂያ ቢሮ የሚያዘጋጃቸው ነው የሚመስሉት። ለኒው ዮርክ ታይምስ ምስጋና ይግባውና አንዳንድ ጊዜ በርዕሰ አንቀጾቹ ላይ የእስራኤልን ፖሊሲዎች ሲተች ይታያል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ ይህ ትችት አልፎ አልፎ በጠንካራ ቃላት ሲታጀብ ይስተዋላል። ታይምስ በግልጽ እንዳስቀመጠው ‹‹ፍልስጤማውያን የራሳቸውን መንግስት ለመመስረት የሚያበቃቸው በቂ ምክንያት አላቸው›› እንደዚያም ቢሆን ታይምስ ሁለቱን ወገኖች ለዓመታት ያስተናገደበት መንገድ ሚዛናዊነት የጎደለው መሆኑ ተጨባጭ ሃቅ ነው።[6] የቀድሞው የኒውዮርክ ታይምስ ዋና አዘጋጅ ማክስ ፍራንክል ለርዕሰ አንቀጽነት በሚመርጣቸው ጉዳዮች ላይ አፍቃሪ እስራኤል መሆኑ ተጽዕኖ ያሳድርበት እንደነበር ሳይሸሸግ በማስታወሻው ላይ እንደሚከተለው አስፍሮታል፡-‹‹በአንደበቴ ለማረጋገጥ ከምችለው በላይ የእስራኤል ጽኑ ደጋፊ ነበርኩ። ይህም ደጋፊነቴ ለእስራኤል በነበረኝ እውቀትና እዚያ በነበሩኝ ጓደኞቼ ምክንያት እየተጠናከረ የሄደ ከመሆኑ የተነሳ መካከለኛው ምሥራቅን የሚመለከቱ ሃተታዎችን እኔ ራሴ ነበርኩ የምጽፋቸው። ከአይሁዳውያን ይልቅ ብዙ አረቦች

እንደሚያረጋግጡት እነዚያን ጽሑፎች ሁሉ ያቀናበርኳቸው ከአፍቃሪ እስራኤል አመለካከቱ በመነሳት ነበር፡፡››[7]

ኮሜንታሪ፣ ዘ-ኒው ሪፐብሊክና ዊክሊ ስታንዳርድን የመሳሰሉት መጽሔቶችም ጭምር በሁሉም አቅጣጫ በቀናዒነት ነበር እስራኤልን ሲደግፉ የቆዩት። የቀድሞው የኮሜንታሪ አዘጋጅ ኖርማን ፓድሆርትዝ አንድ ጊዜ እየሩሳሌም ውስጥ ለተሰበሰቡ ጋዜጠኞች የሚከተለውን መናገሩ ይህን ሃቅ የሚያረጋግጥ ነው፡- ‹‹በአይሁዳውያንም ሆነ በሌሎች የሕትመት ውጤቶች ላይ የሚጽፉ አይሁዳዊያን ሚና በእስራኤል ላይ የሚሰነዘረውን ጥቃት መመከት እንጂ ከአጥቂዎቹ ጋር አብሮ ማጥቃት አይደለም፡፡››[8] ማርቲን ፔሬትዝ የተባለው የብዙ ዘመን የኒው ሪፓብሊክ አዘጋጅ አንድ ጊዜ ‹‹በእስራኤል መንግስት ፍቅር ውድቁያለሁ›› በማለት የተናገረ ሲሆን በጋዜጣው ላይም ከእስራኤል መንግሥት ፓርቲዎች የአንዱ እጅ እንዳለበት ሳይሸሸግ ይፋ አድርጓል፡፡[9]

እስራኤል ውስጥ የተፈጸሙ የተለያዩ ክስተቶችን የሚዘግቡ የመገናኛ ዘዴዎች በርዕስ አንቀጾቻቸው ከሚያወጡዋቸው መልዕክቶች አነስ ባለ ሁኔታ ነው ለእስራኤል የሚያደሉት፡፡

ምክንያቱም አብዛኞዎቹ ዘጋቢዎች ተጨባጭ የሆነን ነገር ይዘው የሚዘግቡና ሃቀኞች ሆነው መገኘት ይፈልጋሉ ብቻ ሳይሆን በሃይል በተያዙት መሬቶችና በደቡብ ሊባኖስ እስራኤል የምታሳየውን ጸባይ በተጨባጭ አድሏዊ ሽፋን ለመስጠት ስለሚቸገሩም ጭምር ነው፡፡ እንደዚያም ቢሆን በሎቢው ውስጥ የሚገኙ ቡድኖች እስራኤልን የሚመለከቱና የማያስደስቷቸውን ዘገባዎች ለማጣጣል ደብዳቤ የመጻፍ ዘመቻ ያደርጋሉ፣ ስላማዊ ሰልፍ ያካሄዳሉ፣ እንዲሁም የህትመት ውጤቶቹን ሰዎች እንዳይገዟቸው እስከማሳደም ድረስም ርቀው ይሄዳሉ፡፡ ፎርዋርድ የተባለው የአሜሪካ አይሁዶች ጋዜጣ መጋቢት 2002 ላይ ባወጣው ዘገባው ላይ ‹‹ጸረ- እስራኤል የሆነ መልዕክት ያዘለን ማንኛውም የመገናኛ ዘዴን ሽፋን ነቅሶ ማውጣትና መቃወም ለብዙ የአሜሪካ አይሁዶች 6000 ማይሎች ርቆ ከሚገኘው የመካከለኛው ምሥራቅ ግጭት ጋር

በስሜት ያገናኛቸዋል። የህልውናቸውን ጉዳይ እንደማረጋገጥ አድርገውም ነው የሚያስቡት›› ብሏል።[10] አንድ የሲ. ኤን.ኤን. ጋላፊ ‹‹አንዳንድ ጊዜ ጸረ-እስራኤል ታሪክ እንዳስተላለፍን በመግለጽ ተቃውሟቸውን የሚያሰሙ ከ6000 በላይ ኢ.ሜይሎችን በአንድ ቀን ብቻ እናገኛለን›› በማለት ተናግረዋል። ቺካጎ፣ ትሪቢዮን፣ ዘ-ሎስ አንጀለስ ታይምስ፣ ዘ ሚያሚ ሔራልድ፣ ዘ-ኒው ዮርክ ታይምስ፣ ፊላደልፊያ ኢኒኳየረርና ዋሽንግስትን ፖስታን የመሳሰሉት ጋዜጦች ደግሞ ባወጧቸው መካከለኛው ምሥራቅን የሚመለከቱ ሪፖርቶች ምክንያት ከፍተኛ የሆኑ የተጠቃሚ አድማዎች (consumer buycotts) አጋጥመዋቸዋል።[11] አንድ ዜና አጠናቃሪ ሚካኤል ማሲንግ ለተሰኘው ጋዜጠኛ ‹‹ጋዜጦች አይፓክንና ሌሎች ቡድኖችን ይፈሯቸዋል። ምክንያቱም ከእነርሱ በኩል የሚመጣ ጫና ምህረት የሌለው ነው። ከእነርሱ ጋር የተጋጨን ጋዜጣ ደፍሮ የሚኾው አዘጋጅ አይገኝም›› በማለት ጉዳዩን አፍርጦታል።[12] በኒውዮርክ የሚገኘው የእስራኤል ቆንስላ ጽ/ቤት የቀድሞ ቃል አቀባይ የነበሩት ሜናሂም ሻሌቭ በአንድ ወቅት እንዲህ የሚል አስተያየት ሰጥተዋል፦ ‹‹እርግጥ ነው ጋዜጠኞች፣ አዘጋጆችና ፖለቲከኞች በራሳቸው ላይ ቅድመ ምርመራ (self censorship) እያካሄዱ እንደሆነ ይሰማኛል። ምክንያቱም እነዚህ አካላት እስራኤልን ከመተቻቸው በፊት ቢያንስ ሁለት ጊዜ ማሰብ ያለባቸው በመሆኑ ነው። እንደዚያ የማያደርጉ ከሆነ በሰዓታት ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ የተናደዱ ሰዎችን ስልኮች ማሰተናገድ ይጠበቅባቸዋል። የአይሁዳውያን ሎቢ ወሳኝ የሆነ ጫና የመፍጠሪያ ዘዴ ነው።››[13]

የአሜሪካ አይሁድ የህትመት ውጤቶች ራሳቸው ከዚህ ጫና ነጻ አይደሉም። በ1989 ለምሳሌ ላሪ ኮለር የተባለውን ዘጋቢ የአይፓክን ታሪክ በሚመለከተው ዝግጅት ላይ እንዲሳተፍ እንዳይመድበው የአይፓክ የመገናኛ ዘዴ (media) ዳይሬክተር ቶቢ ደርሽዊትዝ የዋሽንግተን ጆዊሽ ዊክ አዘጋጅ የሆነውን አንድሪው ካሮልን ካዘዙት በኋላ ምክንያታቸውን ሲያስቀምጡ፦ ‹‹አይፓክን አስመልክቶ ያቀርባቸው የነበሩ ዘገባዎች ትክክለኛነት የጎደላቸው ነበሩ›› ብለዋል። የሆነ ሆኖ ያን ሁሉ ጥረት ቢያደርጉም ኮለርን በሥራው ላይ እንዳይመደብ ለማድረግ አልቻሉም። እናም ኮለር ለቦታው እንደተመደበ

ደርሸዊትዝ እና የአይፓክ የሕግ አማካሪ ዴቪድ ኢፋሲን አንድሪው፣ ካሮልን ጠርተው እንዲህ አሉት፡- ‹‹ላሪ ኮለር በዚህ ሥራ ላይ እስከቆየ ድረስ አይፓክ የእርሱን የቀድሞ ተግባሮች እንደገና መመርመርና ለሙግት መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡›› እንዲህ አይነቱ የጮሌ አካሄድ በካሮል ላይ ጫና ለመፍጠር ቢሆንም ለጊዜው አልሰመረም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በ1991 የአይፓክ የውጭ ፖሊሲ ዳይሬክተር ስቲቨን ሮስን ኮለር ሲበዛ የግራ ዘመም ፖለቲከኞች ደጋፊ መሆኑን ገልጸው ለብዙዎቹ የዋሽንግተን ጀዊሽ ዊክ ጋዜጣ የቦርድ አባላት ደብዳቤ በመላካቸውና ‹‹የተደራጀውን የአይሁድ ማህበረሰብ ለማፈራረስ ይጥራል›› የሚለው ክስ ተጨምሮበት ከሥራው እንዲነሳ ተደረገ፡፡ በመጋቢት 1992 በኮለር ፋንታ ምንም ዓይነት የጋዜጠኝነት ልምድ የሌለው አዘጋጅ ቢመደብም እርሱም ከሶስት ወራት በኋላ ሥራውን በመልቀቁ የቀድሞው የአይፓክ ጋዜጣ ‹ኒር ኢስት ሪፖርት› የዜና አዘጋጅ ቦታውን ተረከቡ፡፡[14]

በጣም ጉልበታም የሆኑ የመገናኛ ዘዴዎችን በመከታተሉ ሂደት ላይ ግንባር ቀደም ሚና ከሚጫወቱት የሎቢው ቡድኖች መካከል ዋነኛው ዘ ኮሚቲ ፎር አኪዮሬሲ ኢን ሚድል ኢስት ሪፖርቲንግ ኢን አሪካ C A M E R A የሚባለው ነው፡፡ ይህ ድርጅት በተለይም ከብሔራዊ የህዝብ ሬዲዮ (አንዳንድ ጊዜ በምጸት ብሔራዊ የፍልስጤም ሬዲዮ እያሉም ይጠሩታል) የሚተላለፉትን መልዕክቶች ይተቻል፡፡[15] የመገናኛ ብዙሃን እስራኤልን ያለአግባብ መተቸታቸውን ለማጋለጥ የራሱን ድረ- ገጽ (web site) ከመክፈቱም በላይ በ2003 ሰላሳ ሶስት በሚሆኑ ከተሞች በሚገኙ የብሔራዊው የህዝብ ሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያዎች የተቃውሞ ሰልፎችን አደራጅቷል፡፡ ከሁሉም በላይ ሬዲዮው መካከለኛውን ምሥራቅ በሚመለከቱ ዝግጅቶች እስራኤልን ይበልጥ መደገፍ የማይችል ከሆነ ገንዘብ የሚያዋጡትን አካላት በማሳመን መዋጮውን እንደሚያቋርጥበት አስፈራራ፡፡ ማስፈሪያውንም ወደ ተግባር በመቀየር የቦስተን ሬዲዮ ጣቢያ ከአንድ ሚሊዮን ዶላር በላይ እንዲያጣ አድርጎታል፡፡ በ2006 ደግሞ በኒውዮርክ ታይምስና በኒውዮርክ ሰን ጋዜጦች ላይ ‹ለፓልስታይን አፓርታይድ ሳይሆን ሰላም› የተሰኘውን የጂሚ ካርተር መጽሀፍ አስመልክቶ ሰፊ የሆነ

የማጥላላት ዘመቻ ከፈተ፡፡ በእነዚያ ጋዜጦች በወጣው ጽሑፍ ላይም የአሳታሚውን ስልክ አብሮ በማውጣት አንባቢያን እየደውሉ ብሶታቸውን እንዲያሰሙ ቀሰቀሰ፡፡[16]

በብሔራዊው የሬዲዮ ስርጭት ላይ ተጨማሪ ጫና የመጣበት ከኮንግረሱ በኩል ነበር፡፡ ለምሳሌ በመጋቢት 2003 ጠንካራ የእስራኤል ደጋፊዎች ከሚባሉት የኮንግረስ አባላት መካከል የካሊፎርኒያዎቹ ዲሞክራቶች ቶም ላንቶስ' ብራድ ሸርማንና ሄነሪ ዋክስማን ለብሔራዊው የህዝብ ሬዲዮ ፕሬዚዳንት ኬቨን ክሎስ ደብዳቤ በመጻፍ ሬዲዮው መካከለኛው ምሥራቅን የተመለከቱ ዘገባዎችን ከማቅረቡ በፊት ውስጣዊ ቁጥጥር እንዲያደርግ ጠየቁ፡፡ ክሎስ ጥያቄውን ባይቀበሉም ጫናውን ለማለዘብ ወደ ተለያዩ የአይሁድ ድርጅቶች እየሄዱ መደራደራቸው አልቀረም፡፡[17]

ሎቢው ተገቢ የሆነ ትኩረት ለማግኘት የሚያደርጋቸው ጥረቶች የተለያየ መልክ ያላቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ በነሃሴ 2003 ኢያን ቡሩማ የተባለ ጸሐፊ በኒው ዮርክ ታይምስ መጽሔት ላይ ‹‹ስለ እስራኤል እንዴት መነጋገር ይቻላል?›› በሚል ርዕስ አንድ መጣጥፍ አውጥቶ ነበር፡፡ ቡሩማ በዚያ መጣጥፉ ላይ አንዳንድ ጊዜ ስለ እስራኤልና ዩናይትድ ስቴትስ ትችት መሰንዘርም ሆነ በእርጋታና ከስሜታዊነት በራቀ መልኩ ሃሳብን ማራመድ አስቸጋሪ መሆኑን፣ ሌላው ቀርቶ እስራኤል ሕግን ተከትሎ ጽዮናዊነትን መተቸት በተለያዩ ቡድኖች ፈጣን የሆነ ውግዘትን በማስከተል ጸረ-ሴማዊ የሚል ቅጥያ እንደሚያሰጥ አብራርቶ ገለጸ፡፡ ለዚህ መጣጥፍ ወዲያውኑ ምላሽ የሰጠው በጊዜው የእየሩሳሌም ፖስት አዘጋጅና አሁን ደግሞ በዎል ስትሪት ጆርናል ጋዜጣ የአምድ አዘጋጅና የጋዜጣው ኤዲቶሪያል ቦርድ አባል ብሬት ስቴፈንስ ነው፡፡ ስቴፈንስ የአጸፋ ምቱን ያሰፈረው በዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ ላይ ምሬት የተሞላበት ግልጽ ድዳቤ ለቡሩማ በመጻፍ ሲሆን ‹‹በእርግጥ አይሁዳዊ ነህን?›› የሚል ርዕስ ነበር ለጽሑፉ የሰጠው፡፡ በዚህ ጽሑፍ ስቴፈንሰን እንዲህ ይላል፡- ‹‹ከሁሉም ነገር የሚያሳስበኝ አይሁዳዊ ነኝ የምትል ከሆነ ነው፡፡›› ይህ ለምን ያሳስባል? ምክንያቱም እንደ ስቴፈንስ አባባል፡ ‹‹ስለ እስራኤል ለመናገርም ሆነ ላለመናገር መጀመሪያ ቢያንስ አይሁድ መሆን ያስፈልጋል፡፡›› የዚህ ደብዳቤ ዋነኛ መልዕክት በአጭሩ፡-

‹‹አይሁድ ያልሆኑ ሰዎች የአይሁዳውያንን ጉዳይ አስመልክተው መናገር የሚችሉት በአይሁዳውያኑ ዘንድ ተቀባይነት ያለውን ነገር ብቻ ነው የሚል ነው።።››[118] በዚህ ርዕስ ዙሪያ ያለው የቁጣ ስሜት ነው ቶኒ ጀድት የተባሉት የታሪክ ምሁር የጻፉትን መጽሐፍ አስምልክቶ የኒው ዮርክ ታይምስ አዘጋጅ በሰጠው መግለጫ በአስተያየት መስጪያ አምድ (op-ed) ሥር አይሁዳዊ መሆናቸውን እንዲገልጹ እስከመጠየቅ ያደረሰው።።[19]

የስቴፈን ሃሳብ በብዙ አይሁዳውያን ዘንድ (የአሜሪካን አይሁዶች ጨምሮ) የሚወገዝ መሆኑ እንዳለ ሆኖ በሎቢው ውስጥ ያሉ የተወሰኑ የአመራር አካላት እስራኤልን አስመልክቶ በሚካሄድ ነጻና ግልጽ ውይይት ምኞት የማይሰማቸው መሆኑ እውነት ነው። የጸረ- ስም ማጥፋ ሊግ (ኤ. ዲ. ኤል) መሪው አብረሃም ፎክስማን የኒው ዮርክ ታይምስ መጽሔት አምድ አዘጋጅ ለሆነው ጀምስ ትራውብ እንዲህ ብለውት ነበር፡- ‹‹ያለ ገደብ ሃሳብን የመግለጽን መብት ተጠቅሞ ሃሰትን በመንዛት እውነትን ማግኘት ይቻላል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው።።›› ትራውብ ለፎክስማን አስተያየት በሰጠው ምላሽ ‹‹ፎክስማን ከልምድ አንደተገነዘቡት እውነት በራሱ ብቻውን ሊያሸንፍ አይችልም። ምክንያቱም የሃሰት ገበያ በጣም ኃያል ነውና›› ብሏል። በዚህ አስተያየት መሠረት ሃሰት ተብሎ የተጠቀሰው ዩናይትስ ስቴትስና እስራኤል ልዩ ግንኙነት እንዲመሰርቱ ሰበብ የሆናቸው የእስራኤል ሞራላዊና ስትራቴጂያዊ ጠቃሚነት ልብ ወለድ ድርሰት ነው። ኤ. ዲ.ዩ.ኤልን የመሳሰሉት የሎቢ ድርጅቶች እስራኤልን መተቸትና ዩ. ኤስ. አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠውን ቅድመ ሁኔታ አልባ እርዳታ የማጠያየቅ አጀንዳ በሕዝቡ ይፋዊ ውይይት ውስጥ ቦታ እንዳይኖራቸው ማድረግ ነው የሚፈልጉት።።[20]

እስራኤልን የሚመለከቱ አዎንታዊ ገጽታዎችን ለማነቃቃት የሎቢው አካላት በሙያው የተካኑ የተለያዩ ሐተታ አቅራቢዎችን የማሳመን ሥራ ይሠራሉ። እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ከሚያከናውኑ አፍቃራ-እስራኤል ድርጅቶች መካከል ዋነኛው የፕሬዝዳንቶች ኮንፈረንስ የሚሰኘው ሲሆን በድረ-ገጹ ባወጣው መግለጫ አሜሪካውያን ስለ እስራኤል በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ከእየሩሳሌም በቀጥታ ወደ አሜሪካ የሚተላለፍ የቶክ ሾው መርሃ

ግብር መዘርጋቱን ገልጿል። ይህን መርሃ ግብር የሚያንቀሳቅሰው አሜሪካ ቮይስ ኢን ኢስራኤል የተባለ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን ካቀረባቸው እንግዶች መካከል አሊቨር ኖርዝ፣ ግሌን ቤክ፣ ሞኒክ ክሮውሊ፣ ሚካኤል ሜድቬድ፣አርምስትሮንግ ዊሊያምስና ሌሎችም ይገኙበታል። በዚህ ዝግጅት አማካይነትም አሜሪካውያኑ አፍቃሪ እስራኤል መልዕክቶችን ለሕዝቡ ያሰራጫሉ።[21]

ይህ ዘርፈ ብዙ የሆነ ጥረት ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች አንዱ ዋና ዋና የሚባሉት የመገናኛ አውታሮች የእስራኤልን ገጽታ የሚያወይቡ መረጃዎችንና ክስተቶችን እንዳይናኙ ማድረግ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የእስራኤልን ስትራቴጂያዊና ሞራላዊ ጠቀሚነት በማጉላት ዩ. ኤስ. አሜሪካ የምትሠጣትን ድጋፍ ተገቢነት ማረጋገጥ ነው። እንግዲህ ይህ ሁሉ ጥረት መቶ በመቶ ስኬት ያስመዘግባል ባይባልም በተወሰነ መልኩ ውጤታማ መሆኑ ግን እውነት ነው።

በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚያስቡ ሐሳብ አፍላቂዎች

በተለያዩ የውይይትና የክርክር መድረኮች በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሚና እየተጫወቱ በሚገኙት ሐሳብ አፍላቂ ድርጅቶችና ግለሰቦች (think tanks) ላይ አፍቃሪ-እስራኤል ሃይሎች ትርጉም ያለው ተጽዕኖ አሳድረዋል። በመንግስት ባለሥልጣናት ወይም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚገኙ ምሁራን ላይ ከመመካት ይልቅ ዋሽንግተን ውስጥ ተቀማጭ የሆኑና ከመንግስት ጋር ተግባብተው የሚሠሩ፣ እንዲሁም ከተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ጋር ሁነኛ ቅርርብ ያላቸውን እነዚህን ሐሳብ አፍላቂ ድርጅቶች እና ግለሰቦች (think tanks) በሚገባ በመጠቀም በህዝቡና በፖለቲካው ምሕዳር ላይ የእስራኤልን መልካም ገጽታ ለማጉላት ተንቀሳቅሰዋል። እነዚህ ሐሳብ አፍላቂዎች በርካታ የሆኑ አጭርና በቀላሉ ሊዋሃዱ የሚችሉ የፖሊሲ ንድፎችን ለሕግ አውጭዎችና ለምንግሥት ባለስልጣናት ያቀርባሉ፣ ሴሚናሮችን ያዘጋጃሉ፣ አጫጭር የአሠራር መመሪያዎችን በማውጣት ለባለስልጣናትና ለበታች ሰራተኞቻቸው ገለጻ

ያደርጋሉ፣ ከተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች የአስተያት መጻፊያ አምዶች (op-eds) ላይ የራሳቸውን የፖለቲካ ትንታኔ በማቅረብ በአንዳንድ ጉዳይ ላይ ሕዝቡ ያለበትን ብሽቦታ በመግፈፍ አቅጣጫ ያስይዛሉ። ለምሣሌ ዘ-አሜሪካን ኢንተርፕራይዝ ኢኒስቲትዩት ወይም ብሩኪንግስ የሚባሉት ተቋማት ለፕሬዝዳንታዊ ውድድሮች ተሳታፊዎች አማካሪዎችን ያቀርባሉ፣ እንዲሁም አዲስ በተዋቀረው መንግስት ውስጥ በብቃት የሚያገለግሉ ባለሰልጣናትን ይጠቁማሉ። ከስልጣን የሚወርዱ ሰዎችን በማስጠጋት ከመንግስቱ ቀጥተኛ አሠራር ወጣ ባለ መንገድ በፖለቲካው ላይ ሚና የሚጫወቱበትን ሜዳ ያመቻቻሉ፤ እንዲሁም አዳዲስ የፖሊሲ ሃሳቦችን በማፍለቅ በዋሽንግተን የፖለቲካ ምሕዳር ላይ እንዲናኙ ያደርጋሉ።[22]

ይህንን የሐሳብ አፍላቂነት ሚና በሚገባ ያጤኑትና እስራኤልም በፖሊሲው መድረክ የሚገባትን ድምጽ ማግኘት እንዳለባት ያመኑት የቀድሞው የአይፓክ ምክትል ፕሬዝዳንት ላሪ ወይንበርግና ባለቤታቸው ባርቢ ወይንበርግ፣ የአይፓክ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ እንዲሁም የምርምር ዳይሬክተር ማርቲን ኢንዲክ በ1985 ዘ-ዋሽንግተን ኢኒስቲትዩት ፎር ኒር ኢስት ፖሊሲ WINEP የተባለውን ሐሳብ አፍላቂ ተቋም መሠረቱ።[23] ምንም እንኳን ደብሊው አይ. ኤን. ኢ.ፒ. ከእስራኤል ጋር ጥብቅ ቁርኝት ቢኖረውና በመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ ሚዛናዊና ሃቀኛ እይታ እንዳለው ቢነገርም ሃቁ ግን ያ አይደለም።[24] ምክንያቱም የተመሠረተውና የሚንቀሳቀሰው የእስራኤልን አጀንዳ ወደፊት ለማራመድ ጥልቅ ፍላጎት ባላቸው ሰዎች በመሆኑ ነው። የአማካሪዎች ቦርድ አባላቱ ታዋቂና አፍቃሪ እስራኤል ኤድዋርድ ሉትዋክ፣ ማርቲን ፔሬትዝ፣ ሪቻርድ ፐርል፣ ጀምስ ውልሲና ሞርትማየር ዘከርማን ናቸው። ድርጅቱ ከእነዚህ ሰዎች ውጭ በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኝን የሌላ አገር ወይም ቡድን ሃሳብ የሚያራምድ አንድም ሰው አላካተተም። በውስጡ የሚሳተፉ አብዛኛዎቹ ሰዎች በሚገባ የተማሩ፤ ቀድሞ ባለስልጣናት የነበሩና ልምድ ያካበቱ ይሁኑ እንጂ በአብዛኛው በመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳዮች ላይ ያላቸው የገለልተኝነት አቋም አነስተኛ በመሆኑ በድርጅቱ ውስጥ የአመለካከት ልዩነት የሚንጸባረቀው በትንሹ ነው።

እንግዲህ ሎቢው በቲንክ ታንክ ድርጅቶች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከደብሊው አይ.ኤን.ኢ.ፒ.ም ያለፈ ነው። በምዕራፍ አራት ላይ በሰፊው እንዳተትነው ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት አፍቃሪ እስራኤል የሆኑ ግለሰቦች የአሜሪካን ኢንተርፕራይስ ኢኒስቲትዩት፣ ዘ- ሴንተር ፎር ሴኩሪቲ ፖሊሲ፣ ዘ- ፎሬን ፖሊሲ ሪሰርች ሴንተር፣ ዘ ሄሪቴጅ ፋውንዴሽን፣ ዘ- ሆድሰን ኢንስቲትዩት፣ ዘ- ኢኒስቲትዩት ፎር ፎሬን ፖሊሲ አናሊስስና ጆዊሽ ኢኒስቲትዩት ፎር ናሽናል ሴኩሪቲ አፌርስ የተባሉትን ሐሳብ አፍላቂ ተቋማት በኃላፊነት ተቆጣጥረዋል። እነዚህ ሁሉ ተቋማት ከሞላ ጎደል አፍቃሪ- እስራኤል (pro israel) ሲሆኑ ዩ. ኤስ. አሜሪካ እስራኤልን መደገፏን የሚቃወሙ ምናልባትም ጥቂት (እነርሱም ካሉ ነው) ግለሰቦችን ሊያቅፉ ቢችሉ ነው።

በቲንክ ታንክ ዓለም ሎቢው የሚያደርገው ተጽዕኖ ሌላው መገለጫ ደግሞ በብሩኪንግ ኢኒስቲትዩሽን ላይ የተከሰተው ለውጥ ነው። ለብዙ ዓመታት የብሩኪንግስ የመካከለኛው ምስራቅ ሲኒዮር ኤክስፐርት የነበሩት ዊሊያም ቢ.ኩዋንድት የታወቁ ምሁርና የቀድሞ ናሽናል ሴኩሪቲ ካውንስል ባለስልጣን ሲሆኑ የአረብ እስራኤልን ግጭት በተመለከተ በሚከተሉት ሚዛናዊ አሰራር ዝና ያተረፉ መሆናቸው ይታወቃል። በእርግጥም ብሩኪንግስ በ1970ዎቹ መካከለኛው ምሥራቅን አስመልክቶ ያወጣቸው በነበሩት ዘገባዎች እስራኤል በሃይል ከያዘቻቸው ቦታዎች የመውጣቷን አስፈላጊነት፣ የፍልስጤማውያን የራስን ዕድል የመወሰን (ነጻ መንግስት የመመስረትን እድል ያገናዘበ)፣ በእየሩሳሌም በሚገኙ ሃይማኖታዊ ሥፍራዎች ህዝቦች የመጠቀም መብታቸው እንዲሁም የእስራኤልን ጸጥታ ማረጋገጥን በተመለከቱ ነጥቦች ላይ አጽንኦት ይሰጥ ነበር። የብሩኪንግስ ጥናት የሚጠናቀረው በተለያዩ የባለሙያ ቡድኖች ሲሆን እነዚያን የጥናት ውጤቶች የካርተር አስተዳደር ባከናወነው የካምፕ ደቪድ (የግብጽና የእስራኤል) ስምምነት በንድፍነት (blue print) የተጠቀመባቸው መሆኑ በሰፊው ይታመናል።[25]

ይሁን እንጂ ብሩኪንግስ በአሁኑ ጊዜ በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ሥራውን የሚያከናውነው ሳባን ሴንተር ፎር ሚድል ኢስት ፖሊሲ በሚሰኘውና

ሄይም ሳባን የተባለው አክራሪ ጽዮናዊና የሆሊውድ ባለጸጋ በ2002 በ13 ሚሊዮን ዶላር ባቋቋመው ድርጅት ሥር ሆኖ ነው፡፡ ኒውዮርክ ታይምስ ይህን ሰው ሲገልጸው ‹‹ምናልባትም በሆሊውድ ውስጥ ከፖለቲካ ጋር እጅግ የተቆራኘ ባለጸጋና ተጽዕኖውንና ገንዘቡን በዋሽንግተን ዙሪያ የሚበትን እንዲሁም ሁሉም ነገር የእስራኤል እንዲሆን የሚመኝ ሰው ነው›› ብሎታል፡፡ ይህ እስራኤልን የዓለም የበላይ ለማድረግ የሚታትር እረፍት የለሽ ሰው ለታይምስ ጋዜጣ የሚከተለውን ተናግሮ ነበር፡- ‹‹እኔ አንድና አንድ የሆነ ጉዳይ ብቻ ያለኝ ሰው ነኝ፡፡ እርሱም እስራኤል ናት፡፡›› የዚህን ሰው ጥረት ያደነቁት አሪዮል ሻሮን እንዲህ የሚል አስተያየት ለመስጠት ተገድደዋል፡- ‹‹እስራኤልና የአይሁድ ህዝቦች በፈለጉት ጊዜ ሁሉ ከጎናቸው የሚቆም ታላቅ አሜሪካዊ ነው፡፡››[26] እናም የሳባን ሴንተር እንዲመሩ የተመረጡት ሰው የቀድሞው የክሊንተን አስተዳደር ባለስልጣንና የአይፓክ የምርምር ማዕከል ምክትል ዳይሬክተር እንዲሁም ደብሊው አይ. ኤን. ኢ. ፒን ከመሠረቱት ሰዎች መካከል አንዱ የሆኑት ማርቲን እንዲክ ናቸው፡፡

በሳባን የተቋቋመና በማርቲን ኢንዲክ የሚመራ የምርምር ተቋም አፍቃሪ እስራኤል ከመሆን ውጭ ሌላ ምርጫ እንደሌለው ለማሰብ ሊቅ መሆንን አይጠቅም ይባል ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን አንዳንድ ጊዜ ያልተጠበቁ ነገሮች ሲከሰቱ ማየት ያለ ነው። የሳባን ማዕከል የአረብ ምሁራንን በመጋበዝ የተለያዩ ሃሳቦች እንዲስተናገዱ ያደርጋል፡፡ ኢንዲክና የሳባን ማዕከል ባልደረቦች በእስራኤልና ፍልስጤማውያን መካከል ያለውን ችግር ለመቅረፍ የሁለት የተለያዩ መንግሥታትን መኖር ይደግፋሉ፡፡ ይሁን እንጂ የሳባን ማዕከል በሚያወጣቸው ጽሑፎቹ ላይ ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል የምትለግሰውን እርዳታ ጥያቄ ውስጥ አስገብቶ አያውቅም፡፡ እንዲሁም አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር እስራኤል የምትከተላቸውን ቁልፍ ፖሊሲዎች አይተችም፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ከተቋሙ የአሠራርና አመለካከት መንገድ ያፈነገጠ ሰው በዚያ እንዲቆይ አይፈቀድለትም። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው የቀድሞው ብሔራዊ ጸጥታ ካውንስል ባለስልጣን ፍላይንት ሌቨርቲ የስልጣን ዘመን ማጠር ነው፡፡[27]

የሳባን ማዕከል አፍቃሪ እስራኤል መሆን ይበልጥ የሚገለጸው የሳባን ፎረም በሚባለውና እውቅ የሆኑ የአሜሪካና የእስራኤል መሪዎች በየአመቱ

በዋሽንግተን ወይም እየሩሳሌም ውስጥ ለሁለት ቀናት በሚያደርጉት ስብሰባ ላይ ነው። ለምሳሌ የ2006ቱ የመወያያ ርዕስ ‹‹አሜሪካና እስራኤል የመካከለኛው ምሥራቅን ግለት ሲጋፈጡ›› የሚል ነበር። በዚያ ፎረም ላይ ከተሳተፉት ሰዎች መካከል የእስራኤል ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዚፒ ሊቪኒ፣ ቢል ክሊንተን፣ ሴናተር ሂላሪ ክሊንተን፣ ሺሞን ፔሬዝ፣ ዊሊያም ክሪስቶል፣ የኮንግረስ አባላት የሆኑት ቶም ላንቶስና ጄን ሃርማን እንዲሁም የእስራኤል የስትራቴጂ ጉዳዮች ሚኒስትር (አሁን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) አቪግዶር ሊበርማን ይገኙበታል። በዚያ ቦታ ላይ አፍቃሪ- አረብ ድምጾች ወይም የአሜሪካንና የእስራኤልን ግንኙነት የሚተቹ ሰዎች በፍጹም አልነበሩም። እንዲኖሩም አልተፈለገም።[28]

እነዚህ ተቋማት የህዝብን አስተሳሰቦችና የፖለቲከኞችንም ፖሊሲዎች ከማስቀየር አንፃር የሚጫወቱት ሚና ታላቅ በመሆኑ ለእስራኤል ግዙፍ ጥቅም ይሰጣሉ። እርግጥ ነው አነስተኛ ቁጥር ያላቸውና በጣም አፍቃሪ እስራኤል ያልሆኑ ኒው አሜሪካ ፋውንዴሽን ዘ ካቶ ኢኒስቲትዩት እና ዘ - ሚድል ኢስት ኢኒስቲትዩትን የመሳሰሉ አነስተኛ ሐሳብ አፍላቂ ተቋማት አሉ። ሆኖም ግን ታላላቆቹና በሚገባ የተደራጁት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ምርምር የሚያካሄዱ ተቋማት (think tanks) አብዛኛውን ጊዜ ለእስራኤል የሚሰግዱና ቅድመ ሁኔታ አልባ የዩ ኤስ. አሜሪካ እርዳታ እንዲሰጣት የሚፈልጉ ናቸው።

በመጨረሻም ሳናነሳው የማናልፈው ስመጥር የሆነ ድርጅት ካውንስል ኦን ፎሬይን ሪሌሽንስ የተባለውና መሠረቱን በኒዮርክ ከተማ ያደረገው ድርጅት ነው። ኤክስፐርት አባላቱ በዋሽንግተን ከሚገኙ ሌሎች ሐሳብ አፍላቂ ድርጅቶች በተለየ ሁኔታ የተለያዩ ሃሳቦችን የሚያንሸራሽሩ ሲሆኑ እስራኤልን በግልጽ ሂስ የሚጠርቡ ከሆኑት እንደ ሄነሪ ሲግማን (የቀድሞው የአሜሪካ ጂዊሽ ኮንግረስ ዳይሬክተር) ካሉት ጀምሮ ዋነኛ አፍቃሪ እስራኤል የሆኑትን እንደ ማክስ ቡት ያሉ ግለሰቦችን አቅፎ የያዘ ተቋም ነው። እንደዚያም ሆኖ ይህ ካውንስል ከግፊት አላመለጠም። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ መስከረም በ2006 የኢራኑን ፕሬዝዳንት ማህሙድ አህመዲን ኤጃድን በመጋበዙ ከየአቅጣጫው ውግዘት ተነሳበት። ታላላቅና ታዋቂ የሆኑ የአይሁድ ድርጅቶች ተቃውሟቸውን በማጧጧፍ ግብግቡን ያወገዙ ሲሆን

ተቃውሞውን ለማብረድ በማሰብ የካውንስሉ ፕሬዝዳንት ሪቻርድ ሄስ የመሰባሰቢያ ዝግጅቱን ደረጃ ከእራት ግብዣነት ወደ የስራ ስብሰባነት ዝቅ ለማድረግ ተገድደው ነበር። የኤ. ዲ. ኤል መሪ ፎክስማን ለኒው ዮርክ ታይምስ መጽሔት አስተያየታቸውን ሲሰጡ፡- ‹‹ከዚያ ሰው (አህመዲን ኤጃድን ማለታቸው ነው) ጋር ዳቦ ለመቁረስ ማሰቡ ራሱ መስመር የሳተ አካሄድ ነበር›› ብለዋል። አህመዲን ኤጃድ እስራኤልንና የሆሎኮስት እልቂትን አስመልክተው የሰጧቸውን አስተያየቶች ስናጤን እነዚህ ሰዎች የወሰዷቸውን እርምጃዎች ለመገንዘብ አይከብድም።[29] ያም ሆኖ ልብ ልንለው የሚገባን ጉዳይ ይህ ሁሉ የሎቢው ጥረት የሚያሳየን በእያንዳንዱ ተቋም ውስጥ የሚባልና የሚደረገውን ነገር ሁሉ በንቃት የመከታተልና ለእስራኤል በሚጠቅም አኳኋን መልክ የማስያዝ ፍላጎት ያለው መሆኑን ነው።

የአካዳሚውን ዓለም መቆጣጠር

ሎቢው እስራኤልን የሚመለከቱ የህዝብ አስተያየቶችንና የፖለቲካ ክርክሮችን በሚፈልገው ሁኔታ እንዳያስኬድ ትልቅ ችግር የሚፈጥርበት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ያቀፈው የአካዳሚው ዓለም ነው። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ብዙ ፕሮፌሰሮች በጡረታ እስከሚለቅቁ ድረስ የያዙትን የአካዳሚ ወንበራቸውን እንደያዙ መቆየት የሚፈልጉ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ክብር የሚሰጠውን ምሁራዊ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመመራመርና ሃሳብን እንደልብ የመግለጽ መብት አሳልፈው መስጠት የማይሹ በመሆናቸው ነው። በዚህም የተነሳ የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ያላቸውን ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ተጠቅመው ባለፉት ሰላሳ ዓመታት በርካታ ቁጥር ያላቸው የውጭ ተወላጅ የሆኑ ተማሪዎችንና ፕሮፌሰሮችን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንዲመጡ ማድረግ ችለዋል። እናም እነዚህ ሰዎች ከአሜሪካውያን ይልቅ እስራኤልን በተደጋጋሚ የሚተቹ ሆነዋል።

ሁኔታው ይህን የሚመስል ቢሆንም የእስራኤል ሎቢ በ1990ዎቹ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች) የሚደረጉ ውይይቶችንና ክርክሮችን ከእስራኤል ጥቅም አንጻር ለመቃኘት በቂ ጥረት አላደረገም። ለዚህም ተጠቃሹ ምክንያት የኦስሎ የሰላም ሥምምነት ገና በሂደት ላይ ስለነበረ ነው። እንደሚታወቀው በእነዚያ ዓመታት በእስራኤልና በፍልስጤማውያን መካከል በአንጻራዊ ሁኔታ ሲታይ አነስተኛ የሆኑ ግጭቶች ብቻ የነበሩ ሲሆን ብዙ ሰዎችም ይህ ግጭት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከሚወገድበት ጫፍ ላይ ደርሷል የሚል እምነት አሳድረው ነበር። በዚህም የተነሳ በ1990ዎቹ በእስራኤል ላይ የሚነሱ ትችቶች መጠነኛ የነበሩ በመሆኑ ሎቢውም ጣልቃ የመግባት ፍላጎቱ አነስተኛ ነበር።

በዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች እስራኤልን የሚመለከቱ ትችቶች መሻሻልና የጀመሩት የኦስሎ የሠላም ሂደት ከፈረሰና አሪዮል ሻሮን በ2001 የካቲት ወር ሥልጣን ከያዙ በኋላ ነበር። ሁኔታው እየተባባሰ ሄዶ በጸደይ 2002 ሁለተኛውን ኢንቲፋዳ ለመምታት እስራኤል የፍልስጤምን ግዛቶች እንደገና

በወረረች ጊዜ የተጧጧፉ ትችቶችና ክርክሮች በየሥፍራው ይነሱ ጀመር። ይህን ያስተዋለው ሎቢ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን መልሶ በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ በኃይል ተንቀሳቀሰ። ሂደቱን ተከትለውም የዲሞክራሲ ቅፍለትን (the caravan for democracy) የመሳሰሉ ቡድኖች እንደ አሸን ፈሉ። እነዚያ ድርጅቶች ከእስራኤል ሳይቀር ንግግር አቅራቢዎችን በመጋበዝ የመካከለኛው ምሥራቅ ብቸኛ የዲሞክራሲ አምባ የሆነችው እስራኤል የገጠማትን ተግዳሮት ማስወገድ የምትችልበትን መንገድ ይሰብኩ ጀመር።[30] ዘ-ጀዊሽ ካውንስል ፎር ፐብሊክ አፌርስ GCPA የተባለው ድርጅት በበኩሉ የእስራኤልን አቋም በየግቢያቸው ለመከላከል ለሚፈልጉ የኮሌጅ ተማሪዎች ተከታታይ የሆኑ የክርክር ጭብጦችንና ሃሳብን የመግለጽ ችሎታን የሚያዳብሩ ሥልጠናዎችን አቀረበ። ሌላውና አዲስ የተመሠረተው ዘ- እስራኤል ኦን ካምፓስ ኮአሊሺን የተባለው ድርጅትም በተለያዩ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ሃያ ስድስት የሚሆኑ ቡድኖችን በማቀፍ የእስራኤልን ጉዳይ ለየተቋማቱ ማህበረሰቦች በሚገባ ለማድረስ ተንቀሳቀሰ።

ምንም አልሰሩም እንዳይባሉ ያክል በቅርቡ የተቋቋመው የክ|ስቲያን ዩናይትድ ፎር ኢስራኤል CUFI አባላት ዴቪድ ፕሮጀክት ከሚባለውና መሠረቱን ቦስተን ካደረገው አፍቃሪ እስራኤል ቡድን ጋር ተቀናጅተው በየተቋማቱ የእስራኤልን ጉዳይ መልክ ለማስያዝ የበኩላቸውን ሙከራ አደረጉ። የእነርሱ ዓላማ በዋነኝነት ያተኮረው ክርስቲያን ተማሪዎች የእስራኤልን ጉዳይ በተመለከተ ያለባቸውን ብኽርታ በመግፈፍና ጽኑ ደጋፊ እንዲሆኑ በማድረጉ ላይ ነበር። የሲ. ዩ. ኤፍ. አይ ዳይሬክተር ዴቪድ ብሮግ ዓላማቸውን በአጭሩ ሲገልጹ፦ ‹‹የሚቀጥለውን ትውልድ ለማነጽ ነው›› ብለዋል። የዴቪድ ፕሮጀክት ዳይሬክተር ቻርልስ ጃኮብስ በበኩላቸው አላማቸውን ሲያስቀምጡ ‹‹እኛ የምናሰለጥናቸው ‹አምላክ ያንን ምድር ለእስራኤል ሰጥቷታል› ከሚለው የተለመደ ቀኖና ፈቀቅ ብለው በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ያለውን ግጭት እንደ ድንበር ይገነኛል ጦርነት ሳይሆን በአረብና አይሁድ መካከል እንደሚካሄድ ዓለም አቀፋዊ ፍልሚያ እንዲመለከቱት ለማድረግ ጭምር ነው›› ብለዋል።[31]

በቀላሉ መገመት እንደሚቻለው አይፓክ ባደረጋቸው የተለያዩ ጥረቶች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማህበረሰብን መልሶ በእጁ ማስገባት ችሏል። አይፓክ ከ1970ዎቹ ጀምሮ በተቋማቱ ግቢዎች ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ወጣት ሰባኪያን እስራኤልን እንዲከላከሉ እያሰለጠነ ሲያሰማራ ቆይቷል። እስራኤል በውጥረት ላይ በሆነችባቸው ጊዜያቶች በኮሌጅ መርሀግብሮች ላይ የሚያፈስሰውን ወጪ በሶስት እጥፍ አሳድጎታል። እንዲህ ዓይነት ጥረት የማድረጉን ዓላማ የአይፓክ የስራ አመራር ማሻሻያ ክፍል ሃላፊ የሆኑት ጆናታን ኬሰለር ሲገልጹ፡- ‹‹በየተቋማቱ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን ብቃት በማሳደግ አፈጻጸማቸውንም ከፍ ማድረግ በብሔራዊ ደረጃ ለሚካሄደው የአፍቃሪ እስራኤል ጥረት (pro Israel effort) ያግዘናል›› ብለዋል። በዚሁ መሠረት በ2003 በጋ ላይ አይፓክ 240 የሚሆኑ የኮሌጅ ተማሪዎችን ሁሉንም ወጪያቸውን ሸፍኖ ወደ ዋሽንግተን ከወሰዳቸው በኋላ የንግግር፤ ክርክርና የማሳመን ችሎታቸውን የሚያጎለብቱበት ለአራት ቀናት የቆየ ስልጠና ሰጥቷቸዋል። ተማሪዎቹ ስልጠናውን ጨርሰው ወደ የመጡበት ሲመለሱ ከየተቋማቱ መሪዎች ጋር ሁለንተናዊ ግንኙነት እንዲመሰርቱና የእስራኤልን ጉዳይ በሚገባ እንዲያስረዷቸው መመሪያ ተሰጣቸው።[32] በ2007 ደግሞ ከ1200 በላይ የሚሆኑና ከ400 ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ ተማሪዎች በአይፓክ ዓመታዊ የፖሊሲ ኮንፈረንስ ላይ የተገኙ ሲሆን ከእነርሱ ውስጥ 150 የሚሆኑት የተማሪዎቹ ፕሬዝዳንቶች ነበሩ።[33]

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አፍቃሪ እስራኤል ተማሪዎችን ለማፍራት የሚደረገው ጥረት የዩኒቨርሲቲ ፋካሊቲዎችን በሥራቸው በሚቀጥሩት የሰው ኃይል ላይ ተጽዕኖ በማድረግ ጭምር ታጅቦ ቀጠለ። ለምሳሌ በ1980ዎቹ የመጀመሪያ አመታት አይፓክ በየተቋማቱ የሚቀጠሩ ፕሮፌሰሮች ጸረ- እስራኤል አቋም ያላቸውና የሌላቸው መሆኑን የሚያጣሩ ተማሪዎችን ቀጥሮ ነበር። አጠቃላይ የሆነው ግኝትም በ1984 ‹‹The AIPAC college Guide exposing the Anti-Israel Campain on campus.›› በሚል ርዕስ ታትሞ ወጣ። በተመሳሳይ ጊዜ የጸረ- ስም ማጥፋት ሊግ (ኤ. ዲ.ኤል) ጸረ- እስራኤል አቋም አላቸው ብሎ የሚጠረጥራቸውን ግለሰቦችና ድርጅቶች ከመዘገበ በኋላ በአነስተኛ ጥራዝ

መልክ አዘጋጅቶ በምስጢር ለሚፈልጋቸው አካላት አሰራጨ፡፡ የዚያ ጥራዝ ይዘት ‹‹ Back ground in formation on pro- Areb sympathizers active on college compus (በኮሌጅ ግቢዎች ውስጥ የሚንቀሳቀሱ አፍቃሪ-አረብ ሰዎች የኋላ ታሪክ) የሚል ነው፡፡ ‹‹እነዚህ ሰዎች›› ይላል ጥራዙ ‹‹የጸረ- ጽዮናዊነት ገጽታቸውን ለጸረ- ሴማዊነት አቋማቸው መደበቂያ መልክ አድርገውታል፡፡››[34]

ጸረ- እስራኤል አቋም አላቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ሰዎችን የማጋለጡ ጥረት ይበልጥ የተፋፋመው ዳንኤል ፓይፕ ‹ካምፓስ›› ዌብሳይት የተባለ ድረ-ገጽ በመክፈት በጸረ ኢስራኤልነት የሚጠረጠሩ ሰዎችን ዶሴዎች ወደ አይፓክ የመረጃ ማከማቻ እንዲያስተላልፉ ተማሪዎችን ባበረታታ ጊዜ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ አሠራር ብዙ ምሁራንን በማስጨነቁና ምን ዓይነት አጸፋ ይደርስብን ይሆን ብለው እንዲሰጉ በማድረጉ ፓይፕ ኋላ ላይ ዶሴዎቹ እንዲወገዱ አድርጓል፡፡ ድረ- ገጹ ግን እስካሆንም ድረስ ያለ በመሆኑ በዩናይትድ ስቴትስ ኮሌጆች ውስጥ ጸረ- እስራኤል አቋም እንደሚያንጸባርቅ የሚያምኑበትን ሰው ጥቆማ ለማድረግ ይጠቀሙበታል፡፡[36]

ዳንኤል ፓይፕ በየተቋማቱ የሚደረጉትን እስራኤልን የማውገዝ ሂደቶች ለመደምሰስ የጀመረው ዘመቻ በዚህ ብቻ የሚገታ አልነበረም፡፡ እስራኤላዊ-አሜሪካዊ የሆነው ምሁርና ደብሊው አይ. ኤን. ኢ. ፒ. እንዲሁም እስራኤልስ ሻሌም ሴንተር በሚባሉት ድርጅቶች ውስጥ የሚሰራውን ማርቲን ክራመር እና ናሽናል ሪቪው በተባለው ጋዜጣ ተባባሪ አዘጋጅና በሁቨር ኢኒስቲቲዩሽን ተመራማሪ የሆነው ስታንሌይ ከርትዝን አስተባብሮ ኮንግረሱን በማነቃቃት ፌደራሉ የዩ. ኤስ. መንግስት ለዩኒቨርሲቲዎች የመካከለኛው ምሥራቅና ሌሎች ክልሎች የጥናት መርሐግብር ማካሄጂያ የሚሰጠውን ድጎማ እንዲያስቆም ወይም እንዲቆጣጠር የማድረግ ዘመቻ ከፈተ፡፡ የዚህ ዘመቻ ዋነኛ ዓላማ በእስራኤል ላይ የሚነሱ ትችቶችን ዝም ለማሰኘት ወይም ቢያንስ ለማጨናገፍ ነው፡፡ በውጤቱም ዩኒቨርሲቲዎች የሚቀጥሯቸው ምሁራን የፓይፕ ክራመርንና ከርትዝን የአቋም መስመር እንዲከተሉ ለማድረግ ነው። እነርሱ የሚደግፉት እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዓለም አቀፍ ጥናትን የሚመለከተው አዋጅ (ኤች. አር. 3077)፣

የፌደራሉ መንግስት በሚልቅቀው በጀት የሚተዳደሩ የዓለም አቀፋዊ ጥናቶች ማዕከላት በመንግስት በተሰየመ ቦርድ እንዲመሩ ይደነግጋል፡፡ ቦርዱ የተጣለበት አደራ (Mandate) ከሚያጠቃልላቸው ጉዳዮች መካከል ጥናት ማካሄጃ የሚሆን ገንዘብ ማግኘት የሚገባቸውን የጥናት ማዕከላት በመለየት ለትምህርት ሚኒስትርና ለኮንግረስ ማሳወቅ ይገኝበታል፡፡[37] ምንም እንኳን ይህ ለእነ ክራመርና ከርትዝ ጥያቄ ምላሽ የሰጠ ሕግ ጉዳት የሌለው ቢመስልም በየተቋማቱ የሚደረገው ጥናት ጸረ- አሜሪካና ጸረ- እስራኤል እንዳይሆን ለማድረግ የታለመ ነበር፡፡[38]

ሕጉ እንደተጻፈ ቢያልፍ ኖሮ የመንግሥትን ድጋፍ የሚሹት ዩኒቨርሲቲዎች የሚያከናውኗቸውን ጥናቶች ያካሄዱ ዘንድ የሚቀጥሯቸው ሰዎች አሁን ያለውን የዩ. ኤስ. አሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የመደገፍና እስራኤልንም ያለመቃወም ግዴታ ይወድቅባቸው ነበር፡፡ ይህ በእንዲህ እያለም አይፓክ፤ ኤ. ዴ. ኤል፣ ዘ- አሜሪካን ጀዊሽ ኮንግረስና ሌሎች አምስት ድርጅቶች የሚገኙባቸው ቁልፍ የሆኑት የሎቢው ዋና ዋና ክፍሎች የአዲሱን ሕግ መጽደቅ ለማሳካት ሲሉ ለኮንግረስ አንድ ደብዳቤ በመላክ አሁን እየተሰራበት ያለው ሕግ ‹‹የፍልስጤማውያንን፣ የአረቦችንና የሙስሊሙን ዓለም ገጽታ ያለምንም ሂስ የሚደግፍና አይሁዳዊያንን ግን ዝቅ በማድረግ ብዙም ቦታ የማይሰጥ ነው›› በማለት ከሰሱ፡፡[39] ኤች አር 3077 በሕግ መወሰኛው ምክር ቤት ድጋፍ ያገኘ ቢሆንም ሴኔቱ ግን በምልዓት ፊጽሞ አላጸደቀውም፡፡[40] ከዚያ በኋላም ቢሆን 2005 ላይ ተመሳሳይ ሕግ ረቅቆ ከቀረበ በኋላ በ2006 የህግ መወሰኛው ምክር ቤት 221 ለ 199 በሆነ ጠባብ ድምጽ ቢያሳልፈውም ሴኔቱ አሁንም ሕጉን ሳያጸድቀው 109ኛው ኮንግረስ የቆይታ ጊዜውን ጨርሶ ተበትኗል፡፡[41]

ይሁን እንጂ ክራመርና ከርትዝ በ2007 ድል ተጎናጽፈዋል፡፡ ይህም የሆነው በኮንግረስ ሃላፊነት የተሰጠው ‹ናሽናል ሪሰርች ካውንስል ስተዲ ኦፍ (VI) ፕሮግራምስ›› የተባለው የዓለም አቀፍና የቋንቋ ጥናቶችን በቅርበት የሚከታተል አካል በኘሬዝዳንቱ እንዲሰየም ሐሳብ በቀረበ ጊዜ ነበር፡፡[42] ናሽናል ሪሰርች ሴንተር (ኤን. አር. ሲ) የተባለው ጥናት አሁን ያሉት የጥናት መርሐ ግብሮች ተግባራዊነታቸው እንዲቀጥል የሚፈልግ ሲሆን

ክራመርና ከርትስ አድሎአዊነት አለ በማለት ያነሱትን ክስ አልተቀበለም፡፡ እርግጥ ነው ከዚህ የጥናት ቡድን አባሎች አንዱ የሆኑት ኬኔት ፕሬዊት ለሪፖርተሮች እንደተናገሩት ‹‹አድሎአዊነት የተስፋፋ ቢሆን ኖሮ በግልጽ ይስተዋል ነበር›› ብለዋል፡፡[43] ታይትል ቪ. አይ. ሴንተር (title VI center) የተባለውንና አሁን በሥራ ላይ ያለውን ሕግ የሚደግፉ አንዳንድ ፖለቲከኞች በሰጡት አስተያየት ይህን መርሐግብር ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውና በፕሬዝዳንቱ የሚሾሙ ሰዎች እንዲመሩት ቢደረግ የእነርሱን ደረጃ ከፍ ከማድረጉም በላይ ተገቢ የሆኑና ለጥናትና ምርምሩ አስፈላጊ ግብዓቶችንም ለማግኘት ጭምር ይጠቅማል፡፡ ይሁን እንጂ ለጥቂት ግለሰቦች ያን ያክል የቁጥጥር ስልጣን መስጠት ፕሬዝዳንት ሆኖ የሚሾመው ሰው የእነ ፓይፕ፣ ክራመርና ከርትዝን አስተሳሰብ ተግባራዊ እንዲያደርግ የሚያስችለው አጋጣሚ እንዳይከሰት ስለሚያሰጋ እንደዚያ ዓይነት ስህተት ከመሥራት መጠንቀቅ ያስፈልጋል የሚል እምነት በብዙዎች ዘንድ አድሯል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሚያዚያ 2007 ላይ የወጣው ታይትል (VI) የተባለውና በሴኔቱ እየተመከረበት ያለው የዓለም አቀፍ የትምህርት መርሐግብርን የሚመለከተው ሕግ በውስጡ የተለያዩ አስተያየቶችን ያካተተ አይደለም የሚል ስሜት ያደረባቸውን ወገኖች የሚያስተናግድበት ስልትና መስመር ተዘርግቶለታል፡፡ ይህውም ቅሬታ ያሰሙት ሰዎች ዩኒቨርሲቲው በሰጣቸው ምላሽ የማይረኩ ከሆነ ቅሬታቸውን የትምህርት ክፍሉ (department of education) መዝግቦ በማስተላለፍ ሚኒስቴሩ እንደገና እንዲመለከተው ያደርጋል፡፡ ረቂቅ ሕጉም ቢሆን ወደ ሚኒስቴሩ ይላክና ሚኒስቴሩ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ዓይነት ቅሬታዎችን እግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሻሻል ያደርገዋል፡፡[44] እንግዲህ ይህ ሐረግ ህግ ሆኖ የሚወጣ ከሆነ ማንም በቀላሉ ሊገምተው እንደሚችለው መካከለኛውን ምሥራቅ በሚመለከቱ ጥናቶች ላይ አንድ ሰው እስራኤልን የሚተች ከሆነ በሎቢው ውስጥ የሚገኙ ቡድኖች ተደጋጋሚ ሮሮ ማሰማታቸውን ይቀጥላሉ ማለት ነው፡፡ እንደዚያ በማድረግም የትምህርት ሚኒስትር ለታይትል ቪ አይ. የሚሰጠውን ድጋፍ እንዲያቋርጥ ያደርጋሉ፡፡ እናም ዩኒቨርሲቲው ድጋፍ ማግኘት ከፈለገ

ጥናቶችን በሙሉ በአፍቃሪ እስራኤል (pro-israel) አቅጣጫ እንዲሄዱ እንዲያደርግ ይገደዳል ማለት ይሆናል፡፡

ጸረ- እስራኤል የሆነ አድሎ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ይፈጸማል ለሚለው ወቀሳ አጸፋ ምላሽ ይሆን ዘንድ በዩናይትድ ስቴትስ ዩኒቨርሲቲዎች መጀመሪያ ከነበሩት 130 የሚሆኑ የአይሁድ ጥናት መርሐግብሮች ሌላ በርካታ በጎ አድራጊዎች ገንዘባቸውን ወጪ በማድረግ የተለያዩ የእስራኤል ጥናት መርሐግብሮችን ዘርግተዋል። በዚህም የተነሳ በየተቋማቱ የእስራኤል ወዳጅ የሆኑ ምሁራን የሚበራከቱበት ዕድል ተፈጥሯል፡፡[45] NYU ይፋ እንዳደረገው ‹ታኡብ ሴንተር ፎር ኢስራኤል ስተዲስ› የሚባል የምርምር ማዕከል ግንቦት 1 ቀን 2003 ላይ የተቋቋመ ሲሆን ተመሳሳይ የሆኑ የጥናት መርሐ ግብሮችም በርክሌይ ብራንዲስንና ኢሞሪንን በመሳሰሉ ሌሎች ትምህርት ቤቶች ተመስርተዋል፡፡ የትህርት አስተዳደር ባለሙያዎች እነዚህ ተቋማት ትምህርትን ለማሳደግ ለሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ትኩረት የሰጡ ቢሆንም በዋነኝነት የእስራኤልን ገጽታ ለመገንባት የተቋቋሙ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም፡፡ የታኡብ ፋውንዴሽን መሥራች ፍሬድ ሌፈር ግልጽ እንዳደረገው የእርሱ ፋውንዴሽን ኤን. ዋይ. ዩ ማዕከልን በገንዘብ የሚያግዘው ‹‹የአረብ ጥናትና ምርምር ማዕከላት የሚረጫቸውን አስተሳሰቦች ለመቋቋም ብሎም ለማክሸፍ ነው፡››[46]

ተመሳሳይ የሆነ እንቅስቃሴ እየተደረገ ያለው ደግሞ የቁማር ንግድ ንጉስ በሆነው አይሁዳዊው ሸልደን ኤድልሰን አማካኝነት ሲሆን እርሱ በመደበው በሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር በጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ ቀድሞ የነበረውን የአይሁድ ስልጣኔ መርሐግብርን (jewish civilization prograrame) የማስፋፋት ሥራ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ሃ ኤሬትዝ ጋዜጣ ነሐሴ 2006 ላይ እንዳተተው የኤድልሰንና መሰሎቹ የአይሁድ ሥልጣኔ እንዲስፋፋ የሚረባረቡ ሰዎች ዋነኛ ዓላማ በጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ ያለውን የአረብ ምሁራን ቁጥርና የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ ለማመጣጠን ነው። የዚህ መርሀግብር የመጀመሪያ ዳይሬክተር ዮሲ ሻይን (ሃርቶግ ስኩል ኦፍ ገቨርንመንት የተሰኘውንና በቴሌአቪብ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘውን ተቋምም መርተዋል) በጆርጅታውን ዩኒቨርሲቲ እንዲህ ዓይነት መርሐግብር መንደፍ

ያስፈለገበትን ምክንያት ሲገልጹ ‹‹ትምህርት ቤቱ የእየሱሳዊያን (ጀዝዊት) በመሆኑ፣ በዋሽንግተን የሚገኝ በመሆኑ፣ እንዲሁም የውጭ ሰዎች አገልግሎት የሚያገኙበት ትምህርት ቤት በመሆኑ ምክንያት ነው›› ብለዋል። በተጨማሪም የዩኒቨርሲቲው ራቢ ሃሮልድ ሁዋይት አዲሱን ተቋም በጆርጅታውን ዩኒቨርሲቲ የአረብ ማዕከል ባለበት የማስፋፋቱን ጠቃሚነት ሲገልጹ፡- ‹‹ምክንያቱም የጆርጅታውን ምሩቃን ማረፊያቸው የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ነው›› ብለዋል።[47]

ሎቢው የትምህርት ተቋማቱን ለመቆጣጠር የነበረው ፍላጎት በተለያዩ አስተዳደራዊና ግላዊ ውሳኔዎች ላይ የሚደነቅ ተጽዕኖ እስከማሳረፍ አድርሶታል። ለምሳሌ በ2002 በጋ በቺካጎ ዩኒቨርሲቲ የሚገኙ አፍቃሪ እስራኤል ቡድኖች ባቀረቡት ስሞታ ‹‹በዩኒቨርሲቲው ውስጥ አይሁድ ተማሪዎችን ማስፈራራትና ጥላቻ የማሳየት አዝማሚያዎች ይታያሉ›› በማለት የትምህርት መምሪያዎች (faculties) እና አስተዳደሩ ችግሩን ለማስወገድ ያደረጉት ምንም ጥረት የሌለ መሆኑን ገልጸዋል። ‹‹ለዚህ የአይሁዳዊያን ቁጣ መፈንዳት አስተዋጽዖ ያደረጉት የትምህርት መምሪያዎቹ (faculties) እና የአስተዳደር ባልስልጣናት ናቸው›› በማለት እነዚህ አካላት ተጠያቂ መሆናቸውንም ከሳሾቹ ይናገራሉ። ክሱን በሚገባ ያዳመጠው የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ተማሪዎቹ ያሉባቸውን ቅሬታዎች ሁሉ ካሰባሰበ በኋላ የማጣራቱን ሥራ አከናውኗል። ሆኖም ግን ከዚያ ሁሉ ክስ ሁለቱ ብቻ እውነታን ያዘሉ ሆነው መገኘታቸው ነበር በመጨረሻ የተገለጸው። ከእነዚህ ሁለት እውነታዎች አንደኛው በማደሪያ የሕንፃ ክፍሎች ጸረ- ሴማዊነትን የሚያንጸባርቁ ስዕሎችና ጽሑፎች መገኘታቸው ሲሆን ያንንም ለማስወገድ ተማሪዎቹ በጉዳዩ ዙሪያ ተገቢውን ውይይት አላደረጉም ነበር ተብሏል። ሁለተኛው ደግሞ አሸዊትዝን የሚመለከት በአንድ ተመራቂ ተማሪ በኢ-ሜይል የተላከ ቀልድ ሆኖ ተገኝቷል። የጉዳዩ አዝማሚያ መልካም ነው ለማለት ባይቻልም በአንድ አይሁዳዊ ተማሪ በ2002 በክሱ ላይ እንደቀረበው ‹‹የማግለልና የማጥቃት ሁኔታን›› የሚያሳይ አለመሆኑ ግን እውነት ነበር። የሆነ ሆኖ ሂደቱ ይህን በመሠለበት ሰዓት በቺካጎ የሚገኘው የእስራኤል ቆንስላ ጽ/ቤት ኃላፊና

በዩናይትድ ስቴትስ የእስራኤሉ አምባሳደር ዩኒቨርሲቲውን ጎበኙ፡፡ የገብኝታቸው ዋና ዓላማ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ላይ ጫና በመፍጠር በግቢው ውስጥ የእስራኤል ገጽታ የተሻለ እንዲሆን ለማስገደድ ነበር፡፡ በተመሳሳይ ጊዜ ስመ- ጥር የሆኑት ፍልስጤማዊ - አሜሪካዊው የታሪክ ባለሙያ ረሺድ ኻሊዲ (ያኔ በቺካጎ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ፋካልቲ ውስጥ ነበሩ) የኢ- ሜይል መቀበያቸው ስፍር ቁጥር በሌለው የተቃውሞ መልዕክት ተጨናንቆ ነበር፡፡[48]

በአንድ ወቅት ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ኻሊዲን ከቺካጎ በማስመጣት ሊቀጥራቸው በፈለገ ጊዜ ያጋጠመውን የቀድሞው የኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ጆናታን ኮል ‹‹ኻሊዲ የሚያራምዱትን የፖለቲካ አስተውሎት የማይወዱ በርካታ ሰዎች የተቃውሞ ድምጻቸውን አሰሙ፡፡›› በማለት ይገልጹታል፡፡ ፕሪንስተን ዩኒቨርስቲም ቢሆን ከጥቂት ዓመታት በኋላ ኻሊዲን ከኮሎምቢያ አባብሎ ለመውሰድ ጥረት በጀመረ ጊዜ ተመሳሳይ ችግር አጋጥሞታል፡፡ ዘግየት ብለው የመጡትና ሌላው ፍልስጤማዊ አሜርካዊ ምሁር ኤድዋርድ ሰኢድ በኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ለብዙ አመታት ያስተማሩ ሲሆን እርሳቸውም ተመሳሳይ ችግር አጋጥሞአቸዋል፡፡ ኮል አሁንም የሚሉት አላቸው፡- ‹‹ኤድዋርድ ሰኢድ የፍልስጤምን ሕዝቦች አስመልክተው የሚሰጧቸው አስተያየቶች በመቶዎች የሚቆጠሩ የተቃውሞ አ-ሜይሎችና ደብዳቤዎች እንዲጎርፉ ምክንያት የሚሆኑ ብቻ ሳይሆኑ የተለያዩ የጋዜጣ አዘጋጆች ወደ እኛ እየደወሉ እንድናወግዛቸው ወይም ከስራቸው እንድናባርራቸው እንዲጠይቁን ጭምር የሚያደርጉ ነበሩ፡፡››[50] የኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ችግር በዚህ ብቻ የሚቋጭ አይደለም፡፡ በ2004 የደቪድ ፕሮጀክት የሚባለው ድርጅት የኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ የመካከለኛው ምስራቅ ጥናት መርሐግብር ጸረ- ሴማዊ መሆኑንና የእስራኤልን አቋም የሚከላከሉ አይሁድ ተማሪዎችንም እንደሚያስፈራራ የሚያሳይ የፕሮፓጋንዳ ፊልም አዘጋጅቶ ነበር፡፡[51] ከዚያ በኋላ ኮሎምቢያ ዩንቨርሲቲ ኒው ዮርክ ሰንን በመሳሰሉት የኒዎኮንሰርቫቲቭ ጋዜጦች ክፉኛ ነበር የተወረፈው፡፡ ይሁን እንጂ ፋካሊቲው ያቋቋመው አጣሪ ኮሚቴ በግቢው ውስጥ አንድ ፕሮፌሰር ለተማሪዎች ጥያቄ ንዴት የተቀላቀለበት መልስ

ከመስጠታቸው ውጪ ሌላ ምንም አይነት ጸረ-ሴማዊ እንቅስቃሴ መኖሩን የሚያሰይ ማስረጃ እንዳልተገኘ ገልጿል። ኮሚቴው በተጨማሪም ይህ የተባለው ፕሮፌሰርም ግልፅ የሆነ የማስፈራራት ዘመቻ እየተደረገበት እንደሚገኝ አረጋግጧል።[52]

አንድ ሰው እነዚህን ክስተቶች ብቸኛና ብጤ የሌላቸው እድርጎ ሊያስብ ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን ተመሳሳይ ሁኔታዎች በየጊዜው እንደሚከሰቱ ለማሳያ የሚከተለውን አጋጣሚ እንመልከት። በ2006 በየል ዩኒቨርሲቲ የታሪክና ሶሺዎሎጂ ትምህርት ክፍል ፕሮፌሰር ጆአን ኮልን የትምህርት ክፍሉ (department) ሃላፊ አድርጎ ለማስቀመጥ ድምፅ ሰጠ። ሰውዬው ‹‹ኢንፎርምድ ኮሜንት›› በተባለውና ትልቅ ተቀባይነት ባለው ስራቸው ይበልጥ የሚታወቁ ሲሆን ከቅርብ አመታት ወዲህ ደግሞ በእስራኤል ላይ የሂስ ዱላቸውን በማሳረፍ ስማቸው እየተወሳ ሄዷል። በዚህም የተነሳ አፍቃሪ እስራኤል የሆኑ የዎል ስታሪት ጆርናልና የዋሺንግተን ፖስት ጋዜጣ አምድ አዘጋጆች የኮልን ለዚያ ቦታ መመረጥ በመቃወም የፃፉ ሲሆን ጆዊሽ ዊክ የተባለው ጋዜጣ በበኩሉ ዩኒቨርስቲውን በመርዳት የታወቁ አይሁዳውያን ለጋሾችን ዝርዝር በማውጣት ተቃውሞውን በመግለፁ የዩኑቨርሲቲው የታሪክና ሶሲዮሎጂ ትምህርት ክፍል የምደባ ኮሚቴ ሃሳቡን ቀይሮ ሰውዮው በቦታው ላይ እንዳይቀመጡ ለመወሰን ተገዷል። እነዚያ ለጋሽ አይሁዳውያን በዩኒቨርሲቲው ላይ ያሳደሩትን ተፅእኖ ይህ ነው ብሎ በትክክል መግለፅ ቢያስቸግርም አጋጣሚው የሚያስገነዝበን ጉዳይ የእስራኤል ደጋፊዎች በየተቋማቱ ውስጣዊ አሰራር ሳይቀር የቱን ያክል መግባት እንደሚችሉ ነው።[53]

እስራኤልን ከትችት ለመከላከል የሚደረገው ጥረት ዒላማ ካደረጋቸው ግለሰቦች መካከል፤ ዩኒቨርሲቲዎችን የሚጎበኙ ፕሮፌሰሮች፤ ተጋባዥ ገለፃ ሰጪዎች (Gust lecturers) የሚገኙ ሲሆን የዚህ ሁሉ ጥረት የመጨረሻ ውጤት በየተቋማቱ በነፃ ሃሳብን የመግለፅና የመከራከር አካዳሚያዊ ነፃነት የሌለበት የመማር ማስተማር ድባብ መፍጠር ነው። በ1984 ስታንፎርድ ዩኒቨርሲቲ የቀድሞ ምሩቅና የኮንግረስ አባል የነበሩትን ጌት ማክ ክሎስኪን እንደ ጎብኚ ገለፃ ሰጪ (visting lecturer) ትምህርት ይሰጡ ዘንድ

ይጋብዛቸዋል። ሰውየው አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠውን ያልተገደበ እርዳታ በዋነኛነት በመቃወም ይታወቃሉ። በ1980 ለኮንግረስ ባቀረቡት የማሻሻያ ሃሳብ አሜሪካ ለእስራኤል ከምትሰጠው እርዳታ ላይ እስራኤል ያለ አግባብ በምእራባዊው ዳርቻ ለምትገነባቸው መንደሮች የምታውለውን ያክል ገንዘብ እንዲቀነስባት ማስወሰን ችለውም ነበር። በዚህ ድርጊታቸው ምክንያት ጸረ-ሴማዊ የሚል ቅጥያ የተለጠፈላቸው ከመሆኑም በላይ በ1982 ለሴኔት ባደረጉት የምርጫ ውድድር እንዲሸነፉ ተደርገዋል። ይሁን እንጂ እሰጥ አገባው እዚያው ላይ መቆም ሲገባው እነሆ አሁን ደግሞ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ተከትሏቸው መጥቷል። እናም የስታንፎርድ ሂለል ቻፕተር ዳይሬክተር ‹‹የማክ ክሎስኪ በጎብኚ ገለፃ ሰጪነት መመደብ በአይሁድ ማህበረሰብ ፊት ላይ ያረፈ ጥፊ ነው›› በማለት ተቃውሟቸውን አሰሙ። የተማሪዎች አመራር ካውንስል አባላት ሰውየው ከሚሰጡት ገለፃ ላይ የቀድሞው የአሜሪካ ረዳት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጆርጅ ቦልን ፅሁፍ ካላስወገዱና አይፓክን የሚደግፍ ሌላ ፅሁፍ ካላካተቱ በስተቀር የሚሰጣቸው ድጎማ እንዲቀነስ ወይም ከነጭራሹ እንዳያስተምሩ ይደረግ ሲል አቋሙን አሳወቀ። ‹‹የተለየ ሂሳብ ላለው ሌላ ሰው ተጨማሪ እድል ይሰጥ›› በማለትም ከዩኒቨርሲቲው የተለመደ አሰራር ውጭ የሆነ ጥያቄ አቀረበ። በመጨረሻም የፋካሊተው አጣሪ ቡድን በደረሰበት ድምዳሜ የተማሪዎቹ ቡድን የአካዳሚክ ነፃነትን ክፉኛ እየተጋፋ መሆኑን በመግለፅ ማክ ክሎስኪ ከፕሬዝዳንቱ መደበኛ የይቅርታ ጥያቄ ከቀረበላቸው በኋላ ስራቸውን እንዲቀጥሉ ተደርገዋል።[54]

እኛ የዚህ መፅሀፍ አዘጋጆች ራሳችን ተመሳሳይ ችግር ደርሶብን ያውቃል። በ2006 መግቢያ ላይ የዩ.ኤስ. አሜሪካ የባህር ኃይል ጦር ኮሌጅ ባዘጋጀው የስትራቴጂ ፎረም የፓናል ውይይት ላይ በየግላችን አንድንገኝ ግብዣ ቀረበልን። የፓናል ውይይቱ ርእስ ‹‹ዘ ኔቸር ኦፍ ፓወር›› የሚል ሲሆን ከመካከለኛው ምስራቅ ወይም ከዩ.ኤስ አሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ጋር ብዙም የሚገናኝ አልነበረም። ይህ መፅሀፍ ከመውጣቱ በፊት አሳትመነው የነበረውን የመጀመሪያውን ‹‹የእስራኤል ሎቢ›› የሚለውን ፅሁፋችንን መውጣት ተከትሎ መጋቢት በ2006 ለኮሌጁ ፕሬዚዳንት በርካታ የኮንግረስ

አባላት ስልክ እየደወሉ በዚያ የፓናል ውይይት ላይ ንግግር እንድናደርግ የመጋበዛችንን አግባብነት ጠየቋቸው።[55] ለፕሬዚዳንቱ ምስጋና ይድረሳቸውና ለእነዚያ ሰዎች ጥያቄ ምንም አይነት ምላሽ ለመስጠት ባለመፍቀዳቸው በዝግጅቱ ላይ ያለምንም ችግር መሳተፍ ቻልን። ይህ ከሆነ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ለስቴፈን ኤም ዋልት (ከዚህ መፅሀፍ አዘጋጆች አንዱ) በሞንታና ዩኒቨርሲቲ ገለፃ እንዲያደርጉ ግብዣ ደረሳቸው። በዚያም ጊዜ ቢሆን እንዲሁም ከበርካታ የፋካልቲው አባላት ውግዘት የተከተለን ሲሆን የፋካልቲውን አስተባባሪ ከቦታው እንዲባረሩ ለማድረግም የተራዘመ ሆኖም ግን ያልተሳካ ዘመቻ ተካሄዷል።[56]

አፍቃሪ-እስራኤል ቡድኖች በየፋካልቲዎቹ ከሚያደርጓቸው የተለያዩ ጥረቶችና በሰው ሃይል አጠቃቀም ላይ እስራኤልን የሚቃወሙ ሰዎችን ለማስወገድ ከሚወስዷቸው እርምጃዎች ጎን ለጎን የእነርሱን አቋም የሚፃረሩ ምሁራዊ ጽሁፎችም እንዳይታተሙ ጫና ያደርጋሉ። ለምሳሌ በ1998 ኤ.ዲ.ኤል (የጸረ ስም ማጥፋት ሊግ)፣ ኖርማን ፊንክልስታይንና ሩት ቤቲና በርንስ የጻፉት "A Nation on Trial" የተባለ መጽሐፍ እንዲህ ዓይነት እጣ አጋጥሞታል። ይህ መጽሐፍ፤ ዳንኤል ጎልድሀገን የጻፈውንና በከፍተኛ ሁኔታ የተሸጠለትን ‹ሂትለርስ ዊሊንግ ኤክስኪውሽነር› የተባለውንና ‹‹ሆሎኮስት›› በሚል መጠሪያ የሚታወቀው የናዚዎች ጭፍጨፋ የራሳቸው የናዚዎች እምነት ወይም የሂትለር እብደት የወለደው ሳይሆን በጀርመን ማህበረሰብ ውስጥ ናዚዎች ከመምጣታቸው በፊት ጀምሮ ስሩን ሰዶ የኖረ የአጥፊዎች የፖለቲካ ዘይቤ (eliminationist ideology) መሆኑን የሚያትተውን መጽሐፍ የሚሀይስ ስራ ነው። የሚገርመው ነገር ልክ እንደጎልድሀገን መጸሐፍ ሁሉ ‹‹ኤ. ኔሽን. ኦን. ትሪያል› የተባለው መጽሐፍ ክብር የሚሰጣቸው ከሆኑ የተለያዩ ምሁራን ውዳሴና ትችትን አስተናግዷል። ይሁን እንጂ የኤ. ዲ.ኤል ዋና ኃላፊ አብርሀም ፎክስማን፡- ‹‹ኤ-ኔሽን ኦን ትሪያል መታተም የሌለበት መጸሐፍ ነው። ምክንያቱም ዋናው ጉዳይ የጎልደንሃገን መጸሐፍ ትክክል ነው ወይም አይደለም የሚለው ሳይሆን ህጋዊ የሆነው ትችት የትኛው መሆኑን የማወቅና ያለማወቅ ጉዳይ ነው›› በማለት ተቃውሟቸውን ገልጸዋል።[57]

ተመሳሳይ የሆነ ታሪክ በ2003 የተከሰተው የሃርቫርዱን የሕግ ፕሮፌሰር በመወከል የሕግ ባለሙያዎች ለካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ የማስፈራሪያ መልእክት በላኩ ጊዜ ነበር። አለን ደርሾዊትዝ የጻፈውን "ዘ-ኬዝ ኦፍ እስራኤል" የተባለውን መጽሐፍ ፉንክልስታይን ‹ቢዮንድ ቸትዝባህ› በሚል ርእስ ባዘጋጀው መጽሀፍ የሒስ መአቱን ያወረደበት በመሆኑ የፊንክልስታይን መጽሐፍ እንዳይታተም ለማድረግ ነበር የህግ ባለሙያዎቹ ማስፈራሪያ ለመላክ የተገደዱት። ደርሾዊትዝ ተመሳሳይ የሆነ ደብዳቤ ለካሊፎርኒያው ገኘር ለአርኖልድ ሽዋዚንገር የጻፈለት ሲሆን (ሽዋዚንገር ገገር እንደመሆኑ ዩኒቨርሲቲ በመሰሉ የህዝብ ሃብቶች ለስም ብቻ የሆነ ስልጣን እንዳለው ይታወቃል) ይህም በፊንክልስታይን ላይ የከፈተው ዘመቻ አካል መሆኑ ነው። ደርሾዊትዝ የኋላ ኋላ የእርሱ ጥረት ነጻውን ፕሬስ ለመጫን እንዳልሆነና የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ባለስልጣናት ግን እንደዚያ ዓይነት ትርጉም እንደሰጡት ለመግለጽ ሞክሯል። የሆነ ሆኖ የፊንክልስታይን መጽሐፍ ያንን ግፊት ተቋቁሞ ለሕትመት በቅቷል።[58]

አሜሪካውያን እስራኤልን የሚመለከቱ ትችቶችን እንዳያነቡና እንዳይሰሙ የማድረጉ ዘመቻ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሳይቀር ተደርጓል። ለምሳሌ የካቲት 2005 ላይ ዘ ኒው ዮርክ ሰን የተባለው ጋዜጣ ባወጣው ሪፖርት መሰረት ለሁለተኛ ደረጃ መምህራን በተዘጋጀውና የኒው ዮርክ ከተማ አስተዳደር የትምህርት ክፍል በገንዘብ በደገፈው የገለጻ መርሃ ግብር ላይ የኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲው ራሺድ ኻሊዲ እንደሚሳተፉ ታወቀ። ከዚያ በኋላ ዘ.ኒው ዮርክ ሰንና የተወሰኑ ፖለቲከኞች ኻሊዲ ከዚያ መርሐግብር እንዲባረሩ ለማድረግ ወዲያው ተንቀሳቀሱ። ዘ- ኒው ዮርክ ሰን፣ ኻሊዲ እስራኤልን፤‹‹ዘረኛ መንግስት›› ሲሉ ጠርተዋታል በማለት ተጠያቂ አደረጋቸው። (ይህን ክስ ኻሊዲ በሃይል ተከላክለዋል) የኻሊዲን በዚያ መርሐግብር መሳተፍ ‹‹የሚያናድድ›› በማለት የተቃወሙት ደግሞ የኒው ዮርኩ ዲሞክራት የኮንግረስ አባል አንቶኒ ላወይነር ሲሆኑ እንደዚያ ብለው የተናገሩት ለኒው ዮርክ ከንቲባነት ይወዳደሩ በነበረበት ጊዜ ነው። የብሩክሊን ሲቲ ካውንስል አባል ሲምቾ ፊልደር የኻሊዲን ተሳትፎ ‹‹የሚያስጠላ›› በማለት ጠርተውታል። ከዚህ ሁሉ በኋላ ነበር የዩኒቨርሲቲው የትምህርት

ክፍል ቻንስለር ጆል ክሌይን የኻሊዲን መሰረዝ በመግለጽ በቀጣዩ ቀን የሚከተለውን የተናገሩት፤‹‹ራሺድ ኻሊዲ ለትምህረት ክፍላችንና ለመምህራን የሙያ ብቃት በሚያላብሰው በዚህ መርሐግብር እንዳይከፈሉ ታግደዋል፡፡ ለወደፊቱም አይካፈሉም፡፡››[59] በቀጣዩ አመት የኒው ዮርክ ሲቲ ካውንስል እስራኤልን የተመለከተ የጥናት መርሃግብር ያጸደቀ ሲሆን ሃሳቡን ያጸደቀውና ያነቃቃው ደግሞ በኒው ዮርክ የሚገኘው የእስራኤል ቆንስላ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ነው፡፡[60] ይህ በእንዲህ እንዳለ የሰላሳ አይሁዳውያን ቡድኖች ሕብረት በመላ ዩናይትድ ስቴትስ የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችን በማሰልጠን የእስራኤል ደጋፊዎች እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል መርሐግብር አቀናጀ፡፡[61]

አፍቃሪ እስራኤል ቡድኖችና ግለሰቦች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚገኙ ተማሪዎች፣ ፕሮፌሰሮች፣ አስተዳዳሪዎችና በራሱ በሥርዓተ ትምርቱ ላይ ያነጣጠሩ አስተያዩቶችንና ሃሳቦችን ለመቅረጽ ባለ ብዙ ግንባር ጦርነት ከፈቱ፡፡ እርግጥ ነው ጥረታቸው በኮንግረስ ወይም በመገናኛ ብዙሃን (media) ላይ ያገኙትን ዓይነት ስኬት ባይመዘገብበትም ያን ያክል መጥፎ የሚባል ግን አልነበረም፡፡ ይህን ለማለት በቂ ምክንያት የሚሆነን በመካከለኛው ምሥራቅ የፖለቲካው ግለት እንዳለ መሆኑ ሲታይና እስራኤልም በኃይል የያዘቻቸውን ግዛቶች የማስፋፋት ተግባሯን ቀጥላ እያለ ከአምሥት ዓመታት በፊት ከነበረው ይልቅ ዛሬ በአሜሪካ ከፍተኛ ተቋማት ውስጥ የሚሰነዘርባት ትችት አነስተኛ ሆኖ መገኘቱን ስናስተውል ነው፡፡[62]

የተቃውሞ ስልቶች

በተደጋጋሚ በትኩረት እንደተጠቀሰው እስራኤልን በመወከል ሎቢ ማድረግ የፖለቲካ አካሄድ የመሆኑን ያክል ከእስራኤል ጋር በሚያያዙ ጉዳዮች የሚኖረውን የሕዝብ አስተያየት ለመቅረጽ የተለያዩ ጥረቶችን ማድረግ እንደሚጠቅም ግልጽ ነው፡፡ ሎቢው በአሁኑ ጊዜ እያደረገ ያለው ተጽዕኖ የዩናይትድ ስቴትስንም ሆነ የእስራኤልን ጥቅም እያስከበረ ነው ብለን ባናምንም ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ አካሄድ በሆነውና በተለመደው የራስን

ጉዳይና ዓላማ የማስፈጸም ስልት (rough and tumble) መሠረት እየሄደ እንደሆነ እናስባለን፡፡ ሆኖም ግን እንዳለመታደል ሆኖ የተወሰኑ አፍቃሪ እስራኤል ግለሰቦችና ቡድኖች እስራኤልን ከትችት ለመከላከል የሚያደርጉትን ጥረት ሕገ-ወጥ ወደሆነ ጠርዝ በመውሰድ እነርሱ የማይፈልጉትን ሃሳብ የሚያራምዱ ሰዎችን ዝም ለማሰኘት ሲሞክሩ ይታያሉ፡፡ ይህ ሙከራቸው በእስራኤል ላይ ትችት የሚያቀርቡ ግለሰቦችን ስም ማጥፋትንና ማስፈራራትን ከዚያም ፈቀቅ ሲል የህይወት ታሪካቸውንና ሥራቸውን እስከማጉደፍና ማበላሸትም ድረስ ይዘልቃል፡፡ ቀደም ብለን ያነሳናቸውና በአካዳሚክ ማሕበረሰቡ ውስጥ ሎቢው የሚያደርገውን ተጽዕኖ የሚያሳዩ በርካታ ምሳሌዎች በዲሞክራሲያዊ ማሕበረሰብ ውስጥ ቦታ እንደሌላቸው የታወቀ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ሎቢው የሚፈልገውን ያክል ጠንካራ የታክቲክ ክንዱን በአካዳሚው ዓለም ውስጥ ማሳረፍ አልቻለም፡፡

ለአብነት ያክል በጥቅምት 2006 አይሁዳዊ በሆኑት የኒው ዮርክ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ምሁር ቶኒ ጆድት ላይ የደረሰውን እንመልከት፡፡ ቶኒ በተደጋጋሚ የእስራኤልን ድርጊቶች በመተቸት ይታወቃሉ። እናም በተጠቀሰው ጊዜ ኒው ዮርክ በሚገኘው የፓላንድ ቆንስላ ገለጻ ያደርጉ ዘንድ ግብዣ የቀረበላቸው ሲሆን የገለጻው ርዕስም ‹‹የእስራኤል ሎቢና የዩ. ኤስ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ›› የሚል ነበር፡፡ ያንን ዝግጅት የፓላንድ መንግስት በገንዘብ ያልደገፈው ሲሆን ዝግጅቱን ያቀናጀው የቆንስላው ጽ/ቤቱ “ኔትወርክ 20/20” ከተባለ መንግስታዊ ያልሆነና ተመሳሳይ ዝግጅቶችን በማመቻቸት ከሚታወቅ ድርጅት አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ተከራይቶ ነበር፡፡ ይህ በእንዲህ እያለም የአሜሪካን ጆዊሽ ኮሚቴ ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ዴቪድ ሃሪስ የዚህ ዝግጅት ወሬ ሸው ይልባቸውና የፓላንድ ቆንስላ ጽ/ቤት ኃላፊን ደውለው ያነጋግሯቸዋል። ሃሪስ ቆየት ብለው ሁኔታውን ሲገልጹ የደወሉት ልክ ‹‹እንደ ፓላንድ ወዳጅ›› ሆነው መሆኑንና ሊደረግ የታሰበው ገለጻ ከፓላንድ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ጋር የሚጋጭ መሆኑን ይገልጹላቸዋል፡፡ የቆንስላው ኃላፊ በተጨማሪም ኤ. ዴ. ኤል ከተባለው ድርጅት ሁለት ተመሳሳይ መልዕክት ሲደርሳቸው እንዲህ ማለታቸው ተወስቷል፡- ‹‹ይህ በእርግጥ ለስለስ ያለ የተጽዕኖ ማድረጊያ መንገድ ነው… እኛ ትልልቅ

ሰዎች እንደመሆናችን እንዲህ ያለውን አካሄድ ለመገንዘብ አይከብደንም፡፡›› ከዚያ በኋላ የቆንስላው ሃላፊ የጀድትን የገለጻ መርሐግብር በመጨረሻው ሰዓት መሰረዛቸው እንደተሰማ ድርጊቱ በነጻ ሐሳብን የመግለጽንና የመወያትን መብት የሚፃረር አካሄድ መሆኑን በመግለጽ የታወቁ አሜሪካውያን ምሁራን ለቆንስላው ማመልከቻ አስገቡ፡፡[63] ጀድት ራሳቸው እስራኤላዊ ቢሆኑም የእስራኤልን ፖሊሲዎች ስለሚተቹ እርሳቸውንም ሆነ ቤተሰባቸውን የመግደል ተደጋጋሚ ዛቻ ይደርሳቸው እንደነበር መናገራቸው ተዘግቧል፡፡[64]

በዩናይትድ ስቴትስ የፈረንሳይ ኤምባሲ የካርመን ካሊንን ‹ባድ ፌይዝ› የተባለ መጽሐፍ መታተም አስመልክቶ ግብጣ ባዘጋጀ ጊዜ ተመሳሳይ ሁኔታ ተከስቷል፡፡ መጽሐፉ በሰፊው የሚያትተው ባለጸጋ የሆነው የፈረንሳይ ባለስልጣን (ሉዊስ ዳርኩዮር) የፈረንሳይ አይሁዶች ወደ ኦሽዊትዝ የእልቂት ካምፕ እንዲጓዙ ስለተጫወተው ታላቅ ሚና ነው፡፡ መጽሀፉ ፈረንሳዊያን በሆሎኮስት እልቂት የተጫወቱትን የተባባሪነት ሚና በሚገባ አጉልቶ የሚያሳይ ቢሆንም የመጽሀፉን ምረቃ አስመልክቶ ያዘጋጀውን ድግስ የሚቃወም አቤቱታ ለኤምባሲው ደረሰው፡፡ ተቃውሞው ያጠነጠነው በካሊን መጽሀፍ ግርጌ ላይ የሚገኝ አንድ አንቀጽ (post script) በያዘው መልዕክት ላይ ነበር፡፡ አንቀጹ እንዲህ ይላል፡- ‹‹የሉዊስ ዳርኩዮርን ታሪክ ሳጠናቅር ያስጨነቀኝ ነገር በፈረንሳይ አይሁዳዊያን ላይ የደረሰው ሽብርና ረዳት የለሽ መሆናቸው ሲሆን ዛሬ ደግሞ የእስራኤል አይሁዳውያን ያንኑ ሽብር በፍልስጤማውያን ሕዝቦች ላይ ሲደግሙት መመልከቴ ነው፡፡›› ከዚህም ከዚያም ለተነሳበት ግፊት የተንበረከከው የፈረንሳይ ኤምባሲ በዚያ የግርጌ አንቀጽ ላይ የተቀመጠውን የደራሲውን ግላዊ አስተያየት እንደማይደግፍ በመግለጽ ግብጣውን መሰረዙን አስታወቀ፡፡[65]

ሌላው በጣም አሳዛኝ አጋጣሚ የተከሰተው ደግሞ መጋቢት 2003 ላይ ‹My Name is Rachel Corrie› በሚል ርዕስ የፍልስጤማውያን ቤት እንዳይፈርስ ጋዛ ውስጥ ተቃውሞ እያደረገች እያለች ቤቱ በላዩዋ ላይ በቡል ዶዘር እንዲደረመስባት ተደርጎ የሞተችውን አሜሪካዊት ወጣት አስመለክቶ የተዘጋጀ ተውኔት በቀረበ ጊዜ ነበር፡፡ ተውኔቱ የተዘጋጀው የኮሪን ማስታወሻ

መሠረት አድርጎ ሲሆን ሚያዚያ 2005 በሮያል ኮርት ቲያትር ቤት በታላቅ አድናቆትና ጭብጨባ ነበር የተከፈተው። ከዚያ በኋላ መጋቢት 2006 ላይ ይኸው ተውኔት የተለያዩና አወዛጋቢ የሆኑ ተውኔቶችን የማሳየት ልማድ ባለው የኒው ዮርክ ቲያትር ወርክሾፕ ሊታይ ቀጠሮ ተያዘለት። ኒው ዮርክ ታይምስ እንደዘገበው፡- ‹‹የቲአትር ቤቱ የአርት ዳይሬክተር፣ የኒው ዮርክ ከተማ የአይሁዳዊያን ሃይማኖት ተከታዮችና የአይሁድ ማህበረሰብ መሪዎች ባሳደሩባቸው ተጽእኖ ቴያትሩ የሚታይበትን ጊዜ ለማራዘም ተገደዱ›› ብሏል። ሎስ አንጀለስ ታይምስ ደግሞ የሰውዬውን አስተያየት እንዲህ በማለት አስቀምጦታል፡- ‹‹አሪዮል ሻሮን ከታመሙና ሃማስ ስልጣን ከያዘ በኋላ የምንሰማው ነገር ሁሉ ቁጣ የተሞላበት ሆኗል››[66] ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ነበር ያ ተውኔት 2006 ማብቂያ አካባቢ ኒው ዮርክ ሮያል ኮርት ፕሮዳክሽን በሚባለው ሌላ ቲያትር ቤት ለ 80 ጊዜያት እንዲታይ የተደረገው። ያ መዘዘኛ ተውኔት ታህሳስ 2006 ላይ ወደ ካናዳ ተወሰደ። በሃገሪቱ የታወቀውና ለትርፍ ያልቆመው ቲያትር ቤት ሊያሳየው ከተዘጋጀ በኋላ በቶሮነቶ የሚገኘውን የአይሁድ ማህበረሰብ ቁጣ በመፍራት እንዳይታይ አድርጓል።[67] ሚያዝያ 2007 ደግሞ የሚያሚ ሞዛይክ ቲያትር ተውኔቱን ሊያሳይ በዝግጅት ላይ እያለ ሚያሚ ሄራልድ ‹‹አናሳ የሆኑና በወኔ የሚጮሁ›› ያላቸው የአይሁድ ማህበረሰቦች ባስነሱት ሁከት ሳይታይ ቀርቷል።[68]

አደገኛ የእስራኤል ተቺዎች ሚባሉትን ሰዎች የማሳደዱ መረን የለቀቀ አሰራር ሎቢ ከሚያደርጉት ታዋቂ ድርጅቶች አንዱን ፍርድ ቤት እስከመቆም አድርሶታል። ጉዳዩ እንዲህ ነው፡- በ1980ዎቹና 90ዎቹ ኤ.ዲ.ኤል(የጸረ ስም ማጥፋት ሊግ)፣ ሮይ በልክ የተባለ በግሉ የመርማሪነት አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ ይቀጥራል። ይህ ሰው በአፓርታይድ ዘመን ለደቡብ አፍሪካ መንግስት መረጃ ያቀብል ነበር። ይህ በእንዲህ እያለም በልክ ከሎስ አንጀለስ የፖሊስ ክፍልና ከሞተር ብስክሌት መረጃ ክፍል ምስጢራዊ ሰነዶችን በመመንተፍ ወንጀል ክስ ይቀርብበታል። ተዘረፉ በተባሉት በሁለቱ ሰነዶች የአስራ ሁለት ሺህ ሰዎችና ስድስት ሺህ የሚሆኑ በካሊፎርኒያ የሚገኙ ድርጅቶች ስም ዝርዝርና ሌሎች መረጃዎች ይገኙ

የነበረ ሲሆን ከፋይሎቹ የተወሰኑትን በልክ ለ ኤ ዲ ኤል ሰጥቷል፡፡ ከነጭ አክራሪዎችና ኒዎ ናዚዎች በተጨማሪ ኤ ዲ ኤል ያነጣጠረው በአረብ አሜሪካውያን ቡድኖች፤ በአይሁድ ተወላጆችና እስራኤልን ይተቻሉ በሚባሉ ሌሎች አካላት ላይ ጭምር ነው፡፡ የሳንፍራንሲስኮ ዲስትሪክት አቃቤ ሕግ ወንጀሉን ስለደረሰበት የወንጀል ማጣራት እንዲደረግ በማዘዙ የፖሊስ መኮንኑ በልክ የፖሊስን ኮምፒውተር ፈቃድ ሳያገኝ በመበርበር ወንጀል ተጠያቂ ተደረገ፡፡ ሆኖም ግን አቃቤ ሕጉ ኤ ዲ ኤልን ህግ ፊት ለማቅረብ አመነቱ፡፡ ምክንያቱም በእርሳቸው እምነት ኤ ዲ ኤል ለበጎ ተግባር የቆመ ድርጅት ነበርና። ከዚያ በኋላ ኤ. ዲ. ኤል አክራሪነትን ለመከላከል ያውሉት ዘንድ ለሳንፍራንሲስኮ ዲስትሪክት የለገሰውን 75.000 ዶላር አቃቤ ሕጉ ለመቀበል ተስማሙ፡፡ ስለሆነም በኤ. ዲ. ኤል ላይ ምንም ዓይነት ክስ ሳይመሰረት ቀረ፡፡

ይሁን እንጂ በሶስት ሰዎች ላይ (ከእነርሱ ሁለቱ አይሁዳውያን የሆኑ) ክስ ሊመሰረትባቸው ግድ ሆነ፡፡ ኤ. ዲ. ኤል በመጨረሻ ይህንንም ከፍርድ ቤት ውጭ በሚደረግ ድርድር ለመጨረስ ባደረገው ጥረት 50.000 ዶላርና የፍ/ቤቱን ሌሎች ወጪዎች ሊከፍል ተስማምቶ ክሱ ተሰረዘ፡፡ የኤ. ዲ. አል. ፕሬዝዳንት አብረሀም ፎክስማን ኤ. ዲ. ኤል. ማንንም የመሰለል ፍላጎት እንደሌለው በመጥቀስ ይከራከራሉ፡፡ ሆኖም ግን እስራኤልን የሚተቹ ሰዎችንና ድርጅቶችን ዝም ለማሰኘት የሚያደርገውን ጥረት ‹‹የአይሁድ ሕዝብ ሰላሙና ጸጥታው ተጠብቆለት የሚኖርበትን ሁኔታ በየትኛውም አካባቢ ለመፍጠር ከምናደርገው ዘርፈ ብዙ ጥረት አንዱ ነው›› በማለት የአሰራራቸውን ሕጋዊነት ለማስረዳት ይሞክራሉ። ዳሩ ግን እውነታው ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው ኤ. ዲ. ኤል. የአይሁድን ሕዝብ ከጸረ-ሴማዊነት እንቅስቃሴም ሆኖ ከዘረኝነት ጥቃት ለመከላከል እየሰራ ያለመሆኑን ነው፡፡ ከዚያ ይልቅ እስራኤልንና አሜሪካ የምትሰጣትን እርዳታ የሚተቹ ሰዎችን ዝም ማሰኘት ነው ዋነኛ ተግባሩ፡፡[69]

አዲሱ ‹‹ጸረ-ሴማዊነት››

ሎቢው እንዴት ተግባሩን እንደሚያከናውን የምናደርገው ገለጻ ጸረ-ሴማዊነት የሚሰኘውን ኃይለኛ መሳሪያውን እንዴት እንደሚጠቀምበት እስካልፈተሸን ድረስ የተሟላ አይሆንም። ማንም ግለሰብም ይሁን ድርጅት የእስራኤልን ድርጊቶች የሚተች እስከሆነና ዩ ኤስ አሜሪካ መካከለኛው ምስራቅን አስመልክቶ በምትከተለው ፖሊሲ ላይ አፍቃሪ እስራኤል ቡድኖች ተጽእኖ ያደርጋሉ የሚል ሃሳብ እስከሰነዘረ ድረስ ጸረ-ሴማዊ የሚለውን ስያሜ የማግኘቱ አጋጣሚ ሰፊ ነው። ምንም እንኳን አይፓክና የፕሬዝዳንቶች ኮንፍረንስ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ ራሳቸው ለመግለጽ ይሉኝታ የማያጠቃቸው ቢሆኑም፣ እንዲሁም የእስራኤል መገናኛ ብዙሃን ራሳቸው ‹‹የአሜሪካ አይሁድ ሎቢ›› እያሉ በግልጽ የሚጠሯቸው ቢሆንም ማንም ሰው ስለ እስራኤል ሎቢ የሚያነሳ ከሆነ ጸረ-ሴማዊ የመባሉ ነገር ያለቀለትና ሳይታለም የተፈታ ነው።[70] የዚህ ተቃርኖ ውጤት እንግዲህ ሎቢው ያለውን ኃይልና ተጽእኖ በየጊዜው እየጠቀሰ ይኩራራል። ትኩረታቸውን በእርሱ ላይ የሚያደርጉ ክፍሎችን ደግሞ ከማጥቃት አይመለስም። ‹‹ክንደ ጠንካሮች መሆናችንን እወቁ፤ ግና ስለኛ ምንም አትበሉ››ነው ነገሩ። ይህ ክስ አሁን አሁን መሰማት የጀመረው በተለይም በአውሮፓ እያንሰራራ ያለውን የመረረ ጸረ-ሴማዊነት ተከትሎ ነው። በጥቅምት 2002 የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ የተባለው ቡድን የበላይ የሆኑት ሞርትማየር ዘከርማን በዩ.ኤስ ኒውስ ኤንድ ዎርልድ ሪፖርት ላይ ጉዳዩን አስመልክተው ሲጽፉ ‹‹አሳፋሪ የሆነው የጸረ-ሴማዊነት ተላላፊ በሽታ›› በሚል ርእስ ስር ‹‹አውሮፓ ዳግም በዚህ በሽታ ተለከፈች›› በማለት አትተዋል። የቦስተን ግሎብ ጋዜጣ አምደኛ (columnist) ጄፍ ጀኮቢ መጋቢት 2004 ላይ አምዱን በሙሉ ‹‹የጸረ-ሴማዊነት ካንሰር በአውሮፓ›› ብሎ ለሰየመው ርእስ አውሎታል።[71] በአውሮፓ ማህበረሰብ የአሜሪካ አምባሳደር በ2004 መግቢያ ላይ በዚሁ ዙሪያ ባደረጉት ንግግር ‹‹አሁንም

ዞረን እዚያው ላይ መጥተናል፡፡ ጸረ-ሴማዊነት በ1930ዎቹ እንደነበረው ሁሉ አስቀያሚ ገጽታውን ተላብሷል›› ብለዋል፡፡[72]

የጸረ-ሴማዊነት እንቅስቃሴ በጣም የተወሳሰበ ጉዳይ እንደመሆኑ ደረጃውን ለመለካት አስቸጋሪ ቢሆንም አሉ የሚባሉት መረጃዎች ሲመዘኑ ግን በተቃራኒ አቅጣጫ ነው እያመላከቱ ያሉት፡፡ በእርግጥም በ2004 ጸደይ ላይ አውሮፓ ውስጥ ጸረ-ሴማዊነት አንሰራርቷል የሚል ክስ በአሜሪካውያን ዘንድ በተለመደበት ጊዜ ኤ.ዲ. ኤልና የፔው ሪሰርች ማእከል ያደረጉት ጥናት ጸረ- ሴማዊነት እያሽቆለቆለ መሆኑን አሳይቷል፡፡[73]

ፈረንሳይን እንውሰድ፤ አፍቃሪ እስራኤል ቡድኖች አውሮፓ ውስጥ ከሚገኙ ሃገራት ሁሉ ከፍተኛ ጸረ-ሴማዊነት የሚታይባት ሃገር እንደሆነች የሚያስቧት ሲሆን የኒው ሪፐብሊክ ጋዜጣ ጸሐፊ ማርቲን ፔሬትዝ ዋና ከተማዋን ፓሪስን ‹‹የጸረ-ሴማዊነት ትልቋ መናሀሪያ›› በማለት ገልጿታል፡፡[74] በ2002 በፈረንሳይ ዜጎች ላይ የተደረገ ጥናት 89 በመቶ የሚሆኑት ከአይሁዳዊያን ጋር መኖርን እንደሚፈቅዱ የገለጹ ሲሆን፤ 87 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ የአይሁዳውያንን ምኩራቦች ማጥቃት አሳፋሪ ጉዳይ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ 85 ከመቶ የሚሆኑት የካቶሊክ ሃይማኖትን የሚከተሉ ሰዎች አይሁዳውያን ንግዱንና የገንዘብ ተቋማትን ተጽእኖ እያደረጉባቸው ነው የሚለውን ክስ እንደማይቀበሉ ይፋ አድርጓል፡፡[75] የፈረንሳይ አይሁዳውያን ማህበረሰብ ፕሬዚዳንት 2003 ላይ ‹‹ፈረንሳይ ከአሜሪካ የበለጠች ጸረ-ሴማዊ አይደለችም›› በማለት ተናግረዋል፡፡[76] ሃ-ኤሬትዝ ጋዜጣ የፈረንሳይ ፖሊስ ያወጣውን ዘገባ ዋቢ አድርጎ ባሰፈረው መሠረት ‹‹ምንም እንኳን ፈረንሳይ ከየትኛውም የአውሮፓ ሀገር የሚበልጡ ሙስሊሞች የሚገኙባት ብትሆንም በ2005 በውስጧ የተመዘገቡ ጸረ-ሴማዊ ክስተቶች 50 በመቶ ቀንሰው ተገኝተዋል›› ብሏል፡፡[77]

በ2006 የካቲት ወር ላይ አንድ የፈረንሳይ አይሁድ በሙስሊም ጋንግስታዎች በጭካኔ በተገደለ ጊዜ በአሥር ሺህ ሚቆጠሩ ፈረንሳውያን ወደ አደባባዮች ወጥተው ጸረ-ሴማዊነትን አውገዘዋል፡፡ፕሬዚዳንት ጚክ ሺራክና ጠቅላይ ሚነስትር ዶሚኒክ ዲ ቪልፒን ለሟቹ በተደረገው

የማስታወሻ ስነ-ሥርአት ላይ በመገኘት ከፈረንሳይ አይሁዳውያን ጋር ያላቸውን የአንድነት መንፈስ ገልጸዋል፡፡[78] ከዚህም በተጨማሪ በ2002 ከሶቪዬት ሕብረት የፈለሱ አይሁዳውያን ወደ እስራኤል ከመሄድ ይልቅ ወደ ጀርመን በመሄዳቸው ዛሬ ጀርመን የአይሁዳውያን ማህበረሰብ ቁጥር በፍጥነት የሚያድግባት ሃገር እንድትሆን አድርጓታል።

ፎርዋርድ የተባለው የአይሁዳውያን ጋዜጣ እንደሚለው ‹‹አውሮፓ በ1930ዎቹ እንደነበረችው መጥፎ ብትሆን ኖሮ አይሁዳውያን በብዛት ወደዚያ ባልጎረፉ ነበር፡፡››[79]

በመሠረቱ አውሮፓ ከጸረ-ሴማዊነት ነጻ እንዳልሆነች እንቀበላለን፡፡ አሁንም ቢሆን አውሮፓ ውስጥ (አሜሪካ ውስጥ እንዳሉት ሁሉ ማለት ነው) መራር የሆኑ ጸረ-ሴማውያን ያሉ መሆኑን ማንም አይክድም፡፡ ሆኖም ግን ቁጥራቸው አነስተኛ ከመሆኑም በላይ ጽንፈኛ የሆነውን አቋማቸውን ብዙሃኑ አውሮፓውያን አይቀበሉትም፡፡ እንዲሁም በአውሮፓ ጥቂት ሙስሊሞች ዘንድም ጸረ-ሴማዊነት መኖሩ አይካድም፡፡ ይሁንና ከእነርሱ ውስጥ የተወሰኑትን ለእንዲህ ዓይነት አቋም ያበቃቸው እስራኤል በፍልስጤማውያን ላይ የምታሳያቸው ባሕሪያት ሲሆኑ ቀሪዎቹ ደግሞ መጀመሪያውኑ ዘረኞች በመሆናቸው ነው፡፡[80] በታላቋ ብሪታኒያ ለምሳሌ The Community security Trust (CST) የተባለው የጸረ-ሴማዊነት ተመልካች ቡድን ባቀረበው ሪፖርት መሠረት በ2006 ከጸረ-ሴማዊነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ድርጊቶች በ31 ከመቶ ከፍ ብለው ተስተውለዋል፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ አስቀያሚ የሆኑ ክስተቶች በቀላሉ መታየት የሌለባቸው ቢሆንም አጠቃላይ ብዛታቸው 594 መሆኑን ስናይ ከ60 ሚሊዬን በላይ በሆነው በታላቋ ብሪታኒያ ሕዝብ ውስጥ የተከሰቱ እንደመሆናቸው ብዙ ናቸው አይባልም፡፡ ከእነርሱ ውስጥም ከሞላ ጎደል አንድ አራተኛ የሚሆኑት ማለት ይቻላል በቀጥታ ከ2006ቱ የሊባኖስ ጦርነት ጋር ተያያዥነት ነበራቸው፡፡ የሲ-ኤስ-ቲ ባልደረባ የሆኑት ማርክ ጋርድነር ‹‹እነኚህ ድርጊቶች በምንም መልኩ በ1930ዎቹ ወይም ቀደም ባሉ ዘመናት ከተፈጸሙ የጸረ-ሴማዊነት ድርጊቶች ጋር አይወዳደሩም›› በማለት ተጨባጩን ሃቅ አስቀምጠውታል፡፡[81] ዘ-እስራኤል ቤዝርድ ግሎባል ፎረም

አጌንስት አንቲ ሴሜቲዝም የተባለውን ጨምሮ በርካታ ሌሎች ቡድኖች ባወጡት ዘገባ እንደገለጹት በእነዚህ ጊዜያት ጸረ-ሴማዊነትን የሚያንጸባርቁ ክስተቶች እየቀነሱ መጥተዋል፡፡ ያም ሆኖ አንዳንድ የማይዘገቡ ክስተቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ እግምት ውስጥ በማስገባት እውነተኛ የሆኑ ጸረ-ሴማዊ ክስተቶች ቁጥር ከፍ ወይም ዝቅ የማለት አዝማሚያ የሚኖራቸው መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው፡፡[82]

አሁን ደግሞ ጉዳዩን ያለምንም ብዥታ መመልከት ከቻልን አፍቃሪ እስራኤል ቡድኖች ‹‹አዲሱ ጸረ-ሴማዊነት›› በማለት የሚጠሩት እስራኤልን በማንኛውም ሁኔታ ከመተቸት ጋር ተያያዥነት ያለው ስያሜ (ፍረጃ) እየታየ ይኸዉል፡፡[83] ለምሳሌ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ በ2006 ካተርፒለር ኢንኮርፖሬትድ ከተባለው የአሜሪካ ከባድ ተሸከርካሪ አምራች ኩባንያ ጋር የነበረውን ግንኙነት ለማቋረጥ በመወሰን ድምጽ ሰጠ፡፡ ለዚህ እርምጃ ዋነኛው መነሻ ምክንያት ካተርፒለር የሚሰራቸው ቡል ዶዘሮች የፍልስጤማውያንን ቤቶች ማፈራረሳቸው ነበር፡፡ የሲኖዶሱን እርምጃ ወዲያው የተቃወሙት የእንግሊዝ ዋና ራቢ (የአይሁድ ካህን) ‹‹እርምጃው በብሪታኒያ ውስጥ ያለውን የአይሁድ ክርስቲያን ግንኙነት ይጎዳል›› ብለዋል፡፡ ራቢ ቶኒ ቤይፊልድ የተባሉት የተሻሻለው ጁዲያዝም (reformed judiasm) ዋና ራቢ ደግሞ ‹‹በጸረ-ጽዮናዊነት መሬት ላይ እየበቀለ የሚገኝ የጸረ-ሴማዊነት ስር በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን መካከለኛ ደረጃ ስልጣን ላይ በሚገኙ ካህናት ስብእና ውስጥ እያደገ ይገኛል›› ብለዋል፡፡[84]

ሃቁን ማየት ለሚችል ማንም አካል የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ያንን አቋም በመውሰዷ ጸረ-ጽዮናዊ ወይም ጸረ-ሴማዊ የሚል የአጥፊነት ታርጋ ሊለጥፍባት አይገባም ነበር፡፡ ምክንያቱም ያደረገችውን ማድረጓ ለሌላ ሳይሆን የእስራኤልን ፖሊሲ መቃወሟን ለማሳየት ብቻ ነበርና፡፡[85]

የእስራኤል ደጋፊዎች አሁን አሁን ያመጡትን ‹‹አዲሱ ጸረ-ሴማዊነት›› የሚሰኘውን ዘይቤ እስራኤልን ከትችት ለመከላከል በየጊዜው እንደ ጋሻ እየተጠቀሙበት ይኸዉሉ፡፡ እስራኤል በ1967 የያዘቻቸውን የአረብ መሬቶች እንድትለቅ ከፍተኛ ግፊት ይደረግባት በነበረው ዓመት በ1974 የኤ.ዲ.ኤል

አባላት የሆኑት አርኖልድ ፎርስተርና፤ ቤንጃሚን ኤፕስቲን ‹‹The New Anti-Semitism›› የሚል መጽሐፍ አሳተሙ፡፡ በመጽሐፋቸው ያነሱት የመከራከሪያ ሃሳብ፡- ‹‹ጸረ- ሴማዊነት እያደገ መሄዱን ለማወቅ ምሳሌ የሚሆነን ሌሎች ማህበረሰቦች የእስራኤልን ድርጊቶች ለመደገፍ ፈቃደኛ ሆነው አለመገኘታቸው ነው›› የሚል ነው፡፡[86] በ1980ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት እስራኤል ሊባኖስን መውረሯና በፍልስጤማውያን ምድርም አዳዲስ የሰፈራ መንደሮችን ማስፋፋቷ የቀሰቀሰው ተቃውሞ አዳዲስ ትችቶችን አስከተለባት፡፡ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ዩ. ኤስ. አሜሪካ ለዓረብ ሃገራት አዳዲስ የጦር መሳሪያዎችን ለመሸጥ መስማማቷ ሲታከልበት የኤ.ዲ.ኤል. የበላይ ናታን ፐርልሙተርና ባለቤታቸው ሩት ኣን ፐርልሙተር፣ ‹‹The Real Anti-Semitism in America›› የሚል መጽሐፍ አሳትመው እንዲያሰራጩ አደረጋችው፡፡ ባልና ሚስቱ በመጽሐፋቸው ላይ ባነሱት ጭብጥ ‹‹ጸረ- ሴማዊነት እንደገና መመለሱን ከምናይባቸው ምልክቶች መካከል እስራኤል ከአረቦች ጋር ሰላም እንድትመሰርት ግፊት እየተደረገባት መሆኑና አዋክስ የሚባሉት ተዋጊ ጀቶች ለሳኢዲ አረቢያ መሸጣቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው›› ይላሉ፡፡[87] በተጨማሪም፡- ‹‹ማናቸውም የጸረ-ሴማዊነት አንቅስቃሴዎች እየተነቃቁ የሚገኙት በአይሁዳውያን ላይ ጥላቻን በማሳየት ብቻ ሳይሆን በአይሁዳውያን ጥቅሞች ላይ ጉዳት በማድረስ (በተለይም የእስራኤልን ደህንነት አደጋ ላይ በመጣል) ጭምር ነው፡፡ ይህም ትክክለኛውን ጸረ-ሴማዊነት (በናዚ ጊዜ የነበረውን አይነት) ጎትቶ ያመጣል›› በማለት ይገልጻሉ፡፡[88]

ይህ ከላይ የቀረበው መከራከሪያ ሃሳብ በስነ አመክኒዮ (logic) ያልተደገፈ መሆኑን ግልጽ የሚያደርግልን በ1990ዎቹ የጸረ-ሴማዊነት እንቅስቃሴ በጣም አነስተኛ የነበረ መሆኑ ነው፡፡ እንደዚያም የሆነበት ዋነኛው ምክንያት እስራኤል በኦስሎ የሰላም ሂደት ላይ ተሳታፊ ስለነበረች ነው፡፡ አንድ እስራኤላዊ ምሁር በ1995 የታዘቡትን ሲጽፉ ‹‹በሮማ ኢምፓየር ክርሲቲያኖች ስልጣን ከያዙ ጀምሮ አሁን አንደሚታየው ያለ የጸረ-ሴማዊነት ክስ ዋጋ ያጣበት ጊዜ አልታየም›› ብለዋል፡፡[89] ከዚያ በኋላ በ2002 እስራኤል

በኃይል በያዘቻቸው የፍልስጤም ግዛቶች በምትፈጽማቸው ጭካኔ የተሞላባቸው ድርጊቶች ምክንያት የጸረ-ሴማዊነት ክስ በየሥፍራው እንደጉድ ተዛመተ፡፡

በእስራኤል ላይ የሚነሱ ትችቶችን የሚቃወሙ ወገኖች ጉዳዩን በቀጥታ ከሕልውናዋ ጋር ሊያያይዙት ይሞክራሉ፡፡ ናታን ሻረንስኪ የተባሉት ከቀድሞዋ ሶቪዬት የፈለሱና አሁን ደግሞ የታወቁ ደራሲና ፖለቲከኛ ‹‹አዲሱ ጸረ-ሴማዊነት የእስራኤልን ፖለቲካ በመተቸት መልክ የመጣ ሲሆን አድሏዊና የእስራኤልን መንግስት በሕልውና መቀጠል ጥያቄ ላይ የሚጥል ነው›› ብለዋል፡፡[90] የዚህ አባባል አንድምታ የእስራኤልን ድርጊቶች (ወይም የደጋፊዎቿን ድርጊቶች) የሚተች ማንም ሰው ድርጊቱ የእስራኤልን ህልውና ከመጻረር የሚቆጠር በመሆኑ ሰውየው የአይሁዳውያን ጠላት ነው የሚል ነው። ሆኖም ግን ይህ ክስ ሃሰት ነው፡፡ ምክያቱም የእስራኤልን ድርጊቶች መተቸትንና በሕልውና የመቀጠሏን ጉዳይ ያደበላልቃልና፡፡ እውነቱን ለመናገር እስራኤልን የሚተቹ ምዕራባውያን በሕልውና የመቀጠሏን ጉዳይ እምብዛም አጠያያቂ ሲያደርጉ አይታዩም፡፡ ከዚያ ይልቅ በፍልስጤማውያን ላይ የምታሳያቸውን ባሕሪያት ነው የሚሐይሱት፡፡ ይህ ትችት ሕጋዊ ብቻ ሳይሆን ብዙ እስራኤላውያን ሳይቀር የሚጋሩትም ጭምር ነው፡፡

ምዕራባውያን ተቺዎቿ በእስራኤል ላይ ነቀፋ የሚያቀርቡት አድሏዊ በመሆናቸው አይደለም፡፡ ምንም እንኳን ጥቂቶቹ በእስራኤል ላይ ከመጠን ያለፈ ትችትና ነቀፋ ሲሰነዝሩ ቢስተዋሉም እስራኤልም የምትመዘነው በአብዛኛው የምዕራቡ ዓለም ሕዝብ በሚጠቀምበት የዲሞክራሲ መለኪያ ነው፡፡ እስራኤልና አሜሪካውያን ደጋፊዎቿ በተደጋጋሚና አጽንኦት ሰጥተው እንደሚገልጹት ‹‹እስራኤል በመካከለኛው ምሥራቅ የምትገኝ ብቸኛ የዲሞክራሲ አምባ በመሆኗ ከአሜሪካ ጋር ልዩ ግንኙነት ልትመሰረት ይገባታል›› መባሉ ይህን መመዘኛ የበለጠ አስፈላጊ ይደርገዋል፡፡ ምክንያቱም እስራኤል እንደ ብሪታንያ፣ ካናዳ፣ ዴንማርክና ዩናይትስ ስቴትስ እንጂ እንደ በርማ ወታደራዊ ጁንታ፣ እንደ ፔርቬዝ ሙሸረፏ ፓኪስታን ወይም እንደ ፈደል ካስትሮዋ ኩባ ዓይነት ባህሪ ማሳየት አይጠበቅበትምና። እስራኤል

በፍልስጤማውያን ላይ የምትፈጽማቸው ግፎች ለትችት ያጋልጧታል። ምክንያቱም ድርጊቶቿ በሰፊው ተቀባይነት ያገኘውን የሰብዓዊ መብት ጥበቃ እና ዓለም አቀፋዊ ህግጋትን እንዲሁም የራስን እድል በራስ የመወሰን ብሔራዊ መብትን የሚጻረሩ ናቸው። እስራኤል እነዚህን ጉዳዮች ባለማክበሯ ትችት የሚደጋገምባት ብቸኛ አገር አይደለችም። ዩናይትድ ስቴትስ በአቡግሬይብ (ኢራቅ) እስር ቤት በፈጸመቻቸውና በጓንታናሞ ታራሚዎች ላይ በፈጸመቻቸው የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ክፉኛ ተተችታለች። ሆኖም ግን አሜሪካን አድሏዊነት ተፈጸመብኝ በማለት አላማረረችም። ምክንያቱም እራሷ የቀረጸቻቸውን የሰብዓዊ መብት ጥበቃ እሴቶችና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኙትን የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ደንቦችን ልትመራባቸው ይገባልና። እስራኤልም ከዚህ በተለየ ሁኔታ መታየት የለባትም።

ታላቁ ዝም ማሰኛ መሳሪያ

የጸረ- ሴማዊነት ክስ እስራኤልን የሚተቹ ግለሰቦችንና ቡድኖችን ጸጥ እንዲሉ ለማድረግ (በተለይም በአሜሪካ ውስጥ) ሁነኛ መሳሪያ ሆኖ በስፋት ሲሰራበት ቆይቷል። ይህ ስልት በብዙ ምክንያቶች አዋጪ መሆኑ ግልጽ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ጸረ- ሴማዊነት ሆሎኮስተን ጨምሮ ከተለያዩ ሰይጣናዊ ድርጊቶች ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ ባለፉት ዘመናት በብዙ ማህበረሰቦች ዘንድ ሲኮነን ቆይቷል። የጸረ- ሴማዊነት ክስ እጅግ በጣም ኃያል የሆነ ቅጥያ ሲሆን አንዱ ከመሬት ተነስቶ በሌላው ላይ በቀላሉ ሊለጥፈው የሚችል መሆኑ ይበልጥ አደገኛ ያደርገዋል። እናም ማንም የተከበረ መሆን የሚፈልግ ሰው በስብዕናው ላይ በዚህ ያደፈ ብሩሽ የማጥቆር ሥራ እንዲሰራበት አይሻም። ብዙ ሰዎች ጸረ- ሴማዊ ተብለው እንዳይፈረጁ በመፍራት እስራኤል የምታሳያቸውን አንገብጋቢ ባሕሪያትና ከዩ.ኤስ አሜሪካ ያለገደብ የሚሰጣትን እርዳታ መተቸት ማቆማቸውን ያለምንም ጥርጥር መናገር ይቻላል።

በሁለተኛ ደረጃ እስራኤልን የሚነቅፉ ሰዎችን ስም ማጉደፍና ሎቢው በእነዚህ ሰዎች ላይ የሚለጥፈው የጸረ-ሴማዊነት ታርጋ ሰዎቹን በሕዝቡ ዘንድ እንዲተፉና እንዲገለሉ የማድረግ ኃይል አለው። አንድ ጊዜ በዚህ ክስ የተለከፈ ሰው የፈለገውን ያክል ሃቀኛ ቢሆንና ስነ- አመክኒዮን (logic) የተከተሉ የመከራከሪያ ሃሳቦችን ቢያቀርብም በመገናኛ ብዙሃን፣ በመንግስት ባለሥልጣናትና ተስሚነት ባላቸው የፖለቲካ ሰዎች ሳይቀር ንግግሩ ተቀባይነት አያገኝም። በተለይ ፖለቲከኞች ከእንዲህ ዓይነት ሰው ጋር ቅርርብ ለመፍጠር ያመነታሉ። ምክንያቱም ያን ቢያደርጉ በራሳቸው ሕይወትና የወደፊት እድገት (career) ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድርባቸው ስለሚችል ነው።

ሶስተኛ ይህ ታክቲክ በአብዛኛው የታለመለትን ግብ ሲመታ የቆየበት ዋናው ምክንያት ማንም ቢሆን ጸረ-ሴማዊ ከሚለው ክስ ነጻ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚችልበት መንገድ ስለሌለ ነው። በአንድ ሰው ስሜት ውስጥ የሚገኙ እሳቤዎችና መነቃቃቶች በቀላሉ የሚታዩ እስካልሆኑ ድረስ መለየት እንደማይቻለው ሁሉ ማንም ቢሆን ከጸረ- ሴማዊነት ጋር የሚጋጩ ባሕሪያትን እንደሚያንጸባርቅ እንኳ ለማሳየት ቢጥር ያን ያክል ክብደት አይሰጠውም። ለዚህም ነው እስከ ቅርብ ጊዜያት ድረስ የጸረ ሴማዊነት ክስ እስራኤልን ወይም ሎቢውን የሚነቅፍን ማንኛውንም ሰው ዝም ለማሰኘትና ነቀፋው ቢሰነዘር እንኳ ዋጋ እንዳይሰጠውና እንዲንኳሰስ የማድረጊያ ፍቱን ዘዴ ሆኖ ሲያገለግል የቆየው።

የጸረ-ሴማዊነት ክስ ምንም እንኳን መጥፎ መሆኑን ቢያውቁም ብዙ አሜሪካውያን አይሁዶች አሁንም ቢሆን ሲያስተጋቡት ይሰማል። የሆሎኮስት እልቂት ያስከተለው የሰቆቃ ታሪክ በአይሁድ ዲያስፖራ ላይ ብዙ የሚያስጨንቁ ሁኔታዎችን ቢፈጥርም ቅሉ ቁጥራቸው በርካታ በሆነ የአሜሪካ አይሁዶች አመለካከት ላይ የበለጠ ተጽዕኖ ማሳደሩ እውነት ነው። ፒተር ኖቪክ ‹The Holocaust in American Life› በተባለው መጽሐፉ ግልጽ እንዳደረገው ክስተቱ በአሜሪካ አይሁዶች ንቃተ ህሊናና አእምሮ ላይ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ብዙ የአሜሪካ አይሁዶች በዙሪያቸው ያለውን ዓለም የሚገነዘቡት በሆሎኮስት መነጽር ነው። ያለምንም ማጋነን ብዙዎቹ

አምሳያ የሌለው ግፍ ሰለባዎች መሆናቸውን ነው የሚያምኑት፡፡ ምንም እንኳን አይሁዳውያን አሜሪካ ውስጥ ታላቅ ስኬት የተጎናጸፉ ቢሆንም ብዙዎች በአንድ ወቅት መራር ጽዋ ሊያስጎነጫቸው የሚችል የጸረ-ሴማዊነት አደጋ ሊመጣ እንደሚችል ያምናሉ፡፡ ጃክ ወርስማየር እንዲህ ይላ፡- ‹‹በማንኛውም ዘዴ በአገር ውስጥ ያለው ጸረ-ሴማዊነት እየቀነሰ ቢሆንም ብዙ አሜሪካውያን አሁንም ቢሆን ሌሎች አይሁዳውያን የዘረኝነት ሰለባ እየሆኑ እንዳሉ ነው የሚያምኑት›› የኒው ዮርክ ታይምስ ጋዜጣ አምደኛ (columnist) የሆነው ፍራንክ ሪች ይህን አስተሳሰብ እንደሚደግፍ ሲገልጽ የሚከተለውን ብሏል፡- ‹‹ልክ እንደ ሌሎች አይሁዳውያን ሁሉ ምናልባት እኔም መላው ዓለም ጸረ-ሴማዊ እንደሆነ ነው የማምነው፡፡››[91]

በአሜሪካ አይሁዳውያን ዘንድ የተፈጠረው እንዲህ ዓይነቱ ጠንካራ የፍርሃት ስሜት በግልጽ የተስተዋለው እስራኤል በ2002 በመላው ዓለም ውግዘት በደረሰባት ጊዜ ነበር፡፡ “ቪሌጅ ቮይስ” በተባለው ጋዜጣ ላይ የሚጽፈው ናታን ሄንቶፍ በዚያ ጊዜ የሆነውን ሲያስተውስ ‹‹በድምጽ ማጉሊያ ‹አይሁዳውያን የሆናችሁ ሁሉ ወደ ታይም አደባባይ ተሰባሰቡ!› ተብሎ ቢለፈፍ ፈጽሞ አያስገርመኝም ነበር›› ብሏል፡፡ ሮን ሮዘንባውም ደግሞ በኒው ዮርክ ኦብዘርቨር ሲጽፍ፡- ‹‹አዝማሚያዎቹ እንደሚያሳዩት ሁለተኛው ሆሎኮስት መምጣቱ የሚቀር አይመስልም›› በማለት ስጋቱን ገልጿል፡፡ የጉዳዩ አሳሳቢነት እያደገ በመምጣቱ በኒው ሪፓብሊክ ጋዜጣ ላይ የሚጽፈውና ጽኑ የእስራኤል ደጋፊ በመሆኑ የሚታወቀው ሊዮን ዊስልቲዮር ‹ሂትለር ኢዝ ዴድ.. ዘ-ኬዝ አጌንስት ጆዊሽ ኤትኒክ ፓኒክ›› በሚል ርዕስ ጽሑፍ ለማዘጋጀት ተገድዷል፡፡ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያሉትን አይዳውያን አስመልክቶ ሲጽፍ፡- ‹‹ማህበረሰቡ እንዳለ የሚከተለውን ጥፋት እያሰበ ተጨንቋል፡፡ ምሁራዊ ራስን መግዛት ጠፍቷል፡፡ ሞት በእያንዳንዱ አይሁዳዊ ደጅ ላይ አድፍጧል፡፡ ፍርሃት ነግሷል፡፡ ምክንያታዊነት ሐዲዱን ለቋል፡፡ በትክክል ያልተነገሩና ቁጣን የሚያጭሩ አባባሎች አካብበውናል፡፡ በደፈናው የሆሎኮስ ድባብ በዙሪያችን ሰፍኗል›› ብሏል፡፡[92] በአጭሩ ለማስቀመጥ ብዙ የአሜሪካ አይሁዶች አንድ ሰው በተለይ እንደነርሱ አባባል “አህዛብ” ወይም አይሁዳዊ ያልሆነ (gentile) ሆኖ እስራኤልን ወይም ሎቢ

የሚያደርጉ አይፓክን የመሠሉ ድርጅቶችን የሚነቅፍ ከሆነ በልቡ ጸረ-ሴማዊ ሳይሆን አይቀርም ብለው መደምደም ቀላል ሆኖ ያገኙታል፡፡

በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የተነሳ የእስራኤልን ፖሊሲዎች የሚነቅፍ ሰው ባጋጠማቸው ቁጥር ፈጥነው ‹ጸረ-ሴማዊ› የሚለውን ስም ይለጥፉበታል፡፡ ከሁሉም በላይ በዚህ ዙሪያ ከፍተኛ ውዝግብ ያስነሳው ጂሚ ካርተር የጻፉት ‹palastine peace not Apartied› (ለፖለስታይን አፓርታይድ ሳይሆን ሰላም) የተባለው መጽሐፋቸው ነው፡፡ ምንም እንኳን ርዕሱ የሚያናድድ ቢሆንም መጽሐፉ የእስራኤልን ስትራቴጂያዊ ሁኔታ ያላገናዘበ ወይም ጨርሶ ድጋፍ የሚነፍግ አይደለም፡፡ ካርተር፣ እስራኤል ምዕራባዊውን ዳርቻ መቆጣጠሯንና እዚያ በሚኖሩ ፍልስጤማውያን ላይ የምትፈጽመውን በደል ነቅፈዋል፡፡ በተጨማሪም እነዚህን ጉዳዮች አስመልክቶ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ሃቀኛ የሆነ ውይይት ማድረግ አስቸጋሪ መሆኑን በጽኑ ኮንነዋል፡፡ ዮሲ ቤሊን የተባሉት የታወቁ እስራኤላዊ ፖለቲከኛ የታዘቡትን ሲገልጹ ‹‹ካርተር በመጽሐፋቸው ስለ እስራኤል ከጻፉት ውስጥ እስራኤላውያን ራሳቸው ያልተናገሩት አንድም ትችት የለም›› ብለዋል፡፡[93] ካርተር የተጠቀሙበት ‹አፓርታይድ› የሚለው አገላለጽ ብዙዎቹን ያስቆጣ ሲሆን በካርተር ላይ ቁጣቸውን ካስተጋቡት ሰዎች መካከል የኖቤል ተሸላሚው ዴዝሞንድ ቱቱና የደቡብ አፍሪካ የደህንነት ሚኒስተር ሮኒ ካስሪልስ ይገኙበታል፡፡[94]

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ኤ. ዲ. ኤልና ሲ. ኤ. ኤም. ኢ. አር. ኤን የመሰሰሉ ድርጅቶች በታወቁ ጋዜጦች የአስተያየት መስጫ አምዶች የካርተርን መጽሐፍ አብጠልጥለውታል፡፡ በርካታ ትችት አቅራቢዎች ካርተር ያነሷቸውን ሃሳቦች በማስመልከት ብዙ ነገር ጻፉ፡፡ ሌሎች ደግሞ በቀድሞው ፕሬዝዳንት ላይ ግላዊ ጥቃት ሰነዘሩ፡፡[95] አብረሃም ፎክስማን ለምሳሌ ‹‹እኔ እንደማምነው ሰውዬው በጸረ- ሴማዊነት እንቅስቃሴ ውስጥ ተነክረዋል›› በማለት ዘልፈዋቸዋል፡፡ ማርቲን ፔሬትዝ ደግሞ ‹‹ካርተር በታሪክ መዝገብ ውስጥ አይሁዶችን በመጥላት ስማቸው ሰፍሯል›› በማለት ጽፏል፡፡[96] ዲቦራህ ሊፒስታድት የተባሉት የታሪክ ባለሙያና የሆሎኮስትን እልቂት በማስተባበል የታወቀውን የዴቪድ ኃርቪንግን ሥራ በመተቸት

እውቅ ስራ ያቀረቡት ሰው ዋሽንግተን ፖስት ላይ ‹‹ካርተር በተደጋጋሚና ምናልባትም ሳያስቡት ባሕላዊ በሆነው የጸረ-ሴማዊነት ሥም ማጥፋት ውስጥ ተነክረዋል›› ካሉ በኋላ፡- ‹‹ካርተር በሰነዘሯቸው አንዳንድ አመለካከቶችና የኩ-ክሉክስ ክላን[5] መሪ በሆነው ዴቪድ ዱክ አስተሳሰብ መካከል ተመሳሳይነት ይስተዋላል፡፡›› በማለት ሃሳባቸውን ቋጭተዋል፡፡[97] ካርትር ራሳቸው እንዲህ ማለታቸው ተወስቷል፡- ‹‹ጸረ-ሴማዊ ተብያለሁ' ዘረኛ ተብያለሁ' የሰውን ሃሳብ የሚቀዳ ተብያለሁ፣ ፈሪም ተብያለሁ፡፡››[98] እስራኤልንና ግብጽን በማስታረቅ የተሸላላቸውና ከማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር በበለጠ ሁኔታ የእስራኤልን አጠቃላይ ጸጥታ ለማረጋገጥ ደፋ ቀና ያሉት የሰላም ጀግና በዚህ አንጉል ስያሜ መጠራታቸው ያስደንቃል፡፡

ተመሳሳይ የሆነ አጋጣሚ በአነስተኛ ሁኔታ የተከሰተው ደግሞ የቀድሞው ኒዎ ኮንሰርቫቲቭ እሳቤ አቀንቃኝ ፍራንሲስ ፋኩያማ፣ በ2004 ቻርለስ ካራውታመር በአሜሪካ ኢንተርፕራይስ ኢኒስቲትዩት ያደረገውን ገለጻ በመንተራስ የትችት ጽሑፍ ባሳተመ ጊዜ ነበር፡፡ የፋኩያማ ትችት ጠንካራ ትንታኔ ቢሆንም ትህትና የተሞላበት ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ ፋኩያማ ክራውታመርን፡- ‹‹ተሰጥኦ ያለው አሳቢና የሚያነሳቸው ሃሳቦች ትኩረት የሚስቡ ናቸው፡፡» በማለት ካመሰገነው በኋላ፡- ‹‹ሆኖም ግን ከሙስሊሙ ዓለም ጋር እንዴት መነጋገር እንደሚችል ያለው ሃሳብ በአብዛኛው እስራኤል ካላት ልምድ የተወሰደ ነው›› ማለቱ ክራውታመርን አበሳጭቶ ፋኩያማን ጸረ- ሴማዊ የሚል ክስ እንዲለጥፍበት አድርጎታል፡፡[99]

እኛ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጆችም ተመሳሳይ ጥቃት ደርሶብናል፡፡ የመጀመሪያው መጽሐፋችን ረቂቅ ‹‹የእስራኤል ሎቢ›› በለንደን ሪቪው ኦፍ ቡክስ በ2006 መጋቢት ወር ላይ በታተመ ጊዜ በሃሰት በተቀነባበረ ክስ ጸረ-ሴማዊ የሚል ስያሜ ተሰጥቶናል፡፡ አሊዮት ከኾን በዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ ላይ የእኛን ጽሑፍ አስመልክቶ ‹‹የስ ኢት ኢዝ አንቲ ሴሜቲክ›› በሚል ርዕስ ውግዘቱን አወረደብን። ኒው ዮርክ ሰን ጋዜጣ ደግሞ የኩ

[5] ኩ ክላክስ ክለን አሜሪካ ውስጥ የሚገኙ አናሳ ማሕበረሰቦችን ለማጥቃት በሚስጥር የተደራጀ የኘሮቴስታንት እንቅስቃሴ ነው (ተርጓሚው)

ክሉክስ ክላን መሪ ከነበረው ዴቪድ ዱክ ጋር አመሳስለን።[100] ኤ. ዲ. ኤል የእኛን ጽሑፍ አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ፡- ‹‹በአይሁዳውያን ኃይልና ባላቸው ይዞታ ላይ የተሰነዘረ ዓይነተኛ አሉባልታና የጸረ-ሴማዊነት ሴራ›› በማለት ሥራችንን ያብጠለጠለው ሲሆን በጽሑፋችን ውስጥ፡- ‹‹ሎቢው ራሱን የቻለና ሕጋዊ በሆነ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚሳተፍ በራስ አነሳሽነት የተቋቋመ ቡድን ነው›› በማለት በተለይ ያሰፈርነውን አባባል ግምት ውስጥ ሳያስገባው ቀርቷል። ዘ ኒው ሪፐብሊክ የእኛን ሥራ ለመተቸት አራት ዓይነት ጽሑፎችን አዘጋጅቶ ጥቃቱን የከፈተብን ሲሆን ሁሉም ትችቶች ጸረ-ሴማዊ በመሆናችን ዙሪያ ነበር ያጠነጠኑት።[101] በዎል ስትሪት ጆርናል የአስተያየት መስጫ ላይ ዊሊያም ክሪስቶል ‹‹ጸረ አይሁዳውያን›› መሆናችንን በመግለጽ ክስ አቅርቦብናል። ሩዝ ዋይስ የተባሉ የሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የይዲሽ ስነ-ጽሑፍ ፕሮፌሰር ደግሞ ጽሑፋችንን በቀጥታ ያያያዙት በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን በጀርመን አገር ተከስቶ ከነበረ የለየለት ጸረ-ሴማዊነት ንቅናቄ ጋር ነው።

የሃ ኤሬትዝ ጋዜጣ ጽሑፍ አቅራቢ የሆነው ሻሙኤል ሮዝነር የካርተርን መጽሐፍ በተቸበት መጣጥፍ ላይ ‹‹የቀድሞው ፕሬዝዳንትና የሰላም ኖቤል አሸናፊው (ካርተርን ማለቱ ነው) የዋልትና ሜርሸይመርን ያክል ጸረ-ሴማዊ አይደሉም››[102] በማለት የዚህ መጽሐፍ አዘጋጆች (እኛ) ጠርዝ የለሽ ጸረ-ሴማዊ መሆናችንን ለመግለጽ ሞክሯል።

በእስራኤል ነቃፊዎች ላይ የጸረ-ሴማዊነት ታርጋ የመለጠፍ ሂደት አዲስ ምዕራፍ (ምናልባትም ኢዲስ ሕግ) እየተከተለ የመጣው 2007 ላይ ሲሆን የአሜሪካ አይሁድ ኮሚቴ የኢንዲያና ዩኒቨርሲቲ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ፕሮፌሰር አልቪን ሮዝንፊልድ ‹‹እያደገ የመጣው የአይሁድ አስተሳሰብና አዲሱ ጸረ-ሴማዊነት›› በሚል ርዕስ የጻፉትን መጽሐፍ ባሳተሙ ጊዜ ነበር። ሮዝንፊልድ ሊበራል የሆኑና እስራኤልን በመንቀፍ የሚታወቁ የአሜሪካ አይሁዶችን (ለምሳሌ ጸሐፊ ተውኔት ቶኒ ኩሽነር፣ የታሪክ ባለሙያ ቶኒ ጀድት፣ ባለቅኔው አድሪያኔ ሪችና የዋሽንግተን ፖስት አዘጋጅ ሪቻርድ ኮኾን) ‹‹አዲስ ጸረ-ሴማዊነት የሚያራምዱና የእስራኤልን በሕልውና መኖር የካዱ›› በማለት ፈርጀዋቸዋል። የኮሚቴው ዋና ስራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር

ዶቪድ ሃሪስ በሮዝንፊልድ መጽሐፍ መግቢያ ላይ የሚከተለውን ሃሳብ አስፍሯል፡- ‹‹የዚህ አዲስ ጸረ-ሴማዊነት ንቅናቄ አሳዛኝ ገጽታ የተወሰኑ አይሁዳውያን በጽዮናዊነት ንቅናቄ እና በአይሁዳዊቷ አገር ላይ የሚሰነዝሩት የቃላት ጥቃት ነው፡፡››[103]

በሮዝን ፊልድ ትችት ዒላማ ውስጥ የገቡት አይሁዳውያን ግን ሴትየዋ የጫኑባቸውን በርካታ ክሶች አይቀበሉም፡፡ የቲኩን ፕሮጀክት አባል የሆኑት ራቢ ሚካኤል ለርነር የእነዚህ አግባብነት የሌላቸው ክሶች የመጨረሻ ውጤት ምን እንደሆነ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ነጻ የሆኑና እንዲያውም በጣም ተራማጅ አስተሳሰብ ያላቸውን የኮንግረስ አባላት በመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳዮች ዙሪያ ስናነጋግራቸው በግል የሚነግሩን እስራኤል የምትከተለው ፖሊሲ የዩናይትድ ስቴትስን ፍላጎት የሚጻረር ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሠላም ጭምር የማይበጅ መሆኑን ሲሆን ዳሩ ግን ይህን በግልጽ እንዳይናገሩ ጸረ-ሴማዊ ተብለው እንዳይፈረጁ ይፈራሉ፡፡ ከእነርሱ የተወሰኑት በቅርቡ እንደገለጹልኝ “ይኼ የጸረ-ሴማዊነት ፍረጃ ጂሚ ካርተርን ለመሰለ የሞራል ልዕልና ባለቤት ሳይቀር ከተሰጠ ከእንግዲህ ማንም ፖለቲከኛ ሊያመልጥ አይችልም” በማለት ተናግረዋል፡፡››[104]

በእነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ውስጥ እውነተኛ ጸረ-ሴማዊነት መኖሩን የሚያረጋግጡ ምንም ዓይነት ማስረጃዎች አልተገኙም፡፡ የጸረ- ሴማዊነት እውነተኛ ገጽታ የሚገለጸው አይሁዳውያን ከሌሎች ሕዝቦች የተለዩ መሆናቸውን በብዙ መንገዶች ለማሳየት በመሞከር' እነርሱን ከሌሎች ሕዝቦች ነጥሎ በማውጣት' በአነስተኛም ሆነ ሰፊ በሆነ መጠን በማሰቃየትና በማጥቃት ነው፡፡ ጸረ-ሴማውያን፣ ህጋዊ በሆነ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚሳተፉ' ስልጣን ለመያዝ የሚወዳደሩ' ለምርጫ ቅስቀሳ ገንዘብ የሚያዋጡ' የተለያዩ መጣጥፎችንና መጽሐፎችን የሚጽፉ፣ ሎቢ የሚያደርጉ ቡድኖችን የሚያደራጁ አይሁዳውያንን ሁሉ ምስጢራዊ በሆነ ሴራ ላይ እንደተሰማሩ አድርገው ነው የሚቆጥሯቸው፡፡ እውነተኛ ጸረ-ሴማዊነት አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም አይሁዳውያን ያላቸውን ሙሉ ፖለቲካዊ መብት ከመካድም አልፎ በእነርሱ ላይ የሚነሳን ተቃውሞና እነርሱን ማሰቃየትን ያበረታታል። ሌላው ይቅርና በመካከለኛ ደረጃ የሚገኝ

የጸረ-ሴማዊነት እንቅስቃሴ እንኳ በጉልህ በሚታዩና በማይቀየሩ ባህሪያትና አስተሳሰቦች (stereotype) የተተበተበ ከመሆኑ የተነሳ “አይሁዳውያን በጥርጣሬና በንቀት ሊያዙ ይገባል›› የሚሉ አስተሳሰቦችን ከመርጨት አልፎ አይሁዳውያን በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ በሁሉም ዘርፍ በመሳተፍ የተዋጣላቸው መሆናቸውን በጭፍን ይክዳል። እንግዲህ የጸረ- ሴማዊነት እንቅስቃሴ ከሌሎች የዘረኝነት ድርጊቶች ጋር ተመሳሳይነት ያለው እንደመሆኑ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በመላው አውሮፓና በዩናይትድ ስቴትስ የተወገዘ መሆኑ ይታወቃል።


ከዚህ ጋር ሲነጻጸር ከሞላ ጎደል ሁሉም አይሁድ ያልሆኑ (genetiles) እና አይሁዶችም ሆነው የእስራኤልን ፖሊሲ እንዲሁም ሎቢው በዩ. ኤስ. አሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ የሚነቅፉ ወገኖች እነዚህን ባህሪያትና አስተሳሰቦች በጥልቅ የሚረብሹ ሆነው ስለሚያገኙዋቸው -ውድቅ ያደርጓቸዋል። ከዚያ ይልቅ እነርሱ የሚያምኑት አይሁዳውያን ልክ እንደሌሎች ሕዝቦች እንደሆኑ ነው። ማለትም ከመካከላቸው መልካሞችም ክፉዎችም ይገኛሉ። ደረጃቸውም ከሌላው የማሕበረሰብ አካል የተለየ አይደለም። በተጨማሪም እስራኤል ልክ እንደ ሌሎች ሃገራት የራሷን ጥቅም ለማስከበር ብርቱ ጥረት የምታደርግ፣ አንዳንድ ጊዜ በሳልና አርቆ አሳቢነት የሚታይባቸውን ፖሊሲዎች የምትከተል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በስትራቴጂየዊ ስሌት ሲታሰቡ የሞኝ ሥራ የሚመስሉና እንዲውም ኢ-ሞራላዊ የሆኑ ፖሊሲዎችን የምትተገብር አገር እንደሆነች ያምናሉ። እንግዲህ ይህ ዓይነቱ ምልከታ ከጸረ-ሴማዊነት ጋር የሚቃረን መሆኑ ግልጽ ሲሆን አይሁዳውያንን ልክ እንደማንኛውም ሕዝብ መመልከትንና እስራኤልንም ቢሆን እንደ ሌሎች ሕጋዊ ሃገራት የመቁጠርን ተገቢነት ነው የሚያሳየው። በዚህ አመለካከት መሠረት እስራኤል መልካም ነገር ስታደርግ መወደስና ክፉ ነገር ስትፈጽም ደግሞ መነቀፍ ይገባታል። አሜሪካውያንም ቢሆኑ እስራኤል የአገራቸውን ጥቅም የሚጻረር ነገር ስትፈጽም ሊተቿትና ሊነቅፏት ይገባል። እንዲሁም ለእስራኤል ግድ አለን የሚሉ አሜሪካውያን እስራኤል የአሜሪካን ብቻ ሳይሆን የራሷንም ጥቅም የማያስከብር ነገር ስትፈጽም በግልጽ ይተቿት ዘንድ ነጻ መሆን አለባቸው። እዚህ ላይ ልዩ

ግንኙነት ወይም አድሏዊ አሰራር ብሎ ነገር የለም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አብዛኛዎቹ የሎቢው ነቃፊዎች የሎቢውን ድርጊት እንደ አድማ ወይም ሴራ አይመለከቱትም፡፡ ከዚያ ይልቅ ሎቢው አፍቃሪ እስራኤል ድርጅቶች የሚያንቀሳቀሱትና እንደ ሌሎች በራስ ፍላጎት የተቋቋሙ ቡድኖች መሆኑን ነው የሚቀበሉት፡፡ በጥቅሉ ምንም እንኳን የጸረ-ሴማዊነት ክስ ውጤታማ የሆነ ስም የማጥፊያ ዘዴ ቢሆንም ብዙውን ጊዜ እውነተኛ መሠረት የለውም፡፡

እውነቱን ለመናገር የጸረ-ሴማዊነት ውንጀላ ክርክሮችንና በነጻ የሚሰነዘሩ ትችቶችን ዝም የማሰኘት ሃይሉን ማጣት ጀምሯል፡፡ ለምሳሌ በጂሚ ካርተር መጽሐፍ ላይ የተሰነዘረው ጥቃት የቀድሞው ፕሬዝዳንት መጽሐፋቸውን ለሕዝብ ይፋ ከማድረግ (በብራንዲስ ዩኒቨርሲቲ ያደረጉትን የተዋጣለትና የተሳካ የማስተዋወቅ ሥራ ጨምሮ) አላገዳቸውም፡፡ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎችና ዋና ዋና የሚባሉ የሕትመት ውጤቶች ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የእስራኤልን ፖሊሲና ሎቢው የሚያደርገውን ተጽእኖ ብልህነት በተሞላበት ሁኔታ እየተቹ ይገኛሉ፡፡[105] ዊሊያም ክሬስቶል ራሱ እስራኤልንና የሎቢውን አሰራር የሚነቅፉ ሰዎችን ጸረ-ሴማዊ ብሎ መፈረጁ ሰዎችን ዝም የማሰኘት ጉልበቱን እያጣ መሄዱን አምኖ መቀበሉን በዎል ስትሪት ጆርናል ላይ ሲጽፍ ‹‹ዋና ዋና የሚባሉት የአይሁድ ድርጅቶች በጸረ-ሴማዊነት ካርድ በተደጋጋሚ በመጫወታቸው ምክንያት ይህ ካርድ ዋጋ እንዲያጣ አድርገውታል” ብሏል፡፡[106] ለዚህ ሁኔታ መከሰት ግልጽ ምክንያት ጸረ ሴማዊ ያልሆኑ ነገር ግን የእስራኤልን ፖሊሲና ሎቢው ከዩ.ኤስ. አሜሪካ ፍላጎት በተጻራሪ የሚፈጽማቸውን ድርጊቶች በመንቀፋቸውና በመተቸታቸው ብቻ ጸረ-ሴማዊ ተብለው የሚከሰሱ ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ መምጣቱ ነው፡፡

እዚህ ላይ ግልጽ ሆነን መገኘት ይኖርብናል፡፡ ጸረ-ሴማዊነት የተናቀና ውዳቂ ድርጊት ሲሆን ራሱን የቻለ ረዥምና አስገራሚ ታሪክ አለው፡፡ ስለሆነም በሰለጠነው ዓለም የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ እንደገና እንዳያንሰራራ በጥንቃቄ የሚከታተሉት ከመሆኑም በላይ አልፎ አልፎ ከተከሰተም በጽኑ ያወግዙታል፡፡ ሁላችንም ብንሆን በአረቡና በሙስሊሙ ዓለም (እንዲሁም

በሌሎች ማህበረሰቦች ለምሳሌ፤ በሩሲያ) እውነተኛ ጸረ-ሴማዊነት መኖሩ ሊረብሸን ይገባል። በአሜሪካና አውሮፓም ቢሆን በተወሰኑ ማህበረሰቦች ዘንድ እስካሁንም ድረስ ያልጠፋ መሆኑም ጭምር አሳሳቢ ነው። ይሁን እንጂ እውነተኛውን ጸረ-ሴማዊነትና በእስራኤል ፖሊሲዎች ላይ የሚሰነዘሩ ሕጋዊ ትችቶችን ለያይተን መመልከት ግድ ይለናል። ምክንያቱም በሁለቱ መካከል ያለው ጉልህ ልዩነት እንዲደበዝዝ ማድረግ እውነተኛውን ዘረኝነት ለመዋጋትና የአሜሪካን የውስጥ ፖሊሲ በብልህነትና በምሁራዊ አቀራረብ ለመተቸት አስቸጋሪ ያደርግብናል። አሜሪካ እስራኤልን ያለምንም ቅድመ ሁኔታና ገደብ እንድትረዳት የሚገፏትን ቡድኖች እንቅስቃሴ አስመልክተው አሜሪካውያን በነጻነት መወያየት ይኖርባቸዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ የሌሎች በራስ ፍላጎት የሚደራጁ ቡድኖችን የፖለቲካ እንቅስቃሴም እንዲሁ ያለምንም የመገለል ወይም የሥም ማጥፋት ፍራቻ መመርመርና ማጠያየቅ መቻል አለብን።


ክፍል ሁለት
የኤቢው
ተግባር
ሲገለጽ

የክፍል ሁለት መግቢያ

የእስራኤል ሎቢ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ኮንግረሱ ለእስራኤል የሚሰጣት እርዳታ ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ አጀንዳ ብቻ የሚገታ ቢሆን ኖሮ ያን ያክል ባላስጨነቀ ነበር። ምንም እንኳን ገንዘቡን ለተሻለ አላማ ማዋል ይቻል ነበር ተብሎ ቢታሰብም ዩናይትድ ስቴትስ እጅግ ባለጸጋ የሆነች ሃገር እንደመሆኗ በያመቱ ከ 3 ቢሊዮን ዶላር በላይ ለእስራኤል መስጠት አይከብዳትም። ይሁን እንጂ ሎቢው የሚያደርገው ጥረት በዚህ እርዳታ ብቻ የተገታ አይደለም። ልክ እንደሌሎቹ በጋራ ጥቅም ዙሪያ የተሰባሰቡ ቡድኖች ሁሉ በበርካታ የዩ ኤስ አሜሪካ የውጭ ፖሊሲዎች፣ በተለይም መካከለኛውን ምስራቅ በሚመለከቱት ላይ ተጽዕኖውን ለማሳረፍ ነው የሚንቀሳቀሰው። በእርግጥ ይህን ዓይነቱን ጥረት ለማድረግ ግፊት የሚያደርጉ መነሻዎችን መረዳት አይከብድም። ምክንያቱም ምንም እንኳን ቁሳዊ እርዳታ ጠቃሚ ቢሆንም የአለምን ብቸኛ ልእለ ሃያል ሐገር እምቅ አቅምና ተደማጭነት ለራስ ጥቅም ማዋል መቻል ትልቅ ነገር ነው።

ሎቢው የሚያደርጋቸው ተጽዕኖዎች የአሜሪካንም ጥቅም የሚያስጠብቁ ቢሆኑ ኖሮ ማለፊያ በሆነ ነበር። ሆኖም ግን በቀጣዮቹ አምስት ምዕራፎች በስፋት የምንዳስሰው እንደዚያ ያለመሆኑን ነው። በአሁኑ ጊዜ ዩናይትድ ስቴትስ በመካከለኛው ምሥራቅ ሦስት ዋና ዋና የሚባሉ ጥቅሞች አሏት። አንደኛው የፋርስ ባሕር ሰላጤ ነዳጅ ዘይት ወደ ዓለም ገበያ ያለምንም ችግር እንዲፈስ ማስቻል ሲሆን ሁለተኛው ጅምላ ጨራሽ የጦር መሳሪያዎች እንዳይስፋፉ ማድረግና ሶስተኛው ደግሞ በክልሉ የሚመነጨውን ጸረ- አሜሪካ የሆነ የሽብርተኝነት አዝማሚያ መቀነስ ነው። ሎቢው እነዚህን ጥቅሞች የሚያራምዱ ፖሊሲዎችን የሚደግፍባቸው አጋጣሚዎች ባይጠፋም በሎቢው ውስጥ ያሉ ድርጅቶች የሚያራምዷቸው ፖሊሲዎች ውሎ አድሮ ዩናይትድ ስቴትስን የሚጎዱ ሆነው ነው የሚገኙት። እርግጥ ነው በሎቢው ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦችና ድርጅቶች የሚያደርጉት የፖለቲካ ግፊት የሚያስከትለው ውጤቱ እንዲያ እንዲሆን

አይፈልጉ ይሆናል። እንዲያውም እነዚያ አካላት ድርጊታቸው ሁሉ የዩናይትድ ስቴትስንም ጥቅም የሚያስከብር ነው ብለው እንደሚያስቡ ይገመታል። ሆኖም ግን ተሳስተዋል። በእርግጥም እነርሱ ከሚያራምዷቸው ፖሊሲዎች አብዛኛዎቹ ዩናይትድ ስቴትስን ሊጠቅሙ ቀርቶ የእስራኤልንም ጥቅም ጭምር የሚጎዱ መሆኑ ሊሰመርበት ግድ ይላል።

የሎቢው አጀንዳ

ዩ.ኤስ. አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠው እርዳታ ዘላቂነት እንዲኖረው ከማረጋገጥ ባሻገር በሎቢው ውስጥ የሚገኙ ቡድኖች አሜሪካ ያላት ኃይል የእስራኤልን ጥቅም፣ በተለይም ጸጥታዋን በሚያስከብር መልኩ የመካከላቸውን ምስራቅ አካባቢ ለማረጋጋት እንዲውል ይፈልጋሉ። ይህ ፍላጎት በተግባር ሲተረጎም እስራኤል ከፍልስጤማውያን ጋር የምታካሄደውን ረዥም የትግል ሂደት አሜሪካ እንድትደግፍና በክልሉ እስራኤልን የሚቃወሙ እንቅስቃሴዎችን ለመምታት ኃይሏን እንድትጠቀም ማድረግ ነው።

በምዕራፍ አራት ላይ ልንዳስሰው እንደሞከርነው አፍቃሪ እስራኤል በሆኑ ቡድኖችና ማህበረሰቦች መካከል የፍልስጤማውያን መንግስት መመሠረቱን አስመልክቶ ልዩነቶች አሉ። ከሎቢው የበታችና ተራ አባላት ይልቅ አመራር ላይ ያሉት የሃሳቡ ተቃዋሚዎች ናቸው። የሆነ ሆኖ ጥቂት የእስራኤል ደጋፊዎች ሁለቱን ተቀናቃኝ ሃይሎች (እስራኤልንና ፍልስጤማውያንን) በሚዛናዊነት መመልከትን የሚደግፉ ሲሆን አሁንም ጥቂቶች ደግሞ ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መንገድ እስራኤል በኃይል በያዘቻቸው ቦታዎች የምታካሂደቸውን የሰፈራ መንደር ማስፋፋቶች ይደግፋሉ።

ብዙ አፍቃሪ እስራኤል ቡድኖች፣ በተለይም ደግሞ ዋና ዋና የሆኑት የሎቢው አካላት እስራኤል በመካከለኛው ምሥራቅ ብቸኛና ኃያል ሃገር ሆና እንድትቀይ ዩናይትድ ስቴትስ እንድትደግፋት ይፈልጋሉ። እነዚህ አካላት የእስራኤልን ጦር በመሳሪያ አቅርቦት (logistics) እና በገንዘብ በመደገፍ ደረጃውን ከፍ ከማድረግ ጀምሮ በክልሉ የሚገኙ ሐገራትን፣ ማለትም

ኢራንን፣ የሳዳምን ኢራቅና ሶሪያን የመሳሰሉትን ዋና ዋና የእስራኤል ጠላቶች የአሜሪካ ጦር አደብ እንዲያስገዛቸው ይሻሉ። በመጨረሻም ሎቢው የሚፈልገው አሜሪካ እነዚህ አዋኪ መንግስታት የኒኩሌር ቃታ እንዳይጨብጡ እንድታደርጋቸው ነው። ከሎቢ ቡድኖች የተወሰኑት ደግሞ ከዚህ ይበልጥ ራቅ በማለት ዩናይትድ ስቴትስ በኢራን' ኢራቅና ሶሪያ የሚገኙ መንግስታትን ገርስሳ በምተካቸው ከእስራኤል ጋር ተስማምተው የሚኖሩ መንግስታትን እንድታቋቁምላቸው ይመኛሉ። ሆኖም ግን ለዓለም ሰላም የሚበጀው አካሄድ ዩናይትድ ስቴትስ በአጠቃላይ በክልሉ ዲሞክራሲን በማስፋፋት የራሷንም ሆነ የእስራኤልን ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ብታደርግ ነው። የአሜሪካ መሪዎች ሂዝቡላህን ትጥቅ እንዲያስፈቱና ለእስራኤል የምትመች ሊባኖስን ለመመስረት እንዲጥሩ ሎቢው ይገፋፋል። ሆኖም ግን የኢራንንና ሶሪያን መንግስታት ባሕሪ ስርነቀል በሆነ ለውጥ ሳይቀይሩ ይህን ግብ ማሳካት ከባድ ነው። ምክንያቱም ሂዝቡላህን የሚያስታጥቁት እነዚህ አገራት ሲሆኑ በተለይም ሶሪያ በሊባኖስ ፖለቲካ ረዥም የሆነ የጣልቃ ገብነት ታሪክ አላት። ከላይ የዘረዘርናቸውንና ሌሎች ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ሎቢው አምሳያ እንደሌላቸው ሰይጣኖች የሚቆጥራቸውን እነዚህን ኃይላት አሜሪካ አደብ ማስገዛት ካልቻለች ቢያንስ ተጽዕኖአቸውን እንድትከላከል ይሻል።

በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን በእስራኤል ሕልውና ላይ ስጋት የሚደቅኑ ሃይሎችን ለመቋቋም በሎቢው ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቡድኖች ዩናይትድ ስቴትስ በመካከለኛው ምስራቅ በርከት ያለ ጦር እንድታሰማራ ይሻሉ። ወደፊት በሚመጡ ምዕራፎች በዝርዝር እንደምንመለከተው ሎቢው ባሳረፈው ጠንካራ ተጽእኖ ምክንያት ነበር አሜሪካ ኢራቅን የወረረችው። ያም ሁኔት ክልሉን ለእስራኤል ሰላም የሚመች ለማድረግ የተመጀረው ሰፊ ዘመቻ ወይም ጥረት አንዱ አካል መሆኑ ነው። ዛሬም ቢሆን ብዙ የእስራኤል ደጋፊዎች፣ የአሜሪካ ጦር ከኢራቅና ከአካባቢ እንዳይወጣ ግፊት ያደርጋሉ። ምክንያቱም የአሜሪካ ጦር በዚያ አካባቢ እንዲቆይ ቢደረግ የእስራኤልን ጠላቶች ለማስፈራራትና አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ ደግሞ እርምጃ ለመወስድ ሰለሚያመች ነው።

ዩናይትድ ስቴትስና እስራኤል ከመሰከረም 11 በኋላ

ምንም እንኳን ከቀዝቃዛው ጦርነት በኋላ እስራኤል የአሜሪካ ስትራቴጂያዊ አጋር መሆኗን ማሰቡ የሚከብድ ቢሆንም ሎቢው በ1990ዎቹም ቢሆን አጀንዳዎቹን ለማስፈጸም ይገፋ ነበር። ከዚያ በኋላ የመስከረም 2001ዱ ጥቃት ደረሰና አሜሪካም የአረቡንና የሙስሊሙን ዓለም፣ በተለይም የመካከለኛውን ምስራቅ ሁኔታ ቆም ብላ የምታጤንበት ክስተት ተፈጠረ። ስለሆነም ያ ጊዜ ለእስራኤልና ለሎቢው አስጊ የሆነ ጊዜ ነበር ማለት ይቻላል።

የቡሽ አስተዳደር በዩናይትድ ስቴትስና በእስራኤል መካከል የመሠረተው ጥብቅ ቁርኝት ጸረ-አሜሪካ በሆነ የአሸባሪነት ስጋት ላይ ነዳጅ የሚያርከፈክፍ ሰበብ ነው ብሎ መደምደም ነበረበትን? አሜሪካ በአረቡና በሙስሊሙ ዓለም ዘንድ ያላትን ገጽታ ለማሻሻል ራሷን ከእስራኤል ትንሽ በትንሽ ማራቅ ይኖርበታልን? በተለይም ደግሞ የኦሪዮል ሻሮን መንግስት በምዕራቡ ዳርቻ የሚያንጻቸውን የሠፈራ መንደሮች እንዲያቆምና የፍልስጤም መንግስት እንዲመሠረት ያደርግ ዘንድ ፕሬዝዳንት ቡሽ ጫና ማድረግ ይኖርባቸዋልን? ዩናይትድ ስቴትስ ከ1990 ጀምሮ እስራኤልን ከአደጋ ለመጠበቅ በማስብ በመካከለኛው ምሥራቅ በሰፊው ያሰማራችውን ጦሯን ማስወጣት መጀመር አለባትን?

ይህ ሁሉ ከንቱ የሆነ ፍርሃት አልነበረም። በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለት ላይ ልናብራራው እንደሞከርነው አሳማ ቢንላደን የፍልስጤማውያን ጉዳይ ክፉኛ ያብከነክነው እንደነበርና ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል ጠንካራ እርዳታ መስጠቷ ሲያበሳጨው እንደቆየ ማስረጃዎች በግልጽ ያሳያሉ። በተጨማሪም የአሜሪካ ኃይሎች በሳዑዲ አረቢያ የነዳጅ ጉድጓዶች አካባቢ መገኘት የሙስሊሙን ዓለም ቁጣ በማቀጣጠል የአል-ቃኢዳ እርምጃ እንዲፋጠን አድርጎታል። ዩናይትድ ስቴትስ ወደ ቀድሞው አቋሟ ተመልሳ በመካከለኛው ምስራቅ የአደራዳሪነት ሚናዋን በሚገባ በመወጣት የእስራኤል-ፍልስጤምን ግጭት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መፍታት ይኖርበታልን? ዩናይትስ ስቴትስ ለዚህ ዓይነቱ ጥያቄ መልስ ሊሆን

የሚችል ናሙናዊ ድርጊት ከዚህ በፊት አድርጋ ታውቃለች። የሬገን አስተዳዳር በ1980ዎቹ ወታደሮቹን ለስላም አስጠባቂነት በሊባኖስ አስፍሮ ነበር። ሆኖም ግን 240 የሚሆኑ ማሪን ወታደሮቹ ቤይሩት ውስጥ በመኪና ላይ በተጠመደ ቦምብ ጋይተው ካለቁ በኋላ ወዲያውኑ ነበር የቀሩትን ያስወጣው። ፕሬዛዳንት ካርተርና ትልቁ ቡሽም በክልሉ ውስጥ ሰላም እንዲሰፍን እውነተኛ ጥረቶችን አድርገዋል። ይሁን እንጂ ያንን ያደረጉት ለሎቢው ትኩረት ባለመስጠትና በእስራኤል ላይ ጫና በማሳረፍ ነበር።

ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ ከመሰከረም 11ዱ ጥቃት በኋላም ቢሆን እስራኤልና አሜሪካውያን አጋሮቿ ትኩረታቸውን ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ለማዞር መልካም አጋጣሚ ተፈጥሮላቸው ነበር። የቡሽ አስተዳደር በጊዜው እስራኤል በአሸባሪነት ላይ በተከፈተው ጦርነት ወሳኝ የሆነች አጋር መሆኗንና የእስራኤል ጠላት የአሜሪካም ጠላት መሆኑን ቢያምን ኖሮ ሻሮን በፍልስጤማውያን ላይ የሚከተሉትን አቋም ዩናይትድ ስቴትስ በደገፈች ነበር። እንዲሁም የእስራኤል ክልላዊ ጠላቶች በሆኑት ኢራን፣ ኢራቅና ሶሪያ ላይ ጦርነት በከፈተ ነበር። በዚህ አስተሳሰብ መሠረት የአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎች በመካከለኛው ምስራቅ የሚገኙ የእስራኤል ጠላቶችን ማስወገዱ ስትራቴጂያዊ ግባቸው ሊሆን በበቃ ነበር። ምክንያቱም የእስራኤል ጠላቶች የአሜሪካም ጠላቶች ናቸውና። እናም ማንም ሰው ሊገምተው እንደሚችለው በሎቢው ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቡድኖች ይህን ዕድል ወደ ተግባር ለመቀየር በጋራ ሆነው መስራት ጀመሩ።

ልፋታቸው መና ሆኖ አልቀረም። የቡሽ አስተዳደር በመጨረሻ የሎቢውን ሃሳብ ተቀብሎ ሌላኛውን አማራጭ ወደ ጎን ለመግፋት ወሰነ። ዩናይትድ ስቴትስ ቀስ በቀስ እስራኤል ፍልስጤማውያንን፣ ኢራንንና የቀረውን የክልሉን ክፍል አስመልክቶ የምትከተለውን ፖሊሲ መቀበል ብቻ ሳይሆን ለፖሊሲዎቿ የምትሰጣቸውን ምክንያቶችም ጭምር ተቀብላ መከተልን መረጠች። ከዚያ በኋላ የአሜሪካና የእስራኤል መሪዎች ልክ ከአንድ ገጽ ላይ እንደሚያነቡ ሁሉ ቃላቸው ተመሳሳይ ሆኖ አረፈው።

ከዚህ ክስተት የምንረዳው ሃሳብ ይህ ውጤት ያልተጠበቀ እንደነበር ነው። በዚህ የነገሮች አካሄድ መሠረት ቡሽና ሻሮን (አሁን ደግሞ ኦልመርት) ዓለምን የሚመለከቱት ተመሳሳይ በሆኑ መነጽሮች ነው ማለት ነው። ስለሆነም ፕሬዝዳንት ቡሽና አማካሪዎቻቸው ከሎቢው የሚሹት አነስተኛ የሆነ ግፊት ብቻ ነበር። ምክንያቱም ከአረቡና ከሙስሊሙ ዓለም ጋር እንዴት መነጋገር እንዳለባቸው ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ (ከመስከረም 11 በኋላም ጭምር) የእስራኤልን ሃሳብ ተቀብለው ነበርና።[1]

ከመስከረም 11 በኋላ የዩ.ኤስ. አሜሪካ ፖሊሲ እንዴት እንደተለወጠ የሚያሳየው ይህ አገላለጽ የሚጎድለው ነገር አለ። ምክንያቱም አልፎ አልፎ ብቅ የሚለውን በቡሽ አስተዳደርና በእስራኤል መንግስት መካከል የነበረውን አለመግባባት ያላገናዘበ ነውና። ከመስከረም 11 በኋላ በዓመቱ መጀመሪያ ቡሽና ሻሮን ፍልስጤምን ጨምሮ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ተወዛግበዋል። በሁለቱ ሰዎች መካከል የነበረው ውዝግብ ጋብ ካለ በኋላ እንኳ ፍልስጤማውያንን በተመለከተ በመካከላቸው የነበረው ልዩነት አልተወገደም ነበር ማለት ይቻላል። እርግጥ ነው ቡሽ የእስራኤል -ፍልስጤማውያንን ግጭት ለመፍታት ያደርጉት የነበረው ጥረት በሁለቱ መካከል ስምምነትን ለማስፈንና የአረቦችን ቁጣ ለማብረድ ያለመ ነበር። ይህ አመለካከት በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር' በአሜሪካ የስላላ ተቋም' እንዲሁም በጦር ኃይሎች ውስጥ ታላቅ ድጋፍ አስገኝቶላቸው ነበር። ቡሽ በተጨማሪም ሶሪያን አስመልክቶ ከእስራኤልና ከሎቢው ጋር መሠረታዊ ልዩነት ነበራቸው። ይሁን እንጂ ሎቢው በቡሽ ላይ ጫና በማሳደር የራሱን የፖሊሲ አማራጭ ተቀብለው እንዲያራምዱ አስገድዷቸዋል።

በተጨማሪም ዩ.ኤስ. አሜሪካ ኢራቅንና ኢራንን አስመልክታ የምትከተላቸውን ፖሊሲዎች፣ እንዲሁም የቡሽ አስተዳደር መካከለኛው ምሥራቅን የዲሞክራሲ አምባ ለማድረግ የነደፈውን ታላቅ እቅድ ጭምር በመቅረጽ በኩል ሎቢው ወሳኝ ሚና ተጫውቷል። ሎቢው በዚህ ብቻ ሳይወሰን እስራኤል በ2006 ሊባኖስን የመውረሯን ትክክለኛነት የአሜሪካ ሁለቱም ፓርቲ ፖለቲከኞች ያለምንም ማቅማማት ይደግፉ ዘንድ ለማግባባት ሌት ተቀን ይሰራ ነበር።

እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች አወዛጋቢ እንደመሆናቸው መጠን በቀላሉ የተከናወኑ አልነበሩም፡፡ የኢራቅ ጦርነት ከመደረጉ በፊትና ከተደረገም በኋላ በርካታ ፖለቲከኞች የፕሬዝዳንት ቡሽ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲ፣ በተለይም ኢራቅን ለመውረር መወሰናቸው ቢያንስ በተወሰነ መልኩ እስራኤልን ለመጥቀም ያለመ ነበር የሚል አስተያየት አላቸው፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ እስራኤልም ሆነች ዋና ዋና የሚባሉ አፍቃሪ-እስራኤል አሜሪካውያን የተቃውሞ ሃሳብ ያላቸው ሲሆን ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብ የሚያራምዱትን አካላት ሁሉ ጸረ-ሴማውያን ናቸው ብለው መፈረጃቸው አያስደንቅም፡፡ ሆኖም ግን ጉዳዩ አወዛጋቢ ይሁንም አይሁን በሃቅ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም ሎቢው በአሜሪካ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲ ላይ ከባድ ተጽዕኖ እያደረግምን? የሚያደርግ ከሆነ ውጤቱ ዩናይትድ ስቴትስን ነው ወይስ እስራኤልን የጠቀመው? የሚሉትን ጥያቄዎች መመልከቱ ብልህነት ነው፡፡ ለመጀመሪያው ጥያቄ የሚኖረው መልስ ‹‹አዎን›› የሚል ሲሆን ለሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ የሚኖረው መልስ በእኛ እምነት ‹‹ሁለቱንም አይጠቅምም›› የሚል ነው፡፡

የቡሽ አስተዳደር መካከለኛው ምሥራቅን አስመልክቶ የሚከተላቸውን ፖሊሲዎች በጥልቀት ለመፈተሽ፣ እስራኤል በኃይል በያዘቻቸው ግዛቶች ያሻትን እንድታደረግ ዩ. ኤስ. አሜሪካ የምትሰጣትን ድጋፍ እናስቀድምና ኢራቅን ለመውረር ያደረገቸውን ውሳኔ እናስከትል፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ዩናይትድ ስቴትስ ክልሉን ወደ ዲሞክራሲ ለማሸጋገር የወጠነችውን ፖሊሲ በተመለከተ ሶሪያንና ኢራንን ትኩረት ሰጥተን ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡ በመጨረሻም አሜሪካ የ2006ቱን የሊባኖስ ጦርነት የያዘችበትን መንገድ እንመረምራለን፡፡ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ሎቢው ጠንካራ ተጽዕኖ ባይፈጥር ኖሮ ወይም በሎቢው ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ ቡድኖች የተለየ የፖለቲካ መንገድ ተከትለው ቢሆን ኖሮ ዛሬ የአሜሪካ ፖሊሲ የተለየ ሊሆን በቻለ ነበር፡፡ አሜሪካ የምትወስደው እርምጃም እንደዚያው ከብሔራዊ ጥቅሟ ጋር አብሮ የሚሄድና ለእስራኤልም ጭምር የተሻለ በሆነ ነበር፡፡

ምዕራፍ ሰባት

ሎቢውና የፍልስጤማውያን ሁኔታ

ምንም እንኳን አሁን በስፋት የተዘነጋ ቢሆንም በ2001 ማብቂያና እንደገናም በ2002 የጸደይ ወራት የቡሽ አስተዳደር በአረቡና በሙስሊሙ ላለም ክፉኛ የተንሰራፋውን ጸረ-አሜሪካ ስሜት ለመቀነስ እስራኤል በኃይል በያዘቻቸው መሬቶች የምታራምደውን የማስፋፋት ፖሊሲ እንድታቆምና የፍስጤማውያንም ምንግስት እንዲመሠረት ግፊቱን አጠናክሮ ነበር። የመስከረም አስራ አንዱን ጥቃት ተከትሎ የአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎች የእስራኤል ፍልስጤምን ጉዳይ እልባት መስጠት ወይም ቢያንስ ለዚያ የቀረበ አንድ ዓይነት ጥረት ማድረግ አል-ቃኢዳን የመሰሉ አሸባሪ ቡድኖች ድጋፍ እንዳያገኙ ለማድረግ ከማስቻሉም በላይ የጸረ-አሸባሪነት ሕብረት የመገንባቱን ሂደት በማፋጠን ታላቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለው አሰቡ።[1]

ይሁን እንጂ የቡሽ አስተዳደር ቴሌአቪቭ ፖሊሲዋን እንድትቀይር ማሳመን ሳይችል መቅረቱ ብቻ ሳይሆን በመጨረሻ የእስራኤል ጠጣር መስመረኞች (hard liners) በፍልስጤማውያን ላይ የሚከተሉትን አቋም ደግፎ አረፈው። ጊዜ ባለፈ ቁጥር ቡሽና ወታደራዊ አማካሪዎቻቸው ጭምር እስራኤል የአቋሟን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የምታቀርባቸውን ምክንያቶች ተቀብለው በሥራ ላይ በማዋላቸው የእስራኤልና አሜሪካ አቋም አንድ ዓይነት ሊሆን በቅቷል። የካቲት 2003 ላይ የወጣው ዋሽንግተን ፖስት እንዲህ የሚል የማጠቃለያ ሃሳብ የያዘ ርዕስ አስፍሮ ነበር። ‹‹ቡሽና ሻሮን መካከለኛው ምሥራቅን አስመልክቶ ያላቸው አቋም ተቀራርቧል።››[2] ለዚህ የቡሽና አማካሪዎቻቸው የአቋም ማፈግፈግ ዋነኛው ምክንያት የሎቢው ተጽዕኖ ነበር።

ታሪኩ የሚጀምረው መስከረም 2001 ላይ ነው። አሪዮል ሻሮን በሃይል በተያዙት ግዛቶች ቁጥብነትን እንዲያሳዩና በሁለተኛው ኢንቲፋዳ የተቀጣጠለውን የኃይል ድርጊት እንዲገቱ ፕሬዝዳንት ቡሽ ግፊት ማድረግ ጀመሩ። የቡሽ አስተዳደር -ኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ እንደገለጸው- በሻሮን ላይ ታላቅ ግፊት በማድረግ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ሽሞን ፔሬዝ (ምንም እንኳን

ቡሽ የአራፋትን አመራር ክፉኛ የሚተቹ ቢሆንም) ከአራፋት ጋር እንዲገናኙ ፈለጉ።[3]

አዲሱ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ቡሽ ቀደም ብለው ጥቅምት ወር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የፍልስጤማውያን መንግስት መመስረቱን እንደሚደግፉ ይፋ አድርገው ነበር። ይህ ክስተት በራሱ አስደናቂ መሻሻል የተደረገበት ነው። ምክንያቱም የሁለት መንግስታት የመፍትሔ ሃሳብን ለመተግበር ፕሬዛዳንት ክሊንተን በትጋት የሰሩ ቢሆንም በቢሯቸው እስከቆዩባት የመጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ‹‹የፍልስጤም መንግስት›› ምትለዋን ቃል ትንፍሽ አላሉም ነበር።[4] ፕሬዝዳንት ቡሽም ቢሆኑ ከመስከረም11ዱ ጥቃት በፊት በአረብ እስራኤል ግጭት ላይ እጃቸውን ላያሰገቡና ከደሙ ንጹህ ነኝ የሚል አቋም ለመከተል ይመርጡ እንደነበር ተነግሯል። ከዚያ በኋላ ግን የመስከረም 11ዱ ክስተት ሃሳባቸውን እንዲቀይሩ አድርጓቸዋል።

በዚያ ያልተጠበቀ የአቋም ለውጥ የተደናገጡት የእስራኤል መሪዎች ዋሽንግተን ምናልባት የአረቦችን ልብ ለማግኘት ብላ አይሁዳዊቷን አገር ለሽያጭ እንዳታቀርባት ስጋት አደረባቸው። ዋሽንግተን ፖስት ለአሪዮል ሻሮን የሚቀርቡ ምንጮችን ጠቅሶ ባቀረበው ዘገባ፦ ‹‹ዩናይትድ ስቴትስ በምትመራው ጥምሩ ኃይል ውስጥ ኢራንንና ሶሪያን ለማካተት መወሰኗን ሻሮንን አበሳጭታቸዋል›› ብሏል።[5] በጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ሻሮን በንዴት ቱግ ብለው ‹‹አረቦችን ለማባበል ሲሉ እኛን አሳልፈው ሊሰጡን ይሻሉ›› በማለት ቡሽን ወረፉ። ‹‹እስራኤል›› አሉ ሻሮን ቀጠል አድርገው ‹‹ችኮዝላቫኪያን አትሆንም።››[6] ይህን አስተያየት ከሰጡ ከሰዓታት በኋላ የእስራኤል ጦር ሄብሮን ውስጥ የሚገኙ ብዙ የፍልስጤማውያን መንደሮችን ወረረ።[7] አሪዮል ሻሮን ‹‹እስራኤል ችኮዝላቫኪያ አትሆንም›› ያሉበትና ቡሽም ‹‹ለምን ከኔቪል ቻምበርሊይን ጋር ያመሳስሉኛል›› ብለው የተቆጡበት አጋጣሚ አንድ ታሪካዊ ክስተትን የሚያስታውስ ነው። ጉዳዩ የተከሰተው እ.ኤ.አ መስከረም 28 ቀን 1938 በተደረገውና የሚዩኒክ ውል (Munich pact) እየተባለ በሚጠራው ስምምነት ወቅት ነበር። ነገሩ እንዲህ ነው፤ የጀርመኑ ቻንስለር አዶልፍ ሂትለር ከጀርመን ድንበር አጠገብ የምትገኘውንና ጀርመንኛ ቋንቋ ተናጋር ሕዝብ ያላትን ሱደተንላንድ የተባለች የችኮዝላቫኪያ ግዛት ወደ ጀርመን ግዛት ለመቀላቀል እንደሚፈልግ ግልጽ አደረገ። እንግሊዝና

ፈረንሳይ ቀደም ብሎ በተደረገው የአንደኛው የአለም ጦርነት ተሰላችተው ስለነበር ሌላ እሰጥአገባ ላለመፍጠር በማሰብ ሂትለር የጠየቀውን እንዲያገኝና ከዚያ በኋላ ግን አንድም የአውሮፓ ግዛት እንዳይጠይቅ ቃል በማስገባት የሚዩኒክን ውል ፈረሙ፡፡ በዚያ ስምምነት ላይ ይበልጥ ሚና የነበራቸው የእንግሊዙ ጠ/ሚኒስትር ኔቪል ቻምበርሊይን በመሆናቸው ሂትለር ቻምበርሊይን እንዳቁላቸው ብዙዎች ለመገንዘብ አልተቸገሩም፡፡ እንግዲህ አሪዮል ሻሮን ችኮዝላቫኪያን ማንሳታቸው ‹‹ቡሽ ከአረቦች ጋር ተሻርከው የእስራኤልን ግዛት ሊሰጡና እስራኤልም እንደ ችኮዝላቫኪያ ልትሆን አትችልም›› ማለታቸው ነው፡፡

የሁዋይት ሃውስ ፕሬስ ጸሐፊ አሪ ፍሊሸር የሻሮንን ንግግር ‹‹ተቀባይነት የሌለው››[8] በማለት አጣጣሉት፡፡ ከዚያ በኋላ ኦሪየል ሻሮን ዘግየት ብለውም ቢሆን ይቅርታ ይደረግላቸው ዘንድ ጥያቄያቸውን ለአሜሪካ መንግስት ቢያቀርቡም መሰረታዊ የሆነው ችግር ሳይፈታ ነበር የቆየው፡፡[9] ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ጥቅምት ወር ላይ የእስራኤሉ የቱሪዝም ሚኒስትር ሪሃቪን ዚቪ በአንድ የፍልስጤም አንጃ ታጣቂዎች መገደላቸውን ተከትሎ የእስራኤል ጦር በፍልስጤማውያን ቁጥጥር ስር ወዳሉት የምዕራቡ ዳርቻ ቦታዎች በመግባት ሌላ ትልቅ ወረራ አካሄደ፡፡ በዚህ ጊዜ ቡሽ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሸሞን ፕሬዝ ጋር በግል ተገናኝተው ‹‹እስራኤል በተቻለ ፍጥነት ጦሯን እንድታስወጣ እንሻለን›› በማለት ያላቸውን ሃሳብ ገለጹላቸው፡፡[10] ዳሩ ግን የእስራኤል መንግስት ያንን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ከዚያ ቦታ የሚወጣው ብቀላውን ሙሉ በሙሉ ሲያጠናቅቅና አረፋትም በፍልስጤም ግዛቶች ውስጥ በቁጥጥር ሥር ሲሆኑ ብቻ መሆኑን አስታወቀ፡፡ ዘ ጋርዲያን የተባለው የእንግሊዝ ጋዜጣ እንደጻፈው ‹‹ጆርጅ ቡሽ ወደ ሥልጣን ከመጡ ጀምሮ ኦሪዮል ሻሮን የያሲር አራፋትን ሕልውና ስጋት ላይ የሚጥልና የፍልስጤማውያንን ግዛት የሚያፈራርሰውን ወረራ እንዲያቆሙ የቀረበላቸውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ከዋሽንግተን ጋር በተደጋጋሚ ተወዛግበዋል፡፡›› ብሏል፡፡

ከዚያ በኋላ ሻሮንና አፍቃሪ እስራኤል የሆነው ሎቢ እያደገ የሄደውን አለመግባባት በማስወገድ ዩናይትድ ስቴትስና እስራኤል በጋራ የሽብርተኝነት

ስጋት የተደቀነባቸው አገራት መሆናቸውን የቡሽ አስተዳደርና የአሜሪካ ሕዝብ እንዲያምኑ ለማድረግ በፍጥነት ተንቀሳቀሱ፡፡ የእስራኤል መሪዎችና ቁልፍ የሆኑ የሎቢው ቡድኖች በቀጣዮቹ ዓመታት ትኩረት ሰጥተው በተደጋጋሚ ሲያነሱት የነበረው ጉዳይ በአሳማ ቢን ላደንና በአራፋት መካከል መሠረታዊ ልዩነት የሌለ መሆኑን ነበር፡፡ ስለሆነም እስራኤል በምርጫ ሥልጣን የያዙትን የፍልስጤማውያን መሪ ያሲር አራፋትን በማግለል ከእርሳቸው ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነትም ሆነ ንግግር ላለማድረግ ወሰነች፡፡ ሻሮን የረዥም ጊዜ ወዳጃቸውና አድናቂያቸው ለሆነው የኒውዮርክ ታይምሱ ዊሊያም ሳፋር ታህሳሥ 2002 ላይ እንዲህ ብለውት ነበር፡- “እናንተ በአሜሪካ የምትገኙ ሕዝቦች በሽብርተኝነት ላይ ጦርነት ከፍታችሁዋል፡፡ እኛ በእስራኤል የምንገኝም ከሽብርተኝነት ጋር ጦርነት ላይ ነን፡፡ ስለሆነም ሁላችንም ተመሳሳይ ጦርነት እያካሄድን ነው፡፡››[12]

ሻሮን፣ ዩ.ኤስ አሜሪካ መካከለኛው ምሥራቅን አስመልክቶ የምትከተለውን ፖሊሲ በተመለከተ መጨነቅ የጀመሩት የመስከረም 11ጥቃት ከደረሰ በኋላና ቡሽ የፍልስጤማውያን መንግሥት እንዲመሠረት የሚፈልጉ መሆናቸውን ከመግለጻቸው ጥቂት ሳምንታት በፊት ነበር፡፡ መስከረም14 ላይ ከአሜሪካ አይሁዳውያን መሪዎች ጋር በስልክ ሲነጋገሩ እንደገለጹት እርሳቸውን የሚያሳስባቸው ጉዳይ በዋነኝነት ቡሽ አረፋትን ከቢን ላደን የተለዩ አድርገው የሚመለከታቸው ከሆነና የጸረ-ሽብርተኝነትን ሕብረት ለማጠናከር ያግዛቸው ዘንድ የአረቦችን ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ በእስራኤል ላይ ጠንካራ አቋም ያሳዩ እንደሆነ ነው፡፡ እናም ሻሮን የሎቢው መሪዎች እንዲረዷቸው ተማጽኑ፡፡[13] ሆኖም ግን በዚያ ንግግራቸው የተገኘ ውጤት አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው የመስከረም 11 ዱ ጥቃት ባስተከለበት ድንጋጤ ግራ እንደተጋባ ነበርና፡፡ በዚህም የተነሳ በዚያ ሰዓት የአሜሪካ ፖሊሲ በምን አቅጣጫ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ አስቸጋሪ ነበር፡፡ ሁሉም ነገር ምስቅልቅሉ በወጣበት በዚያ ጊዜ ዘ ኒው አሜሪካን ሴንቸሪ የተባለው ድርጅት መስከረም 20 ላይ በርካታ የኒዎኮንሰርቫቲቭ የፖለቲካ አመለካከት አራማጆች ፊርማቸውን ያኖሩበትን ደብዳቤ ለቡሽ አቀረበ፡፡ ከእነርሱም ውስጥ ዊሊያም ቤኔት፣ ኢሊዮት ኮኸን፣ አሮን ፍሪድበርግ፣ ራውል ማርክ ግሬችት' ሮበርት ኬጋን፣ ቻርለስ ክራውታመር፣ ጂን ኪርክፓትሪክ' ዊሊያም ክሪስቶል' ሪቻርድ ፐርልና ኖርማን ፖድሆርትዝ ይገኙበታል፡፡

በደብዳቤው ውስጥ የሰፈረው መልዕክት፣ እስራኤል በዓለም አቀፍ ሽብርተኝነት አንጻር የአሜሪካ ጠንካራ ወዳጅ መሆኗን ይገልጽና ዩናይትድ ስቴትስ ለፍልስጤማውያን አስተዳደር የምትሰጠውን ማንኛውንም ድጋፍ እንድታቆም ይጠይቃል፡፡[14]

ሽብርተኝነትን ለማሸነፍ ቡሽ የነደፉት ዝርዝር ፖሊሲ በግልጽ የታወቀው የሁለት መንግስታትን የመፍትሄ ሃሳብ የሚደግፉ መሆናቸውን ካስታወቁ በኋላ ሲሆን ሻሮንም ሆኑ ሎቢው በዚህ አጀንዳ እንደማይደሰቱ ይታወቅ ነበር፡፡ ይህ የቡሽ አቋም ግልጽ እንደተደረገ አይፓክ ባወጣው መግለጫ፡- ‹‹ቡሽ እንዲህ ዓይነቱን ሃሳብ እንዲያራምዱ ምክር የለገሷቸው አማካሪዎቻቸው አሜሪካ በሽብርተኝነት ላይ የከፈተችውን ዘመቻ የሚሸረሽር አቋም እንዲወስዱ አድርገዋቸዋል፡፡ ፕሬዝዳንቱ ሽብርተኝነትን የሚደግፉና የሚያራምዱ አካላትን በመቅጣት ፋንታ ሽልማት እንዲሰጧቸው ገፋፍተዋቸዋል››[15] ብሏል፡፡ ዋና ዋና የሚባሉት የአሜሪካ አይሁዳውያን ድርጅቶች ፕሬዝዳንቶች ኮንፈረንስ የበላይ የሆኑት ሞርትማየር ዘከርማን ደግሞ፡- ‹‹ቡሽ የተሳሳተና አርቆ ማስተዋል የጎደለው ፖሊሲ እየተከተሉ ነው›› በማለት ተችተዋል፡፡[16] ከዚያ በኋላ አፍቃሪ እስራኤል የሆኑ ድርጅቶች ይህን መልዕክት ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ከመደጋገም ታቅበው አያውቁም ማለት ይቻላል፡፡

ዋና ዋና ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ የሎቢው አካላት በቡሽ አስተዳደር ላይ ጫና በማሳረፍ ሻሮን እስከፈለጉ ድረስ የእስራኤል ጦር በቅርቡ በያዛቸው የፍልስጤም ግዛቶች ውስጥ እንዲቆይ የማድረግ ጥረታቸውን ጀመሩ፡፡ የኤ.ዲ.ኤል. ፕሬዚዳንት አብረሃም ፎክስማን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮሊን ፓወል ጥቅምት 23 ደብዳቤ በመጻፍ የዩኤስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ እስራኤል በቅርቡ ከተቆጣጠረቻቸው ቦታዎች እንድትወጣ መጠየቁ እንዳስጨነቃቸው ሲገልጹ፣ “ይህ አስተያየት ትክክለኛ ነው ብለን አናምንም፡፡” ካሉ በኋላ ቀጥለው፣ “አሜሪካ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ስትከተለው የኖረችው የእስራኤልን ራስን የመከላከል መብት የሚያጸድቅ ፖሊሲዋና ይህ የአሁኑ አቋሟ የሚጻረሩ ናቸው፡፡ ዛሬ ዓለም በሙሉ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት በተባበረበት ጊዜ እንዳለመታደል ሆኖ የፍልስጤም አስተዳደር ብጥብጥንና ሽብርተኝነትን ለማስወገድ እርምጃዎችን ከመውሰድ

እምቢተኛ ሆኗል ››፡፡ በማለት ሀሳባቸውን አጠቃልለዋል።[17] ዙከርማን በበኩላቸው የፎክማንን ሃሳብ ሲያስተጋቡ፡- ‹‹ቡሽ እስራኤልን ለመጫን የወሰዱት እርምጃ ተገቢነት የሌለው፣ ከመጠን ያለፈ፣ አሜሪካ በአሸባሪነት ላይ ከከፈተችው ጦርነት አኳያ ሁኔታዎችን ያላገናዘበ ነው›› በማለት ተናግረዋል፡፡[18]

ሎቢው በተጨማሪም በኮንግረሱ ውስጥ የሚያደርገውን የተለመደ ተግባሩን ቀጥሎ ነበር፡፡ ህዳር 16 ላይ ሰማኒያ ዘጠኝ የሚሆኑ ሴናተሮች ለቡሽ በላኩት ደብዳቤ ፕሬዚዳንት አራፋት በእስራኤል ላይ የሚደረጉ አመፆችን ለማስቆም አስፈላጊውን እርምጃ እስኪወስዱ ድረስ ከእርሳቸው ጋር ላለመገናኘት ያሳለፉትን ውሳኔ ጠቅሰው አወደሷቸው፡፡ ሴናተሮቹ በተጨማሪም እስራኤል ፍልስጤማውያንን እንዳትበቀል የዩናይትድ ስቴትስ ተጽእኖ ከማሳረፍ እንድትቆጠብ እና አስተዳደራቸውም እስራኤልን በጽናት እንዲደግፍ በደብዳቤያቸው ቡሽን አሳሰቡ፡፡ ኒውዮርክ ታይምስ ‹‹ደብዳቤው የተጻፈው ከሁለት ሳምንታት በፊት በአሜሪካ አይሁዳውያን መሪዎችና ቁልፍ በሆኑ ሴናተሮች መካከል ከተካሄደው ስብሰባ በተገኘው የመነቃቃት መንፈስ ነው›› በማለት ገልጿል፡፡ ቀጥሎም ‹‹ አይፓክ በተለይ ደብዳቤውን በማርቀቅና ሁነኛ ሀሳብ በማዋጣት የላቀ ድርሻ ነበረው›› ብሏል፡፡ [19]

በነዳር ወር ማለቂያ አካባቢ በቴሌአቪቭና በዋሽንግተን መካከል የነበረው ግንኙነት ማለፊያ የሚባል መሻሻል አሳይቷል፡፡ ይህም በከፊል በሎቢው ጥረት የተገኘ ነው ሊባል ቢችልም፣ በዋነኝነት አሜሪካ በአፍጋኒስታን ባደረገችው ጦርነት የመጀመሪያ ምዕራፍ ድል ማግኘቷ አል-ቃዒዳን ለመፋለም የአረቦችን ድጋፍ አስፈላጊነት ዝቅ ስላደረገው ነበር፡፡ እናም ሻሮን ታህግሥ መጀመሪያ ላይ ዋይት ሃውስን በመጎብኘት ከቡሽ ጋር ወዳጃዊ ውይይት አደረጉ፡፡ እርግጥ ነው የሁለቱ ሰዎች ውይይት ከመደረጉ በፊት እስራኤል ውስጥ የተፈጸሙ ሶስት የአጥፍቶ ጠፊ የቦምብ ጥቃቶችን ለመበቀል የእስራኤል ጦር ጋዛ ውስጥ የተመረጡ ኢላማዎችን መትቶ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ታዲያ ቡሽ እስራኤልን ያልወቀሱ ሲሆን፣ ለወደፊቱም ከእንዲህ ዓይነቱ ድርጊት እንዲቆጠቡ አላስጠነቀቁም፡፡ ከዚያ ይልቅ የዋይት ሃውስ ቃል አቀባይ አጽንዖት ሰጥተው የተናገሩት መልእክት እንዲህ የሚል ነበር፡- ‹‹

እስራኤል ሉዓላዊ የሆነች ሐገር ናት፡፡ ስለሆነም በሰላም የመኖር መብቷ የተረጋገጠ ነው፡፡›› በተመሳሳይ ጊዜ አራፋት ሽብርተኝነትን ለማስቆም የበለጠ እንዲሠሩ ቡሽ ጠይቀዋል፡፡[20]

ሻሮን እንደገና የካቲት/2002 ላይ የወዳጅነት ጉብኝት ለማድረግ ወደ ዋይት ሃውስ መጡ፡፡ በዚያ ጊዜም ቢሆን አራፋት ሽብርተኝነትን ይደግፋሉ በማለት ሻሮን ደጋግመው የከሰሷቸው ሲሆን፣ የእስራኤል ፍልስጤምን ግጭት ለመፍታት እንዳይቻል የሚያደርጉ ዋነኛው መሰናክል እርሳቸው መሆናቸውን በመጥቀስ አማረዋል፡፡ ቡሽ በዚህ ጊዜ ይህን አባባል ያለምንም ተቃውሞ በግልጽ ተቀበሉ፡፡ ከዚያም በላይ ከወር በፊት በጥር 2002 ከተከሰተው የካሪን ኤ. (Karine A) ጉዳይ ጀርባ አራፋት አሉበት መባሉን አምነዋል፡፡ (ካሪን ኤ ሃምሳ ቶን የሚሆን የጦር መሣሪያና ተቀጣጣይ ፈንጂ ተጭና ከኢራን ከተነሳች በኋላ ቀይ ባሕር ላይ በእስራኤል ባሕር ኃይል የተያዘች የፅቃ ጫኝ መርከብ ናት)፡፡ ምንም እንኳን ማስረጃዎች በጊዜው ግልጽ ባይሆኑም የመጨረሻ ማረፊያዋ ጋዛ እንደሆነ ተገምቷል፡፡ እርግጥ ነው አንዳንዶች መሣሪያው ሊባኖስ ውስጥ ለሚገኘው ሂዝቡላህ የተላከ ነበር በማለት ይከራከራሉ፡፡ [21]

ምንም እንኳን ጉዳዩ ከአረፋት ጋር በቀጥታ የሚያያዝ መሆኑን የሚያሳዩ ግልጽ ማስረጃዎች ባይኖሩም፣ የእስራኤል መንግሥትና ሎቢው ‹‹አራፋት እነዚያን መሣሪያዎች በእስራኤል ላይ ለሚያካሂዱት ጦርነት ሊያውሏቸው አስበው ነበር›› የሚለውን አባባል ክፉኛ አስጮሁት፡፡[22] የፍልስጤማውያኑ መሪ የካሪን ኤ.ጉዳይ ፈጽሞ እንደማይመለከታቸው በመግለጽ ያስተባበሉ ሲሆን፣ የአረፋትን ንጽህና የሚቃረን ምንም ዓይነት ግልጽ ማስረጃ አለመቅረቡን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮሊን ፓወልና ሌሎችም ባለስልጣናት አምነዋል፡፡[23] ይሁን እንጂ በመጨረሻ ላይ ቡሽ የእስራኤልንና የወዳጆቿን አቋም ደገፉ፡፡ ከዚያም ሻሮንን በዋይት ሃውስ ከጎናቸው አድርገው እንዲህ አሉ፡- ‹‹ሚስተር አራፋት በአሁኑ ቅጽበት የምንናገረውን እንደሚሰሙን አምናለሁ፡፡ ከዚህ በላይ ግልጽ መሆን አልችልም፡፡ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት አቅማቸው የሚችለውን ሁሉ ማድረግ አለባቸው፡፡ ሙሉ በሙሉ የጦር መሣሪያ ተጭና ባገኘናት ካሪንኤ መርከብ ጉዳይ በመጀመሪያ ተደንቀናል፡፡ ቀጥሎም ምናልባትም ያ መሣሪያ ለሽብር ጥቃት እንደሚውል ስናስብ እጅግ በጣም ቅሬታ ተሰምቶናል፡፡››[24]

ሎቢው ቡሽን ሲያዋርድ

የአሜሪካና የእስራኤል ግንኙነት በመልካም ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሰለበት ወቅት መጋቢት 2002 ላይ በአይሁድ ፋሲካ ዕለት የሃማስ አጥፍቶ ጠፊ ሰላሳ እስራኤላውያንን ገደለ፡፡ በዚህ ጊዜ በሁለቱ ሀገራት መካከል እንደገና ውጥረት ነገሠ፡፡ የፍልስጤማውያን አስተዳደር ድርጊቱን አወግዞ ኃለፊነቱን የሚወስዱትን ወገኖች አፈላልጎ እንደሚቀጣ አስታወቀ፡፡ ዳሩ ግን አስተዳደሩ ተመሳሳይ ጥፋት የሠሩ ሰዎችን በመቅጣት ረገድ ከዚያ በፊት ይህ ነው የሚባል ተግባር ሲፈጽም አልታየምና አሁን የገባው ቃል ለእስራኤል ስሜት አልሰጣትም፡፡ በመሆኑም ሻሮን አጠቃላይ የሆነ ራስን የመከላከል ክተት አወጁና ከሞላ ጎደል በምዕራቡ ዳርቻ የሚገኙ ዋና ዋና ሥፍራዎችን ተቆጣጠሩ፡፡[25] ወረራው እንደተከሰተ የእስራኤል ድርጊት አሜሪካ በአረቡና በሙስሊሙ ዓለም ያላትን ገጽታ እንደሚያበላሸውና በአሸባሪነት ላይ የተጀመረውንም ጦርነት እንደሚጎዳው በመግለጽ ሻሮን ወረራውን አብቅተው መውጣት እንዲጀምሩ ሚያዝያ 4 ቀን ቡሽ አሳሰቡ፡፡ ከሁለት ቀናት በኋላ፣ ‹‹የምናገረው ነገር ግልጽ ነው፡፡ ያለምንም መጓተት ጦርዎን ያስወጡ››፡፡ በማለት ማሳሰቢያቸውን ለሻሮን ደግመው አሰሙ፡፡ ሚያዝያ 7 ቀን የቡሽ ጸጥታ አማካሪ የነበሩት ኮንዶሊዛ ራይስ ለሪፖርተሮች በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፡- ‹‹ያለምንም መጓተት ማለት ያለምንም መጓተት ነው፡፡ ያም አሁን ማለት ነው፡፡›› ሲሉ የአሜሪካን ትዕግሥት ማጣት በሚያሳብቅ ሁኔታ ተናገሩ፡፡ በዚያው ዕለት ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፓወል በሁለቱም ወገኖች ላይ ግፊት ለማሳደርና ጦርነቱን አቁመው እርቅ እንዲያወርዱ ለማድረግ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አመሩ፡፡

የቡሽ አስተዳደር ባጋጠመው ኃይለኛ ጫና ፍም ላይ እንደተጣደ ወጥ ይንተከተክ ጀመር፡፡ የጫናው ምንጭ ሎቢው ሲሆን፣ ዓላማውም አስተዳደሩ መካከለኛው ምሥራቅን አስመልክቶ የተለዬ መንገድ እንዲከተል ለማድረግ ነው፡፡ በሎቢው ዒላማ ውስጥ በዋነኛነት የገቡት ደግሞ የእስራኤል ጉዳይ ብዙም እንደማይገዳቸው የሚታመኑት ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ኮሊን ፓወል

ሲሆኑ፣ አሁን በሚያደርጉት ጉዞ ከአራፋት ጋር ለመገናኘት እንዳሰቡም ታውቋል፡፡ ፓወል መካከለኛው ምሥራቅ ደርሰው ብዙም ሳይቆዩ ነበር ከምክትል ፕሬዚዳንቱ ዲክ ቼኒ ቢሮና ከፔንታጎን የሚነሳውና የእስራኤል ጠንካራ ደጋፊዎች ያቀጣጠሉት የፖለቲካ ወላፈን ይገርፋቸው የጀመረው፡፡ ያ ወላፈን ፕሬዚዳንቱንና የብሔራዊ ፀጥታ አማካሪያቸውን ኮንዶሊዛ ራይስንም እስኪበቃቸው ገርፎ እስራኤል በኃይል ዳግም በያዘቻቸው አካባቢ ያሻትን እንዳትፈጽም የሚያሳድሩባትን ግፊት እንዲያቆሙ አድርጓቸዋል፡፡ በዚህም የተነሣ ራይስ በተደጋጋሚ እየደወሉ ፓወልን ያስጨነቋቸው ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ በንግግራቸው ውስጥ የተግሳጽ ቃናም እንደነበረበት ተወስቷል፡፡ ራይስ ያስተላለፉት መልእክት በዋይት ሃውስ ውስጥ የሚገኝ አንድ ሰው አመለካከት ሊሆን እንደሚችል ፓወል አላጡትም፡፡ [26]

በመገናኛ ብዙሃን (Media) በኩልም ቢሆን ኒዎኮንሰርቫቲቮች በፓወል ላይ ጫና ማሳረፋቸውን ቀጥለው ነበር፡፡ ሮበርት ኬጋንና ዊሊያም ክሪስቶል በዊክሊ ስታንዳርድ ጋዜጣ የሚያዝያ 11 እትም ላይ፡- ‹‹ፓወል በአሸባሪዎችና አሸባሪዎችን በሚዋጉ አካላት መካከል ያለውን ግርዶሽ በመንቀል ነገሩን ሁሉ አደበላልቀውታል›› [27] በማለት ጽፈዋል፡፡ በቀጣዩም ቀን ለዊክሊ ስታንዳርድ የሚጽፈው ዴቪድ ብሩክስ፡- ‹‹ፓወል የዩ.ኤስ.አሜሪካን ክብር ጎድተዋል፡፡ ..መካከለኛው ምሥራቅን አስመልክቶ የምትከተለውን ፖሊሲም አጣጥለዋል፡፡ እንዲሁም ከሁሉም በላይ የሞራል ግልጽነታችንን ክፉኛ ሸርሽረዋል፡፡›› በማለት ሀሳቡን አስፍሯል፡፡[28] በጊዜው ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ሆነው የእስራኤልን ጉዳይ ሲያስፈጽሙ የነበሩት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንጃሚን ናታንያሁ፣ ፓወል ገና እስራኤል ሳይደርሱ፣ ‹‹ጉዞአቸው የሚያስገኘው አንዳች ነገር አይኖርም›› በማለት ተናግረዋል፡፡[29] ናታንያሁ ትክክል ነበሩ፡፡ ምክንያቱም በቡሽ አስተዳደር የነበረው የኃይል ሚዛን በፍጥነትና ሙሉ ሙሉ ከኮሊን ፓወል በተቃራኒ በመዞሩ ዋሽንግተን ውስጥ የነበሩት ምክትላቸው ወደ እስራኤል ደውለው፣ ‹‹እኔ እዚህ ብቻዬን የማደርገው ጠፍቶኛል፡፡ ሰዎቹ በእርስዎ ላይ እየተሳለቁ ነው›› አሏቸው፡፡[30] ፓወል ቆየት ብለው መካከለኛው ምሥራቅ

ውስጥ የቆዩባቸውን እነኚያን አሥር ቀናት፡- ‹‹እጅግ በጣም አስቀያሚና ቅዥት ውስጥ ያሳለፍኳቸው›› በማለት ገልጸዋቸዋል።[31]

የሆነ ሆኖ ፓወል እስራኤል ውስጥ እያሉ ነበር መልዕክቱ የገባቸው። እናም ገና እስራኤልን ሳይለቁ ከኦሪዮል ሻሮን ጋር በመሆን ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡ ጊዜ በገጽታቸው ላይ መልዕክቱ የገባቸው መሆኑ ተንፀባርቋል። የሰንደይ ቴሌግራፉ ጆን ሲምፕሰን የፓወልን ሁኔታ ከታዘበ በኋላ እንዲህ በማለት ጽፏል፡- ‹‹ሚስተር ፓወል ራሳቸው ሳይሆን ሰዎች የሚወዱላቸውን ነገር ለመሥራት የተዘጋጁና በሰው ሀሳብ የሚመሩ ይመስሉ ነበር። ያለምንም ጥርጣሬ ያረጋገጡት ነገር ሻሮን በዋሽንግተን ያላቸውን ድጋፍ ጥንካሬና ጓደኞቻቸው በፕሬዚዳንቱ ላይ ምን ያክል ተጽዕኖ እንዳሳደሩባቸው ነበር።››[32] ናታንያሁ የተገናገሩት ትንቢት እውነት መሆኑ ተረጋገጠ። የፓወል ጉዞ በእርግጥም ያስገኘው አንዳች ነገር አልነበረም።

ሁለተኛው የሎቢው ዒላማ ቡሽ ራሳቸው ነበሩ። በአይሁዳውያን መሪዎችና በክርስቲያን ወንጌላውያን አማካይነት ከግራ ከቀኝ እየተዋከቡ ነበር የቆዩት። ቶም ዴላይ እና ዲክ አርሚ በተለይ እስራኤልን የመርዳቱን አስፈላጊነት በግልጽ ይናገሩ ነበር። ዴላይና የሴኔቱ አናሳዎች (Minority) መሪ ትሬንት ሎት ሚያዝያ 10 ቀን ዋይት ሃውስን በንበኙ ጊዜ እስራኤልን እንዲደግፉ ቡሽን አስጠንቅቀዋቸዋል።[33] በቀጣዩ ቀን ደግሞ በታይም መጽሔት ዘገባ መሠረት፣ ‹‹በሬቨረንድ ጄሪ ፋልዌል የሚመራ የወንጌላውያን ቡድንና የቀድሞው ፕሬዚዳንታዊ እጩ ተወዳዳሪ ጋሪ ባውር ለቡሽ ደብዳቤ ጽፈው ሻሮን ከምዕራባዊው ዳርቻ እንዲወጡ ጫና እንዳያደርጉባቸው ጠይቀዋቸዋል። ተከታዮቹ ተመሣሣይ ነገር እንዲያደርጉ ፋልዌል ባቀረበው ተማጽኖ መሠረት ዋይት ሃውስ በስልክና በኢ-ሜይል መልዕክቶች ተጨናነቀ። በቀጣዩ ቀን የተለያዩ ምንጮች እንዳስታወቁት የፕሬዚዳንቱ ሲኒዩር ረዳቶች ለፋልዌል ደውለው ቡሽ ከሻሮን ጎን መቆማቸውን አረጋገጡለት››[34]

ፕሬዚዳንት ቡሽ አቋማቸውን መቀየራቸውን ካሳበቁባቸው ውጫዊ መገለጫዎች ውስጥ በዚያው ዕለት ማለትም ሚያዝያ 11 ቀን (ሻሮን

ጦራቸውን በኃይል ከያዟቸው የፍልስጤም ግዛቶች ማስወጣት አለባቸው በማለት በሞገቱ በሳምንቱ) አሪ ፍሌሸር እንዲህ ብሎ ነበር፡- ‹‹ቡሽ፣ ፕሬዚዳንት ሻሮን የሰላም ሰው ናቸው የሚል እምነት አደረባቸው፡፡››[35] ቡሽ ይህን እምነታቸውን ሚያዝያ 18 ቀን ማለትም ፓወል የመካከለኛው ምሥራቅ ተልዕኮአቸው ተጨናግፎ በተመለሱበት ዕለት ነበር ለሪፖርተሮች የገለጹት፡፡ ሻሮን ለእርሳቸው ጥሪ በአርኪ ሁኔታ መልስ በመስጠት በፍጥነትና ሙሉ በሙሉ ከያዙት አካባቢ መውጣታቸውን ተናገሩ፡፡[36] ሆኖም ግን ሃቁ ከዚህ በተቃራኒው ነበር፡፡ ሻሮን መውጣት ይቅርና ሊወጡ እንደሚችሉ እንኳ ምልክት አላሳዩም፡፡ ቡሽ ጉዳዩን ዳግም ለማንሳት አለመፈለጋቸው ግልጽ ነበር፡፡ እስራኤል ብቀላዋን ማጠናቀቋን ሚያዝያ 21 የገለጸች ቢሆንም፣ አጥቂ ጦሯ በብዙ የፍልስጤማውያን መሬቶች ላይ እንደሰፈረ ነበር፡፡

በሎቢው ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ቡድኖችም ግፊት ማድረጋቸውን አጠናክረው ቀጠሉ፡፡ የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስና ዩናይትድ ጀዊሽ ኮሚቴ ሚያዚያ አጋማሽ ላይ የተካሄደውን ስብሰባ (ሰልፍ) አስተባበሩ፡፡ በዚያ ሰልፍ ላይ አርሚ፣ ናታንያሁ፣ ዙከርማን' በኮንግረሱ የአናሳዎቹ መሪ ሪቻርድ ጌፓርትድና ሌሎች ዋና ዋና የመንግሥት ባለሥልጣናት ተገኝተዋል፡፡ ምክትል የመከላከያ ሚኒስትሩ ፓወል ዎልፎዊትዝ በሰልፉ ላይ ባሰሙት ንግግር ስለፍልስጤማውያን ስቃይና ስለሚመሠረተው የፍልስጤም መንግሥት በጠቀሱ ጊዜ ሰልፈኛው ‹‹አረፋት ይውደሙ!›› በማለት ተቃሞውን በጩኸት አሰማ፡፡ የአሜሪካ ጽዮናውያን ማህበር (ዚድ.ኦ.ኤ) ዋና ሥራ አስኪያጅ ሞሮቶን ክሌይን፣ ‹‹ቡሽ መልእክቱ ደርሷቸው በእስራኤል ላይ ጫና ማድረጋቸውን የማያቆሙ ከሆነ በዚህ ሰልፍ የሚገኘው ታላቅ እድል አመለጠ ማለት ነው›› አሉ፡፡ ለተሰበሰበው ሕዝብ ምላሽ የሰጡት ስማቸው ያልተገለጸ የመንግሥት ባለሥልጣን፡- ‹‹የፖሊሲ መሠረቱ ብዙ ሕዝብ የሚደግፈው መሆኑ አይደለም›› በማለት ተናገሩ፡፡ ሆኖም እኒሁ ባለሥልጣን ‹‹ከአይሁዳውያን መሪዎች ብዙ ሰምተናል፡፡ ይሁንና ይህ የአይሁዳውያን ሰልፍ የበለጠ ይናገራል፡፡›› በማለት ሁኔታውን እንደሚገነዘቡት ገለጹ፡፡[37]

በዚያው ሰዓት ኮንግረስ ሻሮንን ለመደገፍ እየተንቀሳቀሰ ነበር። ሚያዝያ አጋማሽ ላይ ናታንያሁ ካፒቶል ሂልን በመጎብኘት በዚያ ከሚገኙ አርባ የሚሆኑ ሴናተሮች ጋር ተገናኝተው መከሩ።[38] ግንቦት ሁለት ቀን ኮንግረሱ የመንግሥቱን ተቃውሞ ችላ ብሎ ለእስራኤል ያለውን ድጋፍ (በሴኔቱ ውስጥ 94 ለ2፣ በተወካዮቹ ምክር ቤት ደግሞ 352 ለ21) በሆነ ድምፅ አረጋገጠ። በሁለቱም ምክር ቤቶች የተላለፉት ውሳኔዎች ‹‹ዩናይትድ ስቴትስ ከእስራኤል ጋር በአንድነት ትቆማለች!›› ከሚል የአቋም ማጠናከሪያ መግለጫ ጋር ነበር የቀረቡት። እንዲሁም፣ ‹‹ሁለቱ ሀገራት ሽብርተኝነትን ለመዋጋት በጋራ ይቆማሉ› ያሲር አረፋት እያራመዱት ያለውን የሽብር ጥቃትም እናወግዛለን” የሚሉትንም የተወካዮች ምክር ቤት አቋሞች መግለጫዎቹ አካትተዋል።[39]

ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሁለቱም የኮንግረስ ክፍሎች የተውጣጣው የጋራ የእውነት አፈላላጊ ቡድን ወደ እስራኤል ተጓዘ። ቡድኑ ባወጣው መግለጫ ሻሮን (ያኔ ከቡሽ ጋር በዋሽንግተን ውስጥ ተሰብስበው ነበር) ከአረፋት ጋር እንዲደራደሩ የአሜሪካ መንግሥት የሚያሳድርባቸውን ጫና እንዲቋቋሙ ጠየቀ።[40] ከዚያም ግንቦት 9 ቀን በተወካዮች ምክር ቤት የእርዳታ በጀትን የሚያደላድለው ንዑስ ኮሚቴ እስራኤል ሽብርተኝነትን የምትከላከልበትን አቅሟን ታጠናክር ዘንድ ተጨማሪ 200 ሚሊዮን ዶላር ሊሰጣት ወሰነ። ዋይት ሃውስ የኮንግረሱን አቋም ተመቃወመ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ኮሊን ፓወልም ከኮንግረሱ መሪዎች ጋር በመምከር ውሳኔውን ለማስቀልበስ ጥረት አደረጉ። ይሁን እንጂ ሎቢው መጀመሪያውኑ ሁለቱ የኮንግረሱ ክፍሎች እንዲደግፉት አድርጎ ስለነበር የፓወል ጥረታት ሳይሳካ ቀረ። ቡሽም ያለፍላጎታቸውም ቢሆን የተባለው ገንዘብ ለእስራኤል እንዲሰጥ በመስማማት ፊርማቸውን አኖሩ።››[41]

በእንዲህ ዓይነት አኳኋን ነበር ሻሮንና ሎቢው በዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚዳንትና በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ላይ ድል የቀዳጁት። ‹ማአሬቭ› በተባለው የእስራኤል ጋዜጣ ላይ የምትሠራው ቺሚ ሻሌቭ፣ ‹‹ሻሮን ባገኙት ድል የተሰማቸውን እርካታ በተሸናፊው ፓወል ፊት እንኳ ሊደብቁት አልፈለጉም።›› ብላለች። የቡሽ ሽንፈት በእርግጥም በመላው ዓለም በሚገኙ

የፖለቲካ ተንታኞች ዘንድ ፈጽሞ የሚዘነጋ አልነበረም። የስፔኑ ዕለታዊ ጋዜጣ ‹ኤልፓኦስ› የውጭ አስተየዬት ሰጭዎችን ሀሰብ ካሰባሰበ በኋላ ድምዳሜውን እንደሚከተለው አቅርቦ ነበር፦ ‹‹የአንድ ሀገር ክብደት የሚመዘነው በክስተቶች ላይ በምታሳድረው ተጽዕኖ ከሆነ ልዕለ ኃያሏ ዩ.ኤስ. አሜሪካ ሳትሆን እስራኤል ናት።››[42] ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ ጥልፍልፎሽ በበዛበት የፖለቲካ ጨዋታ የድሉ ባለቤት ሻሮን ወይም እስራኤል ሳይሆኑ፣ ዩናይትድ እቴትስ ውስጥ ያሉት አፍቃሪ እስራኤል ሎቢስቶች መሆናቸው መታወቅ አለበት፡

“የነገሮች ይበልጥ እየተቀየሩ መሄድ...”

ይህ ሁሉ መሰናክል እንዳለ ቢሆንም፣ ቡሽ ሁለተኛውን ኢንቲፋዳ ለማብቃትና ከእስራኤል ጋር በሰላም ለመኖር የፈቀደ የፍልስጤማውያን መንግሥት ለመመሥረት የሚያደርጉትን ጥረት ቀጠሉ። በእርሳቸው እምነት የአረብ እስራኤልን ግጭት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መፍታት የአሜሪካ ብሔራዊ ፍላጎት እንደሆነ ይሰማቸው ነበር። ይሁን እንጂ ቡሽ ያንን ዓላማቸውን ለማሳካት አልታደሉም። ለዚህም በዋነኛነት እንደምክንያት የሚጠቀሰው ከ2002 ጀምሮ በእርሳቸውና በእስራኤል ሎቢ መካከል የነበረው የኃይል አለመመጣጠን ነው። ያ ሁኔታ የእስራኤል መሪዎች ቡሽ የሚያራምዷቸውንና እነርሱን የሚያስደስታቸውን የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲዎች ችላ እንዲሉ ወይም ዋጋ እንዲያሳጧቸው የሚያደርግ የተጽዕኖ ኃይል አቀዳጅቷቸዋል።

ቡሽ ያካበቧቸውን በርካታ ችግሮች ወደጎን ብለው ሰኔ 24 ቀን 2002 ላይ መካከለኛው ምሥራቅን የሚመለከት ንግግር አደረጉ።[43] ያ ንግግራቸው በሁለት ምክንያቶች ጠቃሚ ነበር ማለት ይቻላል። የመጀመሪያው አራፋት የሰላም ንግግሩ ወደፊት ከመራመዱ በፊት ሥልጣናቸውን መልቀቅ ያለባቸው መሆኑን የሚያሳስብ መሆኑ ነው። ‹‹ሰላም›› አሉ ቡሽ ‹‹አዲስና የተለየ የፍልስጤማውያን የፖለቲካ መሪ ማግኘት ትፈልጋለች።›› የቡሽ ንግግር ያመጣውን ውጤት የሃ› ኤሬትዙ ዶቪድ ሲገልጽ፦ ‹‹ዘላለማዊ

የፍልስጤማውያን ብሔራዊ ንቅናቄ መሪ እንደሆኑ በሚታሰቡት ያሲር አረፋት ላይ የተፈጸመ ፖለቲካዊ ግድያ ነበር›› ብሎታል::[44] አራፋት እንዲገለሉ ለወራት ሲጠይቁ ለነበሩ እስራኤላውያን ሁኔታው የሚያስፈነድቅ ነበር:: እርግጥ ነው ቡሽ በንግግራቸው ውስጥ የአረፋትን ከፖለቲካው መድረክ ዘወር የማለት አስፈላጊነት እንዲያካትቱ ያደረጓቸው ናታን ሻረንስኪና ቤንጃሚን ናታንያሁ ሲሆኑ፣ ሁለቱም ተጽዕኖ ፈጣሪና የወግ አጥባቂው ፓርቲ አባላት ነበሩ::[45] ሃ ‹ኤሬትዝ በዚህ ጉዳይ ላይ ‹‹አሪዮል ሻሮን ከራሳቸው ሀሳብ ጋር ተስማሙ›› በሚል ርዕስ ሥር ሃተታውን አቅርቧል::[46]

ሁለተኛው፣ ቡሽ የፍልስጤማውያንን መንግሥት በ2005 ለመመሥረት ጥሪ ማቅረባቸው ነው:: ዓላማቸውንም ለማሳካት በኃይል በተያዙት ግዛቶች እስራኤል የምታደርጋቸው የሰፈራ ግንባታዎች የግድ መቆም እንዳለባቸው ገለጹ:: ከዚያ በኋላ የፀጥታው ሁኔታ መሻሻል ካሳዩ የእስራኤል ወታደሮች ከመስከረም 28/2000 በፊት ወደነበሩበት (ሁለተኛው ኢንቲፋዳ ሲጀመር ይዘውት ወደነበረው) ሥፍራ እንዲያፈገፍጉ ይደረጋል:: ቡሽ በሰፊው ትችት የሚቀርብባቸው በጊዜው የእስራኤል ኃይሎች የሚሠፍሩበትና ፍልስጤማውያንም የሚረከቡት መሬት ከየት እስከየት እንደሆነ ቁርጥ አድርገው አለመናገራቸው ነው::[47] ምንም እንኳን ቡሽ የወደፊቱን ስምምነት አስመልክተው ያደረጉት ንግግር ብዙም ግልጽ ባይሆንም፣ ጠቃሚ እንደነበር ግን አይካድም:: የቡሽ አስተዳደር ‹‹ሮድ ማፕ›› እየተባለ የሚጠራውንና በእስራኤልና ፍልስጤማውያን መካከል ስምምነት እንዲኖር የሚያስችለውን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ በጊዜው ከአውሮፓ ሕብረት፣ ከሩሲያና ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጋር በቅርበት ሠርቷል:: ‹‹አራትዮሽ›› የተባለው ቡድን በተለየ ሁኔታ በቡሽ ንግግር ውስጥ ከተጠቀሱት ዋና ዋና ጉዳዮች የተውጣጡ አላባዎችን በመቀነስ ዕቅዱን ነደፈ::

የቡሽ አስተዳደር በ2002 በጋ ላይ ‹‹ሮድ ማፕ›› የእስራኤል -ፍልስጤምን ችግር ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የማስወገጃ ምርጥ መንገድ መሆኑን በመወሰን ይፋ አደረገ። እንደዚያም ቢሆን እስከ 2003 ፀደይ ወራት ድረስ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የተሠራው ትንሽ ብቻ ነበር። የመዘግየቱ ዋነኛ

ምክንያት እንደሆነ የተጠቀሰው አራፋትን ከሥልጣን መንበር ዘወር እንዲሉ ለማድረግ የማሳመኑ ሂደት ጊዜ የሚወስድ መሆኑና የአራትዮሹ ቡድን በሮድ ማፑ ዝርዝር ይዘቶች ዙሪያ የሚሠራቸው በርካታ ተግባሮች ስለነበሩ ነው። በተጨማሪም የቡሽ አስተዳደር ከኢራቅ ጋር ለሚደረገው ጦርነት ዝግጅት በማድረግ ሥራ ላይ ተጠምዶ የነበረ በመሆኑም ጭምር ነው። በመጨረሻም ሮድ ማፑን አስመልክቶ ጠንከር ያሉ እንቅስቃሴዎች የተጀመሩት መጋቢት 7 ቀን፣ ማለትም አራፋት ሥልጣናቸውን በመቀነስ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርገው ለሾሟቸው ማህሙድ አባስ እንደሚሰጡ ምልክት ባሳዩ ጊዜ ነበር።[48] ይህ ከሆነ ከሳምንት በኋላ መጋቢት 14 ቀን ቡሽ ሮድ ማፑን ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ይፋ አደረጉ። ሚያዝያ 30 የአራትዮሽ ቡድኑ የዚያን የሰላም እቅድ ዝርዝር ሁኔታ ገለጸ።[49]

በሰኔ ወር መጀመሪያ ላይ ፕሬዚዳንቱ የሮድ ማፑን ሂደት ለማነቃቃት ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በመሄድ የማህሙድ አባስ ሥልጣን ከአራፋት ይልቅ ጠንካራ እንደሆነ ለማሳየት ጥረት አደረጉ። በጊዜው ቡሽ ሳዳምን ከሥልጣን ማባረር የመቻላቸው ስኬት ያነናጸፋቸው ክብር ሰማይ ደርሶ ነበር። ተልዕኮአቸውን በድል ማጠናቀቃቸውን አስመልክተው ‹ዩ.ኤስ.ኤስ. አብረሃም ሊንከን› በተባለችው መርከብ ላይ ግብዣ ያደረጉ ሲሆን፣ ከጦርነቱ በኋላ ኢራቅን መልሶ የመገንባት ሂደት እንደሚጀመርም ይፋ አድርገዋል። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የተነሳ አሜሪካ ውስጥ የነበራቸው ተቀባይነት ማደጉ በሪከርድ ደረጃ ተመዝግቧል። ስለሆነም ሁለቱንም ወገኖች እንደልባቸው ለመጫንና የሰላሙን ሂደት ለማራመድ የሚያስችላቸው የፖለቲካ ክንድ ማግኘታቸው ግልጽ ነበር። በመጀመሪያ ደረጃ የአረብ መሪዎችን ግብጽ ላይ ካነጋገሩ በኋላ በቀጣዩ ቀን አባስንና ሻሮንን አቀባ በተባለችው የዮርዳኖስ ከተማ አግኝተው አወያዩ። ይሁን እንጂ ጉዞውን ከማድረጋቸው በፊት እስራኤል የሰላሙን ሀሳብ እንድትቀበል ቡሽ ጫና ሊያደርጉባት በመቻላቸው ላይ ሪፖርተሮች ጥርጣሬ ነበራቸው። ምክንያቱም የሁለተኛ ፕሬዚዳንታዊ ዘመን ምርጫ 2004 ላይ ስለሚደረግ ተጽዕኖ እንዳያመጣባቸው በመስጋታቸው ነው። ለዚህ የሪፖርተሮች የስጋት ጥያቄ ቡሽ መልስ ሲሰጡ ‹‹እንዴታ፣ ጫና አደርጋለሁ እንጂ›› ካሉ በኋላ

አያይዘውም፣ ‹‹አድምጡኝ ክቡራን! ፖለቲካዊ ጫና በማድረግ ወደፊት ለመንዝ ባልወስን ኖሮ፤ ወደዚያ አልሄድም ነበር ›› በማለት ተናገሩ።[50]

ቡሽ ከሁለቱም አካላት ጋር ያደረጉት ስብሰባ ሞቅ ያለና የሰላሙን ሂደት በቀጥታ ለማነቃቃት የመቻላቸው ጅማሮ መስሎ ነበር። ይሁን እንጂ ሮድ ማፕ የትም አልደረሰም። ምክንያቱም ሻሮን አልፎ አልፎ ከአራቱ የሰላሙ ሂደት ተጓዳኞች ጋር በዕቅዱ ዙሪያ ከመነጋገራቸው ውጭ የፍልስጤማውያን መንግሥት መቋቋሙን በግልጽ በመቃወማቸውና ከፍልስጤማውያንም ጋር ስምምነት ማድረጉ የኋላ ኋላ በኃይል በተያዙት መሬቶች ላይ የፍልስጤምን መንግሥት ለማቋቋም የታለመ እስከሆነ ድረስ በዚያ ድርድር የመሳተፍ ፍላጎት ስላልነበራቸው ነው። ሻሮን ሮድ ማፕን በግልጽ እንደሚቃወሙት ከመጋቢት 2003 በፊትም ይታወቅ ነበር። ዋሽንግተን ፖስት በታህሣሥ 16/2002 እትሙ ርዕሰ አንቀጽ ላይ የሚከተለውን አስፍሮ ነበር፡- ‹‹....ምንም እንኳን ሻሮን ለመራጮች የቡሽን የሰላም ሀሳብ ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውን ቢገልጹም፤ የእርሳቸው ልዑካን ቡድን አባላት ግን ከአሜሪካ አቻዎቻቸው ጋር በተገናኙ ጊዜ የሮድ ማፕን ረቂቅ በኃይል ነበር የተቃወሙት። በእስራኤል የፕሬስ ሪፖርት መሠረት ሚስተር ሻሮን በቅርቡ በተደረገው የካቢኔ ስብሰባ ላይ የቡሽ አስተዳደር ያቀረበውን የሰላም ዕቅድ ‹የማይረባ› በማለት አጣጥለውታል።››[51]

መጋቢት 2003 ላይ ቡሽ ሮድ ማፕን ተግባራዊ ማድረጉን እንደሚገፉበት በተናገሩ ጊዜ ሻሮን በይፋ ምንም ነገር ለመናገር አልፈለጉም። የዝምታቸውም ዋነኛ ምክንያት ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅን ለመውረር እየተዘጋጀች ባለችበት ሁኔታ ቡሽን ለመተቸት ስላልፈለጉ ነበር። የሆነ ሆኖ ሻሮን በዕቀዱ ላይ የነበራቸው አመለካከት አልተቀየረም። ቺሚ ሻሌቭ በፎርዋርድ ጋዜጣ ላይ ባወጣችው መጣጥፍ፣ ‹‹የሻሮንና የአማካሪዎቻቸው ስትራቴጂያዊ ዒላማ በዋነኛነት ሮድ ማፕን ለመሸርሸርና ከዩ.ኤስ.አሜሪካ ጋር በአራትዮሽ የአስታራቂ ቡድን (Madrid Quarter) ውስጥ ያሉትን ሶስቱን (የአውሮፓ ሕብረትን፣ ሩሲያንና የተባበሩት መንግሥታትን) በሂደቱ ላይ ጉልህ ሚና እንዳይኖራቸው ማድረግ ነው ›› በማለት ተችታለች።[53] ሚያዝያ አጋማሽ ላይ የወጣው ሃ› ኤፊቴዝ ጋዜጣ ደግሞ በርዕሰ አንቀጹ

ላይ ባሰፈረው ጽሑፍ ‹‹ሻሮን የሰላም ስምምነት ይደረግ ዘንድ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማሟላት ዝግጁ አልነበሩም፡፡ በግልጽ እንደሚታየው የሰፈራ መንደር ግንባታቸውን ለማቆምም ሆነ የምዕራቡ ዳርቻ ከእስራኤል ቁጥጥር እንዲወጣ አይፈልጉም›› ብሏል፡፡[54]

ሻሮን ለሮድ ማፕ ያላቸውን ተቃውሞ ስናስብ ሞርትማየር ዙከርማንን የመሰሉና በሎቢው ውስጥ ያሉ ቁልፍ ድርጅቶችን በበላይነት የሚያንቀሳቅሱ ሰዎች የቡሽን ዕቅድ ‹‹የትም የማያደርስ›› ብለው በመጥራታቸው ላንደነቅ እንችላለን፡፡[55]

መጋቢት 14 ሮድ ማፕን ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ቡሽ በገለጹ በሰዓታት ጊዜ ውስጥ ብሔራዊ የፀጥታ አማካሪያቸው ኮንዶሊዛ ራይስ በዋይት ሐውስ ከአይሁዳውያን መሪዎች ጋር ስብሰባ ተቀመጡ፡፡ ሃ› ኤሬትዝ ጋዜጣ ላይ የሰፈረ አንድ ጽሑፍ እንዳተተው ‹‹የስብሰባው ዓለማ የአሜሪካ አይሁዳውያን ለሮድ ማፑ የሚያሳዩትን ገለልተኝነት ወይም ቁጥብነት ለመስበር ነበር” ብሏል፡፡[56] ይሁን እንጂ በዚያ ጽሑፍ እንደተጠቀሰው ‹‹ራይስ በዚያ ስብሰባ ላይ የተገኙትን ተሳታፊዎች ሃሳብ ሊያገኙት አልቻሉም ነበር፡፡›› በተለይ የኤ.ዲ.ኤል. የበላይ አብርሃም ፎክስማንና የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ማልኮለም ሆኔሊን አሳሳቢ ነበሩ፡፡ ምንም እንኳን ሆኒሊን የሮድ ማፕን ዕቅድ በተመለከተ እርምጃ ለመውሰድ የእስራኤልን አቋም መጠበቅ ያስፈልጋል ባይ ቢሆኑም፣ በጉዳዩ ይበልጥ በመግፋት በአጽንኦት እንደተናገሩት ‹‹እስራኤል ቁጥብነትን ወይም ገለልተኝነትን ከመረጠች የአይሁድ ማህበረሰብ የእስራኤልን አቋም ይደግፋል››

አይፓክ በበኩሉ በካፒቶል ሂል ያሉ የኮንግረስ አባላትን ፊርማ የያዘ ደብዳቤ ለፕሬዚዳንት ቡሽ በመላክ እስራኤል ሮድ ማፕን እንድትቀበል ጫና እንዳያደርጉና ማንኛውንም ስምምነት ከማድረጓ በፊት ፍልስጤማውያን እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የፀጥታ አጠባበቅ ሥርዓትን እንዲያሰፍኑ ጠየቀ፡፡ በዚህ ደብዳቤ ላይ 85 ሴናተሮችና 283 የተወካዮች ምክር ቤት (ኮንግረስ) አባላት ፊርማቸውን አኑረዋል፡፡[57] አይፓክ በመጨረሻ ሮድ ማፕን የተቀበለው ሲሆን፣ እቅዱን በግልጽ የተቃወሙ በሎቢው

ውስጥ የሚገኙ ቡድኖችም ነበሩ።[58] በርካታ አፍቃሪ እስራኤል ሀተታ አቅራቢዎች የቡሽ አስተዳደር የሮድ ማፕን እቅድ ወደፊት ለማራመድ ያደረገውን ግፊት ክፉኛ ተችተዋል። ለምሳሌ ቻርለስ ክራውታመር በዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ ላይ፣ ‹‹አራፋት ሥልጣን ላይ እያሉ የሮድ ማፕን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ መሞከር ራስን በራስ የማጥፋት ሂደት ነው›› በማለት ጽፏል።[59] የኒው ዮርክ ታይምሱ ቶማስ ኤል ፍሪድማን ግን ዋና ዋና የሚባሉት የአይሁድ ድርጅቶች የሰላሙን ሀሳብ ባለመቀበላቸው ተችቷቸዋል።[60] የሰላሙን መንገድ ከሚያራምዱትና ቲኩን ኮሚዩኒቲ እና እስራኤል ፖሊሲ ፎረም ከተባሉት ቡድኖች በተጨማሪ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው አፍቃሪ-እስራኤል ቡድኖች ብቻ ናቸው የሮድ ማፕን ዕቅድ ሞቅ ባለ ስሜት የደገፉት። ይህ የሚያሳየው እቅዱ ለወደፊቱ ጥሩ እድል እንደማይገጥመው ነው።

በመሆኑም ሚያዝ4ያ 30 ላይ ዝርዝር አፈጻጸሙ ይፋ የተደረገው ሮድ ማፕ ለእስራኤል ጠላር መስመረኞች ብዙም ደንታ አልሰጣቸውም። በቀጣዩ ቀን ሃ-ኤሬታዝ ጋዜጣ ላይ በወጣ አስተያየት ብራድሊ በርስተን ‹‹እነዚህ ሰዎች አቋማቸው ይህ ከሆነ ፈገግ የሚሉት ለምንድን ነው?›› በማለት ይጠይቃል።[61] መልሱ የቡሽ አስተዳደር ከሻሮንና ከወታደራዊ አዛገኖቻቸው ጋር ባደረገው ተከታታይ ውይይት የሰላሙን እቅድ አስመልክቶ ያላቸውን ስጋት በተመለከተ የጋራ መግባባት ላይ በመድረሳቸው ነው።[62] ፋይናንሽያል ታይምስ ባቀረበው ሪፖርት ‹‹ኢሊዮት አብራምስና ስቴፈን ሃድሊ የተባሉ ሁለት የቡሽ ብሔራዊ ፀጥታ ምክር ቤት ቁልፍ ሰዎች ሮድ ማፕን አስመልክቶ ከዩ.ኤስ. አሜሪካ በኩል ምንም ዓይነት ጫና እንደማይደርስባቸው ለሻሮን አረጋግጠውላቸዋል›› ብሏል።[63]

አሁንም ቢሆን ቡሽ ሰኔ 2003 ላይ መካከለኛው ምሥራቅን ከጎበኙ በኋላ ጉብኝቱ የሰላሙን እቅድ አንድ እርምጃ ወደፊት ማስጠጋቱ ስለማይቀር ሻሮን መጨነቃቸው የግድ ነበር። ቡሽ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ከተመለሱ ከጥቂት ቀናት በኋላ እስራኤል ከሃማስ ቁልፍ መሪዎች አንዱ የሆኑትን ለመግደል ያልተሳካ ሙከራ አደረገች። ይህ የግድያ ሙከራ በአምስት ቀን ውስጥ ከተደረጉ ሰባት የግድያ ሙከራዎች የመጀመሪያው ነበር።[64] ሻሮን ከዚያ በኋላ በጉዳዩ ዙሪያ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮሊን ፓወል ጋር

ባደረጉት ንግግር በሽብር ጥቃት እጃቸው በሌለ ሰዎች ላይ እንዲህ ዓይነት ግድያ ከእንግዲህ እንደማይፈጸም ቃል ገቡላቸው።[65] የሚገርመው ነገር ሃማስ ከዚህ የግድያ ሙከራ አንድ ቀን ቀደም ብሎ የተኩስ አቁም ውሉን ለማደስ መነጋገር እንደሚፈልግ ይፋ አድርጎ የነበረ መሆኑ ነው።[66] ከዚያም በተጨማሪ ፎርዋርድ ጋዜጣ እንደዘገበው በአቀባ (ዮርዳኖስ) በተደረገው የማስማሚያ ስብሰባ ወቅት ሻሮን ልምድ አልባ የሆኑትን የፍልስጤም ጠቅላይ ሚኒስትር የሚያውክ ማንኛውንም ጠብ ጫሪ ድርጊት ለማስወገድ ተስማምተው ነበር።[67] አስተያየት ሰጭዎች እንደሚያምኑት የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ድርጊቶች የሚያሳዩት ሰውዬው የሮድ ማፕን ዕቅድ ከባሕር በታች ለመጣል ማሰባቸውን ነው። ‹‹የሃማስን ቁልፍ አባላት ለመግደል የተጀመረው ንቁ ዘመቻ›› ይላል ሃ›ኤሪትዝ ጋዜጣ፡- ‹‹በእስራኤል በኩል በሚገባ የታሰበበት ነበር።››[68]

የሆነ ሆኖ በነገሮች አካሄድ ቡሽ አልተደሰቱም። ስለሆነም ሰኔ 10 ላይ ‹‹እስራኤል በቅርቡ እያካሄደችው ባለው የሄሊኮፕተር ግድያ ተረብሼያለሁ›› በማለት ለስለስ ባለ ሁኔታ ሻሮንን ወቀሱ። ዋሽንግተን ፖስት እንዳለው የቡሽ ወቀሳ መካከለኛና በጠንካራ ቃላት ያልታጀበ ቢሆንም፣ በሎቢው ውስጥ ያሉት ጠጣር መስመረኞች (Hard Liners) እስራኤልን አስመልክቶ ለስለስ ያለ ወቀሳ እንኳ እንዲደረግ ስለማይፈልጉ ቡሽ አቋማቸውን እንዲያስተካክሉ ለማድረግ እንቅስቃሴያቸውን ጀመሩ። ቶም ዴላይ ከቡሽ ረዳት ጋር በግል ከተገናኙ በኋላ ‹‹ቡሽ እስራኤልን መንቀፋቸውን የሚቀጥሉ ከሆነ ኮንግረሱ ለእስራኤል ያለውን ድጋፍ የሚያሳይ ውሳኔ እንዲያሳልፍ አደርጋለሁ›› በማለት አቋማቸውን ግልጽ አደረጉ። ሰኔ 11 ቀን ምሽት ላይ ቡሽ የሆሎኮስት ማስታወሻ ሙዚዬምን መከፈት አስመልክቶ አንድ መቶ ከሚሆኑ የአይሁድ መሪዎች ጋር ራት በሉ። በዚያ ምሽት ቡሽን በግል ለማነጋገር እድል ያገኙት ማልኮለም ሆኒሊን ፕሬዚዳንቱና በዋይት ሐውስ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ባለሥልጣናት ድርጊታቸው ገንቢ ሊሆን እንደሚገባ መገንዘባቸውን ተናገሩ። ሕዝቡ በተሰጡት አስተያየቶች ቅር መሰኘቱንና ዋይት ሐውስም ይህን ይገነዘባል ብለው እንደሚያምኑ በመግለጽ ሐሳባቸውን አጠቃለሉ።[69]

በቀጣዩ ቀን ሰኔ ላይ ዋይት ሐውስ አቋሙን ሙሉ በሙሉ መቀየሩንና የእስራኤል ጽኑ ደጋፊ መሆኑን አሳወቀ። ዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ ባወጣው ዘገባው "ዋይት ሐውስና ሌሎች ባለስልጣናት የዲኘሎማሲ ትኩረታቸውን ከእስራኤል ድርጊት አንስተው፣ የዓረብ መሪዎች እስራኤልን ለሚያጠቁ አሸባሪዎች ምንም ዓይነት ገንዘብ ድጋፍና እርዳታ እንደማያደርጉላቸው በገለጹበት የባለፈው ሳምንት የግብጽ ስብሰባ ላይ አተኮሩ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮሊን ፓወል የአረብ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮችን ሁሉ በዚያ ስብሰባ ላይ እያሉ በስልክ በማነጋገር አዲሱን እርምጃቸውን መደገፋቸውን ገልጸዋል።" ብሏል።[70] የዋይት ሐውስ ፕሬስ ጸሐፊ አሪ ፍሌሸር እንዲህ ይላሉ፡- "ዋናው ጉዳይ ያለው ከእስራኤል ጋር አይደለም። አሸባሪዎች ናቸው የሰላሙን ሃሳብ ለማደናቀፍና ወደፊት እንዳይራመድ ለማድረግ ንፁሐኑን እየገደሉ የሚገኙት"[71] በዚያው ወር የኮንግረሱ የተወካዮች ምክር ቤት 399 ለ5 በሆነ ድምፅ እስራኤል ሽብርተኞችን የመዋጋት ተገቢ የሆነ ምክንያት እንዳላት ገልጿል።[72]

ቡሽ በአረቡና በሙስሊሙ ዓለም ጸረ-አሜሪካ ስሜት የቀሰቀሰውን የእስራኤልን ድርጊት ለመግታት ያደረጉት ሙከራ በመክሸፉ በፀረ-ሽብርተኝነት ዘመቻቸው ላይ ታላቅ ውድቀት ያስከተለባቸው ከመሆኑም ተጨማሪ ውርደትንና ሽንፈትን በማስተናገድ ነበር ትግላቸውን ያሳረጉት።[73]

ለሮድ ማፕ የአንድ ወገን ድጋፍ

ተመሣሣይ የሆነ አጋጣሚ የተከሰተው ሐምሌ 2003 ላይ የቡሽ አስተዳደር የእስራኤልን የደህንነት አጥር ግንባታ ተቃውሞ ድምፁን ባሰማ ጊዜ ነበር፡፡ ይህ የእስራኤል እርምጃ በሁለቱ ተቀናቃኝ ክፍሎች መካከል እንዲሰፍን በሚጠበቀው የሁለት መንግሥታት ምሥረታ የሰላም ሂደት ላይ ትልቅ ጋሬጣ ሆኖ ብቅ አለ፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ የግምብ አጥር ከማነጽም በላይ ርቆ የሚሄድ፣ በተግባር ሲፈተሽ በኃይል ከተያዘው የምዕራቡ ዳርቻ ተጨማሪ የፍልስጤማውያንን መሬት ለመውሰድ ያለመና በሺዎች በሚቆጠሩ ፍልስጤማውያን ላይም ተጨማሪ አበሳን የሚያስከትል በመሆኑ ነው፡፡[74] ቡሽ ከፍልስጤማውያኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ማህሙድ አባስ ጋር ነሐሴ 25 ቀን በዋይት ሐውስ በሰጡት የጋራ ጋዜጣዊ መግለጫ ‹‹ይህ በምዕራቡ ዳርቻ የሚገነባ የግንብ አጥር በፍልስጤማውያንና በእስራኤላውያን መካከል ሊሰፍን የሚገባውን መተማመን የሚሸረሽርና ግንኙነታቸውን አስቸጋሪ የሚያደርግ መሆኑን ከአሪዮል ሻሮን ጋር ተነጋግሬበታለሁ›› አሉ፡፡[75] ዳሩ ግን ከሶስት ቀናት በኋላ ኦሪዮል ሻሮን ቡሽን በሁዋይት ሐውስ ከጎናቸው አቁመው የግንቡን አጥር እንደሚገፉበትና በተቻላቸው አቅም በፍልስጤማውያን ላይ የሚያደርሰውን መከራ ለመቀነስ እንደሚጥሩ ተናገሩ፡፡ ቡሽ በዚያ ጊዜ አሪዮል ሻሮንን አልነቀፉም፡፡ በዚያ ፋንታ የሻሮንን ሀሳብ እንደሚደግፉና የፍልስጤማውያን ሽብርተኝነት ለሰላሙ ሂደት ጋሬጣ እንዳይሆን መስጋታቸውን በመግለጽ ብቻ ተወሰኑ፡፡[76]

ይህም ሆኖ የቡሽ አስተዳደር የፀጥታ አጥር እየተባለ በሚጠራው ግንብ ላይ ያለውን ቅሬታ ከመግለጽ አልተቆጠበም፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮሊን ፓወል ባደረጉት አንድ ቃለ ምልልስ፡- ‹‹የግንቡ አጥር እስራኤል ተጨማሪ የፍልስጤማውያንን መሬት ለመቀማት የምታደርጋቸው ጥረቶች አካል ነው›› በማለት በድፍረት ተናግረዋል፡፡ ኮንዶሊዛ ራይስም በበኩላቸው በሚያዝያ ወር ለእስራኤል ሊሰጣት ከተወሰነላት የ9 ቢሊዮን ዶላር የብድር ዋስትና ላይ ለአጥሩ የሚውለውን ያክል ገንዘብ አስተዳደራቸው ሊቆርጥ

እንደሚችል ግልጽ አደረጉ።[77] በኮንግረሱ ውስጥ ያሉ የእስራኤል ደጋፊዎች ሀሳቡን ተቃውመው መንቀሳቀስ በመጀመራቸው ሴናተር ቻርለስ ስኩመር ‹‹ፕሬዚዳንቱ የኮንግረሱን ውሳኔ በማጠፍ እስራኤል ራሷን የምትከላከልበትን ዕቅድ እንዳትፈጽም ሊቀጧት ከወሰኑ ኮንግረስ ማንኛውንም ሁኔታ ተጠቅሞ የብድር ገንዘቡ ለእስራኤል እንዲለቀቅላት ከማድረግ አይመለስም›› በማለት አስፈራሩ።[78] ይሁን እንጂ እስራኤላውያን ራሳቸው በጉዳዩ ላይ ብዙ የተጨነቁ አልመሰሉም። አንድ ከፍተኛ የእስራኤል ባለሥልጣን የተሰማቸውን ሲናገሩ፡- ‹‹እኛ በአሁኑ ጊዜ ምንም ዓይነት ጫና የለብንም። …. ዩናይትድ ስቴትስ አንፀባራቂ የሆነ ዲሞክራሲ ያላት ሀገር እንደሆነች እናውቃለን። ይህ አስተዳደር በፖለቲካ ባሕል የሚመራ እንደመሆኑ መጠን አንዳንድ ጊዜ እውነታዎች የሚገለጹት የፖለቲካ ጫናዎች ሲኖሩ እንደሆነም እንገነዘባለን›› አሉ።[79]

የብድር ዋስትናው ጉዳይ የትም ወድቆ አልቀረም። የቡሽ አስተዳደር ሕዳር መጨረሻ አካባቢ በዚያ ዓመት ለእስራኤል ከሚለቀቅላት 3 ቢሊዮን ዶላር ላይ 289.5 ሚሊዮን ዶላር የሚሆነው ተቀንሶ እንዲሰጣት ወሰነ። ሎቢው ከዚያ በላይ ገፍቶ ለመከራከር አልፈለገም። ምክንያቱም በእስራኤል ላይ የተወሰነባት ቅጣት እውነቱን ለመናገር በእጅ አንጓ ላይ እንዳረፈ ደካማ ጥፊ ብዙም ለሕመም የማይዳርግ በመሆኑ ነው። ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል እንደ ስጋና ድንች የሚቆጠረውን ቁሳዊ እርዳታዋን ከማዝነብ አልተቆጠበችም። ከብድር ዋስትናው 10 በመቶ የሚጠጋ መጠን ብትቀንስ በእስራኤል ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ኢምንት ነው። ይህውም ከአጠቃላዩ የብድር ገንዘብ ላይ ቀላል የሆነ የወለድ መጠን ጭማሪ ብቻ ነው። የቀድሞው የእስራኤል የፋይናንስ ሚኒስትር እንደገመቱትም በያመቱ 4 ሚሊዮን ዶላር ወለድ መክፈል እስራኤልን ለመሰለ ሀብታም አገር ከባድ አይደለም።[80]

የቡሽ አስተዳደር በ2003 ማብቂያ አካባቢ አነስ ያለ ድል ተቀዳጀ። ይህ ሊሆን የቻለው ሻሮን አራፋትን ከምዕራባዊው ዳርቻ እንዲለቁ በማድረግ ከፍልስጤም ምድር አስወጥተው በግዞት ሊልኳቸው በፈለጉ ጊዜ ነበር። በዚያ ጊዜ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ኮሊን ፓወልና የብሔራዊ ፀጥታ ኃላፊዋ

ኮንዶሊዛ ራይስ የፍልስጤማውያኑን መሪ ከሀገር የማስወጣቱ ሀሳብ በዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ለእስራኤል ግልጽ አደረጉ። የእስራኤል መሪዎችም መልእክቱ ስለደረሳቸው አራፋት በምዕራባዊው ዳርቻ በራማላህ ቢሯቸው መቆየት ችለዋል።[81]

ሆኖም ግን ይህ አነስተኛ ድል የነገሮች አዝማሚያ መቀየሩን የሚያመለክት አይደለም። ከዚያ በተቃራኒ ሻሮን የቡሽን ሮድ ማፕ ዕቅድ ማፈራረስ በመጀመር የራሳቸውን የተናጠል እርምጃ ወስደው ከፍልስጤም መሬት (ከጋዛ) ወጡ።[82] ከዚያም በአሜሪካ የብሔራዊ ፀጥታ ምክር ቤት የመካከለኛው ምሥራቅና ሰሜን አፍሪካ ዋና ዳይሬክተር የሆነውን ታዋቂ የኒዎኮንሰርቫቲቭ አሳቤ አራማጅ ኢሊዮት አብራምስን ጋብዘው ሮም ከተማ ውስጥ ምስጢራዊ ስብሰባ አደረጉ። በዚያ ስብሰባ ላይ ሻሮን፣ አሜሪካዊ አይሁድ ባለሥልጣን ለሆነው ኢሊዮት አብራምስ በሮድ ማፕ ላይ የተጠቀሰውን በስምምነት የሚፈጸም ሠፈራ ወደጎን ብለው የራሳቸውን የሠፈራ ዕቅድ በፍልስጤማውያን መሬት ላይ ለመፈጸም ማቀዳቸውን አወጉት።[83] ይህ አዲሱ የሻሮን ፖሊሲ እንደሚያስረዳው በቀጣዮቹ ጥቂት ወራት እስራኤል በጋዛ ያላትን የሠፈራ መንደሮች ሁሉ በመልቀቅ ለፍልስጤማውያን ታስረክባለች። ከዚያም የተወሰኑ የምዕራቡን ዳርቻ ሥፍራዎች ትመልሳለች። ሆኖም ግን ሰፊና አወዛጋቢ የሆነውን የፍልስጤማውያን ምድር እንደያዘች ትቀያለች።

ሻሮን እነዚህን የተጠቀሱትን መሬቶች ለፍልስጤማውያን ለመመለስ የወሰኑት በፍልስጤማውያን ላይ በየጊዜው በሚደርስባቸው መከራና ስቃይ አዝነው አይደለም። ከዚያ ይልቅ እስራኤል ጋዛንና ሁሉንም ምዕራባዊውን ዳርቻ እንደያዘች ብትቀይ ‹‹ብታላቋ እስራኤል›› ውስጥ አረቦች አይሁዳዊያንን ብዙም ሳይቆዩ በቁጥር እንደሚበልጧቸው ስለተገነዘቡ ነው። በሌላ አባባል የጠቅላይ ሚኒስትሩን ፖሊሲ የሚዘውረው የሕዝብ ቁጥር ጉዳይ ነው ማለት ነው።[84]

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል በሻሮን ፖሊሲም ሆነ በአፈጻጸሙ ላይ ፍልስጤማውያን ምንም ነገር እንዲናገሩ ወይም እንዲያደርጉ እድል አልተሰጣቸውም። እስራኤል የአዲሱን አሠፋፈር ዕቅድና አፈጻጸም ከራሷ ፍላጎት አኳያ ብቻ በማስኬድ ፍልስጤማውያን የራሳቸው መንግሥት

እንዳይኖራቸው ነው የሻሮን ፍላጎት። ዶቭ ዊስግላስ የተባሉት የሻሮን የቅርብ አማካሪ እንደሚከተለው በማለት ሁኔታውን በግልጽ አስቀምጠውታል፡- ‹‹ከድርጊታችን ያገኘነው ዋነኛ ጥቅም .... የፖለቲካውን ሂደት ማቀዝቀዝ ነው። ያንን ሂደት ስታቀዘቅዘው የፍልስጤማውያን መንግሥት እንዳይመሠረት መከላከል ትችላለህ ማለት ነው። ይህ ማለት ደግሞ ስደተኞች ተመልሰው እንዳይገቡ፤ የድንበሩንና የኢየሩሳሌምን ጉዳይ አስመልክቶ ውይይት እንዳይካሄድ ማድረግ ቻልክ ማለት ነው፡፡ በአጠቃላይም ይህን ሁሉ ጉዳይ የያዘውን የፍልስጤማውያን መንግሥት የሚሰኘውን ማዕቀፍ ከአጀንዳህ ጨርሶ ማስወገድ ማለት ሌላ ሳይሆን ይኸው ነው፡፡›› ዊስግላስ ጨምረው ሲናገሩ፡- ‹‹የሻሮን ዕቅድ በእውነቱ የአስከሬን ማድረቂያ ፎርማሊን እንደማለት ነው፡፡ ለዚያ አካባቢ አስፈላጊ የሆነውን የፎርማሊን ግብዓት ታቀርባለህ፡፡ ከዚያ በኋላ በፍልስጤም ምድር ውስጥ የፖለቲካ ድርድር የሚባል ነገር አይኖርም›› ብለዋል፡፡[85]

ማንም ቢሆን ሻሮን በተናጠል በፈጸሙት በዚህ ድርጊት ቡሽ እንደሚናደዱ መገመት አይከብደውም፡፡ በተለይም ደግሞ የብሔራዊ ፀጥታ አማካሪዋን ‹‹ሮድማፕ በአካባቢው ዘላቂ ሰላም የሚያመጣ ብቸኛ መፍትሄ ነው››[86] የሚለውን እምነታቸውን ታሳቢ ስናደርግ ነገሩ እንደሚጦዝ መገመት እንችላለን፡፡ ይሁን እንጂ በትክክል የሆነው እንደዚያ አይደለም፡፡ በፀደይ ወር 2004 ቡሽ በይፋ የአሪዮል ሻሮንን የተናጠል እርምጃ (Unilateral Disengagement) ‹‹ድፍረት የተሞላበት የጀግና እርምጃ›› በማለት አወደሱት፡፡ ሻሮን ይህን እርምጃቸውን አጥብቀው እንዲገፉበት ሌላውም ዓለም ከምስጋና ጋር ማሳሰቡን ቀጠለ፡፡[87] ከዚያ በኋላ ቡሽ ሚያዝያ 14 ላይ ከሊንደን ጆንሰን ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውንና እያንዳንዱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሲከተለው የኖረውን ፖሊሲ በመቃረን እስራኤል በ1967 ከያዘቻቸው የፍልስጤማውያን ግዛቶች ሁሉ ለመውጣት እንደማትገደድ፣ ፍልስጤማውያን ስደተኞችም ወደቀድሞው መንደራቸው እንዲመለሱ እንደማይፈቀድላቸው፣ ከዚያ ይልቅ አዲስ በሚመሠረተው የፍልስጤማውያን መንግሥት እንደሚሰፍሩ ተናገሩ፡፡[88] ቀደም ሲል የነበረው የአሜሪካ ፖሊሲ በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ እስራኤልና

ፍልስጤማውያን ስምምነት ላይ ይደርሳሉ የሚል ነበር። ይህ የቡሽ አባባል በመካከለኛው ምሥራቅ ቁጣ የቀሰቀሰ ሲሆን፣ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ግን ቡሽ እንደገና ለመመረጥ የተነሱበት ዓመት እንደመሆኑ አዲስ የድጋፍ ማቀጣጠያ የፖለቲካ ርዕስ ሆኖ ማገልገሉ አልቀረም።[89]

ቶማስ ኤል ፍሪድማን የተባለው የእስራኤልን አቋም በመተቸት የሚታወቅ ተንታኝ ‹‹ሚስተር ሻሮን የፍልስጤማውያኑን መሪ አራፋትን በራማላህ ቢሯቸው እንዳሉ በቁም እንዳሰሯቸው ሁሉ፤ ጆርጅ ቡሽንም በእንቁላላማው ቢሮ (Oval office) በቁም አስረዋቸዋል። ልዩነቱ ሚስተር አራፋት የሚጠበቁት በታንክ መሆኑና ሚስተር ቡሽ ደግሞ በአፍቃሪ እስራኤል አይሁድና-ክርስቲያን ሎቢስቶች፣ እንዲሁም ምክትላቸው በሆኑትና ሻሮን ያዘዟቸውን ሁሉ ከመፈጸም በቀር ተቃውሞ በማያነሱት ዲክ ቼኒና ምርጫ በሚደረግበት ዓመት በእስራኤል ላይ ምንም ዓይነት ጫና ማድረግ አያስፈልግም በሚሉ የፖለቲካ ጠቢቦች መሆኑ ነው›› ብሏል።[90]

በእነዚያ ጊዜያት ሁሉ እስራኤል በምዕራባዊው ዳርቻ አሜሪካ እየተቃወመቻትም ቢሆን፣ የሠፈራ ግንባታዋን የቀጠለች ሲሆን፣ ይህም በተለይ በሮድ ማፑ ላይ እስራኤል አዳዲስ የሠፈራ መንደሮችን ማነጽ ብቻ ሳይሆን ነባሮቹንም የማስፋፋት ሂደቱን እንድትገታው የተገለጸ መሆኑን የሚቃረን ነው።[91] እስራኤል በተጨማሪም የፍልስጤማውያንን መሪዎች መግደሏን የቀጠለች ሲሆን፣ በተለይም ግድያው ቢያንስ ከዩ.ኤስ.አሜሪካ እይታ አንፃር የሚኖረው ፋይዳ አነስተኛ ሆኖ በሚታይበት ጊዜ ጭምር ነበር ያን የምታደርገው። ለምሳሌ የእስራኤል መከላከያ ሠራዊት (አይ.ዲ.ኤፍ) ፍልስጤማውያን ያቀረቡትን የተኩስ አቁም ሃሳብ በማጣጣል ሐምሌ 22 ቀን 2002 ላይ ሸይኽ ሷሊህ ሸሃዳ የተባሉትን የሃይማኖት ዋነኛ መሪና አስራ አራት ሰዎችን (ከእነርሱ ውስጥ ዘጠኙ ልጆች ናቸው) በመግደል የሰላሙን ተስፋ ሁሉ አጨልሞታል። ዋይት ሐውስ ግድያውን ‹‹ጭካኔ የተሞላበት የኃይል ድርጊት›› በማለት ያወገዘው ቢሆንም፣ እስራኤል ተመሣሣይ ግድያዎችን እንዳትፈጽም ለማስገደድ አልቻለም።[92] ቀደም ሲል እንደገለጽነው አዲስ የተኩስ አቁም ስምምነት ይደረጋል ተብሎ እየታሰበ ባለበት በሰኔ 2003 እስራኤል ሌላውን የሃማስን መሪ ዶክተር አብዱል አዚዝ አልለ-ራንቲሲን ለመግደል ያልተሳካ መከራ በማድረጓ ሊመክን ችሏል።

መጋቢት 22/2004 ላይ እስራኤል የሃማሱን መንፈሳዊ መሪ ሸይኽ አህመድ ያሲንን አሜሪካ ሠራሽ በሆነው ሄል ፋዬር ሚሳዬል በተሸከርካሪ ወንበራቸው ላይ እንዳሉ ገድላቸዋለች፡፡ ይህ እርምጃ አሜሪካ በመካከለኛው ምሥራቅ በምታራምደው አቋም ላይ ታላቅ ዱላ ያሳረፈ ነበር፡፡ እንደዚያ ለማለት የሚቻለው ግድያው የተፈጸመው አሜሪካ ሠራሽ በሆነ ሄሌኮፕተርና ሚሳዬል በመሆኑ ብቻ ሳይሆን እንደልብ መንቀሳቀስ የማይችሉትንና በተሸከርካሪ ወንበር ተቀማጩን ሼኽ እስራኤል እንድትገድል አሜሪካ አረንጓዴ መብራት ያሳየቻት መሆኑን በዓረቡ ዓለም ውስጥ ያሉ ብዙ ወገኖች የሚያምኑ በመሆኑ ጭምር ነው፡፡ የዋሽንግተን ፖስት አምደኛ (Columnist) ጂም ሆግላንድ በግድያው ማግሥት በጻፈው መጣጥፍ ላይ፡- ‹‹የአሜሪካ ወዳጅ ከሆኑት መሪዎች ሁሉ ከቻርለስ ደጎል በስተቀር የዩናይትድ ስቴትስን ዘመናዊ ዲፕሎማሲና ስትራቴጂ በበለጠ ጽናትና ኃይል እንደ አሪዮል ሻሮን ያወሳሰበው ማንም የለም፡፡ ሻሮን የእስራኤልን ጥቅም ለማስከበር ትንፋሽን ቀጥ አድርጎ በሚያቆም የጦረኝነትና ተጋፊነት መንፈስ በሚያደርጉት ሩጫ ብዙዎችን ያለአማራጭ አስቀርተዋል” ብሏል፡፡ [93] ይህ በሆነ ከወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሚያዝያ 17/2004 ቀን እስራኤል ዶክተር ራንቲሲንም ገደለች፡፡ [94]

አረፋት ቢሞቱም የተለወጠ ነገር አልነበረም

አራፋት ሕዳር 2004 ላይ ከሞቱ በኋላ ማሕሙድ አባስ አዲሱ የፍልስጤማውያን መሪ ሆነው ብቅ በማለት ጥር 2005 ላይ የተካሄደውንና የውጭ ታዛቢዎች ትክክለኛነቱን የመሰከሩለትን ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ አሸንፈው ሥልጣናቸውን አጠናከሩ፡፡ ማንም ሊገምተው እንደሚችለው ይህ ክስተት የሰላሙን ሂደት ወደፊት በማራመድ አባስ ለእስራኤል እውቅና እስከሰጡና ሽብርተኝነትን እስካወገዙ ድረስ ግጭቱ የሚፈታበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ነበር ሁሉም ያመነው፡፡[95] ከዚያም በላይ ቡሽ የድጋሚውን ምርጫ ማሸነፍ በመቻላቸው ለዘብተኛውን አባስን ለማገዝ ወይም ለመደገፍ የሚችሉበት ሁኔኛ አጋጣሚ ተፈጥሮ ነበር፡፡ የቡሽ አስተዳደር አዲሱን የፍልስጤማውያን መሪ ከመጀመሪያውም አንስቶ የደገፈ

ቢሆንም፣ ራሱን የቻለ የፍልስጤም መንግሥት እንዲመሠረት መርዳት ባለመቻሉ የቡሽ የሥልጣን መደላድል እንዲሸረሸር ምክንያት ሆኗል።

ቡሽ አባስን ለማገዝ ያደረጉት ጥረት አነስተኛ እንዲሆን ያደረገው ዋነኛ ምክንያት መጀመሪያውኑ የሻሮንን (በኋላም እርሳቸውን የተኳቸውን የኢሁድ ኦልመርትን) ከፍልስጤማውያን ምድር የመውጣት የተናጠል እርምጃ የደገፉ በመሆናቸው ነው። ቡሽ የሮድ ማፕን እቅድ የመተግበርን አስፈላጊነት በተደጋጋሚ ቢናገሩም ፍልስጤማውያን የራሳቸውን መንግሥት እንዲመሠርቱ የሚያስችላቸው ሁነኛ እርምጃ ማሳየት ባለመቻላቸው እቅዳቸው ከውጥኑ ነበር የመከነው።

የአሜሪካ ጽዮናውያን ሕብረትና ኦርቶዶክስ ኦርጋናይዜሽንን የመሳሰሉት አንዳንድ አፍቃሪ እስራኤል ቡድኖች እስራኤል ለፍልስጤማውያን አንድ ጋት መሬት ተቆርሳ እንዳትሰጣቸው ተቃውመዋል። በሌላ በኩል ደግሞ የፀረ-ሰም ማጥፋት ሊግ፣ የአሜሪካ አይሁዳውያን ኮንግረስና የአሜሪካ አይሁዳውያን ኮሚቴን የመሳሰሉት ዋናዋና የሎቢው ቡድኖች የሻሮንን የተናጠል እርምጃ ደግፈዋል። የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ በሚሰኘው ሌላው የሎቢ ድርጅት ውስጥ ከሚገኙ አመራሮች ከ60-75 ከመቶ የሚሆኑት የተናጠሉን እርምጃ በመደገፋቸው ሎቢው የሻሮንንና የቡሽን የፖሊሲ ለውጥ በታላቅ ስሜት ባይሆንም ደግፎታል።[96]

ሻሮን ከአባስ ጋር ሰላም ለማውረድ ባለመፍቀድ ባሳዩት አንገብጋቢ ሁኔታ አባስ ለፍልስጤማውያን ሕዝቦች ተጨባጭ የሆነ ጥቅም ሲያቀርቡ አልታዩም። እናም 2006 ላይ በተካሄደው ምርጫ ሃማስ ፋታህን በዝረራ እንዲያሸንፈው አስተዋጽኦ አድርገዋል። የሃ› ኤሬትዝ ጋዜጣ አዘጋጅ የሆነው ብራድሊ በርስተን የፍልስጤማውያኑ ምርጫ ከመደረጉ በፊት እንዲህ በማለት ተንብዩ ነበር፡- ‹‹በቀጣዩ ሳምንት በሚደረገው ምርጫ እስራኤል የሃማስ የምርጫ አስፈጻሚ ማናጀርነት ሚናዋን በሚገባ ተወጥታ የፍልስጤምን ፓርላማ የሃማስ አባላት ባይሞሉት ምናለ በሉኝ።››[97] እናም ሃማስ ሥልጣን ላይ አስኳለ ድረስ እስራኤል ላለመደራደር ሌላ ምክንያት የምታገኝ ሲሆን፣ የቡሽ አስተዳደርም ቢሆን ከፍልስጤማውያን ጋር እንድትደራደር ግፊት ለማሳደር እንደሚችገር ግልጽ ነው።

ነገሮች የበለጠ ሲከፉ እስራኤል የጀመረችው በተናጠል ከፍልስጤማውያን መሬት የመልቀቅ እርምጃ በ2006 ቡሽ ኢሁድ ኦልመርትን በዋይት ሃውስ

ተቀብለው ካስተናገዱ ከሁለት ወራት በኋላ ፈረሰ፡፡[98] እስራኤል ነሐሴ 2002 ላይ ኃይሏን በሙሉ ከጋዛ ከሳበች በኋላ ያችን ቁራጭ ምድር ዙሪያ ገባዋን መልሳ በመክበብ የፍልስጤማውያንን ኑሮ መላ ቅጡን አሳጣችው፡፡ በዚህ ጊዜ የጋዛ ፍልስጤማውያን ወደ እስራኤል ሮኬት ማስወንጨፋቸውን የቀጠሉ ሲሆን፣ ሰኔ 25/2005 ላይም አንድ የእስራኤል ወታደር መማረክ ቻሉ፡፡ እስራኤል ይህን ክስተት ጭራሽ የሚገባ ሆኖ ስላላገኘችው ከሶስት ቀናት በኋላ ከሞላ ጎደል መልሳ ጋዛን ተቆጣጠረች፡፡[99] እስራኤል የተናጠል እርምጃ መውሰዷን ቀጥላ ከተወሰኑ የምዕራባዊው ዳርቻ ግዛቶች ብትለቅና ፍልስጤማውያን ብቻቸውን ቢቀሩ በጋዛ የሆነው ሁኔታ መልሶ እንደሚከሰት ለብዙዎቹ እስራኤላውያን በተለይም ደግሞ ለጠ/ሚኒስትሩ ኦልመርት ግልጽ ሆነላቸው፡፡

ይህ ከሆነ ጥቂት ሳምንት ቆይቶ ሐምሌ 1 ቀን 2006 ሂዝቡላህ በእስራኤል ሊባኖስ ድንበር የተወሰኑ የእስራኤል ወታደሮችን ከገደለ በኋላ ሁለት የሚሆኑትን መማረኩን ተከትሎ ጦርነት ስለተጫረ ሂዝቡላህ ወደ ሰሜን እስራኤል ሮኬቶችንና ሚሳዮሎችን ያዘንብ ጀመር፡፡ ክስተቱ እስራኤል 2000 ላይ ከደቡብ ሊባኖስ በወሰደችው የተናጠል እርምጃ መውጣቷን ታሳቢ በማድረግ ከምዕራባዊው ዳርቻም ብትወጣ በእርሷና በፍልስጤማውያን መካከል ያለው ውዝግብ እልባት እንደማያገኝ የሚያረጋግጥላት ተጨማሪ ምክንያት ነበር፡፡ ስለሆነም የእስራኤል ሕዝብ ድጋፍ ከኋላቸው እንዳለ የተሰማቸው ኦልመርት 2006 በጋ ላይ የተናጠል እርምጃውን ውድቅ በማድረግ መሬት የመልቀቁን ሂደት ሙሉ በሙሉ አቋረጡት፡፡ ከዚያ በኋላ ኦልመርት ለቻይናው የዜና ወኪል ገርንሁዋ ጥር/2007 ላይ በሰጡት ቃለ ምልልስ፣ በድንገተኛ ሁኔታ ታመው ሥልጣን ከለቀቁት ሻሮን ወንበሩን በ2006 በተቀበሉ ጊዜ እስራኤል የምትከተለው በተናጠል የፍልስጤማውያንን መሬቶች የመልቀቅ እርምጃ የሁለቱን ኃይሎች ችግር እስከመጨረሻው ድረስ ይፈታዋል ብለው ተስፋ አድርገው እንደነበር ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ግን ተሳስተው ነበር፡፡ ምክንያቱም አሁን ያለው ሁኔታ በግልጽ እንደሚያሳየው የሁለቱን ኃይሎች ችግር በትክክል የሚፈታው የተናጠል እርምጃ በመውሰድ ሳይሆን በድርድር በሚገኝ የሁለት መንግሥታት መፍትሄ ብቻ ነው፡፡[100]

ራይስ “የፓወል እጣ” ደረሳቸው[101]

የቡሽ መስተዳደርም ቢሆን ውሎ አድሮ እስራኤል የተከተለችው የተናጠል እስትራቴጂ ውጤት የማያመጣ መሆኑን መገንዘቡ አልቀረም። ስለሆነም እንደገና ወደ ቀድሞው የሮድ ማፕ እቅዱ ተመልሶ ሊገፋበት ወሰነ። እናም በ2006 መገባደጃ አካባቢ የሰላሙን ሀሳብ የማነቃቃቱን ኃላፊነት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ ኮንዶሊዛ ራይስ ወስደው የፍልስጤምንና የእስራኤልን መሪዎች በማቀራረብ እንዲነጋገሩ ለማድረግ ተንቀሳቀሱ።[102] የእርሳቸው ግብ አጠቃላይ የሆነውን የሰላም ሃሳብ ዝርዝሮች ለመንደፍና በእርሳቸው አባባል ‹‹የፖለቲካው አድማስ›› ምን መምሰል እንዳለበት ለመወሰን የሚያስችል ንግግር ለማስጀመር ነበር።

ራይስ እስራኤልንና ፍልስጤማውያኑን ወደ ሰላም ድርድሩ እንዲመጡ አምርረው በመግፋት ላይ እያሉ የሳዑዲ ባለሥልጣናት በበኩላቸው 2002 ላይ ለአረብ ሊግ አቅርበውት የነበረውን የሰላም ዕቅድ አሁንም በ2007 መልሰው ሊያቀርቡት እንደሚችሉ አመኑ። ይህ እንደ አዲስ የሚቀርብ የሰላም ዕቅድ እንደመጀመሪያው ሁሉ እስራኤል ከፍልስጤማውያን ጋር ብቻ ሳይሆን ከቀሪዎች ሃያ ሁለት የአረብ ሊግ አባላት ጋርም ጭምር ሰላምና የተረጋጋ ግንኙነት መመስረት እንድትችል የሚያደርግ ነው። በምላሹ ደግሞ እስራኤል በኃይል ከያዘቻቸው የፍልስጤማውያን መሬቶችና ከጎላን ከፍታዎች እንድትወጣና ዋና ከተማው ምሥራቅ እየሩሳሌም የሆነ ነፃ የፍልስጤም መንግሥት ይመሠረት ዘንድ እንድትስማማ፣ እንዲሁም ፍልስጤማውያን ስደተኞችን በተመለከተ ሁለቱ ተደራዳሪዎች በሚያስቀምጡት የውሳኔ ሃሳብ መሠረት ‹‹ትክክለኛ መፍትሄ›› እንዲገኝላቸው ዕቅዱ ይጠይቃል።[103] ሳዑዲዎች አጽንኦት ሰጥተው እንደገለጹት ያቀረቡት የሰላም ሃሳብ ለስምምነት መሠረት የሚጥል እንጂ ሲፈልጉ የሚቀበሉት፣ ሳይፈልጉ ደግሞ ውድቅ የሚይደርጉት ዓይነት የድርድር መነሻ አይደለም።

ሳዑዲም ሆነች አሜሪካ የእስራኤል ፍልስጤማውያንን ግጭት ለማብቃት የሚያነሳሳቸው ታላቅ የሆነ የየራሳቸው ምክንያትና ጥቅም አላቸው።[104] ዩ.ኤስ.አሜሪካን ለምሳሌ ብናስቀድም እስራኤል በኃይል የያዘቻቸውን የአረብ መሬቶች ይዛ እንድትቆይ ማገዟን እስከገፋችበት ድረስ በአንጻሯ የሚነሳውን የሽብርተኝነት ችግር የሚያባብስ ነዳጅ ማርከፍከፍ ብቻ ሳይሆን የቡሽ አስተዳደር ከኢራቅ ጋር ለጀመረው ጦርነት የአረብ መንግሥታትን እገዛ ለማግኘትና የኢራንንም ኒኩሊዬር መርሃግብር አስመልክቶ ለመነጋገር ሁኔታዎችን አስቸጋሪ ያደርግበታል። ሳዑዲዎች በበኩላቸው በኢራን ጉዳይ ከአሜሪካ ጋር መሥራት ይሻሉ። ሆኖም ግን ያንን እንደልባቸው ለማድረግ እንዳይችሉ የሚያደርጋቸው ምክንያት አለ። ይኸውም የሳዑዲ ሕዝብ አሜሪካ ለእስራኤል በምትሰጠው እገዛ ምክንያት በፍልስጤማውያን ላይ የሚደርሰውን ግፍ እየተመለከተ ስለሚቆጭ ሀገሩ ከአሜሪካ ጋር መሥራቷን በበጎ ዓይን አይመለከተውም። ሳዑዲዎች የእስራኤል-ፍልስጤም ችግር መፍትሄ እንዲያገኝ የሚፈልጉበት ሌላው ምክንያታቸው ደግሞ ኢራን፣ እስራኤል በኃይል በያዘቻቸው መሬቶች ላይ በሚገኙ አክራሪ ፍልስጤማውያን ላይ ተጽዕኖዋን እያሰፋች በመሆኑ ነው።

ይህን ሁሉ ተጨባች ሁኔታ እግምት ውስጥ ስናስገባ ይኼኛውም የሰላም ሂደት የምር ወደፊት የሚራመድ መስሎ መታየቱ አልቀረም። ዳሩ ግን በትክክል የሆነው እንደዚያ አልነበረም። ኦልመርት ለአረብ ሊግ የሰላም ሃሳብ ያደረባቸው ስሜት አነስተኛ ስለነበር እንደ 2002ቱ ሁሉ የሰላሙ ጥረት ውድቀት እንደሚገጥመው መገመት አላስቸገረም። የእስራኤሉ ጠ/ሚኒስትር በተለይ በተወሰኑ የሰላሙ እቅዱ ነጥቦች ዙሪያ ደስተኛ አልነበሩም ማለት ይቻላል። ለአብነት ያክል እስራኤል ከያዘቻቸው ከሁሉም ግዛቶች ትወጣለች መባሉና የፍልስጤማውያን ስደተኞችን ወደ ሐገራቸው የመመለስ መብት በተመለከተ በተለይ ለእየሩሳሌም ፖስት መጋቢት 2007 በሰጡት ቃለ ምልልስ፡- “ይህን ችግር አስመልክቶ በሚነሳ ማንኛውም የእስራኤል ኃላፊነት ዙሪያ የማደርገው ስምምነት የለም።›› በማለት ተቃወሚቸውን ገልጸዋል። ከዚያም እንዲህ በማለት አከሉ፡- ‹‹አንድም

የፍልስጤም ስደተኛ ወደ እስራኤል መመለሱ ፈጽሞ ተቀባይነት አይኖረውም”::[105]

ሆኖም ግን ይህም ጉዳይ ሆነ ሌሎቹ አወዛጋቢ ነጥቦች እስራኤል በስምምነቱ ዙሪያ ለመደራደር ዝግጁ ሆና እስከተገኘች ድረስ መፍትሄ የማይበጅላቸው አልነበሩም። ሃ› ኤሬትዝ ጋዜጣ በመጋቢት መገባደጃ ላይ በወጣ ርዕሰ አንቀጹ ይህን ነጥብ እንደሚከተለው በማለት በሚገባ አስቀምጦታል፡- ‹‹እውነተኛ መንግሥት የሰላም ሃሳቦችን ለመቀበልና ለመደራደር ፈቃደኛነት አያንሰውም። በሂደቱም የማይቀበላቸውን ጉዳዮች አስመልክቶ ቁጥብነትን በማሳየትና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ደግሞ በመነጋገር የክልሉን ሰላም እልባት ለማስያዝ ይተጋል።››[106] ይህ በእንዲህ እያለም በግንቦት አጋማሽ ላይ ኢሁድ ኦልመርት ከአረቦች ጋር የሰላም ስምምነት ማድረግ ባለመቻላቸው የፀረ-ስም ማጥፋት ሊጉ አብርሃም ፎክስማንና የኖቤል ተሸላሚው ኤሊ ዌይሰልን ጨምሮ በብዙ ሰዎች በሰፊው ተተቹ። በዚያ ሁሉ ትችት መካከል ብቻቸውን ኃላፊነቱን ለመውሰድ የተገደዱት ኦልመርት -የአረብ ሊግ ያነቃቃውን የሰላም እቅድ እስራኤል እንደምታጤነውና ልትመክርበት ዝግጁ መሆኗን የገለጹ ቢሆንም፣ ለይስሙላ ካደረጉት ንግግር በመለስ አንድም የሚጨበጥ ተግባር አልፈጸሙም። እንዲያውም በተቃኒው እስራኤል ለሰላሙ ሃሳብ መውደቅ ተጠያቂዎቹ አረቦች መሆናቸውን በመግለጽ ዲፕሎሲያዊ ዘመቻ ከፈተች።[107]

ኦልመርት የአረብ ሊግን የድርድር ሃሳብ ይቀበሉ ዘንድ የቡሽ አስተዳደር አንዳች ግፊት ማድረግ ሲገባው የአረብ መሪዎች የሰላሙን እቅድ ለእስራኤል ተስማሚ ይሆን ዘንድ እንዲያሻሽሉት ይጠይቅ ነበር።[108] ኮንደሊዛ ራይስ የሰላሙን ሂደት ወደፊት ለማራመድ ያደረጉት ጥረት መና ቀርቷል። የካቲት 2007 ላይ አሥራ አምስት ከሚሆኑ ዋና ዋና የአይሁዳዊያን ድርጅት መሪዎች ጋር ባደረጉት ስብሰባ የእርሳቸው መንግሥት በእስራኤል ላይ ጫና ከማሳረፍ መቆጠብ ብቻ ሳይሆን ‹‹የፖለቲካው አድማስ›› ምን መምሰል እንዳለበት እንኳ የራሱን አስተያየት ከመስጠት መቆጠቡን ግልጽ አደረጉ።[109] ራይስ ከዚያ በኋላ የካቲት 19 ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ተጉዘው ኦልመርትንና አባስን በማገናኘት እንዲነጋገሩ

አደረጉ። ሆኖም ግን ራይስ በሰላም ድርድሩ ላይ ነፍስ ለመዝራት ያደረጉት ጥረት የእስራኤሉ ጠ/ሚኒስትር በኃይል የተያዙትን ግዛቶች መልቀቅን በሚመለከት በዝርዝር ለመነጋገር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ሳይሳካላቸው ቀረ። ከዚያ በኋላ ኦልመርትም ሆኑ አባስ ከሴትዮዋ ጋር በመሆን ጋዜጣዊ መግለጫ ለመስጠት አሻፈረን ማለታቸው እውነት ነው። ይህ ሁሉ ከሆነ ከአጭር ጊዜ በኋላ ለንባብ የበቃው ኒውዮርክ ታይምስ በርዕሰ አንቀጹ ላይ ባወጣው ጽሑፍ ‹‹የእየሩሳሌሙ ጨዋታ›› በሚል ርዕስ ስር፡- ‹‹ራይስ ሌላው ቀርቶ ሁለቱ መሪዎች ቅር እያላቸው የተስማሙበትን የጋራ መግለጫ እንኳን ሲያነቡ መሪዎቹን ከጎናቸው እንዲቆሙ ማድረግ አልቻሉም›› ብሏል።[110] መጋቢት 2007 ላይ ራይስ ወደ እስራኤል ተመልሰው በመሄድ ኦልመርትን ካገኙ በኋላ በእስራኤልና በፍልስጤማውያን መካከል ያገናኝነት ሚና መጫወት የሚችሉበት እድል ይኖር እንደሆነ ለማረጋገጥ ተጨማሪ ሙከራ አደረጉ። ይኼኛው ጉዟቸው በስምንት ወራት ውስጥ አስራ ሰባተኛው ነበር። ኦልመርት የራይስን የዲፕሎማሲ ደላላነት ሚና ያለምንም መሸፋፈን ነበር ውድቅ ያደረጉት። ተቃውሟቸውንም ለመግለጽ ራይስ ከሁለቱ ግንኙነት በኋላ ሊሰጡት ያሰቡትን ጋዜጣዊ መግለጫ እንዲሰርዙ አስገደዷቸው። የለንደኑ ዴይሊ ቴሌግራፍ የኦልመርትንና የራይስን ስብሰባ አስመልክቶ ‹‹እስራኤል ለራይስ ያሳየችው የንቀት ስሜት›› በሚል ርዕስ በቀጣዩ ቀን ባወጣው ጽሑፍ አትቷል።[111] የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ይህን በመሰለ አሳፋሪ ሁኔታ ባዶ እጃቸውን ወደ ዋሽንግተን ለመመለስ የተገደዱ ሲሆን የቡሽ አስተዳደርም ጊዜው አልቆ ቢሮውን ከመልቀቁ በፊት በአረብ እስራኤል ውዝግብ ላይ ትርጉም ያለው የሰላም እርምጃ የማሳየት እድሉ የተመናመነ መሆኑ ግልጽ ወጣ።

ይህ የተፈጠረው ውጤት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯን ብቻ ሳይሆን የአሜሪካንም ብሔራዊ ጥቅም ጭምር ያዋረደ እንደመሆኑ በሁለት ምክንያቶች የተከሰተ ነበር። በመጀመሪያ ኦልመርት ልክ ከእርሳቸው በፊት እንደነበሩት እንደ ሻሮን ሁሉ ከፍልስጤማውያን ጋር ለሚደረግ ስምምነት ደንታ ያልነበራቸው መሆኑ ነው። ምክንያቱም የሰላም ስምምነት የሚደረግ

ከሆነ እስራኤል ከሞላ ጎደል ሁሉንም የምዕራቡን ዳርቻ መልቀቅና በዚያ ላይ ራሱን የቻለ ነፃ የፍልስጤማውያን መንግሥት እንዲቋቋም መፍቀድ ስለሚኖርባት ነው። ኦልመርት የተወሰነውን የምዕራቡን ዳርቻ ግዛት ለመልቀቅ ዝግጁ መሆናቸውን ግልጽ ያደረጉ ቢሆንም፣ አብዛኛው ክፍል ግን የእስራኤል እንደሆነ እንዲቆይ ይፈልጋሉ። 2006 ማብቂያ ላይ መንግሥታቸው በአስር ዓመት ውስጥ የመጀመሪያውን አዲስ የሠፈራ መንደር በምዕራባዊው ዳርቻ እንደሚመሰርት ይፋ ያደረገ ሲሆን፣ በቀጣዩ ወር እስራኤል ‹ ማአሌህ አዱሚም › በሚባለው ነባሩና ትልቁ የእስራኤል የሠፈራ መንደር አዳዲስ ቤቶቹን እንደምታንጽ ገለጸች።[112] ምንም እንኳን ሰላም ማለት 95 ከመቶና ከዚያ በላይ የሚሆነውን የምዕራባዊውን ዳርቻ ለፍልስጤማውያን መመለስን የሚጠይቅ ቢሆንም ቅሉ እስራኤል ከሰላም ይልቅ ግዛት ማስፋፋቱን ነው ሁልጊዜም ስትመርጥ የሚታየው።[113]

‹‹እውነተኛዋ የሰላም ጠንቅ እስራኤል ሳትሆን ጥር 2006 ላይ በምርጫ ሥልጣን የያዘው ሃማስ ነው። ምክንያቱም ሃማስ እስራኤል እንድትጠፋ የሚፈልግ ድርጅት ነውና›› የሚል ክርክር ሊነሣ ችላል። ሃማስ በፍልስጤማውያን ዘንድ ያለው ተቀባይነት ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር የሰላሙን ጥረት ይበልጥ እያወሳሰበው መምጣቱ አያጠያይቅም። የሆነ ሆኖ ይህ ችግር በራሱ የማይወገድ ወይም መፍትሄ የማይበጅለት አይደለም። እስራኤል ሰላም እንዲመጣ ከልብ የምትፈልግ ከሆነና ከፍልስጤማውያን ጋር እርቅ ማውረድ ከሻች ከአረብ ሊግ፣ ከማህሙድ አባስና ሌላው ቀርቶ በሃማስ አንጃ ውስጥ ከሚገኙ ለዘብተኛ አቋም ያላቸው ክፍሎች ጋር በመደራደር ተስፈንጣሪዎቹን የሃማስ አባላትና ኢስላሚክ ጂሃድን የመሳሰሉትን ቡድኖች ማግለል ትችላለች።[114] ይሁን እንጂ እስራኤል በየጊዜው ቁጥሩ እያደገ ከመጣውና ከአይሁዳዊቷ ሀገር ጋር ሃቀኛ ሰላም የመመስረት ፍላጎት ካለው የአረብ ሕዝብ ጋር ለእርቅ ለመሥራት ያላት ተነሳሽነት አነስተኛ ነው። በዚህ አካሄድ የዘወተረችው እስራኤል መለስተኛ አቋም ያላቸውንና ሰላማዊ ቡድኖችን በመገፍተር ‹‹የመጨረሻው መፍትሄ የሚገኘው በጠብመንጃ አፈሙዝ ብቻ ነው›› ብለው የሚያምኑትን አንጃዎች በየጊዜው እያጠናከረቻቸው ትገኛለች።

በሁለተኛ ደረጃ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚገኙ አፍቃሪ-እስራኤል ኃይሎች፣ ዩናይትድ ስቴትስ -በተለይም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮንደሊዛ ራይስ- የኦልመርትን መንግሥት ወደ ሰላሙ ጠረጴዛ ለመግፋት እንዳይችሉ በማድረጋቸው ነው፡፡ ዋይት ሐውስ ውስጥ ተቀምጦ በእስራኤል ላይ ምንም ዓይነት ትርጉም ያለው ግፊት እንዳይደረግ መሰናክል ሲፈጥር የቆየው ደግሞ ኢሊዮት አብራምስ ነው፡፡ እርግጥ ነው አብራምስ ብቻውን አልነበረም፡፡ ከምክትል ፕሬዚዳንቱ ዲክ ቺኒ ጋር የሚሠሩ ሁለት ኃይለኛ ኒዎኮንሰርቫቲቮችን ከጎኑ አሰልፎ ነበር፡፡ እነርሱም ጆን ሃናህ እና ዴቪድ ውርምሰር ናቸው፡፡ ጋዜጠኛው ጂም ሎቤ ከተለያዩ ምንጮች እንዳገኘው በመግለጽ ባወጣው ሪፖርት እንዲህ ብሏል፡- ‹‹ራይስ የሚያደርጉትን የተሳካ የማደራደር ሙከራ እንዲገፉበት የሚያደርግ ተስፋ እንዳይኖራቸው ለማድረግ አብራምስ ብዙ ነገሮችን በዘዴ ያከናውን ነበር፡፡ እንዲሁም በየጊዜው ትዕግስታቸው እየተሟጠጠ የመጡት የሳዑዲው ንጉሥ አብደላህ ለፍልስጤማውያን የመጨረሻ መፍትሄ እንዲመጣ የሚያደርጉትን ግፊትም ለማምከን ይተጋ ነበር፡፡››[115]

አብራምስ የኦልመርት ኤታማጆር ሹም ከሆኑት ዮራም ቱርቦዊዝና የኦልመርት ዲፕሎማሲያዊ አማካሪ ከሆኑት ሻሎም ቱርግማን ጋር የጠበቀ ትስስር ነበረው፡፡ እነዚህ ሁሉ፣ የቡሽ አስተዳደር በእስራኤል ላይ ጫና በመፍጠር ኦልመርት የማይፈልጉትን እንዲፈጽሙ እንዳያደርጋቸው የሚሠሩ ነበሩ፡፡ ዳንኤል ሌቪ የተባሉ የቀድሞው የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር አማካሪ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹ራይስ የሰላም ሃሳቡን በማራመዱ ሂደት ላይ የቀናቸው በሚመስል ጊዜ ዮራም ቱርቦዊዝና ሻሎም ቱርግማን ዋይት ሐውስ ውስጥ ለሚገኘው አጋራቸው ኢሊዮት አብራምስ መልዕክት ይልካሉ፡፡ እርሱ ደግሞ በተራው ምክትል ፕሬዚዳንቱን ዲክ ቺኒን በመቀስቀስ ፕሬዚዳንቱን እንዲነዘንዟቸው ያደርጋል፡፡››[116] በተመሳሳይ ሁኔታ በመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ ላይ ለረዥም ጊዜ በውጭ ጉዳይ አማካሪ ሆነው የሠሩት ሄኔሪ ሲግማን እንደሚከተለው ብለዋል። ‹‹ዩናይትድ ስቴትስ በፖለቲካው ሂደት ጠንካራ እርምጃ በመውሰድ የመካከለኛውን ምሥራቅ ጉዳይ እያንቀሳቀሰች የመሆኗ አነስተኛ ፍንጭ በተሰማ ቁጥር

ኤሊዮት አብራምስ በምስጢር ከኦልመርት ልዑካን ጋር አውሮፓ ውስጥ ወይም በሌላ ሥፍራ ይገናኝና እንዲህ ዓይነቱ ስጋት ፈጽሞ እንደሌለ ያረጋግጥላቸዋል፡፡››[117] ራይስ የካቲት 19 ከኦልመርትና ከአባስ ጋር ለሚያደርጉት ስብሰባ እስራኤል በገቡ ቅጽበት የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ራይስን ባሉበት ትተው ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ከአንድ ቀን ቀደም ብሎ ከቡሽ ጋር ዓይን ለዓይን እየተያዩ መነጋገራቸውን (በሳተላይት መሆኑ ነው) አሳወቁ፡፡ አሉፍ ቤንና ሻሙኤል ሮዝነር ሃ›ኤሬትዝ ጋዜጣ ላይ ሲጽፉ ‹‹መልዕክቱ ግልጽ ነበር፡፡ ከእንግዲህ ራይስ የሚናገሩት ነገር ከቁጥር የሚገባ አይደለም፣ የሚል አንደምታ ያለው ነው›› ብለዋል፡፡[118]

ሁዋይት ሐውስ ውስጥ ያለው የኃይል ሚዛን ከራይስ በተቃራኒ እያመዘነ መሄዱ ይበልጥ ግልጽ የሆነው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አማካሪ የነበረው ፊልፕ ዘሊኮው በ2000 ዓ.ል. ኃላፊነቱን በገዛ ፈቃዱ በለቀቀ ጊዜ ነበር፡፡ ዘሊኮው የራይስ የረዥም ጊዜ ጓደኛ፣ አብሮዋቸው መጽሐፍ ያዘጋጀ (Co-author) እና ከቅርብ አማካሪዎቻቸው አንዱ ነበር፡፡ በ2006 የበጋው መገባደጃ አካባቢ ራይስ እስራኤልንና ፍልስጤማውያንን ለማስማማት ጠንከር ያለ ጥረት እንዲያደርጉ ዘሊኮው አበረታቷቸዋል፡፡ በተጨማሪም ዋሽንግተን' አረብ መንግሥታትና አውሮፓውያን አንድ ላይ ሕብረት እንዲፈጥሩና በኢራን አንዣር እንዲቆሙ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይሰማው ነበር፡፡ ይህን ሃሳቡን በመስከረም 15/2006 የአይሁዳውያን ድርጅት የሆነው ዋሽንግተን ኢንስቲትዩት ፎር ኒር ኢስት ፖሊሲ ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ ይፋ አደረገ፡፡[119] ንግግሩን ተከትሎ አፍቃራእስራኤል ከሆኑ ድርጅቶች መጫጫህ ተከሰተ፡፡ ኒውዮርክ ታይምስ እንዳለው፡- ‹‹የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከዚህ ንግግር ራሱን በፍጥነት ያራቀ ሲሆን፣ የእስራኤል ባለሥልጣናትም በዘሊኮው ንግግር ግራ መጋባታቸውን በመግለጻቸው ዩናይትድ ስቴትስ የኢራንንና የፍልስጤምን ጉዳይ ሁለት የተለያዩ አጀንዳዎች አድርጋ የምትቆጥራቸው መሆኗን ራይስ ለእስራኤሏ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዚፒ ሊቪኒ አረጋገጡላቸው፡፡[120] ዘሊኮው በቀጣዩ ወር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሥራውን በፈቃዱ እንደሚለቅ አስታወቀ፡፡ ምንም እንኳን ስማቸው እንዲገለጽ ያልፈለጉ የዋይት ሐውስ ምንጮች እንዳስታወቁት ዘሊኮው፣

አሜሪካ መካከለኛው ምሥራቅን በተመለከተ በምትከተለው ፖኪሲ ደስተኛ እንዳልነበረ የገለጹ ቢሆንም ቅሉ፣ በሥራ መልቀቂያ ደብዳቤው ላይ ይህ ነው የሚባል ጠንካራ ምክንያት አልጠቀሰም፡፡ መጋቢት 2007 ላይ ራይስ በዘሊኮው ምትክ ከቀንደኛ ኒዎኮንሰርቫቲቮች አንዱ የሆኑትንና ፕሮጀክት ፎር ኒው አሜሪካን ሴንቸሪ (ፒ.ኤን.ኤ.ሲ) የተሰኘውን ሐሳብ አፍላቂ (Think Thank) ድርጅት የመሩትን ኢሊዮት ኮኸንን ሾሙ፡፡[121]

ራይስ በቢሯቸው ሆነው የሰላሙን ሂደት እንደልባቸው ማንቀሳቀስ እንዳይችሉ የሚያደርጋቸው ማነቆ እንዳለ ቢሆንም፣ በሃማስ ኪሣራ የፋታሁን መሪ አባስን ለመርዳት ይጥሩ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሎቢው ያንን ጥረታቸውንም ቢሆን ውጤታማ እንዳይሆን ማሰናከሉ አልቀረም፡፡ በተለይም ደግሞ ፕሬዚዳንት ቡሽ ጥር 2007 ላይ ለአባስ መንግሥት የፀጥታውን ክፍል ለማጠናከሪያ የሚያውለው 86 ሚሊዮን ዶላር ለመስጠት መወሰኑን ተከትሎ ሁኔታው ተጋግሎ ነበር፡፡ የኒውዮርኳ ዲሞክራትና ቀንደኛ የእስራኤል ደጋፊ፣ እንዲሁም ምክር ቤቱ ለተለያዩ ጉዳዮች የመደበውን በጀት የሚያከፋፍለው ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኒታ ሎዊ ውሳኔውን አገዱት፡፡[122] ሌላው አፍቃሪ-እስራኤል ሕግ አውጪ አንቶኔ ወይነር ለራይስ ደብዳቤ በመጻፍ የገንዘቡን ጥያቄ እንዲሰርዙ አሳሰቧቸው፡፡[123] የአሜሪካ ጽዮናውያን ድርጅት ፕሬዚዳንት ሞሮቶን ክሌይን በዚያ ጊዜ ‹‹ቡሽ በሃማስና በአል-ቃኢዳ ላይ ጠንካራ እንደሆኑ ሁሉ በአባስ ላይም ጠንካራ ሊሆኑ ይገባል›› አሉ፡፡[124]

ክሌይን በአባስ ላይ የሰነዘሩትን ለእርቅ ቦታ የማይተው አስተያየት ብዙዎች የአይሁድ ድርጅት መሪዎች ይጋሯቸዋል፡፡[125] አባስ ምንም እንኳን የሁለት መንግሥታትን የመፍትሄ ሃሳብ ለመተግበር ዝግጁነታቸውን ቢገልጹና ከእስራኤል ጋር በሰላም ለመኖር ቢፈልጉም የካቲት 2007 ላይ ከሃማስ ጋር የጥምረት መንግሥት ለመመስረት በመስማማታቸው አይሁዳዊያን ተናደውባቸው ነበር፡፡ አይፓክ በኮንግረሱ ላይ ግፊት በማድረግ የዩ.ኤስ.አሜሪካ መንግሥት በጥምሩ የፍልስጤም አስተዳደር መንግሥት ሥር ካሉት ባለስልጣናት ጋር -አባስን ጨምሮ- እንዳይነጋገር ለማድረግ ሞክሮ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ያ ጥረቱ አልሰመረለትም፡፡[126] በመሆኑም የቡሽ

አስተዳደር ኒታ ሎዊን ላለማስቀየም ለአባስ መንግሥት የሚሰጠው እርዳታ ከ86 ሚሊዮን ወደ 59 ሚሊዮን ዝቅ እንዲል አደረገ፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን የአባስ መንግሥት ገንዘቡን ለሥልጠና፣ ከጦር መሣሪያ ውጭ ያሉ አስፈላጊ ነገሮችን ለመሸመቺያ' እንዲሁም በእስራኤልና በጋዛ መካከል ያሉትን ወሳኝ የፀጥታ ጥበቃ ቦታዎች የተሻሉ ለማድረግ ብቻ እንዲያውለው ግዴታ እንዲገባ ጭምር ተደረገ፡፡ ሎዊ በዚህ ሃሳብ በመስማማታቸው ገንዘቡ በመጨረሻ ተላለፈ፡፡[127]

የሆነ ሆኖ የቡሽ አስተዳደር ሃማስን ለመነጠልና ለማግለል ያደረጋቸው ሙከራዎች በሚገባ የከሸፉት ስኔ 2007 ላይ ሃማስ የፋታህን ተዋጊዎች ከጋዛ ምድር ጠራርጎ ባስወገደ ጊዜ ነበር፡፡ የአባስን ኃይል ለማጠናከር እስራኤል በወሰደቻቸው የዘገዩ እርምጃዎች ፍልስጤማውያን እስረኞችን ለመፍታትና የግብር ዕዳቸውን ለመሰረዝ የወሰነች ሲሆን፣ ቴሌአቪቭና ዋሽንግተን በጋራ በፍልስጤም አስተዳደር ላይ ተጭነው የቆዩ የተወሰኑ የኢኮኖሚ ማዕቀቦችን ለማላላት ቃል ገቡ፡፡ ይሁን እንጂ የፍልስጤማውያኑ መሪ በተስፈንጣሪዎቹ ላይ የበላይነትን ለመቀዳጀት የሚያስፈልጋቸውን እውነተኛ የሥልጣን ማረጋገጫ ምልክት ከእስራኤል በኩል ሳያገኙ ቀሩ፡፡ ስለሆነም ውዝግቡ አሜሪካ በአረቡና በሙስሊሙ ዓለም ያላትን ሥፍራ ከጊዜ ወደጊዜ እየጎዳው መቀጠሉ አይቀሬ ነው፡፡

ማጠቃለያ

ሎቢው ባይኖር ኖሮ የቡሽ አስተዳደር በእስራኤልና በፍልስጤም መካከል ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን ሙሉ ፍላጎት ነበረው። ዩናይትድ ስቴትስ በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሌሎች መንግሥታት ባህሪያቸውን እንዲቀይሩና የእርሷን ጥቅም እንዲያከብሩ ለማድረግ በርካታ ዘዴዎችን የመጠቀም ታሪክ ያላት ሀገር ናት። ዋሽንግተን ከሶቪዬት መሪዎች ጋር ተደጋጋሚ ስምምነቶችን ስታደርግ የመቆየቷን ያክል ሶቪዬት ከፈራረሰች በኋላ ዩክሬየን፣ ካዛክስታንና ቤላሩስ የኒኩሊዬር መሣሪያዎቻቸውን እንዲያስረክቡ ወይም እንዲያወድሙ ጫና አድርጋባቸዋለች። በሊቢያም ላይ ተመሳሳይ ጥረት በማድረግ በመጨረሻ ሊቢያን ማሳመን በመቻሏ የጅምላ ጨራሽ የጦር መሣሪያ መርሃ-ግብሯን እንድትተውና በምትኩ በርካታ የሆኑ የኢኮኖሚ ማዕቀቦች እንዲነሱላት አድርጋለች። የክሊንተን አስተዳደር በሰርቢያ ላይ ከባድ የአየር ድብደባ ካደረገ በኋላ በ1999 ከኮሶቮ እንድትወጣ አስገድዷታል። እንዲሁም የቡሽ አስተዳደር በርካታ ሀገራት የዓለም አቀፉን የወንጀል ችሎት ለማቋቋም የወጣውን ስምምነት እንዳይፈርሙ ጫና አድርጎባቸዋል። በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 10 ላይ በሚገባ እንደምናብራራው ኢራን የጀመረችውን ኒኩሊየር የመታጠቅ ፍላጎት እንድትተው ለማሳመን አሜሪካ ረዥም ርቀት ተጉዛለች። በአንጻሩ በእስራኤል፣ በፍልስጤማውያንና ጉዳዩ በሚመለከታቸው የአረብ ሀገራት ላይ ጫና በማሳረፍ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የምታደርገው ጥረት ቀጣይነት የጎደለውና ለስኬትም ያልታደለ ነው።

ዩናይትድ ስቴትስ የእስራኤል ፍልስጤምን ችግር ለማስወገድ ቆርጣ ከተነሳች ታላቅ የሆነ እምቅ ተጽእኖ የማሳረፍ አቅም አላት። ለምሳሌ ለእስራኤል የምትሰጣትን ኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ እርዳታ ሙሉ በሙሉ እንደምታቋርጥ ብታስፈራራ፣ ይህም አልበቃ ካለ እስራኤልን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማግለል ብትወስን ለተግባራዊነቱ ከባድ ጥረት አይጠይቃትም። በዚህ ሃሳብ ከገፋችበት ባለፈው ምዕተ ዓመት መገባደጃ

ላይ ደቡብ አፍሪካን እንድትገለል ካደረገችበት ሁኔታ የበለጠ ሊሳካላት ይችላል። ፍልስጤማውያንን በተመለከተ ደግሞ ለረዥም ጊዜ ሕልማቸው ሆኖ የቆዬው የራሳቸውን ነፃ መንግሥት እውን እንዲሆን በማድረግ ከዚሁ ጋር ሰፊ የሆነ የኢኮኖሚ እርዳታን ብታቀናጅበት ሁሉም ነገር የሰመረ ይሆናል። በምላሹ ፍልስጤማውያን ሁሉንም ዓይነት የሽብር ድርጊት ያቆማሉ። እስራኤል ውስጥ የፖለቲካ ልዩነቶች ጎልተው እስከቀጠሉና በፍልስጤምም በሚገባ የተደራጀ አመራር እስከታጣ፣ እንዲሁም በሁለቱም በኩል ለእርቅ እጅ የማይሰጡ ቡድኖች እስካልጠፉ ድረስ የመጨረሻውን ሰላም ማምጣቱ ቀላል አይሆንም። ሆኖም ግን ምንም ባለመሥራት ወይም በተለመደውና እስራኤልን በጽናት እየረዱ በመጓዝ ነገሮችን የተሻሉ ማድረግ አይቻልም። በተቃራኒው ይህ የአሜሪካ ፖሊሲ ለፍልስጤማውያንም ሆነ ለእስራኤል ሁኔታዎችን መጥፎ ከማድረጉም በላይ፣ አሜሪካ በመላው ዓለም ሕዝብ ዘንድ ያላት ዝና ከጊዜ ወደጊዜ እየተሸረሸረ በመሄዱ ኢራቅንና ኢራንን በመሳሰሉት ሀገራት ያጋጠሟትን ችግሮች ለመፍታት ትኩረት እንዳታደርግ አስቸጋሪ ሁኔታን ፈጥሮባታል።

እስራኤል በብዙ አሜሪካውያን ዘንድ ያላትን መልካም ገጽታ ስናጤን ይህ ትንታኔ ከእውነታው የራቀ ነው ብለን ልናስብ እንችላለን። ቡሽ እስራኤልን ከፍልስጤማውያን በተቃራኒ የሚረዱበት ምክንያት የአሜሪካ ሕዝብ እስራኤልን በኃይል ስለሚደግፍ ነው ልንልም እንችላለን። ፕሬዚዳንቱም ሲያደርጉ የቆዩትና እያደረጉም ያሉት ሌላ ሳይሆን የሕዝባቸውን መሻት ማሟላት ነው እንልም ይሆናል። ዳሩ ግን ይህ አተረጓጎም የአሜሪካ ሕዝብ፣ እስራኤል በገዛ ሰላሙ ላይ የምታሳድረው ተጽእኖ እንዳለና ለሀገሩም ጠንቅ መሆኗን በትክክል ቢገነዘብ በእርሷ ላይ ጫና እንዲደረግ ከመጠየቅ ወደኋላ የማይል መሆኑን ያገናዘበ አይደለም። ምንም እንኳን የዩናይትድ ስቴትስ ሕዝብ ከፍልስጤማውያን ይልቅ ለእስራኤላውያን የበለጠ ሀዘኔታ ያለው ቢሆንም፣ ሁለቱንም ክፍሎች በእኩል ዓይን የመመልከት ፖሊሲን የሚደግፈው ሕዝብ ቁጥሩ ቀላል እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። ለምሳሌ በ2002 ቡሽ በእስራኤል ላይ ጠንካራ ጫና ለማሳደር የጀመሩትን ጥረት ብዙ አሜሪካውያን ደግፈውት ነበር። ከሚያዝያ 10-11 የተደረገው የታይምስ ሲ.ኤን.ኤን. ጥናት እንዳረጋገጠው 60 ከመቶ የሚሆኑ አሜሪካውያን ሻሮን በቅርቡ ከያዟቸው የፍልስጤማውያን መሬቶች

የማይወጡ ከሆነ ዩ.ኤስ.አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጠው እርዳታ እንዲቋረጥ የሚሹ ነበሩ፡፡ በተጨማሪም 75 ከመቶ የሚሆኑት ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፓወል እስራኤልን ሲጎበኙ ከአራፋት ጋር እንዲገናኙ ይፈልጉ ነበር፡፡ ሻሮንን በተመለከተ 30 ከመቶ የሚሆኑት ብቻ ታማኝ እንደሆኑ የሚያምኑ ሲሆን፣ 35 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ ጦር ናፋቂ እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡ 20 ከመቶ የሚሆኑት አሸባሪ ሲሏቸው 25 ከመቶዎቹ የዩናይትድ ስቴትስ ጠላት ብለዋቸዋል፡፡[128]

ከአንድ ዓመት በኋላ ግንቦት 2003 ላይ በሜሪላንድ ዩኒቨርስቲ የተደረገ ሌላ ጥናት ይፋ እንዳደረገው 60 ከመቶ የሚሆኑ አሜሪካውያን እስራኤል የመካከለኛውን ምሥራቅ ችግር ለመፍታት የአሜሪካን ጫና የማትቀበል ከሆነ የሚሰጣት እርዳታ እንዲቋረጥባት ይሻሉ፡፡ ይህ አሃዝ በፖለቲካው መስክ ንቁ ተሳትፎ በሚያደርጉ አሜሪካውያን ዘንድ ወደ 70 ከመቶ ከፍ ብሎ ተገኝቷል፡፡ እርግጥ ነው 73 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ ዩናይትድ ስቴትስ ሁለቱንም ወገኖች እንዳትረዳ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ 17 ከመቶ የሚሆኑት አሜሪካውያን ብቻ የእስራኤልና ፍልስጤማውያን ግጭት ‹‹በሽብርተኝነት ላይ የሚደረገው ጦርነት አካል ነው›› የሚለውን የቡሽና የሻሮን ሀሳብ የሚጋሩ መሆናቸውን ማወቅ ጠቃሚ ነው፡፡ 54 ከመቶ የሚሆኑ የመጠይቁ መላሾች ደግሞ ሁለቱ ቡድኖች ለቁራጭ መሬት ሲሉ የሚጋደሉ መሆናቸውን እንደሚያምኑ ገልጸዋል፡፡ ይህ ጥናት በተጨማሪም ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ አሜሪካውያን ስለ ሮድ ማፕ የሚያውቁት ዝርዝር ነገር ባይኖርም 55 ከመቶ የሚሆኑት ለሮድ ማፕ አዎንታዊ አመለካከት አላቸው፡፡ የሮድ ማፕን ጠቃሚነትና በውስጡ የያዛቸውን ቁልፍ ጉዳዮች ከተገነዘቡ በኋላ ደግሞ ደጋፊዎቹ ወደ 75 ከመቶ ከፍ ብለዋል፡፡ [129] በ2005 የፀረ-ስም ማጥፋት ሊግ (ኤ.ዲ.ኤል.) ባደረገው ተመሳሳይ ጥናት 78 ከመቶ የሚሆኑ አሜሪካውያን መንግሥታቸው እስራኤልንም ሆነ ፍልስጤማውያንን መደገፍ እንደሌለበት የሚያምኑ መሆናቸውን ይፋ አድርጓል፡፡[130]

በእስራኤል ላይ ጫና ማሳረፍ የአሜሪካን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስከብር ሆኖ እስከተገኘ ድረስ የአሜሪካ ሕዝቦች እንደሚደግፉት ከመስከረም 11 በኋላ ተረጋግጧል፡፡ ፕሬዚዳንት ቡሽም ቢሆኑ ፍልስጤማውያን የራሳቸውን

መንግሥት እንዲመሠርቱ ማስቻል የእስራኤል ፍልስጤምን ግጭት የሚያበቃ ብቸኛው መፍትሄ መሆኑን አምነው ተቀብለዋል፡፡ የእርሳቸው አስተዳደርም ያንን ግብ ለማሳካት በተለያዩ አጋጣሚዎች ሙከራ አድርጓል፡፡ ሆኖም ግን ዋናው ቁልፍ ጉዳይ የሕዝቦች አስተያየት በጎ መሆን ወይም የፕሬዚዳንቶች መነሳሳት አይደለም፡፡ እስራኤል የሰላሙን ሃሳብ እንድትቀበል ዩናይትድ ስቴትስ ጫና እንዳታደርግባት ሁሉንም ነገር ያወሳሰበውና እንዳይቻል ያደረገው ሎቢው ነውና፡፡

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው የቡሽ አስተዳደር የፍልስጤማውያንን መንግሥት መቋቋም የሚመለከተውን ሃሳብ በ2001 ማብቂያ ላይ ነበር የደገፈው፡፡ በ2002 ፀደይ ላይ እስራኤል በምዕራባዊው ዳርቻ ከሚገኙ በርካታ ፍልስጤማውያን አካባቢዎች ኃይሏን ታስወጣ ዘንድ ለመምከርና የሰላሙን ሂደት ለማስጀመር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ኮሊን ፓወል ወደዚያው ላከ፡፡ በዚያው ዓመት ቡሽ የሮድ ማፕን የሰላም እቅድ ይፋ ያደረጉ ሲሆን፣ እቅዱ ነፃና ዲሞክራሲያዊ የሆነ የፍልስጤም መንግሥት የሚመሠረትበትን የጊዜ ሰሌዳ ያካተተ ነበር፡፡ በቀጣዩ ዓመት ቡሽ ወደመካከለኛው ምሥራቅ ተጉዘው የሮድ ማፕን የሰላም ሃሳብ ለማነቃቃት ጥረት አደረጉ፡፡ እስራኤል በ2006 በወሰደችው የተናጠል እርምጃ ከተሰናከለ በኋላም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ ኮንዶሊዛ ራይስ ግጭቱን ለማስቆም የሚያግዙ ተደጋጋሚ ጥረቶችን አድርገዋል፡፡

በእያንዳንዱ አጋጣሚ ሎቢው የቡሽ አስተዳደርን ጥረቶች ለማምከን በፍጥነትና በብቃት ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ በሎቢው ውስጥ ያሉ ቡድኖች ይህን ጥረታቸውን ለማሳካት የተለያዩ ታክቲኮችን ይጠቀሙ የነበረ ሲሆን፤ ከእነርሱም ውስጥ ግልጽ ደብዳቤ መጻፍ፣ በኮንግረሱ ውስጥ የሚጠቅማቸውን ውሳኔ እንዲያልፍ መጣር፣ የተለያዩ የሕትመት ውጤቶችን የአስተያየት መስጪያን (Op-ed) በሚገባ መጠቀም፣ ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠት፣ ከአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣናት፣ ተጽእኖ ፈጣሪ ከሆኑ የአይሁድ መሪዎችና ወንጌላውያን ቡድኖች ጋር ቀጥተኛ ውይይቶችን ማድረግ ይገኙበታል፡፡ ኢሊዮት አብራምስን የመሳሰሉ አፍቃሪ-እስራኤል የመንግሥት ባለሥልጣናት በበኩላቸው የእስራኤል ባለሥልጣናት የሰላሙን ሃሳብ ውድቅ እንዲያደርጉ የበኩላቸውን ግፊት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ቡሽ የሰላሙን ሃሳብ ለማራመድ ተጽእኖ በማድረግ

ፋንታ (የሮድ ማፕን የሰላም እቅድ ዳር ለማድረስ የእስራኤልን ትብብር በጽኑ ከመሻት ይልቅ) ሩጫቸውን ያሳረጉት የሻሮንን (በኋላም የኦልመርትን) ፖሊሲ በመደገፍ ነበር። የቀድሞው የብሔራዊ ፀጥታ አማካሪ ብሬንት ስኮውክሮፍት ጥቅምት 2004 ላይ እንዲህ የሚል ትችት ሰንዝረው ነበር፡- ‹‹ሻሮን ፕሬዚዳንት ቡሽን በትንሿ ጣታቸው ላይ አስረው እያሽከረከሯቸው ነው።››[131]

እስራኤል የዩናይትድ ስቴትስን ተጽእኖ መቃወምና መጣስ ብቻ ሳይሆን ፍልስጤማውያንን በተመለከተ እርሷ መከተል የመረጠችውን መንገድ ጭምር እንድትጓዝበት ማድረጉ ተሳክቶላታል። ይህም በፈቀደኛነት የተደራጁት የተለያዩ አፍቃሪ-እስራኤል ቡድኖች የፖለቲካ ጡጫ ውጤት መሆኑ ነው። ምንም እንኳን የሕዝብ አስተያየት መለኪያዎች በስፋት እንደሚያመለክቱት ፍልስጤማውያን የራሳቸውን መንግሥት እንዲመሠርቱ መደረጋቸውን አሜሪካውያን የሚደግፉ ቢሆንም፣ በሎቢው ውስጥ ያሉ ቡድኖች በተለይም ደግሞ ጠጣሩን መስመር የሙጥኝ ያሉት ክፍሎች ይህን አይቀበሉም። በመሆኑም አይፓክ እና የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስን የመሳሰሉን ከባባድ የሎቢ ድርጅቶች በዩ.ኤስ. አሜሪካ ባለሥልጣናትና በሚከተሏቸው የፖሊሲ አማራጮች ላይ በሚያሳድሩት ጫና ምንም እንኳን እንደ አጠቃላይ ሁኔታው ለዩናይትድ ስቴትስም ሆነ ለእስራኤል መጥፎና ጎጂ ቢሆንም ሁልጊዜም አሸናፊዎች ለመሆን ችለዋል።

እስራኤል በፍልስጤማውያን ላይ የምትከተላቸውን ፖሊሲዎች ዩ.ኤስ.አሜሪካ በዘላቂነት እንድትደግፍ ማድረግ በሎቢው ውስጥ ያሉ ቡድኖች ዋነኛው ግብ ቢሆንም፣ ዓላማቸው ግን በዚህ ላይ ብቻ የሚገታ አይደለም። እስራኤል የክልሉ የበላይ ሆና እንድትቆይ የሚያስችላትን እርዳታ አሜሪካ እንድትለግሳትም ይሻሉ። የእስራኤል መንግሥትና ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚገኙ አፍቃሪ-እስራኤል ቡድኖች የቡሽ አስተዳደር ኢራቅን' ሶሪያንና ኢራንን አስመልክቶ የሚከተላቸውን ፖሊሲዎች ለመቅረጽም ሆነ መካከለኛው ምሥራቅን እንዳሻቸውና በሚፈልጉት መንገድ እንደገና ለማደራጀት ይሠራሉ። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ሎቢውና እስራኤል፣ ዩ.ኤስ.አሜሪካ በኢራቅ ላይ የ2003ቱን ወረራ እንድታደርግና አጠቃላይ ክልሉን ወደ ዲሞክራሲያዊ እርምጃ የመውሰድ ተስፋ እንዲያድርባት እንዴት ተጽእኖ እንዳሳደሩባት እንመለከታለን።

ምዕራፍ ስምንት

ኢራቅንና መካከለኛው ምሥራቅን ወደ ዲሞክራሲ የማሸጋገር ህልም

ለመሆኑ ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅን ለምን ወረረች? ‹The Assassins Gate: America in Iraq› በተባለው መጽሐፉ ጆርጅ ፔከር የሚከተለውን ብሏል፡- “ይህን ጥያቄ በእርግጠኝነት መመለስ አይቻልም፡፡ ስለሆነም የኢራቅን ጦርነት የሚመለከተው ይህ ጥያቄ እጅግ በጣም አስደናቂ ምስጢር እንደሆነ ይቆያል፡፡” በቡሽ አስተዳደር የመጀመሪያ ፕሬዚዳንታዊ ዘመን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፖሊሲ ዕቅድ አውጪ ዋና ዳይሬክተር የነበሩት ሪቻርድ ሄል እንዲህ ማለታቸውን ፔከር ጽፏል፡- ‹‹የዚህን ጥያቄ መልስ ሳላውቅ ወደ መቃብሬ እወርዳለሁ፡፡››[1]

በአንድ በኩል በጉዳዩ ላይ በአንዱ ወይም በሌላው መልኩ እጃቸውን ያስገቡ ሰዎች ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ያለማግኘታቸውንና ጥርጣሬ ላይ መውደቃቸውን ለመረዳት አያስቸግርም፡፡ ምክንያቱም ሳዳም ሁሴንን ለመጣል ያደረጉት ውሳኔ አሁንም ቢሆን ለማሰብ የሚከብድ ነገር ነውና፡፡ ሳዳም ሁሴን ምህረት የማያውቅ' አምባገነንና የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ መጨበጥን ጨምሮ በርካታ የሚያስጨንቁ ሕልሞች የነበሩት ሰው ቢሆንም፣ በጊዜው የነበረው ብቃት እነዚህን ሕልሞችን እውን ለማድረግ አላስቻለውም ነበር፡፡ ያደራጀው ታላቅ ጦር በ1991 የባህረ ሰላጤው ጦርነት ክፉኛ የተመታበት ከመሆኑም በላይ፣ ከዚያ በኋላም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባስተባበረው ማዕቀብ ለረዥም ጊዜያት ኃይሉ ሲዳከም ቆይቷል፡፡ በዚህ ሳቢያ ኃያልነቱ በወረቀት ላይ ብቻ ሆኖ የቀረው የኢራቅ ጦር በ2003 በአሜሪካና በአጋሮቿ ኃይል በቀላሉ ሊፍረከረክ በቅቷል፡፡ የተባበሩት መንግሥታት የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ተቆጣጣሪ ቡድን የኢራቅን የኒኩሌር መርሐ-ግብር ሙሉ በሙሉ ያጠፉ ሲሆን፣

በመጨረሻም ሳዳም በመጋዘን ያስቀመጣቸውን የኬሚካልና ባዮሎጂካዊ መሣሪያዎቹን እንዲያወድም ተገድዷል። በሳዳም ሁሴንና በኡሳማ ቢን ላደን መካከል አለ ስለሚባለው ግንኙነት (በእርግጥ ሁለቱ የማይስማሙ ጠላቶች ነበሩ) ትክክለኛና አሳማኝ ማስረጃ ማቅረብ ካለመቻሉም በላይ፣ በወቅቱ ቢን ላደንና ባልደረቦቹ አፍጋኒስታን ወይም ፓኪስታን ውስጥ ይገኙ የነበረ መሆኑ ይታወቃል። ይህ በእንዲህ እያለ ማንም መገመት እንደሚችለው ከመስከረም 11 በኋላ ዩናይትድ ስቴትስ በአል-ቃዒዳና በታሊባን ላይ አትኩሮቷን ታደርጋለች ተብሎ ሲታሰብ የዓለም ንግድ ማዕከልንም ሆነ ፔንታጎንን ካነሳዱት አካላት ጋር ምንም ግንኙነት የሌላት የሆነችውንና በየጊዜው እየተዳከመች የሄደችውን ኢራቅን ለመውረር ተነሣች። ውሳኔውን ከዚህ አቅጣጫ ሲመለከቱት እውነትም በጣም የሚያስገርም ነው።

ከሌላ አቅጣጫ ከተመለከትነው ግን ውሳኔውን ለመገንዘብ ያን ያክል ከባድ አይሆንም። ዩናይትድ ስቴትስ በዓለም ላይ እጅግ ኃያሏ ሀገር በመሆኗ እርሷ እስከፈለገች ድረስ ሳዳምን ለማባረር እንደማያቅታት የታወቀ ነው። ዩናይትድ ስቴትስ ረዥም ጊዜ የፈጀውን የቀዝቃዛውን ጦርነት ድል ያጣጣመች ሲሆን፣ በትልቁ ቡሽ ጊዜ ደግሞ በ1991 ኢራቅን ከኩዌት አባርራለች። በ1995 ላይም የባልካንን ጎሣዎች እርስበርስ ከመጫረስ በመታደግ በ1999 ላይ ሰርቢያን ክፉኛ ቀጥቅጣ የክልሉን ሰላም አስተማማኝ ለማድረግ ጥራለች። ከመስከረም 11ዱ ውርጅብኝ በኋላ የአፍጋንን የታሊባን መንግሥት በፍጥነት መገርሰስ መቻሏ ሲደመርበት የጦር ኃይሏን የአይበገሬነት ገጽታ ከፍ ያደረገው በመሆኑ ወደ ኢራቅ መዝመት አላስፈላጊና ብልህነት የጎደለው መሆኑን ጦርነቱን ለመክፈት ላቆበቆቡት ፖለቲከኞች ተናግሮ ለማሳመን ሁኔታዎችን አስቸጋሪ አድርጓቸዋል። አሜሪካውያን በእርግጥም መስከረም 11 ከደረሰው አደጋ በኋላ በጣም የደነገጡ በመሆናቸው በአቅራቢያቸውም ይሁን ራቅ ባለ ቦታ የሀገራቸውን ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ማንኛውንም የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ለመታጠቅ የሚፈልግን ኃይል እንደማይታገሱ ግልጽ ነበር። ያ ጦርነት እንዲደረግ ጽኑ ፍላጎት ያሳዩ ክፍሎች ሳዳምን በማስወገድ በአካባቢው ያሉ በእነርሱ አጠራር- ወስላታ (rouge) መንግሥታት አሜሪካ ከፈለገች ካ

ተረኞቹ እነርሱ እንደሚሆኑ በማሰብ ፈርተው አካሄዳቸውን ለማስተካከል እድል ይሰጣቸዋል የሚል እምነት አሳደሩ። ስለሆነም ጦርነቱ ከመደረጉ በፊት ዩናይትድ ስቴትስ በተመሳሳይ ጊዜ በአንድ በኩል እጅግ ጉልበት ያላትና በጦር ኃይሏ የምትተማመን በሌላ በኩል ደግሞ በደረሰባት አደጋ ክፉኛ የቆሰለችና መፃዒውን ጊዜም ፀጥታዋን አስመልክቶ ሥጋት ያየለባት ሆና ትገኝ ነበር። ይህ ደግሞ እንዳለመታደል ሆኖ አደገኛ የሆነ ቅንጅት በመሆኑ ጦርነቱን አይቀሬ አደረገው።[2]

እነዚህ ሁሉ ነገሮች አንድ ላይ ተደምረው ከስትራቴጂያዊ አግባብ አንፃር ሲመዘኑ ጦርነቱ እንዲደረግ የሚያስወስን ሁኔታን የፈጠሩ ሲሆን፣ ያንን ምርጫ የአሜሪካ አስተዳደር ይበልጥ እንዲገፋበት የሚቀሰቅሱ ኃይሎች መኖራቸውን ደግሞ መገንዘብ አይከብድም። ይሁን እንጂ በዚህ ስሌት ውስጥ ያልተካተተና እርሱ ባይኖር የኢራቅ ጦርነት እንደማይካሄድ በእርግጠኝነት መናገር የሚያስችል ሌላ ምክንያትም አለ። ያ መሠረታዊ ነገር የእስራኤል ሎቢ ሲሆን በተለይም የኒዎኮንሰርቫቲቭ የፖሊሲ አውጪዎችና በፖለቲካው ጨዋታ የተካኑ አፍቃሪ-እስራኤል ባለሥልጣናት ከመስከረም 11ዱ ጥቃት በኋላ ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅን እንድትወር ደጋግመው ይትጉቱ ነበር። እነዚያ የጦርነት አናፋሽ አንጃዎች ሳዳምን ማስወገድ የአሜሪካንና የእስራኤልን ስትራቴጂያዊ አቋም የሚያሻሽል እንደሆነና ክልሉን ወደ ዲሞክራሲያዊ አምባነት በመቀየር ዩናይትድ ስቴትስንም ሆነ እስራኤልን በእኩል ደረጃ ይጠቅማል የሚል እምነት ነበራቸው። እናም የእስራኤል ባለሥልጣናትና የቀድሞ የእስራኤል መሪዎችም ዕቅዱን ደግፈው ተነሱ። ምክንያቱም ዩናይትድ ስቴትስ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት ቀንደኛ ጠላቶቻቸው አንዱንና በ1991 በስከድ ሚሳዬል የደበደባቸውን ባላንጣቸውን ስትገነድስላቸው ለማየት በመጓጓታቸው ነው።

የሆነ ሆኖ እስራኤልና ሎቢው ያሳደሩት ተጽእኖ የቡሽ አስተዳደር ኢራቅን በ2003 እንዲወር ያስቻለው ብቸኛ ምክንያት አይደለም ሊባል ቢችልም፣ ወሳኝ የሆነው መሠረታዊ ነገር ነው ማለት ግን ይቻላል። ብዙ አሜሪካውያን ጦርነቱ ለነዳጅ ሲባል (ሃሊበርተን ለተባለው የአሜሪካ ነዳጅ ኩባንያ ግዙፍ ጥቅም ለማስገኘት) የተደረገ እንደሆነ ያምናሉ። ይሁን እንጂ

ጉዳዩ እንዲያ መሆኑን ለማሳመን የሚያግዙ ጠንካራ ማስረጃዎች አልተገኙም፡፡ ሌሎች ታዛቢዎች ደግሞ በቡሽ አስተዳደር ውስጥ የነበሩና ካርል ሮክን የመሰሉ የፖለቲካ አማካሪዎችን ተጠያቂ በማድረግ ጦርነቱ ሀገሪቱ (አሜሪካ) በሪፖብሊካኖች እጅ እንደሆነች እንድትቆይ ለማድረግ የተወጠነ ማኪያቬሊያዊ ዘዴ ነው ይላሉ፡፡ እርግጥ ነው ይኼኛው ሀሳብ የተወሰኑ ደጋፊዎችን አላጣም፡፡ ሆኖም ግን የአባባሉን እውነተኛነት የሚደግፉ በቂ ማስረጃዎች ካለመኖራቸውም በላይ፣ ዋና ዋና የሚባሉ ዲሞክራቶች ጦርነቱን የደገፉበትን ሁኔታ በተጨባጭ ማብራራት አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ጦርነቱ መካከለኛውን ምሥራቅ ወደ ዲሞክራሲ ለማሸጋገር የተደረገ የመጀመሪያው ግልጽ ጥረት እንደሆነም ተነግሯል፡፡ ይህ አመለካከት እውነት ነው፡፡ ዳሩ ግን ወደፊት በዝርዝር እንደምናየው ብዙ ተስፋ የተጣለበት ይህ ዕቅድ የእስራኤልን ፀጥታ በማረጋገጡ ላይ ይበልጥ ያዘነበለ ነበር፡፡

እስካሁን ከተጠቀሱት አማራጭ ገለጻዎች በተለዩ መልኩ በእኛ እምነት ጦርነቱ የተካሄደው ቢያንስ በመልካም ጎኑ እስራኤልን ይበልጥ ከስጋት ነፃ ለማድረግ በነበረ ፍላጎት ነው፡፡ ይህ ፍላጎት ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት አወዛጋቢ የነበረ የመሆኑን ያክል አሁንም ይበልጥ አወዛጋቢ ሆኖ በመቀጠሉ ኢራቅን ወደ ስትራቴጂያዊ ውድመት ቀይሯታል፡፡ ይበልጥ ግልጽ ለመሆን ጦርነቱ እንዲደረግ የገፋፉ ግለሰቦችና ቡድኖች በሂደቱ እስራኤልም ሆነች አሜሪካ ተጠቃሚዎች እንደሚሆኑ ነበር ያመኑት፡፡ ሆኖም ግን ሊከተል የሚችለውንም ውድቀት አስቀድመው መገመት ያለመቻላቸው ያገጠጠ ሃቅ ነው፡፡

የተለያዩ ማስረጃዎችን ከመመርመራችን በፊት በርካታ ቁጥር ያላቸው አዋቂዎችና የተከበሩ ሰዎች ጦርነቱ በቀጥታ ከእስራኤል ፀጥታ ጋር ግንኙነት ያለው እንደሆነ በግልጽ መናገራቸውን እንመልከት፡፡ ለአብነት ያክል (ከ2001-2003) የፕሬዚዳንቱ የውጭ ጉዳይ ደህንነት አማካሪ ቦርድ አባል የነበረውና የ9/11 መርማሪ ኮሚሽን ዋና ዳይሬክተር በመሆን ያገለገለው፣ እንዲሁም ከ2005 - 2006 የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮንዶሊዛ ራይስ አማካሪ ሆኖ የሠራው ፊሊፕ ዘሊኮው መስከረም 10/2002 በቨርጂኒያ ዩኒቨርስቲ ለተሰበሰቡ አድማጮች ሳዳም ለአሜሪካ ቀጥተኛ ስጋት

እንዳልሆኑ ገልጿል፡፡ ‹‹ሳዳም እውነተኛ ስጋት የሚፈጥሩት›› አለ ዘሊኮው፡- ‹‹ለእስራኤል ብቻ ነው፡፡››[3]

በጡረታ የተገለሉት የኔቶ የቀድሞ አዛዥና የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ተወዳዳሪ ዊስሊ ክላርክ ነሐሴ 2002 ላይ እንዲህ ብለው ነበር፡- ‹‹ሳዳም ሁሴን ለአሜሪካን ስጋት አይፈጥሩም መባሉ ምናልባትም እውነት መሆኑን ጦርነቱን የደገፉ ወገኖች አሁን በቅንነት ሊነግሯችሁ ይችላሉ፡፡ ግና የኒኩሌር መሣሪያ ታጥቀው ከሆነ በእስራኤል ላይ ሊጠቀሙት ይችላሉ የሚል ስጋት እንደነበራቸው አይሸሽጉችሁም፡፡›› [4]

ሪቻርድ ፐርል በሚመሩትና ኢንፍሎዌንሻል ዲፈንስ ፖሊሲ ቦርድ በተባለው ድርጅት ውስጥ በአባልነት የሚሠሩትን እውቅ ኒዎኮንሰርቫቲቭ ምሁር ሩት ዌድግውድን አንድ የጀርመን ጋዜጠኛ ጥር 2003 ላይ ቃለ መጠይቅ አድርጎላቸው ነበር፡፡ ‹‹ለምን ይሆን ጦርነቱን (የኢራቅን ማለት ነው) የሚደግፉት?›› በማለት ጠየቃቸው፡፡ እርሳቸውም፡- ‹‹ትህትና የጎደለኝ ልሆን እችላለሁ፡፡›› ካሉ በኋላ ጀርመን ከእስራኤል ጋር ያላትን ልዩ ግንኙነት አስታውሰው ወደተጠየቁት ጥያቄ መልስ በማለፍ ‹‹ሳዳም በአሁኑ ጊዜ በእስራኤል ላይ የደቀነው ስጋት አለ፡፡ ይህ ነው ቀላሉ እውነታ›› አሉ፡፡ ዌድግ ጉድ የጦርነቱን ምክንያታዊነት ለመግለጽ ኢራቅ በጀርመን ወይም በዩናይትድ ስቴትስ ላይ ስጋትን ደቅናለች ለማለት አልዳዳቸውም፡፡[5]

ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅን ከመውረሯ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ጋዜጠኛው ጆ ክሌይን በታይምስ መጽሔት ላይ የሚከተለውን ጽፎ ነበር፡-

‹‹ጠንካራዋ እስራኤል ከኢራቅ ጋር የሚደረገውን ጦርነት ምክንያታዊነት እጅግ በጣም ተቀብላዋለች፡፡ እናም ስማቸውን ለመጥቀስ ባንደፍርም በቡሽ አስተዳደር ውስጥ በሚገኘው የኒዎኮንሰርቫቲቭ አንጃ አባላትና በበርካታ የአሜሪካ አይሁድ ማህበረሰብ ዘንድ ጉዳዩ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው እንደሆነ እናውቃለን፡፡››[6]

የቀድሞው ሴናተር ኧርነስት ሬሊንግስ ተመሳሳይ የሆነ ሀሳብ በግንቦት ወር 2004 ላይ በመሰንዘር ኢራቅ በቀጥታ ለአሜሪካ ስጋት እንደማትፈጥር ከገለጹ በኋላ፣ ‹‹ያቺን ሀገር የምንወራት ለምንድን ነው?››[7] የሚል ጥያቄ

ያነሳሉ፡፡ ‹‹መልሱን ሁሉም ያውቀዋል›› ካሉ በኋላ አያይዘው ‹‹ምክንያቱም የወዳጃችንን የእስራኤልን ፀጥታ የተረጋገጠ ለማድረግ ነው›› በማለት ሀሳባቸውን አጠቃልለዋል፡፡ ይህን ንግግራቸውን ተከትሎ በርካታ የታወቁ የአይሁድ ቡድኖች ሬሊንግስን ፀረ-ሴማዊ በማለት ፈርጀዋቸዋል፡፡ የፀረ-ስም ማጥፋቱ ሊግ (ኤ.ዲ.ኤል) በተለይ ‹‹ይህ፣ አይሁዳውያን ዓለምን ለመቆጣጠርና እንደፈለጉ ለማሽከርከር ሴራ እየሸረቡ ነው የሚል ያረጀና ያፈጀ የፀረ- ሴማዊነት አሉባልታ ርዝራዥ አስተሳሰብ ነው››[8] በማለት ነበር የወነጀላቸው፡፡ ይሁን እንጂ ሆሊንግስ ክሱን የማይቀበሉ መሆኑን በመግለጽ ቀደም ባሉት ዘመናት የአይሁዳውያን ጠንካራ ደጋፊ መሆናቸውን ጠቅሰው የተናገሯቸው ነገሮች በሙሉ ግልጽና በእውነታ ላይ የተመሠረቱ እንደመሆናቸው ‹‹እኔን ፀረ- ሴማዊ በማለታችሁ ይቅርታ እንዳደርግላችሁ ልትጠይቁኝ ይገባል››[9] በማለት ተቺዎቻቸውን ገስጸዋል። ፓትሪክ ቡቻናን፣ አርኖልድ ደ ቦርችግራቭ ማውሪን ዳውድ፣ ጆርጅ አኔጊየር፣ ጋሪ ሃርት፣ ክሪሰ ማቲውስ፣ የቨርጂኒያው ዲሞክራት ኮንግረስማን ጀምስ ፒ ሞራን፣ ሮበርት ኖቫክ፣ ቲም ሩሰርት እና ጄኔራል አንቶኒዞኒ የተባሉ ታዋቂ ሰዎች፣ ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅን እንድትወር አፍቃሪ-እስራኤል ጠጣር መስመረኞች ግፊት እያደረጉ መሆናቸውን ተናግረዋል ወይም ፍንጭ ሰጥተዋል።[10] ሮበርት ኖቫክ በተለይ ጦርነቱ ከመደረጉ በፊት፡- ‹‹የሻሮን ጦርነት›› በማለት የሰየሙት ሲሆን እስከዛሬም እንደዚያ እያሉ ነው የሚጠሩት፡፡ ሚያዝያ ወር 2007 ላይ ኖቫክ እንዲህ ሲሉ ተደመጡ፡- ‹‹ያ ጦርነት እንዲጀመር በተደረገው ውሳኔ ላይ የእስራኤል ድርሻ ታላቅ እንደሆነ አምናለሁ፡፡ ገና ጦርነቱ ሳይጀመር በዋዜማው ሻሮን ከሴናተሮች ጋር ተቀራርበው ሲነጋገሩ፡- ‹አሜሪካውያን ሳዳም ሁሴንን ማስወገዱ ከተሳካላቸው የእስራኤል የፀጥታ ችግሮች እንደሚወገዱ አምናለሁ› ብለዋል፡፡››[11]

እስራኤል ከኢራቁ ጦርነት ጋር ያላት ግንኙነት ጦርነቱ ከመጀመሩ ከብዙ ጊዜ በፊት ጀምሮ በሰፊው ይታወቅ ነበር፡፡ አሜሪካ ልታደርገው ያሰበችው ወረራ ዜና 2002 ማለቂያ አካባቢ የተለያዩ ጋዜጦችን ርዕሶች ባጣበበባቸው ጊዜያት ሚካኤል ኪንስሊ የተባለው ጋዜጠኛ የሚከተለውን ጽፎ ነበር፡- ‹‹የእስራኤልን ሚና አስመልክቶ ሕዝቡ ውይይት እንዲያደርግ አልተፈቀደለትም፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥ ተዘግቶበት እንደተቀመጠ ዝሆን

ማለት ነው። እስራኤል ከጦርነቱ ጋር ግንኙነት እንዳላት ሁሉም ሰው ያውቃል። ነገር ግን ማንም ስለእርሱ አያነሳም።››[12] ለዚህ ዋነኛው ምክንያት እንደሚካኤል አገላለጽ፣ ‹‹ፀረ-ሴማዊ እባላለሁ ብሎ መፍራት ነው።›› ጦርነቱ ከመጀመሩ ሁለት ሳምንት በፊት ናታንጉትማን በሃ›ኤሬትዝ ጋዜጣ ላይ ባወጣው ዘገባ ‹‹እስራኤልን ከጦርነቱ ጋር የሚያያይዙ ድምፆች በየጊዜው ከፍ እያሉ ነው። ጆርጅ ቡሽ እስራኤልን ለመርዳት ያላቸው ፍላጎት የአሜሪካን ወታደሮች ታላቅ ወደሆነው የባሕረ ሰላጤው ጦርነት እንዲልኳቸው የሚያደርጋቸው ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ በነዚህ ድምጾች ይታመናል። ድምፆቹ የሚመጡትም ከየአቅጣጫው ነው›› ብሏል።[13] ከጥቂት ቀናት በኋላ ቢል ክለር (አሁን የኒውዮርክ ታይምስ ዋና አዘጋጅ ነው)። ሲጽፍ፣ ‹‹ይህ ጦርነት ለእስራኤል ተብሎ የሚደረግ ጦርነት ነው የሚለው ሃሳብ ከምናስበው በላይ በስፋት የሚነገርና የብዙዎች ጽኑ አቋም ሆኗል›› ብሏል።[14] በመጨረሻም ጦርነቱ ካበቃ ከሁለት ዓመታት በኋላ ግንቦት 2005 ላይ የአሜሪካ አይሁድ ኮሚቴ አባል የሆኑት ባሪ ጃኩብ እንዳመኑት እስራኤልና ኒዎኮንሰርቫቲቮች፣ ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅን እንድትወር በማድረግ ኃላፊነቱን እንደሚሸከሙ ሲነገር የነበረው አባባል በዩ.ኤስ የደህንነት አባላት ዘንድ ‹‹መጥፎ ሁኔታ›› ተደርጎ ነበር የሚቆጠረው።[15]

አንዳንዶች በእርግጠኝነት እንደሚከራከሩት የቡሽ አስተዳደር ኢራቅን ለመውረር የወሰነው ለእስራኤል ደህንነት በማሰብ ነው የሚል ወገን ሁሉ ፀረ-ሴማዊ አሊያም ደግሞ አይሁዳውያንን የሚጠላ ነው። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቶች ክሶች በአብዛኛው ሀሰተኛ ውንጀላዎች ናቸው። በቀጣዮቹ ምዕራፎች ይበልጥ ልናሳየው እንደምንጥረው ሎቢው ያ ጦርነት እንዲደረግ ያሳደረው ተፅእኖ ወሳኝ እንደነበር የሚያመለክቱ በርካታ ማስረጃዎች አሉ። ይህ ማለት ግን እስራኤልም ሆነች ሎቢው የአሜሪካን የውጭ ፖሊሲ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረውታል ብሎ ማረጋገጫ መስጠት አይደለም። ከዚያ ይልቅ እነዚያ አካላት (እስራኤልም ሆነች ሎቢው) በተወሰነ ፖሊሲ እና አጀንዳ ዙሪያ የሚፈልጉትን ግብ ለመምታት ተፅእኖአቸውን ሲጠቀሙ ቆይተዋል ማለት ነው። ሁኔታዎች ከዚህ የተለዩ መልክ ቢኖራቸው ኖሮ፣ ዩናትድ ስቴትስ ወደኢራቅ ጦርነት አትገባም፣ እስካሁንም እዚያ አትገኝም ነበር።

እስራኤልና የኢራቅ ጦርነት

እስራኤል ምንጊዜም ኢራቅን እንደጠላት ስትቆጥራት ቆይታለች፡፡ በተለይም በ1970ዎቹ ፈረንሳይ ለሳዳም ሁሴን የኒውክሊየር ማፀግበሪያ (Neculear Reactor) ልትሰጣቸው በተስማማች ጊዜ ጉዳዩ ይበልጥ አሳሰባት፡፡ ከሁሉም በላይ ያስጨነቃት ኢራቅ ምናልባት የኒውኩሌር ማፀግበሪያውን አቶሚክ ቦምብ ለማምረት ልትጠቀምበት የመቻሏ ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህ ሥጋት ምላሽ ይሆናትም ዘንድ በ1981 ኦሲራክ የተባለውን የኢራቅ የኒውኩሌር ማፀግበሪያ ተቋም በሚገባ ሥራ ከመጀመሩ በፊት በቦምብ አጋዩችው፡፡[16] ኢራቅ ምንም እንኳን በተጠቀሰው መልክ መሰናክል ቢገጥማትም የኒውኩሌር መርሐ-ግብሯን በተበታተነና ምስጢራዊ በሆነ ሥፍራ እንደቀጠለችበት ይታመናል፡፡ ይህ ሁኔታ ነበር እንግዲህ እስራኤል የ1991ዱን የባህረሰላጤውን ጦርነት በሙሉ ስሜት እንድትደግፈው ያደረጋት፡፡ በዚያ ወቅት ዋናው ፍላጎቷ የኢራቅን ወታደሮች ከኩዌት ማስወጣት ሳይሆን ሳዳምን ከሥልጣን በማስወገድ በተለይም የኢራቅን የኒኩሌር መርሃ-ግብር ማፈራረስ ነበር፡፡[17] ዩናይትድ ስቴትስ በመጀመሪያው የባሕረ ሰላጤው ጦርነት ወቅት ሳዳም ሁሴንን ከሥልጣን ማባረር ባይሆንላትም፣ የተባበሩት መንግሥታት የጦር መሣሪያ ተቆጣጣሪዎች ቡድን በባግዳድ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ያም ቢሆን ታዲያ የእስራኤልን ስጋት ጨርሶ አላጠፋውም፡፡ ሃ›ኤሬቴዝ ጋዜጣ በየካቲት 26/2001 እትሙ ባሰፈረው ጽሑፍ ‹‹ኢራቅ በክልሉ ከኢራን የበለጠ ያለመረጋጋትን ፈጥራለች፡፡ እንደዚያ የሆነው ያልታረመና ኃላፊነት የጎደለው ባሕሪ ባላቸው ሳዳም ሁሴን ምክንያት መሆኑን ሻሮን ያምናሉ›› ብሏል፡፡[18]

የሻሮን አስተያየት እውነትም ተቀባይነት ያለው የሚያስመስለው ሁኔታ የተፈጠረው በ2002 የቡሽ አስተዳደር በኢራቅ ላይ ሌላ ጦርነት ለማድረግ ከምር እያሰበ መሆኑ በታወቀ ጊዜ ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ የተወሰኑ የእስራኤል ባለሥልጣናት ለዩ.ኤስ.ባለሥልጣናት ኢራን ከኢራቅ በበለጠ ሁኔታ አስጊ እንደሆነች ገልጸውላችው ነበር፡፡[19] ይሁን እንጂ የሳዳምን መወገድ

ካለመቃወማቸውም በላይ፣የቡሽ አስተዳደር ወደ ኢራቅ እንዳይዘምት ለማሳመን ፈጽሞ አልሞከሩም፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅን እንዳትወር በመቃወም ደጋፊዎቻቸው ሎቢ እንዲያደርጉ ለማነሳሳትም አልጣሩም፡፡ እንዲያውም የእስራኤል መሪዎች በተቃራኒው ሲጨነቁ የነበረው ምናልባትም ዩናይትድ ስቴትስ የሳዳምን ጉዳይ ብቻ ስትከታተል ኢራንን ችላ ልትላት ትችላለች እያሉ ነበር፡፡ የቡሽ አስተዳደር ክልሉን መልክ ለማስያዝ ታላቅ ዕቅድ ነድፎ መንቀሳቀስ ከጀመረ ኢራቅን በፍጥነት ድል አድርጎ ጊዜ ሳያጠፋ ወደ ኢራንና ሶሪያ ፊቱን እንዲመልስላቸው ማድረግ ነበር ትልቁ ግባቸው፡፡ እናም አሜሪካውያን ወረራውን እንዲያደርጉ በኃይል ግፊት ማድረጋቸውን ቀጠሉ፡፡

በአጭሩ ለማስቀመጥ እስራኤል በኢራቅ ላይ ዘመቻ እንዲደረግ የማነሳሳቱን ሥራ በግልጽ አልሠራችም ይባል ይሆናል፡፡ ያንን ያደረጉት ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያሉ ኒዎኮንሰርቫቲቮች ሲሆኑ፣ ከመስከረም 11 ጥቃት በኋላ የቡሽን መንግሥት ገፋፍተው ወደ ጦርነቱ በማስገባት ግንባር ቀደሙን ኃላፊነት ይወስዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ እስራኤል ኒዎኮንሰርቫቲቮችን በመገፋፋት ጦርነቱን ለቡሽ አስተዳደርና ለአሜሪካን ሕዝብ ለመሸጥ በግልጽ ከእነርሱ ጋር አላበረችም ማለት አይቻልም፡፡ እርግጥ ነው ጦርነቱ ከመደረጉ ከአንድ ወር በፊት የእስራኤል መሪዎች ሲጨነቁ የነበረው ምናልባት ቡሽ በመጨረሻው ሰዓት ጦርነቱን ላለማድረግ ይወስኑ ይሆናል ብለው ሲሆን፣ ፕሬዚዳንቱ እግራቸውን አለማቀዝቀዛቸውን ማረጋገጥ ይፈልጉ ነበር፡፡

እስራኤላውያኑ ጥረታቸውን የጀመሩት በ2002 የቡሽ አስተዳደር የኢራቅን ጦርነት ለአሜሪካ ሕዝብ ይፋ ከማውጣቱ ጥቂት ወራት አስቀድሞ ነበር፡፡ የቀድሞው የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንጃሚን ናታንያሁ ሚያዝያ አጋማሽ ላይ ወዲህ ወደ ዋሽንግተን ከመጡ በኋላ ሴናተሮችንና የዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ አዘጋጆችን እንዲሁም ሌሎች ታዋቂ ሰዎችን በማነጋገር ሳዳም የኒኩሊየር መሣሪያ እየሠሩ መሆኑንና በልብስ ወይም በሚታዘል ቦርሳ አማካይነት ወደ አሜሪካን ምድር ሊያስገቡት እንደሚችሉ ገለጹ፡፡[20] ይህ ከሆነ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ የሻሮን ቃል አቀባይ ሬናን ጌሰን ለክሌቭላንድ ሪፖርተር የሚከተለውን ተናገሩ፡- ‹‹ሳዳም ሁሴን አሁን

እንዲቆሙ ካልተደረገ ከአምስት ወይም ከስድስት ዓመታት በኋላ የኑክሊየር መሣሪያ ከታጠቀ፣ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎችን የማስወንጨፍ አቅም ካዳበረች ኢራቅ ጋር መደራደር ሊኖርብን ነው፡፡››[21]

በግንቦት ወር አጋማሽ ላይ የቀድሞው የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትርና አሁን ደግሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆኑት ሽሞን ፔሬዝ በሲ.ኤን.ኤን.ቱሌቪዥን መስኮት ብቅ ብለው ‹‹ሳዳም ሁሴን እንደ ቢን ላደን ሁሉ በጣም አደገኛ በመሆናቸው ዩናይትድ ስቴትስ እጇን አጣጥፋ በመቀመጥ የሚያደርሱትን ውድመት መጠበቅ የለባትም፡፡ ሳዳም የኒኩሌር መሣሪያ እያነጹ ባሉበት በአሁኑ ጊዜ እርሳቸውን ከሥልጣን የማስወገጃው ትክክለኛ ሰዓት ደርሷል›› በማለት ተናገሩ፡፡[22] ከአንድ ወር በኋላ ደግሞ ሌላው የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሁድ ባራክ በዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ የአስተያየት ማስፈሪያ አምድ (Op-ed) ላይ ባሰፈሩት ሃሳብ፡- ‹‹የቡሽ አስተዳደር ከሁሉም በፊት ማተኮር ያለበት በኢራቅና ሳዳም ሁሴንን በማስወገድ ላይ ነው፡፡ ሳዳም ከተወገዱ የአረቡ ዓለም ገጽታ የተለዬ ይሆናል›› ብለዋል፡፡ [23]

ነሐሴ 12 ቀን 2002 ባራክ ለክኔሴት (የእስራኤል ምክር ቤት) የውጭ ጉዳይና የመከላከያ ኮሚቴ ንግግር ባደረጉ ጊዜ፡- ‹‹ኢራቅ ለእስራኤል ታላቅ አደጋ ነች ›› ብለዋል፡፡ [24] ከዚያም ነሐሴ 16 ቀን ማለትም ምክትል ፕሬዚዳንት ዲክ ቼኒ የጦርነቱን መጀመር ናሽቪሊ ቴኔሲ ላይ በተደረገው የቀድሞ የውጭ ሀገር ዘማቾች ስብሰባ ላይ ከመግለጻቸው አሥር ቀናት ቀደም ብሎ ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅን ማጥቃቷን እንዳታዘገየው እስራኤል አጥብቃ ለመነቻት፡፡ ሻሮን ለቡሽ አስተዳደር ባቀረቡት ማሳሰቢያ፡- ‹‹ጦርነቱን ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ለወደፊቱ አካባቢውን አስተማማኝ ካለማድረጉም በላይ፣ በኋላ እርምጃ ለመውሰድ ያስቸግራል ›› ብለዋል፡፡

የሻሮን ቃል አቀባይ ሬናን ጊሰን በበኩላቸው፣ ‹‹ጥቃቱን ማንተቱ ለእርሱ (ሳዳምን ማለታቸው ነው) የጅምላ ጨራሽ መሣሪያውን አፋጥኖ እንዲሠራ ጊዜ መስጠት ነው›› አሉ፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፔሬዝ ደግሞ ለሲ.ኤን.ኤን.ቴሌቪዥን በሰጡት ቃለምልልስ እንዲህ አሉ፡- ‹‹ዛሬ ያለው ችግር ‹ቢሆን ኖሮ› የሚለው ሳይሆን ‹መቼ› የሚለው ነው፡፡ ስለሆነም የማጥቃቱን ጊዜ ማራዘሙ ታላቅ ስህተት መፈጸም ነው፡፡ ምክንያቱም ሳዳም እጃቸውን አጣጥፈው የሚቀመጡ ሰው አይደሉምና፡፡››

ምክትል የመከላከያ ሚኒስትሩ ዋይዝማን ሽሪ ተመሳሳይ ሃሳብ በመሰንዘር፣ ‹‹አሜሪካውያን ወረራውን አሁን ካላደረጉት ለወደፊቱ ማድረጉ የማይታሰብ ነው፡፡ በአንድና በሁለት ዓመት ውስጥ ሳዳም ሁሴን የጅምላ ጨራሽ መሣሪያቸውን ሰርተው ይታጠቃሉ›› ብለዋል፡፡ ሲቢ.ኤስ. ቴሌቪዥን በበኩሉ በመካሄድ ላይ ያለውን ሁኔታ ታዝቦ ላስተላለፈው ምርጥ ትንተና የሚከተለውን ርዕስ ሰጥቶት ነበር፡- ‹‹እስራኤል ዩ.ኤስ.አሜሪካን፡- ኢራቅን ማጥቃትሽን አታዘግይ፣ አለቻት፡፡››[25]

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ግን ፔሬዝና ሻሮን የሚያደርጉትና እያደረጉ ያሉት ግፊት ሁሉ ይፋ እንዲወጣና የጦርነት ናፋቂ መሆናቸው እንዲታወቅም ሆነ ዩናይትድ ስቴትስን ጦርነት ውስጥ እንድትገባ መገፋፋታቸው ትኩረት እንዲሰጠው አይፈልጉም፡፡ ከዚያ ይልቅ አሜሪካ የምትወስደውን እርምጃ ከራሷ ግምገማና መነሻ አንጻር እንድታደርገው ነበር የሚሹት፡፡[26] ይሁን እንጂ ፓትሪክ ቡቻናን የመሰሉ አንዳንድ አሜሪካውያን ተቺዎች ‹‹ከ1991ዱ የባሕረ ሰላጤው ጦርነት ጀርባ ሆነው ጦርነቱን ሲገፋፉ የነበሩት የእስራኤል መከላከያ ጦርና ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚገኙ ደጋፊዎቹ ናቸው›› ብለው እንደሚከራከሩ የእስራኤል መሪዎችም ሆኑ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ደጋፊዎቻቸው ያውቃሉ፡፡[27] ኃላፊነትን ከራስ ላይ መገፍተር ጥሩ የፖለቲካ ስሜት ሊሰጥ ይችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን የእስራኤል መሪዎች በየጊዜው ሲሰጧቸው ከነበሩ ይፋዊ መግለጫዎች መረዳት እንደሚቻለው ሳዳም የአይሁዳዊቷ ሀገር ዋነኛ ስጋት መሆናቸውን እንደሚያምኑና እርሳቸውን ከሥልጣን እንዲያወርድ የቡሽን አስተዳደር ይቀሰቅሱ እንደነበር ግልጽ ነው፡፡

የተለያዩ የዜና ዘገባዎች እንዳስተላለፉት ‹‹የእስራኤል የደህንነት ባለሥልጣናት ባሰባሰቡት መረጃ መሠረት ኢራቅ ባዮሎጂያዊና ኬሚካላዊ መሣሪያ ለመሥራት ጥረቷን እያፋጠነች መሆኑን ገልጸዋል፡››፡[28] ጌሬዝ ለሲ.ኤን.ኤን. ቴሌቪዥን በሰጡት አስተያየት፡- ‹‹እኛ የምናስበውና የምናምነው እርሳቸው (ሳዳም) የኒኩሌር መሣሪያ ለመታጠቅ በመጣር ላይ መሆናቸውን ነው›› ብለዋል፡፡[29] ሃ› ኤሬትዝ ፡- ‹‹ሳዳም በቅርቡ ለኢራቅ የአቶሚክ ኃይል ኮሚሽን ባስተላለፉት ትዕዛዝ ሥራውን ይበልጥ እንዲያፋጥን አሳስበዋል›› ሲል ዘግቧል፡፡[30] እስራኤል የኢራቅን ጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች መርሃ-ግብር አስመልክታ ለዋሽንግተን የማስጠንቀቂያ ዘገባዎችን ትሰጥ የነበረው በሻሮን አስተሳሰብ፡- ‹‹በእስራኤልና በአሜሪካ መካከል የነበረው ስትራቴጂያዊ ትብብር መቼም ቢሆን ተደርጎ በማይታወቅ ሁኔታ ወርድና ስፋት ባገኘበት ጊዜ ነው፡፡››[31] ወረራውን ተከትሎ ኢራቅ የጅምላ ጨራሽ ጦር መሣሪያ እንደሌላት በተረጋገጠ ጊዜ የአሜሪካው ሴኔት የደህንነት ኮሚቴና የእስራኤሉ ክኔሴት የተለያዩ ዘገባዎችን በተናጠል በማውጣት እስራኤል ኢራቅን አስመልክቶ ለቡሽ አስተዳደር ትሰጣቸው የነበሩ መረጃዎች ሁሉ ውሸት መሆናቸውን ይፋ አደረጉ። በጡረታ የተገለሉ አንድ የእስራኤል ጄኔራል እንዳስታወቁት፡- ‹‹የኢራቅን ጅምላ ጨራሽ መሣሪያ አስመልክቶ በአሜሪካና እንግሊዝ የስለላ ተቋማት ይቀርቡ የነበሩ መግለጫዎች በሙሉ ይገኙ የነበረው ከእስራኤል የስለላ ምንጮች ነበር›› ብለዋል፡፡[3]

እስራኤል፣ ሌላ ሀገር ለእርሷ ብሎ እጅግ ውድ ዋጋ የሚያስከፍል ድርጊት እንዲፈጽም የገፋፋች ብቸኛ ሀገር አለመሆኗ እውነት ነው፡፡ ብዙ ሀገራት አደጋ በተደቀነባቸው ጊዜ በሌሎች ሀገሮች ኪሣራ ያንን አደጋ ለማስወገድ ጥረት ሲያደርጉ የታዩበት አጋጣሚ በርካታ ሲሆን፣ ዩናይትድ ስቴትስ ራሷም ብትሆን ይህ ዓይነቱን አሠራር ተግባራዊ በማድረግ የዳበረ ታሪክ አላት፡፡[33] ለምሳሌ በ1980ዎቹ ከአብዮታዊት ኢራን የተደቀነባትን አደጋ ኢራቅን በማስታጠቅና በመርዳት ልትወጣው ሞክራለች፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በ1979 ሶቪዬት ሕብረት አፍጋኒስታንን በወረረች ጊዜ እርሷን ከዚያ ለማስወጣት በርዕዮተ ዓለም ለማትመስላቸውና ለማይመስሏት አፍጋኖች

እርዳታዋን ታንቆረቁር ነበር። ዩናይትድ ስቴትስ እነዚህን ጦርነቶች ለማካሄድ ወታደሮቿን አልላከችም። እዚያ የሚገኙና ውጊያ ለማድረግ የራሳቸው በቂ ምክንያት ያላቸውን ኃይሎች ከኋላ ሆና ማገዝን ነበር የመረጠችው።

ይህን ሁሉ ነገር እግምት ውስጥ ስናስገባ እስራኤላውያኑ በክልሉ ውስጥ ለእነርሱ አደገኛ የሚባለውን ጠላታቸውን ዩናይትድ ስቴትስ እንድትደመስስላቸው መፈለጋቸው አያስደንቅም። ያም ሆኖ ግን ጆርጅ ቡሽ በ2002 የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት በኢራቅ ላይ እንዲዘምቱ ይፈቀድላቸው ዘንድ በጠየቁ ጊዜ የእስራኤል መሪዎች አዝነዋል። የበለጠ የተጨነቁት ደግሞ የተባበሩት መንግሥታት የመሣሪያ ፈታሽ ቡድን ወደ ኢራቅ ተመልሶ እንዲገባ ሳዳም በፈቀዱ ጊዜ ነበር። እነዚህ ሁኔታዎች የእስራኤልን መሪዎች ጭንቀት ውስጥ ሊከቷቸው የቻሉት የጦርነቱን አዝማሚያ የማስቀረት ዕድል ስለሚፈጥሩ ነው። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፔሬዝ በጊዜው ለሪፖርተሮች እንዲህ ብለው ነበር፦ ‹‹ሳዳም ሁሴንን ለማውረድ ዘመቻ መደረጉ የግድ ነው። የመሣሪያ ቁጥጥርና ተቆጣጣሪዎች ለጥሩ ሰዎች መልካም ዘዴ ናቸው። ሆኖም ግን ታማኝነት የሚጎድላቸው ሰዎች ተቆጣጣሪዎችን በቀላሉ ሊያታልሏቸው ይችላሉ።››[34]

በመስከረም ወር መገባደጃ ላይ ሻሮን ሞስኮን በጎበኙ ጊዜ አዲሱን የመሣሪያ ተቆጣጣሪ ቡድን በኃላፊነት እንዲመሩ ለተመረጡት የሩሲያ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን የተሳካ ፍተሻ ለማድረግ የዘገዩ መሆናቸውን ነግረዋቸው ነበር።[34] ፔሬዝ በበኩላቸው በተባበሩት መንግሥታት ሂደት ያደረባቸውን ስጋት በመግለጽ በየካቲት አጋማሽ 2003 ፈረንሳይ በጸጥታው ምክር ቤት ያላትን ሚና ጥያቄ ውስጥ አስገብተው በትችት ሸንቆጥ አድርገዋታል።[36]

እስራኤል የመሣሪያ ተቆጣጣሪ ቡድኑን እንቅስቃሴ በጽናት የምትቃወም ብቸኛ ሀገር ሆና መታየቷ የማይመች አቋም እንዲኖራት አድርጓታል። ማርክ ፐርልማን መስከረም 2002 ፎርዋርድ ጋዜጣ ላይ ባወጣው ጽሑፍ እንዲህ ብሏል፦ ‹‹የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የመሣሪያ ተቆጣጣሪ ቡድን ወደ ኢራቅ ገብቶ ተግባሩን እንዲያከናውን ሳዳም ሁሴን ያለምንም

ቅድመ ሁኔታ መፍቀዳቸው እስራኤልን በዚህ ሳምንት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በመክተት የቡሽ አስተዳደር ዋነኛ ዓላማ የኢራቅን መንግሥት መገርሰስ መሆን እንዳለበት የምትደግፍ ብቸኛ ሀገር ሆና እንድትታይ አድርጓታል››።[37]

የተባበሩት መንግሥታትን የዲፕሎማሲ አካሄድ ወደጎን በማድረግ እስራኤል ሳዳም ሁሴንን በቀጥታ ከሂትለር ጋር አመሳስለቻቸው። ምዕራቡ ዓለም አሁን በሳዳም አንጻር መቆም ካልቻለ በ1930ዎቹ በናዚ ጀርመን ላይ የፈጸመውን ዓይነት ስህተት መድገሙ አይቀሬ ነው የሚል እምነት አሳድራለች። የታወቁት እስራኤላዊ ምሁር ሻሎም አቪነሪ በሎስ አንጀለስ ታይምስ ጋዜጣ ላይ ሲጽፉ፣ ‹‹በ1930ዎቹ የተደረገው ጀርመንን የመለማመጥ ዲፕሎማሲ ያስከተለውን ሁኔታ የሚያወግዙ ሁሉ ዛሬ በኢራቅ ላይ ጠንካራ እርምጃ ባለመውሰዳቸው ተመሳሳይ ታሪክ መድገማቸው አይቀርም።››[38] ከዚህ አባባል እንደምታ የምንገነዘበው የኢራቅን መወረር የሚቃወም ወይም እስራኤል ከፍልስጤማውያን ጋር እንድትስማማ ግፊት የሚያደርግ ሁሉ በናዚ ጊዜ እንደነበሩት ኒቪል ቻምበርሊይን ተለማማጭ መሆኑ በመጪው ትውልዶች ዘንድ ይታወቃል የሚል መልዕክት ነው። ኢየሩሳሌም ፖስት ጋዜጣ በተለይ የአክራሪነት አቋም በማንጸባረቅ በተደጋጋሚ በሚያወጣቸው ርዕስ አንቀጾችና የአስተያየት መስጫ አምዶቹ ላይ በአብዛኛው ጦርነቱን የሚደግፉ አቋሞችን ያንጸባርቅ የነበረ ሲሆን፣ አልፎ አልፎ ብቻ ነበር ተቃራኒ ሀሳቦችን ያስተናግድ የነበረው።[39] ለአብነት ያህል በርዕሰ አንቀጽ ይወጡ ከነበሩት ጽሑፎች መካከል በአንዱ ላይ እንዲህ የሚል ሀሳብ ሰፍሮ ነበር፡- ‹‹ሳዳምን ማባረር በሽብርተኝነት ላይ የሚደረገው ጦርነት ወሳኝ ምዕራፍ እንደሆነ ይቆጠራል። ይህ ሳይሆን ከቀረ ግን ጦርነቱን ማሸነፍ ይቅርና በሚገባ እንኳ መጀመር አይቻልም።››[40]

ሌሎች የእስራኤል እውቅ ሰዎችም እንደ ሻሮንና ፔሬዝ ሁሉ የጦር ነጋሪት ከመጎሰም በቀር የዲፕሎማሲውን ክርክርና መመላለስ አልፈቀዱትም። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሁድ ባራክ በ2002 በኒውርክ ታይምስ የሀሳብ መስጫ አምድ ሥር ሲጽፉ፡- ‹‹ሳዳም ሁሴን የኒኩሌር መርሃ-ግብር ባለቤት መሆናቸው የመወገዳቸውን ጉዳይ አጣዳፊ ያደርገዋል›› ካሉ በኋላ ቀጥለው ‹‹እንግዲህ ትልቅ አደጋ የሚከሰተው በስንፍና (ችላ ባይነት) የተነሣ ነው›› ብለዋል።[41] ከእርሳቸው ቀድመው ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት

ናታንያሁ ከጥቂት ሳምንት በኋላ በዎል ስትሪት ጆርናል ላይ ‹‹ሳዳምን የማስወገዱ ምክንያታዊነት›› በሚል ርዕስ ባሰፈሩት ጽሑፍ፡- ‹‹እኔ የምናገረው የአብዛኛዎቹ እስራአላውያን ድጋፍ ያለውንና የሳዳምን መንግሥት አስቀድሞ በመምታት የሚገኘውን ጥቅም አስመልክቶ ነው፡፡ ምክንያቱም እኚህ ሰው የኒኩሌዬር መሣሪያ በእጃቸው ለማስገባት እየሞከሩ ነው›› ብለዋል፡፡[42]

የናታንያሁ ተጽእኖ በጋዜጣ ላይ ከመጻፍና በቴሌቪዥን አስተያየት ከመስጠት ፈቀቅ ያለ ነበር፡፡ ምክንያቱም በዩ.ኤስ. የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የተማሩ እንደመሆናቸው በእንግሊዝኛ ቋንቋ በሚገባ ይራቀቃሉ፡፡ የአሜሪካ ፖለቲካዊ ባህልም ቢሆን ጥርሳቸውን የሸረፉበት እንደመሆኑ፣ ማወቅ ብቻ ሳይሆን በጥሩ ሁኔታ የመጠቀም ችሎታ አላቸው፡፡ ከቡሽ አስተዳደር ውጭም ሆነ በአስተዳደሩ ውስጥ ከሚገኙ ኒዎኮንሰርቫቲቮች ጋር ጥሩ ግንኙነት አላቸው፡፡ ከዚያም በላይ፣ በካፒቶል ሄል (ሁለቱ የአሜሪካ ምክር ቤቶች የሚገኙበት ህንፃ) ንግግር ለማድረግ ወይም ቃላቸውን ለመስጠት በተለያዩ አጋጣሚዎች በተደጋጋሚ ተገኝተዋል፡፡[43] ኢሁድ ባራክም ቢሆኑ እንዲሁ ከአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎች፣ ፖለቲከኞች፣ የደህንነት ኤክስፐርቶች እና የተለያዩ ባለሙያዎች ጋር ማለፊያ የሚባል ግንኙነት አላቸው።

የእስራኤል መንግሥት የሚያደርገው ጥረት ጦርነቱ ሊጀመር አንድ ወር ያህል እስኪቀረው ድረስ አልበረደም ነበር፡፡ ሃ› ኤሬትዝ ለምሳሌ የካቲት 17/2003 ላይ ባቀረበው ጽሑፍ ‹‹የእስራኤል የመከላከያ ጦር በኢራቅ የሚደረገውን ጦርነት በጉጉት እየተጠባበቀ ይገኛል፡፡ የእስራኤል ወታደራዊና ፖለቲካዊ መሪዎችም እንዲሁ የጦርነቱን መጀመር በናፍቆት እየተጠባበቁ ነው›› ብሏል፡፡ ከአስር ቀናት በኋላ ጀምስ ቤኔት በኒውዮርክ ታይምስ ላይ ያወጣው ጽሑፍ ርዕሱ እንዲህ ይል ነበር፡- ‹‹እስራኤል እንዲህ ትላለች፡- የኢራቅ ጦርነት ለክልሉ ጠቃሚ ነው!›› መጋቢት 7/2003 ለንባብ የበቃው ፎርዋርድ ጋዜጣ ‹‹ዩ.ኤስ አሜሪካ በኢራቅ ላይ የምታደርገው ዘመቻ በመዘግየቱ እየሩሳሌም እየተነጫነጨች ነው›› የሚል ዘገባ ይዞ ወጥቶ ነበር፡ ፡ ስለሆነም የእስራኤል መሪዎች ጦርነቱ እንዲዘገይ ሳይሆን በፍጥነት እንዲካሄድ ይፈልጉ እንደነበር እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ግልጽ ያደርጋሉ፡፡[44]

ይህን ሁሉ ነገር ታሳቢ ስናደርግ ቢል ክሊተን በ2006፡- ‹‹እያንዳንዱ የማውቀው እስራኤላዊ ፖለቲከኛ ‹ሳዳም ሁሴን ታላቅ ስጋት ፈጣሪ በመሆናቸው የጅምላ ጨራሽ ጦር መሣሪያ ባይኖራቸውም እንኳ መወገድ አለባቸው› ብሎ ያምናል›› ማለታቸው አያስደንቅም፡፡[45] ይህ የጦርነት

ፍላጎት በእስራኤል መሪዎች አካባቢ ብቻ የተወሰነ አይደለም። በ1990 በሳዳም ወረራ ከተፈጸመባት ኩዌትና ከራሷ ከአሜሪካ በስተቀር መላ ሕዝቧና መሪዎቿ ጦርነቱን የደገፉባት ብቸኛ ሀገር እስራኤል ነበረች። በ2002 የተደረገ ጥናት እንዳረጋገጠው 58 ከመቶ የሚሆኑት የእስራኤል አይሁዶች ‹‹ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅን እንድትወር እስራኤል መገፋፋት አለባት›› ብለው የሚያምኑ ናቸው።[46] ከአንድ ዓመት በኋላ በ2003 የተደረገ ሌላ ጥናትም እንዲሁ 77.5 ከመቶ የሚሆኑት የእስራኤል አይሁዶች ኢራቅ በዩናይትድ ስቴትስ እንድትወረር መደገፋቸውን አረጋግጧል።[47] በቶኒ ብሊዬር ብሪታኒያ በተደረገ ጥናት 51 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች ጦርነት መደረጉን የተቃወሙ ሲሆን 39 ከመቶ የሚሆኑት ብቻ ደግፈዋል።[48]

ይህ ያልተለመደ ሁኔታ ነበር ጌዲዮን ሌቪ የተባለው የሃ›ኤሬትዝ ጋዜጠኛ፣ እንግሊዝ ውስጥ በኢራቅ ላይ የሚደረገውን ጦርነት ተቃውመው 50,000 የሚሆኑ ዜጎች ሰላማዊ ሰልፍ ሰያደርጉ እስራኤል ውስጥ ግን ሰዎች ሰልፍ አለማድረጋቸውን እንዲጠይቅ ያነሳሳው።[49] በ2002 ማብቂያ ላይ ለምሳሌ የአሜሪካ ፖለቲካ አማካሪዎች ቡድን ‹የእስራኤል ፕሮጀክት› የተሰኘውን ስድስት ገጽ ደብዳቤ አሜሪካ ውስጥ ለሚገኙ እስራኤላውያንና አፍቃሪ-እስራኤል መሪዎች አሰራጭቶ ነበር። የደብዳቤው ርዕስ ‹‹ስለኢራቅ ማሰብ›› የሚል ሲሆን፣ የአሜሪካ ሕዝብ ስለጦርነቱ የሚኖረውን አስተያየት ለማለዘብ እንደ መመሪያ የሚያገለግል ነበር።[50] ጽሑፉ ‹‹ዓላማህ የመንግሥት ለውጥ ማምጣት እስከሆነ ድረስ የሚያጋጥምህን ተቃውሞ ግምት ውስጥ አስገባና በቋንቋ አጠቃቀምህ ላይ ጥንቃቄ ይኑርህ። ጦርነቱ የሚደረገው አሜሪካን ለመከላከል ሳይሆን እስራኤልን ለመከላከል እንደሆነ አድርገው አሜሪካውያን እንዲያስቡና እንዲያምኑ አታድርግ›› ይላል።[51]

እንደዚያ በማሰብ ይመስላል በርካታ ዘገባዎች እንዳመለከቱት ሻሮን በጦርነቱ ዋዜማ የእስራኤል ዲፕሎማቶችና ፖለቲከኞች በኢራቅ ላይ ስለሚወሰደው እርምጃ ምንም ነገር እንዳይናገሩ ያስጠነቀቁት። ምክንያቱም በሻሮን እምነት የቡሽ አስተዳደር ሳዳምን እንዲገረስስ እስራኤል የምትገፋፋ ሀገር ተደርጋ መታየት የለባትም። ይህ የሚያሳየው ‹‹እስራኤል የኢራቅን መወረር ትደግፋለች›› የሚለው አስተሳሰብ እያደገ መሄዱ የእስራኤልን መሪዎች ያስጨነቃቸው መሆኑንና እንደዚያ ዓይነቱ ስዕል ደግሞ በስፋት እንዲታወቅ ያለመፈለጋቸውን ነው።[52]

ሎቢውና የኢራቅ ጦርነት

በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደሞከርነው የኢራቅን ጦርነት ከኋላ ሆነው ሲቀሰቅሱ የነበሩት ወሳኝ የሆኑ የዓለም አካባቢዎችን ፖለቲካ በአሜሪካ የበላይነት እየታገዙ ለመቅረጽ ፍላጎት ያላቸው ጥቂት የኒዎኮንሰርቫቲቭ ቡድን አካላት ናቸው። ሳዳምን ከሥልጣን ለማውረድ ያለሙት ገና ከ1990ዎቹ ጀምሮ ሲሆን ያንን በማድረግ ዩናይትድ ስቴትስም ሆነች እስራኤል ተጠቃሚ ይሆናሉ የሚል እምነት ነበራቸው።[53] ከዚህ ቡድን አባላት መካከል በቡሽ አስተዳደር ውስጥ ፓውል ዎልፎዊትዝና ዶግላስ ፈይዝ በፔንታጎን የእዝ ተዋረድ በሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ የሥልጣን እርከን ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ ሪቻርድ ፐርል፣ ኬኔት ኤድልማንና ጀምስ ውልሲ ደግሞ ተጽእኖ ፈጣሪ የሆነው የዲፌንስ ፖሊሲ ቦርድ አባላት ናቸው። በምክትል ፕሬዚዳንቱ ቢሮ ውስጥ ዋነኛ ባለሥልጣን የሆኑት ስኩተር ሊቢ፣ በሚኒስትር ማዕረግ የጦር መሣሪያ ቁጥጥርና የዓለም አቀፋዊ ጸጥታ ኃላፊ ጆን ቦልተን፣ የእርሳቸው ልዩ ረዳት ዴቪድ ውርምሰር፣ በብሔራዊው ጸጥታ ካውንስል የመካከለኛው ምሥራቅ ኃላፊው ኢሊዮት አብራምስና ሌሎች ኒዎኮንሰርቫቲቮች ናቸው። ይህ ቡድን በተጨማሪም ሮበርት ኬጋን፣ ቻርለስ ካራውታመር፣ ዊሊያም ክሪስቶልና ዊሊያም ሳፊርን የመሳሰሉ የታወቁ ጋዜጠኞችንም ያካትታል።

የኒዎኮንሰርቫቲቭ እሳቤ አራማጆች ቁልፍ ከሆኑ የስልጣንና የሐላፊነት ቦታዎች ላይ እንዲቀመጡ ማድረግ በእስራኤልና በአሜሪካዊያን ደጋፊዎቿ ዘንድ ጠቃሚና አዎንታዊ እርምጃ እንደሆነ ተደርጎ ነው የሚታየው። ጥር 2001 ላይ ፓውል ዎልፎዊትዝ ምክትል የመከላከያ ሚኒስትር ሆነው በተሾሙ ወቅት እየሩሳሌም ፖስት ሁኔታውን ሲዘግብ፡- ‹‹አይሁዳውያንና አፍቃሪ-እስራኤል ማህበረሰቦች በደስታ ጮቤ ረግጠዋል›› ብሏል።[54] በጸደይ 2002 የወጣው ፎርዋርድ ጋዜጣ ዎልፎዊትዝን ‹‹በቡሽ አስተዳደር ውስጥ ዋነኛው አፍቃሪ-እስራኤል ድምፅ›› ብሏቸዋል። ዘግዬት ብሎ 2002 ላይ ይኼው ጋዜጣ ዎልፎዊትዝን ከሌሎች ሃምሳ ከሚሆኑ ሰዎች ጋር አንድ

ላይ ‹‹የአይሁዳዊያንን ጉዳይ በሚገባ የሚከታተሉ ንቁ ተሳታፊ (activist)›› በማለት መርጧቸዋል።[55] በተመሳሳይ ጊዜ ዴ አይ..ኤን.ኤስ.ኤ. የተባለው ድርጅት የሄንሪ ኤም ጃክሰን ‹‹ዲስቲንጉሽድ ሰርቪስ አዋርድ›› የተባለውን ሽልማት በእስራኤልና ዩናይትድ ስቴትስ መካከል መልካም ትብብር እንዲኖር ላደረጉት አስተዋጽኦ አበርክቶላቸዋል። እየሩሳሌም ፖስት ጋዜጣ ደግሞ ዎልፎዊትዝን ‹‹እጅግ የተመሰጡ አፍቃሪ-እስራኤል›› በማለት ካሞካሻቸው በኋላ ‹‹የ2003 የዓመቱ ምርጥ ሰው›› ብሏቸዋል።[56]

የዶግላስ ሬይዝን ጉዳይ ደግሞ ካየን ጦርነቱን ከመቀስቀስ አንፃር ያላቸው ሚና የሚመዘነው ለእስራኤል ከነበራቸው የረዥም ጊዜ ትብብርና በዚያ ከሚገኙ ጠላር መስመረኞች ጋር ካላቸው ቅርርብ አኳያ መሆን አለበት።። ፌይዝ ጆዊሽ ኢንስቲትዩት ፎር ናሽናል ሴኩሪቲ ኦፌይርስና የአሜሪካን ጽዮናውያን ማህበር (ዜድ.ኦ.ኤ) ከመሳሰሉ ቁልፍ የሎቢ ድርጅቶች ጋር ትስስሮሽ አላቸው።። በ1990ዎቹ በጻፏቸው የተለየዩ መጣጥፎቻቸው እስራአል የምታደርገውን የሠፈራ ግንባታዎች በመደገፍ፡- ‹‹ሁሉንም የያዘቻቸውን ቦታዎች ለራሷ ማስቀረት አለባት›› ብለዋል።[57] ከዚህም በተጨማሪ በምዕራፍ 4 ላይ እንደገለጽነው ፌይዝ ከሪቻርድ ፐርልና ዴቪድ ውርምሰር ጋር በመሆን ‹‹ክሊን ብሪክ›› የሚሰኝ ሪፖርት በ1996 አዘጋጅተዋል።[58] ያንን ጽሑፍ ያዘጋጁት ቀኝ አክራሪ በሆኑ የእስራኤል ምሁራን ቀስቃሽነት ነበር።። የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሆኑ ለታሰቡት ቤንጃሚን ናታንያሁ ወደ ሥልጣን መምጣት፣ ከመጡም በኋላ፡- ‹‹የሳዳም ሁሴንን ከሥልጣን መውረድ ዋነኛ ስትራቴጂያዊ አጀንዳቸው አድርገው የሚይዙት መሆናቸውን›› ሪፖርቱ ያሳያል።። በተጨማሪም ሪፖርቱ እስራኤል አጠቃላዩን መካከለኛው ምሥራቅን እንደገና ሥርዓት የማስያዝ ሚና እንዲኖራት ጥሪ አድርጓል።። ይሁን እንጂ ናታንያሁ ሥልጣን ከያዙ በኋላ የእነርሱን ምክር ያልተጠቀመብት ቢሆንም፣ ፌይዝ፣ ፐርልና ውርምሰር፣ የቡሽ አስተዳደር ተመሳሳይ ግቦችን እንዲከተል ጥረት ማድረጋቸውን ቀጥለዋል። ይህን ሁሉ ያስተዋለችው የሃ-ኤሬትዝ ጋዜጣ ፀሐፊ አኪቫ ኤልዳር፡- ‹‹ፌይዝና ፐርል ለአሜሪካ መንግሥት ታማኝነታቸውን በማሳየትና የእስራኤልንም ጥቅሞች በማስጠበቅ መካከል

በዘረጉት መስመር እየተራመዱ ይገኛሉ›› በማለት ማስጠንቀቂያ አዘል ጽሑፍ አቅርባለች።[59] ጆርጅ ፔከር ‹ዘ አሳሲንስ ጌት› በተባለው መጽሐፉ፡- ‹‹ሉይዝና ውርምሰር ጦርነቱን ከመደገፍ ጀርባ ዋናው እያንቀሳቀሳቸው ያለው ኃይል የእስራኤልን ጸጥታ የማረጋገጡ ጉዳይ ነው›› ብሏል።[60]

ጆን ቦልተንና ስኩተር ሊቢም እንዲሁ ጠንካራ የእስራኤል ደጋፊዎች ናቸው። ጆን ቦልተን በተባበሩት መንግሥታት የአሜሪካ አምባሳደር በነበሩ ጊዜ በሙሉ ፍላጎትና በጽናት ነበር የእስራኤልን ጥቅሞች ለማስከበር ሲሠሩ የኖሩት። ለዚህም ነበር ግንቦት 2006 ላይ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የእስራኤል አምባሳደር በቀልድ መልክ ቦንልተንን ሲገልጿቸው፡- ‹‹በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ የእስራኤል ቡድን ምስጢራዊ አባል ያሏቸው። ዲፕሎማቱ ንግግራቸውን ቀጥለው ‹‹ምስጢሩ አሁን ተጋልጧል። እኛ በዚያ የምንገኝ ዲፕሎማቶች አምስት ብቻ አይደለንም። ቦልተንን ጨምሮ ስድስት ነን›› ብለዋል።[61] ቦልተን ለዚያ ቦታ በ2006 እንደገና በአወዛጋቢ ሁኔታ ሲመረጡም አፍቃሪ-እስራኤል ቡድኖች ደግፈዋቸው ቆመዋል።[62] ስኩተር ሊበንን በተመለከተ ዋይት ሐውስን 2005 ማለቂያ ላይ ለቅቀው ሲወጡ ፎርዋርድ ጋዜጣ እንዲህ ብሎ ነበር፡- ‹‹የእስራኤል ባለሥልጣናት ሊቢንን ይወዷቸዋል። እርሳቸውን ሲገልጿቸውም ጠቃሚ አጋራቸውና ከእስራኤል ጋር የተያያዙ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሁልጊዜም አሳቢነታቸውን ያሳዩ ወዳጅ መሆናቸውን ይገናገራሉ።›› ብሏል።[63]

ከቡሽ አስተዳደር ውጭ የሚገኙ ኒዎኮንሰርቫቲቮች በመንግሥቱ ውስጥ እንዳሉቱ የሀገራቸው ልጆች ሁሉ ለእስራኤል ጉዳይ ሁለንተናቸውን አሳልፈው የሰጡ ናቸው። ለአብነት ያክል ቻርለስ ክራውታመር ሰኔ 10 ቀን 2002 ላይ በእየሩሳሌም ‹ዘ ጋርዲየን ኦፍ ጽዮን አዋርድ › የተባለውን ሽልማት በባር ኢላን ዩኒቨርስቲ ሲሸለም የተናገረውን እንመልከት።[64] የንግግሩ ዋና ይዘት እስራኤል በኦስሎ የሰላም ስምምነት ሂደት መሳተፏ የአይሁዳዊነትን መንገድ መሳት ነው፣ የሚል ሲሆን፣ ክራውታመር በተለይም ራሱን ከእስራአል ጋር በግልጽ በማዛመድ እውነተኛ እስራኤላዊ መሆኑን አሳይቷል። በንግግሩ በአንድ ቦታ ላይ እንዲህ አለ፡- ‹‹ከዛሬ 36

ዓመት በፊት በዛሬዋ ቀን የስድስቱ ቀን ጦርነት ተጠናቀቀ፡፡ያ ዕለት አዲስ ዘመን መግባቱን ያመለከተ ነበር፡፡ እየሩሳሌም እንደገና ተዋሃደች፡፡ ቴምፕል ማውንት የእኛ የእስራኤላውያን ብቻ ሆነ›› ብሏል፡፡ ክራውታመር ንግግሩን በመቀጠል፡- ‹‹በዚህ ምሽት በማቀርበው ጽሑፌ እንደ ሕዝብና እንደ አይሁድ መንግሥት ያሉብን ችግሮች በዚህ መነቃቃት ወቅት በትክክል ሥር እየሰደዱ መሆናቸውን ነው የምገልጽላችሁ›› ብሏል፡፡ ክራውታመር ልክ እንደሌሎች ኒዎኮንሰርቫቲቭ ባለሙያዎች (pundit) ሁሉ የኢራቅ ጦርነት እስከተደረገበት የመጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ጦርነቱን ያለማቋረጥ ሲደግፍ ቆይቷል፡፡

ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ ኒዎኮንሰርቫቲቮች አይሁድ አሜሪካውያንና ከእስራኤል ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ቢሆኑም ቅሉ፣ ጦርነቱን የሚደግፉ አንዳንድ ግንባር ቀደም አባላት ግን አይሁዳውያን አልነበሩም፡፡ ጆን ቦልተንን ጨምሮ ፕሮጀክት ፎር ኒው አሜሪካን ሴንቸሪ በተባለው ድርጅት የተረቀቀውንና ለቡሽና ክሊንተን የተላከውን ግልጽ ደብዳቤ ከፈረሙት ውስጥ የቀድሞው የሲ.አይ.ኤ ዳይሬክተር ጀምስ ውልሲና የቀድሞው የትምህርት ሚኒስትር ዊሊያም ቤኔት አይሁዳውያን ካልሆኑት ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ በተለይም ደግሞ ውልሲ ሳዳም ከመስከረም 11ዱ ጥቃት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ ከጠላፊዎቹ አንዱ የሆነው መሐመድ አታ ከኢራቅ የደህንነት ሰው ጋር ፕራግ (ቼክ ሪፖብሊክ) ውስጥ ግንኙነት አድርጓል መባሉን ለማጣራት ብዙ ደክመዋል፡፡ ታሪኩ ከአጠራጣሪነት አልፎ ሀሰት መሆኑም በስፋት ታምኖበታል፡፡ ይሁን እንጂ ውልሲና ምክትል ፕሬዚዳንቱ ዲክ ቸኒ ጦርነቱን ለማስጀመር ይህን ጉዳይ እንደ ዋነኛ ምክንያት አድርገው ተጠቅመውበታል፡፡[65]

የኢራቅን ጦርነት ወደፊት በመግፋት ኒዎኮንሰርቫቶች ብቸኛ የሎቢው ክፍሎች አልነበሩም፡፡ ቁልፍ የሆኑ የአፍቃሪ-እስራኤል ድርጅቶች መሪዎችም ዘመቻው እንዲደረግ ሲያደፋፍሩ ነበር፡፡ ዋናው ነገር ደግሞ ብዙ የኒዎኮንሰርቫቲቭ የፖለቲካ ዘይቤ አራማጆች ራሳቸው ከእነዚህ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው የመሆኑ ሃቅ ነው፡፡ 2002 መስከረም አጋማሽ ላይ የጦርነቱ አይቀሬነት ግልጽ በሆነበት ሰዓት ሚካኤል ጉልድበርግ ‹ሳሎን›

በተባለው መጽሔት ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል፡- ‹‹ዋና ዋና የሚባሉት የአይሁድ ድርጅቶች መሪዎች አሜሪካ ባግዳድን እንድትወር ከሚፈልጉት ጠንካራ ደጋፊዎች መካከል ይገኛሉ››[66] ተመሳሳይ የሆነ ሀሳብ የተንጸባረቀው ደግሞ ባግዳድ ከተወረረች በኋላ በታተመው ፎርዋርድ ጋዜጣ ርዕሰ አንቀጽ ላይ ነበር፡፡ እንዲህ ይነበባል፡- ‹‹ፕሬዚዳንት ቡሽ የኢራቅን ጦርነት ለሕዝቡ ይፋ ባደረጉ ጊዜ የአሜሪካ ዋና ዋና የአይሁድ ድርጅቶች እርሳቸውን በመደገፍ ጨኽዋል፡፡ የማህበረሰቡ መሪዎችም ዓለም ሳዳም ሁሴንንም ሆነ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያቸውን እስከወዲያኛው እድትገላገል ድምጻቸውን አሰምተዋል፡፡ አንዳንድ ቡድኖች እንዲያውም የኢራቁ መሪ መወገድ በመካከለኛ ምሥራቅ ሰላምን ለማምጣትና አሜሪካ በሽብርተኝነት ላይ የጀመረችው ዘመቻ በድል እንዲጠናቀቅ ወሳኝ የሆነ እገዛ ያደርጋል እስከማለት ርቀው ሄደዋል፡፡›› ርዕሰ አንቀጹ ቀጥሎ ደግሞ፡- ‹‹ለእስራኤል ደህንነት መጨነቅ የዋና ዋናዎቹ አይሁድ ቡድኖች የትኩረት ማዕከል ሆነ›› ብሏል፡፡[67]

ምንም እንኳን ዋነኛ ከሚባሉት የአይሁድ ቡድኖች መካከል ጦርነቱን ያልደገፉ አሉ ለማለት ባያስደፍርም፤ ድጋፋቸውን በመግለጽ ዙሪያ ግን ልዩነቶች ተስተውለውባቸዋል፡፡ ዋናው ጭንቀታቸው በግልጽ ጦርነቱን እንደሚደግፉ መታወቁ፡- ‹‹ጦርነቱ የሚካሄደው ለእስራኤል ተብሎ ነው›› የሚል ስሜት በሕዝቡ ዘንድ ሊያሳድር ይችላል የሚል ነበር፡፡[68] የሆነ ሆኖ ዘ-ጆዊሽ ካውንስል ፎር ፐብሊክ አፌርስና የፕሬዚዳንቶች ኮፈረንስ በኢራቅ አንባር የኃይል እርምጃ እንዲወሰድ (እንደ መጨረሻ አማራጭ) የሚደግፉ መሆናቸውን 2002 ማብቂያ ላይ ገለጹ፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ በሎቢው ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ዋና ዋና ድርጅቶች ተመሳሳይ አቋም አንጸባረቁ፡፡[69] ወረራውን በግልጽ ከደገፉት መካከል የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ ሊቀመንበር ሞርትማየር ዙከርማን አንዱ እንደመሆናቸው ይህንኑ አቋማቸውን በተለያዩ አጋጣሚዎች ለሕዝቡ ይፋ አድርገዋል፡፡ ዙከርማን ነሐሴ 2002 ማብቂያ ላይ በዩ.ኤስ. ኒውስ ኤንድ ዎርልድ ሪፖርት ጋዜጣ ላይ ሲጽፉ፤ (የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ራሳቸው ናቸው) ‹‹ሳዳምን መገርሰስ የሚያመጣውን መዘዝ አደገኛነት የሚገልጹ ሰዎች ፕሬዚዳንት ቡሽ፣ በቁም

ቅዠት ውስጥ መኖር የባሰ አደገኛ መሆኑን በመግለጽ ያስቀመጡትን ሐሳብ በወጉ አልተገነዘቡም፡፡ ስለሆነም ለችግሩ ምርጥ የተባለው መፍትሄ ማስታገሻውን መድሃኒት መውሰድ ብቻ ነው›› ብለዋል፡፡[70]

የአሜሪካ አይሁድ ኮንግረስ ፕሬዚዳንት ጃክ ሮስንና ‹ሪሊጅየስ አክሽን ሴንተር ኦፍ ሪፎርምድ ጁዳይዝም› የተባለው ሃይማኖታዊ ድርጅት መሪ ራቢ ዴቪድ ሳፐርስታይን ዋነኞቹ የጦርነት አናፋሾች ነበሩ፡፡ ሊበራል በሆነ የፖለቲካ አመለካከታቸው የሚታወቁትና ዋሽንግተን ፖስት ‹‹በካፒቶል ሂል የሚገኙት አርአያነት ያለው ሃይማኖታዊ ሎቢ አድራጊ›› ያላቸው ሳፐርስታይን መስከረም 2002 ላይ ‹‹የአይሁድ ማህበረሰብ ሳዳም ሁሴን ያሳደሩበት ስጋት ሲወገድ ማየት ይፈልጋል›› በማለት ተናግረዋል፡፡[71] በኒው ዮርክ አይሁድ ማህበረሰብ ዘንድ በስፋት ተነባቢ እንደሆነ የሚታወቀው ‹ጆዊሽ ዊክ› ጦርነቱን እንደሚደግፍ ግልጽ አድርጓል፡፡ የጋዜጣው አዘጋጅና አሳታሚ የሆነው ጋሪ ሮዝንብላት ታህሣሥ አጋማሽ በወጣው እትም ርዕሰ አንቀጽ ላይ እንዲህ ብሏል ‹‹ዋሽንግተን በሳዳም ሁሴን ላይ ልታደርገው ያሰበችው የማይቀር ጦርነት በእስራኤል ላይ ታላቅ ስጋት የደቀነውን የዓለማችንን አደገኛ አምባገነን የማስወገጃው ብቸኛ አማራጭ ነው›› ካለ በኋላ በመቀጠል ‹‹ስለሆነም ይህ ማን አለብኝ ባይ ሰይጣናዊ ፍላጎቱን ግልጽ ባደረገ ጊዜ እመኑት፡፡ ይህ ነው ከሂትለርና ከሆሎኮስ እልቂት ያተረፍነው ትምህርት፡፡ ሌላም ተጨማሪ ነገር አልለ፡፡ በቶራህ የተጻፈው ሕግ የሚለው ‹ጠላትህ ሊገድልህ በፊገ ጊዜ አንተ መጀመሪያ ግደለው› ነው፡፡ ራስን መከላከል የተፈቀደ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር ነውና›› ብሏል፡፡[72] አይፓክ እና ኤ.ዲ.ኤል ጦርነቱን የደገፉ ቢሆንም፣ በአነስተኛ ደረጃና በቁጥብነት ነበር አቋማቸውን የገለጹት ፡፡

እነሆ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ዛሬ ጦርነቱ ወደ ጥፋትና ውድመት ተቀይሯል፡፡ የእስራኤል ደጋፊዎች አንዳንድ ጊዜ ‹‹በሎቢው ውስጥ ጉልህ ሚና ያለው አይፓክ ወረራውን አልደገፈውም›› እያሉ ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡[73] ሆኖም ግን ይህ አባባል በተፈጥሮ የሰው ልጅ የተጎናጸፈውን ዕውቀት (Common Sence) ይፃረራል፡፡ ምክንያቱም አይፓክ ሁልጊዜም እስራኤል የምትፈልገውን ነገር የሚደግፍ በመሆኑና እስራኤል ደግሞ ዩናይትድ

ስቴትስ ኢራቅን እንድትወር ጽኑ ፍላጎት የነበራት በመሆኑ ነው። አይፓክ 2003 ላይ ጦርነቱ ወዲያው እንደተጀመረ ባዘጋጀው ዓመታዊ ኮንፈረንስ ላይ ናታን ጉትማን ባቀረበው ሪፖርት ‹‹አይፓክ ለእስራኤል ጥሩ የሆነን ማንኛውም ነገር ይደግፋል። ስለሆነም እስራኤላውያን ጦርነቱን እስከደገፉት ድረስ በሺህ የሚቆጠሩ የአይፓክ ሎቢስቶች በዋሽንግተን ተሰብስበው ድጋፋቸውን ገልጸዋል›› ብሏል።[74] የአይፓክ ዋና ዳይሬክተር ሃዋርድ ኮር 2003 ጥር ላይ ለኒውዮርክ ሰን ጋዜጣ በሰጡት ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው መናገራቸው ጉዳዩን ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል፦ ‹‹የዩ.ኤስ. አሜሪካ ጦር ኢራቅን እንዲወር ኮንግረስን ሎቢ ማድረጉ ባለፉት ዓመታት አይፓክ ካገኛቸው ስኬቶች መካከል ዋነኛው ነው››[75] የኢራቅ ጦርነት ሊጀመር ባለበት ሰሞን የአይፓክ ፖሊሲ ዳይሬክተር የነበሩት ስቲቨን ሮስን በጀፍሪ ጎልድ በርግ ዘገባ መሠረት ‹‹ኢራቅ እንድትወረር አይፓክ ሎቢ አድርጓል›› ብለው መናገራቸውን ገልጿል።[76]

አይፓክ ከወረራውም በኋላ ቢሆን ዩ.ኤስ.አሜሪካ የኢራቅ ቆይታዋን እንድታራዝም በጽናት ደግፏል። 2003 ማለቂያ ላይ የቡሽ አስተዳደር የሴኔቱን ዲሞክራቶች ለጦርነቱ ተጨማሪ ገንዘብ እንዲመደብ እንዲፈቅዱ ለማድረግ በተቸገረ ጊዜ የዲሞክቲክ ሴናተሮችን ድጋፍ አስተዳደሩ ያገኝ ዘንድ ሎቢ እንዲያደርግ ሪፖብሊካን ሴናተሮች አይፓክ ጠየቁት። የአይፓክ ሰዎች ከተወሰኑ ዲሞክራት ሴናተሮች ጋር ውይይት ካደረጉ በኋላ ገንዘቡ ሊለቀቅ በቅቷል።[77] ቡሽ ግንቦት 2004 ላይ የኢራቁን ፖሊሲያቸውን አስመልክተው በአይፓክ መድረክ ላይ ንግግር ባደረጉበት ወቅት አድማጮቻቸው ለ23 ጊዜያት ያክል ከመቀመጫቸው እየተነሱ አጨብጭበውላቸዋል።[78] አይፓክ ባዘጋጀው የ2007ቱ ኮንፈረንስ አሜሪካውያን ስለ ኢራቅ የነበራቸው ስሜት ወደ ብስጭት የተቀየረበት ጊዜ ስለነበር ም/ፕሬዚዳንት ቼኒ በኢራቅ ስለመቆየት ንግግር አደረጉ። እንደ ኢየሩሳሌም ፖስቱ ዴቪድ ሆርቪዝ አባባል በዚያ ጊዜ ቼኒ ‹‹ማለፊያ የሚባል በጨኸት የተገለጸ ድጋፍ አግኝተዋል››[79] በተወካዮች ምክር ቤት የአናሳዎቹ (Minorities) መሪ ጆን ቦህነር ደግሞ ‹‹አሜሪካ በኢራቅ የሚገጥማት ውድቀት ለእስራኤል መንግሥት ቀጥተኛ ስጋት

እንደማያስከትል የሚያምን የዚያ ውድቀት የመጨረሻ ውጤት ምን ያህል መጥፎ መሆኑን ለማወቅ ገና ማሰብ እንኳን ያልጀመረ እንደሆነ ይገንዘብ›› የሚለውን ንግግራቸውን እንዳሰሙ ሁሉም ከመቀመጫው ተነስቶ ነበር ያጨበጨበላቸው። ከዚያ በተቃራኒ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔ ናንሲ ፔሎሲ የቡሽ አስተዳደር ቀስ በቀስ ኃይሉን በኢራቅ እየጨመረ የመሄዱን ስትራቴጂ በተቹ ጊዜ ሁሉም አድማጭ አጉረመረመ።[80]

ቡሽ በኢራቅ ያደረጉትን ዘመቻ እስከመጨረሻው የደገፈና ጦርነቱን አስመልክቶ ምንም ተቃውሞ ያላሰማ ድርጅት አይፓክ ብቻ አይደለም። ፎርዋርድ ጋዜጣ መጋቢት 2007 ላይ እንደዘገበው፡- ‹‹ አብዛኛዎቹ አይሁዳውያን ድርጅቶች ጦርነቱን አስመልክቶ ተቃውሞ ማሰማት የማይፈልጉ በመሆናቸው የአስተዳደሩን እያንዳንዱን እርምጃ ይደግፋሉ›› ብሏል።[81] አብዛኞዎቹ የአሜሪካ አይሁዳውያን ጦርነቱን አስመልክቶ ያላቸውን ዝንባሌ እግምት ውስጥ ካስገባን (ጦርነቱን እንደሚቃወሙ ስለሚታወቅ) ይህ የድርጅቶቹ እርምጃ የሚያስደነግጥ ነው። የጋሉፕ ድርጅት በ2005 የተደረጉ አስራ ሦስት የሚሆኑ ጥናቶችን መሠረት ያደረገ ግኝቱን በ2007 ይፋ ሲያደርግ እንደገለጸው የአሜሪካ አይሁዳውያን በአብዛኛው (77 ከመቶ) የኢራቅን ጦርነት በመቃወም ጦርነቱን ከተቃወሙ የአሜሪካ ዜጎች (52 ከመቶ) በልጠው ተገኝተዋል[82] ኢራቅን በተመለከተ ታላላቆቹና ሀብታሞቹ የአሜሪካ አይሁዳውያን ድርጅቶች ከአሜሪካ አይሁድ ዜጎች አንፃር ሲታዩ የተለዩ መንገድ የሚከተሉ መሆናቸው በግልጽ ተስተውሏል። ጥቂት የአይሁድ ድርጅቶች ብቻ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ጀምሮ የተቃወሙት ሲሆን፣ እስከአሁንም ድረስ እንደተቃወሙት ይኖራሉ። በዚህ ረገድ ቲክም ኮሚዩኒቲ እና ጀዋሽ ቮይስ ፎር ፒስ የተባሉ ድርጅቶች ይጠቀሳሉ። ይሁን እንጂ ምዕራፍ 4 ላይ እንደተገለጸው እነዚህ ቡድኖች ተገቢውን የገንዘብ ድጋፍ አያገኙም። እናም አይፓክን እንደመሳሰሉ ድርጅቶች ተጽዕኖ ማድረግም አይችሉም።

ይህ በሎቢው ውስጥ በሚገኙ ቡድኖችና በአሜሪካ አይሁዶች መካከል ያለው የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ትኩረት ሊቸረው የሚገባ ጠቃሚ ነጥብ ነው። ምንም እንኳን ታዋቂ የሆኑ የእስራኤል መሪዎች፣ ኒዎኮንሰርቫቲቮችና

በርካታ የሎቢው መሪዎች ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅን እድትወር የሚፈልጉ ቢሆንም፣ ሰፊው የአሜሪካ አይሁዳውያን ማህበረሰብ ግን አይፈልግም ነበር፡ : [83] ሳሙኤል ፍሪድማን የተባሉ የኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ የጋዜጠኝነት ሙያ ፕሮፌሰር ጦርነቱ እንደተጀመረ የፔው ምርምር ማዕከል በሀገር አቀፍ ደረጃ ያወጣቸውን ዘገባዎች ጠቅሰው እንዳስተላለፉት ከአጠቃላዩ የአሜሪካ ማህበረሰብ አንጻር ጦርነቱን የደገፉት አይሁዳውያን 52% ለ62% ናቸው ብለዋል፡፡[84] ስለሆነም በኢራቅ የተደረገው ጦርነት በአይሁድ ሕዝቦች ተጽዕኖ የተደረገ ነው ማለት አብይ ስህተት መፈጸም ይሆናል፡፡ ከዚያ ይልቅ ጦርነቱ በአመዛኙ በሎቢው ተጽዕኖ በተለይም በኒዎኮንሰርቫቲቭ ክንፉ አማካይነት የተደረገ ነው ማለቱ ነው የሚቀለው፡፡ ስለዚህ ቀደም ብለን እንደገለጽነው ሁሉ ሎቢው ሁልጊዜም ቢሆን እወክለዋለሁ የሚለውን ብዙሃኑን ማህበረሰብ የማይወክልና የእርሱንም ድምፅ በትክክል የማያንጸባርቅ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ለምታመነታዋ አሜሪካ ጦርነቱን መሸጥ

ኒዎኮንሰርቫቲቮች ሳዳምን በጦር ኃይል የማውረዱን ሀሳብ ጆርጅ ደብሊው ቡሽ ሥልጣን ሳይጨብጡ በፊት ነበር የወጠኑት፡፡ የጦርነት ነጋሪት ጉሸማቸውን የጀመሩት ገና በ1998 መግቢያ ላይ ፕሬዚዳንት ክሊንተን ሳዳምን ያወርዱ ዘንድ ሁለት ደብዳቤዎችን ጽፈው በጠየቁ ጊዜ ነበር፡፡ የመጀመሪያውን ደብዳቤያቸውን (ጥር 26 ቀን 1998) ዘ ፕሮጀክት ፎር ኒው አሜሪካን ሴንቸሪ በተባለው ድርጅት አነሳሽነት ነበር ያቀናበሩት፡፡ በደብዳቤው ላይ ፊርማቸውን ካኖሩት መካከል ኢሊዬት አብራምስ፣ ጆን ቦልተን፣ ሮበርት ኬጋን፣ ዊሊያም ክሪስቶል፣ ሪቻርድ ፐርል፣ ዶናልድ፣ ራምስፌልድና ፓወል ዎልፎዊትዝ ይገኙበታል፡፡ ሁለተኛው ደብዳቤ የተዘጋጀው ደግሞ የካቲት 19 ቀን 1998 ኮሚቴ ፎር ፒስ ኤንድ ሴኩሪቲ ኢን ዘ ገልፍ በተባለ ድርጅት አነሳሽነት ነው፡፡

ይህ ድርጅት የተቋቋመው በ1990 በሪቻርድ ፐርል፣ በቀድሞዋ የዲሞክራቲክ ናሽናል ኮሚቴ የፖለቲካ ዳይሬክተር አን ሊዊስና በቀድሞው

የኒውዮርክ ዲሞክራት ኮንግረስማን ስቴፈን ዶ.ሶላርዝ አማካይነት ነበር። ይኸኛውም ደብዳቤ የተፈረመው ቀደም ሲል በተላከው ደብዳቤ ላይ ከፈረሙ ሰዎች በተጨማሪ በዶግላስ ሬይዝ፣ ሚካኤል ሌዲን፣ በርናርድ ሊዊስ፣ ማርቲን ፔሬትዝና ዴቪድ ውርምሰር ነበር።[85]

ከእነዚህ በከፍተኛ ደረጃ የተቀነባበሩ ደብዳቤዎች በተጨማሪ ኒዎኮንሰርቫቲቮችና በሎቢው ውስጥ ያሉ አጋሮቻቸው በ1998 ኢራቅን ነፃ የማውጣት ሕግን (Iraq Liberation Act) ኮንግረሱ እንዲያጸድቅላቸው ለማድረግ በትጋት ተንቀሳቅሰዋል። ይህ ሕግ የአሜሪካ መንግሥት የሳዳም ሁሴን አገዛዝ ተወግዶ በምትኩ በዲሞክራሲያዊ ወግ የሚመራ መንግሥት እንዲቋቋም የሚያደርገውን ጥረት እንዲደግፍ (እንዲያስፈጽም) አደራ (Mandate) ያኖናጽፈዋል። ኒዎኮንሰርቫቲቮች በተለይ ለዚህ ሕግ የጋለ ስሜት አድሮባቸዋል። ምክንያቱም በኢራቅ የመንግሥትን ለውጥ የሚፈቅድ ብቻ ሳይሆን ሳዳምን ለመጣል ለሚነሳሱ ቡድኖች ወጪ የሚሆን 97 ሚሊዮን ዶላር በጀት ስለሚፈቅድም ጭምር ነው።[86] ኒዎኮንሰርቫቲቮች በዋነኛነት ለዚህ ተግባር ብቁ ነው ብለው የገመቱት የኢራቅ ብሔራዊ ኮንግረስ (አይ.ኤን.ሲ.) የሚባለውንና ከእነርሱ ጋር ተባብሮ በሚሠራው አህመድ ቻሊቢ የሚመራውን ቡድን ነው። ሪቻርድ ፐርል፣ ዎልፎዊትዝና ጀምስ ውልሲ ሕጉን ደግፈው ሎቢ ለማድረግ የጣሩ ሲሆን፣ ጄ.አይ.ኤን.ኤስ.ኤ. የተባለው ድርጅትም እንዲሁ ጥረት አድርጓል።[87] ሕጉ በተወካዮች ምክር ቤት (ሃውስ) 360-ለ38 በሆነ ድምፅ እንዲሁም በሴኔቱ ደግሞ በሙሉ ድምፅ ካለፈ በኋላ ፕሬዚዳንት ክሊንተን ጥቅምት 31/1999 ፊርማቸውን አኑረውበታል።

ክሊንተን ኢራቅን ነፃ የማውጣት ሕግን ብዙም ባይደግፉትም ድምጽን በድምጽ በመሻር መብታቸው (Veto) ተጠቅመው ውድቅ እንዳያደርጉት የግማሽ ዘመን ምርጫ (Mid-term election) ከፊት ለፊታቸው ይጠብቃቸው ነበር።[88] እንደዚያም ቢሆን እርሳቸውም ሆኑ ቁልፍ የሆኑ አማካሪዎቻቸው ቻሊቢን ዝቅ አድርገው ነበር የሚገምቷቸው። ስለሆነም ሕጉን ተግባራዊ ለማድረግ የሠሩት ጥቂት ብቻ ነው ማለት ይቻላል። እንዲያውም ክሊንተን ቢሯቸውን የመልቀቂያቸው ጊዜ እንደተቃረበ

ከተመደበው ገንዘብ ውስጥ የኢራቅ ብሔራዊ ኮንግረስን (አይ.ኤን.ሲ)ለመሳሰሉት ቡድኖች እንዲለቀቅ ያደረጉት በጣም ጥቂቱን እጅ ብቻ ነው፡፡ ፕሬዚዳንት ሳዳምን የማስወገዱን አስፈላጊነት በአንደበታቸው ከመናገር ባለፈ ለተግባራዊነቱ ያደረጉት ጥረት ኢምንት ከመሆኑም በላይ፣ እንዲያውም የዩ.ኤስ.አሜሪካን ወታደራዊ ኃይል ተጠቅመው የኢራቁን አምባገነን ለማውረድ ጭራሽ አላሰቡበትም ማለት ይቻላል፡፡[89] በአጭሩ ኒዎኮንሰርቫቲቮች የጦርነቱን አስፈላጊነት በክሊንተን ዘመን አሜሪካውያንን ማሳመን አልቻሉም ነበር ማለቱ ያስኬዳል፡፡

በቡሽ የመጀመሪያቹ የሥልጣን ወራትም ቢሆን ምንም እንኳን በርካታ ኒዎኮንሰርቫቲቮች ቁልፍ የሥልጣን ቦታዎች ላይ ቢቀመጡና የዓላማቸው ግለት ባይበርድም ኢራቅ እንድትወረር ለማድረግ በቂ ተነሳሽነትን መፍጠር አልቻሉም፡፡ ሪቻርድ ፐርል ኋላ ላይ እንደተናገሩት፡- ‹‹በእነዚያ የቡሽ የመጀመሪያ የሥልጣን ወራት በአስተዳደሩ ውስጥ ሳዳምን የመገርሰሱ ሃሳብ ምንም ዓይነት ድጋፍ አላገኘም ነበር›› ብለዋል፡፡[90] እርግጥ ነው መጋቢት/2001 ላይ የወጣው ኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ እንደዘገበው አንዳንድ ሪፖብሊካኖች ራምስፌልድና ዎልፎዊትዝ በምርጫ ጊዜ ይጠቀሙበት የነበረውን ሳዳምን የመገርሰስ ዓላማ ያልተው መሆናቸውን በመግለጽ ሲያማርሩ ተሰምተዋል። በተመሳሳይ ጊዜ የወጣው ዋሽንግተን ታይምስ ጋዜጣ በርዕሰ አንቀጹ ላይ ‹‹ሽብር ናፋቂዎች የሰላም እርግቦች ይሆናሉን?›› የሚል ርዕስ ይዞ ወጣ። የዚያ ጽሑፍ መነሻ ምክንያት ጥር 26/1992 ፒ.ኤን.ኤ.ሲ.. ለፕሬዚዳንት ክሊንተን የላከው ደብዳቤ ይዘት ነበር፡፡[91]

በ2004 ላይ የወጡት የሪቻርድ ክላርክ ‹‹Against All Enemies›› እና የሮን ሱስ ኪንድ ‹The Price of loyality› የተባሉት መጻሕፍት ያገኙትን ተቀባይነትና ያስነሱትን ውዝግብ እግምት ውስጥ ካስገባን ቡሽና ቼኒ ኢራቅን ለመውረር ያሰቡት ገና ሥልጣን እንደተቆናጠጡ ጥር 2001 ማብቂያ ላይ ነው ብለን ልናስብ እንችላለን፡፡[92] ሆኖም ግን ይህ ዓይነቱ መደምደሚያ የተሳሳተ ነው፡፡ እነርሱ በእርግጥም ሳዳምን የማውረድ ፍላጎት ሊኖራቸው ቢችል እንኳ ከመስከረም 11 በፊት ኢራቅን ለመውረር ማሰባቸውን በግልጽ የሚያመለክቱ ማስረጃዎች አልተገኙም፡፡ ቡሽ ለምሳሌ

በ2000 ባደረጉት የምርጫ ቅስቀሳ ሳዳምን የመጣል ሃሳብ አላራመዱም። ከመስከረም 11ዱ ጥቃት በፊት በሳዳም ላይ ጦርነት ለመክፈት አስበው እንደማያውቁ ለቦብ ውድዋርድ አጫውተውታል።[93] በምርጫ ዘመቻው ወቅት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አማካሪያቸው የነበሩት ኮንዶሊዛ ራይስ 2000 ላይ የውጭ ጉዳይን አስመልክቶ በጻፉት ድንቅ ጽሑፍ ላይ ‹‹ዩናይትድ ስቴትስ ኒኩሌዩር ከታጠቀች ኢራቅ ጋር መኖር አለባት›› ካሉ በኋላ ‹‹የሳዳም መደበኛ ወታደራዊ ጉልበት ክፉኛ ተደቁሷል። ስለሆነም የእርሳቸውን መንግሥት አስፈሪ የሚያደርገው ምንም ዓይነት ሁኔታ የለም›› ብለዋል።[94]

ምክትል ፕሬዚዳንት ቼኒ በ1990ዎቹ ኢራቅን መውረር ስትራቴጂያዊ ጅልነት ነው ብለው ያምኑ ስለነበር በ1998 በፕሬዚዳንት ክሊንተን ጊዜ ኒዎኮንሰርቫቲቮች በላኳቸውና ክሊንተን በኢራቅ ላይ እርምጃ እንዲወስዱ በጠየቁበት ደብዳቤዎች ላይ ፊርማቸውን አላኖሩም።[95] የ2000 የምርጫ ቅስቀሳ በተቃረበ ጊዜም በዚሁ አቋማቸው ጸንተዋል። በ1991 የትልቁ ቡሽ ዘመን የመከላከያ ሚኒስትር በነበሩበት ወቅት ባግዳድን ላለመውረር የተደረሰበትን ውሳኔ ዛሬም ማክበሩን እንደሚመርጡ ግልጽ በማድረግ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ኢራቅን በተመለከተ አሁን የያዝነውን አቋም እንደያዝን ልንቀጥል እንፈልጋለን።››[96] ስለሆነም 2001 የመጀመሪያ ወራት ላይ የፕሬዚዳንቱንም ሆነ የእርሳቸውን ሃሳብ የሚያስቀይር ነገር እንደነበር የሚያመለክቱ ምንም ዓይነት ማስረጃዎች አልተገኙም። ምናልባትም ቀደም ሲል ጀምሮ በ1998 ለክሊንተን በተላኩት ደብዳቤዎች ላይ ፊርማቸውን ያኖሩትና ጦርነቱን የደገፉት የቡሽ ባለሥልጣን መከላከያ ሚኒስትር ራምስፌልድ ብቻ ነበሩ። እርሳቸው በእርግጥም ኢራቅን ለመውረር ክፉኛ ሐገር ሲነቀንቁ መቆየታቸው ይታወቃል። የነዳጅ ኩባንያዎች፣ የጦር መሣሪያ አምራቾች፣ ክርስቲያን ጽዮናውያን ወይም ኬሎግ ብራውንና ሩትን የመሳሰሉት የመከላከያ ተቋራጮች (Defence Contractors) ኢራቅ እንድትወረር ሚና አልተጫወቱም። ስለሆነም ከሁሉም በፊት የጦር አቀንቃኞች ሆነው በብቸኝነት የቆዩት ኒዎኮንሰርቫቲቮች ነበሩ ማለት ነው።

እንደዚያም ቢሆን ምንም እንኳን ኒዎኮንሰርቫቲቮች ብቸኛቹ የጦር አቀንቃኞችና የዚያ ወረራ ዋና አቀናባሪ መሐንዲሶች ቢሆኑም፣ ክሊንተንንም ሆነ ቡሽን በማሳመን ኢራቅ እንድትወረር ማድረግ አልቻሉም። እናም ዓላማቸውን ለማሳካት አንዳች አጋዥ አጋጣሚ (ክስተት) ለማግኘት በመሻት ሲጠባበቁ ቆይተዋል። ያም ክስተት እንደ አጋጣሚ በመስከረም 11 ላይ ብቅ አለላቸው። በተለይም ያ ዘግናኝ ዕለት ቡሽና ቼኒ አስተሳሰባቸውን እንዲቀይሩና ሀገራቸውን ለመከላከል ከሚወስዷቸው እርምጃዎች አንዱ ሳዳምን ከሥልጣን ማውረድ እንዲሆን አድርጎታል። ጆርጅ ፔከርን በዚያ ሰሞን ሮበርት ኬጋን ቃለ መጠይቅ ካደረገለት በኋላ ፔከር እንዲህ ማለቱን ጽፏል። ‹‹መስከረም 11 ሁሉም ነገር የተቀየረበት ዕለት ነበር። ከዚህ ሌላ ምንም ነገር ማለት አይቻልም። አሁን ያሉት ቡሽ መስከረም 10 ላይ የነበሩት አይደሉም።›› ስኩተር ሊቢ፣ ፓውል ዎልፎዊትዝና የፕሪንስተን ዩኒቨርስቲ የታሪክ ባለሙያው በርናርድ ሊዊስ ፕሬዚዳንቱና ምክትላቸው የጦርነትን አማራጭ እንዲቀበሉ ግፊት ካሳደሩ ኒዎኮንሰርቫቲቮች መካከል ዋነኞቹ ናቸው። ለእነርሱ መስከረም 11 አሮጌውን የጦርነት አስተሳሰባቸውን ወደ አሜሪካ ባለሥልጣናት አእምሮ ለማሸጋገር መልካም አጋጣሚ የፈጠረላቸው ማለፊያ ቀን ነበር። በሮበርት ኬጋን አባባል መሠረት ‹‹ለዓለም የሚያቀርቡት ተዘጋጅቶ የተቀመጠ አስተሳሰብ ነበራቸው።›› ይህን አስተሳሰባቸውን ደግሞ በደረሰው ታላቅ ጥፋት ምን ዓይነት ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ መከተል እንደሚገባቸው ገና በቅጡ ባልወሰኑት ፕሬዚዳንቱና ምክትላቸው ላይ መጫኑ በጣም ቀላል ነበር የሆነላቸው።[98]

በተለይም ደግሞ የዎልፎዊትዝ ባሕሪ ግልጽ የወጣበት አጋጣሚ የተስተዋለው ወዲያው ነበር። መስከረም 15/2001 ላይ ከቡሽ ጋር በካምፕ ዴቪድ ባደረጉት ስብሰባ ከአፍጋኒስታን በፊት ኢራቅን የመምታትን አስፈላጊነት ለቡሽ አቀረቡ። ያንንም ያደረጉት በዩናይትድ ስቴትስ ላይ በደረሰው ጥፋት የሳዳም እጅ ስለመኖሩ ምንም የተጨበጠ ማስረጃ ባልተገኘበትና ቢንላደንም የሚገኘው አፍጋኒስታን ውስጥ መሆኑ እየታወቀ ነው።[99] ዎልፎዊትዝ ኢራቅን የመምታቱን አስፈላጊነት በየጊዜው እያነሱ

መጨቃጨቅ በማብዛታቸው ምክትል ፕሬዚዳንቱ ቼኒ ‹‹ኢራቅን የመውረሩን አስፈላጊነት ደጋግመህ እየጠቀስክ ከእንግዲህ ባታውከን መልካም ነው›› በማለት እንዲገስጿቸው ግድ ብሏቸዋል፡፡[100] አንድ የሪፐብሊካን ፓርቲ ሕግ አርቃቂ የዎልፎዊትዝን ጉዳይ አንስተው ሲናገሩ ‹‹እርሱ የኢራቅን ጉዳይ በየሰዓቱ በማንሳት ልክ እንደ በቀቀን እየደጋገመ የፕሬዚዳንቱን ነርቭ አውኮት ነበር›› ብለዋል፡፡[101] ቡሽ በመጨረሻም የዎልፎዊትዝን ሃሳብ ውድቅ አድርገው ወደ አፍጋኒስታን የሚደረገውን ዘመቻ ያስቀደሙ ቢሆንም፣ የኢራቅ ጉዳይ ያለቀለት ባለመሆኑ ፕሬዚዳንቱ ህዳር 2001 ላይ የዩ.ኤስ. ወታደራዊ እቅድ አውጭዎችን ሰብስበው ኢራቅን ለመውረር የሚያበቃ ጠንካራና ተጨባጭ እቅድ እንዲያዘጋጁ አዘዟቸው፡፡[102]

በሌላ አቅጣጫም እንዲሁ ኒዎኮንሰርቫቲቮች ይህንኑ ዓላማቸውን ለማራመድ ደፋ ቀናውን ተያይዘውት ነበር፡፡ ምንም እንኳን ሙሉ ታሪኩን ባናገኝም በርናርድ ሉዊስንና የጆን ሆፕኪንግስ ዩኒቨርስቲው ፉአድ አጀሚን የመሳሰሉት ምሁራን ምክትል ፕሬዚዳንቱ የኢራቅን መወረር እንዲደግፉ ለማድረግ ጠቃሚ ሚና እንደተጫወቱ የሚያሳዩ ማስረጃዎች ይገኛሉ፡፡[103] በእርግጥም የስኮኘ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የሆነው ጃኮብ ወይስበርግ፣ ሉዊስን ሲገልጻቸው፡- ‹‹ምናልባትም ከኢራቅ ወረራ ጀርባ የሚገኝ ወሳኝ የሆነ ምሁራዊ ተጽእኖ አድራጊ›› ብሏቸዋል፡፡[104] ቼኒ ሩቅ መሄድ ሳያስፈልጋቸው እዚያው ቢሯቸው አካባቢ ያሉት ኤሪክ ኤድልማንና ጆን ሃናህ የተባሉት ኒዎኮንሰርቫቲቭ ረዳቶቻቸውም እንኳን ታላቅ ተጽዕኖ እንዳሳደሩባቸው ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ግን በምክትል ፕሬዚዳንቱ ላይ ከሁሉም በላይ ታላቁን ተጽዕኖ ያሳረፉባቸው የእርሳቸው ኢታማዦር ሹም የሆኑት ስኩተር ሊቢ ናቸው፡፡ ሊቢ በአስተዳደሩ ውስጥ ከነበሩት የከበደ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ግለሰቦች አንዱና በኢራቅ ላይ የነበራቸው አስተሳሰብ የቅርብ ጓደኛቸውና መካሪያቸው ከሆኑት ፓውል ዎልፎዊትዝ ጋር ተመሳሳይ ነበር፡፡ [105] ከመስከመረም 11 በኋላ ኒዎዮርክ ታይምስ ባወጣው ዘገባ፡- ‹‹በቡሽ አስተዳደር ውስጥ በፓወል ዎልፎዊትዝና ስኩተር ሊቢ የሚመሩ ከፍተኛ ባለሥልጣናት አፍጋኒስታን በሚገኘው የኡሳማ ቢን ላዲን መረብ ላይ ብቻ ሳይሆን በኢራቅና በሊባኖስ ቤካ ሸለቆ ውስጥ በሚገኙ የተጠረጠሩ ቦታዎች

ላይ ሰፊ ጥቃት እንዲከፈት ተጽዕኖ አሳድረዋል›› ብሏል።[106] ፕሬዚዳንት ቡሽ በ2002 መግቢያ ላይ ሳዳምን ለማባረር እንዲወሰኑ ካደረጓቸው ጉዳዮች አንዱ የምክትላቸው አቋም መሆኑ እውነት ነው።[107]

በቡሽ አስተዳደር ውስጥ ያሉ ኒዎኮንሰርቫቲቮች በኢራቅ ላይ ጦርነት እንዲደረግ ታላቅ ተጽዕኖ ያሳደሩ መሆናቸውን የሚያሳዩና እግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ሁለት ጉዳዮችም አሉ። የመጀመሪያው ሰዎቹ ሳዳምን ከሥልጣን ለማውረድ ቁርጥ ውሳኔ ላይ መድረስ ብቻ ሳይሆን፣ በጣም አብዝተው ይጨነቁ የነበረ መሆኑን ያሳያል። አንድ የቡሽ አስተዳደር ከፍተኛ ባለሥልጣን በ2003 ሁኔታውን በአርምሞ ካስተዋሉ በኋላ እንዲህ ብለው ነበር፡- ‹‹እኔ እንደማምነው በአስተዳደሩ ውስጥ የነበሩ የተወሰኑ ሰዎች ይህን ጉዳይ አምልኮት በሚመስል ሁኔታ ይዘውት የነበረ ከመሆኑ የተነሣ በኢራቅ ላይ እርምጃ ካልተወሰደ የዓለም ፍጻሜ የሚደርስ እስኪመስል ድረስ ሃይማኖታዊ መልክ ሰጥተውት ነበር።›› አንድ የዋሽንግተን ፖስት ጋዜጠኛ የኢራቅ ወረራ ሊጀመር ሰሞን ሁሉም ላይና ታች ሲዋከብ በነበረበት ጊዜ ኮሊን ፓዎል ከዋይት ሐውስ ስብሰባ ተመልሰው እንዲህ ማለታቸውን ጠቅሷል። ‹‹በእየሱስ! ምን ዓይነት በኢራቅ ፍቅር መለከፍ ነው!›› በቦብ ውድዋርድ ዘገባ መሠረት ደግሞ የዲፌንስ ፖሊሲ ቦርድ አባል የሆኑት ኬኔት ኤድልማን (የታወቁ የኒዎኮንሰርቫቲቭ እሳቤ አራማጅ ናቸው) እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ጊዜው እየገፋ በሄደ ቁጥር ‹ጦርነት ይደረግ› የሚለው ድጋፍ እየቀነሰ የሄደ ይመስላል። እናም እኔ በዚህ መሐል ጦርነቱ ሳይጀመር እንዳልሞት ፈራሁ››[108]

ሁለተኛ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ በስለላው ተቋማትና በራሱ በወታደሩ አካባቢ ወደ ኢራቅ ለመዝመት የሚታዬው ፍላጎት አነስተኛ ነበር። ምንም እንኳ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ኮሊን ፓወል የፕሬዚዳንቱን ውሳኔ ውሎ አድሮ የተቀበሉት ቢሆንም መጥፎ ሀሳብ መሆኑን ያምኑ ነበር። በእርሳቸው ቢሮ አካባቢ የነበሩ በተለያዩ ደረጃ የሚገኙ ባለሙያዎችም ሃሳባቸውን ተጋርተዋል። ይሁን እንጂ በዚያው ቦታ ላይ ያሉና ለየት ያለ ሀሳብ ያራምዱ የነበሩ ሁለት ቁልፍ ሰዎችም ነበሩ። እነርሱም ጆን ቦልተንና ዶቪድ ውርምሰር ሲሆኑ ሁሉም ከዋይት ሐውስ ጋር ጥብቅ ቁርኝት

ያላቸው ኒዎኮንሰርቫቲቮች ናቸው። የሲ.አይ.ኤው ኃላፊ ጆርጅ ቴኔት ደግሞ ዋይት ሐውስ በኢራቅ አንጻር የጀመረውን ዕቅድ የሚደግፉ ቢሆኑም፣ ያን ያህል የበረታ የጦረኝነት መንፈስ የለባቸውም። ነገር ግን በስለላው አገልግሎት አካባቢ ጦርነት የማድረጉን ሂደት አሳማኝ ሆኖ ያገኙት ጥቂት ሰዎች ነበሩ። ለዚህም ነው ወረድ ብለን እንደምናብራራው ኒዎኮንሰርቫቲቮች የራሳቸውን የስለላ ግብረ-ኃይል እስከማደራጀት የደረሱት። ጦር ኃይሉ በተለይም የእግረኛው ሠራዊት የኢራቅን ዘመቻ በጥርጣሬ ነበር የሚያየው። የጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹሙ ጄኔራል ኤሪክ ሽንስኪ ለዘመቻው የሚያስፈልጉ ወታደሮችን ቁጥር በዕቅዱ ነድፈው ባቀረቡበት ወቅት ዎልፎዊትዝ ‹‹ብቃት የጎደለው ግምት›› የሚል ብርቱ ትችት ነበር ያወረዱባቸው። ራምስፊልድም ቢሆኑ ዘግየት ብለው በጦርነቱ አጠቃላይ ዕቅድ ላይ ያላቸውን ጥርጣሬ ከመግለጽ አልተቆጠቡም።[109] በቡሽ አስተዳደር ውስጥ የነበሩት የጦር ነጋሪት ጎሻሚዎች በአብዛኛው በዋይት ሐውስና ፔንታጎን ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ላይ የነበሩ ሲቪሎች ሲሆኑ ከሞላ ጎደል ሁሉም ኒዎኮንሰርቫቲቮች ነበሩ።

ኒዎኮንሰርቫቲቮች ኢራቅን መውረር በሽብርተኝነት ላይ የሚደረገውን ዘመቻ ለማሸነፍ አስፈላጊ መሆኑን ለማሳመን ጊዜ የሚያባክኑ አልነበሩም። ጥረታቸው በከፊል በቡሽ ላይ፣ በከፊል ደግሞ ከአስተዳደሩ ውስጥም ሆነ ውጭ ጦርነቱን የሚቃወሙ ኃይሎችን በመቋቋሙ ላይ ነበር። መስከረም 13/2001 ጀ.አይ.ኤን.ኤስ.ኤ. ‹‹ሂደቱ ከቢን ላደን አልፎ የሚሄድ ነው›› በሚል ርዕስ ባዘጋጀው ጋዜጣዊ መግለጫ ‹‹ የኦሳማ ቢን ላደንን ወንጀለኛነት ለማረጋገጥ ረዥም ሂደት የሚጠይቅ ምርምርና ማስረጃ ማሰባሰብ አያስፈልግም። እርሱ በንግግርም በድርጊትም ጥፋተኛ ነው። የእርሱ ታሪክ የተሞላው ተወቃሽ በሚያደርጉት ክስተቶች ነው። ሳዳም ሁሴንም ቢሆኑ እንደዚያው ናቸው። ባለፉት ጊዜያት የወሰድናቸው እርምጃዎች በበቂ ሁኔታ የተጠናከሩ አልነበሩም። አሁን ግን ይህን ችልተኝነታችንን ለመቀየር የሚያስችለንን አጋጣሚ የግድ መጠቀም ይኖርብናል›› ብሏል።[110] ይህ ከሆነ ከአንድ ሳምንት በኋላ በመስከረም 20 ዋና ዋና የሚባሉ ኒኮንሰርቫቲቮችና አጋሮቻቸው የተካተቱበት ቡድን ለቡሽ

የሚሰጥ ግልጽ ደብዳቤ በማዘጋጀት የሚከተለውን ማስጠንቀቂያ አዘል መልዕክት አስፍሮ ላከላቸው፡- ‹‹ምንም እንኳን ኢራቅን ከመስከረም 11ዱ ጥቃት ጋር በቀጥታ የሚያያይዛት ተጨባጭ ማስረጃ ባይገኝም፣ ማንኛውም ሽብርተኝነትንና ደጋፊዎቹን ለማጥፋት ያለመ ስትራቴጂ በኢራቅ የሚገኙትን አምባገነን ሳዳም ሁሴንን ማስወገድን ሊያካትት ይገባል››[111] ደብዳቤው በተጨማሪም ‹‹እስራኤል በዓለምአቀፉ ሽብርተኝነት አንፃር በተከፈተው ዘመቻ ታማኝ የዩ.ኤስ.አሜሪካ አጋር እንደሆነች ትቆያለች›› በማለት ቡሽን ያስገነዘባል፡፡ ከአንድ ሳምንት በኋላ ደግሞ መስከረም 28 ቀን በወጣው ዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ ላይ ቻርለስ ክራውታመር ባሰፈረው ጽሑፍ ‹‹አፍጋኒስታን ውስጥ ግዳጃችንን ካጠናቀቅን በኋላ ቀጣይዋ ሶሪያ ትሆናለች፡፡ ከዚያም ኢራንና ኢራቅ ይከተላሉ፡፡ በሽብረተኝነት ላይ የከፈትነው ዘመቻ በኢራቅ ይጠናቀቃል፡፡ ይህም ራዕያችን እውን የሚሆነው በዓለም እጅግ በጣም አደገኛ አሸባሪ የሆነውን የሳዳምን መንግሥት ገርስሰን ባግዳድን ስንቆጣጠር ነው ›› ብሏል፡፡ ከዚያም ጥቅምት 1 ቀን በወጣው ዊክሊ ስታንዳርድ ጋዜጣ ሮበርት ኬጋንና ዊልያም ክሪስቶል፣ የታሊባን መንግሥት እንደተሸነፈ ወዲያው በኢራቅ የመንግሥት ለውጥ እንዲደረግ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡[112] ሚካኤል ባሮንን የመሰሉ ምሁራንም ገና የዓለም ንግድ ማዕከል ፈርሶ አቧራው እንኳን ሳይረጋጋ ነበር በዩ.ኤስ.ኒውስ ኤንድ ወርልድ ሪፖርት ላይ፡- ‹‹ይህ ጥቃት እንዲደርስ ኢራቅ ድጋፍ ያደረገችና ምናልባትም ጥቃቱን ያቀደች መሆኗን የሚያሳዩ ማስረጃዎች ተገኝተዋል›› በማለት የጻፉት፡፡[113]

በቀጣዮቹ አሥራ ስምንት ወራት ኒዎኮንሰርቫቲቮች ኢራቅ እንድትወረር ለማድረግ የሚያስችል ድጋፍ ለማሰባሰብ የማያቋርጥ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ ሚያዝያ 3 ቀን 2002 ላይ ሌላ ግልጽ ደብዳቤ አዘጋጅተው ለቡሽ በመላክ ሳዳምን የማስወገዱ ጉዳይ ከእስራኤል ጸጥታ ጋር በቀጥታ እንደሚያያዝ ለማስረዳት ሞክረዋል፡፡[114] ደብዳቤው ፕሬዚዳንቱ እያካሄዱት ላሉት የጸረ-ሽብርተኝነት ዘመቻ እንዲሁም የእስራኤልን መንግሥት ለመደገፍ ያሳዩትን ጥረት በማድነቅ ይጀምርና ዩናይትድ ስቴትስና እስራኤል ተመሳሳይ ጠላት እንዳላቸውና የሚዋጉትም ተመሳሳይ

ጦርነት እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ደብዳቤው ይቀጥልና ቡሽ ሳዳም ሁሴንን ከሥልጣን የማውረድ ዕቅዳቸውን እንዲያፋጥኑ ይጠይቃል፡፡ ‹‹ምክንያቱም›› ይላል ደብዳቤው ‹‹ያ የማይሆን ከሆነ እስራኤላውያን ወዳጆቻችንና እኛም ራሳችን እስከዛሬ ያሳለፍነው መከራ በታላቅ ሰቆቃ ታጅቦ እንደገና ብቅ ሊል ይችላል፡፡›› ደብዳቤው የሚያሳርገው በሚከተለው መልዕክት ነው፡- ‹‹እስራኤል ከሽብርተኝነት ጋር የምታደርገው ውጊያ የእኛም ውጊያ ነው፡፡ የእስራኤል ድል የእኛ ድል ወሳኙ ክፍል ነው፡፡ በሞራላዊና ስትራቴጂያዊ ምክንያቶች እስራኤል ከሽብርተኝነት ጋር በምታደርገው ጦርነት ከጎኗ ልንቆም ይገባል፡፡››

የዚህ ደብዳቤ መሠረታዊ ዓላማ አራፋት፣ ቢን ላደንና ሳዳም ሁሴንን በአንድ ላይ በማድረግ እስራኤልንና ዩናይትድ ስቴትስን የሚያስጉና የሚያስፈሩ ጭራቆች አድርጎ ለመሳል ነው፡፡ በተጨማሪም ዩናይትድ ስቴትስ እነዚህን ሰዎች ከባድ ጠላቶች አድርጋ እንድትቆጥራቸውና ለሁለተኛው ኢንቲፋዳ እስራኤል ያሳየችውን የጠጣር መስመር አጸፋ (Hard line response) ተገቢ አድርጎ ለማቅረብ ነው፡፡ ቀደም ባለው ምዕራፍ እንደተገለጸው በቡሽ አስተዳደርና በሻሮን መንግሥት መካከል የነበረው ግንኙነት 2002 ሚያዝያ ላይ ይህ ደብዳቤ እየተጻፈ በነበረበት ጊዜ ሁሉ በጠብ ሻክሮ ነበር፡፡ ከደብዳቤው ላይ ፊርማቸውን ካኖሩት መካከል ኬኔት፣ ኤድልማን፣ ዊልያም ቤኔት፣ ሊንዳ፣ ሻቬዝ፣ ኤሊዮት ኮኸን፣ ሚድጊ፣ ዶክተር፣ ፍራንክ ጋፍኒ፣ ራውል ማርክግሪችት፣ ዶናልድ ኬጋን፣ ሮበርት ኬጋን፣ ዊሊያም ክሪስቶል፣ ጆሹዋ ሙራቪችክ፣ ማርቲን ፔሬትዝ፣ ሪቻርድ ፐርል፣ ዳንኤል ፓይፕ፣ ኖርማን ፖድሆርትዝና ጀምስ ውልሲ ይገኙበታል፡፡

አፍቃሪ--እስራኤል የሆኑ፣ ሆኖም ግን ኒዎኮንሰርቫቲቭ ያልሆኑ ሌሎቹ ፖለከኞችም ቢሆኑ የጦርነት አታሞ ደላቂዎች መሆናቸውን አሳይተዋል፡፡ የጦርነቱ ሁኔታ ትልቅ እመርታ ያሳየው 2002 ላይ የኬኔት ፓላክ 'ትሪቲንግ' ስቶርም (አስፈሪው ማዕበል) የሚል የመጥፎ ገድ ስያሜ የተሰጠው መጽሐፍ በታተመ ጊዜ ነበር፡፡ መጽሐፉ ሳዳም አደጋን የሚደቅኑና መሠረተ ቢስ ጥላቻ የሚያሳዩ ሰው መሆናቸውን በመጥቀስ

እርሳቸውን ከጥፋት ለማገድ የመከላከያ ጦርነት ማድረጉ ለምርጫ የሚቀርብ ጉዳይ አለመሆኑን ያትታል። ፖላክ የቀድሞ የክሊንተን አስተዳደር ባለሥልጣንና በዚያ ጊዜ ሳዳምን ከሥልጣን ማባረር የማይመስል ቅዠት እንደሆነ በግልጽ ይናገሩ የነበሩ በመሆናቸው አሁን አቋማቸውን ቀይረው የጦርነት ደጋፊ በመሆን መጽሐፍ እስከመጻፍ መድረሳቸው (ምንም እንኳን መጽሐፉ በመረጃዎች የተሞላ ቢሆንም) መጠነኛ ግርታን መፍጠሩ አልቀረም።[115] ፖላክ ‹ካውንስል ፎር ፎሬን ሪሊሽንስ› ከተባለው ድርጅት ለቅቀው ‹በብሩኪንግስ ሳባን ሴንተር ፎር ሚድል ኢስት ፖሊሲ› በተሰኘው ተቋም ውስጥ በመግባታቸው በዚያን ጊዜ እርሳቸውና የሳባን ሴንተር ዳይሬክተር ማርቲን ኢንዲክ ከጦርነቱ በፊት በነበሩት ወራቶች በርካታ ጽሑፎችንና አስተያየቶችን በተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ ለማውጣት ችለው ነበር። በእነዚያ ጽሑፎቻቸው ሳዳምን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጦር መሣሪያ ፈታሽ ቡድን አማካይነት ከእኩይ ድርጊት ለማቀብ መሞከር ትክክለኛ መፍትሄ አለመሆኑንና ኃይልን ተጠቅሞ ከእርሳቸው መገላገል አማራጭ የሌለው ትክክለኛ እርምጃ እንደሆነ በመጥቀስ ደጋግመው ቀስቅሰዋል።[116]

ኒዎኮንሰርቫቲቮችና አጋሮቻቸው ከእስራኤላውያን ጋር ተመሳሳይና ከሞላ ጎደል አንድ ዓይነት ቋንቋ በመጠቀም ጦርነቱን ለማስጀመር ጥረዋል። በ1990 ሚዮኒክ ላይ የተደረገውን ውል (Munich pact) በተደጋጋሚ እየጠቀሱ ሳዳምንም ከሂትለር ጋር፣ እንዲሁም ጦርነቱን የተቃወሙትን (ብረንት ስኮውክሮፍትና ሴናተር ቸክ ሄግልን) ከእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ኒቭል ቻምበርሊይን ጋር እያነጻጸሩ ነበር የሚከራከሩት[117] እስራኤልና ዩናይትድ ስቴትስ የተጋፈጡት ጨለምተኛና ጨፍጋጋ ‹‹ዓለም አቀፋዊ ሽብርተኝነት ነው››፤ እንዲሁም በኒው-ዮርክ ታይምሱን አምደኛ ዊሊያም ሳፊርን አባባል ለመጥቀስ ኢራቅ ‹‹የዓለም ሽብርተኝነት ማዕከል ነች።››ይላሉ[118] ጦር አናፋሾቹ ሳዳምን የሚስሏቸው በዩናይትድ ስቴትስና እስራኤል ላይ የጅምላ ጨራሽ ጦር መሣሪያን ከመጠቀምና ለአሸባሪዎችም ከማስተላለፍ የማይመለሱ አጋሚዶ እንደሆኑ አድርገው ነው።[119] ዲፕሎማሲንና የሶስትዮሽን የተባበሩት መንግሥታት የመሣሪያ ፈታሾች

እንቅስቅሴ እንደ ድክመት በመቁጠር የኒዎኮንሰርቫቲቭ አፈቀላጤዎች በኢራቅ ያሉትን የተባበሩት መንግሥታት ፈታሾች አናንቀዋል። የፈረንሳይን ስም ማንሳት አያስፈልግም።[120] በእርግጥም እነርሱ ያረጀ ያፈጀውን የእስራኤላውያን ብሂል በማስታወስ የኃይል ሚዛኑን ማስተካከል በመካከለኛው ምሥራቅ ያለውን ታላቅ ፋይዳ በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል ቆርጠው የተነሱ መሆናቸውን ለማሳዬት ጥረዋል። በአጭሩ የቻርለስ ክራውታመርን አባባል ለመጥቀስ ‹‹ከሁሉም በላይ ክብርን የሚገዛው ኃይል ነው።››[121]

‹‹ለፕሬዚዳንቶች የሚጻፉ ግልጽ ደብዳቤዎች፣ በጋዜጣ አምዶች ላይ የሚሰፍሩ መጣጥፎች፣ መጽሐፍት፣ አስተያየቶች በፖሊሲ ቀረጻው ሂደት ላይ ያላቸው ሚና ተጋንኗል›› ብሎ የሚከራከር ሰው ሊኖር ይችላል። ‹‹ሆነም ቀረም በአንጻራዊ ሁኔታ ቢታይ፣ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ የሚጻፉ ግልጽ ደብዳቤዎችን የሚያነቡ ሰዎች ቁጥር አነስተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ብዛት ባላቸው የአሜሪካ የተለያዩ ጋዜጦች ላይ ከኢራቅ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው እጅግ በርካታ ርዕሰ አንቀጾች፣ መጣጥፎችና አስተያየቶች ይታተሙ የለምን?›› ሊልም ይችላል። ይሁን እንጂ ይህ ዓይነቱ አመለካከት የተሳሳተ ነው። ለፕሬዚዳንት ቡሽና ክሊንተን በተጻፉ ደብዳቤዎች ላይ ፊርማቸውን ያኖሩ ሰዎች ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑና በካፒቶል ሂል ከሚገኙ የተለያዩ ፖሊሲ አውጪ ግለሰቦችና የሕግ አርቃቂዎች ጋር ግንኙነት ያላቸው ሲሆን፣ ከተወሰኑት ጋር ደግሞ በተለያዩ አጋጣሚዎች አብረው የሠሩና የሚቀራረቡ ናቸው። እርግጥ ነው ለክሊንተን በተጻፉት ደብዳቤዎች ላይ የፈረሙ ሰዎች ራምስፊልድ፣ ዎልፎዊትዝና ዶግላስ ሬይዝን ጨምሮ በቡሽ አስተዳደር ዘመናት የፖሊሲ አውጪዎች ሆነዋል። ስለሆነም ከመስከረም 11 እስከ ኢራቅ ወረራ ድረስ ባለው ጊዜ ለቡሽ በተጻፉ ደብዳቤዎች ላይ ፊርማቸውን ያስቀመጡ ሰዎች ጨኽታቸውን የገደል ማሚቶ በልቶት አልቀረም ማለት ነው። ይህ እውነታ በሁለቱ የዩ.ኤስ.አሜሪካ ግንባር ቀደም ጋዜጦች፣ ማለትም በዋሽንግተን ፖስትና በኒው-ዮርክ ታይምስ ላይ ኢራቅን አስመልክተው በተደጋጋሚ ሲጽፉ ለነበሩት ቻርለስ ክራውታመርና ዊሊያም ሳፊርም ይሠራል። የእነርሱ

አስተያየቶች በዩናይትድ ስቴትስ አስተዳደር ውስጥም ሆነ ውጭ በሚገኙ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች ዘንድ ትልቅ ሞገስ የሚቸራቸው ከመሆኑም በላይ፣ የኒዎኮንሰርቫቲቮች መጽሔት በሆነው ዊክሊ ስታንዳርድ ላይ እንደሚወጡት ጽሑፎች ነው የሚቆጥሩት፡፡ ከአስተዳደሩ ውጪ በሆኑ ሰዎች የሚወጡ እነዚህ ጽሑፎች በቡሽ አስተዳደር ውስጥ ሆነው የኢራቅን መወረር አስፈላጊነት እያነሱ ለሚከራከሩ ሰዎች ታላቅ የሀሳብ ምርኩዞች ሆነዋቸው ነበር ማለት ይቻላል። የዚህ ሁሉ ጥረት ዋነኛ ምክንያት የሚካሄዱትን ክርክሮች ሁሉ በመርታት ኢራቅን የመውረሩ ሃሳብ አሸናፊ ሆኖ እንዲወጣ ማስቻል ነው፡፡ ወረራ ማካሄድ አስፈላጊና ጠቃሚ እንደሆነ የማሳያ ስዕል መፍጠር፤ ይህን ሃሳብ የሚቃረኑ ሰዎች በሽብርተኝነት ላይ የላላ አቋም ያላቸው መሆናቸውን ማጉላት፣ የአሜሪካንና የእስራኤልን እጣ ፋንታ በሞራላዊና ስትራቴጂያዊ ምክንያታዊነት እሳቤ አንድ ላይ ማስተሳሰር፣ የኒዎኮንሰርቫቲቭ እሳቤ አራማጆች ታክቲኮች ናቸው፡፡ እናም በዚያም በዚህም ብለው አይቀሬ የሆነውን ጦርነት ለማቀጣጠል በቅተዋል፡፡[122]

በኢራቅ ላይ የስለላ መረጃዎችን ማሰባሰብ

የኢራቅን ወረራ በተመለከተ ድጋፍ ለማግኘት ከሕዝብ ግንኙነት ቁልፍ ተግባሮች አንዱ ሳዳምን ምንጊዜም መወገድ የሚገባቸው ፤ አስፈሪና አምባገነን አድርጎ ለመሳል የሚያስችሉ የሥለላ መረጃዎችን ማሰባሰብ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ተገቢውን ጥረት ለማድረግ ኃላፊነቱን የወሰዱት ስኩተር ሊቢ ሲሆኑ ወደ ሲ.አይ.ኤ. ቢሮ በተደጋጋሚ እየተመላለሱ ጦርነቱን ለማስጀመር የሚያስችሉ በቂ መረጃዎች ይኖሩ እንደሆነ በማለት ለመለቃቀም ሞክረዋል። ሊቢ በተጨማሪም የኢራቅን አስጊነት አስመልክቶ 2003 ላይ ለኮሊን ፓወል የቀረበውን ዝርዝር ሪፖርት በተባባሪነት አዘጋጅተዋል፡፡ ፓዎል ያኔ ለተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት የሚያቀርቡትን አስከፊ ዘገባ እያዘጋጁ ነበር፡፡[123] ቦብ ዊድዋርድ እንደተናገረው፣ ‹‹ሊቢ ካገኙት ልቅምቃሚ ወሬ በመነሳት አስቀያሚ ከሆነ መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡››[124] ምንም እንኳን ፓወል የሊቢን አገም

ጠቀም የሆነ መረጃ፣ ‹‹ በአብዛኛው የማይመስል ነው›› በማለት ያጣጣሉባቸው ቢሆንም፣ ለተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ራሳቸው ያቀረቡት ዘገባም ቢሆን (አሁን ዘግይተው ራሳቸው ፓዎል እንዳመኑት) በስህተቶች የተሞላ ነበር።[125]

የስለላ መረጃዎችን ለማንቀሳቀስ የተደረገው ጥረት ጦር ናፋቂ ከሆኑ የሕትመት ውጤቶች ዘንድ በመድረሱ ከመስከረም 11 በኋላ ሁለት ድርጅቶች ተመስርተው ለመከላከያ ሚኒስትር ዲኤታ ዶግላስ ፌይዝ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ተደረጉ።[126] የጸረ-ሽብርተኝነት ገምጋሚ ቡድንም፣ በአል-ቃኢዳና በኢራቅ መሳከል ያለውን ግንኙነት እንዲመረምር (የስለላው ማሕበረሰብ ሊያገኘው ያልቻለውን) ኃላፊነት ተሰጠው። የቡድኑ ቁልፍ አባላት ዴቪድ ውርምሰርና ሪቻርድ ፐርልና ከሁለቱ ጋር ማለፊያ ቅርርብ ያለው ሊባኖሳዊ አሜሪካዊው ሚካኤል ማሉፍ እንዲሆኑ ተደረገ። የኒውዮርክ ታይምሱ ሪፖርተር ጀምስ ራይሰን እንደጻፈው፡- ‹‹ የእስራኤል የስለላ ተቋም ፓውል ዎልፎዊትዝ በሲ.አይ.ኤ ላይ እምነት እንዳይኖራቸው ለማድረግ ድብቅ ሚና ተጫውቷል›› ብሏል። እናም ይህ በሲ.አይ.ኤ. አሠራር አለመደሰታቸው ዎልፎዊትዝ እምነታቸውን በኢራቁ ተቃዋሚ መሪ አህመድ ቻሊቢ ላይ እንዲጥሉ አድርጓቸዋል።[127]

ዘ. ኦፊስ.ኦፍ ስፔሻል ፕላንስ (ኦ.ኤስ.ፒ) የተሰኘው ድርጅት በኢራቅ ላይ ጦርነት ለመክፈት የሚያስችሉ ማስረጃዎችን እንዲያሰባስብ መመሪያ ተላለፈለት። ድርጅቱን እንዲመሩ የተሰየሙት ከፓወል ዎልፎዊትዝ ጋር ቅርበት ያላቸው ኒዎኮንሰርቫቲቭ አብራም ሸልስኪ ሲሆኑ፣ አብረዋቸው እንዲሠሩ ከተመደቡት መሳከል የአፍቃሪ-እስራኤል ቲንክ ታንክ አባሎች የሆኑት ለአብነት ያክል ከአሜሪካን ኢንተርፕራይስ ኢንስቲትዩት ሚካኤል ሩቢን፣ ከዋሽንግተን ኢንስቲትዩት ፎር ኒር ኢስት ፖሊሲ ዴቪድ ሽንከርና ከኮሌጅ እንደተመረቀ ለጠቅላይ ሚኒስትር ሽሞን ፕሬዝ ሲሠራ የቆዬው ሚካኤል ማኮቭስኪን የመሳሰሉት ናቸው።[128] ኦ.ኤስ.ፒ. መረጃዎችን በብዛት የሚያገኘው ከአህመድ ቻላቢና ከሌሎች ኢራቃዊ ስደተኞች እንዲሁም ከበርካታ የእስራኤል የስለላ ምንጮች ነው። ዘ ጋሪዲያን ጋዜጣ ባወጣው ዘገባው ‹‹ በጊዜው በአሪዮል ሻሮን ቢሮ ውስጥ ከሞሳድ ጎን ለጎን የሚሠራ

ልዩ (ad-hoc) ቡድን ተደራጅቶ ኢራቅን የሚመለከቱና ሞሳድ ይፋ ሊያደርጋቸው ያልተዘጋጀባቸውን የስለላ መረጀዎች ለቡሽ አስተዳደር ያቀብል ጀመር ›› ብሏል፡፡[129] የፔንታጎን ኢንስፔክተር ጄኔራል በየካቲት ወር ይፋ ባወጣው ዘገባ ኦ.ኤስ.ፒ. የሚያሰራጫቸውን የደህንነት መረጃዎች ‹‹በእኛ እምነት አጠቃላዩ የስለላው ማሕበረሰብ በጋራ ከደረሰበት ስምምነት ጋር የሚቃረኑና ተገቢ ያልሆኑ መረጃዎች ናቸው›› ቦማለት አጣጥሏቸዋል፡፡[130]

በፔንታጎንና ዋይት ሐውስ ውስጥ የሚገኙ ኒዎኮንሰርቫቲቮች ኢራቅን አስመልክቶ ለሚያገኙት መረጃ በቻላቢና በሰዎቻቸው ላይ በከባዱ ጥገኛ መሆን ብቻ ሳይሆን፣ ሳዳም ከወረዱ በኋላ ለወደፊቱ ኢራቅን የመምራቱን ኃላፊነት የሚረከቡ ታጋይ እንደሆኑ አድርገው ነበር ቻላቢን የሚቆጥሯቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሲ.አይ.ኤና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቻላቢ የማይታመኑና ለቦታው አስተማማኝ ያልሆኑ እንደሆኑ ነበር የሚያስቡት፡፡ ስለሆነም እርሳቸውን ማራቁን መርጠዋል። ያ ከባድ መደምደሚያ አሁን ትክክለኛ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፣ እንደምናውቀው ቻላቢና አይ.ኤን.ሲ.. ለዩናይትድ ስቴትስ ያቀበሉት መረጃ ሁሉ ውሸት በመሆኑ ከዩናይትድ ስቴትስ ወራሪ ኃይል ጋር የነበራቸው ግንኙነት ወዲያውኑ ሊቋረጥ በቅቷል፡፡ ቻላቢን ምንም እንኳን ቢያስተባብሉም ኋላ ላይ ለኢራን መረጃዎችን በማቀበል ወንጀል ተከሰዋል፡፡ ኒዎኮንሰርቫቲቮች ቻላቢን ‹‹ የኢራቅ ጆርጅ ዋሽንግተን ›› በማለት ቢያሞካሿቸውም ሰውዬው እዚህ ግባ ከሚባል ቁም ነገር ላይ የሚውሉ ሆነው አልተገኙም፡፡[131]

ታዲያ ለምንድን ነው ኒዎኮንሰርቫቲቮች ቻላቢን ያቀፉት? የኢራቅ ናሽናል ካውንስል (አይ.ኤን.ሲ) መሪ በሎቢው ውስጥ ካሉ ግለሰቦችና ቡድኖች ጋር ትስስር ለመፍጠር ረዥም ርቀት በመጓዛቸው ምክንያት ነው፡፡ በተለይም ደግሞ ጄ.አይ.ኤን.ሲ.ኤ. ከተባለው ድርጅት ጋር ይበልጥ የሚቀራረቡ ሲሆን ከ1997 ጀምሮ በተካሄዱ የድርጅቱ የቦርድ ስብሰባዎች፣ ሲምፖዚየምና ሌሎች ክስተቶች ላይ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡[132] በተጨማሪም አይፓክ፣ .ኤ.ኢ..አይ.ና፣ ዘ ሆድሰን ኢኒስቲትዩት ቻላቢን ‹‹ብርቅዬ ተፈጥሮ ያላቸው፣ በአረቡ ዓለም ውስጥ ጠልቀው የገቡና በመሠረታዊነት የምዕራቡ ዓለም ሰው የሆኑ›› እያሉ ያሞካሹዋቸዋል፡፡[133] ምሽግ ውስጥ የነበሩት ቻላቢ በሕዳር

2005 በኤ.ኢ.አይ ጉባዔ ላይ ለስምንተኛ ጊዜ ንግግር ለማድረግ በተገኙ ጊዜ የቲንክ ታንክ (የመንግሥት አማካሪ ድርጅቶች) ፕሬዚዳንት ‹‹ታላቅና በጣም ጎበዝ ኢራቃዊ አርበኛ፣ ነፃና ነፃ አውጪ›› በማለት ነበር ለጉባኤው እድምተኞች ያስተዋወቋቸው።[134] የቻላቢ ሌላው ትልቅ ደጋፊ በርናርድ ሊዊስ ሲሆን፣ ባግዳድ ነፃ ከወጣች በኋላ የኢራቅ መሪ ይሆናሉ በማለት ይከራከርላቸው ነበር።[135]

ሎቢው ላደረገላቸው ድጋፍ አጸፋ ይሆን ዘንድ ቻላቢ ሥልጣን ላይ ከተደለደሉ በኋላ ከእስራኤል ጋር መልካም ግንኙነት ለመመሥረት ቃል ገቡ። በዶግላስ ፌይዝ የቀድሞ የሕግ ባልደረባ ኤል ማርክ ዜል አባባል መሠረት ቻላቢ እስራኤል ውስጥ ከምትገኘው ሃይፋ ከተማ ተነስቶ እስከ ኢራቋ ሞሱል ከተማ ድረስ ተዘርግቶ የነበረውንና ኋላ ላይ የተቆረጠውን የነዳጅ ማስተላለፊያ ቧንቧ መልሰው ለማስቀጠል ቃል ገብተዋል።[136] እንዲህ የመሰለውን አባባል ነው የእስራኤል ደጋፊ የሆኑና በኢራቅ የመንግሥት ለውጥ እንዲደረግ የሚሹ ኃይሎች መስማት የሚሹት። ሕልማቸው እውን ይሆን ዘንድም ቻላቢን መደገፋቸውን ቀጠሉ። ማቲው በርገር የተባለው ጋዜጠኛ በጅዊሽ ጆርናል ላይ ቸለቢ ከአፍቃሪ እስራኤል ወገኖች ጋር የፈጠሩትን መግባባት እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡- ‹‹የኢራቅ ናሽናል ኮንግረስ (አይ.ኤን.ሲ) ከሎቢው ወገኖች ጋር ያለውን ግንኙነት በእየሩሳሌምና በዋሽንግተን የአይሁዳዊያንን ተጽዕኖ ለማነቃቃትና ለእርሱ የሚያደርጉትን እገዛ እንዲጨምሩ ለማድረግ ሊጠቀምበት አስቧል። አይሁዳዊያን ቡድኖች በበኩላቸው በእስራኤልና በኢራቅ መካከል ያለው ግንኙነት በሚገባ ይሻሻል ዘንድ አይ.ኤን.ሲ.. የግድ የሳዳም ሁሴንን አገዛዝ መተካት እንዳለበት ሙሉ እምነት አሳድረዋል››[137] ናታን ጉትማን ‹‹የአሜሪካን አይሁድ ማህበረሰብና የኢራቅ ተቃዋሚ ቡድን በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ለመደበቅ ለአራት ዓመታት ያክል ሲሰቃዩ ቆይተዋል ››በማለቱ ልንደነቅ አይገባም።[138]

ኒዎኮንሰርቫቲቮችና አጋሮቻቸው ሲደክሙ የኖሩት ያለምንም ጥቅም በብላሽ አልነበረም። እርግጥ ነው ዩናይትድ ስቴትስ በኢራቅ ላይ እንድትዘምት ለማድረግ አልቻሉ ይሆናል። ቀደም ባሉት ምዕራፎች ለማብራራት

እንደሞከርነውም የመስከረም 11ዱ ጥቃት ባይኖር ኖሮ ምናልባትም ፕሬዚዳን ቡሽና ምክትላቸው ዲክ ቺኒ ስር ነቀል የሆነ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን ለመከተል አይችሉም ነበር። ምክትል መከላከያ ሚኒስትሩን ፓውል ዎልፎዊትዝን የመሰሉ ኒዎኮንሰርቫቲቮች ከ1998 ጀምሮ በኢራቅ የመንግሥት ለውጥ እንዲመጣ ሲጥሩ የቆዩ እንደመሆናቸው የመስከረም 11ዱ ጥቃት እንደተደረገ ሁኔታውን ለዓላማቸው ማስፈጸሚያነት ከመጠቀም አላቅማሙም። በዚሁ አካሄዳቸው ተጠቅመውም ምንም እንኳን ሳዳም ከአል-ቃኢዳ ጋር ትስስሮሽ እንዳላቸው የሚያሳይ ጉልህ ማስረጃ ባያገኙም የእርሳቸው መውረድ በሽብርተኝነት ላይ የተጀመረውን ዘመቻ በአሸናፊነት ለመወጣት ወሳኝ እንደሆነ አድርገው ማቅረቡን ችለውበታል።

ሪቻርድ ፐርል የኢራቅ ጦርነት እውን ይሆን ዘንድ ኒዎኮንሰርቫቲቮች ስለተጫወቱት ሚና ለጆርጅ ፒከር እንዲህ በማለት አጫውቶታል፡- ‹‹ቡሽ የአስተዳደራቸውን ሥፍራዎች በብረንት ስኮውክሮፍትና ጂም ቤከር በተመረጡ ሰዎች ሞልተዋቸው ቢሆን ኖሮ አሁን የተፈጠረው የፖለቲካ ምስቅልቅል ባልተፈጠረና የመንግሥታቸውም ገጽታ እንዲህ ባልጠለሸ ነበር።››[139]

የኒው ዮርክ ታይምሱ ቶማስ ኤል ፍሪድማን ግንቦት 2003 ላይ ለሃ‹ኤሬትዝ ጋዜጠኛ አሪ ሻቪት ተመሳሳይ ሃሳብ እንደሚከተለው አጋርቶታል፡- ‹‹ያ ጦርነት ኒዎኮንሰርቫቲቮች የፈለጉት ጦርነት ነው።...ያ ጦርነት ኒዎኮንሰርቫቲቮች የፈጠሩት ጦርነት ነው...። ከፊለግክ እዚሁ ዋሽንግተን ውስጥ በአምስት የሕንፃ ክፍሎች (Blocks) ውስጥ በተቀራራቢ ሥፍራ የሚገኙ የሃያ አምስት ሰዎችን ስም ልዘርዝርልህ እችላለሁ። እነዚህን ሰዎች ከአንድ ዓመት ወይም ከአንድ ዓመት ከመንፈቅ በፊት ወደ ምድረበዳ መውሰድ ቢቻል ኖሮ የኢራቅ ጦርነት እውን አይሆንም ነበር። ›› እኛም በሪቻርድ ፐርልና በፍሪድማን ሃሳብ የምንስማማ ከመሆናችን በተጨማሪ የኢራቅ ጦርነት እንዲደረግ ካስቻለው ውሳኔ ላይ ለመድረስ የግለሰቦች፣ የሃሳቦችና የክስተቶች አንድ ላይ መጣመር ወሳኝነት የነበረው መሆኑንም እንቀበላለን።[140]

እውን የኢራቅ ጦርነት የነዳጅ ዘይት ጦርነት ነውን?

ይህን መጽሐፍ የሚያነቡ የተወሰኑ ሰዎች ‹‹የእስራኤል ሎቢ ኢራቅ እንድትወረር የተወሰነ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችል እንደሆነ እንጂ ለወረራው በተደረገው የውሳኔ ሂደት ላይ የሚኖረው ሁለንተናዊ ክብደት በመጠን አነስተኛ ነው›› ሊሉ ይችላሉ፡፡ ብዙ አሜሪካውያንና የውጭ ሰዎችም “2003 ላይ ለተፈጸመው የኢራቅ ወረራ ዋነኛው መነሻ የእስራኤል ሎቢ ሳይሆን የነዳጅ ዘይትን ለመቆጣጠር የነበረ ጽኑ ፍላጎት ነው” በማለት ይከራከራሉ፡፡ በዚህ ትረካ አንድ ገጽታ እንደተጠቀሰው “የቡሽ አስተዳደር የመካከለኛውን ምሥራቅ የነዳጅ ክምችት ለመቆጣጠር ወስኗል፡፡ ምክንያቱም ዩናይትድ ስቴትስ ያንን ማድረጓ በፓለቲካ ባላንጣዎቿ ላይ ትልቅ የጂኦፓለቲካዊ ተጽዕኖ ለማሳረፍ እንድትችል ያግዛታል” የሚል አባባል ይሰማል፡፡ በዚህ አባባል መሠረት ኢራቅን መውረር ይህን ግብ ለማሳካት እንደትልቅ እርምጃ ይቆጠራል፡፡ ከዚህ አባባል ጋር ተያያዥነት ያለው ሌላ ትረካ ደግሞ “ሌሎች የነዳጅ አምራች መንግሥታትና በተለይም የነዳጅ ኩባንያዎች ከኢራቅ ጦርነት ጀርባ የሚገኙና የነዳጅ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምርላቸው በመሻት ለትርፋቸው የሚያደቡ ወንጀለኞች ናቸው ” የሚል ነው፡፡ ሌላው ይቅርና ፎርማን ቾምስኪን የመሳሰሉት እስራኤልንና ሎቢውን በመተቸት የሚታወቁ ምሁራን ጭምር በፊልም ባለሙያው ማይክል ሙር 2004 ላይ ‹ፋራናይት 9/11› በተባለ ዘጋቢ ፊልም በስፋት የተንጸባረቀውን ይህን ሃሳብ ይጋራሉ፡፡[141]

ኢራቅ በዋነኛነት የተወረረችው ለነዳጅ ተብሎ ነው የሚለው አባባል ነዳጅ በዘመናችን በዓለም ምጣኔ ሃብት ላይ እየተጫወተ ያለውን ቁልፍ ሚና ያገናዘበ ነባር አባባል እንደሆነ ይታወቃል፡፡[142] ይሁን እንጂ አገላለጹ ስነ-አመክኖአዊነት የጎደለውና የዘልማዳዊ አባባል (empirical) የመሆን አደጋ የተደቀነበት ነው፡፡ ምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለጸው የዩ.ኤስ.አሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎች የፋርስ ባሕረ-ሰላጤን ነዳጅ አንድ ጡንቻው የፈረጠመ መንግሥት አጠቃልሎ እንዳይቆጣጠረው ሲጨነቁ ኖረዋል፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ በባሕረ-ሰላጤው ውስጥ ከሚገኙ በርካታ የነዳጅ አምራች ሀገራት

ጋር ትስስር የፈጠረች ቢሆንም፣ የቡሽን አስተዳደር ጨምሮ የትኛውም የአሜሪካ መንግሥት የአካባቢውን የነዳጅ አምራች ሀገራት በመውረር በመላው ዓለም በሚገኙ ሀገራት ላይ አስገዳጅ ተጽዕኖ ለማሳደር አልሞከረም። ዩናይትድ ስቴትስ ምናልባትም ዋና የነዳጅ አምራች በሆነች አንዲት ሀገር ውስጥ አብዮት ቢካሄድ ወይም በአንዳች ምክንያት ወደ ዓለም ገበያ የሚፈሰው ነዳጅ ቢቋረጥ ወረራ ልታደርግ ትገደድ ይሆናል። ሆኖም ግን በኢራቅ ያለው ሁኔታ ከዚህ የተለዬ ነው። ሳዳም ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ ለሆነ ማንኛውም ተጠቃሚ ነዳጃቸውን ለመሸጥ ፍላጎት ነበራቸው። በሌላ በኩል ደግሞ እንደተባለው ዩናይትድ ስቴትስ በባሕረ-ሰላጤው የሚገኝን በነዳጅ የበለጸገ ሀገር ለመውረር ፍላጎት ያላት ቢሆን ኖሮ፣ ትልቅ ሕዝብና አነስ ያለ ነዳጅ ካላት ኢራቅ ይልቅ ብዙ ነዳጅና አነስ ያለ ሕዝብ ያላትን ሳዑዲ አረቢያን መውረር ይቀልላት ነበር። ከዚያም በላይ ቢን ላደን የተወለደውና ያደገው ሳዑዲ አረቢያ ሲሆን የመስከረም 11ዱን ጥቃት ካደረሱት አሥራ አምስት ሰዎች ውስጥ አሥራ አንድ የሚሆኑቱ የሳዑዲ ዜጎች ነበሩ። (ከኢራቅ የተሳተፈ ማንም አልነበረም።) የቡሽ ዋነኛ ዓላማ የነዳጅ ዘይትን መቆጣጠር ቢሆን ኖሮ የመስከረም 11 ክስተት ዓይነተኛ የጦርነትና የወረራ ማመካኛ ሊሆን በቻለም ነበር። ሳዑዲ አረቢያን መውረር በእርግጥ ቀላል ሥራ እንዳልሆነ ይታወቃል። ቢሆንም ግን ትልቅ ሕዝብና የታጠቀ ሠራዊት ያላትን ኢራቅን ለመውረር ከመሞከር ይልቅ የተሻለና አነስተኛ ጥረት የሚጠይቅ ተግባር እንደሆነ ግልጽ ነው።

ከ2002-2003 ባለው ጊዜ የቡሽ አስተዳደር ኢራቅን እንዲወር የሚገፋፋው የነዳጅ ፍላጎት ውጥረት እንደነበረበት የሚያሳዩ መረጃዎችን ማግኘት ያስቸግራል። በንጽጽር ካየነው ከ1990-1991 በነበሩት ዓመታት የሳዑዲ መሪዎች በኩዌት ላይ ወረራ የፈጸመችውን ኢራቅን በፍጥነት ያስወጡ ዘንድ የአሜሪካን መሪዎች ጫት ማት ይጫኑ እንደነበር ይታወቃል። በዚያ ወቅት ሳዑዲዎች ልክ እንደ በርካታ የአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎች ሁሉ ሳዳም በቀጣይነት ሳዑዲን ሊወሩ ይችላሉ የሚል ፍርሃት አድሮባቸው ነበር። ያን ማድረግ ከቻሉ ደግሞ በክልሉ የሚገኘውን አብዛኛውን የነዳጅ ሀብት በቁጥጥራቸው ስር ያገባሉ ማለት ነው። በጊዜው በአሜሪካ የሳዑዲ ባለሙሉ

ሥልጣን አምባሳደር የነበሩት ልዑል ባንደር ሳዳምን ከኩዌት ለማባረር አፍቃሪ-እስራኤል ከሆኑ ቡድኖች ጋር ሳይቀር በመተባበር ሲሠሩ የቆዩትም ለዚህ ነበር፡ ፡[143] ዳሩ ግን ሁለተኛውን የባሕረ-ሰላጤውን ጦርነት በተመለከተ ጉዳዩ ለዬት ያለ መልክ ነበር የተላበሰው። በዚያ ጊዜ ሳዑዲ አረቢያ፣ አሜሪካ በኢራቅ ላይ ልታደርገው ያሰበችውን ጦርነት በግልጽ ነበር ተቃወመችው።[144] ሳዑዲዎች ጦርነቱ ኢራቅን በመፈረካከስ መካከለኛው ምሥራቅን ወደ አለመረጋጋት ያስገባዋል የሚል ስጋት ነበራቸው። በተጨማሪም ኢራቅ እንደተፈራው ባትፈረካከስና መረጋጋት ቢሰፍንባት እንኳ የሺዓ መስመር ተከታዮችን ሥልጣን የመያዝ አጋጣሚ ሰፊ ያደርገዋል። ያ ማለት ደግሞ ኢራን በክልሉ አብዛኛዎቹ የሱኒ መንግሥታት ላይ የበላይነቷን የምታጠናክርበትን ዕድል ይከፍትላታል። ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ ሳዑዲዎች በሀገር ውስጥ እያደገ የመጣው ጸረ-አሜሪካ ስሜት አሜሪካ ኢራቅን ከወረረች በኋላ የበለጠ ይባባስና ሌላ መዘዝ ያመጣል ብለውም ይሠጋሉ።

የነዳጅ አምራች ኩባንያዎች ከሳዳሚ ኢራቅም ሆነ ከኢስላማዊት ሪፐብሊክ ኢራን ጋር የተለሳለሰ ግንኙነት በመፍጠር አጠቃላይ ሰላም እንዲኖር ነው የሚሹት። የ2003ቱን የኢራቅ ወረራ ሎቢ ሊያደርጉ ይቅርና ጦርነቱ ራሱ የማይረባ ሀሳብ እንደሆነ ነው የቆጠሩት። መስከረም 2002 ላይ በታተመው ዘ. ኒው ሪፖብሊክ ጋዜጣ ላይ ፒተር ቤናርት ሲጽፍ ‹‹በእነዚያ ዓመታት ሁሉ የአሜሪካ ነዳጅ ኩባንያዎች ሎቢ ሲያደርጉ የነበረው ጦርነት እንዲደረግ ሳይሆን ማዕቀቡ እንዲነሳ ነው›› ብሏል።[145] የነዳጅ ድርጅቶች ሁልጊዜም የሚናፍቃቸው ብዙ ትርፍ ማግኘት እንጂ ጦርነት አይደለም።

ክልሉን ወደ ዲሞክራሲ የማሸጋገር ሀልም

የኢራቅ ጦርነት አስቸጋሪና ሊያመልጡት የማይችሉት ክፉ ማጥ ተደርጎ አልነበረም የተገመተው። ከዚያ ይልቅ መካከለኛው ምሥራቅን የአሜሪካንና እስራኤልን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚያመች ሁኔታ እንደገና ለማደራጀት ለተጀመረው ታላቅ ሂደት እንደ መጀመሪያ እርምጃ ነበር የተቆጠረው። በተለይም ደግሞ ዩናይትድ ስቴትስ ሳዳምን ካስወገደች በኋላ ወደመጣችበት እንድትመለስ ሳይሆን ኢራቅን በፍጥነት ወደ ዲሞክራሲያዊው እመርታ

በማሸጋገር በአካባቢው ለሚገኙ አምባገነን መሪዎች እንደ ሞዴል እንድትታይ ለማድረግ ጭምር ነበር አልማ የተነሳችው። ምንም እንኳን በኢራቅ የሚታየውን ውጤት በተወሰኑ የአካባቢው ሀገራት ለመተግበር ሠይፍን መጠቀም የግድ ቢልም የኋላ ኋላ ዲሞክራሲን ለማዳረስ ጠቀሜታው የጎላ እንደሚሆንም ተገምቷል። እናም አንድ ጊዜ በክልሉ ዲሞክራሲ መቀጣጠል ከጀመረ ሀገራቱ ከእስራኤል እና አሜሪካ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በመከባበርና በወዳጅነት ላይ የተመሠረተ እንደሚሆን ተጠብቋል።

‹ክሊን ብሪክስ› በተሰኘው ጥናት መሠረት ደግሞ የእስራኤልና ፍልስጤምም ችግር ሁነኛ መፍትሄ የሚያገኝና ሌሎችም ግጭቶች የሚወገዱ በመሆናቸው በክልሉ የሚኖር የሸብርተኝነት እንዲሁም የኑክሌር መሣሪያን የማስፋፋትን ችግር በትልቅ መጠን እንደሚቀንስ በሰፊው ታምኖበታል።

ምክትል ፕሬዚዳንቱ ዲክ ቼኒ ይህን በተስፋ የተሞላ ክልላዊ ሽግግር አስመልክተው ነሐሴ 26/2002 ላይ ቪ.ኢ.ፍ ደብሊው በተባለው ቴሌቪዥን መግለጫ በመስጠት አስተዳደራቸው የኢራቁን ጦርነት አስፈላጊነት ለማስረዳት ሞክረዋል። ‹‹አንድ ጊዜ አስፈሪ የሆኑት ሥጋቶች ከተወገዱ›› አሉ ቼኒ በንግግራቸው ‹‹በክልሉ የሚገኙ ነፃነትን የሚወዱ ሕዝቦች የመጨረሻውን ሰላም የሚያጎናጽፏቸውን የዲሞክራሲ እሴቶች በየሀገሮቻቸው በመትከልና የመጨረሻውን ሰላማዊ ሁኔታ በማምጣት ጽንፈኞች የሚከተሉትን የጅሀድ ስትራቴጂ መልሰው እንዲያጤኑት ያደርጓቸዋል። ለዘብተኛ አቋም የሚከተሉ የሕብረተሰቡ ክፍሎችም ተገቢ ቦታቸውን ስለሚይዙ የእስራኤል-ፍልስጤምን የሰላም ሂደት ለማራመድ ያለንን ዕድል ያሰፋልናል››[146] ቼኒ ይህንን ሀሳባቸውን በቀጣዮቹ ስድስት ወራት ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሲደጋግሙት ቆዩ።

ፕሬዚዳንት ቡሽም እንዲሁ ተመሳሳይ በሆነ ግለት ኢራቅን ለመውረር ያነሳሳቸው ክልሉን ወደ ዲሞክራሲና ሰላም የማሸጋገር ፍላጎት እንደሆነ እየጠቀሱ ደስኮሩ። የካቲት 26/2003 ለኤ.ኢ.አይ. አድማጮቻቸው ‹‹ዩናይትድ ስቴትስ ነፃነትንና ሰላምን በመካከለኛው ምሥራቅ ኮትኩታ

ታሳድጋለች" ካሉ በኋላ ንግግራቸውን ቀጥለው "ዓለም የዲሞክራሲን በየቦታው መሠራጨት ይፈልጋል። ምክንያቱም ነፃና የተረጋጉ ሀገራት ጭካኔ የተሞላባቸው ግድያዎች የሚፈለፈሉባቸው አምባዎች አይሆኑም። አሁን እንደምናየው በመካከለኛው ምሥራቅ ነፃነት የመጎናጸፍ ፍላጎቶች ተስፋ በሚሰጥ አኳኋን እዚህም እዚያም እየተንጸባረቁ ነው። በኢራቅ የምናገኘው ስኬት ለመካከለኛው ምሥራቅ የሰላም ሂደት አዲስ መደላድል በመፍጠር እውነተኛና ዲሞክራሲያዊ ሰላምን ለፍልስጤም ያመጣላታል"[147] በማለት ንግግራቸውን ደመደሙ።

ይህ በተስፋ የተሞላ ስትራቴጂ መሠረቱን የጣለው ከሞላ ጎደል ሃይማኖታዊ ቀኖና በሚመስል እምነት ሲሆን፣ ዩ.ኤስ.አሜሪካ ቀደም ብላ ትከተለው ከነበረው ፖሊሲ ፈጽሞ የተለየና ቡሽም ሆኑ ቼኒ ከመስከረም 11 በፊት ሊቀበሉት የሚችሉት ስለመሆኑ ምንም ዓይነት ምልክት ያልታየበት ነበር ማለት ይቻላል። በእውነቱ ሁለቱ ወንዶችም ሆኑ የብሔራዊ ጸጥታ አማካሪያቸው ኮንዶሊዛ ራይስ፣ የክሊንተን አስተዳደር በምርጫ ውድድር ወቅት ያራምደው የነበረውን ክልሉን ወደ ዲሞክራሲ የማሸጋገር ሂደት በጽኑ ይተቹ ነበር። ታዲያ አሁን እንዲህ ዓይነት የአቋም ለውጥ በአንድ ጊዜ እንዴት ሊከሰት ቻለ? መጋቢት 2003 በዎል ስትሪት ጆርናል ላይ የወጣ አንድ ጽሑፍ እንዳተተው ዩ.ኤስ.አሜሪካ መካከለኛው ምሥራቅን አስመልክቶ ያላትን አቋም እንድትቀይር ከኋላ ሆነው ያነሳሷት ዋነኛ ኃይል እስራኤልና በሎቢው ውስጥ ያሉ ኒዎኮንሰርቫቲቮች ናቸው። በጋዜጣው ርዕሰ አንቀጽ ላይ የወጣ ሌላ ጽሑፍ ደግሞ እንዲህ ይላል፦ "የፕሬዚዳንቱ ሕልም አንድን ሀገር ሳይሆን ክልሉን እንዳለ መቀየር ነው። ይህ የአፍቃሪ-አሜሪካ ዲሞክራሲያዊ ግብ ከጀርባው በእስራኤልና በኒዎኮንሰርቫቲቮች ግፊት የሚነዳ ነው።"[148]

ነሐሴ 2002 ላይ ዮቫል ስቲንትዝ የተባሉ የሊኩድ ፓርቲ ተወካይና የክኔሴት (የእስራኤል ምክር ቤት) የውጭ ጉዳይና መከላከያ ኮሚቴ አባል ለክሪስቲያን ሳይንስ ሞኒተር ጋዜጣ በሰጡት አስተያየት፦[149] "ኢራቅን የዩ.ኤስ.አሜሪካ ወታደሮች ከተቆጣጠሩና በአፍጋኒስታን እንዳለው ዓይነት የመንግሥት ለውጥ ካመጡ የኢራቅ ወታደራዊ ጦር ሰፈር የአሜሪካም

ወታደራዊ ጦር ሰፈር(base) ስለሚሆን ሶሪያ፣ ሂዝቡላህንና ኢስላሚክ ጅሀድን የመሳሰሉ አሸባሪ ድርጅቶችን እንዳትረዳና የሊባኖስም ጦር ሂዝቡላህን እንዲበታትን፣ እንዲሁም ምናልባትም ሶሪያ በሊባኖስ ያላት ይዞታና ተጽዕኖ እንዲያከትም ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በእውነቱ አዲስ ቅርጽ ያለው መካከለኛው ምሥራቅን ልንመለከት እንችላለን›› ብለዋል፡፡[150] በተመሳሳይ ሁኔታ አሉፍ ቤን የካቲት 2003 ሃ›ኤሬትዝ በተባለው ጋዜጣ ላይ ባሰፈረው አስተያየት እንዲህ ብሏል፡- “ከፍተኛ የእስራኤል መከላከያ ባለሥልጣናትና የብሄራዊ ፀጥታ አማካሪውን ኤፍሬም ሄሌቪን የመሳሰሉ ለአሪዮል ሻሮን የሚቀርቡ ሰዎች ጦርነቱ ካበቃ በኋላ እስራኤል የሚኖራት መጻኢ ሁኔታ እንደ ጽጌረዳ አበባ የፈካ እንደሚሆን ይጠብቃሉ፡፡ ይህ የተጀመረው ሳዳምን የመጣል ዘመቻ ተፋፍሞ በመቀጠል አራፋትን፣ የሂዝቡላሁን መሪ ሀሰን ነስረላህን፣ ባሽር አል-አሳድን፣ የኢራንን አያቶላዎችና ምናልባትም ሙዓመር ጋዳፊን እንደሚያዳርስ ይታመናል፡፡ ከእነዚህ መሪዎች ጋርም ሽብርተኝነትና የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ተጠራርገው ይወገዳሉ፡፡››[152]

ሃሌቪ የካቲት 2003 ላይ በሚዮኒክ የሚከተለውን ማለታቸውን ኒው ዮርክ ታይምስ ዘግቧል፡- ‘‘ሳዳም ከተወገዱ በኋላ ከባግዳድ የሚነሳው የለውጥ ማዕበል ሰፊ ክልሎችን በማዳረስ ቱህራንን፣ ደማስቆንና ራማላህን ይመታል’’[153] የጽሑፉ አቅራቢ እንደገለጸው ‹‹ሳዳም ከተገረሰሱ የዶሚኖው ቁጥር መገለባበጡን በመቀጠል ለሌሎችም መዳረሱ እንደማይቀር እስራኤል ተስፋ አድርጋለች፡፡ በዚህ ተስፋ መሠረት ለዘብተኛ አቋም የሚከተሉና ለውጥ ፈላጊዎች በፍልስጤማዊው ያሲር አራፋትና በየመንግሥቶቻቸው ላይ አዳዲስ ጫናዎችን ማሳደራቸውን ይቀጥላሉ፡፡›› ፎርዋርድ ጋዜጣ ክልሉን ወደ ዲሞክራሲ የማሸጋገሩን ሂደት አስመልክቶ ጦርነቱ ከመደረጉ በፊት እንዲህ በማለት አጠቃልሎታል፡-“የእስራኤል ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ አመራር አባላት የኢራቁ ጦርነት የመካከለኛውን ምሥራቅ ችግሮች ወደ ክብ ጠረጴዛ በማምጣት እስራኤልን ከገባችበት የግጭት አረንቋ መንጭቆ የሚያወጣትን አጋጣሚ ያመቻቻል የሚል እምነት አድሮባቸዋል፡፡”[154]

‹‹የእስራኤል መሪዎች የተወሳሰበ ባሕሪ ያላቸውና የአካባቢያቸውን አስቸጋሪ ተጨባጭ ሁኔታ ከማንም በላይ የሚረዱ እንደመሆናቸው፣ በዚህ ዕቅድ መሳካት ያምናሉ ወይም ተስፋ ጥለዋል ማለት ያስቸግራል›› የሚል የመከራከሪያ ሀሳብ ይነሳ ይሆናል፡፡ ሁኔታውን ከዚያ እቅጣጫ ካየነው የእስራኤል መሪዎች የሀገራቸውን የቆዳ ስፋት ለማሳደግ አዳዲስ ካርታዎችን በየጊዜው እያሻሻሉ በማውጣት የማይጨበጥ የተስፋ ዳቦ የመጋጥ ልማድ አላቸው። የዚህን አባባል እውነትነት ለማረጋገጥ ተምኔታዊውን የኤሬትዝ እስራኤልን መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ የሚያሳየውንና የግብጽን፣ የሶሪያን፣ የዮርዳኖስንና የፍልስጤምን መስተዳደር በርካታ ግዛቶች እንዲያጠቃልል የታሰበውን ካርታ ተግባራዊነት የጽዮናውያን መሪዎች ሁለት ምዕተ ዓመታት ሙሉ በተስፋ ሲጠባበቁ መኖራቸውን ማየቱ ብቻ ይበቃል። ዴቪድ ቤንጎሪዮን በ1965ቱ የስዊስ ጦርነት ሁሉንም የምዕራቡን ዳርቻ፣ የሊባኖስንና የግብጽን ከፊል ግዛቶች ለመቆጣጠር ተስፋ አድርገው ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አሪዮል ሻሮን በ1982 ሊባኖስን በመውረር አፍቃሪ እስራኤል (Pro-Israel) የሆነና የክርስቲያኖች የበላይነት ያጠላበት መንግሥት በመመስረት እዚያ የሚገኘውን የፒ.ኤል.ኦ. ኃይል ለአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ ከሰባበሩ በኋላ በኃይል የተያዙትን ግዛቶች እስከወዲያኛው ተቆጣጥሮ የመቆየት ሕልም ክፉኛ አናውሏቸው ነበር። ከእቅዳቸው ውስጥ ፒ.ኤል.ኦን ከሊባኖስ ማባረሩ ብቻ ነበር የሰመረላቸው። እንግዲህ ይህን ታሪክ ስናስብ የእስራኤል መሪዎች እነርሱ ሊፈጽሙት ያልቻሉትን ዕቅዳቸውን ዩናይትድ ስቴትስ ልትፈጽምላቸው እንደምትችል ተስፋ ማድረጋቸው ምን ያስደንቃል ?

መካከለኛው ምስራቅን እንደገና ከማደራጀት አንጻር የሎቢው አቋም ሲገመገም

በ2002 በርካታ ኒዎኮንሰርቫቲቮች መካከለኛውን ምሥራቅ ለአሜሪካና ለእስራኤል ተስማሚ ሥፍራ ለማድረግ እና ዲሞክራሲን ለማስፋፋት ያስችላል ያሉትን እቅድ በከባዱ ይዘው ያብተለትሉ ነበር፡፡ ያንን እቅዳቸውን የነደፉት ገና በ1990ዎቹ ዩ.ኤስ. አሜሪካ ከቀዝቀዛው ጦርነት በኋላ የምትከተለው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እነርሱ እንዳሰቡት ያለመሆኑን በተገነዘቡ ጊዜ ነበር፡፡

ኒዎኮንሰርቫቲቮች ብቻ ሳይሆኑ አፍቃሪ እስራኤል የሆኑ ቡድኖችም በአብዛኛው ዩ.ኤስ.አሜሪካ በመካከለኛው ምሥራቅ በቀጥታ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነትን እንድታደርግ ፍላጎት ነበራቸው፡፡ ምክንያቱም እስራኤልን ከአደጋ መጠበቅ የሚቻለው በዚያ መንገድ መሆኑን ያምኑ ስለነበር ነው፡፡ በተለይም ደግሞ በርካታ ቁጥር ያላቸው የአሜሪካ ወታደሮች በዚያ ክልል በቋሚነት ሰፍረው የማየት ፍላጎት ነበራቸው፡፡[155] ይሁን እጂ ይሽኛውን ዓላማቸውን በተመለከተ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት ስኬታቸው ውስን ነበር፡ ፡ ምክንያቱም አሜሪካ በክልሉ የነበራት ሚና የሐይል ሚዛንን በማመጣጠን ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ዋሽንግተን በአካባቢው ያሉ ኃይሎችን እርስበርስ እያጋጨች የኃይል ሚዛኑን የማስተካከል ፖሊሲን መከተል መረጠች፡፡ በዚህም ፖሊሲዋ መሠረት ነበር ኢራንና ኢራቅ ጦርነት ላይ በነበሩባቸው ከ1980-88 ባሉት ዓመታት የሬገን አስተዳደር አብዮታዊቷን ኢራንን ለሚወጉት ሳዳም ሁሴን እርዳታውን ያጎርፍ የነበረው፡፡

ሆኖም ግን ይህ ፖሊሲ ከመጀመሪያው የባሕረ-ሰላጤው ውጊያ በኋላ ተቀየረ፡፡ ይህውም የክሊንተን አስተዳደር የሁለትዮሽ ግንኙነትን በማያውክ መልኩ የሌላውን ሀገር ኃይልና ድንበር አክብሮ አብሮ መኖርን (Dual Containment) ለመከተል በመምረጥ የፖሊሲ ለውጥ አደረገ፡፡ በዚህ አዲስ ፖሊሲ መሠረት ዩናይትድ ስቴትስ ኢራንንና ኢራቅን ለመቆጣጠር

እርስበርሳቸው ከማጋጨት ይልቅ ወደ ክልሉ በቂ የጦር ኃይል ካስገባች በኋላ ሁሉንም በአንድ ጊዜ ለመቆጣጠር የሚያስችላትን ሁኔታ አመቻቸች። የዚህ ፖሊሲ ዋና አፍላቂ ማርቲን ኢንዲክ ሲሆን፣ ይህን ስትራቴጂ በግንቦት 1993 WINEP ከተባለው ድርጅት ውስጥ እያለ ነበር ያፈለቀው። ከዚያም በናሽናል ሴኩሪቲ ካውንስል የመካከለኛው ምሥራቅና ደቡብ ኢሲያ ጉዳዮች ዳይሬክተር በነበረ ጊዜ ተግባራዊ አደረገው።[156] የኢንዲክ ብሩኪንግስ ባልደረባ የሆነው ኬኔት ፓላክ የሌላውን ሀገር ኃይልና ድንበር አክብሮ መኖርን (Dual Containment) አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት ‹‹ ይህን ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ በዋነኛነት ያስፈለገው የእስራኤልን ጥቅሞች ለማስከበር ነው። በተለይም ደግሞ እስራኤል ለክሊንተን አስተዳደር እቅድና ለሰላሙ ሂደት ወደፊት መጓዝ ፈቃደኛ የምትሆነው ከኢራን በኩል ስጋት እንደማይደቀንባት ካመነች ብቻ መሆኑን ግልጽ አድርጋለች›› ብሏል።[157]

የሆነ ሆኖ በዚህ ፖሊሲ ያለመርካት አዝማሚያ በ1990ዎቹ በስፋት ይንጸባረቅ ጀመር። ምክንያቱም ዩናይትድ ስቴትስ በሁለት እርስበርስ የተጋጩ ሀገራት ዓይን እርቅ የማይገባው ጠላት (Mortal Enemy) ተደርጋ ስለምትታይና ሁለቱንም ሀገራት ባሉበት ሁኔታ አዘላ መጓዝ ስለሚኖርባት ነው። ወደፊት በሚመጣው ምዕራፍ 10 ላይ እንደተብራራው አይፓክና ሌሎች በሎቢው ውስጥ ያሉ ቡድኖች ይህን ፖሊሲ ዘላቂነት እንዲኖረው ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ኮንግረሱና ፕሬዚዳንት ክሊንተንም አጠናክረው እንዲጠቀሙበት አሳምነዋቸዋል። ኒዎኮንሰርቫቲቮች ከዚያም በላይ ርቀው የሄዱበት ሁኔታ በግልጽ ተስተውሏል። ይህ በሳዳም ሁሴን ላይ ስላልሠራ እርሳቸው የግድ ወርደው በሌላ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት መተካት አለባቸው ብለው ነበር የሚያምኑት። ይህ አስተሳሰባቸው የተንጸባረቀው በ1998 መጀመሪያ አካባቢ ለፕሬዚዳንት ክሊንተን በዓፋቸው ደብዳቤዎችና ኢራቅን ነፃ ለማውጣት የረቀቀውን ደንብ በደገፉ ጊዜ ነበር።

በተመሳሳይ ጊዜ በመካከለኛው ምሥራቅ ዲሞክራሲን ማስራጨት የሚለው እምነት ክልሉን ያዳረሰ ዜና ቢሆንም፣ በኒዎኮንሰርቫቲቮች አካባቢ ደግሞ ይበልጥ ሥሩን እየሰደደ የሄደ እምነት ሆነ። ቀዝቃዛው ጦርነት እንደተጀመረ አካባቢም ቢሆን ጥቂት ኒዎኮንሰርቫቲቮች በዚህ ሃሳብ

ተማርከው የነበረ ቢሆንም፣ እስከ 1990ዎቹ መገባደጃ ድረስ ግን በስፋት ተቀባይነትን አላገኘም ማለት ይቻላል። [158] ይህ አስተሳሰብ በእርግጥም በግልጽ የተንጸባረቀው በ1996 "ክሊን ብሪክ" የተባለውን ጥናት የኒዎኮንሰርቫቲቭ ቡድን አባላት ለቤንጃሚን ናታንያሁ በማቅረብ ወደሥልጣን የሚወስዳቸውን ምርጫ ማሸነፍ እንዲችሉ በረዷቸው ጊዜ ነበር። በ2002 ኢራቅን የመውረሩ ነገር አንገብጋቢ የሆነ ጉዳይ መሆኑ በታወቀ ጊዜ ክልሉን ወደ ዲሞክራሲ የማሸጋገሩም ሂደት በተወሰኑ ኒዎኮንሰርቫቲቮች ዘንድ የሃይማኖት ቀኖና እስኪመስል ድረስ እየተለመደና እየተዘወተረ ከመሄዱ የተነሣ የዩ.ኤስ.አሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖ/ሲ. ማዕከላዊ የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ ቁጭ አለ። [152] ስለሆነም የእስራኤል መሪዎች፣ ኒዎኮሰርቫቲቮችና የቡሽ አስተዳደር ኢራቅን መውረር መካከለኛው ምሥራቅን እንደገና ለማደራጀት የመጀመሪያው ተስፋ ሰጪ እርምጃ መሆኑን አመኑበት።

ማጠቃለያ

የቡሽ አስተዳደር ለኢራቅና ለሰፊው የመካከለኛው ምሥራቅ ክልል ያቀደው ወደ ዲሞክራሲ ሽግግር የማድረግ ሂደት ከሸፏል ማለት ይቻላል። የአሜሪካ ጦር ኃይል ውጊያውን ማሸነፍ ካለመቻሉም በላይ፣ ዲሞክራሲን ወደ ክልሉ የመውሰድ ዕድሉ አነስተኛ ተስፋ ብቻ ነበር የሚታይበት። ኢራን በበኩሏ በዚህ በሚገባ ያልታቀደ ጀብደኝነት ዋናዋ ተጠቃሚ ለመሆን ችላለች። ከዚያ በኋላ የኢራቅ ዕጣ እንዳይደርሳት በመስጋት የኒኩሌር መሣሪያ ለመታጠቅ ቁርጥ ውሳኔ አድርጋለች። ሶሪያም ብትሆን ልክ እንደ ኢራቅ ሁሉ ከዋሽንግተን ጋር ያላት ግንኙነት እንደተበላሸ በመሆኑ ሁለቱ መንግሥታት፣ የአሜሪካ ጦር ኃይል ኢራቅ ውስጥ በማይወጣው የውግያ ማጥ ውስጥ እንዲቆይ የሚችሉትን ሁሉ እንዳደረጉ ነው የሚገመተው። ሃማስ አሁን ጋዛን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሯል። የፍልስጤም አስተዳደርም ለሁለት እንደተሰነጠቀ የቀረ ሲሆን፣ ከእስራኤል ጋር የሚደረገው ሰላምም የማይጨበጥ እንደሆነ ቀጥሏል። ሂዝቡላህም በሊባኖስ ውስጥ ከተደረገው የ2006ቱ ጦርነት በኋላ እስራኤልን ለመገዳደር መቻል ብቻ ሳይሆን ጠንካራነቱንም አስመስክሯል። ‹‹ አዲሱ የመካከለኛው ምሥራቅ ውልደት ያስከተለውን የምጥ ውጋት እየታዘብን እንገኛለን ›› በማለት ነበር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ ኮንዶሊዛ ራይስ አሳዛኝ (የሚያስቆጭ) አባባላቸውን ያስቀመጡት። ይህ ሁሉ እንግዲህ ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅን ከመውረሯ በፊት አይታው የማታውቀው ያለመረጋጋትና አደገኛ ሁኔታ መፈጠሩን ነው የሚያሳየው።[160]

የኢራቅ ጦርነት ለእስራኤል ለራሷም ቢሆን የበጀት አልሆነም። ምክንያቱም ኢራን በክልሉ ያላት ተሰሚነት ከፍ እንዲል ስላደረገው። ፎርዋርድ ጋዜጣ 2007 መጀመሪያ ላይ ባወጣው ዘገባ፡- ‘‘ዛሬ በእስራኤል በርካታ የሆነና እያደገ የሚሄድ የሕዝቦች ጩኸት አይሁዳዊቷ ሀገር ሳዳም ከተወገዱ በኋላ በበለጠ አደጋ ላይ ትገኛለች በማለት እያሳሰበ ይገኛል’’ብሏል።[161] አማትዚያ ባረም የተባሉ እስራኤላዊ የኢራቅ ጉዳይ ኤክስፐርትና ከአይፓክ ጋዜጣ

ከኒር ኢስት ሪፖርት ጋር ቃለ ምልልስ ያደረጉ፣ እንዲሁም ከጦርነቱ በፊት የሳዳምን መባረር በመደገፍ የተከራከሩ ሰው አሁን እንዲህ ይላሉ፡- ‘‘ዛሬ የማውቀውን ጉዳይ ያኔ አውቄው ቢሆን ኖሮ (አሁን ጥር/2007 ላይ ሆነው) ጦርነቱ እንዲደረግ አልደግፍም ነበር፡፡ ምክንያቱም የሳዳም አደገኝነት ከገመትኩት በታች ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡” ሰውዬው ቀጥለው ሲናገሩ፡- “ያ ወረራ ከጠበቅኩት በላይ ነበር እጅግ ብዙ የሽብርተኝነትን እንቅስቴን የወለደው” ብለዋል፡፡ የእስራኤል የሀገር ውስጥ ስለላ ድርጅት ሺን ቤት ኃላፊ የሆኑት የቫል ዲስኪን የካቲት 2006 ላይ እንዲህ ብለዋል“እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ሳዳምን ማባረር የነበረብን አይመስለኝም››[162]

ዩናይትድ ስቴትስ ከዚህ አውዳሚ ሁኔታ ራሷን የምታወጣበትን መንገድ እያማተረች ባለችበት ጊዜ የቡሽ አስተዳደር ከኢራንና ከሶሪያ ጋር በመነጋገር የእስራኤል ፍልስጤማውያንን ጉዳይ እልባት እንዲያደርግለት ግፊት እየበዛበት ይገኛል፡፡ ኒዎኮንሰርቫቲቮችና እስራኤል ራሷ በሚገባ ጠንቅቀው የሚያውቁት ሃቅ ወደ ቴሌአቪቭ የሚወስደው መንገድ የሚያልፈው በባግዳድ በኩል መሆኑን ነው፡፡ አሜሪካ የኢራቁን ጦርነት ካሸነፈች ፍልስጤማውያን እስራኤል የምታቀርበውን የስምምነት ሀሳብ ለመቀበል ይገደዳሉ የሚል አስተሳሰብ ሰፍኖ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የኢራቅ የጋራ ጥናት ቡድን (bipartisan Iraq study group)፣ የብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር ቶኒ ብሌዬር እና ሌሎች ፖለቲከኞች የሚያምኑት ተቃራኒውን ሲሆን ይኸውም ‹‹ወደ ባግዳድ የሚወስደው መንገድ የሚያልፈው በቴሌአቪቭ በኩል ነው›› የሚለውን ነው፡፡[163] በሌላ አባባል ግልጽ የሆነ የፍልስጤማውያንን መንግሥት ማቋቋም ዩናይትድ ስቴትስ በኢራቅና በሌሎች የክልሉ ችግሮች ዙሪያ ለመወያየትና መፍትሄ ለማግኘት ያስችላታል ማለት ነው፡፡ እንደዚያም ቢሆን እስራኤልና ሎቢው እንዲህ ዓይነቱን የመከራከሪያ ሀሳብ በማጣጣል አሜሪካ በኢራቅ የገጠማት ችግር ከፍልስጤማውያን ሁኔታ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም በማለት ጠንክረው ተከራክሩ፡፡ 2006 ህዳር ወር ላይ የኢራቅ ጥናት ቡድን ዘገባ ከመለቀቁ በፊት ሃ›ኤሬቴዝ ባሰፈረው ጽሑፍ፡- ‘‘አዲሱ ኮንግረስ ፍልስጤምን በሚመለከት ጉዳይ አሁን ካለው ሁኔታ (Status quo) የተለዬ መንገድ

እንዳይከተል ለማድረግ የአይሁድ ሎቢ የተለመደ ጥረቱን እንደሚቀጥል ጠቅላይ ሚኒስትር ይሁድ አልመርት ተስፋ አድርገዋል›› ብሏል፡፡[164] በተመሣሣይ ሁኔታ በርካታ አፍቃሪ-እስራኤል ቡድኖች ዩናይትድ ስቴትስ የእርሷን የመደራደሪያ ሃሳብና ጥያቄዎች እስካልተቀበሉ ድረስ ከኢራንና ከሶሪያ ጋር ለመነጋገር ፈቃደኛ መሆን አይኖርባትም የሚል አቋም ያራምዳሉ፡፡[165]

የቡሽ አስተዳደር ከኢራቅ ጦሩን እንዲያስወጣ የሚጠይቅ ግፊት እየበረታበት ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ በሌላ በኩል ደግሞ የእስራኤል መሪዎች ጦሩ በዚያ ቆይቶ ሥራውን እንዲጨርስ ነው የሚያበረታቱት፡፡ ለምን? ምክንያቱም የዩ.ኤስ. አሜሪካ ጦር ከኢራቅ ቢወጣ የእስራኤል ጸጥታ አደጋ ላይ ይወድቃል ብለው በማመናቸው፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሊቪኒና ጠቅላይ ሚኒስትር ኦልመርት መጋቢት 2007 በተደረገው የአይፓክ ዓመታዊ ጉባዔ ላይ ይህን ጉዳይ አንስተዋል፡፡ ሊቪኒ ሲናገሩ፡- “የላዕላይ ገጽታ ወሳኝ ሚና በሚጫወትበት በዚህ ክልል ሀገራት ድክመታቸውን ማሳየትና ለጽንፈኞች መንበርከክ የለባቸውም” ብለዋል፡፡[166] ኦልመርት ደግሞ ስህተት ላይ የጣላቸውን አባባል ሲናገሩ፡- ‘‘ለእስራኤል ጸጥታ የሚጨነቁ ኃይሎች፣ እንዲሁም ለመላው መካከለኛው ምሥራቅ መረጋጋት የሚያስቡ ሁሉ አሜሪካ በኢራቅ ስኬት እንድታገኝና ኃላፊነት በተመላበት ሁኔታ እንድትወጣ የማድረግን አስፈላጊነት ማመን አለባቸው” አሉ፡፡ አልመርት ንግግራቸውን ቀጥለው እንዲህ ነበር ያሉት፡- “አሜሪካ በኢራቅ የሚቀናት ከሆነ የእስራኤል ደህንነት አስተማማኝ ይሆናል፡፡ ይህን ጉዳይ ደግሞ የእስራኤል ወዳጆች ያውቁታል፡፡ ለእስራኤል የሚጨነቁ ሁሉ በሚገባ ይገነዘቡታል፡፡››[167] የኦልመርትን ንግግር የተለያዩ ሰዎች ነቅፈውታል፡፡ ምክንያቱም የእርሳቸው ንግግር፡- “አሜሪካ ኢራቅን እንድትወር እስራኤል ደግፋታለች’’ የሚለውን አባባል ያረጋገጠ ተጨማሪ ማስረጃ ሆኖ በመቆጠሩ ነው፡፡ በሃ›ኤሬትዝ ጋዜጣ ላይ የሚጽፈው ብራድሊ በርስተን በተለይ አልመርት በአደባባይ የአሜሪካውያንን በዚያ መቆዬት በመደገፋቸው በግሉ ተናዶባቸውል፡፡ ለጠቅላይ ሚኒስትሩም አንድ አጠር ያለ መልዕክት አስተላልፏል፡፡-‹‹ እስራኤል ከዚህ የተጋጋለ ክርክር ዘወር ማለት አለባት፡፡›› [168]

ኦልመርት ሕዳር 2006 ላይ ዋይት ሃውስን በጎበኙ ጊዜ አሜሪካ በኢራቅ ቆይታ ማድረግ መቀጠሏን እንዲህ በማለት ነበር የደገፉት፡- “አሜሪካ በኢራቅ የምታደርገውን ዘመቻ በመቀጠሏ በጣም የተደነቅንና የተበረታታን መሆናችንን መግለጽ እፈልጋለሁ።››[169] በዚህ የኦልመርት ጦርነት ናፋቂ ንግግር ሌላው ይቅርና የእስራኤል ቋሚ ደጋፊዎች እንኳን ቅር መሰኘታቸው አልቀረም። ለአብነት ያክል ኮንግረስማን ጋሪ ኤከርማን እንዲህ ብለዋል፡- “በኦልመርት ንግግር ደንግጫለሁ። ይህ ፈጽሞ ከእውነት የራቀ ነው። እዚህ ያለን ብዙዎቻችን እንደምንገነዘበው ያራመድነው ፖሊሲ ጥልቅና ሰፊ ውድመትን ነው ለዩናይትድ ስቴትስ ያመጣባት።››[170]

ይህን ጉዳይ ዛሬ በስፋት ያስተዋሉ ብዙ አሜሪካውያን ጦርነቱን በተመለከተ የኮንግረስማን ኤከርማንን ስሜት የሚጋሩ መሆናቸው አያስደንቅም። በሌላ በኩል ደግሞ ጥቂት እስራኤላውያንና የእነርሱ አጋር የሆኑ አሜሪካውያን ለዚያ ጦርነት መቀስቀስና ላስከተለው አጠቃላይ ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት እስራኤልን ተጠያቂ ላለማድረግ ሌላ የተለዩ ታሪክ በመጻፍ እያዘጋጁ ይገኛሉ። ለምሳሌ መጋቢት/2007 ላይ የእየሩሳሌም ፖስት ዋና አዘጋጅ የሆነው ዴቪድ ሆርቪትዝ፡- “ዩ.ኤስ. አሜሪካ ኢራቅን እንድትወር ያበረታታቻት እስራኤል ናት የሚለው የሀሰት ወሬ” በሚል ርዕስ ጽሑፍ አስነብቧል።[171] በተመሣሣይ ሁኔታ የቀድሞው የጃፌ ስትራቴጂክ ጥናት ማዕከል ኃላፊ የነበሩትና አሁን ደግሞ ክራውን ሴንተር ፎር ሚድል ኢስት የብራንዲስ ጥናት ማዕከል በሚሰኘው ተቋም ኃላፊ በመሆን እያገለገሉ ያሉት ሻይ ፊልድማን ለዋሸንግተን ፖስቱ ግሌን ፍራንክል 2006 ክረምት ላይ እንዲህ ብለውት ነበር፡-- “ተመልከት! እስራኤል ማንንም ቢሆን በኢራቅ ላይ ዘመቻ ይከፍት ዘንድ አልቀሰቀሰችም። እስራኤልን ከዚህ ጉዳይ ጋር ማያያዝ የማይረባ ነገር ነው። እስራኤል ኢራቅን አስጊ እንደሆነች ጠላት አድርጋ አትመለከታትም። ከዚያም ሌላ የቡሽን ዲሞክራሲን በክልሉ የማስፋፋት አጀንዳን የመገፋፋት ፍላጎት የላትም።››[172] ይህ አስተያየት ያለምንም ጥርጥር የሚያንጸባርቀው ፊልድማን የእስራኤልን ፍላጎትና ተጋፍጣቸው የነበሩትን ስጋቶች በተንሻፈፈ እይታ እንዴት እንደተመለከቷቸው ነው። በተጨማሪም ቀደም ብለን በስፋት እንደዘረዘርነው የእስራኤል መሪዎች፣ አፍቃሪ-እስራኤል ኃይሎችና ኒዎኮንሰርቫቲቮች ኢራቅን ለማስወረር ያደረጉትን ርብርብ በሚጻረር መልኩ በኢራቅ የደረሰው

ሁለንተናዊ ውድመት የሚያስከትለውን ወቀሳና ኃላፊነት ለመሸሽ የሚያደርጉትን ጥረት ነው።

ከዚያም የበለጠ WINEP ውስጥ ተመራማሪ የሆኑት ማርቲን ክራመር፡- ‹‹እስራኤልንና ሎቢውን ከኢራቅ ጦርነት ጋር ለማቆራኘት የሚደረግ ጥረት ሁሉ ሃሰት ነው›› በማለት ሽምጥጥ አድርገው ክደዋል። ይህንን አባባላቸውን ለማሳመን ያቀረቡት የመከራከሪያ ሃሳብ፡- “የኢራቅ ጦርነት ከመደረጉ አንድ ዓመት በፊት ኢራን ከኢራቅ የባሰ ስጋት የፈጠረች ሀገር መሆኗን ለዩናይትድ ስቴትስ አሳውቀናል›› የሚል ነበር።[173] ሆኖም ግን ከላይ እንደተገለጸው ኢራን ለእስራኤል የበለጠ አደጋ የደቀነች መሆኗ ወደ ኢራቅ የሚደረገውን ዘመቻ ሊያስቆመው አልቻለም። እንዲያውም ከዚያ በተቀራኒ የእስራኤል ከፍተኛ ባለሥልጣናት ያላቸውን ችሎታ ተጠቅመው ዩናይትድ ስቴትስ ሳዳምን ከመውረር እንዳትቆጠብና ከዚያም በኋላ ቢሆን ፊቷን ለእስራኤል ስጋት ፈጣሪ ወደሆኑ ሌሎች መንግሥታት እንድትመልስ ነበር በጽኑ ይታገሉ የነበረው። ባለሥልጣናቱ -እውነቱን ለማስቀመጥ - አሜሪካ ከኢራቅ በፊት በኢራን ላይ ወረራዋን ብታስቀድም ይመርጡ ነበር። ሆኖም ግን እንደማርቲን ክራመር አባባል ‹‹ለሳዳም መወገድ የሚያፈስሱት እንባም አልነበራቸውም።›› ከዚያ ይልቅ መሪዎቻቸው በአሜሪካ ሬዲዮኖችና ቴሌቪዥኖች፣ በጋዜጦች የሀሳብ መስጫ አምዶች (Op-eds)፣ ኮንግረስ ፊት ቀርበው የምስክርነት ቃል በመስጠት፣ እንዲሁም በምክትል ፕሬዚዳንቱ ቢሮና ፔንታጎን ውስጥ ተሰግስገው ከሚገኙ ኒዎኮንሰርቫቲቮች ጋር በቅርበት በመሥራት ወደ ኢራቅ የሚደረገውን ዘመቻ በማቀድና በማቀናጀት ብዙ ሚና ተጫውተዋል።

በጃፌ ማዕከል ስትራቴጂስት የሆኑት ዮሲ.አልፈር አሁን እንደሚገልጹት፡- “የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ሻሮን ኢራቅን ስለመውረር ከበድ ያለ ቁጥብነትና ተቃውሞ የነበራቸው በመሆኑ ይህንኑ ጉዳይ በመግለጽ ቡሽን አስጠንቅቀው ነበር’ ብለዋል። አልፈር ጨምረው ሲያስረዱ፡- ‘‘ሻሮን የተሰማቸውን ስሜት በግልጽ አውጥተው ተናግረውት ቢሆን ኖሮ ምናልባትም ጦርነቱን ማስቆም በቻሉ ነበር።›› ካሉ በኋላ፡- ‹‹ሻሮን የነበራቸውን ተቃውሞና ትችት በግልጽ በማውጣት ኢራቅን መውረር የእስራኤልን ዋነኛ ጥቅም የሚጎዳ መሆኑን ማስረዳት ችለው ቢሆን ኖሮ በዩናይትድ ስቴትስና በመላው ዓለም ጦርነቱን አስመልክቶ በተደረገው

ክርክር ላይ ለውጥ አያመጡም ነበርን?›› በማለት አስተያየታቸውን በጥያቄ ደምድመዋል።[174] ይህ በመሠረቱ የተለመደና አንድ ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ አለመገኘትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ ተራ ማደናገሪያ ነው። ምክንያቱም ቡሽ ጦርነቱን እንዳያደርጉ ሻሮን ምክር የለገሷቸው ስለመሆኑ የሚያሳይ በግልጽ የተቀመጠ ማስረጃ አይገኝምና። የእስራኤሉ መሪ ሻሮንና ቁልፍ አማካሪዎቻቸው ጦርነቱን በጽናት የሚደግፉ ስለመሆናቸውና ቡሽም ሳይዘገዩ እንዲጀምሩት ያበረታቱም እንደነበር የሚያሳዩ በርካታ ማስረጃዎች ግን ይገኛሉ። ሻሮን ጦርነቱን ማድረግ ስህተት እንደነበር ካመኑ ለምን ይሆን የእርሳቸው ቃል አቀባይ የኢራቅን ጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች አስመልክተው በተደጋጋሚ ይናገሩ የነበረው? እንዲሁም ሻሮን ራሳቸውስ ቢሆኑ የቡሽ አስተዳደር ጦርነቱን ማዘግዬቱ ለወደፊቱ እርምጃ ለመውሰድ መልካም ሁኔታን አይፈጥርም ብለው በተደጋጋሚ ማስጠንቀቅ ለምን አስፈለጋቸው?[175]

ምናልባት ሻሮን ጦርነቱን በተመለከተ በአደባባይ ከሚናገሩት የተለየ አስተያየት በጓዳ ሰጥተው ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱን ያልተጨበጠ ወሬ በማንጠልጠል ብቻ ሻሮን ጦርነቱን ይቃወሙ ነበር ብሎ ለመናገር የሚያስችል ምንም ዓይነት በቂ ምክንያት አይገኝም። ለምን ቢባል ተጨባጩ ሁኔታ የሚያሳየው ሻሮን በተፈጥሯቸው በስተቀር ስሜታቸውን አምቀው የመያዝ ባህሪ የሌላቸው መሆኑ ሲሆን፤ ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር በዚህ ጉዳይ ላይ አለመግባባት ቢፈጠርና ይህም የእስራኤልን ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ቢገኝ በአደባባይ ከመግለጽ ይቆጠባሉ ተብሎ ስለማይታሰብ ጭምር ነው። በአጭር አነጋገር የዩሲ አልፈርን የመከራከሪያ ሃሳብ ተጨባጩ እውነታም ሆነ ሥነ-አመክኒዬ አይደግፉትም።

“ድል አንድ ሺህ አባቶች ያሏት ሲሆን ሽንፈት ግን ወላጅ አልባ ነች ” የሚለው የፕሬዚዳንት ኬኔዲ አባባል በኢራቅ የደረሰውን ሁልቆ መሣፍርት የሌለው ውድመት ለመሸሸና ኃላፊነት ላለመውሰድ የሚደረገውን ሽኩቻ በግልጽ የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ ለዚህ ሁኔታ ተስማሚ ነው። ይሁን እንጂ ኢራቅ ጦርነቱ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ አልነበረም በእንዲህ ዓይነት አስፈሪ ሁኔታ ላይ የወደቀችው። በ2003 የመጀመሪያዎቹ አጭር የጸደይ ወራት ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅ ውስጥ አስደናቂ ድል የተቀዳጀች በመምሰሏ ጦርነቱን አስመልክቶ ኃላፊነቱን

ላለመውሰድ ከእስራኤላውያኑ ጋር እሰጥ አገባ ማድረግ አላስፈለገም ነበር፡፡ እንዲያውም የስኬት መስኮቶች ሁሉ የተከፈቱ በመሰሉበት በዚያ ሰዓት ቁልፍ እስራኤላውያንና አሜሪካውያን አጋሮቻቸው የቡሽ አስተዳደር ጡንቻውን በሶሪያና ኢራን ላይ ጭምር ለማሳረፍ እንደሚችልና እነርሱም የሳዳም እጣ እንደሚደርሳቸው ተስፋ አድርገው ነበር የተንቀሳቀሱት፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በዚያ ወቅት የተከሰተውን የነባራዊ ሁኔታ መመቻቸት ያስተዋሉት እስራኤልና ሎቢው በዩ.ኤስ.አሜሪካ ፖሊሲ ላይ ተጽዕኖ በማሳረፍ በሶሪያና በኋላም በኢራን ላይ ያሳደሩትን ጫና ለማየት እንሞክራለን፡፡

ምዕራፍ ዘጠኝ

በሶሪያ ላይ የተነጣጠረ ሚላማ

አሜሪካ ከሶሪያ ጋር ያላት ግንኙነት ለሃምሳ ዓመታት ያክል ሻክሮ ቆይቷል። በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት በበዓዝ ፓርቲ የሚመራው የሶሪያ መንግሥት የሶቪዮቶች ደንበኛ ሆኖ ከመቆየቱም በላይ፣ አምባገነናዊ በመሆን ከባድ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ከማድረሱም በተጨማሪ እስካሁንም ድረስ መሠረታዊ የሰው ልጅ መብቶችን አያከብርም። ፕሬዚዳንት ቡሽ አስከፊ በሆነው ‹‹የሰይጣን ዛቢያዎች (axis of evil)›› ፍረጃቸው ውስጥ ሶሪያን ያላከተቱ ቢሆንም በአሜሪካ ጥቅሞች ላይ ተግዳሮት ከሚቀሰቅሱ ወስላታ መንግሥታት (rogue States) መካከል ሶሪያ አንዷ እንደሆነች ነው የሚታመነው። ዩ.ኤስ.አሜሪካ ከሶሪያ አንፃር የምትከተለው ፖሊሲ የበለጠ የጠላትነት ስሜት እያየለበት የመጣው ከመስከረም 11ዱ ጥቃት በኋላ ነበር። ከዚያም 2003 ላይ ባግዳድ በአሜሪካ ጦር እጅ ስትወድቅ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ደማስቆም ተመሣሣይ እጣ የማይቀርላት መሆኑን ብዙዎች አመኑ። ይሁን እንጂ በኢራቅ የነበረው ሁኔታ በየጊዜው እያሽቆለቆለ መሄዱ ለጊዜውም ቢሆን ይህን የወረራ ወሬ ጋብ እንዲል አድርጎታል። እንደዚያም ቢሆን አሜሪካ ከደማስቆ ጋር ያላት ግንኙነት ያልተሻሻለ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም የጠላትነት ስሜት እንደተላበሰ ቀጥሏል።

ማንም ቢሆን በበለጠ ገለልተኛነት የሶሪያን ጉዳይ ቢያስተውል፣ ዩ.ኤስ. አሜሪካ ከዚያች የአረብ ሀገር ጋር ያላት ግንኙነት እንዴት የጠላትነት ሊሆን እንደቻለ በግልጽ መገንዘብ አይችልም። እርግጥ ነው ዋሽንግተንና ደማስቆ የተለዩ ወዳጃዊ ግንኙነት ኖሮአቸው አያውቅ ይሆናል። ሆኖም ግን በጋራ ጥቅማቸው ዙሪያ በበርካታ አጋጣሚዎች ሲተባበሩ ቆይተዋል። ከዚህም በላይ የሶሪያ በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ የጦር ኃይል ብቃት የዩ.ኤስ.አሜሪካ ጥቃሞችን ስጋት ላይ የሚጥል አይደለም። አሁን ያለውን

ተጨባጭ ሁኔታ ስናስተውል ሶሪያ በአሜሪካ ዓይን የመንግሥት ለውጥ እንዲደረግባቸው ከታሰቡት ሀገራት ተርታ መደመሯ ያስደንቃል። ምክንያቱም እርሷን የመሰሉ አምባገነን መንግሥታት በመካከለኛው ምሥራቅም ሆነ በሌላው የዓለም ክፍል የአሜሪካን ድጋፍ እንደልባቸው እያገኙ ተቀምጠዋልና።

የቡሽ አስተዳደር በሶሪያ አንፃር የሚከተለው የማያቋርጥ የሆነ የጠላትነት ፖሊሲ ከስትራቴጂ አኳያ ሲመዘን ብስለት የጎደለው ሆኖ ይታያል። በተለይም ደግሞ አሜሪካ የምታንጸባርቀው ይህ አቋም በአረቡና በሙስሊሙ ዓለም ያላትን ገጽታ እየጎዳባት ያለ ሲሆን የኒኩሊዩር መሣሪያ እንዳይስፋፋ የምታደርገውን ጥረትና ኢራቅን የማረጋጋቱንም ሂደት በማወሳሰብ ከሽብርተኝነት ጋር የጀመረችውን ግብግብም እንዲሁ እያባባሰው ይገኛል። ስለሆነም እዚህ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ፕሬዚዳንት ቡሽ ከደማስቆ ጋር በጋራ መከባበር ላይ የተመሠረተ የትብብር ግንኙነት እንዲያጎለብቱ የሚጠይቁ ጥሪዎች እየጎሉ መምጣታቸው አያስደንቅም። ለምሳሌ 2000 ላይ የኢራቅ ጥናት ቡድን (Iraq Study Group) ባቀረበው ጥሪ መሠረት አሜሪካ ከሶሪያ ጋር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ንግግር እንድትጀምር ጠይቋል።[1] በዚያው ወር ላይ ሶስት የዩ.ኤስ.አሜሪካ ሴናተሮች ከሶሪያው ፕሬዚዳንት በሻር አል-አሳድ ጋር ለመነጋገር ወደ ደማስቆ የተጓዙ ሲሆን፣ ሚያዝያ 2007 ላይ ደግሞ የምክር ቤቱ ዓፈ-ጉባዔ ናንሲ ፔሎሲ፣ ቶም ላንቶስና ሄነሪ ዋክስማንን ጨምሮ አፍቃሪ-እስራኤል የሆኑ ስድስት የጋራ ምክር ቤት አባላትን በመምራት የሰላሙን ሂደት ወደፊት ለመግፋት የሚቻልበትን ሁኔታ ለመመካከር ወደ ሶሪያ ተጉዘዋል።[2]

የቡሽ አስተዳደር ሶሪያን በተመለከተ የሚከተለው ፖሊሲ በየጊዜው እየጋለ የሚሄድ የጠበኝነት መንፈስ እንዲላበስ በማድረግ በኩል እስራኤልና ሎቢው ጉልህ ሚና ተጫውተዋል። ሎቢው ምንም እንኳን በሁለቱ ሀገራት መካከል ጠቃሚ የሆኑ የትብብር ሂደቶችን የሚጎዳ ቢሆንም፣ ዩናይትድ ስቴትስ ሶሪያን እንድታገልላትና ጫናም እንድታሳድርባት በብርቱ ሲሠራ ቆይቷል። የሎቢው ጫና ባይኖር ኖሮ ዋሽንግተን ከሶሪያ ጋር የሚኖራት ግንኙነት የተለዩና ምናልባትም የአሜሪካን ብሔራዊ ጥቅም ያገናዘበ ሊሆን በበቃ ነበር።

ሶሪያ የምታሳድረው ስጋት

ሶሪያ ለዩናይትድ ስቴትስም ሆነ ለእስራኤል ያን ያክል አስጊ ኃይል አይደለችም፡፡ የመከላከያ በጀቷ ከእስራኤል የመከላከያ በጀት አንድ አምስተኛ በታች እንደሆነና የእግረኛ ጦሯም ሆነ የአየር ኃይሏ ጠንካራ ባለመሆኑ ከባድ ጦርነት ቢቀሰቀስ የእስራኤል ኃይል በቀላሉ እንደሚደመስሰው ይታመናል፡፡[3] በ1982 የእስራኤል ጦር ሊባኖስን በወረረ ጊዜ ሶሪያን በቀላሉ ማባረር የቻለ መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ ያ ጊዜ ደግሞ ሶሪያ የሶቪዬትን ትልቅ እርዳታ በቀጥታ ታገኝ የነበረበት ጊዜ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሶቪዬት ከወደቀች በኋላ ደማስቆ ራሷን ችላና ከማንም ወታደራዊ እርዳታ ሳታገኝ ነው የቆየችው፡፡ በሌላ በኩል ግን እስራኤል በየዓመቱ ከአሜሪካ ጠቀም ያለ ወታደራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እርዳታ ታገኛለች፡፡ ስለሆነም በሶሪያና በእስራኤል መካከል የሚደረግ ጦርነት ያልተመጣጠነ ስለሚሆን ይመስላል የሶሪያ መሪዎች ከእስራኤል ጋር የሚደረጉ ግጭቶችን ለማስወገድ ብዙ ጥንቃቄ ሲያደርጉ ይስተዋላሉ፡፡

የአሜሪካ ጦርም ቢሆን ሶሪያን ለማሸነፍ የሚገጥመው ችግር በጣም ውስን እንደሚሆን ነው የሚታመነው፡፡ የሶሪያ ጦር ከኢራንም ሆነ ከሳዳሚ ኢራቅ ጋር ሲነፃፀር በጣም ደካማ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚያ ላይ ከ1982 የሊባኖስ ውጊያ በኋላ ጠንከር ያለ የውጊያ ብቃትን የሚጠይቅ አጋጣሚ አላሳለፈም፡፡ አሁን እንዳለችው ኢራንም ሆነ የሳዳሚ ኢራቅ ሶሪያ በክልሉ ጡንቻማ ኃይል ሆና ለመውጣት ትችል ዘንድ ከወታደራዊ ብቃት ጎን ለጎን የሕዝቧም ቁጥር አነስተኛነት የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሮባታል፡፡ ሶሪያ በአሜሪካና በእስራኤል ላይ ፊት ለፊት የማይካሄዱ የተለያዩ ደባዎችን በመፈጸም ጸጥታቸውን የማናጋት አቅም ቢኖራትም ጠንካራ ወታደራዊ ስጋት ግን አይደለችም፡፡

በተጨማሪም ሶሪያ የኒኩሊዩር መሣሪያን የማነጽ መርሐ-ግብር የሌላት ከመሆኑም በላይ፣ ለወደፊቱም በዚያ አቅጣጫ የምታመራ አትመስልም፡፡ የኬሚካል መሣሪያ ሊኖራት ይችላል፡፡ ይህም በ1973 ከግብጽ ያገኘችው ሲሆን የባዮሎጂያዊ ጦር መሣሪያ መርሐ-ግብርም እንደሚኖራት ይታመናል፡፡[4] ሶሪያ በእስራኤልና በክልሉ በሚገኙ ሌሎች ሀገራት ላይ የኬሚካል መሣሪያ ልታስወነጭፍባቸው የሚያስችሏት በርካታ ባሊስቲክ ሚሳዮሎችን

ታጥቃለች፡፡ ሆኖም ግን እስራኤልን ይህ አያሰጋትም፡፡ ምክንያቱም ራሷ ኬሚካላዊ፣ ባዮሎጂያዊና የኒኩሊዬር መሣሪያዎችን የታጠቀች በመሆኑ ሶሪያ በእርሷ ላይ ከምታደርሰው ጥፋት ይልቅ እርሷ በሶሪያ ላይ የምታደርሰው ውድመት በእጅጉ የከፋ እንደሚሆን ስለምታምን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ እስራኤል የሶሪያን ኬሚካላዊ መሣሪያዎች በሚገባ የምትቋቋምበትን ሥርዓት ፈጥራለች፡፡[5]

የሶሪያ ችግር የመፍጠር ችሎታ ይበልጥ ጥገኛ የሆነው ሂዝቡላህ፣ ሃማስና ኢስላሚክ ጀሃድን ለመሣሠሉ ቡድኖች በምታደርገው ድጋፍ ላይ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ቡድኖች እስራኤልን የሚያሰጓት ቢሆንም ከአል-ቃዒዳ በስተቀር ሂዝቡላህን ጨምሮ በአሜሪካ ላይ ቀጥተኛ ስጋት መፍጠር አይችሉም፡፡ በሂብሩ ዩኒቨርስቲ በሶሪያ ጉዳይ ተጠባቢ የሆኑት ሞሼ ማኦዝ እንዲህ ይላሉ፡- ‘‘ሁሉም እንደሚያውቀው ሶሪያ ቅዱስ አይደለችም፡፡ ሆኖም ግን ከሁሉም በላይ እስራኤልን የሚያሰጋት ሂዝቡላህ ነው’’[6] ከዚህም በላይ ሶሪያና አል-ቃዒዳ መራር የሆኑ ጠላቶች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ቢን ላንደን ሱኒ ሆኖ የኢስላም መሠረተኛ ሲሆን አሳድ ግን የሺዓ ዝንጣይ የሆነው አለዊ (አላዋይት) ሃራጥቃ ተከታይና የዓለማዊ (Secular) መንግሥት መሪ ናቸው፡፡ እርግጥ ነው አል-ቃዒዳ ከሶሪያው ሙስሊም ወንድማማቾች ቡድን ጋር ግንኙነት እንዳለው ይታመናል፡፡ የሙስሊም ወንድማማቾች ቡድን ሴኩላሪስት ከሆነው የበዓዝ መንግሥት ጋር ላለፉት ሃያ የሚሆኑ ዓመታት ሲዋጋ ቆይቷል፡፡[7] ለደማስቆና ዋሽንግተን አል-ቃዒዳ የጋራ ጠላታቸው እንደመሆኑም ከመስከረም 11 በኋላ ቢን ላደንንና ድርጅቱን አል-ቃይዳን የሚመለከቱ ጠቃሚ መረጃዎችን ሶሪያ ለዋሽንግተን መስጠት መጀመሯ አያስደንቅም፡፡ እንግዲህ ይህን ሁሉ ነገር እግምት ውስጥ ስናስገባው በዓለም አቀፍ ደረጃ በሽብርተኝነት ላይ ከሚደረገው ጦርነት በተቃራኒ የተለያዩ አሸባሪ ቡድኖችንና መንግሥታትን በአንድ ላይ ያስተሳሰረ ሆኖ አሜሪካንና እስራኤልን በዋነኛነት ዒላማ ያደረገውን ዓለም አቀፋዊ ሽብርተኝነትን ትደግፋለች መባሉ ስህተት ላይ ይጥላል፡፡ ሆኖም ግን ‘‘ዋነኛ አጀንዳቸው እስራኤልን ብቻ ማጥቃት የሆነ ሽብርተኛ ድርጅቶችን ሶሪያ ትረዳለች›› መባሉ እውነት ነው፡፡

‹‹ሶሪያ ለአሜሪካም ቢሆን የስጋት ምንጭ ናት፡፡ ምክንያቱም በኢራቅ የሚገኙ አማጺያንን ትረዳለችና›› የሚል መከራከሪያ ሊነሳ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ይህ አባባል በአሳማኝ ማስረጃዎች የተደገፈ ካለመሆኑም በላይ፣ የቡሽ አስተዳደር በዚህ ጉዳይ ይበልጥ ተጠያቂ የሚያደርገው ሶሪያን ሳይሆን ኢራንን ነው፡፡ እንዲህ ሲባል ግን ሶሪያ በድንበሯ በኩል አሜሪካን ለሚዋጉ የኢራቅ አማጺያን የተወሰነ መሣሪያ ሲሰርግ አይታ እንዳላየች በመሆን ችላ አላለችም ለማለት አያስደፍርም፡፡ በዚያም ላይ ዋሽንግተን ከመስከረም 11 በኋላ በሶሪያ አንጻር መከተል የጀመረችው ፖሊሲ አሜሪካን በኢራቅ ውስጥ በተዘፈቀችበት የጦርነት ማጥ ውስጥ እንድትቆይ የሚያደርግ ስልትን የሶሪያ መንግሥት እንዲመርጥ የገፋፋው መሆኑ የታወቀ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አሜሪካ ኢራቅ ውስጥ ለገጠማት አበሳ ሶሪያ ዋነኛዋ ምንጭ አለመሆኗ ውሎ አድሮ ታውቋል፡፡ ፕሬዚዳንት ቡሽና የጦር አበጋዞቻቸው የአሳድን አስተዳደር ባያስፈራሩት ኖሮ የአሜሪካ ወራሪ ኃይል በኢራቅ ተጨማሪ ፍዳ እንዲቀበል ደማስቆ ያላት ፍላጎት አነስተኛ በሆነ ነበር፡፡ እናም ከዚህ ሁሉ ትንታኔ አንጻር ሶሪያ ለዩናይትድ ስቴትስ ታላቅ ስጋትን የማትደቅን ብቻ ሳይሆን ከዓለማችን ብቸኛ ልዕለ ኃያል ጋር ለመጋጨት በቂ ምክንያት የላትም ብሎ መደምደም ያስኬዳል፡፡

እንዲያውም ደማስቆ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በብዙ ሁኔታዎች ከዋሽንግተን ጋር መልካም ግንኙነት ያሳየችባቸው አጋጣሚዎች ተከስተዋል፡፡ ለምሳሌ በ1991 ኢራቅን ከኩዌት ለማስወጣት በተደረገው ዘመቻ ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር ሆና ዘምታለች፡፡ በ1990ዎቹ ደግሞ አሜሪካ በእስራኤልና በሶሪያ መካከል መቀራረብ እንዲኖር ለማድረግ ጥረት ታደርግ በነበረበት ጊዜም እንዲሁ የሶሪያና የአሜሪካ ግንኙነት ማለፊያ ከሚባል ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር፡፡ [8] በ1994 እንዲያውም ፕሬዚዳንት ክሊንተን ደማስቆ ድረስ ተጉዘው ከፕሬዚዳንት ሃፊዝ አል-አሳድ ጋር ተገናኝተዋል፡፡ ያ ጉብኝት አንድ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ከሃያ ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረገው ጉብኝት በመሆኑ ይታወቃል፡፡ ከጉብኝቱ በኋላ ክሊንተን እንዲህ ብለው ነበር፡- ‹‹ወደዚያ ሄጂያለሁ፡፡ ምክንያቱም በመካከላችን ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል መነጋገራችን ወሳኝ በመሆኑ፡፡››[9] ይህ ከሆነ በኋላ በ2002 ማለቂያ ላይ ሶሪያ በጸጥታው ምክር

ቤት ቋሚ ያልሆነች አባል በነበረች ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የመሣሪያ ፈታሽ ቡድን ወደ ሳዳሚ ኢራቅ ተመልሶ ሥራውን እንዲያከናውን የሚያስችለውን የውሳኔ ቁጥር 1441 ደግፋለች። ምንም እንኳን 2005 ላይ ሶሪያ ከሊባኖስ ፈጽማ እንድትወጣ የቡሽ አስተዳደር ቁልፍ ሚና ቢጫወትም፣ ለብዙ ዓመታት ያክል (ከ1976 -89) የቆየውን የሊባኖስ የእርስ በርስ ጦርነት ለማብቃትና ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ አሜሪካ ከሶሪያ ጋር አብራ ሠርታለች። [10]

የሶሪያ ፕሬዚዳንት አሳድ ራሳቸው የአሜሪካ ጠላት ተደርገው የመቆጠር ፍላጎት አልነበራቸውም። የቀድሞው የቡሽ አስተዳደር ባለሥልጣንና በሶሪያ ጉዳይ ቀዳሚ ባለሙያ የነበሩት ፍሊዬንት ሌቨሬት ሁኔታውን ሲገልጹ፦ ''በሻር ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚፈልጉ መሆኑን በተደጋጋሚ ገልጸዋል። ይህ ፍላጎት ደግሞ ከአባታቸው ሃፊዝ ጊዜ ጀምሮ የሶሪያን ስትራቴጂያዊ ፍላጎት እውነታ ያገናዘበ ነበር'' ብለዋል። ሌቬሬት ጨምረው ሲናገሩ፦ ''አሳድ ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት በሀገር ውስጥ ለሚያደርጉት ተሃድሶ እንደ አንድ ወሳኝ ግብአት ይመለከቱት ነበር''[11] በማለት ገልጸዋል። ሰይሙር ኸርሽ 2003 ላይ አሳድን በደማስቆ ቢሯቸው ከጎበኙ በኋላ እንደተናገሩት፦ አሳድ የራሳቸውንም ሆነ የሃገራቸውን ገጽታ መቀየር ይፈልጋሉ›› ብለዋል። [12]

ሶሪያ በተጨማሪም ከ1990ዎቹ ጀምሮ ከእስራኤል ጋር የሰላም ስምምነት ለማድረግ ስትጥር ቆይታለች። 2000 ላይ እንዲያውም ሁለቱ ሀገራት ስምምነት ለመፈራረም ተቃርበው ነበር። ሆኖም ግን በጊዜው የነበሩት የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሁድ ባራክ በመጨረሻው ሰዓት ላይ እግራቸውን መሳተት አመጡ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሶሪያውያን ድርድሩን ለማስጀመር ለበርካታ ጊዜያት ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል። ሆኖም ግን ባራክን የተኳቸው አሪዮል ሻሮንና ኢሁድ ኦልመርት የሰላሙን ሃሳብ በማዳፈን ከሶሪያ ጋር የፍጥጫውን ፖሊሲ መቀጠሉን መረጡ። ሁለቱ የእስራኤል መሪዎች የራሳቸው ጠብ ጫሪነት ሳያንሳቸው አሜሪካም ሶሪያን እንደ አደገኛ ጠላት እንድትቆጥራት ለማድረግ ግፊት ሲያደርጉ መቆየታቸው ገሀዱ እውነታ ነው።

እስራኤልና የጎላን ከፍታዎች

በዋሽንግተን፣ ቴሌአቪቭና ደማስቆ መካከል ያለውን የፖለቲካ ዥዋዥዌ፣ እንዲሁም ሎቢው በዚህ ጉዳይ ላይ የሚጫወተውን ሚና ለማወቅ እስራኤል 2000 ላይ ከአሳድ ጋር የሠላም ስምምነት ለመፈራረም ቀርባ ያፈረሰችበትን ሁኔታ በቅድሚያ መመርመር ያሻል።[13]

በሶሪያና በእስራኤል መካከል ያለው ግጭት ዋና ምክንያት የጎላን ከፍተኛ ቦታዎች ናቸው። እስራኤል ያንን ቦታ በ1967 ከሶሪያ ጋር በተደረገ ውጊያ ሰማኒያ ሺህ የሚሆኑ የሶሪያ ዜጎችን በማባረር ነበር የተቆጣጠረችው። የእስራኤል ሕግ ከ1981 ጀምሮ በእስራኤል እጅ ባለው የጎላን ከፍታዎች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን ተዘርግቷል።[14] በተባረሩት ሶሪያውያን ምትክ አሁን ሰማኒያ ሺህ የሚሆኑ አይሁዳውያን በሰላሳ ሁለት መንደሮችና በአንድ ከተማ ላይ ሠፍረው ይገኛሉ።[13] ሶሪያ ይህ ግዛቷ እንዲመለስላት ለማድረግ ከልብ ስትጥር ቆይታለች። የኋላ ኋላም የፖለቲካ ጥረት አላዋጣ ቢላት ሂዝቡላህንና ሃማስን የመሣሠሉ ቡድኖችን በመርዳት በእስራኤል ላይ ጫና የማሳደሩን ስልት ተከትላለች። በ1994 ጠቅላይ ሚኒስትር ራቢን በመርህ ደረጃ የጎላን ከፍታዎችን በሙሉ ለሶሪያ ለመመለስና በምትኩም በሁለቱ ሀገራት መካከል ስምምነትና ሰላም እንዲወርድ ለማድረግ ተስማሙ። በዚያ የራቢን እቅድ መሠረት እስራኤል ከጎላን ከፍታዎች ሙሉ በሙሉ በመልቀቅ ወደ ሰኔ 4/1967 ይዞታዋ ትመለሳለች። ሶሪያ በበኩሏ ሂዝቡላህን፣ ሃማስንና ኢስላሚክ ጅሃድን መርዳቷን ታቆማለች።[16]

ራቢን በቀጣዩ ዓመት ዕቅዳቸውን ሳያስፈጽሙ ቢሞቱም እርሳቸውን የተኳቸው ሽሞን ፔሬዝና በኋላም ቤንጃሚን ናታንያሁ በመርህ ደረጃ ወደ ሰኔ 4/1967ቱ ድንበር ለመመለስ መስማማታቸውን ይፋ አድርገዋል። የፔሬዝ የሥልጣን ቆይታ አጭር በመሆኑ ቃላቸውን ወደ ተግባር ለመቀየር አላስቻላቸውም። ናታንያሁን ግን በተለያዩ ምክንያቶች ይህን ዕቅድ ቅድሚያ ሊሰጡት አልፈቀዱም። ናታንያሁን የተኳቸው ኢሁድ ባራክም እንዲሁ

ምንም እንኳን ወደ 1967ቱ ድንበር ሙሉ ለሙሉ ለመመለስ ባይወስኑም ጎላንን የመልቀቅ ፈቃደኝነት አሳይተዋል።[17]

በ1990ዎቹ በሶሪያና በእስራኤል መካከል የነበረው ግንኙነት ከሰላም ስምምነት ላይ ለመድረስ በተወሰነ መልኩ ጥረት የሚያደርጉበት ጊዜ ስለነበር ያን ያክል ለክፉ የሚሰጥ ሳይሆን ቆይቷል። ጂሚ ካርተር በ1979 በካምፕ ዴቪድ ግብጽንና እስራኤልን ለማስታረቅ እንደጣሩት ሁሉ፣ የክሊንተን አስተዳደርም ሁለቱን ሀገራት ለማስማማት ከልብ ሲሠራ ቆይቷል። ይህም ማለት ሶሪያና ዩናይትድ ስቴትስ (ምንም እንኳን ሶሪያ የአንድ ፓርቲ አምባገነንነት የሰፈነባት ሀገር መሆኗ ቢታወቅም በእነዚያ ጊዜያት ማለፊያ ግንኙነት የነበራቸው መሆኑን ያሳያል። እስራኤልም ብትሆን ያኔ በደማስቆና በዋሽንግተን መካከል የተጀመረውን ልባዊ ስምምነት በበጎ መንፈስ ነበር የተቀበለችው። ፕሬዚዳንት ክሊንተን በ1994 ጥቅምት ወር ላይ ደማስቆን ከጎበኙ በኋላ በኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ላይ በወጣ ጽሑፍ ‹‹እስራኤል የክሊንተንን ጉዞ ከሶሪያ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚያሻሽል አጋጣሚ አድርጋ ትቆጥረዋለች›› ብሏል።[18]

በ1999 መገባደጃ ላይ ክሊንተን በእስራኤልና በሶሪያ መካከል አንዳች ዓይነት የስምምነት ውል ሊቋጠር እንደሚችል ሙሉ እምነት አሳድረው ነበር። ባራክ ባደረጉት ጠንካራ ግፊት የተነሣም በምዕራባዊ ቨርጂኒያ በምትገኘው ሸፐርድስታውን ግዛት ጥር 2000 ላይ ሁለቱን አገናኙዋቸው። ይሁን እንጂ የእስራኤል ሕዝብ የጎላን ከፍታዎችን ለሶሪያ ስለመመለስ ያለው ስሜት ቀዝቃዛ መሆኑን ባራክ ተገነዘቡ። ከዚያ በኋላም ሂደቱን በማጓተት ጠንካራ ተደራዳሪነታቸውን ማሳየት ጀመሩ። በዚህም የተነሣ ንግግሩ የከሸፈ መሆኑ ግልጽ ሆነ። የክሊንተን ዋና አደራዳሪ የነበሩት ዴኒስ ሮስ ዘግየት ብለው ስለሁኔታው ሲገልጹ፡-‘‘ባራክ ሂደቱን ባያቀዘቅዙት ኖሮ በጥር 2000 ከሙሉ ስምምነት ላይ ይደረስ ነበር’’ ብለዋል።[19] ከዚያ በኋላ ሁለት ወር ዘግይቶ አሳድና ክሊንተን ጄኔቫ ላይ ቢገናኙም ድርድሩ የትም ሊደርስ አልቻለም። ምክንያቱም አሳድ ባራክን ሊያምኗቸው አልቻሉምና። ክሊንተን ለሂደቱ መጨናገፍ ሶሪያ ሳትሆን እስራኤል ተጠያቂ መሆኗን በግልጽ አስቀምጠውታል።[20]

ከዚያም ሻሮን በ2004 ሥልጣን ሲረከቡ በእስራኤልና በሶሪያ መካከል የተጀመረውና መልካም አዝማሚያ እየያዘ የመጣው ግንኙነት ብልሽልሽቱ ወጥቶ ቁጭ አለ፡፡ የዚያም ጦስ በሶሪያና በአሜሪካ መካከል የነበረውን ግንኙነትም እንዲሁ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳረፈበት፡፡ ከእርሳቸው በፊት ከነበሩት አራቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮች በተለዬ ሁኔታ ሻሮን የጎላን ከፍታዎችን ለሶሪያ ለመመለስ ምንም ዓይነት ፍላጎት አላሳዩም፡፡ "ምን የሚመለስ መሬት አለ?" ካሉ በኋላ ጨምረው "እኔ በበኩሌ እንዲህ ዓይነቱን ነገር ከሀሳቤ አላገባውም" በማለት አቋማቸውን ግልጽ አደረጉ፡፡[21] ሻሮንን የተካቸው ኢሁድ ኦልመርትም ቢሆኑ፣ ‹‹የጎላን ከፍታዎች ለሁልጊዜውም በእጃችን እንደሆኑ ይቆያሉ›› በማለት የሻሮንን ፈለግ መከተሉን መረጡ፡፡[22]

አወዛጋቢውን የጎላን ከፍታዎች ምድር ለሁልጊዜውም ይዞ ለመቆዬት የእስራኤል መሪዎች ያደረጉት ጥረት እስራኤል ውስጥ ሰፊ ተቀባይነት አስገኝቶላቸዋል፡፡ የአውሮፓ ሕብረት ዋና ጸሐፊ የሆኑት ሃቪዬር ሶላና መጋቢት/2007 ላይ ሶሪያ በ1967 የተነጠቀችውን የጎላን ከፍታዎች መልሳ እንድትቆጣጠር ለማገዝ ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ለዚህ የሶላና አስተያየት የክኔስት (የእስራኤል ምክር ቤት) የሊኩድ ፓርቲ አባል የሆኑት ይዝራኤል ካትዝ እንዲህ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡- "እስራኤል የሁልጊዜውም ግዛቷ አካል ከሆነውና ለፀጥታዋ መጠበቅ ወሳኝ ሚና ካለው የጎላን ከፍታዎች አታፈገፍግም››፡፡[23] ቤንጃሚን ናታንያሁም አሁን ግልጽ እያደረጉት ባለው አቋማቸው የጎላን ከፍታዎች በእስራኤል ቁጥጥር ስር እንዲቆይ ይፈልጋሉ፡፡[24] የእስራኤል ሕዝብ በሰጠው አስተያየትም ጎላን የእስራኤል ግዛት አካል እንደሆነ እንዲቆይ የሚፈልግ መሆኑን በግልጽ አመላክቷል፡፡ ለአብነት ያክል ታህሣሥ/2006 የተደረገ ጥናት 64 ከመቶ የሚሆኑ እስራኤላውያን የሀገራቸው ጦር ጎላን መልቀቁንና ከሶሪያ ጋር ስምምነት ማድረጉን እንደሚቃወሙ አሳይቷል፡፡ 19 ከመቶ የሚሆኑት ብቻ ናቸው ሂደቱን ደግፈው የተገኙት፡፡ ቀደም ሲል ጥቅምት 2006 ላይ የተደረገ ጥናትም ቢሆን 70 ከመቶ የሚሆኑት እስራኤላውያን ጎላን ሙሉ

ለሙሉ ለሰላም ብሎ መልቀቅን የተቃወሙ መሆናቸውንና 16 ከመቶ ብቻ ድጋፍ መቸራቸውን አረጋግጧል።[25]

ጎላን የመልቀቁን ሂደት አስመልክቶ ካለው ስር የሰደደ ተቃውሞ ጎን ለጎን በእስራኤል ገዥ ፓርቲዎች በተለይም በወታደራዊ ክፍሉ አካባቢ ከሶሪያ ጋር ስምምነት መደረጉን የሚደግፉ በርካታዎች ናቸው። የእስራኤል መከላከያ ጦር ኤታ-ማጆር ሹም በ2004 እስራኤል የጎላን ከፍታዎችን ለሶሪያ በመመለስ ሙሉና አስተማማኝ ጸጥታ የምታገኝ ከሆነ ያለ ጎላን ከፍታዎችም ራሷን መከላከል ስለማያቅታት ስምምነት ብታደርግ መልካም እንደሚሆን ተናግረዋል።[26] እስራኤል ከሶሪያ ጋር በመደራደር ጎላን ከመለሰችላት የረዥም ጊዜ ጠላቷ ከሆነችው ሀገር ጋር ሰላማዊ ግንኙነት መመሥረት ብቻ ሳይሆን ሂዝቡላህ፣ ሃማስና ኢስላሚክ ጅሃድ ከሶሪያ የሚደረግላቸው እርዳታ ይቋረጣል። እንዲሁም ኢራንም ብትሆን እነዚህን አካላት በጦር መሣሪያ ለማገዝ አስቸጋሪ ይሆንባታል። ከሁሉም በላይ ጠቃሚው ጉዳይ ደግሞ ሁኔታው ሶሪያ ሊባኖስ ውስጥ ሂዝቡላህን በልጓም ለመያዝ የሚያስችል የተጽዕኖ አቅም የሚፈጥርላት መሆኑ ነው። እንዲህ ዓይነት ክርክር የተነሣው ሂዝቡላህ 2006 ላይ የእስራኤልን ጦር ገትሮ በመያዝ አልበገር ባይነቱን ካስመሰከረ በኋላ ነው። የቀድሞዎቹን የእስራኤል ኤታማዦር ሹምና የሀገር ውስጥ ስለላ ድርጅት (ሺን ቤት) የበላይ ጨምሮ በርካታ ቁጥር ያላቸው ታዋቂና ተፅዕኖ ፈጣሪ እስራኤላውያን ከሶሪያ ጋር ሰላም እንዲወርድ የሚጥር ፎረም ለማቋቋም ችለዋል። የዚያ ፎረም ዋና ዓላማ የእስራኤል መንግሥት ከሶሪያ በኩል የሚነሱ የሰላም ፍንጮችን እንዲቀበል ማሳመንና በደማስቆና ቴሌአቪቭ መካከል እውነተኛ ሰላምን ማስፈን ነው።[27] የኢሁድ ኦልመርት መከላከያ ሚኒስትር አሚር ፔሬትዝ ከደማስቆ ጋር የሚደረገውን የሰላም ስምምነት እንደሚደግፉ ሁሉ ሃ›ኤሬቲዝ ጋዜጣም እንዲሁ የዚሁ ስምምነት ደጋፊ ነው።[28] ሆኖም ግን ይህ ሃሳብ በአሪዬል ሻሮንም ሆነ በኢሁድ ኦልመርት ዘንድ በጽኑ የተወገዘ መሆኑ ይታወቃል።

አሁን ያሉት የእስራኤል መሪዎች የጎላን ከፍታዎችን ለሶሪያ ለመመለስ ፈቃደኛ እስካልሆኑ ድረስ ከደማስቆ ጋር የሰላም ስምምነት ለማድረግ

ፍላጎት የላቸውም ማለት ይቻላል።"[29] ድር ድር ቢጀምሩ ስለምን ሊናገሩ ይችላሉ? ሃሳበ ግትር መሆናቸውን በተግባር በሚገልጽ ሁኔታ ሶሪያ ታማኝነት የሚጎድላት ሀገር ናት' የሚልና መሰል የተለመዱ ክሶቻቸውን ሊሰነዝሩ ነውን? ለዚህም ነው በዋሽንግተን የሶሪያ አምባሳደር 2004 ላይ፡- "ስለ ሰላም ብዙ በተናገርን ቁጥር ብዙ ጥቃት ነው የደረሰብን" በማለት የተናገሩት።[30] እንግዲህ እስራኤል ሶሪያን በተመለከተ ከትብብር ይልቅ የጠላትነት ስሜትን መከተሉ የተሻለ የፖሊሲ ምርጫዋ አድርጋለች። እንደ እስራኤል መሪዎች ፍላጎት ከሆነ የቡሽ አስተዳደር ሶሪያን ሁልጊዜም በጠላትነት እንደፈረጀ ቢቆይ ምርጫቸው ነው። በ1990ዎቹ እስራኤል ከሶሪያ ጋር በትብብር ትኖር የነበረ ቢሆንም፣ ከ2001 በኋላ ግን ዩ.ኤስ.አሜሪካ ሶሪያን አደገኛና የሰላም ጠንቅ አድርጋ እንድታያት ለማድረግ እስራኤልና የአሜሪካ ደጋፊዎቿ በትጋት ነበር የተንቀሳቀሱት።

ሶሪያ አሁንም ቢሆን የጎላን ከፍታዎችን ለማስመለስ ተስፋ በማድረግ የሰላም ድርድሩ እንደገና እንዲጀመር ተደጋጋሚ ሙከራዎችን በማድረግ ላይ ትገኛለች።[31] ዳሩ ግን የእስራኤል መሪዎች ሌላው ቀርቶ ንግግር እንዲጀመር እንኳ ፈቃደኞች ሆነው አልተገኙም። የሶሪያ መንግሥት ታህሣሥ 2003 ላይ ያንቀሳቀሰውን የሰላም ሂደት አስመልክቶ ሃ› ኤሬትዝ በተሰኘው ጋዜጣ ላይ ዘ› ኢቭ ስቺፍ አስተያየቱን እንደሚከተለው አስፍሯል፡- "የሶሪያው ፕሬዚዳንት ከእስራኤል ጋር ንግግር እንዲጀመር ላቀረቡት ሃሳብ ጠቅላይ ሚኒስትር አሪዮል ሻሮን ዝምታን መምረጣቸው በጣም የሚያስደንቅ ነገር ነው። አንዳች ቃል ከአንደበታቸው ይወጣል ብለን ባለፉት ጊዜያት ብንጠብቅም አንድም ነገር ለመናገር አልፈቀዱም።"[32]

2006 ታህሣሥ ወር አጋማሽ ላይ ፕሬዚዳንት አሳድ ለጣሊያኑ ላ› ሪፖብሊክ ጋዜጣ በሰጡት አስተያየት ኦልመርት ከእርሳቸው ጋር እንዲነጋገሩ ሲያሳስቡ ‹‹ከሶሪያ ጋር ተደራደሩ፣ እንደ ብዙ እስራኤላውያን አባባል፡- 'ይህን ማድረጋችሁ ቀጥ ያለ ገደልን እንደመውጣት ቢቆጠርም እንኳ የምታጡት ነገር የለም›" ብለዋል።[33] በተመሣሣይ ጊዜ የሶሪያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ አስተያየታቸውን ሲሰጡ ሶሪያ ከእስራኤል ጋር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ንግግር ለመጀመር

ዝግጁ መሆኗንና እንደዚያ ማድረጓም ከመደራደር አቋሟ ላይ ተጽእኖ ሊፈጥር እንደሚችል ጭምር ተናግረዋል።[34] ኦልመርት በበኩላቸው ያንን ንግግር ለመጀመር የሚያስችላቸውን አጋጣሚ ውድቅ ካደረጉ በኋላ ከሶሪያ ጋር ላለመደራደራቸው ቡሽን ተጠያቂ አድርገዋል።[35] የጠቅላይ ሚኒስትሩ አስተያየት የያዘውን አንደምታ ብዙ እስራኤላውያን የሚጋሩት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለቡሽ ያላቸው ታማኝነት ባያግዳቸው ኖሮ ከአሳድ ጋር ሊደራደሩ ይችሉ እንደነበር ነው ከኦልመርት አስተያየት መገንዘብ የሚቻለው።

ዳሩ ግን ይህ አባባል ፈጽሞ አሳማኝ አይደለም። እንደዚያ ለማለት የሚስችለን ዩ.ኤስ.አሜሪካ እስራኤልን ከሶሪያ ጋር እንዳትነጋገር ያልከለከለቻት መሆኑን በዋሽንግተን የእስራኤል አምባሳደር ማመናቸው ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን እስራኤል ጥቅሟን በሚመለከት ጉዳይ ከየትኛውም የዩ.ኤስ.አሜሪካ መሪ ትዕዛዝ የመቀበል ባሕሪ የሌላት መሆኑን ጭምር ነው።[36] ኦልመርት ከሶሪያ ጋር ትርጉም ያለው ድርድር የማድረግ ልባዊ ፍላጎት እንዳላቸው የሚያሳዩ ሁነኛ ማስረጃዎች አይገኙም። አንድ ከፍተኛ የእስራኤል መንግሥት ባለሥልጣን፣ ለሃ-ኤሬትዙ ጋዜጠኛ አሉፍ ቤን እንደገለጹለት፡- "እስራኤል አስፈላጊነቱን ከወሰነች ከሶሪያ ጋር ለመደራደር የአሜረካን ፈቃድ አትጠብቅም" ብለዋል።[37] ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከድርድሩ ጠረጴዛ ራሳቸውን ማራቃቸው ሊያስደንቀን አይገባም። ለምን ቢባል የመከላከያ ሚኒስትሩን አሜር ፔሬትዝን አባባል ለመጥቀስ፡- "ስምምነት ሁሌም ዋጋ ስለሚያስከፍል ነው።›› ያም የኅላን ከፍተኛ ቦታዎችን ለሶሪያ የመመለስ ዋጋ ሲሆን፣ እንዲያ ማድረጉን ደግሞ ኦልመርት ፈጽሞ አይሞክሩትም። ስለሆነም ኦልመርት ሁልጊዜም ሰበብ እየደረደሩ መቆየቱን መርጠዋል። የሃ›ኤሬትዝ ሪፖርተር ጌዲዮን ሳሜት ሁኔታውን አስመልክቶ ሲተች፡- "ኦልመርት እውነተኛውን ምክንያት መቀበል የማይፈልጉ በመሆኑ ባጭሩ ከኅላን ከፍታዎች መውረድ አይሹም" ብሏል።[38]

በተመሣሣይ ሁኔታ ሶሪያ ከእስራኤል ጋር ሰላም ለማውረድ ፍላጎት ያላት መሆኑና እስራኤል በተቃራኒው ሰላማዊ ድርድር የማትሻ መሆኗ የተገለጸው ጥር 2007 ላይ ነበር። ይህ የሆነው የሁለቱ ሀገራት ልዑካን

ስምምነት ላይ ለመድረስ በሚል ከመስከረም 2004 እስከ ሐምሌ 2006 ባለው ጊዜ አውሮፓ ውስጥ በምስጢር እየተገናኙ ይነጋገሩ እንደነበር በተረጋገጠ ጊዜ ነበር። ስብሰባዎቹ ይፋ የወጡ ባለመሆናቸው በሁለቱም መንግሥታት በኩል ፖሊሲ አውጪዎችን ያካተቱ አልነበሩም። ይሁን እንጂ ሁለቱም መንግሥታት ንግግሮቹን በተመለከተ በቂ መረጃ ነበራቸው። በሃ›ኤሬትዝ ዘገባ ‹‹የእስራኤል ተወካዮች ከአውሮፓ አደራዳሪዎችና ምክትል ፕሬዚዳንት ፋሩቅ ኤል ሻራ' ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዋሊድ ሙዓሊምና በጄኔራል ማዕረግ የሶሪያ ደህንነት ኃላፊን ጨምሮ ከከፍተኛ የሶሪያ ባለሥልጣናት ጋር ስምንት የተለያዩ ስብሰባዎችን አድርገዋል።››[39] በመጨረሻም ሁለቱ ወገኖች በደረሱበት ስምምነት መሠረት እስራኤል ሰኔ 4/1967 ወደነበረችበት የሁለቱ ሀገራት ድንበር እንድትመለስ ጥሪ አደረጉ። በአጸፋው ሶሪያ ሂዝቡላህንና ሃማስን ከመርዳት እንድትቆጠብ እንዲሁም ከኢራን ጋር ያላትንም ግንኙነት እንድታላላ ተስማሙ። ንግግሩ የቆመው ሶሪያ ስምምነቱ ከንግግር አልፎ ይፋዊ ደረጃ (Officeal Level) ይኑረው የሚል ጥያቄ ባነሳች ጊዜ ሲሆን የኦልመርት መንግሥት እንቢታውን አሳይቷል።

ከዚያ በኋላ ሚያዝያ 2007 ላይ የአሜሪካ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ናንሲ ፔሎሲ ደማስቆ ሄደው ከአሳድ ጋር በመገናኘት ኦልመርት ከእርሳቸው ጋር ለመደራደርና ከስምምነት ላይ ለመድረስ ዝግጁ መሆናቸውን እንደገለጹላቸው ተናገሩ።[40] ይሁን እንጂ ፔሎሲ የኦልመርትን አቋም በሚገባ አልተገነዘቡም ነበር ማለት ይቻላል። የእስራኤል መንግሥት ከአሳድ ጋር ለመደራደር ፍላጎት የሌለው መሆኑን ፔሎሲ እንዲያውቁት ለማድረግ ‘‘ሶሪያ ከሰይጣን ዛቢያዎች ጋር ልትመደብ የሚገባትና በመካከለኛው ምሥራቅ ሽብርተኝነትን የምታስፋፋ ሀገር ናት ” የሚል ይፋዊ መግለጫ አወጣ።[41]

ኦልመርት የጎላን ከፍታዎችን አስመልክቶ የሚከተሉት አቋም በየጊዜው መዋዠቅ እየታየበት መቀጠሉ አልቀረም። ለምሳሌ ሰኔ 2000 ላይ አንድ መግለጫ ወጥቶ ኦልመርት ከሶሪያ ጋር ለመነጋገር ዝግጁ ሲሆኑ እንደሚችሉ ቢሰማንም፣ ም/ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ሽሞን ፔሬዝ፡-

“ሶሪያ እውነተኛ ድርድር ለማድረግ ዝግጁ አይደለችም” በማለት ወትሮም በቋፍ በነበረው የሰላም ሀሳብ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ቸለሰብት።[42] ለወደፊቱ በእስራኤል ፖለቲካ ላይ የበላይነት የሚኖረው እንደ ራቢን ያለ መሪ ሲመጣ በሁለቱ ሀገራት መካከል ሰላም ሰፍኖ ጎላንም ለባለቤቱ ሶሪያ የሚመለስበት አጋጣሚ እንደሚኖር ጥርጥር የለውም። እስከዚያው ድረስ ግን ሊያከራክረን የሚችለው ሃሳብ እስራኤል እስከ ሁልጊዜውም ጎላን ለሶሪያ ላትመልስ ትችላለች የሚለው አይደለም። ከዚያ ይልቅ እስራኤል ደማስቆን አስመልክቶ የምትከተለው ፖሊሲ ምንም ይሁን ምን ዩ.ኤስ.አሜሪካ በሶሪያ አንፃር በምትከተለው ፖሊሲ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑ ነው።

አሪዮል ሻሮን 2001 ላይ ሥልጣን ከመያዛቸው አንድ ወር ቀደም ብሎ አሜሪካን መምራት የጀመረው የቡሽ አስተዳደር ያለፍላጎቱም ቢሆን የአሳድን መንግሥት ለማግለልና ጫና ለማሳደር ሲሞክር ቆይቷል። እንዲህ በሚባልበት ጊዜ ምናልባትም፡- ‹‹ሶሪያ ሃማስንና ሂዝቡላህን የመሳሰሉ ሽብርተኛ ድርጅቶችን ሙሉ በሙሉ መርዳቷን ቀጥላለች። እንዲሁም ቡሽ፡- “ወስላታ መንግሥታት ” ካሏቸው ተርታ የምትመደብ ናት›› የሚል ክርክር ሊነሳ እንደሚችል ይገመታል። ሆኖም ግን ከእነዚህ ድርጅቶች አንዳቸውም ቢሆኑ የዩ.ኤስ.አሜሪካን ጥቅሞች በቀጥታ ስጋት ላይ ጥለው የማያውቁ ሲሆኑ ሶሪያም የጎላን ከፍታዎችን ትመልስላት ዘንድ በእስራኤል ላይ ጫና ለማሳደር እነዚህን ድርጅቶች ከመጠቀም ውጪ ምርጫ የሌላት መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል። እስራኤል ከሶሪያ ጋር ሰላም በማውረድ ሶሪያ ከሃማስና ከሂዝቡላህ ጋር ያላት ትስስር እንዲያበቃ ማድረግ ትችላለች። ለዚህም ነው ምንም እንኳን ሶሪያ እነዚህን ሽብርተኛ የሚሰኙ ድርጅቶች መርዳቷን ባታቆምም ቅሉ፣ የእስራኤል መሪዎች በ1990ዎቹ ከእርሷ ጋር ስምምነት ለማድረግ የቻሉት።

ቀደም ብለን እንደገለጽነው በዩ.ኤስ. አሜሪካ መንግሥት ውስጥ ሶሪያን የምር ጠላት አድርጎ በመያዝ ረገድ ጠንካራ ተቃውሞ ሲነሳ ቆይቷል። ሲ.አይ.ኤና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተለይ ከሶሪያ ጋር በጠላትነት መተያየት ስትራቴጂያዊ ብስለት የጎደለው አካሄድ መሆኑን ሲገልጹ ቆይተዋል። እስራኤልና ሎቢው ግን ከዚህ ተቃራኒ በሆነ አቅጣጫ ነበር የተጓዙት። በመጨረሻም የዚህ ጉዟቸው እድገት የኋላ ኋላ ከፕሬዚዳንት ቡሽ ጋር ያፋጠጣቸው ሲሆን፣ ሁኔታው ከመስከረም 11ዱ ጥቃት ወዲህ

ምን ይመስል እንደነበርና ዩ.ኤስ.አሜሪካ የተከተለችው ፖ.ሊ.ሲ ወዴት እንዳመራ በቀጣዮቹ ርዕሶች ለመዳሰስ እንሞክራለን።

ቴልአቪቭና ደማስቆ ከመስከረም 11 በኋላ

ሶሪያ ለዩናይትድ ስቴትስም ሆነ ለእስራኤል አደገኛ የሆነች የስጋት ምንጭ መሆኗን ከመጀመሪያው ጀምሮ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሻሮንና የጦር መኳንንቶቻቸው ለቡሽ አስተዳደር ግልጽ አደረጉ።[43] ይሁን እንጂ ከ2003 በፊት ዋሽንግተን ትኩረቷን በሶሪያ ላይ እንድታደርግ ግፊታቸውን አላጠናከሩም ነበር። ይህን ያደረጉት የቅድሚያ ትኩረታቸውን ለኢራን ሰጥተው የነበረ በመሆኑና የኢራቅ ጦርነት እንዲጀመር ግፊት የሚያደርጉበት ሰዓት ስለነበር የዋሽንግተን ልብ በተለያዩ ጉዳዮች እንዳይከፋፈል በመስጋታቸው ነው። ሆኖም ግን ልክ መጋቢት አጋማሽ 2003 ላይ ባግዳድ በአሜሪካ እጅ እንደወደቀች የእስራኤል መሪዎች፣ ዩናይትድ ስቴትስ በሶሪያ ላይ ትኩረቷን እንድታሳርፍና ጦሯን አዝምታ የሶሪያን መንግሥት ባሕሪ ወይም ደግሞ አገዛዙን ራሱን እንድትቀይረው ለማድረግ ጉትጎታቸውን ተያያዙት።[44]

ሻሮን ሚያዝያ 15/2003 ላይ ' የዲኦት አህሮኖት ' ለተባለው ታዋቂ የአይሁድ ጋዜጣ በሰጡት ከፍተኛ ግምት የተሰጠው ቃለ ምልልስ- "አሳድ አደገኛ ሰው ናቸው። የሚሰጡት ውሳኔም እንደዚያው ጎጂ ነው" ካሉ በኋላ፤ ''የኢራቅ ጦርነት ከመጀመሩ በፊት ወታደራዊ መሣሪያዎች ከኢራቅ ተጓጉዘው ወደ ሶሪያ እንዲገቡ አድርገዋል'' በማለት ከሰዋቸዋል። ከዚያም ሶሪያ ሃማስንና ሂዝቡላህን መደገፏን እንድታቆም፣ እንዲሁም የኢራን ሪፖብሊካን ዘብ ከሊባኖስ ቤካ ሸለቆ እንዲለቅ፣ ከኢራን ጋር የሚደረግ ማንኛውም ትብብር እንዲቆም፣ ሂዝቡላህ ከእስራኤልና ከሊባኖስ ድንበር ተነስቶ በምትኩ በሊባኖስ ሠራዊት እንዲተካ፣ ሂዝቡላህ በእስራኤል ላይ ያነጣጠራቸውን ሚሳዬሎች እንዲያነሳ ‹‹ከባድ›› ያሉትን ጫና ዩናይትድ ስቴትስ እንድታሳርፍ ጠየቁ።[45] ይህን የሻሮንን ድፍረት ያዘለ ጥያቄ ያስተዋሉ አንድ ከፍተኛ የእስራኤል ዲፕሎማት ሻሮን በደማስቆና

በዋሽንግተን መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክተው የሚሰጡት ምክር ለስለስ ያለና ገደቡን ያላለፈ ቢሆን እንደሚመረጥ አስጠንቅቀዋል።[46]

የቡሽ አስተዳደር በሶሪያ ላይ ጠንካራ እርምጃ እንዲወስድ የሚጠይቁት ከፍተኛ የእስራኤል ባለስልጣን ሻሮን ብቻ አይደሉም። የመከላከያ ሚኒስትሩ ሻውል ሞፋዝ ማኣሪቭ ለተባለው የእስራኤል ጋዜጣ ሚያዝያ 14 2003 በሰጡት ቃለ ምልልስ፡- ‹‹እኛ ከሶሪያውያን የምንጠይቃቸው በርካታ ዝርዝር ጉዳዮች ያሉን እንደመሆኑ እነዚያን ጉዳዮቻችንን የምናስፈጽመው ደግሞ በአሜሪካ በኩል ነው›› ብለዋል።[47] ሁለት ሳምንት ዘግይቶ የሻሮን ብሔራዊ ጸጥታ አማካሪ ኤፍሬም ሄልቪ ወደ ዋሽንግተን መጥተው የዩ.ኤስ.አሜሪካ ባለሥልጣናት በሶሪያ ላይ ‹‹ወሳኝ›› ያሉትን እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበዋል። ሄልቪ የሶሪያን ጅምላ ጨራሽ መሣሪያ አደገኛነት ከማስጠንቀቃቸውም በላይ፣ አሳድን “ኃላፊነት የማይሰማቸው ውዳቂ” ብለዋቸዋል።[48] ሄልቪ ግንቦት 3 ቀን 2003 በተደረገው የደብሊው አይ.ኤን.ኢ.ፒ. ኮንፈረንስ ላይ ባደረጉት ንግግር አሳድን “መጥፎ ተጽዕኖ ለመፍጠር የሚጥሩ” ሲሉ ከወረፏቸው በኋላ፣ “ባረጀውና ባፈጀው የማጭበርበሪያ ስልታቸው ላይ እንዲቆዩ አንፈቅድላቸውም” በማለት ዝተዋል። ሄልቪ በመጨረሻም እንዲህ አሉ፡- “በዚያ ወጣት’ ኩሩና ልምድ አልባ የሶሪያ ፕሬዚዳንት (በሻር አል-አሳድን ማለታቸው ነው) የውሻ ክራንቻ ላለመነከስ ከጦርነት በመለስ የምንወስዳቸው በርካታ እርምጃዎች ይኖራሉ።››[49]

ሳዳም ከተውገዱ በኋላ ሶሪያ የኢራቅን ያክል ወይም ከርሷ ይበልጥ አደገኛ እንደሆነች የቡሽ አስተዳደር ይገነዘብ ዘንድ ለማሳመን እስራኤል ትጥር ነበር። በእርግጥ ስለ ሶሪያ አደገኝነት የተነገረው ሁሉ፣ የሶሪያን አጠቃላይ አቅም ካጤንነው፣ ውሸት ነው ብለን መደምደም እንችላለን። ለምን ቢባል አሥራ ዘጠኝ ሚሊዮን ሕዝብና ከአሜሪካ የመከላከያ በጀት ጋር ሲነፃፀር 1/300ኛ የሚሆን የመከላከያ በጀት ያላት ሀገር እንደምን አደገኛ የሆነ ስጋት ልትደቅን እንደምትችል ግልጽ አይደለምና። እንደዚያም ሆኖ እንደ እስራኤላዊው ስትራቴጂስት ዮሲ.አልፊር አባባል፣ “ሶሪያ ከኢራቅም የበለጠ በእስራኤል ላይ ትልቅ ጉዳት የማድረስ አቅም አላት።” ዋሽንግተን ፖስት ባቀረበው ዘገባ በ2003 ሚያዝያ አጋማሽ ላይ ሻሮንና ሻውል ሞፋዝ በሶሪያ

ላይ በከፈቱት ዘመቻ የአሳድን እንቅስቃሴዎች አስመልክተው ለዩናይትድ ስቴትስ መረጃዎችን እያቀበሉ የጦርነት ነዳጅ ማርከፍከፉን ተያይዘውት ነበር።[50]

እስራኤል የሶሪያን ገጽታ በማጠልሸቱ ዘመቻ ገፍታ "ደማስቆ ከፍተኛ የሳዳም አገዛዝ አባላት የሆኑ ባለሥልጣናትን ወደ ሀገሯ እንዲገቡ አድርጋለች" በማለት ከስሰቻት በኋላ ከዚያም በከፋ ሁኔታ የኢራቅን ጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ጭምር መደበቋን ተናግራለች።[51] 2003 ነሐሴ ወር ላይ ቦምብ የጫነ ከባድ መኪና ባግዳድ የሚገኘውን የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጽ/ቤት ባነጎደው ጊዜ በተባበሩት መንግሥታት የእስራኤል አምባሳደር፣ "መኪናውን የላከችው ሶሪያ ናት" በማለት ያለምንም መረጃ ኃላፊነቱን በእርሷ ላይ ደፈደፉት።[52] በተመሣሣይ አጋጣሚ በዩናይትድ ስቴትስ የእስራኤል አምባሳደር የነበሩት ኢትማር ራቢኖቪች፣ ሳይሙር ኧርሽ ለተባሉ እስራኤላዊ እንዲህ ብለዋቸው ነበር- ‹‹ሶሪያውያን የመስከረም 11 ዱን ጥቃት የሚመለከት መረጃ ደርሷቸው የነበረ ቢሆንም፣ ለዩናይትድ ስቴትስ ባለማካፈላቸው ተደንቂያለሁ።››[53] እርግጥ ነው ይህን ጉዳይ አስመልክቶ እጅግ በጣም አነስተኛ መረጃ ሊኖር ወይም ደግሞ ምንም ዓይነት መረጃ ላይኖር ይችላል። ይሁን እንጂ እስራኤላውያኑ ዩናይትድ ስቴትስን በማደናገር ሌላ የአረብ አገዛዝን ለመጣል እንድትነሳና እንደልማዷ ጦርነት ውስጥ እንድትዘፈቅ ለማድረግ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የሌለ መሆኑን ነው ከዚህ ድርጊታቸው መገንዘብ የምንችለው።

ሎቢውና ደማስቆ ከመስከረም 11 በኋላ

በሎቢው ውስጥ ያሉ ጥቂት ሰዎች በመስከረም 11ዱ ጥቃት መንታዎቹ ሕንፃዎች ከመውደቃቸው በፊት ጀምሮ በሶሪያ ላይ ዓይናቸውን ጥለው ነበር። በ1996 "ክሊን ብሪክ" የተባለውን ጥናት ጥቂት ኒዎኮንሰርቫቲቮች ያዘጋጁት ናታንያሁን ለሥልጣን ለማብቃት በማሰብ ነበር። በተጨማሪም ዳንኤል ፓይፕና ዘይድ አብደልኑር የተባሉት ሁለት የዩ.ኤስ. ኮሚቴ ፎር ፍሪ ሊባኖን (ዩ.ኤስ.ሲ.ኤፍ.ኤል) አባላት እ.ኤ.አ. በ2000 ዓ.ል በጋራ

ባዘጋጁት ሪፖርት ሶሪያ ከሊባኖስ ኃይሏን እንድታስወጣ፣ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎቿን እንድታስወግድና ሽብርተኝነትን መደገፏን እንድታቆም ዩናይትድ ስቴትስ ጫና ታደርግባት ዘንድ ጥሪ አድርገዋል።[54] SCFL የሎቢው አጋር ድርጅት ሲሆን ኢሊዮት አብራምስ፣ ዶግላስ ፊ,ፊፍዝ፣ ሪቻርድ ፐርልና ዴቪድ ውርምሰር ዋና ዋና ከሚባሉት ደጋፊዎቹ ውስጥ ይገኙበታል። እነዚህ ሰዎች አፍቃሪ-እስራኤል የሆኑት የኒው ዮርኩ ዲሞክራት ኮንግረስማን ኢሊዮት ኤንግል እንዳደረጉት ሁሉ በ2000ው ሪፖርት ላይ ፈርመዋል።[55]

ይህ ሀሳብም ሆነ ሌሎቹ መሰል ጥረቶች በክሊንተን የአስተዳደር ዘመናት በዋሽንግተን ያን ያክል ግለት ሊፈጥሩ አልቻሉም። ምክንያቱም እስራኤል በእነዚያ ጊዜያት ከሶሪያ ጋር ስምምነት ላይ ለመድረስ ዝግጁ ስለነበረች ነው። ከእነዚያ ጠጣር መስመር ተከታዮች ጥረት ባሻገር በሎቢው ውስጥ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ቡድኖች ሶሪያን የሚመለከተውን የክሊንተን ፖሊሲ ለመገዳደር የሚያበረታታቸው ሁኔታ አልነበረም። ምክንያቱም የፕሬዚዳንቱ አቀራረብ የእስራኤላውያኑን ባሕሪ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነበርና። ሆኖም ግን ሻሮን በ2001 ሥልጣን ላይ እንደወጡ ሶሪያን አስመልክቶ እስራኤል ትከተለው የነበረው አስተሳሰብ በሚያስደንቅ ሁኔታ ተቀየረ። ያንን ለውጥ ተከትሎ በሎቢው ውስጥ የሚገኙ በርካታ ቡድኖች ደማስቆን አስመልክቶ ፍጥጫ ያለበት አካሄድ እንዲኖር ግፊት ማድረግ ጀመሩ።

በ2002 ጸደይ ወራት ኢራቅ ዋነኛዋ የትኩረት ማዕከል በሆነች ጊዜ አይፓክ ሶሪያን "የሰይጣን ዛቢያዎች" ተብለው በቡሽ ከተፈረጁት ሀገራት ተርታ እንድትሰለፍ ለማድረግ ሕግ እንዲረቀቅ ጥረቱን ያፋፋመ ሲሆን፣ ኮንግረስማን ኤንግል ‹‹የሶሪያ አካውንቲቢሊቲ አክት›› የሚባለውን ረቂቅ ኮንግረሱ ያጸድቅላቸው ዘንድ አቀረቡ።[56] ያ ረቂቅ ሕግ ሶሪያ ከሊባኖስ የማትወጣ ከሆነ፣ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ማምረቷን ካላቆመችና ሽብርተኝነትን መደገፏን ካልተወች ማዕቀብ እንደሚጣልባት ያስጠነቅቃል[57] ሕጉ በተጨማሪም ሶሪያና ሊባኖስ እስራኤል ጋር ሰላም ለመፍጠር ወሳኝ እርምጃ እንዲያደርጉ ጥሪ ያደርጋል። የሕጉ ረቂቅ አይፓክን ጨምሮ በበርካታ የሎቢው ቡድኖች የተደገፈ ሲሆን፣ እንደ ጀዊሽ ቴሌግራፊክ

ኤጀንሲ አገላለጽ፡- “የሕጉ ረቂቅ የተቀናበረው ኮንግረስ ውስጥ በሚገኙ አንዳንድ የእስራኤል ወዳጆች ነበር፡፡” ጀዊሽ ቴሌግራፊክ ኤጀንሲ (ጄ.ቴ.ኤ) በተጨማሪ እንደገለጸው፡- “በቡሽ አስተዳደር ውስጥ የነበረና የረቂቅ ሕጉን ማለፍ በጉጉት ሲከታተል፣ እንዲሁም ከኢሁድ ኦልመርት ቢሮ ጋር ተደጋጋሚ ግንኙነት ሲያደርግ የቆዬው ኤሊዮት አብርምስ ነው” ብሏል፡፡[58]

የቡሽ አስተዳደር በበኩሉ ‹የሶሪያ አካውንቴቢሊቲ አክት› የተሰኘውን የሕግ ረቂቅ 2002 ላይ ተቃውሞታል፡፡ ምክንያቱም ረቂቁ አልፎ ሕግ ከሆነ የኢራቅን ጦርነት ለማስተባበር ሁኔታዎችን አስቸጋሪ ከማድረጉም በላይ፣ ደማስቆ አል-ቃዒዳን የተመለከቱ ጠቃሚ መረጃዎችን ለአሜሪካ እንዳትሰጥ ያደርጋታል የሚል ፍርሃት ስላደረበት ነው፡፡ ስለሆነም ኮንግረሱ የሳዳም ጉዳይ እስኪለይለት ድረስ ረቂቅ ሕጉን በመሳብ እንዲዘገይ ተስማማ፡፡

ይሁን እንጂ በሚያዝያ 2003 ባግዳድ እንደተወረረች ሎቢው በሶሪያ አንፃር ጀምሮት የነበረውን ዘመቻ እንደገና ለማደስ ተንቀሳቃሰ፡፡ በኢራቅ ላይ የተወሰደውን እርምጃ ተከትሎ በተገኘው ድል የተበረታቱ የእስራኤል ደጋፊዎች ሶሪያ ባሕሪዋን እንድትቀይር መደረጓ ብቻ ስላላረካቸው አገዛዙ እንዳለ እንዲወገድ ፈለጉ፡፡ ፓውል ዎልፎዊትዝ ‹‹ የሶሪያን አገዛዝ የመቀየሪያው ጊዜ አሁን ነው ›› በማለት ተናገሩ፡፡ ሪቻርድ ፐርል ደግሞ እንዲህ በማለት ለአንድ ጋዜጠኛ አቋሙን አሳወቀ፡- ‹‹በክልሉ ለሚገኙ ጠብ ጫሪ መንግሥታት ማስተላለፍ የምንፈልገው አጭር መልዕክት፣ “ቀጣዮቹ ባለተራ እናንተ ናችሁ የሚል ነው፡፡››[59] በተጋፊነቱ የሚታወቀውና በሪቻርድ ፐርል የሚመራው፣ እንዲሁም ፖሊሲ ቦርድን የሚመራው ኬኔት ኤድልማን፣ የኢልዮት ኮኸንና መሰል ኒዮኮንሰርቫቲቮችን በአባልነት ያቀፈው ዲፈንስ ፖሊሲ ቦርድ የተባለ ተቋምም እንዲሁ ሶሪያን በተመለከተ የጠጣር መስመር አቀንቃኝ ነበር፡፡[60]

ከአብራምስ፣ ፐርልና ዎልፎዊትዝ በተጨማሪ በሶሪያ የአገዛዝ ለውጥ እንዲኖር ግፊት ከሚያደርጉት ቁልፍ ሰዎች መካከል የዩ.ኤስ.ምክትል ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር (ኋላ ላይ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአሜሪካ አምባሳደር) ጆን ቦልተን አንዱ ናቸው፡፡ ቦልተን የኢራቅ ጦርነት ከመደረጉ

አንድ ወር ቀደም ብሎ ፕሬዚዳንት ቡሽ ሳዳምን ከጣሉ በኋላ ሶሪያን፣ ኢራንንና ሰሜን ኮሪያን አከታትለው እንደሚወርሩ ለእስራኤል መሪዎች ነግረዋቸው ነበር።[61] በዚያው ሰሞን ቦልተን ሐምሌ አጋማሽ ላይ ከኮንግረሱ ፊት ቀርበው የሶሪያ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ መካከለኛው ምሥራቅን ስጋት ላይ ከሚጥልበት ደረጃ ላይ የደረሰ በመሆኑ ኮንግረሱ ፈጥኖ መላ እንዲያበጅለት ለማድረግ ተዘጋጁ።›› ሲሉ አሳስበዋል። ዳሩ ግን ሲ.አይ.ኤና ሌሎች የመንግሥት ወኪሎች "ቦልተን ጉዳዩን ከሚፈለገው በላይ እያስጮሁት ነው" በማለት ተቃውሟቸውን በማሰማታቸው የቡሽ አስተዳደር ሶሪያን አስመልክቶ ቦልተን ምንም ዓይነት የምስክርነት ቃል ለኮንግረሱ እንዲሰጡ ሳይፈቅድላቸው ቀረ።[62] እንደዚያም ሆኖ ቦልተን ለረዥም ጊዜ ተገትተው የሚቆዩ አልነበሩም። እናም መስከረም 2003 ላይ ከኮንግረሱ ፊት ቀርበው ‹‹ሶሪያ በመካከለኛው ምሥራቅ የአሜሪካን ጥቅም ስጋት ላይ ጥላለች›› በማለት አሳሰቡ።[63]

ሚያዝያ መጀመሪያ ላይ ደብሊው አይ.ኤን.ኢ.ፒ. ባቀረበው ሪፖርት "ሶሪያ ልትዘነጋው የማይገባት መልዕክት ሀገራት እንደ ሳዳም ሁሉ ግዴለሽ፣ እምቢተኛና ኃላፊነት የማይሰማቸው ከሆኑ የእርሳቸውን እጣ መጨለጣቸው የማይቀር መሆኑን ነው" አለ።[64] ሚያዝያ 15 ቀን በታተመው ሎስ አንጀለስ ታይምስ ጋዜጣ ላይ እስራኤላዊ አሜሪካዊው ጋዜጠኛ ዮሲ ክሌይን ሃልቪ ባቀረበው መጣጥፍ ‘‘ቀጣይ ጫናውን በሶሪያ ላይ አድርጉ’’ ሲል አስጠነቀቀ። በዚያው ዕለት ሴንተር ፎር ሴኩሪቲ ፖሊሲ የተባለው ድርጅት መሪና ኒዎኮንሰርቫቲቭ የሆኑት ፍራንክ ጋፍኒ በዋሽንግተን ታይምስ ጋዜጣ ላይ "የቡሽ አስተዳደር የሶሪያን ባሕሪ ለማረቅም ሆነ የአገዛዝ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ዘዴዎችን (ወታደራዊ ኃይልን ጨምሮ) መጠቀም ይኖርበታል" አሉ።[65] በቀጣዩ ቀን እስራኤላዊ አሜሪካዊ የሆነው ጋዜጠኛና የቀድሞው የእስራኤል መንግሥት የፕሬስ ዋና ኃላፊ ዜቭ ቻፌትስ በኒው ዮርክ ዴይሊ ኒውስ ጋዜጣ ላይ፡- ‘‘የሽብር ወዳጅ የሆነችው ሶሪያም መለወጥ አለባት" በሚል ርዕስ ጽሑፍ አስፍሯል። ሎውረንስ ካፕላንም እንዲሁ ሚያዝያ 21 በታተመው ኒው ሪፖብሊክ ላይ አሳድ ለአሜሪካ ስጋት መሆናቸውን ገልጿል።[66]

በሶሪያ ላይ በተከታታይ የቀረቡት ክሶች ቀደም ሲል በሳዳም ላይ ሲቀርቡ ከነበሩት ክሶች ጋር በእጅጉ ተመሣሣይነት ነበራቸው። ናሽናል ሪቪው ኦንላይን በሚሰኘው ጋዜጣ ላይ ወግ አጥባቂ የሆኑት ተንታኝ ጀድ ራቢን አስተያየታቸውን ሲገልጹ፡- "ምንም እንኳን የአሳድ ጦር የወረቀት ነብር ቢሆንም፣ ሰውዬው አሁንም ቢሆን እጅግ አደገኛ ሰው ናቸው" ብለዋል። ጀድ ቀጥለውም "የዚህ አባባል ዋነኛ መሠረት የእስራኤል ምንጭ ሲሆን በእስራኤል ወታደራዊና የስለላ ኃይል እምነት መሠረት አሳድ አርቀው የሚያስቡ መሪ መሆናቸውን ለመገመት በሚያዳግት ሁኔታ እጅግ አደገኛ ናቸው" ሲሉ ሀሳባቸውን አጠቃለዋል።[67] በሞሮኮ የዩ.ኤስ የቀድሞ አምባሳደር ሶሪያ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ በምስጢር ማምረቷንና የሚሳዬል ባትሪና ሮኬት መታጠቋን አስመልክተው ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋል።[68] ሁሉ አሜሪካውያን የእስራኤል ደጋፊዎች ልክ እንደ እስራኤላውያን መሰሎቻቸው ሶሪያ የሳዳምን ጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ደብቃለች ብለው ያምናሉ። "ይህ መሆኑ እኔን አያስደንቀኝም" ይላሉ ኮንግረስማን ኤንግል። አያይዘውም "ኢራቅ ውስጥ ፈልገን ልናገኛቸው ያልቻልነው ጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ዛሬ ሶሪያ ውስጥ እንደሚገኙ የታወቀ ነውና።"[69]

ኮንግረስማን ወደ ካፒቶል ሂል ተመልሰው ኤንግል የሶሪያን አካውንቴቢሊቲ አክት ሚያዝያ 12 ላይ እንደገና አንቀሳቀሱት።[70] ሶስት ቀን ዘግይቶ ሪቻርድ ፐርል ኮንግረሱ ያንን ረቂቅ እንዲያሳልፈው ጥሪ አቀረበ።[71] ሆኖም ግን የቡሽ አስተዳደር የሕጉን ረቂቅ በተመለከተ የነበረው ግለት አነስተኛ ስለነበር አሁንም እንደተንጠለጠለ ቀረ። ነሐሴ አጋማሽ ላይ ኤንግልና የተወሰኑ ፖለቲከኞችን ያቀፈ ቡድንና ከኒውዮርክ የተውጣጡ የአይሁድ መሪዎች ወደ እስራኤል ተጉዘው ለዘጠና ደቂቃ ያክል ሻሮንን በእየሩሳሌም ቢሯቸው አነጋገሯቸው። ኮንግረስማን ኤንግልን በተለይ ላበረከቱት አስተዋጽኦ የእስራኤሉ መሪ ካመሰገኗቸው በኋላ ዩናይትድ ስቴትስ በሶሪያ ላይ ጫና ለማሳረፍ ፈቃደኛ ያለመሆኗን ጠቅሰው አማረሩ። አሁንም ቢሆን የሕግ ረቂቁ ካፒቶል ሂል ላይ እንደገና እንዲቀርብ ለማድረግ ግፊታቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ የሚፈልጉ መሆኑንም ጨምረው ተናገሩ።[72] በቀጣዩ ወር የቡሽ አስተዳደር በሶሪያ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረው ረቂቅ ሕግ

ሆኖ እንዲጸድቅ በሚያደርገው ጥረት ደካማነት መሰላቸታቸውን የገለጹት ኤንግል ረቂቁን ወደ ኮንግረስ ዳግም ገፉት፡፡ በአይፓክ ሙሉ ትብብርም በካፒቶል ሂል የድጋፍ ድምፅ ማሰባሰባቸውን ቀጠሉ፡፡[73] ቡሽ በሉቢው ሙሉ ኃይልና ትብብር የተደገፈውን ያንን ረቂቅ እንደገና ሊያግዱት እንደማይችሉ ግልጽ ነበር፡፡ እናም ጸረ-ሶሪያ የሆነው ረቂቅ በተወካዮች ምክር ቤት 398 ለ4 እንዲሁም በሰኔቱ 89 ለ4 በሆነ ሰፊ ልዩነት ሊያልፍ ግድ ሆነ፡፡ ቡሽም ታህሣሥ 12/2003 ላይ ሕግ ሆኖ ይወጣ ዘንድ ፊርማቸው አኖሩበት፡፡[74]

ቡሽ ያቅማሙት ለምንድን ነው?

ምንም እንኳን ኮንግረሱ በሶሪያ ላይ ሽምቀቆውን ለማጥበቅ በጅምላ ቢንቀሳቀስም ቅሉ የቡሽ አስተዳደር ግን ያን ፖሊሲ መከተሉ በሚያስገኘው ፋይዳ ላይ ልዩነቶች ነበሩት፡፡ ፕርል፣ ቦልተንና ዎልፎዊትዝ ከደማስቆ ጋር ጦር ለመግጠም አካኪ ዘራፍ በሚሉበት ሰዓት የዚያኑ ያክል በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በሲ.አይ.ኤ. ውስጥ ሰፊ ተቃውሞ ይስተጋባ ነበር፡፡[75] ፕሬዚዳንቱ ራሳቸውም ቢሆኑ -እንደ ጆዊሽ ቴሌግራፊክ ኤጀንሲ አገላለጽ- ዋይት ሃውስ ውስጥ በሕጉ ረቂቅ ላይ ፊርማቸውን ባኖሩ ጊዜ እንዲህ ብለው ነበር፡- “እኔ የማልፈልገው ሕግ ቢሆንም፣ ፊርማዬን ግን የግድ ማኖር አለብኝ፡፡››[76] ፊርማቸውን ካኖሩም በኋላ ቢሆን ተግባራዊ በማድረጉ ላይ ቀስ ብለው እንደሚንዙ ነበር አበክረው የገለጹት፡፡[77]

ቡሽ ለማመንታታቸው ጥሩ ምክንያት ነበራቸው፡፡ ቀደም ሲል እንደገለጽነው የሶሪያ መንግሥት ለዩናይትድ ስቴትስ አል-ቃዒዳን የሚመለከቱ መረጃዎችን ከመስከረም 11 ጀምሮ ያቀርብ የነበረ ከመሆኑም በላይ፣ በባሕረ ሰላጤው አካባቢ የታቀደ የሽብርተኝነት ጥቃት ሊኖር እንደሚችልም አስጠንቅቆ ነበር፡፡[78] በተጨማሪም የመስከረም 11ዱን ጥቃት ካደረሱት ሰዎች መካከል የተወሰኑትን እንደመለመላቸው የሚታመነውን ሙሐመድ ዛማርን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለሲ.አይ.ኤ. መርማሪዎች ሰጥቶ ነበር፡፡ በጊዜው በዋይት ሀውስ ውስጥ የሚሠሩት ፍላይንት ሌቨሬት፡- “ፕሬዚዳንቱ

በደብዳቤም ሆነ በስልክ ከበሻር ጋር በተገናኙ ጊዜ ሁሉ አል-ቃዒዳን በተመለከተ ሶሪያ ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር ስለምታደርገው ትብብር ምሥጋናቸውን ያቀርቡላቸው ነበር" ብለዋል።[79]

ስለሆነም የአሳድን አገዛዝ ዒላማ ውስጥ ማስገባት እነዚህን ሁሉ ውጤታማ ግንኙነቶች አደጋ ላይ በመጣል በአጠቃላይ ዓለም አቀፋዊውን የፀረ-ሽብርተኛ ዘመቻ በተለይም ደግሞ አል-ቃዒዳን ለማጥፋት የሚደረገውን እንቅስቃሴ ያዳክማል። በዚህም የተነሣ ፕሬዚዳንት ቡሽ ከሶሪያ ጋር የመፋጠጡን ፖሊሲ መከተላቸው አሜሪካን ከአደጋ ላይ እንደሚጥላት በሚገባ ተገንዝበውታል።

ቡሽ በተጨማሪም ሶሪያ የኢራቅን ሰርጎ ገቦች ትረዳለች የሚለው ስጋት ከግምት ውስጥ በገባ አኳኋን ለአሜሪካ የስጋት ምንጭ እንዳልሆነች አውቀዋል። አሳድ ከዋሽንግተን ጋር ትብብር ለመፍጠር ምንጊዜም ዝግጁ ናቸው። የፕሬዚዳንት ቡሽ ወታደራዊ ስለላ ዋና አዛዥ እንደሆኑት ሳይሙር ኧርሽ አገላለፅ ሶሪያ ሌላው ቀርቶ የሂዝቡላህን ወታደራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ሳይቀር ለመግታት በሚያስችሉ ሁኔታዎች ዙሪያ ለመወያየት ፈቃደኛ ናት።[80] ዩናይትድ ስቴትስ ከአሳድ ጋር በመጋጨት የምታተርፈው የአረብ ሀገራትን እዚህም እዚያም በመንከስ የማይረባ የምግብ ፍላጎት እንዳደረበት እርኩስ አውሬ መቆጠርን ብቻ ነው። ስለሆነም አሜሪካ ልትደበድባቸው ከምትፈልጋቸው ሀገራት ዝርዝር ውስጥ የሶሪያን ስም ማስገባቷ ደማስቆ በኢራቅ ያለው የአሜሪካ ኃይል በማጥ ውስጥ እየዳከረ እንዲቆይ ተጨማሪ ጥረቶችን እንድታደርግ ስለሚገፋፋት ሶሪያን ለመምታት የሚያስችል ሁኔታ አይኖርም። ፕሬዚዳንቱ በሶሪያ ላይ ማንኛውንም ተጽዕኖ ለማድረግ ቢፈልጉ እንኳ በመጀመሪያ በኢራቅ የጀመሩትን ሥራቸውን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል።

በቡሽ አስተዳደር ውስጥ ያሉ ኒዎክንሰርቪቲቮች ከሶሪያ ጋር የሚደረጉ ትብብሮችን ይቃወማሉ። ሌላው ቀርቶ የሶሪያ የደህንነት ኃይል አል-ቃዒዳን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለዋሽንግተን በመስጠቱ ደስተኞች አይደሉም። "በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በምክትል ፕሬዚዳንቱ ቢሮዎች ውስጥ የሚገኙ ኒዎኮንአረቫቲቮች" ይላሉ ሌቨሬት፡- "አሜሪካን የደማስቆ ባለዕዳ በማድረግ

በሶሪያ መንግሥት ድጋፍ ለሚደረጉ የሽብርተኝነት እንቅስቃሴዎች ትክክለኛውን አፀፋ እንዳትሰጥ ተጽዕኖ ያሳድርባታል፣ በማለት የሶሪያን እርዳታ አይፈልጉም"።[81]

ይሁን እንጂ ፕሬዚዳንት ቡሽ ለዚህ ዓይነቱ፡- "ትክክለኛ አፀፋ" የሚባል ነገር ብዙም ፍላጎት አልነበራቸውም። እንዲያውም ሚያዝያ 2003 አጋማሽ ላይ በኢራቅ የተጀመረውን ጦርነት በድል ማጠናቀቃቸውን ተከትሎ አየሩ ሁሉ በቀጣዩ የሶሪያ ዘመቻ ወሬ በተሞላ ሰዓት እንኳ ፔንታጎን ለሶሪያ ዘመቻ ዕቅድ እንዲነድፍ መመሪያ አልሰጡም ነበር።[82] በአሜሪካና በወዳጆቿ ላይ በራስ የመተማመን መንፈስ አጥልቶ በነበረባቸው የኢራቅ የመጀመሪያ ድል ሰሞናት ቡሽ ሶሪያን አስመልክቶ አእምሯቸው ያልተቀየረ መሆኑ እውነት ነው። ፕሬዚዳንቱ "የሶሪያ አካውንቴቢሊቲ ሕግ" እየተባለ የሚጠራውንና ፊርማቸውን ሲያስቀምጡ ለተግባራዊነቱ እንደማይቸኩሉ ቃል የገቡለትን ሕግ ለማስፈጸም አልተጣደፉም። ይህ ድርጊታቸው ደግሞ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ አፍቃሪ-እስራኤል ጠጣር መስመረኞችን አስቆጥቷል። በ2004 ጸደይ ላይ ኮንግረስማን ኤንግልና ጥቂት ባልደረቦቻቸው ቡሽ ሕጉን ተግባራዊ ለማድረግ ማዘገማቸውን ተከትሎ ባደረባቸው ስጋት አዲስና ጠንካራ የሆነ ሕግ አርቅቀው ለኮንግረሱ እንደሚያቀርቡ በመግለጽ ዛቱ።[83]

ኦልመርት ከሚናገሩት በተፃራሪ ሁኔታ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ በዜና ማሰራጫዎች የሚናፈሰው ወሬ እስራኤል የአሳድን ጥያቄ ተቀብላ የሰላሙ ንግግር ዳግመኛ እንዲጀመር ብታደርግ አሜሪካ በአምንታ የምትቀበለው መሆኗን የሚገልጽ ነበር። ዚኢቭ ስቺፍ ለምሳሌ ታህሣሥ 2003 ላይ በጻፈው አስተያየት ''ከቡሽ አስተዳደር ጋር ቅርበት ያላቸው አሜሪካውያን ምንጮቹ እንደሚገልጹት እስራኤል የአሳድን የሰላም ሃሳብ ብትቀበል ዩናይትድ ስቴትስ በመርህ ደረጃ ከደማስቆ ጋር ወታደራዊ ፍጥጫ ውስጥ ለመግባት ፍላጎት የሌላት ከመሆኑም በላይ፣ አሳድ በሰላሙ ጎዳና እንዲራመዱ ለማድረግ ዝግጁ ናት" ብሏል።[78] ይህ ከሆነ ከወር በኋላ አሉፍ ቤን "ሃ-ኤሬትዝ" በተባለው ጋዜጣ ላይ ''እስራኤል የሶሪያውን ፕሬዚዳንት የአሳድን የሰላም ግብዣ ተቀብላ ድርድሩ እንዲቀጥል ከፈለገች ዩናይትድ ስቴትስ የማትቃወም መሆኗን ከፍተኛ የአሜሪካ ባለሥልጣናት ለእስራኤል አቻዎቻቸው ገልጸውላቸዋል'' በማለት ጽፏል። ቤን "ይሁን እንጂ እስራኤል በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ከሚገኙ የአስተዳደሩ

ባለሥልጣናት ከዚህ ተቃራኒ የሆነ ምክር ትቀበላለች'' ብሏል።[85] በሌላ በኩል ደግሞ እስራኤል ከሶሪያ ጋር መነጋገሯን ዋሽንግተን የምትቃወም መሆኗን የሚያሳዩ ሌሎች ሪፖርቶችም ይገኛሉ።[86] ከደማስቆ ጋር ያለውን ጉዳይ እንዴት መያዝ እንዳለበት በተመለከተ ፖሊሲ አውጭዎች በሚከተሉት የጦረኝነት አስተሳሰብ ምክንያት በቡሽ አስተዳደር ውስጥ የሚገኘው ዝቅተኛው የባለሥልጣናት ክፍል ያለውን ዝንባሌ ለመለየት ያስቸግራል።

ምንም እንኳን ቡሽ አሳድን ለማስወገድ ጠንካራ እርምጃ መውሰድ ባይፈልጉም የጦርነት ፖሊሲን እንዲከተሉ ሎቢው ይገፋፋቸው ነበር።[87] ፕሬዚዳንቱና ቁልፍ የሆኑ አማካሪዎቻቸው ሶሪያን የሚመለከቱ ንግግሮችን ሲያደርጉ፣ የተደበቁ የማስፈራሪያ ስልቶችን ማሰማት ወይም ሶሪያ የኢራቅን ሰርጎ ገቦች እንደምትረዳ እየጠቀሱ በተደጋጋሚ መውቀስን ልማድ አድርገውት ነበር። በተጨማሪም ሊባኖስ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ አንድ ዓይነት ችግር ከተፈጠረ ፈጥነው ሶሪያን ተጠያቂ ያደርጋሉ። ኒዎኮንሰርቫቲቮች በአሳድ አገዛዝ ላይ በተለይም ደግሞ በ2006ቱ የሊባኖስ ጦርነት ጊዜ ወታደራዊ እርምጃ እንዲወስድ ጥሪ ያደርጉ ነበር።[88] በሆድሰን ኢንስቲትዩት ሴንተር ፎር ሚድል ኢስት ፖሊሲ የተባለውን ድርጅት በበላይነት የሚመሩት ሜይራቭ ውርምሰር ጦርነቱ ካበቃ በኋላ በሰጡት አስተያየት፡- "በእስራኤል አንጻር በኒዎኮንሰርቫቲቮች ዘንድ ከፍተኛ ቁጣ ተቀጣጥሎ ነበር። ምክንያቱም እስራኤል ከሂዝቡላህ ይልቅ ከዋናዋ ጠላቷ ከሶሪያ ጋር ብትዋጋ ይሻል እንደነበር ብዙ የአሜሪካ አስተዳደር ክፍሎች እምነት ስለነበር ነው'' ብለዋል።[89]

ማጠቃለያ

እንዳለመታደል ሆኖ ዋሽንግተን ከሶሪያ አንጻር ትከተለው የነበረው የጦረኝነት አቀራረብ ያስገኘላት መልካም ፋይዳ የሌለ ከመሆኑም በላይ፣ የእስራኤልንም የረዥም ጊዜ ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ተገኝቷል። ከመጀመሪያው ጉዳት እንነሳና ሶሪያ ለዋሽንግተን ትሰጣት የነበረውን አል-ቃዒዳን የሚመለከቱ መረጃዎች አቋረጠች።[90] ዩናይትድ ስቴትስ ወደ ኢራቅ ይገቡ የነበሩትን ሰርጎ ገብ ኃይሎች እንድትከላከል አሳድ ያደርጉት የነበረውን እርዳታ በማቀዝቀዝ እንዲያውም በአገልባጩ ሰርጎ ገቦችን በመርዳት ራሳቸውን ከጥቃት የመከላከሉን ስልት እንዲገፉበት ተገደዱ።[91] ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅ ውስጥ በጦርነት ማጥ እንደተዘፈቀች መቆየቷ ሥራዋን ቶሎ እንዳታጠናቅቅና ፊቷን ወደ ሶሪያ እንዳታዞር የሚያደርጋት ስልት መሆኑን መጀመሪያውኑም አሳድ አላጡትም። ደማስቆ በሊባኖስ የሚገኘውን ሂዝቡላህን መርዳቷን በመቀጠሏና ከኢራን ጋር ያላትን ትብብርም በማጠናከሯ ሊባኖስ ውስጥ ሰላም እንዲሰፍን የሚደረገውን ጥረት ያወሳሰበው ከመሆኑም በላይ፣ ኢራን የኒኩሊዬር ቃታ ለመጨበጥ የምታደርገውን ጥረት ለማዳከም እንዳይቻል ሁኔታችን አስቸጋሪ አድርጓቸዋል። እንግዲህ ይህ ሁሉ የሁኔታዎች መለዋወጥ ለዩናይትድ ስቴትስ መልካም ባይሆንም፣ በሎቢው ውስጥ ያሉ ጠጣር መስመረኞች ግን የጦረኝነቱን ፖሊሲ እንድትገፋበት ነው የሚፈልጉት። ከዚያ በመለስ ለየት ያለ አቀራረብ እንዲኖር ሃሳብ በሚያቀርብ አካል ላይ ደግሞ ፈጣን የሆነ ትችት ያዥጎደጉዱበታል።

ባለፈው በጋ ወቅት (2006 ማለት ነው) እስራኤል በሊባኖስ ያጋጠማት ውድቀት እንደተጀመረ በኢራቅ ያለውንና ዩናይትድ ስቴትስ የተጋፈጠችውን ታላቅ ጥፋት ከግምት ውስጥ በማስገባት ይመስላል የሰላም ዘንባባ ለሶሪያ ይዘረጉ ዘንድ በፕሬዚዳንት ቡሽ ላይ ግፊቱ

እያየለባቸው መጥቷል።[92] ደማስቆ በኢራቅ ያለው ሁኔታ እንዲረጋጋ ለማድረግ እንዲሁም የአሜሪካ ወታደሮች በሰላም ከዚያ እንዲወጡና የተወሰነ ስርዓት እንዲሰፍን ልታግዝ ትችላለች የሚል እሳቤ ሰፍኗል። ሶሪያ ሁነኛ አጋሯ ከሆነችው ከኢራን ጋር ያላትን ግንኙነት እንድታቋርጥ በማድረግ ሂዝቡላህንም ማዳከም ይቻላል የሚል ግምት እንዲጎለብት አስችሏል። የምክር ቤቱን አፈ-ጉባዔ ናንሲፔሎሲን ጨምሮ በርካታ ሴናተሮችና የኮንግረስ አባላት የቡሽ አስተዳደርን ተቃውሞ ችላ ብለው ከፕሬዚዳንት አሳድ ጋር ለመነጋገር ወደ ሶሪያ አቀኑ። የጉዟቸው ዓላማ የኢራቅ የጋራ ጥናት ቡድን ባቀረበው ሃሳብ መሠረት በሶሪያና በአሜሪካ መካከል ያለው ግንኙነት እንዲሻሻል ለማድረግ ነው። የሁለቱ ግንኙነት መሻሻል በክልሉ ውስጥ ለተፈጠሩ በርካታ ችግሮች መልክ መያዝ ቁልፍ ሚና ይጫወታልና።

ሆኖም ግን የጎላን ከፍተኛ ቦታዎች ለሁልጊዜውም ይዘው ለመቆየት የሚፈልጉት የእስራኤል መሪዎች ዩናይትድ ስቴትስ ከሶሪያ ጋር ያላትን ግንኙነት እንድታሻሽልና በትብብር ላይ የተመሠረተ መቀራረብ እንድትፈጥር ከቶም የሚፈልጉ አልነበሩም።[93] በሎቢው ውስጥ ትልቅ ጉልበት ያላቸው ቡድኖች የእስራኤልን ሃሳብና ፍላጎት የሚጋሩ እንደመሆናቸው የቡሽ አስተዳደር ከአሳድ አገዛዝ ጋር የጀመረውን የመፈቃቀድ ፖሊሲ እንዲቀይር ለማድረግ ጠንክረው መሥራት ጀመሩ። በውጤቱም ዩናይትድ ስቴትስ ሶሪያን አስመልክቶ ከስትራቴጂያዊ እይታ አንፃር የማይረባ ፖሊሲ እንድትከተል አስገደዷት። የጎላን ከፍታችን ለሰላም ሲል ለሶሪያ በማስረከብ እስራኤልን የበለጠ ስትራቴጂያዊ መረጋጋት እንዲሰፍንባት የሚያደርግ ራቢንን የመሰለ መሪ እስኪመጣ ድረስም የሚኖረው ፖሊሲ ተመሳሳይ እንደሚሆን ይገመታል።

እዚህ ዘንዳ ያለው ታሪክ ቀላልና ያልተወሳሰበ ነው። ያለ ሎቢው ተጽዕኖ የሶሪያ አካውንቴብሊቲ ሕግ አይኖርም። ዩ.ኤስ.አሜሪካና ደማስቆም የአሜሪካን ብሔራዊ ፍላጎት መሠረት ባደረገ ሁኔታ መልካም ግንኙነትን

መሥርተው በመከባበር ይኖራሉ። ማንም ቢሆን ከዚህኛው የተለዬ ፖሊሲን ቢከተል የሶሪያንና የእስራኤልን የሰላም ስምምነት አሁንም ማምጣት ይቻላል። ይህም እውን የሚሆነው የእስራኤልን ሕጋዊነትና ክልሉ የበላይነቷን በማስጠበቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ እምቢተኛ ለሆኑት ሃማስ፣ ሂዝቡላህና ኢስላሚክ ጀሃድ ለሚባሉት ጠላቶቿ እርዳታ በመቀነስ ነው የሚል ሃሳብ ሊያራምድ ይቻላል።

አሜሪካ በሶሪያ አንፃር የምትከተለው የተንጋደደ አካሄድ የሎቢው ተጽእኖ በጉልህ የሚንጸባረቅበት፣ ውጤታማ ያልሆነና የዩናይትድ ስቴትስንም ሆነ የእስራኤልን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ የሚጎደ ብቸኛ መገለጫ አይደለም። ዩ.ኤስ. አሜሪካ በኢራን አንፃር የምትከተለውም ፖሊሲ ተመሳሳይ ታሪክ ያዘለ ስለሆነ ዝርዝሩን ቀጥሎ ባለው ምዕራፍ እንመለከተዋለን።

ምዕራፍ አስር

ኢራን ዒላማ ውስጥ ገብታለች

በ1979 የኢራን አብዮት ከተካሄደበት ጊዜና ኢራን ኢስላማዊ ሪፖብሊክ ከተባለች ጀምሮ በዩናይትድ ስቴትስና በኢራን መካከል የጠላትነት ስሜት ሰፍኖ ቆይቷል። የዩ.ኤስ. አሜሪካ ጣልቃ ገብነት በተለይ የተስተዋለው በ1953 በተደረገውና ሙሐመድ ሪዛ ሻህ ፓህላቪን ለሥልጣን ያበቃው መፈንቅለ መንግሥት በተካሄደ ጊዜ ነበር። አዲሱ የኢራን መንግሥት በአብዮቱ አማካኝነት ሥልጣን ከያዘ በኋላ በርካታ ለሆኑ ተራማጅና ለውጥ ፈላጊ ቡድኖች እርዳታ ማድረጉ ሁለቱ መንግሥታት እርስ በርሳቸው በጥርጣሬ እንዲተያዩና አልፎ አልፎ ብቻ የተወሰኑ ትብብሮችን በማድረግ እንዲወሰኑ አድርጓቸው ቆይቷል።

ኢራን ከሶሪያ ይበልጥ ለዩናይትድ ስቴትስና ለእስራኤል ከባድ ስትራቴጂያዊ ተግዳሮት የምትፈጥር መሆኗ እውነት ነው። ደማስቆና ቴህራን በጋራ ሂዝቡላህን፣ ሃማስንና ኢስላሚክ ጂሃድን የሚደግፉ ሲሆን፤ ሁለቱም የአል-ቃዒዳ ጠላቶች ናቸው። ሁለቱም ኬሚካላዊና ባዮሎጂያዊ መሣሪያዎች እንዳሏቸው ይታመናል። ምንም እንኳን የኋለኛውን በትክክለኛ ማስረጃ ማረጋገጥ ቢያስቸግርም። ሆኖም ግን በኢራንና ሶሪያ መካከል ሶስት መሠረታዊ ልዩነቶች ይስተዋላሉ፦

የመጀመሪያው ኢራን ሙሉ የኑክሌር ነዳጅን የማምረት ብቃት ለመላበስ ትሻለች። ይህ ደግሞ በፈለገች ጊዜ የኒኩሊዬር መሣሪያ ለመገንባት ያስችላታል። ከዚያም በተጨማሪ አስራኤልን ጨምሮ የአካባቢን ሀገራት ሊመታ የሚችልና የኑክሊዬር አረር የመሸከም ብቃት ያለው ሚሰዬል ገንብታለች።[1] ለዚህም ነው እስራኤል በተደጋጋሚ ኢራን ለሕልውናዋ የምታሰጋት ሀገር እንደሆነች የምትገልጸው። ኢራን በቅርብ ዓመታት የአሜሪካን ምድር በኑክሊዬር ሚሳዬል ማጥቃት የሚያስችላት አቅም

እንዳልገነባች ይታወቃል። ይሁን እንጂ በመካከለኛው ምሥራቅና አካባቢው የሠፈረን የአሜሪካ ሠራዊት ወይም የአውሮፓን ሀገራት መምታት ትችላለች።

ሁለተኛው አንዳንድ የኢራን መሪዎች በተለይም ደግሞ አሁን በሥልጣን ላይ የሚገኙት ማህሙድ አህመዲን ኤጃድ የሆሎኮስትን እልቂትና የእስራኤልን በሕልውና የመኖር መብት አስመልክተው የሚረብሹ ንግግሮችን የሚያደርጉ መሆናቸው ነው።[2] ምንም እንኳን አህመዲን ኤጃድ "እስራኤል ከጊዜ ገፆች ላይ መውደም አለባት "ወይም "ከታሪክ ገፆች ላይ መወገድ አለባት" እንደሚሉት ያሉ ንግግሮችን ቢያደርጉም፣ (እስራኤል ከካርታ ላይ መፋቅ አለባት የሚለው ንግግራቸው፣ "ሀገሪቱ እንዳለ ሙሉ በሙሉ መውደም አለባት" የሚል ትርጓሜ በስህተት ሲሰጠው ይስተዋላል። ንግግራቸው እስራኤል መውደም አለባት የሚል አንደምታ ያለው ተደርጎ መወሰድ የለበትም።) እነዚህ ሁሉ ነገሮች እስራኤላውያንንና ሌሎችንም ሰዎች የሚረብሹ ሆነው በቀጠሉበት ሁኔታ ኢራን በ2006 የሆሎኮስትን እልቂት በማስተባበል የታወቁ ዋነኛ ፖለቲከኞችንና ጽንፈኛ የሆኑ ፀረ-ጽዮናውያንን ጋበዘች። ያ ድርጊቷ በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢራን የምትከተለውን የፖለቲካ ዘይቤ ሁሉም እንዲያጠያይቅ አድርጎታል።

በሶስተኛ ደረጃ ኢራን በፋርስ ባሕረ ሰላጤ እጅግ ኃያል የሆነች ኢስላማዊ ሀገር እንደመሆኗ ያንን በነዳጅ ዘይት የበለጸገ አካባቢ በተጽእኖዋ ሥር ልታውለው የሚያስችላት አቅም አላት።[3] ይህንን እውነታ በተለይ አሜሪካ በ2003 ኢራቅን ከወረረች በኋላ በዚያ የደረሰውን በማየት ብቻ ማረጋገጥ ይቻላል። ኢራቅ በትግሉ ዋነኛዋ የኢራን ወደረኛ በመሆን ለብዙ ዘመናት የኖረች ቢሆንም፤ አሁን ግን በተለያዩ አንጃዎች የተከፋፈለችና ጦርነት ያደቀቃት ሀገር በመሆኗ ከእንግዲህ ኢራንን ልታሰጋት አትችልም። ኢራን፣ ሳዳም በሥልጣን ላይ ከነበሩበት ጊዜ ይልቅ አሁን ከዋነኞቹ የኢራቅ የሺዓ አንጃዎች ጋር ግንኙነት መመሥረት ችላለች። ይህ ተጓምራዊ የኃይል ሚዛን መቀያየር አንዳንዶች "በኢራቅ ጦርነት አሸናፊ ሆና የወጣችው ኢራን ናት" እንዲሉ አድርጓቸዋል።[4] እርግጥ ነው ኢራን

በጎረቤቶቿ ላይ ያላትን የኃይል የበላይነት ይበልጥ የምታረጋግጠው የኑክሌር መሣሪያ የተጠቃች እንደሆነ ነው።

ኢራን እያደገ የሚሄድ ፈርጣማ ኃይል ያላት መሆኗ ለዩናይትድ ስቴትስ መልካም አይደለም። ምክንያቱም አሜሪካ ከረዥም ጊዜ አንስቶ በፋርስ ባሕረ-ሰላጤ አካባቢ ማንም ሀገር ጉልበተኛ ሆኖ እንዲወጣ አትፈልግም። ይህ መሠረታዊ ደንብ ነበር በ1980ዎቹ የኢራን ኢራቅ ጦርነት ኢራን እያየለች በሄደችና ጦርነቱን የምታሸንፍ በመሰለች ጊዜ የሬገን አስተዳደር ሳዳምን እንዲረዳ የገፋፋው። ኢራን የኒክሌዬት ባለቤት እንዳትሆን ለመከላከል የሚያነሳሳት በቂ ምክንያት ዩናይትድ ስቴትስ ያላት ሆና ነው የሚሰማት። እስራኤልም በበኩሏ ኢራን የኒኩሌር ባለቤት እንድትሆን አትፈልግም። ምክንያቱም ኢራን የአካባቢው ኃያል ሀገር ሆና ከወጣች ዞሮ ዞሮ የረጅም ጊዜ የእስራኤል የስጋት ምንጭ መሆኗ ስለማይቀር ነው። ኑክሊዬር የታጠቀች ኢራን በአካባቢው መገኘቷ ለእስራኤል መሪዎች የኋላ ኋላ የሁልጊዜ የቁም ቅዠት ስለሚሆንባቸው በጣም ያስጨንቃቸዋል።

ይህን ስንል በክልሉ ከሚገኙ ሐገራት መካከል የኢራን ጉዳይ የሚያስጨንቃት እስራኤል ብቻ ናት ማለታችን አይደለም። የኢራን ጎረቤቶች የሆኑ በርካታ አረብ ሀገራት ጭምር ኢራን ኒኩሊዬር ለመታጠቅ ያላት ፍላጎትና በክልሉ እያደገ የሚሄደው ተጽዕኖዋ ያስፈራቸዋል። ኃያል የሆነች ኢራን ምናልባትም አንድ ቀን የማይፈልጉትን እንዲያደርጉ ልታስገድዳቸው፤ ሌላው ቀርቶ በ1990 ሳዳም ኩዌትን እንደወረሩት ብጤ ልትወራቸው እንደምትችል በማሰብ ይፈራሉ። ሀገራቱ በተጨማሪም በኢራን ላይ ያላቸው ጥርጣሬ እንዳይጠፋ የሚያደርጋቸው ኢራን አረባዊት ሳትሆን የፋርሶች ሀገር በመሆኗ፣ እንዲሁም በክልሉ በኢስላም የሺዓና ሱኒ ክፍፍልን ሚዛን የመጠበቁ ሂደት ጭምር ነው። ኢራን የምትተዳደረው እጅግ በሃይማኖት የተመሰጡ የሺዓ መሪዎች መሆኑ ሳውዲ አረቢያን፣ ኩዌትንና የተባበሩት አረብ ኤምሬትን የመሳሰሉት በሱኒዮች የበላይነት የሚተዳደሩ ሀገራት በአረቡ ዓለም የሺዓዎች ተጽዕኖ እያደገ መምጣት ክፉኛ ያስጨንቃቸዋል። አሁን እንደሚታየው ለመጀመሪያ ጊዜ ሺዓይቶች ኢራቅን እያስተዳደሩ ሲሆን፣ በ2006 ከተደረገው የሊባኖስ ጦርነት በኋላ

የሺዓይቶች ድርጅት የሆነው ሂዝቡላህ በሊባኖስ ተጽዕኖው ከፍ ሊል በቅቷል። ነገሮች እየከፉ እንዲመጡ የሚያደርጋቸው ሌላው ጉዳይ ቴህራን ከተወሰኑ የኢራቅ መሪዋች ጋር መቀራረብ መመስረቷና ሂዝቡላህንም ለረዥም ጊዜ እየደገፈች የምትገኝ መሆኗ ነው።

ዩናይትድ ስቴትስ፣ እስራኤልና የአሜሪካ አጋር የሆኑ ብዙዎቹ የባህረ-ሰላጤው አረብ የኢራን ጎረቤቶች እያንዳንዳቸው ኢራን የኑክሌር ባለቤትና የክልሉ ኃይል እንዳትሆን የሚፈለጉበት የየራሳቸው ፍላጎት አላቸው። ዋሽንግተን፣ እስራኤል ባትኖርም እንኳን የባሕረ-ሰላጤው መንግሥታት በቴህራን እንዳይወረሩ ወይም እንዳይዋጡ ለማድረግ ሁልጊዜም ዝግጁ ናት። ከአረቡ ዓለም የሚጎርፍላት ገደብ የሌለው ድጋፍ ዩናይትድ ስቴትስን በባሕረ-ሰላጤው ያለውን የኃይል ሚዛን እንደተጠበቀ ለማቆየት ሁኔታዎችን ቀላል ያደረገላት ከመሆኑም በላይ፣ ያንን ድጋፍ ማግኘት በራሱ ውጤታማ የሆነ ስትራቴጂን ጠይቋታል።

ዩናይትድ ስቴትስ በኢራን አካያ ብስለት የጎደለው ስትራቴጂ እንድትከተል እስራኤልና ሎቢው ግፊት ሲያደርጉባት ቆይተዋል። በተለይም ደግሞ ዛሬ በቡሽ አስተዳደርና በካፒቶል ሂል የኢራንን የኒኩሊዬ ተቋማት ለማውደም ወታደራዊ እርምጃ የመውሰድን አስፈላጊነት አስመልክቶ በሚደረጉ ንግግሮች ሁሉ ሁለቱ ኃይሎች ዋነኛ ተዋናዮች ናቸው። እንዳለመታደል ሆኖ ይህ ዓይነቱ ማስፈራራት ኢራን የጀመረችውን የኑክሊዬር ግስጋሴ እንድትገፋበት እንጂ እንድታቆመው አላደረጋትም። በ1990ዎቹ ኢራን ምንም እንኳ ከአሜሪካ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማሻሻል ፍላጎት ብታሳይም፣ በኢራን አንባር የጦረኝነት ፖሊሲ ይከተል ዘንድ የክሊንተንን አሰተዳደር እስራኤልና አሜሪካውያን ደጋፊዎቿ ያበረታቱ ነበር። ይህ አካሄድ በቡሽ የመጀመሪያዎቹ የሥልጣን ዓመታት፣ እንዲሁም ፕሬዚዳንት ቡሽ ከኢራን ጋር ስምምነት ያደርጉ ዘንድ የኢራቅ ጥናት ቡድን በታህሣሥ 2006 ሃሳብ ባቀረበ ጊዜ ጭምር ተደግሟል። የሎቢው ተጽዕኖ ባይኖር ኖሮ ዩናይትድ ስቴትስ ለዬት ያለና አስተማማኝ የሆነ የኢራን ፖሊሲ ሊኖራት በቻለ ነበር።

ዩ.ኤስ. አሜሪካ ከኢራን ጋር ለመነጋገር የምታደርገው ጥረት የበለጠ ተቀባይነት እንዲያጣ ያደረገው እስራኤል በኃይል በያዘቻቸው የፍልስጤም ግዛቶች በምታራምዳቸው ጨቋኝ ፖሊሲዎች ምክንያት የአረብ ሀገራትን

ትብብር ለማግኘት አስቸጋሪ ስላደረገባት ነው፡፡ እርግጥ ነው ኮንዶሊዛ ራይስ በ2006 የአረብ እስራኤልን የሰላም ሂደት ለማስጀመር እንዲወስኑ ያደረጋቸው ዋሽንግተን ከኢራን ጋር ያላትን ግንኙነት ከተሻለ ደረጃ ላይ ለማድረስ ከፈለገች የፍልስጤማውያንን ጉዳይ አስመልክቶ በአረብ ሀገራት ሕዝቦች ዘንድ ያለውን ቁጣ ለማብረድ አንድ ዓይነት ስምምነት ላይ መድረስ አለባት ብላ ሳዑዲ አረቢያ በመጽናቷ ነበር፡፡ ምዕራፍ 7 ላይ እንዳብራራነው የራይስ ጥረት ለስኬት አልበቃም፡፡ ምክንያቱም የእስራኤል የወቅቱ መሪዋች ራሱን የቻለ የፍልስጤም መንግሥት እንዲቋቋም ፈቃደኞች ስላልነበሩና ቡሽም ሆኑ ሌላ ማንኛውም ፕሬዚዳንት የእስራኤልን አቋም ያስለውጥ ዘንድ ሎቢው ሁኔታዎችን ቀላል ስላላደረገው ነው፡፡ በአጭሩ ለእስራኤልና አሜሪካውያን ደጋፊዎቿ ምስጋና ይድረሳቸውና ዩ.ኤስ. አሜሪካ በኢራን አካያ ከ199ዎቹ ጀምሮ ውጤታማ ያልሆነ ፖሊሲ በመከተሏ ምክንያት አሜሪካ ከኢራን ጋር የምታደርገውን ንግግር በየራሳቸው ምክንያት ለመደገፍ የተነሣሡ የአካባቢው ሀገራት ያንን ድጋፋቸውን በተግባር እንዳይገልጹት ተደርገዋል፡፡

መጋጨት ወይስ መስማማት

ዩናይትድ ስቴትስ ከ1953 ጀምሮ እርሷ የምትደግፈው የሸህ ሪዛ ፓህላቪ መንግሥት በ1979 በአያቱላህ ኹመይኒ በሚመራው እስላማዊ አብዮት እስኪገረሰስ ድረስ ከኢራን ጋር እጅግ በጣም ጥሩ የሚባል ግንኙነት ነበራት። ከአብዮቱ በኋላ ግን በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ግንኙነት ከሞላ ጎደል ሙሉ በሙሉ የጠላትነት ነው ማለት ይቻላል። እስራኤልም ብትሆን ሻሁ ከተገረሰሱ ጀምሮ ከቴህራን ጋር የጠላትነት ግንኙነት ነው ያላት። ግና በ1980ዎቹ ዩናይትድ ስቴትስም ሆነች እስራኤል ከኢራን በኩል ስጋት አጋጥሟቸው አያውቅም። ምክንያቱም ኢራን በእነዚያ ዓመታት ከኢራቅ ጋር በነበራት የተራዘመ ጦርነት የተነሣ ኃይሏ ሁሉ ተሟጦ ወደ ደካማነት አሽቆልቁላ ስለነበር ነው። የክልሉን የኃይል ሚዛን ለማስተካከል ዩናይትድ ስቴትስ በሁለቱ መካከል መግባባት ሳይፈጠር ጦርነቱ እንዲጠናቀቅ ማድረግን ነበር እንደ አማራጭ ስልት የተጠቀመችው። ይህንን ዓላማዋን ለማሳከትም የኢራንን ሠራዊት ማሰናከል ይችሉ ዘንድ ለሳዳም ሁሴን እርዳታዋን አጉርፋለች። በ1988 ጦርነቱ ሲጠናቀቅ ኢራን ክፉኛ ተዳክማ ስለነበር በመጪዎቹ ጥቂት ዓመታት በክልሉ ላይ ይህ ነው የሚባል ችግር ሳታስከትል ቆይታለች። በተጨማሪም የኢራን የኒኩሌር መርሃ-ግብርም እንዲሁ በ1980ዎቹ በጦርነቱ ምክንያት ምንም ዓይነት እድገት ሳያሳይ ነበር የቆዬው።

እስራኤል የኢራንን የኒኩሌር ኃይል ግንባታ ፍላጎት ተከትሎ በ1980ዎቹ ስጋት እያደረባት መጣ። በ1993 የእስራኤል መሪዎች ኢራን ለእስራኤል ብቻ ሳይሆን፣ ለአሜሪካም ከባድ የስጋት ምንጭ መሆኗን ጠቅሰው ዋሽንግተንን አስጠነቀቁ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሁሉም በኩል መቀዛቀዝ ታይቶ አያውቅም። ምክንያቱም ኢራን በኒኩሌር እነዛዋ እየገፋች በመሆኗ ነው። ዛሬ ብዙ የመስኩ ተጠባቢዎች እንደሚያምኑት በኢስላማዊ መሪዎች የሚተዳደረው አገዛዝ ካልተወገደ፣ ፍላጎቷን መቀየር፤ ወይም ችሎታዋን ማሰናከል ካልተቻለ በስተቀር ኢራን በመጨረሻ የኒኩሌር ባለቤት መሆኗ

አይቀሬ ነው። ሎቢው የእስራኤልን ስጋት በማራገብ ኢራን የኑኩሌር ባለቤት መሆኗ የሚያስከትለውን አደጋ እያስተጋባ ይገኛል።

እስራኤልና ሎቢው በተጨማሪም ኢራን ሂዝቡላህን በመርዳቷ፤ በፍልስጤማውያን ጉዳይ ላይ እጇን በማስገባቷና የእስራኤልን በሕልውና መኖር ለመቀበል ባለመፍቀዷ እጅጉን ተቸግረዋል። የፕሬዚዳንት አህመዲን ኤጃድ ንግግሮች ይህን ስጋት የሚያባብሱት ስለመሆኑ መግለጽ አያሻም። የኢራን ፖሊሲዎች ለአይሁድ መንግሥት ካላቸው ጥልቅ የሆነ አይዶሎጂያዊ ጥላቻ የሚመነጩ እንደሆኑ እስራኤልና ደጋፊዎቿ ቢያምኑም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ኢራን በክልሉ ላይ የሚኖራትን ተሰሚነት ከፍ ለማድረግ የምትጠቀምባቸው አጠቃላይ ስልቶች መሆናቸውን በበለጠ እርግጠኝነት ይናገራሉ። በተለይም ደግሞ ኢራን ለፍልስጤማውያን ጉዳይ ተቆርቋሪ መሆኗ (ሂዝቡላህን የመሰሉ ቡድኖችንም መርዳቷ) በዓረቡ ዓለም ከፍ ያለ ድጋፍን ያስገኘላት ከመሆኑም በላይ፣ በእርሷ አንፃር ጉድኝት የሚፈጥሩ የአረብ ሀገራት የሚያገኙት ድጋፍም ዝቅ እንዲል አድርጎታል። የኢራን የፖለቲካ ኤክስፐርት የሆኑት ትሪታ ፓርሲ በአሳማኝ ሁኔታ እንደሚገልጹት ኢራን ሂዝቡላህንና ፍልስጤማውያንን ለመርዳት ያላት እርግጠኝነት በየጊዜው እንደ አካባቢው ተጨባጭ የፖለቲካ ግለት የሚለያይና ብዙውን ጊዜ ለሚፈጠረው አጠቃላይ ስጋት አፀፋ የሚሆን ምላሽ የሚያስከትል ነው። በ1980ዎቹ በኢራን መንፈሳዊ መሪዎች በሚመራው የኢራን መንግስትና በአብዛኛው ሴኩላሪስቶች ባጥለቀለቁት የፒ.ኤል.ኦ አመራር መካከል የነበረው ግንኙነት ያን ያክል ሞቅ ያለ አልነበረም። ስለሆነም ኢራን ጠጣሩን መስመር የሚከተሉትን ኢስላሚክ ጀሃድን የመሳሰሉ የፍልስጤም አንጃዎችን መርዳት የጀመረችው በ1991 በተደረገው የማድሪድ ኮንፈረንስ እንድትገለል ከተደረገችና የኦስሎው ስምምነት ከተጀመረ በኋላ ነበር። ዩ.ኤስ. አሜሪካ ኢራንን በክልሉ ውስጥ ምንም ዓይነት ሚና እንዳትጫወት ለማድረግ የምትወስደው የማግለል ጥረት ኢራንን ስላስቆጣት አጸፋውን ለመመለስ የኦስሎውን የሰላም ስምምነት የሚቃወሙ አንጃዎችን በመርዳት ሚና መጫወት እንደምትችል ማሳዬት ጀመረች። በጊዜው የነበረውን የዩ.ኤስ. አሜሪካ ፖሊሲ የነደፈው

ማርቲን ኢንዲክ እንዲህ ይላል፡- ‘‘ኢራን እኛ በእርሷ ላይ የምናራምደውን የማግለልና በጽኑ የመቆጣጠር ፖሊሲ ለማክሸፍ በኦስሎ ስምምነት አንጻር የራሷን አፍራሽ ሚና መጫወት ቀጠለች››[5]

የኢራንን የኒኩሌር መርሃ-ግብርና በክልሉ ላይ ያላትን የመግነን ፍላጎት አስመልክቶ ሁለት ሰፊ አማራጮች ፊት ለፊት ተቀምጠዋል። አንደኛው አማራጭ የቀረበው በእስራኤልና ቁልፍ በሆኑ አሜሪካውያን ደጋፊዎቿ ሲሆን፣ ኢራን አንድ ጊዜ የኒኩሌርን ቃታ ከጨበጠች ለቁጥጥር አስቸጋሪ መሆኗ አይቀርም። መሣሪያውንም በአንድ ወቅት በእስራኤል ላይ ልትጠቀም ትችላለች። ምክንያቱም የኢራን መሪዎች ከታሪካቸው እንደምናየው የዓለምን ፍፃሜ በራዕይ እንከታተላለን የሚሉ በመሆናቸው አንድ ጊዜ ቦምቡን ካፈነዱ በኋላ ስለሚከተላቸው ብቀላ አይፈሩም።[6] እንዲሁም ምንም እንኳን ይህን ማድረጋቸው ፈጣንና የብዙ ሕዝብ እልቂትን የሚያስከትል ብቀላ የሚያመጣባቸው ቢሆንም፣ የኒኩሌዩር መሣሪያን ለአሸባሪዎች አሳልፈው ለመስጠት ወይም በራሷ በዩናይትድ ስቴትስ ላይ ለመጠቀም አያመነቱም። ስለሆነም ኢራን በምንም ዓይነት የኑክሊዬር መሣሪያ እንድትታጠቅ ሊፈቀድላት አይገባም። እስራኤል ይህንን ችግር ዋሽንግተን እንድታቃልለው ነው የምትሻው። ሆኖም ግን አሜሪካ ያንን እርምጃ ለመውሰድ የምትጎተት ከሆነ የእስራኤል መሪዎች የራሳቸውን ጦር ኃይል ተጠቅመው ችግሩን ለማስወገድ ከመሞከር አይመለሱም።

ይህ አቋም፣ የእርቅና የዲፕሎማሲ መንገድ ኢራንን የኒኩሌር መርሃ-ግብሯን እንድታቋርጥ ሊያሳምናት እንዳልቻለ ነው የሚያሳየው። ጠጠር ባለ አገላለጽ ለመጠቀም ዩናይትድ ስቴትስ በኢራን ላይ ማዕቀብ እንድትጥልና ኢራን በዚያ ጎዳና መጓዟን የምትቀጥል ከሆነም ጦር ለማዝመት እንድትገደድ ሊያደርጋት ይችላል። በኢራን ላይ ጠንከር ያለ ጫና ለመፍጠር አሜሪካ የአካባቢውን የኃይል ሚዛን ለመጠበቅ ከ1980ዎቹ በፊት ታደርገው እንደነበረው በርከት ያለ ጦሯን በክልሉ እንድታሰፍር እስራኤልና ሎቢው ይሻሉ።

ላለፉት ኣሥራ ኣምስት ዓመታት የኢራንን የኒኩሌር መርሃ-ግብር ኣስመልክቶ ኣሜሪካና እስራኤል ሲከተሉት የነበረው ይህ ስትራቴጂ ከሁለተኛውና የኣሜሪካን ብሔራዊ ጥቅም ይበልጥ የሚያረጋግጥ ከሆነው ስትራቴጂ ጋር ሲወዳደር ቆይቷል። ይህ ሁለተኛው ኣማራጭ ስትራቴጂ እንደሚያረጋግጠው ኢራን ኒኩሌዩር ባትታጠቅ ለዩናይትድ ስቴትስ የተሻለ እንደሚሆን ነው። ያ ሳይሆን ቀርቶ ኢራን የቦምቡ ባለቤት ከሆነች ደግሞ የኒኩሌዩር ባለቤቷ የቀድሞዋ ሶቪዬት ሕብረት በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት በድርድርና በመላ እንደተያዘቸው ብጤ ኢራንንም መያዝ ይቻላል።[7] በተጨማሪም የኢራንን የኒኩሌዩር ግንባታ ለማስቆም የዲፕሎማሲ መንገድና ከኣሜሪካ ጋር ያላትን ግንኙነት በማሻሻል ወደ ተለመደው (Normal) ሁኔታ ማምጣት የተሻለው ኣማራጭ ነው። በዚህ መንገድ ለመጓዝ ኢራንን በጦርነት የማስፈራራቱን ኣጀንዳ ከጠረጴዛው ላይ ማንሳት ግድ ይላል። ምክንያቱም ኢራንን ለመውረር ማስፈራራት መሪዎቿ ራሳቸውንና ሀገራቸውን ከጥቃት ለመጠበቅ የሚያስችላቸውን የኒኩሊዩር መሣሪያ የመታጠቅን ምክንያታዊነት ይበልጥ ያጠናክርላቸዋል። ኢራናውያን ልክ እንደ ኣሜሪካውያንና እስራኤላውያን ሁሉ ኣንድ ሀገር በሌላው ሀገር የጥቃት ዝርዝር ውስጥ እስከሰፈረ ድረስ የኒኩሌዩር መሣሪያ ከሁሉም በላጩ መከላከያ መሆኑን ተገንዝበዋል። የኢራን ካውንስል ኦን ፎሬይን ሪሌሽን ኤክስፐርት የሆኑት ሬይ ተቅያህ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፦ “የኢራን የኒኩሌር ስሌት የተመሠረተው እንዲሁ መሠረተቢስ ከሆነ ኣይዶሎጂ ሳይሆን ከኣመዛዛኝና ብልህ ኣስተውሎት እንደመሆኑ ሰፊ ከሆነ የመጠቃት ስጋት ራስን የመከላከል ብቃትን ለማዳበር ነው። ኢራን በግልጽ እንደሚታየው በዋሽንግተን የጥቃት ዒላማ ውስጥ ገብታለች። ስለሆነም ይህ ግንዛቤዋ የኑክሊዩር መርሃ-ግብሯን እንድታፋጥን ግፊት ፈጥሮባታል።”[8]

ወደ ግጭትና ፍጥጫ ከመግባት ይልቅ የእርቅን መንገድ መምረጡ በላጭ የሆነው ጦርነት የሚስብ ምርጫ ባለመሆኑ ነው። ዩናይትድ ስቴትስ የኢራንን የኒኩሊዩር ተቋማት ማውደሙ ቢሳካላት እንኳ ኢራን በእርግጠኝነት እንደገና የምታንጻቸው ብቻ ሳይሆን በዚያ ጊዜ ተቋማቱ የሚገኙባቸውን ቦታዎች በማራራቅ፣ ሕቡዕ በማድረግና በጠንካራ

የመከላከያ ልባስ በመሸፈን ከጥቃት የምትከላከላቸው ለመሆኑ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል።[9] ዋሽንግተን በኢራን ላይ ጥቃት ብትሰነዘር ኢራን በዩናይትድ ስቴትስ ይዞታቸው ላይ መቼምና የትም ቢሆን የብቀላ ዱላዋን ማንሳቷ የማይቀር ሲሆን፣ ይህም በፋርስ ባሕረ-ሰላጤ የሚተላለፉ የነዳጅ ጫኝ መርከቦችን በመምታትና ኢራቅ ውስጥ በሰፈረው የዩ.ኤስ. ጦር ላይም ሁኔታዎችን የበለጠ መጥፎ ለማድረግ ያላትን የተጽዕኖ አቅም ሁሉ በመጠቀም ሊገለጽ ይችላል። በተጨማሪም ኢራን ከአሜሪካ ጋር በተቃርኖ መስመር ላይ ከሚገኙት ቻይናና ሩሲያ ጋር ያላትን ዝምድና የምታጠናክር ሲሆን፤ ይህ እንዲሆን ደግሞ አሜሪካ አትፈልግም። ሆኖም ግን ከዚህ በተቃራኒ ዩናይትድ ስቴትስ ከኢራን ጋር ያላትን ፍጥጫና በጦር ኃይሏ ማስፈራራቷን ብታስወግድ በአል-ቃይዳ አንጣር የጀመረችውን ጦርነት እንድታሸንፍ በማገዝ፣ ኢራቅ ውስጥ ውጊያው እንዲቆም በማድረግና አፍጋኒስታንም ውስጥ መረጋጋት እንዲሰፍን ቴህራን የራሷን አዎንታዊ ሚና ትጫወታለች። እንዲሁም ከቻይናና ከሩሲያ ጋር የምታደርገውን ግንኙነት ትቀንሳለች።[10]

በአሜሪካና በኢራን መካከል የነበረውን የተመረዘ ግንኙነት ታሪክ ስናጤን ጦርነትና ኃይልን መጠቀም የኢራንን የኒኩሊዩር መርሃ-ግብር ያስቆማል ብሎ ዋስትና መስጠት ያስቸግራል። የእስራኤልን የኒኩሊዩር መርሃ-ግብር ለማስቆም ያለው እድል አነስተኛ መሆኑ ሲታሰብ የኢራን መሪዎች ሀገራቸው የራሷ የኒኩሊዩር መሣሪያ እንዲኖራት ቢሹ ምን ያስደንቃል! እናም የሰላሙ መንገድ ከጦርነት (ግጭት)የተሻለ በመሆኑ መሞከር ያስፈልጋል። የማይሠራ ሆኖ ከተገኘ ዩናይትድ ስቴትስ ወደ ጦርነት ለመግባት ዕድል ይኖራታል።

ዩናይትድ ስቴትስ በአሁኑ ጊዜ ከኢራን ጋር የዕርቅ ስትራቴጂ በመከተሏ ዙሪያ ልዩነቶች ይስተዋላሉ። ለዚህም እንደ ምክንያት የሚወሰደው አስራ አምስት ለሚሆኑ ዓመታት ዩ.ኤስ.አሜሪካ በኢራን ላይ የተከተለችው የፍጥጫው ስትራቴጂ ምንም ፍሬ ያላስገኘ በመሆኑ ነው። የእርቁን መንገድ መከተሉ ከሲ.አይ.ኤ.፤ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከዩ.ኤስ.ጦር ኃይል ጭምር ትልቅ ድጋፍ ያለው ከመሆኑም በላይ፣ ጦር ኃይሉ ራሱ የኢራንን

ኒኩሌዬር ተቋማት በቦምብ ለማጋዬት ያለው ፍላጎት አነስተኛ ነው። የለንደንና ሰንዴይ ታይምስ ጋዜጣ በ2007፡- “ከአሜሪካ ከፍተኛ ወታደራዊ አዛዦች የተወሰኑት ኢራን እንድትደበደብ ዋይት ሃውስ ትዕዘዝ ካስተላለፈ ሥልጣናቸውን ለመልቀቅ ዝግጁ ናቸው” በማለት ከፍተኛ የደህንነት ምንጮችን ጠቅሶ ዘግቧል።[11] ኢራን ከአሜሪካ ጋር እርቅ ለማድረግ ተደጋጋሚ ምልክቶችን አሳይታለች። መሪዎቿ ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻል ተስፋ በማድረግ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ለሰላም ጥሪ ሲያቀርቡ ቆይተዋል። ሌላው ቀርቶ ኢራን ከእስራኤል ጋር እርቅ በማድረግ በትብብር ለመኖር ስትል የኒኩሊዬር መርሃ-ግብሯን ለማቆም ጭምር እንደምትፈልግ በአስደናቂ ሁኔታ ገልጻ ነበር።

ሆኖም ግን እስራኤልና ሎቢው እነዚህ ሁሉ ተስፋ ሰጪ እድሎች ቢቀርቡላቸውም፣ ክሊንተንና ቡሽ ከኢራን ጋር የዕርቁን መንገድ እንዳይከተሉ ለማድረግ አብዝተው ነበር ሲተጉ የቆዩት። ነገር ግን በሚያሳዝን ሁኔታ ይህ ጠጣር የሆነ አቀራረብ እንደተነገረለት ውጤታማ ሊሆን ባለመቻሉ ዩናይትድ ስቴትስ የእርቁን ስትራቴጂ ብትከተል ታገኘው ከነበረው ጥቅም ማጣቱና የጦርነት ፖሊሲ በመከተሏ ምክንያት ያጋጠማት ጉዳት ከባድ ሆኗል።አሁንም ቢሆን ዩናይትድ ስቴትስ የቴህራንን ጉዳይ እንደገና እንዳታጤነውና አቀራረቧን እንዳታስተካክል ለማድረግ እስራኤልና ሎቢው ትልቅ ግብግብ ላይ ናቸው። በዚህ አካሄዳቸው በመግፋት በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ የጠበኝነትና የተጋፊነት ፖሊሲን ታራምድ ዘንድ ዩናይትድ ስቴትስን ወጥረው ይዘዋታል።

የክሊንተን አስተዳደርና ዱዋል ኮንቴይንመንት

በ1993 መጀመሪያ አካባቢ የክሊንተን አስተዳደር ገና ሥልጣን በያዘ ጊዜ የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሳቅ ራቢንና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ሺሞን ፔሬዝ ኢራን ለእስራኤልም ሆነ ለዩናይትድ ስቴትስ እያደገች የመጣች የስጋት ምንጭ መሆኗን በመግለጽ መናገር ጀመሩ። የእስራኤል መሪዎች ኢራንን አደገኛ የሆነች ጠላት አድርገው በመሳል፣ የሶቪዬት ስጋት ከተወገደ በኋላ በቴሌአቪቭና በዋሽንግተን መካከል ያለውን ግንኙነት የማነቃቂያ መንገድ አድርገው ነበር የወሰዱት። ሶቪዬት በመካከለኛው ምሥራቅ የነበራትን ተጽዕኖ ለማዳከም አሜሪካ እስራኤልን ጋሻ አድርጋ ትቆጥራት እንደነበረው ሁሉ አሁንም የኢራንን የመስፋፋት ፍላጎት ለማዳከም ጠቃሚ አጋር አድርጋ እንድትቆጥራት ለማድረግ የእስራኤል መሪዎች ብዙ ጥረዋል። ኢራን የተራቀቀ የኑክሊዬር ተቋም የመገንባት መርሃ-ግብር ያላት መሆኗ እስራኤልን ይበልጥ የሚያሳስባት መሆኑ ተገቢነት ያለው ይመስላል።[12] ዋሽንግተን ፖስት በ1993 መጋቢት አጋማሽ ላይ ባወጣው ዘገባ፡- "በእስራኤል የፖለቲካ ምህዳር ላይ የአሜሪካ የሕዝብ አስተያየትና የፖለቲካ መሪዎች የኢራንን የኑክሊዬር ኃይል ባለቤት የመሆን ፍላጎት የመግታትን አጣዳፊነትና ይህንን ተግባር ለመፈጸም የምትችል ብቸኛ ዓለም አቀፋዊ ኃይል ዩናይትድ ስቴትስ መሆኗን እንዲገነዘቡ የማድረግ ጽኑ ፍላጎት አለ" ብሏል።[13]

የክሊንተን አስተዳደር ለእስራኤል ልመና ምላሽ የሰጠው ቀደም ብለን እንዳብራራነው የዱዋል ኮንቴይንመንት ፖሊሲን ተግባራዊ በማድረግ ነው። ይህ ፖሊሲ መጀመሪያ የተጸነሰው በዋሽንግተን ኢንስቲትዩት ፎር ኒር ኢስት ፖሊሲ ዳይሬክተር በማርቲን ኢንዲክ ነበር። በጊዜው የመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳዮች ረዳት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ሮበርት ፔልትሩ ለኢራናዊቷ ፖለቲከኛ ትሪታ ፓርሲ፡- ‹‹ይህ ፖሊሲ በቀጥታ የእስራኤል ሃሳብ ቅጂ ነው›› ብለዋቸው ነበር።[14] የብሩኪንግስ ሳባ ሴንተር ባልደረባ የሆኑት ኬኔት ፓላክ፣ "ዱዋል ኮንቴይመንት ግርታ ከማይፈጥርባቸው

ጥቂት ቦታዎች መካከል እየሩሳሌም አንዲ ናት" በማለት ገልጸዋል።[15] አዲሱ ፖሊሲ ዩናይትድ ስቴትስ የቆየውንና ከባህር ማዶ ሆና የምታደርገውን የክልሉን የኃይል ሚዛን የማስጠበቅ ስትራቴጂ ትታ በኩዌትና ሳዑዲ በርከት ያሉ ወታደሮችን በማስፈር ኢራንንና ኢራቅን እንድትቆጣጠር ይጠይቃል። በእርግጥም ፖሊሲው አሜሪካ ኢራንን ለመቆጣጠር የበለጠ ትኩረት እንድታደርግ የተነደፈ ሲሆን የኢራንን ጠባይ በአስደናቂ ሁኔታ ለመቀየርም ያለመ ነው። ፖሊሲው ካስቀመጣቸው ግቦች መካከል ኢራን ለሽብርተኞች የምታደርገውን ድጋፍ እንድታቆምና የኒኩሊዬር መርሃ-ግብሯንም እንድትተው ማስገደድ የሚሉትም ይገኙበታል።[16]

የእስራኤል አቋም ይህን ቢመስልም እንኳ ዩናይትድ ስቴትስ ኢራንን አስመልክቶ በ1990ዎቹ ጠጣሩን የፖሊሲ መስመር እንድትከተል የሚያደርጋት በቂ ምክንያት አልነበራትም ማለት ይቻላል። የግድ ከሆነም ተቃራኒውን መስመር ነው መከተል የነበረባት። በ1989 የኢራን ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት ዓሊ አክባር ሃሺሚ ራፍሳንጂኒ ከዋሽንግተን ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻል ዝግጁ የነበሩ ሲሆን፣ ከእርሳቸው በፊት በነበሩት ተከታታይ ስምንት ዓመታት ኢራን ከኢራቅ ጋር ባደረገችው ያላቋረጠ ውጊያ ክፉኛ ተዳቅቃ የነበረች በመሆኗ በዩናይትድ ስቴትስ ላይ ወታደራዊ ስጋት ለመደቀን የሚያስችል አቅም አልነበራትም። በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ የአሜሪካ መሪዎች ትኩረታቸውን በሳዳም ሁሴን ላይ በማድረግ ውጊያ የገጠሙ መሆኑ ይታወቃል።[17] በተጨማሪም የኢራን የኒኩሊዬር መርሃ-ግብር በ1993 ገና መሠረቱ እየተጣለ ነበር ማለት ይቻላል። እስራኤል በኢራን ላይ የፍጥጫው ፖሊሲ እንዲተገበር መጮህ ከመጀመሯ በፊት ጥቂት ሰዎች ዋሽንግተን በኢራን አንፃር ጠንከር ያለ እርምጃ እንድትወስድ ሲያሳስቡ የቆዩ መሆኑ እውነት ነው። ዱዋል ኮንቴይትመንት የተሰኘው የቁጥጥር ስልትም በስፋት ትችት ይወርድበት የጀመረው ገና ይፋ እንደተደረገ ነበር፡[18]

በ1990ዎቹ አጋማሽ አካባቢ ዱዋል ኮንቴይንመንት በተባለው የቁጥጥር ስልት ላይ እርካታ ማጣት እያደገ ሄደ። ምክንያቱም ዩናይትድ ስቴትስ

እርስ በርስ በሚናቆሩ ሀገራት መካከል የጠበኝነት ግንኙነት እንዲቀጥልና ሁለቱም ከመስመር እንዳይወጡ ለማድረግ ብዙ ጥረትና ውጣ ውረድ ስለሚጠይቃት ነው። በመሆኑም ኢራንን በፍጥጫ ከመያዝ ይልቅ በእርቅ መንገድ የማቅረብን ስልት እንድታስብበት ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ግፊቱ እየተጠናከረ መጣ።[19] በተመሳሳይ ጊዜ የክሊንተን አስተዳደር በኢራን ላይ ፖሊሲውን ያጠነክር ዘንድ ግፊት እንዲያደርጉ ራቢን እስራኤል ውስጥ ተዕእኖው አይሎባቸው ነበር።[20] በራቢን ተችዎች አስተሳሰብ መሠረት ዱዋል ኮንቴይመንት እውነተኛ ጥርስ የለውም። ምክንያቱም በአሜሪካና በኢራን መካከል የሚደረገውን ከፍ ያለ የንግድ ልውውጥ ለማስቆም ያደረገው አስተዋጽኦ ኢምንት ነው። እስራኤልና ሎቢው፣ በተለይም ደግሞ አይፓክ፣ ዱዋል ኮንቴይንመንት ሥራ ላይ እንዳይውል፣ የአሜሪካ ኩባንያዎች ከኢራን ጋር የንግድ ሥራ እንዳይሠሩና መዋዕለ ንዋያቸውንም እንዳያፈሱ ለማድረግ መውጫ ቀዳዳውን ሁሉ ለመድፈን ተንቀሳቀሱ። በ1994 አጋማሽ ላይ ኢራናዊቷ ፖለቲከኛ ፖርሲ ባቀረቡት ዘገባ፡- "የእስራኤል መንግሥት ባደረገው የማግባባት ጥረት አይፓክ 74 ገጽ የሚሆን ጽሑፍ አርቅቆ በዋሽንግተን አካባቢ በማሰራጨት ኢራን ለእስራኤል ብቻ ሳይሆን ለዩናይትድ ስቴትስና ለምዕራቡ ዓለም ጭምር እጅግ አደገኛ የሆነች ሀገር ናት በማለት ቅስቀሳ አካሂዷል" ብለዋል።[21] እንደ ፓላክ አባባል ከሆነ ደግሞ "የቀኝ ክንፉ ፓርቲ፣ አይፓክና እስራኤላውያን በኢራን ላይ አዲስ ማዕቀብ እንዲጣል በመጠየቅ ጩኸታቸውን አሰምተዋል"።[22] የክሊንተን አስተዳደርም ቢሆን በአብዛኛው የኦስሎን ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግና የእስራኤልም ደህንነት የተረጋገጠ እንዲሆን ለማስቻል፣ እንዲሁም ኢራን ሂደቱን እንዳታስተጓጉለው ነበር ትኩረት አድርጎ ሲንቀሳቀስ የቆየው።

አይፓክ ሚያዚያ 1995 ላይ ወሳኝ የሆነውን የፖለቲካ ጨዋታውን የጀመረው፡- "አጠቃላይ የሆኑና ዩ.ኤስ.ኤሜሪካ በኢራን ላይ የምትጥላቸው ማዕቀቦች የድርጊት መርሃ-ግብር" በሚል ርዕስ ያዘጋጀውን ዘገባ በለቀቀ ጊዜ ነው።[23] በዚያ ሰዓት በኢራን አንገት ዙሪያ የኢኮኖሚው ሽምቀቆ እንዲጠብቅባት የሚያደርጉ ጠንካራ እርምጃዎች እየተወሰዱ ነበር። እንደ

ፓላክ አገላለጽ የኒውዮርኩ ዲሞክራት ሴናተር አልፎንሴ ደ አማቶ፣ ‹‹ከእስራኤላውያን ባገኙት የተወሰነ ድጋፍ እየታገዙ ጥር/1995 በዩናይትድ ስቴትስና በኢራን መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ግንኙነት ለማብቃት የሚያስችል ረቂቅ ሕግ ለምክር ቤቱ አቀረቡ፡፡"[24] የክሊንተን አስተዳደር ረቂቅ ሕጉን መጀመሪያ ላይ የተቃወመው ሲሆን፣ በምክር ቤቱ ውስጥ እንደተንጠለጠለ ዛሬ ነገ ሲባል ቆዬ፡፡

ነገር ግን ከሁለት ወራት በኋላ ኢራን የሲሪን የነዳጅ ጉድጓዶች እንዲያለማላት ኮኖኮ የተባለውን የአሜሪካውን የነዳጅ ኩባንያ በመረጠች ጊዜ በሎቢው ውስጥ ያሉ ቡድኖች የመጀመሪያውን ስኬት ተቀዳጁ፡፡[25] ኢራን በርካታ ከሆኑ የሌሎች ሀገራት የነዳጅ ኩባንያዎች ኮኖኮን ሆነ ብላ የመረጠችበት ምክንያት ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማሻሻል ፍላጎት ያላት መሆኑን ለማሳዬት ነበር፡፡ ሆኖም ግን ይህ ጥረቷ የትም አልደረሰም፡፡ ምክንያቱም ክሊንተን መጋቢት 14 ቀን ማለትም ኢራን ኮኖኮን ከመረጠችበት ዕለት አንድ ቀን ዘግይተው ውሉን ውድቅ ማድረጋቸውን ገልፀው፣ የአሜሪካ ኩባንያዎች የኢራንን የነዳጅ ጉድጓዶች በማልማቱ ሥራ እንዳይሳተፉ የሚያግድ ትዕዘዝ በማስተላለፋቸው ነው፡፡ ክሊንተን ዘግይተው እንደተናገሩት፡-- ‘‘የኮኖኮን ውል ወድቅ እንዳደርግ ትልቁን ሚና የተጫወቱት የስምምነቱ ጠላት የዓለም አይሁዳውያን ኮንግረስ የቀድሞ ፕሬዚዳንት ኤድጋር ብሮንፍማን ሲኒዬር ናቸው፡፡ አይፓክም ቢሆን ስምምነቱ እንዲቋረጥ የበኩሉን ሚና ተጫውቷል" ብለዋል፡፡[26]

ግንቦት 6 ቀን ፕሬዚዳንቱ ከኢራን ጋር የሚደረጉ የንግድና የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ስምምነቶችን በሙሉ፣ ‘‘የዩናይትድ ስቴትስን ብሔራዊ ደህንነት፣ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ኢኮኖሚ የሚጎዱና ያልተለመዱ ስጋቶችን የሚደቅኑ ናቸው" የሚል ምክንያት ሰጥተው አገዱ፡፡[28] ክሊንተን እነዚህን እርምጃዎች የወሰዱት በዓለም አይሁዳውያን ኮንግረስ ላይ ንግግር ከማሰማታቸው አንድ ሳምንት ቀደም ብለው ነበር፡፡[29] ክሊንተን የኮኖኮ ስምምነት እንዲፈርስ የወሰዱት እርምጃና ሁለቱን ሕጎች ተግባራዊ ለማድረግ ያወጡት ደንብ ‘‘ ለእስራኤል ያለንን ድጋፍ የምናሳይበት መገለጫዎች ናቸው" በማለት ፓላክ ተናግረዋል፡፡[30] ምፀት በሚመስል

ሁኔታ ምንም እንኳን አሜሪካ ከኢራን ጋር ያላትን የንግድና ገንዘብ ነክ ግንኙነት በሙሉ እንድታቋርጥ ጫና ስታደርግ የቆዬችው እስራኤል ብትሆንም፣ ራሷ ግን ከኢራን ጋር የነበራትን የንግድ ትስስሮሽ እንደነበር እንዲቆይ በማድረግ በሶስተኛ ወገኖች (ኩባንያዎች) በኩል የኢራንን ሽቀጦች መግዛቷን ቀጠለች።[31]

ይሁን እንጂ እነዚያ በኢራን ላይ የተወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሎቢውን ሊያረኩት አልቻሉም። ምክንያቱም አስተዳደራዊ ትዕዛዞች ክሊንተን ሃሳባቸውን በቀየሩ ጊዜ በቀላሉ ሊቀለበሱ የሚችሉ በመሆናቸው ነው። ኤ.ኤም.ሮዜንታል የተባሉ የእስራኤል ጠንካራ ደጋፊ የኮኖኮን ስምምነት መፍረስ ተችተው በኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ላይ ባወጡት ጽሑፍ ሲገልጹ፡- "የአስተዳደራዊ ትዕዛዙ ደካማ ጎን ትዕዛዙን የሰጡት ፕሬዚዳንት በፈለጉ ጊዜ ሊሸሩት የሚችሉ መሆናቸው ነው" ብለዋል።[32] ለዚህ የመጨረው ጊዜ ችግር መፍትሄ ይሆን ዘንድ፣ ትሪ ፓሪሲ እንደዘገቡት፡- "አይፓክ በራሱ አነሳሽነት ሴናተር ደ" አማቶ በ1995 ለምክር ቤቱ አቅርበውት የነበረውን ረቂቅ ሕግ እንደገና በመከለስ የኒውዮርኩ ሴናተር በ1996 መልሰው ለምክር ቤቱ እንዲያቀርቡት አግባባቸው" ብለዋል።[33] አዲሱ ረቂቅ በመጨረሻም 'የኢራን ሊቢያ ማዕቀፍ ሕግ' ተብሎ የፀደቀ ሲሆን፣ በሁለቱ ሀገራት ውስጥ የነዳጅ ጉድጓዶችን ለማሰፋፋት የሚፈልጉ ኩባንያዎች ከ40 ሚሊዮን ዶላር በላይ መዋዕለ ንዋይ እንዳያፈስሱ ያግዳል። ምንም እንኳን ይህ ሕግ አውሮፓውያን የአሜሪካ ወዳጆችን ቢያናድድም፣ የተወካዮቹ ምክር ቤት ሰኔ 19/1996 እንዲሁም ሴኔቱ ከአንድ ወር በኋላ በሙሉ ድምጽ ያሳለፈው በመሆኑ ሕጉን የሚቃወሙ ሰዎች በመላው የክሊንተን አስተዳደር ውስጥ በርካታ ቢሆኑም፣ ክሊንተን ነሐሴ 5 ቀን ፊርማቸውን አኑረውበታል። እርግጥ ነው ኬኔት ፓላክ እንደ ጻፉት፡- "የሕግ አስፈጻሚው አካል በርካታ ክፍሎች የዳ› አማቶን ሕግ ይጠሉታል" እውነቱን ለመናገር ‹‹ጥላቻ›› የሚለው ቃል ለዘብ ያለ አገላለጽ ነው። ይሁን እንጂ በርካታ የሆኑ የፕሬዚዳንት ክሊንተን የሀገር ውስጥ ፖሊሲ አማካሪዎች እንዳሳሰቡት ያንን ሕግ ዋይት ሃውስ አልቀበልም ቢል ፍፁም የጅልነት አካሄድ ይሆንበት ነበር።[34]

ክሊንተን በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ለድጋሚ ምርጫ የሚቀርቡ መሆናቸው እግምት ውስጥ ሲገባ የአማካሪዎቹ አባባል ምናልባትም ትክክል ነበር፡፡ የሃ-ኤሬትዝ ጋዜጣ ወታደራዊ ጉዳዮች ዘጋቢ የሆነው ዝኢቭ ስቺፍ በጊዜው "እስራኤል በትልቁ እቅድ ውስጥ ያለች ትንሽ ነገር ናት፡፡ ሆኖም ግን ማንም ቢሆን በፖለቲካው ሂደት ውስጥ ባሉ አካላት ላይ ተጽዕኖ ማሳደር አትችልም ከሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ አይኖርበትም" ብሏል፡፡[35] በተመሳሳይ ሁኔታ በተለያዩ የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች የአስተዳደር ዘመናት በበርካታ የሥልጠን ቦታዋች ላይ የሠሩት ጀምስ ስክሊሲንገር ማዕቀቡ በተጣለ ሰሞን እንዲህ ብለዋል፡- "የእስራኤል ደጋፊዎች በመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲዎቻችን ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ አጋንኖ መመልከት አሁን ባለው አሠራር እምብዛም የሚቻል አይደለም፡፡"[36]

የኮኖኮ ገጠመኝ በተደጋጋሚ ሲነገር የነበረውንና በመካከለኛው ምሥራቅ ፖለቲካ ላይ ‹‹የነዳጅ ዘይት ሎቢ ስውር እጆች አሉ›› የሚለውን አባባል ጥርጣሬ ላይ ጣለው፡፡ ምክንያቱም በዚያ ጊዜ የአሜሪካው የነዳጅ ኩባንያ (ኮኖኮ) ከኢራን መንግሥት ጋር መሥራት ፈለጉ፡፡ ኢራንም ከኩባንያው ጋር ትርፋማ ስለሆነ ንግድ በግልጽ ለመነጋገር ፈቀደች፡፡ ስለሆነም የነዳጁ ኢንዱስትሪ የኮኖኮ ስምምነት መታጠፉን እንደተቃወመ ሁሉ በኢራን ላይ የተደረገውንም ማዕቀብ እንዲሁ ተቃውሟል፡፡[37] ምዕራፍ 4 ላይ እንደገለጽነው ዛሬ ዋነኛ የኢራን ተቃዋሚ ሆነው ብቅ ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንት ዲክ ቼኒ የታወቀው የነዳጅ ኩባንያ ሃሊበርተን ፕሬዚዳንት በነበሩ ጊዜ ዩ.ኤስ. አሜሪካ በ1990ዎቹ በኢራን ላይ የወሰደችውን የማዕቀብ እርምጃ በግልጽ ተቃውመው ነበር፡፡ ዳሩ ግን የነዳጅ ዘይት ፍላጎት በእያንዳንዱ የአይፓክ ወሳኔ ጫና ያርፍበታል፡፡ የዚህ ውጤት የኋላ ኋላ እንደታየው የነዳጅ ኩባንያዋች በዩ.ኤስ.አሜሪካ የመካከለኛ ምሥራቅ ፖሊሲ ላይ ከእስራኤል ሎቢ ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ የሆነ ተጽዕኖ ብቻ እንዲኖራቸው አስችሏል፡፡

ኢራንን አስመልክቶ አሜሪካውያን የሚከተሉት አቋም አንድ ዓይነት የዕርቅ አጋጣሚ ብልጭ በሚልባቸው ጊዜያት ሁሉ አጋጣሚውን በማዳፈን ጠጣሩን መስመር በመከተሉ ሂደት ቀጠለ፡፡ ግንቦት 23/1997 መሐመድ

ካታሚ የኢራን ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡበት ጊዜ ነበር። ካታሚ ከቀደሟቸው ፕሬዚዳንት (አሊ አክባር ሃሺሚ ራፍሳንጃኒ) በበለጠ ከምዕራቡ ዓለምና በተለይም ደግሞ ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር ግንኙነታቸውን ለማሻሻል ተነሳሽነት ነበራቸው። ነሐሴ 4/1997 በዓለ ሲመታቸው በተከበረ ጊዜ ባደረጉት ንግግር፣ እንዲሁም ታህሣሥ 14 በሰጡት የመጀመሪያ ጋዜጣዊ መግለጫ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ጥር 7 ቀን ለሲ.ኤን.ኤን ቴሌቪዥን በሰጡት ቃለ ምልልስ፡- "ለታላቁ የአሜሪካ ሕዝብና ታላቅ ለሆነው ሥልጣኔው" ያላቸውን አክብሮት ገልጸዋል። ካታሚ በተጨማሪም "ኢራን የአሜሪካን መንግሥት ይዞታዎች የማውደም ወይም ለአሜሪካ ጠንቅ የመሆን ዓላማ የላትም" ብለዋል። ኢራንን አስቀያሚ ገጽታ አላብሷት የነበረውን የ1979 የዩ.ኤስ.ኤምባሲ ወረራ ክስተት አስመልክተውም ያደረባቸውን ፀፀት ገልጸዋል። በቴህራንና በዋሽንግተን መካከል ያለውን የጠላትነት ስሜት አስመልክተው ሲናገሩም፣ "ያለመተማመኑን ግድግዳ ሰብረን አዲስ ግንኙነት የምንመሠርትበትን ዕድል መፍጠር አለብን›› ብለዋል።[38]

በተጨማሪም ካታሚ በታሪካዊቷ የፍልስጤም ምድር ላይ የእስራኤል መንግሥት መመሥረቱን እንደማይደግፉ ሲገለጹ፣ "ሽብርተኝነት በሁሉም መልኩና መገለጫዎቹ መወገዝ አለበት" አሉ። ካታሚ በእስራኤላውያን ላይ የሚደርሰውን የሽብርተኝነት ጥቃትም እንዲሁ እንደሚያወግዙ ከተናገሩ በኋላ፣ "ለነፃነታቸው የሚዋጉ ሕዝቦችን መርዳት በእኔ እምነት ሽብርተኞችን መርዳት አይደለም' በማለት ሃሳባቸውን አጠቃለዋል። ይህ የካታሚ ንግግር የኢራንን ከአቋሟ ማፈግፈግ የሚገልጽ ምልክት እንደሆነ ተቆጥሯል። እንዲሁም ሌላ የኢራን ቃል አቀባይ እስራኤል ከፍልስጤማውያን ጋር ስምምነት እስከፈጠረች ድረስ ኢራን እውቅና እንደምትሰጣት በመግለጽ የመንግሥታቸውን አቋም አንጸባርቀዋል።[39]

የካታሚ የአስታራቂነት መንፈስ የታየበት ንግግር በተሰማ ሰሞን የክሊንተን አስተዳደር ከእስራኤልና በኮንግረስ ውስጥ ከሚገኙ አካላት ጋር ከተነጋገረ በኋላ በኢራንና በዩናይትድ ስቴትስ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል የሚያግዙ በርካታ እርምጃዎችን ወሰደ።[40] ክሊንተንና የውጭ ጉዳይ

ሚኒስትሯ ሚድሊን ኦልብራይት ለኻታሚ ንግግር አጸፋዊ ምላሽ ይሆን ዘንድ የምዕራቡን ዓለም ያለፈ ጊዜ ባህሪ ከገለጹ በኋላ ዩናይትድ ስቴትስ ወደ ቴህራን ለሚጓዙ ወይም ከዚያ ለሚመጡ መንገደኞች የቪዛ እቀባዎችን እንደምታላላ አስታወቁ፡፡ የዱዋል ኮንቴይንትመንት መሐንዲስ የነበረውና አሁን ደግሞ በእስራኤል የዩ.ኤስ.አሜሪካ አምባሳደር ሆኖ የተሾመው ማርቲን ኢንዲክ እንኳ ለሪፖርተሮች በሰጠው አስተያየት ‹‹ዩናይትድ ስቴትስ በተደጋጋሚ ግልጽ እንዳደረገችው በኢስላማዊት ሪፖብሊክ ኢራን ላይ ምንም ዓይነት ተቃውሞ (ጥላቻ) የለንም፡፡ ለውይይትም ዝግጁዎች ነን›› አለ፡፡[41] ኢንዲክ እንደዚያ ይበል እንጂ የንግድ ማዕቀቡ የፀና ሆኖ ከመቆየቱም በላይ፣ ‘ዱዋል ኮንቲይንምንት’ የተሰኘው አንድን ሀገር በዓይነ ቁራኛ የመጠባበቅ ስልት የክሊንተን ሁለተኛ ዘመነ ስልጣን እስኪገባደድ ደረስ ሲሠራበት ቆይቷል፡፡ ይህ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ለመቀየር ያለመቻል ችግር በከፊል ሳይሳካ የቀረው ኢራን ውስጥ ባሉ ጠጣር መስመረኞች ተጽዕኖ ሲሆን እንደነርሱ አባባል “ከታላቁ ሠይጣን” ጋር ለመደራደር ኻታሚ የነደፉትን ዕቅድ በጽናት በመቃወማቸው ምክንያት ነበር፡፡[42] ይሁን እንጂ በሌላ በኩል ደግሞ እስራኤልና ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚገኙ ደገፊዎቿ የአሜሪካ-ኢራን ግንኙነት የመሻሻል ተስፋ እንዳይኖረው በማድረግ የራሳቸውን ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል፡፡

ኻታሚ በ1997 ወደ መንበረ ሥልጣን ከመምጣታቸው በፊት ሎቢው በኢራን አንዣር ‘ዱዋል ኮንቴይንመንት’ የተባለውን መርህ በስፋት ተግባራዊ በማድረግ ተጠያቂነትን ይወስዳል፡፡ ያ ፖሊሲ እንደ እውነቱ ከሆነ በቴህራንና በዋሽንግተን መካከል ያለውን ግንኙነት በመመረዝ በዚያኛው ጫፍ (በኢራን) ፖለቲካ ላይ አዲስ የለዘበተኝነት ሀሳብ ይዘው የመጡትን ፕሬዚዳንት የሚቃወሙ ኃይሎች ጥንካሬ እንዲላበሱ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም በታኅሣሥ አጋማሽ 1997 ላይ ኻታሚ ከአሜሪካ ጋር ያላቸው ግንኙነት ይሻሻል ዘንድ ጥሪ ባቀረቡ ጊዜ የእስራኤል መሪዎች ይህን የእርሳቸውን መነቃቃት ውድቅ ለማድረግ የቀደማቸው አልነበረም፡፡ ሃ-ኤሬቲዝ ጋዜጣ ባወጣው ዘገባ “ዋሽንግተን ከኢራን ጋር ያላትን ግንኙነት በተመለከተ የፖሊሲ ለውጥ ልታደርግ የመሆኗ ነገር ያሳደረባትን ስጋት

እስራኤል ለዩናይትድ ስቴትስ ገልጻለች'' ካለ በኋላ ጨምሮ ሲገልጽ፡- "ጠቅላይ ሚኒስትር ናታንያሁ በኮንግረሱ ውስጥ ይህን የመሰለውን ፖሊሲ በኃይል እንዲከላከል አይፓክን ጠይቀዋል" ብሏል፡፡[43]

ናታንያሁ የነገሩትን አይፓክ ፈጽሟል፡፡ በኢራን ጉዳይ ግንባር ቀደም ጠቢብ ከሆኑት አሜሪካውያን አንዱ የሆኑት ጋሪ ሲክ እንዲህ ብለዋል፡- ''ቀስ እያለ መሻሻል ያሳዬው የአይፓክና የኢራን ግንኙነት ኻታሚ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ በአይፓክ. አቋም ላይ አልተንጸባረቀም፡፡ እውነት ነው፤ በ1999 መጀመሪያ አካባቢ አይፓክና በስደት የሚገኘው የኢራን ንጉሣውያን ቤተሰብ፣ እንዲሁም አሸባሪው ሙጃሂዲን-ኸልቅ በኢራን አንፃር የሚደረገው ለውጥ አነስተኛ እንዲሆን ወይም ጭራሽ ምንም ዓይነት ለውጥ እንዳይኖር ባለማቋረጥ ነበር የተንቀሳቀሱት"[44] በጸደይ ወራት 2000 ላይ ክሊንተን የተወሰኑ መድሃኒቶችና የምግብ አቅርቦቶች ወደ ኢራን እንዲሄዱ ቢፈቅዱ ተቀባይነት እንደሚኖራቸው በአሜሪካ የእስራኤሉ አምባሳደር ቢገልጹም፣ አይፓክ ግን ከዚያ ተቃራኒ ነበር የቆመው፡፡ እርግጥ ነው አይፓክ ከኢራን በሚገቡ ካቪያር (ውድ የሆነ ከአሣ እንቁላል የሚገኝ ምግብ) ፣ በፋርስ ምንጣፍና ለምግብነት በሚውሉ ፒስታቺዎስ የሚባሉ ፍሬዎች ላይ እገዳው እንዲነሳ መደረጉን አይቃወምም፡፡ ይሁን እንጂ የፀረ ስም ማጥፋት ሊግ (አይ.ዲ.ኤል) እና የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረስ የተባሉ የሎቢ ድርጅቶች ይህንን ተቃውመዋል፡፡[45] ክሊንተን በሁሉም በኩል ያለውን ሁኔታ ካመዛዘኑ በኋላ የራሳቸውን መንገድ አበጁ፡፡ ምክንያቱም ከኢራን ወደ አሜሪካ የሚገቡት እነዚህ ሸቀጦች አነስተኛ መጠን ያላቸውና ብዙም የማያወዛግቡ በመሆናቸው ነው፡፡ ሆኖም ግን ኻታሚ የዘረጉላትን የእርቀ ሰላም እጅ ለመጨበጥ ዩናይትድ ስቴትስ በቂ ጥረት ሳታደርግ ቀረች፡፡

ዩናይትድ ስቴትስ በ1990ዎቹ ከኢራን ጋር ያላትን ግንኙነት ለማደስ ጥረት አድርጋ ቢሆን ኖሮ ማለፊያ በሆነ ነበር፡፡ "ዱዋል ኮንቲይንመንት›› ይላሉ ብረንት ስኮውክሮፍት፡- ‹‹የማይረባ ሀሳብ ነበር፡፡"[46] ቢሆንም ፕሬዚዳንት ክሊንተን ከኢራን ጋር የሰላሙን መንገድ እንዳይከተሉ የእስራኤል መሪዎች ይከላከሉ ነበር፡፡ ይህን ያደርጉ የነበረው የእስራኤልን ፍላጎት ለመጠበቅ ሲሆን፣ ያ ተጋፊ የሆነ ፖሊሲያቸው የአሜሪካን ብሔራዊ ጥቅም

የማያስከብር እንደሆነ ግን አጥተውት አልነበረም። በኢራን አንፃር ከቆሙና ዋነኛ የጦረኝነት ፖሊሲ አራማጆች ከሆኑት እስራኤላውያን መካከል አንዱ የሆኑት ኤፍሬም ሴነህ ጉዳዩን እንዲህ በማለት እጥር ምጥን ባለ አገላለጽ አስቀምጠውታል፡- ‹‹የዩናይትድስቴትስንና የኢራንን የሰላም ድርድር እንቃወማለን። ...ምክንያቱም የዩ.ኤስ ፍላጎት ከኛ ጋር አብሮ ስለማይሄድ ነው።"[47] ስለሆነም ሎቢው እስራኤልን ተከትሎ መንጎዱን ቀጥሏል።

የቡሽ አስተዳደርና የኢራንን አገዛዝ የመለወጥ ሃሳብ

ምዕራፍ 8 ላይ እንዳብራራነው የመስከረም 11ዱ ጥቃት ከደረሰ በኋላ ፕሬዚዳንት ቡሽ ዱዋል ኮንቲይመንት የተሰኘውን መርህ በመተው በክልሉ ዲሚክራሲያዊ ሽግግር ለማምጣት ያለመ ስትራቴጂን ለመከተል ወሰኑ። የአሜሪካ ጦር አሁን በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የሚገኙ ጠላቶቹን አንድ በአንድ ለመገንደስ ዝግጁ ሆኖ እየተጠባበቀ ይገኛል። በእስራኤል ምልከታ ቡሽ ሊደበድቧቸው በዝርዝር ከያዟቸው ሀገራት መካከል ቅድሚያ ልታገኝ የሚገባት ኢራን ነበረች። ከ1990ዎቹ ጀምሮ የእስራኤል መሪዎች ኢራንን እጅግ አደገኛ ጠላታቸው አድርገው ሲስሏት ቆይተዋል። ምክንያቱም የኒኩሊዩር መሣሪያ ለመታጠቅ ፍላጎት ያላት በመሆኑ ነው። የእስራኤሉ መከላከያ ሚኒስትር ቢንያሚን ቤን-ኤሊዘር ከኢራቅ ጦርነት አንድ ዓመት ቀደም ብሎ እንዲህ ብለው ነበር፡- ‘‘ኢራቅ የችግር ምንጭ ናት። ... ሆኖም ግን ከሁሉ የከፋችው አደገኛ ሀገር ማን ናት? ብላችሁ ብትጠይቁኝ ከኢራቅ ይልቅ ኢራን ናት እላችኋለሁ።”[48]

ዳሩ ግን ሻሮንና የጦር ጄኔራሎቻቸው የፊለጉት በ2002 ዩናይትድ ስቴትስ መጀመሪያ የኢራቅን አገዛዘ ከገነደሰ በኋላ ፊቱን ወደ ኢራን እንዲያዞር ነበር። ስለሆነም የቡሽ አስተዳደር ባስቀመጠው ቅደም ተከተል ላይ የከረረ ተቃውሞ አላስነሱም። የባግዳድ ጉዳይ እንደተጠናቀቀ ኢራን ቀጣይ መሆኗ ብቻ ለእነርሱ በቂያቸው ነበር። ሻሮን ከለንደን ታይምስ ጋዜጣ ጋር በህዳር 2002 ባደረጉት ቃለ ምልልስ ዩናይትድ ስቴትስ ኢራንን እንድትወር በግልጽ ነበር የጠየቁት።[49] ‹‹ኢራን የዓለም አቀፍ ሽብርተኝነት ማዕከል ናት”

በማለት ከተናገሩ በኋላ "የኒኩሊዬር መሣሪያ ለመታጠቅ የምታደርው ጥረትም አደገኛ በመሆኑ የቡሽ አስተዳደር ኢራቅን ካንበረከከ በኋላ በኢራንም ላይ ጠንካር ክንዱን ማሳረፍ አለበት" ሲሉ ሀሳባቸውን ቋጭተዋል፡፡

2003 ማብቂያ አካባቢ ባግድድ በአሜሪካኖች እጅ ከወደቀች በኋላ በዋሽንግተን የእስራኤል አምባሳደር በኢራን የአገዛዝ ለውጥ እንዲደረግ ጥሪ ማድረግ ጀመሩ፡፡ "የሳዳም መውደቅ ብቻውን በቂ አይደለም" ሲሉም ተደመጡ፡፡ ''አሁንም ቢሆን ከሶሪያ እንዲሁም ከኢራን በኩል ታላቅ የሆነ ስጋት ተደቅኖብናል'' አሉም፡፡[50] ይህ ከሆነ ከአስር ቀናት በኋላ ኒውዮርክ ታይምስ ባወጣው ዘገባ፡- ''የኢራን ኒኩሊዬር የመታጠቅ ፍላጎት ዋሽንግተንን ይበልጥ እያሳሰባት ሄዷል፡፡ ይህን ጉዳይ ይበልጥ ትኩረት እንድንሰጠውም ከእስራኤላውያን በኩል ጫናው እያየለብን መጥቷል" ሲል ገልጿል፡፡[51] ሽሞን ፔሬዝ በዎል ስትሬት ጆርናል የአስተያየት አምድ ላይ ሰኔ 25 ቀን፤ "የአያቶላሆችን ኒኩሊዬር ለመከላከል መተባበር አለብን" በሚል ርዕስ ባወጡት ጽሑፍ ቀደም ሲል የኢራቅን አስጊነት በገለጹበት መንገድ ነበር የኢራንንም አስጊ እየሆነች መምጣት የገለጹት፡፡ ፔሬዝ በ1990ዎቹ ሂትለርን በመለማመጥ ያ ሁሉ ጥፋት መድረሱ ትምህርት ሊሆነን ይገባል ባይ ናቸው፡፡ አበክረው ያሳሰቡት "ኢራን የኒሊዬር ባለቤት የመሆን ግስጋሴዋን ካልገታች ዩናይትድ ስቴትስና እስራኤል ይህን ጉዳይ ሊታገሱት አይችሉም" በማለት ነበር፡፡,,[52]

ኒዎኮንሰርቫቲቮችም ቢሆኑ በኢራን የአገዛዝ ለውጥ እንዲደረግ ለመወትወት ምንም ጊዜ አላባከኑም ማለት ይቻላል፡፡ በ2003 የግንቦት ወር መገባደጃ ላይ ኢንተር ፕሬስ ሰርቪስ ባወጣው ዘገባ፡- ‹‹ዩ.ኤስ.አሜሪካ በኢራን የአገዛዝ ለውጥ እንድታደርግ ኒዎኮንሰርቫቲቮች የጀመሩት ግፊት እየተጠናከረ ሄዶ ብዙ ፍሬ እያስገኘ ነው" ብሏል፡፡[53] ‹‹ሰኔ መጀመሪያ አካባቢ ደግሞ በቡሽ አስተዳደር ውስጥና ውጭ ያሉ ኒዎኮንሰርቫቲቮች በቴህራን የአገዛዝ ለውጥ ይደረግ ዘንድ ግፊቸውን ያጠናከሩ መሆናቸውን" ፎርዋርድ ጋዜጣ ዘግቧል፡፡[54]

የኢራቅ ጦርነት ሊደረግ አቅራቢያ ጦርነቱ እንዲጀመር ጩኸታቸውን ሲያሰሙ የነበሩ ዋና ዋና ኒዎኮንሰርቫቲቮች አሁንም በተለመደው ስልታቸው ወደ ኢራን ዘመቻ ይደረግ ዘንድ መወትወታቸውን ተያያዙት። ዊሊያም ክሪስቶል በዊክሊ ስታንዳርድ የግንቦት 12 እትም "ለመጪው የመካከለኛው ምሥራቅ የወደፊት ብሩህ ተስፋ ኢራቅን ነፃ ማውጣት ትልቁ ጦርነት ነበር። .... ይሁን እንጂ ቀጣዩና ትልቁ ጦርነት ኢራንን ነፃ ለማውጣት የሚደረገው ነው" ብሏል።[55] ኢራን እንድትወረር የጦር ነጋሪት ከሚጎስሙት ጠብ ጫሪ ግለሰቦች መካከል ሚካኤል ሌዲን አንዱ ሲሆኑ ሚያዝያ 4 ቀን በታተመው ናሽናል ሪቪው አንላይን ጋዜጣ ላይ እንዲህ በማለት ጽፈዋል፦ "ከእንግዲህ ለዲፕሎማሲ የምንሰጠው እድል አክትሟል። ሽብርተኝነት ዋነኛ አበጋዞች ጋር የምንፋለምበት ጊዜም ደርሷል። ኢራን ሌላው ቢቀር የማይረሳ ድል እንድንጎናጸፍ ታደርገናለች ብዬ አስባለሁ። ምክንያቱም ኢራናውያን አገዛዙ አንገሽግሿቸዋል። ስለሆነም አገዛዙን የሚፋለሙት በጽኑ ፍላጎት ነው። ዩናይትድ ስቴትስ ያላት ድርሻ ኢራናውያንን ፍትሐዊ ለሆነው ትግላቸው ማገዝ ብቻ ነው።"[56]

ሌሎች ተመሳሳይ አስተየየት ያራመዱ ሁለት ባለሙያዎች የሚድልኢስት ፎረሙ ዳንኤል ፓይፕና የደብሊው አይ-ኤን-ኢ-ፒው ፓትሪክ ክላውሰን ሲሆኑ፣ በእየሩሳሌም ፖስት ጋዜጣ ላይ፣ ‹‹ በኢራን ላይ ግፊቱን አፋፍሙት ›› በሚል ርዕስ ባወጡት ጽሑፍ መሠረቱን በኢራቅ አድርጎ ኢራንን የሚዋጋውን ሙጃሂዲን ኸልቅን የቡሽ አስተዳደር እንዲደግፍ ጥሪ አድርገዋል። ይሁን እንጂ የዩ.ኤስ. አሜሪካ መንግሥት ቡድኑን ከአሸባሪ ድርጅቶች ዝርዝር ውስጥ አስገብቶታል። ላውረንስ ካፕላን ሰኔ 9 ቀን ባወጣው ኒው ሪፖብሊክ ጽሑፍ ላይ ‹‹ዩናይትድ ስቴትስ በኢራን የኒኩሊዬር መርሐ-ግብር አንባር ጠንካራ እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል ›› በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ የእርሱ ፍርሃት ብዙ የአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎች ካደረባቸው ስጋት ይበልጥ የገዘፈ መሆኑ ግልጽ ነበር።[57]

ግንቦት 6 ቀን አሜሪካን ኢንተርፕራይስ ኢኒስቲትዩት ከሌሎች ሁለት አፍቃሪ-እስራኤል ድርጅቶች ጋር በመሆን የኢራንን መጻኢ እጣ አስመልክቶ የሚነጋገር የአንድ ቀን ኮንፈረንስ አዘጋጅቶ ነበር።[58] በኮንፈረንሱ ላይ

ንግግር ያደረጉት ጠንካራ የእስራኤል ደጋፊች የሆኑት በርናርድ ሊዊስ፣ ሴናተር ሳምብሮውንባክ፣ ዩሪ ላባራኒና የእስራኢል መከላከያ ኃይል ከፍተኛ አማካሪ (በደቡብ ሊባኖስ የቀድሞ የእስራኤል ጦር አስተባባሪ የነበሩ)፣ ከጂዊሽ ኢኒስቲትዩት ፎር ናሽናል ሴኩሪቲ አፌርስ ሞሪስ አሜቲ (የቀድሞ የአይፓክ ስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር የነበሩ)፣ ሚካኤል ሴዲን፣ ከኤ.ኢ.አይ ራውል ማርክግሬትና ከሆድሰን ኢንስቲቲዩት ማይራቭ ውርምስር ነበሩ፡፡ (ማይራቭ የዴቪድ ወርምስር ባለቤት ናቸው)፡፡ በኮንፈረንሱ ጠረጴዛ ላይ የነበረው ዋነኛ የመነጋገሪያ አጀንዳ ግልጽ ሲሆን፣ “ዩናይትድ ስቴትስ በኢራን የአገዛዝ ለውጥ ለማድረግና ዲሞክራሲን ለመትከል ምን እርምጃ መውሰድ አለባት?” የሚል ነበር፡፡ መልሱን ለመገመት የሚከብድ አልነበረም፡፡ እያንዳንዱ ተናጋሪ ዩናይትድ ስቴትስ የኢራንን ኢስላማዊ ሪፖብሊክ አገዛዝ ለማውረድና በዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለመተካት ብዙ መሥራት እንደሚጠበቅባት በማስገንዘብ ነበር ንግግሩን ያጠናቀቀው፡፡

በዚህ ጥረት መደዳ ሎቢው፣ የኢራን የመጨረሻ ገዢ የነበሩት ሙሐመድ ሪዛ ፓህላቪ ልጅ ከሆነው ሪዛ ፓህላቪ ጋር ግንኙነቱ መስርቶ ነበር፡፡ ፓህላቪ በተጨማሪም ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ከሚገኙ አፍቃሪ-እስራኤል ቡድኖችና ግለሰቦች ጋር ሰፊ ግንኙነት ነበረው፡፡ ይህ ግንኙነት በቀጥታ በሎቢው ውስጥ የነበሩ ተጽዕኖ ፈጣሪ ቡድኖች ከኢራቁ ስደተኛና የተቃዋሚ አንጃ መሪ አህመድ ቻላቢ ጋር ያደርጉት ከነበረው ግንኙነት ጋር ይመሳሰላል፡፡ አፍቃሪ-እስራኤል ቡድኖች -ከእንቅስቃሴያቸው ለመታዘብ እንሚቻለው -እንደ ቻላቢ ሁሉ ፓህላቪም በሀገር ቤት አነስተኛ ተደማጭነት ብቻ ያለው መሆኑን ያላወቁ ይመስል ነበር፡፡ በአጸፋው ፓህላቪ በኢራን የሥልጣን መንበር ላይ የሚቀመጥ ከሆነ ሀገሩ ከእስራኤል ጋር የወዳጅነት ግንኙነት እንደምትመሰርት ግልጽ አደረገ፡፡[59]

ግንቦት 19/2003 ሴናተር ሳም ብሮውንባክ የኢራንን ተቃወሚዎች በገንዘብ ለመርዳትና ዲሞክራሲን በኢራን ለማስፋፋት የሚያስችል የሕግ ረቂቅ ለምክር ቤት የማቅረብ እቅድ እንዳላቸው ገለጹ፡፡ ‘የኢራን ዲሞክራሲ ሕግ’ በሚል ስያሜ የሚታወቀውን ረቂቅ በስደት ላይ ባሉ ኢራናውያን ብቻ ሳይሆን፣ በአይፓክ፣ ጄ.አይ.ኤን.ኤስ.ኤ እና ዘ ኮአሊቪን ፎር ዲሞክራሲ

ኢን ኢራን በተባለው ድርጅት ጭምር ድጋፍ ተችሮታል። ረቂቁን ለምክር ቤቱ ያቀረቡት ሌላው ጠንካራ የእስራኤል ደጋፊ የካንሳሱ ዲሞክራት ብራድ ሸርማን ሲሆኑ ሐምሌ ወር መጨረሻ ላይ 'ተቃዋሚዎችን በገንዘብ መርዳት' የሚለው ሐረግ ብቻ እንዲሰረዝ ተደርጎ በሁለቱም ምክር ቤቶች አለፈ።[60]

ይህንን ሕግ የደገፉ ቡድኖች አበክረው እንደገለጹት ኢራን ዋነኛ የስጋት ምንጭና የሰላም ጠንቅ ናት። ምክንያቱም ሽብርተኝነትን የምትደግፍ ከመሆኗም በላይ፣ የኒኩሌር ባለቤት ለመሆን እየተቃረበች ትገኛለች። በተጨማሪም ዩናይትድ ስቴትስ ባግዳድን ከያዘች በኋላ ላጋጠማት መራር ተጋድሎ ቡድኖቹ ኢራንን ተጠያቂ አድርገዋታል። ፔንታጎን ውስጥ ያሉ ኒኮንሰርቫቲቮች በበኩላቸው ኢራን ግንቦት 12/2003 ሳዑዲ አረቢያ ሪያድ ውስጥ የአሜሪካንና የሌሎች ሐገሮች ዒላማዎችን የመታውን የአል-ቃዒዳ ጥቃት ሳታስተባብር እንዳልቀረች በመግለጽ ጥርጣሬያቸውን ተናግረዋል። ኢራናውያኑ ይህንን ክስ አስተባብለዋል። ሲ.አይ.ኤና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም እንዲሁ የኒዎኮንሰርቫቲቮችን ክስ የተመለከቱት በከፍተኛ ጥርጣሬ ነው።[61] ኒዎኮንሰርቫቲቮች በተጨማሪም ኢራቅ ውስጥ በዩ.ኤስ፣ አሜሪካ ወታደሮች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ኢራን ትደግፋለች በማለት በከፍተኛ ሁኔታ የጮሁ መሆኑ እውነት ነው። ሚካኤል ሊዲን ሚያዝያ 2004 ላይ ሲጽፍ ‹‹ቴህራን ሽብርተኛ የሆኑ ካድሬዎችን ወደ ኢራቅ ድንበር መላኳን እስካላቆመች ድረስ ኢራቅ ሰላም አታገኝም›› ብሏል።[62]

ኢራን እንደተባለው በኢራቅ ያሉ ሚሊሻዎችን የምትረዳ ከሆነ የአሜሪካና የኢራን ፍላጎቶች ሊታረቁ አይችሉም ብሎ ለመደምደም ይከብዳል። ኢራን እንደሚታወቀው አሜሪካ ኢራቅ ውስጥ ለገጠሟት ችግሮች ሁሉ ተጠያቂ አይደለችም። ኢራን ምንም ነገር ባታደርግም እንኳ ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅ ውስጥ እጅግ በተወሳሰበ ሁኔታ ውስጥ መውደቋ የማይቀር ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ኢራን አድርጋለች የተባለችውን ማድረጓ አያስደንቅም። የዓለማችን ብቸኛ ልዕለ ኃያል ሁለቱን የኢራን ጎረቤቶች (አፍጋኒስታንና ኢራቅን) በየተራ በመውረር "የሠይጣን ዛቢያ" ብላ ከምትጠራቸው ሀገራት አንዷ የሆነችውን ኢራንንም ልታሰልስ እየዛተችባት እንደነበር ግልፅ ነውና።

የዩ. ኤስ. አሜሪካ ኮንግረስም ቢሆን በኢራን የአገዛዝ ለውጥ ይደረግ ዘንድ ሕግ አርቅቆ አሳልፏል። እንዲሁም የቡሽ አስተዳደር ለኢራን ተቃዋሚዎች ገንዘብ ከመርዳት ጀምሮ በተለያዩ አጋጣሚዎች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ኢራንንም እንደሚመታ ዛቻ ሲያሰማ ቆይቷል። ታዲያ የትኛውም ሃገር ቢሆን በእንዲህ ዓይነት አስጊ ሁኔታ ውስጥ ቢወድቅ ራሱን ለመከላከል ከተለያዩ የኢራቅ ቡድኖች ጋር ስምምነት አድርጎ የአሜሪካን ወራሪ ጦር ከማጥቃት ይቆጠባልን? እንበልና ከአሜሪካ ጋር ጠበኛ የሆነ አንድ ኃይል ካናዳንና ሜክሲኮን ቢወርና የራሱ ደጋፊዎች የሆኑ መንግሥታትን ለማቆም ቢሞክር ዩናይትድ ስቴትስ በዚያ የሚገኘውን ጠላቷን ጥረት በማመሰቃቀል ሁኔታዎች ለእርሷ ፍላጎት የተመቹ እንዲሆኑ ከማድረግ ትቆጠባለችን? ኢራን በኢራቅ ውስጥ የምታደርገው ጣልቃ ገብነት አሜሪካውያን ላደረባቸው ቅሬታ ጥሩ ምክንያት ሊሆናቸው ይችላል። ያ ማለት ግን ሁኔታውን ኢራን ለአሜሪካ ያላት ጥላቻ የማያቋርጥ ለመሆኑ እንደ በቂ ማሳያ ይቆጥሩታል ማለት አይደለም። በተጨማሪም ጥልቅ ጥላቻ መኖሩ አሜሪካን በቀዝቃዛው ጦርነት ጊዜያት ከሶቪዬት መሪዎች ጋር እንዳትደራደር አላደረጋትም። በእነዚያ ጊዜያት ሞስኮ በሚሊዮን ዶላሮች የሚገመት ወታደራዊ እርዳታ ለሰሜን ቬትናም ስትሰጥ የነበረ መሆኑንና በዚያ የጦር መሣሪያም በሺዎች የሚቆጠሩ አሜሪካውያን ወታደሮች ያልቁ እንደነበር አሜሪካ አላጣችውም። ይህም ሆኖ ግን ከሶቬት ጋር መነጋገርን መምረጧን ማወቁ ይጠቅማል።

እስራኤልን ከጥቃት ለመታደግ ኩነኔ መቆም

እስራኤልና ሎቢው በአስደናቂ ሁኔታ ቡሽንና ሌሎች እውቅ የአሜሪካ ፖለቲከኞችን ኒኩሌዩር የታጠቀች ኢራን ለእስራኤል አደገኛ የስጋት ምንጭ በመሆኗ ያንን ስጋት የመቀነሱ ኃላፊነት የአሜሪካ እንደሆነ ማሳመኑ ተሳክቶላቸዋል። እውነቱን ለመናገር በሎቢው ውስጥ ያሉ የተወሰኑ ሰዎች ያገኙትን ይህን ስኬት ለእስራኤል እንደተደረገ መልካም ውለታ የሚቆጥሩት መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች በሽበሽ ናቸው።

ፕሬዚዳንት ቡሽ መጋቢት 20/2006 ላይ በክሌቭላንድ ባደረጉት ንግግር የእስራኤልን አቋም የሚደግፉ መሆናቸውን በግልጽ አሳይተዋል፡፡ እንዲህ ነበር ያሉት፡- “ከኢራን በኩል የሚነሳው ስጋት እውነት ነው፡፡ ጠንካራዋን አጋራችንን እስራኤልን ማጥፋት ይሻሉ፡፡ ስጋቱ በእርግጥም ከባድ ነው፡፡ … በንግግሬ ግልጽ እንዳደረግሁት አሁንም ደግሜ በግልጽ አስቀምጠዋለሁ፡፡ አጋራችንን እስራኤልን ለመከላከል ኃያሉን ወታደራዊ ክንዳችንን እንጠቀማለን”[63] የቡሽ አባባል ቀደም ሲል ካደረጉት ንግግር ጋር የሚስማማና በሃሳባቸው የፀኑ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከወር በፊት ለሮይተር የዜና ወኪል በሰጡት ቃለ ምልልስ፡- “አስፈላጊ ከሆነ እስራኤልን ከጥቃት ለመከላከል ከጎኗ እንቆማለን” ብለው ነበር፡፡[64] ከዚህም በተጨማሪ አብዛኛዎቹ የ2008ቱ ዲሞክራትና ሪፖብሊካን ፕሬዚዳንታዊ ተወዳዳሪዎች ከፕሬዚዳንት ቡሽ ጋር የሚመሳሰል ሃሳብ ነበር ያራመዱት፡፡ ሚያዝያ 2007 ለምሳሌ ሴናተር ጆን ማኬይን ከቡሽ አባባል ጋር የሚስማሙ መሆናቸውንና ኢራን ለእስራኤል ስጋት የሚፈጥር የኒኩሌዩር መሣሪያ እንዳትታጠቅ የማድረግ ኃላፊነት ዩናይትድ ስቴትስ እንዳለባት ገልፀዋል፡፡[65] ጆን ማኬን ይህንኑ ሃሳባቸውን ግንቦት 2007 ከእየሩሳሌም ፖስት ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ደግመው ያረጋገጡ ሲሆን፤ ባራክ አባማ፣ ሚት ሮምኒ ቢል ሪቻድሰንና ሳም ብሮውንባክም እንዲሁ ተመሳሳይ ሀሳብ ነበር ያራመዱት፡፡[66]

ኢራን የዩናይትድ ስቴትስ ሳይሆን የእስራኤል ታላቅ ስጋት መሆኗን ቡሽ በጋለ ስሜት መግለጻቸውና እስራኤልን ከጥቃት ለመከላከል ሲሉም ከኢራን ጋር ጦርነት እንደሚገጥሙ ማሳወቃቸው በሎቢው የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ አካላትን ያባነነ የደወል ጥሪ ነበር፡፡ 2006 ላይ ፎርዋርድ ጋዜጣ ‹‹የአይሁድ ማህበረሰብ መሪዎች ዋይት ሃውስ እስራኤልን ከማንኛውም የኢራን ጥቃት እንታደጋለን የሚለውን አባባል ከመጠቀም እንዲቆጠብ ጠየቁ፡፡›› በማለት አጋልጧል፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ጉዳይ የሎቢው መሪዎች ኢራን በእስራኤል ላይ ከምታስከትለው ከማንኛውም ስጋት አሜሪካ የምትከላከልላት መሆኗን አልነበረም የተቃወሙት፡፡ የእነርሱ ፍርሃት ቡሽ ይህን ሐሳብ በይፋ መናገራቸው ነው፡፡ የዚህም ምክንያት

አሜሪካ በኢራን ላይ በምታደርገው ዘመቻ አሉታዊ ክስተት እውን ከሆነ በአሜሪካ አይሁዳውያን ላይ እንዳይሳበብ በመፍራት ነው።[67] የፕሬዚዳንቶች ኮንፈረንስ የተሰኘው የሎቢ ድርጅት ምክትል ሊ/መንበር ማልኮለም ሆኖሊን 2006 ላይ እንዲህ ብለው ነበር፡- "ይህን አባባል የምናደንቀው ቢሆንም፣ ጥያቄው ያለው ከእስራኤል ጋር መያያዙ ጠቃሚ ነው ወይስ አይደለም? ከሚለው ላይ ነው"[68]

የእስራኤል መሪዎችም ተመሳሳይ ሀሳብ እንዳላቸው የሚያረጋግጠው አፍቃሪ-እስራኤል ቡድኖች እንዲህ አይነቱን አመለካከት ለመቀየር እንዲሠሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሁድ ኦልመርት ሲያሳስቡ፣ ‹‹የሚደረገው ጦርነት በእስራኤል ስም እንዲሆን አንሻም" ማለታቸው ነው። ይህ አባባል ቡሽ ከተናገሩት ጋር ፈጽሞ ተቃራኒ መሆኑን ልብ ይሏል።[69] ቡሽ ካደረጉት ንግግር ጎን አስተዳደራቸው የኢራንን የኒኩሊዬር መርሃ-ግብር ለማስቆም በትጋት ከመንቀሳቀሱም በላይ፣ ጠንካራ አቋም ነበር የያዘው። ኢራን የኒኩሌዬር ግንባታዋን የማታቆም ከሆነ የኢኮኖሚ ማዕቀብ ለመጣል፣ ከዚያም አለፍ ሲል ወታደራዊ ኃይል ለመጠቀም እንደሚገደድ በመግለጽ አስፈራራ። ‹‹ሁሉም አማራጮች›› አሉ የአሜሪካ መሪዎች "ጠረጴዛ ላይ ነው ያሉት"[70] ጀምስ ባምፎርድና ሰይሙር ኸርሽ በተናጠል እንደገለፁት የኢራቅን ጦርነት እቅድ ያዘጋጁት ሰዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ኢራንን ለመውረር የሚያስቸለውን እቅድ ነድፈው አቅርበዋል። ለምሳሌ በሚኒስትር ማዕረግ የዴፌንስ ፎር ፖሊሲ ኃላፊ የሆኑት ዶግላስ ሬይዝ በ2005 ኢስላማዊቷን ሪፖብሊክ ለመምታት የሚያስችለውን እቅድ በመንደፍ በኩል ጉልህ ሚና ተጫውተዋል። ኸርሽ በ2005 መጀመሪያ ላይ "ኢራንን ለማጥቃት በተነደፈው እቅድ በስፋት ያልታወቀ ሆኖም ግን ከእስራኤል ጋር የተደረገ በርካታ የትብብር ሥራ ነበር" በማለት ገልጸዋል። ዶግላስ ሬይዝ የሚመሩት የመከላከያ ክፍል 8ሲቪል ሠራተኞች ከእስራኤል የጦር ዕቅድ አውጪዎችና አማካሪዎች ጋር በመሆን ኢራን ውስጥ የሚገኙ የኑክሊዬር ኃይል ማመንጫዎችን፣ የኬሚካል መሣሪያ ፋብሪካዎችን፣ የተጠመዱ ሚሳይሎችን አጣርተውና ነድፈው በማቅረብና ለዒላማ በማዘጋጀት ወረራው እንዲፈጸም በቂ ዝግጅት አድርገዋል። ፔንታጎንም ቢሆን ኢራን ውስጥ

የራሱን የስለላ ሥራዎች በመሥራት መረጃዎችን ካሰባሰበ በኋላ በኢራን ላይ አጠቃላይ የሆነ ወረራ ለማድረግ የድርጊት መርሃ-ግብር ቀርጾ አስቀምጧል።[71]

በጥር 2007 የቡሽ አስተዳደር በኢራን ላይ በብዙ መንገድ የሚገለጽ ወታደራዊ ጫናውን አበርትቶ ነበር። ኢርቢል በተባለችው የኢራቅ ከተማ የአሜ56565656ሪካ ጦር አምስት የኢራን ባለሥልጣኖችን ይዞ ያሠራቸው ሲሆን የሀገሬው ኩርዶችና የኢራን መንግሥት ሰዎቹ የኢራን ቆንስላ ጽ/ቤት ባልደረቦች መሆናቸውን ተናግረዋል። ቡሽ ከዚያ በኋላ ባደረጉት ንግግር ወደ ባሕረ-ሰላጤው ተጨማሪ ሠራዊትና ፓትሪዬት የተባለ ፀረ-ሚሳዬል የመከላከያ መሣሪያ በመላክ በባሕረ-ሰላጤው የትብብር ካውንስል ሥር የሚኙትን ሀገራት ከጥቃት እንደሚታደጉ ገለጹ። በተመሳሳይ ጊዜ ባግዳድ ውስጥ የሚገኙ የአሜሪካ ወታደራዊ ሹማምንት ኢራን በመንገድ ላይ ለሚቀበሩ ፈንጂዎች የሚሆኑ የተለያዩ ክፍሎችን ለኢራቅ ሠርጎ ገቦች እያቀበለች የአሜሪካን ወታደሮች እንደምትፈጅ በመጥቀስ ክስ አቀረቡ። የፕሬዚዳንቱ የብሔራዊ ፀጥታ አማካሪ የሆኑት ስቴፈን ሃድሊና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ ኮንዶሊዛ ራይስ የዩ.ኤስ. አሜሪካ ጦር አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ወደ ኢራን ግዛት በመዝለቅ የመንገድ ላይ ተቀባሪ ፈንጂዎችና ሌሎች መሣሪያዎች ወደ ኢራቅ የሚሰርጉባቸውን ምንጮች ለመቆጣጠር የሚያስችለውን እድል ዝግ እንዳላደረገ ገለጹ።[72]

በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ፍጥጫ ይህን በመሰለበት ሰዓት የምክትል ፕሬዚዳንቱ የመካከለኛው ምሥራቅ አማካሪ የሆኑት ዴቪድ ውርምሰር፣ ራይሰና ከኢራን ጋር ከስምምነት ላይ ለመድረስ ፍላጎት አሳይተዋል የሚል ስሜት አደረባቸው። ምንም እንኳን የዲፕሎማሲው ሂደት በወታደራዊ ማስፈራሪያ እየታገዘ ቢሄድና ወታደራዊው እርምጃም እንደ ዋነኛ አማራጭ ባይወሰድም ቅሉ ውርምሰር ኢራን በጥድፊያ እንድትወረር ነበር የሚሹት። በመሆኑም 2007 ላይ በአሜሪካ ኢንተርፕራይስ ኢንስቲትዩትና በዋሽንግተን የሚገኙ ሌሎች ሐሳብ አፍላቂዎች በጉዳዩ ላይ ትኩረት ሰጥተው ከመከሩ በኋላ እንዲህ አሉ፡- "ምክትል ፕሬዚዳንቱ፣ የውጭ ጉዳይ ሚንስትሯና ፕሬዚዳንት ቡሽ ራሳቸው የዲፕሎማሲውን መንገድ መከተልን የመረጡ

ሲሆን፤ ቼኒ ግን ከእስራኤል ጋር በመሆን የኢራንን የኒኩሊዬር ተቋማት በወታደራዊ ኃይል የማፈራረሱን ስትራቴጂ በመምረጣቸው ይህንኑ አቋማቸውን ለፕሬዚዳንቱ በማቅረብ ሊያሳምኗቸው ይሞክራሉ።" የውርምሰር እንቅስቃሴና ሃሳብ ይፋ በተደረገ ጊዜ ራይስ በአስተዳደሩ ውስጥ ኢራንን የተመለከተ ልዩነት አለመኖሩን አስተባብለው ምክትል ፕሬዚዳንቱ የቡሽን ፖሊሲ ሙሉ ለሙሉ እንደሚደግፉ አስረግጠው ተናገሩ።[73]

እንግዲህ ዋሽንግተን ከኢራን ጋር ባላት ግንኙነት አንፃር ከስምምነት ይልቅ የማስፈራራቱን ስትራቴጂ መከተልን ብትመርጥም፣ የአውሮፓ ሕብረት በበኩሉ ለዚህ የፖለቲካ ምስቅልቅል ተቃራኒውን አቅጣጫ በመከተል የዲፕሎማሲውን መፍትሄ ለማስገኘት መሞከሩ አልቀረም። ኢዩ-3 የሚባሉት ሦስቱ ሀገራት (ብሪታንያ፣ ፈረንሳይና ጀርመን) ከቴህራን ጋር የስምምነት ውል ለመቋጠር ኅሐሴ 2003 ያነቃቁት ጥረት ፍሬ አፍርቶ ኢራን ጥቅምት 21 ቀን ዩራንዬም ማበልጸጉን ለመግታትና የዓለም አቀፉ አቶሚክ ኃይል ተቆጣጣሪ ድርጅት ጣልቃ ገብቶ ሂደቱን እንዲከታተል ለማድረግ ተስማማች። ይህንንም ስታደርግ በረኸርም ጊዜ ግፂ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ የኒኩሊዬር መርሐ-ግብሯን በግልጽ ለማካሄድ ከሚያስችል የድርድር ሂደት ውስጥ ለመግባት ፈቅዳ ነው።[74] ይሁን እንጂ በተደረጉት ጥረቶች አርኪ ከሆነ ስምምነት ላይ ለመድረስ ሳይቻል በመቅረቱ ኢራን በነሐሴ 2005 ዩራንዬም የማበልፀጉን ሂደት እንደምትቀጥልበት ይፋ አደረገች። ከዚያም በኋላ ቢሆን ኢዩ-3 የሚባሉ ሀገራት ከኢራን ጋር ንግግር ማድረጋቸውን ያላቆሙ ቢሆንም ንግግሩ ያስገኘው ፋይዳ አልነበረም።

የኢዩ-3 ሀገራት በድርድሩ ሂደት የኢራንን የኒኩሊዬር መርሐ-ግብር ለማስቆም እንዲችሉ ዩናይትድ ስቴትስ ብትፈቅድም፣ ያን ለመሰለው ስምምነት ያላት ጉጉት አነስተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ ስምምነቱን በሥራ ላይ ለማዋልም ዝግጁ አልነበረችም።[75] እናም የቡሽ አስተዳደር ኢራንን በቋሚነት በማስፈራራትና የአውሮፓ ተደራዳሪዎች በኢራን አንፃር ከረር ያለ አቋም እንዲኖራቸው በመገፋፋት ድርድሩ የትም እንደማይደርስ እርግጠኛ መሆን ይፈልግ ነበር። የዲፕሎማሲው ሂደት ስኬት እንደሚያመጣ

ቢፈቀድለት ኖሮ፣ ወታደራዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚደረገው ማስፈራሪያ ከጠረጴዛ ላይ በተወገደ ነበር፡፡

በወታደራዊ ጥቃት ማስፈራሪያ ሲታጀብ የቆዬው የዲፕሎማሲ ጥረት ለችግሩ መፍትሄ እንደማያመጣ ሲታመን፣ የተ.መ.ድ. ፀጥታው ምክር ቤት በኢራን ላይ ማዕቀብ እንዲጥል የቡሽ አስተዳደር በ2005 ግፊት ማድረግ ጀመረ፡፡ በጥረቱ በመግፋቱም በ2006 ታኅሣሥ ወር ላይ ቻይናና ሩሲያ ከብዙ ማንገራገር በኋላ ሃሳቡን ስለተቀበሉት የተወሰኑ ማዕቀቦች በኢራን ላይ እንዲጫኑ ማድረግ ተቻለ።[76] ኢራን የኒኩሊዬር ማበልጸጊያ ተቋማቷን ለመዝጋት ባለመፍቀዷ በ2007 መጋቢት ወር መጨረሻ ላይ የፀጥታው ምክር ቤት ሁለተኛውን ማዕቀብ ሊያሳርፍባት ግድ ሆነ፡፡ ይህ ማዕቀብ የኢራንን የጦር መሣሪያ ወደ ውጭ መላክን፣ ከኢራን የኒኩሊዬር መርሐ-ግብር ጋር ቀጥተኛ ትስስር ባላቸው ሰዎች ላይ የጉዞ እገዳ ማሳረፍንና በመጀመሪያው ማዕቀብ ያልተነኩ ሰዎችንና ድርጅቶችን ገንዘብና ንብረት እንዳይንቀሳቀስ ማድረግን የመሳሰሉ ጠበብ ያለ አድማስ ያላቸው ነገሮችን የሚሸፍን ነበር፡፡[77] ሆኖም ግን የተ.መ.ድ. ማዕቀብ ለተፈጠረው ችግር መፍትሄ አላስገኘም፡፡ ታዲያ መፍትሄው ምን ይሆን ?

አማራጮች

የቡሽ አስተዳደር የኢራንን የኒኩሊዬር መርሐ-ግብር ለማስቆም ሶስት አማራጮች አሉት፡፡ የመጀመሪያው በኢራን ላይ ወታደራዊ ጫና በማብዛትና ከጦርነት በመለስ ያሉ እርምጃዎችን በመውሰድ፣ እንዲሁም ጠንካራ የሆነ የዩ.ኤስ.አሜሪካ ማዕቀብን ጨምሮ እስራኤልንና የአረብ ሀገራትን የሚያካትት ፀረ-ኢራን ሕብረትን በማደራጀት ተጽዕኖ ማሳደር ነው፡፡ ሁለተኛው ወታደራዊ እርምጃ ሲሆን፣ ሦስተኛው ደግሞ ኢራን የኒኩሊዬር መሣሪያ እንዳታመርት የሚያግድ መሠረቱ ሰፊ የሆነ ድርድርና ስምምነት ማድረግ ነው፡፡ እስራኤልና በሎቢው ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ ድርጅቶች፣ በተለይም ኒዎኮንሰርባቲቮች ሁለተኛውን እርምጃ ይደግፋሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከዩ.ኤስ.አሜሪካ መንግሥት ውስጥና ውጭ የሚገኙ በርካታ ሰዎች፣ እንዲሁም ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ጭምር በተለይ በኢራቅ እየሆነ ያለውን ሁሉ ከታዘበ በኋላ ይህን ሃሳብ በጽኑ እንደሚቃወመው ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ከዚያም በተጨማሪ ፕሬዚዳንት ቡሽ ለይስሙላ ካደረጉት ንግግር ባሻገር ወታደራዊውን አማራጭ ለመጠቀም ያላቸው ፍላጎት አነስተኛ መሆኑ ግልጽ እየሆነ ሄዷል፡፡ ይህ ማለት ግን የኃይሉን አማራጭ ሙሉ በሙሉ ሰርዘውታል ማለት አይደለም፡፡

የኢራን አስተዳደር ዩራኒዬም የማበልጸግ ተግባሩን ያቆማል በሚል ተስፋ ቡሽ በ2007 ግፊታቸውን ይበልጥ አጠናከሩ፡፡[78] አስተዳደራቸው በዚያው ዓመት ጥር ወር ላይ ቀጥተኛ የሆኑና በኢራን አንፃር የታለሙ በርካታ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን አደረጉ፡፡ እንዲሁም ፕሬዚዳንቱና ውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ራይስ በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ የአረብ ሀገራት በኢራን አንፃር ከአሜሪካና ከእስራኤል ጎን እንዲቆሙ ለማድረግ ተረባረቡ፡፡ አጠቃላዩ ሁኔታ ይህን በሚመስልበት ሰዓት በሎቢው ውስጥ ያሉና ቡሽ የሚያራምዱትን ፖሊሲ ለጊዜውም ቢሆን የደገፉ ቁልፍ ቡድኖች ተንቀሳቀሱ፡፡ ፎርዋርድ ጋዜጣ መጋቢት 2007 ላይ በተደረገው የአይፓክ ኮንፈረንስ ዋዜማ ‹‹አፍቃሪ-እስራኤል የሆነው ሎቢ በኢራን ላይ ከባድ

የሆነና ከእስላማዊቷ ሪፖብሊክ ጋር የንግድ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ የውጭ ድርጅቶችን ዒላማ ያደረገ ማዕቀብ እንዲጫን ለማድረግ በኮንግረሱ ውስጥ የሕግ ረቂቅ ማዘጋጀት ጀመረ›› በማለት ዘግቧል።[79] ይህ ስትራቴጂ እስካሁን ድረስ ያስገኘው ውጤት የሌለ መሆኑ ነው ትልቁ ጭንቀት። ዩናይትድ ስቴትስ በዚህ መሐል አምስቱን ኢራናውያን በመያዟ በብዙ ኢራቃውያን -በኩርዶች ሳይቀር- በሰፊው ተተችታለች። ከዚያ በኋላ መጋቢት ወር ላይ ኢራናውያን ተመሳሳይ ጨዋታ መጫወት እንደሚችሉ ያሳዩት የኢራንን የባሕር ክልል ጥሰው የተገኙ አስራ አምስት የብሪታኒያ ባሕር ኃይል አባላትን በቁጥጥር ስር ባደረጉ ጊዜ ነበር።[80] ይህ በእንዲህ እያለም ኢራን የኒኩሊዬር መርሐ-ግብሯን ማካሄድና በኢራቅ የሚገኙ የሺዓ ቡድኖችን መደገፏን ቀጠለች። በመሆኑም ወደ ባሕረ-ሰላጤው ተጨማሪ የጦር ሠራዊት በመላክ የቴህራንን ባሕሪ መቀየር የሚቻል ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አልተገኘም። ኮንግረስ በጊዜው በጣም ከባድ የሆነ ማዕቀብ በማሳለፍ ላይ ቢሆንም፣ የቡሽ አስተዳደር ያንን መንገድ በመከተሉ ሂደት ዳተኝነት በግልጽ ይታይበት ነበር። ምክንያቱም ማእቀቡ ከኢራን ጋር ንግድ የሚያካሂዱ ወዳጅ ሀገራትንና ድርጅቶችን ስለሚጎዳቸው ነው። ዩ.ኤስ.አሜሪካ ከእነዚያ ሃገራት ጋር ያላትን ግንኙነትም እንድታቋርጥ እንደሚያደርጋት የተረጋገጠ ጉዳይ ሆነ። ከሁሉም በላይ ዋሽንግተን በኢራን ላይ ተጨማሪ ጫና እንድታሳርፍ ለመርዳት ያበረከቱትን አስተዋጽኦና ያሳዩትን ፈቃደኝነት የሚያቃልል ነው።[81]

የቡሽ አስተዳደር በኢራን አንፃር የአረብ መንግሥታትን ለማስተባበር ያደረገው ሙከራ ያሳዬው መሻሻል አነስተኛ ነው። ምክንያቱም እስራኤል በፍልስጤማያን ላይ የምትፈጽመውን ግፍ አሜሪካ መደገፏን በመቀጠሏ ነበር። መጋቢት ወር ላይ የሳዑዲ አረቢያው ንጉሥ አብደላህ የኢራኑን ፕሬዚዳንት አህመዲን ኤጃድን ለጉብኝት ወደ ሪያድ መጋበዝ ብቻ ሳይሆን ሁዋይት ሃውስን ለመሳብኘት የያዙትን ዕቅድ እስከመሰረዝና ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅን መውረሯን ‹‹ሕገወጥ›› በማለት እስከማውገዝ አድርሷቸዋል። በዮርዳኖስ ዩኒቨርስቲ የስትራቴጂ ጥናት ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ስለ ክስተቱ ሲናገሩ፡- ‘‘አብዱላህ ያደረጉትን ማድረጋቸው

ሽሪካቸውን አሜሪካን ሁልጊዜ የእስራኤልን አቋም ከመደገፍ ይልቅ የእኛንም ሃሳብ አዳምጡ የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ፈልገው ነው'' ብለዋል። ምዕራፍ 7 ላይ እንደገለጽነው ሳዑዲ አረቢያ በ2002 በአረብ ሊግ የተረቀቀውንና የእስራኤል ፍልስጤማውያንን ግጭት እንዲያበቃ የሚያስችለውን የሰላም ሃሳብ እንደገና እያንቀሳቀሰች የነበረችበት ጊዜ ነበር። ዩናይትድ ስቴትስ ደግሞ ሳዑዲ የሰላም ሀሳቡን እንድትቀይረው እየተጫነቻት ነበር። ምክንያቱም እስራኤል አልተደሰተችበትምና። ኮንዶሊዛ ራይስ በዚያ ጊዜ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ለአረብ ሀገራት፡- "እስራኤልን የሚያረካ ነገር ለማቅረብ እንደገና ጥረታችሁን ጀመሩ'' በማለት ጠየቁ። ይህ አባባላቸው ሳዑዲዎችን -በተለይም ንጉሥ አብደላህን- በማስቆጣቱ እርሳቸውም አሜሪካውያን ኢራቅ ውስጥ መገኘታቸውን አስመልክተው ትችታቸውን እንዲያዘንቡ ምክንያት ሆነ።[82]

የማስገደዱ ስትራቴጂ የኢራንን ስሌት ሊያስቀይር አልቻለም። ይህ ነጥብ ኢራንን እንደታላቅ ጠላታቸው ለሚመለከቱት የእስራኤል መሪዎችና ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ለሚገኙ አጋሮቻቸው የተሰወረ አልነበረም። በዚህም የተነሣ ዩ.ኤስ.አሜሪካ በኢራን አንዣር ልትወስደው የምትችለውን ወታደራዊ አማራጭ ችላ እንዳትለው ብዙዎቹ ያለማቋረጥ መወትወታቸውን ተያያዙት። ጠቅላይ ሚኒስትር ኦልመርት ግንቦት 24/2006 የአሜሪካ ኮንግረስ የጋራ ስብሰባ በተደረገ ጊዜ የተናገሩትን ማስታወሱ ተገቢ ነው። ኦልመርት የኢራንን ኒኩሊዩር መሣሪያ ክባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ያልሠለጠነ አካሄድና ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሰቃቂ ትዕይንት፣ እንዲሁም ከኮሚኒስቶቹ ካምፕ ስቃይ የበዛባቸው እስር ቤቶች ጋር ነበር ያመሳሰሉት። ከዚያም አጽንኦት ሰጥተው ሲናገሩ፡- "ኒኩሊዩር የታጠቀች ኢራን ለእስራኤል ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላዩ የዓለም ሰላም ስጋት ናት' አሉ። ‹‹በዓለም ላይ ይህ ጽልመት ሳያጠላ በፊት በመከላከሉ በኩል ዩናይትድ ስቴትስ ቁልፍ ሚና መጫወት ይጠበቅበታል›› በማለትም ንግግራቸውን አሳረጉ።[83]

ይህ ከሆነ ከጥቂት ወራት በኋላ ህዳር 2006 ላይ ኦልመርት ለኒውስዊክ መጽሔት በሰጡት ቃለ ምልልስ፡- ‹‹ኢራን የእርቁን መንገድ ባለመከተሏ

የሚደርስባትን መጥፎ ሁኔታ ካልፈራች በስተቀር ሰላማዊ ድርድር ታደርጋለች ብዬ አላምንም፡፡ ስለሆነም ኢራን መፍራት መጀመር አለባት" አሉ፡፡[84] በ2007 ኦልመርት የጦርነቱን አማራጭ ለማሳመን ዘመቻ ከፈቱ፡፡ በሚያዝያ መጀመሪያ ላይ ለጀርመኑ ፎከስ መጽሔት፡- "የኢራንን የኒኩሊዬር አውታር ሙሉ ለሙሉ ማውደም ባይቻልም ሂደቱ ለዓመታት ወደኋላ እንዲመለስ የሚያስገድድ ምት ማሳረፍ ይቻላል" ሲሉ ሃሳባቸውን ገለጹ፡፡ ኦልመርት እንደገመቱት ሥራው (ድብደባው) ኣሥር ቀናት ሊጨርስ እንደሚችልና አንድ ሺህ ቶም ሃውክ ክሩዝ ሚሳዬሎችን ማስወንጨፍ እንደሚያስፈልግ ሳይጠቅሱ አላለፉም፡፡[85] ይሁን እንጂ አንድ እስራኤላዊ ጄኔራል፣ ቡሽ ኢራንን ለማጥቃት፣ "በቂ የፖለቲካ ኃይል" እንዳላቸው ካጠያየቁ በኋላ በሰጡት አስተያየት፡- "እስራኤል ዲሞክራቲክ ፓርቲውን ሎቢ በማድረግ ... እንዲሁም የዩናይትድ ስቴትስ የጋዜጣ አዘጋጆችን በማሳመን... የኢራንን ጉዳይ የፓርቲዎችና የሁሉም አካላት የጋራ ጉዳይ ማድረግ ያስፈልጋታል" ብለዋል፡፡[86]

የእስራኤል ባለሥልጣናትም ቢሆኑ ኢራን በኒኩሊዬር ግንባታዋ የምትገፋ ከሆነ ራሳቸው ቀድመው እርምጃ እንደሚወስዱ ማስጠንቀቃቸው አልቀረም፡፡ እንዲህ ያለውን ማስፈራሪያ በማሰማት የእስራኤል ባለሥልጣናት ለኢራን ተገቢ ነው ያሉትን መልዕክት ከማስተላለፋቸው ባሻገር ዋሽንግተን ለችግሩ መፍትሄ ትፈልግ ዘንድ ጫና ለማሳደር ጣሩ፡፡ ይህን ያደረጉት በዚህ ጉዳይ ላይ እስራኤል ብቻዋን ምንም ዓይነት እርምጃ እንድትወስድ ዩናይትድ ስቴትስ ስለማትሻ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ሻሮን በ2005፣ "እስራኤልም ብቻ ሳትሆን ሌላውም ዓለም ኒኩሊዬር የታጠቀች ኢራንን አይቀበልም፡፡ ለዚህ ጉዳይ እልባት የመስጠት ችሎታ ያለን ሲሆን፣ ለምንወስደው እርምጃም አስፈላጊውን ዝግጅት ሁሉ አጠናቀናል" በማለት ተናግረዋል፡፡ ለንደን ሰንደይ ታይምስ ጥር/2007 ባወጣው ዘገባው፡- "የእስራኤል ፓይለቶች የኢራንን የኒውክሊዬር ተቋማት ለማውደም የሚያስችላቸውን ልምምድ በመሰል ዒላማ ላይ እያካሄዱ ይገኛሉ" በማለት ቢጠቅስም፣ የእስራኤል ባለሥልጣናት ግን ጉዳዩን በይፋ አስተባብለዋል፡፡ አንድ እስራኤላዊ የመከላከያ ጉዳዮች ተንታኝ ለአሶሺዬትድ ፕሬስ እንደተናገሩት

“ይህ ዓይነቱ ወሬ እንዲለቀቅ የተደረገው ሆነ ተብሎ ማለትም ይህን ተግባር እኛ እንዳንፈጽመውና የእብደት ሥራ ሠርተን እንዳንገኝ የሚያቅበን ኃይል ብቅ እንዲል ለማስገደድ ሊሆን ይችላል” ብለዋል።[87] ይህ መልዕክት በሚገባ ግልጽ ባልሆነበት ሁኔታ የእስራኤሉ ም/ጠቅላይ ሚኒስትርና ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኢቪግዶር ሊበርማን፣ ዶ/ር ስፒግል ለተባለው የጀርመን ጋዜጣ የካቲት 2007 በሰጡት ቃለ ምልልስ፡ ‘‘ችግሩን ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የማይፈታው ከሆነ እስራኤል ብቻዋን ታስወግደዋለች’ ብለዋል።[88]

በሎቢው ውስጥ ያሉ ቡድኖችም እንዲሁ በኢራን ‹‹የአገዛዝ ለውጥ›› እንዲደረግ ከመጠየቅ አልፈው ኒኩሊዬር የታጠቀች ኢራንን መታገስ እንደማይቻልና ዩናይትድ ስቴትስ ችግሩን ለማስወገድ ኃይል መጠቀም እንዳለባት ይወተውታሉ።[89] ኒዎኮንሰርቫቲቭ ምሁራንና ባለሙያዋች በተለይ ኢራን ትልቅ ስጋት እየፈጠረች እንደሆነ በግልጽ ከመናገር አልፈው ኃይል መጠቀም እንደሚያስፈልግና ቢያንስ ወደዚያ ዓይነት አዝማሚያ መግባቱ ኢራንን ለማስፈራራት ግድ እንደሆነ ይናገራሉ። የእነርሱን አስተያየት በኒውዮርክ ደይሊ ጋዜጣ 2006 እትም የሃሳብ መስጫ አምድ (Oped) ላይ የአሜሪካውያን ኢንተርፐራይስ ኢንስቲትዩት ባልደረባ የሆነው ሚካኤል ሩቢን የሚከተለውን ርዕስ ሰጥቶ ጽፎበት ነበር፡- “የኢራንን ችግር ለማስወገድ ለጦርነት እቅድ አውጡ” የኤ.ኢ.አይ. ባልደረባ የሆነው ጆሽዋ ሙራቪችም እንዲሁ ከአንድ ወር በኋላ፤ “ፕሬዚዳንት ቡሽ ቢሯቸውን ከመልቀቃቸው በፊት የኢራንን ኒኩሊዬር ተቋማት በቦምብ ማውደም ይኖርባቸዋል። ኢራን ከእንግዲህ ቦምቡን መሥራቷን እንድታቆም የሚገፋፉት ምንም ዓይነት ሰላማዊ ሁኔታ ይኖራል ብሎ ማሰብ የማይታመን ነው›› ብሎ ነበር።[90] በተመሳሳይ ሁኔታ ሪቻርድ ፐርል ጥር/2007 ላይ እንደሚከተለው ብለዋል፡- “ፕሬዚዳንት ቡሽ በሥልጣን ዘመናቸው ኢራን የኒኩሊዬር መሣሪያ እንደምትታጠቅ በግልጽ ቢያውቁ ኖሮ እርሷን ለማጥቃት ትዕዛዝ ከማስተላለፍ አያመነቱም።"[91] በመጨረሻም ግንቦት 30/2007 ኖርማን ፓደሆርትዝ በስፋት መነጋገሪያ የሆነና ‹‹ኢራንን በቦምብ መምታት አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም። የእኔ ተስፋና ፀሎት ቡሽ

እንዲያደርጉት ነው›› በሚል ርዕስ በዎል ስትሪት ጆርናል ላይ ጽሑፍ አውጥተው ነበር፡፡

አይፓክም እንዲሁ ከኢራን በኩል የተደቀነውን ስጋት ይፋ አድርጎ ወታደራዊው እርምጃ እንዲፋጠን ግፊት ማድረጉን ተያይዞት ነበር፡፡ ባለፉት ሁለት ዓመታት ባደረጋቸው ዓመታዊ ኮንፈረንሶች የኢራንን ጉዳይ በማጉላት የኒኩሌዩር መርሐ-ግብሯን ለማጥቃት በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙሪያ ትኩረት አድርጎ ሲወያይ ቆይቷል፡፡[92] ለምሳሌ ክርስቲያን ዩናይትድ ፎር እስራኤል የተባለውን ድርጅት የሚመራው ጆን ሃጊ በ2007 ኮንፈረንስ ንግግር እንዲያደርግ ተጋብዞ ነበር፡፡ ሃጊ 2006 ላይ ለእየሩሳሌም ፖስት ጋዜጣ በሰጠው መግለጫ፡- “የምዕራባዊውን ዓለም ሥልጣኔ ለመታደግ የኢራንን የኒኩሌር ማንባታ ተቋም በማውደሙ ሂደት ዩናይትድ ስቴትስ ከእስራኤል ጋር ትተባበራለች ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ” ብሏል፡፡[93] ሃጊ 2007 ላይ በተደረገው የአይፓክ ኮንፈረንስ ላይ ንግግር ባደረገ ጊዜ፡- “ይህ ያለንበት ዘመን 1938 እንደሆነ እናስብ፡፡ ኢራንም ጀርመን እንደሆነችና አህመዲን ኢጃድም አዲሱ ሂትለር መሆናቸውን እንዲሁ፡፡ የኢራንን የኒኩሌር ስጋት ለማቆም በግልጽ ከእስራኤል ጎን መቆም አለብን” ሲል ተናገረ፡፡ ታዳሚዎችም ከመቀመጫቸው እየተነሱ ደጋግመው አጨበጨቡለት፡፡[94] ከዚህ በተቃራኒው ሂለሪ ክሊንተን፡- ‹‹በኢራን ላይ ጠንካራ ዱላ ከማሳረፋችን በፊት የሰላም እርምጃው መቅደም አለበት›› በማለት ለአይፓክ ተሰብሳቢዎች ያስተላለፉትን መልእክት ኒዎርክ ፖስት ጋዜጣ በዘገበ ጊዜ በተሰብሳቢዎች ዘንድ ‹‹ትልቅ ማጉረምረም›› መሰማቱ ተገልጿል፡፡[95]

ምናልባትም አይፓክ አሜሪካ በኢራን አንፃር በምትከተለው ፖሊሲ ላይ ያለውን ተጽዕኖ የሚያሳይ ምርጥ ማስረጃ የታዬው ፕሬዚዳንት ቡሽ ኢራንን ከማጥቃታቸው በፊት የፔንታጎንን ፈቃድ እንዲጠይቁ የሚያስገድደውን ሕግ ኮንግረሱ መጋቢት 2007 ላይ ሊያጸድቅ በሞከረ ጊዜ ነበር፡፡ የኢራቅን ጦርነት ካየን ይህ በካፒቶል ሂል የተለመደ የሆነ እርምጃ ሲሆን፣ ኮንግረሱ በሕገ መንግሥት ከተሰጠው ሥልጣን ጋር የሚስማማ አካሄድ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሆኖም ግን አይፓክ እርምጃውን በጽኑ ተቃወመ፡፡ ምክንያቱም ሕጉ በኢራን ላይ የሚወሰደውን ወታደራዊ አማራጭ ከጠረጴዛው ላይ

እንዲህ ስለሚያደርግ ነው። ከዚያ በኋላ በኮንግረሱ ውስጥ ባሉት እፍኝ የማይሞሉ ደጋፊዎቹ ማለትም ጋሪ ኤቨርማን፣ ኢሊዮት ኤንግልና የኔቫዳው ዲሞክራት ሼሊ በርክሌይን በመሳሰሉ አፍቃሪ-እስራኤል ተወካዮች አማካይነት ረቂቅ ሕጉ እንዲወገድ ተደርጓል።[96] ከአንድ ወር በኋላ የሚኖሶታ ስቴት ዲሞክራት ኮንግረስማን ካፑዋኖ ረቂቅ ሕጉ ለምን እንዲወገድ እንደተደረገ ለቀረበላቸው ጥያቄ "አይፓክ" በማለት መልስ ሰጥተዋል። የኦሃዬው ዲሞክራቲክ ፓርቲ ተወካይ ዴኒስ ኩቺኒችም እንዲሁ ተመሳሳይ መልስ ሰጥተዋል።[97]

እስራኤልና በሎቢው ውስጥ ያሉ የተወሰኑ አካላት በኢራን ላይ ወታደራዊ እርምጃ እንዲወስድ ከሚያደርጉት ግፊት ባሻገር ኢራንን በኃይል ለማጥቃት ማስፈራራቱ ውጤታማ ያልሆነ አካሄድ መሆኑ በሰፊው ይታመናል። ከዚያ ፈቀቅ ብሎ የሀገሪቱን የኒኩሊዬር ተቋማት ማጥቃት ደግሞ መዘዙ እጅግ የከፋ ነው የሚሆነው።[98] ምክንያቱም ድርጊቱ መካከለኛውን ምሥራቅ የሚያመሰቃቅለው ከመሆኑም በላይ፤ ኢራንን አስቆጥቶ በዩናይትድ ስቴትስና በአጋሮቿ ላይ የበቀል ዱላዋን እንድታሳርፍ ይጋብዛታል። ያ ሁኔታ አንድ ጊዜ ከተከሰተ ደግሞ ዋሽንግተን በሌላ ሙስሊም ሀገር ላይ ዘመቻ ለማድረግ እንድትገደድ ያደርጋታል። የአሜሪካ ጦር ኢራቅ ውስጥ በምስቅልቅሉ ማጥ ውስጥ እንደተዘፈቀ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፣ ኢራን ከኢራቅ ይልቅ ትልቅ የቆዳ ስፋትና ሕዝብ ያላት ሀገር ናት። በተጨማሪም ኢራን ከተጠቃች የኒኩሌር መርሐ-ግብሯን ልታቆም ይቅርና ጥረቷን በእጥፍ ጨምራ እንደምትቀጥል እርግጠኛ መሆን ይቻላል። ይህም ኢራቅ በ1981 - የኒኩሊዬር ተቋሟ በእስራኤል ከወደመባት በኋላ በድብቅ የኒክሊዬር ኃይል የመገንባት ጥረቷን መቀጠሏን ያስታውሰናል። ለዚህም ነው በአውሮፓ የደህንነት ጉዳዮች ኤክስፐርት የሆኑት ቻርለስ ኩንቻን እንደሚከተለው ማለታቸው የማያስደንቀው፣ " የኢራንን ኒኩሊዬር በተመለከተ አውሮፓ ውስጥ የጦርነት መንገድ ተመራጭ ነው የሚል ፖሊሲ እስካሁን አልገጠመኝም።[99]

ኢራን የኒኪሊዬር መርሃ-ግብሯን ካላቋረጠች ወታደራዊ እርምጃ እንዲወሰድባት የሚፈልግ ሕዝብ ያላት ሐገር እስራኤል ብቻ ናት።

ግንቦት/2007 ላይ በተደረገ ጥናት መሠረት ኢራን እንድትጠቃ የሚፈልጉ እስራኤላውያን አሃዝ ወደ 71 ከመቶ ተጠግቷል።[100] በተመሳሳይ ሁኔታ በሎቢው ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ድርጅቶች በኢስላማዊ ሪፖብሊኳ ላይ ጦርነት እንዲደረግ የሚፈልጉ ሆነው ተገኝተዋል። በ2007 በጡረታ የተገለሉት ጄኔራል ዊስሊ ክላርክ የቡሽ አስተዳደር በኢራን ላይ ለመዝመት ያሰበ ስለሚመስልበት ሁኔታ ተጠይቀው ሲመልሱ፡- ‹‹በእስራኤላውያን የሕትመት ውጤቶች ላይ የሚወጡትን ጽሑፎች ማንበብ አለባችሁ። በጉዳዩ ላይ ምንም እንኳን የአይሁድ ማሕበረሰብ የተከፋፈለ አስተያየት ቢኖረውም ጦርነቱ እንዲደረግ የሚፈልጉ በርካታ ሰዎች ከኒውዮርክ የሚያደርጉት ግፊት በባለሥልጣናቱ ላይ እያረፈ ይኖራል›› ብለዋል። ክላርክ በዚህ ንግግራቸው ፀረ-ሴማዊ የሚል ቅጥያ ወዲያው የተለጠፈላቸው ሲሆን ጋዜጠኛው ማቲው የግሲሲያስ ‹‹ክላርክ የተናገሩት ነገር ሁሉ ትክክል መሆኑን ሁሉም ያውቃል›› በማለት ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ አስቀምጦታል።[101] ጉዳዩን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ የቀድሞው የተ.መ.ድ. የጦር መሣሪያ ተቆጣጣሪ አባል የነበሩትና በኋላም ደራሲ በመሆን በ2000 ‹ታርጌት ኢራን› የሚል መጽሐፍ ያዘጋጁት ስኮት ሪተር እንዲህ ብለዋል፡- “ግዴላችሁም፤ ምንም ጥርጣሬ አይኑራችሁ፣ አሜሪካ ኢራንን ከወረረች ያ ጦርነት እስራኤልንና ሌላውንም አካባቢ ሁሉ የሚያዳርስ ነው የሚሆነው።”[102] በአጭሩ ለማስቀመጥ እስራኤልና ሎቢው በዚህ ጉዳይ ላይ ተጽዕኖ ባይፈጥሩ ኖሮ ኢራንን በወታደራዊ ኃይል ስለመደብደብ ያን ያክል ሞቅ ያለ ውይይት አይኖርም ነበር።

የመጨረሻው መጥፎ አማራጭ

ቀደም ብለን እንደገለጽነው ለቡሽ አስተዳደር ብልጫ ያለው ምርጫ ኢራንን በኃይል እርምጃ ማስፈራራትን በማስወገድ አጠቃላይ ከሆነ ስምምነት ላይ መድረስ ነው።[103] በመሠረቱ ይህ ስትራቴጂ በትክክል ይሠራና አይሠራ እንደሆነ እርግጠኛ መሆን ቢያስቸግርም ቅሉ፣ ባለፉት ጊዜያትም ሆነ ለወደፊቱ ሊሠራ ይችላል ብሎ ለመናገር ጥሩ ምክንያት ይኖራል። ኢራን ከመስከረም 11 በኋላ ከዩናትድ ስቴትስ ጋር መስማማት እንደምትሻ በተለያዩ ሁለት አጋጣሚዎች ምልክቶችን አሳይታለች።[104] ዩናይትድ ስቴትስ የታሊባንን መንግሥት በ2001 ማብቂያ ላይ ለመገርሰስ በዘመተች ጊዜ ኢራን በአፍጋኒስታን ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ኢላማዎችን ከመጠቆም ጀምሮ ከሰሜኑ ተጓዳኝ ጦር ጋር ትብብር በማድረግ ረድታለች። ጦርነቱ እንደተጠናቀቀም ቴህራን በካቡል የአሜሪካ ሽሪክ የሆነ መንግሥት ይቋቋም ዘንድ የበኩሏን አድርጋለች። በተመሳሳይ ጊዜ የኢራኑ ፕሬዚዳንት ካታሚ ከአሜሪካ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻል እንደሚፈልጉና አፍጋኒስታን ውስጥ ያሳዩት የትብብር መንፈስ በዚያ አቅጣጫ ለሚያደርጉት ጉዞ እንደ ዋነኛ እርምጃ እንደሚቆጠር ግልጽ አድርገዋል።

በ1990ዎቹ እንደሆነው ሁሉ በሲ.አይ.ኤና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ የካታሚን ቃል በማመን ከቴህራን ጋር ግንኙነቱን የማደሱ ጥረት ተጀምሮ ነበር። ዳሩ ግን በአስተዳደሩ ውስጥና ከውጭም ያሉ ኒዎኮንሰርቫቲቮች ይህን ሃሳብ በጽኑ በመቃወማቸው ከኢራን ጋር እንደተካረሩ መቆየቱን መረጡ። ቡሽና ቼኒም የእነርሱን ሃሳብ እንዲደግፉ ለማድረግ ግፊታቸውን አጠናከሩ። በዚሁ መሠረት ጥር/2000 ላይ ቡሽ ለሃገሪቱ ሕዝብ ባደረጉት ንግግር ኢራን በአፍጋኒስታኑ ጦርነት ላሳየችው ትብብር ምጸት በሚመስል አኳኋን "የሠይጣን ዛቢያዎች" በሚሉት ስብስብ ውስጥ በማካተት ሸልመዋታል። በተጨማሪም ቡሽ በቀጣዩ ወር ምንም እንኳን ኢራቅ ውስጥ የመንግሥት ለውጥ በማድረጉ ሃሳብ ላይ ቢጠመዱም ቅሉ፣ ከዚያ መልስ የኢራንን መንግሥትም እንደሚያስወግዱ ግልጽ አደረጉ።

የአሜሪካ መንግሥት በእርሷ አንፃር የሚከተለው አቋም ይህንን ቢመስልም ኢራን ቀደም ሲል በክሊንተን አስተዳደር ጊዜ በ1997 እንዳደረገችው ሁሉ ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር ግንኙነቷን ለማሻሻል በ2003 ጥረት ማድረጓ አልቀረም፡፡ ካታሚ የኢራንን የኒኩሊዬር መርሐ-ግብር አስመልክቶም ለመደራደር ዝግጁ መሆናቸውን ገለጹ፡፡ ኢራን እንቅስቃሴዎቿን በሙሉ ግልጽ እንደምታደርግና የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ለመገንባት እቅድ እንደሌላትም ጨምረው አስረዱ፡፡ ሽብርተኝነትን በተመለከተም ኢራን ለየትኛውም የፍልስጤም ተቃዋሚ ቡድን (ሃማስ፣ ኢስላሚክ ጀሃድ ወዘተ...) የምትሰጠውን ቁሳዊ ድጋፍ እንደምታቆምና እስራኤል በ1967 ወደነበረችበት ድንበሯ የምትመለስ ከሆነም ቡድኖቹ በሲቪል እስራኤላውያን ላይ የሚያደርጉትን ጥቃት እንዲያቆሙ ጫና የምታደርግ መሆኗን ገለጹ፡፡ ሂዝቡላህን አስመልክቶ የኢራን ዓላማ በሊባኖስ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ዋነኛ የፖለቲካ ፓርቲ (ድርጅት) እንዲሆን ማድረግ መሆኑን ካስገነዘቡ በኋላ በ2002 ሳዑዲ ያቀረባቸውንና የሁለት መንግሥታትን የመፍትሄ ሃሳብ እንደሚደግፉ ይፋ አደረጉ፡፡ በተጨማሪም ካታሚ ኢራቅ እንድትረጋጋ ለማድረግ ኢራን እገዛዋን እንደምትለግስ፣ በምላሹም አሜሪካ ኢራንን 'የሠይጣን ዛቢያዎች' ከምትላቸው ሀገራት ዝርዝር ውስጥ እንድትሰርዛትና ሃገራቸውን በወታደራዊ ኃይል እንዳታጠቃ እንደሚፈልጉ በግልጽ አስቀመጡ፡፡ ማዕቀቡ እየተደራረበ ቢቀጥልባትም "ኢራን የምትሻው ሰላማዊ የሆነ የኒኩሌዬር ቴክኖሎጅን መጠቀም ነው" በማለት ፍላጎታቸውን ይፋ ያደረጉት ካታሚ ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር አጠቃላይ የሆነ ስምምነት ለማድረግ የሚያስፈልጉ የመፍትሄ ሃሳቦችን ጭምር ነበር ያቀረቡት፡፡[105]

ኢራን ይህን የስምምነት ሃሳብ ያቀረበችው ግንቦት 2003 ዩናይትድ ስቴትስ በኢራቅ አስደናቂ ድል በተቀዳጀችበት አፍላ ወቅት ነበር፡፡ ይህም ድል በአፍጋኒስታን የተገኘውን ተከትሎ የተገኘ ተጨማሪ ድል ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ አጠቃላዩን ሁኔታ የታዘቡ ብዙ ሰዎች ዩናይትድ ስቴትስ ምናልባትም መካከለኛው ምሥራቅን እርሷ በምትፈልገው መልኩ ቅርፅ ማስያዝ የምትችል አድርገው ገምተዋል፡፡ እርግጥ ነው ወቅቱ ኢራን ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር መደራደሯ ግዴታ የመሰለበት ጊዜ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ምክንያቱም ዩ.ኤስ.አሜሪካ የነበራት ክብርና ተደማጭነት የመጨረሻው ጫፍ ላይ የደረሰበትና የኢራንም ጎጂነት ከባድ ሆኖ የታየበት ነበር። እንዳለመታደል ሆኖ አሜሪካ የተሰማትን ጊዜያዊ የድል ስካር መቋቋም ያልቻሉት ቡሽ ከመደራደር ይልቅ ትዕዛዝ ማስተላለፉን ነበር የመረጡት። የቡሽ አስተዳደር በኢራን ላይ ግትር አቋም እንዲከተል ትፈልግ የነበረችው እስራኤል ብቻ ሳትሆን በሎቢው ውስጥ የነበሩ ኒዎኮንሰርቫቲቮችና ሌሎችም አካላት ጭምር ነበሩ። ኻታሚ ያቀረቡትን የሰላም ሃሳብና በኢራንና በዩናይትድ ስቴትስ መካከል አጠቃላይ መግባባት እንዲኖር ያደረጉትን ጥሪ ቡሽ ውድቅ ያደረጉት ሲሆን፣ ባለሥልጣኖቻቸውም ጭምር እንዳይቀበሉት ከልክለዋቸዋል።

ምናልባት ያንን ለሰላም የተዘረጋ እጅ ተቀብለውት ቢሆን ኖሮ ዛሬ በኢራንና አሜሪካ መካከል ትልቅ የመግባባት ዕድል ሊኖር እንደሚችል መገመት አይከብድም። በኢራንም በኩል ቢሆን '' ታላቁ ሠይጣን'' ብለው ከሚጠሩት የአሜሪካን መንግሥት ጋር የሰላም ድርድር ብሎ ነገር እንዳይኖር ወጥረው የያዙ ጠጣር መስመረኞች እንደነበሩ ግልጽ ነው። የሆነ ሆኖ ቡሽ በኻታሚ የቀረበላቸው የእርቅ ሃሳብ ከሌሎች አማራጮች የተሻለ እንደመሆኑ፣ አለመቀበላቸው ሞኝነታቸውን ያሳያል። ቡሽ ያንን የእርቅ ሃሳብ ተቀብለው ቢሆን ኖሮ አሁን በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ግንኙነት ወደ መጥፎ ደረጃ ያደረሱትና ለሚያደርጓቸው ንግግሮች የኃላፊነት ስሜት የማይሰማቸው አህመዲን ኤጃድ ወደ ሥልጣን አይመጡም ነበር። ከዚያ በኋላ የድርድሩ ሃሳብ ባይሳካና ኢራንም የኋላ ኋላ የኒኩሊዩር አረር ወደ ማበጀቱ ሂደት ከተቃረበች ዩናይትድ ስቴትስ ሌላኛውን አማራጭ ከመከተል የሚያግዳት ነገር አልነበረም።

ምንም እንኳን በ2001 ወይም በ2003 እንደነበረው አጋጣሚ ስኬት የማግኘት እድሉ የመነመነ ቢመስልም ዛሬም ቢሆን ከኢራን ጋር መደራደርና መስማማት ይቻላል። የሰላም እድሉ ሊመናመን የቻለው የአሜሪካ የመደራደር አቋም ኢራቅ ውስጥ ባለው ሁኔታ የተሸረሸረ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የኢራን መሪዎች ቡሽን ላለማመን በቂ ምክንያት ያላቸው በመሆኑ ጭምር ነው። ከዚህም በተጨማሪ በኢራን የፕሬዚዳንት መንበር

ላይ ኻታሚን ተክተው ማህሙድ አህመዲን ኢጃድ የተቀመጡ ሲሆን፣ እርሳቸው ደግሞ ከቡሽ አስተዳደር ጋር ለመደራደር ያላቸው ፍላጎት አነስተኛ ነው። የሆነ ሆኖ አሁንም ቢሆን ከስምምነት ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ በቂ ምክንያቶች አሉ ማለት ይቻላል። የሰላሙን መንገድ መከተሉ ኢራን የኒኩሊዬር ባለቤት ለመሆን የጀመረችውን ጉዞ የሚገታ ብቻ ሳይሆን ዩናይትድ ስቴትስ በአፍጋኒስታንና በኢራቅ ያጋጠሟትን ምስቅልቅል ሁኔታዎች መልክ እንድታስይዝ ይረዳታል። ለዚህም ነው የኢራቅ ጥናት ቡድን በ2006 ታህሣሥ ላይ ፕሬዚዳንት ቡሽ ከኢራን ጋር ከመፋጠጥ ይልቅ መስማማቱን እንዲመርጡ ሃሳብ ያቀረበው።[106] የቡደኑ አባላት እንደተገነዘቡት የቡሽ አስዳደር የተከተለው ኢራንን በጠላትነት ፈርጆ የኃይሉን አማራጭ የመከተል ስትራቴጂ ኢራን በአፍጋኒስታንና ኢራቅ በቀጥታ ጣልቃ እንድትገባና በዚያ ያለውን ሰብዓዊና ማህበራዊ ቀውስ በማባባስ ከድጡ ወደማጡ እንድታሽጋግረው ግፊት ፈጥሮላታል። ይህ ደግሞ መሉ በሙሉ ከአሜሪካ ፍላጎት ጋር የሚቃረን ነው ማለት ይቻላል።[107]

ዩናይትድ ስቴትስ ከኢራን ጋር የሰላም ውል እንድትቋጥር የሚፈልጉ በርካታ የዚህ አቋም ደጋፊዎች በራሷ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ይገኛሉ።[108] ቀደም ብለን እንደገለጽነው በሲ.አይ.ኤ፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በወታደሩም ውስጥ ያሉ በርካቶች ይህን ሃሳብ ይደግፋታል። የኢራቅ ጥናት ቡድን ውጤቱን ከመግለጹ በፊት 2006 ህዳር ላይ የተደረገ ጥናት ይፋ እንዳደረገው 75 ከመቶ የሚሆኑ አሜሪካውያን ሀገራቸው ከኢራን ጋር የተሻለ ግንኙነት ማድረግ ትችል ዘንድ ከኢራን መንግሥት ጋር መደራደር እንዳለባት ያምናሉ። 22 ከመቶ የሚሆኑት ብቻ ናቸው ዩናይትድ ስቴትስ በኢራን ላይ ወታደራዊ ኃይሏን ተጠቅማ በማስፈራራት ግፊት እንድታሳድር የሚፈልጉት።[109] በኢራቅ ጥናት ቡድን የቀረበውና ከብዙ ኮሚቴዎች የተውጣጡ ስመጥር ሰዎች የተካፈሉበት የእርቅ ሀሳብ ለሰላሙ ሂደት አስፈላጊነት የቀረበ ሌላው ማስረጃ ነው ማለት ይቻላል። ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ የእስራአልን አቋሞች በብዛት በመተቸት የሚታወቀው የኒውዮርክ ታይምሱ ቶማስ ኤል ፍሪድማንም ጭምር በ2007 በጻፈው አስተያየት ኢራንን "የዩናይትድ ስቴትስ ተፈጥሮአዊ አጋር" ብሏታል።[110]

ምንም እንኳን ዩናይትድ ስቴትስ ከኢራን ጋር አጠቃላይ ከሆነ ስምምነት ላይ መድረሷ ከስትራቴጂያዊነቱ አንፃር መልካም ቢሆንም፣ እንዲሁም በአሜሪካ ውስጥም ሆነ ውጭ ሰፊ ድጋፍ ቢኖረውም፣ በቅርብ ጊዜያት ውስጥ ይደረጋል ተብሎ አይታሰብም። ምክንያቱም እስራኤልና ሎቢው ከ1993 ጀምሮ ከኢራን ጋር የሚደረጉ የስምምነት ጅማሮዎች ውድቅ እንዲደረጉ በትጋት እየተንቀሳቀሱ በመሆናቸው ነው። በእርግጥም ደግሞ ሎቢው፣ የኢራቅ ጥናት ቡድን ባቀረበው ሃሳብ መሠረት የቡሽ አስተዳደር ከኢራን ጋር የጀመረውን የሰላም ጥረት ከመንገዱ ወጥቶ አሰናክሏል። የቡድኑ ዘገባ በወጣ ጊዜ እንደ ፎርዋርድ ጋዜጣ አገላለጽ፡- “የአይሁድ ቡድኖች ከኢራን፣ ሶሪያና ፍልስጤም ጋር የሚደረገውን ንግግር በምሬት ተቃውመውታል›› ብሏል። ‹‹በዚያም አለ በዚህ›› ይላል ፎርዋርድ "ውስጥ አዋቂዎች እንደሚናገሩት የእስራኤል ዋነኛዋ የስጋት ምንጭ ኢራንና የኒኩሊዬር መርሐ-ግብሯ እንጂ ሶሪያም ሆነች ፍልስጤማውያን አይደሉም።”[111]

ኢራን የኒክሊዬር ማበልጸግ ሂደቷን እስካላቆመች ድረስ ወታደራዊ እርምጃ እንደሚወሰድባት ማስፈራራቷን ዩናይትድ ስቴትስ እንድትቀጥል ሎቢው ይፈልጋል። ይሁን እንጂ ይህ ማስፈራሪያ ባለፉት ጊዜያትም ሆነ ለወደፊም ውጤታማ ይሆናል ተብሎ አይጠበቅም። ይህም ሆኖ ጥቂት አሜሪካውያን የእስራኤል ደጋፊዎች በተለይም ኒዎኮንሰርቫቲቮች፣ ዩናይትድ ስቴትስ አሁንም ማስፈራራቷን እንድትቀጥል ይሻሉ። ምንም እንኳን ፕሬዚዳንት ቡሽ ቢሯቸውን ከመልቀቃቸው በፊት ኢራንን ለማጥቃት ሊወስኑ የሚችሉበት የተወሰነ እድል እንዳለ ቢገመትም፤ እርግጠኛ ሆኖ መናገር ግን አይቻልም። የፕሬዝዳንታዊ ተወዳዳሪዎች ካደረጓቸው ንግግሮች መገመት እንደሚቻለው ምናልባት ኢራን የኒኩሊዬር ግንባታዋን ከቀጠለች የእርሳቸው (የቡሽ) ተተኪ የሚሆነው ፕሬዚዳንት ያንን እርምጃ ሊወስድ ይችላል። ዩናይትድ ስቴትስ በኢራን ላይ ጥቃት ከከፈተች እርምጃው ለእስራኤል ተብሎ የተደረገ እንደመሆኑ ለሚፈጠረው አደገኛ ሁኔታ ሎቢው ትልቅ ኃላፊነት መሸከም ይኖርበታል። ምክንያቱም አብዛኛውን ግፊት በማድረግ ይህን የአሜሪካን ብሔራዊ ጥቅም የሚጻረር እርምጃ የገፋፋ በመሆኑ።

ምዕራፍ አስራ አንድ

ሉቢውና ሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት

በ2006 በጋ ላይ እስራኤል ከሊባኖስ ጋር 34 ቀናት የፈጀ ጦርነት አካሄደች። ሐምሌ 12 ቀን ሂዝቡላህ የተባለውና ደቡብ ሊባኖስን የተቆጣጠረው የሺዓይት ቡድን የእስራልን ድንበር አቋርጦ በመግባት በርከት ያሉ ወታደሮች ገድሎና ማርኮ ወደ ድንበሩ አፈገፈገ። ለዚህ ወረራ አጸፋ ይሆን ዘንድ የእስራኤል ጦር በሊባኖስ ላይ ትልቅ ዘመቻ በመክፈት ከአንድ ሺህ አንድ መቶ በላይ ሰዎችን ገደለ። ከሚቾቹ ውስጥ አብዛኛዎቹ ሲቪሎችና በግምት አንድ ሶስተኛው ሕፃናት ነበሩ። የሊባኖስን መሠረተ ልማት፣ ማለትም መንገዶችን፣ ድልድዮችን፣ የቢሮና የመኖሪያ ሕንፃዎችን፣ የነዳጅ ማከፋፈያዎችን፣ ፋብሪካዎችን፣ የውሃ ማከፋፈያ ጣቢያዎችን፣ የአየር ማረፊያዎችን፣ መኖሪያ ቤቶችንና የገበያ አዳራሾችን ሳይቀር አፈራረሰ።[1] ምንም እንኳ የእስራኤልን ራስን የመከላከል መብት የተገዳደረ ማንም ባይኖርም፣ ድንበር ያለፈና ጭካኔ የተሞላበት የሆነው የአጸፋ ምላሿ ግን በመላው ዓለም ውግዘትን አስከተለ።

እስራኤል ምንም እንኳን የአሜሪካን ጠንካራ ድጋፍ ብታገኝም በመጨረሻ ወታደራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ድል ለመቀዳጀት ሳትችል ቀርታለች። በአንጻሩ ሂዝቡላህ ከጦርነቱ በኋላ የሕዝብ ድጋፉና ክብሩ ከፍ ብሎ ሊታይ በቅቷል። የእስራኤል መከላከያ ሠራዊት ኢታማዦር ሹም ጄኔራል ዳን ሃሉትዝ ከጥቂት ወራት በኋላ በዚሁ ጦርነት ጦስ ከኃላፊነታቸው በፈቃዳቸው የተነሱ ሲሆን፣ በእስራኤል መንግሥት በይፋ የተቋቋመና በቀድሞው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ጃኛ አሊያሁ ዊኖግራድ የሚመራ አጣሪ ኮሚሽን የእስራኤልን የጦር አቅድና አያያዝ አስመልክቶ ነቀፋ ሰንዝሯል። በተለይም ደግሞ የዊኖግራድ ኮሚሽን በደረሰበት መደምደሚያ የእስራኤል መሪዎች ለሂዝቡላህ ጠብ ጫሪ ድርጊት ሁሉን ያቀፈ አማራጭ ለመፈለግ ያለመቻላቸውን ተችቷል። "ወታደራዊውን ዘመቻ በአግባቡ ለማቀናጀትና

ትክክለኛውን ዒላማ ለመምታት አለመቻል ዋነኛው የመሪዎች ድክመት ነው" ካለ በኋላ፡- ''ግልጽ ያልሆነና ሊሳካ የማይችል ግብን የመከተል ጥፋት ፈጽመዋል'' በማለት አማርሯል።[2]

ጦርነቱ በሌላ በኩል ለዩናይትድ ስቴትስ ፖለቲካም ቢሆን መጥፎ ውጤት ያስከተለ ነበር። ምክንያቱም የቡሽ አስተዳደር በመካከለኛው ምሥራቅ ካገኛቸው ስኬቶች መካከል እንደ አንዱ የሚቆጠረውንና "የጽድ አብዮት" (Cedar revolution) በሚል መጠሪያ የሚታወቀውን የ2005ቱን አብዮት ተከትሎ በሊባኖስ ሥልጣን ላይ የወጣውን የፉዓድ ሲኞራ መንግሥት ያዳከመ በመሆኑ ነው። ጦርነቱ በተጨማሪም ኢ-መደበኛ (Informal) የሆነውን የሂዝቡላህ፣ ሶሪያና ኢራንን ተጓዳኝነት ይበልጥ እንዲጠናከር በማድረግ በክልሉ ፀረ-ኤሜሪካ አመለካከት እንዲዳብር አድርጓል። የፀረ-ሽብርተኝነቱን ዘመቻ በማዳከምም ዩናይትድ ስቴትስ በአካባቢው የምትከተለውንና ኢራቅንና ኢራንን አስመልክቶ መግባባት ላይ ለመድረስ የጀመረችውን ጥረት ይበልጥ አሠነካክሎታል።

ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ምንም እንኳን የእስራኤል ባለሥልጣናት ጦርነቱን በአግባቡ ይዘው ለመምራት ባለመቻላቸው ቢወቀሱም፣ ዩናይትድ ስቴትስ ገደብና ቅድመ ሁኔታ አልባ እርዳታዋን ከጦርነቱ በፊትም ሆነ በጦርነቱ ጊዜያት ለእስራኤላውያን በመስጠት የጥፋታቸው ተጋሪ ሆናለች። ጦርነቱ ሐምሌ 12 ከመጀመሩ በፊት ሂዝቡላህን ለመውጋት እንደምትሻ እስራኤል ለዩናይትድ ስቴትስ ገልጻላታለች። ዋሽንግተንም አረንጓዴ መብራት በማሳየት መስማማቷን አሳውቃታለች። ከሌላው ዓለምና ከሞላ ጎደል ከሁሉም ዋና ዋና ዲሞክራሲያዊ መንግሥታት በተለዩ መልኩ ዩናይትድ ስቴትስ በጦርነቱ ጊዜ የእስራኤልን ድርጊት ባለመተቸት ትልቅ ግምት የሚሰጠው ዲፕሎማሲያዊና ወታደራዊ ድጋፏን ለግሳታለች። የእስራኤል ሎቢ በጦርነቱ ጊዜ አሜሪካ ከእስራኤል ጎን እንድትቆም ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ ተንቀሳቅሷል።

ሁኔታውን በጽሞና ማጤን ከተቻለ እስራኤል ለሂዝቡላህ ጠብ ጫሪነት አፀፋ ይሆን ዘንድ ያን ያክል የማይመጣጠን ኃይል መጠቀሟን የቡሽ አስተዳደር አለመንቀፉ ስትራቴጂያዊ ስህተት ብቻ ሳይሆን፣ ኢ-ሞራላዊም ጭምር ሆኖ ታይቷል። የአሜሪካ ትችት አልባ ድጋፍ የእስራኤልንም

ፍላጎት የጠበቀ አልነበረም። የዊኖግራድ ኮሚሽን ሪፖርት (ዘገባ) እንዳመለከተው የእስራኤል መሪዎች፡- “ሁሉንም ዓይነት አማራጮች ቢፈትሹ ኖሮ እስራኤል በጣም በተሻለ አቋም ላይ ለመገኘት በበቃች ነበር።” በሌላ አገላለጽ እስራኤል ሲባኖስን ለመውረር በማሰብ እቅዷን ስትገልጽላት ዩናይትድ ስቴትስ ሌላ የተለዬ መንገድ እንድትከተል እስራኤልን ብትገፋፋት ኖሮ የተሻለች ወዳጅዋ ልትሆን በቻለች ነበር። ዩናይትድ ስቴትስ እንዲያ ማድረግ ችላ ቢሆን ኖሮ፣ እስራኤል አጸፋዋን በእርጋታ በማጤን በሲባኖስ የገጠማትን ታላቅ የፖለቲካ ኪሣራ ማስወገድ ይሳካላት ነበር።

ሁለተኛው የሲባኖስ ጦርነት ከመጀመሩ በፊትና በጦርነቱም ጊዜ ሎቢው በዩ.ኤስ.አሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ላይ ከባድ ተጽዕኖ ሲያሳድር መቆየቱን እስራኤላውያኑና ብዙዎቹ አሜሪካውያን ደጋፊዎቻቸው ማመን አይፈልጉም። ይህን ክስ ለማስተባበልም የተለያዩ ማብራሪያዎችን ይሰጣሉ። ከፊሎቹ፡- ‹‹ዩ.ኤስ.አሜሪካ እስራኤል ለምትወስዳቸው የጥቃት እርምጃዎች ሁልጊዜም ፍንክች የማይል ድጋፍ መስጠቷ ሌላ ሳይሆን የአሜሪካ ሕዝብ አይሁዳዊቷን ሀገር ለመርዳት ያለው ጥልቅ የሆነ ዝግጁነት ነፀብራቅ ነው›› በማለትም ይከራከራሉ። ሌሎች ደግሞ ‹‹እስራኤል ከሂዝቡላህ ጋር ባደረገችው ፍልሚያ ራሷን ለአሜሪካ ጥብቅና እንደቆመች ሀገር አድርጋ ነበር የቆጠረችው›› ይላሉ። በዚህ አመለካከት መሠረት የአሜሪካ ሕዝብ፣ መሪዎቹ እስራኤልን በከፍተኛ ደረጃ እንዲደግፉለት ይፈልጋል። ስለሆነም ፕሬዚዳንት ቡሽም ሆኑ ኮንግረሱ እስራኤልን በመደገፍ የሕዝቡን ፈቃድ እየሞሉ ነው። እናም በዚህ የክስተቶች አተረጓጎም መሠረት ከጦርነቱ ጀርባ የነበረው ዋነኛ አንቀሳቃሽ ኃይል የቡሽ አስተዳደር ሲሆን ትዕዛዙን የምትፈጽምለት ደግሞ ደንበኛው የሆነችው እስራኤል መሆኗ ነው። ይህ በአማራጭነት የቀረበ አገላለጽ በተወሰኑ ሰዎች ዘንድ አሳማኝ እንደሆነ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ሆኖም ግን ከተጨባጭ መረጃ ጋር የሚሄድ አይደለም።

ከጦርነቱ በፊት የተነደፈው እቅድ

እስራኤል ባለፉት አርባ ዓመታት ውስጥ ሊባኖስን ለበርካታ ጊዜያት አጥቅታለች፡፡ ይሁን እንጂ በሊባኖስ ግዛት ውስጥ ያደረገችው እውነተኛው ውጊያ አንድ ብቻ ነው፡፡ በሜናሂም ቤጊን የጠቅላይ ሚኒስትርነትና በአሪዮል ሻሮን የመከላከያ ሚኒስትርነት ዘመን በ1982 ሰኔ ወር ላይ እስራኤል ሊባኖስን ወረረች፡፡ ያ ክስተት የተፈጸመው እስራኤል የሊባኖስን ግዛት ለቃ ከመውጣቷ ከአሥራ ስምንት ዓመታት በፊት ሲሆን ከሊባኖስ ገፍቶ ያስወጣትም ሂዝቡላህ ነበር፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስራኤልና ሂዝቡላህ መራር ጠላቶች ሆነው የቆዩ ከመሆኑም በላይ በእስራኤል-ሊባኖስ ድንበር ላይ አልፎ አልፎ ቀለል ያሉ ግጭቶች መከሰታቸው አልቀረም፡፡ ይህ ዓይነቱ ግጭት ነበር ሐምሌ 12/2006 የፈነዳውን ሁለተኛን የእስራኤል ሊባኖስ ጦርነት የቀሰቀሰው፡፡

ሂዝቡላህ ከሶሪያና በተለይም ከኢራን ያገኛቸውን በርካታ ሚሳዬሎችና ሮኬቶች ከእጁ ለማስጣል እስራኤል ከሐምሌ 2ቱ የሂዝቡላህ ተንኳሽ ድርጊት በፊትም ቢሆን ጥቃት የመፈጸም እቅድ ነበራት፡፡ ጄራልድ ስቴይንበርግ የተባሉ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው እስራኤላዊ ስትራቲጂስት ይህን ጉዳይ አስመልክተው ሲናገሩ፡- ‹‹ከ1948 ጀምሮ እስራኤል ካደረገቻቸው ጦርነቶች ሁሉ እንደዚህኛው በሚገባ የተዘጋጀችበት ጦርነት የለም፡፡ ያ ማለት ዝግጅቱ የተጀመረው እስራኤል ከሊባኖስ ከወጣችበት ከግንቦት 2000 ጀምሮ፣ ማለትም ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ፣ ሂዝቡላህ ሚሳዬል እንዳያከማችና እስራኤልንም እንዳያጠቃ ለማገድ የማይቻለው መሆኑ ከታወቀ በኋላ ነበር፡፡ በ2004 ወታደራዊ ዘመቻው የሚፈጀው ጊዜ ሦስት ሳምንታት መሆኑ በሚገባ በእቅዱ ላይ ተነደፈ፡፡ ይህ አሁን በድንገት የፈነዳው ጦርነት ባያሰናክለው ኖሮ፣ ባለፉት ሁለትና አንድ ዓመታት የክለሳው ልምምድ አልቆ ሁሉም ነገር መልክ በያዘ ነበር›› ብለዋል፡፡[3]

በተመሳሳይ ሁኔታ ሳይሙር ኧርሽ እንደዘገቡት፡- “በመካከለኛው ምሥራቅ ጉዳይ ላይ እጃቸውን ያስገቡ የቀድሞና አሁንም ያሉ ባለሥልጣናት እንደገለጹልኝ ሂዝቡላህ የፈጸማቸውን የግድያና የጠለፋ ድርጊቶች እስራኤል

በሂዝቡላህ ላይ ዘመቻ ለመጀመር የሚያስችላት ማለፊያ አጋጣሚ አድርጋ ተጠቀመችበት እንጅ ወትሮውንም ለጦርነት ስትዘጋጅ ነው የባጀችው። ሂዝቡላህ ሁልጊዜም ቢሆን በየወሩ ወይም በየሁለት ወሩ አነስተኛ ትንኮሳ ማድረጉ የተለመደ ነበር" ብለዋል።[4] በእርግጥም የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሁድ ኦልመርት ለዊኖግራድ ኮሚሽን ሂዝቡላህ የእስራኤልን ወታደሮች ከገደለና ከፊሉንም ማርኮ ከወሰደ በኋላ እንደገለጹት "ሂዝቡላህ በተለያዩ ጊዜያት ለወሰዳቸው የትንኮሳ እርምጃዎች አፀፋ ይሆን ዘንድ ዘመቻ እንዲጀመር የወሰንኩት በ2006 መጋቢት ወር ላይ ነበር" ብለዋል። ግጭቱ ከመጀመሩ ከአራት ወራት በፊት መሆኑ ነው። በዚያ ጊዜ ኦልመርት የዘመቻውን አጠቃላይ እቅድ ለማየት ጠየቁ። ምክንያቱም በተፈጠረው ውዝግብ ምክንያት ድንገተኛና በቅጡ ያልታሰበበት እርምጃ ለመውሰድ ባለመፈለጋቸው ነበር። ከእርሳቸው በፊት የነበሩት አሪዮል ሻሮን ህዳር 2005 ላይ ሊባኖስ ውስጥ የሚገኙና በዘመቻው ሊደበደቡ የሚችሉ ዋነኛ ዒላማዎችን እንዲያዘጋጅ ለጦራቸው ትዕዛዝ አስተላልፈው እንደነበር ኦልመርት ጨምረው ገልጸዋል። በድንበር አካባቢ ሂዝቡላህ የእስራኤልን ወታደሮች ለመማረክ ያደረገው ሙከራ ከከሸፈ በኋላ ኦልመርት ሊባኖስን አስመልክቶ የመጀመሪያቸው የሆነውን ስብሰባ ጥር 2006 ላይ (በአባድ የራስ መሳት በሽታ የተለከፉትን ሻሮንን እንዲተኩ ከመመረጣቸው አራት ቀናት በፊት) አደረጉ። ከዚያ በኋላ በሊባኖስ የተፈጠረውን ሁኔታ አስመልክተው ከእርሳቸው በፊት ከነበሩ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ሁሉ በበለጠ ሁኔታ ተከታታይ ስብሰባዎችን አደረጉ።[5]

የእስራኤል ባለሥልጣናት በቡሽ አስተዳደር ውስጥና ውጭ ለሚገኙ ቁልፍ ሰዎች እቅዳቸውን አስመልክቶ ከሐምሌ 12 በፊት በአጭሩ የገለጹላቸው መሆኑ ተወስቷል። ሽርሽ እንዲህ ይላሉ፦ ‘‘በዩ.ኤስ.አሜሪካና በእስራኤል መንግሥታት ዘንድ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ አበጥረው የሚያውቁ የመካከለኛው ምሥራቅ ኤክስፐርቶች እንደገለጹት ከሆነ እስራኤል ሂዝቡላህን ለማጥቃት የሚያስችላትን እቅድ ነድፋ ከሐምሌ 12ቱ የሂዝቡላህ ትንኮሳ በፊት ለቡሽ አስተዳደር ባለሥልጣኖች አካፍላለች።’’ በተመሳሳይ ሁኔታ ማቲው ኬልማን በሳንፍራንሲስኮ ክሮኒክል ላይ ባሰፈረው ጽሑፍ

“ከአንድ ዓመት በፊት ከፍተኛ የእስራኤል የጦር መኮንን ለዩ.ኤስ. እና የሌሎች ሃገራት ዲፕሎማቶች፣ ለጋዜጠኞችና ለሐሳብ አፍላቂዎች (Think Tanks) ዘመቻውን አስመልክቶ የፖለቲካ ጉልበት ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ዝርዝር ማብራሪያ ሰጥቷል። በማብራሪያው ያልተጻፈ ደንብ መሠረት ገለጻውን ያደረገው መኮንን ማንነት አይታወቅም ነበር።”[6]

በጊዜው ተጨባጭ ሆኖ የቀረበ ማስረጃ እንደሚያሳየው እስራኤል ሊባኖስን ለመውረር የነደፈችውን እቅድ የቡሽ አስተዳደር አጽድቆላታል። እንደ ሳይሙር ኸርሽ አባባል፣ በዚያ ዓመት የክረምቱ መጀመሪያ ላይ -ማለትም ሂዝቡላህ ጠለፋውን ከማካሄዱ በፊት- አንድ የዩ.ኤስ. አሜሪካ መንግሥት አማካሪ እንዲህ ብለዋል፡- “በርካታ የእስራኤል ባለሥልጣናት ዋሽንግተንን በተናጠል በመጎብኘት እስራኤል ሊባኖስን በቦምብ ለመደብደብ የሚያስችላትን አረንጓዴ መብራትና ዩ.ኤስ.አሜሪካም ምን ያክል ወጪና የፖለቲካ ድጋፍ እንደምትሰጥ ለማወቅ ችለዋል። እስራኤል የድጋፍ ማሰባሰብ ዘመቻዋን የጀመረችው ዲክ ቼኒ ከሚመሩት ቢሮ ሲሆን፤ የብሔራዊ ጸጥታ ካውንስል የመካከለኛው ምሥራቅ ዴስክ ኃላፊ ኮንዶሊዛ ራይስም ቀጣይዋ ተረኛ ነበሩ።”[7]

ኢሁድ ኦልመርት ሊባኖስን ለማጥቃት ያወጡትን እቅድ ፕሬዚዳንት ቡሽ ለመደገፍ ያበቃቸውን የውሳኔ ሂደት የሚገልጽ በቂ መረጃ አልተገኘም። የሆነ ሆኖ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ኒዎኮንሰርቫቲቮች ቁልፍ ሚና እንደተጫወቱ ለማሰብ በቂ ምክንያት ይኖራል። ከመስከረም 11 በኋላ ሂዝቡላህን ለመቀጥቀጥ ያለሙት ኒዎኮንሰርቫቲቮች ብቻ አልነበሩም። ዋይት ሃውስ ውስጥ የሚኙት ሁለቱ የመካከለኛው ምሥራቅ አማካሪዎችም ጭምር ከጦርነቱ በፊትም ሆነ ጦርነቱ በተካሄደባቸው ጊዜያት ሁሉ ከእስራኤል ጎን ቆመው ሂዝቡላህን ጨምሮ በሌሎች ጠላቶቿ ላይም ጠጣሩን መስመር እንደሚከተሉ አስመስክረዋል።[8] የመጀመሪያው ኢሊዮት አብራምስ ሲሆን በብሔራዊው ፀጥታ ምክር ቤት የመካከለኛው ምሥራቅ ዴስክ የሚሠራ ቁልፍ ሰው ነበር። ኒውዮርክ ታይምስ እንደዘገበው ይህ ሰው፡- ‹‹የቡሽ አስተዳደር በሊባኖስ ጦርነት ወቅት ከእስራኤል ጎን እንዲቆም ለማድረግ ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም›› ብሏል።[9]

ሁለተኛው ሰው ዴቪድ ውርምሰር ሲሆኑ፣ የምክትል ፕሬዚዳንቱ ዲክ ቼኒ የመካከለኛው ምሥራቅ አማካሪ ነበሩ።[10] ውርምሰር በ1996 የተዘጋጀውንና ቤንጃሚን ናታንያሁን ወደ ሥልጣን ያመጣውን፣ እንዲሁም የአስሎውን የሰላም ስምምነት ውድቅ በማድረግ የመካከለኛውን ምሥራቅ ፖለቲካ ለመቀየር ወታደራዊ እርምጃ ወሳኝ ሚና የሚጫወት መሆኑን የሚሰብከውን 'ክሊን ብሬክ' የተባለ ጥናት ካዘጋጁት ሰዎች መካከል አንዱ ናቸው። 'ክሊን ብሬክ' በተለይም በሰሜን "የእስራኤልን ድንበር ደህንነት ለመጠበቅ የሚቻለው ዋነኞቹን የሂዝቡላህ ወኪሎች፣ ማለትም ኢራንን፣ ሶሪያንና ሊባኖስን አደብ በማስገዛት ነው" ይላል። አዳም ሻትዝ በኒውዮርክ ሪቪው ኦፍ ቡክስ ላይ እንደጻፈው "ውርምሰር ከሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት በፊት በሶሪያና ሂዝቡላህ ላይ ግልጽ ጦርነት እንዲታወጅ በኒዎኮንሰርቫቲቮች የሚደገፈውን አቋም በማራገብ የሚታወቁ ወደ ቡሽ አስተዳደር ጠጋ ያሉ ሰው ናቸው" ብሏል።[12] ሳይሙር ኧርሽ ቀደም ብለው እንደጠቀሱ "እስራኤል የዲክ ቼኒንና በብሔራዊ ፀጥታ ምክር ቤት የመካከለኛው ምሥራቅ ዴስክን ድጋፍ ለማግኘት ፍላጎት ነበራት" ብለዋል። ይህን ሲሉ ኦልመርት የኢሊዮት አብራምስንና የውርምሰርን ይሁንታ ይፈልጋሉ ማለታቸው ሲሆን፣ ያንንም አግኝተዋል። ይህ መሠረታዊ የሆነና የማያስደንቅ፣ እንዲሁም አወዛጋቢ ያልሆነ እውነታ እንደመሆኑ ሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት ከመቀስቀሱ አንድ ወር ቀደም ብሎ የቡሽ አስተዳደር በጦርነቱ እቅድ ላይ ስለነበረው ሚና የሚታወቅ ነገር ቢኖር ጥቂት ብቻ ነበር።

እናም እስራኤልም ሆነች ዩናይትድ ስቴትስ ሊባኖስን ለመውረር ሴራ ሲዶልቱ መቆየታቸው እውነት ነው። በሁለቱ ሀገራት ድንበር ላይ በየጊዜው የሚቀሰቅሰው ውጥረትና እስራኤል የሂዝቡላህን ሚሳይሎችና ሮኬቶች አስመልክቶ ያደረባት ስጋት የጦር ኃይሏ ችግሩን ለማስወገድ እቅድ መንደፉን ተገቢ ያደርገዋል።

ታላቁ ድጋፍ እያለ ምን ጎድሎ![13]

ጦርነቱ ከፈነዳ በኋላ በእስራኤል ላይ ከሁሉም አቅጣጫ ከባድ ትችት ቢዥጎደጎድባትም የቡሽ አስተዳደር ያልተለመደ ዲፕሎማሲያዊ ከለላ ሰጥቷታል። በተ.መ.ድ. የእስራኤል አምባሳደር ‘‘ስድስተኛው የእስራኤል ዲፕሎማቶች ቡድን አባል›› በማለት ያሞካሿቸው በተ.መ.ድ. የአሜሪካው አምባሳደር ጆን ቦልተን የፀጥታው ምክር ቤት እስራኤልን በመተቸት ያሳለፈውን ውሳኔ ድምጽን በድምጽ የመሻር መብትን (Veto) ተጠቅመው ውድቅ አድርገውታል። ከዚያም በኋላ በተባበሩት መንግስታት የተኩስ አቁም ውሳኔ እንዳይተላለፍ ለአንድ ወር ያህል ሲከላከሉ ቆይተዋል። እንደዚያ ያደረጉበት ዋነኛው ምክንያት እስራኤል በሂዝቡላህ ላይ ኃይለኛ ጡጫ ለማሳረፍና የቤት ሥራዋን በሚገባ ለማጠናቀቅ እንዲመቻት እድል ለመስጠት ነበር።[14] የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ ኮንዶሊዛ ራይስ በበኩላቸው “የአዲሱ መካከለኛው ምሥራቅ መወለድ የምጥ ውጋት”[15] በማለት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰዎች ጉዳዱን ቀለል አድርገው እንዲመለከቱት ለማድረግ ሞክረዋል። ከዚያ በኋላ የእስራኤል ጦር ወሳኝ የሆነ ድል ሊጎናጸፍ እንደማይችል ግልጽ እየሆነ በመጣ ጊዜ የቡሽ አስተዳደርና እስራኤል የተኩስ አቁም የማድረግ ፍላጎት አሳዩ። በተ.መ.ድ. በኩል ከተደረሰው የስምምነት ቁጥር 1701 ላይ ዩናይትድ ስቴትስ የእስራኤልን ጥቅም ለማስከበር ረዥም ርቀት ተጉዛለች። እርግጥ ነው የተኩስ አቁም ስምምነቱ ፊርማ በተጠናቀቀ ጊዜ የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስቴር ኢሁድ አልመርት ነሐሴ 11 ቀን ለቡሽ ደውለው በፀጥታው ምክር ቤት የእስራኤልን ጥቅም ለማስከበር ላደረጉት ነገር ሁሉ አመስግነዋቸዋል።[16]

ፕሬዚዳንቱ በተደጋጋሚ የእስራኤልን ድርጊቶች በይፋ የደገፉ ሲሆን አንድም ጊዜ የነቀፌታ ቃል ሲያሰሙ አልተደመጡም። በተ.መ.ድ. የአሜሪካ አምባሳደር ጆን ቦልተን ለፀጥታው ምክር ቤት ባሰሙት ንግግር፣ “ሂዝቡላህ ሆነ ብሎ ንፁሃንን ኢላማ እያደረገ ነው” አሉ። በሌላ በኩል ሂዝቡላህ ከሚያደርሰው የሲቪሎች ሞት በብዙ እጅ የላቀ የሆነውን የሊባኖስ ንጹሐን ዜጎች እልቂት “እስራኤል ራሷን ለመከላከል በምትወስደው እርምጃ

ምክንያት የደረሰ አሳዛኝ ክስተት" ሲሉ ተደመጡ።[17] ይህን ከመሰለው ዲፕሎማያዊ ድጋፍ በተጨማሪ የቡሽ አስዳደደር ለእስራኤል ወታደራዊ የስለላ መረጃዎችን አቀብሏል። እስራኤል የነበራት ዒላማቸውን እያነፈነፉ የሚመቱ ቦምቦች ክምችት እየተሟጠጠ በሄደ ጊዜም ከሥር በመተካት ረድቷታል።[18] ጦርነቱ በኃይል እየተፋፋመ በሄደ ጊዜም ከኢራን ለሂዝቡላህ የተላኩ ሚሳዬሎችን ጭነው ወደ ደማስቆ የሚበርሩ አውሮፕላኖች በአየር ክልከላቸው እንዳይበርሩ ቱርክና ኢራቅ እንዳያግዱ አሜሪካ ጫና አድርጋለች።[19] ሻዒ ፊልድማን የተባሉ ከጉዳዩ ጋር በሚገባ ቅርበት የነበራቸው ምሁር በጦርነቱ መገባደጃ አካበቢ እንዲህ ብለው ነበር፦ "ለፕሬዚዳንት ቡሽ ትልቅ አድናቆት አለን።[20]

በሌሎች አጋጣሚች ሲደረግ እንዳስተዋልነው እስራኤል በዚህ ጦርነት ጊዜም ከዩ.ኤስ.ኮንግረስ ጠንካራ ድጋፍ ያገኘች በመሆኑ፣ ኮንግረሱ የሚሠራበት የተለመደው የፖለቲካ ዘይቤ በማያጠራጥር ሁኔታ እንደቀጠለ መሆኑን እንገነዘባለን። ዲሞክራቶችና ሪፖብሊካኖች የእስራኤል ምርጥ ወዳጅነታቸውን ለማስመስከር አንዱ ከሌላው ጋር ተፎካከሩ። አንድ አይሁዳዊ ንቁ የፖለቲካ ተሳታፊ (poleticale activist) ሁኔታውን ከታዘቡ በኋላ እንዲህ ብለዋል፦ "በአፍቃሪ-እስራኤል አቋሞቻቸው የሚፎካከሩ የኮንግረስ አባላትን ማግኘት ምንኛ መልካም ነገር ነው!"[21] በመጨረሻም እስራኤል በሊባኖስ የፈጸመችውን ተግባር አስመልክቶ በሁለቱ ፓርቲዎች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት እስከማይኖር ድረስ አቋሞቻቸው ተዋሃዱ። ይህን ለማለት የሚቻለው በሁለቱ ፓርቲዎች መካከል በሌሎች የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዎች፣ ለምሳሌ የኢራቅን ጉዳይ አስመልክቶ ያላቸውን የጎላ ልዩነት ስናስተውል ነው። የፀረ ስም ማጥፋት ሊግ (ኤ.ዲ.ኤል) ፕሬዚዳንት አብርሃም ፎክስማን፦ "ፕሬዚዳንቱን በሌሎች ጉዳዮች 99 ከመቶ የሚተቹት ዲሞክራቶች በእስኤራል ጉዳይ ግን ሙሉ ደጋፊነታቸውን አሳይተዋል" ብለዋል።[22]

ይህን የሁለቱን ፓርቲዋች የጋራ መግባባት በመንተራስ ሐምሌ 20 ቀን 2006 ላይ የተወካዮች ምክር ቤት ሂዝቡላህን በጠንካራ ቃላት በማውገዝና እስራኤል በሊባኖስ የምትፈጽመውን ድርጊት በመደገፍ ውሳኔ አሳለፈ።

ውሳኔው ያለፈው 410 ለ 8 በሆነ ሰፊ የድምፅ ልዩነት ነበር። ሴኔቱ በበኩሉ በስልሳ ሁለት ሴናተሮች የተደገፈ ተመሳሳይ ውሳኔ አሳለፈ። የሁለቱን ፓርቲ መሪዎች ጨምሮ በተወካዮች ምክር ቤት (The House) እና በሴኔቱ የሚገኙ ዋና ዋና የዲሞክራቲክ ፓርቲ አባላት የኢራቁ ፕሬዚዳንት ኑሪ አል ማሊኪ ለኮንግረሱ ንግግር እንዳያስሙ ለማድረግ ሞክሩ። ምክንያቱም ማሊኪ እስራኤል በሊባኖስ የምታካሂደውን ፖሊሲ በመንቀፋቸው ነው።[23] የዲሞክራቲክ ፓርቲ ሊቀመንበር የሆኑትና ቀደም ሲል በሎቢው ዒላማ ውስጥ ገብተው የነበሩት ሀዋርድ ዲን የኢራቁን ጠቅላይ ሚኒስትር ፀረ-ሴማዊ እስከማለት ነበረ ርቀው የሄዱት።[24] በኮንግረሱ ውስጥ ለእስራኤል የነበረው ድጋፍ በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ የአረብ አሜካውያን መሪዎች ያልጠበቁት ነበር የሆነባቸው። ኒክ ጄ. ራህል የተባሉት የሊባኖስ ዝርያ ያላቸው የዲሞክራቲክ ፓርቲ ኮንግረስማን የተወካዮች ምክር ቤቱን ውሳኔ እንደተመለከቱ "ቃላቶቼን ለዘብ ላድርጋቸውና ሁኔታው ሆዬን አሳምሞኛል" ነበር ያሉት። የአረብ አሜሪካን ኢንስቲትዮትን የሚመሩት ጀምስ ዞግቢ ደግሞ እንዲህ አሉ፡- "ይህ በእውነቱ አስደንጋጭ ነው። ከዚህ የተሻለ ውሳኔ ላይ እንደርሳለን ብዬ አስባለሁ።"[25]

ሴናተር ሂላሪ ክሊንተን፣ ጆን ማኬይን፣ የዴላዌር ስቴት ዲሞክራቲክ ፓርቲ ተወካይ የሆኑት ጆ ባይደንና የቀድሞው የተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ኒወት ጊንግሪችን የመሳሰሉ ተስፈኛ ፕሬዚዳንታዊ ተወዳዳሪዎች እስራኤልን መደገፋቸውን ለመግለጽ ብዙ ተናግረዋል።[26] የተለዬ ስሜት ያንፀባረቁት ሪፖብሊካዊው የኔብራሳ ስቴት ተወካይ ቸክ ሄግል ሲሆኑ፣ እስራኤል በሊባኖስ የፈጸመችውንና አሜሪካ የሰጠቻትን ድጋፍ አስመልክቶ ቆጠብ ያለ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። የሄግልን አስተያየት የኮንግረስ አባላት የሆኑ ባልደረቦቻቸውም ሆኑ ሎቢው ችላ ማለቱን ነው የመረጡት። ሆኖም ግን በፕሬዚዳንታዊው ውድድር ለሚጠብቃቸው ፉክክር ምንም ዓይነት እገዛ እንደማያደርጉላቸው ያለጥርጥር ይታወቃል።[27]

ዋና ዋና የሚባሉ የመገናኛ ብዙሃንም ቢሆኑ ከእስራኤል ጀርባ መቆሙን ነበር የመረጡት። የጋዜጣ አዘጋጆችና አሳታሚዎች፣ እንዲሁም የመገናኛ

ብዙሀኑን ኢንዱስትሪውን የሚመሩ በደርዘን የሚቆጠሩ ታዋቂ አርታዒዎች ጦርነቱ ከተጀመረ ከአንድ ሳምንት በኋላ በተደረገ ዳሰሳ ከሞላ ጎደል አንዳቸውም እስራኤል ሲቪሎችን ማጥቃቷንና የሊባኖስን መሠረተ ልማት ማፈራረሷን እንዳላወገዙ ተረጋግጧል።[28] ሃያ አራት ሰዓት የተለያዩ ዘገባዎችን የሚያቀርቡ የቴሌቪዥንና በሬዲዮ ጣቢያዎች የተሞሉት በሚያሳዝን ሁኔታ አይሁዳዊቷ ሀገር በጠላት እንደተከበበችና ያንን ለመመከት በምታደርገው ጦርነትም ምንም ዓይነት ጥፋት እንዳልፈጸመች በሚገልጹ ስዕሎችና ዘገባዎች ነበር።

ይሁን እንጂ እስራኤል በጋዜጦች የፊት ለፊት ገጾችና በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የቀጥታ ዜና ሽፋኖች ላይ መልካም ገጽታ አልነበራትም። በሀርቫርድ የተደረገ ጥናት እንዳሳዬው ‹‹በኒውዮርክ ታይምስና ዋሽንግተን ፖስት የፊት ለፊት ገጾች ርዕሶች ላይ እስራኤል ቢያንስ ለሁለት ጊዜያት ያክል በተደጋጋሚ ወራሪ ተደርጋ የቀረበች ሲሆን፣ በፎቶግራፎች ደግሞ ለሶስት ጊዜያት ያክል ተመሳሳይ ገጽታ እንድትላበስ ተደርጋ ቀርባለች››[29] የዜና ሽፋንን አስመልክቶ እስራኤልን የሚያጋልጡ ዘገባዎችን በስፋት ማስወገድ የማይቻልባቸው ምክንያቶች እንዳሉ እዚህ ላይ ግልጽ ሊሆን ግድ ነው። ምክንያቱም ሂዝቡላህ በሰሜን እስራኤል መንደሮች ካደረሳቸው ጉዳቶች እጅግ በበለጠ ሁኔታ እስራኤል በሊባኖስ ላይ ያደረሰችው ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ ነው። ጦርነቱ ለ43 ሲቪል እስራኤላውያን ሞትና 300 ለሚሆኑ ሕንፃዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ መውደም ምክንያት መሆኑ ታውቋል። በተቃራኒው የእስራኤል ጦር 750 ሊባኖሳውያን ሲቪሎችን የገደለ ሲሆን በግምት 16000 የሚሆኑ ሕንፃዎችን በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ ማውደሙ ተረጋግጧል።[30] እነዚህ ቁጥሮች እንደታወቁ የጋዜጠኞች ካሜራ በፍጥነት የእስራኤል ዋነኛ ጠላት ሆነ። ሂዝቡላህና የሊባኖስ መንግሥት ጦርነቱ እንደተጀመረ ወዲያው የተኩስ አቁም ስምምነት እንዲደረስ የሚፈልጉ መሆናቸው፣ በአንጻሩ እስራኤል ግን ጦርነቱን ማሸነፍ እንደማይቻል መሪዎቿ እስኪገነዘቡ ድረስ እንዲራዘም ትፈልግ የነበረ መሆኑ መታወቁ በመገናኛ ብዙሐን ዘገባዎች ሽፋን ላይ ጉልህ ተጽእኖ አሳርፏል።

ግጭቱ በቆየባቸው ጊዜያት ሁሉ የአብዛኞቹ ጋዜጦች ርዕሰ አንቀጾች በተከታታይ አፍቃሪ-እስራኤል የሆኑ አቋሞችን ሲያንጸባርቁ የቆዩ ሲሆን፣ የአሜሪካ መገናኛ ብዙሃን ሽፋኖችም ቢሆኑ እንደ አጠቃላይ ሲታዩ የእስራኤልን ገጽታ መልካም አድርገው ያቀርቡ ነበር ማለት ይቻላል። ስለሆነም አሜሪካ ውስጥ የነበሩትን ዋነኛ የዜና ማሰራጫዎች ሁኔታ የብሪታኒያው ጋዜጣ አንዲፔንዳንት በሚከተለው አኳኋን ገልጿቸዋል፡-

‹‹በእያንዳንዱ ግጭት አንዣር የሚቆሙ ሁለት ተቃራኒ ቡድኖች እንደሚኖሩ መቼም ቢሆን የታወቀ ጉዳይ ነው። ሆኖም ግን የሊባኖስን ጦርነት በሚመለከት የአሜሪካ ዜና ማሠራጫዎች የሚዘግቡት ከዚህ ሕግ ውጭ ነው። ሁልጊዜም አንድ ዓይነትና አሰልቺ የሆነ የዘገባ ስልት ይከተላሉ። ይህውም እስራኤልን እንደ ጥሩ፣ ሂዝቡላህን ግን የሰይጣን መገለጫ አድርጎ ማቅረብ ሲሆን፣ ይህም አቀራረብ የውይይትን ስሜት ማቀዝቀዝ ብቻ ሳይሆን ውይይቱን ራሱን አላስፈላጊ ያደርገዋል።››[31]

አሜሪካ ለእስራኤል የሰጠችውን የበዛ ድጋፍ አስደናቂ የሚያደርገው እስራኤል በሊባኖስ የፈጽመቸውን ግፍ በጋለ መንፈስ የደገፈች ብቸኛ ሃገር ዩናይትድ ስቴትስ ሆና በመገኘቷ ነው። ከሞላ ጎደል በዓለም ላይ ያለ ማንኛውም ሃገር እንዲሁም የተ.መ.ድ. አመራር የእስራኤልን ድርጊትና ዋሽንግተን ያቀረበችላትን የማይበገር ድጋፍ ነቅፏል። ያ አጋጣሚ አንድ የተለመደ ጥያቄ በሁሉም ሕሊና ውስጥ ነፍስ እንዲዘራ አድርጓል፡- ይኸውም "ለምን ይሆን ዩናይትድ ስቴትስ ከቀረው ዓለም የተለየችው?" የሚለው ነው።

ስትራቴጂያዊ ስህተት

ከላይ ለቀረበው ጥያቄ መልስ ሊሆን የሚችለው እስራኤልን መደገፍ ለዩናይትድ ስቴትስ እንደ አንድ ስትራቴጂያዊ ስኬት የሚቆጠር መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ትክክል አይደለም። ምክንያቱም የዊኖግራድ ኮሚሽን እንዳስታወቀው፦ ‹‹እስራኤል ከጦርነቱ የገመተችውና ተስፋ ያደረገችው ነገር ከእውነታው የራቀ ነበር።›› እስራኤል የወሰደችው የአጸፋ እርምጃ በስትራቴጂያዊ አስተሳሰብ ደካማ ሆኖ ታይቷል። ስለሆነም የቡሽ አስተዳደር የደገፈው ገና ከመነሻው የተሳሳተ እንደነበር የታወቀ የሆነውን ስትራቴጂ ነበር ማለት ነው።[32]

በሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት የእስራኤላውያን ዋና ግብ የነበረው ሂዝቡላህ እንደ ተዋጊ ኃይል ዳግም እንዳያንሰራራ በማድረግ መምታት ነበር። በተለይም የሂዝቡላህ ሃይሎች በሺዎች የሚቆጠሩ ሚሳዩሎችንና ሮኬቶችን ዳግመኛ ወደ ሰሜን እስራኤል እንዳያስወነጭፉ ድምጥማጣቸውን ለማጥፋት ወስነው ነበር የተንቀሳቀሱት። ጠቅላይ ሚኒስትር ኡሁድ ኦልመርት በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ሀሳባቸውን ሲሰጡ፦ ‹‹የሂዝቡላህ ማስፈራሪያ እንደቀድሞው አይቀጥልም። ከእንግዲህ ሚሳዬሎቹን እንደልብ እያስወነጨፈ ዜጎቻችንን ከስጋት ላይ ሊጥል አይችልም››[33] ብለው ነበር። በተመሳሳይ ሁኔታ ዋሽንግተን የሚገኙት የእስራኤል አምባሳደር እንደሚከተለው አሉ፦ ‹‹ወደዚያ የምንሄደው ሂዝቡላህን ደምስሰን ዋጋ እንዳይኖረው ለማድረግ ነው።››[34] የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስተር ቤንጃሚን ናታንያሁ በበኩላቸው ዎል ስትሪት ጆርናል ላይ፦ ‹‹የእስራኤል ግልጽና ቀጥተኛ ግብ የሂዝቦላህን ሚሳዬሎች ማስወገድ ወይም ማውደም ነው›› በማለት ጽፈዋል።[35]

እስራኤል የሂዝቡላህን ሚሳዬሎችና ሮኬቶች ለማምከን ሁለት የተለያዩ፣ ሆኖም ግን የተሟሉ መንገዶችን የመሞከር ዕድል ነበራት። የመጀመሪያው በሚሳዬሎቹ ላይ በቀጥታ ከአየር ጥቃት በመክፈት ከሞላ ጎደል ሁሉንም ማውደም ሲሆን÷[36] ሁለተኛው አማራጭ ቀጥተኛ ያልሆነ መጠነ ሰፊ

መንገድ መጠቀም ነው። ስለሆነም የእስራኤል ጦር ዓይነተኛ የተባለና በሊባኖስ ሲቪል ሕዝብ ላይ ትልቅ ሕመም የሚያስከትል፣ መኖሪያ ስፍሮችንና መሠረተ ልማቶችን የሚያፈራርስና በርካታ ሕዝብ ሙትና ቁስለኛ የሚያደርግ፣ በርካቶችን ደግሞ ለስደት የሚዳርግ ዘመቻ ለመክፈት ነበር የወሰነው። ሂዝቡሏህ የእስራኤልን ወታደሮች አፍኖ ከወሰደ በኋላ የሚወስዱትን የአጸፋ እርምጃ አስመልክተው ኦልመርት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፡- ‹‹እጅግ የሚያምና በስፋት የሚዳረስ›› በማለት ነበር የገለጹት።[37] የዚያ የቅጣት ዘመቻ ዋነኛ ዓላማ የሊባኖስ ባልሰልጣናት ለሂዝቡሏህ ድርጊት የኋላ ኋላ ተጠያቂ መሆናቸው እንደማይቀር እንዲገባቸው መልዕክት ለማስተላለፍና ሂዝቡሏህ በማንኛውም ጊዜ እስራኤልን የሚያጠቃ ከሆነ ሊባኖስ በአጠቃላይ ትልቅ ዋጋ እንደምትከፍል ለማስገንዘብ ነው። ጠቅላይ ሚኒስተሩ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ግልፅ አቋም ነበር የወሰዱት። ‹‹ሂዝቡሏህን በአባልነት ያቀፈው የሊባኖስ መንግስት የክልሉን ሰላም በማናጋቱ ሊባኖስ የእጇን ማግኘቷ ግድ ነው›› ነበር ያሉት።[38]

እነዚህ ሁለት ስትራቴጂዎች ከመነሻቸው ጀምረው ነበር ለውድቀት የተዳረጉት። ሂዝቡሏህን ከአየር በመደብደብ ሚሳዬሎችን ማውደም ፈጽሞ አይቻልም። ይህ ስትራቴጂ ተጨባጭ ያልሆነ ነበር። ሌላው ቀርቶ "ስማርት" የሚሰኙትንና ዒላማቸውን እያነፈነፉ የሚመቱ ቦምቦችን መጠቀም ቢቻል እንኳ ከአሥር እስከ አሥራ ስድስት ሺህ እንደሚሆኑ የሚገመቱትን ሚሳዬሎች ማውደም የሚቻልበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም።[39] ከዚያም በላይ ከእነዚያ መሳሪያዎች አብዛኛዎቹ በዋሻዎች፣ በመኖሪያ ቤቶች፣ በመስጊዶችና በሌሎች ሰዋራ ቦታዎች የተተከሉ ከመሆናቸውም በላይ የተበታተኑ ናቸው። በተጨማሪም እንበልና የእስራኤል ጦር የሂዝቡሏህን አብዛኛዎቹን ሚሳዬሎችና ሮኬቶች ማውደም ቢሳካላት እንኳ ኢራንና ሶሪያ ወዲያው ነው ምተካቸውን የሚልኩለት። እናም የሂዝቡሏህ ሚሳዬሎችና ሮኬቶች ሰሜን እስራኤልን መደብደባቸውን እንደማያቋርጡ በታወቀ ጊዜ የአየር ላይ ድብደባው ስኬት እንደማያመጣ ወዲያው ግልጽ ሆነ። ሂዝቡሏህ የተኩስ አቁም ሊያደርግ አንድ ቀን ሲቀረው ነሃሴ 13 ላይ ከሌሎቹ ጊዜያት በተለየ ሁኔታ በርካታ ሚሳዬሎችን ማዝነቡንም ልብ ማለት ያሻል።[40]

ሐምሌ መጨረሻ አካባቢ የኦልመርት መንግሥት ችግሩን ለማስወገድ ወደ ሊባኖስ ምድር ገብቶ ሂዝቡላህን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ጠራርጎ የሚያጠፋ የምድር ጦር አሰማራ።[41] ይሁን እንጂ ይሸኛውም ቢሆን ሌላው የሞኝ ስህተት መሆኑ አልቀረም። አንድ ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ የእስራኤል መከላከያ ጦር ከሂዝቡላህ ጋር ሊባኖስ ውስጥ ከ1982-2000 ባለው ጊዜ ውስጥ ሲዋጋ ቆይቷል። በእነዚያ ጊዜያት ሁሉ ሂዝቡላህ ጦሩን ገትሮ የያዘው ሲሆን በመጨረሻም 2000 ላይ ከሊባኖስ ሙሉ ለሙሉ እንዲወጣ አስገድዶታል። ታዲያ እስራኤል ለአሥራ ስምንት ዓመታት ሞክራው ያልተሳካላት ሂዝቡላህን የመደምሰስ የቤት ሥራ እንዴት በጥቂት ሳምንታት ሊሳካለት ይችላል ተብሎ ይታሰባል? የእስራኤል እግረኛ ጦር ዓላማውን ሊያሳካ እንደማይችል ወዲያውኑ ተገነዘበ። ነሃሴ 14 ላይ[42] የተኩስ አቁሙን ከመቀበል ውጪ ምርጫ ሊያገኝ ያልቻለውም ለዚህ ነበር። እስራኤል በአንድ ቀን ብቻ ብዛት ያለው ጦሯ ሙትና ቁስለኛ የሆነውም የተኩስ አቁሙ ሊደረግ ሁለት ቀናት ብቻ በቀሩበት ጊዜ ነበር።[43]

ሂዝቡላህ እንደልቡ እንዲንቀሳቀስ የፈቀደችውን ሊባኖስን ለመቅጣት እስራኤል ያደረገችው ሙከራም እንዲሁ የከሸፈ ስትራቴጂ ነበር። ብዙ የካበቱ ታሪካዊ ሰነዶች የሚያሳዩትና በምሁራን የተጻፉ ልዩ ልዩ ጥራዞች በግልጽ የሚያስረዱት የጠላትን ሃገር ሰላማዊ ሕዝብ በማጥቃት ለወራሪው ሕዝብ እጅ እንዲሰጥና በአገሩ ተዋጊ ሃይል ላይ እንዲነሳ ለማድረግ የሚቻለው አልፎ አልፎ ብቻ ነው።[44] ከዚያ ይልቅ የጠላት የጦር ዱላ ያረፈበት ሕዝብ ቁጣውን በወራሪው ላይ በማድረግ የራሱን መንግሥትና ገዢ ሲደግፍ ነው በብዛት የሚታየው። እስራኤል በሊባኖስ ላይ ከዚህኛው በፊት ለሁለት ጊዜያት ያክል የአየር ድብደባ የፈጸመች ሲሆን የመጀመሪያው በ1993 ያደረገችው (operation accountability) የተባለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በ1996 የተደረገው Operation grapes of worth የተሰኘው ነበር። ሁለቱም በሂዝቡላህ ላይ ትርጉም ባለው መልኩ ጉዳት ያላስከተሉ ሲሆን የህዝብ ድጋፍ እንዳይኖረው ማድረግም አላስቻሉም።[45]

እንግዲህ 2006 ላይም ታሪክ ራሱን ደገመ ለማለት ይቻላል። እስራኤል ሊባኖስን በሂዝቡላህ ጦስ ለመቅጣት በተነሳች ጊዜ ሂዝቡላህ ሊባኖስ ውስጥ (እንዲሁም በመላው የአረቡና ሙስሊሙ ዓለም) የነበረው ተቀባይነት

ጨምሯል፡፡ አብዛኛዎቹ ሊባኖሳውያን ቁጣቸውን በሂዝቡሏህና በሊባኖስ መንግስት ላይ ከማድረግ ይልቅ በእስራኤልና በዩናይትድ ስቴትስ ላይ ነበር ያወረዱት፡፡[46] የእስራኤል ቦምብ ሊባኖስን ክፉኛ ማፈራረሱን መቀጠሉ የሊባኖስ መሪዎች፡- ‹‹ሂዝቡሏህን ትጥቅ ለማስፈታት ተስማሚው ጊዜ አሁን ነው" ብለው እንዲወስኑ ቢያደርጋቸው እንኳ ያንን የማድረግ ችሎታው አልነበራቸውም፡፡ ምክንያቱም ከሊባኖስ መንግሥት ይልቅ ሂዝቡሏህ ይበልጥ ጠንካራና አይበገሬ ነውና፡፡

ሁለት ሳምንት ከፈጀው የምድር ውጊያ በኋላም ሂዝቡሏህ በሰሜን እስራኤል ሰማይ ላይ ሚሳዬሎቹንና ሮኬቶቹን ማምዘግዘጉን ቀጥሎ ነበር፡፡ እናም የእስራኤል የቅጣት ዘመቻ መክሸፉ ታወቀ፡፡ ድል ከእጇ የወጣ መሆኑ ግልጽ ሆነ፡፡ መሪዎቿም ከዚያ በኋላ የሂዝቡሏህን ፊት አውራሪ ጦር ለማስወገድ፣ እንዲሁም ከሂዝቡሏህ ጥቃት እስራኤልን ለመከላከል ዓለም አቀፋዊ ጦር የመስፈሩን አስፈላጊነት አመኑበት፡፡ በመሆኑም በዚህና መሰል አጀንዳዎች ዙሪያም ትኩረታቸውን አሳረፉ፡፡[47] ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ስንመለስ ደግሞ ፎርዋርድ ጋዜጣ፡- ‹‹አንዳንድ ጦረኛ የእስራኤል ደጋፊዎች በጦርነቱ ድል የማጣት ስጋት የተጫናቸው መሆኑን በመግለጽ መጮህ የጀመሩ ሲሆን ጥቂቶቹ ደግሞ ‹እስራኤል እውን አሁንም የዩናይትድ ስቴትስ ስትራቴጂያዊ እሴት ናትን?› በማለት ጥያቄ አንስተዋል›› ሲል ዘግቧል፡፡ ነሃሴ 4 ቀን በወጣው ዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ ላይ ቻርለስ ክራውታመር ሲጽፍ፡- ‹‹ይህ ጦርነት፣ አሜሪካ በሽብርተኝነት ላይ ለከፈተችው ጦርነት እስራኤል ወሳኝ የሆነ አስተዋጽኦ የምታበረክትበትን ልዩ ዕድል ከፍቶላታል፡፡ ይሁን እንጂ ዩናይትድ ስቴትስ በእስራኤል የውጊያ ብቃት ተስፋ ቆርጣለች፡፡ ይህ ሁኔታ የሊባኖሶን ዘመቻ ብቻ ሳይሆን አሜሪካ በእስራኤል ላይ የነበራትን እምነት ሳይቀር አደጋ ላይ ጥሎታል፡፡›› ብሏል፡፡[48]

ጦርነቱ በነሃሴ 14 ሲያበቃ ሁሉም ወገኖች ድል የተቀዳጁ መሆኑን ገለጹ፡፡[49] ሆኖም ግን በብዙዎቹ ገለልተኛ ባለሙያዎች እምነት ሂዝቡሏህ ነበር በጦርነቱ የድል ባለቤት የሆነው፡፡[50] ሂዝቡሏህ በጦሩ አውድ ላይ በሁለንተናዊ መልኩ የተሳካለት በመሆኑ ጦርነቱ ባበቃ ጊዜ ከመቼውም በበለጠ ገዝፎ ታይቷል፡፡ በተጨማሪም አሁንም ቢሆን በሺዎች የሚቆጠሩ

ሚሳዬሎችና ሮኬቶቹን በቁጥጥሩ እንዳደረገ ሲሆን መሳሪያዎቹ የእስራኤል ስጋት እንደሆኑ ቀጥለዋል፡፡ በፖለቲካው መስክም ቢሆን በሊባኖስም ሆነ በመላው ሙስሊሙ ዓለም ሂዝቡላህ ከፍ ያለ ቦታና ከበሬታን አትርፏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የእስራኤል ጦር ሂዝቡላህን በገጠመ ጊዜ ዒላማውን በትክክል መምታት ተስኖት ታይቷል። ጊዜው እየገፋ በሄደ ቁጥርም እስራኤል ውስጥ ሂዝቡላህ የድል ባለቤት መሆኑና እስራኤል ደግሞ ተሸናፊ መሆኗ ግልጽ ሆነ፡፡ የዊኖግራድ ኮሚሽን የተሰየመበት ዋነኛው ምክንያትም በዘመቻው ወቅት በተከሰተው ተስፋ መቁረጥ የደረሰውን ጥፋትና ውጤቱ ያስከተለውን ቀውስ በትክክል አጣርቶ ማቅረብ በማስፈለጉ ነበር።[51] የኮሚሽኑ ዋነኛ ግኝቶች ያለምንም ጥርጥር ያረጋገጡት ሃቅ ሶስቱ የጦርነቱ መሃንዲሶች ማለትም ጠቅላይ ሚኒስትር አልመርት፣ የመከላከያ ሚኒስተሩ አሚር ፔሬታዝና የጦር ሃይሎች ኤታማዦር ሹም ጀነራል ዳን ሃሉትዝ ላጋጠመው ውድቀት ተጠያቂ መሆናቸውን ነው፡፡

በዩ.ኤስ. አሜሪካ ጥቅም ላይ የደረሰ ጉዳት

በሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት እስራኤልም አሸነፈች ሂዝቡላህ የ.ዩ.ኤስ አሜሪካ ጥቅም ገና ከመጀመሪያው እስራኤልን መደገፍ ስትጀምር ጉዳት ላይ እንደወደቀ አያጠያይቅም፡፡ ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደሞከርነው ዩናይትድ ስቴትስ በዚያ ክልል በአሁኑ ጊዜ ሶስት ዋነኛ የሚባሉ ችግሮች ተደቅነውባታል፡፡ የመጀመሪያው የሽብርተኝነት ችግር ሲሆን አል-ቃዒዳን ድል ማድረግ ዋነኛው ግቧ መሆኑ ይታወቃል። ምንም እንኳን ሃማስንና ሂዝቡላህን የመፈረካከስና አቅም የማሳጠት ፍላጎት ቢኖራትም ቅሉ ማለት ነው፡፡ የሶሪያና የኢራን ጉዳይም ሁለተኛው ችግሯ ነው፡፡ ሁለቱም ሽብርተኝነትን የሚደግፉ ሲሆን ኢራን የኒኩሌር ቦምብ ለመስራት የሚያስችላትን ሙሉ የዩራኒዩም ማብላላት ሂደት አጠናቅቃለች፡፡ ሶስተኛው ችግር የኢራቅ ጦርነት ነው። በዚህ ጦርነት አሜሪካ ሽንፈት እንዳይደርስባት ክፉኛ የሚያሰጋ ሁኔታ ተደቅኖባታል፡፡ የቡሽ አስተዳደር በሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት ወቅት ለእስራኤል ያደረገው ሁለንተናዊ ድጋፍ ዋሽንግተን እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የምታደርጋቸውን ጥረቶች አወሳስቧቸዋል፡፡

በሊባኖስ የተፈጠረው ውዝግብ የአሜሪካን የሽብርተኝነት ችግር በሁለት መንገድ አባብሶታል። የመጀመሪያው ጸረ አሜሪካ የሆነ አቋም በአረቡና ሙስሊሙ ዓለም እንዲፈጠር ያደረገ መሆኑ ሲሆን የሂዝቡላህ መሪ ሃሰን ነስረላህ በጦርነቱ ጊዜ ‹‹እስራኤል የታጠቀችው በራሷ በአሜሪካ ውሳኔ የአሜሪካን መሳሪያዎችና ሚሳዬሎች ነው›› በማለት ተናግረዋል፡፡[52] ይህ ዓይነቱ ግንዛቤ በብዙዎች ዘንድ መኖሩ አል-ቃዒዳና ሌሎች አሸባሪ ድርጅቶች ዩናይትድ ስቴትስንና ወዳጆቿን ለማጥቃት የሚፈልጉ አዳዲስ ምልምሎችን እንዲያገኙ ያግዛቸዋል፡፡ ለምሳሌ ጦርነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ነሃሴ 2006 ላይ በተደረገ ጥናት 69 ከመቶ የሚሆኑ የሊባኖስ ዜጎች አሜሪካ "የሊባኖስ ጠላት" መሆኗን እንደሚያምኑ ተናግረዋል፡፡ ከዚያ በፊት አንድ ዓመት ቀደም ብሎ 2005 ላይ ይህ አሃዝ 26 ከመቶ ብቻ ነበር፡፡[53] ነሃሴ 2006 ላይ በተደረገ ሌላ ጥናትም እንዲሁ 64 ከመቶ የሚሆኑት

መላሾች ከጦርነቱ በኋላ ለዩናይትድ ስቴትስ የነበራቸው አመለካከት ከጦርነቱ በፊት ከነበረው የከፋ እንደሆነ ገልጸዋል። ወደ ግማሽ የሚጠጉት መላሾች ደግሞ ጦርነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ለአሜሪካ የነበራቸው አመለካከት ይበልጥ የከፋ እንደሆነ ተናግረዋል።[54] 2006 መገባደጃ ላይ በሳኡዲ አረቢያ፣ በግብጽ፣ በሞሮኮ፣ ዮርዳኖስና ሊባኖስ የተደረገ ጥናት በአምስቱም አገራት ለዩ.ኤስ አሜሪካ የነበረው አመለካከት ባለቀው ዓመት የከፋ መሆኑን አመልክቷል። ቀደም ሲል የነበሩት ችግሮች ማለትም የኢራቅ ጦርነትና ዋሽንግተን በፍልስጤማውያን ላይ የምትከተለው ፖሊሲ እንዳሉ ሆነው እነሆ አሁን ደግሞ የሊባኖስ ጉዳይ ሲጨመር ለችግሩ መባባስ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል።[55] እዚህም እዚያም ለዩናይትድ ስቴትስ ያለው ጥላቻ እየጨመረ መሄዱ ሽብርተኞች በመካከለኛው ምሥራቅም ሆነ የትም ሥፍራ በሕዝብ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት እንዲጨምር አድርጓል።

በተጨማሪም ጦርነቱ ሂዝቡላህ በሊባኖስ የነበረውን ተጽዕኖ ይበልጥ እንዲያሳድግ አግዞታል። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት በአረብ ጠላቶቹ ላይ ተደጋጋሚ የሆነ ድል ሲጎናጸፍ የነበረውን የእስራኤል ጦር ገትሮ በመያዝ ባሳየው ብቃትና ማራኪ የውጊያ ጥበብ እስራኤላውያን የለመዱትን ድል እንዳያገኙ ስላደረገ ነው። እስራኤል ያካሄደችው የቦምብ ዘመቻም እንዲሁ የሂዝቡላህ ተቀባይነት ሰማይ እንዲደርስ አድርጓል። ጦርነቱ እንደተጀመረ በርካታ ሊባኖሳውያን ሂዝቡላህን ጠብ በማጫሩ ተናደውበት የነበረ መሆኑ እውነት ነው። ምክንያቱም በሊባኖስ የቱሪስት እንቅስቃሴ የሚደምቅባቸው ወሳኝ ወራት በመቃረባቸው ነበር።[56] ከጦርነቱ በፊት ብዙ ሊባኖሳውያን ለዩናይትድ ስቴትስ በጎ አመለካከት ነበራቸው። ምክንያቱም የቡሽ አስተዳደር በ2005 ሶሪያን ከሊባኖስ በማስወጣቱ ሂደት ላይ ቁልፍ ሚና በመጫወቱ ነው። ዳሩ ግን ያ ለዩናይትድ ስቴትስ የነበራቸው በጎ አመለካከት ዋሽንግተን የእስራኤልን የጥቃት ዘመቻ በደገፈችበት ሁኔታ ወደ ቁጣ በመቀየሩ በውጤቱ ሂዝቡላህ በሊባኖስ ገዝፎ ብቅ ሊል ቻለ።

ከጦርነቱ በኋላ በሊባኖስ የተደረገ ጥናት እንዳመለከተው 79 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች የሂዝቡላህ መሪ ሃሰን ነስረላህ በጦርነቱ ያሳዩትን የአመራር ብቃት ‹‹ጥሩ›› ወይም ‹‹ከፍተኛ›› ብለውታል። በሌላ ጥናት ደግሞ ከጦርነቱ በኋላ 40 ከመቶ የሚሆኑ መልስ ሰጪዎች ለሂዝቡላህ

የበለጠ አዎንታዊ አመለካከት ሊኖራቸው እንደቻለ የገለጹ ሲሆን ከ30 በመቶ በታች የሚሆኑት ብቻ የበለጠ አሉታዊ አመለካከት እንዳደረባቸው ገልጸዋል።[57] ምንም እንኳን ሂዝቡላህ ለዩናይትድ ስቴትስ ቀጥተኛ ስጋት ባይፈጥርም እስራኤልን ግን ክፉኛ የሚያሰጋት ባላጋራዋ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን ፕሬዝዳንት ቡሽ የደገፉትንና ማለፊያ የዲሞክራሲያዊ ሽግግር መገለጫ እንደሆነ በመጥቀስ ያሞገሱትን የጽድ አብዬት (Cdar revolution) እና ያስከተለውን ለውጥ ሙሉ ለሙሉ ለመቀየር አልሞ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው። በ2006 ማብቂያ ላይ ሂዝቡላህ በየጊዜው እያደገ የመጣውን ጫናውን ፉአድ ሲኞራ በሚመሩት አፍቃሪ አሜሪካ የሊባኖስ መንግስት ላይ በማሳረፍ ከመንበሩ ሊያወርደው ማስፈራራት ጀመረ።[58] በዚህ ጊዜ የተፈጠረው አስጨናቂ ጉዳይ የሂዝቡላህ ድርጊት ሊባኖስን ወደ ሌላ የእርስ በርስ ጦርነት ሊየስገባት ይችላል የሚለው ነው። ዩናይትድ ስቴትስ ከአጋሮቿ ጋር በመሆን ይህ እንዳይሆን የወሰደቻቸው የመከላከያ እርምጃዎች እስካሁን ድረስ ለስኬት የበቁ ሆነዋል። ይሁን እንጂ ችግሩ መልሶ እንዳይነሳ የሚያደርገው ሁኔታ የሚፈጠረው ሂዝቡላህ ባገኘው ድልና ሰፊ ተቀባይነት ያልተደፋፈረ እንደሆነ ብቻ ነው።

በሊባኖስ የተፈጠረው ግጭት ከኢራንና ከሶሪያ ጋር ለመነጋገር ችግር መፍጠሩ አልቀረም። ሁለቱም ሀገራት ሂዝቡላህን እንደሚረዱ ባያጠያይቅም ቅሉ ዩናይትድ ስቴትስ ያንን ግንኙነት የማዳከም ወይም የመበጣጠስና በቴህራንና በደማስቆ መካከል ያለውንም ትስስር እንዲሁ የመስበር ጠንካራ ፍላጎት አላት።[59] በኢራንና በሶሪያ መካከል ያለውን ትስስር የሚለያይ ሽብልቅ ለማስገባት አስቸጋሪ አይሆንም። ምክንያቱም ሁለቱ ተፈጥሯዊ ተጓዳኞች አይደሉምና። ኢራን በሐይማኖት ሥርዓተ የሚመራ መንግስት ያላት (theocratic state) እና ፋርሳዊ ስትሆን ሶሪያ ደግሞ ሴኩላሪስት የሆነ መንግስት የሚገዛትና አረባዊት ናት። እንዳለመታደል ሆኖ የቡሽ አስተዳደር በሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት ጊዜ እስራኤልን በጭፍኑ በመደገፉ ምክንያትና ሂዝቡላህን፣ ኢራንንና ሶሪያን "የሰይጣን ዛቢያ" በማለት አንድ ላይ ጨፍልቆ በመፈረጁ የበለጠ እንዲቧደኑና ግንኙነታቸውን እንዲያጠናክሩ አደረጋቸው።[60]

ይህ በእንዲህ እያለም በርካታ ኒዎኮንሰርቫቲቮች በጦርነቱ መካከል እስራኤልና ዩናይትድ ስቴትስ ሶሪያንና ኢራንን እንዲያጠቁ ጥሪ አቀረቡ።[61] መይራቭ ውርምስር የተባሉት የሁድሰን ኢኒስቲትዩተ ባልደረባ ከጦርነቱ መጠናቀቅ በኋላ በሰጡት አስተያየት፡- ‹‹በርካታ የአስተዳደሩ ክፍሎችና ባለቤቱ ዴቪድ ውርምሰር፣ እንዲሁም አሊዮት አብራምስ ዲምር፣ እስራኤል ከሂዝቡላህ ጋር አንድ ላይ ሶሪያን ባለመምታቷ በጣም ነበር የተናደዱባት›› ብለዋል።[62] ከዚያ በኋላ ውጤቱ ምን ሆነ? ይህ ፖሊሲ ኢራን የእስራኤልንና የአሜሪካን ጥቃት ለመመከት ስትል የኒኩሊዬር መሳሪያ ለመታጠቅ የምታደረገውን ጥረት እንድታፋጥን በቂ ግፊት ፈጠረላት። ኢራንና ሶሪያም ሂዝቡላህን ማስታጠቃቸውን ቀጠሉ። ዩናይትድ ስቴትስ በኢራቅ ውስጥ እየዳከረች እንድትቆይና ሁለቱንም የማጥቃት አቅሟ እንዲዳከም የማድረግ ጥረታቸውንም ተግተው ገፉበት።[63]

እስራኤል ሊባኖስን መደብደቧ ኢራቅ ውስጥም ሌላ መዘዝ አስከትሏል። በሊባኖስ የተፈጸመውን ሁሉ ሲከታተሉ የነበሩት በተለይም የኢራቅ ሺዓይቶች ለሂዝቡላህ (የሺዓ ድርጅት በመሆኑ) ያላቸውን አጋርነት በመግለጽ ከጎኑ እንደሚቆሙ አሳወቁ። ነሃሴ 4 ቀን ባግዳድ ውስጥ ሂዝቡላህን በመደገፍ ሺዓይቶች ያደረጉት ሰልፍ በመካከለኛው ምሥራቅ በትልቅነቱ ተወዳዳሪ አልተገኘለትም።[64] የሊባኖስ ጦርነት እንዳበቃ ይወጡ የነበሩ ሪፖርቶች እንዳመለከቱት በኢራቅ የአሜሪካ ዋነኛ ጠላት በመሆን የሚታወቁትና የሺዓ እስልምና መንፈሳዊ መሪ የሆኑት ሙቅተዳ አል-ሳድርን ሚሊሺያዎች ሂዝቡላህ እያሰለጠናቸው ነበር።[65] ዩናይትድ ስቴትስ ኢራቅ ውስጥ የአገሬው ሰው በአል- ሳድር ዙሪያ እንዳይሰለፍ ለመከላከል ያደረገችው እልህ አስጨራሽ ጥረት ትልቅ ችግር ውስጥ ከታት ቆይታል።

ዩናይትድ ስቴትስ ለዋና ዋና ችግሮቿ፣ ማለትም ለሽብርተኝነት፤ ወስላታ የምትላቸውን መንግስታት (ሶሪያንና ኢራንን) አደብ ለማስያዝ፣ እንዲሁም ለኢራቅ ጦርነት ፍቱን መፍትሔ ለመስጠት ከግብጽ፣ ከዮርዳኖስ፣ ከሳዑዲ አረቢያና መሰል የክልሉ ወዳጅ አገራት ሰፊ ድጋፍ ማግኘት ያሻታል። እነዚህ መንግሥታት ለሂዝቡላህ ፍቅር የሌላቸው ሲሆኑ ዩናይትድ ስቴትስም ሆነች እስራኤል የሚወስዱትን እርምጃ በዝምታ የሚያልፉት

እርምጃው ወሰን ያላለፈና በተረጋጋ ሁኔታ የሚፈጸም ከሆነ ብቻ ነው። እርግጥ ነው በሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት የመጀመሪያዎቹ ቀናት እነዚህ አገራት ሂዝቡሏህን ጠቡን በመጫሩ ክፉኛ ነቅፈውታል። ሆኖም ግን እስራኤል ያልተመጣጠነ ኃይል መጠቀም ስትጀምርና የቡሽ አስተዳደርም እርምጃዋን በጽናት መደገፉን ሲመለከቱ ዋሽንግተንን መንቀፍና እስራኤልን ማውገዝ ጀመሩ። የነዚህ ሐገራት መሪዎች በዩናይትድ ስቴትስና በእስራኤል ላይ ፊታቸውን ያዞሩት በዋነኝነት ራሳቸውን በቁጭት ከነደደው ሕዝባቸው ቁጣ ለመከላከል ነው።[66] አሜሪካ በዚያ ሰዓት የተከተለችው ፖሊሲ በአውሮፓና በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ ሽሪኮቿን በማስቆጣቱ እርሷና እስራኤል እንዲነጠሉና ለጊዜውም ቢሆን የፖለቲካ ተደማጭነት እንዳይኖራቸው አድርጓል። እንዲሁም ፕሬዝዳንት ቡሽ ሽብርተኝነትንና የጅምላ ጨራሽ መሳሪያ ማስፋፋትን በመዋጋት አንጻር እምነት የሚጣልባቸው መሪ መሆናቸውን ከጥርጣሬ ላይ ጥሎታል።[67]

በሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት ምክንያት በአረብ መሪዎችና በሕዝቦቻቸው መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ጦርነቱ እንዳበቃ ወዲያው ይጠፋል እንዲሁም ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ቅሬታ አይፈጥርም ብሎ መገመት ስህተት ነው። አረቦች ለዩናይትድ ስቴትስ ያላቸው ጥልቅ የሆነ የጥላቻ አመለካከት ይቀጥላል። የቡሽ አስተዳደር የኢራንን ምኞት ለመግታት የሚያደርገውን ትግል እንዳያግዙም ሁኔታዎችን አስቸጋሪ ያደርጋቸዋል። የዚህ ችግር ዋነኛው ስረ መሠረት የአረብ ጎዳናዎች ከኢራን ይልቅ አሜሪካን ስለሚፈሩ ነው። በ2007 የተደረገ ጥናት እንዳመለከተው በስድስት አረብ አገራት ውስጥ ከሚገኙ በጥናቱ የታቀፉ ሰዎች ውስጥ 72 ከመቶ የሚሆኑት ዩናይትድ ስቴትስን ትልቋ የስጋታቸው ምንጭ አድርገው እንደሚቆጥሯት ሲናገሩ 11 ከመቶ የሚሆኑት ብቻ ነበሩ ኢራንን የስጋታቸው ምንጭ አድርገው እንደሚቆጥሯት የገለጹት። በተጨማሪም 61 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች ኢራን የኒኩሊዬር ቴክኖሎጂ የመገንባት መብት እንዳላት ተናግረዋል። ይህን ያሉት ከእነርሱ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ኢራን የኒኩሊዬር ቦምብ ለመስራት ወደሚያስችላት ቀጣይ ደረጃ እየተሸጋገረች መሆኗን እያወቁ ነው።[68]

የእስራኤል የመከላከያ ሰራዊት በሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት ያሳየው ደካማ ብቃት ከእንግዲህ ለዩናይትድ ስቴትስ በአካባቢው አስተማማኝ አጋዥ ሊሆን እንደማይችል አመላክቷል። ይህን ማወቅ ለአሜሪካ ጠቃሚ ነው። በምዕራፍ

ሁለት ላይ እንዳብራራነው እስራኤል የምትከተላቸው ፖሊሲዎች የተለያዩ አሸባሪ ድርጅቶች እንዲፈጠሩ የሚያነሳሱ ሲሆን ዩ.ኤስ አሜሪካ፤ ሶሪያንና ኢራንን ከመሳሰሉት አገራት ጋር የምታደርገውን ፍጥጫም ይበልጥ ያወሳስበዋል፡፡ ከእነርሱ ጋር በሚደረግ ትግልም እስራኤል ብዙም አጋዥ ሆና የምትቆጠር ወዳጅ አይደለችም፡፡

እስራኤል በሊባኖስ ላይ የከፈተችውን ጦርነት ማገዝ የዩ.ኤስ አሜሪካ ስትራቴጂያዊ ፍላጎት አልነበረም፡፡ ጦርነቱ በተጋመሰ ጊዜ የቀድሞው የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለስልጣን የተናገሩትን ማስተባበል አይቻልም፡፡ እንዲህ ነበር ያሉት፡- ‹‹በእስራኤልና በዩናይትድ ስቴትስ መንግስታት መካከል የስትራቴጃዊ ፍላጎት መጣጣም በሌለበት ሁኔታ የመነጨውን ፖሊሲ በስራ ላይ ማዋልን መቀጠል ከፍተኛ አደጋን እንደሚያስከትል ጥርጥር የለውም፡፡››[69]

የጦር ሕግጋትን መጣስ

የሞራል ጉዳይን በተመለከተስ ምን የሚባል ነገር ይኖር ይሆን? ‹‹ዩ.ኤ.ስ. አሜሪካ እስራኤልን ለመደገፍ ጠቀም ያለ ስትራቴጂያዊ ዋጋ መክፈሏ ከስትራቴጅ አንጻር ጠቃሚ ባይሆንም ከሞራል አንጻር ግድ ነው›› ተብሎ ሊታሰብ ይችላል፡፡ በእርግጥ እስራኤል ተጠቅታለች፡፡ ቢሆንም አጸፋውን መመለስ የሚገባት የጦርነትን ሕግጋት በማክበር መሆን ይኖርበታል፡፡ ጥቂት የእስራኤል ደጋፊዎች፡- ‹‹የእስራኤል ጦር በሊባኖስ ያሳየው ደካማ አፈጻጸም በአብዛኛው የመነጨው ጦሩ ጥብቅ የሆኑ ሕጋዊና ሞራዊ ደንቦችን መከተልን በመምረጡ ነው›› ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ ለምሳሌ ዘጀዊሽ ኢኒስቲትዩት ፎር ናሽናል ሴኩሪቲ. አፊርስ ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ቶማስ ኒውማን፡- ‹‹በጦርነቱ ጊዜ የእስራኤልን ሠራዊት አላላውስ ያለው ሂዝቡሏህ ሳይሆን የራሷ የእስራኤል ሞራዊ ይዞታዋ ነው›› ብለዋል፡፡[70]

ሆኖም ግን ይህ አባባል ጠጋ ብለው ሲመረምሩት አሳማኝ ሆኖ አይገኝም፡፡ እስራኤል ራሷን የመከላከል መብቷ የተጠበቀ ነው፡፡ ይህ መብቷ ደግሞ ሂዝቡሏህን በወታደራዊ ኃይል እስከመበቀል እንደሚሄድም ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም የእስራኤልን ድርጊት የሚነቅፉ መንግሥታትም ሆኑ ግለሰቦች ለሂዝቡሏህ ወረራ አጸፋ መስጠቷን ጥያቄ ውስጥ አላስገቡም፡፡ ሆኖም ግን ራስን መከላከል ማለት ሁሉንም ዓይነት እርምጃ መውሰድ ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ነው ባይ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ አከራካሪው ጉዳይ በ2006 በጋ ላይ በተካሄደው የሊባኖስ ጦርነት እስራኤል የወሰደቻቸው እርምጃዎች ከጦርነት ሕግጋትና ከሞራል መስፈርቶች አንጻር ትክክል ናቸው ወይ? የሚለው ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደገለጽነው የእስራኤል ስትራቴጂ በግልጽና ሆነ ተብሎ የሊባኖስ ሲቪሎችን የማጥቃትን ግብ የሰነቀ ነበር ማለት ያስኬዳል፡፡ ‹‹እስራኤል የሊባኖስን ሲቪሎች ማጥቃት የጀመረችው የሂዝቡሏህ ሚሳዬሎችና ሮኬቶች የእስራኤልን ሲቪሎች በማጥቃታቸው አጸፋ ለመመለስ ነው›› የሚል እሳቤ ሊኖር ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ጦርነቱ በዚያ

መልኩ አልነበረም የተካሄደው፡፡ ጦርነቱ የተጀመረው ሐምሌ 12 ቀን የሂዝቡሏህ ሃይሎች የእስራኤልን ድንበር ተሻግረው ሶስት የእስራኤል ወታደሮችን ገድለውና ሁለቱን ማርከው በወሰዱ ጊዜ ነበር። ከዚያ በኋላ ሂዝቡሏህ የእስራኤልን ጦር ትኩረት ለማስቀየር በማሰብ ጥቂት ደርዘን ሮኬቶችን ወደ እስራኤል ከተሞች አስወነጨፈ፡፡ ግና በእነዚያ ሮኬቶች አንድም ሲቪል አልሞተም፡፡[71] ነስረሏህ ይህ ከሆነ በኋላ ወዲያው ቤይሩት ውስጥ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፡- ‹‹በደቡብ ሊባኖስ በኩል ያለው ሁኔታ እንዲባባስም ሆነ ጦርነት እንዲኖር አንሻም›› አሉ፡፡[72] ምንም እንኳ የሂዝቡላህ ድርጊት አግባብ ባይሆንም ጦርነት ሊያስነሳ የሚችል ግን አልነበረም፡፡ ምክንያቱም በ2000 ዓ.ል እስራኤል የሊባኖስን ግዛት ለቅቃ ከወጣች በኋላም ሁለቱ ሐይሎች አንዱ በሌላው ላይ ድንበር እያለፈ ሲቆራቆሱ ኖረዋል፡፡[73] ነስረሏህ ራሳቸው ከወራት በፊት ጥቂት የእስራኤል ወታደሮችን ለመጥለፍ እንደወሰኑ ሲገልጹ ተደምጠዋል፡፡[74]

የሆነ ሆኖ እስራኤል ለዚያ ጠለፋ የሰጠችው አጸፋ በሊባኖስ ላይ ግዙፍ የሆነ የቦምብ ድብደባ ማካሄድ ነበር፡፡ ያ እርምጃዋ ደግሞ ሂዝቡሏህ ያጠራቀማቸውን ሚሳዮሎችና ሮኬቶች በሰሜን እስራኤል ከተሞች ላይ እንዲያዘንባቸው አድርጎታል፡፡ ሂዝቡሏህ የእስራኤልን ድንበር ተሻግሮ ጠለፋውን በፈጸመ ማግስት ሐምሌ 13 ቀን የእስራኤል አየር ኃይል ከሌሎች ኢላማዎች ጋር ደርቦ የቤይሩትን ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ደበደበ፡፡ ከዚያ በኋላ በቀጠለው ድብደባ ሐምሌ 14 ቀን ድልድዮችንና መንገዶችን፣ እንዲሁም ቤይሩት ውስጥ የሚገኘውን የነስረሏህን ቢሮ አጠቃ፡፡ ሁኔታው እዚህ ነጥብ ላይ ሲደርስ ሃምሳ የሚሆኑ ሲቪሎች በጥቃቱ መገደላቸውን እንዲሁም የመሠረተ ልማት አውታሮች ውድመት እያሻቀበ መሄዱን ያስተዋሉት ነስረሏህ ‹‹በእስራኤል ላይ ጦርነት ክፈቱ›› በማለት ለተከታዮቻቸው ትዕዛዝ አስተላለፉ፡፡ ያ ማለት የሚሳዬልና ሮኬት ውርጅብኞችሁን በእስራኤል ከተሞች ላይ አዝንቡ ማለት ነው፡፡[75] ስለሆነም ምንም እንኳን ሂዝቡሏህ ሐምሌ 12 ቀን በግልጽ የእስራኤልን ወታደሮች በመግደልና በመማረክ ጠቡን ቢቀሰቅስም ሰፊ አድማስ የሚሸፍን ጦርነት የጀመረችው ግን እስራኤል ነበረች፡፡

ሁሉም ሊባኖሳውያን ተገቢውን ቅጣት ማግኘትና ዋጋ መክፈል እንዳለባቸው የእስራኤል መሪዎች ገና ከመጀመሪያው አንስቶ አጽንኦት ሰጥተው ወስነዋል፡፡ ስለሆነም በሲቪል ዜጎችና ተቋማት ላይ የደረሰው ውድቀት የጦርነቱ አጋጣሚ ውጤት ሳይሆን ሆነ ተብሎና ታቅዶበት በእስራኤል የተፈጸመ ነው፡፡የእስራኤል መከላከያ ሰራዊት ኤታማዦር ሹም ሃሉትዝ በጦርነቱ መጀመሪያ ላይ እስራኤል፡- ‹‹የሊባኖስን የጊዜ አቆጣጠር በ20 ዓመታት ወደ ኋላ ለመመለስ ነበር የወሰነችው›› ብለዋል፡፡[76] ይህ አባባል፡- ‹‹ሁሉንም ነገር በምድርና በአየር ጥቃት በማውደም ሊባኖስን የዛሬ 20 ዓመት ገደማ ወደነበረችበት የስልጣኔ ደረጃ እንመልሳታለን›› የሚል ትርጉም ያዘለ ነው፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ፡- ‹‹ሊባኖስ ውስጥ ምንም የሚተርፍ ነገር የለም›› ማለታቸው ተወስቷል፡፡ ሰውዬው የተናገሩት ትክክል ነበር፡፡ 2000 ላይ የወጣ የአሚኒስቲ ኢንተርናሽናል ሪፖርት ጦርነቱ እንደተጠናቀቀ የእስራኤል ጦር በሊባኖስ የፈጸመውን ጥፋት እንደሚከተለው አቅርቦታል፡-

አራት ሳምንታት ያክል በፈጀው የእስራኤል የምድርና የአየር ጥቃት የሊባኖስ መሠረተ ልማት ተፈጥሮአዊ መቅሰፍት የወረደበት ያክል ነበር ብርቱ ጉዳት የደረሰበት፡፡ የእስራኤል ሃይል ህንፃዎችን በማፈራረስ ከመሬት ጋር አስተካክሏቸዋል፡፡ በርካታ መንደሮችን ወደ ፍርስራሽነት በመቀየር ከተሞችን ጣእረሞት የነገሰባቸው አድርጓቸዋል፡፡ ነዋሪዎቻቸው ደግሞ የቦምብ ድብደባውን በመፍራት ለስደት ተዳርገዋል፡፡ ዋና ዋና መንገዶች፣ ድልድዮችና የነዳጅ ማደያዎች ወደ አፈር ክምርነት ተቀይረዋል። በርካታ ቤተሰቦች በቤታቸው ውስጥ እንዳሉ ወይም ጦርነቱን ፈርተው በካሚዮኖች ሲሸሹ ተደምስሰዋል፡፡ ሌሎቹም በቤቶቻቸው ፍርስራሽ ውስጥ እንደተቀበሩ ለሳምንታት ያክል መቆየት ነበረባቸው። ምክንያቱም ቀይ መስቀልና ሌሎች የሰብዓዊነት ሥራ የሚሰሩ ሰራተኞች የእስራኤልን ጥቃት በመፍራት ሊያወጧቸው ስላልቻሉ ነበር፡፡ ጦርነቱን ሸሽተው የተሰደዱ በሺዎች የሚቆጠሩ ሊባኖሳውያን ወደ ቤታቸው ሲመለሱ የሚያጋጥማቸው ትላልቅ የአፈር ቁልል መሆኑ የማይካድ ነው።

የእስራኤል አየር ኃይል ከሀምሌ እስከ ነሐሴ 14 ድረስ 7000 በሚሆኑ ዒላማዎች ላይ 7000 የአየር ጥቃት አውርዷል። ባሕር ኃይሉ ደግሞ 2500 የሚሆኑ የሚሳየልና የአዳፍኔ ድብደባዎችን አድርጓል። ጥቃቱ ሰፊ ቦታን የሚሸፍን ቢሆንም በተለይም ደግሞ ትኩረቱን በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ ያደረገ ነበር። 1183 ከሚገመተው የንጹሐን ዜጎች ሞት ውስጥ አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት ሕጻናት እንደነበሩ ተረጋግጧል። 4054 የሚሆኑት ደግሞ ቁስለኞች ሆነዋል። 970000 የሚሆኑ የሊባኖስ ዜጎች ለስደት የተዳረጉ ሲሆን መሠረተ ልማቷም እንዳለ ወድሟል። በሊባኖስ መንግሥት ግምት መሠረት 31 የሚሆኑ ወሳኝ ቦታዎች (የአውሮፕላን ማረፊያዎች፤ ወደቦች፤ የውሃና የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ተቋማት፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች) ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወድመዋል። 80 ድልድዮችና 94 መንገዶችም እንዲሁ ወድመት ደርሶባቸው ከጥቅም ውጭ ሆነዋል። ከ25 በላይ የነዳጅ ማደያ ጣቢያዎችና 900 የንግድ ተቋማት ተመትተዋል። በርካታ የመኖሪያ ሰፈሮች፤ ቢሮዎችና ሱቆች ሙሉ ለሙሉ የወደሙ ሲሆን ቁጥራቸው 30.000 ይደርሳል። ቢንት ጀቢልና መኢስ አል-ጀበል በተባሉ ስፍራዎች የሚገኙ ሁለት የመንግስት ሆስፒታሎች ሙሉ ለሙሉ የወደሙ ከመሆኑም በላይ ሌሎች ሶስት የሚሆኑት ደግሞ ጉዳት ደርሶባቸዋል።

አራት ሚሊዮን ሕዝብ ባላት ትንሽ ሃገር ውስጥ ከ25 በመቶ የሚበልጡት ተፈናቃዮች ሆነው ጎዳናዎችን አጣብበዋል። ቤይሩት ውስጥ ብቻ 500,000 የሚሆኑ ሰዎች መጠለያ የሚፈልጉ ነበሩ። ከእነርሱ መሐል ብዙዎቹ በየመናፈሻዎችና በሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች ያለ ውሃና የተሟሉ የንጽህና አገልግሎቶች እንዲሁ ወድቀው ነበር።

የአምኒስቲ ኢንተርናሽናል ልዑካን አባላት በደቡብ ሊባኖስ መንደሮች ያጋጠማቸውም ተመሳሳይ ነገር ነበር። ጎዳናዎች፣ በተለይም ዋና ዋና የሚባሉት በከባድ መሳሪያና በመድፍ አረር ታርሰዋል። በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ደግሞ የክላስተር ቦምብ ተጽዕኖ በሚገባ ይታይ ነበር። ቤቶች ተነጥለው በርቀት መቆጣጠሪያ በሚታዘዙ ሚሳዬሎች ይደበደቡ ነበር። በውጤቱም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድመት አጋጥሟቸዋል። የንግድ

መናኸሪያዎች በተለይም የገበያ አዳራሾችና የነዳጅ ማከፋፈያ ጣቢያዎች ሆነ ተብሎ ነበር ዒላማ ውስጥ እንዲገቡ የሚደረገው። የኤሌክትሪክ አቅርቦት እዚህም እዚያም የተቋረጠ እንደመሆኑ ምግብና ሌሎች መሠረታዊ አቅርቦቶች ወደየመንደሮቹ ሊደርሱ አልቻሉም። በዚህም ላይ የገበያ አዳራሾችና የነዳጅ ማደያዎች በመጋየታቸው ሰዎች ቀያቸውን እየለቀቁ እንዲሰደዱ ግድ ብሏቸዋል። የነዳጅ አቅርቦት መቋረጥ ሰዎች ውሃ እንዳያገኙ አድርጓቸዋል። ምክንያቱም የውሃ ፓምፖች የሚሠሩት አንድም በኤሌክትሪክ ሃይል አለያም ደግሞ በነዳጅ ነውና።"[78]

የእስራኤል የመከላኪያ ኃይል በሊባኖስ ያደረሰውን ጉዳት ገምግሞ ያቀረበ ድርጅት አምኒስቲ ኢንተርናሽናል ብቻ አልነበረም። ዊሊያም አርኪን የተባሉ አሜሪካዊ ወታደራዊ ጠቢብና የአየር ኃይል ባለሙያ በዋሽንግተን ፖስት ቄብሎግ ላይ ሲጽፉ፦ ‹‹እስራኤል ሊባኖስን ለመቅጣት ይህን ዘመቻ በምታካሂድ ጊዜ ከጦርነቱ ቀጠና ውጪ ባሉ ሥፍራዎች ላይ አስደንጋጭ የሆነ ውድመት አስከትላለች። በሊባኖስ ከተሞች ላይ የደረሰውን ጉዳት ከተመለከትኩ በኋላ "ወደቆሻሻ ክምርነት ተቀይረዋል" የሚሉ ቃላት እንደሚያንሳቸው ተረዳሁ። ምክንያቱም ይህን ቃል በተለምዶ የምንጠቀመው ዩ.ኤስ. አሜሪካ የአየር ጥቃት በምትፈጽምባቸው አካባቢዎች የምታደርሳቸውን ጉዳቶች ለመግለጽ ሲሆን፣ እስራኤል ያደረገችው ግን ዩ.ኤስ. አሜሪካ በትክክለኛ የጦር አውደ ግንባሮች፣ በተለይም በአየር ኃይሏ ከምትደርሳቸው ጉዳቶች በእጅጉ የከፋ ነው›› ብለዋል።[79]

እስራኤል ሊባኖስን ለመቅጣት ከወሰደቻቸው እርምጃዎች ሁሉ አውዳሚ የሆነው የክላስተር ቦምቦችን መጠቀሟ ነው። ክላስተር ቦምብ መሬት ላይ ከማረፉ በፊት ሰፊ ቦታ የሚያዳርሱ ትናንሽ ፈንጂዎች ከውስጡ ይበተናሉ። እነዚያ ቦምቦች ዓላማቸውን በትክክል አይመቱም። ይህም ብቻ ሳይሆን ሳይፈነዱ ለብዙ ጊዜ ይቆያሉ። ይህ ማለት ደግሞ ጦርነቱ ካበቃ በኋላም ለረዥም ጊዜያት ያክል ለሰላማዊ ሰዎች ሥጋት እንደሆኑ ይቆያሉ ማለት ነው። እነዚህ ቦምቦች በሲቪሎች መኖሪያ አካባቢ በሚጣሉ ጊዜ ምን ያክል ገዳይ ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት አይከብድም። ዩናይትድ ስቴትስ ሁልጊዜም ‹‹እስራኤል ቦምቦቹን የምትጠቀምባቸው በግልጽ የተቀመጡ

ወታደራዊ ዒላማዎችን ለመምታት ነው›› በማለት ትከራከራለች፡፡[80] ይሁንና እስራኤል በ1982ቱ የሊባኖስ ወረራ ወቅት በሲቪሎች ላይ ክላስተር ቦምብ መጠቀሟ ተረጋግጧል፡፡ የሬገን አስተዳደርም ለስድስት ዓመታት ያክል ክላስተር ቦምብ እንዳይሸጥላት እገዳ አሳርፎባት ቆይቷል፡፡[81] በሁለተኛው የሊባኖስ እስራኤል ጦርነትም የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ መደረሱ በተረጋገጠባቸው የመጨረሻዎቹ ሶስት ቀናት የእስራኤል ጦር የ650,000 ሕዝብ መኖሪያ በሆነው ደቡባዊ ሊባኖስ አንድ ሚሊዮን ያህል የክላስተር ተስፈንጣሪ ቦምቦችን (bomb lets) አዝንቧል፡፡[82] ዓላማው በእነዚያ ትናንሽ ገዳይ ቦምቦች አካባቢውን መሙላት ነበር፡፡ በመድፈኛ ባታሊዮን ውስጥ የነበረ አንድ የእስራኤል ወታደር ‹‹ባለፉት 72 ሰዓታት በአንድ ዒላማ ላይ ብቻ ያሉንን ተተኳሾች ሁሉ አዝንበናቸዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ አቅጣጫችንን ለመቀየር እንኳን አልተጨነቅንም፡፡ በዚህ ባታሊዬን የሚገኙ ጓደኞቼ እንደነገሩኝ እነርሱም ቢሆኑ መደበኛ ተተኳሾችን፣ ክላስተር ቦምቦችንና ማናቸውንም ያገኙዋቸውን ነገሮች አስወንጭፈዋል››[83] በማለት ምስክርነቱን ሰጥቷል፡፡ ጦርነቱ በተካሄደባቸው ጊዜያት ሁሉ የእስራኤል መከላከያ ኃይል በግርድፉ አራት ሚሊዮን የሚጠጉ የክላስተር ቦምብ ተስፈንጣሪዎችን በሊባኖስ ምድር ላይ አዝንቧል:: ጦርነቱ በመጨረሻ ነሐሴ አጋማሽ ላይ ሲቆም በተ.መ.ድ. ባለስልጣናት ግምት መሠረት በደቡባዊ ሊባኖስ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ያልፈነዱ የክላስተር ቦምብ ፍንጣሪዎች እንደሚገኙ ታምኗል፡፡ ሂውማን ራይትስዎች በተባለው ድርጅት ውስጥ የሚያገለግሉ አጥኝዎች ‹‹በደቡባዊ ሊባኖስ ያለው የክላስተር ቦምቦች ጥግግት (density) በየትኛውም የዓለም ክፍል ካለው ይበልጣል፡፡›› ብለዋል፡ :[84] አካባቢው በክላስተር ቦምብ እንዲጥለቀለቅ ካደረጉት የእስራኤል ወታደሮች አንዱ እንዲህ ብሏል፡- ‹‹የፈጸምነው ነገር ሁሉ እብደት የተጠናወተው ሰው የሚፈጽመውን አሰቃቂ ድርጊት ነው፡፡ መላ የደቡብ ሊባኖስ ከተሞችን በክላስተር ቦምብ ሸፈንናቸው፡፡››[85] በተ.መ.ድ የሰብዓዊ መብት ጉዳዮች ኃላፊ የሆኑት ጃን ኤግላንድ የእስራኤልን ድርጊቶች ‹‹አስደንጋጭ እና ሙሉ ለሙሉ ኢ-ሞራዊ›› ሲሉ ገልጸዋቸዋል፡፡[86] ጦርነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በተከተሉት ስምንት ወራት 29 የሚሆኑ ሊባኖሳውያን

በክላስተር ቦምብ ፍንጣሪዎች ሞተዋል። 215 የሚሆኑት ደግሞ የቆሰሉ ሲሆን ከእነርሱ ውስጥ 90ዎቹ ሕጻናት ናቸው።[87]

እስራኤል በሊባኖስ ያካሄደችው አውዳሚ ዘመቻ የጦርነትን ሕግጋት የሻረ እንደሆነ የታወቀ ነው። ይህን ማለት ብቻ በቂ አይደለም። እስራኤል እነዚያን ሕግጋት እንዴት እንደጣሰቻቸው ማወቁ ጠቃሚ ነው።

ዘመናዊ የጦርነት ህግጋትና ፍትሃዊ የውጊያ ንድፈ ሃሳቦች በሲቪልና በወታደራዊ ዒላማዎች መካከል ልዩነት ማድረግን በዋነኛነት ይደነግጋሉ።[88] መንግሥታት አንዱ የሌላውን ወታደራዊ ዒላማዎች በማጥቃት ራሳቸውን መከላከል ያለባቸው መሆኑ ምንም አጠያያቂነት የለውም። ሆኖም ግን የሲቪል ዒላማዎችን (ዒላማዎቹ በጦርነቱ ሂደት ወደ ወታደራዊ ዒላማነት እስካልተቀየሩ ድረስ) ማጥቃት አይችሉም። ለምሳሌ ወታደሮች በጦርነት ጊዜ ትምህርት ቤትን ወይም ቤተ አምልኮትን ቢይዙና ለውጊያቸው እንደ መነሻ (base) አድርገው ቢጠቀሙበት ያንን ትምህርት ቤት ወይም ቤተ አምልኮ ማጥቃት ይፈቀዳል። በተጨማሪም አንደኛው ወገን የጠላትን ወታደራዊ ዒላማዎች በሚመታ ጊዜ እንኳ ተጓዳኝ የሆኑ ድንገተኛ የሲቪሎችን ጉዳቶች ለመቀነስ ጥረት ማድረግ አለበት። ወታደራዊ ዒላማን የሚመቱ መንግስታት ያንን ዒላማ ለማግኘት ብለው የሲቪሎችን ሕይወትና ንብረት የሚያወድም ከልክ ያለፈ እርምጃን ከመውሰድ መቆጠብ አለባቸው። በአጭር አነጋገር መንግስታት ሆነ ብለው የጠላትን ሲቪል ዒላማዎች ያለምንም ልዩነት መደብደብ አይችሉም። ይህም ብቻ ሳይሆን ወታደራዊ ዒላማዎቻቸውን ሲመቱ እንኳ በከፍተኛ ጥንቃቄ መሆን አለበት።

እስራኤል በሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት እነዚህን መሠረታዊ መርሆዎች ማክበር ተስኗት በግልጽ ታይቷል። እንደ ጀኔራል ሃሉትዝ አባባል ከሆነ እስራኤል ሆነ ብላ ነበር የሊባኖስን ሲቪል ህዝብና ተቋማት በስፋት ታወድም የነበረው። የውድመቱ ሁኔታ በይበልጥ በአምንስቲ ኢንተርናሽናል ዘገባ ላይ በግልጽ ተብራርቷል። ‹‹የሊባኖስ መሠረተ ልማት በተፈጥራዊ መቅሰፍት መጠን ነው ውድመት የደረሰበት›› በማለት ገልጾታል። ይህ ዘገባ በሌላ ቦታ ላይ ‹‹የእስራኤል ድብደባ በሲቪል መሠረተ ልማቶች ላይ የጅምላ

ውድመትን አስከትሏል›› በማለት ይገልጻል፡፡ አምንስቲ ኢንተርናሽናል ሕዳር 2006 ላይም የነሐሴውን ዘገባውን ግኝቶች የሚያጠናክሩ ሁነቶችን አውጥቶ ነበር፡፡ ለምሳሌ በደቡብ ሊባኖስ 7500 የሚሆኑ ቤቶች እንደወደሙና 20.000 የሚሆኑት ደግሞ ጉዳት እንደደረሰባቸው ዘግቧል፡፡ እንደ አጠቃላይ የወደሙትም ሆነ ጉዳት የደረሰባቸው ቤቶች በጦርነቱ ጊዜያት ለሒዝቡሏህ ተዋጊዎች መደበቂያነት ወይም መሳሪያ ማከማቻነት መዋላቸውን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች አልተገኙም፡፡ እውነቱን ለመናገር የእስራኤል ሃይሎች ሆነ ብለው ያወድሙ የነበረው ሲቪሎች የሚጠቀሙባቸውንና ለሕልውናቸው አስፈላጊ የሆኑ ዒላማዎችን ነበር፡፡›› በማለት ዘገባውን አጠቃልሏል፡፡[89] እስራኤል በሊባኖስ ያደረሰችውን ጥቃት በተመለከተ ለወጣ ሌላ ጥናት ሂውማን ራይትስዎች በሰጠው ማጠቃለያ፡- ‹‹እስራኤል ከጦርነት መሠረታዊ ሕግጋት ዋነኛው የሆነውን በወታደራዊ ዒላማዎች ላይ ብቻ ጥቃት የማድረስን ደንብ ጥሳለች›› ብሏል፡፡[90] ሌላው ግልፅ የሆነ ጉዳይ እስራኤል ወታደራዊ ዒላማዎችን ስትደበድብ በሲቪሎችና በሲቪል ተቋማት የሚደርሱ ውድመቶችን ለመቀነስ በቂ ጥረት አለማድረጓ ነው፡፡ በሂውማን ራይትስ ዎች ድምዳሜ መሠረት ‹‹ምንም እንኳን እስራኤል በሲቪሎች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ጥረት ማድረጓን ብትገልጽም የጦር ሃይሏ ተዋጊዎችንና ሲቪሎችን የመለየት ስልታዊ ብቃት የተጓደለው መስሎ (ሆነ ብሎ) ተስተውሏል፡፡››[91] ለምሳሌ በደቡብ ሊባኖስ የሆነውን እንመልከት፡፡ እስራኤል ነጻ የተኩስ ቀጠና ብላ በሰየመችው በዚያ አካባቢ የተገኘ ማንኛውም ሰው ዒላማ ይደረጋል፡፡ የአካባቢው ሰዎች ለቅቀው እንዲወጡ ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው በኋላ የእስራኤል ፍትህ ሚኒስትር ሃይም ራሞን ‹‹በደቡብ ሊባኖስ የሚገኙ መንደሮችን ወደ ትቢያነት እንቀይራቸዋለን›› በማለት ሐምሌ 27 ቀን አሳወቁ፡፡ ‹‹በዚያ አካባቢ (በደቡብ ሊባኖስ) የሚገኝ ማንኛውም ሰው ከሂዝቡሏህ ጋር በአንዳች መንገድ ግንኙነት ያለው ሽብርተኛ ነው›› ሲሉም አከሉ፡፡[92] ይሁን እንጂ ማስጠንቀቂያውን ተከትሎ ብዙ ሰዎች ሥፍራውን ለቅቀው ያልሄዱ ሲሆን ከእነርሱ ብዙዎቹ ተዋጊዎች ወይም የሂዝቡሏህ አባላት አልነበሩም፡፡ በአምኒስቲ ኢንተርናሽናል ግምት መሰረት ወደ 120.000 የሚጠጉና

አብዛኞቹ ሲቪሎች የሆኑ ሰዎች በጦርነቱ ጊዜያት ሁሉ በቦታው ነበሩ። ነሐሴ 7 ቀን የእስራኤል መከላከያ ኃይል፡- ‹‹ከሊታኒ ወንዝ በስተደቡብ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም ተሽከርካሪ ሮኬቶችን፤ ወታደራዊ ቁሳቁሶችንና ሽብርተኞችን እንደሚያጓጉዝ ተቆጥሮ በቦምብ እንዲጋይ ይደረጋል›› የሚል በራሪ ወረቀት በተኑ።

እነዚህን ሁሉ ሁኔታዎች እግምት ውስጥ በማስገባት አምኒስቲ ኢንተርናሽናል ሕዳር ወር ላይ ባወጣው ማጠቃለያ ዘገባው፡- ‹‹የእስራኤል ኃይሎች ከባድ የሆኑ ዓለማቀፋዊ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችንና የጦር ወንጀሎችን ፈጽመዋል›› ካለ በኋላ ‹‹በተለይም የእስራኤል አየር ሃይል አንዱን ከሌላው የማይለይና ያልተመጣጠነ ጥቃት በስፍራው አካሂዷል›› ሲል ይከሳል።[94] በተመሳሳይ ሁኔታ ሂውማን ራይትስዎች ባወጣው ዘገባ፡- ‹‹የእስራኤል መከላከያ ኃይል አጠራጣሪ ለሆኑ ወታደራዊ ዒላማዎች ሲል ከፍተኛ የሲቪሎች ጉዳት በተከታታይ ሲደርስ እያየ ችላ ብሏል›› በማለት ሌላ ክስ ያነሳል።[95] ይሁንና አንድም የእስራኤል ባለስልጣን እስራኤል ያልተመጣጠነ ኃይል የመጠቀምን ሕግ መጣሷን ሊያምን አልቻለም። በተ.መ.ድ የእስራኤል አምባሳደር ዳን ጊለርማን ጦርነቱ ከተጀመረ ከአንድ ሳምንት በኋላ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ያልተመጣጠነ ኃይል እየተጠቀምን እንደሆነ ለሚናገሩ ሃገራት የምነግራቸው ነገር ቢኖር፡- ፍርዳችሁ የተሳሳተ ነው፤ እኛ ትክክል ነን፤ በማለት ነው። ምክንያቱም ከተሞቻችሁ የእኛ ከተሞች እንደሚደበደቡት ብጤ ቢደበደቡባችሁ፤ ዜጎቻችሁ የእኛ ዜጎች ላይ የሚደርሰው ዓይነት ሽብር ቢደርስባቸው ኖሮ እኛ ከተጠቀምነው ኃይል የበለጠ ከመጠቀም ወደ ኋላ አትሉም ነበር።"[96]

የሆነ ሆኖ ጊለርማን ያልተመጣጠነ ኃይል መጠቀማቸውን ማመናቸው በራሱ የተለየ አቋም ሆኖ ሊወሰድ የሚችል ነው። ብዙ እስራኤላውያንና አሜሪካውያን ደጋፊዎቻቸው እስራኤል በሊባኖስ ላይ ያልተመጣጠነ ኃይል ተጠቅማለች የሚለውን ክስ ለማስተባበል "እስራኤል እርግጥ ነው በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰላማዊ ሰዎችን ገድላ ይሆናል። ሆኖም ግን ይህ ሊሆን የቻለው ሂዝቡላህ ሰዎችን በሰብዓዊ ጋሻነት ስለተጠቀመባቸው ነው" ሲሉ ይደመጣሉ።[97] አምንስቲ ኢንተርናሽናል በሕዳር ወር ያወጣው ዘገባና

የሂውማን ራይትስዎች ጥናት ግን ከዚህ አባባል ጋር በቀጥታ ይጋጫሉ። እስራኤል ከምታቀርባቸው ክሶች አንዱ፦ ‹‹ሂዝቡሏህ ሲቪሎችን በሰብአዊ ጋሻነት ለመጠቀም ሲል ከደቡብ ሊባኖስ እንዳይወጡ አግዷቸዋል።›› የሚል ነው። ይሁን እንጂ አምንስቲ ኢንተርናሽናል እንዳረጋገጠውና በተጨባጭ የሚታዩ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት እውነታው የተገላቢጦሽ ነው።[98] እንዲያውም የሂዝቡሏህ ተዋጊዎች ከሲቪሎች ጋር ላለመገናኘት ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ እንደነበር ለማመን የሚያስችሉ ጥሩ ምክንያቶች አሉ። ይህውም ፈጥኖም ሆነ ዘግይቶ በእስራኤል ግብረ-አበሮች እንዲህ ዓይነት ስም ማጥፋት እንደሚፈጸምባቸው ያውቁ ስለነበር።[99]

ሂዩማን ራይትስዎች ያቀረበው ዘገባ ሂዝቡሏህ በደቡባዊ ሊባኖስ በሰብዓዊ ጋሻነት ይጠቀምባቸው የነበሩ ሰዎችን ላለመግደል እስራኤል ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጋለች የሚለውን አባባል ይቃረናል። በሌላ በኩል ሂዝቡሏህ በሲቪሎች መኖሪያ ቤቶች ውስጥና አካባቢው አልፎ አልፎ መሳሪያዎቹን ይደብቅ እንደነበር፣ እንዲሁም ሕዝብ በበዛባቸው አካባቢዎች የተ.መ.ድ ታዛቢዎች ባሉበት አቅራቢያ የሮኬት ማስወንጨፊያዎችን ያስቀምጥ እንደነበር ሂውማን ራይትስ ዎች ግልጽ አድርጓል። የሁለቱም ወገኖች ድርጊቶች ከባድ የሆኑ የጦር ሕግጋት ጥሰቶች መሆናቸውንም ገልጿል።[100] በሌላ አገላለጽ ሂዝቡሏህ ተዋጊዎቹንና መሳሪያዎቹን ከጥቃት ለመጠበቅ ሲቪሎችን በጋሻነት መጠቀሙን የሚሳዩ ጥቂት ማስረጃዎች አልጠፉም። ግና እነዚያ ሁኔታዎች የተከሰቱት አልፎ አልፎ እንጂ ሂዝቡሏህ እንደመርህ የሚጠቀምባቸው የአሠራሩ ክፍሎች አልነበሩም። እንደ ሂዩማን ራይትስዎች ዋና ዳይሬክተር ኬኔት ሮዝ አባባል ከሆነ፦ ‹‹አብዛኛዎቹ ሲቪሎች ሲገደሉ በአካባቢያቸው ምንም ዓይነት የሂዝቡሏህ ሃይሎች አልነበሩም።››[101] ሂዩማን ራይትስ ዎች ሃያ አራት ነጥቦችን በጥናቱ በዝርዝር ተመልክቷል። ከጠቅላላዎቹ የንጹሐን ዜጎች ሞት ውስጥ አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት ሲቪሎች ዘገባው እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ መገደላቸውንም ጭምር በሪፖርቱ አካትቷል።[102] ይሁንና፦ ‹‹ሂዝቡሏህ ከእስራኤል ጦር ራሱን ለመከላከል ሆነ ብሎ ሲቪሎችን በጋሻነት የተጠቀመበት አጋጣሚ ስለመኖሩ በዘገባው አልተጠቀሰም።[103]

"ምንም እንኳን ሂዝቡሏህ በጦርነቱ ጊዜያት ሲቪሎችን በሰብዓዊ ጋሻነት ባይጠቀምም ሕዝብ በበዛባቸው ቦታዎች ውጊያ ማድረጉ ይታወቃል፡፡ በተለይም ተዋጊዎች የትውልድ ቀያቸውን ወይም ከተማቸውን ከጥቃት ለመከላከል በሚያደርጉት ጥረት ይህ ሊከሰት ይችላል፡፡›› የሚል መከራከሪያ የሚያነሳም ይኖራል፡፡ ይሁንና እንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎች ሂዝቡሏህ የጦርነትን ሕጎች በመጣስ በሲቪሎች ጋሻነት ከለላ ለማግኘት ሞከረ አያሰኙትም፡፡ ራሱንና ድንበሩን ከጠላት ለመከላከል ከሚያደርገው ሕጋዊ ፍልሚያ ውስጥ የሚካተት ነው፡፡ ጉዳዩ ይህን የሚመስል ከሆነ እስራኤል ሂዝቡሏህን ዒላማ ውስጥ ለማስገባት ሰላማዊ ሰዎችንም አንድ ላይ ከመጨፍለቅ የተሸለ ምርጫ አልነበራትም መባሉ ስህተት ይሆናል፡፡ ‹‹ሂዝቡሏህ በከተሞችና መንደሮች ውስጥ እንዲሁም በዙሪያቸው ውጊያ አካሂዷል›› የሚለው የመከራከሪያ ሃሳብም እንዲሁ አይሰራም፡፡ ምክንያቱም ሂዩማን ራይትስ ዎች በጥናቱ ካካተታቸው ሃያ አራት የሚሆኑ ነጥቦች ውስጥ ‹‹ሂዝቡሏህ ከጦርነቱ በፊትም ሆነ በጦርነቱ ጊዜ ተዋጊ ኃይሎቹንና የውጊያ መሳሪያዎቹን በመኖሪያ አካባቢዎች ማከማቸቱን የሚገልጽ መረጃ አልሰፈረም፡፡››[104] በአጭር አነጋገር የአምንስቲ ኢንተርናሽናል የህዳር ዘገባም ሆነ የሂዩማን ራይትስ ዎች ጥናት እስራኤል ስለ ሂዝቡሏህና ሰላማዊ ሰዎችን በሰብዓዊ ጋሻነት ስለመጠቀሙ ካቀረበቻቸው ክሶች ጋር የሚጋጩ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

በተጨማሪም የእስራኤል ጦር ተኩስ አቁም ከመደረጉ በፊት በደቡባዊ ሊናቦስ ያዘነባቸው ክላስተር ቦምቦች ሲቪልና ወታደራዊ ዒላማን ያልለዩና በዘፈቀደ የተፈጸሙ ድርጊቶች ነበሩ፡፡ አንድ የመድፈኛ ብርጌድ ቀዋጊ ‹‹ዝም ብለን እንደ እብድ ነበር የምንተኩሰው›› በማለት በጊዜው የነበረውን ሁኔታ አስቀምጦታል፡፡[105] ይህን ጭካኔ የተሞላበት የቂም በቀል ድርጊት እንዲህ በቀላሉ ከላይ የቀረቡትን የመከራከሪያ ሃሳቦች በማቅረብ ብቻ በይቅርታ ማለፍ ይከብዳል፡፡ እንዲሁም፡- ‹‹ሂዝቡሏህ በሰሜናዊ እስራኤል ላይ ያለምንም ልዩነት በሚያስወነጭፋቸው ሚሳዬሎቹና ሮኬቶቹ አማካይነት የበርካታ ሲቪሎችን ሕይወት በመቅጠፍ የጦር ወንጀለኝነት ድርጊት

ፈጽሟል›› የሚለው አጸፋዊ የክርክር ሃሳብም ለዚህ የእስራኤል ወንጀል ማቃለያ ሆኖ ሊቀርብ የሚችል ነጥብ አይደለም፡፡

እነዚህን ሁሉ በርካታ መረጃዎች እግምት ውስጥ ስናስገባ ዩናይትድ ስቴትስ በሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት እስራኤልን ያገዘችበት ምክንያት ‹‹ከሞራል አንጻር ትክክለኛው የፖሊሲ ምርጫ በመሆኑ ነው›› ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ሞራላዊ ሁኔታ በእርግጥም ዋነኛ የትኩረት ጉዳይ ሆኖ ቢሆን ኖሮ የቡሽ አስተዳደር እስራኤልም ሆነች ሂዝቡሏህ በሊባኖስ ያደረጉትን ገና ከመጀመሪያ ማውገዝ በተገባው ነበር፡፡

የሎቢው መራር እርምጃ

አይፓክና. ሌሎች አፍቃሪ እስራኤል ድርጅቶች ጦርነቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የአሜሪካ ሙሉ ድጋፍ እንዳይለያቸው በትጋት ነበር የተንቀሳቀሱት፡፡ ጦርነቱ ከተጀመረ ከአራት ቀናት በኋላ ናታን ጉትማን በእየሩሳሌም ፖስት ጋዜጣ ላይ ባወጣው ዘገባ፡- ‹‹የአሜሪካ አይሁድ ማሕበረሰብ እስራኤል በሁለት ግንባር የከፈተችውን ጦርነት ታሽንፍ ዘንድ ድጋፍ ለማሰባሰብ ቤት ለቤት ተንቀሳቅሷል›› ብሏል፡፡[106] ሎቢው በበኩሉ ለአይሁዳዊቷ ሃገር ገንዘብ በማሰባሰብ፣ በጋዜጦች ላይ ገጽታዋን የሚያሳምሩ ጽሑፎችንና ማስታወቂያዎችን በማውጣት፣ የመገናኛ ብዙሃንን እንቅስቃሴ በመቆጣጠር፣ ተወካዮቹን በኮንግረሱ ውስጥ ከሚገኙ ሕግ አውጪዎችና ባልደረቦቻቸው እንዲሁም በቡሽ አስተዳደር ውስጥ ከሚገኙ ፖሊሲ አውጪዎች ጋር እንዲወያዩ በማሰማራትና በመገናኛ ብዙሃን (media) ታላቅ ተጽዕኖ ያላቸውን ሰዎች በማነጋገር እንቅስቃሴዎች ተወጥሮ ነበር የሰነበተው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጦርነቱ ከተጠናቀቀም በኋላ ቢሆን አፍቃሪ- እስራኤል ድርጅቶች እስራኤል ያጋጠሟትን ችግሮችና የፖለቲካ ውድቀቶች አስመልክቶ መፍትሄ ለመፈለግ በትልቅ ውጥረት ሲዋከቡ ቆይተዋል፡፡

በአጠቃላይ ሎቢው ያለውን ተጽዕኖ ለማወቅ የሚከተሉትን ስድስት ክስተቶች (አጋጣሚዎች) ማጤን ይጠቅማል፡-

<u>አንደኛ</u>- ጦርነቱ እንደተጀመረ የተወካዮች ምክር ቤት እስራኤልን በመደገፍ ባወጣው ረቂቅ ሕግ ላይ ‹‹ሁለቱም ወገኖች የሲቪሎችን ሕይወትና የመሠረተ ልማት ውድመትን እንዲከላከሉ›› የሚል ዓረፍተ ነገር በመጨመር እንዲስተካከል ለማድረግ በጋራ የተቀናጀ ጥረት (bipartisan effert) ተደርጓል፡፡ የኮንግረስ አባሏ (በዚያ ጊዜ የአናሳዎቹ መሪ ነበሩ) ናንሲ ፔሎሲና የቨርጂኒያው ሪፐብሊካን ተወካይ ሴናተር ጆን ዋርነር (በጊዜው የሴኔቱ የጦር ኃይሎች አገልግሎት ኮሚቴ ሊቀመንበር ነበሩ) ይህን ለውጥ በመደገፍ ቢያንስ ሞራላዊ ጉዳዮችን እግምት ውስጥ የማስገባትን አስፈላጊነት በማጉላት ድምጻቸውን ካሰሙት ውስጥ ይገኙበታል፡፡ ማንም ቢሆን በቀላሉ ሊያስበው እንደሚችለው የኮንግረስ አባላቱ ይህ ዓረፍተ ነገር ሙሉ ተቀባይነት ባያገኝ እንኳን ቢያንስ ተቃውሞ አይነሳበትም የሚል እምነት ነበራቸው፡፡ ይሁን እንጂ የመጀመሪያውን ረቂቅ ያዘጋጀውና ከዚህ ሕግ ጀርባ ያለው ዋነኛ አንቀሳቃሽ ኃይል አይፓክ አዲስ እንዲጨመር የታሰበውን ሐረግ (ዓ.ነገር) በጽኑ ተቃወመው፡፡ ከዚያ በኋላ የምክር ቤቱ ብዙሃን (majority) መሪ ጆን ቦህነር አዲስ እንዲጨመር ሀሳብ የቀረበበትን አገላለጽ በማስወገድ በቀድሞው ይዘቱ የሕግ ረቂቁ ለድምጽ እንዲቀርብ አድርገው 410 ለ8 በሆነ ውጤት ሊያልፍ ችሏል፡፡

<u>ሁለተኛ</u>- የሜሪላንዱ ዲሞክራቲክ ፓርቲ ተወካይ ክሪስቶፈር ቫን ሆለን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሯ ኮንዶሊዛ ራይስ ሐምሌ 30 ቀን ደብዳቤ በመጻፍ በአስቸኳይ የተኩስ አቁም እንዲደረግና በደቡብ ሊባኖስ የሚሰፍር ዓለም አቀፋዊ ሰራዊት እንዲመደብ ጥሪ አቀረቡ፡፡ ቫን ሆለን የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች በደብዳቤያቸው ውስጥ አካትተዋል፡- ‹‹እስራኤል አሁን እንደምናየው እየወሰደች ያለችው የአጸፋ እርምጃ የሂዝቡላህን ወታደራዊ ይዞታዎችና ንብረቶች ከማውደም የዘለለ ሆኗል፡፡ ድብደባው የሊባኖስን መሰረተ ልማቶች ከማፈራረሱም በላይ ለበርካታ ሰላማዊ ሰዎች ማለቅ ምክንያት ሆኗል፡፡ እንዲሁም 750.000 የሚሆኑ ሰዎች ከቀያቸው ተፈናቅለው እንዲሰደዱ አስገድዷል፡፡ በእርግጥ ሂዝቡላህ ወንጀለኛ ነው፡፡ ሆኖም ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ የመጣውን የጦርነቱን ገፈት የሚቀምሱት የሊባኖስ ዜጎች እንጂ ሂዝቡላህ አይደለም፡፡ በውጤቱም እስራኤል

የምታካሂደውና በዩናይትድ ስቴትስ የተደገፈው የቦምብ ድብደባ ዘመቻዋ ሊባኖሳውያን በሂዝቡሏህ ላይ ያደረባቸውን ቁጣ እንደዘነጉና እስራኤልንና ዩናይትድ ስቴትስን በኃይል ወደ መጥላት እንዲዞሩ አድርጓቸዋል። ይህ ጥላቻቸው ደግሞ በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ነው። የዚህ ሁሉ ውጤት ታዲያ የሂዝቡሏህንና የመሪውን የሃሰን ነስረሏህን ፖለቲካዊ ጥንካሬና ተቀባይነት በመጨመር ደካማውን የሊባኖስ መንግስት ይበልጥ እያዳከመው ይገኛል። ሂዝቡሏህን ከሕዝቡ ለመነጠል የሚያስችለንን እድልና በክልሉ ያለንን ታማኝነት፣ እንዲሁም የማደራደር ተጽዕኖአችንን ጭምር በማባከን ላይ እንገኛለን።"[108]

ምንም እንኳን የሆለን ደብዳቤ፡- ‹‹እስራኤል ራሷን የመከላከል መብቷን ትጠቀም ዘንድ እናግዛት›› የሚል መንፈስ ያለው ቢሆንም ሎቢው ግን እስራኤልን ለመተቸት በመዳፈራቸው በእርሳቸው ላይ የቁጣ መዓቱን አወረደባቸው። ደብዳቤውን እንዳይልኩ ለማድረግም በይፋ ተንቀሳቀሰ።[109] ቫን ሆለን አይፓክን ጨምሮ ከሌሎች ዋና ዋና የአይሁድ ድርጅቶች ጋር ወዲያው ተገናኝተው ይቅርታ እንዲያደርጉላቸው በመጠየቅ የሚከተለውን ተናገሩ። ‹‹ክቡራን! አዝናለሁ። የቡሽን አስተዳደር ውድቀቶች ጠቅሼ ኃይለኛ ትችት መሰንዘሬ እስራኤል አሁን የምታሳየውን ባሕሪዋን እንደመንቀፍ ከተቆጠረብኝ አዝናለሁ። ዓለማዬ ያንን ማድረግ እንዳልሆነ ይታወቅልኝ።"[110] ይህን ካሉ በኋላ ‹‹የእስራኤል ጠንካራ ደጋፊ መሆኔን እቀጥላለሁ›› የሚል መግላጫቸውን በማከል ጉዳዩን ለማለሳለስ ጥረት አደረጉ። ከዚያ ቀጥለው ደግሞ አምስት ቀናት የፈጀ ጉብኝት ለማድረግ ወደ እስራኤል ተጓዙ። (ጉዞውን ያቀናጀው የአይፓክ ተባባሪ የሆነው ዘ አሜሪካን እስራኤል ኢዱኬሽን ፋውንዴሽን የተባለው ድርጅት ነው)። በጉብኝቱ ወቅት ሆለንን አጅበው ወደ እስራኤል ከሄዱት መካከል አፋቃሪ እስራኤል የሆኑና እርሳቸው ከተወከሉበት ክ/ሃገር (state) የመጡ ሶስት የፖለቲካ ተሳታፊዎች (poletical activist)፣ እንዲሁም ከአይፓክ ከራሱ የተውጣጡ አባላት ይገኙበታል።

ሆለን የአይሁድ ማሕበረሰብን ይቅርታ ከጠየቁ በኋላ ዘ ጆዊሽ ኮሚኒዩቲ ሪሌሽንስ ካውንስል አፍ ግሬተር ዋሽንግተን የተባለው ድርጅት በሰጠው

አስተያየት ‹‹ሆለን ከእስራኤል ጎን መሰለፋቸው ይረጋገጥ ዘንድ ለአይሁድ ማሕበረሰብ የሚሰጡትን ድጋፍ መቀጠል አለባቸው..." ብሏል፡፡ በጸረ-ስም ማጥፋት (ኤ.ዲ.ኤል) ድርጅት የዋሽንግተን አካባቢ ዳይሬክተር ደግሞ ‹‹ቫን ሆለን የጻፉት ደብዳቤ ያስከተለውን ጉዳት መጠገን አይቻልም›› በማለት ገልጸዋል፡፡[111] በእውነቱ የዚህ ሁሉ ሂደት ዋነኛ ግብ ቫን ሆለንን መቅጣት አልነበረም፡፡ ከዚያ ይልቅ ሌሎች የኮንግረስ አባላት ከሎቢው መስመር ወጥተው የሚጓዙ ከሆነ ሊከፍሉ የሚችሉት ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ ማሳየት ነው፡፡

<u>ሶስተኛ</u>- ጦርነቱ ከመደረጉ በፊት እስራኤል በሊባኖስ የሚሸነውንና ስልጣን ላይ እንዲወጣ ብዙ የደከሙለትን መንግስት በእርጋት እንድትይዘው፣ እንዲሁም ከሥልጣን እንዳይወርድ ጥንቃቄ እንድታደርግ ፕሬዝዳንት ቡሽ ማበረታቻ ሰጡ፡፡ ‹‹እዚህ ላይ አሳሳቢው ጉዳይ›› አሉ ቡሽ ቀጥለውም ‹‹እስራኤል ራሷን ለመከላከል የምትወስደው እርምጃ በሊባኖስ ስልጣን ላይ ያለውን መንግሥት እንዳያዳክመው ወይም ሥልጣኑን እንዳያሳጣው ነው፡፡ "[112] ቡሽ ግልጽ እንዳደረጉት እርሳቸውም ሆኑ የጦር አበጋዞቻቸው ሃሳባቸውን ለእስራኤል መሪዎች አሳውቀዋቸዋል፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ ሎቢው ቡሽ የያዙት አቋም ተቀባይነት እንደሌለው አበክሮ መግለጽ ጀመረ፡፡ ፎርዋርድ ሐምሌ 14 ቀን በወጣ እትሙ፡- ‹‹የቡሽ አስተዳደር በሊባኖስ የሚገኘውን በዲሞክራሲ የተመረጠ መንግስት እስራኤል በጥንቃቄ እንድትይዘው ያደረገው ጥሪ በእስራኤልና በአይሁድ ማሕበረሰብ ባለስልጣናት ትችት ቀረበበት›› የሚል ዘገባ ይዞ ወጣ፡፡ የኤ.ዲ.ኤል. ፕሬዝዳንት አብረሐም ፎክስማን በጉዳዩ ላይ ያላቸውን አስተያየት ሲሰጡ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹የቡሽ አስተዳደርና የምዕራቡ ዓለም አገራት የሊባኖስን መንግሥት መደገፍ ይፈልጋሉ፡፡ ሆኖም ግን ይህን ማድረግ የተሳሳተ ፖሊሲን መከተል ነው፡፡ ይህ አመለካከታቸው አቡ ማዚንንም ያካትታል፡፡ በእነርሱ እምነት ቦታው ባዶ ከሚሆን አቡ ማዚንና ሲኞራ ቢይዙት ይሻላል፡፡ ሆኖም ግን ትርጉም የሌለውን ነገር መደገፍ በራሱ ልክ አይደለም፡፡ እኛ ከመጀመሪያው አንስቶ አቡ ማዚን የትም እንደማይደርሱና የሊባኖስ መንግስትም ቢሆን ውጤታማ እንደማይሆን እናውቅ ነበር፡፡››[113]

ይህ ትችት በተነሳ ሰሞን ቡሽ፣ ሃገራቸው የምትደግፈውን የቤሩቱን የፉአድ ሲኞራ መንግስት ጥበቃ እንድታደርግለት ለእስራኤል የሚሰጡትን ማስጠንቀቂያ አቆሙ።

<u>አራተኛ</u>- የዋሽንግተን ፖስት ታዋቂ ጋዜጠኛ ቶም ሪክስ በጦርነቱ ሰሞን ለሲ.ኤን.ኤን. ቴሊቭዥን ጣቢያ አንዳንድ የዩ.ኤስ.አሜሪካ ወታደራዊ ጉዳይ ተንታኞች የነገሩኝ ነው በማለት በሰጠው አስተያየት፡-

‹‹እስራኤል ሆነ ብላ የተወሰኑ የሂዝቡሏህን የሮኬት ማስወንጨፊያ ሥፍራዎች ሳትደመስሳቸው ቀርታለች። ምክንያቱም እነዚያ ሮኬቶች ወደ ግዛቷ መወንጨፍ እስከቀጠሉ ድረስ በሊባኖስ ላይ ለመዝመት ስትፈልግ የሞራል ጥያቄ እንዳይነሳባት ያግዟታል›› ብሏል።[114] አስተያየቱን ተከትሎ ዘ- ኮሚቲ ፎር አኪዬሬሲ ኢን ሚድል ኢስት ሪፖርቲንግ ኢን አሜሪካ የተባለው ድርጅት የሪክስን አባባል አውግዟል። የቀድሞው የኒው ዮርክ ከተማ ከንቲባ ኤድ ኮች ለዋሽንግተን ፖስት ዋና አዘጋጅ ሊዮናርድ ደዊይን ጁኒዮር በጻፉት ደብዳቤ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ይህ የሪክሰን አስተያየት ጸረ-ሴማውያን በአውሮፓ ታሳቁን እልቂት በፈጸሙ ጊዜ ይጠቀሙበት ከነበረው ያረጀና የጎፈየ ስም ማጥፋ ጋር ተመሳሳይ ነው።›› ደዊይን ለኮች በጻፉላቸው የመልስ ደብዳቤ እንዲህ የሚል ነገር ጨምረው ላኩላቸው፡- ‹‹ከእንግዲህ በሚያወጣቸው ጽሑፎች ላይ እንዲህ ዓይነት ዓ.ነገሮችን እንዳይጠቀም ለቶም ሪክስ ግልጽ አድርጌለታለሁ።"[115] ለምን? ደዊይን መልስ የላቸውም። ሪክስ ራሱ እንዲህ ብሏል፡- ‹‹የሰጠኋቸው አስተያየቶች ሰዎች የነገሩኝን እንደመሆኑ ትክክለኞች ናቸው። እንዳልተናገርኳቸው ይቆጠርልኝ። ከዚህ በኋላም በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ምንም ነገር ላለመተንፈስ አፌን እዘጋለሁ።"[116]

<u>አምስተኛ-</u> አምንስቲ ኢንተርናሽናልና በተለይም ደግሞ ሂውማን ራይትስ ዎች እስራኤል በሊባኖስ የፈጸመችውን ዘግናኝ ድርጊት አስመልክቶ ባወጡት ጥልቅ ይዘት ያለው ዘገባቸው ምክንያት አፍቃሪ እስራኤል ቡድኖች ሰፊ ሽፋን ያለው የስም ማጥፋት ዘመቻ ከፈቱባቸው። በሔለን ደርሻዊትዝ አገላለጽ፡- ‹‹ከሞላ ጎደል ሁሉም የአይሁዳውያን ማሕበረሰብ አካላት፣

ከሴኩላሪስቱ እስከ ሃይማኖተኛው፣ ከሊበራሉ እስከ ኮንሰርቫቲቩ ሂውማን ራይትስ ዎች ለአንድ ወገን በማድላቱ አውግዘውታል።"[117] ሁለቱም የሰብዓዊ መብት ጠባቂ ድርጅቶች ‹‹እስራኤልን ብቻ ለይተው በመተቸት የሂዝቡሏህን ድርጊቶች ችላ ብለዋል፤ በደቡብ ሊባኖስ ምድር የተፈጸመውን ክስተት አጣመው ተርጉመዋል›› ተብሎ በእስራኤልና በአፍቃሪ እስራኤል ወገኖች የቀረበባቸው ክስ ተገቢነት የለውም። በተመሳሳይ ጊዜ አይፓክ የሚያወጣቸው ጋዜጣዊ መግለጫዎች የእስራኤል መከላከያ ኃይል ሽብርተኞችን ለመመንጠር በሚያደርገው ስልታዊ ፍልሚያ ሲቪሎችን ከጉዳት እንደሚጠብቅ የሚገጹ ነበሩ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ነበር እንግዲህ አይቀሬ የሆነው የጸረ-ሴማዊነት መለያ (ታፔላ) ለሁለቱ የሰብዓዊ መብት አስከባሪ ድርጅቶች፣ ማለትም ለሂዩማን ራይትስ ዎችና ለአምንስቲ ኢንተርናሽናል የተለጠፈላቸው። እዚህ ላይ አስደናቂው ጉዳይ የሂዩማን ራይትስ ዎች ዋና ዳይሬክተር ኬኔት ሮዝ ምንም እንኳን ራሳቸው አይዳዊ ቢሆኑና አባታቸውም በናዚ ጀርመን ማጎሪያ ካምኘ ታስረው የነበረ ቢሆንም የዚህ ስም የማጥፋት ጥቃት ስለባ ከመሆን አላመለጡም። እየሱሳሌም ፖስት ለምሳሌ በጂራልድ ስቴይንበርግ የተጻፈና ‹‹የኬይን ሮዝ ዘረኛ ስም አጥፊነት" የሚል ርዕስ የያዘ ጽሑፍ ይዞ ወጥቶ ነበር። ኒው ዮርክ ሰን ደግሞ በርዕሰ አንቀጹ ላይ ‹‹ሮዝ የጆዳይዝምን ሕግ ሻሩ›› ካለ በኋላ ‹‹ምክንያቱም የእስራኤል መከላከያ ኃይል በሊባኖስ የተከተለውን ስትራቴጂ በመንቀፍ "ዓይን ያጠፋ ዓይኑ ይጥፋ"፣ በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ "ለአንድ ዓይን ሃያ አይኖች ይጥፉ" የሚለውን እጅግ ጥንታዊ ሕግ ቢያንስ ማገናዘብ አቅቷቸዋል›› ሲል ሃሳቡን አጠቃሏል። የጸረ ስም ማጥፋት ሊጉ (ኤ.ዲ.ኤል) ፕሬዝዳንት አብረሃም ፎክስማንም የሮዝን ሀሳብ በማጥላላት፡- ‹‹የጎፈየውን የጸረ ሴማዊነት ዘይቤ የሚከተሉ ገትጋታ›› በማለት ወርፏቸዋል።[119]

ለዚህ ዓይነት ክሶች መልስ ይሆን ዘንድ በጋዜጦች ላይ በዓምደኝነት የሚታወቁት የጆርጅ ታውን ሕግ ፕሮፌሰር ሮዝ ብሩክስ በሎስ አንጀለስ ታይምስ ጋዜጣ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡- ‹‹ለሂውማን ራይትስ ዎች ወይም ለሮዝ ቅርበት ያለው ማንም ሰው እንደሚያውቀው እየሆነ ያለው ነገር ሁሉ

እብደት ነው፡፡ ሂዩማን ራይትስ ዎች ከማንም ጋር የማይወግንና በግጭቶች ጊዜ ማንንም የማይደግፍ (non-partisan) ድርጅት ነው፡፡ ስለሆነም ሮዝን ከጸረ-ሴማዊነት ጋር የማያያዙ ጉዳይ ጤናማ አስተሳሰብ አይደለም፡፡›› ብሩክስ ሃሳባቸውን ቀጥለው ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹ከሁሉም በላይ በሮዝና በድርጅታቸው ላይ ያነጣጠረው የጥላቻ ዘመቻ ስልጣኔ የጎደለው፣ መሠረት የሌለውና ያልተለመደ መሆኑ አይደለም ችግሩ፡፡ ትልቁ ችግር ይህ ዘመቻ የተለመደና የሚደጋገም የመሆኑ ነገር ነው፡፡ አዎን! ማንም እስራኤልን የሚነቅፍ ግለሰብም ሆነ አካል ይደርስብኛል ብሎ የሚጠብቀው የተለመደ ስም ማጥፋት መሆኑ ነው፡፡ ዛሬ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ እስራኤልን አስመልክቶ ሰላማዊ ክርክር ማድረግ አይቻልም፡፡ ምክንያቱም የእስራኤልን ፖሊሲዎች በተመለከተ ትችት ወይም ነቀፋ የሚሰነዘር ማንም ሰው ጸረ-ሴማዊ የሚል ቅጥያ በፍጥነት ይሰጠዋልና፡፡›››[120]

<u>ስድስተኛ</u>- እስራኤል በደቡባዊ ሊባኖስ ምድር ያዘነበችው የክላስተር ቦምብ ውዝግብ ያስከተለውን ጉዳት ለመሸፋፈን (ጎልቶ እንዳይታወቅ ለማድረግ) ሎቢው ጠንክሮ መስራት ያዘ፡፡ ነሐሴ 31 ቀን ብናዒ ብሪዝ ኢንተርናሽናል የተባለው አፍቃሪ-እስራኤል ድርጅት ጃን-ኤግላንድ ለተባሉትና እስራኤል በጦርነቱ የክላስተር ቦምብ መጠቀሟን ለነቀፉ የተ.መ.ድ ባለስልጣን ደብዳቤ በመጻፍ እርሳቸውን የሞራል ጉዳይ ጠባቂና አስታራቂ ሽማግሌ አድርጎ የሾማቸው ሳይኖር ጦርነቱን አስመልክቶ በተጨባጭ ምድር ላይ የሌሉና ያልተገኙ መረጃዎችን፣ እንዲሁም ዓለም ዓቀፋዊ የሰብዓዊ መብት ሕግጋትን በመንተራስ ብቻ በእስራኤል ላይ ጫና በማሳደራቸው ተጠያቂ መሆናቸውን ገለጸላቸው፡፡›››[121] ከአንድ ሳምንት በኋላ ሴኔቱ በሰላማዊ ሰዎች መኖሪያ አካባቢ ክላስተር ቦምብ መጠቀምን ለማገድና እገዳውን ለማይቀበሉ አገራትም መሣሪያው እንዳይሸጥላቸው ወይም በተለያዩ መንገዶች እንዳይተላለፍላቸው የሚከላከል ረቂቅ ለውሳኔ አቀረበ፡፡ በዚያ ጊዜ አይፓክ በሕጉ አንጻር ጠንካራ ሎቢ አደረገ፡፡ በመሆኑም ሕጉ 70-ለ30 በሆነ ድምጽ ውድቅ ተደረገ፡፡[122]

በሎቢው ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ድርጅቶች ዩ.ኤ.ስ አሜሪካ በሊባኖስ በምትከተለው ፖሊሲ ላይ ተጽዕኖ ማድረግ መቻላቸውን አስመልክተው

ግልጽ ውይይት የማድረግ ፍላጎት አሳይተዋል። ለምሳሌ የአይፓክ ፕሬዝዳንት ሃዋርድ ፍሪድማን ለድርጅታቸው ወዳጆችና ደጋፊዎች ኃምሌ 30 ቀን የጻፉትን ደብዳቤ እንዲህ በሚል ሐረግ ነበር የጀመሩት፡- ‹‹ያደረጋችሁትን ሁሉ ተመልከቱ!›› ከዚያም ቀጠል አድርገው "በዓለም ላይ ካሉት አገራት መካከል አንዷ ብቻ ነጠል ብላ በመውጣት በግልጽ እስራኤል የጀመረችውን ሥራዋን ታጠናቅቅ ዘንድ አቋሟን ገለጸች። ያች ሃገር ዩ.ኤስ. አሜሪካ ናት። ለዚህ አቋም ዋነኛዎቹ ምክንያቶች ደግሞ እናንተና መላው የአሜሪካ አይሁድ ማሕበረሰብ ነው"[123] አሉ። ለዚህም ነው ጠቅላይ ሚኒስተር ኦልመርት በጦርነቱ ወቅት "በመላው ዓለም ካሉን ወዳጆችና ደጋፊዎች ሁሉ ታላቅ የሆነውን አይፓክን የሰጠን አምላክ የተመሰገነ ይሁን" ማለታቸው የሚያስደንቀው።[124]

በሁለተኛው የሊባኖስ ግጭት ወቅት አይፓክና ኤ.ዲ.ኤልን የመሳሰሉት ድርጅቶች ብቻ አልነበሩም በፖለቲካው ምህዳር ቁልፍ ሚና ሲጫወቱ የነበሩት። ቻርልስ ክራወታመርንና ዊሊያም ክሪስቶልን የመሰሉ እውቅ ጋዜጠኞችም የላቀ ሚና ነበራቸው። በአጭሩ የዊሊያም ክሪስቶልን አባባል ለመጥቀስ፡- ‹‹እስራኤል የምታካሄደው ጦርነት የእኛም ጦርነት ነው።››[125] በርካታ ክርስቲያን ጽዮናዊያንም እንዲሁ ከእስራኤል ጎላ መቆማቸውን ግልጽ አድርገው ነበር። ለአብነት ያክል ኢቫንጀሊስት ፓት ሮበርትስን በጦርነቱ ወቅት በእየሩሳሌም ፖስት አገላለጽ፡- ‹‹ህልውናዋ በሂዝቡላህ ስጋት ላይ ለወደቀባት ሃገር ያላቸውን ድጋፍ ለማሳየት›› እስራኤልን ለሶስት ቀናት ጎብኝተዋል። ሮበርተሰን ለፖስት በሰጡት መግለጫ፡- ‹‹አይሁዳውያን በአምላክ የተመረጡ ሕዝቦች ናቸው። እስራኤልም በአምላክ ልብ ውስጥ ልዩ ሥፍራ ያላት ሃገር ናት። ስለሆነም እርሱ ከጥፋት ይጠብቃታል። እኛ ወንጌላውያን ክርስቲያኖችም ከእስራኤል ጎን እንቆማለን። ዛሬ በመካከላችሁ የተገኘሁበት አንዱ ምክንያትም ይኸው ነው‹‹[126] ብለዋል። የዋሽንግተን እስራኤል ጎባኤ በዋና ከተማዋ ዋሽንግተን ሐምሌ አጋማሽ ላይ ሲደረግ የጆን ሃጊ ድርጅት የሆነው ክሪስቲያንስ ዩናይትድ ፎር እስራኤል ሶስት ሺህ አምስት መቶ የሚሆኑ ታዳሚዎችን አሳትፏል። የጉባኤው ተሳታፊዎች ወደየመጡባቸው ግዛቶች (states) ከመመለሳቸው በፊት የወከሏቸው

ሴናተሮችና የኮንግረስ አባላት እስራኤልን እንዲደግፉ ግፊት እንደሚያሳርፉባቸው ቃል ገብተዋል።[127] ክርስቲያን ፍሬንድስ ኦፍ ኢስራኤል የተባለው ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ክርስቲያናዊ ያልሆነና አርቆ አስተዋይነት የጎደለው ሃሳብ በማራመድ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹ይህ ጥቃት የተጀመረው እነርሱ በጫሩት ጠብ ምክንያት እስከሆነ ድረስ እስራኤል ልትቀጠቅጣቸው የሚያስችላት ሙሉ መብት አላት።"[128]

እርግጥ ነው ከፍ ሲል የተጠቀሱት ሃይማኖታዊ ሰው እንዳሉትም እስራኤል ቅድመ ሁኔታ እና ገደብ አልባ በሆነው የዩ.ኤስ. አሜሪካ እርዳታና ሎቢው በሚያሳድረው ተጽዕኖ እየታገዘች ሊባኖስን ቀጥቅጣታለች።

የአሜሪካ ሕዝብና ሊባኖስ

ዋሽንግተን በሊባኖስ ጦርነት እስራኤልን በጽናት መደገፏ የሎቢው ተጽዕኖ የፈጠረው ውጤት ነው ወይስ የአሜሪካ ሕዝብ ሁልጊዜም ለእስራኤል ጥልቅ የሆነ ስሜት ስላለው እውን የሆነ? ምናልባት እስራኤል ያን ሁሉ ያልተገደበ ድጋፍ ልታገኝ የቻለችው የአሜሪካ ሕዝብ ጥያቄ ከጀርባ ስላለ ሊሆን ይችላል። የአይፓክ ቃል አቀባይ የሆኑት ጀኒፈር ካናታ በጦርነቱ ጊዜ ይህን የተለመደ የመከራከሪያ ሃሳብ ሊያራምዱ ሞክረዋል። ጀኒፈር ሎቢው ያደረገውን ተጽዕኖ በመካድ፡- ‹‹እስራኤል በሽብርተኝነት ላይ የምታደርገውን ዘመቻ የአሜሪካ ሕዝብ በስፋት የሚደግፍ በመሆኑ በዚህ የጭንቅ ሰዓት ከቅርብ ወዳጃችን ጎን መቆም እንደሚገባን ይገነዘባል›› ብለዋል።[129]

ይህ ዓይነቱ የመከራከሪያ ሃሳብ አሳማኝ አይደለም። በሊባኖስ ጦርነት ጊዜ የሆነው ሁሉ በግልጽ ያየነውና የሰማነው ነው። ዩ.ኤስ.አሜሪካ ስትከተለው የነበረው ፖሊሲ የአሜሪካን ሕዝብ በትክክል የሚወክል አልነበረም። ይህ ሁኔታ ሊባኖስ ውስጥ የተፈጸሙ ስድስት ወሳኝ ጉዳዮችን አስመልክቶ በተደረጉ ጥናቶች በግልጽ ተንጸባርቋል። ግጭቱን ማን ቀሰቀሰው? የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ የኤ.ቢ.ሲ ኒውስ እና ዋሽንግተን ፖስት በጋራ በ2006 ነሐሴ ወር ላይ ባደረጉት ጥናት 46 ከመቶ የሚሆኑት በጥናቱ

የተካተቱ ሰዎች እስራኤልም ሆነች ሂዝቡላህ እኩል ተጠያቂ መሆናቸውን ገልጸዋል። 7% የሚሆኑትም እስራኤልን ለብቻዋ ተጠያቂ አድርገዋል። የሲ.ቢ.ኤስ ኒውስ እና ኒው ዮርክ ታይምስ በሐምሌ 25/ 2006 ባደረጉት ጥናትም እንዲሁ 46 ከመቶ የሚሆኑት መልስ ሰጪዎች፡- ‹‹ሁለቱም ወገኖች ተጠያቂ ናቸው›› ያሉ ሲሆን 5 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ ‹‹በአብዛኛው እስራኤል ናት ተጠያቂዋ›› የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

በጦርነቱ እስራኤል የወሰደችው የአጸፋ ምላሽ ከሚገባው በላይ የተጋነነ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ከሃምሌ 21-23 በተካሄደ የዩ.ኤስ.ኤ ቱደይ ጋሉፕ ጥናት መሠረት 38 ከመቶ የሚሆኑት በጥናቱ የተካተቱ ሰዎች እስራኤል በሊባኖስ ላይ የወሰደቸውን ወታደራዊ እርምጃ እንደማይደግፉ ገጸዋል። እንዲሁም በኤ.ቢ.ሲ.. ፖስት ጥናት 32 ከመቶ የሚሆኑት እስራኤል ከሚፈልገው በላይ ኃይል መጠቀሟን የተናገሩ ሲሆን 48 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ ‹‹እስራኤል ሰላማዊ ሰዎችን የሚያቆስሉና የሚገድሉ ዒላማዎችን መደብደቧ ምክንያታዊ አይደለም›› ብለዋል። 54 ከመቶ የሚሆኑት ‹‹እስራኤል በሲቪሎች ላይ የሚደረጉ ጉዳቶችን ለማስወገድ ብዙ መሥራት አለባት›› በማለት ገልጸዋል።

ዩናይትድ ስቴትስ እስራኤልን በግጭት ወቅት ማውገዝ ወይስ ገለልተኛ መሆን ይገባት እንደሆነ በተመለከተ ዩኤስ.ኤ ቱደይ ጋሉፕ ባደረገው ጥናት 65 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች ዩናይትድ ስቴትስ ከሁለቱም ያልወገነች ገለልተኛ መሆን እንደሚገባት ተናግረዋል። ከነሐሴ 11-15/2006 በተደረገው የዞግቢ ጥናት 52 ከመቶ የሚሆኑት ዩናይትድ ስቴትስ በግጭት ወቅት የገለልተኛነት አቋም መያዝ እንዳለባት አመልክተዋል።[131] በሲቢ.ኤስ. ኒውስና ኒው ዮርክ ታይምስ ጥናት መሠረት 40 ከመቶ የሚሆኑ መላሾች ዩናይትድ ስቴትስ በይፋ እስራኤልንም ሆነ ሂዝቡላህን ከመደገፍ መታቀብና ‹‹ምንም ነገር ከመናገር ወይም ከማድረግ›› መቆጠብ አለባት ብለዋል። ሰባት ከመቶ የሚሆኑት እስራኤልን የነቀፉ ሲሆን አሥራ አራት ከመቶ የሚሆኑት ግን ምን መወሰን ወይም መናገር እንዳለባቸው እርግጠኛ አለመሆናቸውን ገልጸዋል። ሰላሳ ሰባት ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ እስራኤልን የሚደግፉ መሆናቸውን ይፋ አድርገዋል። ኤን.ቢ.ሲ.ኒውስና ዎል ስትሪት ጆርናል ከሐምሌ

21-24/ 2006 ባደረጉት ጥናት 40 ከመቶ የሚሆኑት በጥናቱ የተካተቱ ሰዎች የሊባኖስ ጦርነት ተስፋፍቶ እስራኤል ከሌሎች በአካባቢው የሚገኙ አገራት ጋር ጦርነት ብትገጥም እንኳ ዩ.ኤስ አሜሪካ እርሷን ለማገዝ ጣልቃ መግባት እንደሌለባት ተናግረዋል።

ዩናይትድ ስቴትስና እስራኤል የተኩስ አቁም ስምምነት በፍጥነት እንዲደረግ መስማማት ያለባቸው ስለመሆኑ ሲ.ኤን.ኤን ሐምሌ 19 2006 ላይ ባደረገው ጥናት 43 ከመቶ የሚሆኑት የጥናቱ ተካፋዮች ‹‹እስራኤል በተቻለ ፍጥነት የተኩስ አቁም ስምምነት እንዲደረግ መስማማት አለባት›› የሚል አቋም አራምደዋል። 35 ከመቶ የሚሆኑት፡- ‹‹እስራኤል አስቸኳይና ቅድመ ሁኔታ ያልታከለበት የተኩስ አቁም ስምምነት ማድረግ አለባት›› ብለዋል።

የሊባኖስ ጦርነት ያስከተለው ውጤት የአሜሪካን የሽብርተኝነት ችግር በማባባስ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በማስመልከት ዩ.ኤስ.ኤ. ጋሎፕ ባደረገው ጥናት 44 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች በሊባኖስ እየተካሄደ ያለው ጦርነት ‹‹በዩ.ኤስ. አሜሪካ ላይ የሽብርተኝነት ጥቃት እንዲጨምር ያደርጋል›› ያሉ ሲሆን 31 ከመቶዎቹ ደግሞ የሊባኖስ ጦርነት አሜሪካ ያለባትን የሽብርተኝነት ችግር ያባብሳል ብለዋል። በመጨረሻም በኤ.ቢ.ሲ ኒውስና ዋሽንግተን ፖስት በጋራ የተደረገው ጥናት የሊባኖስ ጦርነት ‹‹በኢራቅ ውስጥ ያለው ሁኔታ ለዩናይትድ ስቴትስ የከፋ እንዲሆን ያደርጋል›› ብሏል።

ባጭሩ ለመናገር አሜሪካውያን ስለ እስራኤልና ስለ ሊባኖስ ጦርነት በሚያስቡትና መሪዎቻቸው በጦርነቱ ጊዜ ይናገሩትና ያደርጉት በነበረው ድርጊት መካከል ሰፊ የሆነ ልዩነት ታይቷል። ስለሆነም የብዙሃኑ አሜሪካውያን አመለካከት የቡሽ አስተዳደርና ኮንግረሱ በ2006ቱ ግጭት ወቅት የወሰኗቸውን አቋሞች የሚደግፍ ሆኖ አልተገኘም።

እውን እስራኤል የአሜሪካን ትዕዛዝ ትፈጽማለች?

አሜሪካ በሊባኖስ የተከተለችውን ፖሊሲ እንድትከተል ተጽዕኖ ያደረገባት ሎቢው ነው የሚለውን አመለካከት ለማጥፋት እየተሠራበት ያለ ሌላው ዘዴ ‹‹ከጦርነቱ ጀርባ ያለች ዋነኛ አንቀሳቃሽ ኃይል ዩናይትድ ስቴትስ ስትሆን፣ የእስራኤል ሚና የታዘዘችውን ከመፈጸም የዘለለ አይደለም።›› የሚለው ነው። በሌላ አገላለጽ እስራኤል ጦርነቱን ያከናወነችውን ለአሜሪካ ባላት ታማኝነት በመካከለኛው ምስራቅ የአሜሪካን ጥቅም ለማስከበር ስትል ብቻ ነው። ‹‹ሁለተኛው የሊባኖስ ጦርነት›› ይላል እስራኤላዊው ጋዜጣኛ ዩሪ አቭኒሪ፡- ‹‹በብዙዎች ዘንድ የውክልና ጦርነት እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል። ይህ ማለት ሂዝቡሏህ የኢራን ተላላኪ ሶለግ ውሻ ሲሆን እስራኤል ደግሞ ለአሜሪካ ያደረች የጥበቃ ውሻ ማለት ናት። ሂዝቡሏህ ገንዘብ፣ ሮኬትና ድጋፍ ከኢስላማዊቷ ሪፓብሊክ ያገኛል። እኛ ደግሞ ገንዘብ፤ ክላስተር ቦምብና ድጋፍ ከዩናይትድ ስቴትስ ይጎርፍልናል"።[132] የሂዝቡሏህ መሪ ሃሰን ነስረሏህ ይህን ጉዳይ አስመልክተው ለአንድ የኢራን ቴሌቬዥን በግልጽ እንደተናገሩት፡- ‹‹የጽዮናዊያኑ ሃገር ሊናቦስን እንድትወር ዩናይትድ ስቴትስ ትዕዛዝ ሰጥታለች። ስለሆነም እስራኤል በመካከለኛው ምሥራቅ የአሜሪካን ጥቅም ለማስጠበቅ ወረራውን ፈጽማለች" ብለዋል።[133]

ምንም እንኳን ብዙ የአሜሪካ ባልሥልጣናት ሂዝቡሏህን እንደጠላት የሚቁጥሩት ቢሆንና እስራኤል እንድትደመሰሰው ቢፈልጉም ቅሉ "እስራኤል ከሂዝቡሏህ ጋር ያለው ግጭት እንዲባባስ ያደረገችው የዋሽንግተንን ፍላጎት ለማስከበር ነው" የሚለውን አባባል አጠራጣሪ የሚያደርጉት አራት ጥሩ ምክንቶች አሉ። እንደተባለው እስራኤል የምትንቀሳቀሰው አሜሪካን ወክላ ቢሆን ኖሮ የቦምብ ድብደባዋ በደቡባዊ ሊባኖስ ብቻ ተወስኖ የሊባኖስን መንግሥት ለመጠበቅና ለማጠናከር ትልቅ ጥንቃቄ ታደርግ ነበር። ለምን ቢባል ፕሬዝዳንት ቡሽ ገና ጦርነቱ እንደተጀመረ ግለጽ ያደረጉት ጉዳይ ጠንካራ መሠረት እንዲኖረው የለፉለት የቤይሩት መንግስት አደጋ እንዲገጥመው የማይሹ መሆኑን ነበር። ጉዳዩ ጠቅለል ተደርጎ ሲገለጽ ጦርነቱ ሊጀመር አካባቢ የእስራኤሉ መከላከያ ኃይል ኢታማዦር ሹም፡- ‹‹የሊባኖስ የዘመን አቆጣጠር ለ20 ዓመታት ወደ

ኃላ እንዲመለስ እናደርገዋለን›› እንዳሉት እንዲሆን ዩናይትድ ስቴትስ ፈጽሞ አትፈልግም ነበር፡፡

የቡሽ አስተዳደር የጦርነቱን እቅድ ከነደፈ በኃላ እስራኤል እንድትፈጽመው አድርጓታል የሚለው አባባልም ቢሆን ያን ያክል ሚዛን የሚደፋ አይደለም፡፡ ቀደም ብለን እንደገለጽነው ሁለተኛውን የሊባኖስ ጦርነት ሂደት የሚመለከተው እቅድ ሐምሌ 12 ሂዝቡሏህ ከፈጸመው ግድያና ጠለፋ ቀደም ባሉት ወራት ተዘጋጅቶ ያለቀ ሲሆን እስራኤል አጋጣሚውን ጦርነቱን ለመጀመር እንደሰበብ ነበር ተጠቀመችበት፡፡ እርግጥ ነው እስራኤል እቅዱን አስመልክታ ለዩ.ኤስ.አሜሪካ ማብራሪያ ሰጥታት ሊሆን እንደሚችልና የእርሷንም ይሁንታ እንዳገኘች ጥርጥር የለውም። ሆኖም ግን እቅዷን እንድትፈጽም አረንጓዴ መብራት ማሳየትና እንደ ወኪል ደንበኛ ‹‹ይህን ሥሪ፣ ያንን ደግሞ አትሥሪ›› ብሎ መመሪያ መስጠት ለየቅል መሆናቸው ልብ ሊባል ግድ ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ "እስራኤል ሊባኖስን በቦምብ እንትደበድብ የቡሽ አስተዳደር ይገፋፋት የነበረው የጦር መሳሪያዎቹን ወደፊት በኢራን የኒኪሌዮር ተቋማት ላይ ለሚያደርገው ድብደባ ብቃታቸውን ለመፈተሽ ነው" የሚል ሃሳብ ሲሰነዘር ይሰማል፡፡ አንድ የዩ.ኤስ. አሜሪካ መንግሥት አማካሪ ለሰይሙር ãርሽ በሰጧቸው አስተያየት፡- ‹‹የኢራንን ተተኳሽ ሚሳዬሎች አድነን በቦምብ ለመምታት፣ እንዲሁም መሸዋለኪያ ዋሻዎችንና ምሽጎችን ከአየር ላይ በምናዘንበው አዳፍኔ ለማፈራረስ የሚያስችለንን ብቃት የምንፈትሸበት አጋጣሚ ሆኖ እያለ ለምን እንቃወማታለን?›› አሉ፡፡[134] የእስራኤልን እቅድ አለመቃወምና ሂዝቡሏህን እንድትደበድብ መገፋፋት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸው እንዳለ ሆኖ የአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎች በሊባኖስ የሚደረገውን ድብደባ ኢራንን ለመምታት እንደመለማመጃ አድርገው ይቆጥሩታል መባሉ ብዙም ስሜት የሚሰጥ ሃሳብ አይደለም፡፡ በእነዚህ ሁለት ተግባራት ውስጥ የሚኖረው መመሳሰል በጣም ትንሽ ነው፡፡ ሚሳዬሎችንና ሮኬቶችን ታጥቆ በሊባኖስ ገጠራማ ስፍራዎች የተደበቀን አነስተኛ የሽምቅ ተዋጊዎች ቡድን ማጥቃትና በኢራን የሚገኙ ቋሚ የኒኩሌር ተቋማትን ማውደም መሠረታዊ ልዩነት ያላቸው ተግባራት ናቸው፡፡ ዩ.ኤስ. አሜሪካ በኢራን ላይ የምትወስደው እርምጃ የተሳካ

እንዲሆን በሂዝቡሏህ ላይ የአየር ጥቃት ማድረግ ምን ዓይነት ትምህርት ሊገኝበት እንደሚችል ግልጽ አይደለም።

በተጨማሪም በ2003 የጸደይ ወራት ማለትም ሳዳም ሊወድቁ አካባቢ አሜሪካ ሂዝቡሏህን ታጠቃላት ዘንድ እስራኤል የጠየቀች መሆኗን የሚያሳይ መረጃ የሚገኝ ሲሆን በተገላቢጦሹ ሲሆን ግን አልታየም። በፎርዋርድ ጋዜጣ ዘገባ መሠረት፡- ‹‹እስራኤላውያኑ አማጺው የሺዓይት ቡድን ሂዝቡሏህ የመካከለኛውን ምሥራቅ መረጋጋት እንዲሁም በመላው ዓለም የሚገኙ የዩናይትድ ስቴትስ ተቋማትን ጸጥታ የሚያሰጋ መሆኑን በመጥቀስ የአሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎችን አስጠንቅቀዋል።››[135] ያም ሆነ ይህ የቡሽ አስተዳደር ሂዝቡሏህን ለመደብደብ መፈለጉን ወይም እስራኤል ራሷ ይህንን የቤት ሥራ እንድትፈጽመው ማበረታታቱን የሚያሳዩ ማስረጃዎች ቢያንስ ይፋዊ በሆነ ሁኔታ አይገኙም።

በመጨረሻም የእስራኤል ታሪክ በግልጽ የሚያሳየን እስራኤል ዩናይትድ ስቴትስን ጨምሮ ሌላን ሃገር ስትለማመጥ ወይም ተላላኪ ስትሆን ታይቶ የማይታወቅ መሆኑን ነው። እስራኤል ሁልጊዜም ቢሆን በሳል የሆነ የአመራር ብቃት ያላት ሆና በተለያዩ ዓለም አቀፋዊ መድረኮች የራሷን ጥቅም ለማስከበር ከነጻነት ጀምሮ ስትፋለም የኖረች ሃገር ናት። ከ1989-1996 ድረስ የሞሳድ የበላይ ኃላፊ የነበሩት ሻብታዒ ሻቢት ይህን ጉዳይ ሲያብራሩ ‹‹እኛ ለራሳችን የሚበጀንንና በላጭ የሆነውን ነገር ሁሉ ስንፈጽም ነው የኖርነው። ተግባራችን ከአሜሪካ ፍላጎት ጋር ተጣጥሞ ከተገኘም ይህ ሊሆን የቻለው በሁለት ወዳጅ ሃገራት መካከል በሚኖር የትብብርና የመግባባት መንፈስ የተከሰተ እንጅ ሌላ አይደለም›› ብለዋል። የሊባኖስን ጦርነት በተመለከተም እንዲህ ብለዋል፡-- ‹‹ሂዝቡሏህ እስከ አፍንጫው የታጠቀና እጅግ ዘመናዊ የሚባለውን የጎሪላ ቴክኖሎጂ የተካነ መሆኑን እናውቃለን። ሆኖም ግን የጊዜ ጉዳይ ሆኖ እንጂ ልንጋፈጠው የግድ ነው።››[136] ይህ አባባል የአንድ ኃይል ወኪል ከሆነ አካል የወጣ ስሞታ አይደለም። ወይም ደግሞ የቀድሞው የእስራኤል መከላከያ ሚኒስቴር ሞሼ ዳያን በአንድ ወቅት፡- ‹‹የአሜሪካ ወዳጆቻችን ገንዘብ፣ የጦር መሳሪያና ምክራቸውን ይለግሱናል። እኛም ገንዘቡንና መሳሪያውን እንወስዳለን። ምክራቸውን ግን ለእነርሱ እንተውላቸዋለን››[137] በማለት እንደተናገሩት በሁለቱ አገራት መካከል የጌታና የሎሌ ግንኙነት የለም።

ማጠቃለያ

ምን ይደረግ?

በዚህ መጽሐፍ ክፍል አንድ በስፋት እንዳየነው በስትራቴጂያዊም ሆነ ሞራላዊ ሁኔታ ዩ.ኤስ. አሜሪካ በአሁኑ ጊዜ ለእስራኤል የምታደረገውን ያልተገደበ እርዳታ ለመግለጽም ሆነ ምክንያታዊነቱን ለማሳመን አይቻልም፡፡ የዚህ ያልተለመደ ግንኙነት ዋነኛ ምክንያት ቀደም ብለን በሰነዘርነው ሃሳብ መሠረት የእስራኤል ሎቢ ነው፡፡ ልክ እንደሌሎቹ በራስ አነሳሽነት የተደራጁ ቡድኖች ሁሉ ሎቢውም በተለያዩ ሕጋዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፍ የዩ.ኤስ. አሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ለእስራኤል በሚመች አቅጣጫ እንዲሄድ ተጽዕኖ ያደርጋል፡፡ አንዳንድ የሎቢው ክፍሎችም እንዲሁ የእስራኤልን ድርጊት የሚነቅፍን ወይም የሚተችን ማንኛውም አካል ዝም ለማሰኘት ወይም ስሙን ለማጥፋት የማይገባ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ምንም እንኳን ሎቢው ሁልጊዜም የሚፈልገውን ሁሉ አግኝቷል ባይባልም ዋና ዋና የሚባሉ ግቦቹን ግን አሳክቷል ማለት ይቻላል፡፡

በክፍል ሁለት ላይ ደግሞ ሎቢው በዩ.ኤስ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖሊሲ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖና ይህ ተጽዕኖ ለዩናይትድ ስቴትስና ለእስራኤል ጭምር ጎጂ መሆኑን ለማሳየት ሞክረናል፡፡ ዋሺንግተን ለእስራኤል የምታደርገው እጅግ የተጋነነ ድጋፍ በአረቡና በሙስሊሙ ዓለም ጸረ-አሜሪካዊነት አቋም እንዲስፋፋ ከማድረጉም በላይ በሌሎች አገራትም እንዲሁ የአሜሪካን ገጽታ አበላሽቶታል፡፡ ሎቢው የዩ.ኤስ. አሜሪካ መሪዎች በእስራኤል ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩ በማድረግ የእስራኤል ፍልስጤማውያን ግጭት እልባት እንዳያገኝ ደንቃራ ሆኗል፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ የእስራኤልን የኒኩሊዬር መርሐ-ግብር አይታ እንዳላየች በመሆንና የሰብዓዊ መብት ረገጣዋን ችላ በማለት በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ሌሎች አገራትን ለመተቸት ስትሞክር መታየቷ መናፍቃዊ አካሄድ ያላት ሃገር መሆኗን ግልጽ

በማድረጉ በአረቡና በሙስሊሙ ዓለም የምታነቃቃውን የፖለቲካ ተሃድሶ አፈር ድሜ አስበልቶታል።

የሎቢው ተጽዕኖ በተጨማሪም ዩ.ኤስ አሜሪካን አውዳሚ ወደ ሆነው የኢራቅ ጦርነት አስገብቷታል። ከሶሪያና ከኢራን ጋርም እርቀ ሰላም አውርዳ መልካም ግንኙነት እንዳታበጅ አግዷታል። እንዲሁም እስራኤል በሊባኖስ ላይ ያደረገችውን በሚገባ ያልታቀደ ጦርነት ዩናይትድ ስቴትስ እንድትደግፍ አድርጎ በሂደቱም ሂዝቡላህ እንዲጠናከር፣ ሶሪያና ኢራን ደግሞ አንድ ላይ እንዲሆኑ በማድረግ የአሜሪካ ገጽታ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲወይብ ምክንያት ሆኗል።

ሎቢው የሚያሳድረው ተጽዕኖ ለእስራኤልም ቢሆን በተለይም ደግሞ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሚበጃት አልሆነም። ዩ.ኤስ. አሜሪካ ለእስራኤል የምትሰጣት መጠነ ሰፊ እርዳታ እስራኤል በሃይል የያዘቻቸውን ግዛቶች በቁጥጥሯ ስር እንዳደረገች ለመቆየት የሚያስችላትን ጥረት የሚያግዝ ትልቅ ድጎማ እንደሆነ የታወቀ ጉዳይ ነው። ዋሽንግተን እስራኤልን በማሳመን ይህን ውጤታማ ያልሆነ ፖሊሲ እንድትተው ለማድረግ እንዳትችል ሎቢው ተጽዕኖ ያሳድራል። ዋሽንግተን ይህን የተስፋፊነት አጀንዳ እንድትደግፍ ሎቢው ማሳመን መቻሉ እስራኤል ከሶሪያ ጋር የሰላም ስምምነት እንዳታደርግ፤ እንዲሁም የኦስሎን የሰላም ሃሳብ ተቀብላ በመተግበር የብዙ እስራኤላውያንን ሕይወት እንዳታተርፍ በማድረግ ጎድቷታል። ይህም ብቻ ሳይሆን እስራኤል የሰላሙን ሃሳብ በመከተል ጠላቶቿ እንዲከፋፈሉና በፍልስጤም ግዛት ውስጥ ያሉ አክራሪ አቋም ያላቸው ሃይሎችም ተቀባይነት እንዲያጡ ለማድረግ የሚያስችላትን ዕድል ነፍጓታል። ለፍልስጤማውያን ሕጋዊ መብቶች እውቅና እንዳትሰጥ እስራኤልን መገፋፋት ለእስራኤል ሰላም መልካም አይደለም። የፍልስጤማውያን መሪዎችን የመግደል፤ የማሰር ወይም የማግለል አሰራር ሃማስን የመሳሰሉ ጽንፈኛ ኃይሎች ወደ ስልጣን እንዲመጡና ለዘብተኛ አቋም ያላቸውና የመደራደሩን ሃሳብ የሚደግፉ የፍልስጤማውያን መሪዎች ወደ ዳር እንዲገፉ ከማድረግ ያለፈ የፈየደው ነገር የለም። ዩ.ኤስ. አሜሪካ ኢራቅን መውረሯን እስራኤልና ሎቢው በስፋት የደገፉትና ያበረታቱት

ቢሆንም ብዙ እስራኤላውያን የሚፈሯት ኢራን በተፈጠረው ሁኔታ ተጠቃሚ እንድትሆንና አይላ እንድትወጣ እድል ፈጥሮላታል፡፡ የዩ.ኤስ. ባለስልጣናት የሊባኖሱን ወረራ እንዲደግፉ ጫና በማሳረፍ አይፓክ፣ ክርስቲያን ዩናይትድ ፎር እስራኤል፣ የጸረ-ስም ማጥፋት ሊግ (ኤ.ዲ.ኤል) እና የፕሬዝዳንቶች ኮንፈረንስን የመሳሰሉት ዋና ዋና የአሜሪካ አይሁዳውያን ድርጅቶች እንጠብቃታለን የሚሏትን ሃገር ጥፋት ውስጥ ጨምረዋታል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ክስተቶች የሎቢው ድርጊት እስራኤልን የሚጎዳ እንደነበረ ግልጽ ነው፡፡

ስለዚህ ምን መደረግ ነው ያለበት? ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የዩ.ኤስ. አሜሪካ ፖሊሲዎች ያደረሱትን ጉዳት ለመቀልበስ አዲስ ስትራቴጂ ነድፎ መከተል የግድ ነው፡፡ ሆኖም ግን አዲስና የተለየ መንገድ መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ ማለት የሎቢውን አቅም የማዳከም ስልት እንደመሆኑ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላትን ይጠይቃል፡-

- ✓ በመካከለኛው ምሥራቅ የዩ.ኤስ አሜሪካን ጥቅሞች ለይቶ ማወቅ፣
- ✓ እነዚህን ጥቅሞች ለማስጠበቅ የሚያግዝ ስትራቴጂ መንደፍ፣
- ✓ ከእስራኤል ጋር አዲስ የሆነ ግንኙነት መመስረት፣
- ✓ የእስራኤል- ፍልስጤማውያንን ግጭት የሁለት መንግሥታትን የመፍትሄ ሃሳብ ተግባራዊ በማድረግ ማጠናቀቅ፣
- ✓ ሎቢውን ገንቢ ለሆነ ዓላማ የሚተጋ አካል ለማድረግ መጣር፡፡

የ.ዩ.ኤስ. አሜሪካ ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?

ከሁሉም በላይ ትልቅ ግምት የሚሰጠው የዩ.ኤስ. አሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የአሜሪካን ሕዝብ ደህንነትና ብልጽግና ማረጋገጥ ነው። ይህን ግብ ለማሳካት ዩናይትድ ስቴትስ ሁልጊዜም ቢሆን የምዕራባዊውን ንፍቀ ክበብ ደህንነት ማረጋገጥን ዋነኛው አስፈላጊ ጉዳይ አድርጋ ትቆጥረዋለች። ከቅርብ አሥርተ ዓመታት ወዲህ ደግሞ ፖሊሲ አውጪዎች በሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚገኙና ሊዋጉላቸውና ሊሞቱላቸው የሚገቡ ሶስት ዋና ዋና ስትራቴጂያዊ ክልሎች እንዳሉ ተገንዝበዋል። እነርሱም አውሮፓ፣ ሰሜን ምስራቅ ኢሲያና የፋርስ ባሕረሰላጤ ናቸው።[1] እነዚህ ክልሎች ጠቃሚ ናቸው። ምክንያቱም ጠንካራ ኃይል የተከማቸባቸው አለያም ደግሞ ወሳኝ የሆኑና በዓለም አቀፋዊው የኃይል ሚዛን ከባድ ስፍራ የሚያሰጡ የተፈጥሮ ሃብቶችን ይዘዋል።

ዩናይትድ ስቴትስ በመካከለኛው ምሥራቅ ሶስት ጉልህ ስትራቴጂያዊ ጥቅሞች አሏት። ያ ክልል በምድራችን ካለው የሃይል አቅርቦት ጠቀም ያለውን እጅ ስለሚሸፍን በዚያ ያለው ዋኛው ጥቅሟ የነዳጅ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ ወደ ዓለም አቀፍ ገበያ እንደልብ እንዲፈስ ማድረግ ነው። ይህ ዓላማዋ አጠቃላይ ክልሉን የመቆጣጠር ፍላጎትን አያካትትም። ዋናው ግቧ በዚያ ክልል የሚገኝ የትኛውም ሃገር ይህን የተፈጥሮ ሃብት ፍሰት የሚያቅብ አቅምና ጉልበት እንዳያዳብርና ያንንም ወደ ተግባር ቀይሮ ችግር እንዳያስከትል መቆጣጠር ነው።

ሁለተኛው ስትራቴጂያዊ ጥቅሟ የመካከለኛው ምሥራቅ አገራት የጅምላ ጨራሽ መሳሪያ ባለቤት እንዳይሆኑ መከላከል ነው። ምዕራፍ ሁለት ላይ እንዳብራራነው የዚህ ጉዳይ አደጋው በኒኩሌዩር የመጠፋፋት ችግር፤ በፖስታ በታሸገ ቦምብ የሚደርስ አደጋ ወይም የኒክሊየር ሐይልን ለአሸባሪዎች በማስታጠቅ የሚደርስ እልቂት አይደለም። አሜሪካ በእነዚህ ምክንያቶች አይደለም የኒኩሌር ሃይል በክልሉ እንዳይስፋፋ የምትሻው። ከዚያ ይልቅ ዋነኛው ምክንያቷ ኃይሏን እንደልቧ ለማስገባትም ሆነ

ለማንቀሳቀስና የክልሉ ነዳጅ እንደልብ እንዲፈስ የምታደርገውን ጥረት ሊያወሳስብባት ስለሚችል ነው፡፡ የጅምላ ጨራሽ መሳሪያ ዝውውር በተጨማሪም ድንገተኛ ወይም ያልተፈቀደ የሆነን የኒኩሊዬር አጠቃቀም አደጋ ከፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ አገራትን ሁኔታ እግምት ውስጥ ካስገባን በሃገራቱ ውስጥ ሊደረጉ በሚችሉ መፈንቅለ መንግስቶች ወይም አብዮቶች ምክንያት የኒክሊየር ሐይል ሐላፊነት በማይሰማቸው እጆች ላይ ሊወድቅ ይችላል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የተነሳ የጅምላ ጨራሽ መሳሪያዎች በክልሉ እንዳይሰራጩ ማድረግ የዩ.ኤስ አሜሪካ ዋነኛ ዓለማ ሆኗል፡፡

ሦስተኛ፡- ዩናይትድ ስቴትስ ጸረ- አሜሪካ የሆነ ሽብርተኝነትን የመቀነስ ግልጽ ፍላጎት አላት፡፡ ይህን ዓላማዋን ከግብ ለማድረስም ስጋት የሚፈጥሩ የሽብርተኞች የተወሳሰቡ ግንኙነቶችን መበጣጠስና አዳዲስ ቡድኖችም እንዳያቆጠቁጡ መከላከል ይኖርባታል፡፡ እንግዲህ እነዚህ ዓላማዎች የሚሳኩት ስፋትና ጥልቀት ባለው ሁኔታ በክልሉ ከሚገኙ ሃገራት ጋር መተባበር ሲቻል ነው፡፡ በተለይም ደግሞ ጸጥታን የሚመለከቱ መረጃዎችን በመለዋወጥና ሕግና ስርዓት የማስፈን እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ጭምር ነው፡፡ በተጨማሪም አል ቃዒዳን የመሰሉት ድርጅቶች የጅምላ ጨራሽ መሳሪያዎችን የሚያገኙበት እድል እንዳይኖር ዩናይትድ ስቴትስ አስፈላጊውን የመከላከል እርምጃ ትወስዳለች፡፡ የጅምላ ጨራሽ መሳሪያ የታጠቁ መንግስታት መሳሪያውን ጥቅም ላይ እንዳያውሉት ከማገድ ይልቅ መሳሪያውን በእጃቸው ያስገቡ ሽብርተኛ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ መቆጣጠር እጅግ ይከብዳል፡፡ ሽብርተኛ ድርጅቶች አንድ ጊዜ እንዲህ ዓይነቱን መሳሪያ በእጃቸው ካስገቡ በአሜሪካና በአጋሮቿ ላይ ከመጠቀም ወደ ኋላ አይሉም፡፡ የፖለቲካ ተሃድሶ እንዲደረግና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ እንዲስፋፋ ማድረግም ይህን ዓለማ ለማሳካት ያግዛል፡፡ ይህም በአካያው ቁልፍ ከሆኑ የክልሉ ሃይሎች ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖር ግድ ይላል፡፡ ምንም እንኳን ዩናይትድ ስቴትስ በክልሉ ፈጣን የሆነ ዲሞክራሲያዊ ሽግግር እንዲኖር የምትሻ ቢሆንም በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ዲሞክራሲን ለማስፋፋት ጠብመንጃን መጠቀምን ግን አትደግፍም፡፡

ምንም እንኳን አሜሪካ የእስራኤልን በህልውና መቆየት መደገፍ እንዳለባት ብናምንም የእስራኤል ጸጥታ ለዩናይትድ ስቴትስ ያን ያክል ወሳኝ የሆነ ስትራቴጂያዊ ጥቅም አለው ማለት ግን አይደለም።[2] እንበልና በእስራኤል ላይ ወረራ ቢፈጸም እንኳን (ይህ መቸም ፈጽሞ ሊሆን የማይችል ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ጠንካራ ወታደራዊ ሃይል ያላት በመሆኑና የኒኩሊዬር ባለቤትም ስለሆነች) የአሜሪካ ሉዓላዊነት፤ ወታደራዊ ኃይሏም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ብልጽግናዋ፣ እንዲሁም ፖለቲካዊ እሴቷ ከአደጋ ላይ አይወድቁም። በተቃራኒው ከፋርስ ባሕረ ሰላጤ አካባቢ የሚጓዝው ነዳጅ መጠኑ ቢቀንስ በአሜሪካ ደህንነት ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ እጅግ ታላቅ ነው። ይህም በመሆኑ ዩናይትድ ስቴትስ የእስራኤልን በህልውና መቆየት የምትደግፈው ደህንነቷን ይበልጥ አስተማማኝ ስለሚያደርገው ሳይሆን አሜሪካውያን ረኻቦሙን የአይሁዳውያን የስቃይ ታሪክ በመገንዘባቸውና የአይሁድ ሕዝብ የራሱ የሆነ መንግሥት ቢኖረው ተመራጭ መሆኑን በማመናቸው ነው። በተደጋጋሚ ልንገልጸው እንደሞከርነው የእስራኤልን በሕልውና መቀጠል ለመደገፍ ጠንካራ ሞራላዊ ምክንያት ይኖራል። እንዲሁም የእስራኤል ህልውና አደጋ ላይ ከወደቀ ዩናይትድ ስቴትስ ልታግዛት እንደሚገባ እናምናለን። ሆኖም ግን አሜሪካውያን ይህን የሚያደርጉት ከሞራል አንጻር ትክክለኛ ድርጊት በመሆኑ እንጂ ለራሳቸው ሕልውና የግድ አስፈላጊ በመሆኑ አይደለም ባዮች ነን።

የተለየ ስትራቴጂ- ‹‹ከጠረፍ ማዶ ያለ አረጋጊ ኃይል›› መሆን

ከመስከረም 11 ጀምሮ ዩ.ኤስ. አሜሪካ መካከለኛውን ምሥራቅ ወደ ዲሞክራሲ የማሸጋገር ፖሊሲ ስትከተል ቆይታለች፡፡ ይህን ተስፋ የሞላበት ስትራቴጂ ለመተግበር የቡሽ አስተዳደር በርካታ ቁጥር ያላቸው የአሜሪካ ወታደሮችን ወደዚያው መላክ ነበረበት፡፡ ይህ፣ ዩ.ኤስ. አሜሪካ በቀዝቃዛው ጦርነት ጊዜ እንኳን ያልፈጸመችው ድርጊት ችግሩ ይበልጥ ያቀጣጠለና በኢራቅ የደረሰውን ውድቀትም ያፋጠነ ነው፡፡ በተጨማሪም በአውሮፓውያንና በአረብ አገሮች ጨምሮ ዩናይትድ ስቴትስ በመላው ዓለም የነበራትን ገጽታ ያጠለሸ ነው፡፡

አሜሪካ መካከለኛውን ምሥራቅ ወደ ዲሞክራሲ አሸጋግራለሁ ማለቷን ትታ ከጠረፍ ማዶ ሆኖ የማረጋጋት ስትራቴጂን (offshore balancing strategy) ብትከተል የተሻለ በሆነ ነበር፡፡ ይህ ስትራቴጂ ብዙ ቦታን የማይሸፍንና ክልሉን ለማዳረስ ብዙ ተስፋ የማይሰጥ ቢሆንም በመካከለኛው ምሥራቅ የዩ. ኤስ. አሜሪካን ጥቅም ከማስከበር አንጻር ግን የበለጠ ውጤታማ ነው፡፡ በዚህ ስትራቴጂ ዩናይትድ ስቴትስ ቀጥተኛና ወሳኝ የሆኑ ጥቅሞቿ ከአደጋ ላይ በሚወድቁ ጊዜ ወታደራዊ ኃይሏን፣ በተለይም የምድር ጦሯሯን ወደ አደጋው አካባቢ ማስጠጋት የሚያስችላት ሲሆን ይህም የሚሆነው የአገሬው ሃይሎች ስጋቱን ራሳቸው ሊቆጣጠሩት የማይችሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡[3] ዋሽንግተን ከዚያ በመለስ በዚህ ስትራቴጂ አቀራረብ መሠረት በዲፕሎማሲው መስክ ብቻ ይበልጥ በማተኮር የአየርና የባሕር ሃይሏ በክልሉ ላይ ያላትን ጥቅም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ምልክቶችን ብቻ እያሳዩና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ለሚፈጠር ሥጋት ፈጥነው አጸፋ ለመስጠት ያላቸውን ዝግጁነት እየገለጹ ይቀመጣሉ፡፡ እነዚህ ሃይሎች አስፈላጊ ሁኔታ በሚከሰት ጊዜ ፈጣን የሆነ ጣልቃ የመግባት እድል ይኖራቸዋል፡፡

ከጠረፍ ማዶ ሆኖ የማረጋገት ስትራቴጂን መከተል የቆየና የተለመደ ስትራቴጂ ሲሆን ዩ.ኤስ. አሜሪካ በቀዝቃዛው ጦርነት ጊዜ መካከለኛውን ምሥራቅ ለማረጋጋት ትጠቀምበት የነበረ ቁልፍ ፖሊሲ ነው። ያኔ ዩናይትድ ስቴትስ ክልሉን የጦር ሰፈሯ ለማድረግ ያልሞከረች ከመሆኗም በላይ የክልሉን ሀገራት ወደ ዲሞክራሲያዊ ሂደት የማሸጋገር ጥረትም አላደረገችም። ከዚያ ይልቅ በክልሉ የሚገኙ የበርካታ ወዳጆች የኃይል ሚዛን ተጠብቆ እንዲቆይ ስትጥርና ይህ የኃይል ሚዛን የሚናጋ በመሰለባቸው ጊዜያት ደግሞ ጣልቃ ለመግባትና ለማረጋጋት የሚያስችላትን ኃይል በማደራጀት ዝግጁ ሆና ትጠባበቅ ነበር። በዚሁ ጥረቷ አካያ ዩናይትድ ስቴትስ በቀዝቃዛው ጦርነት በነዳጅ የበለጸገውን የፋርስ ባህረ ሰላጤ ሶቭየት እንዳትቆጣጠረው ለማገድ የሚያስችላት ፈጣን የጦር ኃይል አዘጋጅታም ነበር። እንዲሁም አብዮታዊ የሆነችው ኢራን በ1980ዎቹ ኢራቅን ክፉኛ ባስጋቻት ጊዜ ዋሽንግተን ወደ ኢራቅ አዘንብላ እርዳታዋን ሰጥታታለች። ሆኖም ግን በ1990 ኢራቅ ኩዌትን ስትወር የክልሉ የኃይል ሚዛን ወደ ሳዳም ማዘንበሉ ግልጽ ሆኖ በመምጣቱ ዩናይትድ ስቴትስ ከበርካታ አገራት የተውጣጣ የህብረ ብሔር ጦር አደራጅታ የሳድምን ጦር በመምታት ኩዌትን ነጻ ለማውጣት ችላለች።

ከጠረፍ ማዶ ሆኖ የማረጋገት ስትራቴጂ በሶስት ምክንያቶች የተነሳ ትክክለኛ ስትራቴጂ ነው ማለት ይቻላል። በመጀመሪያ ዩናይትድ ስቴትስ በየሥፍራው ዝም ብላ በጦር ኃይል ጣልቃ የምትገባበትን አሰራር የሚቀንስ ቢሆንም ጨርሶ ግን አያጠፋውም። ስለሆነም ኢራቅ ኩዌትን በወረረች ጊዜ እንደሆነው ሁሉ አስፈላጊ በሆኑ ቦታዋች ጣልቃ መግባትን አይከለክልም። ይህ ስትራቴጂ መካከለኛው ምሥራቅን እንደገና ለመበወዝና ቅርጽ ለማስያዝ ወታደራዊ ሃይል መጠቀምን ውድቅ የሚያደርግ ሲሆን ሌሎች አገሮች ቢያደርጉት እንደማትደሰተው ሁሉ ዩናይትድ ስቴትስ ራሷም ክልሉን የመቆጣጠር ፍላጎት እንዲኖራት አይጋብዝም። በዚህ አሰራር መሠረት ይህ ስትራቴጂ በክልሉ ያሉ አገራት እርስ በርስ ፍጥጫ ውስጥ ቢገቡ ዩ.ኤስ.አሜሪካ በመጀመሪያ ደረጃ የምታደርገው በዚያ የሚገኙ ወዳጆቿ ያንን አደገኛ የሆነ ጎረቤታቸውን ራሳቸው እንዲፋለሙት ማድረግ ነው።

ዩናይትድ ስቴትስ ከጠረፍ ማዶ ያለች አረጋጊ እንደመሆኗ ጣልቃ የምትገባው በመጨረሻው ሰዓትና አማራጮች ሁሉ ሲሟጠጡ ብቻ ይሆናል፡ ፡ ጣልቃ በምትገባ ጊዜም ሥራዋን በፍጥነት ካጠናቀቀች በኋላ ከአካባቢው ወጥታ ወደ ቀድሞ የጠረፍ ማዶ (offshore) አረጋጊነቷ ትመለሳለች ማለት ነው፡፡

ሁለተኛ፡- ከድንበር ባሻገር ሆና የማረጋጋቱን ሂደት እስከተከተለች ድረስ አሜሪካ በሽብርተኝነት አማካኝነት የሚደርስባት ችግር ይቀንስላታል፡፡ ከ19ኛው መቶ ክ/ዘመን ሁነት የምንወስደው ትምህርት ብሔራዊ ስሜት እና ሌሎች የማንነት መገለጫ ንቅናቄዎች በየአገራቱ ሃያል የሆኑ የፖለቲካ አንቀሳቃሽ ሞተሮች በሆኑ ጊዜ የውጭ ገዥዎች ከየአገራቱ ሕዝቦች የገጠማቸው ተጋድሎና እምቢ ባይነት ትልቅ ደረጃ ላይ ደርሶ የነበረ መሆኑን ነው፡፡[4] የዩ.ኤስ. አሜሪካን ወታደራዊ ኃይሎች ከየሃገራቱ በማራቅ ሲፈለጉ ብቻ የሚመጡና የማረጋጋቱን ሥራ የሚሰሩ የማድረጉ ስትራቴጂ በአረብ መሬት ላይ የዩናይትድ ስቴትስ ወታደሮች በቋሚነት መስፈራቸውን የሚቃወሙ ኃይሎችን ቅሬታ ይቀንሳል፡፡ ይህ ቅሬታ በተደጋጋሚ ሲሆን እንደታየው የሚገለጸው በሽብርተኝነትና ከዚያም ፈቀቅ ሲል በዩናይትድ ስቴትስ ኃይሎች ላይ ባነጣጠረና ሰፋ ያለ ይዘት ባለው የሰርጎ ገቦች ውጊያ ነው፡፡

ሶስተኛ፡- ክልሉን ወደ ዲሞክራሲ ከማሸጋገር ስትራቴጂ በተቃራኒ የጠረፍ ማዶ የማረጋጋት ስትራቴጂ (offshore balancing strategy) ኢራንንና ሶሪያን የመሳሰሉ አገራት የአሜሪካን ጦር ድብደባ የሚፈሩበት ምክንያት እንዳይኖራቸውና የጅምላ ጨራሽ መሳሪያ የመታጠቅ ጉጉት እንዳያድርባቸው ያደርጋል፡፡ የዩ.ኤስ. አሜሪካን ጣልቃ ገብነት ለመቋቋም መፈለጓ ነው ኢራንን በዋነኝነት የኒኩሊዬር ቃታ ለመጫበጥ እንድትተጋ ግፊት የፈጠረባት፡፡ ስለሆነም ኢራን ሉዓላዊነቷ ተከብሮና ማንም ወረራ ሳይፈጽምባት በሰላም የመኖር መብት እንዳላት እንድታምን ለማስቻል ያላሰለሰ ጥረት ቢደረግ ከኒኩሊዬር እነጻ ጥድፊያዋ ማላቀቅና ሰላማዊ የትብብር መንፈስ የምታሳይ ሃገር እንድትሆን ማድረግ ይቻላል። ዩናይትድ ስቴትስ ከመካከለኛው ምሥራቅ የፖለቲካ ሂደት ራሷን ሙሉ ለሙሉ

ታገላለች ማለት ፈጽሞ የማይቻል ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም ግን የጠረፍ ማዶ የማረጋጋት ስትራቴጂን መከተሏ በክልሉ ያሉ አገራት ለዩናይትድ ስቴትስ ያላቸው ፍራቻ አነስተኛ እንዲሆን፣ ከዚህም አልፎ በዚያ ክልል ከሚገኙ ጠላቶቻችን አንዳንዶቹ የእኛን እርዳታ እንዲፈልጉ የሚያደርግ ማበረታቻ ይሰጣቸዋል፡፡ በጠላትነት የሚያዩንን አገራት አንድ ላይ ጨፍልቆ ‹‹የሰይጣን ዛቢያዎች›› ብሎ መጥራት በእኛ አንጻር የተባበረ ክንዳቸውን እንዲያነሱ ከመገፋፋት በስተቀር የሚያመጣው አንዳች ፋይዳ የለም፡፡ ሆኖም ግን ከጠረፍ በመለስ የማረጋጋት ሥራ ጠላቶቻችንን የመከፋፈልና ወደ እኛ እንዲጠጉ የማድረግ እድል እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡ ዩ.ኤስ. አሜሪካ ለረዥም ጊዜ ስትከተለው የቆየችው መርህ ጥቅሟን የሚያስጠብቅላትና በተለይም በፋርስ ባሕረ ሰላጤ አካባቢ ጠበኛ ወይም ተጋፊ የሆነ መንግስት ወይም ቡድን ብቅ ብሎ ስጋት እንዳይደቅን የማድረግ ሂደት በመሆኑ ጥሩ ስትራቴጂያዊ ስሜት የሚሰጥ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ሁኔታው በተግባር ሲገለጽ የጠረፍ ባሻገር ማረጋጋት ስትራቴጂን መከተል አሜሪካ በክልሉ የምትከተላቸውን ፖሊሲዎቿን እንደገና እንድትከልስ ያደርጋታል፡፡ ኢራቅን የተለያዩ ብሔረሰቦችንና ሃይማኖቶችን ወደሚያሳትፍ ዲሞክራሲ የማሸጋገሩን ውጤት አልባ ጥረት አቋርጣ በተቻለ ፍጥነት ከኢራቅ መውጣትና ያንን አጉል ወረራ ማድረጓ በክልሉ ያመጣውን ውጤት መገምገም ይኖርባታል፡፡ ስለሆነም በሶሪያ የሚገኘውን የአሳድ አገዛዝ ለመገርሰስ ከመሞከር ይልቅ እስራኤል ለሰላም ስትል የጎላን ከፍታዎችን ለሶሪያ እንድትመልስ ግፊት ማሳረፍ አለባት፡፡ ይህን ማድረጓ ሶሪያውያንን ለእስራኤል እውቅና ሰጥተው በሰላም ከሚኖሩ የአረብ ሃገራት ተርታ የሚያሰልፍ ብቻ ሳይሆን በሊባኖስ ያለውን ሂዝቡሏህም ከሶሪያ ይነጥላል፡፡ በሶሪያና በኢራን መካከልም የሚለያያቸው ሽብልቅ እንዲገባ ያደርጋል፡፡ ከዚያም በላይ ኢራን ሂዝቡሏህን፣ ሃማስንና ኢስላሚክ ጂሃድን ለመርዳት ያላትን አቅም ያዳክማል፡፡ እንዲሁም አል-ቃዒዳንና ሌሎች አሸባሪ ድርጅቶችን አስመልክቶ ዩናይትድ ስቴትስ የከፈተችውን ዘመቻ እንድትደግፍ ያደርጋታል፡፡

በመጨረሻም ኢራንን በጦር ሃይል ማስፈራራቱ የጅምላ ጨራሽ መሳሪያ የመታጠቅ ጥረቷን ይበልጥ አፋፍማ እንድትገፋበት ስለሚያደርጋት አህመዲን ኤጃድም የህዝቡን ብሔራዊ ስሜት በማነሳሳት በዩናይትድ ስቴትስ ላይ ያለውን ቅሬታ ይበልጥ እንዲያበረታ የማድረግ እድላቸው ይሰፋል፡፡ ስለሆነም ዩናይትድ ስቴትስ የኢራንን የኒኩሌር ፍላጎት አስመልክታ በቀጥታ ድርድር መጀመር ያለባት ሲሆን ይህ እርምጃ ጠጣሩን መስመር የሚከተሉትን የኢራን መሪዎች እንዲገለሉ ያደርጋቸዋል። እርግጥ ነው ይህ ስትራቴጂ ዩናይትድ ስቴትስ በአሁኑ ጊዜ በክልሉ ያጋጠሟትን ችግሮች ሁሉ ያስወግዳል ማለት እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ግን አብዛኝዎቹ በሎቢው ውስጥ ያሉ ቡድኖች ከሚደግፉት ፖሊሲ ይልቅ ለአሜሪካም ሆነ ለእስራኤል የተሻለ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

-እስራኤልን እንደማንኛውም መንግሥት መመልከት-

አዲስ የግንኙነት ቀመር

እስራኤልን በተመለከተስ ምን ለማለት ይቻላል? አዲሱ ስትራቴጂ ዩ.ኤስ. አሜሪካ ከእስራኤል ጋር ያላትን ግኙነት በተመለከተስ ምን ይላል? በተለይም እስራኤል ለአሜሪካ ያላት ስትራቴጂያዊ ዋጋ አነስተኛ እስከሆነ ድረስ ሁኔታው እንዴት ይታያል?

አይሁዳዊቷ ሃገር ከተመሠረተች እነሆ ስልሳ ዓመታትን አስቆጥራለች። ከሞላ ጎደል በዓለም ላይ ያሉ አብዛኞቹ ሃገራት እውቅና ሰጥታዋታል ማለትም ይቻላል። ኢኮኖሚዋ በፍጥነት እያደገ በመሆኑ ምንም እንኳን የምትከተለው የፖለቲካ ሥርዓት በውስጥ መከፋፈልና በሙስና እንዲሁም በተደጋጋሚ በሚፈጠሩ ስም ማጥፋቶች ሽባ የሆነ ቢመስልም አብዛኛዎቹ ዜጎቿ ባለጸጋዎች እየሆኑ ይገኛሉ። እናም ዩናይትድ ስቴትስ እስራኤልን እንደተለየ ወዳጅ አድርጋ መያዟን ትታ የተለመደ ግንኙነት መመሥረት ያለባት ጊዜው አሁን ነው። ከእስራኤል ጋር የምታደርገው ትብብርም ከሌሎች ወዳጅ ሐገራት ጋር ከምታደርገው ትብብር የተለየ መሆን የለበትም። በሌላ አገላለጽ ዩናይትድ ስቴትስ የእስራኤልን በሕልውና መኖር የምትደግፈው የፈረንሳይን፣ የታይላንድን ወይም ደግሞ የሜክሲኮን በህልውና መኖር የምትደግፈውን ያህል ብቻ መሆን አለበት። ማለትም ዋሽንግተን ከእንግዲህ በእስራኤል ጉዳይ ጣልቃ መግባት ያለባት ሕልውናዋ ከአደጋ ላይ ሲወድቅ ብቻ ሊሆን ይገባል።

እስራኤልን እንደማንኛውም ሃገር መመልከት ማለት የእስራኤልና የአሜሪካ ጥቅሞችና ፍላጎቶች አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ ናቸው የሚለውን የማስመሰያ አፈታሪክ ከእንግዲህ አለመከተል፣ እንዲሁም እስራኤል የፈለገችውን ነገር ብትፈጽምም የአሜሪካን እርዳታ በቋሚነት የምታገኝበትን አሰራር መቀየር ማለት ነው። ከዚያ ይልቅ እስራኤል የአሜሪካን ፍላጎት የምትጠብቅ ሆና ስትገኝ አሜሪካ ከርሷ ጋር ልትተባበርና ልትደግፋት ይገባል። የእርሷን ጥቅም ተቃርና በተገኘች ጊዜ ደግሞ አሜሪካ በሌሎች

አገሮች ላይ እንደምታደርገው እርሷንም ትቃወማታለች ማለት ይሆናል፡፡ በተጨማሪም እስራኤል በእርሷ ላይ ያላትን የኢኮኖሚና ወታደራዊ እርዳታ ጥገኝነት ለማስወገድ አሁን የምትሰጣትን እርዳታ ቀስ በቀስ መቀነስና ከነጨራሹ ማቆም ይኖርባታል፡፡ እስራኤል አሁን በጣም የተራመደ ኢኮኖሚ ያላት ሃገር ስትሆን ከጎረቤቶቿ ጋር ሙሉ የሰላም ግንኙነት ስትመሰርትና ከፍልስጤማውያን ጋርም የመጨረሻውን ስምምነት ስታደርግ ኢኮኖሚዋ የበለጠ እንደሚያድግ ይታመናል፡፡

ዩናይትድ ስቴትስ ከእስራኤል ጋር የምታደርገውን የንግድ ግንኙነት የምትቀጥል ሲሆን የአሜሪካና የእስራኤል ኢንቨስተሮችም በሁለቱም ሃገራት የተለያዩ ኢንተርፕራይዞችን በገንዘብ መደጎማቸውን ይገፉበታል፡፡ በባህል፣ በትምሕርትና በሳይንሳዊ ምርምር ዘርፎች የሚያደርጉት ትብብርም አሁን እያደረጉት እንዳለው ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በእስራኤላውያንና በአሜሪካውያን መካከል ያለው የተለየና ቤተሰባዊ ግንኙነትም እንዳለ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ የዩ.ኤስ. አሜሪካ የጦር መሳሪያ አምራቾች (በክልሉ ለሚገኙና አስፈላጊውን የዩ.ኤስ፣ ሕግ ለሚያከብሩ ሌሎች መንግሥታት እንደሚያደርጉት ሁሉ) ለእስራኤልም መሳሪያ ይሸጡላታል፡፡ እንዲሁም ዋሽንግተንና ቴሌአቪቭ ያለምንም ጥርጥር የደህንነትና ሌሎች የጋራ ወታደራዊ ጥቅሞች ያሏቸው መረጃዎችን በመለዋወጥ ይተባበራሉ፡፡ ሆኖም ግን የአሜሪካ ግብር ከፋዮች የሚያዋጡት ገንዘብ ከ1970ዎቹ ጀምሮ ለእስራኤል በእርዳታ መልክ በገፍ መሰጠቱ ከእንግዲህ የሚቀጥልበት በቂ ምክንያት አይኖርም፡፡ በተለይም ይህን እርዳታ ማግኘት የሚገባቸውና የሚያስፈልጋቸው ብዙ አገሮች ባሉበት በአሁኑ ጊዜ ለእስራኤል የሚደረገው እርዳታ ብሔራዊ ጥቅሟን ለማያስከብሩ እንቅስቃሴዎች መደጎሚያ የሚውል ሆኖ እስከቀጠለ ድረስ ሁኔታውን የበለጠ አሳሳቢ ያደርገዋል፡፡ ምንም እንኳ ፍልስጤማውያን የራሳቸውን መንግስት እንዲመሰርቱ የሚደረገውን ጥረት እስራኤል እንድትደግፍ ለማሳመን ዩናይትድ ስቴትስ የተወሰኑ ተጨማሪ ድጋፎችን ማድረግ ቢኖርባትም እስራኤልን እንደማንኛውም ሃገር መመልከት አሁን ለእርሷ በገፍ የሚሰጠውን የዩ.ኤስ. አሜሪካ እርዳታ ትርጉም ባለው መልክ ወደ መቀነስ መምራት ይኖርበታል፡፡

የእስራኤል- ፍልስጤማውያንን ግጭት ማብቃት

ከሁሉም በላይ ዩናይትድ ስቴትስ የእስራኤል ፍልስጤማውያን ግጭት ያበቃ ዘንድ ማንኛውንም የተዕዕኖ ኃይሏን መጠቀም ይኖርባታል፡፡ የኢራቅ የጋራ ጥናት ቡድን በ2006 እንደገለጸው፡- ‹‹ዩናይትድ ስቴትስ የአረብ-እስራኤልን ግጭት በተመለከተ አጠቃላይ የሆነ ሠላም እንዲፈጠር እንዲሁም በሁሉም ግንባሮች ማለትም በሊባኖስና ሶሪያ መረጋጋት እንዲኖር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል...፡፡ ፕሬዝዳንት ቡሽ በ2002 የነደፉትን የሁለት መንግሥታት የመፍትሄ ሃሳብ ተግባራዊ ለማድረግም ዝግጁ መሆን አለባት፡፡ በተጨማሪም አጋሯ የሆነችው እስራኤል የአረብ-እስራኤልን ግጭት በተናጠል ለመፍታት የምትወስደውን እርምጃ መደገፍ አይኖርባትም››፡፡[5]

እንደሚታወቀው የዩ.ኤስ. አሜሪካ መሪዎች በማንኛውም የአካባቢው የሰላም ሂደት ላይ ምንም እንኳን የሰላሙን ሃሳብ ወደፊት ለማራመድ ሙሉ ሐይላቸውን ባይጠቀሙም ይሳተፋሉ፡፡ ዩ.ኤስ. በተጨማሪም እስራኤል በ1967 ወደነበረችበት ድንበር እስከተመለሰች ድረስ በዚያ ክልል ውስጥ ለጸጥታዋ አስተማማኝ ዋስትና ከመስጠት ጋር ‹‹የጸጥታ አጥር›› የሚሰኘውን አዲስ የመሬት ዝርፊያ ስልት ጨምሮ የእስራኤልን የተስፋፊነት ፖሊሲ ውድቅ ማድረጓን በግልፅ ማሳወቅ ይጠበቅባታል፡፡ ምክንያቱም ይህ ፖሊሲ ሲገመገም የአሜሪካንም ሆነ የእስራኤልን የረዥም ጊዜ ጥቅምና ፍላጎት የሚያስጠብቅ አይደለም፡፡

ይህ ማለት የቡሽ አስተዳደር ጀምሮት የነበረውንና (የፍልስጤምን መንግሥት ለመመስረት የጊዜ ሰሌዳ ያስቀመጠውን) ሮድ ማፕን መተውና አሜሪካ ቀደም ሲል ያወጣቸውንና ሰላም ያስገኛል ብላ ያሰበችውን እቅድ ማራመድ ማለት ነው፡፡ በተለይም ደግሞ ዩናይትድ ስቴትስ ግልጽ ማድረግ ያለባት ጉዳይ ይህ ሂደት እስራኤል ከሞላ ጎደል በ1967 ሰኔ ወር ላይ ከያዘቻቸው የፍልስጤም ግዛቶች እንድትወጣና በምትኩ ሙሉ ሰላም እንድታገኝ የሚያደርጋት ሂደት መሆኑን ነው፡፡ እስራኤልና

ፍልስጤማውያን በተጨማሪም በ1948 የእስራኤልን መመሥረት ተከትሎ አገራቸውን ለቅቀው የተሰደዱ ፍልስጤማውያን ወደቀያቸው በሚመለሱበት ሂደት ከስምምነት ላይ መድረስ ይኖርባቸዋል። ምናልባትም ይህን መብት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ማድረግ የእስራኤልን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥልና የማይሳካ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ግን መሠረታዊው የዚህ ደንብ መፈጸም ወሳኝ የሆነ የፍትሃዊነት መገለጫ እንደመሆኑ ፍልስጤማውያንም የመጨረሻውን ስምምነት ለማድረግ የዚህን መብት መሟላት እንደ መስፈርት የሚመለከቱት መሆኑ ግንዛቤ ሊያገኝ ግድ ነው። ይህንን አጣብቂኝ ጉዳይ እልባት ለመስጠት እስራኤል የፍልስጤማውያንን ወደ ምድራቸው የመመለስ መብት መቀበል ይኖርበታል። ይህም ማለት ሕልውናዋ የተመሠረተው የፍልስጤማውያንን መብት በመጣስ መሆኑን መቀበል ማለት ነው። እስራኤል ለዚህ መብት እውቅና ትሰጣለች፣ ፍልስጤማውያንም በበኩላቸው ይህን መብታቸውን ለዘለቄታው ለመተው ተገቢ የሆነ ማካካሻ ሊሰጣቸው ግድ ይላል። ዩናይትድ ስቴትስም ሆነች የአውሮፓ ሕብረት ለፍልስጤማውያኑ ማካካሻ ለመስጠት ሰፊ የሆነ የችሮታና የመልሶ ማቋቋም መርሃግብርን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ምናልባት እንደዚያ ካደረጉ አሁን የእስራኤል ግዛት ወደሆነው የፍልስጤማውያኑ ምድር እስከ ሁልጊዜውም የማይመለሱት ፍልስጤማውያን በቂ የሆነ ማካካሻ በመቀበል የመመለስ ጥያቄያቸውን ከናካቴው መተዋቸውን በይፋ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

አንዳንድ ጊዜ ‹‹እስራኤል እንዲህ ዓይነት ስምምነቶችን ማድረግ አትችልም። ምክንያቱም ትንሽ በመሆኗና ልትጎዳ የምትችልበት አጋጣሚ ስለሚኖር። ፍልስጤማውያን የራሳቸውን መንግሥት እንዲመሠርቱ ካደረገች የበለጠ ትንሽና ደካማ ትሆናለች›› የሚል አባባል ይሰማል። ሆኖም ግን ይህ የተለመደ የመከራከሪያ ሃሳብ እስራኤል ከተመሰረተች በኋላ ከነበሩት ቀደምት አመታት የበለጠ አሁን ምን ያክል ስትራቴጂያዊ ጥንካሬ እንዳገኘች ያጤነ ምልከታ አይደለም። (ከተመሠረተች ብዙም ሳትቆይና የዩናይትድ ስቴትስን እርዳታ እንደልብ ማግኘት ሳትጀምር በርካታ ጠላቶቿን ማሸነፍ ችላ የነበረ መሆኑ እግምት ውስጥ ይገባል)። እስራኤል በ1967 ሰኔ ወር

ላይ ምዕራባዊውን ዳርቻና የጋዛ ሰርጥን ከተቆጣጠረችበት ጊዜ ይልቅ አሁን የተሻለና አስተማማኝ ጸጥታ አላት፡፡ በዚያ ጊዜ እስራኤል የነበራት የመከላከያ በጀት ግብጽ፣ ዮርዳኖስ፣ ኢራቅና ሶሪያ በጋራ ከነበራቸው በጀት ከግማሽ አነስ ያለ ነበር፡፡ ዛሬ እስራኤል ከግብጽና ዮርዳኖስ ጋር የሰላም ሥምምነት ተፈራርማለች፡፡ ኢራቅ ደግሞ በዩናይትድ ስቴትስ የተወረረች በመሆኑ ያን ያክል የስጋት ምንጭ አይደለችም ማለት ይቻላል፡፡ እስራኤል አሁን ያላት ወታደራዊ በጀት ሶሪያና ኢራን በጋራ ካላቸው በጀት ይበልጣል፡፡ ቀደም ሲል በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት የእስራኤል ጠላቶች ከሶቪዬት ሕብረት ጠቀም ያለ ወታደራዊ እርዳታ ያገኙ ነበር፡፡ ዛሬ ያ ልዕለ ሃያል ሃገር በመፈራረሱ ምክንያትና በአንጻሩ እስራኤል ከሌላዋ ልዕለ ሃያል ሃገር ዩ.ኤስ. አሜሪካ ጋር ያላት ትስስር እንዳለ በመሆኑ የምታገኘው የዕርዳታ መጠንም የዚያኑ ያክል ላቅ ያለ ነው፡፡ በ1967 እስራኤል ምንም ዓይነት የኒኩሊዬር መሣሪያ አልነበራትም፡፡ ዛሬ ግን ምናልባትም ሁለት መቶ የሚሆን የኒኩሌር አረር አምርታ ታጥቃለች፡፡ በአጭሩ ከ1967 በፊት በነበረው ክልሏ ውስጥ እስራኤል የበለጠ ደህንነቷ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ወደፊትም እንደዚያ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ በእርግጥ በኃይል በያዘቻቸው ግዛቶች (የጎላን ከፍታዎችን ጨምሮ) ከባድ የጸጥታ ችግሮች እያጋጠሟት መሆኑ እውነት ነው፡፡ ይህ የጸጥታ ችግር በይበልጥም የሚገለጸው በሽብርተኝነት ድርጊት ነው፡፡ ይሁንና በአሜሪካ ውስጥ ያሉ የእስራኤል ደጋፊዎች አሜሪካ የእስራኤልን ወረራ መደገፏን እንድትቀጥል ማድረጋቸው ለዚህ ችግር መፍትሄ አይሆንም፡፡

አንዳንድ እስራኤላውያንና አሜሪካውያን ‹‹እስራኤል ከ1967 ይልቅ ዛሬ ጸጥታዋ አስተማማኝ አይደለም›› ሲሉ ይከራከራሉ፡፡ ‹‹በተለይም ደግሞ ሃማስንና ሂዝቡሏህን የመሳሰሉት ቡድኖች እስራኤልን ለማጥፋት ጠንክረው በመስራት ላይ ሲሆኑ የሚደገፉትም በሶሪያና በኢራን ነው፡፡›› ይላሉ፡፡ ለዚህ አመለካከት አጸፋ የሚሆኑ ሁለት ዓይነት መልሶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ይህ አመለካከት ሽብርተኝነት የእስራኤልን ሕልውና እጅግ አሳሳቢ ከሆነ ሁኔታ ላይ እንደጣለው የሚያስመስል የተጋነነ ፍርሃትን ነው የሚያንጸባርቀው፡፡ የኢራንን ጅምላ ጨራሽ መሳሪያ ለእስራኤል ሕልውና

አስጊ አድርጎ ማቅረብ ምን ያህል የተሳሳተ አመለካከት እንደሆነ በምእራፍ 2 እና 10 ተወያይተናል። ሽብርተኞችን ለእስራኤል ስጋት አድርጎ ማቅረብም ከዚህ ያላነሰ ከንቱ ስጋት ነው። ሁለተኛውና የበለጠ ጠቃሚው ነጥብ እስራኤል በኃይል በያዘቻቸው ግዛቶች ያደረገችውን ወረራ ብታበቃ ተቃዋሚዎቿ የመሰረቱትን አንድነት በመናድና እርስ በርሳቸው እንዲከፋፈሉና በእርሷ ላይ መዓት እንደሚመጣባት የሚነገረውን አስተያየት ሁሉ ፉርሽ ማድረግ ትችላለች። ሶሪያ የጎላን ከፍታዎችን የምታገኝ ከሆነ ከእስራኤል ጋር ሰላም ለማውረድና ለሂዝቡላህና ለሃማስ የምትሰጠውን እርዳታ ለማቆም ቃል ገብታለች። እስራኤል ወረራዋን ማብቃቷና የፍልስጤም መንግሥት እንዲመሠረት መርዳቷ በፍልስጤም ምድር ከኢራን ጎን የሚቆሙትን ሃማስንና ኢስላሚክ ጅሃድን የመሳሰሉ ደጋፊዎቿን ኢራን እንድታጣ ያደርጋታል። እነዚያ ቡድኖች ከዚያ በኋላ የጦረኝነት መንገዳቸውን ቢቀጥሉ ከፍልስጤም እድገትና ብልጽግና በተቃራኒ የቆሙ ጠላቶች እንደሆኑ ተቆጥረው ሕዝቡ ይተፋቸዋል።

እስራኤል ስምምነቱን እንድትፈርም ዩናይትድ ስቴትስ ግፊት ለማድረግ በቂ ምክንያት አላት። ለምን ቢባል እስራኤልን በገንዘብ የምትደግፉት እርሷ እንደመሆኗ ያንን በማድረግ የራሷን ጸጥታ ከአደጋ ላይ ትጥላለች ተብሎ አይጠበቅም። በመሆኑም መደገፍ ያለባትን በግልጽ ለመደገፍና መቃወም የሚኖርባትንም እንደዚያው ለመቃወም ተገቢ ሃገር ያደርጋታል። የክሊንተን እሴቶች (Clinton parameters) የሚባሉትንና ታህሳስ 2000 ላይ የተነደፉትን መሰረታዊ የሰላም ሃሳብ መንደርደሪያዎች እርሳቸውን የተኳቸው ፕሬዝዳንት ቡሽ ‹‹መነሻ ነጥቦቻችን ናቸው›› በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተውባቸዋል። ከመጨረሻው የሥምምነት መቋጫ ላይ የሚደረስ ከሆነ ዩናይትድ ስቴትስና የአውሮፓ ሕብረት ይህን የስምምነት ሂደት በገንዘብ በመደገፍ የእስራኤልና የፍልስጤም መሪዎች በሁለቱም በኩል ከሚገኙ የስምምነቱ ተቃዋሚዎች ጋር የሚያደርጉትን ፍትጊያ ያግዛሉ።

የእስራኤል-ፍልስጤማውያንን ግጭት መፍታት በሌላ መንገድ የአሜሪካን ብሄራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የራሱ የሆነ በጎ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ምንም

እንኳን እስራኤል ወታደራዊ ብቃት ያላትና መልካሳ ምድራዊ አቀማመጧ ጠቃሚ ቢሆንም ለዩናይትድ ስቴትስ ያላት ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ በራሷ በእስራኤል ባሕሪ ምክንያት (ከአካባቢው አገራት የተገለለች በመሆኗ) ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ሄዷል። ፍልስጤማውያን መንግሥት እንዳይኖራቸው እስከተደረጉ ድረስ የእስራኤልም በክልሉ ተገልሎ መቆየት የግድ ስለሚቀጥል ዩናይትድ ስቴትስ የአካባቢውን ሐገሮች በማስተባበር አንዳች ግንባር መፍጠር በምትሻ ጊዜ በዚያ ስብስብ ውስጥ እስራኤል እንዳትካተት ያደርጋታል። ውዝግቡ መፍትሄ አግኝቶ በእስራኤልና በአረቡ ዓለም መካከል መደበኛ ግንኙነት በመመስረት ቢዳብር (ይህም አሁን በአረብ ሊግ የሰላም ሃሳብ እንደቀረበው ማለት ነው) ዩናይትድ ስቴትስ ከዚያ በኋላ እስራኤልን ለመደገፍ የምትከፍለው ዲፕሎማሲያዊ ዋጋ አይኖርም ማለት ይሆናል። እንዲሁም በክልሉ አንዳች ዓይነት ከባድ የሆነ አደጋ በተከሰተ ጊዜ ዩናይትድ ስቴትስና አረብ አጋሮቿ በሚፈጥሩት ጉድኝት ውስጥ እስራኤል እንደልቧ ልትሳተፍ ትችላለች። ስለሆነም ይህ ውዝግብ ቢወገድ እስራኤል በእውነትም በደጋፊዎቿ እንደሚነገርላት በክልሉ ውስጥ ሁነኛ የዩ.ኤስ. አሜሪካ ስትራቴጂያዊ ተጓዳኝ ሆና ብቅ ልትል ትችላለች።

ፍልስጤማውያን የራሳቸውን መንግሥት እንዲመሰርቱ ለማድረግ እስራኤል ፍቃደኛ ሆና ካልተገኘች ወይም ፍትሃዊ ያልሆነና የራሷን የተናጠል ፍላጎት ተከትሎ የሚደረግ እርምጃ ከወሰደች ዩናይትድ ስቴትስ ኢኮኒሚያዊና ወታደራዊ እርዳታዋን ልትቀንስ ወይም ልታግድባት ይገባል። ይህን የምታደርግበት ምክንያት ለእስራኤል የጥላቻ ስሜት ስላደረባት ሳይሆን ወረራው ለዩናይትድ ስቴትስ መጥፎ በመሆኑና ከአሜሪካ ፖለቲካዊ እሴቶች ጋር የሚጻረር ድርጊት ስለሆነም ጭምር ነው። ዩናይትድ ስቴትስ የጠረፍ ማዶ አረጋጊ ሃይል ሆና መቀጠል እስካለባት ድረስ ድርጊቶቿ መሠረት የሚያደርጉት የራሷን ፍላጎትና ጥቅም በማስቀደም እንጂ ተገቢውን ትብብር ለማታሳያት ሐገር በምታደርገው ጭፍን ድጋፍ መሆን የለበትም። ዩናይትድ ስቴትስ ለእስራኤል ግልጽ ምርጫዎችን ልታቀርብላት ግድ ነው። ምርጫዎቹ እስራኤል የምዕራባዊ ዳርቻና የጋዛ ሰርጥ ወረራዋን አብቅታ

መራቱን ለፍልስጤማውያኑ በመመለስ የዩ.ኤስ. አሜሪካ ወዳጅ መሆኗን ማሳየት ወይም በራሷ ውሳኔ እየተመራች ቅኝ ገዢ ሆና መቀጠል ናቸው።

ይህ እርምጃ እንደሚታሰበው ያን ያክል ስር ነቀል አይደለም። ዩናይትድ ስቴትስ ከዚህ በፊት ከቅኝ ገዢ ሃይሎች ጋር ታደርገው እንደነበረው ሁሉ ከእስራኤልም ጋር መነጋገር ብቻ ነው የሚጠበቅባት። ለምሳሌ ዩናይትድ ስቴትስ በቀዝቃዛው ጦርነት መጀመሪያ አካባቢ ብሪታኒያና ፈረንሳይ ቅኝ ግዛቶቻቸውን ሁሉ እንዲተውና ለአገራቱ ነጻነታቸውን እንዲሰጧቸው ግፊት ታደርግ ነበር። እስራኤልንም ቢሆን ከ1956ቱ የስዊዝ ጦርነት በኋላ የግብጽን ድንበር ለቅቃ እንድትወጣ ተጽዕኖዋን አሳርፋባታለች። ዩናይትድ ስቴትስ የራሷን ጥቅም የሚነካ ሆኖ እስካገኘችው ድረስ ጃፓንን፣ ጀርመንንና ደቡብ ኮሪያን ጨምሮ ከበርካታ ወዳጆቿ ጋርም ጭምር ተመሳሳይ ድርድር በማድረግ ከስምምነት ላይ ደርሳለች። ምዕራፍ 7 ላይ እንዳብራራነው የህዝብ አስተያየት ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት የአሜሪካ ሕዝብ የአገሩን ብሔራዊ ጥቅምና ዘላቂ መረጋጋት የሚያመጣ እስከሆነ ድረስ ፕሬዝዳንቱ በእስራኤል ላይ ጠጣሩን መስመር ቢከተሉ ሙሉ ድጋፍ ይቸራቸዋል።

ይህ ዓይነቱ ፖሊሲ ያለምንም ጥርጥር በሁሉም ባይሆንም ታላላቅ በሚባሉት የሎቢው አባል ድርጅቶች ዘንድ ውግዛትን ማስከተሉ አይቀርም። እንዲሁም በጥቂት አሜሪካውያን ዘንድም ቁጣን መቀስቀሱ አይቀር ይሆናል። ከዚህም በላይ አሁን የሚታዩ ሁኔታዎች ለሰላሙ ጥረት ብዙም የሚጋብዙ አይደሉም። እነርሱም በፍልስጤማውያን አንጃዎች መካከል የተከሰተው መሰነጣጠቅ፤ በጊዜው ያሉት የእስራኤል መሪዎች ፖለቲካዊ ደካማነት፤ የቡሽ አስተዳደር በክልሉ ያለው አስቀያሚ ታሪክ፤ በእሰራኤል በራሷ ውስጥ የሁለት መንግስታት የመፍትሄ ሃሳብ ተቀባይነቱ እየተሸረሸረ መምጣቱ ዋናዋናዎቹ ናቸው። ሌላው ይቅርና የሁለት መንግስት ምሥረታ ሃሳብ ጥቂት ጽኑ ደጋፊዎች "የሁለት መንግስታት የመፍትሄ ሐሳብ በእስራኤልና በፍልስጥኤማውያን የሁለትዮሽ ድርድር እልባት ሊያገኝ ይችላል የመባሉ ነገር ያለቀለትና የሞተ ሐሳብ ነው›› የሚል ሙሾ እያወረዱ ይገኛሉ።[6]

ይሁን እንጂ ከእንግዲህ ያለው ምርጫ ምንድን ነው? ጠጣሩን መስመር ተከታይ የእስራኤል ደጋፊዎች ምን የተሻለ አማራጭ አላቸው? የሚሉት ጥያቄዎች በአግባቡ መልስ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

አሁን ያሉትን ተጨባጭ እውነታዎች ካገናዘብን ከላይ የቀረበውን የሁለት መንግሥታት እቅድ አስመልክቶ ሶስት ምርጫዎች ሊኖሩ ይችላሉ። የመጀመሪያው አማራጭ እስራኤል ፍልስጤማውያንን ከ1967 በፊት ከነበሩበት ምድርና አሁን በቁጥጥሯ ሥር ከሚገኙት መሬቶች ጭምር በማስወጣት የዘር ማጽዳት ካደረገች በኋላ አንጡራውን የአይሁድ ማሕበረሰብ ብቻ ማስፈር ነው። ይህ ሃሳብ የአሁኑን የእስራኤል ምክትል ጠቅላይ ሚኒስተርና ውጭ ጉዳይ ሚኒስተር አቪግዶር ሊበርማንን የመሰሉ የጠጣር መስመር ተከታይ ደጋፊዎች የሚያራምዱት ሲሆን ይህን ዓላማ ዳር ለማድረስ መሞከር በሰው ዘር ላይ የሚፈጸም ወንጀል በመሆኑ ማንም ሀቀኛ የሆነ የእስራኤል ወዳጅ እንዲህ ዓይነቱን አሰቃቂ ድርጊት አይደግፍም። የሁለት መንግስታት ምሥረታን ሀሳብ የሚቃወሙ ወገኖች የሚያራምዱት አጀንዳ ይህ ከሆነ በግልጽ ሊያስተጋቡት ይገባቸዋል። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ የዘር ማጽዳት ውዝግቡን አይፈታውም። ምክንያቱም ከአካባቢው የሚባረሩት ፍልስጤማውያን የመጨረሻውን አስከፊ ብቀላ ለማድረግ ስለሚነሳሱና የእስራኤልን በሕልውና መኖር የማይቀበሉ ጽንፈኞችም ስለሚጠናከሩ ነው።

ሁለተኛው አማራጭ የአይሁድና የፍልስጤማውያን መንግስታት ለየብቻ ከሚመሰረቱ ይልቅ በሞግዚትነት የምትተዳደር እና ፍልስጥኤማውያንንም አይሁዶችንም ያቀፈች፣ ለዜጎቿ እኩል ፖለቲካዊ መብቶችን ያጎናጸፈች አንዲት ዲሞክራሲያዊ መንግስት መመስረት ነው። ይህ የመፍትሄ ሃሳብ የተሰነዘረው በጥቂት አይሁዳውያንና ቁጥራቸው እያደገ በሄደ የእስራኤል አረቦች ነው።[7] በዚህ የመፍትሔ ሃሳብ አተገባበር ላይ የተደቀኑ መሰናክሎች ተስፋ የሚያስቆርጡ ናቸው። የሁለቱ ሕዝቦች የግንኙነት ታሪክም የሚያበረታታ አይደለም። ይህን አማራጭ ተግባራዊ ማድረግ በሌላ በኩል የቀድሞዎቹ ጽዬናዊያን መሪዎች ራዕይ የሆነውን ጽዬናዊት ሃገር የመመስረት ሃሳብ ያስቀራል። ይህን አማራጭ የእስራኤል አይሁድ ዜጎች

በፈቃደኝነት ይቀበሉታል ብሎ ለማሰብ የሚኖር ምክንያታዊነት በጣም አነስተኛ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ በሎቢው ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦችና ቡድኖች ለዚህ እቅድ ምንም ፍላጎት አይኖራቸውም ብለን ብንናገር አጋነናችሁ አንባልም። ስለሆነም ይህ የመፍትሄ ሃሳብ መልካምና ተገቢ ነው የሚል እምነት በእኛ ዘንድ የለም።

የመጨረሻው አማራጭ የአፓርታይድ ዓይነት የአገዛዝ ሥርዓት ሲሆን እስራኤል በሃይል የያዘቻቸውን ግዛቶች እንደተቆጣጠረች ትቀይለች። ፍልስጤማውያንም እርስ በርስ በማይገናኙና በኢኮኖሚ ሽባ በሆኑ ግዛቶች (Canton) ውስጥ የተወሰነ ስልጣን ያለው የራስ ገዝ አስተዳደር እንዲኖራቸው ይደረጋል።[8] እስራኤል በደቡብ አፍሪካ ከነበረው የነጮች አገዛዝ በሚነጻጸር መልኩ በሞግዚት አስተዳደር ሥር የነበረውን የፍልስጤም ምድር (mandate Palestine) ለመቆጣጠር ብትሞክር የሚገጥማት ሁከትና ብጥብጥ መሆኑ አይቀሬ ነው። ምክንያቱም የዚያ ዓይነት የአስተዳደር ሥርዓት ለመዘርጋት ከተፈለገ ቁጥሩ ከአይሁዳውያን የሚልቀውን የዓረብ ሕዝብ ሁሉንም ዓይነት የፖለቲካ መብት መንፈግን ግድ ያደርጋል። በማንኛውም መልኩ በአፓርታይድ ዓይነት አገዛዝ ሕዝቡን ለማስተዳደር መሞከር ለረዥም ጊዜ ሲታይ የሚያዋጣ አካሄድ እንደማይሆን የታወቀ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም የዚያ ዓይነቱ አገዛዝ ከሞራል አንጻር አስከፊ ከመሆኑም በላይ ፍልስጤማውያኑም ቢሆኑ የራሳቸውን መንግሥት መመሥረት እስኪችሉ ድረስ የሚዋጉት በመሆኑ ነው። ያ ዓይነቱ አመጽ ደግሞ እስራኤል ብዙ ደምና መስዋእትነት የሚጠይቅ የሆነውን በጫና የማስተዳደርና የእመቃ ፖሊሲዋን እንድትገፋበት ስለሚያደርጋት በዓለም አቀፍ መድረክ ገጽታዋን ማጠልሸቱ የማይቀር ነው።[9]

ከሁለት መንግሥታት ምሥረታ ውጭ ያሉ አማራጮች እነዚህ ብቻ ሲሆኑ ለእስራኤል በጎ የሚመኝ ሁሉ እነዚህን አማራጮች ሊቀበል አይችልም። በተጨማሪም ግጭቱ በእስራኤል ላይ የሚያስከትለው ጉዳት እንዳለ ሆኖ ዩናይትድ ስቴትስም ሆነች ፍልስጤማውያን ይህ አሳዛኝ ሁኔታ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲወገድ ይፈልጋሉ። ለዚህ ችግር መፍትሄ ማፈላለግ በፖለቲካው ሂደት እግረ መንገድና እንደ ጎንዮሽ አጀንዳ ታይቶ የሚፈጸም

አለያም የአሜሪካ ኘሬዝዳንቶች ታሪካቸውን ለማሳመር ወይም የኖቬል ሽልማት ለማግኘት ሲሉ የሚያከናውኑት ሳይሆን በዩናይትድ ስቴትስ ዘንድ ቅድሚያ ሊያገኝ የሚገባው የብሔራዊ ደህንነት ጉዳይ ተደርጎ መወሰድ አለበት። ሆኖም ግን ሎቢው ተጽዕኖ ማድረጉን እስከቀጠለ ድረስ የአሜሪካ መሪዎች ያላቸውን ስልጣን ተጠቅመው በእስራኤል ላይ ጫና በማሳደር በኃይል የያዘቻቸውን የፍልስጤም መሬቶች እንደተለቅና የፍልስጤም ነጻ መንግሥት እንዲቋቋም የማድረግ አቅም አይኖራቸውም።

ጂሚ ካርተርና ጆርጅ ደብሊው ቡሽ ከሌሎች የአሜሪካ ፕሬዝዳንቶች በተለየ መልኩ ለመካከለኛው ምሥራቅ የሰላም ሂደት ትልቅ አስተዋጽኦ ለማድረግ ችለዋል። ያንን ለማድረግ የበቁት ከሎቢው ተጽዕኖ ውጪ በራሳቸው ሥልጣንና አካሄድ በመጠቀም የሠላም ቻርት መንደፍ የተሳካላቸው በመሆኑ ነው። የቀድሞው የእስራኤል ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሻሎም ቤን አሚ እንዲህ በማለት ጽፈዋል፡- ‹‹ካርተር በተለይ ወሳኝ የሆነ እድል የነበራቸውና ዋይት ሃውስ ውስጥ ከኖሩ ፖለቲከኞች ሁሉ የተለየ ስብዕና የተላበሱ ነበሩ። ሆኖም ግን ለአይሁድ ሕዝብ ድምጽና ለሎቢው አስተጋብኦት ጆሮ ዳባ ልበስ ይሉ የነበሩት እርሳቸው ብቻ አልነበሩም። በ1980ዎቹ መጨረሻ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት በመሆን ያገለገሉት ትልቁ ጆርጅ ቡሽም እንዲሁ የእስራኤልን አመራሮች በመገዳደርና የወዳጆቿን ቁጣም ችላ በማለት የአረብ እስራኤልን ሰላም ለማምጣት አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ጥሰው መግባት ችለው ነበር።››[10] ቤን አሚ ትክክል ነበሩ። ሎቢው የእስራኤልን ጥቅም ባለማወቅ ምን ያህል ይገፋ እንደነበር ነው በዚህ አባባላቸው ሊያሰምሩበት የሞከሩት።

ነጻ የፍልስጤም መንግሥት መመሥረቱን እስራኤል ትቀበል ዘንድ አሜሪካ ግፊት ልታደርግባት ግድ ይላታል። ይህ ማለት ደግሞ በተግባር በክሊንተን እሴቶች (Clinten parameters) የተጠቀሱትን የመፍትሄ ሃሳቦች መቀበል እንጂ ሌላ አይደለም። ምንም እንኳን የኢሁድ ባራክ መንግሥት ከፍ ካለ ቁጥብነት ጋር የክሊንተንን እሴቶች በጥር 2001 ቢቀበላቸውም፣ የመፍትሄ ሃሳቡ ቁልፍ ነጥቦች ሰፊ ድጋፍ አልተቸራቸውም። በ2007 በተደረገ ጥናት መሠረት 55 ከመቶ የሚሆኑ እስራኤላውያን የፍልስጤማውያን መንግሥት

